መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና በአፍሪካውያን ዕይታ

ዊልበር ኦዶኖቫን

Copyright © Wilbur O'Donovan 1992, 1996

First published 1992 as Introduction To Biblical Christianity
From An African Perspective by Nigeria Evangelical Fellowship
Ilorin, Kwara State, Nigeria

Second edition published as Biblical Christianity In
African Perspective 1995 by the Paternoster Press
P.O. Box 300, Carlisle, CA3 0QS, UK

All rights reserved by the Paternoster Press. No part of this publication may be reproduced, stored in a retrieval system or transmitted in any form or by any means, electronic, mechanical, photocopying, recording or otherwise without the prior permission of the publisher or a license permitting restricted copying.

ISBN 0-85364-711-9

ትርጉም ግርማዊ ቡኸ

Translation and Amharic publication rights
© 1996 by SIM, Addis Ababa, Ethiopia
All rights reserved

ምስጋና

በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጆችና ሴሚናሪዎች ቤተ መጻሕፍት ውስጥ በሥነ-መለኮት አሳብ ላይ የተጻፉ አያሌ መጻሕፍት ይገኛሉ። ይሁንና፥ በአፍሪካ በሥነ-መለኮት ትምህርት ላይ ለተሰማሩ ሰዎች፥ ለበርካታ ዓመታት በቀላል ቋንቋና ከአፍሪካ ዕይታ አንጻር የተጻፉ የመማሪያ መጻሕፍት ችግር ዓይነተኛ ሆኖ ቆይቷል። በመሆኑም፥ ይህ ችግር ላለፉት ሃያ ዓመታት ያህል በብዙ የአፍሪካ የሥነ-መለኮት ምሁራን ሲዘከር ቆይቷል። በ1988፥ የምዕራብ አፍሪካ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ዋና ጸሐፊ የነበሩት ዶ/ር ዩሱፍ ቱራኪ፥ ይህንኑ ችግር ለዚህ መጽሐፍ ደራሲ ገለጹለት። ደራሲው ለበርካታ ዓመታት በአፍሪካ የሥነ-መለኮት ትምህርት ሲያስተምር ቆይቶ ነበር። ስለ ሆነም ዶ/ር ቱራኪ ደራሲው ከአፍሪካውያን መጋቢያንና የሥነ-መለኮት ምሁራን ጋር በመተባበርና የክርስትናን ሃይማኖት መሠረታዊ አስተምህሮ (ዶክትሪን) ከአፍሪካ ዕይታ አንጻር በመቃኘት ረቂቅ እንዲነድፍ ጠየቁት። ይህም መጽሐፍ የዚያ ጥያቄ ምላሽ በመሆን የተዘጋጀ ነው።

ደራሲው ዶ/ር ቱራኪ ሳበረከቱለት ግበረታቻና ለሙከራ ለተዘጋጀው ዕትም ሳደረጉት ትዕግሥትን የተሞላ ግምገማ ከልብ የመነጨ ምስጋና ያቀርባል። በተጨማሪም፥ ዐውዳዊ ለሆኑ የሥነ-መለኮት መጻሕፍት መገኘት መቆርቆር ለተሰማቸው፥ በአፍሪካ ለሚያገለግሉ የሥነ-መለኮት ምሁራንና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምስጋናውን ያቀርባል። በተለይም ለዶ/ር ቲቴ ቲዮኖ፥ ዶ/ር ታይተስ ኪቫንዚ፥ ዶ/ር ጆሊየስ ሙተንጂ፥ ዶ/ር ሪቻርድ ጌግን፥ ዶ/ር ፖል ባወርስ፥ ዶ/ር ጆን ግሪሽን፥ ዶ/ር ጄምስ ፕሉድማን፥ ዶ/ር ፊሊፕ ስተይን፥ ዶ/ር ሐሩን ሩን፥ ዶ/ር ሉይስ ቱለር፥ ከቡር እስቲፈን አካንግቪ እና አሁን በሕይወት ለሌሉት ክቡሩ ዊሊያም ጂ. ከራውች ከፍተኛ ምስጋና ያቀርባል። እነዚህም ወገኖች የዚህን መጽሐፍ የተለያዩ ክፍሎች በመክለስ፥ ወይም በአፍሪካ ካሳለፉት ዓመታት በመነሣት የጥበብ ምክር የለገሱት ናቸው።

የዚህን መጽሐፍ የሙከራ ዕትም ረቂቅ በመመልከት ላቀረቡልኝ ንጉቢ ሂስና ጠቃሚ አሳቦች ብሎም ምክር፥ በናይጀሪያ የምዕራብ

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና በአፍሪካውያን ዕይታ

አፍሪካ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መጋቢ የሆኑትን ጀርማያ ጋዶ እና የኬንያ ኤ.አይ.ሲ. መጋቢ ኪቢ አራፕ ማዮ ከልብ ለማመስገን ይፈልጋል። በአሁኑ ጊዜ የዶክትሬት ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙት መጋቢ ጋዶ ቀደም ሲል በናይጀሪያ የቢሊሪ መጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ዳይሬክተር ነበሩ። ከሆላንድ ሚቺጋን ዌስተርን ቲዎሎጂካል ሴሚናሪ የቲዎሎጂ የማስተር ዲግሪ የተቀበሉት መጋቢ ማዮ በኬንያ ኤልዶሬት የኤ.አይ.ሲ. ሚሲዮናዊ ኮሌጅ አካዳሚክ ዲን ናቸው። የእነዚህ ሁለት የእግዚአብሔር ባሪያዎች ጎብረትና ማጽናናት ለደራሲው ታላቅ በረከት ነበር። የእነርሱ አገዛ ባይኖር ኖሮ፥ ይህም መጽሐፍ ለፍሬ ባልበቃ ነበር።

በተጨማሪም፥ ደራሲው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን እውነተኛ ታሪኮች ላካፈሉት በርካታ ተማሪዎቹና ወዳጆቹ ምስጋናውን ያቀርባል። እንደዚሁም ሚሲዮናዊቷ መምህርት ዶሪዚ ክሳርክ የእንግሊዝኛውን ሰዋስው ፈር ስላስያዘችለትና ሚካኤል ባተርማንም በበርካታ ተግባራዊ መንገዶች ስላገዘው ምስጋናውን ያቀርባል። እንደዚሁም መጽሐፉ በተለይ ለኢትዮጵያውያን አንባቢያን ወደ አማርኛ እንዲተረጎም ሐሳብ በማቅረብ ያበረታቱኝን ፖል ኤንዝና የኤስ. አይ. ኤም. ሚዲያ ሠራተኞችን፥ ረቂቅ ትርጉሙን ያዘጋጁትን አቶ ግርማዊ ቡሽ፥ በእርማቱ ሥራ የተሳተፉትን ወ/ት ዴቦራ ተገኘወርቅ፥ ወ/ሮ ራሔል ተገኘወርቅ፥ ወ/ት ማሩት ሰይፉ፥ አቶ ወንድሙ ኃይሉን፥ የመጨረሻውን የአርታኢነት ተግባር ያከናወኑትን ሚስ ሩት ክሪመርና አቶ ዓቢይ ደምሴን፥ የሽፋኑን ሥዕል ያዘጋጁትን አቶ አንተነህ አያሌው፥ ትርፍ ጊዜያቸውን በመሠዋት ጽሑፉን በኮምፕዩተር ታይፕ ያደረጉትን ወ/ት ትዕግሥት ኃይሉን ከልብ ያመሰግናል። በተለይም ደራሲው ሰብአዊ ድክመት ሳይሰማት በማያቋርጥ ጸሎቷና በፍቅር ድጋፍዋ መጽሐፉ እንዲጸና ላበረታታችው ባለቤቱ ለኤስቴር የላቀ ምስጋና ያቀርባል። ከሁሉም በላይ፥ ደራሲው የፍጥረታት ሁሉ አምላክ ለሆነው፥ ይህም መጽሐፍ ለተጻፈለትና ሥራውንም ለመፈጸም ብቻውን በብርታቱና በምሪቱ ላስቻለው እግዚአብሔር ምስጋናና ውዳሴ ያቀርባል።

ዊልበር አዶኖቫን

ማውጫ

መግቢያ 1

ሀ. የ«ንጽረተ-ዓለም» ትርጉም ምንድን ነው? 4
ለ. እውን ባህላዊ አፍሪካዊ ንጽረተ-ዓለም አለ? 5
ሐ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ሥነ-መለኮት እንዴት ልንገነባ እንችላለን? 6
መ. ከዚህ ቀደም መጽሐፍ ቅዱሳዊና አፍሪካዊ የሆነ ሥነ-መለኮት ለማዋቀር በተደረገው ጥረት ያጋጠሙ ችግሮች ምንድን ናቸው? 7
ሠ. እነዚህን ያጋጠሙንን ችግሮች በማሸነፍ፥ እውነተኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊና እውነተኛ አፍሪካዊ ሥነ-መለኮት ልንገነባ የምንችለው እንዴት ነው? 8

1. ማንን እና ምንን እንመን? 10

ሀ. በአንድ ነገር ወይም ሰው ማመን ሲባል ምን ማለት ነው? 11
ለ. እውነት ምንድን ነው? 13
ሐ. እውነትን ከወዴት ልናገኝ እንችላለን? 14
- ኢየሱስ ከሴሎች የሃይማኖት መምህራን ጋር ሲወዳደር 15
- የኢየሱስ ተአምራት ማረጋገጫ 17
መ. የምናምነው ነገር በተግባራችን ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድረው እንዴት ነው? 18
ሠ. እውነት የሆነውን ነገር ስታምን ምን ይከሰታል? ውሸት የሆነውንስ ስታምን? 19
ረ. ማንን እንመን? 20
ማጠቃለያ 20

2. መጽሐፍ ቅዱስ – የእምነታችን መሠረት 23

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ እንዲያው የሰዎች ቃል ሳይሆን፥ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ እንዴት ልናውቅ እንችላለን? 24
- የሐዋርያት ምስክርነት መረጃ 25
- የትንቢት መረጃ 25

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና በአፍሪካውያን ዕይታ

- አንዳንድ የተፈጸሙ ትንቢቶች ምሳሌዎች 26
- መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ የሚያረጋግጥ ሌላ መረጃ 28
- የመጽሐፍ ቅዱስ አንድነት 29
- የሰውን ሕይወት ለመለወጥ መጽሐፍ ቅዱስ የያዘው ኃይል 30
- የጸሎት መልሶች 30

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ብቸኛ መገለጽ ነው፣ ወይስ ሌሎችም ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላኩትን መገለጾች ያካተቱ መጻሕፍት አሉ? 31

ሐ. ኢየሱስ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣንና ትክክለኛነት ምን አስተማረ? 31

መ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚታዩ የአሳብ ግጭቶችስ? 33

ሠ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የማንረዳቸውስ ነገሮች? 34

ረ. በብሉይና አዲስ ኪዳን መካከል ያለው ግንኙነት ምንድን ነው? 35

ሰ. መጽሐፍ ቅዱስ በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ተጻፈ ሲባል ምን ማለት ነው? 37

ማጠቃለያ 40

3. መጽሐፍ ቅዱስ ወደ እኛ እንዴት እንደ መጣ 43

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት አገኘን? 44
- በመጀመሪያ ሥነ-ቃል ነበር 44
- የሥነ-ቃል መጻፍ መጀመር 44
- የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና ምንድን ነው? 45
- ሴፕቱዋጀንት 47
- ቩልጌት 47
- ጥንታዊ መዛግብት 47
- የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ የመነጨው ከምንድን ነው? 47

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ ከአንዱ ቋንቋ ወደ ሌላው በመተርጎሙና ለበርካታ መቶ ዓመታት ከትውልድ ትውልድ እየተላለፈ በመምጣቱ ተለውጦ ይሆን? 49
- የሙት ባሕር የመጻሕፍት ጥቅልሎች 49
- የመጽሐፍ ቅዱስ ዋንኛ አስፈላጊ መዛግብት የትኞቹ ናቸው? 50

ሐ. ዐበይት የእንግሊዝኛ ትርጉም መጻሐፍ ቅዱሶች የትኞቹ ናቸው? 51

ማውጫ

መ. የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ የተለየው ለምንድን ነው? 52

ሠ. ከሁሉም ትክክለኛ የሆነው የእንግሊዘኛ መጽሐፍ ቅዱስ እትም የትኛው ነው? 54

ማጠቃለያ 55

4. ልንረዳው የማንችለው አምላክ 58

ሀ. ከአፍሪካ ባህላዊ ሃይማኖቶችና ከተፈጥሮ ስለ እግዚአብሔር ምን ልንማር እንችላለን? 59

ለ. በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር የተሰጠን ተጨማሪ መገለጥ ምንድን ነው? 62

ሐ. እንዴት አንድ አምላክ ምስት አካላት ሊሆን ይችላል? 63

መ. እግዚአብሔር ሰው በሆነ ጊዜ ምን ተከሰተ? 66

ሠ. እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ ሊገኝ የሚችለው እንዴት ነው? 69

ማጠቃለያ 70

5. ኢየሱስ ክርስቶስ – እግዚአብሔርን የገለጸው «ሰው» 73

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ምን ይነግረናል? እርሱ ማን ነው? 74

ለ. በኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጹ የእግዚአብሔር ባሕርያት የትኞቹ ናቸው? 77

- የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነትና ቸርነት 77
- የእግዚአብሔር ሉዓላዊነትና ሁሉን አዋቂነት 82
- የእግዚአብሔር ፍቅር 88
- የእግዚአብሔር ርኅራኄና መልካምነት 91
- የእግዚአብሔር ቅድስናና ቁጣ 95
- የእግዚአብሔር ፍትሕና ምሕረት 101
- የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ህልውናና አለመለወጥ 104

ሐ. ከእግዚአብሔር ሰሞች ስለ እግዚአብሔር ምን እንማራለን? 108

ማጠቃለያ 114

6. ሰው – ገዥውና ዓመፀኛው 118

ሀ. እኛ ማን ነን? ከየትስ መጣን? 119
- ዘመናዊው ሳይንስ ስለ ሰው ነፍሳት ጅማሬ ምን ይላል? 124
- ሰዎች ከአናሳ እንስሳት በአዝጋሚ ለውጥ እያደጉ እንደ መጡ የሚናገረውስ ፍልስፍና ምን ይላል? 125
- መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ወንድና ሴት ጅማሬ ምን ይላል? 128

ለ. ለምን እንኖራለን? 129
ሐ. ሰዎች በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩት እንዴት ነው? 130
- የእግዚአብሔር አምሳል የእግዚአብሔርን ባሕርይ ሊያንጸባርቅ 131
- የእግዚአብሔር አምሳል የእግዚአብሔርን ጠባያት ሊያንጸባርቅ 132

መ. እውን ሰው ከእንስሳት ይለያል? 133
ሠ. ሰው ለእግዚአብሔር ባለመታዘዙ ምን ተከሰተ? 135
ረ. እግዚአብሔር ሰውንና ምድርን በመርገሙ ምን ተከሰተ? 136
ሰ. ኃጢአት በሰው ሁሉ ላይ የደረሰው እንዴት ነው? 138
ሸ. ኃጢአተኞች ሆነን የተወለድነው ለምንድን ነው? 138

ማጠቃለያ 141

7. ኢየሱስ ክርስቶስ – የደኅንነታችን ምንጭ 144

ሀ. የእግዚአብሔር ፍቅርና ይቅርታ ምን ያህል ታላቅ ነው? 148
ለ. የሰው ደኅንነት የተከናወነው እንዴት ነው? 151
- የክርስቶስ መሥዋዕት 153
- መጽሐፍ ቅዱሳዊ የኃጢአት ፍች 156

ሐ. የደኅንነት ፍች ምንድን ነው? 159
- ደኅንነት ከዚህ ቀደም 159
- ደኅንነት ባሁኑ ጊዜ 160
- ደኅንነት በሚመጣው ጊዜ 160

መ. የደኅንነት ውጤቶች ምንድን ናቸው? 161
ሠ. ደኅንነት ከአፍሪካ ችግሮች ጋር የሚዛመድባቸው አንዳንድ መንገዶች የትኞቹ ናቸው? 166

ረ. ቅድስና ምንድን ነው? 168
- ቅድስና ከዚህ ቀደም 168
- ቅድስና ባሁኑ ጊዜ 169
- ቅድስና በሚመጣው ጊዜ 172
ሰ. የኢየሱስ ከሞት መነሣት እውነት እንደ ሆነ እንዴት እናውቃለን? 173
ሸ. በዛሬው ጊዜ የክርስቶስ ትንሣኤ ለክርስቲያኖች የሚሰጠው ትርጉም ምንድን ነው? 177
ቀ. የክርስቶስ ዕርገት ዓላማ ምን ነበር? አሁንስ ምን በማድረግ ላይ ይገኛል? 179
በ. የሚድነው ማን ነው? 181
ማጠቃለያ 185

8. መንፈስ ቅዱስ - ክርስቲያኖችን የሚቀድሰውና የሚያበረታታው 188

ሀ. መንፈስ ቅዱስ አካል እንደ ሆነ እንዴት እናውቃለን? 190
ለ. መንፈስ ቅዱስ አምላክ እንደ ሆነ እንዴት እናውቃለን? 191
ሐ. መንፈስ ቅዱስ ከወልድና ከአብ የተለየ አካል ነው? 191
መ. በመጽሐፍ ቅዱስ ሥራውን ለመግለጽ ከተጠቀሱት ተምሳሌቶች፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ምን እንማራለን? 192
- መንፈስ ቅዱስ እንደ እሳት 192
- መንፈስ ቅዱስ እንደ ሕያው ውኃ 193
- መንፈስ ቅዱስ እንደ ርግብ 194
- መንፈስ ቅዱስ እንደ ተቀደሰ ዘይት 195
- መንፈስ ቅዱስ እንደ ነፋስ 196
ሠ. ዛሬ መንፈስ ቅዱስ በማያምኑ ሰዎች መካከል ምን ይሠራል? 196
- መንፈስ ቅዱስ በዓለም የከፋትን መበራከት ይከላከላል 196
- መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ስለ ኃጢአታቸው በመውቀስ፥ ትኩረታቸውን ወደ ክርስቶስ ይመራል 197
ረ. መንፈስ ቅዱስ ለክርስቲያኖች ምን ይሠራል? 199
ሰ. ለእያንዳንዱ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ዕቅድ ምንድን ነው? 200
ሸ. መንፈስ ቅዱስ ክርስቲያኖች ክርስቶስን ይመስሉ ዘንድ እንዴት ይለውጣቸዋል? 201

ቀ. ለሁሉም ክርስቲያኖች በአጠቃላይ የመንፈስ ቅዱስ ዕቅድ ምንድን ነው? 207
በ. በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማለት ምን ማለት ነው? 207
- ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ የሚሞላው እንዴት ነው? 210
- በመንፈስ ቅዱስ መሞላታችንን እንዴት እናውቃለን? 211
- ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ከተሞላ ኃጢአት የማይነካው ፍጹም ሰው ይሆናል? 213
ማጠቃለያ 214

9. ቤተ ክርስቲያን - የተሰፋፋች የእግዚአብሔር ቤተሰብ 217

ሀ. ቤተ ክርስቲያን ምንድን ናት? 219
ለ. የቤተ ክርስቲያን አባላት እነማን ናቸው? 221
ሐ. እውነተኛዪቱ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የትኛዪቱ ነች? 223
መ. የእግዚአብሔር መቅደስ የሚገኘው የት ነው? 223
ሠ. ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል እንደ ሆነች የሚያሳዩ ሦስት አስፈላጊ ተግባራዊ ተዛምዶዎች ምንድን ናቸው? 225
- ማኅበረሰብ 225
- የጎብረት ጸሎት 228
- መንፈሳዊ ስጦታዎች 233
ረ. ክርስቲያን የትኛውን መንፈሳዊ ስጦታ እንደ ተቀበለ እንዴት ያውቃል? 234
ሰ. ቤተ ክርስቲያን ከሰው ልጅ ጋር ላላት ግንኙነት የእግዚአብሔር ዕቅድ ምንድን ነው? 235
ሸ. የቤተ ክርስቲያን ዓላማ ምንድን ነው? 237
- ምስጋናና አምልኮተ-እግዚአብሔር 237
- የወንጌል ስርጭትና ምስክርነት 237
- ሰናይ ምግባራት 238
- ጎብረትና መታነፅ 239
- በክርስቶስ የሚገኝ ዘላለማዊ ርስት 239
ቀ. በአዲስ ኪዳን በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያኑ መካከል ያለውን ግንኙነት ለመግለጽ ያገለገሉ ዐበይት ግብራሪያዎች ምንድን ናቸው? 240

ማውጫ

በ. እንዲህ የበረከቱ የተለያዩ የእምነት ክፍሎችና አብያተ ክርስቲያናት የሚታዩት ለምንድን ነው? 241

ተ. ኢየሱስ ለቤተ ክርስቲያኑ የሰጣቸው ሥርዓቶች ምንድን ናቸው? 242

- የውኃ ጥምቀት 242
- ቅዱስ ቁርባን 245

ቸ. ዐበይት የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው? 246

- ኤጲስ ቆጶሳዊ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር 246
- የፕረስቢቴሪያል የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር 247
- ኮንግርጌሽናል የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር 247

ኀ. በአዲስ ኪዳን መሠረት በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ዐበይት የመሪነት ስፍራዎች የትኞቹ ናቸው? 248

- ሽማግሌ 248
- ዲያቆን 251

ማጠቃለያ 252

10. ክርስቲያንና የመናፍስት ዓለም 256

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መናፍስት ዓለምና ከዚያ ዓለም ጋር ስላለን ግንኙነት ምን ይላል? 258

ለ. መላእክት እነማን ናቸው? 259

ሐ. መላእክት ምን ይመስላሉ? 261

መ. የተለያዩ የመላእክት ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው? 264

ሠ. የቅዱሳን መላእክት ባሕርያት የትኞቹ ናቸው? 264

ረ. ቅዱሳን መላእክት የእግዚአብሔርን ሰዎች የሚረዱባቸው አንዳንድ መንገዶች የትኞቹ ናቸው? 265

ማጠቃለያ 268

11. የክፋት ምንጭና የሰይጣን ዘዴዎች 271

ሀ. የክፋት ምንጩ ምንድን ነው? 271

ለ. ሌሎች መላእክት በሰይጣን ዓመፅ ውስጥ እንዴት ሊሳተፉ ቻሉ? 275

ሐ. የአሁኑን የዓለም አሴቶች ዘይቤ የሚቆጣጠረው ማን ነው? 277

መ. ክርስቲያን ያልሆኑ ሃይማኖቶች ምንጭ ምንድን ነው? 278

ሠ. አጋንንት ምንድን ናቸው? 281

ረ. እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ፥ የአጋንንት ሥራዎች ምንድን ናቸው? 282
- የአጋንንት አሠራር ዓይነቶች 283
ማጠቃለያ 288

12. መንፈሳዊ ውጊያ 291

ሀ. አንድ ክርስቲያን ወደ ኋላ የሚጎትተውን የኃጢአት ተፈጥሮውን እንዴት ሊያሸንፍ ይችላል? 293
ለ. ክርስቲያን የዓለምን ፈተናዎች እንዴት ሊያሸንፍ ይችላል? 296
ሐ. ክርስቲያን የሰይጣንን ጥቃቶች እንዴት ሊያሸንፍ ይችላል? 298
- ቀጥተኛ የአጋንንት ጥቃት 302
- ለመንፈሳዊ ውጊያ መንፈሳዊ መሣሪያዎች 305
መ. የመንፈሳዊ ጦር ዕቃዎች ምንድን ናቸው? እንዴትስ እንጠቀምባቸዋለን? 306
- እውነት 307
- ጽድቅ 307
- የሰላም ወንጌል 307
- እምነት 307
- ደኅንነት 309
- የእግዚአብሔር ቃል 309
- ጸሎት 309
- ትሕትና 310
ማጠቃለያ 311

13. በባህላዊ እምነቶችና ልምምዶች ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት 314

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሙታን መናፍስት ምን ያስተምራል? 316
ለ. ክርስቲያን ከቅድመ-ትውልዶቹ ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት፥ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? 319
ሐ. የሙታንን መናፍስት በተመለከተ፥ እውነቱ ምንድን ነው? በአጋንንት የመታለል ውጤቱ ምንድን ነው? 322
መ. በጋኔን ስለ መያዝ የመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት ምንድን ነው? 324

ማውጫ

ሠ. የአጋንንት ተጽዕኖ የደረሰባቸውን ወይም በአጋንንት ቁጥጥር ሥር የወደቁትን ሰዎች ክርስቲያኖች እንዴት ሊረዱአቸው ይችላሉ? 326

ረ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መንግሥተ ሰማይና ሲኦል ምን ይላል? 329

ሰ. መጽሐፍ ቅዱስ ከሙታን ጋር ስለ መነጋገር ምን ይላል? 332

- ክርስቲያን ከሙታን ጋር ስለ መነጋገር ምን ምላሽ ሊኖረው ይገባል? 333

ሸ. በአካለ መጠን መድረሻ ባህላዊ ሥርዓቶች ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት ምንድን ነው? 335

- የሴት ልጅ ግርዘት እንደ አካለ መጠን መድረሻ 336

- መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ግርዘት የሚሰጠው አጠቃላይ ትምህርት 339

- በአካለ መጠን መድረሻ ባህላዊ ልምምዶች ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ አመለካከት 340

- ለጎሳዊ የአካለ መጠን መድረሻ ልምምድ ክርስቲያናዊ አማራጭ 341

ቀ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ምትሐት ምን ይላል? 343

- በምትሐት ስለ መገልገል የክርስቲያን ምላሽ ምንድን ነው? 347

በ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ምዋርተኝነት ምን ይላል? 348

- እግዚአብሔር ምዋርተኝነትን የሚኮንነው ለምንድን ነው? 350

- ለምዋርተኝነት የክርስቲያን ምላሽ ምንድን ነው? 351

ማጠቃለያ 352

14. አምስት አስፈላጊ ጉዳዮች በአፍሪካ - አመራር፥ የሐሰት ነቢያት፥ ቅይጥነት፥ አማላጆች፥ መንግሥት 355

ሀ. በዛሬው ጊዜ እግዚአብሔር ክርስቲያኖችን የሚመራው እንዴት ነው? 356

ለ. ክርስቲያን ሐሰተኛና እውነተኛ ነቢያትን የሚለየው እንዴት ነው? 362

ሐ. የመቀየጥ ችግሮች – ክርስቲያን ሊሳተፍባቸው የሚችልባቸው ልማዶች፥ ሥርዓቶችና ሌሎች ባህላዊ ልምምዶች የትኞቹ ናቸው? 363

መ. በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሊያግልድ
የሚችል ማን ነው? 369
ሠ. ክርስቲያን ለአገሩ መንግሥት የሚኖረው
ኃላፊነት ምንድን ነው? 370
ማጠቃለያ 374

15. ቤተ ክርስቲያንና ባህላዊ መድልዎ 378

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቲያኖች ባህላዊ ጅማሬ (ጎሳ፥
ነገድ፥ ዘርና ጾንጾ) ምን ይላል? 379
ለ. የተለያየ ባህል ባላቸው አባላት ሳቢያ በቤተ ክርስቲያን
ውስጥ የተከሰቱ አንዳንድ ችግሮች የትኞቹ ናቸው? 383
ሐ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የባህላዊ መድልዎ
ችግሮች እንዴት ይታለላሉ? 385
መ. ከተለያዩ ባህሎች፥ ዘሮችና ጾንጾዎች አኳያ እግዚአብሔር
ለቤተ ክርስቲያን ያለው ዕቅድ ምንድን ነው? 388
ማጠቃለያ 390

16. ጋብቻ፥ ወሲብና ቤተሰብ ከመጽሐፍ
ቅዱስ አንጻር 393

ሀ. ለጋብቻ የእግዚአብሔር ዕቅድ ምንድን ነው? 394
- ጋብቻ የእግዚአብሔር አሳብ ነበር 394
- ጋብቻ - በሰብአዊ ግንበረሰብ የመጀመሪያው ተቋም 395
- ለጋብቻ የእግዚአብሔር ዕቅድ 396
- የእግዚአብሔር ዕቅድ በጋብቻ ውስጥ ለሚኖር አንድነት 398
ለ. ለባሎችና ለሚስቶች የእግዚአብሔር ዕቅድ ምንድን ነው? 400
- የእግዚአብሔር ዕቅድ ለባል 400
- የእግዚአብሔር ዕቅድ ለሚስት 401
- የእግዚአብሔር ዕቅድ ለባልና ለሚስት እንደ ወላጆች 403
ሐ. ስለ ወሲብ የእግዚአብሔር ዕቅድ ምንድን ነው? 404
- የምኞት ችግር 406
- ፍቅር ወይስ ምኞት? 407

ማውጫ

መ. ለክርስቲያኖች ቤተሰባዊ ሕይወት የእግዚአብሔር ዕቅድ ምንድን ነው? 410

ሠ. ከአንድ በላይ ስለ ማግባት የመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት ምንድን ነው? 411

ረ. እግዚአብሔር ስለ ፍች ምን ይላል? 416

- ችግሮች በጋብቻ ውስጥ 417

ሰ. የትዳር ጓደኛ ስለ መምረጥ አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያዎች ምንድን ናቸው? 418

ሸ. ክርስቲያን ባለትዳሮች የመካንነትን ችግር እንዴት ይወጣሉ? 420

ማጠቃለያ 422

17. የመከራና የሕመም፥ የአስማት፥ የጥንቆላና የጉበኛነት ተያያዥ ችግሮች 426

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰው ልጆች መከራ መቀበል ምን ይላል? 427

ለ. የበሽታ መነሾዎች ምንድን ናቸው? 436

ሐ. ክርስቲያን አስማት፥ ጥንቆላ፥ ምትሐት፥ እርግማንና ድግምትን እንዴት መቋቋም ይችላል? 443

- ክርስቲያኖች አስማት፥ ምትሐት፥ ድግምት፥ ወይም እርግማን እንደ ተደረገባቸው ሲጠረጥሩ ምን ማድረግ አለባቸው? 448

መ. ክርስቲያን የጉበኛነትን ችግር እንዴት ሊመለከት ይገባል? 449

- መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጉቦ ምን ይላል? 450

- ጉቦ ስሕተት የሆነው ለምንድን ነው? 451

ማጠቃለያ 453

18. የክርስቶስ መመለስና የዘመን መጨረሻ 457

ሀ. ታሪክ ወዴት እያመራ ነው? 458

- እግዚአብሔር በዓለም ውስጥ ምን እየሠራ ነው? 459

- ሰይጣን በዓለም ውስጥ ምን እየሠራ ነው? 463

ለ. የዚህን ዘመን ፍጻሜ የሚያመለክቱ ክስተቶች ምንድን ናቸው? 465

- ስለ እስራኤል ሕዝብ የተሰጡ ትንቢቶች 466

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና በአፍሪካውያን ዕይታ

- ስለ ሰይጣን የተሰጡ ትንቢቶች 467
- ስለ ቤተ ክርስቲያን የተሰጡ ትንቢቶች 469
- በግኅበረሰቡ ውስጥ ስለሚኖሩ ሁኔታዎች የተሰጡ ትንቢቶች 470
- ስለ ተፈጥሮአዊው ዓለም የተሰጡ ትንቢቶች 471

ሐ. የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ምን ይመስል ይሆን? 471
መ. ክርስቶስ መቼ ይመለሳል? 474
ሠ. አንድ ሰው ለዚህ ዘመን የመጨረሻ ክስተቶችና ለክርስቶስ መመለስ እንዴት ሊዘጋጅ ይችላል? 475
ረ. ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ ስለሚኖሩ የክስተቶች ቅደም ተከተል ከሚናገሩት ዐበይት ጽንሰ-አሳቦች (ቲዎሪዎች) አንዳንዶቹ ምንድን ናቸው? 479
ሰ. ክርስቶስ ለምን ይመለሳል? 481
1. ኢየሱስ ሕዝቡን ወደ ራሱ ይሰበስባል 482
2. ኢየሱስ ሙታንን ሁሉ ያስነሣል 482
3. ኢየሱስ ባሪያዎቹን፥ ቅዱሳኑንና ነቢያቱን ይሸልማቸዋል 483
4. ኢየሱስ ሰይጣን በዚህ ዓለም ላይ ያለውን ቁጥጥር ከፍጻሜ ያደርሰዋል 483
5. ኢየሱስ ከተግባራቸው አኳያ በሰዎች ሁሉ ላይ ፍርድ ይሰጣል 483
6. ኢየሱስ በዚህ ዓለም ላይ የጽድቅ መንግሥት ይመሠርታል 486
7. ኢየሱስ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ይፈጥራል፥ ተፈጥሮንም ሁሉ ወደ ፍጹምነት ያድሰዋል 486

ማጠቃለያ 488

የቃላት ፍቺ 491

መግቢያ

ካሌብ ከአገሩ የአፍሪካዊ ሚሲዮን ድርጅት ጋር ወደ ገጠር ወጣ ብሎ በባህላዊ ወግ በተያዙት ሕዝቦች መካከል የቤተ ክርስቲያን ግቋቋም ተግባር እንዲያከናውን ተመድቦ ነበር። በዚያች መንደር ክርስቲያኖች ካለመኖራቸውም በላይ፥ የመንደሩ ሽማግሌዎች በወንጌሉ ሥራ አልተደሰቱም ነበር። በባህላዊ እምነቶቻቸው ጠንካሮች ነበሩ። ለጥቂት ወራት የተደረገው ስብከትም ፍሬ አላሳየም። ካሌብ ወንጌሉ የባህሉን ግርዶሽ በጣጥሶ እንዲያልፍ ጸለየ።

በዚያን ዓመት በመንደሪቱ በቂ ዝናብ አልተገኘም ነበር። አዝመራ ቢዘራም ይጠወልግ ነበርና፥ የመከሩ ጉዳይ ተስፋ የሚጣልበት አልሆነም። ስለ ሆነም ዝናብ በጣም አስፈላጊ ነበር ። በዚህ አጋጣሚ ዕድሉን ለመጠቀም ካሌብ ወደ መንደሪቱ ሽማግሌዎች ቀረበ። ዝናብ እንዲመጣ ወደ መጽሐፍ ቅዱሱ እግዚአብሔር ቢጸልይ ይደግፉ እንደ ሆነ ጠየቃቸው። በጣም ደስ አላቸው። ይሁንና፥ ካሌብ በጸሎቱ ላይ ቅድመ-ሁኔታን አስቀመጠ።

የመጽሐፍ ቅዱሱ እግዚአብሔር ዝናብ በመስጠት ጸሎቱን ቢመልስ፥ ቃሉ (መጽሐፍ ቅዱስ) እውነት እንደ ሆነ ይስማሙ ይሆን? ወሩን ሁሉ ሲነግራቸው እንደ ነበረው፥ ጸሎቶቹ ሁሉ ምላሽ የሚያገኙበትና ሰዎች የኃጢአት ይቅርታ ሊያገኙ የሚችሉበት በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ እንደ ሆነ ያምኑ ይሆን? ሽማግሌዎቹ እናምናለን በማለት በካሌብ ቅድመ-ሁኔታዎች ተስማሙ።

ካሌብም ወደ ቤቱ ተመልሶ ይጸልይ ጀመር። የእግዚአብሔር ቃል እውነትና የእነዚህ ወገኖች ነፍሳት ፈተና ላይ ወድቀው ነበር። ካሌብ ለ28 ሰዓታት በጉልበቱ ተንበርክኮ ጸለየ። በመጨረሻም፥ እግዚአብሔር ለረኃም ጊዜ ላያቋርጥ የሚወርድ፥ ከባድ ዝናብ አመጣ። በዚህም ጊዜ፥ ካሌብ በጭቃው ውስጥ እየተንቦጫረቀ የመንደሩ ሽማግሌዎች ወደ ተሰባሰቡበት ግቢ ደረሰ። እነርሱም ለመስማትና ለማመን ተዘጋጅተው ነበር። ብዙም ሳይቆይ የአመኑት ሰዎች ለጸሎትና ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በካሌብ ቤት ይሰበሰቡ ጀመር። በእነዚህ አማኞች ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተች ስትሆን፥ እስከ ዛሬም ድረስ በማደግ ላይ ትገኛለች።

ይህ እውነተኛ ታሪክ የዚህን መጽሐፍ ርዕሰ-ጉዳይና የመጽሐፍ ቅዱሱን እግዚአብሔርን ያስተዋውቃል። ይህ እግዚአብሔር በተገኘበት ስፍራ ሁሉ፥ እርሱ ከሁሉም በላይ ነው። በመሆኑም፥ እርሱን ማግኘት ማለት በሕይወት ከሁሉም የላቀ ሀብት ማግኘት ማለት ነው።

ለመሆኑ፥ እግዚአብሔር በትክክል ምን እንደሚመስል ታውቃለህ? ምናልባትም እግዚአብሔር እንዴት ሦስት አካላት ሊሆንና መልሶ

ደግሞ እንዴት አንድ አምላክ እንደሚሆን ጥያቄ ፈጥሮብህ ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ ከየት እንደመጣ ለሌላው ሰው ልታብራራለት ትችላለህ? ክርስቶስ እግዚአብሔር ቢሆን ኖሮ እንዴት በኃጢአት ይፈተናል ብለህስ ተደንቀህ ታውቃለህ? ክፉ መናፍስት ከወዴት ይመጣሉ? ክርስቲያን አንድ ሰው ቢረግመው ምን ሊያደርግ እንደሚችል ታውቃለህ? ልጅ ለመውለድ ያልቻሉትን መካን ባለትዳሮች እንዴት ትመክራለህ? ክርስቲያን ለቅድመ-ትውልዶቹ ምን ኃላፊነት ይኖረዋል? ቤተ ክርስቲያን ከአንድ በላይ ጋብቻን ልታስወግድ የምትችልበት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መንገድ የትኛው ነው? ይህ መጽሐፍ እነዚህንና ከአፍሪካ ክርስትና ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን በርካታ ሌሎች ጉዳዮች ይመለከታል።

ይህ የመግቢያ መጽሐፍ እንደ መሆኑ፥ የክርስትናን ሥነ-መለኮት ቅኝት ከባህላዊ የአፍሪካ ዕይታ አንጻር በማዛመድ ሊነበብ በሚችል መልኩ ያቀርባል። ይህንን ዓላማ በመንተራስ፥ የክርስትና እውነቶችን ከባህላዊ የአፍሪካ ሕይወት ዓውድ ጋር በሚዛመዱበት መልኩ ይዳስሳል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ሌሎች የሥነ-መለኮት ምሁራን የበለጠ ጥልቅ ምርምር ሊያደርጉባቸው የሚገቡ አንዳንድ ጉዳዮችም ይነሣሉ። በመሆኑም፥ ምናልባትም ይህ መጽሐፍ የአፍሪካ ደራሲያን የራሳቸውን የጥናት ውጤት እንዲህ በተጻፈ መልኩ እንዲያዘጋጁ ያነቃቃቸው ዘንድ ደራሲው ልባዊ ጸሎቱን ያቀርባል። እንዲሁም፥ በዚህ መጽሐፍ ያልተካተቱትን አስፈላጊ ጉዳዮች የማቅረቡም ጉዳይ ሊተኮርበት ይገባል።

ምንም እንኳ ይህ መጽሐፍ እያንዳንዱን የሥነ-መለኮት ጥያቄ ባይመልስም፥ ይብልጥ አስፈላጊና አስቸጋሪ የሆኑትን ጉዳዮች ለማቅረብ ጥረት ያደርጋል። ለተጨማሪ ምንባብ የሚረዱ መጻሕፍት ከእያንዳንዱ መጽሐፍ በስተ መጨረሻ ላይ ተጠቁመዋል። እነዚህም መጻሕፍት በተለይ የተመረጡት ለማንበብ ስለሚቀሉ፥ ወይም የርዕሰ-ጉዳዩን ጭብጥ በተሻለ ሁኔታ ስለሚሸፍኑ፥ ወይም ለአፍሪካ ዓውድ ልዩ ትኩረት ስለሚሰጡ ነው። አንባቢው እነዚህን መጻሕፍት ባቅራቢያው ከሚኖር የመጽሐፍ

ቅዱስ ኮሌጅ ቤተ መጽሐፍ ሊያገኝ የሚችል ከሆነ፥ አንዱን ወይም ሁለቱን ቢያነብ መልካም ነው።

በእያንዳንዱ ምዕራፍ መጨረሻ፥ ጥያቄዎችና የቡድን መልመጃዎች ተሰጥተዋል። እነዚህ የቤት ሥራዎች የተዘጋጁት የምዕራፉን እውነታ በአንባቢው አእምሮ ውስጥ ለመቅረጽ ነው። በመሆኑም፥ እነዚህ የምዕራፉ ከለሳዎች ብቻ ሳይሆኑ፥ እውነታን ከተጨባጭ የሕይወት ልምምዶች ጋር የሚያዛምዱ ናቸው። አንባቢው እነዚህን መልመጃዎች ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ቢሠራ መልካም ነው።

በአፍሪካ ቤተ ክርስቲያን በፍጥነት እያደገች ነው። አንዳንዶችም አህጉሪቱ በ2000 ዓ.ም. በዓለም ከሁሉም የምትልቅ ክርስቲያናዊት ክፍለ ዓለም እንደምትሆን ይናገራሉ። ምንም እንኳ አባባሉ እውነት ሊሆን ቢችልም፥ ብዙ የአፍሪካ ክርስቲያኖች አሁኑም ከባህላዊ ጥያቄዎችና ምላሽ ካላገኙላቸው ችግሮች ጋር በመታገል ላይ ናቸው። ይህ ግለት ግን ለጥያቄዎቹ ምላሾች የሉም ግለት አይደለም። ይልቁንም፥ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት፥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ሚሲዮናውያን የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ ከሚገኙ ሰዎች ልዩ ችግሮች ጋር ለማዛመድ አልቻሉም ግለት ነው። ስለዚህ የዚህ መጽሐፍ ዓላማ ለእንደዚህ ዓይነቶቹ ጥያቄዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መልሳቸውን መስጠት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ለሰው ልጅ ሁሉ የወረደ መገለጥ በመሆኑ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት የተዘጋጀው ለአንድ የሕዝብ ቡድን ብቻ አልነበረም። እግዚአብሔር «እናንተ የምድር ዳርቻ ሁሉ፥ እኔ አምላክ ነኝና፥ ከእኔም በቀር ሌላ የለምና ወደ እኔ ዘወር በሉ ትድኑማላችሁ» ይላል (ኢሳ. 45:22)። በመሆኑም፥ የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት በሁሉም ጊዜ ለሚኖሩ ሰዎች ሁሉ እንዲደርስ የታሰበ ነው። ይሁንና፥ ለእያንዳንዱ የሕዝብ ቡድን የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት እንግዳ ነገር መስሎ ይታያል - ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር የመጣ መገለጥ ነውና። እግዚአብሔር ሰዎች የታሉን መልእክት እንዲረዱ ስለሚፈልግ፥ መጽሐፍ ቅዱስ በዓለም ለያንዳንዱ የሕዝብ ቡድን ትርጉም መስጠቱ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው።

ይህ መጽሐፍ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ከአፍሪካ ሁኔታ አንጻር ለመግለጽ ይፈልጋል። በመሆኑም፥ ክርስቲያናዊ ሥነ-መለኮትን ከአፍሪካዊ

ዕይታ አንጻር ለማዳበር የተደረገ ጥረት ነው። ይህንንም ለማድረግ የሚከተሉትን ዋና ዋና ጥያቄዎች መመለስ ያሻል፡-

ሀ. የ«ንጽረተ-ዓለም» ትርጉም ምንድን ነው?

ለ. እውን ባህላዊ አፍሪካዊ ንጽረተ-ዓለም አለ?

ሐ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ሥነ-መለኮት እንዴት ልንገነባ እንችላለን?

መ. ከዚህ ቀደም መጽሐፍ ቅዱሳዊና አፍሪካዊ የሆነ ሥነ-መለኮት ለማዋቀር በተደረገው ጥረት ያጋጠሙ ችግሮች ምንድን ናቸው?

ሠ. እነዚህን ያጋጠሙንን ችግሮች በማሸነፍ፥ እውነተኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊና እውነተኛ አፍሪካዊ ሥነ-መለኮት ልንገነባ የምንችለው እንዴት ነው?

ሀ. «የንጽረተ-ዓለም» ትርጉም ምንድን ነው?

ከታሉ እንደምንረዳው፥ ንጽረተ-ዓለም አንድ ሰው ስለሚኖርባት ዓለም የሚኖረው ዕይታ ወይም አመለካከት ሲሆን፥ ይኸውም በእርሱና በሌሎች ላይ የሚደርሱትን ክስተቶች የሚረዳበትና የሚተረጉምበት፥ ብሎም ሕይወትንና የሚኖርባትን ዓለም የሚረዳበት መንገድ ነው። እንደዚሁም አንድ ሰው እውነት ስለ ሆነውና እውነት ስላልሆነው ነገር የሚኖረው እምነት ማለት ነው።

በዓለም የተለያዩ የሕዝብ ቡድኖች የተለያዩ አመለካከቶች አሉአቸው። አንድ ዓይነት ቋንቋ ቢናገሩም እንኳ፥ ሕይወትን የሚረዱበትና የሚገልጹበት መንገድ አንዱን ለሌላው እንግዳ ያደርገዋል። አንድ ሰው የያዘው የዓለም አመለካከት በሚኖርበት የሕዝቦች ቡድን አስተሳሰብ ላይ ይመሠርታል። ባደገበት ኅብረተሰብ፥ ባስተማረው ቤተሰብና መምህራን አመለካከት ላይ ይመሠረታል። የአንድ ሕዝብ ንጽረተ-ዓለም የተመሰኑ የሕዝብ ቡድኖች ለምን አኗኗራቸውን እንደዚያ እንደሚያደርጉ ለመረዳት አንድ ቁልፍ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስም የራሱ የሆነ የዓለም አመለካከት አለው። መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የተላከ መገለጥ ስለ ሆነ፥ አመለካከቱ ትክክለኛ የእውነታ ዕይታ ነው። አንድ ሰው የእግዚአብሔርን እውነት በትክክል እንዲረዳ ከተፈለገ፥ ከራሱ አመለካከት ጋር የሚቃረኑ አንዳንድ ነገሮች ቢኖሩበትም እንኳ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የቀረበውን አመለካከት

መቀበል አለበት። በዚህ መጽሐፍ የመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት ከተለያዩ የሰብአዊ ልምምድ ገጽታዎች አኳያ ይቀርባል።

ለ. እውን ባህላዊ አፍሪካዊ ንጽረተ-ዓለም አለ?

በዓለም ሁሉም የሕዝብ ቡድን የራሱ የሆነ አመለካከት አለው። ይህም ሊወርድ ሊዋረድ በመጣው ባህል ላይ የሚደገፍ ነው። የተለያዩ የሕዝብ ቡድኖችን ከግጥናት እንደምንረዳው፥ በበርካታ አፍሪካዊ ባህላዊ ቡድኖች መካከል አንዳንድ ጠንካራ ተመሳሳይነቶች አሉ። ብዙ ሰዎች የአንድ ወይም የሌላ አገር ዜጋ ከመሆን ይልቅ፥ አፍሪካዊ የመሆን ጠንካራ ስሜት ይሰማቸዋል። ከእነዚህ ተመሳሳይነቶች አንዳንዶቹ ምንድን ናቸው?

የመጀመሪያው የጋራ ልምምድ፥ በማኅብረሰቡ ውስጥ ከተመሳሳይ ቤተሰብና ጎሳ ለተስፋፉ ሌሎች ሰዎች የሚሰጥ አጽንኦት ነው። አፍሪካውያን የተስፋፋው ቤተሰብ፥ ጎሳና ነገድ አካል በመሆን ማንነታቸውንና የሕይወትን ትርጉም ወደ ግግኘቱ ያዘነብላሉ። በሕይወት ውስጥ ለጋራ ተሳትፎ፥ ለጋራ ታሪክና ለጋራ ፍጻሜ ጠንካራ ስሜት አላቸው። በአፍሪካ ያለው እውነታ «እኔ የምኖረው ማኅበረሰቡ ስላለ ነው» ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። ስሜቱ ከሌሎቹ ቡድኖች በላይ በአንዳንዶቹ የበለጠ ሊጠነክር ቢችልም፥ በሁሉም ዘንድ በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው።

ቀጣዩ ተያያዥ አሳብ በሕያዋንና በሙታን መካከል የሚኖረው ግንኙነት ነው። የማኅበረሰቡ አባል የመሆኑ አንዱ ግረጋገጫ፥ አንድ ሰው ከዚህ ቀደም ከሞቱት ሰዎች ጋር የሚኖረው ግንኙነት ነው። አብዛኛዎቹ የባህላዊ አፍሪካዊ ሕዝቦች ቡድኖች ከቅድመ-ትውልዶቻቸው መናፍስት ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነት በጣም አስፈላጊ እምነቶች አሉአቸው።

ሦስተኛው የጋራ አሳብ ስለ መናፍስት ዓለም ያላቸው ግንዛቤና፥ እንዲሁም በመናፍስት ዓለምና በሥጋዊ ዓለም መካከል ስላለው ግንኙነት የሚወስዱት ተመሳሳይ አቋም ነው። እያንዳንዱ አፍሪካዊ የእግዚአብሔርን መኖር ያውቃል። እንዲሁም፥ በዙርያው የመናፍስት ዓለም እንዳለ ያምናል። በባህላዊቷ አፍሪካ በሥጋዊ ዓለምና በመንፈሳዊ ዓለም መካከል የሚኖረው የግንኙነት ስሜት ጠንካራ ነው።

አራተኛው የጋራ ነጥብ ከሕይወት ቀዳሚ ነገሮች ጋር ይያያዛል። አፍሪካውያን ከቴክኖሎጂና ከቁሳዊ ነገሮች ይልቅ፥ ለሰዎችና ለሰብአዊ ግንኙነቶች የላቀ ቅድሚያ ወደ መስጠቱ ያዘነብላሉ።

ለብዙ የአፍሪካ ሕዝቦች የጋራ የሆነው አምስተኛው ነጥብ፥ የቅኝ አገዛዝና በኋላም የተገኘው የነፃነት ታሪክ ነው።

ስድስተኛው ሕይወትን በጅምላ የመመልከቱ ጉዳይ ነው። ይህም ማለት የሕይወት የተለያዩ ክፍሎች ልክ እንደ እንድ ሸማ ድርና ማግ በመሆን ወደ አንድነት ይመጣሉ ማለት ነው። ሕይወት ወደ ተለያዩና ወዳልተያያዙ ክፍሎች አትከፋፈልም። ሁሉም አካላት በአንድነት ሕይወት የተባለ ውብ ገጽታ ይመሠርታሉ።

ሰባተኛው አሳብ የሕይወትን ክስተቶች፥ በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ እንደሚታየው የመርሐ-ግብሮችና የጊዜ አትኩሮት ውጤቶች አድርጎ ከማየት ይልቅ በዘፈቀደ እንደሚፈጸሙ የመቁጠር ጉዳይ ነው።

ሌሎችም ለአፍሪካ ሁኔታ በጋርዮሽ የሚዛመዱ ጉዳዮች አሉ፤ ይሁንና፥ እነዚህ ሰባቱ የክርስትናን ሥነ-መለኮት ከባህላዊ አፍሪካዊ ዕይታ አንጻር ለመጻፍ በቂ ምክንያቶች ናቸው።

ሐ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ሥነ-መለኮት እንዴት ልንገነባ እንችላለን?

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥነ-መለኮት ማለት አንድ ሰው በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ውስጥ አንድን የተወሰነ ርዕሰ-ጉዳይ በሚጋፈጥበት ጊዜ፥ መጽሐፍ ቅዱስ በዚያ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ትምህርት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በአንድ በተወሰነ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ የሚሰጠውን ትምህርት ለማጽናት ሦስት ደረጃዎች ያስፈልጋሉ፦

በመጀመሪያ፥ ርዕሰ-ጉዳዩ በተጠቀሰባቸው ስፍራዎች ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚያ ርዕሰ-ጉዳይ የሚናገራቸውን ነገሮች በጥንቃቄ መመልከት አለብን።

ሁለተኛ፥ ርዕሰ-ጉዳዩን በተመለከተ እነዚህ ሁሉ አሳቦች ምን እንደሚሉ መወሰን አለብን። ይህም የሚከናወነው እያንዳንዱን ዓረፍተ ነገር ከትክክለኛ የሰዋሰው ግምገማ አኳያ በጥንቃቄ በመመርመር ነው። ከዚያም እያንዳንዱን ዓረፍተ ነገር ዓረፍተ ነገሩ ከተዋቀረበት ታሪካዊ ሁኔታ አኳያ መገምገም አለብን። ይህንንም በመከተል፥ በርዕሰ-ጉዳዩ ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ አስተምህሮ ምን እንደ ሆነ ለመረዳት፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለርዕሰ-ጉዳዩ የሚናገሩትን የተለያዩ ዓረፍተ ነገሮች እርስ በርሳቸው ማወዳደር አለብን። ብዙ ስሕተቶች የተፈጸሙት

አንድን ጥቅስ ከዓውደ-ንባቡ ነጥሎ በማውጣት፥ ወይም ያ ጥቅስ በዚያው ርዕሰ-ጉዳይ ላይ ከሌሎች ጥቅሶች ጋር እንደሚዛመድ ካለማስተዋል ነው።

ሦስተኛ፥ መጽሐፍ ቅዱስ በርዕሰ-ጉዳዩ ላይ የሚያቀርበውን ትምህርት ከዛሬው ሕይወት ጋር ማዛመድ አለብን። አንድ ሰው እነዚህን ሦስት ደረጃዎች በጥንቃቄ ከተከተለ፥ እውነተኛ የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርትና እግዚአብሔር በሕይወቱ (ወይም በሕይወታ) እንዴት እንዲጠቀምበት እንደሚፈልግ ያውቃል። በዚህም መጽሐፍ ውስጥ እነዚህኑ ሦስት ደረጃዎች ተከትለን እናጠናለን።

መ. ከዚህ ቀደም መጽሐፍ ቅዱሳዊና አፍሪካዊ የሆነ ሥነ-መለኮት ለማዋቀር በተደረገው ጥረት ያጋጠሙ ችግሮች ምንድን ናቸው?

ከ1960 ዓ. ም. በፊት የነበረው ዐቢይ ችግር፥ የክርስትናን ሥነ-መለኮት ከአፍሪካ ዓውድ ጋር ለማዛመድ የተደረገው ጥረት እጅግ አናሳ መሆኑ ነበር። ብዙ አፍሪካውያን በሥነ-መለኮት ትምህርቱ ውስጥ በማስረሻነት ምዕራባዊ ጉዳዮችን ብቻ ማቅረቡ ጥልቅ ጥያቄዎቻቸውን እንዳልመለሰ፥ ወይም ከአፍሪካ ባህል ጋር የተቆራኙትን አንዳንድ መንፈሳዊ ችግሮቻቸውን አንዳልፈታ ተገነዘቡ። ብዙውን ጊዜ ምዕራባዊ የአስተሳሰብና የትምህርት ዘዴዎች ከአፍሪካ መንገዶች ጋር አልተዛመዱም ነበር።

ከዚህም የተነሣ ብዙ አፍሪካውያን ሥነ-መለኮትን ለሰው ልጅ ሁሉ የሚያስፈልግ አጽናፈ-አቀፋዊ ሳይሆን (እውነቱ ይኼ ሆኖ ሳለ)፥ ምዕራባዊ ፍልስፍና አድርገው ተረጎሙት። ታሪካዊው እውነታ ግን ሥነ-መለኮት ወደ አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ ከመምጣቱ በፊት ወደ አፍሪካ እንደ ደረሰ ነው። ይህም በሐዋርያት ሥራ 8:27-39 ከኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ሕይወት ሊታይ ይችላል።

የምዕራቡን ሥነ-መለኮት ድካም ለማስተካከልና እውነተኛ አፍሪካዊ ሥነ-መለኮት ለመፍጠር፥ ላለፉት ሃያ አምስት ዓመታት የተለያዩ አሳቦች ቀርበዋል። ለአፍሪካ ባህላዊ ሕይወት ከፍተኛ ትኩረት ለመስጠት፥ አንዳንዶቹ የአፍሪካን ባህላዊ ሃይማኖቶች አሳቦች ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ጋር ለማገናኘት ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። ይህም ሂደት «ሲንክርቲዝም» ተብሎ የሚጠራውን ቅይጥ አምልኮ አስከተለ። ቅይጥነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ከሆነ ሥነ-መለኮት ውስጥ ሊበቅል አይችልም። ወደ

እውነት ለመድረስ የእግዚአብሔር ቃል ከሌሎች ሃይማኖታዊ እምነቶች ጋር መቀላቀል የለበትም።

የተፈለገው የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ከሌሎች ሃይማኖቶች ጋር መቀላቀል ሳይሆን፥ ዳሩ ግን የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ከአፍሪካ ሕይወትና ልምምድ ጋር በሚዛመድ መልኩ ማቅረብ ነው። በሌላ አባባል፥ ሥነ-መለኮት እውነተኛ ክርስቲያናዊና በተጨማሪም በአገላለጽ እውነተኛ አፍሪካዊ መሆን አለበት። ይህ ሁኔታ ቀደም ብሎ በሥራ ላይ የመታየቱን ምሳሌ የምንመለከተው፥ በተለያዩ የቤት ክርስቲያን ቡድኖች ከተቀነባበረው አገርኛ ክርስቲያናዊ መዝሙር ነው።

ሠ. እነዚህ ያጋጠሙንን ችግሮች በማሸነፍ፥ እውነተኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊና እውነተኛ አፍሪካዊ ሥነ-መለኮት ልንገነባ የምንችለው እንዴት ነው?

ምዕራባዊውን የሥነ-መለኮት ተጽእኖ ለማቃለልና የቅይጥነትን አደጋ ለማስወገድ፥ ሦስት የሂደት ደረጃዎች በመፍትሔነት ቀርበዋል፡-

1. በመጀመሪያ፥ «መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ ምን ይላል?» ብለን መጠየቅ አለብን?

2. ሁለተኛ፥ «መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ ከሚናገረው ጋር የአፍሪካ ባህል እንዴት ይዛመዳል?» የሚለውን ጥያቄ ማስከተል አለብን። በሌላ አባባል፥ ከዚህ ርዕሰ-ጉዳይ ጋር የሚያያዙ ትክክለኛ የአፍሪካ እምነቶችና ልምምዶች ምንድን ናቸው?

3. ሦስተኛ፥ «መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ የሚናገረውን አሳብ ከአፍሪካ ባህል ጋር በግልጽ በሚዛመድ መልኩ እንዴት ልንገልጸው እንችላለን?» የሚለውንም ጥያቄ ማከል አለብን።

በዚህ መጽሐፍ የእነዚህን ሦስት ጥያቄዎች መመሪያዎች እንከተላለን።

ሕይወትን ለመለወጥ፥ ሥነ-መለኮትን ከባህላዊ ተዛማጅነት አኳያ ማቅረቡ ወሳኝ ነው። ከዕለታዊ ሕይወትም ጋር ሊዛመድ ይገባል። የእግዚአብሔርን እውነት ከአካባቢው ባህል ጋር የማዛመዱ ተግባር፥ «አካባቢያዊነት» (“contextualization”) ይባላል። ዛሬ በአፍሪካ የአካባቢያዊነትን ፍልስፍና ተግባራዊ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው።

ከፍተኛ ውጤት ለማግኘት፥ 'አካባቢያዊነት ሂደት የሚከተሉትን ደረጃዎች ማጠቃለል አለበት፡-

1. መፍትሔ የሚያሻውን ባህላዊ ችግር ወይም ጉዳይ ደንግግ (ፍች ስጥ)።

2. መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጉዳይ ምን እንደሚል በግልጽ ተረዳ።

3. ባህሉ ስለ ጉዳዩ ምን እንደሚልና ምክንያቱም ምን እንደ ሆነ ለይተህ እወቅ።

4. በጉዳዩ ላይ በመጽሐፍ ቅዱሳዊና አካባቢያዊ ሁኔታ መካከል፥ ምን ምን ባህላዊ ተመሳሳይነቶች ወይም ልዩነቶች እንዳሉ ወስን።

5. መጽሐፍ ቅዱስ በጉዳዩ ላይ የሚለውን እንዴት ከባሕልህ ጋር እንደምታዛምድ ወስን።

6. በጉዳዩ ላይ የእግዚአብሔርን አመለካከት ለመልመድ፥ ሕዝቦችህ እንዴት አመለካከታቸውንና እምነቶቻቸውን እንደሚቀይሩ ወስን።

7. ሕዝቦችህ በጉዳዩ ላይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ልምምዳቸውን እንዴት እንደሚለውጡ ወስን።

8. ሕዝቦችህ አስፈላጊውን ለውጥ እንዲያደርጉ ለመረዳት ምን ማድረግ እንዳለብህ ወስን።

9. ሕዝቦችህ ችግሩን ለማስወገድ እንዲችሉ ለመርዳት፥ ቤተ ክርስቲያንህ ምን ዕቅድ ልታወጣ እንደምትችል ወስን።

መጋቢያንና ክርስቲያን መሪዎች በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናታቸው እነዚህን ደረጃዎች ቢጠቀሙ፥ ምእመኖቻቸው ከጌታ ጋር በሚኖራቸው ጉዞ አዲስ መንፈሳዊ ጉልበት፥ ጥንካሬና ተሐድሶ ሊያገኙ ይችላሉ።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያለው የቀን አቆጣጠር እንደ ኤሮፓውያን ቀን አቆጣጠር ነው።

ምዕራፍ 1

ማንን እና ምንን እንመን?

አውጅና ሞብዋኒ ወደ መምህራን ኮሌጅ ከገቡበት ጊዜ አንሥቶ መልካም ጓደኞሞች ሆነዋል። በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ያደጉ ሲሆን የኖሩትም ባህላዊ ሃይማኖትን በሚከተሉ ቤተሰቦች መካከል ነበር። አንዳንድ የኮሌጅ ጓደኞቻቸው ቤተ ክርስቲያን ይካፈሉ ነበርና፥ ወደ ኮሌጅ ከመጡበት ጊዜ አንሥቶ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዱ ነበር። ዛሬ የሚወያዩት ከክርስቲያን ጓደኞቻቸው በተማሩዋቸው አንዳንድ አዳዲስ አሳቦች ላይ ነው።

አውጅ፡- «ክርስቲያን ጓደኞቻችን ስለ እምነታቸው ብዙ እንደሚናገሩ አስተውያለሁ። አንድ ሰው የሚያምነው ነገር በጣም አስፈላጊ እንደ ሆነ የሚያምኑ ይመስላል።»

ሞብዋኒ፡- «እኔም ይህንኑ አስተውዬ በሚናገሩአቸው አንዳንድ ነገሮች ግራ ተጋብቻለሁ። እውን አንድ ሰው የሚያምነው ነገር ምንስ ቢሆን በሕይወቱ ላይ ለውጥ ያመጣ ይሆን? ለእኔ እንደሚመስለኝ፥ የምትሠራው ነገር ከምታምነው የበለጠ አስፈላጊ ነው።»

አውጅ፡- «እኔም በዚህ አሳብ እስማማለሁ። ግን ሰዎች የሚያደርጉትን ነገር የሚያደርጉት ለምንድን ነው? ከሚያምኑት ነገር የተነሣ አይደለም? ለምሳሌ አባቴንና እኅቴን ውሰድ። አባቴ በሚታመምበት ጊዜ ሁልጊዜም ወደ ጠንቋይ ቤት እንጂ፥ ምን ቢደረግ ወደ ሆስፒታል አይሄድም። እንግዲህ አባቴ ወደዚያ የሚሄደው በሽታውን ማን እንደሚያመጣበት ካለው እምነት የተነሣ አይደለምን?

«አኅቴ ደግሞ የሕክምና ሥልጠና ተቀብላለች። ስለ ሆነም፥ በታመመ ጊዜ ሁሉ ወደ ሆስፒታል ወይም ወደ መድኃኒት መደብር ይሄዳል። በሽታውን ምን እንደሚያመጣውና እንዴትም ከበሽታው እንደሚድን የሚያስረዳው እምነቱ ከሥልጠናው የተገኘ ነው።»

ሞብዋኒ፡- «ምናልባት ትክክል ልትሆን ትችላለህ። ክርስቲያኖች ሰው ሲሞት ለሚከናወኑ ሥነ-ሥርዓታዊ ተግባራት ለምን ግድ እንደሌላቸው በማሰብ እደነቅ ነበር። ባለፈው ዓመት አንድ ዘመዳችን ሲሞት፥ አባቴ ዘመድ ሲሞት የሚሰጠውን የፍየልና የዶሮዎች መሥዋዕት አቅርቦ ነበር።

በተጨማሪም፥ ምንም እንኳ ጊዜው የአዝመራ መሰብሰቢያ ወቅት ቢሆንም፥ ይህንኑ መሥዋዕት ለማድረግ የሦስት ቀናት ሥርዓታዊ ጉዞ ወደ ተራሮች አሻቅቦ ወጥቷል። ክርስቲያኖች ጊዜውን በከንቱ ከሚያጠፋ እርሻውን ቢቀጥል ይሻላል አሉ። በመሆኑም፥ አንድ ሰው የሚያምነው ነገር በተግባራቱ ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል የሚለው እውነት ይመስላል። ይሁንና፥ አንድ ሰው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ፥ ምን ማመን አለበት?»

በዚህ ምዕራፍ፥ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ እንሻለን፦

ሀ. በአንድ ነገር ወይም ሰው ማመን ሲባል ምን ማለት ነው?

ለ. እውነት ምንድን ነው?

ሐ. እውነትን ከወዴት ልናገኝ እንችላለን?

መ. የምናምነው ነገር በተግባራችን ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድረው እንዴት ነው?

ሠ. እውነት የሆነውን ነገር ስታምን ምን ይከሰታል? ውሸት የሆነውንስ ስታምን?

ረ. ማንን እንመን?

ሀ. በአንድ ነገር ወይም ሰው ማመን ሲባል ምን ማለት ነው?

ከላይ በተከታተልነው ውይይት ውስጥ፥ የአውጀ አባት ጠንቋይ በሽታችውን ለማዳን በመቻሉ ያምናሉ። በተቃራኒው፥ የአውጀ አጎት በሠለጠኑ የሕክምና ባለሙያዎችና በመድኃኒቶቻቸው ኃይል ያምናሉ፤ የሁለቱም አቋም እምነታቸውን ከመደገፍ የመነጨ ነበር። አንደኛው በጠንቋይ ላይ ሌላኛው እምነታቸውን በሕክምና ዶክተር ላይ አድርገዋል። ይሽውም በበሽታቸው ጊዜ ሊረዱዋቸው እንደሚችሉ ነው። የሁለቱም እምነት የመጣው ከሌሎች ሰዎች ከተማሩት ነው። የሁለቱም እምነት ወደ ተወሰኑ ተግባራት መርቶአቸዋል።

ተግባራታቸውም ባመኑት ሰው ችሎታና ኃይል መተማመናቸውን ያሳያል። በአንድ ሰው በምናምንበት ጊዜ ያ ሰው እንደሚረዳን እንተማመናለን። በወንበር ላይ የመቀመጥ ምሳሌ በአንድ ነገር ላይ ስለ መደገፍ ቀላል ግብራርያ ይሆንልናል። አንድ ሰው ወንበሩ እንደሚሸከመው እስካላመነ ድረስ፥ በወንበሩ ላይ አይቀመጥም። አንዳንድ

ሰዎች እምነታቸውን በሰባራ ወንበር ላይ በማስቀመጣቸው ሊወድቁ አዝነው ተመልሰዋል። በችግርህ ጊዜ እንዲረዳህ ትክክለኛ ባልሆነ ሰው ላይ እምነትህን ስትጥልና ያም ሰው ሳይረዳህ ሲቀር፥ ምንኛ የባሰ ኃዘን ይገጥምሃል?

አስተዋይ ከሆንህ፥ እምነት እንደሚጣልበት መረጃ በሰጠህ ሰው ላይ ብቻ እምነትህን ትጥላለህ። በአውሮፕላን መጓዝን በምሳሌነት ተመልከት፦ ወደ አውሮፕላኑ ከመግባትህ በፊት፥ በአውሮፕላኑም በነጂውም ላይ እምነት ሊኖርህ ይገባል። አውሮፕላኑ እንደሚበርርና ነጂውም አውሮፕላኑን ሊያበር እንደሚችል ማመን አለብህ። ምናልባትም እምነትህ የተመሠረተው በአውሮፕላን ነጂው የደኅንነት ሪኮርድና የአውሮፕላኑ ባለቤት በሆነው አየር መንገድ ላይ ይሆናል። ይሁንና፥ የአውሮፕላኑና የአውሮፕላን አብራሪው አስተማማኝ መሆን ወይም አለመሆን የሕይወትና የሞት ጉዳይ ሊሆን ይችላል።

በግል ችግርህ ጊዜ እንደሚረዳህ ልትታመንበት የምትችለው ሰው ምንኛ አስፈላጊ ነው! በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአትህን እንደሚያስተሰርይልህ ልትታመንበት የምትችለው መኖሩ ምንኛ አስፈላጊ ነው!

እውን ሰዎችን በችግራቸው ጊዜ ሊረዳቸው የሚችለው ማን ነው? ጸሎታቸውን የመመለስ ኃይል ያለው ማን ነው? የሰዎችን ኃጢአቶች ይቅር ብሎ የዘላለምን ሕይወት ሊሰጣቸው የሚችል ማን ነው? ሰዎች በማን ሊያምኑና ከመራራ ኃዘን ሊጠበቁ ይችላሉ? ሁሉም ሰው የእምነት ዘይቤ አለው። ጥያቄው ግን የእምነቶችህ ውጤቶች ምን ያስከትላሉ የሚለው ነው። እምነትህ ዘላለማዊ ሕይወት ያስከትል ይሆን ወይስ ዘላለማዊ ሞት?

የሰው እምነት ማረጋገጫ የሚመጣው በችግር ቀን ነው። አንድ ሰው ትልቅ ችግር በሚያጋጥመው ወቅት ፊቱን የሚመልሰው እውነተኛ እምነት ወደ ጣለበት ሰው ወይም ነገር ነው።

ሁሉም ሰው በአንድ ነገር ወይም በአንድ ሰው ያምናል። ለብዙ ሰዎች እምነታቸው የመነጨው ከሌሎች ሰዎች ከሰሙት ነገር ነው። ብዙ ጊዜ የተናገሩአቸው ሰዎች ራሳቸው በመታለል እውነቱን ሳያውቁት ይቀራሉ። ስለ ሆነም፥ እውነቱን ማመን በጣም አስፈላጊ ነው። ይሁንና፥ እውነቱ ምንድን ነው? ከሁሉም የሚልቀው እውነታ ምንድን ነው?

ለ. እውነት ምንድን ነው?

እውነት ውሸት ወይም ስሕተት ከሆነው አሳብ በተቃራኒ የሚታይ ትክክለኛ ነገር ነው። እውነት የሕይወትን የመጨረሻ እውነታዎች የሚመለከት አሳብ ነው። እውነት ከመጨረሻው የላቀ እውነታ ጋር ስለሚሄድ፥ የሰውን ፍጻሜ ይወስነዋል።

አንዳንድ ሰዎች አንድ ነገር በከፍል መምህር አፍ ከተነገረ ወይም በመጽሐፍ ውስጥ ከተጠቀሰ እውነት እንደ ሆነ ያስባሉ። የሚያሳዝነው ግን ሁልጊዜም እንደዚያ አለመሆኑ ነው። አንዳንድ ጊዜ መምህሩም ራሱ ስሕተት የሆነውን ትምህርት ይቀበልና ለሌሎችም ይህንኑ ስሕተት ያስተምራል። አንዳንድ ጊዜ ጸሐፊው ራሱ እውነቱን ስለማያውቅ፥ መጻሕፍቱም እውነት ያልሆነውን አሳብ ያቀርባሉ። በሌላ ጊዜም ሰዎች ሆን ብለው ሌሎችን ለማታለል ይሞክራሉ።

ከዚህ በታች እውነት ባለመሆኑ ያመኑበትንም ብዙ ሰዎች የነዳ አንድ ምሳሌ ቀርቦአል። በበርካታ አውሮፓውያንና አሜሪካውያን ምሁራን ዘንድ፥ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው ሳይሆን፥ የትክክለኛና ስሕተተኛ ነገር ፍጹማዊ መመዘኛዎች የሉም የሚል እምነት ይታያል። እነዚህም ሰዎች እግዚአብሔር ለባሕርያቸው በኃላፊነት እንደሚጠይቃቸው አያምኑም። ከራሳቸው አሳብ ባሻገር፥ ስሕተትና ትክክል የሆነውን ነገር ለመለካት መመዘኛ የላቸውም። ትክክልና ስሕተት ስለ ሆነው ነገር የራሳቸውን ደንቦች ያወጣሉ።

እነርሱ የሚያወጡአቸው ደንቦች በግል ሊያደርጉአቸው የሚፈልጉአቸው ነገሮች ናቸው። ዛሬ በሰሜን አሜሪካ እንዲህ የሚል አንድ የታወቀ አባባል አለ፡- «መልካም መስሎ ከተሰማህ አድርገው።» ይህንኑ የሞኝነት አሳብ መከተል በአውሮፓና አሜሪካ የከፋ ወሲባዊ ኃጢአት አስተከትሏል። በምዕራቡ ማኅበረሰብ ውስጥ የቤተሰብን መፈራረስ አንሰራፍቷል። ሰዎች እግዚአብሔር ለባሕርያቸው በኃላፊነት እንደሚጠይቃቸው ስለማያምኑ፥ ቤተሰቦች በዝሙት ፍች ጦስ በመለያየት ላይ ይገኛሉ። ከእግዚአብሔር እውነት ይልቅ በራሳቸው አሳቦች ያምናሉ። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «በገዛ ልቡ የሚታመን ሰው ሰነፍ ነው» ይላል (ምሳሌ 28፡26)። ይህ ጥቅስ ዛሬ በብዙ የዓለም ክፍሎች እውነትነቱን እያስመሰከረ ነው።

ሐ. እውነትን ከወዴት ልናገኝ እንችላለን?

አንድ ሰው እውነትን እንዳመነ እርግጠኛ የሚሆነው እንዴት ነው? ከዚህ በፊት፥ አፍሪካውያን ምን እንደሚያምኑ ለመወሰን የሕዝቦቻቸውን ባህል መለስ ብለው ይመለከቱ ነበር። በበርካታ ባህላዊ አፍሪካዊ ማኅበረሰቦች ውስጥ፥ የእውነት አሳብ፥ ከሽማግሌዎች ወይም ከጎሳው ቅድመ-ወላጆች ሕይወትና ሰብአዊ ልምምዶች ጋር በተያያዘ መልኩ፥ ከአንዱ ትውልድ ወደ ሌላው ሊወርዱ ከመጡ ተረቶችና አፈ ታሪኮች ጋር የተያያዘ ነው። በዘመናዊቷ አፍሪካ፥ ይህንን ወይም ያንን እናምናለን ብለው የሚጋገቱ በተለይም ብዙ አዳዲስ የፖለቲካ ድምፆች ይደመጣሉ። ዛሬ ለአፍሪካውያን ብዙ የማሳመኛ አሳቦች ይቀርቡላቸውል።

በተጨማሪም፥ አያሌ ሃይማኖቶች የራሳቸው የሆኑ የተቀደሱ ጽሑፎች አሉአቸው። እንዲሁም ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔር ነቢያት እንደ ሆኑ ይናገራሉ። በእውነቱ ትክክለኛው ማን ነው? እውነቱን በርግጠኝነት የምንለይበት መንገድ ይኖር ይሆን?

ኢየሱስ፥ «እኔ ለእውነት ልመሰክር ስለዚህ ተወልጃለሁ» ብሏል (ዮሐ. 18፡37)። ኢየሱስ ይህንን ሲናገር፥ የሮም ባለሥልጣን የሆነው ጴንጤናዊው ጲላጦስ፥ «እውነት ምንድን ነው?» ሲል ጠየቀው (ቁ. 38)። ጲላጦስ ከሁሉም ስለ ላቀው የመጨረሻ እውነታ እየጠየቀው ነበር። የፖለቲካ ሰው እንደ መሆኑ፥ ጲላጦስ ብዙዎቹ ሰዎች እንደ ራሱ ውሸታሞች እንደ ሆኑ ያውቅ ነበርና፥ ኢየሱስ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው እውነቱን ብቻ እንደሚናገር ለማመን ከበደው።

ኢየሱስ ለእውነት ሊመሰክር እንደ መጣ ነገረው። እንዲሁም፥ «እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ» ብሏል (ዮሐ. 14፡6)። አክሎም፥ «በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» ብሏል። ኢየሱስ እንዲህ ዓይነቱን አባባል ሊያረጋግጥልን ይችል ይሆን?

ኢየሱስ ትክክል ከነበር፥ ሌሎች የሃይማኖት መሪዎችና በርካታ የጎሳ መሪዎችም ሳይቀሩ በስሕተት ጎራ ይገኛሉ ማለት ነው - ኢየሱስ ለእነርሱ ሌላ ዕድል እንደሚኖራቸው አልገለጠም ነበርና። በዮሐንስ 10፡8 ላይ ኢየሱስ፥ «ከእኔ በፊት የመጡ ሁሉ ሌቦችና ወንበዴዎች ናቸው . . . በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል» ብሏል። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እግዚአብሔር አብ የሚያደርስ መንገድ ነው? እውን ሕይወትን የሚሰጠው እርሱ ብቻ ነው? የክርስቶስን አባባሎች እንዴት ልንፈትን እንችላለን?

የአንድን ሰው የባሕርይ መልካምነትና ጥንካሬ እንዴት ለመፈተን ይቻላል? መልካም ባሕርይና ለበጎ ምግባር ተጠናክሮ መነሣት በጣም አስፈላጊዎች ናቸው። በታሪክ እውን በባሕርዩ ፍጹም የነበረው ማን ነው? በታሪክ ኃይሉን ሌሎችን ለመርዳት ብቻ የተጠቀመው ማን ነው? በችግሬ ጊዜ እኔን ለመርዳት ኃይል ያለው ማን ነው? ጸሎቶቼን ለመመለስ ኃይል ያለው ማኒ ነው?

በአፍሪካ ኃይል አስፈላጊ ነው። እንዲሁም፥ ኃይል ሰዎችን ሊያታልል ይችላል። ምትሐታዊ ተግባራትን ለማከናወን ወይም ርግማንን ለማወጅ ኃይል የሚጠቀሙ ሰዎችም አሉ። አንዳንዶች በሽታን የመፈወስ ኃይል አላቸው። እንግዲህ እንዲህ ዓይነት ሰዎች ኃይል አላቸው። ይሁንና፥ ኃይላቸውን የሚጠቀሙት እንዴት ነው? ኃይላቸውን ለሌሎች ለሚበጅ ተግባር ብቻ ይሆን የሚጠቀሙት? ወይስ ለራሳቸው ጥቅም፥ ወይም ገንዘብ ለማግኘት? ባሕርይና ኃይል የሚፈተነው እንግዲህ በዚህ ነው።

የእግዚአብሔር ኃይል ከማንኛውም ሌላ ኃይል እንደሚልቅ ሁሉም ይረዳዋል። ይሁንና፥ እግዚአብሔር ኃይሉን የሚጠቀመው ለሰው ለሚበጅ ተግባር ነው። አንድ ሰው ከእግዚአብሔር እውነቱን እንደ ተቀበለ ቢናገር፥ ኃይሉን የሚጠቀመው ለሌሎች ለሚበጅ ተግባር እንጂ፥ ለራሱ ጥቅም እንዳልሆነ የሚያመለክት መረጃ ማግኘት አለብን። በታሪክ እንዲህ ዓይነት ሰው ታይቶ ያውቃል? ማን እውነት እንዳለው ለማወቅ፥ እስኪ ኢየሱስ ከርስቶስን ከሌሎች እውነትን እንደሚያስተምሩ ከሚናገሩ ሰዎች ጋር በአጭሩ እናነጻጽር። እስኪ ኃይሉን ለሌሎች ለሚበጅ ተግባር ብቻ ማን እንዳዋለው እንመልከት። እስኪ ጸሎት የመመለስ ኃይል ያለው ማን እንደ ሆነ እንመልከት።

ኢየሱስ ከሌሎች የሃይማኖት መምህራን ጋር ሲወዳደር

በታሪክ ከድንግል የተወለደ ሌላ ሰው ማን ነበር? እንደ ኢየሱስ ለሌሎች የሚበጅ ተግባር የፈጸመና ኃጢአት የሌለበትና ፍጹም ሕይወት የኖረው ሌላ ሰው ማን ነው? የሚንጹው እምነት ከሪሽና ለተከታዮቹ ግዕበሱንና ሞገሱን ጸጥ ያሰኘው መቼ ነበር? መምህር ኮንፊዩሽዩስ ትምህርቱን ለሚከታተሉ ከ5000 ለሚበዙ ወንዶችና ሴቶች እንጀራ አጥግቦ ያስተረፋቸው መቼ ነበር? የቻይናው ግኦ ስቱንግ የሚጥል በሽታ ያደረበትን ሰው የፈወሰው መቼ ነበር? ማርክስ ወይም ሌኒን የመበለቲቱን ብቸኛ ልጅ ከሙታን ያስነሡት መቼ ነበር?

ከኢየሱስ በስተቀር በታሪክ የተጠቁትን ሰዎች የእርዳታ ጣር ጩኸት ሰምቶ የመለሰ ማን ነበር? ከአብዱ ሰው እጅግ በርካታ አጋንንት አውጥቶ ጨንቱን የመለሰለት የትኛው ነቢይ ነበር? የሰርግ ሥነ-ሥርዓታቸውን ለሚያከብሩ ሙሽሮች ደስታ ይሆን ዘንድ፥ ስድስት የድንጋይ ጋኖች ውኃ ወደ ወይን ጠጅ የለወጠው የትኛው መምህር ወይም ሃይማኖታዊ መሪ ነበር? መሐመድ ለሰው ልጆች ኃጢአት የሞተው መቼ ነበር? መሐመድ ለሰዎች ዘላለማዊ ሕይወት ለመስጠት ከሙታን የተነሣው መቼ ነበር?

የእነዚህ ጥያቄዎች መልሶች ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ከኖሩት ሰዎች ሁሉ እንደሚለይ ያሳያሉ። ከኢየሱስ በቀር እነዚህን ነገሮች ያደረገ ግንም አልነበረም። በበሽታ፥ በኃዘንና ሞት ላይ ኃይል ያለው ኢየሱስ ብቻ ነው። በአጋንንትና በተፈጥሮ ኃይላት ላይ ኃይል ያለው ኢየሱስ ብቻ ነው። ኢየሱስ የችግርተኛ ሰዎችን ጸሎት ለመመለስ ኃይሉን ተጠቅሟል። በሞትና ሕይወት ላይ ሥልጣን ያለው ኢየሱስ ነው። ኢየሱስ በተአምራቱ በምድርና በሰማይ ላይ ሥልጣን እንዳለው አሳይቷል (ማቴ. 28፡18)። ይሁንና፥ ኢየሱስ ሥልጣኑን የተጠቀመው ለሰው ልጆች በጎነት ብቻ ነው። ከኢየሱስ ጋር የሚወዳደር ሌላ የሃይማኖት መምህር ማን ነው?

በፍቅር ተግባራቱና በኃይሉ፥ ኢየሱስ የሚናገረውን ነገር እውነትነት አረጋግጧል። ከድንግል መወለዱ፥ ኃጢአት ያልነካው ሕይወቱ፥ የፍቅርና የምሕረት ተአምራቱ፥ የኃጢአታችን ስርየቱ፥ ለሕዝብ መራራቱ፥ በሽታቸውን መፈወሱ፥ ጸሎታቸውን መመለሱ፥ ልቡ ለተሰበረበት ደስታን መልሶ ለመፈጠሪ መቻሉ፥ በተፈጥሮ ላይ ኃያል መሆኑ፥ በአጋንንት ላይ ማየሉ፥ ለኃጢአታችን መሞቱና ከሙታን መነሣቱ፥ ይኼ ሁሉ ኢየሱስ ብቻ መንገድ፥ እውነትና ሕይወት እንደ ሆነ ያረጋግጣል። እነዚህ ነገሮች እርሱ ብቻ የሰው ልጅ አዳኝ እንደ ሆነ ያረጋግጣሉ። ሰዎች ሊታመኑበትና ከትካዜ ሊጠብቁ የሚችሉት በእርሱ ብቻ ነው።

በክርስቶስ ማመን፥ ቀደም ሲል በተጠቀሰው ምሳሌ እንደ ተገለጸው ይበልጥ በአውሮፕላኑና በአውሮፕላን ነጂው እንደማመን ነው። ይህም ማለት አንድ ችግር ወይም ቀውጢ ሁኔታ በሚከሰትበት ጊዜ የሚያደርገውን እንደሚያውቅ እናምናለን ማለት ነው። እንዲሁም፥ በችግር ውስጥ በምንሆንበት ጊዜ እንደሚረዳን እናምናለን ማለት ነው። ክርስቶስ ሰው የሆነ አምላክ እንደ ሆነ እናምናለን ማለት ነው። በፈንታችን በመስቀል ላይ የሞተው እርሱ እንደ ሆነ እናምናለን ማለት ነው። ከሙታን እንደ ተነሣና ሞትን እንዳሸነፈ እናምናለን ማለት ነው። ኃጢአታችንን ይቅር እንደሚለን እናምናለን ማለት ነው። በምትሐቶች፥

ወይም በሥርዓቶች፥ ወይም በቅድመ-ትውልድ መንፈሶች፥ ወይም በጠንቋዮች ከማመን ይልቅ፥ በእርሱ እናምናለን ማለት ነው። በክርስቶስ ማመን ማለት በዚህ ሕይወትና ከሞትንም በኋላ ስለሚፈጸምብን ነገር ሁሉ በእርሱ ላይ እንደገፋለን ማለት ነው።

ኢየሱስ ከሌሎች በታሪክ ታላላቅ ሃይማኖታዊ መምህራን ከነበሩት ሁሉ የተለየ ነበር፤ ይህም ሌሎች የእግዚአብሔርን ቃል ሲያስተምሩ፥ እርሱ ግን የእግዚአብሔር ቃል በመሆኑ ነው (ዮሐ 1፡1፥ 14፤ ራእይ 19፡13)። ቁርዓንም እንኳ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ ይመሰክራል (ሱረቱ 4፡171)። ሌሎች ስለ እውነት የሰበኩ ሲሆን፥ እውነቱ ግን ኢየሱስ ነበር (ዮሐ. 14፡6፤ 18፡37)። ሌሎች ሰዎች እንዴት እንደሚኖሩ የተናገሩ ሲሆን፥ ኢየሱስ ግን ከማንኛውም ሰው በተለየ ሁኔታ ኃጢአት ያልነካውን ፍጹም ሕይወት ኑሮአል። ሌሎች ነቢያት ለሰዎች ስለ እግዚአብሔር ያስተማሩ ሲሆን፥ ኢየሱስ ግን ራሱ እግዚአብሔር በመሆኑ እግዚአብሔርን ለሰዎች ገልጾላቸዋል (ዮሐ. 1፡1፤ ቆላ. 2፡9)።

የኢየሱስ ተአምራት ማረጋገጫ

የአንድ ሰው ቃላት እውነተኛነት ከሚፈትንባቸው መንገዶች አንዱ፥ የሰውዬው ጠላቶች የሚናገሩትን በመስማት ነው። ይህ ዘወትር በፖለቲካ ሕይወት ሲፈጸም እናያለን። አንድ የፖለቲካ ሰው ስለ ራሱ ወይም ስለ ፓርቲው አያሌ ነገሮችን ይናገራል፤ ይሁንና፥ ብዙም ሳይቆይ ጠላቶቹ ደስ የማያሰኙና ያ የፖለቲካ ሰው ሊደብቃቸው የሚፈልጋቸውን ሐቆች ገሃድ ያወጣሉ።

ጻሐፍትና ፈሪሳውያን ኢየሱስን አጥብቀው ይቃወሙት ነበር። ከተራው የእስራኤል ሕዝብ ጋር ያለው እውቅናና ተወዳጅነት አስቀንቶአቸው ነበር። ሃይማኖታዊ ግብዝነታቸውንና ትዕቢታቸውን ያጋልጥ ነበረና፥ አምርረው ጠሉት። የክርስቶስን ተአምራት ፉርሽ ለማድረግ የሚሻ ሰው ቢኖር ከጻሐፍትና ፈሪሳውያን ሊቀድም አይችልም ነበር። እስኪ እነዚህ የክርስቶስ ጠላቶች በተአምራቱና መልካም ሥራዎቹ ላይ የሚሰነዝሩአቸውን ቃላት እንመልከት። ተአምራት እንደ ሠራ ከደው ይሆን? መልካም ሥራዎችን ፍጹም እንዳልሠራ ተናግረው ይሆን?

እስኪ በዮሐንስ 10፡32 ክርስቶስ ላቀረበላቸው ጥያቄ፥ ጠላቶቹ የሰጡትን ምላሽ እንመልከት። ጥያቄው፥ «ከአባቴ ብዙ መልካም ሥራ

አሳየኋችሁ፤ ከእነርሱ ስለ ማናቸው ሥራ ትወግሩኛላችሁ?» የሚል ሲሆን፥ የጠላቶቹ መልስ የሚከተለው ነበር፡- «ስለ መልካም ሥራ አንወግርህም፤ ስለ ስድብ፤ አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለ ማድረግህ ነው እንጂ» (ዮሐ. 10፡33)። በመልሳቸው፥ እንደ እውነቱ ከሆነ ኢየሱስ ታላላቅ ተአምራትን እንደ ፈጸመ አምነው ተቀብለዋል። ይሁንና፥ እነዚህን ተአምራት ለመሥራት የቻለበትን ምክንያት ለመቀበል አልፈለጉም። የሚያስደንቀው እውነት ይህ ነው - የክርስቶስ ጠላቶች ያስቀመጡአቸው ዓረፍተ ነገሮች ኢየሱስ በትክክል ሰዎችን ለመርዳት ታላላቅ የፍቅርና የሥልጣን ተአምራት እንዳደረገ ከሚያሳዩ እጅግ ጠንካራ ታሪካዊ ማረጋገጫዎች አንዳንዶቹ ሆነው መገኘታቸው ነው!

የክርስቶስ ጠላቶች ኃጢአት ካልነካው ሕይወቱ ጥፋት ሊያገኙ አልቻሉም ነበር። በዮሐንስ 8፡46 ኢየሱስ፥ «ከእናንተ ስለ ኃጢአት የሚወቅሰኝ ማን ነው?» በማለት ጠይቋል። አሁንም የክርስቶስ ጠላቶች ከሕይወቱ የማንኛውንም ኃጢአት መረጃ በማግኘት ጥፋተኛ ሊያደርጉት አልቻሉም ነበር። ይልቁንም የአምላክነት እዩኝታውን በመቃወም፥ ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ (ዮሐ. 8፡59)። በመሆኑም፥ እጅግ የከፉ ጠላቶቹ ሳይቀሩ ኃጢአት-አልባነቱን ተቀብለው ነበር። ቁርዓንም እንዲሁ የኢየሱስን «ጥፋት-አልባነት» ያስተምራል (ሱረቱ 19፡19)።

እስቲ በታሪክ ውስጥ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ስላጋጠመው ሌላ ሰው ለማሰብ ሞክር። አንድ ሰው ኃጢአት ሠርቶ እንደማያውቅ ቢናገር፥ የዚያ ሰው ጠላቶች ወዲያው የጥፋቶቹን መረጃዎች አከታትለው ያቀርቡበታል። ቁርዓንም እንኳ የመሐመድን ተራ ሰው መሆን በጸጋ ይቀበላል (ሱረቱ 47፡19፤ 48፡1-2)። ኢየሱስ ግን ኃጢአት-አልባ በመሆኑ፥ በእርሱ ላይ ምንም ክስ ሊቀርብበት አይችልም። እነዚህን ሁሉ ሐቆች አጣምረን ስንመለከት፥ ኢየሱስ ስለ ራሱ እንደ ተናገረው ፍጹም ሰው እንደ ነበር እንረዳለን። እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ፥ የዓለም መድኃኒት ነው!

መ. የምናምነው ነገር በተግባራታችን ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድረው እንዴት ነው?

አስቀድመን እንደ ተመለከትነው የምናምነው ነገር ተግባራችንንና ግንኙነታችንን ይወስነዋል። ሰዎች የሚያደርጉትን ነገር በዚያው መንገድ የሚያደርጉት ለምንድነው? ይህ የሚሆነው እውነት ነው ብለው በልባቸው

ውስጥ ካስቀመጡት መመሪያ የተነሣ ነው። የዚህ ተግባር አሳዛኝ ምሳሌ በሰው መፈጠር ወቅት ተፈጽሞአል። በዔድን ገነት ሰይጣን ለሔዋን «ሞትን አትሞቱም» (ዘፍ. 3፡4) ባላት ጊዜ ከእግዚአብሔር እውነት ይልቅ ይህንኑ የሰይጣንን ውሸት አመነች። ይህንኑም ውሸት ስላመነች፥ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመተላለፍ እግዚአብሔር ከከለከለው ዛፍ ፍሬ ወሰዳ በላች (3፡6)። ከዚህም የተነሣ፥ እግዚአብሔር እንደ ተናገረው (2፡17) ሞት በሰው ልጆች ሁሉ ላይ ደረሰ (ሮሜ 5፡12)።

ይህ መጽሐፍ በክርስቲያን እምነትና በክርስቲያን ባሕርይ መካከል የሚገኘውን ግንኙነት ግልጽ ለማድረግ ይጥራል። ሥነ-መለኮት ስለ እግዚአብሔር የሚጠኑ አሳቦች ብቻ የሚስተናገዱበት አይደለም። ከዚህ በተጨማሪ፥ ሰዎች ከሕያውና እውነተኛው አምላክ ጋር የግል ግንኙነት ሲኖራቸው ሥራቸው ምን እንደሚመስል የሚከታተል ተግባራዊ ጥናትም ነው።

ስለ እግዚአብሔር ምን ታምናለህ? ስለ ሰውስ ምን ታምናለህ? ስለ ሕይወትና ሕይወት ከየት እንደመጣ ምን ታምናለህ? ስለ ኃጢአት፥ በሽታ፥ ኃዘንና ሞት ምን ታምናለህ? ስለ መናፍስትና የመናፍስት ዓለም ምን ታምናለህ? ስለነዚህ ነገሮች ያለህ እምነት ሕይወትህን የምትኖርበትን ሁኔታና ከሞትህም በኋላ የዘላለሙን ጊዜ የምታሳልፍበትን ስፍራ ስለሚወስን፥ ይህ መጽሐፍ እነዚህንና ሌሎችንም አስፈላጊ የሕይወት ጥያቄዎች ይመልስልሃል።

ሠ. እውነት የሆነውን ነገር ስታምን ምን ይከሰታል? ውሸት የሆነውንስ ስታምን?

የምታምነው ነገር የሞትና የሕይወት ጉዳይ ነው። ከብዙ ዓመታት በፊት የሕክምና ዶክተሮች በሽታ የሚመጣው በደም ውስጥ ከሚገኝ አንድ ነገር እንደ ሆነ ያምኑ ነበር። ምንም እንኳ እምነታቸው እውነት ቢሆንም፥ በዚያን ጊዜ የነበሩ ዶክተሮች በደም ውስጥ የተበላሸውን ነገር እንዴት እንደሚያድኑ አያውቁም ነበር። ከዚህም የተነሣ፥ አንድ ሰው በሚታመምበት ጊዜ በሽታውን ለማስወገድ እንዲቻል፥ በቂ ደም ከሰውዬው ሰውነት መወገድ አለበት ወደሚል እምነት አመሩ! ይህም ተግባር የመጀመሪያው የዩናይትድ እስቴትስ ፕሬዝዴንት በነበሩት ጆርጅ ዋሽንግተን ላይ በሕክምና ዶክተር አማካኝነት ተፈጽሞባቸዋል። ዋሽንግተን በሽምግልና ዘመናቸው ሕመም ይሰማቸው ነበር። በመሆኑም፥

ዋሽንግተንን ያከመው ዶክተር ሕይወታቸውን ለማትረፍ ቢሻም፥ ያመነበት የአሠራር መንገድ የተሳሳተ ስለ ነበር፥ ደም ፈሷቸው እንዲሞቱ አደረገ።

በመንፈሳዊ ጉዳዮችም ይኼ ተመሳሳይ ሁኔታ ሊፈጸም ይችላል። በጣም ታማኝ ልንሆንና ዳሩ ግን ታማኝነታችን በስሕተት ላይ በመመሥረቱ ወደ ዘላለም ሞት ልናመራ እንችላለን። በዮሐንስ 8፡24 ኢየሱስ፥ «እኔ እንደ ሆንሁ ባታምኑ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ» ብሏል።

ረ. ማንን እንመን?

እውነት ያለውና ልንታመንበት የሚገባው ማን ይሆን? የእግዚአብሔር ቃል፥ «እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና» ይለናል (የሐዋ. 4፡12)። ያ ስም ቡድሃ አይደለም። ማርክስ ወይም መሐመድም አልሆነም። ያ ከስሞች ሁሉ በላይ የሆነው ስም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ፊልጵ. 2፡9)። ኢየሱስ፥ «በሩ እኔ ነኝ፣ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል» ብሏል (ዮሐ. 10፡9)።

ኢየሱስ የሰማይና የምድር ጌታ ነው። በሰማይና በምድር ምላስ ሁሉ የኢየሱስን ጌትነት የሚመሰክርበት ቀን ይመጣል (ፊልጵ. 2፡9-10)። የሚያሳዝነው ግን ብዙዎቹ ጌትነቱን የሚመሰክሩ ቢሆንም፥ የራሳቸው ጌታ ግን እንደ ሆነ ሊናገሩ አይችሉም። ኢየሱስ፥ «በዚያ ቀን ብዙዎች፡- ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ ይሉኛል። የዚያን ጊዜም፡- ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ» ብሏል (ማቴ. 7፡22-23)።

ይሁንና፥ ኃጢአታቸውንና ይቅርታው እንደሚያሻቸው ለመናዘዝ አሁን ራሳቸውን በፊቱ ላዋረዱትና እርሱንም ጌታቸውና አዳኛቸው አድርገው ለተቀበሉት፥ እውነትም ጌታቸው ይሆንላቸውና የዘላለምን ሕይወት ያወርሳቸዋል (ዮሐ. 1፡12፣ 3፡16)።

ማጠቃለያ

ዛሬ በዓለም እውነትን ይዘናል የሚሉ ብዙዎች አሉ። እንግዲህ፥ ማንን እንመን? እውነትን ከወዴት እናገኛለን? እውነትስ ራሱ ምንድን ነው?

እውነት ትከክለኛ የሆነውን አሳብ የሚያቀርብ ዓረፍተ ነገር ነው። ምንም እንኳ በታሪክ አያሌ የሃይማኖት መምህራንና ነቢያት እውነትን እናስተምራለን ብለው ቢነሡም፥ እንደ ተናገረው በፍጹም ፍቅር፥ በፍጹም ቅድስናና በፍጹም ኃይል ሕይወቱ፥ መንገድ፥ እውነትና ሕይወት መሆኑን ያረጋገጠው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው (ዮሐ. 14፡6)። በታሪክ ኢየሱስን ከሌሎች ሰዎች ጋር ስናወዳድር፥ እንደ እርሱ ያለ ማንም እንዳልነበር እንረዳለን።

የምናምነው ነገር እውነት የመሆኑ ጉዳይ በጣም ወሳኝ ነው። ተግባሮቻችን የሚመነጩት እውነት ነው ብለን ከምናምነው ነገር ነው። እውነት የሆነውን ማመናችን እጅግ አስፈላጊ ሲሆን፥ ይህ ካልሆነ ግን ለዘላለሙ ሕይወታችንን እናጣለን። በኢየሱስ ክርስቶስ ብናምን፥ እውነትን፥ ለኃጢአታችን የእግዚአብሔርን ይቅርታና ከእግዚአብሔር ጋር ለዘላለም የመኖርን በረከት እናገኛለን።

በምዕራፍ 1 ላይ የተመሠረቱ የመወያያ ጥያቄዎችና መልመጃዎች

1. በትምህርት ቤትህ ውስጥ «እርሱ ዓለምንና በውስጧ ያሉትን ሁሉ ስለ ፈጠረ፥ መንገዶች ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ያመራሉ፤ ለእርሱ ታማኝ እስክ ሆንህ ድረስ፥ የትኛውንም ሃይማኖት ብትከተል ለውጥ የለውም» ለሚልህ ሰው ምን ምላሽ ትሰጣለህ?

2. የአንድ ዩንቨርስቲ ፕሮፌሰር፥ «ዘመናዊ ሳይንስ መጽሐፍ ቅዱስን ፉርሽ አድርጎታል። በመሆኑም፥ ለሰው ልጅ ችግር መፍትሔ የሚገኘው የበለጠ ምርምርና የተሻለ ትምህርት ሊቀርብ ብቻ ነው» ይላል። የዚህን ፕሮፌሰር አሳብ ለማምከን፥ በቡድኑ ፊት ምላሽ ስጥ።

3. አንድ ሙስሊም ተማሪ፥ «ኢየሱስ ነቢይ እንደ ነበር እናምናለን፤ ይሁንና፥ መሐመድ የመጨረሻውና ከነቢያትም ሁሉ የሚልቅ ነው» ይላል። ለዚህ ሰው ምን ዓይነት ምላሽ ትሰጣለህ?

4. የአንድ ትምህርት ቤት የሃይማኖት መምህር፥ «ብሉይ ኪዳን ለአይሁዶች ክርስትና መዘጋጃ እንደ ነበረው ሁሉ፥ የአፍሪካ ባህላዊ ሃይማኖትም ለአፍሪካውያን ክርስትና መዘጋጃ ነው» ይላል። አራት አራት አባላት በሚገኙበት ቡድን ተከፋፍላችሁ 1ኛ ነገሥት 18፡17-39 በክፍል

ውስጥ አጥኑና መጽሐፍ ቅዱስ ለዚህ ዓረፍተ ነገር የሚሰጠውን ምላሽ አግኙ።

5. በአፍሪካ ሕይወት ከመጽሐፍ ቅዱስ ምላሽ የሚሹትን ተግባራዊ ችግሮች ዘርዝሩ። ሦስት አባላት በሚገኙበት ቡድን ተከፋፈሉና ለእነዚህ ችግሮች መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠውን ምላሽ አግኙ።

6. ሦስት አባላት በሚገኙበት አናሳ ቡድን ተከፋፈሉና እያንዳንዱ ቡድን የሚያውቃቸው ሰዎች የሚከተሉአቸውን የሐሰት እምነቶች ይዘርዝሩ። ከዚያም እነዚህ እምነቶች ለተግባራቸው እንዴት መሳኝ እንደ ሆኑ አሳዩ።

7. በአፍሪካ «እውነት» ምንድን ነው? ወደ እውነት ግንዛቤ እንዴት ትደርሳለህ?

8. ኢየሱስ ከመናፍስት፥ ቅድመ-ትውልድና አማልክት የሚለየው በምን መንገዶች ነው?

SUGGESTED FOR FURTHER READING

Kato, Byang. Theological Pitfalls In Africa. Kisumu; Kenya: Evangel Publishing House, 1975.

McDowell, Josh. Evidence That Demands A Verdict. Amersham: Scripture Press, 1990.

McGrath, Alistair. Explaining Your Faith. Leicester: InterVarsity Press, 1995.

Parrinder, Edward G. Africa's Three Religions. London: Sheldon Press, 1976.

ምዕራፍ 2

መጽሐፍ ቅዱስ – የእምነታችን መሠረት

ግጋጂ፡- «ሙስሊሞች አገሪቱ ልትመራ የምትችለው በሙስሊም ሕግ መሠረት እንደ ሆነ የሚናገሩት ለምንድን ነው?»

ንያንዘኑ፡- «ጓደኛዬ ሳኑሲ ቁርዓን ከእግዚአብሔር ዘንድ ለነቢዩ መሐመድ የወረደ መለኮታዊ መገለጥ እንደ ሆነ ይናገራል። ይህም ቁርዓን የእግዚአብሔርን ሕግና እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለውን ፈቃድ እንደሚይዝ ይናገራል። የእርሱን ፈቃድ ባንጠብቅና በቁርዓኑ በተገለጹት ሕግጋቱ ባንኖር፥ ሁላችንም በእግዚአብሔር እንቀጣለን።»

ግጋጂ፡- «ይሁንና ጓደኛዬ ፒተር መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የተሰጠ መለኮታዊ መገለጥ እንደ ሆነና እግዚአብሔርን ለማወቅም ሆነ ደኅንነቱን ለማግኘት፥ መጽሐፍ ቅዱስን ማመን እንዳለብን ይናገራል። የሁለቱንም መጻሕፍት ክፍሎች አነብ ነበርና፥ ከመለኮታዊ ምንጭ የተቀዱ ይመስላሉ። እንግዲህ፥ የትኛው ከእግዚአብሔር እንደ ሆነ እንዴት እናውቃለን?»

ንያንዘት፡- «ለዚህ ጥያቄ የሚሆን መልስ የለኝም። እኛ ግን በመንደራችን የምንከተለው አምልኮ ሽማግሌዎቻችን በአፈ-ታሪክ ያስተላለፉልንን ነው።»

አብዛኛዎቹ ታላላቅ የዓለም ሃይማኖቶች የራሳቸው የሆኑ አፈ-ታሪኮችና የተቀደሱ ጽሑፎች አሉአቸው። ተከታዮቻቸውም የእነዚህን ባህላዊ ታሪኮችና መጻሕፍት ከእግዚአብሔር ዘንድ መገኘት ይናገራሉ። አንድ ሰው ከእነዚህ መጻሕፍት የትኛው በትክክል ከእግዚአብሔር እንደ መጣ የሚያውቀው እንዴት ነው? እውነትን እንድናገኝ ከተፈለገ፥ ይህ አስፈላጊ ጥያቄ ነው። በመሆኑም፥ በዚህ ምዕራፍ የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንመለከታለን፡-

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ እንዲያው የሰዎች ቃል ሳይሆን፥ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ እንዴት ልናውቅ እንችላለን?

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ብቸኛ መገለጽ ነው፥ ወይስ ሌሎችም ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላኩትን መገለጾች ያካተቱ መጻሕፍት አሉ?

ሐ. ኢየሱስ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣንና ትክክለኛነት ምን አስተማረ?

መ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚታዩ የአሳብ ግጭቶችስ?

ሠ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የማንረዳቸውስ ነገሮች?

ረ. በብሉይና አዲስ ኪዳን መካከል ያለው ግንኙነት ምንድን ነው?

ሰ. መጽሐፍ ቅዱስ በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ተጻፈ ሲባል ምን ማለት ነው?

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ እንዲያው የሰዎች ቃል ሳይሆን፥ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ እንዴት ልናውቅ እንችላለን?

ሁሉም ሰው ለሚያምነው ነገር የሆነ መሠረት አለው። ይህም መሠረት፥ መጽሐፍ፥ ወይም የወላጆቹ አስተምህሮ፥ ወይም የሌሎች ሰዎች አስተሳሰብ ሊሆን ይችላል። ሁላችንም ስለ ትክክለኛ የሕይወት ጉዳዮች አንዳንድ ነገሮችን የምናምን ስንሆን፥ ሁላችንም ለእነዚህ እምነቶቻችን መሠረቶች አሉን። ብዙ ሰዎች እምነቶቻቸውን የሚመሠርቱት ከእግዚአብሔር እንደ ተገለጹ በሚያምኑባቸው መጻሕፍት ላይ ነው። የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ የሚናገረውን አሳብ ሊደግፍ የሚችል መጽሐፍ ይኖር ይሆን?

ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያኖች ስለ ክርስቶስ የሚናገሩአቸው ነገሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብቻ የሚገኙ ይመስላቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስን ልናምን እንችላለን? መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያኖች እንደሚሉት የእግዚአብሔር ቃል ይሁን፥ ወይም በሰዎች የተጻፈ ሌላ ተራ መጽሐፍ ይሁን እንዴት እናውቃለን? በግልጽ እንደሚታወቀው፥ በክርስቶስና በቃሉ ላይ የሚኖረን እምነት በትክክል መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር በመምጣቱ ወይም ባለመምጣቱ እውነት ላይ ይመሠረታል።

ይህንን ጥያቄ ለመመለስ እግዚአብሔር ራሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያስቀመጠልንን መረጃ ልንመረምር ያሻል። ከዚያም፥ መጽሐፍ ቅዱስን ከእግዚአብሔር እንደ ተገኙ መገለጦች አድርገው ከሚናገሩ ሌሎች ሃይማኖታዊ መጻሕፍት ጋር እናወዳድራለን።

የሐዋርያት ምስክርነት መረጃ

መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ነቢያትና ሐዋርያት ተብለው ይታወቁ በነበሩ ሰዎች ነበር። ለዚህ ተግባር በብሉይ ኪዳን ውስጥ በአብነት የሚጠቀሰው፥ አምስቱን ቀዳሚ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የጻፈው ሙሴ ነው። የሙሴን የእግዚአብሔር ነቢይነት አይሁዶች፥ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ሁሉ ያለ ጥርጥር ይቀበላሉ። በአዲስ ኪዳን ውስጥ በዋቢነት የሚጠቀሰው የዮሐንስን ወንጌል የጻፈው ሐዋርያው ዮሐንስ ነው። በአንዳንድ አጋጣሚዎች፥ እንደ ሉቃስ ወንጌል የእግዚአብሔርን ቃል እንዲጽፉ በሐዋርያት ሥልጣን በተሰጡአቸው ሌሎች ሰዎችም የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ተጽፈዋል።

የትንቢት መረጃ

ከእግዚአብሔር በቀር የወደፊቱን ጉዳይ ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው በዓለም ላይ የለም። በመሆኑም፥ ወደፊት የሚመጣውን ነገር መቶ በመቶ ሳያዛንፍ የሚተነብይ መጽሐፍ ከእግዚአብሔር የመጣ መገለጽ መሆን አለበት። ይህንንም የሚያደርገው ብቸኛው መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

እግዚአብሔር ሰዎች የወደፊቱን በመተንበይ ብቃታቸውን እንዲያስመሰክሩ ይጠይቃቸዋል። በትንቢተ ኢሳይያስ፥ «እንደ እኔ ያለ ማን ነው? ይነግና ይጥራ ይናገርም፤ የሚመጣውም ነገር ሳይደርስ ይንገሩኝ» ይላል (44፡7)። በዚህ ፈተና መሠረት፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ በስተቀር በዓለም ቅዱስ የተባለው መጽሐፍ ሁሉ ውድቅ ይሆናል - ሁልጊዜም የወደፊቱን በትክክል ሊተነብይ ስለማይችል።

በዘዳግም 18፡21፥ እግዚአብሔር የብዙዎች ጥያቄ የሆነውን አሳብ ያቀርባል፡- «እግዚአብሔር ያልተናገረውን ቃል እናውቅ ዘንድ እንዴት ይቻለናል?» በቁጥር 22 የእግዚአብሔር መልስ በጣም ቀላል ነው። «ነቢዩ በእግዚአብሔር ስም በተናገረ ጊዜ የተናገረው ነገር ባይሆን ባይመጣም፥ ያ ነገር እግዚአብሔር ያልተናገረው ነው።»

በሌላ አባባል፥ የመገለጹ ከእግዚአብሔር መሆን አለመሆን የሚፈተነው በፍጻሜው ነው። ከእግዚአብሔር የሆነ ትንቢት ሁልጊዜም በትክክል ይፈጸማል። እዚህ ላይ ነው እንግዲህ ብዙ ነቢያት ከእግዚአብሔር አለመሆናቸውን የሚያስመሰክሩት። ዛሬ በአፍሪካ በራሳቸው ዘይቤ የሚተነብዩ በርካታ ነቢያት አሉ። አንድ «ነቢይ» ከአሥሩ ዘጠኙ እጅ ቢይዝለት፥ ከእግዚአብሔር የተላከ ነቢይ አይደለም። የእግዚአብሔር ትንቢቶች አሥር በአሥር እውነት ናቸው። እግዚአብሔር ከቶውንም ሰለማይሳሳት፥ ቃሉ ሊዛነፍ አይችልም።

ራሳቸውን ከእግዚአብሔር እንደ መጡ መገለጾች አድርገው ከሚያቀርቡ መጻሕፍት ሁሉ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ሁልጊዜም ትንቢቱ የሚጸናለት ብቸኛ መጽሐፍ ነው። ሌሎች መጻሕፍት ሁሉ አንድም በዚህ ፈተና ይወድቃሉ፤ አሊያም ውድቀቱን በመስጋት ትንቢት ከሚባል ነገር ያርቃሉ። የተፈጸሙ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች ከተአምራት የሚተናነሡ አይደሉም። በመሆኑም፥ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ ያረጋግጣሉ።

አንዳንድ የተፈጸሙ ትንቢቶች ምሳሌዎች

በ1000 ዓ. ዓ. አካባቢ በንጉሥ ዳዊት በተጻፈው መዝሙር (22) ውስጥ፥ ስለ አንድ ሰው ስቅለት በዝርዝር የቀረበ ገለጻ እናገኛለን። የዚህም ገለጻ ዝርዝሮች ከአንድ ሰው ጋር የሚስማሙ ሲሆን፥ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። መዝሙር (22)፡16-18 እንዲህ ይላል፡- «ብዙ ውሾች ከብበውኛልና፤ የክፋተኞች ጉባኤም ያዘኝ፤ እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ። አጥንቶቼ ሁሉ ተቆጠሩ፤ እነርሱም አዩኝ ተመለከቱኝም። ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ፥ በቀሚሰም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ።» አንድ ሰው ክስተቱን ሳይመለከት፥ እንዲህ ያለ ገለጻ ሊጽፍ የሚችለው እንዴት ነው? ይህ ገለጻ የተጻፈው ክስተቱ ከመፈጸሙ 1000 ዓመታት የኋሊት ርቆ ነበር! ይህም ብቻ አይደለም።

ሮማውያን በ250 ዓ. ዓ. አካባቢ ወንጀለኞችን የመቅጫ መንገድ አድርገው እስክ ፈለሰፉበት ጊዜ ድረስ፥ ስቅለት በማንኛውም ሰብአዊ ፍጥረት ታይቶ አይታወቅም ነበር። በሌላ አባባል፥ መዝሙረ ዳዊት የተጻፈው ማንም ሰው ሊሰቀል ከመታየቱ ከ750 ዓመታት በፊት ነበር ማለት ነው። በመሆኑም ይህ መዝሙር ከእግዚአብሔር መገለጽ ውጭ የተጻፈበትን ሁኔታ የሚያብራራ አጥጋቢ ማብራሪያ የለም። ይህም ትንቢት ይህንኑ ክስተት ለሰው የገለጸው እግዚአብሔር እንደ ሆነ ያረጋግጣል።

ነቢዩ ኢሳይያስም፥ መሢሑ ለሕዝቡ ኃጢአት እንደሚሰቀልና በምትካቸውም እንደሚሠቃይ ገልጾአል። ኢሳይያስ 53፡5፥ «እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቆሰለ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበር፥ በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን» ይላል።

ኢሳይያስ በተጨማሪም፥ ከክርስቶስ ልደት ሰባት መቶ ዓመታት ቀደም ብሎ ስለ ኢየሱስ ሞት ሌሎች ሁለት አስገራሚ ዝርዝሮች ገልጾአል። «ከክፉዎች ጋር መቃብሩን አደረጉ፥ ከባለጠጎችም ጋር በሞቱ» (53፡9)። ዝርዝሮቹም የክርስቶስ ስቅለት ከክፉዎች ጋር፥ ዳሩ ግን ሞቱ ከባለጸጋ ሰው ጋር እንደሚያያዝ ነው። በትክክለኛው ከስተት የተሰቀለው በሁለት ወንበዴዎች መካከል ሲሆን (ማቴ. 27፡38፥ 44)፥ ከዚያ በኋላ የተቀበረው በሀብታሙ የአርማትያሱ ዮሴፍ መቃብር ውስጥ ነበረ (ማቴ. 27፡57-60)።

በመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች ውስጥ ስሕተቶች የሉም። በክርስቶስ ዘመን የነበሩ የአይሁድ የሃይማኖት መሪዎች ብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ ያውቁ ነበር። ሰብዓ ሰገል መሢሑ የሚወለድበትን ስፍራ ለመጠየቅ ወደ ሄሮድስ ዘንድ በመጡ ጊዜ፥ የሃይማኖት መሪዎቹ ለንጉሥ ሄሮድስ ትክክለኛ መልስ ከብሉይ ኪዳን ትንቢት ሊሰጡት ችለዋል።

«አንቺም ቤተልሔም ኤፍራታ ሆይ፥ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፤ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ፥ በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል» (ሚክ. 5፡2፤ ማቴ. 2፡1-6)። መሢሑ ከቤተልሔም እንደሚወለድ መናገራቸው ትክክል ነበር። መሢሑ ኢየሱስ በቤተልሔም ተወልዶአልና (ሉቃ. 2፡4-7)።

በተጨማሪም፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሌሎችም ጉዳዮች የሚናገሩ አያሌ ትንቢቶች አሉ። በአፍሪካ ከአሁን ጀምሮ ወደፊት ለሚመጡ 200 ወይም 500 ዓመታት በምድራቸው ስለሚሆነው ነገር ምንም ሳያዛንፍ በትክክል ሊተነብይ የሚችል ማን ነው? መጽሐፍ ቅዱስ ግን እንዲህ ዓይነቶቹን ትንበያዎች እየደጋገመ ያቀርባል። ለምሳሌ፥ እግዚአብሔር የአይሁድ መቅደስ በናቡከደነፆር ከተደመሰሰ በኋላ የፋርሱ ንጉሥ ቂሮስ ለዳግም ግንባታው ዓዋጅ እንደሚያስነግር ተንብዮአል (ኢሳ 44፡28)። ይህ ትንበያ ቂሮስ ከመወለዱ ከ200 ዓመታት በፊት የተነገረ ሲሆን፥ ልክ እግዚአብሔር እንዳለው ተፈጽሞአል (ዕዝራ 1፡1-3)።

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ የሚያረጋግጥ ሌላ መረጃ

መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር የተጻፈ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ የሚያሳይ ሌላም መረጃ አለ። የዚህ መረጃ አንዳንድ ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው። ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ሦስት ነጥቦች በበለጠ ዝርዝር እንመለከታለን።

1. መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ምናልባትም ከ40 በሚበልጡ ሰብአዊ ጸሐፊዎች ነው። ይህም የጽሕፈት ሥራ የተከናወነው በተለያዩ የታሪክ ወቅቶችና ጊዜያት ግላዊ ትውውቅ ባልነበራቸው ሰዎች ነው። ይህም ሆኖ፥ በአንድ ጸሐፊ የተጻፈ አንድ መጽሐፍ ይመስል ግለፍያ ቅንጅት አለው። ለዚህም ምክንያቱ ትክክለኛው ደራሲ በሰብአዊ ጸሐፊዎች ውስጥ መልእክቱን ያስተላልፍ የነበረው እግዚአብሔር መሆኑ ነው።

2. ምንም እንኳ መጽሐፍ ቅዱስ የሳይንስ መጽሐፍ ባይሆንም፥ ሰዎች ግኝቶችን ከማወቃቸው ከረጅም ጊዜያት በፊት ስለ በርካታ ሳይንሳዊ ግኝቶች በትክክል ይናገራል።

3. ሞቶ የተነሣው ኢየሱስ ክርስቶስ ብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ ይመሰክራል።

4. መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ በክርስቶስ ስላለው ደኅንነት የሚያቀርበውን መልእክት የሚያምኑ ሰዎች በባሕርያቸው ባለማቋረጥ ከኃጢአተኛነት ወደ መንፈሳዊነት ይለወጣሉ - እጅግ ከፉ ሰዎች የሆኑትም ሳይቀር።

5. የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች በተፈጸሙባቸው ስፍራዎች ስለ ነበሩ ጥንታዊ ሥልጣኔዎች የሚደረጉ (የከርሰ-ምድር) ጥናቶች፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን አያሌ ታሪካዊ ዝርዝር ጉዳዮች እውነተኛነት አጠናክረዋል።

6. እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ለክርስቲያኖች ብዙ የተስፋ ቃሎችን ሰጥቶአል። ክርስቲያኖቹም በመጽሐፍ ቅዱስ የተሰጡትን ቅድመ-ሁኔታዎች ሲያሟሉ፥ እግዚአብሔር እነዚህን የተስፋ ቃሎች ይፈጽምላቸዋል። እጅግ ተደጋግመው የተፈጸሙ የተስፋ ቃሎች ከጸሎት ጋር የተያያዙ ናቸው። በዓለም ይህንኑ መረጃ ሊያቀርብ የሚችል ሌላ የተቀደሰ መጽሐፍ የለም።

7. የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች የእግዚአብሔር ቃል እንደ ተሰጣቸው ያውቁ የነበሩ ሲሆን፥ ይህንኑም ገልጸዋል (1 ተሰ. 2፡13)።

8. በሰብአዊ ታሪክ መጽሐፍ ቅዱስ ከማንኛውም መጽሐፍ በላቀ ሁኔታ ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጉሞአል። እንዲሁም፥ በዓለም ከማንኛውም መጽሐፍ በበለጠ ቁጥር ተሰራጭቷል።

9. መጽሐፍ ቅዱስ እምነታቸውን በክርስቶስ ላይ በሚጥሉ ሰዎች ሕይወት ተአምራት እንደሚፈጸሙ የተስፋ ቃል ይሰጣል። የቤተ ክርስቲያንም ታሪክ እንዲህ ባሉ ተአምራት የተሞላ ነው።

10. በዓለም ውስጥ ከሚገኙና ከሁሉም ባህል ከተውጣጡ ክርስቲያኖች፥ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ የሚገልጽ ተያያዥነት ያለው ምስክርነት ይደመጣል። ይህም የእግዚአብሔር ሕዝቦች መጽሐፍ ቅዱስን ሲያነቡ፥ መንፈስ ቅዱስ ከሚገልጽላቸው ውስጣዊ ምስክርነት የሚመጣ ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ አንድነት

የመጽሐፍ ቅዱስን አንድነት ልብ በል። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ መጽሐፍ ሳይሆን፥ አርባ በሚያህሉ ሰዎች በተለያዩ ጊዜያትና ስፍራዎች የተጻፈ የስድሳ ስድስት መጻሕፍት ጥምረት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን እንደ ዛሬው የመገናኛና የጉዞ ነጻነት አልነበረም። እነዚህ ጸሐፊዎች ብዙዎቹ ሌሎች ምን እንደሚጽፉ ወይም ወደፊት ምን እንደሚጻፍ አያውቁም ነበር። የሚያውቁት ነገር ቢኖር እግዚአብሔር እንዲጽፉ የሚነግራቸውን መልእክት ብቻ ነበር።

ይሁንና ተአምራዊው ሐቅ ይኼ ነበረ - እነዚህ የመጽሐፍ ጥቅልሎች ሁሉ በበርካታ ዓመታት የጊዜ ገደብ ቀስ በቀስ ከተሰባሰቡና በአንድ መጽሐፍ መልክ ከተቀመጡ በኋላ፥ ልክ አንድ ተከታታይ ታሪክ የሚገኝበት አንድ መጽሐፍ እንደ ሆነ ታወቀ። እንግዲህ፥ እግዚአብሔር እውነተኛው ደራሲ ሆኖ ሰብአዊ ጸሐፊዎቹን ባይመራ ኖሮ፥ ይኼ እንዴት ሊከሰት ይችል ነበር! አሁን ስናነበው፥ መጽሐፍ ቅዱስ በአንድ ሰው የተጻፈ አንድ መጽሐፍ ይመስላል። እግዚአብሔር ካልሆነ፥ ይህንን አንድነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያቀደው ማን ነው?

የሰውን ሕይወት ለመለወጥ መጽሐፍ ቅዱስ የያዘው ኃይል

መጽሐፍ ቅዱስ በማንበብ በክርስቶስ ላመኑ ሰዎች፥ መጽሐፍ ቅዱስ በሕይወታቸው ላይ የሚያስገኘው ግብረ-ገባዊ ለውጥ ምን ዓይነት ነው? ለመሆኑ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ባለማቋረጥ ኃጢአተኞችንና ክፉ ሰዎችን ወደ ቅዱሳንነት የለወጠ ሌላ መጽሐፍ በታሪክ ውስጥ ይገኛል? ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው «የሚያስገርም ጸጋ» የሚለው የእንግሊዝኛ መዝሙር ጸሐፊ የሆነው ጆን ኒውተን ነው፤ እርሱም ከትውልዱ እጅግ የከፉ ከሚባሉ ሰዎች አንዱ ሲሆን ባርያ ፈንጋይም ነበር። ይሁንና፥ ይህ ሰው ወደ ክርስቶስ ከመጣና ስለ ኃጢአቱ ንስሐ ከገባ በኋላ፥ መንፈሳዊ ሰው ሆነ።

ተመሳሳይ ታሪክ ስለ ሌሎችም በርካታ ኃጢአተኛ ሰዎች ሊነገር ይችላል። በአፍሪካ በጥንቆላ፥ በምግባረ-ብልሹነትና በጭካኔ ወጥመድ ታስረው የነበሩ አያሌ ሰዎች በክርስቶስ ወደ መልካምና መንፈሳዊ ሰው ወደ መሆን ተለውጠዋል። ታዲያ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሌላ የሰዎችን ሕይወት ባለማቋረጥ እንዲህ የለወጠ መጽሐፍ የተኛው ነው? መልሱ የተኛውም አይደለም የሚል ይሆናል - እውነተኛ መለኮታዊ ምንጭነት ያለው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነውና! ይህም እግዚአብሔር፥ በመጽሐፍ ቅዱስ አማካኝነት ዓላማው ሰዎችን ከኃጢአተኛነት ወደ ቅዱስነት መለወጥ እንደ ሆነ የሚናገር አምላክ ነው። ኤፌሶን 2፡10፥ «እኛ ፍጥረቱ ነንና፥ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን» ይላል።

የጸሎት መልሶች

በክርስቶስ ላይ እምነታቸውን ያስቀመጡ ሰዎች የተለማመዱአቸውን የጸሎት መልሶች ተመልከት። ከየትኛውም ዘርና ባህል የሆኑ ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው አንዳንድ ጊዜ ይጸልያሉ። ይሁንና፥ ዘወትር የተመሰኑ መልሶች ለጸሎቶቻቸው እንደሚሰጡ ሊመሰክሩ የሚችሉት ክርስቲያኖች ብቻ ናቸው።

ይህም የሆነው እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚቀርቡትን ሰዎች ጸሎቶች ለመመለስ ቃል ስለ ገባ ነው (ዮሐ. 16፡24)። እግዚአብሔር ቸር አምላክ በመሆኑ፥ አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያን ያልሆኑትን ሰዎች ጸሎት ጭምር ይመልሳል። ይህ ግን አልፎ አልፎ የሚፈጸም ነው። ሰዎች በክርስቶስ እንዲያምኑ የሚመራው መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ለጸሎት ምላሽ ጥርጊያውን የሚከፍተው በክርስቶስ

ማመን ነው። ይህም ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ ያሳየናል።

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ብቸኛ መገለጽ ነው፥ ወይስ ሌሎችም ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላኩትን መገለጾች ያካተቱ መጻሕፍት አሉ?

መጽሐፍ ቅዱስን ከሌሎች ራሳቸውን ከእግዚአብሔር እንደ ተሰጡ መገለጦች አድርገው ከሚናገሩ መጻሕፍት ጋር ማወዳደሩ ተገቢ ነው። ከዚህ በላይ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ የሚያሳዩትን አያሌ ጠቃሚ እውነታዎች ተመልከተናል።

እንግዲህ ሌላውም ቅዱስ ነኝ ባይ መጽሐፍ እውነትም ከእግዚአብሔር ከሆነ፥ ከዚህ በላይ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የዘረዘርናቸው ሐቆች ለዚሁም መጽሐፍ በእኩል ደረጃ መሥራት አለባቸው ማለት ነው። ከእግዚአብሔር እንደ መጡ የሚናገሩትን መጻሕፍት በጥንቃቄ ስንመረምር ግን፥ ሁላቸውም ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ነጥቦች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጎን መቆም ይሳናቸዋል። በመሆኑም፥ እውነተኛ መለኮታዊ ምንጭነት ያለው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው በማለት እንደመድማለን። ከእግዚአብሔር የመጣ ብቸኛ መገለጥ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

ይህም ወደ ሌላ አስፈላጊ ጥያቄ ይመራናል - የመጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛነት እንዴት ነው? ይህንን ጥያቄ ለመመለስ፥ ኢየሱስ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛነት የተናገረውን እንመልከት።

ሐ. ኢየሱስ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣንና ትክክለኛነት ምን አስተማረ?

1. ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቃል እውነት እንደ ሆነ ተናግሮአል። «ቃልህ እውነት ነው» (ዮሐ. 17፡17)።

2. ኢየሱስ ብሉይ ኪዳን በታሪካዊ ይዘቱ ትክክል እንደ ሆነ ተናግሮአል። በማቴዎስ 12፡40-41 የዮናስ በዓሣ ነባሪ ሆድ ውስጥ መቆየት ታሪክ እውነት እንደ ሆነና ወደፊትም የፍርድ ቀን እንደሚመጣ አመልክቷል።

3. ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ሕግ አንዲት አናሳ ነጥብ ከምትወድቅ፥ ሰማይና ምድር ቢያልፉ እንደሚቀል ተናግሮአል (ማቴ. 5፡18)። በሌላ

አባባል፥ የእግዚአብሔር ቃል ቋሚና ለዘላለም የማይለወጥ ነው [መዝ. (119)፡89]።

4. ኢየሱስ ሰማይና ምድር ቢያልፉ እንኳ፥ የእግዚአብሔር ቃል እንደማያልፍ ተናግሮአል (ማቴ. 24፡35)።

5. ኢየሱስ፥ መዝሙር (110) እና በእርሱም አመልካችነት ብሉይ ኪዳን በሙሉ በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር እንደ ተጻፈ ገልጾአል (ማር. 12፡36)። እንዲሁም፥ ከእርሱ ዕርገት በኋላ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ተጨማሪ መገለጥ (አዲስ ኪዳን) እንደሚኖር ተናግሮአል (ዮሐ.16:13)።

6. ኢየሱስ የተጻፈውን ብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ቃል ሲል ጠርቶታል (ማር. 7፡13)።

7. ኢየሱስ መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ ትክክል በመሆኑ፥ የአንቀጾችን የጊዜ አጠቃቀም (ኃላፊ፥ ያሁን ወይም የወደፊት ጊዜ) ጨምሮ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላትም ሳይቀሩ ልክ እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ እንደ ተቀረጹ አስተምሯል (ማር. 12፡26-27)። እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊ በራሱ የአጻጻፍ ስልት እግዚአብሔር የሰጠውን. አሳብ ከመግለጹ ባሻገር፥ ይህ የቃላት ትክክለኛነት እውን ሊሆን ችሏል።

8. ኢየሱስ የመጽሐፍ ቅዱስ የተሰፋ ቃሎችና ትንቢቶች ሁሉ መፈጸም እንዳለባቸው ገልጾአል (ዮሐ. 10፡35ለ፤ ማቴ. 5፡18)።

ከእነዚህ የክርስቶስ አባባሎች በመነሣት፥ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛነትና ሥልጣንነት ተገቢ መረዳት ልንደርስ እንችላለን። የብሉይ ኪዳን ነቢያትና የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎችም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛነትና በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር መጻፍ ሌሎች ነገሮችን ብለዋል። እነዚህም አሳቦች ከኢየሱስ ትምህርት ባገኘነው ግንዛቤ ላይ ተጨማሪ እገዛ ያደርጋሉ። ለምሳሌ ጳውሎስ፥ «የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል» ብሏል (2 ጢሞ. 3፡16)። ሐዋርያው ጴጥሮስም፥ «ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ» ብሏል (2 ጴጥ. 1፡21)።

ከእነዚህና ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ አባባሎች፥ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር መጻፍ፥ ሥልጣንና ትክክለኛነት አጠቃላይ አሳብ ልናዘጋጅ እንችላለን። ይህ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛነት የሚዘጋጀው አ ጠቃላይ አሳብ የኢየሱስና ሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፍት ዐረፍተ ነገሮች ማጠቃለያ ነው። አጠቃላዩም አሳብ የሚከተለው ነው፥-

> በብሉይና አዲስ ኪዳን የተጠቃለለው ሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ፥ መጀመሪያ እነዚያን ቃላት ለጻፉት ሰዎች እንደተሰጠው፥ ትክክለኛና ሙሉ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ይህም በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ተላልፎ በእያንዳንዱ ሰብአዊ ጸሐፊ ቃላትና ስልት አማካኝነት ለሰዎች የተሰጠ ነው። እነዚህ ጽሑፎች ከስሕተት የጸዱና እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያስተላለፈውን መገለጥ የያዙ ነበሩ። ሰው ለደኅንነትና ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ለማድረግ የሚያስፈልገው ሁሉ በብሉይና አዲስ ኪዳን ውስጥ ይገኛል።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በቅዱሳት መጻሕፍት መዛግብት መረጃ በኩል ሰፊ ግኝቶች እውን በመሆናቸው፥ ዛሬ የምንጠቀምባቸው ዘመናዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ዕትሞች መጀመሪያ ጸሐፊዎቹ ከጻፉዋቸው ቀደምት ሰነዶች ጋር እጅግ የቀረበ ተመሳሳይነት እንዳላቸው ለማረጋገጥ ተችሏል።

መ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚታዩ የአሳብ ግጭቶችስ?

አንዳንድ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ በአስተሳሰብ ግጭቶችና በስሕተቶች የተሞላ እንደ ሆነ ይናገራሉ። እርግጥ አንድ ዓይነት ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ መጻሕፍት ክፍል ሲተረክ፥ አንዳንድ ጊዜ ዝርዝር ጉዳዮች የሚጋጩ ይመስላሉ። ለዚህም አብነት የኢየሱስን የትንሣኤ ታሪክ ከአራቱ ወንጌላት ልንመለከት እንችላለን። ዋናው ታሪክ አንድ ዓይነት ሆኖ፥ ዝርዝሮቹን በተመለከተ እያንዳንዱ ታሪክ ከሌላው የተለየ ነው። ጸሐፊዎቹ ኢየሱስ ከሙታን ተነሥቶ በተከታዮቹ እንደ ታየ ዘግበዋል። እንዲህ ዓይነቶቹን ችግሮች እንዴት እናስወግዳለን?

ለእነዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለሚገኙ የይምሰል ግጭቶች መፍትሔ የሚገኘው፥ አንዳንዴ ምንባቡን በጥንቃቄ ከማጥናት ሲሆን፥ ሌላ ጊዜ ደግሞ በክስተቱ ዙርያ የነበሩትን ታሪካዊ ሁኔታዎች በጥንቃቄ ከማጥናት ነው። ለምሳሌ፥ አራቱን የትንሣኤ ታሪኮች በመውሰድ በጥልቅ

ስንመረምር፥ ታሪኮቹ ባልተማሩ የዓይን ምስክሮች ወይም የእነዚህን ዓይን ምስክሮች ምስክርነት በሰሙ ሰዎች እንደ ተጻፉ እንረዳለን።

አያሌ ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው የተነሣውን አምባጓሮ ቢገልጹ፥ የሁሉም ታሪኮች አንድ ዓይነት ሊሆኑ አይችሉም። የአምባጓሮው ጠቅላላ ዘገባ አንድ ዓይነት ሊሆን ቢችልም፥ እያንዳንዱ ተማሪ በግሉ የተመለከታቸውን ዝርዝር ጉዳዮች ማከሉ አይቀርም። በመሆኑም፥ እያንዳንዱ ገለጻ ከሞላ-ጎደል ይለያያል። በአራቱ ወንጌላት ውስጥ የሚገኙ የትንሣኤ ታሪኮችም እንዲሁ ናቸው።

በአንዳንድ የይምሰል ግጭቶች ሳቢያ፥ ታሪኮቹ ለምን የማይስማሙ እንደሚመስሉ ለመረዳት፥ እውነተኛውን ታሪካዊ ሁኔታ በሚገባ ማወቅ ያሻል። አንዳንድ ጊዜ ያ ዝርዝር መረጃ በታሪክ ውስጥ ስለሚጠፋ ለይምሰሉ ግጭት የሚቀርብ ምላሽ ይታጣል። በ1947 እ. ኤ. አ. የተገኘው የሙት ባሕር የመጻሕፍት ጥቅልል መረጃ፥ በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ሕይወት ምን ይመስል እንደ ነበረ በበለጠ እንድንረዳ አድርጎናል። በተጨማሪም፥ እነዚህ መጻሕፍት ምሁራን ለአያሌ ዓመታት የተጠቀሙባቸውን የአሁኑን ጊዜ የብሉይ ኪዳን መዛግብት ትክክለኛነትም አረጋግጠዋል። ከሁሉም በላይ፥ ከላይ እንደ ተመለከትነው ክርስቶስ የቅዱሳት መጻሕፍትን ፍጹም ትክክለኛነት በትምህርቱ ገልጾአል። ከእነዚህም ምክንያቶች የተነሣ፥ ምንም እንኳ የይምሰል ግጭቶቹን በተመለከተ ጥያቄዎችን በሙሉ ምላሽ ባያገኙም፥ በመጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛነት ልናምን እንችላለን።

ሠ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የማንረዳቸውስ ነገሮች?

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እጅግ የተማሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን እንኳ በእርግጠኛነት የማያውቋቸው ምንባቦች አሉ። ለብዙዎቻችን ደግሞ እንዲህ ዓይነቶቹ ምንባቦች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በርካታ ናቸው። በሉቃስ 10፡21 ኢየሱስ፥ «የሰማይና የምድር ጌታ አባት ሆይ፥ ይህን ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ሰውረህ ለሕፃናት ስለ ገለጥህላቸው አመሰግናለሁ» ይላል። ይህ ዓረፍተ ነገር ምናልባትም እግዚአብሔር አብ ሆን ብሎ ለአንዳንድ የሕይወት ጥያቄዎች የሚሆኑትን መልሶች፥ ከዕቡያንና ከተማሩ ሰዎች አእምሮ እንደ ሰወረ ይገልጻል። ምናልባት ይህንን ያደረገው ሰዎች ሁሉ ራሳቸውን እንዲያዋርዱና በፊቱም የሕፃንን ልጅ ዓይነት እምነት ይዘው እንዲቀርቡ ይሆናል። የእግዚአብሔርን ጥበብ ማግኘት በአንድ ሰው

የትምህርት ደረጃ ላይ አይደገፍም። ይኼማ ቢሆን ኖሮ፥ የእግዚአብሔርን ጥበብና ማዳን የሚያገኙት የተማሩ ሰዎች ብቻ ይሆኑ ነበር። ሆኖም፥ እንደምናየው ሰዎች ሁሉ የትምህርት ደረጃቸው ከማንዛቤ ሳይገባ የእግዚአብሔርን ደኅንነትና ጥበብ ሊያገኙ ይችላሉ። መዝሙረኛው፥ «ምስክርህ ትዝታዬ ነውና፥ ካስተማሩኝ ሁሉ ይልቅ አስተዋልሁ» ይላል [መዝ. (119)፡99]።

ምንም እንኳ ለእያንዳንዱ ችግር በቂ ማብራሪያ ልናቀርብ ባንችልም፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛነትና ሥልጣን ረገድ ኢየሱስ በተናገራቸው ቃላት ላይ እምነታችንን በአስተማማኝ ሁኔታ ልንመሠርት እንችላለን። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር እነዚህን ችግሮች ይረዱ ዘንድ ለሰዎች ብርሃን ሲቸራቸው፥ ሌላ ጊዜ ግን ይህንኑ አያደርገውም። አንዳንድ ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራርያዎችና «ኢንሳይክሎፒዲያዎች» ጥያቄዎቻችንን ሊመልሱ ይችላሉ።

ረ. በብሉይና አዲስ ኪዳን መካከል ያለው ግንኙነት ምንድን ነው?

አንዱ አስፈላጊ ጥያቄ በብሉይና አዲስ ኪዳን መካከል ያለውን ግንኙነት የሚመለከት ነው። ያ ግንኙነት ምንድን ነው? የብሉይ ኪዳን ዓላማ ምንድን ነው? እግዚአብሔር ክርስቲያን ከብሉይ ኪዳን እንዲማር የሚፈልጋቸው ምን ዓይነት ነገሮች ናቸው?

የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች በሙሉ በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ተመርተው ስለ ጻፉ፥ መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት ከሁሉም የሚሻለው መጽሐፍ ቅዱስ ራሱን እንዲያብራራ መፍቀድ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘውን አንድ ጥቅስ ከሌላው ጋር ማመሳከሩ፥ የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርቶች ለመረዳት ይረዳናል። አዲስ ኪዳን በብሉይ ኪዳን ላይ የቀረበ መለኮታዊ የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ማብራሪያ ነው።

የዕብራውያን መጽሐፍ በብሉይና አዲስ ኪዳን መካከል ያለውን ግንኙነት በዝርዝር ያብራራል። በአዲስ ኪዳን ሌሎች ምንባቦች ተጨማሪ ብርሃን ያቀርቡልናል። የዕብራውያን መጽሐፍ የብሉይ ኪዳን ተቋሞች፥ ሥርዓቶችና ልማዶች በእግዚአብሔር የተሰጡት፥ የአዲስ ኪዳኑን የደኅንነት መንፈሳዊ እውነታዎች በሥዕላዊ መግለጫ ለማመላከት ወይም በጥላነት ለማንጸባረቅ እንደ ሆነ ይነግረናል። ዕብራውያን 10፡1 እንዲህ ይነበባል፡- «ሕጉ ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር እውነተኛ አምሳል ሳይሆን የነገር ጥላ

አለውና፥ ስለዚህም በየዓመቱ ዘወትር በሚያቀርቡት በዚያ መሥዋዕት የሚያቀርቡትን ሊፈጽም ከቶ አይችልም።»

በብዙ የአፍሪካ ክፍሎች የሕይወት ዘይቤ ከብሉይ ኪዳን ዘመን ጋር የሚመሳሰል በመሆኑ፥ አያሌ ሰዎች በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከሚገኙ ታሪኮች ጋር የሚቀራረብ ስሜት ያድርባቸዋል። በዚህም ምክንያት በተለይ እያደገ የመሄድ ተፈጥሮ ያለውን የእግዚአብሔርን መገለጥ ከመጽሐፍ ቅዱስ መረዳት ለሰው አስፈላጊ ነው።

ይህንኑ አዳጊ መገለጽ ለመረዳት፥ በእግዚአብሔር ግብረ-ገባዊ ሕግጋት፥ ሥርዓታዊ ሕግጋትና ሕዝባዊ ሕግጋት መካከል የሚገኙትን ልዩነቶች መገንዘብ አለብን። የእግዚአብሔር ግብረ-ገባዊ ሕግጋት፥ ከአንዱ የታሪክ ወቅት ወደ ሌላው በተሸጋገርን ቁጥር የሚለወጡ አይደሉም። ሥርዓታዊና ሕዝባዊ ሕግጋት፥ በተለያዩ የታሪክ ወቅቶች ይለያያሉ። ዛሬ እግዚአብሔር የሚፈልገው የብሉይ ኪዳኑን ከፊል መገለጥ ከመከተል ይልቅ፥ በአዲስ ኪዳን ሙሉ መገለጥ እንድንኖር ነው።

ዛሬ ለክርስቲያኖች የብሉይ ኪዳን የሥርዓት መሥዋዕቶችን ማቅረብ አስፈላጊ አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስ እነዚህን ሥርዓቶች በሞቱና ትንሣኤው ፈጽሞአቸዋል (ዕብ. 10፡1-10)። ዛሬ ለብሉይ ኪዳን የምግብና ሕዝባዊ የመተዳደርያ ሕግጋት የመገዛት ግዴታ የለብንም (ማር. 7፡18-19፤ ቆላ. 2፡16-17)።

በዘጸአት፥ ዘሌዋውያንና ዘኍልቁ የሚገኘው ዓይነት ሙሉው የብሉይ ኪዳን ሥርዓታዊ ሕግ፥ በክርስቶስ የሚገኘውን ደኅንነት አያሌ ገጽታዎች ለማብራራት እግዚአብሔር ያዘጋጀው የመግለጫዎች ተከታታይ ቅንጅት ነበር። ቆላስይስ 2፡16-17፥ «እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ ወይም ስለ በዓል ወይም ስለ ወር መባቻ ወይም ስለ ሰንበት ማንም አይፍረድባችሁ፤ እነዚህ ሊመጡ ያሉት ነገሮች ጥላ ናቸውና፥ አካሉ ግን የክርስቶስ ነው» ይላል። ኢየሱስም፥ «እኔ ሕግንና ነቢያትን ልሽር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም» ብሏል (ማቴ. 5፡17)።

ከትንሣኤ በኋላ፥ ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን ትርጉም ለደቀ መዛሙርቱ ያብራራ ጀመር። ሉቃስ ከክርስቶስ ከሁለት ደቀ መዛሙርቱ ጋር በኤማሁስ መንገድ ያደረገውን ውይይት እንደሚከተለው ይዘግባል፡- «ከሙሴና

ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ስለ እርሱ (ኢየሱስ) በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጎመላቸው» (ሉቃ. 24፡27)።

ኢየሱስ ከሙታን እስከ ተነሣበት ጊዜ ድረስ፥ በክርስቶስ ሕይወትና ሞት ዙርያ የነበሩ ክስተቶች ለደቀ መዛሙርቱ ግልጽ አልነበሩም (ማቴ. 16፡21-22፤ ሉቃ. 24፡19-21)። ከትንሣኤው በኋላ እስካረገበት ጊዜ በነበሩት 40 ቀናት ክርስቶስ በሰጣቸው ትምህርቶች (የሐዋ. 1፡3) እና በዕለተ-ብዓለ-ሃምሳ በመንፈስ ቅዱስ በተበረከተላቸው አብርሆት አማካኝነት (የሐዋ. 2፡1-4)፥ ደቀ መዛሙርት የብሉይ ኪዳንን በርካታ መሥዋዕቶችና ሥርዓቶች ምንነት በትክክል ይረዱ ጀመር።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ የቀረቡ በርካታ መንፈሳዊ እውነቶች፥ በብሉይ ኪዳን ታሪካዊ ክስተቶች አማካኝነት በእግዚአብሔር ተብራርተዋል። ጳውሎስ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ስለ ተፈጸሙት ስለ እነዚህ አንዳንድ ክስተቶች ሲናገር፥ «ይህም ሁሉ እንደ ምሳሌ ሆነባቸው፥ እኛንም የዘመናት መጨረሻ የደረሰብንን ሊገሥጸን ተጻፈ» ብሎአል (1 ቆሮ. 10፡11)።

ስለ ሆነም፥ ብሉይ ኪዳን ክርስቲያን ሊያነበውና በትክክል ሊገነዘበው የሚገባው አስፈላጊ መጽሐፍ ነው። ብሉይ ኪዳን በትንቢት፥ በሥርዓት፥ በታሪክና በእውነተኛ የሕይወት ገጠመኝ የበለጸገ ነው። ከእነዚህ ምንባቦች፥ ክርስቲያን ስለ እግዚአብሔር መንገዶች፥ ደኅንነትና ለሰው ስላለው ፈቃድ ጠቃሚ ትምህርት ሊገበይ ይችላል።

ሰ. መጽሐፍ ቅዱስ በእስትንፋስ-እግዚአብሔር ተጻፈ ሲባል ምን ማለት ነው?

እግዚአብሔር ቃሉን ያስተላለፈበትን መንገድ ማወቁ አስፈላጊ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ» ይላል (2 ጴጥ. 1፡21)። በሌላ አባባል፥ መንፈስ ቅዱስ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎችን መርቶአቸዋል ማለት ነው። ይህም ማለት አእምሮአቸውን በዚህ ዓይነት በማንቀሳቀሱ፥ እርሱ እንዲጽፉ የፈለገውን በትክክል ጽፈዋል ማለት ነው። ይህም ሆኖ፥ በራሳቸው ቃላትና የአጻጻፍ ዘይቤ መግለጻቸውን ልብ ልንል ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስ፥

«መጽሐፍ ሁሉ» (ሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ) በዚህ ዓይነት በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር እንደ ተጻፈ ያስተምረናል (2 ጢ.ሞ. 3፡16)።

እግዚአብሔር እያንዳንዱን ቃል ለባሪያዎቹ በመናገር አላጻፋቸውም። እንዲያማ ቢሆን ኖሮ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘው እያንዳንዱ መጽሐፍ ሙሉ ለሙሉ ተመሳሳይ ይሆንና የስልት ወይም የቃላት አጠቃቀም ልዩነት ከቶውንም አይስተዋልም ነበር። እውነቱ ግን እያንዳንዱ መጽሐፍ ከሌላው የተለየ መሆኑ ነው። እያንዳንዱ መጽሐፍ የጸሐፊውን ቋንቋ፥ ባህልና ስብእና ያንጸባርቃል። ይህም የሆነው፥ እግዚአብሔር እያንዳንዱ ጸሐፊ የራሱን ቃላት እንዲጠቀም በመፍቀዱ ነው። በመሆኑም፥ ጸሐፊዎች የጻፉት ቃላት እግዚአብሔር እንዲጻፉ የፈለጋቸው ናቸው። የዚህም ምሥጢሩ የጸሐፊዎቹ በመንፈስ ቅዱሱ «መነዳት» ነው (2 ጴጥ. 1፡21)።

እንዲሁም፥ በዮሐንስ 1፡1-2፥ 14 እና በራእይ 19፡13 ኢየሱስ ክርስቶስም «የእግዚአብሔር ቃል» ተብሎአል። መጽሐፍ ቅዱስ በሰው ቋንቋ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ ሁሉ፥ ክርስቶስም በሰው ሥጋ የእግዚአብሔር ቃል ነበር። በመጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃልነትና በክርስቶስ የእግዚአብሔር ቃልነት መካከል አያሌ ድንቅኛ ተመሳሳይነቶች አሉ።

ክርስቶስ ኃጢአት የሌለበት ሲሆን፥ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ከስሕተት የጸዳ ነው። የክርስቶስ የተቀደሰ ሕይወት የሰዎችን ኃጢአቶች ሲያጋልጥ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ንጹሕ ትምህርት የሰዎችን ኃጢአቶች ያጋልጣል። ክፉ ሰዎች ክርስቶስን በመጥላት በስቅላት ሲገድሉት፥ በታሪክ ሁሉ ክፉ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ጠልተው እስከናካቴው ለማጥፋት ጥረዋል። እርሱን ለማጥፋት ከተደረጉ ጥረቶች ባሻገር፥ ክርስቶስ አምላክነቱን በማስመስከር ከሙታን ተለይቶ ተነሥቷል። መጽሐፍ ቅዱስም የማጥፊያ ሙከራዎቹን ሁሉ ተቋቁሞና የተሰነዘሩበትን ትችቶች ሁሉ አልፎ፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላከ መጽሐፍ መሆኑን አረጋግጧል። ክርስቶስ የመጣው ሰዎች ከኃጢአት የሚላቀቁበትን ደኅንነት ለማምጣት ሲሆን፥ መጽሐፍ ቅዱስ የተሰጠው ያንኑ ደኅንነት ለሰው ልጆች ለመግለጽ ነበር። ክርስቶስ የመጣው ከሁሉም ዘሮችና ባህሎች ሰዎችን ለማዳን ሲሆን፥ መጽሐፍ ቅዱስም በዓለም ከማንኛውም መጽሐፍ በላቀ ቁጥር ተሰራጭቶ ለበርካታ ዘሮችና ባህሎች ተዳርሷል።

እስትንፋሰ-እግዚአብሔር፥ መገለጥና አብርሆት

መንፈስ ቅዱስ ለእኛ መጽሐፍ ቅዱስን ለማድረስ የተጠቀመባቸውን ሁኔዎታዎች ለመግለጽ ያገለገሉትን እነዚህን ሦስት ቃላት መረዳቱ አስፈላጊ ነው - እስትንፋሰ-እግዚአብሔር፥ መገለጽና አብርሆት።

እስትንፋሰ-እግዚአብሔር ("Inspiration")፥ መጽሐፍ ቅዱስን የጻፉ ሰዎች ቃሉን ይመዘግቡ ዘንድ፥ እግዚአብሔር አእምሮአቸውን ያነሣሣበት (ያንቀሳቀሰበት) ሂደት ነው። አሁን እግዚአብሔር ይህንኑ ተግባር ፈጽሞአል። አሁን መጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ ስላለቀ (ራእይ 22፡18-19)፥ ምሳሌ 30፡6፥ «እንዳይዘልፍህ፥ ሐሰተኛም እንዳትሆን በቃሉ አንዳች አትጨምር» በማለት ያስጠነቅቅናል። ዛሬ መጽሐፍ ቅዱስን የጻፉ ሰዎች የነበራቸው ዓይነት እስትንፋሰ-እግዚአብሔር እንዳለው አድርጎ የሚናገር ማንም ሰው አይኖርም።

መገለጥ ወይም ራእይ ("Revelation")፥ እግዚአብሔር ለመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች እነርሱ በራሳቸው ሊያውቁአቸው የማይችሉአቸውን ነገሮች ያስታወቀበት ተግባር ነው። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን እግዚአብሔር ስለ ፍጥረት ታሪክ ለሙሴ ያስታወቀበት መገለጥ ነው (ዘፍ. 1-4)። ሌላው የመገለጥ ምሳሌ፥ ሰው ሊገምተው የማይችል የነበረው እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል (ሥላሴ) የሚያስረዳ እውቀት ነው። አሁን መጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ ስላለቀ፥ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሁሉ የሚያስተላልፋቸው እስትንፋሰ-እግዚአብሔር ያረፈባቸው መገለጦችም አብቅተዋል። በሌላ አባባል፥ አሁን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ምንም ነገር ልንጨምር አንችልም [ዘዳ. 4፡2፤ መዝ. (119)፡89]። በዚህም ምክንያት፥ ክርስቲያኖች የሞርሞኖችንና እንደዚሁም ከእግዚአብሔር የመጡ አዳዲስ መገለጦች የሚል ቅጽል አስከትለው የሚያንጎራብቡትን መጻሕፍት ሊቀበሉ አይችሉም።

ይህም ሲባል፥ እንግዲህ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ምንም ነገር አይገልጽም ማለት አይደለም። የሐናንያና ሰጲራን ጉዳይ በተመለከተ ለጴጥሮስ በተሰጠው የእውቀት ስጦታ፥ እግዚአብሔር ስለ ማታለላቸው የተወሰኑ እውነቶችን ለጴጥሮስ ገልጾአል (የሐዋ. 5፡1-10)። ዛሬም እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ ተመሳሳይ ስጦታዎችን ለቤተ ክርስቲያኑ

ይሰጣል። ይሁንና፥ ይህ በሁሉም ባህል ለሚገኙ ሕዝቦች ሁሉ ከተሰጡት የመጽሐፍ ቅዱስ መገለጦች ለየት ይላል።

አብርሆት ("Illumination") መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃል ለሚያነቡና ለሚያጠኑ ሰዎች መረዳትን የሚሰጥበት ሂደት ነው። ይህንንም በትውልድ ሁሉ ለሕዝቡ ያደርጋል። ዛሬ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃል እንረዳ ዘንድ አእምሮአችንን እንዲከፍት ልንጸልይና በታማኝነት ጸሎታችንን ሊመልስ ልንመለከት እንችላለን። መዝሙረኛው በመዝሙር (119)፡18፥ «ዓይኖቼን ከፈት፥ ከሕግህም ተአምራትህን አያለሁ» ሲል፥ እንዲህ ላለው አብርሆት መጸለዩ ነበር።

ማጠቃለያ

የብሉይና አዲስ ኪዳን መጻሕፍት ለጻፉአቸው ሰዎች እንደ መሰጠታቸው መጠን፥ ምሉዕነት፥ ሥልጣን ያላቸው፥ የመጨረሻና ትክክለኛ የእግዚአብሔር ቃል ናቸው። ኢየሱስ ክርስቶስም ያመነውና ያስተማረው ይህንኑ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነን ከሚሉ ሌሎች የሃይማኖት መጻሕፍት ሁሉ ጋር ሲነጻጸር፥ ብቸኛ የእግዚአብሔር ቃልነቱን ያረጋግጣል። መጽሐፍ ቅዱስ ከሌሎች መጻሕፍት አንድኛው እንኳ የማይፈጽመውን ተግባር ይፈጽማል። በትክክል የወደፊት ክስተቶችን ይተነብያል - ከቶውንም አይሳሳትም።

በተጨማሪም፥ በአያሌ ሌሎች ፈተናዎች ተፈትኖ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን አረጋግጧል። እግዚአብሔር ራሱ የመጽሐፍ ቅዱስን መጻፍ በእስትንፋሱ ተቆጣጥሮ፥ በመለኮታዊ መገለጥ ለሰዎች ሰጥቷል። የምንረዳውም ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ አብርሆት ነው።

በምዕራፍ 2 ላይ የተመሠረቱ የመወያያ ጥያቄዎችና መልመጃዎች

1. በአንድ ዩንቨርስቲ የሃይማኖት ፕሮፌሰር የሆነ ምሁር፥ መጽሐፍ ቅዱስ በዓለም ውስጥ በሃይማኖት ርዕሰ-ጉዳይ ላይ ከተጻፉ አያሌ መጻሕፍት አንዱ እንደ ሆነ፥ ከሌሎችም መጻሕፍት እንደማይልቅና እንደማይተናነስም ይናገራል። ከቡድኑ ውስጥ አያንዳንዱ ሰው ለዚህ ፕሮፌሰር የቃል ምላሽ ያዘጋጅ። ከዚያም ከሌሎቹ በፊት፥ ሦስት ሰዎች ምላሾቻቸውን ያቅርቡ።

2. በቡድኑ ውስጥ ያለውን እያንዳንዱን ሰው ከሌላው ሃይማኖት ተከታይ ጓደኛው ጋር የተወሰነ ጊዜ እንዲያሳልፍ አድርግ። ከዚያም ያንኑ የሌላ ሃይማኖት ተከታይ፥ ከሃይማኖታዊ ወጉ ወይም ከተቀደሰው መጽሐፉ አሉኝ የሚላቸውን ሦስት ዋንኛ ነገሮች እንዲነግረው ይጠይቀው። ከዚያ በኋላ፥ ክርስቲያኑ ከመጽሐፍ ቅዱስ እጅግ አስፈላጊዎች ናቸው የሚላቸውን ሦስት ጥቅሶች ያካፍለው።

3. በቡድኑ ውስጥ እያንዳንዱ ተማሪ ለጸሎቱ ያገኛቸውን እምስት ምላሾች ይዘርዝር። ከዚያም እያንዳንዱ ተማሪ እነዚህ የጸሎት ምላሾች መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ ለማሳየት ለምን እንደሚረዱ ያብራራ።

4. ተማሪዎቹን ሦስት አባላት በሚገኙበት ቡድን ከፈላቸው። እያንዳንዱ አናሳ ቡድን ስለ ክርስቶስ የመጀመሪያው መምጣት አምስት ትንቢቶችን ከብሉይ ኪዳን በማውጣት፥ ፍጻሜአቸውን ከአዲስ ኪዳን እንዲያሳይ አድርግ።

5. እያንዳንዱ ግለሰብ መዝሙር (22)ን በጥንቃቄ በማንበብ፥ በዚህ መዝሙር ስለ ክርስቶስ የተነገሩትን ዝርዝር ጉዳዮች በሙሉ እንዲያወጣ አድርግ።

6. እያንዳንዱ ሰው ስለ ራሱ የሕይወት ልምምድ በቃል የሚቀርብ ምስክርነት እንዲያዘጋጅ ጠይቅ፤ ይህም ምስክርነት በክርስቶስ ከማመኑ የተነሣ፥ እግዚአብሔር ባሕርዩን ከኃጢአት ወደ ጽድቅ እንዴት እንደ ለወጠው አጉልቶ የሚያሳይ ይሁን።

7. ተማሪዎቹን ሦስት አባላት በሚገኙበት ቡድን ከፈላቸው። እያንዳንዱ ቡድን ማርቆስ 12፡26-27ን በጥንቃቄ ያንብብ። እያንዳንዱ ቡድን ክርስቶስ ይህንን ምንባብ፥ ሀ) የትንሣኤን እውነትነትና ለ) መጽሐፍ ቅዱስ በውስጡ ካካተታቸው እያንዳንዳቸው ቃላት ጋር ጭምር ትክክል እንደ ሆነ ለማሳየት የተጠቀመበትን መንገድ ይግለጽ።

8. እያንዳንዱ ሰው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ በአራት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ላይ ያደረገለትን አብርሆት ይመዝግብ።

9. ዛሬ ብሉይ ኪዳን ከክርስቲያኖች ጋር አይዛመድም ለሚል ሰው፥ እንዴት ምላሽ ትሰጣለህ?

10. አንድ ሰው ብሉይ ኪዳንም የአዲስ ኪዳንን ያህል የእግዚአብሔር ቃል በመሆኑ፥ ክርስቲያኖች የብሉይ ኪዳን አማኞች ያደረጉአቸውን (የብሉይ ኪዳን የምግብ ሥርዓቶችን እንደ መጠበቅ ያሉትን) ነገሮች ማድረግ ይገባቸዋል ቢልህ፥ ምን ምላሽ ትሰጣለህ? ለምላሽህ ድጋፍ የሚሆኑትን ጥቅሶች ስጥ።

11. ስለ ወደፊት ጉዳዮች ለማወቅ ጠንቋዮችን ወይም ሞራ ገላጮችን ማማከር ትክክል ነው ወይስ ስሕተት? በቡድን ተወያዩ።

12. የአፍሪካን አፈ-ታሪኮችና ሥነ-ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በማወዳደር በቡድን ተወያዩ።

SUGGESTED FOR FURTHER READING

Bruce, F. F. The Books and the Parchments. London: Marshall Pickering, reissued 1988.

Bruce, F. F. The New Testament Documents. Leicester: Inter Varsity Press, 1960.

Goldsworthy, G. According to Plan: The Unfolding Revelation of God in the Bible. Leicester: Inter Varsity Press, 1991.

Lindsell, Harold. The Battle For The Bible. Grand Rapids, Michigan: Zondervan, 1976.

MacArthur, John F. Focus on Fact: Why You Can Trust The Bible. Old Tappan, New Jersey: Fleming Revell, 1977.

Packer, J. I. God Has Spoken. London: Hodder, 2nd edn 1979.

ምዕራፍ 3

መጽሐፍ ቅዱስ ወደ እኛ እንዴት እንደ መጣ

ኪንዶ፡- «መጽሐፍ ቅዱስ ከየት መጣ?»

ያልዱት፡- «እኔም ራሴ ይህንን ጉዳይ ለማወቅ እፈልጋለሁ። ምንም እንኳ አንዳንድ ታሪኮችን የሰማሁ ብሆንም፥ እርግጠኛውን ነገር አላውቅም። የማያምኑ ጓደኞቼ ብዙውን ጊዜ ስለዚህ ጉዳይ ይጠይቁኛል።»

ኪንዶ፡- «በትምህርት ቤት የሃይማኖት አስተማሪዬ መጽሐፍ ቅዱስ መጀመሪያ ከተጻፈበት ጊዜ አንሥቶ ብዙ ለውጦች እንደ ተካሄዱበት ይናገራል። የዚህን አሳብ እውነትነት ወይም ሐሰተኛነት የምናረጋግጥበትን መንገድ ብናገኝ እንዴት መልካም ነበር።»

ያልዱት፡- «የካቶሊክ እምነት ተከታይ የሆነው ጓደኛዬ ጆን፥ የዚህን ዓይነቶቹን ጥያቄዎች እንደምትመልስ ልንተማመንባት የሚገባው በቤተ ክርስቲያን ነው ባይ ነው። ግን አንድ ነገር ታውቃለህ? ዛሬ መጽሐፍ ቅዱሱን ስመለከት ከኔው የተለየ ሆኖ አገኘሁት። የእርሱ መጽሐፍ ቅዱስ ከእኛው የበረከቱ መጻሕፍት አካቶ ይዞአል። ለምን ይሆን? ትክክለኛውስ የማን ይሆን?»

በመጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት እንዳገኘን መከለሱ አስፈላጊ ነው። የተለያዩ እትሞችና ትርጉሞች መታየት የጀመሩት መቼ ነው? ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ እንደ ተመለከትነው፥ መጽሐፍ ቅዱስ መጀመሪያ ለጻፉት ሰዎች ሊሰጥ ትክክለኛና እስትንፋስ-እግዚአብሔር ያረፈበት ነበር። ከጥንት እስከ ዛሬ እየተላለፈ ሲመጣ ተለውጦ ይሆን፥ ወይስ አሁንም መሠረታዊ ይዘቱ ያው ነው? የካቶሊኮች መጽሐፍ ቅዱስ ከሌሎች ካቶሊክ ካልሆኑት መጽሐፍ ቅዱሶች በቁጥር የሚበልጡ መጻሕፍትን ያካተተው ለምንድ ነው? በዚህ ምዕራፍ የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንመለከታለን።

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት አገኘን?

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ ከአንዱ ቋንቋ ወደ ሌላው በመተርጎሙና ለበርካታ መቶ ዓመታት ከትውልድ ትውልድ እየተላለፈ በመምጣቱ ተለውጦ ይሆን?

ሐ. ዐበይት የእንግሊዝኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱሶች የትኞቹ ናቸው?

መ. የሮም ካቲሊክ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ የተለየው ለምንድን ነው?

ሠ. ከሁሉም ትክክለኛ የሆነው የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ እትም የትኛው ነው?

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት አገኘን?

መጽሐፍ ቅዱስ በመጻፍ ሂደት 1500 ዓመታትን ያህል አስቆጥሮ ወደ እኛ የደረሰ የ66 መጻሕፍት ስብስብ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት እንዳገኘን መረዳቱ ለእኛ አስፈላጊ ነው። ዛሬ ያለንን መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ማግኘቱ ደረጃ የመሩን ክስተቶች እንደሚከተለው በአጭሩ በማጠቃለያ መልክ ቀርበዋል።

በመጀመሪያ ሥነ-ቃል ነበር

በመጀመሪያ (ዘፍጥረት 2 እና 3) እግዚአብሔር ከአዳምና ሔዋን ጋር በዔድን ገነት የአትክልት ስፍራ ፊት ለፊት ይነጋገር ነበር። እግዚአብሔር የተናገራቸው ነገሮችና የሌሎች ነገሮች ግንዛቤዎች ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል (ሥነ-ቃል) ይተላለፉ ነበር። ምናልባትም ይህ የሆነው ልክ በአፍሪካውያን መንደሮች ሽማግሌዎችና ወጣቶች በምሽት በእሳት ዙሪያ ተሰብስበው አፈ-ታሪኮችን ከአንዱ ወደ ሌላው ትውልድ በሚያስተላለፉበት መልክ ይሆናል። በዚያን ጊዜ ምንም ዓይነት የተጻፉ መጻሕፍት ወይም የመጻሕፍት ጥቅልሎች አልነበሩም።

የሥነ-ቃል መጻፍ መጀመር

በኋላ እግዚአብሔር በፍጥረትና በኋለኛው የሰው ልጅ ታሪክ ወቅት የተፈጸመውን ነገር ለሙሴ ገለጸለት (ዘጸ. 12፡7፥ 8፤ ዘዳ. 29፡29)። ሙሴም ከእግዚአብሔር የሰማቸውን ነገሮች በመጽሐፍ ጥቅልል ውስጥ አሰፈረው (ዘጸ. 24፡4)።

ሥዕላዊ የአጻጻፍ ዘይቤ የተጀመረው በመጀመሪያው የሰው ታሪክ፥ ምናልባትም በኖኅ ዘመን ከተፈጸመው የውኃ ጥፋት በኋላ ይሆናል። በአብርሃምና ኢዮብ ዘመን (በ2000 ዓ. ዓ. አካባቢ) መስጴጦምያ በሽብልቅ መሳይ ቅርፃቅርጾች መጻፍ የተለመደ ነበር። የዚህ ዓይነቱ ጽሑፍ የሚዘጋጀው መጻፊያ ዘንጉን በለስላሳ ሸክላ ውስጥ በመጫን

ነበር። መጻፊያ ዘንጉም ከጫፉ ላይ አነስተኛ የሽብልቅ ቅርጽ ያለው ነበር። በመሆኑም፥ የተለያዩ የሽብልቆችን ውህዶችና ቅርጾች በማገናኘት ቃላትን ይሠሩ ነበር።

ሙሴ ፔንታቱክ የሚባሉትን አምስት የመጀመሪያ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ጽፎአል። ሙሴ በግብፅ በፈርዖን ቤተ መንግሥት የተማረ በመሆኑ፥ እነዚህን ጥንታዊ ጽሑፎች ለመመዝገብ ሄሮግሊፊክስ የሚባለውን የግብፃውያን ሥዕላዊ የአጻጻፍ ስልት ሳይጠቀም አይቀርም። እነዚህ ጽሑፎች የመጽሐፍ ጥቅልሎች በሚባሉ ረዣዥም ልዩ ወረቀቶች ላይ በእጅ ይጻፉ ነበር። የመጽሐፍ ጥቅልሎቹም የሚዘጋጁት በዓባይ ወንዝ ዳርቻ ከሚበቅለው የሸምበቆ ተክል ከሚሠራው «ፓፒረስ» ከተባለ ነገር ነበር። ሌሎች የመጽሐፍ ጥቅልሎች ደግሞ ከደረቅ የፍየል ቆዳ የሚዘጋጁ ናቸው። እነዚህ የመጽሐፍ ጥቅልሎች እስከ 30 ሜጣ የሚረዝሙና ከዘጠኝ እስከ አሥር ኢንች ከፍታ ያላቸው ነበሩ። አንዳንድ ጥቅልሎች በውስጣቸው ከአንድ የሚልቁ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ያካትቱ ነበር።

ከጊዜ ወደ ጊዜ እግዚአብሔር ቃሉን ይጽፉ ዘንድ ሰዎችን አስነሥቷል (2 ጴጥ. 1፡21)። እነዚህም ሰዎች፥ ምናልባትም ከመጽሐፈ ኢዮብ ጀምሮ፥ እግዚአብሔር እንዲጽፉ የፈለገውን ነገር ጽፈዋል።

የመጀመሪያዎቹ የመጻሕፍት ጥቅልሎች ለተለያዩ ቡድን ሰዎች ተነበዋል። የመጀመሪያዎቹ ጥቅልሎች ሲነትቡ፥ የያዙትን ቁም ነገር ላለማጣት መገልበጡ የግድ ሆነ። በዚህም የጽሕፈት ሥራ ተጀመረ። ጸሐፍቱ በጥንቃቄ ቃል በቃል የመጻሕፍቱን ምንባቦች ይገለብጡ ነበር።

የመጀመሪያዎቹ መጻሕፍት ቅጂዎች በከፍተኛ ጥንቃቄ በእጅ ይገለበጡ ነበር። ጸሐፍቱ ብዙውን ጊዜ በጠቅላላው መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙትን ፊደላት ይቆጥሩና ጽፈው ሲያበቁ ተመልሰው ያመሳክሩ ነበር። እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ሲገለብጡ ስሕተት እንዳይፈጽሙ፥ የመጽሐፉን ማዕከላዊ ፊደል ለይተው ይመለከቱ ነበር። በመሆኑም መንፈስ ቅዱስ በእነዚህ ጸሐፍት ልብ ውስጥ እንዲህ ያለ ታላቅ የጥንቃቄ መንፈስ በማስቀመጥ፥ የመጽሐፍ ቅዱስን ሽግግር ከለውጦችና ከስሕተቶች ይጠብቅ እንደ ነበር እንመለከታለን። የብሉይ ኪዳን መዛግብት ቅጂዎች የተጻፉት በዕብራይስጥ ቋንቋ ነበር።

የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና ምንድን ነው?

ቀኖና የሚለው ቃል መመዘኛ ወይም መመሪያ የሚል አሳብ አለው። በዚህ አሳብ ዙርያ ሰዎች የሚያነሡአቸው ጥያቄዎች የሚከተሉትን

ያጠቃልላሉ፡- ሰዎች እስትንፋሰ-እግዚአብሔር ያረፉባቸውንና ተራ መጻሕፍትን እንዴት ለይተው አወቁ? በሌላ አባባል፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚካተቱትን መጻሕፍት እንዴት አወቁ? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተካተቱ መጻሕፍት የቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖና፥ ማለትም መመዘኛ ወይም ተቀባይነት ግግኝታቸው የተረጋገጠላቸው መጻሕፍት በመባል ይታወቃሉ።

በብሉይ ኪዳን ዘመን መጻሕፍትን እንደ እግዚአብሔር ቃል የመቀበሉ ወይም ያለመቀበሉ መንገድ በእግዚአብሔር ሕዝቦች የሚወሰን ነበር። የእግዚአብሔር ሕዝቦች፥ በተለይም በእግዚአብሔር ሕግ የሠለጠኑ ካህናት፥ ከእግዚአብሔር የሆኑትን መጻሕፍት ለይተው ያውቁ ነበር። ዕዝራ ለዚህ ዓይነቱ ካህን መልካም ምሳሌ ነው (ዕዝራ 7፡10)። ምናልባትም ይህ እውቅና ሊገኝ የቻለው ልክ አንድ ልጅ የአባቱ ስም በደብዳቤው ውስጥ ባይኖርም እንኳ፥ ልጁ ከአባቱ የተላከውን ደብዳቤ ለይቶ በሚያውቅበት መንገድ ይሆናል።

በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ የእግዚአብሔርን ቃል ለይቶ ያወቀበትና ያከበረበት ምሳሌያዊ ገጠመኝ፥ ካህኑ ዕዝራ ነህምያ 8፡1-8ን ካነበበበት ሁኔታ በግልጽ ሊታይ ይችላል። ሕዝቡ ቆመው ካዳመጡ በኋላ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ለይተው እንዳወቁና እንዳከበሩ በግላየት፥ ሰግደው አመለኩ (ነህ. 8፡5-6)።

በአዲስ ኪዳን ዘመን የእግዚአብሔርን ቃል የመለየቱ ሂደት ይበልጥ ፈር የያዘ ነበር። የአዲስ ኪዳን የመጻሕፍት ጥቅልሎች ከተጻፉ ብዙም ሳይቆይ፥ የትኞቹ በትክክል የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆኑ ለመወሰን እያንዳንዱ መጽሐፍ ተመርምሯል። ከሁሉም የሚልቀው ምርመራ (ፈተና) ይኼ ነበር - መጽሐፉ ወይም ደብዳቤው የተጻፈው ከክርስቶስ ሐዋርያት በአንዱ ነው፥ ወይስ ጽሑፉ ሐዋርያዊ ድጋፍ አግኝቷል? ሌላው ፈተና ደግሞ፥ ይህ መጽሐፍ ወይም መዛግብት የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ ተስማምተዋል? የሚል ነበር።

አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያኖች ግን መጽሐፉን እንደ ጻፈው በርግጠኝነት ሳያውቁ ሲቀሩ፥ መጽሐፉ በቀኖና ውስጥ ይጨመር ወይስ አይጨመር ለሚለው ሞጋች ጥያቄ ውሳኔ ለመስጠት ለአብያተ ክርስቲያናት ረዥም ጊዜያት ወስዱል (ለምሳሌ፥ የዕብራውያን መጽሐፍ)። በ397 ዓ. ም.

በሰሜን አፍሪካ ካርቴጅ በዋለው ጉባኤ፥ ዛሬ በአዲስ ኪዳናችን ውስጥ የሚገኙ መጻሕፍት የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና አካላት ተደርገው ተጠቃለሉ።

ሴፕቱዋጀንት

በብሉይና አዲስ ኪዳን መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ ግሪክ የሮም ዓለም የንግድ ቋንቋ ሆኖ አደገ። በመሆኑም፥ ብሉይ ኪዳን በሰባ ሁለት የአይሁድ ምሁራን አማካኝነት በ250 ዓ. ዓ. አካባቢ ወደ ግሪክኛ ተተረጎመ። ይህም የብሉይ ኪዳን እትም ሴፕቱዋጀንት በመባል ይታወቃል። በኋላም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሲጻፉ፥ እነርሱም በግሪክኛ ተጻፉ።

ቩልጌት

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እጅግ አስፈላጊ ከሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች አንዱ የተከናወነው ጀሮም በተባለ ካቶሊካዊ ምሁር አማካኝነት በ388 ዓ. ም. ነበር። ይህ ቩልጌት የተባለው ሥራው ከሴፕቱዋጀንትና ከአዲስ ኪዳን መዛግብት ወደ ላቲን የተተረጎመ ነበር። ትርጉሙ ዛሬ የምንጠቀምባቸውን 66 መጻሕፍት አካቶ ይዞ ነበር።

ጥንታዊ መዛግብት

በሦስተኛው ምዕተ-ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥንታዊ መዛግብት «ኮዴክስ» በሚባል ቅርጽ ይቀመጡ ነበር። ሁለት ወይም ከዚያ ሲበዙ ደግሞ «ኮዲሴዝ» ይባላሉ። ኮዴክስ የግስታወሻ ደብተር በሚመስል ቅርጽ ተዘጋጅተው፥ እንደ መጽሐፍ የተያያዙትን በእጅ የተጻፉ ገጾች ያጠቃልል ነበር። በእጅ ይጻፉ ስለ ነበር፥ በጣም ጥቂት ኮዲሴዝ (መጽሐፍ ቅዱሶች) ብቻ ይገኙ ነበር፤ በመሆኑም፥ በአግባቡ ደረጃ የሚገኘው የቤተ ክርስቲያን አባል ከቶውንም አይቶአቸው አያውቅም ነበር። የነበሩት እነዚሁ ጥቂት ቅጂዎችም ቢሆኑ፥ በገዳማት ተወስነው በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መነኮሳትና ካህናት ይጠኑ ነበር። ከ1000 ዓመታት በኋላ የማተሚያ መሣሪያ እስከ ተፈለሰፈበት ጊዜ ድረስ፥ ተራው የቤተ ክርስቲያን አባል የራሱ የሆነ መጽሐፍ ቅዱስ አልነበረውም።

የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ የመነጨው ከምንድን ነው?

የዮሐንስ ወንጌል ከላቲኑ ቩልጌት መጽሐፍ ቅዱስ «አንግሎ-ሳክሰን» ("Anglo-Saxon") ወደ ተባለ በጣም ጥንታዊ የእንግሊዝኛ ቋንቋ በ735 ዓ. ም. በእንግሊዝ አገር ተተረጎመ። የትርጉም ሥራውም የተከናወነው ቤዳ በተባለ መነኩሴ አማካኝነት ከመሞቱ ጥቂት ቀደም ብሎ ነበር። በ1384

ጆን ዊክሊፍ የተባለ እንግሊዛዊ ከጥቂት ወገኖች ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ መለሰ። በዚያን ጊዜ ይህንኑ የዊክሊፍ የትርጉም ሥራ ለማተምና ለማሰራጨት የሚቻልበት ምንም ዓይነት መንገድ አልነበረም።

በታሪክ መጽሐፍ ቅዱስን በስፋት ለማሰራጨትና ለማገልገል ከሁሉም የላቀው ፍልሰቴ የሕትመት መሣሪያ ነው። ይህም የሕትመት መሣሪያ በ1456 ዓ. ም. በጀርመን በጆሐን ጉተንበርግ አማካኝነት ተፈለሰፈ። መጀመሪያ ያተመው መጽሐፍ የመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰነ ክፍል ነበር። የሕትመት መሣሪያ ብዙዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ባለቤት እንዲሆኑ አደረገ። የመጀመሪያው የጀርመንኛ መጽሐፍ ቅዱስ በ1467 ዓ. ም. ታተመ። የመጀመሪያ የፈረንሳይኛ ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስ በ1487 ዓ. ም. ታተመ።

በ1526 ዊልያም ቲንዴይል ለተራው የቤተ ክርስቲያን ምእመን የእንግሊዝኛ ቋንቋ አዲስ ኪዳን አዘጋጀ። ይሁንና፥ የዚህ ዓይነቱ ተግባር ቤተ ክርስቲያን በአባሎቿ ላይ የሚኖራትን አገዛዝ ስለሚቀንስ፥ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በቲንዴይል የትርጉም ሥራ አልተደሰተችም ነበር። በዚህ ጊዜ ተራው ሰው ራሱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረው ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ይስማማ እንደ ሆነ ለማረጋገጥ ይችል ነበር። በመሆኑም፥ ለእንግሊዝኛ ተናጋሪዎች ሁሉ ላበረከተው ለዚህ ብሩክ አገልግሎቱ፥ ዊልያም ቲንዴይል በ1536 ታፍኖና ተቃጥሎ ተገደለ - ለእግዚአብሔር ቃል መስፋፋት ራሱን የሰጠ ሰማዕት!

የመጽሐፍ ቅዱስ መታተምና መሰራጨት፥ ብዙ ክርስቲያኖች ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ለቀው እንዲወጡ ያደረገ ጠቃሚ ለውጥ ነበር። ይህም ማርቲን ሉተርና ጆን ካልቪን የመሪነቱን ሚና ወደ ተጫወቱበት የፕሮቴስታንት እምነት ተሐድሶ አቀና።

ሉተር መጀመሪያ የካቶሊክ እምነት ቄስ ነበር። ሁኔታውን ከመረዳቱ የተነሣ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ለመከፋፈል አልፈለገም ነበር፤ ዳሩ ግን የቤተ ክርስቲያኒቱ አባቦች በግልጽ የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት በመቃወማቸው፥ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አባቦች ጋር አለመስማማቱን መረጠ። ሉተር ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጋር ያልተስማማበት አንድኛው ነጥብ፥ አንድ ሰው እንዴት ሊድን ይችላል የሚለው ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም» ይላል (ኤፌ. 2፡8-9)። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ደኅንነት የሚገኘው

በእምነት ላይ ሥራ ሲጨመር ነው በማለት ታስተምራለች። ዛሬም ፕሮቴስታንቶች ከካቶሊኮች ጋር በዚህ ጉዳይ አይስማሙም።

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ ከአንዱ ቋንቋ ወደ ሌላው በመተርጎሙና ለበርካታ መቶ ዓመታት ከትውልድ ትውልድ እየተላለፈ በመምጣቱ ተለውጦ ይሆን?

ብዙውን ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሲሰነዘር የምንሰማው ትችት ለበርካታ መቶ ዓመታት እየተላለፈ በመምጣቱ ተለውጧል የሚል ነው። ክርስቲያኖች ሁልጊዜም መንፈስ ቅዱስ የመጽሐፍ ቅዱስን መጻፍ በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር እንደ መራው ሁሉ፥ የመተላለፉንም ሂደት እንደ ጠበቀው ያምናሉ። እስከ 1947 ዓ. ም. ድረስ ይህንን ለማረጋገጥ የሚቻልበት መንገድ በእውነቱ አልነበረም። እስከ 1947 ድረስ የዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ ቅጂዎች ከመካከለኛው ዘመን ርቀው አይሄዱም ነበር። እነዚህም «ማሶሪትስ» ("Masoretes") በተባለው የመኑሳት ተዋረድ ተገልብጠው የተጠበቁ የዕብራይስጥ መጻሕፍት ነበሩ። እነዚህን መዛግብት ማመሳከር የሚቻልባቸው ቀደምት ሰነዶች ስላልነበሩ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ሲገለጥና ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ ተለውጦ እንደ ሆነ የሚያውቅ አልነበረም።

የሙት ባሕር የመጻሕፍት ጥቅልሎች

በ1947 ዓ. ም. አንድ የዓረብ እረኛ ልጅ አንዳንድ እጅግ ጥንታዊ የመጻሕፍት ጥቅልሎችን አግኝቷል፤ እነዚህንም ጥቅልሎች ያገኘው በእስራኤል አገር በሙት ባሕር አካባቢ በአንዳንድ ዋሻዎች ከነበሩ ማድጋዎች ውስጥ ነበር። የመጽሐፍ ጥቅልሎች የተደበቁት በመጀመሪያው ምዕተ-ዓመት በአጥባቂ የአይሁድ ወንድማማቾች ነበር። ከእነዚህ ጥቅልሎች ከመጽሐፈ አስቴር በስተቀር፥ ከጠቅላላው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ቁርጥራጮች ተገኝተዋል። እነዚህም ጥቅልሎች በአሁኑ ጊዜ እጅግ የላቁ የመጽሐፍ ቅዱስ ግኝቶች ሆነዋል።

የሙት ባሕር የመጽሐፍ ጥቅልሎች መገኘት የመጽሐፍ ቅዱስን ትውልዳዊ ተዋረድ ትክክለኛነት አጠናክሯል። ሃያሲያን ዛሬ የያዝነው መጽሐፍ ቅዱስ ከመጀመሪያዎቹ መዛግብት ሙሉ ለሙሉ መለየት እንዳለበት ተናግረው ነበር። ይሁንና፥ የሙት ባሕር የመጽሐፍ ጥቅልሎች የብሉይ ኪዳን «ማሶሬቲክ» መጻሕፍት ከእነዚሁ መዛግብት ጋር አንድ ዓይነት እንደ ሆኑ ገልጸው አሳይተዋል። የሙት ባሕር የመጻሕፍት

ጥቅልሎች ምሁራን የኋለኛ መዛግብቶቻቸውን ከእነዚህ እጅግ ጥንታዊ ከሆኑት ጋር እንዲያስተያዩ አስችለዋል። ባስተያዩዋቸውም ጊዜ፥ በይዘታቸው አንድ ዓይነት መሆናቸውን ተረድተዋል።

ከሙት ባሕር የመጻሕፍት ጥቅልሎች፥ በክርስቶስ ዘመን የተጻፈ የኢሳይያስ መጽሐፍ ሙሉ ቅጂ ይገኛል። ምሁራን የኢሳይያስን የመጽሐፍ ጥቅልል ከ«ማሶሬቲክ» መጽሐፍ ጋር የምዕራፉን ቁጥር እየተከተሉ አመሳክረዋል። በውጤቱም ምንም እንኳ የኢሳይያስ የመጽሐፍ ጥቅልል ከ«ማሶሬቲክ» መጽሐፍ የ1000 ዓመታት ዕድሜ ብልጫ ቢኖረውም፥ ምንባቡ አንድ ዓይነት ሆኖ ተገኝቷል። ይህም ግኝት ጸሐፍቱና መነኮሳቱ የመጽሐፍ ቅዱስን የመጽሐፍ ጥቅልሎች በእጃቸው ሲገለብጡ ምን ያህል ጥንቃቄ እንዳደረጉ አሳይቷል። በተጨማሪም፥ መንፈስ ቅዱስ የመጽሐፍ ቅዱስን ትውልዳዊ ተዋረድ በትክክል እንደ ጠበቀ አሳይቷል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ዋንኛ አስፈላጊ መዛግብት የትኞቹ ናቸው?

የመጽሐፍ ቅዱስ ዋንኛ አስፈላጊ መዝግብት ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል። አንባቢው የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ ለማወቅ፥ እነዚህን ስሞች በሌሎች መጻሕፍት ውስጥ ሊመለከት ይችላል።

1. ኮዴክስ ሲናይቲከስ ("Codex Sinaiticus") - ከብሉይ ኪዳንና ከግሪኩ አዲስ ኪዳን 75 በመቶ።

2. ከዴክስ ቫቲከነስ ("Codex Vaticanus") - ከብሉይ ኪዳንና ከግሪኩ አዲስ ኪዳን 90 በመቶ።

3. ከዴክስ አለክሳንድሪነስ ("Codex Alexandrinus") - ከብሉይ ኪዳንና ከግሪኩ አዲስ ኪዳን 90 በመቶ።

4. ቩልጌት የላቲን ትርጉም።

5. የብሉይ ኪዳን «ማሶሬቲክ» የዕብራይስጥ የመጻሕፍት ጥቅልሎች።

6. የሙት ባሕር የመጻሕፍት ጥቅልሎች።

ሐ. ዐበይት የእንግሊዝኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱሶች የትኞቹ ናቸው?

1. «ከቨርዴይል» («Coverdale») መጽሐፍ ቅዱስ - 1535 ዓ. ም. ይህ በእንግሊዝኛ ለመጀመሪያ ጊዜ ሙሉ ለሙሉ የተተረጎመ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

2. ኪንግ ጄምስ ቬርዥን (KJV) - 1611 ዓ. ም. የኪንግ ጄምስን የመጽሐፍ ቅዱስ እትም የተረጎሙ ሰዎች፥ ዛሬ ምሁራን የሚጠቀሙባቸውን ጥንታዊ መዛግብት ለማግኘት አልታደሉም ነበር። ይሁንና፥ መንፈሳዊ ሰዎች በመሆናቸው በየዕለቱ ሥራቸውን ከመጀመራቸው በፊት ይጸልዩ ነበር።

3. እንግሊሽ ሪቫይዝድ ቬርዥን - 1881።

4. አሜሪካን እስታንዳርድ ቬርዥን - 1901።

5. ሪቫይዝድ እስታንዳርድ ቬርዥን ("RSV") - 1952።

6. ዘ ኒው አሜሪካን እስታንዳርድ ባይብል ("NASB") - 1960።

7. ጉድ ኒውስ ባይብል ("GNB") - 1976።

8. ዘ ኒው ኢንተርናሽናል ቬርዥን ("NIV") - 1978። ይህ እትም ምሁራዊ ከመሆኑም፥ ለማንበብም ቀላል ነው።

«RSV» «NASB» እና «NIV» ለማዘጋጀት፥ ምሁራን ከ1930 ዓ. ም. በፊት ከነበሩ ተርጓሚዎች የተሻሉ ጥንታዊ መዛግብትና በቅርቡ የተመዘገቡ የከርሰ-ምድር ውጤቶች ነበሩዋቸው።

በተለያዩ ትርጉሞችና እትሞች መካከል የሚገኘው ልዩነት ምንድን ነው?

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የተዘጋጁት በአንድ ግለሰብ ሲሆን፥ ሌሎቹ ደግሞ በምሁራን ኮሚቴ ነው። በኮሚቴ የሚሠራው ሥራ የትብብርና የብዙ ምሁራንን እውቀት የማቀናጀት ጥቅም ይጎላበታል። በመሆኑም፥ በእንዲህ ዓይነት የትርጉም ኮሚቴዎች የሚዘጋጁ እትሞች በአንድ ግለሰብ ከሚሠሩት የበለጠ ታሪካዊ ጥራትና ትክክለኛነት ነበራቸው።

«RSV» «NASB» እና «NIV» ከፍተኛ ችሎታ የነበራቸው ምሁራን በሚገኙባቸው ኮሚቴዎች የተዘጋጁ የእንግሊዝኛ ቋንቋ እትሞች ናቸው። «ዊይማውዝ፥» «ሞፋት፥» «ጉድስፒድ» እና «ፊሊፕስ» እትሞች በአንድ ሰው የተከናወኑ ትርጉሞች ምሳሌዎች ናቸው። «ዘ ሊቭንግ ባይብል» (በአማርኛው «ሕያው ቃል» አዲስ ኪዳን እትም) ይበልጥ በነጻ ትርጉም የተሠራ ነው። የተሠራውም በአንድ ሰው ነው። ምንም እንኳ ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ለማንበብ ቀለል በማለቱ ጠቃሚ ቢሆንም፥ ትክክለኛ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ እንዲሆን ታስቦ የተሠራ አልነበረም። ጥንቃቄ ለተሞላበት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፥ በምሁራን ኮሚቴ ከተሠሩ ዘመናዊ እትሞች መምረጥ ያሻል። ከእነዚህ ዘመናዊ እትሞች አንዳንዶቹ የግርጌ ማጣቀሻዎች ስላሉአቸው፥ በአንድ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ አንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ከተዛማጅ ጥቅሶች ጋር ማስተያየት ይቻላል። እንዲህ ዓይነቱ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ ለትጉ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ በጣም ጠቃሚ ነው።

መ. የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ የተለየው ለምንድን ነው?

የካቶሊኮችን መጽሐፍ ቅዱስ አንብበህ ከሆነ፥ ካቶሊኮች ባልሆኑ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የማይገኙ አንዳንድ ተጨማሪ መጻሕፍትና የመጻሕፍት አካላት ተጨምረው ሳትመለከት አልቀረህም። እነዚህም ተጨማሪ መጻሕፍት የአዋልድ መጻሕፍት ይባላሉ። እነዚህ መጻሕፍት የተጨመሩት ለምንድነው? አዋልድስ ምንድን ነው? ትክክለኛው መጽሐፍ ቅዱስ አዋልድ መጻሕፍት ያሉበት ነው፥ ወይስ የሌሉበት?

አዋልድ መጻሕፍት

በብሉይና አዲስ ኪዳን ዘመን መካከል በሚገኝ የጊዜ ገድብ ውስጥ ጥቂት መጻሕፍት ተጽፈዋል። ከእነዚህም መጻሕፍት አንዳንዶቹ በጊዜው ታሪክ ላይ የተመረኮዙ ሲሆኑ፥ አንዳንዶቹ ደግሞ አፈ-ታሪኮች ናቸው። እነዚህም መጻሕፍት በአንድነት አዋልድ መጻሕፍት በመባል ይታወቃል።

ቤተ ክርስቲያን ከመጀመሪያው ምዕተ-ዓመት ጀምሮ እነዚህን መጻሕፍት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጎን ትጠቀም ጀመር። ይሁንና፥ ከብሉይ ኪዳን የቀኖና መጻሕፍት ጋር እኩል የእግዚአብሔር ቃል መሆናቸውን የሚያረጋግጥ አጠቃላይ ግንዛቤ አልነበረም። በ388 ዓ. ም. ቩልጌትን የተረጎመው የካቶሊክ ምሁር ጭምር እነዚህን መጻሕፍት እንደ

እግዚአብሔር ቃል አልቆጠራቸውም ነበር። በዚህም ምክንያት የቩልጌት መጽሐፍ ቅዱስ ዛሬ በፕሮቴስታንቶች መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን 66 መጻሕፍት ብቻ አጠቃሎአል።

በፕሮቴስታንት ተሐድሶ ጊዜ፥ ሌላው የካቶሊክ ምሁር ማርቲን ሉተርም የአዋልድ መጻሕፍት የእግዚአብሔር ቃል አካላት እንዳልሆኑ ገልጾአል። ይሁንና፥ የአዋልድ መጻሕፍት በሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አማካኝነት በ1546 ዓ. ም. በተጠራው በትሪንት ጉባኤ ውሳኔ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቃለዋል። ይህም የተደረገው ከሉተርና ከፕሮቴስታንት ተሐድሶው ጋር መራራ ክርክር ከተጧጧፈ በኋላ በመሆኑ፥ በከፊል ፀረ–ሉተር አቋም ለማሳየት ነበር። በዚህም ጉባኤ የአዋልድ መጻሕፍትን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለማካተት፥ በጣም ጠባብ በሆነ የድምፅ ብልጫ ተወሰነ። ለዚህ ነው የሮም ካቶሊክ መጽሐፍ ቅዱስ ከፕሮቴስታንቱ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለየው።

ምንም እንኳ ዛሬም ቢሆን ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት የአዋልድ መጻሕፍትን የመጽሐፍ ቅዱስ አካላት አድርገው ባይቀበሉአቸውም፥ እነዚህ መጻሕፍት ታሪካዊና መንፈሳዊ ጠቀሜታ እንዳላቸው ሊታወቅ ይገባል። ባሁኑ ጊዜ በልዩ የ«RSV» እንግሊዝኛ ትርጉም ሕትመት ውስጥና በሰማንያ አሐዱ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛሉ። የ17ቱ የአዋልድ መጻሕፍት ስሞች የሚከተሉት ናቸው። ሦስተኛና አራተኛ መቃቢያን የሚጨመሩት በምሥራቃዊት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብቻ ነው። እነዚህ ሁለቱ መጻሕፍት በካቶሊኮች መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ ተለያዩ መጽሐፍት አይቆጠሩም።

ኤስድራስ ቀዳማዊ	መጽሐፈ መቃብያን ካልዕ
ኤስድራስ ካልዕ	መጽሐፈ ዮዲት መጽሐፈ ጦቢት
መጽሐፈ ጥበብ	መጽሐፈ አስቴር
መጽሐፈ መክበብ	መጽሐፈ ባሮክ
ተረፈ ኤርምያስ	መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ
የሱዛና ታሪክ	ቤልና ዘንዶው
ጸሎተ ምናሴ	መጽሐፈ መቃቢያን ሣልስ
መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ	መጽሐፈ መቃቢያን ራብዕ

ሠ. ከሁሉም ትክክለኛ የሆነው የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ እትም የትኛው ነው?

ከ1611 እስከ 1945 ዓ. ም. ድረስ እጅግ በክፍተኛ ስፋት ይነበብ የነበረው የኪንግ ጄምስ መጽሐፍ ቅዱስ ነበር። የኪንግ ጄምስን እትም ያዘጋጁ ወገኖች ለጌታ የተሰጡ መንፈሳዊ ሰዎች ነበሩ። እግዚአብሔርም ለሥራው መሰጠታቸውን አክብሮታል። የሚያሳዝነው የኪንግ ጄምስ እትም የሚጠቀምበት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ከዛሬው ዘመን የተለየ መሆን ነው። በተጨማሪም፥ የኪንግ ጄምስ እትም በዘመኑ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውቀት አንጻር በርካታ ግኝቶች ይጎድሉታል። ከዚህ የተነሣ፥ ምንም እንኳ አሁንም በብዙ ክርስቲያኖች ቢወደድም፥ ዛሬ ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥንቃቄ ለተሞላበት ጥናት ከሁሉም የተሻለ ትክክለኛ እትም ሆኖ ሊቀርብ አይችልም።

በ1952 «ሪቫይዝድ እስታንዳርድ ቬርዥን» («RSV») የተባለው መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ ተጠናቆ ታተመ። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ከቀድሞው የበለጠ ዘመናዊ ምሁራዊ ተሳትፎና ምርምር የሚገኝበት ነበር። በመሆኑም፥ «RSV» ከፍተኛ ምሁራዊ እውቀት የዋለበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ነው። ይህም ከዘመናዊ የእንግሊዝኛ ቋንቋና ከዘመናዊ የመዛግብት ግኝት አኳያ ጠቃሚ እርምጃ ነበር።

ምናልባት ከሁሉም በላይ በቀጥታ ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ የተመለሰው ትክክለኛ ትርጉም፥ በ1960 ዓ. ም. የታተመው የ«ኒው አሜሪካን እስታንዳርድ ባይብል» («NASB») ይሆናል። ይህ እትም እያንዳንዱን የግሪክ አንቀጽ በትክክለኛው የእንግሊዝኛ የጊዜ አመልካች ለመግለጽ ይጥራል። የ«NASB» ተርጓሚዎች እጅግ ዘመናዊ በሆኑት መዛግብትና የከርሰ-ምድር ግኝቶች የተጠቀሙ ግሩም ምሁራን ነበሩ።

ይበልጥ በቅርብ ጊዜ የታተመውና በእንግሊዝኛ ተናጋሪው ዓለም ሁሉ በጣም ተወዳጅነትን ያተረፈው «ኒው ኢንተርናሽናል ቬርዥን» («NIV») የተባለው እትም ነው። ይህም እትም የላቀ የምሁራዊነት ብቃት የሚታይበት ነው። ከ«NASB» እና «RSV» በላይ በቀላሉ የመነበብ ጠቀሜታ አለው። አሁንም፥ በተለይ ለዘመኑ ተነባቢነት የተተረጎመው ሌላው የቅርብ ጊዜ እትም ደግሞ፥ «ዘ ባይብል ኢን ቱዴይስ እንግሊሽ ቬርዥን» («BTEV») ወይም «ጉድ ኒውስ ባይብል» በመባል አዘወትሮ

የሚጠራው ነው። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ፥ በተለይ እንግሊዝኛ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ ቋንቋ ለሆነባቸው ሰዎች ጠቃሚ ነው።

ማጠቃለያ

መጽሐፍ ቅዱስ በ40 ወይም ከዚያ በሚልቁ ጸሐፊዎች የተጻፈና ከ1500 በሚበልጡ ዓመታት የጊዜ ገደብ ህልውናውን ያገኘ የ66 መጻሕፍት ስብስብ ነው። በመጀመሪያ ስለ ጥንት ታሪኮች እየተነገረ ከተውልድ ተውልድ የሚተላለፍ አፈ-ታሪክ ነበር። በኋላም፥ ምናልባትም ከኢዮብና ሙሴ መጻሕፍት ጀምሮ፥ እነዚህ ታሪኮች ተጻፉ። እግዚአብሔር እውነቱን ለነቢያቱ መግለጹን ሲቀጥል፥ ይበልጥ ተጨማሪ መጻሕፍት በተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ላይ ይጨመሩ ጀመር። የእግዚአብሔር ሕዝቦች በነቢያት ወይም ሐዋርያት እንደ ተጻፉ ከሚነገርላቸው በርካታ መጻሕፍት መካከል የትኞቹ በእርግጥ ከእግዚአብሔር የተሰጡ (ቀኖናዊ) መሆናቸውን ይለዩ ጀመር።

ብሉይ ኪዳን የተጻፈው የዕብራውያን ቋንቋ በሆነው በዕብራይስጥ ነበር። አዲስ ኪዳን የተጻፈው በሮም የአገዛዝ ዘመን የፍልስጥኤም ቋንቋዎች በነበሩት በግሪክና አረማይክ ነበር። በ388 ዓ. ም. 66ቱ ቀኖናዊ የብሉይና የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጀሮም በተባለ ምሁር በላቲን ቋንቋ ተተረጎሙ። ይህ ቩልጌት በመባል የሚታወቀው ትርጉም፥ ዛሬ በፕሮቴስታንት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን 66 መጻሕፍት ያካተተ ነበር። የሮም ካቶሊክ መጽሐፍ ቅዱስ 15 ተጨማሪ መጻሕፍት ይዞአል፤ እነዚህም 15 መጻሕፍት በ1546 ዓ. ም. በሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ውሳኔ የተጨመሩ ናቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተተረጎመው በ1384 ዓ. ም. በጆን ዊክሊፍ ነበር። ይሁንና፥ በ1456 ዓ. ም. በጆርመን የግተሚያ መሣሪያ እስኪፈለሰፍ ድረስ፥ መጽሐፍ ቅዱሱ በሰፊው አልተሰራጨም ነበር። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ፥ እጅግ በከፍተኛ ስፋት ግልጋሎት ያበረከት የነበረው በ1611 ዓ. ም. የታተመው የኪንግ ጄምስ መጽሐፍ ቅዱስ ነበር። ዘመናዊ የክርስ-ምድር ግኝቶች ባለፉት 50 ዓመታት በብዛት በመገኘታቸው ምሁራንን አያሌና በጣም ትክክለኛ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ እትሞችን ወደ እንግሊዝኛ እንዲተረጉሙ ረድተዋቸዋል። በ1947 ዓ.ም. የተገኙት የሙት ባሕር የመጽሐፍ

ጥቅልሎች፥ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ከአንዱ ትውልድ ወደ ቀጣዩ በጸሐፍት በጥንቃቄ እየተገለበጡ ሲተላለፉ እንደ ቆዩ ለምሁራኑ አረጋግጠዋል። በመሆኑም፥ ዛሬ በእጃችን ያለው መጽሐፍ ቅዱስ ከቀደምት መዛግብት ጋር እጅግ ተቀራራቢ እንደ ሆነ በርግጠኝነት ልንናገር እንችላለን።

በምዕራፍ 3 ላይ የተመሠረቱ የመወያያ ጥያቄዎችና መልመጃዎች

1. የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክን በተመለከተ፥ የማስተማርያ ዕቅድ ንድፍ አውጣ። ንድፍህ አንድ የ12 ዓመት ልጅ ወይም ትልቅ ሰው ለማስተማር የተዘጋጀ ይሁን።

2. ክፍሉን በቋንቋ ቡድኖች ከፋፍል፣ እያንዳንዱ ቡድን መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት በመጀመሪያ ወደ ቋንቋው እንደ ተተረጎመ የሚያሳይ ታሪክ ይጻፍ። ምናልባት ትክክለኛ መረጃ የሚሰጡ ሰዎችን ለማግኘት፥ ለያንዳንዱ ቡድን ጥቂት ሳምንታት ሊወስድ ይችላል።

3. አሥራ አምስት ሰዎችን ምረጥና፥ እያንዳንዳቸው የተለያዩ የአዋልድ መጻሕፍትን እንዲያነቡ አድርግ። ከዚያም፥ እያንዳንዱ አንባቢ የንባቡን ዘገባና ያነበበውን መጽሐፍ አጠቃላይ አሳብ ያቅርብ። ዘገባው ከምንባቡ የተገኘውን መንፈሳዊ ጠቀሜታ ማካተት አለበት።

4. ሁለት ሰዎች የሴፕቱዋጀንት ትርጉም እንዴት እንደ ተተረጎመና እንደዚሁም ከብሉይ ኪዳን መዛግብት ስለሚለይባቸው አንዳንድ መንገዶች ዘገባ እንዲደቀርቡ አድርግ።

5. ከሦስት እስከ አሥር የሚደርሱና ተመሳሳይ ቋንቋ የሚናገሩ አባላት ያሉበትን ቡድን አቋቁም። እያንዳንዱ ቡድን ከመጽሐፍ ቅዱስ የተውጣጡ አያሌ አዝማሾችን በቋንቋቸው እንዲዘምሩ አድርግ። ከመዘመራቸው ቀደም ብለው ግን የመዝሙሩን የአግርኛ ትርጉምና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኝበትን ክፍል በጥቁር ሰሌዳው ላይ ያስፍሩ። በቋንቋቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ተወስደው የተዘመሩ መዝሙሮች ባይኖሩ፥ ቡድኑ አንድ መዝሙር ያዘጋጅ።

6. ከሁለት እስከ ስድስት የሚደርሱ አባላት የሚገኙበትን የትርጉም ቡድኖች መሥርት። እያንዳንዱም ቡድን በክፍሉ ውስጥ የተለያዩ የቋንቋ

ቡድኖችን ይወክል። እያንዳንዱ ቡድን ከአባላቱ ጋር በመተባበር መዝሙር (23)ን እና (34)ን ከአማርኛ ወደ ራሱ ቋንቋ ይመልስ።

7. ዛሬ በዓለም ምን ያህል የትርጉም ሥራዎች እንደ ተከናወኑና ምን ያህል እንደ ቀሩ በመገምገም ጭምር፥ የወቅቱን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም እድገት በዘገባ መልክ አቅርብ። በአገርህ አሁንም ገና መጽሐፍ ቅዱስ ያልተተረጎመባቸውን ቋንቋዎች ዘርዝር። ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት በሚከተለው አድራሻ ጽፈህ ልትጠይቅ ትችላለህ፦

Wycliffe Bible Translators, 736 Mercury Avenue, Duncanville, Texas 75137 U. S. A.

8. ዛሬ ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስን ዋጋ ለማሳጣት የሚሞክሩባቸውን መንገዶች በተመለከተ፥ የቡድን ውይይት አድርጉ።

SUGGESTED FOR FURTHER READING

Bruce, F. F. The History Of The Bible In English. Cambridge: Lutterworth, 1986.

Duthie, A. How To Choose Your Bible Wisely. Carlisle: Paternoster Press, 1995.

Renwich, A. M. and Harman, A.M. The Story of the Church. Leicester: Inter Varsity Press, 2nd edn, 1985.

Schaaf, Ype. On Their Way Rejoicing. Carlisle: Paternoster Press, 1995.

ምዕራፍ 4

ልንረዳው የማንችለው አምላክ

ሐሰን፡– «ባለፈው ዓመት ቢትሮስ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ሦስት አካላት እንዳሉት እንደሚያምኑ ነግሮኝ ነበር። እንዴት እንዲህ ያለ ነገር ያምናሉ? አምላክ ካለ፥ መሆን የሚችለው አንድ አካል ብቻ ነው።»

ግጋጂ፡– «ይህ ልክ እኔ ስነግርህ የነበርሁት ነው። እነዚህ ክርስቲያኖች ግራ ተጋብተዋል። በሦስት አማልክት ያምናሉ። አንድ አብ ከሚሉትና እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ ከሚሉት በተጨማሪ ኢየሱስ ክርስቶስም አምላክ እንደ ሆነ ይናገራሉ። ይሁንና በራሳቸው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር የሚጸልይበትን ክፍል አግኝቻለሁ። እኔው ራሴ በማቴዎስ 27፡46፥ ‹አምላኬ፥ አምላኬ፥ ስለ ምን ተውኸኝ?› የሚል ቃል አይቻለሁ። እርሱ ለእግዚአብሔር የሚጸልይ ከሆነ፥ እንዴት እግዚአብሔር ሊሆን ይችላል?»

ሐሰን፡– «አንድ ሙስሊም መምህር ኢየሱስ ነቢይ እንደ ነበር ነግሮኛል። እንዲሁም በዮሐንስ 20፡17 ክርስቶስ፥ ‹እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ዐርጋለሁ› ያለበትን ክፍል አሳይቶኛል። እርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚያርግ ከሆነ፥ እንዴት እግዚአብሔር ሊሆን ይችላል?»

ግጋጂ፡– «ትክክል የተናገርህ ይመስለኛል፥ ሐሰን። ይሁንና፥ አሁንም እነዚህ በክርስቶስ የተደረጉትን ተአምራት የሚገልጹ ታሪኮች ግራ ያጋቡኛል። አንድ ሰው ነቢይ ብቻ ከሆነ፥ እንዴት አድርጎ ዓይነ–ስውራን ሊያበራ፥ ወይም ማዕበሉን ጸጥ ሊያደርግ፥ ወይም በውኃ ላይ ሊራመድ፥ ወይም ሙታንን ሊያስነሣ ይችላል? በመሆኑም፥ ስለዚህ ኢየሱስ ስለ ተባለው ሰው አንድ የተለየ ነገር መኖር አለበት። ከሙታን የመነሣቱስ ጉዳይ? ስለዚህ ነገር ምን እንደማስብ እንጃ።»

ስለ እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጹትን እንግዳ እውነቶች ለመረዳት ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ሐሰንና ግጋጂ የመጀመሪያ ሰዎች አይደሉም። እነዚህ እውነቶች መጀመሪያ በእግዚአብሔር ነቢያትና ሐዋርያት ከተጻፉበት ጊዜ አንሥቶ፥ ሰዎች በእነዚህ ጉዳዮች ግራ ሲጋቡ ኖረዋል። ምናልባትም ሰዎች እግዚአብሔርን በመረዳቱ በኩል እርሱ ራሱን ለእነርሱ መጀመሪያ ከገለጸበት ወቅት የላቀ ዕድገት አላሳዩም

ይሆናል። እርሱ እግዚአብሔር ነውና ልንረዳው አንችልም። በዚህ ምዕራፍ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ እንሻለን፦

ሀ. ከአፍሪካ ባህላዊ ሃይማኖቶችና ከተፈጥሮ ስለ እግዚአብሔር ምን ልንማር እንችላለን?

ለ. በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር የተሰጠን ተጨማሪ መገለጥ ምንድን ነው?

ሐ. እንዴት አንድ አምላክ ሦስት አካላት ሊሆን ይችላል?

መ. እግዚአብሔር ሰው በሆነ ጊዜ ምን ተከሰተ?

ሠ. እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ ሊገኝ የሚችለው እንዴት ነው?

ሀ. ከአፍሪካ ባህላዊ ሃይማኖቶችና ከተፈጥሮ ስለ እግዚአብሔር ምን ልንማር እንችላለን?

አፍሪካውያን ከሁሉም ፍጥረታት የላቀ ላዕላይ ህላዌ እንዳለ በመገንዘቡ ረገድ የበለጸገ ልምድ ያላቸው ናቸው። አንድ ሰው እንደ ተቸው፥ ምናልባትም የእግዚአብሔርን ህልውና የማያውቅ በአፍሪካ የተወለደ አፍሪካዊ ላይገኝ ይችላል። በአንዳንድ አገሮች የሞኒት መኪናዎችና ታክሲዎች ከፊት ለፊታቸው የእግዚአብሔርን ስም መጥቀስ ብቻ ሳይሆን፥ ስለ እግዚአብሔር አንዳንድ መሠረታዊ እውነት የሚያንጸባርቅ ሐረግ ወይም ዓረፍተ ነገር አንጠልጥለው ይዞራሉ። በአንዳንድ ባህሎች የሰዎች ስሞች የእግዚአብሔርን ስም ወይም ወደ እግዚአብሔር የሚያመለክት ቃል ይጨምራሉ። በመሆኑም፥ በዓለም ሁሉ እግዚአብሔር የታወቀበትና ተቀባይነት ያገኘበት ክፍለ-አህጉር ቢኖር አፍሪካ ነው።

እግዚአብሔር በአፍሪካ በጣም መታወቁ ሊያስደንቀን አይገባም። በዘመናዊቷ አፍሪካ እንኳ የሚበዛው ሕዝብ የሚተዳደረው አሁንም ገና በግብርና ነው። ብዙዎቹ ገበሬዎች ደግሞ ለሰብላቸው ማደግ ዝናብ ሊሰጥ በሚችለው እግዚአብሔር ላይ በቀጥታ የሚደገፉ ናቸው። አንዳንድ ሰዎች ዝናብ «የእግዚአብሔር ምራቅ» እንደ ሆነ ይናገራሉ። እንደ «ዳሰነች» ባሉ አንዳንድ ባህሎች፥ ይኸው ተምሳሌት የእግዚአብሔርን በረከት ለመግለጽ ያገለግላል፤ ይህም የሚሆነው በሚባረኩት ሰዎች ላይ በአፍ የቋጠሩትን ውኃ በመርጨት ነው። ጥያቄው እንግዲህ፥ ስለ እግዚአብሔር ያለው ባህላዊ አፍሪካዊ አሳብ ምን ያህል ትክክል ነው? የሚል ይሆናል።

እግዚአብሔር የሕይወት ፈጣሪና ደጋፊ እንደ ሆነ ይታመንበታል። ከፍጥረቱ ሁሉ፥ ከሌሎች አማልክት ሁሉ፥ ከመናፍስት ሁሉና ከሰዎች ሁሉ በላይ ከፍ ተደርጎ ይከበራል። እግዚአብሔር ከአያሌ ሰዎች ዕለታዊ ሕይወት የተለየና የተገለለ ከሚመስልባቸው ምክንያቶች እንዱ ከፍተኛ ክብር ስለሚሰጠው ነው። በመሆኑም፥ በአማላጆች አማካኝነት መቅረብ አለብን ብለው ያስባሉ። የትኛው ተራ ሰው ነው በተገቢ አማላጆች በኩል ዳር ዳር ሳይል፥ በቀጥታ ወደ አንድ ታላቅ ንጉሥ ፊት ለመቅረብ የሚያስብ? አንድ ሰው በገዛ መንደሩ እንኳ ከአለቃው ፈቃድ ሳይሰጥና በተገቢ አማላጆች በኩል ሳያልፍ፥ ንጉሡ ወይም አለቃው ወዳለበት ክፍል ዘው ብሎ አይገባም። እንግዲህ፥ አንድ ሰው በከፍተኛ ባህላዊ እምነት ተጽእኖ ሥር እስከ ኖረ ወደ ሰማዩ ንጉሥ ሊቀርብ የሚችልበት ሁኔታ ምንኛ የጠበበ ነው?

እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ("Omnipotent") ሆኖ ይቆጠራል። በግኩዩዎች አባባል፥ «ተራሮችን የሚያንቀጠቅጠውና ወንዞችን የሚያፈልቀው እርሱ ነው።» እርሱ ሁሉን አዋቂ ("Omniscient") ነው፤ በዩሩባዎች አባባል፥ «የሰዎችን ውጫዊና ውስጣዊ ክፍል የሚመለከት እርሱ ነው።» እርሱ የመጨረሻው ፈራጅና በሁሉም ስፍራ የሚገኝ ("Omnipresent") ነው። በአፍሪካ ስለ እግዚአብሔር ያለው ባህላዊ አመለካከት፥ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው ሁሉን ከሚችል አምላክ መገለጥ ጋር በጣም የተቀራረበ መሆኑ የታወቀ ነው። እንዲሁም ደግሞ ስለ እግዚአብሔር የሚነገሩ ብዙ ባህላዊ አመለካከቶች ሰውን ወክለው ከፍ ወዳለው አምላክ ሊያቀርቡ የሚችሉትን የአማላጆችን ደጀ ጠኝነት የሚጠይቁ መሆናቸው ግለጽ ነው። ምንም እንኳ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ መገለጥ ጋር ቢቃረንም፥ በአማልክትና በቅድመ-ትውልድ መናፍስት የአማላጅነት ሥራ ማመኑ፥ አፍሪካውያን ስለ እግዚአብሔርና ከፍጥረቱ ጋር ስላለው ግንኙነት በሚይዙት ጽንሰ-አሳብ ውስጥ ትልቅ ስፍራ አለው።

አንዳንዴ፥ ቀውጢ ቀን ሲደርስና በተለይም የመናፍስት አማላጆች ሁኔታውን ለመለወጥ ኃይል የሌላቸው በሚመስልበት ጊዜ፥ ተራ ሰዎች ጸሎቶችን ለእግዚአብሔር በቀጥታ ያቀርባሉ። ስለ ሆነም፥ እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ ቅርብ፥ በሌላ ጊዜ ደግሞ ከዕለታዊ ሕይወት ሩቅ ተደርጎ የሚቆጠርበት ሁኔታ እንዳለ እንመለከታለን። ይሁንና፥ ለተራው ዕለታዊ ሕይወት እግዚአብሔርን በአናሳ የሰዎች ጥያቄዎች ማስቸገር እንደማይገባ ይታመናል። በባህላዊ አመለካከት መሠረት፥ ሽማግሌዎችና የቀደምት ትውልድ መናፍስት የዕለት ተዕለቱን የሕይወት ጉዳዮች ይቆጣጠራሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን በተመለከተ ለሚቀርቡ ለእነዚህ አሳቦችና ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ስላለው ግንኙነት ምን ይላል? መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የህልውናውንና የተግባሩን ግልጽ መረጃ በዓለም ውስጥ እንዳኖረ ይነግረናል። ሮሜ 1:19–20፥ «እግዚአብሔር ስለ ገለጠላቸው፥ ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና። የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀመሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና፤ ስለዚህም እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙት አጡ» ይላል። ስለ ሆነም፥ በአፍሪካ ሁሉ እግዚአብሔር በከፍተኛ ደረጃ መታወቁ አያስገርምም።

የሚያሳዝነው፥ ሰዎች እግዚአብሔርን በመረዳቱና ከእርሱ ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ወደ ጥፋት የሚነጉዱት ልክ በዚህ ነጥብ ላይ መሆኑ ነው። የሮሜ መልእክት 1:21 ማብራሪያውን በመቀጠል፥ «ነገር ግን በአሳባቸው ከንቱ ሆኑ የማያስተውለውም ልባቸው ጨለመ» ይላል። እግዚአብሔር የባህላዊ ሃይማኖትን ዘይቤዎች የማይወደው በአማልክትና በቅድመ-ትውልድ መናፍስት («በሌሎች አማልክት») ላይ በመደገፋቸው ነው። ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ለሙሴ በተሰጠው የመጀመሪያ ትእዛዝ እግዚአብሔር፥ «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ» ብሎአል (ዘጸ. 20:3)። በመቀጠልም፥ «አትስገድላቸው፥ አታምልካቸውም፤ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና» ብሎአል (ቁ. 5)።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፥ እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር ግላዊና ቀጥተኛ ግንኙነት ለማድረግ እንደሚፈልግ ግልጽ ነው። አምላክና ጌታ እርሱና እርሱ ብቻ ነው። ሰዎች ማናቸውንም ሌሎች አማልክት ወይም መናፍስት እንዲያከብሩ፥ እንዲፈሩ፥ እንዲያመልኩ፥ እንዲገዙላቸውና እርዳታ እንዲጠይቁአቸው አይፈልግም። እግዚአብሔር በእርሱና በሰው ልጆች መካከል ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር በአማላጅነት የሚቀበለው ማንም የለም (1 ጢሞ. 2:5)።

እንደ እውነቱ ከሆነ፥ በዓይናችን የምንመለከተው ፍጥረት የእግዚአብሔርን ህልውና የሚገልጽ ሲሆን፥ የአፍሪካ ባህላዊ ሃይማኖቶችም ይህንኑ ያጠናክራሉ። ይህም ሆኖ፥ ልናይ ወይም ልንሰማ ወይም ልንዳስስ በምንችለው ሐቅ ላይ በመመሥረት፥ እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል እምብዛም ልናውቅ አንችልም። እርግጥ ዙሪያችንን

ከከበበው ዓለም ታሳቅ ኃይሉንና ጥበቡን የሚያመለክት መረጃ ልንመለከት ስለምንችል፥ እርሱ እንዳለ እናውቃለን። በተጨማሪም፥ ለፈጠራቸው ነገሮች የሚያደርገውን እንክብካቤ የሚያመለክት መረጃ ስለምናይ፥ ስለ ባሕርዩም የተወሰነ ግንዛቤ ይኖረናል። ይህም በጫካ ውስጥ የአንድን እንስሳ ዱካ እንደ ማየት ነው። እንስሳውን ላንመለከት ብንችልም፥ ከዱካው በመነሣት በዚያ በኩል እንዳለፈ ልንናገር እንችላለን። እንዲሁም፥ ከዱካው መጠንና ቅርጽ በመነሣት፥ ስለ እንስሳው መጠን የተወሰነ አሳብ ልናገኝ እንችላለን።

በሕይወት ዙሪያ ለሚፈጸም ተአምር ኃላፊው እግዚአብሔር ካልሆነ ከቶ ማን ሊሆን ይችላል? ሰዎች በሙቶ ለሚቆጠሩ ዓመታት ሕይወት ያላቸውን ነገሮች ሲያጠኑ ቆይተዋል፤ ይሁንና፥ ሕይወት ያለውን ነገር በመሥራት አሁንም እግዚአብሔር ያደረገውን ነገር ለመቅዳት አልቻሉም። እግዚአብሔር ካልሆነ፥ የተፈጥሮን ሚዛንና ጥምረት ያበጀ ማን ሊሆን ይችላል? እግዚአብሔር ካልሆነ፥ ዝናብን የሚሰጥና የሚነሣ ማን ነው? ለአያሌ ዓመታት ሰዎች ዝናብ ለመፍጠር ሲፍጨረጨሩ ኖረዋል፤ ይሁንና፥ ዛሬም ከመጀመሪያው ሙከራቸው የተሻለ ውጤት ሊያሳዩ አልቻሉም።

ይህ የማይታይ አምላክ ማን ነው? ምን ይመስላል? ተፈጥሮን በመመልከት እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ውስን አሳብ ልናገኝ እንችላለን። በዙሪያችን ካለው ዓለም በጣም ትልቅ ኃይልና እውቀት እንዳለው እናያለን። እንደ ዝናብ፥ እህልና ምግብ፥ እንዲሁም ለያንዳንዱ ዓይነት እንስሳት ተቃራኒ ፆታ በመስጠት ለፍጥረቱ ከሚያሳየው እንክብካቤ፥ እግዚአብሔር ፈቃድና ስሜት እንዳለውና ለፈጠራቸው ፍጥረታት እንደሚገደው ልንመለከት እንችላለን። በዓለም ውስጥ ልንመለከት የምንችለው ነገር የእግዚአብሔር ተፈጥሮአዊ መገለጥ ("Natural Revelation") በመባል ይታወቃል። ይህ ተፈጥሮአዊ መገለጥ በምድር ላይ ለሚኖሩ ሰዎች ሁሉ የተሰጠ ነው።

ለ. በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር የተሰጠን ተጨማሪ መገለጥ ምንድን ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ተፈጥሮአዊ ባሕርይ ከተፈጥሮ ልንረዳ በማንችልበት መንገድ ይገልጻል። እግዚአብሔር ማንነቱንና ምንነቱን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ገልጾልናል። የዚህ መገለጥ እጅግ አስደናቂው ክፍል እግዚአብሔር ራሱን ለሰው ልጅ የናዝሬቱ ኢየሱስ በተባለው ሰው አማካኝነት መግለጹ ነው። በመሆኑም፥ ኢየሱስ ክርስቶስን በማጥናት

አያሌ የእግዚአብሔርን ባሕርያት ልንረዳ እንችላለን። በክርስቶስ የተገለጹትን የእግዚአብሔርን ባሕርያት በምዕራፍ 5 እናጠናለን።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር የሚገልጸው ተጨማሪ ነገር ምንድን ነው? መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር የሚገልጻቸው አንዳንድ ነገሮች ከአእምሮአችን ግንዛቤ በላይ የላቁ ናቸው። ከዚህም የተነሣ፥ ብዙ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የገለጸውን እውነት ያገላሉ። ይሁንና፥ ለማብራራት የሚከብደን ስለ እግዚአብሔር የተገለጸው እውነት ብቻ አይደለም። ለምሳሌ፥ ሰዎች በቀላሉ የኤሌክትሪክ ኃይል ሊያመነጩና ለብዙ ዓላማዎች ሊገለገሉበት ይችላሉ። ይሁንና፥ በሳይንስ የመግሪያ መጻሕፍት ውስጥ የኤሌክትሪክን ኃይል ለማብራራት ሲሞክሩ፥ የኤሌክትሪክን ኃይል መግለጽ ከባድ ርዕሰ-ጉዳይ በመሆኑ፥ በአስቸጋሪ ቃላት ይጠቀማሉ።

ከረዥም ጊዜያት በፊት፥ ሰዎች በምሽት በጠራ ሰማይ ላይ በሌጣ ዓይናቸው የተመለኑ ከዋክብትን ብቻ ይቆጥሩ ነበር። በኋላ ቴሌስኮፕ (የሩቁን አቅርቦ የሚያሳይ መሣሪያ) በመፈልሰፉ፥ ሰዎች ሊቆጥሩ ወይም ሊገምቱ ከሚችሉዋቸው የበለጡ ከዋክብት በሰማይ ላይ እንዳሉ ለመረዳት ችለዋል። የእግዚአብሔርም ነገር እንዲሁ ነው። ጠቅላላው የእግዚአብሔር እውነት የሰው አእምሮ ከሚያስበው የላቀ ነው።

ሐ. እንዴት አንድ አምላክ ሦስት አካላት ሊሆን ይችላል?

መጽሐፍ ቅዱስ በዓለም ውስጥ ማንም ሰው የማያስበውን እውነት ስለ እግዚአብሔር ይገልጻል። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ (ዘዳግ. 6፡4) እና ከእርሱም በቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ ይገልጻል (ኢሳ. 45፡5)። እንዲሁም ደግሞ ይኸው መጽሐፍ ቅዱስ፥ እግዚአብሔር አንድ እንዳልሆነና ዳሩ ግን ሦስት የተለያዩ አካላት – እግዚአብሔር አብ፥ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እንደ ሆነ ይገልጻል። ለምሳሌ፥ በኢሳይያስ 9፡6 መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ሕፃን ተወልዶልናልና . . . ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል» ይላል። በዚህ ምንባብ፥ መካር (በዮሐንስ 14፡26 ለመንፈስ ቅዱስ ከተሰጠው «አጽናኝ» የሚል ስም ጋር አንድ ዓይነት ነው)፥ አምላክ፥ አባትና የሰላም አለቃ የሚሉ ቃላት ሁሉ የሚመለደውን ሕፃን ለመግለጽ አገልግለዋል። የሚመለደው ልጅ አዳኙ ኢየሱስ ነበር

(ማቴ. 1፡21)። በተጨማሪም፥ «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር» የሚል ፍች ያለው አማኑኤልም ለኢየሱስ የተሰጠ ስም ነው (ማቴ. 1፡23)።

ስለ ሥላሴ በተጠቀሰው ሌላ ክፍል፥ ኢየሱስ ሰዎች በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ (ስሞች ሳይሆን) ስም እንዲጠመቁ አዞአል (ማቴ. 28፡19)። በዚህ ስፍራ አንድ ስምና ሦስት አካላት ተጠቅሰዋል። 1ኛ ቆሮንቶስ 8፡4፥ «ከአንዱም በቀር ማንም አምላክ እንደሌለ እናውቃለን» ይላል። ያዕቆብ 2፡19ም አጋንንት እንኳ አንድ አምላክ እንዳለ እንደሚያውቁ ይናገራል። እግዚአብሔር አንድ ህላዌና ሦስት አካላት እንዴት ሊኖረው ይችላል?

የሥላሴን እውነታ ለመቀበል ትልቅ ችግር አለብን። በእኛ አመለካከት፥ አንድ ህላዌ ብቻ ካለ፥ ሊኖር የሚችለው አንድ አካል ብቻ ነው። ይህም የሆነው እኛ ሰብአዊ ሰዎች ስለ ሆንንና የተፈጠርነውም በዚሁ መንገድ ስለ ሆነ ነው። እያንዳንዳችን አንድ ህላዌና አንድ አካል ነን። እግዚአብሔር ግን እንዲህ አይደለም። እርሱ አንድ ህላዌ ሲኖረው፥ ሦስት አካላት እንዳሉት መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል። ይሁንና፥ አንዲት ዝንብ የሰውን ያህል ልትረዳ እንደማትችል፥ ሰብአዊ አእምሮም እግዚአብሔርን ሙሉ ለሙሉ ሊረዳው አይችልም።

ሦስቱ የእግዚአብሔር አካላት እርስ በርሳቸው የሚነጋገሩ ሲሆን፥ እርስ በርሳቸውም የተዛመዱ ናቸው። ይህም በዘፍጥረት 1፡26፣ 3፡22 እና በሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሊታይ ይችላል። ኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜ ሦስቱም የእግዚአብሔር አካላት የተገኙ ሲሆን፥ እርስ በርሳቸው ተዛምደው እናያለን። አብ ድምፁን በማሰማት፥ «የምወድህ ልጄ አንተ ነህ፥ በአንተ ደስ ይለኛል» አለ። በዚሁ ቅጽበት መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል በክርስቶስ ላይ ወረደ (ማር. 1፡9–11)።

መጽሐፍ ቅዱስ አብ እግዚአብሔር እንደ ሆነ ያስተምራል (ሮሜ. 1፡7)። *መጽሐፍ ቅዱስ* ወልድ እግዚአብሔር እንደ ሆነ ያስተምራል (ዕብ. 1፡8)። *መጽሐፍ ቅዱስ* መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር እንደ ሆነ ያስተምራል (የሐዋ. 5፡3–4)። ይሁንና፥ *መጽሐፍ ቅዱስ* አንድ አምላክ ብቻ እንዳለና እርሱንም የሚመስል እንደሌለ በግልጽ ያስተምጣል (ዘዳ. 4፡35)። በኢሳይያስ 44፡6–7 እግዚአብሔር፥ «እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ፥ ከእኔ ሌላም አምላክ የለም» ይላል። ይህ የእግዚአብሔርን ተፈጥሮ የሚያመለክተው መገለጥ በጣም ከባድ በመሆኑ፥ ክርስቲያናችን ጨምሮ

ሰዎች ሁሉ ከዚህ አሳብ ጋር ይታገላሉ። እርሱ እግዚአብሔር ነውና፥ ልንረዳው አንችልም።

እያንዳንዱ የእግዚአብሔር አካል የተለያየ ሥራ አለው። እግዚአብሔር አብ አጽናፈ-ዓለሙን ይገዛል። ስለ ሁሉም ነገሮች የመጨረሻ ውሳኔዎችን ይሰጣል (የሐዋ. 1፡7፤ 17፡24–26)። በአፍሪካ የሞነት መኪና ላይ የተንጠለጠለው ጥቅስ በትክክል፥ «እግዚአብሔር ይሁን ካለ የሚቃወም ማን ነው?» ይላል። እግዚአብሔር ወልድ አጽናፈ-ዓለሙ የተፈጠረበት ወኪል ሲሆን፥ በቃሉ ነገሮችን ሁሉ አጣምሮ ይዞአል (ዕብ. 1፡2–3)። እርሱ የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉ የበላይ አለቃ ነው (ራእይ 19፡11–14)። ራሱን በማዋረድ ወደ ምድር መርዶ፥ የሰውን ደኅንነት በመስቀል ላይ የፈጸመው እርሱ ነው (ቆላ. 1፡19–20)። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ዛሬ በዓለም (ዮሐ. 16፡7–14)፥ በተለይም በቤተ ክርስቲያን ተግቶ የሚሠራው የሥላሴ አካል ነው (1 ቆሮ. 12፡1–13)።

ብዙውን ጊዜ ሙስሊሞች ክርስቲያኖች በሦስት አማልክት እንደሚያምኑ ይናገራሉ። የይሖዋ ምስክሮች ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔር የተፈጠሩ ከሁሉም የላቀ መልአክ እንደ ሆነ ይናገራሉ። «ዩኒቴሪያንስ» ("Unitarians") ክርስቶስ ታላቅ ሰው እንጂ የመለኮት ባሕርይ እንዳልነበረው ይናገራሉ። ችግሩ የመነጨው እነዚህ ቡድኖች እያንዳንዳቸው እግዚአብሔርን ከሰብአዊ ዕይታ አንጻር ለመረዳት ከመሞከራቸው ነው። እውነቱ ሲታይ ደግሞ እግዚአብሔር ለማንኛውም ሰብአዊ አእምሮ ግንዛቤ እጅግ የላቀ ነው። ስለ እግዚአብሔር ሊኖረን የሚችለው ብቸኛ ትክክለኛ እውቀት የሚገኘው እርሱ ስለ ራሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከገለጸው ነው።

በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔርን አንድነት ለመግለጽ የተጠቀመበትን የዕብራይስጥ ቃል በጥንቃቄ ማጥናቱ መረዳታችንን ያሳድገዋል። ይህ ቃል «ኢቻድ» የሚል ሲሆን፥ በዘዳግም 6፡4 ተጠቅሶ ይገኛል፦ «እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ (ኢቻድ) እግዚአብሔር ነው።» ይህ ቃል እግዚአብሔር ለጋብቻ ያቀደውን ዓይነት ጥምረታዊ አንድነት ይገልጻል («ሁለቱ አንድ ይሆናሉ» ዘፍጥረት 2፡24)። የባቢሎን ግንብ ይሠሩ የነበሩትን ሰዎች «አንድ» መሆን ለመግለጽም አገልግሏል (ዘፍጥ. 11፡6)። በዕብራይስጥ ቋንቋ ፍጹማዊ አንድነትን ለመግለጽ

የሚያገለግል ሌላ «ያቺድ» የሚባል ቃል አለ። ይህ ቃል ግን እግዚአብሔርን ለመግለጽ አላገለገለም።

አንዳንድ ጊዜ የሥላሴን እውነታ እንረዳ ዘንድ ማነጻጸሪያዎች ይቀርቡልናል። አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔርን እንደ ውኃ አድርጎ መመልከት እንደሚቻል ያስባሉ። ውኃ አንድ ንጥረ-ነገር ቢሆንም፥ በተመሳሳይ ጊዜ እንደ ተን፥ ፈሳሽና በረዶ መልክ ሊገኝ ይችላል። ከእነዚህ ሦስት ቅርጾች የምንረዳው፥ ሦስቱም ተመሳሳይ ንጥረ-ነገር ሲኖራቸው፥ ዳሩ ግን የተለያዩ ባሕርያት አሏቸው። ይህ ማነጻጸርያ በሕይወት ውስጥ ተራ የሆነው ነገር እንኳ፥ በተመሳሳይ ጊዜ አንድና ሦስት ሊሆን እንደሚችል በግሳየቱ ረገድ ብቻ ይጠቅመናል።

ማነጻጸሪያዎችን ስንጠቀም መጠንቀቅ አለብን። እግዚአብሔር ውኃን ወይም ሰብአዊ አእምሮአችን ሊያስብ የሚችለውን ማንኛውንም ሌላ ነገር አይመስልም። እንደ እውነቱ ከሆነ፥ ሰብአዊ ማነጻጸሪያዎች ሁሉ ሥላሴ የሆነውን የእግዚአብሔርን ተፈጥሮ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተገለጸበት መልኩ ለማሳየት አይችሉም። በመሆኑም፥ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር የሚገልጽልንን ሁሉ በእምነት መቀበል አለብን። በሦስት አካላት የተገለጸ አንድ አምላክ ብቻ አለ። እርሱንም የሚመስል ማንም የለም (ኢሳ. 44:6–7)።

እንግዲህ፥ ክርስቶስ ወደ አባቱና ወደ አምላኩ እንደሚያርግ የተናገረው ለምንድን ነው (ዮሐ. 20:17)? አምላኩ አድርጎ ወደ እግዚአብሔር የጸለየውስ ለምንድን ነው (ዮሐ. 17:1፤ ማቴ. 27:46)? ኢየሱስ ራሱ አምላክ ከሆነ (ዮሐ. 1:1)፥ አብ ከእርሱ እንደሚበልጥ ለምን ተናገረ (ዮሐ. 14:28)? እንዲህ ዓይነቶቹ ጥያቄዎች ብዙውን ጊዜ በይሖዋ ምስክሮችና የተገለጸውን የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ለመቀበል በማይፈልጉ ሰዎች ተነሥተዋል። በመሆኑም፥ እነዚህን ጥያቄዎች ቀጥለን እንመልሳለን።

መ. እግዚአብሔር ሰው በሆነ ጊዜ ምን ተከሰተ?

በፊልጵስዩስ 2:5–8 ላይ ፥ እነዚህን አስቸጋሪ ጥያቄዎች ለመረዳት የሚያግዝ ቁልፍ ተሰጥቶናል። ቁልፉም «ኢኮኖሰን» የሚል የግሪክ ቃል ሲሆን፥ «ራሱን ባዶ አደረገ» ተብሎ ተተርጉሞአል። ፊልጵስዩስ 2:5–8 እንዲህ ይላል፦ «በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን፥ እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር

ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም፥ ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ (ኢከኖሰን)፥ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፥ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ።»

ሥጋና ደም ያለው ሰው ሆኖ በመቀየሩ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር አብ ጋር የነበረውን እኩልነት ወደ ጎን ተወው (ፊልጵ. 2፡6)። ሙሉ ለሙሉ ራሱን ከሰው ዘር ጋር ለማስተባበር፥ ከመለኮታዊ ክብሩ ራሱን ባዶ አደረገ። ይህም ሲባል (በተሠገዎ ወቅት) የእግዚአብሔር ባሕርያት አልነበሩትም ማለት ሳይሆን፥ የእግዚአብሔር ባሕርያት ብዙውን ጊዜ በስብእናው ይዋጡ ነበር ማለት ነው። በምድራዊ ሕይወቱ አብ እንዲጠቀምባቸው ሲፈልግ ካልሆነ በቀር፥ ሆን ብሎ በእነዚህ መለኮታዊ ባሕርያቱ ላለመገልገል መረጠ። ክብሩንና ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን እኩልነት የምንለብሰውን ልብስ አውልቆን ከምናስቀምጥበት ሁኔታ ጋር በሚመሳሰል መልኩ ወደ ጎን ተዋቸው። ያም ልብሱ አሁንም የእኛው ቢሆንም፥ በምርጫችን አውልቀን እንደምናስቀምጠው ማለት ነው።

በምድር ላይ ባሳለፈባቸው ሠላሳ ሦስት ዓመታት ከእግዚአብሔር አብ ጋር የነበረውን እኩልነት ከመተው በተጨማሪ፥ ኢየሱስ በሰብአዊ አካል ሥጋና ደም ውስጥ ከማደር የሚመጡትንም ውስንነቶች ተቀብሏል (ዕብ. 2፡14)። ይህም ተሠገዎ ("Incarnation") የምንለው ነው። እኛ በሰውነታችን እንደምንታሰር ሁሉ፥ እርሱም በሥጋና ደም ሁኔታዎች ታሰረ። እንደኛው ሁሉ ሰውነቱ ረሃብ፥ ድካምና ሥቃይ ይሰማው ነበር (ዕብ. 4፡15)። በዕድገቱ ወቅት እንደማንኛውም ልጅ ለመራመድ፥ ለማንበብና ለመጻፍ መማር ያስፈልገው ነበር (ሉቃ. 2፡52)። በምድራዊ ሕይወቱ፥ የእግዚአብሔር ክብርና ባሕርያት በኢየሱስ ሰብአዊነት ተደብቀው ነበር።

ኢየሱስ በምድራዊ ሕይወቱ ብዙውን ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል መሆኑን በተአምራቱ አሳይቶአል (ዮሐ. 10፡37–38)። ሰዎችን ከሙታን እንደ ማስነሣት ያሉ እግዚአብሔር ብቻ ሊያደርጋቸው የሚችላቸውን ነገሮች በማድረግ፥ እርሱም እግዚአብሔር እንደ ሆነ አሳይቶአል (ዮሐ. 11፡43–44)። እንዲሁም፥ መልኩ በተለወጠበት ተራራ ላይ ጴጥሮስ፥ ዮሐንስና ያዕቆብ መለኮታዊ ክብሩን ተመልክተዋል (ማቴ. 17፡2–7)። ምንም እንኳ የአጭር ጊዜ ገጠመኝ ቢሆንም፥ የኢየሱስ መልክ

የተለመጠበት ሁኔታ እጅግ አስፈሪ በመሆኑ፥ ደቀ መዛሙርቱ ይህንኑ የአምላክነቱንና የክብሩን ጨረፍታ በፍጹም አልዘነጉም (2 ጴጥ. 1፡16–18)።

በምድራዊ ሕይወቱ በሥጋና ደም ውስጥ እንዳደረ ሰው፥ ኢየሱስ ሁሉን አዋቂነቱን ("Omniscience") ያልተጠቀመበት ጊዜ ነበር። በማቴዎስ 24፡36፥ ኢየሱስ የሚመለስበትን ጊዜ ከአባት ብቻ በቀር ማንም እንደማያውቅ ተናግሮአል። በማቴዎስ 4፡3–4 ድንጋይን ወደ እንጀራነት ለመለወጥ እንዳልፈለገበት ሁኔታ፥ ሁሉን ቻይነቱን ("Omnipotence") ያለተጠቀመባቸው ጊዜያት ነበሩ። ሊቀ–ካህናችን ለመሆን (ዕብ. 2፡17–18፤ 4፡14–15) እና ደኅንነታችንን ለመፈጸም (ዕብ. 2፡9–10)፥ ራሱን ፍጹም ሰው አድርጎ ገደበው።

እኛ ግድረግ እንደሚኖርብን ሁሉ፥ ክርስቶስ ሰው በመሆን ለሚያስፈልገው ለማንኛውም ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ተደገፈ። በምድረ በዳ ረሃቡን ለማጥገብ ድንጋይ ወደ ዳቦነት አልቀየረም (ማቴ. 4፡3–4)። ይልቁንም፥ እኛ ልናደርግ እንደሚገባን ሁሉ፥ ለዕለታዊ ምግቡ በእግዚአብሔር ላይ ተደገፈ። ልክ እኛ በምድር ላይ ለሚያስፈልጉን ነገሮች በጸሎት እግዚአብሔርን እየጠየቅን በእርሱ ላይ መደገፍ እንዳለብን ሁሉ፥ እርሱም ምድራዊ ፍላጎቱን ለማሟላት በጸሎት በእግዚአብሔር ላይ ተደገፈ (ሉቃ. 6፡12)። ሊቀ–ካህናችን በመሆኑ፥ በምትካችን ለአብ እንደ አምላኩ አድርጎ ጸለየ (ዮሐ. 17፡1–26)። በዚህ ምክንያት ኢየሱስ በምድራዊ ሕይወቱ ሳለ ከእርሱ ይልቅ አብ እንደሚበልጥ መናገሩ ትክክል ነበር (ዮሐ. 14፡28)።

ኢየሱስ አምላክነቱን ትቶ ፍጹም ሰብአዊነትን ስለ ለበሰ፥ ልክ እንደ እኛው ከሕይወት ጋር ይታገል ነበር (ዕብ. 4፡15)። ከፍጹም ሰብእናው የተነሣ፥ በድካማችንና በፈተናዎቻችን ሊራራልን ይችላል። በትግሎቻችን ሊረዳን ይችላል (ዕብ. 2፡18፤ 4፡16)። ልክ እንደ እኛው ስለ ተሠቃየ፥ በእግዚአብሔር አብ ፊት እንደ ታላቅ ሊቀ ካህናችን ሊወክለን ሙሉ ብቃት አለው (ዕብ. 4፡14–16)። ሥቃያችንንና ድካማችንን በሕይወቱ ስለ ተለማመደ፥ አሁንም እንኳ በሰማይ ሆኖ በርኅራኄና በኃዘኔታ ይማልድልናል (ሮሜ 8፡34፤ ዕብ. 7፡25)።

ሠ. እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ ሊገኝ የሚችለው እንዴት ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በአጽናፈ-ዓለም ውስጥ በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ እንደሚገኝ ያስተምራል። ይህም የእግዚአብሔር ባሕርይ በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ መገኘት ("Omnipresence") በመባል ይታወቃል። የአፍሪካ ባህላዊ ሃይማኖቶችም በእግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ የመገኘት ባሕርይ ያምናሉ። የላንጊ ጎሳ፥ «እርሱ እንደ አየር ነው» ይላል። የንጎምቤ ጎሳ ስለ እግዚአብሔር ሲናገር፥ «ሁሉንም ነገር ይሞላል» ይላል። የባሩንዲ ጎሳ፥ «በሁሉም ስፍራ የሚገኝ» ይላል። ባህላዊ የአፍሪካ ሃይማኖት ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔርን በአንዳንድ መንገዶች ከሰማይ ጋር ያዛምደዋል።

ንጉሥ ሰሎሞን፥ «እነሆ፥ ሰማይ ከሰማያትም በላይ ያለ ሰማይ ይይዝህ ዘንድ አይችልም፤ ይልቁንስ እኔ የሠራሁት ቤት እንዴት ያንስ ይሆን?» ሲል አውጇል (2 ዜና 6፡18)። ንጉሥ ዳዊትም፥ «ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ፥ አንተ በዚያ ነህ፤ ወደ ሲኦልም ብወርድ፥ በዚያ አለህ» ብሎአል [መዝ. (139)፡7–8]። በኤርምያስ መጽሐፍ፥ «ሰው በስውር ቢሸሸግ፥ እኔ አላየውምን? ሰማይና ምድርንስ የሞላሁ እኔ አይደለሁምን? ይላል እግዚአብሔር» (ኤር. 23፡24)።

ከእነዚህ ጥቅሶች እግዚአብሔር በአጽናፈ-ዓለም ውስጥ በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ እንደሚገኝ እንረዳለን። እንደ እውነቱ ከሆነ፥ አሳቡ ሰብአዊ አእምሮአችን ሊረዳ ከሚችለው በላይ ነው። እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ እዚህና እዚያ ሊገኝ የሚችለው እንዴት ነው? በዓለም ሁሉ የሚገኙትን ሰዎች ጸሎቶች እየሰማና እየመለሰ ሳለ፥ ጸሎታችንን ሊሰማና ሊመልስ የሚችለው እንዴት ነው? ምክንያቱም ለመረዳት የሚያስቸግር አይደለም። ይኸውም እግዚአብሔር መንፈስ ሲሆን (ዮሐ. 4፡21–24)፥ መንፈስ ደግሞ የግድ በቦታ የተወሰነ አለመሆኑ ነው።

ችግራችን የሰውነታችንና የአእምሮአችን ውስንነት ነው። እኛ በአንድ ጊዜ ልንገኝ የምንችለው አንድ ቦታ ብቻ ነው። በአንድ ጊዜ ልንነጋገር የምንችለው ከአንድ ሰው ጋር ብቻ ነው። በመሆኑም፥ ከዚህ በተለየ መንገድ እግዚአብሔር እንዴት እንደሚሠራ ለመረዳት እንቸገራለን።

አንዳንድ ጊዜ ልጆቻችን፥ እግዚአብሔር በዓለም በአንድ ጊዜ የሚጸልዩትን ሰዎች ጸሎት እንዴት ሊሰማና ሁላቸውንም እንዴት ሊመልስ

እንደሚችል ይጠይቃሉ። ትልልቅ ሰዎች ሆነን እንኳ ይህንን ጥያቄ ለመመለስ እንቸገራለን። እውነቱ ግን እግዚአብሔር ሰው አለመሆኑ ነው። እርሱ እግዚአብሔር ሲሆን፥ እርሱን የሚመስል ማንም የለም (ኢሳ. 40፡18)። እርሱ በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ ይገኛል (ኤር. 23፡24)። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «የእግዚአብሔር ዓይኖች በስፍራ ሁሉ ናቸው፤ ክፉዎችንና ደኅችን ይመለከታሉ» ይላል (ምሳሌ 15፡3)።

እግዚአብሔር መንፈስ ስለ ሆነ እርሱን ከማንኛውም ዓይነት ምስል ወይም አምሳል ጋር እንዳናወዳድር ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል (ዘጸ. 20፡4፤ ዘዳግ. 4፡15–19)። ምስል ወይም የእግዚአብሔርን ቅርፅ መሥራቱ ጣዖትን ማምለክ ሲሆን፥ ከጣዖት አምልኮ እንድንጠበቅ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል (1 ዮሐ. 5፡21)። የኢየሱስን ምድራዊ አካል በተመለከተ ጳውሎስ፥ «እኛ ከአሁን ጀምሮ ማንንም በሥጋ እንደሚሆን አናውቅም፤ ክርስቶስንም በሥጋ እንደ ሆነ ያወቅነው ብንሆን እንኳ አሁን ግን ከእንግዲህ ወዲህ እንደዚህ አናውቀውም» ብሏል (2 ቆሮ. 5፡16)። እግዚአብሔር መንፈስ ስለ ሆነ እግዚአብሔርን በመንፈስና በእውነት ለማመለክ መማሩ አስፈላጊ ነው (ዮሐ. 4፡24)።

ማጠቃለያ

ከተፈጥሮ መገለጥ አምላክ እንዳለ እናውቃለን። ህልቆ–መሳፍርት የሌለው ኃይልና ጥበብ እንዳለውም በቀላሉ ልንመለከት እንችላለን። በልዩ መገለጥ መጽሐፍ ቅዱስ ግንም ሰው በምድር ላይ ሊገምት የማይችለውን እውነት ስለ እግዚአብሔር ይገልጻል። እርሱ አንድ ህላዌ ሲሆን፥ አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ተብለው በሚጠሩ ሦስት አካላት ይኖራል። ሦስቱም አካላት በእኩል ደረጃ እግዚአብሔር ናቸው። ሦስቱም አካላት በአንድነት አንድ የበላይ ህላዌ ናቸው። እርሱ ፈጣሪና የነገሮች ሁሉ ደጋፊ ነው። በምድራዊ ሕይወቱ ኢየሱስ በትክክል አብ ከእርሱ ይበልጥ እንደ ነበር ገልጾአል (ዮሐ. 14፡28)። ይህንንም የተናገረው ሥጋና ደም ያለው ሰው ሆኖ በመቀየሩ፥ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር አብ ጋር የነበረውን እኩልነት ወደ ጎን ስለ ተወውና እንደ ተራ ሰዎች በአብ ላይ ጥገኛ ስለ ሆነ ነው (ፊልጵ. 2፡6–7)። ደኅንነታችንን ለመፈጸም ሲል የሰብአዊ አካልን ውስንነትና ድካም ተቀበለ። መንፈስ በመሆኑ፥ እግዚአብሔር በዓለም በሁሉም ስፍራ በአንድ ጊዜ ይገኛል። ምንም እንኳ ይህንን

እውነት ልንረዳ ባንችልም፥ በምንገኝበት ስፍራ ሁሉ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር እንዳለ መረዳቱ የመጽናናት ምንጭ ይሆንልናል።

በምዕራፍ 4 ላይ የተመሠረቱ የመወያያ ጥያቄዎችና መልመጃዎች

1. አንድ አምላክ ብቻ እንዳለ አጥብቆ ለሚከራከር ሙስሊም የሥላሴን እውነት እንዴት ታብራራለህ?

2. ተማሪዎችህን ሦስት ወይም አራት አባላት በሚገኙባቸው ቡድኖች ከፈላቸው። የእግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ መገኘት ማጽናኛ ወይም ማበረታቻ የሚሆንላቸውን የሰዎች ጉድለቶችና ፍርሃቶች ዘርዝር።

3. አምስት ሰዎች በሚገኙባቸው ቡድኖች ከፈላቸው። እያንዳንዱ ቡድን በእያንዳንዱ የሥላሴ አካል፥ ማለትም በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ የሚሠሩትን የሥራ ዓይነቶች በአስተዋጽኦ መልክ ያቅርብ።

4. ሀ. አብ እግዚአብሔር እንደ ሆነ፥

ለ. ወልድ እግዚአብሔር እንደ ሆነ፥

ሐ. መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር እንደ ሆነና

መ. አንድ አምላክ ብቻ እንዳለ የሚያመለክቱትን ጥቅሶች በማውጣት፥ የሥላሴን እውነታ የሚደግፍ መከላከያ በጽሑፍ አዘጋጅ።

5. በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ፥ ማጋጂ ክርስቶስ ራሱ ወደ እግዚአብሔር እየጸለየ እንዴት እግዚአብሔር ሊሆን ይችላል ሲል ላቀረበው ጥያቄ እንዴት ትመልሳለህ?

6. እግዚአብሔርን አፍሪካውያን ሁሉ በሚያውቁበት መንገድ በማወቅና ኢየሱስ በዮሐንስ 17፡3 ላይ እንደሚለው እግዚአብሔርን በማወቅ መካከል ያለውን ልዩነት በተመለከተ በቡድን ተወያዩ።

7. ተማሪዎቹን አራት አባላት በሚገኙበት አነስተኛ ቡድን ከፈላቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ አምላክ እንደ ሆነና መንፈስ ቅዱስ አምላክ እንደ ሆነ በግልጽ የሚያስተምሩትን ጥቅሶች ወይም ምንባቦች አግኙ። እያንዳንዱ ሰው እነዚህን ማጣቀሻዎች ከሙስሊም ወይም ከይሖዋ ምስክር አማኞች ጋር በሚከራከርበት አጋጣሚ ይጠቀምባቸው ዘንድ በመጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ መጻፍ አለበት። እያንዳንዱ ቡድን በጥቅስ ማውጫና

በጥቅሶች ማስተያያ መጽሐፍ ቅዱስ ("cross-reference Bible") ሊጠቀም ይችላል።

SUGGESTED FOR FURTHER READING

McGrath, A. Understanding the Trinity. Michigan: Zondervan, 1990.

Milne, B. Know the Truth. Leicester: InverVarsity Press, reprinted 1991.

Packer, J. I. Knowing God. London: Hodder 2nd edn., 1993.

Shelly Bruce L. Christian Theology In Plain Language. Waco, Texas: Word Books, 1985.

Smail, T. The Forgotten Father. London: Hodder, 1980.

ምዕራፍ 5

ኢየሱስ ክርስቶስ – እግዚአብሔርን የገለጸው «ሰው»

«በነገውም (ኢየሱስ) ናይን ወደምትባል ወደ አንዲት ከተማ ሄደ፥ ደቀ መዛሙርቱም ብዙ ሕዝብም ከእርሱ ጋር አብረው ሄዱ። ወደ ከተማዪቱም በር በቀረበ ጊዜ፥ እነሆ፥ የሞተ ሰው ተሸከመው አወጡ፤ እርሱም ለእናቱ አንድ ልጅ ነበረ፥ እርስዋም መበለት ነበረች፥ ብዙም የከተማ ሕዝብ ከእርስዋ ጋር አብረው ነበሩ። ጌታም ባያት ጊዜ አዘነላትና፦ አታልቅሽ አላት ቀርቦም ቃሬዛውን ነካ፥ የተሸከሙትም ቆሙ፤ አለውም፦ አንተ ጎበዝ እልሃለሁ፥ ተነሣ። የሞተውም ቀና ብሎ ተቀመጠ ሊናገርም ጀመረ፥ ለእናቱም ሰጣት» (ሉቃ. 7፡11–15)።

እግዚአብሔር ምን ይመስላል? ይህ ሰዎች በታሪክ ሁሉ ያነሡት ጥያቄ ነው። ከኢየሱስ ተከታዮች አንዱ የነበረው ፊልጶስ የጠየቀውን ቀጥሎ ተመልከት። «ጌታ ሆይ፥ አብን አሳየንና ይበቃናል» (ዮሐ 14፡8)። ሁላችን እንደምንመኘው ሁሉ፥ ፊልጶስም እግዚአብሔርን ሊያይ ፈለገ። እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ለማወቅ ፈለገ። ከሞላ–ጎደል ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔርን ለማየት ይጓጓሉ። እርሱን ለማየትና በትክክል ምን እንደሚመስል ለማወቅ ይሻሉ። ኢየሱስ ለፊልጶስ ጥያቄ ሲመልስ እንዲህ አለ፦ «አንተ ፊልጶስ፥ ይህን ያህል ዘመን ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቶአል» (ዮሐ. 14፡9)። ኢየሱስ ለፊልጶስ እርሱ ራሱ (ኢየሱስ) የእግዚአብሔርን ባሕርያት እንደ ያዘ መናገሩ ነበር። የዕብራውያን መጽሐፍ ጸሐፊ፥ «እርሱም (ልጁ) የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ» እንደ ሆነ ይናገራል (ዕብ. 1፡3)። በሌላ አባባል፥ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ባሕርያት በትክክል ይገልጻል ማለት ነው።

ለሰዎች እግዚአብሔር በሚቀጥለው ማክሰኞ ከቀኑ በ8፡00 ሰዓት በአዲስ አበባ እስታዲዬም እንደሚታይ ብንናገር፥ እግዚአብሔርን ለመመልከትና የሚናገረውንም ለመስማት የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ግልብጥ ብለው መውጣታቸው የማይቀር ነው። ይሁንና፥ እግዚአብሔር ከ2000 ዓመታት በፊት በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ወደ ዓለማችን መጥቶ ነበር።

የሚያሳዝነው በዚያን ጊዜ ብዙ ሰዎች በእርሱ ያላመኑ ሲሆን፥ ዛሬም ሁኔታው ያው ያለማመን ጎልቶ የሚታይበት መሆኑ ነው።

አስቀድመን እንደ ተመለከትነው፥ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቶስ የሚያስተምረውን ለማመን፥ መጽሐፍ ቅዱስን ለማመን መቻል አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ እውነትና የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ እርግጠኞች መሆን አለብን። ስለ ሆነም፥ በምዕራፍ 2 መጽሐፍ ቅዱስ እውነትና የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ ለማረጋገጥ መረጃ አቅርበናል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቶስ የሚያስተምረንን ነገር ልናምን እንችላለን። በዚህ ምዕራፍ ስለ ክርስቶስ ማንነት፥ ስላደረጋቸው ነገሮችና እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል፥ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን እውነት እንመለከታለን።

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ምን ይነግረናል? እርሱ ማን ነው?

ለ. በኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጹ የእግዚአብሔር ባሕርያት የትኞቹ ናቸው?

ሐ. ከእግዚአብሔር ስሞች ስለ እግዚአብሔር ምን እንማራለን?

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ምን ይነግረናል? እርሱ ማን ነው?

«ኢየሱስም ብዙ ሰዎች ሲከቡት አይቶ ወደ ማዶ እንዲሻገሩ አዘዘ . . . ወደ ታንኳም ሲገባ ደቀ መዛሙርቱ ተከተሉት። እነሆም፥ ማዕበሉ ታንኳዪቱን እስኪደፍናት ድረስ በባሕር ታላቅ መናወጥ ሆነ፤ እርሱ ግን ተኝቶ ነበር። ደቀ መዛሙርቱም ቀርበው፦ ጌታ ሆይ፥ አድንን፥ ጠፋን እያሉ አስነሡት። እርሱም፦ እናንተ እምነት የጎደላችሁ፥ ስለ ምን ትፈራላችሁ? አላቸው፤ ከዚህ በኋላ ተነሥቶ ነፋሱንና ባሕሩን ገሠጸ፥ ታላቅ ጸጥታም ሆነ። ሰዎቹም፦ ነፋሳትና ባሕርስ እንኳ የሚታዘዙለት፥ ይህ እንዴት ያለ ሰው ነው? እያሉ ተደነቁ» (ማቴ. 8፡18–27)።

ኢየሱስ ክርስቶስ ምን ዓይነት ሰው ነው?

ጥቂት ሰዎች ክርስቶስን እውነተኛ ሰው አልነበረም ይላሉ። ሰው ቢመስልም በትክክል መንፈስ ነበር ይላሉ። ይህ ብዙ ሰዎች መናፍስትን በተመለከቱበት የአፍሪካ አህጉር ተቀባይነት ያለው ገለጻ ይሆናል። ይሁንና፥ ኢየሱስ መንፈስ ብቻ አልነበረም። ተራ ሰውም አልነበረም። እንደኛ ሥጋና ደም ያለው ትክክለኛ ሰው ነበር። ከሴት የተወለደና እንደ

ግንኛውም አይሁዳዊ ልጅ ያደገ ነበር (ሉቃ. 2፡51–52)። በትንሽ ከተማ ውስጥ የአናጢነትን ሥራ ያከናውንና በጎረቤቶቹ በደንብ ይታወቅ ነበር። አራት ወንድሞችና ሁለት ወይም ከዚያ የሚበልጡ እህቶች በነበሩበት ቤተሰብ ውስጥ አድጎአል (ማር. 6፡3)። ሰው በመሆኑም እንደ ማንኛውም ሰው፥ ደክሞአል (ዮሐ. 4፡6)፤ ተጠምቶአል (ዮሐ. 4፡7)፤ ተርቦአል (ማቴ. 4፡2)፤ እንዲሁም እንቅልፍ ተኝቶአል (ማቴ. 8፡24)።

ኢየሱስ በታሪክ ውስጥ የተመዘገበ ትክክለኛ ሰው ነበር። ቀለል ያለ አኗኗር ያሳለፈና ከአገሩ ርቆ ያልሄደ ሰው ነበር። ለብዙ ዓመታት መደበኛ ትምህርት አልተከታተለም። ከቶውንም ፖለቲካዊ ወይም ወታደራዊ መሪ ሆኖ አያውቅም። ይህም ሆኖ፥ ይህ ሰው በምድር ላይ ከኖሩት ሰዎች ሁሉ የሚለይበት ነገር ነበረው።

ማንም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ሊወዳደር አይችልም። በታሪክ ምዕራፍ ውስጥ ብቻውን ያለ ተወዳዳሪ ይቆማል። እርሱ በዘመናት ሁሉ ከኖሩት ሰዎች ሁሉ ይለያል። ከድንግል መወለዱ፥ ኃጢአት ያልነካው ሕይወት መምራቱ፥ የተቀደሰ ባሕርዩ፥ ወደር የለሽ ፍቅሩ፥ የተረጋገጡ ተአምራቶቹ፥ በነገሮች ላይ የነበረው ኃይሉ፥ የመሥዋዕትነት ሞቱ፥ የድል ትንሣኤውና ወደ ሰማይ ማረጉ ሁሉ አንድ ነገር ይጠቁሙናል፤ እንዲህ ያለ ሰው ከቶውንም አልነበረም የሚል። ኢየሱስ ሰው የሆነ አምላክ ነው። ሰብአዊነትን የተላበሰ አምላክ!

የዮሐንስ ወንጌል፥ «በመጀመሪያ ቃል ነበር፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበር» በማለት ይጀምራል (ዮሐ. 1፡1)። ከዚያም በዮሐንስ 1፡14፥ «ቃልም (ኢየሱስ) ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ» ይላል። በሌላ አባባል፥ እግዚአብሔር የሰውን ሥጋ ለበሰ።

ወረድ ብሎም ዮሐንስ፥ «መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው» ብሏል (1፡18)። ኢየሱስ፥ «እኔን ያየ አብን አይቶአል» ብሏል (ዮሐ. 14፡9)። ጳውሎስም፥ «በእርሱ (በክርስቶስ) የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራልና» ሲል ጽፎአል (ቆላ. 2፡9)። የዕብራውያን መጽሐፍ ጸሐፊም፥ «ስለ ልጁ ግን፦ አምላክ ሆይ፥ ዙፋንህ እስከ ዘላለም ድረስ ይኖራል . . . ይላል» ሲል ገልጾአል (ዕብ. 1፡8)። እነዚህ ሁሉ ጥቅሶች

ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እንደ ሆነ በግልጽ ያስተምራሉ። እግዚአብሔር ራሱን በሰው ግለትም በናዝሬቱ ኢየሱስ አካል ለሰው ልጆች ገልጾአል።

ስለ እግዚአብሔር የምናውቀው ነገር በግምታዊ አስተሳሰባችን ላይ አይመሠረትም። እግዚአብሔር እውነቱን በመጽሐፍ ቅዱስ ለእኛ ሊገልጽ ስለ መረጠ፥ ስለ እግዚአብሔር ልናውቅ እንችላለን። እግዚአብሔር ሰው የመሆኑን እውነት ለመረዳት እጅግ የሚያስቸግር ላይሆን ይችላል። በአንዳንድ የአፍሪካ ባህሎች፥ ከታላላቅ ቅድመ-ትውልዳዊ ነገሥታት ወይም ተዋጊዎች አንዱ ወይም ከዚያ የሚበልጡት በሰው አምሳል የነበሩ አማልክት እንደ ሆኑ ይታሰባል። መጽሐፍ ቅዱስ፥ እግዚአብሔር ከተራ አማልክት አንዱ፣ ወይም ቅድመ-ትውልዳዊ መንፈስ ላይሆን፥ ከሁሉም የሚልቀው ላዕላይ ህላዌ ("Supreme Being") ራሱ በናዝሬቱ ኢየሱስ አማካኝነት ምድራዊ አካል እንደ ለበሰ ይገልጻል።

አርዮሳውያን ("Arians") በክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያ ዓመታት የነበሩ ሕዝቦች ነበሩ። እነዚህም ወገኖች አርዮስ የተባለውን የአሌክሳንድሪያ ከተማ ሽማግሌ የተሳሳተ ትምህርት ተከተሉ። አርዮስ ኢየሱስ በትክክል አምላክ እንዳልሆነና በእግዚአብሔር የተፈጠረ ሰው ሆኖ ከሌሎች ሰዎች እንደሚበልጥ አስተማረ። ከረዥም ጊዜ በፊት እንደ ነበሩ አርዮሳውያንና ዛሬም ተመሳሳይ የተሳሳተ አሳብ እንደሚያስተምሩ የይሖዋ ምስክሮች (ጆባዎች)፥ ብዙ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደሚያስተምረው በኢየሱስ አምላክነት ለማመን አይፈልጉም። እውነቱን በአእምሮአቸው ለመረዳት ስለሚቸገሩ፥ ጭራሽ ያገሉታል። በምዕራፍ 4 እንደ ተመለከትነው፥ ሙሉውን የእግዚአብሔር እውነት አእምሮአችን ሊረዳው ከሚችለው እጅግ የላቀ ነው። እንግሊዛዊው ደራሲ ሲ ኤስ ሉውስ፥ «እግዚአብሔርን ልረዳው ብችል ኖሮ፥ እርሱ እግዚአብሔር ሊሆን አይችልም ነበር» በማለት ይህንኑ የሰብአዊ ግንዛቤ ውስንነታችንን ገልጸዋል። በሌላ አባባል፥ ሉውስ በቀላሉ የምንረዳው አምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጸውን የላቀ ህላዌ ሊወክል እንደማይችል መግለጻቸው ነበር።

መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰውና ፍጹም አምላክ እንደ ሆነ ያስተምራል። እርሱ ሰው የሆነ እግዚአብሔር ነው። እርሱን የሚመስል ግንም የለም። ሰዎች በዓይኖቻቸው፥ በጆሮዎቻቸውና በሌሎችም የስሜት አውታሮቻቸው እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ሊያውቁ አይችሉም። ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ማንነትና ምን

እንደሚመስል ለሰዎች ይገልጻል። ስለ ሆነም፥ እግዚአብሔር ማን እንደ ሆነና ምን እንደሚመስል ለማወቅ ከፈለግን፥ የናዝሬቱ ኢየሱስን ማጥናት አለብን።

ለ. በኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጹ የእግዚአብሔር ባሕርያት የትኞቹ ናቸው?

የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነትና ቸርነት

ኢየሱስ እንዴት እግዚአብሔርን ገለጸው? እግዚአብሔር ምን ይመስላል?

– ኢየሱስ በውኃ ላይ ተራምዷል (ማር. 6፡45–51)።

– የበለሲቱን ዛፍ ከመቅጽበት አድርቋል (ማቴ. 21፡19–20)።

– ነፋስና ማዕበልን አዞአል፤ አነርሱም ታዘውለታል (ሉቃ. 8፡22–25)።

– ከአንድ ሰው ውስጥ የአጋንንትን ሌጌዎን (ጭፍራ) አስወጥቷል (ማር. 5፡1–16)።

– ስግብግብና ምግባረ–ብልሹ የሆነውን የአንድ ቀራጭ ባሕርይ ወደ እውነተኛና ለጋስነት ለውጧል (ሉቃ. 19፡1–9)።

– ለአራት ቀናት ሞቶ የቆየውን ሰው አስነሥቷል (ዮሐ. 11፡38–44) ።

– የጋብቻው በዓል አከባበር እንዲቀጥል ለማድረግ ውኃ ወደ ወይን ጠጅ ለውጧል (ዮሐ. 2፡1–11)።

– ከአምስት ትናንሽ እንጀራና ከሁለት ዓሣ ከ5000 የሚበዙ ረሃብተኞችን መግቦ 12 መሶብ አስተርፎአል (ማቴ. 14፡15–21)።

– ሌሊቱን ሁሉ ሲደክሙ አድረው ምንም ያላገኙ ዓሣ አጥማጆችን፥ መረባቸው ሊቀደድ እስኪደርስ ድረስ በርካታ ዓሦች እንዲይዙ አድርጓል (ዮሐ. 21፡3–6)።

የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት

ሁሉም ሰው ለማለት ይችላል የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት ይገነዘባል። የአፍሪካ ሕዝቦበዙሪያቸው የሚገኘውን የእግዚአብሔርን ተፈጥሮአዊ ፍጥረት በመመልከት፥ ይህን እውነት ለአያሌ ክፍለ–ዘመናት

ተረድተዋል። የዙሉ ጎሳዎች፥ እግዚአብሔር «እንደ አንበሳ በማግሣት ሕዝቦችን በሽብር የሚያናውጥ» እንደ ሆነ ይናገራሉ።

የኢየሱስን ሕይወት ስንመለከት፥ ስለ እግዚአብሔር ኃይል ምን እንረዳለን? ከዚህ በላይ ደግሞ፥ እግዚአብሔር ኃይሉን ስለሚጠቀምበት ሁኔታ ምን እንማራለን?

ኢየሱስ ነፋስንና ማዕበልን በማዘዝ ጸጥ ባሰኘ ጊዜ፥ ደቀ መዛሙርቱ ተደንቀው ነበር። ምን ዓይነት ሰው ነው ቃል በመናገር ኃይለኛ የተፈጥሮ ኃይላትን ሊቆጣጠር የሚችል? በአንዳንድ በኩል የታመሙትን መፈወስ ቀላል ሊመስላቸው ይችላል። ምናልባትም እግዚአብሔር ኢየሱስ ስለ በሽተኞቹ የሚያቀርበውን ጸሎት እየመለሰ እንደ ሆነ ያስቡ ይሆናል። ይሁንና፥ አንድ ሰው ለነፋስና ማዕበል ተናግሮ እንዲታዘዙለት የሚያደርገው እንዴት ነው? ይህ ምን ዓይነት ሰው ነበር?

በሌላ ጊዜ፥ ኢየሱስ በውኃ ላይ ተራምዶ ሂዷል። እንዴት ተራ ሰው በውኃ ላይ ሊራመድ ይችላል? ኢየሱስ የተፈጥሮን ዓይነተኛ ሕግጋት ለመለወጥ ወይም ለማቆም የሚችል ይመስላል። እንዲህ ዓይነት ነገሮችን እንዴት ሊያደርግ ይችላል? በምድር ላይ አንድ ተመሳሳይ ነገር ተፈጽሞአል። ለበለስ ዛፍ ቃል በመናገሩ፥ በፊቱ ወዲያው ደርቃ ሞታለች (ማቴ. 21፡19–21)። አንድ ተራ ሰው ቃልን ብቻ በመናገር እንዴት የዛፍን ሕይወት ሊነጥቅ ይችላል?

የኢየሱስ የኃይሉ መጠን ከደቀ መዛሙርት የመረዳት ችሎታ በላይ ነበር። በበሽታና በአካለ-ስንኩልነቶች ላይ ኃይሉን ገልጾአል (ማቴ. 12፡10–13)። በአጋንንት ላይ ኃይሉን ገልጾአል (ማቴ. 8፡28–32)። ውኃን ወደ ወይን ለመለወጥ ኃይሉን አሳይቷል (ዮሐ. 2፡1–11)። ከጥቂት እንጀራና ዓሣ ብዙ ሕዝብ ለመመገብ የሚያስችል በቂ ምግብ በመፍጠር ኃይሉን አሳይቷል (ማቴ. 14፡15–21)። በቁሳዊውም ሆነ በመንፈሳዊው ዓለም ላይ ኃይሉን አሳይቷል። በተጨማሪም ስግብግብና ምግባረ-ብልሹ የነበረውን ቀራጭ ዘኬዎስን እንደ ለወጠው (ሉቃ. 19፡1–8)፥ የተበላሸ ባሕርይ ያላቸውን ሰዎች ወደ እውነተኛነት ለመለወጥ ኃይል እንዳለው አሳይቷል። ይህ ምን ዓይነት ሰው ነበር?

ከዚያም፥ ኢየሱስ ከሁሉም የላቀውን ተአምር አድርጓል። ከእግዚአብሔር በቀር ማንም የማይሠራውን ተአምር ሠርቷል። አንድ ሰው ከሙታን አስነሥቷል፤ ከሞተ አራት ቀናት የተቆጠሩበትን ሰው

(ዮሐ. 11፡38–44)! እውነቱ ቀስ በቀስ ለተከታዮቹ ይከሰት ጀመር። ይህ ሰው ኃይል ያለው መሆን ብቻ ሳይሆን፥ በምድርና በሰማይ ሁሉ ሥልጣን ያለው መስሎ ታየ። ስለ ሆነም፥ ከተራ ነቢይ መብለጡ የግድ ነበር። ማን ነበር እርሱ? እግዚአብሔር ነበር?

ኢየሱስ የሠራቸው ተአምራት እያንዳንዳቸው ዓላማ ነበራቸው። ባብዛኛው ከእነዚህ ዓላማዎች አንዱ ማንነቱን ለመግለጽ ነበር። ኢየሱስ፥ «እኔን ስንኳ ባታምኑ አብ በእኔ እንደ ሆነ እኔም በአብ እንደ ሆንሁ ታውቁና ታስተውሉ ዘንድ ሥራውን እመኑ» ብሏል (ዮሐ. 10፡38)። ተአምራቱ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ብቻ የሆነው ኃይል እንደ ነበረው ያሳያል። እግዚአብሔር ብቻ ሊያደርግ የሚችለውን ነገር አድርጓል። በምድርና በሰማይ በሚገኙ ነገሮች ሁሉ ላይ ኃይሉን ገልጾአል። በነገሮችና በሰዎች፥ በተፈጥሮ ኃይሎችና በመናፍስት ዓለም ላይ ሳይቀር ኃይል እንዳለው ገልጾአል።

ስለ ኢየሱስ እንግዳ የሚሆነው ነገር ቢኖር ኃይሉን የሚጠቀምበት መንገድ ነበር። በሁሉም ሁኔታዎች ማለት ይቻላል፡ ኃይሉን የሚጠቀመው ለሰዎች በጎ ተግባር ለመዋል ወይም መከራ የሚቀበሉትን፥ ተስፋ የቆረጡትን ወይም ሕይወት ፈት የነሣቸውን ወገኖች ለመርዳት ነበር። በአፍሪካ እንደሚገኙ አያሌ ባለመድኃኒቶችና ጠንቋዮች ፈውስን በመስጠቱ ወይም እርዳታ በመለገሱ ከሰዎች አንዳች ገንዘብ አልተቀበለም ነበር። የረዳቸው ሰዎች እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ታላቅ ነገር ለሌሎች እንዲያስረዱ ከመናገር የበለጠ ነገር አልጠየቃቸውም ነበር (ማር. 5፡18–19)።

ለኢየሱስ ክርስቶስ ተአምራትና ሕይወት ሊሰጥ የሚችለው ትክክለኛ ማብራሪያ አንድ ብቻ ነው። ብዙ ሰዎች እንደሚሉት፥ እርሱ ታላቅ የግብረ–ገብ መምህር ብቻ አልነበረም። የይሖዋ ምስክሮች እንደሚሉት፥ ከሁሉም የሚበልጥ መልአክ አልነበረም። ሙስሊሞች እንደሚያስተምሩት፥ ከነቢያት አንዱ አልነበረም። እንዲህስ አይደለም – ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ እግዚአብሔር ነው! ይህ በሕይወቱና በተአምራቱ ውስጥ ተመልክቷል። እንደ እርሱ ያለ ሰው ከቶውንም አልነበረም። መጽሐፍ ቅዱስ በቆላስይስ 2፡9፥ «በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራልና» ይላል።

የእግዚአብሔር ቸርነት

አፍሪካውያን ሕይወትን የሚሰጠውና የሚያቆየው እግዚአብሔር እንደ ሆነ በሚገባ ይረዳሉ። ይህም ባሕርይ የእግዚአብሔር ቸርነት ይባላል። በኦቪምቡንዱ ጎሳዎች ዘንድ ለእግዚአብሔር የተሰጠው ስያሜ «ለፍጥረታቱ የሚያስፈልገውን የሚያሟላ» የሚል ትርጉም አለው። እግዚአብሔር፥ በተለይም ዝናብ በመስጠት ሰው እህል እንዲያመርት የሚያስችል አምላክ መሆኑ በግልጽ ይታወቃል። ብዙውን ጊዜም፥ «ዝናብ ሰጪ» በመባል ይጠቀሳል። እንዲሁም ደግሞ ከሁሉም የሚበልጠውን የሰው ሕይወት ስጦታ ከማጎፀን የሚያስገኝ ተብሎ ይታወቃል።

እነዚህ አሳቦች ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ይስማማሉ። እግዚአብሔር ለኢዮብ በተናገረ ጊዜ፥ በሚከተሉት ጥያቄዎች ኢዮብን ተፈታትኖታል፦ «የውኖች ብዛት ይሸፍንህ ዘንድ ቃልህን ወደ ደመናት ታነግ ዘንድ ትችላለህን? መብረቆች ሂደው፦ እነሆ፥ እዚህ አለን ይሉህ ዘንድ ልትልካቸው ትችላለህን?» (ኢዮብ 38፡34–35)። እግዚአብሔር በመዝሙረኛው በኩል፥ «እነሆ፥ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው» ሲል ተናግሯል [መዝ. (127)፡3]።

5000 ሰዎችን የመመገብና ዓሦችን የመያዙ ተአምር፥ በክርስቶስ ሕይወት የተፈጸመውን የእግዚአብሔርን ቸርነት ያሳየናል። ጌታ ሕዝቡን እንደ ተራበ ወደ ቤቱ ለመስደድ ስላልፈቀደ፥ እነርሱን ለመመገብ በርካታ እንጀራና ዓሣ አዘጋጀ (ማቴ. 14፡15–21)። እግዚአብሔር ምግብ እንደሚያስፈልገን ስለሚያውቅ፥ ከእንስሳት በተጨማሪ፥ ለሰብል መብቀል አስፈላጊ የሆኑትን ዝናብ፥ የፀሐይ ብርሃን፥ አፈርና ዘር በመስጠት የምግብ ፍጆታችንን ያሟላል (ማቴ. 5፡45፤ የሐዋ. 14፡17)። ከ5000 የሚበልጡትን ሰዎች በመመገብ፥ ጌታ ለሰው ልጅ ምግብ የሚሰጥበትን ተለምዶአዊ ዘገምተኛ ሂደት አልፎ ምግቡን በፍጥነት አድርሶታል። በሌላ ጊዜ፥ ደቀ መዛሙርት የገቢ ምንጫቸው የሆነውን ዓሣ አጥምዶ የመያዝ ችግራቸውን በመረዳት፥ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ዓሦች ሰጥቷቸዋል (ዮሐ. 21፡3–6)። ዓሦቹን በመስጠት፥ ኢየሱስ በተጨማሪም ያለ እግዚአብሔር እገዛ ድካማቸው ከንቱ እንደ ሆነ አስተምሮአቸዋል (ዮሐ. 21፡5–6)።

ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር በተፈጥሮ ለሰዎች የማረስ ጥንካሬ በመስጠትና (ዘፍጥ. 2፡15) ምድርም እህል እንድታበቅል በማድረግ (ኢሳ. 55፡10)፥ የሚያስፈልገንን ነገር ያሟላልናል። እንዲሁም ደግሞ ለ2 ሚሊዮን እስራኤላውያን በምድረ በዳ ለ40 ዓመታት መና እንዳዘነበው፥ ከተፈጥሮአዊ በላቀ መለኮታዊ አሠራርም ይህንኑ ሊያደርግ ይችላል። ይሁንና፥ በእግዚአብሔር ተአምራት ላይ ተገቢ አመለካከት ሊኖረን ይገባል። እግዚአብሔር የሚያስፈልጉንን ነገሮች የሚያሟላበት የተለመደው መንገድ በተፈጥሮ ሕግጋትና ወቅቶች አማካኝነት እንጂ፥ በመለኮታዊ ተአምራት አይደለም። በመሆኑም፥ እግዚአብሔር እስራኤላውያን እህል ሊያመርቱ በማይችሉበት ምድረ በዳ በሚቆበዘበዙበት ወቅት መና ያወረደላቸው ሲሆን፥ ይህ መና የማውረድ ተግባር ሊያርሱና እህል ሊያመርቱ ወደሚችሉባት የከነዓን ምድር ሲገቡ አብቅቷል (ኢያሱ 5፡12)። በየትኛውም መንገድም ይሁን፥ አሁንም ለሰዎች የሚያስፈልገውን ነገር የሚያሟላው እግዚአብሔር ነው። መዝሙር (145)፡16፥ «አንተ እጅህን ትከፍታለህ፥ ሕይወት ላለውም ሁሉ መልካምን ታጠግባለህ» ይላል።

ሕይወት ከእግዚአብሔር እጅ የሚመጣ የቸርነት ስጦታ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን፥ በጋብቻ ልጆች መወለዳቸው ከጌታ የሚመጣ ስጦታ ነው [መዝ. (127)፡3]። ይሁንና፥ ብዙ ባህላዊ ወግ አጥባቂ ሰዎች እንደሚያምኑት፥ ባለትዳሮች ልጅ ለመውለድ ባይችሉ፥ ይህ የእግዚአብሔር ርግማን ተደርጎ መወሰድ የለበትም። ቀጥሎ ጋብቻ በሚናገረው ምዕራፍ ውስጥ የመካንነትን ችግሮች ቀፈብ ብለን እንመለከታለን።

በተጨማሪም፥ እግዚአብሔር እያንዳንዳችን በምድር ላይ ምን ያህል ቀናት እንደምንኖር ይወስናል (ዕብ. 9፡27)። መዝሙረኛው፥ «የተፈጠሩ ቀኖቼ ሁሉ አንድ ስንኳ ሳይኖር በመጽሐፍህ ተጻፉ» ብሎአል [መዝ. (139)፡16]። ኢየሱስ ክርስቶስ በቸርነቱ ሕይወትን ይሰጣል፤ ያቆያል፤ ይወስዳልም። እንዲሁም፥ በቃሉ ዓለምን ያጸናል (ዕብ. 1፡3)። ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወት ሰጪ እንደ ሆነ የሚያመለክተው እጅግ ታላቅ መረጃ የተገኘው፥ በዚህ ምዕራፍ መጀምሪያ ላይ እንደ ተጠቀሰው ታሪክ፥ ለሞቱት ሰዎች ሕይወትን መልሶ በዘራባቸው ጊዜያት ነው (ሉቃ. 7፡11–15)።

እግዚአብሔር በብዙ የተለያዩ መንገዶች ለሰዎች የሚያስፈልጉትን ነገሮች ያሟላል። እግዚአብሔር የሰዎችን እጅግ የጠለቁ ስሜታዊ መሻቶች ስለሚያውቅ፥ በቤተሰብና ጋብቻ አማካኝነት እነዚያን መሻቶች ለማሟላት አጠቃላይ ልግስና አድርጎላቸዋል። በዓለም ሁሉም ሰብአዊ ፍጥረት በሌላው ሰው ሊወደድና ሊመሰገን ይፈልጋል። ጋብቻ ይህንኑ የወንዶችና ሴቶች ጥልቅ ፍላጎት ያሟላል። እግዚአብሔር ፍቅር ስለ ሆነ (1 ዮሐ. 4፡8)፥ ለሰዎች በጋብቻ ውስጥ የፍቅርን፥ የአንድነትንና የስሜታዊ ደኅንነትን ስጦታ ሰጥቷቸዋል። ይሁንና፥ ሰዎች ሁሉ የመጋባት ዕድል ስለማይገጥማቸው፥ እግዚአብሔር እነዚህን መሻቶች ለማሟላት ለሌሎች መንገዶችን አዘጋጅቷል። ይህ ሊሆን የሚችልበት አንዱ መንገድ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ኅብረት አማካኝነት ነው።

በገሊላ ቃና ሰርግ ላይ የተፈጸመው ተአምር (ዮሐ. 2፡1–11)፥ ኢየሱስ ነገሮችን ለመለወጥ ኃይል እንዳለው ያሳየናል። (እንደ ውኃ ያሉትን) ተራ የሕይወት ነገሮች ወስዶ (እንደ ወይን) ልዩ ወደ ሆኑ ነገሮች ሊለውጥ ይችላል። በዚህ አጋጣሚ ኢየሱስ በነገሮች ጥረትና በሕይወት ጥራት ላይ ኃይል እንዳለው አሳይቷል። እንዲሁም፥ በዚህ አጋጣሚ ለወጣት ሙሽሮች ደስታ በግሉ ግድ እንደሚለው ገልጾአል። ኢየሱስ ወደ አንድ ሰው ሕይወት ውስጥ በሚገባበት ጊዜ፥ የዚያ ሰው የሕይወት ጥራት ይለወጣል። ውኃው ወደ ወይን ጠጅ እንደ ተለወጠ ሁሉ፥ (እንደ አዲስ ኪዳኑ ዘኬዎስ) ራስ–ወዳድነትና ስግብግብነት የተጫጫነውም ሰው ሰጪና ለጋሽ ይሆናል (ሉቃ. 19፡8)።

የእግዚአብሔር ሉዓላዊነትና ሁሉን አዋቂነት

ኢየሱስ እግዚአብሔርን እንዴት ገለጸው? እግዚአብሔር ምን ይመስላል?

– እርሱ አጽናፈ–ዓለሙ የተፈጠረበትና በቃሉም የሚያጸናው ነው (ዕብ. 1፡2–3)።

– እርሱ በሰማይም ይሁን በምድር ሥልጣን ሁሉ የተሰጠው ነው (ማቴ. 28፡18)።

– እርሱ ዓለምን ከመፍጠሩ አስቀድሞ የእርሱ ሕዝቦች እንሆን ዘንድ የመረጠን ነው (ዮሐ. 15፡16፤ ኤፌ. 1፡4)።

– እርሱ ገና ሳይሆን በፊት የወደፊቱን የሚያውቅ ነው (ሉቃ. 21፡1–28)።

– እርሱ አንዳንድ ጊዜ ለደቀ መዛሙርቱ ወደፊት ስለሚሆነው ነገር ዝርዝር ጉዳዮችን የገለጸ ነው (ማር. 14፡12–16)።

– እርሱ ድሀዱቱ መበለት ምን ያህል እንደ ሰጠች፥ ለምን እንደ ሰጠችና ምን ያህል እንደ ቀራት ያወቀ ነው (ማር. 12፡42–43)።

– እርሱ የሳምራዊቷን ሴት ስውር ኃጢአቶች ያወቀ ነው (ዮሐ. 4፡17–18)።

የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት

ሉዓላዊነት ማለት በአንድ መንግሥት፥ መልከዓ ምድራዊ ክልል፥ ወይም ግዛት ላይ ፍጹም አገዛዝ ወይም ሥልጣን ማግኘት ማለት ነው። ሉዓላዊ የሆነ ሰው ፍጹም ገዥ ነው። በአንድ የአፍሪካ የጭነት መኪና ፊት ለፊት ላይ ስለ እግዚአብሔር ሉዓላዊነት፥ እግዚአብሔር በአጽናፈ–ዓለሙ ላይ ከሁሉም የሚበልጥ ገዥ እንደ ሆነ የሚገልጽ ቀላልና ዳሩ ግን ጥልቅ መልእክት ያለው ዓረፍተ ነገር ተለጥፎአል። ዓረፍተ ነገሩም፥ «ማንም ንጉሥ እግዚአብሔርን አያህልም» የሚል ነው።

ይህም ደግሞ እውነት ነው። እግዚአብሔር ሁሉን ይገዛል። እግዚአብሔር ትዕቢተኛና ትምክህተኛ የነበረው የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር አእምሮውን እንዲያጣ አድርጓል (ዳን. 4፡28–33)። ከሰባት የዕብደት ዓመታት በኋላ፥ ናቡከደነፆር በእግዚአብሔር ፊት በሚገባ ተዋረደ። ለግዛቱ ሁሉ ባሰራጨው ግልጽ ደብዳቤም፥ «ልዑሉንም ባረከሁ፥ ለዘላለም የሚኖረውን አመሰገንሁ አከበርሁትም፤ ግዛቱ የዘላለም ግዛት ነውና፥ መንግሥቱም ለልጅ ልጅ ነውና። በምድርም የሚኖሩ ሁሉ እንደ ምናምን ይቆጠራሉ፤ በሰማይም ሠራዊት በምድርም ላይ በሚኖሩ መካከል እንደ ፈቃዱ ያደርጋል፤ እጁንም የሚከለክላት ወይም፦ ምን ታደርጋለህ? የሚለው የለም። አሁንም እኔ ናቡከደነፆር የሰማይን ንጉሥ አመሰግናለሁ፥ ታላቅም አደርገዋለሁ፥ አከብረውማለሁ። ሥራው ሁሉ እውነት፥ መንገዱም ፍርድ ነውና፥ በትዕቢትም የሚሄዱትን ያዋርድ ዘንድ ይችላልና» (ዳን. 4፡34–37) ሲል መስክሯል። በአንድ ወቅት ለዳንኤል ሦስት ጓደኞች፥ «ከእጁስ የሚያድናችሁ አምላክ ማን ነው?» (ዳን. 3፡15) የሚል

የዓመፅ ምላሽ ከሰጠው ንጉሥ ይህንን አስደናቂ ምስክርነት መስማት ምንኛ ይገርማል!

በእርግጥ እግዚአብሔር ከሁሉም የላቀ የበላይ ንጉሥ በመሆኑ፥ በሁሉም ላይ ይገዛል [መዝ. (103)፡19]።

በመጽሐፈ ኢዮብ የወደቀው መልአክ ግለትም ሰይጣን ኢዮብን ከመፈተኑ በፊት ከእግዚአብሔር ዘንድ ፈቃድ ማግኘት የግድ ያስፈልገው ነበር (ኢዮብ 1፡6–12)። በኋላም ኢዮብ ራሱ፥ «ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደ ሆንህ፥ አሳብህም ይከለከል ዘንድ ከቶ እንደማይቻል አወቅሁ» በማለት የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት መስክሯል (ኢዮብ 42፡2)! ሰይጣን ወደ ሰዎች ሕይወት አስከፊ መከራዎች ለማምጣት ፈቃድ ያገኘባቸው ዕድሎች እንኳ፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የተቀደሰ በር ግለፍ እንደሚያስፈልጋቸው መረዳት ምንኛ የሚያጽናና እውነት ነው! እግዚአብሔር ብቻውን ይገዛል!

በአጽናፈ-ዓለሙ ውስጥ በሚገኙ ነገሮች ሁሉና በሰዎች ሁሉ ላይ የላቀ ሥልጣን ያለው ይህ እግዚአብሔር ማን ነው? ስሙስ ማን ነው? ኢየሱስ፥ «ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ» ብሏል (ማቴ. 28፡18)። የመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻው መጽሐፍ በሆነው በዮሐንስ ራእይ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰማይን ሠራዊት ሲመራ ተመልክቷል። በልብሱም ላይ ዘላለማዊ የማዕረግ ስሙ ተጽፎአል! ይህም፥ «የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ» የሚል ነው (ራእይ 19፡16)። በፊልጵስዩስ መልእክት፥ ጳውሎስ አንድ ቀን፥ «በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም» እንደሚንበረከኩና «መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ» እንደሚመሰክር ይገልጻል (ፊልጵ. 2፡10–11)። ምንም ዓይነት ጥያቄ ሊኖር አይችልም። ኢየሱስ ክርስቶስ የአጽናፈ-ዓለሙ ንጉሥ ነው!

እግዚአብሔር ሉዓላዊ ነው። እግዚአብሔር ማንንም ሳያማክር ይወስናል። (እርሱን እንደ መረጡት ለሚያስቡ) ለደቀ መዛሙርቱ፥ «እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም . . . ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬአችሁም ሊኖር ሾምኋችሁ» በማለት አስገርሞአቸዋል (ዮሐ 15፡6) ።

ኢየሱስ ክርስቶስ በነገሮች ሁሉ ላይ ሉዓላዊ ገዥ እንደ ሆነ በከፍተኛ ተግባራዊ ተዛምዶ የሚገልጽ አንድ እውነት በዮሐንስ ራእይ ውስጥ

ይገኛል። ኢየሱስ በፊልድልፍያ ቤተ ክርስቲያን ለሚገኙ ክርስቲያኖች፥ «በአንተ ፊት የተከፈተ በር ሰጥቼአለሁ ማንም ሊዘጋው አይችልም» ብሎአል (ራእይ 3፡8)። ከዚህ ከፍ ብሎ ለዚህች ቤተ ክርስቲያን፥ «የዳዊት መክፈቻ ያለው፤ የሚከፍት፥ የሚዘጋም የሌለ፤ የሚዘጋ፥ የሚከፍትም የሌለ፤ ቅዱስና እውነተኛ የሆነው» ሲል ራሱን ገልጾአል (ቁ. 7)። ጌታን ለማገልገል ሕይወታቸውን ለሚሰጡ ክርስቲያኖች ይህ ምንኛ የሚያጽናና እውነት ነው። የሚያገለግሉት በነገሮች ሁሉ ላይ ሉዓላዊ ሥልጣን ያለውን ጌታ ነው። እርሱ የአገልግሎትን በር ሊከፍት፥ ማንኛውም የዓለም ኃይል ሊዘጋው አይችልም!

ይህንንም መላው ዓለም በ1990ዎቹ መጀመሪያ ላይ በቀድሞዪቱ ሶቭዬት ኅብረት ደርሶ የተመለከተው ነው። በ1918ቱ የኮሚኒስት አብዮት ወቅት የቀድሞዎቹ ከሐዲ መሪዎች፥ ለዘላለም በእግዚአብሔር እውነት ላይ በር እንደሚዘጉ አጥብቀው ወስነው ነበር። ይሁንና፥ የእግዚአብሔር ሕዝቦች እግዚአብሔር ኮሚኒዝምን አጥፍቶ ዳግም ለወንጌሉ ብርሃን በር እንዲከፍቱ ንቅተው ጸለዩ። ኢየሱስ ክርስቶስም ይህንኑ ጸሎት በመመለስ፥ የወንጌሉን በር አስፍቶ ከፈተው፤ ኮሚኒዝምንም አስወገደው፤ ይህም በመሆኑ፥ የሩሲያ መንግሥት ለትምህርት ቤቶች ክርስቲያን መምህራንን ለመቅጠር ሲሻ፥ የ«ኢየሱስ» ፊልም በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች እንዲታይ ጠይቋል፤ ኢየሱስ የከፈታቸው በሮች ተከፍተው እንዲቆዩ ሲወስን፥ ማንም እንዲዘጋቸው አይፈቅድም። ሲዘጋው ደግሞ ማንኛውም የዓለም ኃይል ሊከፍተው አይችልም። በአንድ የአፍሪካ የጭነት መኪና ላይ የተጠንጠለጠለ ጥቅስ እንደሚለው፥ «እግዚአብሔር አም ሲል፥ ማን አይደለም ይላል?» እግዚአብሔር ሉዓላዊ ነው።

የእግዚአብሔር ሁሉን አዋቂነት

ከእግዚአብሔር የሚሰወር አንድም ነገር የለም። ይህም ባሕርይ ሁሉን አዋቂነት ይባላል። እግዚአብሔር ስለ ሕይወታችን ሁሉንም ነገር ያውቃል። ከሌሎች የምንደብቀውንና ከራሳችንም እንኳ ለመደበቅ የምንጥረውን ነገር ሁሉ ያውቃል! በራሳችን ላይ ያሉትን የጸጉሮች ቁጥሮች የመሳሰሉትንና፥ እኛ ራሳችን የማናውቃቸውን የሕይወታችንን ገጽታዎች ሳይቀር ያውቃል (ሉቃ. 12፡7)። እንቅስቃሴአችንንና አሳባችንን ሁሉ ያውቃል። መዝሙረኛው፥ «አንተ መቀመጤንና መነሣቴን አወቅህ፤ አሳቤን ሁሉ ከሩቅ አስተዋልህ . . . መንገዶቼን ሁሉ ቀድመህ አወቅህ። ገና ከመናገሬ በፊት ምን ለማለት እንደማስብ ታውቃለህ» ይላል [መዝ.

(139)፡2–4 – የመጨረሻው ቁጥር ከአዲሱ የ1980 ዓ. ም. ትርጉም የተወሰደ]። እርሱ ስላለፈው፥ አሁን ስላለውና ወደፊት ስለሚመጣው ሁሉ ያውቃል። በአጭሩ፥ እርሱ ሁሉንም ያውቃል። ይህ ባሕርይ ሁሉን አዋቂነት ("Omniscience") ተብሎ ሊታወቅ፥ ለሕይወታችን ትልቅ አስፈላጊነት አለው።

እግዚአብሔር የወደፊቱን ስለሚያውቅ፥ የሚያስደንቀው ነገር አይኖርም። እርሱ ሊታለል፥ ወይም ሊፈራ፥ ወይም ሊረታ አይችልም። እርሱ ከመከሰቱ በፊት የማያውቀው ምንም ነገር በማንኛውም ሰው ሊደርስም ሆነ በየትኛውም ስፍራ ሊከናወን አይችልም። እንዲሁም ደግሞ እያንዳንዱ ተግባር የሚያስከትለውን ውጤት ያውቃል። ስለ ሆነም፥ ሰይጣንን ጨምሮ፥ ማንም ቢሆን እግዚአብሔርን በተሳካ ሁኔታ ሊታወም አይችልም። ዕቅዶቹንም የሚያኮላሽ ማንም የለም (ኢዮብ. 42፡2፤ ኤፌ. 1፡11)።

ኢየሱስ በሰማርያ በሚገኝ የሲካር የውኃ ጉድጓዱ፥ ለሴቲቱ በሕይወቷ ስለ ነበሩ ስውር ኃጢአቶች በመናገር የእግዚአብሔርን ሁሉን አዋቂነት ገልጾአል (ዮሐ. 4፡17–18)።

እርሱ አስቀድሞ ያላወቀው ምንም ነገር ከእግዚአብሔር ልጆች በአንዱ ላይ እንደማይደርስ መረዳት አለብን። እንዲሁም ከፍጹም ፈቃዱና ፍቅሩ አኳያ ወደፊት ምን እንደሚያደርግ አስቀድሞ ወስኖአል። መዝሙረኛው፥ «ለእኔ የተወሰኑልኝ ቀኖቼ ገና ከመጀመራቸው በፊት፥ በመዝገብህ ሰፍረዋል» ይላል [መዝ. (139)፡16 – ከ1980 ዓ. ም. ትርጉም]። ከማይዛነፍ እውቀቱና ከማይገሠሥ ኃይሉ የተነሣ፥ እግዚአብሔር ነገሮች ሁሉ እርሱን ለሚወዱት ለበጎ እንዲሆኑ የማድረግ ችሎታ አለው (ሮሜ 8፡28)። ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ ከሚገኙ እጅግ አስደናቂና አጽናኝ እውነቶች አንዱ ነው።

(እንደ ኢዮብ) በአስከፊ ሁኔታ ውስጥ የሚዋልል አማኝ በዓይነ–ሕሊናህ ተመልከት። ለዚያ ሰው ሁኔታው ሁሉም ያከተመበት መስሎ ሊታየው ይችላል። ይሁንና፥ እግዚአብሔር ጋና ከመፈጸሙ በፊት ይህንኑ ሁኔታ ያውቅ ነበር። በተጨማሪም፥ ይህንኑ ለማድረግ ቃል ስለ ገባ ሁኔታውን እንዴት ወደ በጎነት እንደሚለውጥም ያውቃል (ሮሜ 8፡28)። ኢየሱስ በሰማይና በምድር ሥልጣን ሁሉ ስላለው፥ እጅግ ከከፉ ሰዎች

ወይም ከወደቁ መላእክት ዕቅዶች መልካም ነገር እንዲወጣ ሊያደርግ ይችላል።

ችግሮች በሚጫጫኑብን ጊዜ እንዴት እግዚአብሔር በሕይወታችን ነገሮችን ለበጎ እየሠራ እንዳለ መረዳት በጣም የማይመስል ነገር ነው። ምናልባት በሰማይ ቤት ሕይወታችን መለስ ብለን ወደ ኋላ በመመልከት እንረዳው ይሆናል፤ ደግሞም፥ እግዚአብሔር እንዲሁ እንደሚሆን ይናገራል። እርሱ ደግሞ አይዋሽም። በእኛ በኩል፥ እግዚአብሔርን በአስቸጋሪ ሁኔታዎች መታመንንና እነዚህንም ሁኔታዎች ለበጎነት ለመጠቀም እንደሚችል ማመንን መማር አለብን።

መጽሐፈ ኢዮብ ይህንኑ እውነት ያስተምራል። እግዚአብሔር ሰይጣን ኢዮብን በብዙ አስጨናቂ መከራዎች እንዲያሠቃይ ፈቀደለት። ምንም እንኳ ኢዮብ ምን እየተፈጸመ እንዳለና ምክንያቱስ ምን እንደ ሆነ ባይረዳም፥ እግዚአብሔር ለኢዮብ ምን እንደሚያደርግለት ያውቅ ነበር። በመጨረሻም፥ ልክ ሮሜ 8፡28 እንደሚያስተምረን፥ እግዚአብሔር እርሱን ለወደደው ኢዮብ እነዚህን መከራዎች ለበጎ አደረጋቸው።

ለክፉ ሰዎች ወይም ለወደቁ መላእክት እግዚአብሔርን ማሸነፍ የማይቻል ነው። በዚህ ምክንያት ክርስቲያኖች «በሁሉ እንዲያመሰግኑ» ተነግሮአቸዋል (1 ተሰ. 5፡18)። የዚህ ዓይነቱ እምነት ሰው በእኛ ላይ ከሚያውጠነጥናቸው ክፉ ዕቅዶች የተነሣ የሚመጣብንን ፍርሃት እንድናሸንፍ ይረዳናል [መዝ. (27)፡1–3]። የዚህ ዓይነቱ እምነት ሰይጣን በሕይወታችን ላይ ያለውን ኃይል ያስወግዳል (ራእይ 12፡11)።

በዔድን ገነት ሰውን ለማጥፋት ሰይጣን ለወጠናቸው ዕቅዶች እግዚአብሔር ምን እንዳደረገ ተመልከት። ከመፈጸሙ በፊት፥ እግዚአብሔር ሁኔታውን እንዴት እንደሚያስተናግድ ዕቀደ። ከዓለም መሠረት አስቀድሞ፥ እግዚአብሔር እንዴት በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ደኅንነታችንን እንደሚፈጽም ዕቀደ (ኤፌ. 1፡4፤ 1 ጴጥ. 1፡20)። ከዚህም እግዚአብሔር እጅግ ከከፉ ሁኔታዎች መልካም ለማድረግ እንደሚችል እናያለን።

መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ለገዛ ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለ ሁላችን አሳልፎ የሰጠው ያው ከእርሱ ጋር ደግሞ ሁሉን ነገር እንዲያው እንዴት አይሰጠንም?» ይላል (ሮሜ 8፡32)። እግዚአብሔር የወደፊቱን ከስተት ስለሚያውቅና በሕይወታችን ላይ ጉዳት የሚያስከትሉትን ሁኔታዎች ለመለወጥ በሰማይም ሆነ በምድር ሙሉ ሥልጣን ስላለው፥ ይህንኑ

ሊያደርግ ይችላል። እርሱ ሁሉን ያውቃል። እርሱ ነገሮችን ሁሉ ይቆጣጠራል። እርሱ ሁሉን አዋቂና ሉዓላዊ አምላክ ነው።

ዮሴፍ ከወንድሞቹና በጓላም በግብፅ አገር ከሌሎች ሰዎች እንዴት የመረረ ግፍ እንደ ተፈጸመበት አስታውስ (ዘፍጥ. 37–40)። ዮሴፍ ላደረገው መልካም ነገር ሁሉ፥ ፍጻሜው በግብፅ ወኅኒ ቤት መግቀቅ ሆነ (ዘፍጥ. 40፡23)። ይሁንና፥ እግዚአብሔር የዮሴፍን ሁኔታ መለወጥ ብቻ ሳይሆን፥ ኃጢአተኛ ወንድሞቹ እንኳ እስኪባረኩ ድረስ በጎነትን ከዚያ አበቀለ (ዘፍጥ. 41–50)። ዮሴፍ ይህንን ተአምር እግዚአብሔር እንዳደረገ ተገነዘበ። ዮሴፍ ለወንድሞቹ፥ «እናንተ ክፉ ነገርን አሰባችሁብኝ፥ እግዚአብሔር ግን ዛሬ እንደ ሆነው ብዙ ሕዝብ እንዲድን ለማድረግ ለመልካም አሰበው» ብሏል (ዘፍጥ. 50፡20)።

እንዲሁም፥ ማርያምና ማርታ ስለ ወንድማቸው አልዓዛር መታመም እንዴት አስቸኳይ መልእክት እንደ ላኩ አስታውስ (ዮሐ. 11፡3)። ይሁንና፥ ኢየሱስ አልዓዛር እንዲሞትና የእህቶቹ ልብ እንዲሰበር ፈቀደ (ዮሐ. 11፡4–19)። በእኛም ሕይወት አዘውትሮ የሚፈጸመው ይኸው ነው። ልባችን ይሰበርና ጌታ እንደ ረሳን አድርገን እናስባለን። ኢየሱስ ማርያምንና ማርታን አልረሳቸውም ነበር። በመጨረሻም አልዓዛርን ከሞት በማስነሣት፥ ከሕመሙ ከመፈወስም የበለጠ በጎነትን አድርጓል።

እግዚአብሔር ዳዊት ታላላቅ ኃጢአቶችን እንደሚፈጽም ቢያውቅም እንኳ፥ የእስራኤል ንጉሥ እንዲሆን መረጠው። የመረጠውም ዳዊት እንደ እግዚአብሔር ልብ በመሆኑ ነው (1 ሳሙ. 13፡14) ። ዳዊትም ኃጢአቱን እንደሚናዘዝና በዚህም ልምምድ ውስጥ እንደሚያድግ ያውቅ ነበር። ሌሎቹ የእሴይ ልጆች መልካም ቢመስሉም (1 ሳሙ. 16፡5–7)፥ ዳዊት የነበረው ዓይነት አፍቅሮተ–እግዚአብሔር አልነበራቸውም። እግዚአብሔር ይህንን ያውቅ ነበር። እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂና ሉዓላዊ አምላክ ነው።

የእግዚአብሔር ፍቅር

ኢየሱስ እግዚአብሔርን እንዴት ገለጸው? እግዚአብሔር ምን ይመስላል?

– እርሱ የሙሉ ጤናማነትና ከሌሎች ሰዎች ጋር ተገቢ ግንኙነት የማድረግ ተስፋ ያልነበራቸውን አሥር ከማኅበረሰቡ የተገለሉ ለምጻሞች ፈውሶአል (ሉቃ. 17፡11–19)።

– እርሱ በእንባዋ እግሮቹን ያጠበችለትን ጋለሞታ ሴት ይቅር ለማለት ፈቅዶአል (ሉቃ. 7፡36–48)።

– እርሱ አንድ ብቸኛ ልጅዋ ለሞተባት የናይን መበለት አዝኖላታል። እርሱ ልጁን ከሞት አንሥቶ ዳግም ለእናቱ ሰጥቷል (ሉቃ. 7፡11–15)።

– እርሱ ያሠቃዩትንና የገደሉትን ሰዎች ይህንኑ ተግባር በመፈጸም እንዳሉ ሳሉ እንኳ ይቅር ያላቸው ነው (ሉቃ. 23፡34)።

– እርሱ ገና ኃጢአተኞችና ዓመፀኞች ሳለን ለኃጢአታችን ዋጋ የከፈለልን ነው (ኢሳ. 53፡5፤ ሮሜ 5፡8፤ 1 ጴጥ. 2፡24)።

ለብዙ ሰዎች የእግዚአብሔር እጅግ አስፈላጊ ባሕርይ ለሰው ልጅ ያለው ፍቅር ነው። ምንም እንኳ ባህላዊ አፍሪካውያን ብዙውን ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ባይናገሩም፥ ዝናብ፥ እህል፥ ልጆችንና ሥጋዊ ጉድለቶችን በመሙላት የሚያሳየውን በጎነት ያውቁታል። በአፍሪካ አመለካከት የእግዚአብሔር በጎነትና ፍቅሩ በቅርብ የተቆራኙ ናቸው።

ሁልጊዜም እውነተኛ ፍቅር በይበልጥ የሚታየው በተግባር እንጂ በቃላት አይደለም። ብዙውን ጊዜ ፍቅር ለተፈቃሪው በጎነት በሚውል አንድ ልዩ ተግባር ይገለጻል። የእግዚአብሔር ፍቅር ለፍጥረታቱ በጎነት ባደረጋቸው ተግባራት ተገልጾአል። የእግዚአብሔር ፍቅር በኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወትና ተግባራት ውስጥ በይበልጥ ግልጽ ሆኖ ታይቷል። ኢየሱስ በተግባሮቹ ምስክርነት፥ ፍቅር የእግዚአብሔር ባሕርይ ቀዳሚ አካል እንደ ሆነ አሳይቷል። ኢየሱስ የፍቅርን ጥልቀት ከሰብአዊ መረዳት በላቀ መልኩ አሳይቷል። እርሱን የገደሉትን ሰዎች ይህንኑ ተግባር በመፈጸም ላይ እንዳሉ ይቅር አላቸው። በመስቀል ላይ እየተሠቃየ፥ ወደ እግዚአብሔር አምላክ በመጮኽ፥ «አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» አለ (ሉቃ. 23፡34)።

በይፋዊ ሕይወቱ ሁሉ፥ ኢየሱስ የቸርነት፥ የፍቅርና የምሕረት ተግባራትን ፈጽሞአል። በሽተኞችን በመፈወስ፥ የዓይነ–ስውራንን ዓይኖች በማብራት፥ ለምጻሞችን በማንጻት፥ አጋንንትን በማስወጣት፥ ሙታንን በማስነሣት ህልቆ–መሳፍርት በሌላቸው መንገዶች ለሰዎች ሥቃይና ጉድለት አገልግሎቱን አበርክቷል።

የዚህ ምዕራፍ የመክፈቻ ታሪክ የኢየሱስ ክርስቶስን ፍቅርና ርኅራኄ በከፍተኛና ልብን በሚነካ መንገድ ይገልጻል። የመበለቲቱ ብቸኛ ልጅ ሞቶ ነበር። ባሏን በማጣቷ ከአንድ ልጁ በቀር ማንም አልነበራትም። ልጁ፣

ከባኋ ሞት ጀምሮ ብቸኛው የቁሳዊ ድጋፍዋ ምንጭና የስሜታ መጽናኛና መበረታቻ ሊሆን ይችላል። እንግዲህ፥ የሞተባት ይኸው ብቸኛ የመጽናኛና የእርዳታ ምንጭ ነበር ማለት ነው። ልጁ ሞተ። ኢየሱስ ይህችን ድሀ ሴት ተመለከተ፤ በሁሉን አዋቂነቱም በልቧ ውስጥ ያለውን ሥቃይና ጭንቀት አወቀ። በአንድ ጊዜ በሁሉን ቻይ ኃይሉና የርኅራኄ ፍቅር በምትገልጥ አንዲት ዓረፍተ ነገር፥ ኢየሱስ የዚህችን ድሀ ሴት ሕይወት ከምስኪንነት ጭንቀት በደስታ ወደ ሚያስፈነድቅ ሁኔታ ለወጠው። በልቧ የተሰማትን ስሜት ለመግለጽ ቃላት አይገኙም።

ኢሳይያስ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለሰው ልጆች ስለ ተገለጠው ስለዚህ አስደናቂ የእግዚአብሔር ፍቅር ይናገራል። መሢሑ፥ «በአመድ ፋንታ አክሊልን፥ በልቅሶም ፋንታ የደስታን ዘይት፥ በጎዘንም መንፈስ ፋንታ የምስጋናን መጎናጸፊያ» እንደሚሰጣቸው ይናገራል (ኢሳ. 61፡3)። ይህ ለዚህች ድሀ መበለት ምንኛ እውነት ነበር! ከዚያስ በኋላ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ሰዎች ይህ እንዴት እውነት ነበር! ለብዙዎቻችን፥ በመጀመሪያ ወደ ንስሐና በእርሱ ወደማመን ያመጣን የክርስቶስ ፍቅር ነው። በታሪክ ሁሉ እንደዚህ ሰው ሌሎችን የወደደ የለም። ይህ የእግዚአብሔር ልብ ነው። ከፍ ያለው እግዚአብሔር በትክክል ይህንን ይመስላል። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም፥ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና» ይላል (1 ዮሐ. 4፡8)።

አንድ ወላጅ ልጁን ከእሳት ወይም በውኃ ከመስጠም አደጋ ለማትረፍ ሕይወቱን ይሰጥ ይሆናል፤ ዳሩ ግን ጤነኛ አእምሮ ያለው ማንም ሰው ለማያውቀው እንግዳ በፈቃዱ ነፍሱን አይሰጥም፤ ለጠላት ደግሞ ይህንን ማድረግ ከቶውንም አይታሰብም። ኢየሱስ ያደረገው ግን ይኸው ነው። ከዓመፃችን የተነሣ የእግዚአብሔር ጠላቶች ሳለን ሕይወቱን ለእኛ አሳልፎ ሰጠ። ጳውሎስ፥ «ስለ ጻድቅ የሚሞት በጭንቅ ይገኛልና፤ ስለ ቸር ሰው እንኳ ሊሞት የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል። ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል» ይላል (ሮሜ 5፡7–8)።

ከፍቅሩ የተነሣ፥ ኢየሱስ እርሱን በምግደል ላይ የሚገኙትን ሰዎች ይቅር ይላቸው ዘንድ አብን በመጠየቅ፥ በመስቀል ላይ ጸለየ (ሉቃስ 23፡34)። ለሰዎች ካለው ፍቅር የተነሣ፥ የአጽናፈ-ዓለሙ ንጉሥ ግርማዊነቱን በሰማይ ጥሎ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሰዎች አገልጋይ ሆነ (ማር. 10፡45፤ ፊልጵ. 2፡6–7)።

እግዚአብሔር እንዴት የሰዎች አገልጋይ ሊሆን ይችላል? አሳቡ ራሱ ከአእምሮአችን በላይ ነው። ይሁንና፤ ይኸው ሆኖአል። ኢየሱስ የሰዎች ትሑት አገልጋይ ከመሆን ያለፈ ነገርም አድርጓል። እርሱ ራሱ በክፉ ሰዎች ሊሠቃይና ሊገደል ፈቀደ (ፊልጵ. 2፡8)። ለምን? ምክንያቱም ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ ስለ ወደደንና ይቅርታ ማግኘታችንንና ደኅንነታችንን በአስተማማኝ ሁኔታ ሊፈጽምልን ስለ ወሰነ ነው (ኤፌ. 1፡4፤ ራእይ 13፡8)። እግዚአብሔር እንዴት ከመወለዳችን አንኳ አስቀድሞ ሊወደን ይችላል? ይህ የሆነው እግዚአብሔር ፍቅር በመሆኑ ነው (1 ዮሐ. 4፡8)። ይህ ዓይነተኛ ባሕርዩ ነው። ፍቅር የሚኖረው እግዚአብሔር ስላለ ነው። እንዲሁም፥ የእግዚአብሔርን ፍቅር በኢየሱስ አየን።

የእግዚአብሔር ርኅራኄና መልካምነት

ኢየሱስ እግዚአብሔርን እንዴት ገለጸው? እግዚአብሔር ምን ይመስላል?

- እርሱ የሳምራዊቷን ሴት ባዶነትና የስሜት ጠባሳዎች ተመልከቶ፥ በምትኩ የምትኖርበትን ነገር የሰጣት ነው (ዮሐ. 4፡4–29)።

- እርሱ ዲዳና ደንቆሮ የነበረውን ሰው ፈውሶ፥ እንዲናገርና እንዲሰማ ያደረገው ነው (ማር. 7፡31–37)።

- እርሱ በሁኔታው የተበሳጨ ደቀ መዛሙርት ማጉረምረማቸውን ቢቀጥሉም፥ ዳሩ ግን ሕፃናትን በክንዶቹ እንደ ታቀፈ የባረካቸው ነው (ማር. 10፡13–16)።

- እርሱ የአንድን ሰው የሰለለ እጅ ወዲያው የፈወሰ ነው (ማር. 3፡1–6)።

- እርሱ ወንድማቸው ሞቶባቸው በመራራ ኀዘን ተውጠው ላያቸው ወዳጆቹ ያነባና የሞተ ወንድማቸውን በማስነሣት ኀዘናቸውን ወደ ደስታ የለወጠ ነው (ዮሐ. 11፡33–44)።

- እርሱ ከሚነዱና ከሚሠቃዩ ሰዎች የሚመጡትን የኃዘን ጩኸቶች ሰምቶ በመመለስ፥ እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑበትን ምክንያት የሚሰጥ ነው (ሉቃስ 18፡37–42)።

የእግዚአብሔር ርኅራኄ

ኢየሱስ ለሚነዱና ለሚሠቃዩ ሰዎች ይራራላቸዋል። ርኅራኄ አንድ ሰው የሌላውን ሰው ችግር ለማስወገድ ሲል ማንኛውንም መሥዋትነት ለመክፈል ግድ የሚሰኝበት ዝንባሌ ነው። ኢየሱስ ስንታመም፥ ወይም ስንዝል፥ ወይም ተስፋ ስንቆርጥ ግድ ይሰኛል። እርሱ የሚሠቃዩትን፥ የሚነዱትንና ከማኅበረሰቡ የተገለሉትን ሰዎች ጩኸትና ጸሎት ይሰማል።

እርሱ ለመፈወስ፥ ለመርዳት፥ ለማዳን፥ ለማደስ ኃይል አለው። እርሱ ተስፋ የቆረጡትን ለመርዳትና በሕይወት የመኖር ደስታ ለማደስ በኃይሉ ሊጠቀም ይሻል (ሉቃ. 18:42–43)። በኢሳይያስ 61:1 ክርስቶስ በነቢዩ አማካኝነት፥ «የጌታ እግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥ ለድሆች የምሥራችን እሰብክ ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶኛልና፤ ልባቸው የተሰበረውን እጠግን ዘንድ» ሲል ተናግሯል። ኢየሱስ የሚያፈቅር፥ ግድ የሚሰኝና በችግራችን ጊዜ የሚረዳንን አምላክ ገለጸልን። ኢየሱስ ጸሎታችንን የሚመልስ አምላክ ገለጸልን።

እግዚአብሔር ምን ይመስላል? እስካሁን ስለ ኢየሱስ ካጠናነው፥ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ፥ ሉዓላዊና ሁሉን አዋቂ አምላክ እንደ ሆነ ተመልክተናል። እርሱ ለማድረግ ከመረጠ፥ የሚሳነው ምንም ነገር የለም። ይሁንና፥ በዚህ ኃይሉ የሚጠቀመው ለሰው ልጆች በጎነት እንጂ፥ ለራሱ አይደለም። እግዚአብሔር ግድ የሚሰኝና ሩኅሩኅ እንደ ሆነና ለፍጥረቱም የፍቅር ልብ እንዳለው ተመልክተናል። ሥቃያችንንና ሕመማችንን ያውቃል – ግድም ይለዋል። ከእኛ በተቃራኒ፥ ለሥቃያችን መፍትሔ ለመስጠትም ኃይል አለው። የታመመን ለመፈወስ፥ ለምጻሙን ለማንጻት፥ ኃጢአተኛን ይቅር ብሎ ለመመለስ ይችላል። የወደቀን ደግፎ ለማንሣትና ልቡ የተሰበረበትን ለመፈወስ ይችላል። ኅዘናችንን ወደ ደስታ፥ ጭንቀታችንን ወደ ምስጋናና ውዳሴ ሊለውጥ ይችላል።

የእግዚአብሔር መልካምነት

እንዲሁም፥ ከእነዚህ ምሳሌዎች እግዚአብሔር መልካም እንደ ሆነ እንረዳለን። የተቸገሩትን ለመርዳትና ሥቃያቸውን ለማስወገድ ኃይሉን ተጠቅሞአል። በተፈጥሮው መልካም በመሆኑ፥ ኃይሉን የተጠቀመው መልካም ለማድረግ ነው። እንዲያውም፥ ከእግዚአብሔር በቀር እውነተኛ

መልካምነት ማንም የለውም። ኢየሱስ ለባለጸጋው ወጣት ገዢ፥ «ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ማንም የለም» ብሎአል (ሉቃስ 18፡19)።

እግዚአብሔር መልካምና ሩኅሩኅ ከሆነ እንግዲህ ክርስቲያኖች ለምን ይሠቃያሉ? ስለ እግዚአብሔር መልካምነትና ርኅራኄ የሚናገረው እውነት ለክርስቲያኖች ትልቅ የመረዳት ችግር ይፈጥራል። እግዚአብሔር መንፈሳዊ ሰዎች እንዲሠቃዩ የሚፈቅደው ለምንድ ነው? እግዚአብሔር አንዳንዶቹን ሲፈውስ፥ ሌሎቹን የማይፈውሰው ለምንድ ነው? አንዳንድ ክፉታቸው በግልጽ የሚታወቅባቸው ሰዎች ከሥቃይ ሲያመልጡ፥ አንዳንድ ሕይወታቸውን ለእርሱ የሰጡ ክርስቲያኖች በከፍተኛ ሥቃይና ሕመም እንዲማቅቁ የሚያደርገው ለምንድን ነው?

አንዳንድ ሰዎች ሥቃይ ሁሉ ከጠንቋዮችና ከክፉ መናፍስት እንደሚመጣ ያስባሉ። ጠንቋዮችና አጋንንት ክፉ ኃይል እንዳላቸው እውነት ነው። ወደ በኋላ ይህንኑ ጉዳይ ጠለቅ ብለን እንመለከታለን። ይሁንና፥ በስፋት የምንመለከተው የሰው ልጅ ሥቃይ ከጠንቋዮችና ከአጋንንት እንደሚመጣ ተደርጎ ሊታመን አይገባም። ሌሎች ደግሞ ሥቃይ በሰውየው ሕይወት ከሚገኝ የተሰወረ ኃጢአት ወይም ከእምነት ማነስ እንደሚመጣ ያስባሉ። አንዳንድ ጊዜ የተሰወረ ኃጢአት ወይም የእምነት አጦት ምክንያት ሊሆን ቢችልም፥ ይህ ለሥቃይ ሁሉ መንስዔ ሊሆን አይችልም። በዮሐንስ ምዕራፍ ዘጠኝ ዓይነ-ስውር ሆኖ ስለ ተወለደው ሰው፥ ኢየሱስ ኃጢአቱ ለዓይነ-ስውርነቱ ምክንያት እንደ ሆነ የሚገልጸውን አሳብ አልተቀበለም (ዮሐ. 9፡2-3)። የኢዮብን ሥቃይ ተመልከት። ጌታ ራሱ ኢዮብ ነቀፋ የሌለበት እንደ ሆነ መስክሯል (ኢዮብ 1፡8)! በተጨማሪም፥ ወንጌላት እንዴት ኢየሱስ ትንሽ ወይም ምንም እምነት የሌላቸውን አንዳንድ ሰዎች እንደ ረዳ ይተርካሉ (ማር. 9፡24-27)። በመሆኑም፥ ስለሚበዛው ሥቃያችን አንድ ምሥጢር አለ ማለት ነው። ያንን ሁሉ ወደፊት በሰማይ ሊገልጽልን የሚችለው ጌታ ብቻ ነው።

በኃጢአት መሠራጨትና በሰዎች ሕይወት ላይ ባስከተለው ውድቀት የተነሣ፥ ክፋት በነገሠበት ዓለም እንኖራለን። ሰውነቱ በክፉ በሽታ ተመርዘ እንደሚያቃትት ሰው ሁሉ፥ ዓለምም ለመሞት በማጣጣር ላይ ይገኛል። ከሥቃያችን አንዳንዱ በራሳችን ኃጢአትና ሞኝነት ባጠቃው ውሳኔአችን የተነሣ የሚመጣ ነው። ይሁንና፥ በዓለማችን ላይ ከሚፈጸመው ሥቃይ የሚበዛው የሌሎች ሰዎች ኃጢአትና ኃጢአታቸውም በማኅበረሰቡ ላይ ከሚያስከትለው ውጤት የሚመጣ ነው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን

በ1994 ዓ. ም. በሩዋንዳ መራራ ሥቃይ የቀመሱትና የሞቱት በሺህ የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች ሁኔታ ነው። ከእነዚህ ክርስቲያኖች ብዙዎቹ የተሠቃዩትና የሞቱት በራሳቸው ሕይወት ስለ ነበረው ኃጢአት ሳይሆን፡ ዳሩ ግን የነሰኻነት ኃጢአት አስከፊ ውጤት በሆነው በሁለቱ ጎሳዎች ጦርነት ብቀላ ሳቢያ ነው።

ከኃጢአት ውጤቶች የተነሣ፥ አያሌ ሰዎች የመቋቋም ዓቅምን ከሥጋዊ ሥቃይ በላይ በመፈታተን የሚያማቅቁ ስሜታዊና አእምሮአዊ ችግሮች ይታወካሉ። ለምሳሌ፥ የወላጆቻቸው ፍቅር ወደ ጥላቻና ፍች ሲለወጥ የተመለከቱትን ልጆች ስሜታዊ ሥቃይ ተመልከት። በዚህ ጊዜ፥ ልጆቹ የወላጆቻቸው ኃጢአታዊ አመለካከትና ቁጣ ገፈት ቀማሾች ይሆናሉ። በተጨማሪም፥ በዓለም ውስጥ ብዙ ሥቃይ ከሰይጣን ተግባር ይመነጫል። ኢየሱስ ሰይጣን ከመጀመሪያው ነፍሰ-ገዳይ እንደ ሆነ ተናግሯል (ዮሐ. 8፡44)።

ኢየሱስ የታመሙትን እንደ ፈወሰና ኃጢአተኞችን በንስሐ እንደ መለሰ እናውቃለን። ዛሬም ይህንኑ የማድረግ ኃይል እንዳለው እናውቃለን። ኢየሱስ አእምሮአዊና ስሜታዊ ብሎም ሥጋዊ ችግሮችን ለመፈወስ ይችላል። የሰው መንፈስ ዘላለማዊ በመሆኑ፥ ልብንና አእምሮን መፈወስ ሰውነትን ከመፈወስ የበለጠ አስፈላጊ ነው።

ኢየሱስ ዛሬም በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ እርሱ በመረጠበት ስፍራና ጊዜ ሁሉ ተአምራትን ይፈጽማል። በሌላ ጊዜ ደግሞ አያደርገውም። በገሊላም ሆነ በይሁዳ የታመሙትን ሁሉ አልፈወሰም ነበር። አንዳንዶቹን ሲፈውስ ሌሎቹን ላለመፈወስ የመረጠው ለምንድን ነው? በመጽሐፍ ቅዱስ ለዚህ ጥያቄ የተሰጠ መልስ አይገኝም። እርሱ አምላክ በመሆኑ፥ ከሁሉም የተሻለውን አድርጓል። ማንም ሊጠይቀው አይችልም። በምሕረቱ ውስጥ ምሥጢር አለ!

ኢየሱስ «መንግሥትህ ትምጣ። ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን» ብለን እንድንጸልይ አስተምሮናል (ማቴ. 6፡10)። በሰማይ በሽታ፥ ወይም ዓይነ-ስውርነት ወይም ሥቃይ ወይም ሞት እንደሌለ እናውቃለን (ራእይ 21፡4)። ይሁንና፥ ይህ ጸሎት ሁለት ክፍሎች አሉት። በመጀመሪያ፥ «መንግሥትህ ትምጣ» ብለን እንድንጸልይ ተነግሮናል። የእግዚአብሔር መንግሥት ሙሉ ለሙሉ በምድር ላይ እስካልተመሠረተች ድረስ፥ «ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን» ለሚለው ጸሎት ሙሉ ምላሽ ማግኘቱ የማይመስል

ነው። የዚህ መጽሐፍ የመጨረሻ ምዕራፍ የክርስቶስ መንግሥት በመጨረሻ ስትመጣ ሁኔታው ምን እንደሚመስል ይገልጻል። ይህም የሚሆነው እርሱ ወደዚህ ዓለም ሲመለስ ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ በሰማይ እንደ ሆነ በምድርም የሚሆነው የዚያን ጊዜ ብቻ ነው።

በሕይወት ምላሽ ያላገኘንላቸው ብዙ ጥያቄዎች አሉ። ሙሴ የተገለጹት ነገሮች ሁሉ ለእኛና ለልጆቻችን ሲሆኑ፥ ያልተገለጹት ደግሞ ለእግዚአብሔር እንደ ሆኑ ጽፎአል (ዘዳ. 29፡29)። ያልተመለሱትን ጥያቄዎች ለእግዚአብሔር በመተው፥ ለእኛ ላለመግለጽ ለመረጣቸው ነገሮች እግዚአብሔርን መተማመኑ ጥበብ ነው። እግዚአብሔር መልካምና ሩኅሩኅ እንደ ሆነ እናውቃለን። ማወቅ የሚያስፈልገንም ይህንኑ ነው።

የእግዚአብሔር ቅድስናና ቁጣ

ኢየሱስ እግዚአብሔርን የገለጸው እንዴት ነው? እግዚአብሔር ምን ይመስላል?

- እርሱ ቅዱስ፥ ነቀፋ የሌለበትና ንጹሕ ነው (ዕብ. 7፡26)።

- እርሱ ምንም ኃጢአት ያልፈጸመና ምንም ውሸት ያልተናገረ ነው (1 ጴጥ. 2፡22)።

- እርሱ ተከሶ በቀረበ ጊዜ ዳኛው ምንም በደል አላገኘሁበትም ያለው ነው (ሉቃ. 23፡4)።

- እርሱ እጅግ የከፉ ጠላቶቹ በደል ሊያገኙ ያልቻሉበት ነው (ዮሐ. 8፡46፤ 10፡32-33)።

- እርሱ አጋንንት እንኳ «የእግዚአብሔር ቅዱሱ» ብለው የጠሩት ነው (ማር. 1፡24፤ ሉቃስ 4፡34)።

- እርሱ የፈሪሳውያንን ኃጢአትና ግብዝነት በሁሉም ፊት በይፋ ያጋለጠ ነው (ማቴ. 23፡1-33)።

- እርሱ ስግብግብ ገንዘብ ለዋጮችን ከመቅደስ በጅራፍ ገርፎ ያባረራቸው ነው (ዮሐ. 2፡14-16)።

- እርሱ አጋንንት እንጠፋለን ብለው በፊቱ የተንቀጠቀጡለት ነው (ማር. 1፡24)።

የእግዚአብሔር ቅድስና

በአፍሪካ ባህላዊ እምነቶች ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔርን ኃጢአት-አልባ ፍጹምነት በቃላቸው ባይገልጹትም በልባቸው ግን ይረዱታል። ይህም ከእግዚአብሔር ጋር በተያያዙ ሥርዓቶች የግድ አስፈላጊ በሆኑ ጥብቅ ደንቦች ተንጸባርቋል። የቩርባ ሕዝቦች ስለ እግዚአብሔር ሲናገሩ፥ «ነውር የሌለበት ንጹሕ ንጉሥ» ይላሉ። ይሁንና፥ ምንም እንኳ እግዚአብሔር በአፍሪካውያን ዘንድ ንጹሕና ጥፋት የሌለበት መሆኑ ቢታወቅም፥ ባጠቃላይ መልኩ ግን ኃጢአት በእግዚአብሔር ቅድስና ላይ የሚፈጸም አስቀያሚ ተግባር ተደርጎ አይታይም። ይልቁንም፥ ኃጢአት በማኅበረሰቡ ላይ ኃፍረት ወይም ርኩሰት የሚያመጣ ባሕርይ ተደርጎ ይታሰባል። በዚህ አሳብ ላይ በምዕራፍ 7 ውስጥ በይበልጥ እንነጋገራለን።

በብሉይ ኪዳን ቅድስና የሚለው ቃል ከተራ ግልጋሎት ለእግዚአብሔር ግልጋሎት የመለየትን አሳብ ያመለክት ነበር። በመቅደስ ለአምልኮ የሚያገለግሉ ቁሳዊ ነገሮችና ልብሶች ሲቀደሱ፥ ከተራ ግልጋሎት ተለይተው ለእግዚአብሔር ተለይተዋል ወይም ተሰጥተዋል ማለት ነበር (ዘሌ. 8፡10)። ስለ ሆነም፥ ቅድስና ለእግዚአብሔር የተሰጠ ወይም የተሰየ ወይም የተሰጠ ማለት በመሆኑ፥ ከርኩሰት የነጻ ነበር።

እግዚአብሔርን በተመለከተ፥ ቅድስና ከባሕርዩ ጋር መዛመድ አለበት። እርሱ ፍጹም፥ ከጥፋት የራቀ፥ ንጹሕና ከማንኛውም የኃጢአት ርኩሰት የነጻ ነው። ነቢዩ ዕንባቆም እግዚአብሔርን፥ «ዓይኖችህ ክፉ እንዳያዩ ንጹሕን ናቸው፥ ጠማምነትንም ትመለከት ዘንድ አትችልም» ብሎአል (ዕንባ. 1፡13)። ኢዮብም፥ «እነሆ፥ . . . ከዋክብትም በፊቱ ንጹሓን አይደሉም» ብሏል (ኢዮብ 25፡5)። በእግዚአብሔር ዘንድ ከተውንም ኃጢአት፥ ርኩሰት ወይም ግድፈት የለም። እርሱ እንደ ሰው አይደለም። እርሱ ሙሉ ለሙሉ ጻድቅ ነው። እርሱ የሚያደርገው ነገር ሁሉ ትክክለኛና ፍጹም ነው። መልካምን እንጂ፥ ከተውንም ክፉ ነገር አያደርግም።

በአንድ በኩል ለእግዚአብሔር ቅድስናው ዋነኛ መሠረታዊ ባሕርዩ ነው። ሁሉም ባይሆኑ አብዛኛዎቹ የግብረ-ገብ ባሕርያቱ ከቅድስናው ጋር የተያያዙ ናቸው። እግዚአብሔር ቅዱስ ስለ ሆነ፥ መልካም ነው። እርሱ ቅዱስ ስለ ሆነ፥ ሩኅሩኅ ነው። ቅዱስ ስለ ሆነ፥ ቸርና አፍቃሪ ነው።

ቅዱስ ስለሆነ፥ ፍትሕ አድራጊ ነው። ቅዱስ ስለ ሆነ፥ በኃጢአት ላይ ከፍተኛ ቁጣ ያወርዳል። ቅዱስ ስለ ሆነ፥ ለሕዝቡ ታማኝ ነው።

እግዚአብሔር ቅዱስ ስለ ሆነ፥ ኃጢአትን በከፍተኛ ደረጃ ይጠላል (ዕብ. 7፡26፤ 1 ጴጥ. 1፡15–16)። እንዲሁም፥ ኃጢአት ፍጹም ፍጥረቱን ስላበላሸው ኃጢአትን ይጠላል (ዘፍጥ. 1፡31)። ስለ ሆነም ኃጢአትን በሞት ቅጣት ኮንኖታል (ዘፍጥ. 2፡17፤ ሮሜ 6፡23)። የኃጢአት ጥላቻው በኃጢአት ላይ ያለውን ቁጣ ይገልጻል።

ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ቅድስና የገለጸው እንዴት ነው? ስለ ክርስቶስ ሐዋርያት የጻፉአቸው ዓረፍተ ነገሮች ምንም ዓይነት ኃጢአት እንዳልነበረበት ያስተምራሉ (ዕብ. 7፡26፤ 1 ጴጥ. 2፡22)። ኢየሱስ የጠሉትንና በመጨረሻም የገደሉትን የአይሁድ መሪዎች፥ «ከእናንተ ስለ ኃጢአት የሚወቅሰኝ ማን ነው?» (ዮሐ. 8፡46) ሲል ጥያቄ ተፈታትኖአቸዋል። የሚያስገርመው፥ ክርስቶስን ለማናናቅ መንገድ የሚሹ ሰዎች ራሳቸው ከሕይወቱ አንዲት ኃጢአት ወይም ጥፋት ለመጥቀስ አልቻሉም ነበር! ይህ በእውነቱ የሚያስገርም ነገር ነው። ይህ ኢየሱስ ያቀረበው ጥያቄ በሌላ ሰው ተጠይቆ ቢሆን ኖሮ፥ የዚያ ሰው ጠላቶች ኃጢአቶቹን ወይም ጥፋቶቹን ለመዘርዘር እጅግ በፈጠኑም ነበር።

ኢየሱስ በጲላጦስ የፍርድ ችሎት ፊት በቀረበ ጊዜ፥ ጲላጦስ ብዙ ጊዜ ኢየሱስ፥ ከማንኛውም ዓይነት በደል ንጹሕ እንደ ሆነ ገልጾ ነበር (ሉቃስ 23፡4፥ 14፥ 22)። የጲላጦስ ሚስት ወደ ጲላጦስ መልእክት በመላክ፥ ኢየሱስ «ጻድቅ ሰው» እንደ ሆነ ገለጸች (ማቴ. 27፡19)። መልአኩ ገብርኤል የኢየሱስን መወለድ ለማርያም ሲያውጅ፥ ኢየሱስን «ቅዱሱ» ብሎታል (ሉቃስ 1፡35)። የሙስሊሞች ቁርዓን እንኳ ኢየሱስ «ጥፋትን እንዳልፈጸመ» ይመሰክራል (ሱረቱ 19፡19)።

ምናልባት የኢየሱስን ቅድስና በተመለከተ ከሁሉም የላቀ ምስክርነት የመጣው ጨርሶም ካልተጠበቀ ምንጭ ነው ለማለት ይቻላል። ኢየሱስ አጋንንትን ሲያጋፍጥ፥ «የእግዚአብሔር ቅዱሱ» በማለት ጠርተውታል (ማር. 1፡24፤ ሉቃ. 4፡34)! ክርስቶስ ከፈሪሳውያን ጋር ያደረገው ተግዳሮትና ገንዘብ ለዋጮችን ከመቅደስ ያባረረበት ቁጣም ንጽሕናውንና ለኃጢአት ያለውን ጥላቻ ይገልጻል።

የክርስቶስ መፈተን ስለ እግዚአብሔር ቅድስና ብዙ አማኞችን ግራ የሚያገቡ ሁለት አስፈላጊ ጥያቄዎችን ያስነሣል። ክርስቶስ እግዚአብሔር

ከሆነ፥ እንዴት ኃጢአት ለማድረግ ይፈተናል? መጽሐፍ ቅዱስ፥ «እግዚአብሔር በክፉ አይፈተንም» ይላል (ያዕ. 1፡13)። ሁለተኛ፥ ቢፈተንም እንኳ፥ እግዚአብሔር ቅዱስ ስለ ሆነና ኃጢአት ሊሠራ ስለማይችል፥ ምን ትርጉም ሊሰጥ ይችላል? ለእነዚህ ሁለት ጥያቄዎች የሚሰጠው መልስ ስለ ክርስቶስ ምድራዊ ሕይወት ጥልቅ መረዳትን ያስገኝልናል።

የመጀመሪያውን ጥያቄ ለመመለስ ክርስቶስ በአንድ አካል የተዋሃዱ ሁለት ባሕርያት እንደ ነበሩት ልናስታውስ ይገባል። እኛ አንድ ሰብአዊ ባሕርይ ያለን ሰዎች ነን። ክርስቶስ ግን ሁለት ባሕርያት ነበሩት። ክርስቶስ እንደ እኛው ፍጹም ሰው ሲሆን፥ በተመሳሳይ ጊዜ ፍጹም አምላክ ነበር። እርሱ ከፊል ሰውና ከፊል አምላክ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ነበር። ክርስቶስ በተፈተነ ጊዜ፥ ለፈተና የተጋለጠው የክርስቶስ ሰብአዊ ተፈጥሮ እንጂ አምላካዊ ተፈጥሮ አልነበረም። እርሱ እንደ እኛው ሙሉ ለሙሉ ሰው ስለ ነበር፥ በሰብአዊ ተፈጥሮው የሕይወት መከራዎች፥ ትግሎች፥ ሥቃይና ተስፋ መቁረጥ ሊሰሙት ይችል ነበር። ምንም እንኳ አምላካዊ ተፈጥሮው ሊፈተንና ኃጢአት ሊሠራ ባይችልም፥ ሰብአዊ አእምሮውና ሰውነቱ ግን በኃጢአት ሊፈተን ይችል ነበር። ፈተና በራሱ ኃጢአት እንዳልሆነም መረዳት አለብን። ፈተና ወደ ኃጢአት የሚገፋፋ ማባበያ ነው።

በተጨማሪም፥ ኢየሱስ ፍጹም ሰብአዊ ተፈጥሮ እንዳለው መረዳቱ ሁለተኛውንም ጥያቄ ይመልሰዋል። ልክ የእኛ ሰውነት ለኃጢአት እንደሚፈተን ሁሉ፥ የኢየሱስ ሰብአዊ ሰውነትና አእምሮም ለኃጢአት ሊፈተን ይችል ነበር። ለምሳሌ፥ በጌቴሴማኔ የአትክልት ስፍራ የነበረውን የኢየሱስን ባሕርይና ቃላት ስንመለከት፥ የመከራው ሥቃይ እንዴት በጥልቀት እንደ ተሰማው እንረዳለን። ላቡ እንደ ደም ጠብታ በሚንጠባጠብበት በከፋ የሥቃይ ስሜቱ ወቅት፥ ኢየሱስ ቢቻል አብ የመከራውን ጽዋ እንዲያስቀርለት ጩኾ ተማጸነ (ሉቃስ 22፡42–44)። የመስቀሉን ሥቃይና መስቀሉ የሚያስከትለውን ከአብ የመለየት ሁኔታ ለማስወገድ፥ የኢየሱስ ሰብአዊ ተፈጥሮ በከፍተኛ ሁኔታ ይፈተን ነበር (ማቴ. 27፡46)። ኢየሱስ ወደ ዓለም የመጣው ለዚሁ በመስቀል ላይ ለመሞቱ ዓላማ እንደ ሆነ ያውቅና ለሌሎችም ይናገር ስለ ነበር፥ ይህ የሚያስደንቅ እውነት ነው (ዮሐ. 10፡17–18)! ይሁንና፥ ወደ መስቀሉ የሚሄድበት ሰዓት በደረሰ ጊዜ፥ ሰብአዊ ተፈጥሮው ከሚያሸብረው እውነታ ጋር ይታገል ጀመር።

በሰብአዊ አእምሮውና አካሉ ምክንያት፥ የኢየሱስ ሥቃይ፥ መከራና ፈተና ሁሉ ትክክል ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ከመከራው መታዘዝን እንደ ተማረ ይናገራል (ዕብ. 5፡8)። ለዚህ ነው በአብ ፊት የሚራራ ታላቅ ሊቀ-ካህናችን ሊሆን የበቃው (ዕብ. 4፡14-15)።

የእግዚአብሔር ቁጣ

እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ያለውን ፍቅር ከመግለጹ በተጨማሪ፥ ኢየሱስ እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ያለውንም ቁጣ ገልጾአል። ኢየሱስ የፈሪሳውያንን ግብዝነት በግልጽ ተቃውሞአል (ማቴ. 23፡1-33)። ግብዞች መሆናቸውን እንዴት አወቀ? በግልጽ ወደ ልባቸው በመመልከት፥ በሰዎች ፊት ለማስመሰል የሚሞክሩትን ሳይሆን ትክክለኛ አሳባቸውን አወቀ። ፈሪሳውያን ቁጹሳን እንደ ሆኑ ቢያስመስሉም፥ ከዚህ ባሕርይ ርቀው ነበር። ሃይማኖታዊ ልምምዶቻቸው ሁሉ ውጫዊ ሥርዓቶች ብቻ ነበሩ። ጌታ ልባቸውን ስለሚያውቅ፥ በዚያ ልባቸው ውስጥ በተመለከተው የትዕቢት፥ የስግብግብነትና የራስ ወዳድነት አሳቦች ተቆጥቶ ነበር። ለፈሪሳውያኑ ኃጢአታቸው የሲኦልን ቅጣት እንደሚያስከትልባቸው ቃል ገባ (ማቴ. 23፡33)! ክርስቶስ ፈሪሳውያንን ከኮነነበት መንገድ፥ እግዚአብሔር በልብ ውስጥ ያለውን እንደሚያይ እንረዳለን። እርሱ ሊታለል የማይችል ፍትሐዊና አድልዎ የማያደርግ ዳኛ ነው። የኢየሱስ ፈሪሳውያንን መኮነን እግዚአብሔር በግብዝነትና በሌሎችም ኃጢአቶች ላይ እንደሚቆጣ ይገልጻል።

በተጨማሪም፥ ኢየሱስ ፈሪሳውያንን ከኮነነበት ሁኔታ፥ ማናቸውም ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች ከእግዚአብሔር የፍትሕ ፍርዶች ወይም በኃጢአት ላይ ከሚያወርደው ቁጣ እንደማያድኑን እንረዳለን። ብዙ ሰዎች ልክ እንደ ፈሪሳውያኑ፥ በሃይማኖታዊ ልምምዶቻቸው ይታለላሉ። እንደ ጥምቀት፥ መደበኛ ጸሎቶች፥ ወይም ለድሆች መመጽወት በመሳሰሉ አንዳንድ ሥርዓቶች ወይም ሃይማኖታዊ ልምምዶች በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የሚያገኙ ይመስላቸዋል። እነዚህ ወገኖች፥ ሰው ፊትን እንደሚያይና እግዚአብሔር ግን ልብን እንደሚያይ ይዘነጋሉ (1 ሳሙ. 16፡7)።

ኢየሱስ ገንዘብ ለዋጮችን በጅራፍ እየገረፈ ከመቅደሱ ካስወጣበትም ሁኔታ እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ እንደሚቆጣ እንመለከታለን። ምንም እንኳ እርሱ አንድ ሰው ቢሆንና እነርሱ በቁጥር ቢበራከቱም፥ ከቁጣው ጋር ሲጋፈጡ ሸሽተው ወጡ። የእግዚአብሔር ቁጣ በኃጢአት ላይ በጣም ከባድ ነው። እርሱ ወደፊት ኃጢአትን ሁሉ ይቀጣል (ዕብ. 2፡2)።

ለዲያብሎስና ለመላእክቱ በኃጢአታቸው ምክንያት ዘላለማዊ ቅጣት አዘጋጅቶላቸዋል (ማቴ. 25፡41)። ኃጢአታቸው ይቅር ያልተባለላቸው ሰዎችም ወደዚያው ተመሳሳይ የቅጣት ስፍራ ይጣላሉ (ማቴ. 25፡41)።

የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው (ሮሜ 6፡23)። ማንም ሰው ሰናይ ምግባራትን በመከወን፥ ወይም ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ፥ ወይም ሃይማኖታዊ ጉዞ በማድረግ፥ ወይም ሥርዓታዊ ጸሎቶችን በመድገም፥ ወይም ለድሆች በመመጽወት፥ ወይም በሌላ በማንኛውም ሃይማኖታዊ ልምምድ ከሞት ቅጣት አያመልጥም። እግዚአብሔር በኃጢአታችን ላይ ከሚያፈርደው ቁጣ የምናመልጥበት አንድ መንገድ ብቻ አለ። ኢየሱስ ስለ እኛ በመስቀል ላይ የፈጸመውን መሥዋዕት መቀበል አለብን (2 ቆሮ. 5፡21)። ኢየሱስ በእኛ ምትክ እንደ ኃጢአት መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ተሠውቷል (ሮሜ 8፡3)። እርሱ በምትካችን የከፈለልንን መሥዋዕት ካልተቀበልን፥ እያንዳንዳችን ለኃጢአታችን የሞትን መሥዋዕት እንከፍላለን። እግዚአብሔር የሚቀበለው ሌላ መሥዋት፥ ወይም ሥርዓት፥ ወይም ሃይማኖታዊ ተግባር የለም። የዕብራውያን ጸሐፊ፥ «እንዲህ ያለውን ታላቅ መዳን ቸል ብንለው እንዴት እናመልጣለን?» (ዕብ. 2፡3) ሲል አስጠንቅቆናል።

ኢየሱስ ከክፉ መናፍስት ጋር ካደረጋቸው ግድድሮች ምን እንማራለን? በኃጢአት ላይ ያለውን ቁጣና ቅድስናውን ለየት ባለ መንገድ እንመለከታለን። እንዲሁም፥ በአጽናፈ-ዓለሙ ሁሉ ላይ ያለውን ሉዓላዊ ሥልጣን እንመለከታለን። ከእነዚህ ግድድሮች ኢየሱስ የመናፍስት ሁሉ ጌታ እንደ ሆነ ልንመለከት እንችላለን።

ያኔም ሆነ ዛሬ ከቅድስናውና ከእግዚአብሔርነቱ የተነሣ፥ ክፉ መናፍስት በኢየሱስ ክርስቶስ ይሸበራሉ። አጋንንት በትክክል የእግዚአብሔር ቅዱሱ እንደ ሆነ ገልጸዋል (ማር. 1፡24፤ ሉቃ. 4፡34)። በብሉዲ ኪዳን፥ እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ራሱን እንደ ቅዱሱ አድርጎ ገልጾአል [መዝ. (71)፡22፤ (89)፡18፤ ኢሳ. 1፡4፤ 5፡19፤ 10፡20፤ ሆሴ. 11፡9]። ከዚህ ውስጥ ለዛሬ ዘመን የሚስማማ አንድ አስፈላጊ ተዛምዶ እናገኛለን። ይኸውም አንድ ሰው ከእንግዲህ የሰይጣንን ጥላቻ ወይም የቅድመ-ትውልድ መናፍስትን ቁጣ መፍራት አያስፈልገውም። ኢየሱስ ክርስቶስ፥ መላእክትን ሁሉና መንፈሳዊ ፍጥረታትን ጨምሮ፥ ሁሉንም ነገር ፈጥሮአል (ቆላ. 1፡16)። እርሱ በእነዚህ ሁሉ ላይ ጌታ ነው። እርሱ ለጸሎት ምላሽ በመስጠት፥ ሕዝቡን ከሰይጣንና ከክፉ መናፍስት ጥቃቶች

ነፃ ለማውጣት ከፍተኛ ፈቃደኛነትና ችሎታ አለው [መዝ. (50)፡15 ፤ 2 ተሰ. 3፡3]። ክፉ መናፍስት ሁሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚገዙ መረዳት አስፈላጊ ነው (ሉቃ. 4፡34)። እርሱ አምላካቸው ሲሆን፥ ወደፊትም የመጨረሻ ዳኛቸው ይሆናል።

ኢየሱስ፥ «ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ» ብሏል (ማቴ. 28፡18)። በአጽናፈ-ዓለሙ የሚገኙ መናፍስት ሁሉ ከሥልጣኑ ሥር ናቸው። መልካሞቹ በፍርሃትና በአክብሮት ያገለግሉታል [መዝ. (103)፡20–21]። ክፉዎቹ ደግሞ እንደሚፈርድባቸውና ለኃጢአታቸውና ለዓመፃቸው እንደሚቀጣቸው ስለሚያውቁ፥ ይፈሩታል፤ በህልውናውም ፊት ይንቀጠቀጣሉ (ማቴ. 8፡29፤ ያዕ. 2፡19)። ኢየሱስ ጌታህ ከሆነ፥ የሌሎችን መናፍስት ኃይል መፍራት አያስፈልግህም። እግዚአብሔር ከእርሱ በቀር ማንንም እንዳናገለግል ይፈልጋል (ማቴ. 4፡10፤ ዘዳ. 6፡13)። ለቅድመ-ትውልዳዊ መናፍስት በፍርሃት መገዛት አላስፈላጊ ብቻ ሳይሆን፥ ስሕተትም ጭምር ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ በምንሆንበት ጊዜ፥ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመሆን እርሱ ጌታችንና አምላካችን ይሆናል።

የእግዚአብሔር ፍትሕና ምሕረት

ኢየሱስ እግዚአብሔርን እንዴት ገለጸው? እግዚአብሔር ምን ይመስላል?

– እርሱ አንድ ሰው ሴትን በምኞት ከተመለከተ፥ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል ያለ ነው (ማቴ. 5፡28)።

– እርሱ አንዲት ኃጢአተኛ ሴት እግሮቹን በእንባዋ እንድታጥብና በጸጉሮቿ እንድታብስ የፈቀደና ኃጢአቷን ይቅር ያላት ነው (ሉቃስ 7፡36–48)።

የእግዚአብሔር ፍትሕ

እግዚአብሔር ፍትሕ አድራጊ ነው። ፍርዶቹ ሁሉ ሙሉ ለሙሉ ትክክል፥ ተገቢና አድልዎ የሌለባቸው ናቸው። አንድም ቀን ተሳስቶ አያውቅም። አንድም ቀን ተገቢ ያልሆነ ወይም ብልሹ ተግባር ፈጽሞ አያውቅም። እርሱ ኃጢአትን ችላ ብሎ አያልፍም። በዘኍልቁ 14፡18፥ «እግዚአብሔር ታጋሽና ምሕረቱ የበዛ፥ አበሳንና መተላለፍን ይቅር የሚል፥ ኃጢአተኞችንም ከቶ የማያነጻ» ይላል። ወደ ዕብራውያን የተላከው መልእክት፥ «በመላእክት የተነገረው ቃል ጽኑ ከሆነ፥ መተላለፍና

አመለታዘዝም ሁሉ የጽድቅን ብድራት ከተቀበለ፥ እኛስ እንዲህ ያለውን ታላቅ መዳን ቸል ብንለው፥ እንዴት እናመልጣለን?» ሲል በጥያቄ ይሞግተናል (ዕብ. 2፡2–3)።

እግዚአብሔር በግልጽ ክፉውንና መልካሙን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ደጋግሞአል። ክፉ የሆነው የትኛው እንደ ሆነ ይነግረንና ይኮንነዋል። መልካም የሆነውም የትኛው እንደ ሆነ ይነግረንና እንድንከተለው ያበረታታናል። በዓለም ሁሉም ባህል ክፉና መልካም ስለ ሆነው ነገር የራሱ አስተሳሰብ አለው። በማኅበረሰቡ ዘንድ የሚኖረንን ተቀባይነት ስለሚወስኑ፥ ስለ መልካምና ክፉ የሚኖሩን ባህላዊ አስተሳሰቦች እጅግ ጠቃሚ ይመስሉናል። ይሁንና፥ እንደ እውነቱ ከሆነ ዋናው ቁም ነገር እግዚአብሔር ክፉንና መልካምን የሚደነግግበት ሁኔታ ነው። በማኅበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለውንና በእግዚአብሔር ዘንድ የተኮነነውን ተግባር ብንፈጽም፥ በጣም በጣም ከፍተኛ በሆነ ችግር ውስጥ ተዘፍቀናል ማለት ነው። እግዚአብሔር እንደ ክፉ የሚቆጥረውን ተግባር ብንፈጽም፥ እንግዲህ ፍትሐዊ ቅጣት ይጠብቀናል ማለት ነው፤ ይህም ቅጣት ምናልባትም ለልጆቻችን ሊተርፍ ይችላል – ኃጢአታችን ልጆቻችንንም ይጎዳቸዋልና (ዘጸ. 34፡7)። በአንዳንድ ባህሎች፥ ደምን መበቀል እንደ መልካም፥ ብሎም እንደ ጀግንነት ተግባር ይቆጠራል። ይሁንና፥ እግዚአብሔር በቃሉ ሁሉንም የግድያ ዓይነቶች ኮንኖአል (ዘጸ. 5፡17)። እንዲያውም፥ እግዚአብሔር ነፍሰ–ገዳይ በሞት እንዲቀጣ አዟል (ዘፍጥ. 9፡6)።

ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን የሙሴ ሕግጋት ለአድማጮቹ በተነተነ ጊዜ የእግዚአብሔርን ፍትሕ ገልጾአል። ኢየሱስ ምኞትንና ዝሙትን በተመለከተ ስለ ተናገረው አሳብ ልንደነቅና ለመከላከልም እንሞክር ይሆናል። ለእኛ ዝሙት ተግባር ነው፥ ለእግዚአብሔር ግን ስውር የልብ ምኞት ነው። ኢየሱስ አንድ ሰው ሴትን በምኞት ዓይን ቢመለከት፥ በልቡ ዝሙት ፈጽሞአል ብሏል (ማቴ. 5፡28)። እኛ ይህ አግባብነት የጎደለው ፍርድ ነው በማለት አምርረን እናጉረመርማለን። የዚህ ኃጢአት ተሳላፊዎች እንደ ሆንን ስለምናውቅ፥ ይህንኑ ፍርድ እንጠላለን። እውነቱ ግን ሊታይ፥ ፍርዱ ሙሉ ለሙሉ ትክክል ነው። ተግባራት በልብ የተሰወረው ምኞት ውጤቶች ናቸው። እግዚአብሔር የራሳችንን ልብ እንደምናታልል ያውቃል። እርሱ ሁሉንም ስለሚያውቅ፥ በልባችን ውስጥ የሚመላለሰውን በትክክል ያውቃል።

እግዚአብሔር እንደ አንድ ምድራዊ ዳኛ ሁሉ፥ የሰውን ተግባራት አይመረምርም። በቀጥታ ወደ ልባችን ይመለከትና ለባሕርያችን ምክንያቶቹ

ምን ምን እንደ ሆኑ ያውቃል። ስለ ሆነም፥ ፍርዱ በልባችን ዓላማ ዋንኛ ጥያቄዎች ላይ የተመሠረተ ነው። ለምንድን ነው የምናደርገውን የምናደርገው? ለዚህ ጥያቄ እውነተኛውን መልስ የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው። በሰዎች ልብ ውስጥ የሚፈጸመውን የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ በመሆኑ፥ ትክክለኛውን የፍርድ ብያኔ ሊሰጥ የሚችለውም እርሱ ብቻ ህነው። በአጽናፈ-ዓለሙ ሁሉ ብቸኛው ፍትሐዊ ዳኛ እርሱ ነው። አብርሃም፥ «የምድር ሁሉ ፈራጅ በቅን ፍርድ አይፈርድምን?» ብሏል (ዘፍጥ. 18፡25)።

የእግዚአብሔር ምሕረት

መልካም የምሥራች አለ። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ፍትሐዊና ሁሉን አዋቂ በመሆን ኃጢአተኛነታችንን ቢያውቅም፥ መሐሪ አምላክ ነው። መሐሪም በመሆኑ፥ የሚገባንን ቅጣት ሁሉ አይሰጠንም። ዳዊት፥ «እንደ ኃጢአታችን አላደረገብንም፥ እንደ በደላችንም አልከፈለንም» ሲል ጽፎአል [መዝ. (103)፡10]።

ኢየሱስ በፈሪሳዊው ስምዖን ቤት ሳለ ወደ እርሱ የመጣችውን ጋለሞታ ሴት በኃጢአት የተበላሸ ሕይወት ያውቅ ነበር (ሉቃ. 7፡39)። በተጨማሪም፥ ስምዖን የማያውቀውን ነገር ያውቅ ነበር። ሴቲቱ በልቧ ለኃጢአቷ እውነተኛ ጸጸት ገብቷት ነበር። በመሆኑም፥ ታላቅ ምሕረቱን ገለጸላት። ለስምዖንም፥ «ብዙ ያለው ኃጢአቷ ተሰርዮላታል» አለው (ሉቃስ 7፡47)። እግዚአብሔር ወደ ሰው ልብ በማየት፥ የእልኸኝነት ትዕቢት ወይም የንስሐ ትሕትና እንዳለ ይረዳል። እውነተኛ ንስሐ እንዳለ ሲያይም፥ ታላቅ ምሕረቱን ይገልጻል። ንጉሥ ዳዊት ለኃጢአቶቹ በተናዘዘ ጊዜ እግዚአብሔር ያደረገለት ይህንኑ ነው [መዝ. (51)፡1–4]። በመዝሙር (51)፡17 ዳዊት፥ «የእግዚአብሔር መሥዋዕት የተሰበረ መንፈስ ነው፥ የተሰበረውንና የተዋረደውን ልብ እግዚአብሔር አይንቅም» ብሏል።

የንጉሥ ዳዊት ኃጢአት፥ ንስሐና ይቅርታ ታሪክ ስለ እግዚአብሔር ፍትሕ በሚኖረን ግንዛቤ ላይ አንዳንድ መረዳቶችን ይጨምርልናል። እግዚአብሔር መሐሪ በመሆኑ፥ ዳዊት ስለ ኃጢአቱ ከልቡ ተጸጽቶ ንስሐ በገባ ጊዜ ይቅርታ አገኘ [2 ሳሙ. 12፡13፤ መዝ. (32)፡5]። ይሁንና፥ ምንም እንኳ እግዚአብሔር ዳዊትን ይቅር ቢለውም፥ በኃጢአቱ መዘዝ የተነሣ በዳዊትና በቤተሰቡ ምድራዊ ሕይወት ላይ ችግር እንደሚደርስበት ገለጸለት። ከእግዚአብሔር የኃጢአትን ይቅርታ ማግኘት ማለት

ለፈጸምነው በደል የእኛችንን አንቀበልም ማለት አይደለም። አንድ ሰው ሌላውን በመግደሉ ከእግዚአብሔር ይቅርታ ቢያገኝም፥ የሞተውን ሰው ከሞት አያስነሣውም። አንድ ሰው በወሲባዊ ግድፈቱ የተነሣ የኤድስ በሽታ ቢሸምት፥ ከእግዚአብሔር ይቅርታ ማግኘቱ የኤድስን ቫይረስ አይገድለውም። ነቢዩ ናታን ለዳዊት ኃጢአቱን ለማሳመን ባቀረበ ጊዜ፥ ይህንኑ የምድራዊ የኃጢአት ውጤቶች እውነታ አብራርቶለታል (2 ሳሙ. 12:9-11)።

የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ህልውናና አለመለወጥ

ኢየሱስ እግዚአብሔርን እንዴት ገለጸው? እግዚአብሔር ምን ይመስላል?

- እርሱ ከአብርሃም ጋር የተነጋገረና (ዘፍጥ. 18:1-33) ከአይሁድ መሪዎች ጋር ስለ አብርሃም ከመከራከሩ ከ2000 ዓመታት በፊት በምድር ላይ የተመላለሰ ነው (ዮሐ. 8:56-59)

- እርሱመልኩ በተለወጠበት ተራራ ለሙሴ ከመናገሩ ከ1400 ዓመታት አስቀድሞ (ዮሐ. 8:57-59፤ ማቴ. 17:2) ከሚቃጠል ቁጥቋጦ ውስጥ ሆኖ ለሙሴ የተናገረው ነው (ዘጸ. 3:3-14)።

- እርሱ የዳዊት ከተማ በሆነችው ቤተልሔም እንደ መልካሙ እረኛ ከመወለዱ ከ1000 ዓመታት በፊት (ዮሐ. 10:14፤ ሉቃስ 20:41-44)፥ ንጉሥ ዳዊት እንደ እረኛውና እንደ ጌታው ያወቀው ነው [መዝ. (23):1]።

የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ህልውና

እግዚአብሔርን በተመለከተ የአፍሪካ ባህላዊ እምነቶች ተያያዥነት ባለው መልኩ ስለ ዘላለማዊ ህልውናው ይናገራሉ። ዮርባዎች እግዚአብሔርን፥ «ከቶውንም የማይሞት ታላቅ የማይነቃነቅ ዓለት» በማለት ይጠሩታል። ንጎምቤዎች፥ «ዘላለማዊ ደን» ይሉታል። አፍሪካውያን እግዚአብሔርን ዘላለማዊ፥ ጅማሬ ወይም ፍጻሜ እንደሌለው አድርገው መመልከታቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ከተሰጠን መገለጥ ጋር ሙሉ ለሙሉ ይስማማል።

ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ህልውና የገለጸበት መንገድ አንዳንዶቻችንን እጅግ ሊያስገርመን ይችላል። የዮሐንስ ወንጌል፥ «በመጀመሪያ ቃል ነበረ . . . ቃልም እግዚአብሔር ነበረ» በማለት

ይጀምራል (ዮሐ. 1፡1)። በዮሐንስ 1፡14 መሠረት፥ «ቃል» የሚለው ክርስቶስን ያመለክታል። ምንም እንኳ እንደ ማርያም ልጅ ሥጋና ደም የለበሰ ሰው ሆኖ ወደ ዓለም ቢመጣም፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁልጊዜም ነበረ። እርሱ ጅማሬና ፍጻሜ የለውም። ኢየሱስ ለአይሁድ መሪዎች ሲናገር፥ «እውነት እውነት እላችኋለሁ . . . አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ» ብሏል (ዮሐ. 8፡58)። እኛ የኢየሱስን ቃላት መልእክት በሙሉ ልንረዳ ባንችልም፥ እርሱ ይናገራቸው የነበሩ አይሁዶች ግን ሙሉ ለሙሉ ተረድተውት ነበር! በዚህም ኢየሱስ ራሱን ከሚቃጠለው ቁጥቋጦ ውስጥ ሆኖ ለሙሴ እንደ ተናገረው እግዚአብሔር አድርጎ ስላቀረበላቸው፥ ወዲያው ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ (ዘጸ. 3፡13-14)። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከኢየሱስ ጋር ሲከራከሩ አይሁዶች፥ «ስለ መልካም ሥራ አንወግርህም፤ ስለ ስድብ፤ አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለ ማድረግህ ነው እንጂ» ሲሉ መልሰውለታል (ዮሐ. 10፡33)።

በራእይ መጽሐፍ ኢየሱስ ለሐዋርያው ዮሐንስ፥ «አትፍራ፤ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ፥ ሞቼም ነበርሁ እነሆም፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ሕያው ነኝ» ብሏል (ራእይ 1፡17-18)። በዕብራውያን መጽሐፍ ስለ ክርስቶስ፥ «ስለ ልጁ ግን፡- አምላክ ሆይ፥ ዙፋንህ እስከ ዘላለም ድረስ ይኖራል» ተብሎ ተጽፎአል (ዕብ. 1፡8)። በኋላም የዕብራውያን ጸሐፊ፥ «ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው» ብሏል (ዕብ. 13፡8)። ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና ሁልጊዜም የኖረ በመሆኑ፥ በብሉይ ኪዳን ለአብርሃምና ለሙሴ መታየቱ ሊያስደንቀን አይገባም።

ከአይሁዶች ጋር ባደረገው ውይይት፥ ኢየሱስ ለአብርሃም የታየበትን ጊዜ አመልክቷል (ዮሐ. 8፡56-57)። ለአብርሃም የመገለጹ ታሪክ በዘፍጥረት 18፡1-33 ተመዝግቧል። በተጨማሪም፥ በብሉይ ኪዳን ለአዳምና ሔዋን (ዘፍጥ. 3፡8-21)፥ ለቃየን (ዘፍጥ. 4፡4-15)፥ ለኢያሱ (ኢያሱ 5፡13-15)፥ ለማኑሄ (መሳ. 13፡17-22)፥ እና ለሌሎችም በርካታ ሰዎች ታይቷል። በአዲስ ኪዳን፥ ሰዎች ኢየሱስ ማን እንደ ሆነ ከመለየታቸው በፊት አጋንንት በሚገባ ማንነቱን ተገንዘቡ (ማር. 1፡24)።

በብሉይ ኪዳን የክርስቶስ መገለጽ እንደ «ቲዎፋኒስ» ("theophanies") ወይም አካላዊ መገለጽ ተደርጎ ይወሰዳል። ቲዎፋኒ ክርስቶስ እንደ ማርያም ልጅ ሆኖ በምድር ላይ ከመመላለሱ በፊት፥ እግዚአብሔር ለሰዎች በአካል የተገለጸበት ሁኔታ ነበር። በብሉይ ኪዳን

የክርስቶስ ለሰዎች መገለጽ፥ የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ህልውና ያሳየናል። እነዚህን ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን ዘመን የተገለጸባቸውን ሁኔታዎች ስንረዳ፥ በብሉይና በአዲስ ኪዳን መገለጾቹ መካከል ስላለው ልዩነት መጠየቃችን አይቀርም።

በብሉይና በአዲስ ኪዳኑ የክርስቶስ ምድራዊ ህልውና መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት አስፈላጊ ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን አንድ መልአክ ሊያደርግ በሚችልበት ሁኔታ በተለያዩ ጊዜያት ለሰዎች ይገለጽ ነበር። እንዲያውም፥ እንዳንድ ጊዜ በብሉይ ኪዳን ምድራዊ መገለጹ (በመሳፍንት 2፡1-5 እንደ ተመለከተው) «የእግዚአብሔር መልአክ» በሚል መልኩ ሰፍሯል። የሶምሶን አባት ለነበረው ማኑሄ የእግዚአብሔር መልአክ ሆኖ ተገልጾአል (መሳ. 13፡1-23)።

በአዲስ ኪዳን ግን፥ ክርስቶስ ለሰዎች እንዲያው በአጋጣሚ በሰብአዊ አካል አልተገለጸም። ይልቁንም፥ ከሰብአዊት እናት ተወልዶ፥ ሥጋና ደም ለብሶ በገሊላ ሰዎች መካከል ኖሯል። ይህንንም ያደረገው ደኅንነታችንን ለመፈጸም ሲል ነው - ደኅንነታችንን ለመፈጸም በሥጋ መሞት የግድ ያስፈልገው ነበረና። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው» ይላል (ሮሜ 6፡23)። በብሉይ ኪዳን በአካል በተገለጸባቸው ሁኔታዎች ኢየሱስ ምንጩ ሰማያዊ በሆነ አካል ታየ እንጂ፥ ምድራዊውን ሥጋና ደም የለበሰ ሰው አልነበረም።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ በተመዘገበው ምድራዊ ሕይወቱ፥ ኢየሱስ ሥጋና ደም የለበሰ፥ እንዲሁም ከኃጢአት በቀር ማንኛውንም ሰብአዊ ውስንነት የያዘ ሰው ነበር። እንደ እኛው ለማንበብና መጻፍ መማር ያስፈልገው ነበር። መድከምና መተኛት ነበረበት። መራብና መመገብ፥ መሠቃየትና እንደ እኛው መፈተን የሕይወቱ ገጽታዎች ነበሩ (ማር. 1፡13፤ ዕብ. 4፡15)። እርሱ ስለ ኃጢአታችን ሲል በመስቀል ላይ በሥጋ ሞቷል (ዮሐ. 19፡30-33)።

እንደ ሰማያዊ አካል፥ ኢየሱስ እንደ እኛ ሊሠቃይና ሊፈተን ስለማይችል ታላቅ ሊቀ-ካህናችን ሊሆን አይበቃም ነበር (ዕብ. 8፡1)። እንደ ሰማያዊ አካል፥ በሥጋዊ አካል ሊሞትና ለኃጢአት የሞትን ቅጣት ሊከፍል አይችልም ነበር (ዘፍጥ. 2፡17፤ ሮሜ 6፡23)። እንደ ሰማያዊ አካል፥ አዳኛችን ሊሆን አይበቃም ነበር።

በተመሳሳይ ሁኔታ፡ ማንኛውም መልአክ የሰውን ደኅንነት ሊፈጽም አይችልም ነበር፡ ምክንያቱም መላእክት ሰማያዊ አካላት ስለ ሆኑ በሥጋ ሊሞቱ አይችሉም (ሉቃስ 20:36)። ኢየሱስ በፋንታችን ይሠቃይና ይሞት ዘንድ ከሴት ተወልዶ ከሥጋና ደም እንደ ተገኘ ሰው በምድር ላይ መኖር ነበረበት (ዕብ. 2:9፡ 14)። ይህንንም በማድረግ፡ ኢየሱስ ኃጢአታችን በእኛ ላይ ያመጣውን የሞት ቅጣት ከፍሎልናል (ዕብ. 10:10፡ 12፡ 1 ጴጥ. 2:24፡ ሮሜ 8:3)።

ሰው ሊሰማው የሚገባና ከማናቸውም ይልቅ የላቀ ዜና እነሆ፡- ኢየሱስ፡ እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ የሚያወርደውን አስፈሪ ቁጣ በመስቀል ላይ ለእኛ ሲል ተሠቃይቷል። ስለ ሆነም፡ እምነታችንን በእርሱ ላይ ካስቀመጥንና በእምነት ወደ እርሱ ከቀረብን፡ ከቁጣው ልንድንና የዘላለም ሕይወት ተስፋ ሊኖረን ይችላል (ሮሜ 5:1፡ 1 ተሰ. 1:10)።

የእግዚአብሔር አለመለወጥ

ኢየሱስ ከጊዜ ጊዜ በብሉይ ኪዳንና እንደገና ደግሞ በአዲስ ኪዳን መገለጹን አስመልክቶ የእግዚአብሔርን ሌላ አስፈላጊ ባሕርይ ገልጾልናል። እግዚአብሔር አይለወጥም (ሚልክ. 3:6፡ ዕብ. 13:8)። እርሱ ለዘላለም ያው ነው። እግዚአብሔር ዛሬ ከእኛ ጋር እንደ ሆነው፡ ከ4000 ዓመታት በፊት ከአብርሃምም ጋር በባሕርዩና በተግባራቱ ያው ነበር። ዛሬ ከእኛ ጋር እንደ ሆነው፡ ከ3000 ዓመታት በፊት ከንጉሥ ዳዊትም ጋር በባሕርዩና በተግባራቱ ያው ነበር። እንዲያውም፡ ዳዊት እግዚአብሔርን እንደ ዛሬ ክርስቲያን እረኛዬ ብሎ ይጠራው ነበር [መዝ. (23):1፡ ዮሐ. 10:14]። ስለ ሆነም፡ ወደፊትም በባሕርዩና በተግባራቱ እንደማይለወጥብን እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን። ፍቅሩ፡ ርኅራኄው፡ በጎነቱ፡ ፍትሐዊነቱና በኃጢአት ላይ ያለው ጥላቻ ከቶም አይለወጥም። መጽሐፍ ቅዱስ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና፡ ዛሬና ለዘላለም ያው እንደ ሆነ ይናገራል (ዕብ. 13:8)።

ምናልባት ሁልጊዜም አንዳችን በሌላችን ወይም በቤተሰባችን ላይ ልንደገፍ አንችልም ይሆናል፡ ዳሩ ግን ሁልጊዜም በኢየሱስ ላይ ልንደገፍ እንችላለን። እርሱን ሙሉ ለሙሉ ልንታመን እንችላለን። እርሱ ከወንድም ይልቅ የሚቀርብ ጓደኛ ነው (ምሳሌ 18:24)። ስለ ሆነም፡ ታዛዥነታችንና አምልኮአችን ለእርሱ ይገባል። እርሱ ስለማይለወጥ፡

ከቶውንም አይጥለንም ወይም አይተወንም (ዕብ. 13:5-6)። እርሱ ለበጎቹ ሕይወቱን የሰጠ መልካም እረኛ ነው (ዮሐ. 10:14-15)።

ሐ. ከእግዚአብሔር ስሞች ስለ እግዚአብሔር ምን እንማራለን?

በአፍሪካ ባህል፥ ስሞች በጣም አስፈላጊዎች ናቸው። ስሞች ብዙውን ጊዜ የተሰያሚውን ባሕርይ፥ የትውልዱን ሁኔታና የቤተሰብ ሐረጉን በመግለጽ ትርጉም በሚሰጥ መልኩ ይሰጣሉ። የአንድ ሰው ስም ብዙውን ጊዜ ቤተሰቡን፥ ጎሳውን ወይም ነገዳዊ ተዛምዶዎቹን ይገልጻል። ብዙውን ጊዜ ለልጅ የሚሰጠው ስም የአንድን የታወቀ ቅድመ-ዝርያ ባሕርይ ያንጸባርቃል። እንደዚሁም አንድ ሰው ሌላ ማንም የማያውቀው (እርሱ ግን እንደ እውነተኛ ስሙ አድርጎ የሚቆጥረው) ስውር የግል ስም ይኖረዋል። አንዳንድ ሰዎች ይህንኑ የምሥጢር ስም ለሌላ ሰው ከገለጹ፥ በዚያ ሰው ቁጥጥር ሥር የሚወድቁ ይመስላቸዋል። ኢየሱስ ክርስቶስም ከራሱ በቀር ማንም የማያውቀው የምሥጢር ስም እንዳለው መረዳቱ አስገራሚ ነው (ራእይ 19:12)።

መጽሐፍ ቅዱስ ለእግዚአብሔር አያሌ ስሞችን ይሰጣል። እነዚህም ስሞች ስለ እግዚአብሔር ባሕርይና ጠባይ የተለያዩ ነገሮችን ይገልጻሉ። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን ለእስራኤላውያን የሚታወቅበት «ያህዌ» ("Yahweh") የሚለው ስም ነው። ይህ ስም በ«ኒው ኢንተርናሽናል ቨርዥን» እና «ኒው አሜሪካን እስታንዳርድ ባይብል» «ጌታ» ("THE LORD") ተብሎ ተተርጉሞአል። ዕብራውያን ይህንን ስም እጅግ ቅዱስ አድርገው ስለሚቆጥሩ ሊጠሩት አይደፍሩም። ያህዌ የሚለው ስም «መሆን» ከሚለው የዕብራይስጥ አንቀጽ ጋር የተያያዘ ሲሆን፥ «ህልውናው እስኪታወቅ ድረስ መገኘት» የሚል አሳብ ያዘለ ነው። ያህዌ ለሚለው ስም አንደኛው አተረጓጎም፥ እግዚአብሔር ራሱን «የመሆን መነሾ» (ማለትም «ፈጣሪ») አድርጎ እንደ ገለጸ ያሳያል። ሌላው አተረጓጎም ደግሞ «ያለው» የሚል ነው።

ከዚህ ተመሳሳይ በሆነ መገለጥ፥ እግዚአብሔር ራሱን በሚቃጠል ቁጥቋጦ ውስጥ ለሙሴ «እኔ ነኝ» በሚል ስም ገልጾአል (ዘጸ. 3:14)። ይህም ራሱን ሕያው አድርጎ የገለጸበት ነው። ቀደም ሲል እንደ ተመለከትነው፥ ክርስቶስ ለአይሁድ መሪዎች ራሱን በዚህ ስም አስተዋውቋል፦ «አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ» (ዮሐ. 8:58)። በዘጸአት

3፡1-15 የዕብራይስጡ ምንባብ ሙሴን የጠራውና ከሚታጠል ቁጥቋጦ ያነጋገረው ያህዌ (ጌታ) እንደ ሆነ ይገልጻል (ዘጸ. 3፡4፥ 7፥ 15)። እንዲሁም፥ ዘጸአት 3፡1-15 «የእግዚአብሔር መልአክ» በግልጽ እንደ ጌታ የተጠቀሰበት ምንባብ ነው (ዘጸ. 3፡2)።

በዘጸአት 3፡14 «እኔ ነኝ» በሚለው ስሙ፥ እግዚአብሔር እንደ ሥላሴ ሁለተኛ አካል ከመገለጡም፥ በራሱ ህልውና እንደሚኖርና የኃላፊ፥ ያሁን ወይም የወደፊት ጊዜ የሌለው ዘላለማዊ አምላክ መሆኑን አሳውቋል። «እኔ ነኝ» የሚለው የእግዚአብሔር ስም መገለጽ፥ ክርስቶስ በራእይ መጽሐፍ ለሐዋርያው ዮሐንስ በሰጠው መልእክት ራሱን፥ «ያለውና የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ፡- አልፋና ዖሜጋ (የግሪክ የፊደል ገበታ የመጀመሪያና የመጨረሻ ፊደላትን) በማለት ከገለጸበትም ጋር ሊዛመድ ይችላል (ራእይ 1፡8)። በኋላም በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ ኢየሱስ ይህንኑ የራሱን መገለጽ ለዮሐንስ፥ «አትፍራ፤ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ፥ ሞቼም ነበርሁ እነሆም፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ» በማለት አስፋፍቶታል (ራእይ 1፡17-18)።

ጳውሎስ በሮሜ 10፡13 ላይ ኢዩኤል 2፡32ን በጠቀሰበት ጊዜ ያህዌ የሚለውን ስም ለክርስቶስ አውሏል። እንደዚሁም በሮሜ 10፡12-14፥ ጳውሎስ ለደኅንነት የክርስቶስን ስም ለሚጠሩት የኢዩኤል 2፡32ን መልእክት ተጠቅሞአል። ኢዩኤል፥ «የእግዚአብሔርን (የያህዌን) ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል» ሲል ጽፎአል (ኢዩ. 2፡32)።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ የእግዚአብሔር ስሞች አንዳንድ ባሕርያቱን፥ አንዳንድ ሥራዎቹንና ከሰው ልጅ ጋር ያለውን ግንኙነት ይገልጻሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ለእግዚአብሔር የተሰጡ ብዙ ዓይነት ስሞችና ማዕረጎች አሉ። አንዳንዶቹ የግል ስሞች ሌሎቹ ደግሞ ጥምረት የሚታይባቸው ናቸው። በዚህ መጽሐፍ ይበልጥ የሚታወቁትን የእግዚአብሔር ስሞች ብቻ በአጭሩ እንመለከታለን።

የግል ስሞች

- አዳኝ፡- የሚያድን ማለት ነው። በአፍሪካ አንዳንድ የፖለቲካ መሪዎች የሕዝብቸው አዳኞች እንደ ሆኑ ገልጸዋል። ይሁንና፥ ያለው አዳኝ አንድ ብቻ ሲሆን፥ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ኢየሱስን በተመለከተ፥ መልአኩ የግርያም እርሱ ለነበረው ዮሴፍ፥ «እርሱ ሕዝቡን

ከኃጢአታቸው ያድናቸዋል» ብሏል (ማቴ. 1፡21)። ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም የመጣበት ዋንኛ ምክንያት ኃጢአተኞችን ለማዳን ነው (1 ጢሞ. 1፡15)።

- የእግዚአብሔር ልጅ፡- ይህ የክርስቶስ የማዕረግ ስም፥ እንደ ሥላሴ ሁለተኛ አካል ከእግዚአብሔር አብ ጋር በእኩልነት ደረጃ የሚገኝበትን ልዩ ግንኙነት ይገልጻል (ቆላ. 2፡9)። ኢየሱስ ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ በማለት ጠርቷል (ዮሐ. 5፡25፤ 10፡36፤ 11፡4)። አብዛኛዎቹ ሙስሊሞችና አንዳንድ ክርስቲያኖችም ሳይቀሩ ይህንኑ የክርስቶስን ስም በተሳሳተ መንገድ ይረዱታል። ሙስሊሞች እግዚአብሔር ሚስት ስለሌለው፥ ልጅም እንደሌለው በአጽንኦት ይናገራሉ። ትክክል ናቸው። ዋና አሳባቸውም እግዚአብሔር ሰዎች በሚዋለዱበት ዘዴ በመጠቀም ልጅ እንደሌለው ነው።

አንዳንድ ክርስቲያኖችም እንኳ በዚህ የክርስቶስ የማዕረግ ስም ግራ ተጋብተዋል፤ ይህም የሆነው በአንዳንድ በኩል የኒቂያ ጉባኤ ከተጠቀመበት ቃል የተነሣ ነው። የጉባኤው መግለጫ ክርስቶስ «ከዓለማት ሁሉ በፊት ከአብ የተወለደ» መሆኑን ይገልጻል። «መወለድ» የሚለው የተወሰደው በዮሐንስ 1፡18 እና 3፡16 «ሞኖጂነስ» ከሚለው የግሪክ ቃል ነው። ሞኖጂነስ የሚለው ቃል በእነዚህ ሁለት ጥቅሶች ውስጥ «ልዩ» ወይም «ከዓይነቱ ብቸኛ» የሚል ትርጉም አለው። ይህ ቃል ምናልባት «ምትክ የሌለው አንድ ብቸኛ» ተብሎ በተተረጎመበት «ኒው ኢንተርናሽናል ቨርዥን» መጽሐፍ ቅዱስ ከሁሉም በተሻለ ሁኔታ ተገልጾአል። በሌላ አባባል፥ በአጽናፈ-ዓለሙ «የከብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ (የእግዚአብሔር)» የመሆን ልዩ ስፍራ ያለው ኢየሱስ ብቻ ነው (ዕብ. 1፡3)። በኢየሱስ ዘመን የነበሩ አይሁዶች የዚህን ስም ትርጉም ተረድተው ነበር - የሰው ልጅ የአባቱን ባሕርይ እንደሚይዝ ሁሉ፥ የእግዚአብሔርም ልጅ የእግዚአብሔር ባሕርይ ያለው እንደ ሆነ። ስለ ሆነም፥ አይሁዶች ሊገድሉት ፈለጉ፤ ምክንያቱም «እግዚአብሔር አባቴ ነው ስላለ» (ዮሐ. 5፡18)።

- የሰው ልጅ፡- ይህ በፍጥረታት ሁሉ ሊመለክና በሕዝቦች፥ ቋንቋዎችና ወገኖች ሁሉ ላይ ሊገዛ በዘመናት የሸመገለው ሆኖ ለቀረበው (እግዚአብሔር አብ) የተሰጠ የብሉይ ኪዳን ስም ነው (ዳን. 7፡9-14)። ኢየሱስ ይህንን ስም በወንጌላት ውስጥ ከማንኛውም ሌላ ስም በበለጠ ለራሱ ተጠቅሟል። በዮሐንስ 5፡27፥ ኢየሱስ ፍርድ ሁሉ ለእርሱ

እንደሚሰጥ ገልጾአል፤ ምክንያቱም እርሱ የሰው ልጅ ሲሆን፥ ይህም ምናልባት በዳንኤል መጽሐፍ ውስጥ የሚገኘውን ምንባብ የሚያመለክት ይሆናል።

- ቅዱሱ፡- ይህ እግዚአብሔር በኢሳይያስ 10፡17 እንደ ተጠቀሰው ቅዱስ ባሕርዩን ለመግለጽ፥ ራሱን ለእስራኤል ያስተዋወቀበት ስም ነው። አጋንንት እንኳ እግዚአብሔርን በዚህ ስም መጥራታቸውን መረዳቱ ከፍተኛ ዋጋ አለው (ሉቃስ 4፡34)።

- ሁሉን ቻይ፡- በብሉይም ሆነ አዲስ ኪዳን እግዚአብሔር ራሱን የማይዘለቅ ብርታት ያለው ሁሉን ቻይ አምላክ አድርጎ ገልጾአል (ዘፍጥ. 17፡1፥ ራእይ 1፡8)።

- የእግዚአብሔር ቃል፡- ኢየሱስ ነቢያት እንዳደረጉት የእግዚአብሔርን ቃል መናገር ብቻ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔር ቃል ተብሎ ተጠርቷል (ዮሐ. 1፡1፥ 14፤ ራእይ 19፡13)። እርሱ በሙስሊም ቁርዓን ውስጥ እንኳ በዚህ ስም ይታወቃል (ሱረቱ 4፡171)።

- የነገሥታት ንጉሥ፡- ሐዋርያው ዮሐንስ በራእዩ ውስጥ ኢየሱስን የዚህን ዓለም ገዥዎች ሁሉ እንደሚገዛ ንጉሥ አይቶታል። እርሱ የጌቶች ጌታና የነገሥታት ንጉሥ ነው (ራእይ 19፡16)። በኤፌሶን 1፡20-22 እና ቆላስይስ 1፡16 መሠረት፥ ሉዓላዊነቱ በሰብአዊ ነገሥታትና ጌቶች ላይ ብቻ ሳይሆን በመንፈሳዊ ዓለም ውስጥ የሚገኙትን ገዥዎችና መላእክትም ይጨምራል። ኢየሱስ የሁሉም ጌታ ነው (የሐዋ. 10፡36)!

- አማኑኤል፡- ይህ «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር» የሚል ትርጉም ያለው የብሉይ ኪዳን ስያሜ ነው (ኢሳ. 7፡14)። ይህ ስም የእግዚአብሔርን በኢየሱስ ክርስቶስ በተሠገዎ ("incarnation") መገለጥ ይመሰክራል። በክርስቶስ እግዚአብሔር በሰዎች መካከል መጥቶ ኖረ (ዮሐ. 1፡1፥ 14፥ 18)።

- የምድር ሁሉ ፈራጅ፡- ይህ አብርሃም በዘፍጥረት 18፡25 እግዚአብሔርን የጠራበት ስም ነው። ይህም ሥልጣን በዮሐንስ 5፡22፥ 27 እና በጳውሎስ በሐዋርያት ሥራ 17፡31 ክርስቶስን እንደሚመለከት አጽንኦት ተሰጥቶታል።

- የእግዚአብሔር በግ፡- ይህ መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ የጠራበት ስም ነው (ዮሐ. 1፡29፥ 36)። ይህ ስም እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ የሚያወርደውን ቁጣ ለመመለስ (ለማስተሰረይ) ክርስቶስ በእግዚአብሔር የተሰጠውን የመሥዋዕት በግ የመሆን ተልእኮ መፈጸሙን ይገልጻል። ይህም ተግባሩ ቀደም ሲል እግዚአብሔር በግብፅ ላይ ካወረደው ፍርድ እስራኤላውያንን በታደገበት የፋሲካ በግ ደም ተምሳሌትነት፥ተገልጾአል (ዘጸ. 12፡3-13 እና 1 ቆሮ. 5፡7)።

- የይሁዳ ነገድ አንበሳ፡- ይህ ክርስቶስ ወደዚህች ዓለም እንደ ድል-ነሺ ንጉሥ በሚመለስበት ጊዜ፥ የሚኖረውን ንጉሣዊ ኃይል ለመግለጽ የቆመ ተምሳሌታዊ የማዕረግ ስም ነው (ራእይ 5፡5)። ስለ ሆነም፥ ይህ በማቴዎስ 24፡30 የሰው ልጅ ሆኖ ከተገለጸበት ስም ጋር የተያያዘ ነው (ዳን. 7፡13)። ስሙ ከይሁዳ ነገድ የመምጣቱን ሰብአዊ የዘር ሐረግ ያንጸባርቃል። መጀመሪያ ክርስቶስ እንደ እግዚአብሔር በግ፥ የንጽሕና፥ የደካማነትና የመሥዋዕት ተምሳሌት ሆኖ መጥቷል። በሁለተኛው ግን ክርስቶስ እንደ ይሁዳ አንበሳ፥ የሥልጣንና የማይነቃነቅ ኃይል ተምሳሌት ሆኖ ይመጣል። ብዙውን ጊዜ አንበሳ «የእንስሳት ንጉሥ» በመባል ይታወቃል።

- ድንቅ መካር፡- ይህ ስም በብሉይ ኪዳን የተሰጠና የተገለጸ ነው (ኢሳ. 9፡6፤ ምሳሌ 8፡13-19)። ለአማኞች ምክር፥ ማጽናኛና ጥበብ የመስጠቱ አገልግሎት በመንፈስ ቅዱስ ይከናወናል (ዮሐ. 14፡26፤ 16፡13፥ 14፤ ያዕ. 1፡5)።

- መሐሪ (ሩኅሩኅ)፡- ጌታ ለሙሴ አሥሩን ትእዛዛት በሰጠ ጊዜ ይህንኑ ስም ገለጸለት (ዘጸ. 34፡6-7)። ይህ በኢየሱስ ክርስቶስ በፍጹምነት የተገለጸውን የእግዚአብሔርን ታላቅ ርኅራኄ ለሰው ልጆች ያሳያል። መዝሙር (145)፡8-9፥ «እግዚአብሔር ሩኅሩኅና መሐሪ ነው፥ ከቁጣ የራቀ፥ ምሕረቱም የበዛ ነው፤ እግዚአብሔር ለሚታገሡት ቸር ነው። ምሕረቱም በሥራው ሁሉ ላይ ነው» ይላል።

- እኔ ነኝ፡- ይህ ስም እግዚአብሔር ሙሴን እስራኤላውያንን ከግብፅ ባርነት እንዲያወጣ በላከው ጊዜ ራሱን ዘላለማዊ አምላክ አድርጎ በማስተዋወቅ ለሙሴ የሰጠው ነበር (ዘጸ. 3፡14)። ይህ ስም የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ህልውናና አለመለወጥ ያንጸባርቃል።

- አልፋና ዖሜጋ፡- እነዚህ የግሪክ ቋንቋ የፊደል ገበታ የመጀመሪያና የመጨረሻ ፊደላት ናቸው። ኢየሱስ ዘላለማዊ ህልውናውን በማሳየት፥ ራሱን በእነዚህ ቃላት አማካኝነት ለዮሐንስ ገልጾአል (ራእይ 1፡8 እና 22፡13)። በተመሳሳይ ምንባብ፥ ኢየሱስ ራሱን እንደ ሁሉን ቻይና ጌታ አምላክ አድርጎ ገልጾአል።

- መሢሕ፡- ይህ «የተቀባ» የሚል ትርጉም ያለው ማዕረግ ነው። በሴፕቱዋጀንት መጽሐፍ ቅዱስ ይህ ማዕረግ «ክርስቶስ» ማለትም «መሢሑ» ተብሏል። ስለ ሆነም «ክርስቶስ» ስም ሳይሆን ማዕረግ ነው። «ክርስቶስ» የሚለው ማዕረግ «መሢሑ» ማለት ነው። በመሆኑም፥ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚለው ስም «ክርስቶስ የሆነው ኢየሱስ» ወይም «መሢሑ ኢየሱስ» የሚል ትርጉም ይኖረዋል። መሢሑ፥ አይሁዶች ከፖለቲካ ባርነትና ጭቆና ያወጣቸው ዘንድ እንደሚመጣ ሲጠባበቁት የቆዩት ነው። ኢየሱስ ይኸው ፖለቲካዊ መሢሕ እንደሚሆን በማሰብ፥ ብዙ ሕዝብ ከፋሲካ በፊት በዋለው እሑድ ሊያነግሡት ፈለጉ (ዮሐ. 12፡13-14)፤ ይሁንና፥ የፖለቲካ ጥማታቸውን ባለማርካቱ በኋላ ተነሡበት (ማር. 15፡13-15)።

- የሰላም አለቃ፡- ይህ ማዕረግ እግዚአብሔር የሰላም ምንጭ መሆኑን ይገልጻል። ይህም ሦስቱ የሥላሴ አካላት በተገለጹበትና (ኢሳ. 9፡6) የወደፊቱ የክርስቶስ ምድራዊ ሰላማዊ አገዛዝ በተተነበየበት ምንባብ (ኢሳ. 9፡7) ለኢሳይያስ ተገልጾለታል።

- መልካም እረኛ፡- ይህ ስም በእግዚአብሔር ሕዝብ ዘንድ እጅግ ተወዳጅ ከሆኑት አንዱ ነው። ልክ ዛሬ ክርስቲያኖች እንደ መልካም እረኛቸው አድርገው እንደሚያውቁት (ዮሐ. 10፡14)፥ ንጉሥ ዳዊትም ክርስቶስን እንደ እረኛው አውቆት ነበር [መዝ. (23)፡1]። እርሱ ለበጎቹ ግድ መሰኘት ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ሕይወቱን ለበጎቹ ሲል አሳልፎ የሰጠ ነው (ዮሐ. 10፡2-11)።

- የክብር ንጉሥ፡- አስፈሪው፥ የከበረው፥ ሁሉን ቻዩና ዳግም የሚመለሰው መሢሕ የክብር ንጉሥ ተብሎ ተጠርቷል [መዝ. (24)፡7]። ወደፊት ዳግም የኢየሩሳሌምን ደጆች በድል ይሻገራል [መዝ. (24)፡8-10]።

የጥምረት ስሞች

በብሉይ ኪዳን ያህዌ የሚለው የእግዚአብሔር ስም ከሌላ ቃል ጋር በመያያዝ፥ ጥምር ስም የሰጠባቸው አጋጣሚዎች በርካታ ናቸው። እነዚህም ጥምር ስሞች ባሕርዩን ይገልጻሉ።

- ያህዌ-ኤሎሂም፡- «እግዚአብሔር አምላክ (አምላኬ)» (ዘፍጥ. 2፡7)።

- ያህዌ-ይርኤ፡- «እግዚአብሔር ያዘጋጃል» (ዘፍጥ. 22፡13-14)።

- ያህዌ-ጽድቀኑ፡- «እግዚአብሔር ጽድቃችን» (ኤር. 23፡6)።

- ያህዌ-ራያ፡- «እግዚአብሔር እረኛዬ» [መዝ. (23)፡1]።

- ያህዌ-ራፋ፡- «እግዚአብሔር ፈዋሽ» (ዘጸ. 15፡26)።

- ያህዌ-ሻሎም፡- «እግዚአብሔር ሰላም» (መሳ. 6፡24)።

- ያህዌ-ንሲ፡- «እግዚአብሔር ዓላማዬ» (ዘጸ. 17፡15)።

ሌሎች የጥምረት ስሞች እግዚአብሔርን ለማመልከት የሚያገለግለውን ቃል (ኤል) ከሌላ ቃል ጋር ያጣምራሉ።

- ኤል-ሻዳይ፡- ሁሉን ቻይ አምላክ (ዘፍጥ. 17፡1)።

- ኤል-ኤሊዮን፡- ልዑል እግዚአብሔር (ዘፍጥ. 14፡18)።

- ኤል-ሮኢ፡- የሚያይ አምላክ (ዘፍጥ. 16፡13)።

- ኤል-ኦላም፡- ዘላለማዊ አምላክ (ዘፍጥ. 21፡33)።

ማጠቃለያ

ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል የገለጸ ሰው ነው። ኢየሱስ ሰው የሆነ አምላክ ነው። እርሱ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ነው። የእግዚአብሔርን ባሕርያት ለመረዳት ከፈለግን፥ በኢየሱስ ሕይወትና ሥራዎች ውስጥ በይፋ ተገልጸው ልንመለከት እንችላለን። ኢየሱስ ሁሉን የሚችል ኃይል የሚጠይቁትን ተአምራት፥ ለምሳሌ እንደ የዓይነ-ስውርን ዓይኖች ማብራት፥ በውኃ ላይ መራመድና ሙታንን ማስነሣት የመሳሰሉትን በመሥራት፥ የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት ገልጾአል። ለሰርጉ በዓል ውኃን ወደ ወይን ጠጅ በመለወጥ፥ ለብዙ ሕዝቦች እንጀራና

ዓላ በማዘጋጀትና ለደቀ መዛሙርቱ እጅግ ብዙ ዓላዎችን እንዲይዙ በመርዳት፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ አሳይቷል። በሰዎች፥ በተፈጥሮና በመናፍስት ዓለምም ላይ ሳይቀር በነበረው ተቆጣጣሪነት፥ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት አሳይቷል። የሳምራዊቷን ሴት ሕይወት ምሥጢር ዝርዝር ጉዳዮችና ድህዪቱ መበለት ከሙዳይ ምጽዋቱ ላይ የጣለችውን ገንዘብ ትክክለኛ ቁጥር በመናገሩ፥ የእግዚአብሔርን ሁሉን አዋቂነት ገልጾአል።

ለድሆች፥ ለበሽተኞችና ለተቸገሩ ሰዎች ባደረጋቸው ህልቆ-መሳፍርት በሌላቸው የምሕረትና የፈውስ ተግባራቱ የእግዚአብሔርን ርኅራኄና መልካምነት ገልጾአል። ከእነዚህም ተግባራቱ ለምጻሞችን ማንጻት፥ አካለ-ስንኩላንንና ሽባዎችን መፈወስ፥ የድህዪቱን መበለት ብቸኛ ልጅ ከሙታን ማስነሣት ይገኙበታል። በምድር ላይ ከእርሱ በቀር ሌላ ሰው ያልሞከረውን ፍጹምና ከኃጢአት የጸዳ ሕይወት በመኖር፥ የእግዚአብሔርን ቅድስና አሳይቶናል። ስግብግብ የቤተ መቅደስ ገንዘብ ለዋጮችን በማጋለጥ የእግዚአብሔርን ፍትሐዊነት አሳይቶናል። የዘመኑን ሃይማኖታዊ ግብዞች ኃጢአት በመጋፈጥና ገንዘብ ለዋጮቹን ከመቅደስ በማስወጣት፥ እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ እንደሚቆጣ አሳይቷል። እግሮቹን በንስሐ እንባዎች ያጠበችውን ጋለሞታ ሴት ይቅር በማለት፥ የእግዚአብሔርን ምሕረት ገልጾአል። ራሱን ከዶ ሌሎችን በማገልገልና በመጨረሻም ሕይወቱንና ነፍሱን በመስቀል ላይ ለዓለሙ ኃጢአት በመስጠት፥ እግዚአብሔር ፍቅር እንደ ሆነ አሳይቷል። በቤተልሔም ከመወለዱ ከ2000 ዓመታት ቀደም ብሎ ለአብርሃም ሲገለጽ፥ በምድር ላይ ለ33 ዓመታት ሰዎችን በማገልገል፥ ከትንሣኤው በኋላ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በመነጋገር፥ እንዲሁም አሁን ለሕዝቡ (በአብ ፊት) ለመማለድና ጸሎታቸውን ለመመለስ ለዘላለም ሕያው ሆኖ በመኖር፥ የእግዚአብሔርን ዘላለማዊነትና አለመለወጥ ገልጾአል።

እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ ያለ ሰው ከቶውንም ታይቶ አያውቅም። እርሱ አምላክ የሆነ ሰው፥ ሰው የሆነ አምላክ ነው። እርሱ በምድር ላይ ለሁሉም ባህል ሕዝቦች የማይታየውንና ዘላለማዊ የሆነውን እግዚአብሔርን የሚገልጽ ሰው ነው።

በምዕራፍ 5 ላይ የተመሠረቱ የመወያያ ጥያቄዎችና መልመጃዎች

1. እግዚአብሔር ለሰው ልጅ በሚሰጠው የፍርድ ተግባር ማንኛውም ሰብአዊ ንጉሥ በማይችለው መንገድ ሙሉ ለሙሉ ፍትሐዊ እንዲሆን የሚያደርገው የትኛው ባሕርዩ ነው?

2. እግዚአብሔር ምሕረቱንና ይቅርታውን የሚያሳየው ለምን ዓይነት ሰው ነው?

3. በሚከተሉት በኢየሱስ ሕይወት በተፈጸሙ ክስተቶች የተገለጹት የእግዚአብሔር ባሕርያት የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ለሳምራዊቱ ሴት በውኃው ጉድጓድ ስላለፈው ኃጢአቷ ሲናገር (ዮሐ. 4፡18)።

ለ. አልዓዛርን ከሞት ሲያስነሣ (ዮሐ. 11፡43-44)።

ሐ. ዓይነ-ስውሩን (ማቴ. 9፡27-30) እና ለምጻሞችን (ሉቃስ 17፡12-14) ሲፈውስ።

መ. ፈሪሳውያንን በግብዝነታቸው ሲኮንን (ማቴ. 23፡1-33)።

ሠ. ገንዘብ ለዋጮችን ከመቅደስ ሲያባርር (ዮሐ. 2፡14-16)።

ረ. የጋለሞታዪቱን ኃጢአት ይቅር ሲል (ሉቃስ 7፡47-48)።

ሰ. ከ2000 ዓመታት በፊት ከአብርሃም ጋር የተነጋገረበትን መቅት ሲጠቅስ (ዮሐ. 8፡56-57)።

4. ክፍሉን ሦስት ወይም አራት አባላት በሚገኙባቸው ቡድኖች ከፋፍል። እያንዳንዱ ቡድን ቢያንስ አንድ ያገባ ሰው እንዳለው አረጋግጥ። እያንዳንዱ ቡድን ልጅ ሊያገኙ ያልቻሉትን ክርስቲያን ባለትዳሮች እንዴት እንደሚመክር ይወያይ። እያንዳንዱ ቡድን፥ የማማከሩ አካል በማድረግ አንድ ወይም ከዚያ የሚበልጡትን የእግዚአብሔርን ባሕርያት መጥቀስና ይህንኑ ባሕርይ ለመግለጽ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማቅረብ አለበት።

5. ኢየሱስ ከነቢይ እንደማይበልጥ ለሚያምን ሙስሊም፥ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ለማሳየት ምን መረጃ ትሰጣለህ?

6. መዝሙር (84)፡11ን እንደ መነሻ ነጥብ በመጠቀም፥ ትዳር የምትናፍቅ ሴተ-ላጤን እንዴት እንደምትመክር ግለጽ።

7. ስለ እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂነትና ሉዓላዊነት በሚናገሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በመጠቀም፥ ውድ ልጅን በቅርቡ በአደጋ ላጣ ለአንድ ሰው

እንዴት እንደምትመክር ግለጽ። እነኝህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶች በዝርዝር አስፍር።

8. ለአንድ አረማዊ አረጋዊ የኢየሱስን ታሪክና አዳኝነት ከነገርኸው በኋላ፥ እርሱ ግን ክርስቶስን ለመከተል ቢፈልግም፥ መናፍስት ሊቆጡትና ቤተሰቡን በበሽታ ሊቀጡ እንደሚችሉ መስጋቱን ይነግርሃል። ለዚህ ሰው ምን ምላሽ ትሰጣለህ? እርሱንስ ለመምከር የትኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ትጠቀማለህ?

9. ኢየሱስ ከቅድመ-ትውልዶች ለምን እንደሚበልጥ በቡድን ተወያዩ።

10. የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነትና ፈቃድ በኢየሱስ የተገለጸባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው?

11. የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት በክርስቶስ ሕይወት ውስጥ የታየው እንዴት ነው?

12. አራት አባላት በሚገኙባቸው ቡድኖች ተከፋፈሉና በክርስቶስ የተገለጸው፥ የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት፥ እንደ ምን በሽታን፥ ክፉ መናፍስትን፥ ጠንቋዮችንና ሌሎች ችግሮችን ለሚፈሩ ሰዎች እገዛ እንደሚያደርግ ተወያዩ።

SUGGESTED FOR FURTHER READING

Green, Michael. Who is this Jesus? London: Hodder, 1991.

McGrath, Alister. Understanding Jesus. Michigan: Zondervan, 1990.

McDowell, J. More than a Carpenter. Eastbourne: Kingsway, 1979.

Morris, Leon. The Lord from Heaven. Leicester: InterVarsity Press, 1995.

Packer, J. I. Knowing God. London: Hodder, 2nd edn 1993.

ምዕራፍ 6

ሰው – ገሸው‌ና ዓመፀኛው

«የነገሮች ሁሉ ለጋሽ የሆነው እግዚአብሔር ዓለምን በውስጧ ከሚገኙ ነገሮች ሁሉ ጋር ፈጠረ። ሰማይን የራሱ የመኖሪያ ስፍራ አድርጎ ፈጠረ። ሰማይ እንዳይወድቅ ለመከላከል፥ ልክ ከብ የጎጆ ቤት በዓምዶች እንደሚደገፍ በዓምዶች አስደገፈ። እግዚአብሔር ፀሐይንና ጨረቃን ከፈጠረ በኋላ፥ ደመናትን ሠርቶ በሰማይ አስቀመጠ። ከዚያም የመብረቅ ምንጭ የሆነውን ትልቅ አውራ ዶሮ ሠራ። አውራ ዶሮው በመልኩ ቀይ ሲሆን፥ የሚቀመጠው በደመናት መሀል ነው። ክንፎቹን በሚያርገበገብበት ጊዜ ሁሉ መብረቅ ይሆናል፤ ኩኩሉ ሲልም ነጎድጓድ ይሆናል።

«እግዚአብሔር ፀሐይን ከፈጠረ በኋላ፥ ‹ፀሐይዋ ለማን ታበራለች?› ሲል ራሱን ጠየቀ። ይህም እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ሰው ለመፍጠር እንዲወስን አደረገው። የተፈጠረው ሰው መናገርና ማየት ስለሚችል፥ የሚያናግረው ሌላ ሰው ያስፈልገው ነበር። ስለ ሆነም፥ እግዚአብሔር ባልደረባ እንድትሆነው የመጀመሪያይቱን ሴት ፈጠረ። ከዚያም፥ በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል መለያየት የሌለበት ግሩም «ወርቃማ ዘመን» ነበር። ከዚያ በኋላ ግን አንድ አስከፊ ነገር ተከሰተ። እነዚህ እግዚአብሔር የሠራቸው የሰው ልጆች እስስት የተባለው ፍጥረት ከምግባቸው እንዲያካፍሉት ያቀረበላቸውን ጥያቄ በተደጋጋሚ ችላ አሉ። ስለዚህም፥ እስስቱ እነርሱን ለመቅጣት በማሰብ ስለ ረገማቸው፥ የሰው ልጆች ለበሽታና ብሎም ለሞት የተጋለጡ ሆኑ።»

ስለ ሰው ልጅ አፈጣጠር ታሪክና ስለ ዘመኑ አሳዛኝ ሁኔታዎች፥ በዚህ መልኩ የሚተርከው አንድ የአፍሪካ ባህላዊ አፈ-ታሪክ ነው። ስለ ሰው አፈጣጠር እውነቱ ምንድን ነው? ሰው ከበሽታ፥ ከኃዘንና ከሞት ጋር የሚታገልባቸው ትክክለኛ ምክንያቶች ምንድን ናቸው? ዓለም በእንዲህ ያለ ታላቅ ጥፋት ላይ የምትገኘው ለምንድን ነው?

ከየት እንደ መጣን፥ ለምን እዚህ እንደምንኖር፥ ሕይወትስ ለምን እንዲህ ያለ ታላቅ ትግል እንደ በዛባት የሚያመለክተው ጥያቄ ሰዎችን በምድር ላይ ከኖሩበት ጊዜ አንሥቶ ግራ ሲያጋባቸው ኖሯል። እግዚአብሔር ግን ለእነዚህ ፍጹም አስፈላጊ ለሆኑ ጥያቄዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምላሽ ሰጥቷል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ፡ ለሚከተሉት

ጥያቄዎች ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎችና እግዚአብሔር በቃሉ አማካኝነት የሰጣቸውን መልሶች እናወዳድራለን፡-

ሀ. እኛ ማን ነን? ከየትስ መጣን?

ለ. ለምን እንኖራለን?

ሐ. ሰዎች በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩት እንዴት ነው?

መ. እውን ሰው ከእንስሳት ይለያል?

ሠ. ሰው ለእግዚአብሔር ባለመታዘዙ ምን ተከሰተ?

ረ. እግዚአብሔር ሰውንና ምድርን በመርገሙ ምን ተከሰተ?

ሰ. ኃጢአት በሰው ሁሉ ላይ የደረሰው እንዴት ነው?

ሸ. ኃጢአተኞች ሆነን የተወለድነው ለምንድን ነው?

ሀ. እኛ ማን ነን? ከየትስ መጣን?

ቺንዶ፡- "ጋርባ፡ ከየት የመጣን ይመስልሃል? ሙስሊምና ክርስቲያን ጓደኞቼ ከረዥም ዘመናት በፊት እግዚአብሔር ሰውን ከምድር አፈር እንዳበጀው ይናገራሉ። ይሁንና፡ በትምህርት ቤት የምንማራቸው መጻሕፍት ሰው ‹ሊዮሉሽን› በሚባል የአዝጋሚ ለውጥ ሂደት ከትናንሽ እንስሳት እንደ መጣ ያስተምራሉ። በሌላ በኩል ደግሞ፡ በመንደሬ የሚገኙ ሽማግሌዎች የሰው ነፍሳት ሰዎች ከመወለዳቸው በፊት እንደ ነበሩና ዝም ብለው ወደ ተለያዩ ሴቶች ማኅፀን ውስጥ እንደሚገቡ ይናገራሉ።"

ጋርባ፡- "የሳንይስ መምህሬ የሆኑት ሚስተር ኢብራሂም፡ መጽሐፍ ቅዱስ ዓለም በስድስት ቀናት እንደ ተፈጠረች ስለሚናገር እንደማያምኑበት ገልጸዋል። ሳይንቲስቶች ዓለም በሚሊዮን በሚቆጠሩ ዓመታት መፈጠሯን እንደ ደረሱበት ተናግረዋል።

"አንድ ቀን ወዳጄ ጴጥሮስ እንዳስብ ያደረገኝን ጥያቄ ለሚስተር ኢብራሂም አቀረበ። የሳይንስ መጽሐፎቻችን እንደሚሉት በእርግጥ ሰው ከአናሳ እንስሳት መጥቷል ብለው ያምኑ እንደ ሆነ ጠየቃቸው። ሚስተር ኢብራሂምም ሳይንቲስቶች ሰዎች ከአናሳ እንስሳት መምጣታቸውን እንዳረጋገጡ መለሱ። ከዚያም ጴጥሮስ መምህሩ ሳይንቲስቶች በቤተ-ሙከራ (ላብራቶሪ) ውስጥ አንዱን እንስሳ ወደ ሌላ ስለ ለወጡበት ሁኔታ

ለክፍሉ ተማሪዎች ምሳሌ እንዲሰጡ ጠየቀ። ሚስተር ኢብራሂም ይህንን ሊያደርጉ አልቻሉም።»

ቺንዶ፡- «እንደሚመስለኝ የመንደሬ ሽማግሌዎች ለዚህ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ አላቸው። ከሕዝባችን አንዳንዶቹ ዘመዶቻቸውን ከሞቱ በኋላ አይተዋል ወይም በሕልም በእነዚህ ዘመዶቻቸው ተጎብኝተዋል፤ ስለ ሆነም መንፈሶቻቸው አሁንም በአቅራቢያቸው አሉ ማለት ነው። ለልጆቻቸው ሊታዩ ከቻሉ፥ በእናት ማኅፀን ውስጥስ ወደ ሕፃኑ ለመግባት ምን ይሳናቸዋል? እነዚህ ሽማግሌዎች እግዚአብሔር ሰብአዊ ነፍሳትን ሁሉ ከረዥም ጊዜያት በፊት እንደ ፈጠረና ከአንዱ ትውልድ ወደ ሌላው በተመሳሳይ ቤተሰብ ውስጥ እንደ ተወለዱ ይናገራሉ። ያንን ነፍስ የያዘው ልጅ ሲሞት፥ ነፍሱ በማኅፀን የሚፀነሰውን ልጅ እስኪያገኝ ድረስ ተመልሶ ወደ መናፍስት ዓለም ይሄዳል። ነፍሱ አዲስ በሚወለደው ልጅ ውስጥ ሌላ ሕይወት ስለሚኖር፥ አንዱ ነፍስ በተመሳሳይ ቤተሰብ ውስጥ ለብዙ ዘመናትና ትውልዶች እየተወለደ ይቀጥላል። ይሁንና፥ የነፍሱ ከፊል አካል በመናፍስት ዓለም ውስጥ ቀርቶ በሕይወት ለሚኖረው ሰው ጠባቂ መንፈስ ይሆናል። ብዙውን ጊዜ ሰውየው የቀድሞ ሕይወቱን አያስታውስም። በተወለደው ልጅ ክፉ መንፈስ የሰብአዊ ነፍስን ስፍራ ከወሰደ፥ አካለ-ስንኩል ወይም የተቃወሱ ወይም መንታ ልጆች ይወለዳሉ።»

ጋርባ፡- «ማን ትክክል እንደ ሆነ እንዴት እናውቃለን?»

ሰዎች ከየት እንደ መጡና ማንነታቸውስ ምን እንደ ሆነ የሚያመለክተው ጥያቄ በአፍሪካ በጣም አስፈላጊ ነው። በአፍሪካ አብዛኛዎቹ ባህላዊ እምነቶች የተማከሉት በሰዎችና ሰዎች በሚኖሩባቸው ማኅበረሰቦች ውስጥ ነው። ባጠቃላይ፥ በአፍሪካ ሕይወት ሰዎችን ያማከለ ነው ልንል እንችላለን። በመሆኑም፥ ባህላዊ እምነቶችም ሰዎችን ያማከሉ ናቸው። በሕይወት የሚኖሩና ከዚህ በፊት የሞቱት ሁሉ ከፍተኛ አስፈላጊነት አላቸው። ስለ ሆነም፥ የሰው ምንጭ ጥያቄ በጣም አስፈላጊ ነው።

በአንዳንድ የአፍሪካ ክፍሎች የቺንዶ መንደር ሽማግሌዎች እምነት ጥብቅ ነው። ከዚህ በፊት የሞተው ሰው መንፈስ ህልውና በባሕርይ ተመሳሳይነትና በልጁ ውስጥ እንደሚኖር ለታመነው ቅድመ-ትውልድ ልጅ በመገኘቱ ይረጋገጣል። አንዳንድ ጊዜ ቅድመ-ትውልዱ ራሱ ለወላጆች ለሚወለደው ልጅ የራሱን ስም እንዲሰጡት በሕልም ይናገራል።

ከመወለዳቸው በፊት የሰው ነፍሳት ስለ መኖራቸው መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? ዘመናዊ ሳይንስ በዚህ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ የሚጨምረው ማብራሪያ ይኖር ይሆን? እነዚህን ጥያቄዎች በመጠኑ ጠለቅ ብለን እንመለከታለን።

በማኅፀን ውስጥ ተፀንሶ ሕይወት ከመጀመሩ በፊት፣ አስቀድሞውኑ የሰው ነፍሳት እንዳሉ የሚያመለክተው አሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካለመገኘቱም በላይ፥ በዘመናዊ ሳይንስም አልተደገፈም። መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ዘመናዊው ሳይንስ የሰው ስብእናና ነፍስ የሚሠሩት በማኅፀን ውስጥ በሚፀነሱበት ጊዜ እንደ ሆነ ያመለክታሉ። በተጨማሪም፥ ዘመናዊ ሳይንስ ለሰው ልጅ ቅድመ-ህላዌ ደጋፊ ሆኖ ለቀረበው መረጃ ምክንያቱን ያብራራል።

በሰው ልጅ ነፍሳት ላይ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን ለመረዳት፥ እግዚአብሔር ሰውን በመጀመሪያ እንዴት እንደ ፈጠረው መረዳት አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሰውን ከምድር አፈር እንዳበጀው ይናገራል (ዘፍጥ. 2፡7)። በዚህ ዓይነት የሰውን ሥጋዊ አካል አበጀ። ከዚያም እግዚአብሔር በፈጠረው ሥጋዊ ሰውነት ላይ «የሕይወትን እስትንፋስ» እፍ በማለቱ ሰው «ሕያው ነፍስ» ያለው ሆነ (2፡7)።

እግዚአብሔር ወደ አዳም ሰውነት ሕይወትን እፍ ባለ ጊዜ፥ የአዳምን ነፍስ ፈጠረ። አዳም ከተፈጠረ በኋላ፥ እግዚአብሔር ሴቲቱን ከወንድ ፈጠረ (ዘፍጥ. 2፡21-22)። ከዚህ ነጥብ በኋላ፥ የወደፊት ሰብአዊ ፍጥረታት በጋብቻ ውስጥ ወንድና ሴት በሚያደርጉት ወሲባዊ ግንኙነት እየተፈጠሩ ወደ ዓለም እንዲገቡ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነበር (ዘፍጥ. 1፡27-28፣ 2፡24፣ 4፡1)። ሳይንቲስቶች በማይክሮስኮፕ በመጠቀም የወንዱ ዘር ("sperm") ከሴቲቱ እንቁላል ጋር በሚገናኝበት ጊዜ የሚከሰተውን ዝርዝር ሁኔታ ሊመለከቱ የቻሉት አሁን በሃያኛው ክፍለ ዘመን ብቻ ነው። ያንን ሂደት ስንረዳ፥ የሰውን ነፍስ ምንጭ እንረዳለን።

አዳምና ሔዋን ከተፈጠሩ በኋላ፥ እግዚአብሔር እንዳይበሉ የከለከላቸውን የዛፍ ፍሬ በመብላት በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ፈጸሙ (ዘፍጥ. 3፡6፥ 11)። የአዳም ኃጢአት መንፈሳዊ ሞት (የእግዚአብሔርና የሰው መለያየት - ዘፍጥ. 3፡10) እና ሥጋዊ ሞት (የነፍስ ከሥጋ መለየትና ይህንኑ ተከትሎ የሚመጣ የሥጋ መውደም - ዘፍጥ. 3፡19) አስከትሏል። እነዚህ ሁለቱም «መለየቶች» ከእግዚአብሔር ቀዳሚ ዓላማ ጋር

የግይስግሙ ናቸው። እርሱ የፈለገው ሰብአዊ ፍጥረታት በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በኅብረት ከእርሱ ጋር እንዲጣመሩና የሰው ሥጋና ነፍስ በአንድነት ተያይዘው እንዲኖሩ ነበር።

ሰው ሲሞት ነፍስ ከሥጋ ይለይና ሥጋ ወደ አፈሩ ይመለሳል (ዘፍጥ. 3፡19)። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፥ ሰው ሲሞትበት ጊዜ የሰው ነፍሳት ከሥጋ ተለይተው በሁለት ቡድኖች እንደሚከፈሉ እንረዳለን። ነፍሳት የሚለዩት በዚህ ሕይወት ከክርስቶስ ጋር ካላቸው ግንኙነት አኳያ ነው (ሉቃ. 23፡40-43)። የክርስቶስ የሆኑ ሰዎች ነፍሳት ወደ ክርስቶስ እቅፍ ይወሰዳሉ [መዝ. (49)፡15፤ ሉቃ. 23፡43፤ 2 ቆሮ. 5፡8)። ከዚያም፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመለስ ይዞአቸው እስከሚመጣ ድረስ ከእርሱ ጋር ይኖራሉ (1 ተሰ. 4፡14)። ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ፥ የክርስቶስ የሆኑት ሰዎች ነፍሳት የትንሣኤ አካል ይለብሳሉ (1 ተሰ. 4፡14-16)። እነዚህ ነፍሳት የትንሣኤን አካላት ከተቀበሉ በኋላ፥ ለዘላለም ይህን የትንሣኤ አካላቸውን እንደ ለበሱ ይኖራሉ (1 ተሰ. 4፡16-17)። ይህ እግዚአብሔር ለዳኑት ሕዝቦቹ ያዘጋጀው ደኅንነት ፍጻሜ ነው (ሮሜ 8፡23)።

የተቀሩት ነፍሳት ግን ሲኦል በሚባል ስፍራ ታስረው ይቆያሉ [ሉቃ. 16፡23፥ 26፤ መዝ. (49)፡14]። በሲኦል ውስጥ ማንነታቸውን ሳይስቱ በንቃት ይቆዩና የመጨረሻውን የእግዚአብሔር ፍርድ በዚያው ስፍራ ይጠባበቃሉ (ዕብ. 9፡27፤ ራእይ 20፡11-13)። በምዕራፍ 13 በይበልጥ ስለ ሲኦል እንነጋገራለን። ስለ ባለጸጋውና አልዓዛር በተነገረው ታሪክ ውስጥ (ሉቃ. 16፡19-31)፥ ምንም እንኳ በሲኦል የነበረው ሀብታሙ ሰው አልዓዛር ተመልሶ ወንድሞቹ ወደ ሲኦል እንዳይመጡ እንዲያስጠነቅቃቸው አጥብቆ ቢፈልግም፥ የእርሱም ሆነ የአልዓዛር ነፍስ የመመለስ ፈቃድ እንዳላገኙ ኢየሱስ በግልጽ አስረድቷል (ሉቃ. 16፡27-31)። ምናልባት ከዚህ ለየት የሚሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አሳቦች ሊኖሩ ይችላሉ። እነርሱን በምዕራፍ 13 እናቀርባለን።

የባለጸጋውና የአልዓዛር ታሪክ፥ የሙታን መናፍስት ወደ ሕያዋን የመመለስ ፈቃድ እንደማይሰጣቸው በሚገባ ይገልጽልናል። የሰው ነፍሳት እንዲኖሩ የተፈቀደላቸው በአንድ ሰው ሰውነት ውስጥ ብቻ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ለሰዎችም ‹አንድ ጊዜ› መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደ ተመደበባቸው» ይላል (ዕብ. 9፡27)። ነፍሳት ከአንድ በሚበዙ

የሰው ሰውነቶች ለመኖር ቢችሉ ኖሮ፥ ከአንድ ጊዜ በላይ ለመሞት ይችሉ ነበር። ይህ ዓረፍተ ነገር የሰው ነፍሳት በዚህ ሕይወት አንድ ጊዜ ብቻ እንደሚኖሩ ግልጽ ያደርጋል። እንዲሁም፥ ከሞት በኋላ የሚከሰተው ቀጣይ ክንዋኔ የእግዚአብሔር ፍርድ እንደ ሆነ ይገልጻል።

ልጅ በማኅፀን ውስጥ ከመፀነሱ በፊት የሰው ነፍሳት ህልውና እንደሌላቸው፥ መጽሐፍ ቅዱስ ሌላም መረጃ ያቀርባል። ዔሳውና ያዕቆብ ከመወለዳቸው በፊት ስለ ነበረው ሁኔታ የሚናገረው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፥ የሰው ነፍሳት ከሰው መፀነስ በፊት ህላዌ እንደሌላቸው ያረጋግጣል። ጳውሎስ፥ ያዕቆብና ዔሳው ከመወለዳቸው በፊት ክፉም ሆነ በጎ ተግባር እንዳልፈጸሙ ይነግረናል (ሮሜ 9፡11)። ይህም የሰው ነፍሳት በኃላፊነት የሚያስጠይቅ ተግባር መፈጸም የሚጀምሩት ከተወለዱ በኋላ መሆኑን ያመለክታል። መጽሐፍ ቅዱስ ለሰዎች ሁሉ ሕይወትንና እስትንፋስን የሚሰጠው እግዚአብሔር እንደ ሆነ ይገልጻል (መክ. 12፡7፤ የሐዋ. 17፡25)። በዘካርያስ 12፡1 የሰውን መንፈስ በውስጡ የሚፈጥረው እግዚአብሔር እንደ ሆነ በግልጽ ተጠቅሶአል። ስለ ሆነም፥ እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ አባቦች የሰው ነፍሳት ከሰው መወለድ አስቀድመው እንደሚኖሩ የሚናገረውን አሳብ ፉርሽ ያደርጉታል። ከመጀመሪያው ወንድና ከመጀመሪያዪቱ ሴት በስተቀር፥ የሰው ነፍሳት አፈጣጠር የሚጀምረው በእናት ማኅፀን ውስጥ ፅንስ በሚፀነስበት ጊዜ ነው።

በታሪክ ፍጻሜ ላይ ክርስቶስ እያንዳንዱን የሰው ነፍስ ከራሱ የትንሣኤ አካል ጋር ያዋህደዋል (ዮሐ. 5፡28-29)። የክርስቲያኖች የትንሣኤ አካላት በራሱ በክርስቶስ የከበረ የትንሣኤ አምሳል ይሠራሉ (ፊልጵ. 3፡20-21)። የሌሎቹ ሰዎች የትንሣኤ አካላት ግን ለኃፍረትና ለዘላለማዊ ጉስቁልና ይሰጣሉ (ዳን. 12፡2፤ ዮሐ. 5፡29)። ስለ ሆነም፥ እያንዳንዱ የሰው ነፍስ ከራሱ ከወንድየው ወይም ከራሷ ከሴትዮዋ ሰውነት ጋር የተያያዘ ፍጻሜ አለው። ነፍስ በዚህ ሕይወት፥ ከሥጋና ደም አካል ጋር የተጋጠመች ስትሆን፥ በሚመጣው ሕይወት ደግሞ፥ ከትንሣኤ አካሏ ጋር ትጋጠማለች። በመሆኑም፥ ለእያንዳንዱ የሰው ነፍስ አንድ ውስን አካል እንዳለ ልብ ልንል ይገባል።

ይህ ሙታን በሚታዩባትና ሰዎች ከሙታን ጋር በሚነጋገሩባት አፍሪካ ብዙ ጥያቄዎችን ያስነሣል። ለእነዚህ «ሙታንን» ለሚገለጹባቸው ሁኔታዎች መጽሐፍ ቅዱስ የሚያቀርበውን ማብራሪያ መረዳቱ አስፈላጊ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ሌሎች መናፍስት (የሰው መናፍስት ሳይሆኑ አጋንንት)

ወደ ሰው ሰውነት ሊገቡና የገቡባቸውን ሰዎች ስብእናና ገጽታዎች ሳይቀር በከፍተኛ ደረጃ ሊለውጡ እንደሚችሉ በግልጽ ያስረዳል (ማር. 5፡2-9)። የሙታንን መታየት ይበልጥ ልናምንበት የምንችለው፥ አጋንንት ራእያዊ መገለጦችን ለሰዎች ሊያሳዩ እንደሚችሉ ስንረዳ ነው (ራእይ 16፡13-14)። የሞቱ ሰዎች ራእያዊ ምስሎች በአፍሪካ የሚዘወተሩትን አጅግ በርካታ ሁኔታዎች ያብራራሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው፥ የሰው ነፍሳት በሞት ከሰውነት ሲለዩ፥ በእግዚአብሔር የሚኖሩባቸው የተወሰኑ ስፍራዎች ይሰጧቸዋል። ስለ ሆነም፥ በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ዕቅድ የሰው ነፍስ ከአንድ የበለጡ የሰው አካላትን እንደማይይዝ አድርገን መደምደም አለብን።

ዘመናዊው ሳይንስ ስለ ሰው ነፍሳት ጅማሬ ምን ይላል?

ዘመናዊው ሳይንስ በሰው ነፍስ ጅማሬና ስብእና ላይ በቂ ግብራሪያ አለው። የሥነ-ሕይወት ሳይንስ ("Biological Science") ብዙውን ጊዜ በልጆችና በወላጆቻቸው ወይም ይበልጥ ራቅ ባሉ ቅድመ-ትውልዶቻቸው መካከል የሚታየውን የገጽታና የባሕርይ መመሳሰል ያብራራል። ሳይንቲስቶች የእያንዳንዱ ሰው ሥጋዊ፥ አእምሮአዊና ስሜታዊ ባሕርያት በሰውዬው ሕያዋን ሕዋሳት ("cells") እምብርት ("nucleus") በሚገኙ የ«ጥንተ-ንጥራዊ ትእዛዛት» ("chemical instructions") ስብስብ ውስጥ እንደ ተካተቱ ለማስረዳት ችለዋል።

እነዚህ ጥንተ-ንጥራዊ ትእዛዛት የሚገኙት፥ እጅግ ጥቃቅን ነገሮችን አጉልቶ በሚያሳይ ማይክሮስኮፕ አማካኝነት በምናያቸው በጣም ቀጫጭን ክሮችን በሚመስሉ ነገሮች ውስጥ ነው። እነዚህም ቀጫጭን «ክሮች» «ክሮሞዞምስ» ("chromosomes") ይባላሉ። እያንዳንዱ ክር ወይም ክሮሞዞም የተጠላለፉ የመሰላል ደረጃዎችን የሚመስሉ የጥንተ-ንጥራዊ ጥንዶች ውስብስብ ገጽታ አለው። የእነዚህ ጥንተ-ንጥራዊ ጥንዶች ቡድኖች «ጂንስ» ("genes") ይባላሉ። እንግዲህ፥ እያንዳንዱ ሰው በእናቱ ማኅፀን ውስጥ በሚፀነስበት ጊዜ ሥጋዊ፥ አእምሮአዊና ስሜታዊ ባሕርያቱን ባመዛኙ የሚወስኑት እነዚህ ጂንስ ናቸው። በሌላ አባባል፥ የሰው ስብእና የሚጀምረው በፅንስ ጊዜ ነው ማለት ነው።

እነዚህ ክሮሞዞሞች በመራባት ሂደት በወንድና ሴት ("sperm & egg") ውህደት አማካኝነት ከትውልድ ትውልድ ስለሚተላለፉ፥ ልጆች

በዚህ ዘመን ከእነርሱ ቀደም ብለው የኖሩትን ቅድመ-ትውልዶች በከፍተኛ ደረጃ መምሰላቸው ልንጠብቀው የሚገባን እውነት ነው። እንዲያውም፥ ሕዋሶቻቸው በወላጆቻቸው ሕዋሶቻቸው ከነበሩ ተመሳሳይ ጥንተ-ንጥራዊ ትእዛዛት (ጂንስ) የተሠሩ በመሆናቸው፥ እንዲህ ዓይነቱን ትውልዳዊ ተመሳሳይነት ሊያሳዩ ይገባል። አንደኛው የጂንስ ስብስብ ከእናት ሌላኛው የጂንስ ስብስብ ከአባት ይተላለፋል። ልጁ ከሁለቱ ወላጆቹ የወረሰውን ባሕርይ ያንጸባርቃል፤ ወላጆቹም ራሳቸው ከእነርሱ በፊት ከነበሩ ወላጆቻቸው ነበር ጂኖቻቸውን ያገኙት።

ሰዎች ከአናሳ እንስሳት በአዝጋሚ ለውጥ እያደጉ እንደ መጡ የሚናገረውስ ፍልስፍና ምን ይላል?

«National Geographic» በኖቬምበር 1985 እትሙ «ጥንታዊው ሰው ሲፈለግ» (The Search For Early Man) በሚል ርዕስ ባወጣው ጽሑፍ ውስጥ የአያሌ ሳይንቲስቶች አሳብ ግጠቃለያ ይገኛል። ከገጽ 574-577፥ በጸሐፊዎቹ አስተሳሰብ ከጦጣ መሰል እንስሳ ዛሬ ወዳለንበት ዘመናዊ የሰው ደረጃ ለመሸጋገር የወሰዱብንን ደረጃዎች የሚያሳይ ሥዕል ቀርቦአል። ይህ ሥዕል ዛሬ በአውሮፓና ሰሜናዊ አሜሪካ ከሁሉም የላቀ እውቀት ኤንዳላቸው የሚታመንባቸውን የበርካታ ምሁራን አሳብ ይዞአል። ይህም የአዝጋሚ ለውጥን ("evolution") ንድፈ-አሳብ በከፊል ያጠቃልላል።

የአዝጋሚ ሂደት ለውጥ፥ ሕይወት በምድር ላይ የተጀመረው ከብዙ ዘመን በፊት በባሕር ውስጥ በአጋጣሚ ጥንተ-ንጥሮች ("chemicals") በመዋሃዳቸው እንደ ሆነ ያስተምራል። ብዙ ሳይንቲስቶች፥ ይህ ከሆነ በኋላ በሚሊዮን በሚቆጠሩ ዓመታት ቀላል የሕይወት መልኮች ቀስ በቀስ እንደ ተፈጠሩ ያምናሉ። ከዚያም በተጨማሪ ብዙ ሚሊዮን ዓመታት ጊዜ ውስጥ፥ እነዚህ የሕይወት መልኮች ቀስ በቀስ በመለወጥ የተለያዩ ቅርፆች ያዙ። በዚህ ንድፈ-አሳብ ትንተና መሠረት፥ እጅግ በጣም ረዥም ጊዜ ከወሰደ በኋላ አንዱ ዓይነት እንስሳ ወደ ሌላ ተለወጠ። በመጨረሻም፥ እንደ ዝንጀሮ ("baboons and gorillas") ዓይነት እንስሳት ታዩ። የሰው ልጆችም ቀስ በቀስ ከእነዚህ ከፍተኛ የእድገት ደረጃ ከደረሱ እንስሳት በቅለው ወጡ። ሥዕሉ የንድፍ ሥራ እንጂ፥ ከፎቶግራፍ እንዳልሆነ ልብ ልንል ይገባል። ይህ የሳይንቲስቶች አሳብ ብቻ ነው። የትኛውም ሳይንቲስት ይህ ሂደት በተግባር ሲከናወን ቆሞ አላየም። ከዚህም በላይ፥ ምንም እንኳ ከሰባ ለሚልቁ ዓመታት ሙከራዎች ቢደረጉም፥ ማንኛውም

ሳይንቲስት በቤተ-ሙከራው ውስጥ እንዲህ ዓይነት ለውጥ ለማየት አልቻለም።

ይህን የአዝጋሚ ለውጥ ሂደት ፅንሰ-አሳብ የሚደግፍ የቤተ-ሙከራ መረጃ እስካልተገኘ ድረስ፣ ለምን ይሆን እጅግ ብዙ ሳይንቲስቶች የአፈጣጠራችን መንገድ ይኼ እንደ ሆነ የሚያምኑት? ለዚህ ጥያቄ አጥጋቢ መልስ አለ። መልሱም ሕይወት ባላቸው ነገሮች መካከል ከሚታየው ከፍተኛ ተመሳሳይነት ጋር ይዛመዳል። «ሻቡን» እና «ጎሪላ» የሚባሉ የዝንጀሮ ዓይነቶች በሰውነት አፈጣጠራቸው ከሰው ልጅ ጋር በጣም ስለሚቀራረቡ፥ ሳይንቲስቶች ሰዎች እያደጉ የመጡት ጎሪላዎችን ከመሳሰሉ እንስሳት እንደ ሆነ ገመቱ። እንዲሁም ደግሞ፥ በሁሉም ሕይወት ባላቸው ነገሮች መካከል በሚገኘው የሕይወት ሂደት ውስጥ ትልቅ ተመሳሳይነት አለ። ለምሳሌ፥ እንስሳት ሁሉ ምግብ ይበላሉ፤ ቆሻሻውን ደግሞ ከአካላቸው ያስወግዳሉ።

ከዚህ በተጨማሪ፥ እንስሳትና ዕፅዋት ቁጥጥር በሚደረግባቸው የግራቢያ ሙከራዎች ("controlled breeding experiments") ለተመሰነ ደረጃ ሊለምዱ እንደሚችሉ የሚያሳዩ ብዙ የላብራቶሪ ሙከራዎች አሉ። ችግሩ፥ ሳይንቲስቶች አንዱን ዓይነት እንስሳ ወይም ተክል ወደ ሌላ ዓይነት ሊለውጡ አለመቻላቸው ነው። እግዚአብሔር በግልጽ ሕይወት ባላቸው ነገሮች ላይ ሥነ-ሕይወታዊ ገደብ አብጅቶአል። ለምሳሌ፥ ውሾች ወደ ፈረስነት ሊለወጡ አይችሉም። ይህን ግርዶሽ ከበቅሎ እንመለከታለን። ወንዱ አህያ ሴቷን ባዝራ ሲያጠቃ፥ ውጤቱ በቅሎ ነው። የዚህ ዓይነቱ ከስተት ቅይጥ-ውህደት ("hybrid") ይባላል። በቅሎዋ የባዝራይቱን የእካል መጠን ከአህያው ጥንካሬ፥ ጽናትና ድንዳኔ ጋር ታዋህዳለች። ይሁንና፥ በቅሎዎች መካን በመሆናቸው አይወልዱም። የዕፅዋት ቅይጥ-ውህደትም ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ውጤት ይሰጣል። ይህም እግዚአብሔር በእያንዳንዱ እንስሳና ተክል ላይ ያስቀመጠው ሥነ-ሕይወታዊ ገደብ እንዳለ ያመለክታል።

የዚህ ገደብ ተዛምዶ በብሉይ ኪዳን ለሰው ልጆች ተሰጥቶ እናያለን። እግዚአብሔር በግልጽ የሰው ልጅ ከእንስሳ ጋር የወሲብ ግንኙነት እንዳያደርግ አዟል (ዘሌ. 18:23)። ይህ ከሆነ፥ እግዚአብሔር ሰውዬውም እንስሳውም እንዲገደል ወስኗል (ዘሌ. 20:15-16)።

የአዝጋሚ ለውጥ ("evolution") አሳቦች እውነት ወይም ውሸት መሆናቸውን እንዴት እናውቃለን? የተፈጥሮ መረጃ ምን ይነግረናል? በመጀመሪያ፥ በመሬት ውስጥ የሚገኘው የእንስሳት አጽም ዘገባ እንደሚያረጋግጠው በተለያዩ ዓይነት እንስሳት አጽሞች መካከል ግልጽ የሆነ ልዩነት አለ። እንግዲህ ኢቮሉሽን እውነት ቢሆን ኖሮ፥ እነዚህ አጽሞች አንዱ የእንስሳ ዓይነት ወደ ሌላው የእንሰሳ ዓይነት በአዝጋሚ ለውጥ ለመቀየሩ በቂ መረጃዎች በሰጡንም ነበር። ይሁንና፥ የዚህ ዓይነቱ በጣም ዘገምተኛ ለውጥ የሚታይበት የአጽም ዘገባ በምድር ላይ አይገኝም። በሁለተኛ ደረጃ፥ ኢቮሉሽን እውነት ቢሆን ኖሮ፥ ቢያንስ በአንዳንድ አጋጣሚዎች ሳይንቲስቶች በቤተ-ሙከራዎቻቸው አንዱን ዓይነት እንስሳ ወይም ተክል ወደ ሌላ የመለወጡን ሂደት ለመድገም በቻሉም ነበር። ይሁንና፥ ይህንን ለማድረግ አይችሉም። በተጨማሪም፥ ኢቮሉሽን ምላሽ የማይገኝላቸው ሌሎች ችግሮችም አሉበት።

በተመሳሳይ እንስሳት ወይም ዕፅዋት ውስጥ አናሳ ለውጦች እንደ ተደረጉ ለማሳየት ካልሆነ በቀር፥ የኢቮሉሽንን ንድፈ-አሳብ በሳይንሳዊ መንገድ ለማስደገፍ በጣም አስቸጋሪ ነው። በመሆኑም፥ የተለያዩ ዓይነት ውሾች ቢኖሩም፥ ሁሳቸውም ውሾች ናቸው። በጣም ብዙ የተለያዩ ዓይነት ወፎች ቢኖሩም፥ ወፎች ከሌሎች ፍጥረታት ሁሉ በጣም የተለዩ ናቸው። የዘፍጥረት መጽሐፍ እንደሚለው፥ እግዚአብሔር እነዚህን የተለያዩ ዓይነት ፍጥረታት በተለያየ ሁኔታ ፈጥሮአል (ዘፍጥ. 1፡24-25)።

በሌላ በኩል ደግሞ በእግዚአብሔር ምሪት በተከናወነ የኢቮሉሽን ዓይነት የሚያምኑ አንዳንድ ክርስቲያኖች አሉ። ይህም የአማንያን ኢቮሉሽን ("theistic evolution") ይባላል። የዚህ ዓይነት አመለካከት ያላቸው ሰዎች፥ በእርግጥ የኢቮሉሽን ሂደት ተግባራዊ ሆኗል ይሉና፥ ዳሩ ግን፥ ኢቮሉሽን እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ለመፍጠር ሆን ብሎ የተጠቀመበት መንገድ እንደ ሆነ ያስረዳሉ። በመሆኑም፥ እኛ የተገኘነው በአጋጣሚ ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ብርቱ ዓላማና ዕቅድ ነው ሲሉ ያብራራሉ። ይሁንና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተዘገበውን የሰው ፍጥረት ታሪክ እንደ ቀጥተኛ እውነት ሳይሆን፥ እንደ ቅኔ ወይም ተረት አድርገው ይተረጉማሉ።

«ለምን እንኖራለን?» ለሚለው ጥያቄ፥ ዓለማዊ የኢቮሉሽን ፍልስፍና አራማጅ የሆነው፥ ከተፈጥሮ አጋጣሚያዊ ለውጦች የተነሣ እንደምንኖር ይነግረናል። የምንኖረው በሚሊዮን በሚቆጠሩ ጊዜያት ከተፈጸሙ ግብታዊ

ሥነ-ሕይወታዊ ለውጦች የተነሣ ነው ይሉናል። በእጭሩ እነዚህ ሳይንቲስቶች ሰው በእግዚአብሔር የመፈጠሩን እውነት ለመቀበል አይፈልጉም።

ዛሬ በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ በሚገኙ አብዛኛዎቹ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች፥ ኢቮሉሽን የጅግራዎች ብቸኛውና ትክክለኛው ንድፈ-አሳብ ተደርጎ ይቀርባል። ይህንን ንድፈ-አሳብ ያቀረብነው፥ ዛሬ እጅግ ብዙ አፍሪካውያን በአውሮፓና በአሜሪካ በመግር ላይ ስለሚገኙ ነው። ከምዕራቡ ዓለም ሰልጥነው የሚመለሱ ብዙ አፍሪካዊ መምህራን የኢቮሉሽንን አሳቦች ለተማሪዎቻቸው እያስተላለፉ ናቸው። በመሆኑም፥ እነዚህን አሳቦች ማወቅ አስፈላጊ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ወንድና ሴት ጅግራ ምን ይላል?

መጽሐፍ ቅዱስ የሰውን አፈጣጠር ሌሎች እንስሳት ሁሉ ከተፈጠሩ በኋላ የተከናወነ ልዩ የእግዚአብሔር ክንውን አድርጎ ይገልጸዋል። በብሉይም ሆነ አዲስ ኪዳን፥ በቀረበው የሰው አፈጣጠር ታሪክ ውስጥ የተመዘገቡ ክስተቶች በቀጥታ እንደ ተፈጸሙ ተደርገው ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የሰውን አፈጣጠር እንደሚከተለው ይገልጻል፡- «እግዚአብሔርም አለ፡- ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር . . . እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው» (ዘፍጥ. 1፡26-27)። በዘፍጥረት ምዕራፍ 2፥ እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ሰው አዳምን እንዴት እንደ ፈጠረው በትክክል የሚገልጽ ይበልጥ ዘርዘር ያለ ታሪክ ይገኛል። «እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ» (ዘፍጥ. 2፡7)።

የመጀመሪያዪቱ ሴት (ሔዋን) አፈጣጠር እንደሚከተለው ተገልጾአል፡- «እግዚአብሔር አምላክም አለ፡- ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፤ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት . . . እግዚአብሔር አምላክም በአዳም ከባድ እንቅልፍን ጣለበት፥ አንቀላፋም፤ ከጎኑም አንዲት አጥንትን ወስዶ ስፍራውን በሥጋ ዘጋው። እግዚአብሔር አምላክም ከአዳም የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራት፤ ወደ አዳምም አመጣት» (ዘፍጥ. 2፡18-22)።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሰውን በምድር ላይ ከሚኖሩ ፍጥረታት ሁሉ በተለየ መንገድ፥ ለተለየ ተግባር፥ ልዩ ፍጥረት አድርጎ እንደ ፈጠረው ይገልጻል። ሰው የአጋጣሚ ውጤት አይደለም። እግዚአብሔር ለመኖራችን ምክንያትና ዓላማ ነበረው።

የባህላዊ ሕዝቦች አብዛኛዎቹ ቡድኖች የሰውን አፈጣጠር በተመለከተ፥ በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ የቀረበው ዓይነት ታሪክ አላቸው። አንዳንድ ጊዜ እነዚህ ታሪኮች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ሊመሳሰሉ፥ በሌላ ጊዜ ደግሞ ይለያሉ። በአፍሪካ በሚገኙ ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔር ሰውን የመፍጠሩ ጉዳይ ባጠቃላይ ግንዛቤ ያገኘ ሲሆን፥ የአፈጣጠሩ ትክክለኛ ዝርዝሮች የሚገኙት ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብቻ ነው።

ለ. ለምን እንኖራለን?

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሰውን በራሱ አምሳልና መልክ እንደ ፈጠረው ይናገራል (ዘፍጥ. 1፡26-27)። ይህ ስለ ማንኛውም እንስሳ ያልተነገረ ነው። በመሆኑም፥ ሰዎች ከእንስሳት ሁሉ የተለዩ ናቸው። በእግዚአብሔር አምሳል የመፈጠራችን እውነታ እግዚአብሔር ለምን እንደ ፈጠረን ለመረዳት ያግዘናል።

በዘፍጥረት 2፡18 እግዚአብሔር፥ «ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም። የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት» ብሏል። ሰው ማኅበራዊ ፍጥረት እንደ መሆኑ፥ ጓደኛ ያስፈልገው ነበር። እንዲሁም እግዚአብሔር ራሱ ከሰው ጋር ኅብረት ለማድረግ ይፈልግ ነበር (ዘፍጥ. 3፡8-9)። ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ስለ ተፈጠረም፥ እግዚአብሔር የሰብአዊ ፍጥረታትን ኅብረት እንደሚፈልግ ልንገምት እንችላለን። ይህ በዔድን ገነት የነበረውን የሰይጣንን ተግባር ያብራራልናል። ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ያመፀ አካል እንደ መሆኑ፥ ከዚህ ከራሱ ተግባር ጋር በሚመሳሰል መልኩ ሰውንም በእግዚአብሔር ላይ በማሳመፅ እግዚአብሔርን ሊጎዳ ፈለገ። እንዲህ ዓይነቱ ዓመፅ እግዚአብሔር ከአዳምና ከሔዋን ጋር የነበረውን የቅርብ ግንኙነት የሚያቋርጥ ነበር። የሚያሳዝነው፥ ደግሞ የተፈጸመውም ልክ እንደዚያው መሆኑ ነው (ዘፍጥ. 3፡8-9)። በክርስቶስ መስቀል ላይ፥ እግዚአብሔር በሰው ልጅና በራሱ መካከል ይህንኑ የተቋረጠ ግንኙነት ለማደስ የወጠነውን ዕቅድ እንመለከታለን (ቆላ. 1:20)።

እግዚአብሔር ልክ ራሱ በአጽናፈ-ዓለሙ ላይ እንደሚገዛው ሁሉ [መዝ. (103)፡19]፥ ሰውም በምድር በፍጥረቱ ላይ እንዲገዛ ዐቅዶ ነበር (ዘፍጥ. 1፡26)። እንደዚሁም ሰዎች በእግዚአብሔር አምሳል ስለ ተፈጠሩ፥ እግዚአብሔር የራሱን ቅድስናና በጎነት እንዲያንጸባርቁ ይፈልግ ነበር። ይሁንና፥ አዳምና ሔዋን ባለመታዘዝ ወድቀው ኃጢአት አደረጉ። ከዚህም የተነሣ፥ የሰው ልጆች ምግባረ-ብልሹዎች ሆኑ። በአንዳንድ መንገዶች በምግባራቸው ይገዙዋቸው ከነበሩት እንስሳት በታች ሆኑ። እንስሳት ሥቃያቸውን ለማየት ወይም ከምድረ-ገጽ ጨርሰው ለማጥፋት ሲሉ ብቻ ሌሎች እንስሳትን አያስጨንቁም፤ አይጎዱምም። አንዳንድ ጠማማ ሰዎች ግን ይህንኑ ያደርጋሉ። እንስሳት የሚዋጉት፥ ምግብ ለማግኘት ሲጥሩ፥ ልጆቻቸውን ሲከላከሉ፥ የጾታ ጓደኞቻቸውን ሲጠብቁ፥ ወይም አንዳንድ ተፈጥሮአዊ ልማድ ለማከናወን በሚፈልጉበት ጊዜ ነው። ሰዎች ግን ከትዕቢት፥ ከጎሰኝነት፥ ከራስ ወዳድነትና ከስግብግብነት የተነሣ፥ በሌሎች ሰዎች ላይ ክፋትን በጥንቃቄና በምቀኝነት ያቅዳሉ። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ እጅግም ክፉ ነው፤ ማንስ ያውቀዋል?» ይላል (ኤር. 17፡9)።

እንስሳት እንደ ሰው ልጆች ክፉውንና መልካሙን ለይተው አያውቁም። ስለ ሆነም፥ እግዚአብሔር ከሰዎች የኃላፊነት ግዴታ የሚጠይቀውን ባሕርይ ሊጠብቅ፥ ከእንስሳት ግን አይጠብቅም። እግዚአብሔር ሰዎችን ለውሳኔዎቻቸውና ለባሕርያቸው በኃላፊነት ይጠይቃቸዋል። ልክ እግዚአብሔር ለሚያደርገው ነገር ፈቃድ እንዳለው ሁሉ፥ ሰዎችም ለሚያደርጉት ነገር የመምረጥ ፈቃድ አላቸው። የእንስሳት ተግባራት በልምዳቸውና በተፈጥሮአቸው ላይ የተመሠረቱ ናቸው። የሰዎች ተግባራት ግን በአስተሳሰባቸውና በውሳኔዎቻቸው ላይ የተመሠረቱ ናቸው።

ሐ. ሰዎች በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩት እንዴት ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሰውን በአምሳሉና በመልኩ እንደ ፈጠረው ይናገራል (ዘፍጥ. 1፡26-27)። ሰው በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረው በምን መልኩ ነው?

እግዚአብሔር መንፈስ እንጂ ሥጋዊ ፍጥረት ስላልሆነ (ዮሐ. 4፡24)፥ የእግዚአብሔር አምሳል ማለት ከእግዚአብሔር ጋር በሥጋ መመሳሰል

አይደለም። በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረው ሥጋዊ ያልሆነው የሰው ክፍል ነው። መስተዋት ከመስተዋቱ ፊት ለፊት የቆመውን ነገር አምሳል ወይም ምስል ነጸብራቅ መልሶ ያንጸባርቃል። እኛም እንደዚሁ የእግዚአብሔርን ባሕርይና ጠባይ ለማንጸባረቅ ተፈጥረናል። የእግዚአብሔር ባሕርይ ምንድን ነው? እናንጸባርቃቸው ዘንድ እግዚአብሔር የሚፈልጋቸው ጠባያትስ የትኞቹ ናቸው?

የእግዚአብሔር አምሳል የእግዚአብሔርን ባሕርይ ሊያንጸባርቅ

የእግዚአብሔር ባሕርይ ፍጹም ቅድስና፥ ጽድቅና በጎነት ነው። ሰው በመጀመሪያ ሲፈጠር ቅዱስ፥ ጻድቅና መልካም እንደ ሆነ ልንገምት እንችላለን፤ መጽሐፍ ቅዱስም ይህንኑ አሳብ ያጠናክራል (ኤፌ. 4፡24)። እግዚአብሔር ሰዎችን የፈጠራቸው ቅድስናውንና በጎነቱን ያንጸባርቁ ዘንድ ነው። የመጀመሪያው ወንድና የመጀመሪያዪቱ ሴት ኃጢአት በማድረጋቸው፥ የሰው ምስል በተሰበረ መስተዋት ውስጥ እንደሚበላሽ ሁሉ፥ ቅዱሱም የእግዚአብሔር አምሳል ረክሶ ተበላሸ። የመጀመሪያው ወንድና ሴት በኃጢአት ስለ ወደቁ፥ የሰው ባሕርይ አሁን ከቅድስና ይልቅ ለብልሹነት ተጋለጠ። ሰዎች የሚሠርቁት፥ የሚያታልሉት፥ የሚዋሹት፥ የሚያመነዝሩት፥ መሲባዊ ግድፈት የሚፈጽሙትና ጦርነት የሚቀሰቅሱትም ለዚህ ነው።

በሰው ልጅ ደኅንነት ውስጥ ከእግዚአብሔር ታላላቅ ዓላማዎች አንዱ በኃጢአት የተበላሸውን የእግዚአብሔርን አምሳል ማደስ ነው (ኤፌ. 4፡24)። ይህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከላዊ ጭብጦች አንዱ ነው። ዘሌዋውያን 20፡7፥ «እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝና ሰውነታችሁን ቀድሱ፥ ቅዱሳንም ሁኑ» ይላል። የዚህ ዓረፍተ ነገር ዓውደ-ንባብ ለአፍሪካ አንድ አስፈላጊ ተዛምዶ አለው። ከዚህ ክፍ ብሎ በሚገኘው ቁጥር፥ እግዚአብሔር፥ «መናፍስት ጠሪዎችንና ጠንቋዮችንም በሚከተል፥ በሥራቸውም በሚያመነዝር፥ በዚያ ሰው ላይ ፊቴን አከብዳለሁ» ይላል (ቁ. 6)። ብዙ የአፍሪካ ክርስቲያኖች ችግር ወይም ቀውጢ ሁኔታ በሚያጋጥማቸው ጊዜ፥ ወደ ሞራ ገላጮች፥ መናፍስት ጠሪዎችና ምትሐት አድራጊዎች ፊታቸውን ለማዞር ይፈተናሉ። እግዚአብሔር እነዚህን ልምምዶች ትተን ወደ እርሱ እንድንመለስ ይጠራናል። ኢሳይያስ፥ «መናፍስት ጠሪዎችንና ጠንቋዮችን ጠይቁ ባሉአችሁ ጊዜ፥ ሕዝቡ ከአምላኩ መጠየቅ አይገባውምን?» ሲል ያስጠነቅቀናል (ኢሳ. 8፡19)።

በዘሌዋውያን 20፡7 መሠረት፥ በችግር ጊዜ ከባህላዊ አዋቂዎች ይልቅ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ የትድስና አካል ነው።

በአዲስ ኪዳን ሐዋርያው ጴጥሮስ፥ «እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለ ተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ» ብሏል (1 ጴጥ. 1፡15-16)። የአዲስ ኪዳን የቅድስና ተሟምዶ፥ «እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን» በሚለው የኤፌሶን 2፡10 መልእክት ውስጥ ይገኛል። ለሌሎች መልካሙን ማድረግ ላግል ቅድስና በጣም አስፈላጊ ከሆኑት ምግባራት አንዱ ነው።

የእግዚአብሔር ክብር በተቀደሰው የመልካምነትና የመልካም ሥራ ባሕርዩ ይታያል። ኢየሱስ፥ «በምድር ላይ አከበርሁህ» ብሏል (ዮሐ. 17፡4)። በሌላ አባባል፥ ኢየሱስ በመልካምነቱና በመልካም ሥራዎቹ የእግዚአብሔርን ቅዱስ ባሕርይ ሙሉ ለሙሉ አንጸባርቋል ማለት ነው። እግዚአብሔር እኛም ይህንኑ እንድናደርግ ይፈልጋል። የፈጠረንም የመልካምነትና የመልካም ሥራ ባሕርያቱን እንድናሳይ ነው። በመሆኑም፥ ሰውን በራሱ አምሳል ፈጠረው። ስለዚህም ነው፥ የዌስት ሚንስተር የአምነት መግለጫ፥ «የሰው ዋንኛ ግብ (ዓላማ) እግዚአብሔርን ማስከበር ነው» የሚለው። ሰው የተፈጠረው ቅዱስ ባሕርዩን በማንጸባረቅ፥ እግዚአብሔርን ለማስከበር ነው። ይህ ለሰው መኖር እጅግ አስፈላጊው ምክንያት ነው። ማንኛውም ሰው በሕይወቱ ሊያደርግ የሚችለው ከሁሉም የሚልቀው ነገር የእግዚአብሔርን ቅዱስ ባሕርይ ማንጸባረቅ ነው።

የእግዚአብሔር አምሳል የእግዚአብሔርን ጠባያት ሊያንጸባርቅ

ቀደም ሲል ከተመለከትነው በተጨማሪም፥ በሰው ውስጥ የሚገኘው የእግዚአብሔር አምሳል በእግዚአብሔር የስብእና ጠባያት ይታያል። እንደ እግዚአብሔር ሁሉ ሰውም የግሉ የሆነ ጠባይ፥ እውቀት፥ ስሜትና ፈቃድ አለው። ሰዎች በእግዚአብሔር አምሳል ስለ ተፈጠሩ፥ ስለ ባሕርያቸውና ስለ ጸባያቸው እግዚአብሔር በኃላፊነት ይጠይቃቸዋል።

ሰው የሚረዳ አእምሮ ስላለው፥ ለማሰብ ይችላል። የእግዚአብሔር አሳቦች ወደር በሌለው ሁኔታ ከእኛ የላቁ ቢሆኑም (ኢሳ. 55፡8-9)፥ ሰዎች በማሰባቸውና በማቀዳቸው እንደ እግዚአብሔር ናቸው። እንደ እግዚአብሔር፥ አሳቦችን በቃላት ለመግለጽ ይችላሉ። በቃላትና ሥዕሎች አማካኝነት መረጃዎችን ከአንዱ ሰው ወደ ሌላው፥ ከአንዱ ትውልድ ወደ

ተጣፍ ያስተላልፋሉ። እንስሳት የተለምዶ ተግባራት ከማከናወን በቀር፥ ይህንን ለማድረግ አይችሉም። እግዚአብሔር የልቡን አሳቦች በመጽሐፍ ቅዱስ በተጻፉልን ቃላት አማካኝነት ለሰው ልጆች አስተላልፎአል።

ሙ. እውን ሰው ከእንስሳት ይለያል?

ሰዎች ለማሰብና ለማቀድ ስለሚችሉ፥ እንደ ከዚህ በፊት ያልነበሩትን መኪናና ኮምፒዩተር የመሳሰሉትን ነገሮች ሊያዘጋጁና ሊሠሩ ይችላሉ። ይህም የሆነው ሰዎች የሁሉም ፈጣሪ በሆነው አምላክ አምሳል ስለ ተፈጠሩ ነው። ሰዎች ከሌሎች ሰዎች ጋር በመነጋገር፥ በማንበብ፥ በማሰላሰል፥ አተኩረው በመመልከትና የቀድሞውን በማስታወስ እውቀት ያገኛሉ። እንደ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ባያውቁም፥ ሰዎች በማጥናት፥ በልምድና ከሌሎች በመማር እውቀታቸውን ሊያሳድጉ ይችላሉ። ከትምህርትና ከልምድ በሚያገኙት እውቀት ብቻ የሰው ልጆች ከሌሎች እንስሳት ሁሉ በከፍተኛ ደረጃ ይለያሉ። በተቃራኒው፥ እንስሳት ከተፈጥሮ ባገኙት እውቀት ብቻ ተወስነው ይኖራሉ። ምንም እንኳ እንስሳት ቢማሩም፥ የመማራቸው ሁኔታ ከሰው ልጆች ጋር ሲነጻጸር በጣም ዝቅተኛ ነው።

ምንም እንኳ ሰዎች እንደ እንስሳቱ ከተፈጥሮ ያገኙአቸው እውቀቶች ቢኖሩአቸውም፥ እንደ እንስሳቱ በተፈጥሮ እውቀት ተወስነው አይኖሩም። ሰዎች በአእምሮአቸው ተጠቅመው በመወሰን፥ የተፈጥሮ እውቀቶቻቸውን ለመቆጣጠር ይችላሉ። በእውቀታቸው ላይ በመመሥረት ውሳኔ ማድረግ ስለሚችሉ፥ ሰዎች በአካባቢያቸው ነገሮችን ልመለወጥ ይችላሉ። እንደ እግዚአብሔር፥ ከዚህ በፊት ያልነበሩትን ነገሮች ለመፍጠር ይችላሉ። ለዚህም ብዙ ምሳሌዎችን መመልከት ይቻላል።

ወፎች በተፈጥሮ እውቀታቸው (በደመ-ነፍስ) ከቅጠሎችና ቅርንጫፎች ጎጆአቸውን ይሠራሉ። እያንዳንዱ ዓይነት ወፍ እውቀቱ እንደሚወስንለት የተወሰነ ዓይነት ጎጆ ይሠራል። እያንዳንዱ ዓይነት ወፍ ሁልጊዜም አንድ ዓይነት ጎጆ ይሠራል። ሰዎች ግን ለማሰብና ከሌሎችም ለመማር ስለሚችሉ፥ አንድ ዓይነት ሕንፃ ወይም ቤት ብቻ በመሥራት ተወስነው አይኖሩም። ሰዎች ተፈጥሮአዊ የደመ-ነፍስ እውቀታቸውን ሳይሆን አሳባቸውንና እውቀታቸውን በመጠቀም፥ ብዙ ዓይነት ሕንፃዎችንና ቤቶችን ይሠራሉ። አንድ ሰው ብዙ የተለያዩ ዓይነት ሕንፃዎችን ሊሠራ ይችላል።

ወፎች ከተፈጠሩበት ሁኔታ አንጻር በአየር ላይ ሊበሩ ሲችሉ፥ ሰዎች ግን ለበረራ አልተፈጠሩም። ይሁንና፥ ወፎችን በመመልከትና የተፈጥሮን ሕግጋት በማጥናት፥ ሰዎች የበረራ መመሪያዎችን በማግኘታቸው፥ በመጨረሻ ከወፎች ከፍ ብለውና በበለጠ ፍጥነት የሚበሩ አውሮፕላኖችን ሠርተዋል። ሰዎች ፈጣሪ በሆነው አምላክ አምሳል በመፈጠራቸው፥ ከዚህ በፊት ያልነበሩትን ነገሮች (ለምሳሌ አውሮፕላን) ሠርተዋል። የሰው ልጆች አዳዲስ ነገሮችን የመፍጠር ችሎታ እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ፥ እግዚአብሔር የባቢሎንን ግንብ ይሠሩ ስለ ነበሩ ሰዎች፥ «ያሰቡትን ሁሉ ለመሥራት አይከለከሉም (አይሳናቸውም)» ብሏል (ዘፍጥ. 11፡6)። ይህ የሰውን ልጅ እውቀትና ኃይል በተመለከተ አስፈሪ አባባል ነው። ሰዎች እግዚአብሔር አይደሉም፤ ሙሉ ለሙሉ ግን በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥረዋል።

በእግዚአብሔር አምሳል እንደ መፈጠራቸው፥ ሰዎች በዙሪያቸው ከሚገኙ ነገሮች ሁሉ የተለዩ ናቸው። ውሳኔዎችን የሚያደርጉባቸው ፈቃዶች አሏቸው። የሚያደርጉትን ለመምረጥ ነፃ ናቸው። ይህ የሚያደርጉትን ነገር የማሰብና የመወሰን ችሎታ ከእግዚአብሔር ለሰዎች የተሰጠ ታላቅ ስጦታ ነው።

ሆኖም ይህ፥ የመምረጥ ነፃነታቸው ሰዎችን ስለ ጠባያቸው በእግዚአብሔር ዘንድ በኃላፊነት ተጠያቂ ያደርጋቸዋል። በዔድን ገነት እግዚአብሔር ለአዳም በአትክልቱ ስፍራ የመደሰትን ነፃነት ሰጠው (ዘፍጥ 2፡16)። እንዲሁም፥ መልካምና ክፉ የምታስታውቀውን የዛፍ ፍሬ ላለመብላት የመታዘዝን ነፃነት ሰጠው (ዘፍጥ. 2፡17)። በመታዘዝና ባለመታዘዝ ነፃነት መካከል ስላለው ልዩነት፥ እግዚአብሔር ለአዳም ባይታዘዝ የከፋ ውጤት (ሞት) እንደሚጠብቀው አስጠነቀቀው (ዘፍጥ 2፡17)።

እግዚአብሔር አዳምን ለውሳኔው ኀተጸቂ አደረገው። አዳም ኃጢአት የሠራው እግዚአብሔርን ላለመታዘዝ ስለ መረጠ ነበር። ኃጢአት ለእግዚአብሔር ፈቃድ አለመታዘዝ ነው። ከአዳም አለመታዘዝ የተነሣ፥ እግዚአብሔር በሰው ልጅና በምንኖርባት ዓለም ላይ መርገምን አወጀ (ዘፍጥ. 3፡17-19)። የሰው ልጆች ለዚህች ዓለም ሁኔታና በሽታ፥ ሞት፥ ኃዘን፥ ጥላቻ፥ ጎሰኝነት፥ ሙርነት፥ ምግባረ-ብልሹነት፥ ወንጀል፥ ጭካኔና

የተፈጥሮ መዛባትን ጨምሮ፥ ለሚኖሩበት ጉስቁልና ሁሉ ሙሉ ለሙሉ ተጠያቂዎች ናቸው (ሮሜ 8፡20-22)።

ሠ. ሰው ለእግዚአብሔር ባለመታዘዙ ምን ተከሰተ?

እግዚአብሔር ለሰው ያለመታዘዝ ውጤቱ ሞት እንደሚሆን ገልጾአል (ዘፍጥ. 2፡17)። ሞት ምን ያህል አስከፊ እንደ ሆነ አዳም ብዙም አልተረዳም ነበር። የሰው አካል ሥጋዊ ሞት የአስከፊው ሞት ቅጣት አንድ ክፍል ብቻ ነው። ሞት በሰው ህልውና ውስጥ ያለውን ማናቸውንም ነገር ይዳስሳል። የሰውን ሥጋ፥ አእምሮ፥ ስሜት፥ ግንኙነቶች፥ ጋብቻ፥ የቤተሰብ ሕይወት፥ ማኅበረሰብ፥ መንግሥትና ግዑዟንም ምድር ሳይቀር ይዳስሳል። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት፥ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ» ይላል (ሮሜ 5፡12)።

በአዳም ኃጢአት የተነሣ የተወሰነው የመጀመሪያው የሞት ፍርድ፥ በሰው ልጆችና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው የቀረበ ግንኙነት መቋረጥ ነበር። አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ለመደበቅ በመሞከር፥ ጥፋተኛ ወንጀለኛነታቸውን አረጋገጡ (ዘፍጥ. 3፡8)። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፥ ሰዎች ከእግዚአብሔር በመሸሽ ላይ ይገኛሉ።

ከእግዚአብሔር በላይ የሚያስፈልገን ማንም የለም። ይሁንና፥ በኃጢአት ምክንያት የበደለኛነት ስሜት ተጭኖን እግዚአብሔርን ስለምንፈራ፥ ከርሱ ለመሸሽ እንጥራለን። ሰዎች ሊጸልዩና እግዚአብሔርም ጸሎታቸውን ሊመልስ ያሻቸዋል፤ ይሁንና፥ ኃጢአታቸውና ዓመፃቸው ከእግዚአብሔር ስለሚለያቸው፥ ጸሎታቸውን አይመልስም (ኢሳ. 59፡1-3)።

አዳም ምን እንዳደረገ እናውቃለን። እግዚአብሔር፥ «ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍ በውኑ በላህን?» በማለት ሲጠይቀው፥ ኃጢአቱን እንዲናዘዝና ይቅርታ እንዲጠይቅ ዕድል ሰጥቶታል (ዘፍጥ 3፡11)። ኃጢአቱን በመቀበል ፈንታ፥ አዳም ከትዕቢቱ የተነሣ ሴቲቱንና እግዚአብሔርን ራሱን ይወቅስ ጀመር (ዘፍጥ. 3፡12)። ዛሬም ሰዎች እንደዚያ ናቸው። ከራሳቸው ኃጢአታዊ ዓመፅና ትዕቢት ለሚመጡ ችግሮች አሁንም ሌሎችንና እግዚአብሔርን ይወቅሳሉ። ኃጢአታቸውን ከመቀበልና ራሳቸውን በእግዚአብሔር ፊት ከማዋረድ ይልቅ፥ ከሌሎች

ጋር መዋጋቱንና መሠቃየቱን ይመርጣሉ። በእርግጥ የሰው ልጅ የወደቀና ኃጢአተኛ ነው። በመሆኑም፥ የምንኖርባትን ምድር ጉስቁልና ወዳጠቃት ምስኪን ዓለምነት ቀይረናታል።

ረ. እግዚአብሔር ሰውንና ምድርን በመርገሙ ምን ተከሰተ?

አዳም እግዚአብሔርን ላለመታዘዝ ስለመረጠና (ዘፍጥ. 3፡6) ዕድልም በተሰጠው ጊዜ ከኃጢአቱ ንስሐ ለመግባት ስላልፈለገ (ዘፍጥ. 3፡12)፥ እግዚአብሔር በሰው ልጅና በምድርም ላይ ርግማንን አወጀ። እንዲሁም፥ የፈተነቻቸውንም እባብ ረግሟል (ዘፍጥ. 3፡14-19)። ዛሬ ሕይወት ለምን እንደዚህ እንደሆነ ለመረዳት፥ የዚህን ርግማን ይዘት መረዳቱ አስፈላጊ ነው።

እግዚአብሔር ሴቶች ልጆች እንዲወልዱ አደረገ (ዘፍጥ. 1፡28)። ርግማኑ ግን የሴቶችን የምጥ ሥቃይ በከፍተኛ ደረጃ አስከትሏል (ዘፍጥ. 3፡16)። እግዚአብሔር ወንዶችን እንዲያርሱና በእጆቻቸው እንዲሠሩ አደረገ (ዘፍጥ. 2፡15)። ርግማኑ ግን በሥራ የሚገኘውን ደስታ አስወግዶ፥ ጣርንና ላብን ተካ። በሴላ አባባል፥ የወንዶችና ሴቶች የተለመደው ሥራ እንዳለ ሆኖ፥ በአስደሳችነት ምትክ ከባድና አሠቃቂ ሆነ። እግዚአብሔር ምድርን የፈጠራት ፍሬን በቀላሉ አትረፍርፋ እንድታበቅል ነበር (ዘፍጥ. 1፡11-12)። ርግማኑ ግን ምድርን የምግብ እህል ለማብቀል ይበልጥ አስቸጋሪ አደረጋት (ዘፍጥ. 3፡17)። ኃጢአት ደስታን ከሰዎች ሕይወት በማስወገዱ፥ ሕይወት በረከት በመሆን ፈንታ መርገም ሆነ።

ሰዎች ብዙውን ጊዜ ለምን እንደ ርዕደ-ምድር፥ የነፋስ ማዕበል፥ የውኃ ሙላት፥ ድርቅ እና ሌሎችም የሰውን ሕይወት የሚያጠፉና ከፍተኛ ሥቃይ የሚያስከትሉ የተፈጥሮ አደጋዎች እንደሚፈጸሙ ከሚያነሡ ጥያቄዎች ጋር ይፋጠጣሉ። ምንም እንኳ መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን ነገሮች በዝርዝር ባይገልጽም፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ጠቅላላው ተፈጥሮአዊ ፍጥረት ኃጢአት በዓለም ውስጥ በመኖሩ ምክንያት በከፍተኛ ደረጃ እንደ ታወከ የሚያስረዳ ጠንካራ አሳብ ይገኛል። ከዘፍጥረት እንደምንረዳው፥ ሰው በኃጢአት እንደ ወደቀ፥ ወዲያውኑ እግዚአብሔር ምድር እንደ እሾህና አሜኬላ የመሳሰሉትን ተዋጊ ነገሮች እንድታመርት አወጀ (ዘፍጥ. 4፡18)። ይህም ያለ ጥርጥር ኢየሱስ ከሰይጣን ሥራ ጋር ያመሳሰላቸውን፥ እንደ

ጊንጥና እባብ የመሳሰሉትን ሌሎች ተናዳፊ ፍጥረቶች የሚጨምር ነው (ሉቃ. 10፡19)።

በሉቃስ 10፡19 ኢየሱስ የሐዋርያቱ ሥልጣን «በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ» እንደሚሆን ሲናገር፥ በተፈጥሮአዊው ዓለም ከዚህም የበለጡ የኃጢአት ውጤቶች እንዳሉ አመልክቷል። በመጽሐፈ ኢዮብ፥ ሰይጣን ኢዮብን ይጎዳ ዘንድ እግዚአብሔር ሲፈቅድለት፥ ሰይጣን በመብረቅ አማካኝነት የኢዮብን በጎችና የበጎቹን እረኞች ፈጃቸው (ኢዮብ 1፡16)። እንዲሁም በከፍተኛ የነፋስ ማዕበል አማካኝነት ልጆቹን ገደላቸው (ኢዮብ 1፡19)። በተጨማሪም፥ በሥጋዊ በሽታ አማካኝነት ኢዮብን በሕመም መታው (ኢዮብ 2፡7)። ኃጢአት በተፈጥሮአዊ ዓለም ላይ ያስከተላቸውን ውጤቶች በማጠቃለል፥ ጳውሎስ «ፍጥረት ሁሉ እስከ አሁን ድረስ አብሮ በመቃተትና በምጥ መኖሩን እናውቃለን» ብሏል (ሮሜ 8፡22)።

የሚያሳዝነው ሐቅ፥ የሰው ልጅ ሰይጣን የቀሰቀሰው ተግባር ተሳታፊ በመሆን በእግዚአብሔር ላይ ማመፁ ነው። ከዚህም የተነሣ፥ እስከ አሁን ድረስ የሰው ልጅ ከተቀረው ፍጥረት ጋር የዚያን አስከፊ ዓመፅ ውጤቶች በመጋፈጥ እየተሠቃየ ነው። በእግዚአብሔር ላይ ከተደረገው ኃጢአት የተነሣ፥ በሽታ፥ ወንጀል፥ ምግባረ-ብልሹነትና ጨቋኝ መንግሥታዊ አገዛዝ፥ የፈራረሱ ቤቶች፥ የሰው ልጆች ጭካኔዎች፥ ጎስቋላነት፥ ጦርነትና ተፈጥሮአዊ አደጋዎችም ጭምር የሕይወታችን ክፍሎች ሆነዋል። አስከፊው እውነታ ይኼ ነው - «የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው» (ሮሜ 6፡23)!

ኢየሱስ የማዳን ሥራው አካል በማድረግ ኃጢአት የገፈፈውን የእግዚአብሔርን በረከት ለመመለስ መጣ (ዮሐ. 10፡10)። ምንም እንኳ ከርስቶስ ዳግም እስኪመለስ ድረስ ፍጥረት በኃጢአት ውጤቶች እያቃሰተ የሚቀጥል ቢሆንም (ሮሜ 8፡21)፥ አሁን ሰዎች በክርስቶስ ሞት የኃጢአታቸውን ይቅርታ ሊያገኙ (ኤፌ. 1፡7) እና ከእግዚአብሔር ጋር ሊታረቁ ይችላሉ (ቆላ. 1፡21-22)። ኢሳይያስ 61፡3፥ እግዚአብሔር «በልቅሶ ፋንታ የደስታን ዘይት፥ በኃዘንም መንፈስ ፋንታ የምስጋናን መጎናጸፊያ» እንደ ሰጠን ይናገራል።

ሰ. ኃጢአት በሰው ሁሉ ላይ የደረሰው እንዴት ነው?

አዳም መልካምና ክፉ ከምታስታውቀው የዛፍ ፍሬ በመብላት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ላለመታዘዝ መረጠ (ዘፍጥ. 3፡6)። በዚህም አለመታዘዙ ምክንያት ቅዱስና ጻድቅ ዳኛ ከሆነው እግዚአብሔር ቅጣት ሊቀበል ተገባው። ምናልባት ለእኛ ግልጽ የማይሆን ነገር ቢኖር የአዳም ኃጢአት ለተቀረው የሰው ዘር እንዴት እንደ ተዳረሰ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ልጅ በሙሉ በአዳም በደልና ኩነኔ ውስጥ እንደ ተካተተ ይገልጻል (ሮሜ 5፡18-19)። ምናልባት አንዳንድ አማኞች የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የተላለፈው አዳም እንጂ እኛ ባለመሆናችን፥ የሰውን ልጅ ሁሉ በአዳም በደልና ቅጣት ውስጥ ማካተቱ የእግዚአብሔርን ፍትሕ-አልባ ብያኔ እንደሚያመለክት ሊያስቡ ይችላሉ። የሰው ልጅ በሙሉ በአዳም ኃጢአት ውስጥ የተካተተው እንዴት ነው?

ይህንን ለመረዳት ለሌላው ጥያቄ ምላሽ ማግኘት አለብን - ኃጢአተኞች የሆንነው ኃጢአት ስለምንሠራ ነው፥ ወይስ ኃጢአትን የምንሠራው ከትውልዳችን ኃጢአተኞች ስለ ሆንን ነው? መጽሐፍ ቅዱስ ለዚህ ጥያቄ የሚሰጠው መልስ ግልጽ ነው። ኃጢአትን የምንሠራው ኃጢአተኞች ሆነን ስለ ተወለድን ነው። መዝሙር (51)፡5፥ «እነሆ፥ በዓመፃ ተፀነስሁ፥ እናቴም በኃጢአት ወለደችኝ» ይላል።

ብዙ ሰዎች ኃጢአተኞች የሆንነው ኃጢአት ስለምንሠራ ብቻ እንደ ሆነ ያስባሉ። ኃጢአት አስካልሠራን፥ ኃጢአተኞች የማንሆን ይመስላቸዋል። ይሁንና፥ ኃጢአት የማይሠራው ማን ነው? የትኛው ልጅ ነው ውሸት እንዴት እንደሚናገር መማር የሚያስፈልገው? እውነቱ ግን ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞች ሆነው መወለዳቸው ነው። መናገር ወይም መራመድ ከጀመርንበት ጊዜ ጀምሮ፥ ኃጢአት ወደ ማድረጉ እናዘነብላለን። በመክብብ 7፡20 ንጉሥ ሰሎሞን፥ «በምድር ላይ መልካምን የሚሠራ ኃጢአትንም የማያደርግ ጻድቅ አይገኝምና» ብሏል።

ሸ. ኃጢአተኞች ሆነን የተወለድነው ለምንድን ነው?

ኃጢአተኞች ሆነን የተወለድነው የሰው ልጆች ሁሉ መላጆቻችን ከነበሩት አዳምና ሔዋን ኃጢአታዊ ተፈጥሮ ስለ ወረስን ነው። የሰውን ጠባያት የሚወስነው «የጂን መረጃ» እንደሚያመለክተው፥ የሰው ባሕርይ በእርባታ አማካኝነት ከአንዱ ትውልድ ወደ ሌላው ይተላለፋል። በመሆኑም፥

ከአዳምና ሔዋን ሰው የመሆንን ጠባይ ሁሉ ወርሰናል። ሰዎች ሁሉ በሰውነታቸው የአዳምና ሔዋንን ሰብአዊ ተፈጥሮ ይዘዋል።

የአዳምና ሔዋን መውደቅ የሰብአዊ ተፈጥሮአቸውን ዓይነተኛ ባሕርይ ጎድቷል። ይህ የኃጢአት ተፈጥሮ ለሁሉም ሌሎች የሰው ልጅ ትውልዶች ደርሷል። አዳምና ሔዋን የሰው ልጆች ሁሉ ወላጆች ስለ ነበሩ፥ ሁላችንም በተዘዋዋሪ መንገድ በመራቢያ ዘራቸውና በሰብአዊ ተፈጥሮአቸው «ውስጥ» ነበርን። በዚህ መልኩ፥ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ በሙሉ ከአንድ ጋብቻ እንደሚመጣ አንድ ቤተሰብ አድርጎ ይመለከታል። ስለ ሆነም፥ የሰው ልጅ በሙሉ አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር ላይ ከፈጸሙት ኃጢአት ጋር ተጠቃሏል። አዳም የሰብአዊ ፍጥረት አባት በመሆኑ፥ አዳም ኃጢአትን ባደረገ ጊዜ ሁላችንም በአዳም «ውስጥ» በመገኘታችን፥ የኃጢአታዊ ዓመፁ ተካፋዮች ሆነናል።

በተጨማሪም፥ ወላጆች ለልጆቻቸው በሚያስተላልፉት ከፉ ምሳሌ አማካኝነት ኃጢአት ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላው ይተላለፋል። ልጆች ከአዳም ዘመን ጀምሮ በአዳም የኃጢአት ተፈጥሮ የተበላሸውን የወላጆቻቸውን ጠባይ ወርሰው ያድጋሉ።

ኃጢአት፥ በዓለም ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የተወለደውን ሕፃን እንኳ ሳይቀር አበላሽቶታል። ቃየን ባደገ ጊዜ የራሱን ወንድም በመግደል ነፍሰ-ገዳይ ሆነ (ዘፍጥ. 4፡8)። በተጨማሪም፥ ኃጢአት እግዚአብሔር ለጋብቻ ሕይወት ያቀደውን አንድነትና ታማኝነትም አበላሽቷል። እግዚአብሔር በጥበቡና በበጎነቱ አንዲት ሴት ለሰውዬው ፈጥሮ አመጣለት (ዘፍጥ. 2፡22)። ይሁንና፥ ከአዳም ከወረሱት የኃጢአት ተፈጥሮ የተነሣ፥ ብዙም ሳይቆይ ሰዎች ከአንድ የበዙ ሚስቶች ማግባት ጀመሩ (ዘፍጥ. 4፡19)፤ ይህም በሚስቶች መካከል ምቀኝነትንና በቤት ውስጥ ግጭትን ይፈጥር ጀመር። በኋላ ደግሞ ወንዶች ያገቡአቸውን ሚስቶች መፍታት ጀመሩ፤ ይህም በቤተሰቡ ውስጥ የበለጠ መራርነት፥ ሥቃይና ሕመም ያስከትል ጀመር (ዘዳ. 24፡1-3)። እንግዲህ፥ እግዚአብሔር መፋታትን እንደሚጠላ መናገሩ ያስደንቅ ይሆን (ሚልክ. 2፡15-16)?

በሽታ፥ ሳስኝነት፥ ትዕቢት፥ መራርነት፥ ጥላቻ፥ ፍች፥ ብቀላ፥ ወንጀልና ዛሬ በዓለም ውስጥ የሚገኘው የሥቃይ ዓይነት ባብዛኛው ከሰው ልጅ ኃጢአት የመጣ ነው። የኃጢአት ውጤት ሞት ነው (ሮሜ 6፡23)። ሥጋዊ ሞት ለኃጢአት ከተመሰነው የኃጢአት ቅጣት አንዱ አካል ብቻ

ነው። ሞት በሰው ልጅ ማኅበራዊ ሕይወት (ትዕቢት፥ ስግብግብነት፥ ራስ-ወዳድነት፥ ውሸት፥ ጥላቻ፥ ክህደት፥ ኅሰኝነት፥ ወንጀል)፥ ትዳር (ግጭት፥ አለመተማመን፥ ፍች)፥ የፖለቲካ ሕይወት (ምግባረ-ብልሹነት፥ ጭቆና፥ ጦርነት)፥ እና በተቀረውም በሰው ልጅ ህልውና ውስጥ ሊታይ ይችላል። በሮሜ 5፡12 ላይ እንደ ተገለጸው፥ ሁሉም ኃጢአትን ስላደረጉ፥ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ። እኛ ሁላችን የአዳምና ሔዋን ልጆች በመሆናችን፥ ኃጢአታዊ ተፈጥሮአቸውን እንካፈላለን (ሮሜ 5፡19፤ 1 ቆሮ. 15፡49)።

የአዳም ኃጢአት እኛንም የሚመለከትበት ሦስተኛ መንገድ አለ። አንዳንድ ሰዎች ምናልባት እግዚአብሔር አዳም በእነርሱ ፋንታ እንዲፈተን ማድረጉ ትክክል እንዳልሆነ ሊያስቡ ይችላሉ። እግዚአብሔር ከእኛ አንደኛውን ሳይሆን፥ አዳምን ለፈተና ያጋለጠው ለምንድን ነው? የኦሎምፒክ ውድድር ግብራሪያ ምናልባት ይህንን አሳብ ለመረዳት ይጠቅመናል። በኦሎምፒክ ውድድር በየአራት ዓመቱ፥ እያንዳንዱ አገር ከሁሉም የላቁ ተወዳዳሪዎቹን ሕዝቡን እንዲወክሉ ይመርጣል። በውድድሩ አንድ ግለሰብ ካሸነፈ፥ አገሩ በሙሉ ይደሰታል - የድሉም ተካፋይ ይሆናል። አገራቸውን ወክሎ የተወዳደረው ተወዳዳሪ ሲያሸንፍ፥ ሕዝቡ ሁሉ «አሸንፈናል!» ሲል ያወካል።

እንደዚሁም፥ አባታችን አዳም የመጀመሪያው ሰውና የሁላችንም አባት ስለ ነበር፥ የሰውን ልጆች በሙሉ በእግዚአብሔር ፊት ወክሎአል። በተጨማሪም፥ በእግዚአብሔር ፍጹም ሆኖ በመፈጠሩ ከሰው ልጆች ሁሉ የላቀ ጻድቅና ፍጹም ነበር። ድል-ነሺ የመሆን አድል ያለው ሰው ቢኖር አዳም ነበር። እርሱ ሻምፒዮን ነበር። ግናችንም ብንሆን ይህንኑ ልናደርግ አንችልም ነበር። ዳሩ ግን ይህ ሻምፒዮናችን በመሸነፉ፥ በውድድሩ ድል አጣን!

እግዚአብሔር ግን ሌላ ታላቅ ሻምፒዮን አዘጋጅቶ ነበር። «የኋለኛው አዳም» አይሸነፍም ነበር። የኋለኛው አዳም ኢየሱስ የሰውን ዘር የሚያድን እውነተኛ ሻምፒዮን ሆነ። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ኋለኛው አዳም (ክርስቶስ) ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ» ይላል (1 ቆሮ. 15፡45)። ጳውሎስ፥ «ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉ» ሲል ጽፎአል (1 ቆሮ. 15፡22)። አስከፊው ዜና፥ «የኃጢአት ደመወዝ ሞት» መሆኑ ነው። መልካሙ ዜና፥ «የእግዚአብሔር የጸጋ

ስጦታ . . . በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት» መሆኑ ነው (ሮሜ 6፡23)።

ማጠቃለያ

በአፍሪካም ሆነ በምዕራቡ ዓለም ስለ ሰው አፈጣጠር የተለያዩ ንድፈ-አሳቦች አሉ። ይሁንና፥ ስለ ሰው አፈጣጠር እውነቱን ለማወቅ መደ እግዚአብሔር መገለጥ መመልከት አለብን።

እውነቱ፥ እግዚአብሔር ሰውን ብሩህ አእምሮና እንደ እግዚአብሔር ያለ ነፃ ፈቃድ በማቀዳጀት፥ ልዩና የከበረ አካል አድርጎ በራሱ አምሳል የፈጠረው መሆኑ ነው። የተፈጠረውም ምድርን እንዲገዛና የእግዚአብሔርን ጽድቅ በማሳየት፥ እግዚአብሔርን እንዲያስከብር ነበር። ይሁንና፥ የእግዚአብሔርን ዕቅድ በማጓላት ፋንታ፥ ሰው በእግዚአብሔር ላይ በማመፁ በሰው ዘርና በተቀረውም ፍጥረት ላይ አስከፊ ሥቃይና ርግማን አስከትሏል። አዳም በኃጢአቱ በራሱና በሰው ልጅ ሁሉ ላይ ሞትን ሲያመጣ፥ በሰው ዘርና በምድርም ላይ እርግማን አድርሷል። አዳምና ሔዋን የሰው ዘር ሥጋዊ ወላጆች በመሆናቸው፥ የሰው ልጅ ሁሉ ኃጢአታዊ ተፈጥሮአቸውን ወርሶአል። ከአዳም በኋላ፥ በዓለም ላይ የሚወለድ ሕፃን ሁሉ ኃጢአተኛ ሆኖ ተወልዷል። እግዚአብሔር አዳምን ፍጹም ሰው አድርጎ ስለ ፈጠረው፥ በሰው ዘር ምትክ እንዲፈተን ማድረጉ አግባብ ነው። አዳም ኃጢአት በማድረጉ ምክንያት የሰው ዘር ከደኅንነት ተለይቶ ጠፋ። ክርስቶስ ለሰው ልጅ ኃጢአት የሞት ቅጣት ስለ ተቀበለ፥ የኋለኛው አዳም በሆነው ክርስቶስ የሰው ዘር ሊድን ይችላል።

በምዕራፍ 6 ላይ የተመሠረቱ የመወያያ ጥያቄዎችና መልመጃዎች

1. አዳም ኃጢአት ባደረገ ጊዜ፥ የሰው ልጅ «በአዳም ውስጥ» የነበረው እንዴት ነበር?

2. የሰው ነፍሳት በማኅፀን ውስጥ በተፀነሱ ሕፃናት ውስጥ ዳግም ሊገቡና ብዙ ጊዜ ተደጋግመው ሊወለዱ እንደማይችሉ መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት እንደሚያሳይ ግለጽ።

3. አራት አባላት በሚገኙባቸው ቡድኖች ከፋፍላቸው። እያንዳንዱ ቡድን ኃጢአት ዓለምን ያበላሸባቸውን መንገዶች ሁሉ ይዘርዝር። የቡድኖቹን

ዝርዝሮች አንድ ላይ በማሰባሰብ፥ ኃጢአት ዓለምን ያበላሸባቸውን መንገዶች ሙሉ ለሙሉ የሚያስረዳ ዝርዝር አዘጋጁ።

4. ከዚህ በላይ በሦስተኛው ጥያቄ ላይ በተዘረዘሩት ነጥቦች በመጠቀም፥ ቡድኖቹ የክርስቶስ ደኅንነት እንዴት የዘረዘሩዋቸውን ግልጽ የኃጢአት ውጤቶች ሊያስወግድ እንደሚችል ይወስኑ።

5. የአዳም ኃጢአት ለምን ወደ ተቀረው የሰው ልጅ እንደ ተላለፈ፥ ሦስት ምክንያቶች በመስጠት አብራራ።

6. ከ10-16 የዕድሜ ክልል ውስጥ ለሚገኙ ወጣቶች ሰው እንዴት በእግዚአብሔር አምሳል እንደ ተፈጠረ ለማብራራት፥ የሰንበት ትምህርት አዘጋጅ። በትምህርቱም ውስጥ ታሪኮችን ወይም ማብራሪያዎችን ጨምር።

7. በጎሳ ቡድን ከፈላቸው። የሰው ኃጢአታዊ ተፈጥሮ ውጤት በሆኑ የጎሰኝነት ገጽታዎች ላይ ተወያዩና ዝርዝሮቹን ጻፉ።

8. በዚያው የጎሳ ቡድን ውስጥ፥ እግዚአብሔር ለዚህ የጎሰኝነት ችግር እያንዳንዱ የጎሳ ቡድንና እያንዳንዱ ግለሰብ ምን እንዲያደርግ እንደሚፈልግ፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ መረጃ አንጻር ወስኑ።

9. ሰው ለምን ይኖራል? ለሚለው ጥያቄ የአፍሪካ ባህላዊ አመለካከት የሚሰጠውን ምላሽ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከት ጋር አወዳድር።

10. ያገቡና ያላገቡ ሰዎችን በቡድን አስቀምጥ። ያላገቡት ሰዎች ቡድን፥ እንዴት ኃጢአታዊ ተፈጥሮአቸው ከተቃራኒ ፆታዎቻቸው ጋር ሊኖራቸው የሚገባውን ጤናማ ግንኙነትና የፍቅር ሕይወት እንዳበላሸው የሚያስቡአቸውን መንገዶች ሁሉ ይዘርዝሩ። ያገቡትም ደግሞ እንደዚሁ እንዴት ኃጢአታዊ ተፈጥሮአቸው ጋብቻቸውን፥ እንዲሁም ከትዳር ጓደኞቻቸውና ከልጆቻቸው ጋር የሚዛመዱበትን መንገድ እንዳበላሸው የሚያምኑባቸውን ነጥቦች ሁሉ ይዘርዝሩ።

11. የቁጥር 10 መልመጃ እንዳለቀ፥ ሁለቱ ቡድኖች እግዚአብሔር እንዴት የዘረዘሩአቸውን ትክክለኛ ያልሆኑ ልምዶች በመልካም እንዲተኩ እንደሚፈልግ ለመረዳት፥ በጥቅስ ማውጫዎች በመጠቀም መጽሐፍ ቅዱስን ይመርምሩ።

12. በአፍሪካ ሰዎች በእርግማንና በውጤቱ ላይ ባላቸው አስተሳሰብ ላይ ተወያዩ። ይህ እግዚአብሔር ካወጀው መርገምና ከመርገሙ ውጤት ጋር እንዴት ይወዳደራል?

13. በአፍሪካውያን ግንዛቤ ኃጢአት ምንድን ነው? ይህ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ የኃጢአት ግንዛቤ ጋር እንዴት ይወዳደራል?

14. የቡድኑ አባላት ስለ ሰው አፈጣጠር አንዳንድ የአፍሪካውያንን አፈ-ታሪኮች ያካፍሉ።

15. አፍሪካውያን፥ እግዚአብሔርን ከአሳባቸው ጋር ለማስማማት የሚሞክሩባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው?

SUGGESTED FOR FURTHER READING

Hoekema, Anthony A. Created In The Image Of God. Carlisle: Paternoster Press, 1994.

Houston, J.M. I Believe in God the Creator. London: Hodder, 1979.

McDonald, H.D. The Christian View of Man. London: Marshall Pickering, 1981.

Roberts, Linleigh J. Let Us Make Man. Edinburgh: Banner of Truth Trust, 1988.

ምዕራፍ 7

ኢየሱስ ክርስቶስ - የደኅንነታችን ምንጭ

ከፖጋና ጉናቲ የተባሉት ወጣቶች የአፍሪካ ባህላዊ ሃይማኖት ከሚከተሉ ቤተሰቦች የመጡ ናቸው። ወደ ኮሌጁ ከመጡበት ጊዜ አንሥቶ ክርስቲያንና ሙስሊም ጓደኞቻቸው ስለ እምነታቸው ሲነጋገሩ በአጽንኦት ሲያዳምጡአቸው ቆይተዋል። ከፖጋና ጉናቲ ስለ እግዚአብሔር እውነቱን ለማወቅ የሚፈልጉ እውነተኛ ወጣቶች ናቸው። ከጓደኞቻቸው ጋር ይበልጥ በተነጋገሩ ቁጥር፥ ብዙ ጥያቄዎች ይፈጠሩባቸዋል።

ከፖጋ፦ «ክርስቲያኖች ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያገኙበት ብቸኛው መንገድ ክርስቶስ እንደ ሆነ ይናገራሉ።»

ጉናቲ፦ «ለምን እንደዚያ እንደሚሉ ይገርመኛል። ሁላችንም አንድ አምላክ እንዳለ እናውቃለን፤ በእርሱም እናምናለን። እንዲያውም፥ ሁላችንም በየራሳችን ቋንቋ እግዚአብሔርን የምንጠራበት ስም አለን። አንድ ሰው እውነተኛ ከሆነ፥ በራሱ መንገድ እግዚአብሔርን ለማግኘት መቻል አለበት።»

ከፖጋ፦ «እንዲሁም ክርስቲያኖች ሰዎች የኃጢአት ይቅርታ ሊያገኙ የሚችሉት በክርስቶስ አማካኝነት ብቻ እንደ ሆነ ይናገራሉ።»

ጉናቲ፦ «የእግዚአብሔር ይቅርታ እንዲህ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? በበኩሌ ግን የሕዝባችን ሽማግሌዎች የሚናገሩትን በበለጠ በተግባር ልናውለው የሚገባን ትክክለኛ ነገር እንደ ሆነ አስባለሁ። ደግሞም ባህላችንን ባልከተል፥ እንደ ዓመፀኛ በመቆጠር እቀጣለሁ። እንደሚመስለኝ እግዚአብሔር የጠባያችንን ኃላፊነት በእነዚህ ሽማግሌዎች እጅ አስቀምጦአል።

«በመንደራችን ያለው ሁኔታ በእጅጉ እያሳሰበኝ ነው። ለምሳሌ በቅርቡ አጎቴ በቡዳዎች ተበልቶ ሞተ። ይህን ደግሞ የነገረኝ በመንደራችን ያለው ጠንቋይ ነው።»

ከፖጋ፦ «እኔም ክርስቲያን ጓደኞቼ የነገሩኝ ነገር ግራ አጋብቶኛል። እግዚአብሔር እንደሚወደንና ዳሩ ግን ኃጢአተኞችን በሲኦል እንደሚቀጣ

ይነግሩኛል። ሰዎችን የሚወድ አምላክ ማንኛውንም ሰው ወደ ሲኦል የሚልከው ለምንድን ነው?»

ጉናቲ፦ «ይህ ጥሩ ጥያቄ ነው። ክርስቲያኖች እንደሚሉት እግዚአብሔር ሰዎችን የሚወድ ከሆነ፥ ሁሉንም ይቅር የማይለው ለምንድን ነው? ሙስሊም ጓደኞቼ እግዚአብሔር በፍርድ ቀን ምሕረት ለሚጠይቁት ይቅርታ እንደሚያደርግ ይናገራሉ።»

ከፖጋ፦ «የማይገባኝ ነገር ቢኖር፥ የክርስቶስ ሞት ዛሬ ከእኛ ጋር ምን ዝምድና እንዳለው ነው። ይህን የመሰለው ከረዥም ዘመናት በፊት የተከናወነ የአንድ ሰው ሞት አሁን ለእኛ እንዴት ዋጋ ሊኖረው ይችላል?»

እነዚህ ምናልባት አንድ ሰው ሊጠይቃቸው የሚችላቸው በጣም አስፈላጊ ጥያቄዎች ናቸው። እግዚአብሔር ሰዎችን የሚወድ ከሆነ፥ ለምን ሁሉንም ሰው ይቅር አይልም? የእግዚአብሔርስ ይቅርታ እንዲህ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? ለመሆኑ የክርስቶስ ሞት ከእኛ ጋር ምን ዝምድና አለው? ከ2000 ዓመታት በፊት የተከናወነው የአንድ ሰው ሞት እንዴት የሰውን ልጅ ታሪክ ሊለውጥ ይችላል?

ጉናቲ ያቀረበው አሳብ ምናልባትም አንዳንድ ክርስቲያኖችንም ጨምሮ በብዙዎቹ አፍሪካዎያን የሚታመንበት ነው። አፍሪካውያን ይበልጥ የሚያተኩሩት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ከማግኘት ይልቅ፥ በሕዝባቸው ዘንድ ተቀባይነት ማግኘቱን ነው። በብዙ የአፍሪካ የፍጥረት ታሪኮች፥ እግዚአብሔር ከሰው ልጆች የተለየው በተለያዩ ምክንያቶች እንደ ሆነ ይነገራል። በአንድኛው ታሪክ፥ አንዲት ሴት እህል ስትወቃ ሳለ በመውቂያው እያከታተለች እግዚአብሔርን ስለ መታችው ከሰው ልጆች አንደ ራቀ ነው። በሌላው ታሪክ፥ በሰማይና ምድር መካከል ገመድ ነበር። ገመዱን ግን አንድ ጅብ ስለ በጠሰው፥ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰውና እግዚአብሔር ሊገናኙ አልቻሉም። ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን እግዚአብሔር አሁን ሩቅ ይመስላል፤ ከዚህም የተነሣ፥ ለዕለታዊ ኑሮ እግዚአብሔርን ከማወቅ ይልቅ የመንደር ሽማግሌዎችና የጎሳ ቅድመ-ትውልዶች ፈቃድ መጠየቁ የበለጠ አስፈላጊ ይመስላል።

በተጨማሪም፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታ ማግኘቱ ከጠንቋዩ ዛቻ ጥበቃ ከማግኘቱ ጋር በእኩል ደረጃ የሚታይ አይመስልም። ብዙ የበሽታና ሞት አደጋዎች ከጠንቋዮች እንደሚመጡ ተደርገው ይታመናሉ። ስለዚህ

ክርስቲያኖችን ጨምሮ፥ ብዙ ሰዎች ከእግዚአብሔር ይልቅ ጠንቋዮችን በመፍራት ይኖራሉ።

በአፍሪካውያን አመለካከት ለሰው ሕይወት ከፍተኛ ከበሬታ ስለሚሰጠው፥ የሕይወት ኃይል፥ አስተማማኝ ኑሮና ብዙ ልጆችን መውለድ ተቀዳሚ ስፍራ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ናቸው። ባህላዊ የደኅንነት አመለካከት አለ ብንል እንኳ፥ የዚያ ባህላዊ አመለካከት እጅግ አስፈላጊ ነገሮች በጎሳው ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት፥ ከክፉ ኃይላት መጠበቅና የሕይወት ኃይል ማግኘት ናቸው። ይህ ከመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት ጋር እንዴት ይነጻጸራል? በአፍሪካ በማኅበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት በማግኘት፥ ከክፉ ኃይላት በመጠበቅና የሕይወትን ኃይል በመያዝ በኩል ለሚታየው ችግር ከኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የሚዛመዱ ነገሮች ምንድን ናቸው? በደኅንነት ውስጥ ክርስቲያኖች ሊመለከቱአቸው የሚገቡ ሌሎች እውነታዎች ምንድን ናቸው? የኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የአፍሪካውያንን የልብ መሻት ሁሉ የሚያሟላው እንዴት ነው?

የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ አስፈላጊነት

ከአራቱ ወንጌላት አንድ ሦስተኛ የሚሆነው የክርስቶስን ሕይወት የመጨረሻ ጥቂት ቀናት፥ የሞቱንና የትንሣኤውን ዝርዝሮች ይዘግባል። ከዚህ በተቃራኒ፥ ከልደቱ ታሪክ በስተቀር ስለ መጀመሪያዎቹ ሠላሳ ዓመታት ሕይወቱ ዝርዝር መግለጫ የሚሰጠን አንድ አጭር ምንባብ ብቻ ነው (ሉቃስ 2፡41-52)። ሐዋርያት ስለ ክርስቶስ ሲናገሩ፥ በመጀመሪያ ደረጃ ስለ ሞቱና ትንሣኤው ይናገራሉ (የሐዋ. 2፡22-36፤ 1 ቆሮ. 15፡1-4)። ለምን ይሆን?

ይህ የሆነው የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ደኅንነት ለወጠነው ዕቅድ መሠረቶች ስለ ሆኑ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፥ መንፈስ ቅዱስ እንደ ክርስቶስ ሞት ሳለው ከፍተኛ ጉዳይ፥ የወንጌልን ሰፊ ክፍል በመስጠት አጽንኦት ያደርጋል።

ከዚህም ሁለት ነገሮች እንግራለን፡- በመጀመሪያ፥ ወንጌላት ሙሉ ለሙሉ የኢየሱስን የሕይወት ታሪክ እንደግይዳስሱ እንረዳለን። በክርስቶስ ሕይወት ውስጥ የተረጸሙና ከሰው ደኅንነት ጋር የሚዛመዱ ክስተቶች ተመርጠው ተጽፈዋል። በሁለተኛ ደረጃ፥ በክርስቶስ መምጣት ውስጥ እጅግ አስፈላጊ ክስተቶች ሞቱና ትንሣኤው ነበሩ። እነዚህ ሁለት ነጥቦች እጅግ ወሳኝ በመሆናቸው እግዚአብሔር እውነቱን እንድንረዳ አጥብቆ ይፈልጋል።

የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ እጅግ አስፍላጊ ክስተቶች ናቸው። ያለ ክርስቶስ ሞት እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን ሰው ወደ ቅዱስ መኖሪያው የሚያስገባበት መንገድ የለም። በመስቀል ላይ በተፈጸመው የክርስቶስ ሞት፥ የሰው ልጆች ከኃጢአት ቅጣት የሚያመልጡበት መንገድ ተዘጋጀ። በክርስቶስ ሞት አማካኝነት ከእግዚአብሔር ጋር ልንታረቅ እንችላለን።

በክርስቶስ ትንሣኤ አማካኝነት በእርሱ ለሚያምኑት የሞት ቅጣት ተነሣ (2 ጢሞ. 1፡10)። ኢየሱስ፥ «እኔ ሕያው ነኝና እናንተ ደግሞ ሕያዋን ትሆናላችሁ» ብሎአል (ዮሐ. 14፡19)። ያለ ክርስቶስ ትንሣኤ፥ ምንም የዘላለም ሕይወት ተስፋ ሊኖር አይችልም። የክርስቶስ ትንሣኤ ለእያንዳንዱ ክርስቲያን በሰማይ ለመኖር ዘላለማዊ ሕያው ተስፋ ይሰጣል (1 ጴጥ. 1፡3-4)። በተጨማሪም፥ ትንሣኤ ሕይወትን ከኃጢአት እስራትና ቁጥጥር ነፃ ያወጣል። ጳውሎስ፥ «እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ» ሲል ጽፎአል (ሮሜ 6፡4)።

በዚህ ምዕራፍ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ዓላማና ወደ ሰማይ በማረጉ አስፈላጊነት ላይ እናተኩራለን። በዚህም የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ እንሞክራለን፡-

ሀ. የእግዚአብሔር ፍቅርና ይቅርታ ምን ያህል ታላቅ ነው?

ለ. የሰው ደኅንነት የተከናወነው እንዴት ነው?

ሐ. የደኅንነት ፍች ምንድን ነው?

መ. የደኅንነት ውጤቶች ምንድን ናቸው?

ሠ. ደኅንነት ከአፍሪካ ችግሮች ጋር የሚዛመድባቸው አንዳንድ መንገዶች የትኞቹ ናቸው?

ረ. ቅድስና ምንድን ነው?

ሰ. የኢየሱስ ከሞት መነሣት እውነት እንደ ሆነ እንዴት እናውቃለን?

ሸ. በዛሬው ጊዜ የክርስቶስ ትንሣኤ ለክርስቲያኖች የሚሰጠው ትርጉም ምንድን ነው?

ቀ. የክርስቶስ ዕርገት ዓላማ ምን ነበር? አሁንስ ምን በማድረግ ላይ ይገኛል?

በ. የሚድነው ማን ነው?

ሀ. የእግዚአብሔር ፍቅርና ይቅርታ ምን ያህል ታላቅ ነው?

«እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአልና በዚህ ፍቅርን አውቀናል» (1 ዮሐ. 3፡16)።

ኢየሱስ የመጣበት እጅግ አስፈላጊው ምክንያት ለሰው ኃጢአት መሥዋዕት ሆኖ ለመሞት ነው። የእርሱ ሞት ሰዎች ይቅርታ እንዲያገኙና ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲያደርጉ መንገድ ከፈተ (2 ቆሮ. 5፡18-19)። የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው የቀረበ ግንኙነት፥ ሰው በዔደን ገነት በፈጸመው ኃጢአት ተቋረጠ (ዘፍጥ. 3፡8-24)።

የሰው ልጅ በኃጢአቱ የሞተ ነበር (ኤፌ. 2፡1-2)። ሰዎች ለኃጢአታቸው የእግዚአብሔርን ፍትሐዊ ፍርድ ተቀበሉ (ሮሜ 1፡18)። እግዚአብሔር ቅዱስና ፍትሐዊ ፈራጅ አምላክ በመሆኑ [መዝ. (143)፡2]፥ ከዚያ ፍርድ ለማምለጥ አይቻልም ነበር (ዕብ. 2፡2-3)። እርሱ ኃጢአትን የሚቀጣ ሲሆን፥ ሰዎችም ሁሉ በፊቱ ኃጢአተኞች ናቸው (መክ. 7፡20፤ ሮሜ 2፡11-12፤ 3፡23)።

በአፍሪካ ብዙ የሕዝብ ቡድኖች ከፉ መሥራት በቤተሰቡ ወይም በጎሳው ላይ ኅፍረት የሚያስከትሉ ተግባራትን እንደ መፈጸም አድርገው ያስባሉ። የሚያሳዝነው ግን የተወሰኑ የሕዝብ ቡድኖች ተቀባይነት እንዳላቸው አድርገው የሚቆጥሯቸው አንዳንድ ነገሮች በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸው መሆናቸው ነው። ለምሳሌ፥ አንዳንድ ቡድኖች ያላገቡ ሰዎች የወሲብ ግንኙነት እንዲፈጽሙ ይፈቅዳሉ፤ እግዚአብሔር ግን ይህ ኃጢአት እንደ ሆነና ቅጣትንም እንደሚያስከትል ይናገራል (1 ቆሮ. 6፡18፤ 1 ተሰ. 4፡3-6፤ ራእይ 2፡20-22)

ክፉ መሥራት በቤተሰብ ወይም በጎሳ ላይ ኅፍረት የማስከተል ጉዳይ ብቻ አይደለም። ክፉ ሥራ ኃጢአት ነው። ኃጢአት ደግሞ የእግዚአብሔርን ሕግጋት መተላለፍ ነው። መልካምና ክፉ ምን እንደ ሆነ የወሰነው እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ዳኛ ስለ ሆነ፥ ባህልን ወይም ወግን ሳይመለከት ትክክለኛውና ትክክል ያልሆነው ምን እንደ ሆነ ወስኖአል። የእርሱ የመልካምና የክፉ ድንጋጌ የእግዚአብሔር የግብረ-ገብ ሕግ ተብሎ ይጠራል። ይህም ሕግ በአሠርቱ ትእዛዛት ተጠቃሎ ቀርቧል (ዘጸ. 20፡1-17)። በአዲስ ኪዳን መልእክቶች ውስጥ ደግሞ በበለጠ በሙላት ተብራርቷል። ኃጢአት በእግዚአብሔር የተደነገገው እንጂ፥ እኛ አሳፋሪ ነው ብለን የምናስበው ነገር አይደለም። በአንዱ ባህል አሳፋሪ የሆነው ነገር በሌላው አሳፋሪ ላይሆን ይችላል።

አንዳንድ ሰዎች በእግዚአብሔር ፍቅርና ፍትሕ ግራ ይጋባሉ። አንድ ምግባረ-ብልሹ ዳኛ ጉቦ ለመቀበል ሲል ጥፋትን እንደሚያቃልል ሁሉ፥ እግዚአብሔርም በተወሰነ ደረጃ የሰውን ኃጢአት እንደሚያቃልል ያስባሉ። እንዲያውም የእግዚአብሔር ፍቅር፥ ቅድስናውንና ፍትሐዊ ፍርዱን ወደ ጎን እንደሚያገልለውም ያስባሉ።

ዳሩ ግን እግዚአብሔር እንደ ብዙዎቹ ሰብአዊ ዳኞች ምግባረ-ብልሹ አይደለም፤ እርሱ ኃጢአትን አያቀልልም። አድልዎም አያሳይም (ቆላ. 3፡25)። አንደኛው የእግዚአብሔር ባሕርይ ሌላውን ለመሰረዝ ወይም ለማስወገድ አይችልም። እርሱ አፍቃሪና በተመሳሳይ ጊዜ ፍትሐዊ ዳኛ ነው። በመሆኑም፥ ፍቅሩ ፍትሐዊነቱን ወደ ጎን ሊለው ወይም ሊያስወግድ አይችልም (ዘፍጥ. 18፡25)፤ እንደዚሁም ፍትሐዊነቱ ፍቅሩን ሊያስወግድ አይችልም (መኃልይ 8፡7)።

እግዚአብሔር የፈጠራቸውን ሕዝቦች ይወዳል (ኤር. 31፡3፤ ዮሐ. 3፡16)። በመሆኑም፥ በኃጢአታቸው ምክንያት ለዘላለም ከእርሱ እንዲለዩ አይፈልግም። የእግዚአብሔር ፍቅር ሰዎች ከእርሱ ጋር እንዲቀራረቡና ኅብረትም እንዲያደርጉ ይናፍቃል። ይሁንና፥ የእግዚአብሔር ቅድስናና ፍትሐዊነት፥ ሰዎች ለኃጢአታቸው ፍርድንና ቅጣታቸውን እንዲቀበሉ ይሻል። እግዚአብሔር ኃጢአተኛ ሰዎችን በተቀደሰ ማደርያው ታግሦ ሊያኖራቸው አይችልም። እንግዲህ፥ ምን ማድረግ ነበረበት?

ኢየሱስ ሰዎች በጥረታቸው ራሳቸውን ሊያድኑ እንደማይችሉ ገልጾአል (ማቴ. 19፡25-26)። ሰዎች በኃጢአት ላይ ከሚወርደው የእግዚአብሔር

ቁጣ ራሳቸውን ሊያድኑ አይችሉም። ማንም ሰው እግዚአብሔር ለኃጢአት ከሚሰጠው የሞት ብያኔ ሊያድነው የሚችል ብቁ የሆነ ተግባር ሊያከናውን አይችልም (ዘፍጥ. 2፡17፤ ሮሜ 6፡23)። ይሁንና፥ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይና ሁሉን አዋቂ በመሆኑ፥ ኃጢአተኛ የሆነውን የሰው ልጅ ማዳን ጨምሮ፥ የማይቻለው ነገር የለም (ማቴ. 19፡26)። እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ቅጣት የሚሰጥበትንና በተመሳሳይ ጊዜ ፍቅሩንና ይቅርታውን ለሰዎች የሚያሳይበትን መንገድ ለማዘጋጀት ይችል ነበር።

እግዚአብሔር እንዴት ይህንን ሊፈጽም ቻለ? ፍትሐዊና ቅዱስ መሆኑ እንዳለ ሆኖ፥ ኃጢአትን ሊቀጣና በተመሳሳይ ጊዜ ኃጢአተኞችን ከወደቁበት የፍርድ ውሳኔ ሊያወጣ የሚችለው እንዴት ነው? የሚቀጥለው አንድ የትምህርት ቤት ታሪክ እግዚአብሔር እንዴት ይህንን እንዳደረገ ለመረዳት ይረዳናል።

የመምህራን ኮሌጅ ተማሪ የሆነው ባባ ብዙ ዋጋ የከፈለበት ውድ የሙዚቃ ማዳመጫ ቴፕ ነበረው። አንድ ቀን ከመኝታ ክፍሉ ተሰረቀበት። ባባም በጣም ተቆጣ። አዳሙ የሚባለውን ተማሪ ማንም ሰው ሳይኖር ከአንድ ጊዜ በላይ ወደ ክፍሉ ሲገባ ስላየው፥ እርሱ ነው የወሰደው ሲል ጠረጠረ። በተጨማሪም፥ አዳሙ ለወንድሙ የት/ቤት ክፍያ ገንዘብ እንደሚፈልግ ያውቅ ነበር። አንድ ቀን ባባ በስውር ወደ አዳሙ ክፍል ዘው ብሎ ገባ። ቴፑን ባያገኘውም፥ በአዳሙ ሳጥን ውስጥ ብዙ ገንዘብ ተመለከተ። ባባም በጣም ተናደደ።

የቴፑን መሰረቅ የሚያውቅ አንድ ኢሳ የሚባል የአዳሙ ጓደኛ ነበር። ለኢሳ አዳሙም ባባም ጓደኞቹ ስለ ነበሩ፥ በነገሩ በጣም አዘነ። ኢሳ ከባባ ለተሰረቀው ቴፕ ማካካሻ ገንዘብ መክፈልና ለዚህም የራሱን አዲስ ቢስክሌት መሸጥ እንዳለበት ከውሳኔ ደረሰ። እንዳሰበውም ቢስክሌቱን ሸጠና ወደ ባባ አመራ። ለባባም የሆነውን ሁሉ እንደ ሰማና አዳሙ በሠረቀው ቴፕ ምትክ ገንዘብ ለመክፈል እንደሚፈልግ ነገረው። ባባ ከአዳሙ ጋር እንዲጣላ አልፈለገም ነበር። ኢሳ ለአዳሙ ባደረገው በዚህ መልካም ነገር የባባ ልብ ተነካ። ኢሳ ቀደም ብሎ ቢስክሌቱን የሸጠ በመሆኑ፥ ገንዘቡን ሊቀበለው ወሰነ። እጅግ የቅርብ ጓደኛው የነበረውን የኢሳን አሳብ ሊቃወም አይችልም ነበር። ኢሳ ለባባ የእንድን አዲስ ቴፕ ሙሉ ዋጋ ከፈለው።

ባባ አዳሙን ጠራውና ቴፑ እንደ ጠፋበትና ከሳጥኑ ብዙ ገንዘብ እንዳገኘ ነገረው። አዳሙ በጣም ተቆጣ። ባባ ጠንካራ ወጣት በመሆኑ፥

ቢፈልግም ሊመታው ይችል ነበር። አዳሙ እንደ ተነቃበት አወቀ። ቴፑን እንደ ሠረቀ አመነ፤ ግን ምን ሊያደርግ ይችላል? ቴፑን ሽጦ ከገንዘቡ የተወሰነውን ስለ ተጠቀመበት፥ ቴፑንም ገንዘቡንም ሊመልስለት አይችልም ነበር። አዳሙ በፍርሃት ይንቀጠቀጥ ጀመር።

ባባ ኮስተር ብሎ ተመለከተው። ከዚያም፥ ኢሳ ያደረገውን ነገር ነገረው። የቴፑ ዋጋ ስለ ተከፈለለት፥ ይቅር እንደሚለውና ጉዳዩንም እንደሚተወው ነገረው። አዳሙ የሚመልሰው ቃል አልነበረውም። ያለቅስ ጀመር። ባባ ለአዳሙ አንድ ነገር ብቻ እንዲያደርግ እንደሚፈልግ ነገረው። አዳሙ ወደ ኢሳ ዘንድ ሄዶ ላደረገው ነገር ምስጋና እንዲያቀርብና ከዛሬ ጀምሮ በዚህ ዓይነት የውስልትና ተግባር ዳግመኛ እንዳይሳተፍ ነገረው። አዳሙ ወዲያው ምንም ጊዜ ሳያባክን ኢሳን ፈልጎ አገኘው፤ ይሁንና፥ ምን እንደሚል አያውቅም ነበር። የጋፍረት ስሜት ወረረው። ለቴፑ ለከፈለው ገንዘብ የሚመልስለት አልነበረውም። ኢሳ ገንዘቡን እንዲመልስለት እንደማይፈልግና ይልቁንም አዳሙ ለወደፊቱ መልካም ሰው እንዲሆን እንደሚሻ ገለጸለት። ከዚያም፥ ኢሳ አዳሙን በፍቅር እጆች ሲያቅፈው አዳሙ ዳግም ያለቅስ ጀመር።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አዳሙ ኢሳ የሚጠይቀውን ማንኛውንም ነገር ለማድረግ ዝግጁ ሆነ። እንዲያውም፥ በኮሌጁ ውስጥ የቀረውን ጊዜ በሚችለው በማንኛውም መንገድ ኢሳን ለመርዳቱ ተግባር አዋለ። የዕድሜ ልክ ጓደኛሞች ሆኑ። በተጨማሪም፥ ሁኔታው በአዳሙና ባባ መካከል ያለውን ግንኙነት ለወጠው። ባባ ቃሉን በመጠበቅ ጉዳዩን ሁለተኛ አላነሣውም። ባባና አዳሙ ሁለቱም ከኢሳ ጋር ካላቸው መልካም ግንኙነትና ኢሳም ካደረገው በጎ ተግባር የተነሣ፥ በፍቅር የተሳሰሩ ጓደኛሞች ሆኑ።

ለ. የሰው ደኅንነት የተከናወነው እንዴት ነው?

ከላይ የተጠቀሰው ታሪክ የሰው ልጅ ደኅንነት እንዴት እንደ ተገኘ የሚያሳይ አሳብ ይሰጠናል። በተጨማሪም፥ እንደ አማላጅ፥ ይቅርታ፥ ዕርቅ፥ ምትክና ቅድስና የመሳሰሉት ቃላት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ደኅንነትን ለመግለጽ እንዴት እንዳገለገሉ ያብራራል። የእነዚህም ቃላት ፍች ወደፊት በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ይብራራል።

በዚህ ታሪክ፥ አዳሙ በባባ ላይ የፈጸመው ኃጢአት የሁለቱን ግንኙነት ከማቋረጡም በላይ፥ ባባ በአዳሙ ላይ እንዲቆጣ አድርጓል። ባባ

አዳሙ ለጥፋቱ ገንዘብ እንዲከፍል ወስኖ ነበር። ሆኖም ግን ኢሳ የቴፑን ዋጋ በመክፈል፥ የአዳሙን ጥፋት አካካሰው። ኢሳ በዚህ አድራጎቱ ባባ አዳሙን ይቅር የሚልበትን መንገድ አመቻቸ። ይሁንና፥ ኢሳ ይቅርታውን ተግባራዊ ለማድረግ ቢስክሌቱን ማጣት ነበረበት። የኢሳ ጣልቃ መግባት በባባና በአዳሙ መካከል ያለውን ግንኙነት ከማስተካከሉም በላይ፥ አዳሙም ለኢሳ የአመስጋኝነትና የታዛዥነት ልብ እንዲኖረው አድርጓል።

ምንም እንኳ ፍጹም ገላጭ ማብራሪያ ባይሆንም፥ ይህን ታሪክ በክርስቶስ ካገኘነው የደህንነታችን ታሪክ ጋር ልናወዳድረው እንችላለን። አዳም በእግዚአብሔር ላይ የፈጸመው ኃጢአት በሰው ልጅና በእግዚአብሔር መካከል የነበረውን ግንኙነት በማቋረጥ፥ በኃጢአታችን ላይ የእግዚአብሔርን ቁጣ አስከተለ። ይሁንና፥ ለኃጢአታችን የአብን ቅጣት በመቀበል፥ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ቅዱስ ቁጣ ሊታደገን ችሏል። ኢየሱስ፥ አብ ሰዎችን ይቅር የሚልበትን መንገድ አመቻቸ፣ ይሁንና ይህን የአብ ይቅርታ አስተማማኝ ለማድረግ ለኢየሱስ የራሱን ሕይወት አስከፍሎታል። የኢየሱስ መሥዋዕት በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል የነበረውን ግንኙነት ለመጠገን ችሏል። በትክክል ኢየሱስ ያደረገልንን ብናውቅ፥ በቀረው ዘመናችን ሁሉ እርሱን ለማገልገል ከመፍቀድ በቀር ሌላ የምንወስደው እርምጃ አይኖርም።

አዳሙ ኢሳ ያደረገለትን በጎነት ሲመለከት፥ ተግባሩ ልቡን እጅግ ስለ ነካው ከኃጢአታዊ ጠባዩ ተመልሶአል። እኛም ኢየሱስ ያደረገልንን በትክክል ስንረዳ፥ ከትዕቢታችን፥ ከኃጢአተኛና ከራስ-ወዳድ ጠባያችን እንድንመለስ ያነቃቃናል። መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ደኅንነት የሚመራ ንስሐ የሚለው ይህንኑ ነው (2 ቆሮ. 7፡10)። ኢሳ ላደረገለት ውለታ አዳሙ በማመስገን ብቻ ላይወሰን ታዛዥና የዕድሜ ልክ ጓደኛ ሆነ። እኛም ለኢየሱስ የዚህ ዓይነት አመስጋኝ ልብና ታዛዥነት ካለን፥ እግዚአብሔር ይህንኑ በመጠቀም ኃጢአተኛ ባሕርያችንን ወደ መንፈሳዊና ቅዱስ ባሕርይ ይለውጠዋል (2 ቆሮ. 5፡15)።

ከላይ በተመለከትነው ታሪክ፥ ኢሳ በባባና አዳሙ መካከል አማላጅ ሆነ። ኢሳ ጣልቃ ገብቶ የቴፑን ዋጋ ባይከፍል ኖሮ፥ ባባ አዳሙን ወደ ፍርድ ችሎት ወስዶ ባስከፈለው ነበር። በአብዛኛዎቹ የአፍሪካ ማኅበረሰቦች፥ አንድ ወጣት አንዲት ልጃገረድ እንዲያገባ ከተፈለገ፥ ከልጂቱ ወላጆች ጋር የሚያገናኝ አማላጅ ያስፈልገዋል። ከላይ ባየነው ታሪክ፥ የአዳሙና ባባን የተቋረጠ ግንኙነት ለማደስ ኢሳ አማላጅ ሆነ።

እንደ እግዚአብሔር ቃል፥ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የተቋረጠውን ግንኙነት ሊያድስ የሚችል ብቸኛ አማላጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ጠንቋይ ይህንን ሊያደርግ አይችልም። ሙስሊም መምህር ወይም ድንግል ማርያም ሊያደርጉት አይችሉም። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው» ይላል (1 ጢሞ. 2፡5)። እግዚአብሔር አብንና ኃጢአተኛውን ሰው ዳግም ወደ ቀረበ ኅብረት ሊያመጣ የሚችለው እርሱ ብቻ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ የኃጢአት ዋጋ ሞት እንደ ሆነ ይናገራል (ሮሜ 6፡23)። በኃጢአት ላይ የሚወርደው የሞት ቅጣት በምድር ላይ የሰውን ሕይወት ጠቅላላ ክፍልና ተግባር ጎድቷል። ግለሰቦች በቃላቸውና በጠባያቸው ብልሹዎችና ክፉዎች ናቸው። ከራስ-ወዳድነትና ኃጢአታዊ አመለካከታቸው የተነሣ፥ ባሎችና ሚስቶች በየዕለቱ ይጋጫሉ። በታማኝነት ለመኖር የገቡትን ቃል ተላልፈው ዝሙት ይፈጽማሉ። ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ ይሰርቃሉ፤ ያታልላሉ። ልጆች ልክ እንደ ወላጆቻቸው ውሸታሞች በመሆን ያድጋሉ። ከትዕቢታቸውና ለብቀላ ካላቸው ጥማት የተነሣ፥ ነገዶችና ጎሳዎች እርስ በርሳቸው ይዋጋሉ። አገሮችም በተመሳሳይ ምክንያቶች ጦርነት ያካሂዳሉ። ዓለም በበሽታ፥ ሥቃይ፥ ትካዜ፥ ምሬት፥ ከዳተኛነት፥ በፈራረሱ ቤቶች፥ ጭካኔ፥ ጥላቻ፥ ጉስቁልና፥ ግድያ፥ አስገድዶ የወሲብ ግንኙነት በመፈጸም፥ በጦርነቶችና በመጨረሻም በሞት ታታስታለች፤ ይህም ሁሉ ከሰው ኃጢአት የመነጨ ነው።

የክርስቶስ መሥዋዕት

ስለ ሰው ደኅንነት መራራው እውነት፥ ሰው እንዲድን ከተፈለገ እግዚአብሔር ራሱ ለመሠቃየት መገደዱ ነው። እያንዳንዱ ሰው ለራሱ ኃጢአት የሞትን ቅጣት ስለ ተሸከመ፥ ማንም ሰው ሌሎች ሰዎች ለኃጢአታቸው የተቀበሉትን የእግዚአብሔርን ቅጣት ሊወስድ አይችልም ነበር። ሆኖም ግን፥ እኛ ልንቀበለው ስለሚገባን ኩነኔ፥ ፍርድና ቅጣት፥ ቅዱሱ፥ ንጹሑና ፍጹሙ ኢየሱስ መሠቃየት ነበረበት (ኢሳ. 53፡4-6፥ 9-10)። እግዚአብሔር ወልድ በኃጢአታችን ላይ የወረደውን የእግዚአብሔርን ቅዱስ ቁጣ ተቀበለ (1 ጴጥ. 2፡24)። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፥ እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ» ይላል (1 ጴጥ. 2፡24)።

ይህንን በማድረጉ፥ እግዚአብሔር ፍትሐዊ ዳኛና መሐሪ አዳኝ መሆኑን አሳየ። ራሱን በራሳችን ምትክ በመስቀል ላይ በመቸንከር ኃጢአታችንን ሙሉ ለሙሉ ለመቅጣት ቻለ። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው» (2 ቆሮ. 5፡21) ።

በኃጢአታችን ላይ እግዚአብሔር የሚገልጸውን አስከፊ ቁጣ በመስቀል ላይ በመሸከም፥ ኢየሱስ በኃጢአታችን ምክንያት ልንቀበለው ከሚገባን ፍርድና ቅጣት ነፃ አውጥቶናል (ሮሜ 3፡24-26)። በክርስቶስ የመስቀል ላይ ሥቃይ አማካኝነት፥ አሁን በኢየሱስ የሚያምኑ ሰዎች ዳግም ወደ እግዚአብሔር ሊቀርቡና ሊቀደሱ ይችላሉ። ይህም ክርስቶስ በተሰቀለ ጊዜ የመቅደሱ መጋረጃ በመለኮታዊ ኃይል ከላይ እስከ ታች በመቀደዱ በተምሳሌት ተገልጸአል (ማቴ. 27፡51)። የተቀደደው መጋረጃ በመቅደሱ የእግዚአብሔር ህልውና የሚገኝበትን ቅድስተ ቅዱሳን ገልጾ አሳይቶአል (ዕብ. 9፡7)። በክርስቶስ መሰቀል የእግዚአብሔር ፍትሕና የእግዚአብሔር ፍቅር ሁለቱም በአርኪ ሁኔታ ተፈጸሙ።

በአፍሪካ ባህላዊ ሃይማኖቶች መሥዋዕት የተለመደ ጭብጥ ነው። በአንዳንድ ባህላዊ የመሥዋዕት አሳቦችና መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቶስ መሥዋዕት በሚናገረው መካከል ከፍተኛ ተመሳሳይነት አለ። በባህላዊ ልማድ አራት ወይም አምስት የመሥዋዕት ምድቦች አሉ። ይህም የማርገቢያ መሥዋዕት፥ የመተኪያ መሥዋዕት፥ የማማለጃ መሥዋዕት፥ የቁርባን መሥዋዕትና የስጦታ መሥዋዕት የሚባሉትን ያጠቃልላል። ከእነዚህ መካከል የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ፥ ክርስቶስ ለኃጢአታችን ሲል ስለ ፈጸመው መሥዋዕት ያለንን ግንዛቤ ሊያሳድግ የሚችል ባህላዊ ፍች አላቸው።

በማርገቢያ መሥዋዕት ጊዜ፥ ባብዛኛው ሽማግሌዎች ከባህላዊው አምላክ ምክር ለመጠየቅ የሚገደዱበት ከፍተኛ የሆነ ችግር ወይም ቀውጢ ሁኔታ ይኖራል። ሁኔታውን ለማስተካከል ምን ሊደረግ እንደሚችል ይጠይቃሉ። ይህንን ከፍተኛ ችግር የሚፈጥሩትን ቅድመ-ትውልዶች ወይም አማልክት ቁጣ ለማርገብ (ለመመለስ) የሚችለው መሥዋዕት የትኛው ነው? ከዚያም፥ ችግሩን ለማቃለል የሚችል መሥዋዕት ይታዘዛል። ችግሩ ከፍተኛ ከሆነ፥ ብዙውን ጊዜ ውድ ዋጋ የሚያወጣ መሥዋዕት ይደረጋል። ጥንት በአንዳንድ ቡድኖች ለከፍተኛ ችግሮች የሰው መሥዋዕት ማቅረብ ያስፈልግ ነበር።

ኃጢአት የሰው ልጅ የሚጋፈጣቸውን አብዛኛዎቹን ችግሮች አስከትሏል። እንደ እውነቱ ከሆነ፥ የእግዚአብሔር ቁጣ ከኃጢአተኛው ሰው እንዲመለስ፥ የማርገቢያ መሥዋዕት የግድ በአስቸኳይ ሊቀርብ ይገባል። ይሁንና፥ የዚህን መሥዋዕት አስፈላጊነት የደነገጉት ወንዶች ወይም ሴቶች ሳይሆኑ፥ እግዚአብሔር ራሱ ነው። ሰዎች ራሳቸውን ለማዳን ሊያደርጉ የሚችሉት ነገር አልነበራቸውም። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶአልና» ይላል (ሮሜ 5፡6)።

የኢየሱስ ክርስቶስ መልካም የምሥራች ይኼ ነው፡- በክርስቶስ የማርገቢያ መሥዋዕት የተገታው፥ አንድ ችግር ወይም ቀውጢ ሁኔታ ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን የሰዎች ሁሉ ሥቃይና ኃዘን መንስኤ የሆነው ኃጢአት አልባት አግኝቷል። የኃጢአት የመጨረሻ ውጤቱ ሞት ነው (ሮሜ 6፡23)። መጽሐፍ ቅዱስ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ «በወንጌል ሕይወትንና አለመጥፋትን ወደ ብርሃን አውጥቶአል» ይላል (2 ጢሞ. 1፡10)።

በባህላዊ እምነቶች የምትክ መሥዋዕት ከመርገቢያ መሥዋዕት ከማርገቢያ በጣም ተመሳሳይ ነው። አንድ ሰው በአምላክ ቁጣ ሥር እንደ ሆነ ሲታመን፥ በዚያ በሚሠቃየው ሰው ፈንታ ምትክ ካልቀረበ ሰውዬው እስከሚሞት ድረስ መከራው ይቀጥላል። ብዙውን ጊዜ በመሥዋዕትነት የሚታዘዘው በግ ነው። ኢየሱስ ለአንዳንድ ማብራሪያ ለማይገኝላቸው አደጋዎችም ሳይቀር፥ ለሰው ልጅ ችግሮች ምንጩ ኃጢአት እንደ ሆነ ግልጽ አድርጓል (ሉቃ. 13፡2-5)። መጽሐፍ ቅዱስ ኃጢአታችን ጊዜ ጠብቆ እንደሚያገኘን ያስጠነቅቀናል (ዘኍ. 32፡23)። ኃጢአታችን እስከ ሞት ድረስ ያሠቃየናል። «ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ትሞታለች» (ሕዝ. 18፡4)።

እግዚአብሔር ለሰው ኃጢአት በክርስቶስ አማካኝነት ሙሉ የምትክ መሥዋዕት ሰጥቷል። እስራኤላውያን በግብፅ ላይ በወረደው የእግዚአብሔር ቁጣ እንዳይጠፉ የፋሲካው በግ ደም እንደታደጋቸው ሁሉ (ዘጸ. 12:5-13)፥ የእግዚአብሔር የፋሲካ በግ የሆነው የኢየሱስ ደም በኃጢአታችን ላይ ከሚመጣው የእግዚአብሔር ቁጣ ያድነናል (1 ቆሮ. 5፡7)። መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስ ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ፥ «እነሆ፥ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» ብሎአል (ዮሐ. 1፡29)!

መጽሐፍ ቅዱሳዊ የኃጢአት ፍች

በብሉይ ኪዳን ውስጥ «ኃጢአት»ን ለመግለጽ ከሁሉም በላይ ተደጋግሞ የተጠቀሰው የዕብራይስጥ ቃል «ቻታ» ("chata") የሚል ነው። የዚህም ቃል ትርጉም ምልክቱን መሳት ማለት ነው። በአዲስ ኪዳን ተመሳሳይ ፍች ያለውና «ሃማርቲያ» ("hamartia") የሚለው የግሪክ ቃል ኃጢአትን ለማመልከት አገልግሎአል። ከእነዚህ ቃላት እንደምንረዳው፥ ኃጢአት የእግዚአብሔርን የቅድስና ምልክት መሳት ማለት ነው። እግዚአብሔር እንድንሆን በሚፈልግብንና በሚጠብቅብን ደረጃ መኖር ይሳነናል። እግዚአብሔር ቅዱስና ንጹሕ ሲሆን፥ እኛ ግን ቅዱሳንና ንጹሐን አይደለንም።

እግዚአብሔር በሚፈልግብን ደረጃ ላይ እንደማንገኝ ስለምናውቅ፥ የኃፍረት ስሜት ይጫጫነንና ከእግዚአብሔር ለመሸሽ እንጥራለን። መንፈሳዊ ዕራቁትነታችንን በሁኔታዎች ወይም በሌሎች ሰዎች በማመካኘት ልንሸፍን እንሞክራለን። እንዲህ ዓይነቱ ነባር በመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችንም ላይ ደርሶአል። አዳምና ሔዋን እግዚአብሔር እንዳይበሉ የከለከላቸውን ፍሬ በበሉ ጊዜ እግዚአብሔርን መታዘዝ ተስኖአቸው ነበር። በዚህም ጊዜ ኃጢአታቸውን ከመቀበልና ለጥፋታቸው የእግዚአብሔርን ይቅርታ ከመጠየቅ ይልቅ፥ አዳም ሚስቱንና እግዚአብሔርን ሲወቅስ (ዘፍጥ. 3:11-12)፥ ሔዋን ደግሞ እባቡን ወቅሳለች (ዘፍጥ. 3:13)።

ኃጢአትን ስላደረጉ ኃፍረት ተሰምቶአቸው ከእግዚአብሔር ለመሸሸግ ሞከሩ (ዘፍጥ. 3:7-10)። ሥጋዊ ዕራቁትነታቸውን ተገንዝበው፥ ሰውነታቸውን በቅጠል ለመሸፈን ጣሩ (3:7)። ምናልባት ይህንን ያደረጉት እግዚአብሔርን ባለመታዘዛቸው ስላፈሩ ይሆናል። በተመሳሳይ ሁኔታ ወንጀል የሚፈጽሙ ሰዎች በግዴታ ወይም በተምሳሌት እጆቻቸውን ይታጠባሉ። ይህ በተወሰነ ደረጃ በደላቸውን እንደሚያስወግድ ያስባሉ። ኢየሱስ እንዲሰቀል ያዘዘው ጴንጤናዊው ጲላጦስ ይህንኑ አድርጓል (ማቴ. 27፡24)።

አዳምና ሔዋን ኃጢአት ባደረጉ ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን የቅርብ ግንኙነት አጥተዋል። የእርሱን ትእዛዝ ስለ ተላለፉ፥ ከዔድን ገነት አስወጣቸው (ዘፍጥ. 3:23)።

ባብዛኛው የአፍሪካ ማኅበረሰቦች፥ አንድ ሰው ኅሳው በሚጠብቀው ሁኔታ ካልተመላለሰ የኅሳውን ተቀባይነት ያጣና ኃፍረቱ አንገት የሚያስደፋው ሆኖ ይኖራል። ከምንም ነገር በላይ የአፍሪካ ሰዎች በራሳቸው ሕዝቦች መከበርንና ተቀባይነት ማግኘትን ይሻሉ። በመሆኑም፥ አንድ ሰው የራሱን ወገኖች እንዳሳፈረ ሲገነዘብ ከፍተኛ ኃፍረትና ተቀባይነት ማጣት ይሰማዋል። አንድ ሰው የራሱን ወገኖች ሲያሳፍር፥ ከእነርሱ ጋር የነበረውን የቅርብ ግንኙነት ያጣና ዳግም ተቀባይነት የሚያገኝበትን መንገድ ይፈልጋል።

በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የተቋረጠውን ግንኙነት ለማደስ፥ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ኃጢአታችንንና ኃፍረታችንን ተቀበለ (1 ጴጥ. 2:24)። ክርስቶስ ስለ እኛ ኃጢአት ስለ ተደረገ፥ እግዚአብሔር አብ በመስቀል ላይ ሳለ ፊቱን አዞረበት። ለዚህ ነው ኢየሱስ፥ «አምላኬ፥ አምላኬ፥ ስለ ምን ተውኸኝ?» ሲል የጮኸው (ማቴ. 27፡46)። በመስቀል ላይ፥ ኢየሱስ በእግዚአብሔር አብም በሰዎችም ተንቆ ነበር (ኢሳ. 53፡3-4)። ኢየሱስ እኛ ከእግዚአብሔር ልንቀበል የሚገባንን ኃፍረትና ተቀባይነት ማጣት ወሰደ (ኢሳ. 53፡5)። በእኛ ምትክ ተቀባይነትን አጣ። በመሆኑም፥ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ኃፍረታችንንና ተቀባይነት ማጣታችንን ስለ ወሰደ፥ እግዚአብሔር አሁን ሊቀበለንና ይቅር ሊለን ይችላል።

ሆኖም አንዳንድ ሰዎች በኅሳቸውና በቅድመ-ትውልዶቻቸው ተቀባይነት ለማግኘት ብቻ ያስባሉ። እንግዲህ ለመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን በእግዚአብሔር ይቅር መባልና ተቀባይነት ማግኘት አስፈላጊ ከነበር፥ ለእያንዳንዳችንም በተመሳሳይ ሁኔታ በእግዚአብሔር ይቅር መባሉና ተቀባይነት ማግኘቱ አስፈላጊ መሆኑን እንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች ሊገነዘቡ ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በክርስቶስ የሆኑትን ሰዎች ኩነኔ እንዳስወገደ ይናገራል (ሮሜ 8፡1)።

ከኢየሱስ ሞት የተነሣ፥ ማንኛውም ሰው አሁን ከኃጢአቱ ንስሐ በመግባትና በክርስቶስ በማመን (ዮሐ. 1፡12)፥ ከሞትና ከዘላለም ቅጣት ሊድን ይችላል (ዮሐ. 3፡16)። በክርስቶስ የሚያምኑ ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ከርሱ ጋር ይያያዛሉ። መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህ ወገኖች የ«አካሉ» ክፍል እንደ ሆኑ ይናገራል (1 ቆሮ. 12፡27)። ከእርሱ ጋር ለዘላለም በሰማይ ይኖራሉ (ዮሐ. 14፡1-3)። ክርስቶስ ኃጢአትን፥

ኃፍረትን፥ ሞትንና ሰይጣንን አሸንፎአል (ቆላ. 2፡13-15)። ወንጌሉ ይኸው ነው። የደኅንነታችን መልካም የምሥራች ይኸው ነው። ይህ የሰው ልጅ ከሰማቸው ዜናዎች ሁሉ የሚልቅ ነው!

በሕይወት ውስጥ ከደኅንነት በላይ አስፈላጊ የሆነ ነገር የለም። በዘላለሙ መንግሥት፥ ሰዎች ግን በአንደኛነት ደረጃ በጨረቃ ላይ እንደ ተራመደ፥ ወይም ታላቁ የአገር መሪ ግን እንደ ሆነ፥ ወዲም በአንድ ዘመን የትኛው ቡድን የዓለምን የእግር ኳስ ዋንጫ እንደ ወሰደ በማሰብ አይጨነቁም። ክብር፥ ምስጋናና ውዳሴ ሁሉ ደኅንነታችንን ሰፈጸመው ለኢየሱስ ክርስቶስ ይሆናል።

አንድ ሰው ኃጢአቱ ይቅር እንደ ተባለለትና እንደሚድን እንዴት ሊያውቅ ይችላል?

ይህ አስፈላጊ ጥያቄ ከደኅንነት ጋር የተያያዘ ነው። አንድ ሰው በትክክል የኃጢአት ይቅርታ እንዳገኘና ወደ መንግሥተ ሰማይ እንደሚሄድ እርግጠኛ ሊሆን ይችላል? አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት አንድ ሰው ወደ መንግሥተ ሰማይ ስለ መሄዱ እርግጠኛ ሊሆን እንደማይችል ያስተምራሉ።

አንድ ሰው በመልካም ጠባዩ የዘላለም ሕይወት ሊያገኝ አይችልም። አንድ ሰው ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ፥ የክርስትና ስም በመሰየም፥ ለድሀ በመመጽወት፥ ወይም በመጠመቅ፥ የዘላለምን ሕይወት ሊያገኝ አይችልም። ደኅንነት ማንም ሰው በዓለማዊ ሕይወቱ በሚሠራው የሚገኝ ሳይሆን የእግዚአብሔር ስጦታ ብቻ ነው (ኤፌ. 2:8-9)። ሰው የዘላለምን ሕይወት ሊያገኝ የሚችለው ከኃጢአቱ ንስሐ በመግባትና ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታውና አዳኙ አድርጎ በማመን ነው (ማር. 1፡15)። ይህንን የሚያደርጉ ሰዎች እንደሚድኑና በሰማይ ከክርስቶስ ጋር እንደሚኖሩ የተናገረው እግዚአብሔር እንጂ ሰው አይደለም። የእግዚአብሔርን ቃል ለማመን ከቻልን፥ ኃጢአታችን ይቅር እንደ ተባለና ከእግዚአብሔር ጋር በሰማይ እንደምንኖር ዋስትና ሊኖረን ይችላል።

እንግዲህ ስለ ደኅንነት እርግጠኛ መሆን ካልተቻለ፥ ለምንድን ይሆን ኢየሱስ ስለ ደኅንነት ዋስትና እጅግ ጠንካራ ዓረፍተ ነገሮችን ያስቀመጠው? (ለምሳሌ፥ ዮሐ. 3፡16፤ 5፡24፤ 6፡37፤ 10፡9፤ ራእይ 3፡20)። ለመሆኑ እግዚአብሔር ይዋሻል? እግዚአብሔር የሚሰጠንን የተስፋ ቃል እናምናለን ወይስ አናምንም? እጅግ የታወቀው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ፥ «በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው

እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንዲያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና» ይላል (ዮሐ. 3፡16)። የኢየሱስን ቃላት ለማመን ከቻልን፥ የደኅንነት ዋስትና ሊኖረን ይችላል። ሌላም በመንፈስ ቅዱስ ሕያው ለሆነ (ዳግም ለተወለደ) ክርስቲያን የተሰጠ የደኅንነት ዋስትና አለ። ይህም በክርስቲያኑ ልብ ውስጥ የሚሰማው የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል» ይላል (ሮሜ 8፡16)።

ሐ. የደኅንነት ፍች ምንድን ነው?

ደኅንነት የሚለው ቃል ነፃ መውጣትን ወይም ከአደጋ መትረፍን ያመለክታል። በመሆኑም፥ መዳን ማለት ከአንድ ነገር መትረፍ ማለት ነው። ከእሳት አደጋ መዳን ማለት በአደጋው ተቃጥሎ ከመሞት መትረፍ ማለት ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ደኅንነት ምን ዓይነት ነፃ መውጣት ወይም መትረፍን ያመለክታል? የክርስቶስ ማዳን ማለት ከኃጢአትና ከኃጢአት አስከፊ ውጤቶች መዳን ማለት ነው። ይህም እግዚአብሔር ብቻ ሊፈጽመው የሚችል መለኮታዊ ተግባር ሲሆን፥ ከዚህ ቀደም ሆነ፥ አሁን ወይም ወደፊት ከሚሠራው ማናቸውም ኃጢአት መዳን ማለት ነው።

ክርስቲያኖች አሁን ከኃጢአት ኩነኔና ኃጢአታቸው ሊያስከትለው ከሚገባው ቅጣት ነፃ ወጥተዋል ማለት ነው (ሮሜ 8፡1)። አሁን በአእምሮአቸው፥ በስሜታቸው፥ በጠባያቸውና በግንኙነታቸው፥ ከኃጢአት ኃይል ነፃ ሊወጡ ይችላሉ ማለት ነው (ሮሜ 6፡14)። ወደፊትም ኃጢአት በአካላቸውና በዓለምም ላይ ጭምር ከሚያስከትለው ጉስቁልና ነፃ ይሆናሉ ማለት ነው (ሮሜ 8፡21-23)።

ደኅንነት ከዚህ ቀደም

ኢየሱስ በሞቱ እኛንም ለሞት ቅጣት ከሚዳርግ ኃጢአት አድኖናል (ሮሜ 6፡23)። ከክርስቶስ ጋር በእምነት ከተጣበቅን፥ እግዚአብሔር ለኃጢአታችን አይኮንነንም፤ አይቀጣንምም (ሮሜ 8፡1)። በኃጢአት ላይ ከሚወርደው አስፈሪ የእግዚአብሔር ቁጣ ድነናል (ሮሜ 5፡9)። በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት ነጽተን ጻድቃን ናችሁ ተብለናል (2 ቆሮ. 5፡21)። ለዚህ ነው አሁን እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር ሊል

የሚችለው። በራእይ 1፡5፥ «ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን» የሚል ዓረፍተ ነገረ እናገኛለን። ይህ ከዚህ ቀደም የተከናወነ ደኅንነት ነው (1 ቆሮ. 6፡11)።

ደኅንነት ባሁኑ ጊዜ

ኃጢአታችን ይቅር በሚባልበት ጊዜ እንኳ ገና ችግሮች ይኖሩብናል። አሁንም የኃጢአት ተፈጥሮ ባለው ሥጋና ደም ውስጥ እንኖራለን። ስለዚህስ ምን ማድረግ አለብን? ወደ ቁልቁል በሚስበን ኃጢአታዊ ተፈጥሮአችን ላይ ድል ልንቀዳጅ የምንችለው እንዴት ነው? በትንሣኤውና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል፥ ኢየሱስ በሕይወታችን የኃጢአትን ኃይል የምናሸንፍበትን መንፈሳዊ ብርታት ሰጥቶናል (ሮሜ 8፡11-13)። የእግዚአብሔርን እርዳታ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በእምነት ልንቀበል እንችላለን (ሮሜ 8፡11፤ ገላ. 3፡14)። ይህንኑ ድል ለማግኘት፥ ሰውነታችንንና አእምሮአችንን ለኃጢአታዊ ተፈጥሮአችን ከማስገዛት ይልቅ (ገላ. 5፡13-16)፥ ለክርስቶስ ማስረከብ አለብን (ሮሜ 12፡1-2)።

ክርስቲያን በኃጢአት ላይ ድልን ለመቀዳጀት ሁነኛ ውጊያ ይገጥመዋል። ይህ ውስጣዊ ትግል ክፍተኛ ቢሆንም (ገላ. 5:17)፥ ለሥጋችን ከመገዛት ለእርሱ ከተገዛን እግዚአብሔር በመንፈሱ ይረዳናል (ሮሜ 8:12-13)። «ድል» ውጊያን ስለሚያመለክት፥ ጦርነቱ በአሸናፊነት ተጠናቋል ማለት ነው።

ለዚህ ድል ምሥጢሩ በክርስቲያን ውስጥ በሚኖረው መንፈስ ቅዱስ የሚሠራው የክርስቶስ የትንሣኤ ኃይል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፥ ክርስቶስ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው እርሱ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ፥ ለሚሞተው ሰውነታችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል» ይላል (ሮሜ 8፡11)። ይህ አሁን ከኃጢአት መዳን ነው (ሮሜ 5:10) ።

ደኅንነት በሚመጣው ጊዜ

ኢየሱስ ሲመለስና መንግሥቱን ሲመሠርት፥ ከማንኛውም ኃጢአትና በዓለም ላይ ከሚያስከትላቸው አስከፊ ውጤቶቹ ነፃ ያወጣናል (ሮሜ 8፡18-25)። በዚያ የወደፊት ቀን፥ ደኅንነታችን ሙሉ ይሆናል። የክርስቶስን ዓይነት የትንሣኤ አካል ይኖረናል (1 ተሰ. 4፡16-17፤ ፊልጵ. 3:20-21)። ዓለምም ራሷ እንኳ ፍጹም ሰላምና ውበት ወዳለበት ስፍራነት

ትቀየራለች (ኢሳ. 65፡17-25፤ ሮሜ 8፡21)። በዚህም ምክንያት ጳውሎስ፥ «ካመንንበት ጊዜ ይልቅ መዳናችን ዛሬ ወደ እኛ ቀርቦአልና» ብሏል (ሮሜ 13፡11)። ይህ ወደፊት ከኃጢአት መዳን ነው (1 ጴጥ. 1:5)።

መ. የደኅንነት ውጤቶች ምንድን ናቸው?

ከኃጢአቱ ንስሐ ገብቶ ኢየሱስን እንደ አዳኙና ጌታው አድርጎ በተቀበለው ሰው ሕይወት ምን ይከሰታል? (ማር. 1፡15፤ ዮሐ. 1፡12፤ የሐዋ. 20፡21)።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የደኅንነትን ውጤቶች የሚገልጸው ቁልፍ ቃል «አዲስ» የሚለው ነው። ጳውሎስ፥ «ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል» ሲል ጽፎአል (2 ቆሮ. 5፡17)። ፍጹም አዲስ ብስክሌት፥ ፍጹም አዲስ ልብስ፥ ወይም ፍጹም አዲስ የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃ አይተህ ታውቃለህ? ነገሮች አዲስና ብልሽት ያልነካቸው ሆነው ሲታዩ በጣም ውብ ናቸው። ደኅንነትም እንዲሁ ነው። አዲስ የሕይወት ጥራት፥ አዲስ የኑሮ ብርታት፥ አዲስ ተስፋ፥ አዲስ ደስታ፥ አዲስ የምስጋና መዝሙር፥ አዲስ ሰላም፥ በክርስቶስ የሚገኝ የተትረፈረፈ ሕይወት ተሰጥቶናል (ዮሐ. 10፡10)። በዚህ በክርስቶስ በሚገኘው አዲስ ሕይወት የተቀበልናቸው አንዳንድ እጅግ አስፈላጊ ነገሮች ቀጥሎ ተመልክተዋል፦

ይቅርታ - ለፈጸምናቸው ኃጢአቶች ከእንግዲህ አስጨናቂውን ዋጋ አንከፍልም ማለት ነው። ባባ የቴፑ ዋጋ በኢሳ በኩል ስለ ተከፈለለት፥ አዳሙን ይቅር ከማለቱም በላይ ጉዳዩንም ዳግም ላያነሣው ረስቶታል። ኢየሱስ ለኃጢአታቸው ሙሉውን ዋጋ ስለ ከፈለላቸው፥ በክርስቶስ የሚያምኑ ሰዎች ለኃጢአታቸው ሁሉ ይቅርታ አግኝተዋል (ኤፌ. 1፡7)።

ዕርቅ - የተቋረጠው ግንኙነት መፈወስ ማለት ነው። ኢሳ ከፈጸመው ተግባር የተነሣ፥ በአዳሙና በባባ መካከል የተቋረጠው ግንኙነት ተጠግኗል። ባለትዳሮች ሲለያዩና ከዚያ በኋላ ተመልሰው ወደ አንድነት ሲመጡ ታርቀዋል እንላለን። በክርስቶስ የሚያምኑ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ታርቀዋል። ከኃጢአታቸው የተነሣ ከተለዩት በኋላ፥ ከእግዚአብሔር ጋር ወዳለው የፍቅር ግንኙነት ተመልሰዋል ማለት ነው (ቆላ. 1፡21-22፤ ሮሜ 5፡10)።

መቤዠት - ይህ ከጥንታዊ የባርያ ንግድ የተወሰደ ቃል ነው። ባርያ ለሽያጭ ሲቀርብ በባለቤትነት ለመውሰድ የሚፈልገው ሰው፥ ገንዘብ ከፍሎ መግዛት (መቤዠት) የግድ ያስፈልገው ነበር። እኛ የኃጢአት ባርያዎች ሆነን ለሞት የተኮነንን ነበርን። ኢየሱስ ለእግዚአብሔር አብ ፍትሕ በተከፈለው በራሱ ደም ለራሱ ገዛን (ተቤዠን) (ዕብ. 9፡11-12)። ከዚህ የተነሣ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ከእንግዲህ የራሳችንን ሳንሆን የእግዚአብሔር እንደ ሆንን ይናገራል። የራሱን ደም በሚያስከፍል ከፍተኛ ዋጋ በክርስቶስ ተገዛን (1 ቆሮ. 6፡20፤ ኤፌ. 1፡7፤ ራእይ 5፡9)።

ጽድቅ - በአንድ በሆነ ክስ ለተወነጀለ ሰው በሕግ «ጥፋተኛ አይደለህም» የሚል አወጃ ግለት ነው። እኛም በእግዚአብሔር የፍርድ ችሎት ፊት ለኃጢአታችን «ጥፋተኞች አይደላችሁም» የሚል አወጃ ተደርጎልናል (ሮሜ 5፡1፥ 9)። ይህም የሆነው ኢየሱስ በመስቀል ላይ ኃጢአታችንን ስለ መሰደዱና በእግዚአብሔር አብ ለኃጢአታችን ጥፋተኛ ስለ ተባለ ነው (2 ቆሮ. 5፡21)። ስለ ሆነም፥ እርሱ የሞት ፍርዳችንን በመቀበል ተሠቃየ። እንግዲህ፥ የምንሠቃይበት የሞት ፍርድ ስለ ተነሣልን፥ እግዚአብሔር «ጥፋተኞች አይደላችሁም!» ሲል አውጆአል። በዚህም ጽድቅን አገኘን!

እግዚአብሔር ራሱ ጥፋተኞች አይደላችሁም ሲል ስላወጀ፥ ሰይጣንን ጨምሮ ማንም በእግዚአብሔር ፊት በጥፋተኝነት ሊከሰን አይችልም (ሮሜ 8፡33)። ከእንግዲህ፥ ለኃጢአታችን በእግዚአብሔር ፊት እንኮነንም(ሮሜ 8:1)። አንዳንድ ሰዎች ጸድቃችኋል የሚለውን ቃል «ልክ ኃጢአት ሠርቼ እንደማላውቅ ሁሉ» ስሚል አባባል ይረዱታል።

ማስተሰረያ - በኃጢአታችን ላይ እግዚአብሔር የሚያወርደውን ቁጣ ለማርካት ወይም ለመመለስ የሚደረግ ነው። በባባና በአዳሙ ታሪክ እንደ ተመለከትነው፥ ኢሳ የቴፑን ሙሉ ዋጋ በመክፈል፥ ባባ በአዳሙ ላይ የያዘውን ቁጣ አስፍቋል (አስተሰርዮአል) ። በሌላ አባባል፥ ባባ በአዳሙ ላይ በጥፋተኝነቱ ያደረበትን ንዴት አብርዶል። በባህላዊ እምነቶች የመናፍስትን ቁጣ ለማርገብ (ለመመለስ) የተወሰኑ መሥዋዕቶች ይቀርባሉ። ከእንግዲህ፥ ክርስቲያኖች እንዲህ ዓይነት መሥዋዕቶችን ማቅረብ አያስፈልጋቸውም። የክርስቶስ ደም እግዚአብሔር በኃጢአታችን ላይ የሚያወርደውን ቁጣ ስለሚያረካ (ሮሜ 3፡24-25፤ 1 ዮሐ. 2፡2)፥

በዘላለሙ መንግሥት እግዚአብሔር ራሱ ይቅር ያለውን ክርስቲያን ሊኮንን የሚችል ማንም የለም (ሮሜ 8:33-34)።

አዲስ ልደት - በክርስቶስ በምናምንበት ጊዜ አንድ አስደናቂ ነገር ይፈጸማል። ከመንፈሳዊ ሞት ወደ መንፈሳዊ ሕይወት እንሻገራለን (ኤፌ. 2:1፥ 4-5)። ኢየሱስ፥ «እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል እርሱም አሁን ነው፤ የሚሰሙትም በሕይወት ይኖራሉ» ብሏል (ዮሐ. 5:25)። ኢየሱስ ስለ ዳግም ልደት ተአምር እየተናገረ ነበር። ጥቂት ቆየት ብሎም አንድ ቀን የሞቱትን ሁሉ ወደ ሕይወት እንደሚያመጣ ተናግሯል (ዮሐ. 5:28-29)።

ይህም መለወጥ፥ «መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ» ተብሎ ተጠርቷል (ቲቶ 3:5)። በዳግም ልደት፥ ሥላሴው አምላክ ራሱ በክርስቲያኑ ውስጥ ለመኖር ይመጣል (ዮሐ. 14:16-17፥ 23፤ ሮሜ 8:9)። ይህ ምንኛ የሚያስደንቅ ነገር ነው! በዳግም ልደት አማካኝነት፥ እግዚአብሔር በትክክል በሕዝቡ መካከል ለመኖር ይመጣል፤ ያለ ዳግም ልደት፥ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ልንገባና (ዮሐ. 3:5) የክርስቶስ ልንሆን አንችልም (ሮሜ 8: 9)።

በክርስቲያኑ ሕይወት ውስጥ የእግዚአብሔር ማደር ፍጹም ለውጥ ያስከትላል። እርሱ በሕይወታችን ውስጥ በመኖሩ፥ ኢየሱስ ቃል የገባልንን አዲስና የተትረፈረፈ ሕይወት ለመኖር ኃይልን እንለብሳለን (ዮሐ. 10:10)። የእግዚአብሔር መገኘት በፈተናና በኃጢአተኛ ዝንባሌዎቻችን ላይ ድልን እንድንቀዳጅ ሊረዳን ይችላል። ለዚህ ነው የክርስቶስ ወንጌል ክፉ ሰዎችን ወደ መልካምነት የሚለውጠው። ለዚህ ነው ባለፉት 2000 የታሪክ ዓመታት እንደ ተመሰከረው ለተጣሉት፥ ለተገዱና ለተቸገሩ የዓለም ሕዝቦች እርዳታ የሚለግሱት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በአብዛኛው በክርስቲያኖች የተጀመሩት። ዳግም መወለድ ማለት በእግዚአብሔር መንፈስ ሕያው መሆን ማለት ነው!

ጸጋ - በክርስትና መዝገበ ቃላት ውስጥ ከሚገኙ እጅግ ውብ ቃላት አንዱ ነው። ቃሉ «በነፃ መስጠት» ከሚል አሳብ ጋር የተዛመደ ነው። ጸጋ፥ እግዚአብሔር በተለይም በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ለሰው ልጆች ያሳየውን ያልተገባ ቸርነት ያመለክታል። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ጸጋው

በእምነት አድኖአችኋልና» ይላል (ኤፌ. 2፡8)። በሌላ አባባል፥ የዳንነው ሙሉ ለሙሉ በማይገባንና ዳሩ ግን በክርስቶስ በኩል በተሰጠን ታላቅ የእግዚአብሔር ፍቅር፥ ምሕረትና በጎነት ነው ማለት ነው። ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ፥ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ልናገኝና ሕዝቦቹ ልንሆን እንችላለን። ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ፥ የዘላለም ሕይወት ሊኖረን ይችላል። አንዳንድ ሰዎች ጸጋ የሚለውን ቃል፥ በክርስቶስ ኪሳራ የተገኘ የእግዚአብሔር ባለጸግነት ("God's Riches At Christ's Expense") በማለት ይተረጉሙታል።

በተጨማሪም፥ ጸጋ እግዚአብሔር ለሰው ዘር፥ በተለይም ለገዛ ሕዝቡ የሚያሳያቸውን ሌሎች የቸርነት ተግባራት ሁሉ ያጠቃልላል። ይህ በዕለታዊ ሕይወታችን ውስጥ የሚፈጸም የእግዚአብሔር ፍቅር፥ በጎነትና እርዳታ ነው። ዝናብ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሁሉ የሚሰጠው ተራ ጸጋው ነው። ብርታት፥ መጽናኛና በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ የሚፈጸም የመንፈስ ቅዱስ እገዛ፣ እንዲሁም ለጸሎቶቻችን የምናገኛቸው ምላሾች ሁሉ እግዚአብሔር ለዳኑት ሕዝቦቹ የሚሰጣቸው ልዩ ጸጋዎች ናቸው።

የማደጎ ልጅነት - ብዙውን ጊዜ እውነተኛ ወላጆቻቸው በመሞታቸው ምክንያት ወላጆች የሌሉአቸው ልጆች በማደጎነት ይወሰዳሉ። ወላጅ የሌለው ልጅ በማደጎነት ሲወሰድ፥ የልጁ ወይም የልጂቱ አባት ያልነበረው ሰው አዲስ የአባትነት ሚና ይጫወታል። ወላጅ የሌለውም ልጅ የአዲሱ ቤተሰብ ሕጋዊ አባል ይሆናል። የክርስቶስም ደኅንነት እንዲሁ ነው። እግዚአብሔር በማደጎ ልጅነት ሊያሳድገን ስለ ፈቀደ፥ አዲሱ አባታችን ይሆናል (ሮሜ 8፡15-16፤ ኤፌ. 1፡5)። በመሆኑም፥ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ የእግዚአብሔር ልጆች እንሆናለን (1 ዮሐ. 3፡1-2)። ከሰይጣን መንግሥትም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንሻገራለን (ቆላ. 1፡12-13)።

ውርስ - የእግዚአብሔር ልጆች ስለ ሆንን፥ የእግዚአብሔር ቤተሰብ በሆነችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመልካም እድልና የኃላፊነት ሚና ይኖረናል። ስለ ቤተ ክርስቲያን በምንነጋገርበት ክፍል በእነዚህ እድሎችና ኃላፊነቶች ላይ በይበልጥ እናተኩራለን። አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ስለ ሆንን፥ አንድ ቀን የእግዚአብሔር የሆነውን ሁሉ ከክርስቶስ ጋር እንወርሳለን (ሮሜ 8፡16-17፤ ኤፌ. 1፡11፥14)። ይህ ውርስ ምን ያህል ይሆን? ሁሉም የእግዚአብሔር ስለ ሆነ፥ የሁሉም ነገር ተካፋዮች እንሆናለን (1 ቆሮ. 3፡21-23)! ሰብአዊ አእምሮአችን ይህንን ሊገነዘብ

ባይችልም፥ በምናባችን ከምንገምተው ከማንኛውም ነገር እንደሚሻል እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን (1 ቆሮ. 2፡9፤ ራእይ 21፡6-7)።

ጸሎት - በአንድ ወቅት በጥርጣሬ ወይም በጭንቀት ጸልየን ይሆናል፤ ወይም ደግሞ ጭራሹንም አልጸለይንም ይሆናል። አሁን ግን እግዚአብሔር ለእርዳታ የምናሰማውን ጩኸት ሰምቶ እንደሚመልስ ሙሉ ለሙሉ እርግጠኞች ሆነን፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ወደ ፊቱ ልንቀርብ እንችላለን (ዮሐ. 16፡23-24)። ስለ አንድ ጉዳይ የአገርህን የመንግሥት ባለሥልጣን ለማነጋገር ብትፈልግ፥ አይሳካልህም ይሆናል። ቢሳካልህም እንኳ ከረዥም ጊዜያት በፊት ቀጠሮ መቀበልና የብዙ ባለሥልጣናትን ቢሮ ማለፍ ይኖርብሃል። እንዲህም ሆኖ፥ በቀጠሮ ከተጣበበው ጊዜው በጣም ጥቂት ደቂቃ ብቻ ሊሰጥህና በዚያም ላይ ላይረዳህ ይችላል።

የሁሉም ባህልና ሃይማኖት ተከታዮች ይጸልያሉ፤ ይሁንና፥ ከእግዚአብሔር ፈቃድ አኳያ ሲጸልዩ ጸሎታቸው እንደሚመለስ ሙሉ ዋስትና ያላቸው ክርስቲያኖች ብቻ ናቸው (1 ዮሐ. 5፡14-15)። ክርስቲያኖች እንደ መሆናችን፥ በኢየሱስ ስም በመጸለይ በማንኛውም ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ልንቀርብ እንችላለን (ዮሐ. 16፡24)። እንዲያውም፥ በችግራችን ጊዜ የሚረዳንን ኃይል ለመቀበል በድፍረት ወደ እግዚአብሔር ዙፋን እንድንቀርብ የሚያበረታታ ቃል ተሰጥቶናል (ዕብ. 4፡16)። ክርስቲያኖች እንደ መሆናችን፥ የክርስቶስን ስም ተሸክመናል። እኛ የእርሱ ነን። የክርስቶስም ስለ ሆንን፥ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር በሁሉም ጊዜ በጸሎት ወደ እርሱ እንድናመጣው ያደፋፍረናል (ኤፌ. 6፡18፤ ፊልጵ. 4፡6)። እግዚአብሔር ጸሎታችንን ለመመለስ ፍላጎቱም ኃይሉም አለው (ማር. 11፡22-24)፤ ይሁንና፥ እኛ እንደ ፈቃዱ መጸለይን መማር አለብን(1 ዮሐ. 5:14-15)። መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ ልናውቅ እንችላለን (ዮሐ. 15፡7)።

የዘላለም ሕይወት - ይህ የአንድ ስፍራ ስያሜ ሳይሆን፥ ከኢየሱስ ጋር እንደ አዳኝና ጌታ እንዲሁም ከእግዚአብሔር አብ ጋር እንደ አባት የሚኖረንን ግላዊ ግንኙነት የሚያመለክት ነው (ዮሐ. 17፡3)። የዘላለም ሕይወት የሚጀምረው እምነታችንን በክርስቶስ ላይ ከጣልንበት ጊዜ ጀምሮ እንጂ፥ ገና ወደፊት ስንሞት የሚደርስ አይደለም። ወደ በኋላ ሥጋችን የሚሞት ቢሆንም፥ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ግን እስከ

አዲሱ ቤታችን ግለትም እስከ መንግሥተ ሰማይ ድረስ ይቀጥላል (ዮሐ. 14፡3)!

ቤተ ክርስቲያን - እምነታችንን በክርስቶስ ላይ በምንጥልበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ተብላ የምትጠራው የአካሉ ክፍል እንሆናለን (ቆላ. 1፡18፥ 24)። አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ሳትሆን፥ የሕዝቦች ቡድን ነች። ቤተ ክርስቲያን በምድርና በሰማይ እምነታቸውን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያደረጉ የሁሉም ሰዎች ጥርቅም ነች (ገላ. 3፡26-27፤ ኤፌ. 3፡15)። በክርስቶስ ከግመናችን የተነሣ፥ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ስንጠመቅ፥ የክርስቶስ አካል ክፍሎች እንሆናለን (1 ቆሮ. 12፡13)። ጌታችን እንድንፈጽመው ያዘዘን የውኃ ጥምቀት (ማቴ. 28፡19)፥ በክርስቶስ በግመናችንና እግዚአብሔር በውስጣችን በፈጸመው የዳግም ልደት ተግባር የተነሣ በሕይወታችን የሚከሰተውን መንፈሳዊ ለውጥ የሚያሳይ ውጫዊ ምልክት ነው። በመሆኑም የውኃ ጥምቀት በእምነት ከክርስቶስ ጋር እንደ ተባበርንና የቤተ ክርስቲያን አካል እንደ ሆንን በይፋ ከመመስከር ባሻገር፥ ሊያድነን ወይም የቤተ ክርስቲያን አካል ሊያደርገን አይችልም።

ሠ. ደኅንነት ከአፍሪካ ችግሮች ጋር የሚዛመድባቸው አንዳንድ መንገዶች የትኞቹ ናቸው?

የኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በዓለም ሁሉ የሚገኙትን ሰዎች እጅግ አንገብጋቢ መንፈሳዊ ፍላጎቶች ያሟላል። አወቁትም አላወቁት የሰዎች ሁሉ ትልቁ ችግር ከእግዚአብሔር ዘንድ የኃጢአት ይቅርታ ማግኘትና ግላዊ ግንኙነት መመሥረቱ ነው። ይህ ይቅርታና ግንኙነት ደግሞ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ተስተካክሏል። ሞቱ ለኃጢአታችን ይቅርታ አስገኝቶልናል። ይቅርታው ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ አመቺ መንገድ ስለ ከፈተ፥ ሰዎች አሁን እግዚአብሔርን እንደ አባታቸውና አረኖቸው አድርገው ሊቀርቡት ይችላሉ።

እያንዳንዱ አፍሪካዊ ከእግዚአብሔር ጋር ከታረቀና ከክርስቶስ ጋር እንደ ጌታውና አዳኙ የግል ግንኙነት ከመሠረተ፥ አፍሪካውያን የሚሠቃዩባቸው ጥልቅ ችግሮች በተትረፈረፈ መልኩ እልባት ያገኛሉ (ዮሐ. 10፡10)። ለምሳሌ፥ በግጎበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት በግግኘቱ ረገድ ያለውን ችግር እንውሰድ። ምድራዊ ቤተሰብ የሚመሠረትበት ግጎበረሰብ አስፈላጊ ቢሆንም፥ ከዚህ ምድራዊ ሕይወት አይዘልቅም። ከዚህ በተቃራኒ፥

የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝቦች ማኅበረሰብ (ቤተ ክርስቲያን) ለዘላለም ይኖራል። በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ከእግዚአብሔር ጋር የግል ግንኙነት ስንመሠርት፥ የዚህ የእግዚአብሔር ሕዝቦች የሚገኙበት ዘላለማዊ ማኅበረሰብ አካላት እንሆናለን። እግዚአብሔር በዘላለማዊው የተስፋፋ ቤተሰቡ ውስጥ ይቀበለንና ለዘላለም በመንግሥቱ ሰማይ ከሚኖሩትና በክርስቶስ እህቶችና ወንድሞች ከሆኑት ወገኖች ጋር ኅብረት እናደርጋለን። ማንኛውም ምድራዊ ማኅበረሰብ ይህንኑ ከእግዚአብሔርና ከሕዝቡ ጋር የሚኖር ዘላለማዊ ተቀባይነት ሊያጎናጽፈን አይችልም።

በአፍሪካ ከከፉ መናፍስተ ኃይላት ጥበቃ ለማግኘት ሰዎች የሚቸገሩበትን ሁኔታ ተመልከት። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ፥ በአጽናፈ-ዓለሙ ሁሉ እጅግ ወደ ላቀ የሥልጣንና ኃይል ደረጃ ከፍ ከፍ ያለውን የእርሱን ጥበቃና ዋስትና ለሁሉም ክርስቲያን ይሰጣል (ማቴ. 28፡18፤ ኤፌ. 1:20-22፤ ፊልጵ. 2፡8-9)። ጠንቋይ፥ አስማተኛ፥ ቅድመ-ትውልዳዊ መንፈስ፥ አጋንንት ወይም ሰይጣንም ራሱ ቢሆን የነገሥታትን ንጉሥ ሊገዳደር አይደፍርም። በአጽናፈ-ዓለሙ ሁሉ የሚገኙ ፍጥረታት ሁሉ የክርስቲያኖች ታላቅ አምላክና አዳኝ ለሆነው ለኢየሱስ ክርስቶስ በመገዛት በፍርሃት መስገድ አለባቸው (ፊልጵ. 2፡10፤ ቲቶ 2፡13)። ክርስቲያን ከጠንቋዮችና ከከፉ መናፍስት ፍራቻ ሙሉ በሙሉ ነፃ ሊወጣ ይችላል።

እስቲ በሕይወት ለመቆየት ያለውን የመሻት ኃይል ተመልከት። መጽሐፍ ቅዱስ ሕይወት የእግዚአብሔር ስጦታ እንደ ሆነ ይናገራል (ዘካ. 12፡1፤ የሐዋ. 17፡25)። ሕይወት የእግዚአብሔር ስጦታ ከሆነና ክርስቲያኑ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆነ (1 ዮሐ. 3፡2)፥ እግዚአብሔር የራሱን ልጆች በሕይወት ሙሉ ስጦታ ሊባርክ እንደሚፈልግ መታመን አለበት። ኢየሱስም፥ «እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ» ብሏል (ዮሐ. 10፡10)። ክርስቲያኖች አዲስ ልደትን ሲቀበሉ (ከእግዚአብሔር ሲወለዱ)፥ ሕይወት-ሰጪ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተሰጥቶአቸዋል (ቲቶ 3፡5)። ኢየሱስ ክርስቶስን ከሙታን ያስነሣው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነበር (ሮሜ 8፡11)። ያ የላቀ የሕይወት ኃይል ነው። አንድ ሰው ሕይወት ሰጪውን ራሱን በልቡ ከመያዝ የባለጠ ምን ኃይል ሊኖረው ይችላል (ዮሐ. 14፡16-17)? እንደ እውነቱ ከሆነ፥

የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የአፍሪካን ክርስቲያኖች ዓይነተኛ ፍላጎቶች ያሟላል።

ረ. ቅድስና ምንድን ነው?

ቅድስና ለተቀደሰ ዓላማ የመለየት ሂደት ነው። በብሉይ ኪዳን፥ የተወሰኑ ዕቃዎች በመገናኛው ድንኳን የአምልኮ ሥርዓቶችን ለማቅረብ ለተለየ አገልግሎት ሲመረጡ፥ እንደ ተቀደሱ ይገለጽ ነበር (ዘሌ. 8፡10፤ ዘኍ. 7፡1)። በብሉይ ኪዳን፥ ዕቃዎችን (ዘሌ. 8፡15)፥ አልባሳትን (ዘሌ. 8፡30)፥ ሕዝቦችን (ዘሌ. 8፡23-24፤ ዘኍ. 8፡17)፥ ለእግዚአብሔር ለመለየት (ለመቀደስ) ደም ወይም የቅባት ዘይት ያገለግሉ ነበር። ሰባተኛው ቀን እንኳ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ነበር (ዘፍጥ. 2፡3፤ ዘጸ. 20፡11)። በቅድስና ውስጥ አስፈላጊው አሳብ ከዓለም ለእግዚአብሔር መለየት ነው። በዘሌዋውያን 20፡26 እግዚአብሔር፥ «እኔ እግዚአብሔር ቅዱስ ነኝና፥ ለእኔም ትሆኑ ዘንድ ከአሕዛብ ለይቻችኋለሁና ቅዱሳን ትሆኑልኛላችሁ» ብሏል።

ስንቀደስ፥ ከዓለም ተለይተን የእግዚአብሔር ቅዱሳን ሕዝቦች እንሆናለን። ይበልጥ እየተቀደስን ስንመጣ ይበልጥ እግዚአብሔርን እየመሰልን እንሄዳለን። ክብሩን ማንጸባረቅ እንጀምራለን። እግዚአብሔርም የሚፈልገው ይህንኑ ነው (1 ጴጥ. 2፡9)። ሰዎች ልክ እንደ ራሱ ቅዱሳን እንዲሆኑ ይፈልጋል (1 ጴጥ. 1፡15-16)። ለዚህም ነው በመጀመሪያ ሰውን በአምሳሉ የፈጠረው (ዘፍጥ. 1፡27)። እግዚአብሔር አምሳሉን በሕዝቡ ውስጥ ለማደስ ይፈልጋል (ኤፌ. 4፡24፤ ቲቶ 2፡14)። ይህንንም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚያደርግበት ሂደት መቀደስ ይባላል (2 ተሰ. 2፡13)። ስለ ሆነም፥ መቀደስ በክርስቲያን ሕይወት የመንፈስ ቅዱስ የመለወጥ ተግባር ሲሆን፥ የባሕርይ ቅድስና ደግሞ የዚሁ ተግባር ውጤት ነው። እንደ ደኅንነት ሁሉ፥ የመቀደስ ሂደት የበፊት፥ ያሁንና የወደፊት ገጽታዎች አሉት።

ቅድስና ከዚህ ቀደም

የከዚህ ቀደሙ ቅድስናም ቢሆን እግዚአብሔር በአሁኑ ጊዜ ከክርስቶስ ጋር በማዛመድ ከሚመለከትበት ሁኔታ ጋር የተያያዘ ነው። በክርስቶስ ስላመንን፥ እግዚአብሔር አብ አሁን በመንፈሳዊ ሁኔታ በክርስቶስ ውስጥ እንደ ሆንንና ከዚህም የተነሣ ከዓለም እንደ ተለየን አድርጎ ይመለከተናል

(ሮሜ 6፡3-6፤ ቆላ. 3፡3)። አሁን እኛን በሚመለከትበት ጊዜ ከእኛ ይልቅ ቅዱስ የሆነውን ክርስቶስን ስለሚያይ፥ ቅዱሳን አድርጎ ያየናል። ከዚህም የተነሣ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስ «ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ጽድቅ ቅድስናም ቤዛነትም» እንደ ሆነልን ይናገራል (1 ቆሮ. 1፡30)። ኢየሱስ ራሱ ቅድስናችን ነው። እግዚአብሔር በክርስቶስ ቅዱሳን እንደ ሆንን አውጇአል (ዕብ. 10፡10)።

በዚህ ምክንያት፥ መጽሐፍ ቅዱስ ቀድሞውኑ እንደ ተቀደስን ይናገራል (1 ቆሮ. 6፡11)። ምንም እንኳ በዕለታዊው ልምምዳችን ውስጥ የተሟላ እውነታ ባይሆንም፥ ይህ በእግዚአብሔር ፊት ሕጋዊ ስፍራችን ነው። በክርስቶስ ደም ስለ ተቀደስን፥ አሁን ለእግዚአብሔር ተለይተናል (ሮሜ 5፡9)።

ቅድስና ባሁኑ ጊዜ

ባሁኑ ጊዜ፥ ቅድስናችን ዕለት በዕለትና በዝግታ በባሕርያችን ይበልጥ እየተቀደስን ማደግ ነው። በባባና በአዳሙ ታሪክ፥ ኢሳ የቴጵን ዋጋ ለማግኘት እንደማይፈልግና ዳሩ ግን አዳሙ መንገዱን እንዲያስተካክል መሻቱን ገልጾአል። በክርስቶስ ያገኘነውም ደኅንነት እንዲሁ ነው። ኢየሱስ ላደረገልን ነገር ከቶውንም ዋጋ ልንከፍለው አንችልም። ይልቁንም፥ ኢየሱስ መንገዳችንን እንድንቀይር፥ ከዕለታዊ ሕይወታችን ኃጢአትን እንድናስወግድ ይሻል (ቆላ. 3፡5-9)። መልካሙን ለማድረግ እንድንጀምር ይፈልጋል (ቆላ. 3፡12-14፤ ቲቶ 2፡14)። ይህ ዕለት በዕለት ይበልጥ ቅዱስ እየሆኑ የመሄዱ ሂደት የአሁን (ወይም አዳጊ) ቅድስና ይባላል (1 ተሰ. 5፡23፤ 1 ጴጥ. 1፡14-16)።

ባለፈውና ባሁኑ ጊዜ ቅድስና መካከል ያለውን ግንኙነት መረዳት ያሻናል። ለዚህ በማብራሪያ መጠቀሙ ይረዳናል። እንበልና ለተባበሩት መንግሥታት የአገርህ አምባሳደር ሆነህ ተሹመሃል። ይህ ሹመት ከጸደቀበት ዕለት ጀምሮ፥ ሕጋዊ አምባሳደር ትሆናለህ። ይሁንና፥ ኃላፊነትህን ለመወጣት ከመጀመርህ በፊት ለጥቂት ወራት ጥንቃቄ የተሞላበት ዝግጅትና ሥልጠና ማድረግ ይኖርብሃል። እንግዲህ፥ አምባሳደር ሆኖ በመሾምህ ሕጋዊ እውነታና አምባሳደር ሆነህ በየዕለቱ በምታከናውናቸው ትክክለኛ ተግባራት መካከል ልዩነት እንዳለ ታያለህ። በተመሳሳይ ሁኔታ፥ በእግዚአብሔር ተቀድሰሃል ተብሎ ከመታወጅ (ሃላፊ ቅድስና) እና በዕለት ተዕለት ባሕርያችን እየተቀደሱ በመምጣት (አዳጊ

ቅድስና) መካከልም በጣም ትልቅ ልዩነት አለ። ሃላፊ ቅድስና ልክ በክርስቶስ ባመንንበት ጊዜ ሊፈጸም፥ የአሁን (አዳጊ) ቅድስና ግን የመላው የሕይወት ዘመን ሂደት ነው።

እግዚአብሔር አዳጊ ቅድስናን በሕይወታችን የተሟላ ለማድረግ በአያሌ መንገዶች ይጠቀማል። ከሁሉም በላይ አስፈላጊዎቹ መንገዶች የእግዚአብሔር ቃል (ኤፌ. 5፡26)፥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ (2 ተሰ. 2፡13)፥ እና የጌታ የሥነ-ሥርዓት መመሪያዎች ናቸው (ዕብ. 12፡10)። በመጀመሪያ የእግዚአብሔር ቃል በሕይወታችን ውስጥ የሚያስከትላቸውን የማንጻት ውጤቶች እንመለከታለን። የእግዚአብሔር ቃል የተሰጠን ምን እንደምናምን ሊያስተምረን፥ ስለ ኃጢአታችን ሊገሥጸን፥ ስንባዝን ሊመልሰንና እንዴት የተቀደሰ ሕይወት መኖር እንዳለብን ሊያሳየን ነው (2 ጢሞ. 3፡16፤ ዮሐ. 17፡17)።

ይሁንና፥ የትኛው ትክክል እንደ ሆነ ማወቅና ትክክል የሆነውን ነገር ማድረግ ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ትክክል የሆነውን ነገር መግር ቀላል ሊሆን፥ ማድረጉ ግን ከዚያ ይልቅ በጣም የከበደ ነው። ለሰውም ልጅ እጅግ ከባዱ ችግር ይህ ነው። ሰዎች ትክክለኛው ነገር የትኛው እንደ ሆነ ያውቃሉ፤ ዳሩ ግን አያደርጉትም። ከጥቂት ዓመታት በፊት የመንግሥት ባለሥልጣናት የሚገኙበት ቡድን ወደ አንድ የአስተዳደር ክልል ፍርድ ቤት በመምጣት፥ አባላቱን ስለ በርካታ ምግባረ-ብልሹ ተግባሮቻቸው ከሥራ አፈናቀላቸው። ከጥቂት ዓመታት በኋላ፥ ደግሞ ከእነዚህ የመንግሥት የበላይ ባለሥልጣናት መካከል አንዳንዶቹ ተመሳሳይ ድርጊት ፈጽመው ኖሮ ከሥራ ተባረሩ። እንግዲህ እነኚህ ባለሥልጣናት ትክክለኛው ነገር የትኛው እንደ ሆነ አሳምረው ቢያውቁም ሊፈጽሙት ግን አልቻሉም ነበር።

ትክክል የሆነውን ነገር እንድናደርግ የሚያስችለን የመንፈስ ቅዱስ ኃይል፥ በክርስቶስ ባመንን ጊዜ ወደ ሕይወታችን ይመጣል (ሮሜ 8፡9-14)። የእግዚአብሔርን ቃል እንድንታዘዝና ፈቃዱን እንድንፈጽም ውስጣዊ ኃይል የሚሰጠን መንፈስ ቅዱስ ነው (ሮሜ 8፡4)። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማስቀደም እንድንሻ የሚረዳን መንፈስ ቅዱስ ነው (ፊልጵ. 2፡13)። በውስጣችን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ከሌለ፥ ኃጢአተኛው ሰብአዊ ተፈጥሮአችን ስለሚጫጫነን፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ልንፈጽም አንችልም (ሮሜ 7፡18፤ 8፡11)።

እግዚአብሔር ለአሁኑ ቅድስናችን የሚጠቀምበት ሌላው መንገድ በቅጣትና በሥቃይ ነው። ልክ ታማኝ አባት ልጁን እንደሚቀጣ እግዚአብሔርም ይቀጣናል (ዕብ. 12፡5-10)። ምንም እንኳ ለጊዜው ከባድና የማያስደስት ቢሆንም (ዕብ. 12፡11)፥ የእግዚአብሔር ቅጣት መልካም ፍሬ አለው። ቅጣቱ የበለጠ ቅዱስ እንድንሆን ይረዳናል (ዕብ. 12:10)። ከዚህ ጋር በቅርብ የሚዛመደው ባጠቃላይ የመከራ ጉዳይ ነው። እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ አማኞች ይብልጥ ቅዱሳንና ንጹሐን እንዲሆኑ ለመርዳት፥ በመከራ ውስጥ ያሳልፋቸዋል (1 ጴጥ. 4፡1-2)።

ከእግዚአብሔር ቃል፥ ከመንፈስ ቅዱስ ሥራ፥ ከቅጣትና መከራ በተጨማሪ፥ እግዚአብሔር አዳጊ ቅድስናችንን ለመፈጸም የሚጠቀምባቸው አያሌ ሌሎች መንገዶች አሉት። እነዚህም፥ እምነትን (የሐዋ. 26፡18፤ ኤፌ. 3፡17)፥ ከክርስቶስ ጋር ያለንን መንፈሳዊ አንድነት (ሮሜ 6:4-5) እና ዳግም የተወለዱ አማኞች የሚገኙበትን የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ኅብረት ያጠቃልላሉ (ዕብ. 10፡25)።

የእግዚአብሔርን ቃል የማንጻት ተግባር በእምነት እንቀበላለን። የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በእምነት ከሕይወታችን ጋር እናዛምዳለን። ከክርስቶስ ጋር የሚኖረንን የመንፈሳዊ አንድነታችንን እውነታ በእምነት እንለማመዳለን። የእግዚአብሔርን ቅጣትና በሕይወታችን ውስጥ የሚያመጣቸውን መከራዎች በእምነት እንቀበላለን።

ከእነዚህ የቅድስና መንገዶች በተጨማሪ፥ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል በመሆን በክርስቶስ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ለሆኑት ወገኖች ለምናሳየው ባሕርይ ተጠያቂዎች እንሆናለን። እግዚአብሔር የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ተሳትፎአችንን ፲ሕይወታችን ለሚፈጽመው የአዳጊ ቅድስና ሂደት አስፈላጊ ነገር አድርጎ ይጠቀምበታል። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ነገዶችና ጎሳዎች ባህላዊ እሴቶቻቸውን ከሚጠብቁበት መንገድ ጋር በጣም ተመሳሳይ ነው። በጎሳው ውስጥ የሚገኙ ግለሰቦች የፈለጉትን የማድረግ ነፃነት የላቸውም። ለሕዝባቸው ባህል ተቀባይነት ባለው መንገድ ባሕርያቸውን መቅረጽ አለባቸው። በተመሳሳይ ሁኔታም፥ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለሚገኘው የእግዚአብሔር ሕዝቦች ማኅበረሰብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመዘኛዎች ተሰጥተዋል። የእነዚህን መመዘኛዎች መከበር መከታተሉ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ኃላፊነት ነው። ይህም ሂደት በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙትን ሰዎች ሁሉ በኅብረታቸው ለሚገኙ ሌሎች ሰዎች ኃላፊነት እንዲሰማቸው ያደርጋል። በዚህ ዓይነት

እግዚአብሔር የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ጎብረት ለአዳጊ ቅድስናችን ይጠቀምበታል።

ስለ አሁኑ ጊዜ ደኅንነትና ስለ አሁኑ ጊዜ ቅድስና ተነጋግረናል። በአሁን ደኅንነትና አሁን ቅድስና መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? ልዩነቱ የአሁን (አዳጊ) ቅድስና ይበልጥ ቅዱስ የመሆን ሂደት ሲሆን፥ የአሁን ደኅንነት የአሁን ቅድስና ዓላማ መሆኑ ነው። ዓላማውም በሕይወታችን በኃጢአት ቁጥጥር ወይም አገዛዝ ሥር መሆን እንደሌለብን ነው።

ቅድስና በሚመጣው ጊዜ

ከተነጋገርንባቸው ከሁለቱ ቅድስናዎች በተጨማሪም፥ የወደፊት የቅድስና ገጽታ አለ። ፍጹም ቅዱሳን የምንሆነው በሰማይ ኢየሱስን ስንገናኘው፥ ወይም ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም ሲመለስ ነው - የትኛውም በቅድሚያ ቢፈጸም (ኤፌ. 5፡27፤ ዕብ. 12፡23)። ከኃጢአተኛ ሰብአዊ ተፈጥሮአችን የተነሣ፥ በዚህ ሕይወት ከቶውንም ፍጹም ቅዱሳን ልንሆን አንችልም። አንዳንድ ሰዎች በዚህ ሕይወት ከኃጢአት ተለይተው ሙሉ ለሙሉ ቅዱሳን እንደ ሆኑ ይናገራሉ። እንዲህ የሚሉ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል አይረዱም (ሮሜ 7፡21-23፤ ገላ. 5፡17)። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፥ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም» ይላል (1 ዮሐ. 1፡8)። እውነቱ እግዚአብሔር ባሁኑ ጊዜ ዕለት በዕለት በሕይወታችን ውስጥ አዳጊ ቅድስና እየሠራ መሆኑ ነው። አንድ ቀን በሞት ወይም በምጽአቱ ጊዜ ከጌታ ጋር ስንገናኝ፥ የቅድስናችን ተግባር ይፈጸማል። በመጨረሻም፥ ፍጹም ቅዱሳን እንሆናለን (1 ዮሐ. 3፡2፤ ይሁዳ 24)።

የእግዚአብሔር ደኅንነት የተፈጸመው በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ፥ በመንፈስ ቅዱስ መምጣትና በክርስቶስ የከበረ ዳግም ምጽአት ነው። የክርስቶስን ሞትና ሞቱም ለሰው ልጆች ያስገኛቸውን ውጤቶች በጥንቃቄ መርምረናል። አሁን ደግሞ አትኩሮታችንን በክርስቶስ ትንሣኤ ላይ እናደርጋለን።

ሰ. የኢየሱስ ከሞት መነሣት እውነት እንደ ሆነ እንዴት እናውቃለን?

የክርስቶስ ትንሣኤ የክርስትና የማዕዘን ዓለት ነው። ይህ ክርስትናን በዓለም ካሉት ሌሎች ሃይማኖቶች ከሚለይባቸው እውነታዎች አንዱ ነው። የወንጌሉ ጠቅላላ እውነታ በክርስቶስ ትንሣኤ ላይ ይደገፋል። ጳውሎስ፥ «ክርስቶስ ካልተነሣ እምነታችሁ ከንቱ ናት፤ እስከ አሁን ድረስ በኃጢአታችሁ አላችሁ» ሲል ጽፎአል (1 ቆሮ. 15:17)። ሌሎች የሞቱ የሃይማኖት መሪዎችና ነቢያት ሁሉ ባሁኑ ጊዜ ከመቃብር በታች ናቸው። ከሞት የተነሣው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። አሁንም ሆነ ከዚህ በፊት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች እንደሚመሰክሩት፥ ኢየሱስ በትክክል ሕያው ነው። ሕያውነቱን እንዴት አውቁ? ጸሎታቸውን ስለሚመልስና ለመፈጸም ቃል የገባቸውን ምልክቶችና ድንቆች አሁንም ስለሚሠራ ነው (ማር. 16:17-18፤ ዮሐ. 15:7፤ ዕብ. 2:4)።

ብዙ ተጠራጣሪዎች የክርስቶስን ትንሣኤ ለመቀበል ይቸገራሉ። «ኢየሱስ በትክክል ከሞት መነሣቱን እንዴት እናውቃለን?» ሲሉም ይጠይቃሉ። ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ታሪካዊውን ዘገባ በጥንቃቄ መመርመር አለብን። ትንሣኤ በትክክል እንደ ተፈጸመ ከታሪክ ልናረጋግጥ እንችላለን? አንድ ታሪካዊ ክስተት የሚረጋገጥባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው? በሕግ ችሎት ፊት ተቀባይነት የሚያገኘው መረጃ የትኛው ነው?

አንድ የሕግ ችሎት አንድን ጉዳይ በሚመረምርበት ጊዜ፥ ብዙውን ጊዜ ሁለት ዓይነት መረጃዎችን ይቀበላል።

1. ክስተቱ ሲፈጸም የነበረውን የዓይን እማኝ ምስክርነት።

2. በክስተቱ ዙሪያ የሚሽከረከሩ የአካባቢ መረጃዎች።

እስኪ የክርስቶስን ትንሣኤ መረጃ እውነትነት ለመፈተን፥ በእነዚህ መረጃዎች አንጠቀም። ይህንንም በማድረግ፥ የክርስቶስን ትንሣኤ በሕጋዊ መንገድ ለማረጋገጥ እንደሚቻል እንረዳለን።

በቅድሚያ የክርስቶስን ትንሣኤ የዓይን አማኞች ምስክርነት ተመልከት። የተለያዩ ዓይነት የዓይን እማኞች ነበሩ። በመጀመሪያ፥ በትንሣኤው ማለዳ በሰውነቱ ላይ ሽቶ ለመቀባት በመጡ አማኝ ሴቶች ታይቷል። ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ቢጠራጠሩም፥ እነዚህ ሴቶች ግን ምስክርነታቸውን ጠብቀዋል። ሁለተኛ፥ ከትንሣኤው በኋላ አርባ ቀናት በቆየበት ጊዜ የተመለከቱት ደቀ መዛሙርት የዓይን እማኞች ነበሩ (የሐዋ.

1:3)። የዓይን እማኝነታቸውም ማረጋገጫ ከሞት ተነሥቶ ለተመለከቱት ጌታ ለመሠቃየትና ለመሞት መፍቀዳቸው ነው (የሐዋ. 4:20፤ 7:59፤ 12:1-2)። ከዚያም መታብሩን የሚጠብቁ ወታደሮች ነበሩ። የአማኝነታቸው ማረጋገጫ ደቀ መዛሙርት የኢየሱስን ሥጋ ሠርቀው እንደ ወሰዱ አድርገው ለማስተባበል ከሃይማኖት መሪዎች ጉቦ መቀበላቸው ነው (ማቴ. 28:12-13)።

የወንጌሉ የትንሣኤ ታሪኮች የተጻፉበት መንገድ ከዓይን እማኞች መገኘታቸውን ያሳያል። እያንዳንዳቸው አራቱ ወንጌላት በአናሳ ጉዳዮች ብቻ መለያየታቸው በራሱ በዓይን እማኞች ለመጻፋቸው መረጃ ይሆነናል። በትልቁ ክስተት ላይ ሲስማሙ፥ በዝርዝር ገለጻው ውስጥ አንዳንድ ልዩነቶች ይገኛሉ። ይህም የአራቱን ወንጌላት ታሪኮች እውነትነት ይደግፋል።

አራት ሰዎችን ጠርተህ ስለ አንድ የእግር ኳስ ጨዋታ ውጤት ብትጠይቅ፥ ሁሉም የትኞቹ ቡድኖች እንደ ተጫወቱና ማን እንዳሸነፈ ባልተለያየ ድምፅ ይነግሩሃል። ይሁንና፥ እያንዳንዱ ሰው ለጨዋታው መግለጫ የሚሰጠው ከራሱ ዕይታ አንጻር ነው። እያንዳንዱ ተመልካች በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ተጨዋቾችን ይመለከታል። አራቱ ወንጌላት የክርስቶስን ታሪኮች የሚያቀርቡትም እንዲሁ ነው። እያንዳንዱ የወንጌሉ ጸሐፊ በደንብ የሚያውቃቸውን የታሪኩን ዝርዝሮች ስለሚጽፍ፥ እያንዳንዱ ታሪክ በመጠኑ ከሌላው ይለያል፤ ይሁንና፥ አራቱም ወንጌላት ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ በሚገልጽ ዓቢይ ክስተት ላይ ይስማማሉ።

ከትንሣኤው ታሪክ የዓይን እማኞች በተጨማሪ፥ ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ በተለያዩ ጊዜያትና ሁኔታዎች በአያሌ ግለሰቦችና ቡድኖች እንደ ታየም ልንረዳ ይገባል። ኢየሱስ በአንድ ጊዜ ወይም በአንድ ስፍራ ብቻ አልታየም። ከሩቅ ብቻ ሳይሆን፥ ከቅርብ ርቀትም ታይቷል። ከደቀመዛሙርቱ ጋር ተራምዷል፤ ተነጋግሯል፤ ተመግቧልም (ሉቃ. 24:13-43)። እንዲያውም፥ ከትንሣኤው በኋላ ለአርባ ቀናት ያህል የታየ ሲሆን፥ በዚያን ጊዜም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አንዳንድ ረዣዥም ውይይቶችን አካሂዷል (ማቴ. 28:16-20፤ ሉቃ. 24:13-43፤ ዮሐ. 21:1-23፤ 1 ቆሮ. 15:4-7)። ብዙ ሰዎች በአፍሪካ እንዳዩት ዓይነት፥ መንፈስ ብቻ ሆኖ አልተገለጸም ነበር። ሥጋና አጥንት ያለው የትንሣኤ አካል እንደ ለበሰም ተረጋግጦአል (ሉቃ. 24:36–43)።

ከዓይን እማኞች ምስክርነቶች፥ ስለ ሐዋርያው ቶማስ የተዘገበው በተለይ አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም ይህ ሰው የቅርብ ወዳጆቹ የሆኑት ሐዋርያት ክርስቶስን ከሞት ተነሥቶ በሕይወት እንዳገኙት የሚያመለክተውን የዓይን አማኝነት ለማመን በጽኑ የተቃወመ በመሆኑ ነው (ዮሐ. 20፡24-25)። ከአንድ ሳምንት በኋላ ቶማስ ራሱ ከሞት የተነሣውን ጌታ ለማየትና አሳብ ለመለዋወጥ ቻለ። ከዚያም እጅግ በመደነቅ፥ «ጌታዬ አምላኬ» አለ (ዮሐ. 20፡24-29)!

ለክርስቶስ ትንሣኤ ሁለተኛው ዓይነት የአካባቢ መረጃ ከትንሣኤው ጋር ከተያያዙ ሁኔታዎች የመጣ ነው። ከዚህ መረጃ ጥቂቱን በማጠቃለያ መልክ እንደሚከተለው እናቀርባለን፦

1. የባዶው መቃብር እውነታ፥ የኢየሱስ ሥጋ ወዴት ሄደ? የሚለውን ጥያቄ ያስነሣል። ብዙ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች ለባዶው መቃብር ማብራሪያ ለማቅረብ ቢጣጣሩም፥ ማብራርያቸው ሁሉ በትክክል የተፈጸመውን ነገር የማፍረስ ዓቅም ያጥረዋል። በተራ ቁጥር 7 ለዚህ የሚሆነውን ምሳሌ ተመልከት።

2. ተያያዥነት ባለውና የድምፅ ልዩነት ባልታየበት ሁኔታ፥ ሁሉም ሐዋርያት ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት እንደ ተነሣ መስክረዋል። ሐዋርያት ኢየሱስን ከትንሣኤው በኋላ በሕይወት ያዩት ሲሆን፥ ወንጌሉን በሰበኩበት ጊዜ ሁሉ ይህንኑ እውነታ አውጀዋል (ለምሳሌ፥ የሐዋ. 2፡32)። ይህ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍና በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የተረጋገጠ ነው።

3. ሁሉም የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ስለ ትንሣኤው በአመለካከታቸው ከፍርሃትና አለማመን ወደ ጀግንነት፥ ደስታና እርግጠኛነት በሚያስደንቅ ሁኔታ ተለውጠዋል። የክርስቶስ ትንሣኤ ካልሆነ፥ እንግዲህ ይህንን ለውጥ ምን አመጣው? የክርስቶስ ሐዋርያት በስቅለቱ ወቅት ከነበሩበት ፍርሃትና ስጋት ከትንሣኤው በኋላ በሥቃይና ሞት ዙርያ ሳይቀር ወደ ብርታት፥ ደስታና ድፍረት የተሞላበት ምስክርነት የመለወጣቸው እውነታ፥ ትንሣኤው በትክክል እንደ ተፈጸመ የሚያሳይ ታላቅ ማረጋጫ ነው (የሐዋ. 5፡29-42፤ 12፡1-2)። ብዙ ሰዎች በሚገኙበት ትልቅ ቡድን እንዲህ ዓይነቱ ያልተለመደና ፍጹም የባሕርይ ለውጥ ከትንሣኤ ወዲያ መታየቱ እንዲህ በቀላሉ የሚታለፍ ነገር አይደለም። ሰዎች ልክ የቀድሞ ሐዋርያት እንዳደረጉት፥ ውሸትነቱን ለሚያውቁት ወይም ለሚጠራጠሩት

ነገር ለመሠቃየትና ለመሞት አይፈቅዱም። ሐዋርያቱ እውነትነቱን ስላረጋገጡ ለመሠቃየትና ለመሞት ፈቅደዋል።

4. የክርስቲያኖች ሁሉ ጠላት የሆነው የጤርሴሱ ጳውሎስ አስደናቂ ለውጥም የክርስቶስን ትንሣኤ ያረጋግጣል (የሐዋ. 9፡1-19)። ከሞት የተነሣውን ክርስቶስን በደማስቆ መንገድ ባይመለከት ኖሮ፥ ሳውልን ምን ነገር ሙሉ ለሙሉ ይለውጠው ኖሯል (የሐዋ. 9፡3-7)?

5. ኢየሱስ ዛሬም የተስፋ ቃሎቹን በመጠበቅ ጸሎትን ይመልሳል፤ በእርሱ ላመኑት ደግሞ ሕይወትን የሚለውጥ ኃይል ይሰጣል። እርሱ ከሞት ካልተነሣ ይኼ እንዴት ይሆናል? በዓለም ውስጥ እያንዳንዱ እውነተኛ ክርስቲያን ከተመለሱለት ጸሎቶች በመንሣት፥ የኢየሱስ ክርስቶስን ሕያውነት ሊመሰክር ይችላል።

6. የአይሁድ ሐዋርያት የአምልኮ ቀናቸውን ከሰባተኛው ቀን ወደ መጀመሪያው ቀን ለውጠዋል። ይህም ለውጥ በመጀመሪያው የሳምንቱ ቀን አንድ አስደናቂ ነገር እንደ ተፈጸመ ያሳያል። ለአይሁዳዊ ሰው የዚህ ዓይነቱ የአምልኮ ቀን ለውጥ የማይታሰብ ነበር (ሉቃ. 24፡1-8፤ የሐዋ. 20፡7-8)።

7. ትንሣኤውን በግልጽ ከሚያሳዩ እውነታዎች አንዱ የአይሁድ የሃይማኖት መሪዎች፥ የክርስቶስን መቃብር ለሚጠብቁ ወታደሮች ጉቦ መስጠታቸው ነው። ደቀ መዛሙርቱ የክርስቶስን አካል ሠርቀው እንደ ወሰዱ አድርገው እንዲያውጁ ጉቦ ተሰጣቸው (ማቴ. 28፡11-15)። ይህም የአያሌ ነገሮችን እውነትነት ያረጋግጣል። በመጀመሪያ፥ የኢየሱስ ሰውነት በትክክል ከመቃብሩ እንደ ተወሰደና በማለዳ ድንጋዩ እንደ ተንከባለለ ያረጋግጣል። ሁለተኛ፥ አንዳንድ ክርስቲያን ያልሆኑ ስዎች እንደሚሉት፥ ሰውነቱ ወደ ሌላ ስፍራ እንዳልተወሰደና ወታደሮች በነበሩበት ዮሴፍ ባዘጋጀው መቃብር እንደ ተቀበረ ያረጋግጣል። ሦስተኛ፥ በትክክል ትንሣኤው እንደ ተፈጸመ ያረጋግጣል፤ አንድ ሰው የኢየሱስን ሰውነት ወስዶ ቢሆን ኖሮ፥ ወታደሮቹ ይናገሩ ነበር።

ወታደሮቹ በጉቦ ተታልለው እንዲናገሩ እንደ ተደረገው፥ ሐዋርያት ሰውነቱን ሠርቀው ቢሆን ኖሮ፥ እነኚህ ሐዋርያት እንደ ሞተ ለሚያውቁት ሰው ለመሠቃየትና ለመሞት ፈልገዋል ማለት ነው። ይህም ማለት የሚበሰብስ አስከሬን ይዘው ነበር ማለት ነው። በዓለም ውስጥ የትኛውም የሰዎች ቡድን ለዚህ ዓይነቱ የዕብደት ተግባር ስምምነቱን

አያሳይም። በመጨረሻም አንድ ሰው ምሥጢሩን ማውጣቱ አይቀርም። የክርስቶስን ትንሣኤ በተመለከተ ግን የሚጋለጥ ምሥጢር አልነበረም። ደቀ መዛሙርት በዚህ ዓይነቱ ማታለል የሚያገኙት ነገር በፍጹም አለመኖሩ ብቻ ሳይሆን፥ የከፋ ሥቃይ ይጠብቃቸው ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን፥ የመረረ ስደትና ሞት የደረሰባቸው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ በመመስከራቸው ነው።

8. የክርስቶስን የትንሣኤ እውነታ ፉርሽ ለማድረግ የሚጥሩ አያሌ መጻሕፍት በኢ-አማንያን ተጽፈዋል። የእነዚህም ወገኖች አሳቦች በጥንቃቄ ተጠንተው በግሩም ሁኔታ ምላሽ አግኝተዋል። የክርስቶስ ትንሣኤ ምናልባትም በኢ-አማንያን በከፍተኛ ደረጃ የተካደ የታሪክ ክስተት መሆኑ አስገራሚ ነው። ይሁንና፥ ትንሣኤውን ፉርሽ ለማድረግ የተደረጉ የኢ-አማንያን ሙከራዎች ሁሉ ራሳቸው ፉርሽ ሆነዋል። በትክክል የተፈጸመን ክስተት እንዳልተፈጸመ አድርጎ ማሳመን አይቻልም። ሆን ብለው ትንሣኤውን ፉርሽ ለማድረግ የተነሡ አንዳንድ ሰዎች፥ ታሪካዊ መረጃዎችን በጥንቃቄ ሲመረምሩ ለክርስቶስ ተግርከዋል።

የተትረፈረፈ የታሪክ መረጃ የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ ያረጋግጣል። እንደ ተናገረው፥ ከሞት ተነሥቶ (ሉቃስ 18፡32-33)፥ ለዘላለም ሕያው ሆኖ ይኖራል (ራእይ 1፡18)። የዓለሙን ሁሉ ታሪክ የለወጠው የዚህ ድንቅኛ ክስተት ፍች ምንድን ነው? ለክርስቲያኖችና ለሰው ልጆች ሁሉ፥ የትንሣኤው ውጤቶች ምንድን ናቸው?

ሸ. በዛሬው ጊዜ የክርስቶስ ትንሣኤ ለክርስቲያኖች የሚሰጠው ትርጉም ምንድን ነው?

በሞቱና ትንሣኤው፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአትን፥ ሰይጣንንና ሞትን አሸንፎአል። ይህ ዛሬ በሕይወት ለሚኖር ክርስቲያን ምን ትርጉም ይሰጣል? በክርስቶስ ትንሣኤ የተፈጸሙ ነገሮችና ትንሣኤው ለክርስቲያኖች ምን ትርጉም እንደሚሰጥ የሚያሳይ ማጠቃለያ እነሆ፡-

1. ከክርስቶስ ትንሣኤ የተነሣ፥ አሁን ሕያው ተስፋ አለን - ስንሞት ወደ መንግሥተ ሰማይ እንደምንሄድ እርግጠኞች ነን (1 ጴጥ. 1፡3-4)። በትንሣኤው፥ ክርስቶስ ሞትን አጥፍቶ በእርሱ ለሚያምኑት ሁሉ

የዘላለምን ሕይወትና ሕያውነትን አጎናጽፎአል (2 ጢሞ. 1፡10፤ ዮሐ. 11፡25፤ 14፡19)።

2. ትንሣኤው ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውም አምላክም እንደ ሆነ፣ ማለትም አምላክ የነበረ ሰውና ሰው የሆነ አምላክ እንደ ሆነ ያረጋግጣል (ሮሜ 1፡4፤ ዕብ. 1፡8፤ ቆላ. 2፡9)።

3. ትንሣኤው ክርስቲያኖች ልክ እንደ ክርስቶስ የትንሣኤ አካል እንደሚኖራቸው ያረጋግጣል (ፊልጵ. 3፡20-21)። ክርስቲያን ልክ የክርስቶስን በሚመስል ትንሣኤ ለመነሣት ወደፊት አሻግሮ ይመለከታል እንጂ፥ እንደ ባህላዊ ሃይማኖቶች አስተምህሮ ቅድመ-ትውልዳዊ ታላቅ መንፈስ ለመሆን አይናፍቅም።

4. ኢየሱስ ሰውን ሁሉ ከሞት እንደሚያስነሣ ተስፋ ስለ ሰጠ (ዮሐ. 5፡28-29)፥ የክርስቶስ ትንሣኤ ለሰው ልጅ በሙሉ ትንሣኤ እንደሚኖር ያረጋግጣል። አንዳንዶች ለሕይወት፥ ሌሎች ደግሞ ለፍርድ ይነሣሉ (ዮሐ. 5፡28-29)።

5. ትንሣኤው የክርስቶስ የተስፋ ቃሎች፥ ንግግሮችና ትንበያዎች ሁሉ እውነት እንደ ነበሩ ያረጋግጣል (ማር. 8፡31፤ ዮሐ. 11፡25-26)።

6. የክርስቶስ ትንሣኤ ለአማኙ የክርስትናን ሕይወት ለመምራት መተማመኛ የሚሆነው የትንሣኤ ኃይል እንዳለ ያረጋግጣል (ኤፌ. 1፡19-22፤ 3፡20)።

7. የክርስቶስ ትንሣኤ በትክክል የኃጢአትን ይቅርታ እንደምናገኝ ያረጋግጣል (1 ቆሮ. 15፡17-20)።

8. ትንሣኤው አሁን በሰማይ በአብ ቀኝ ስለ እኛ የሚማልድ ሊቀ ካህን እንዳለን ያረጋግጥልናል (ሮሜ 8፡34)።

9. ትንሣኤው ቁሳዊው ፍጥረት በሙሉ ዳግም ከቀድሞው በተለየ ሁኔታ እንደሚታደስ ያረጋግጣል (ሮሜ 8፡19-23)።

10. ትንሣኤው እግዚአብሔር አብ፥ ክርስቶስ ለኃጢአታችን ያቀረበውን መሥዋዕት ሙሉ ለሙሉ እንደ ተቀበለ ያረጋግጣል (ሮሜ 4፡25)።

11. ትንሣኤው በመጨረሻ በሰው ልጆች ሁሉ ላይ ፍርድ እንደሚሰጥ ያረጋግጣል (የሐዋ. 17:31)። ትንሣኤው መጽሐፍ ቅዱስ ፍጹምና ትክክለኛ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ ያሳያል። በመሆኑም፥ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምራቸው የሥነ-መለኮት አስተምህሮዎች ሁሉ እውነት ናቸው።

ቀ. የክርስቶስ ዕርገት ዓላማ ምን ነበር? አሁንስ ምን በማድረግ ላይ ይገኛል?

ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ፥ ከአርባ ቀናት ለሚበዙ ጊዜያት ለደቀ መዛሙርቱ ሲታይ ቆይቷል (የሐዋ. 1:3)። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው፥ በዚህ ጊዜ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት አስተምሮአቸዋል። ኢየሱስ ከማረጉ በፊት የነበረውን ይህንኑ የመጨረሻ ጊዜ፥ እርሱ ወደ ሰማይ ከሄደ በኋላ ኃላፊነታቸው ምን እንደሚሆን ለደቀ መዛሙርቱ ለመናገር ተጠቅሞበታል።

በዚህ ጊዜ ውስጥ የነበረው ዋንኛው ልዩነት፥ ኢየሱስ በስፍራና በሰዓት ያልተገደበ የትንሣኤ አካል መልበሱ ነው። ከዚህም የተነሣ በሮች ተዘግተው ሳሉ ከየት መጣ ሳይባል በመካከላቸው ይገኝ ነበር (ዮሐ. 20:19)። አንዳንድ አፍሪካውያን ዘመዶቻቸው ከሞቱ በኋላ መንፈሳቸውን እንደ ተመለከቱ ስለሚናገሩ፥ እነዚህን የክርስቶስን የመታየት ሁኔታዎች ሊረዱ ይችላሉ።

ይሁንና፥ ክርስቶስ ከትንሣኤ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ በታየባቸው ሁኔታዎች ውስጥ አንድ ዐቢይ ለውጥ ነበር። ይኸውም የመንፈሱ መታየት ብቻ አለመሆኑ ነው። በሉቃስ 24:39 ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንደ ተናገረው፥ ጌታ የትንሣኤውን ሥጋና አጥንት ለብሶ ነበር (ሉቃስ 24:41-43)።

በዚህ ጊዜ፥ እንደ ተጠራጣሪው ቶማስ ያሉ የደቀ መዛሙርት ጥርጣሬዎችና ጥያቄዎች ሁሉ ተወግደው ነበር (ዮሐ. 20:24-29)። ኢየሱስ ወደ ሰማይ ባረገ ጊዜ፥ ደቀ መዛሙርቱ የሞቱንና ትንሣኤውን ወንጌል ለሰዎች ሁሉ ለማወጅ ብቻ ሳይሆን፥ ሊያስፈልግም ለእርሱ ለመሠቃየትና ለመሞት ተዘጋጅተው ነበር (የሐዋ. 5:29-32፥40፤ የሐዋ. 7:56-60)። ኢየሱስ ለሰዎች ደኅንነት በምድር ላይ የሠራው ሥራ

ተፈጸመ። አሁን በምድር ላይ ለሚገኙ ነገዶችና ሕዝቦች ማዳኑን የማወጁ ሥራ፥ እኛን ጨምሮ በትውልዶች ሁሉ በሚገኙ ደቀ መዛሙርት ላይ አርፎአል (ኢሳ. 45፡22፤ ማቴ. 28፡19-20)።

የደኅንነቱን ሥራና ደቀ መዛሙርቱን የማሠልጠኑን ተግባር ከፈጸመ በኋላ፥ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ እያዩት በትንሣኤው አካል ወደ ሰማይ ዐረገ (የሐዋ. 1፡9-11)። በዚህም ጊዜ፥ ሁለት ቅዱሳን መላእክት ቀርበው ለደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ባረገበት መልኩ፥ እንዲሁ ሰዎች እያዩት በትንሣኤው አካል ወደ ዓለም እንደሚመለስ ነገሩአቸው። በምዕራፍ 18 ደግሞ ምጽአቱን ዘርዘር አድርገን እንመለከታለን።

አሁን ኢየሱስ እግዚአብሔር ለዓለም የነበረውን የደኅንነት ዕቅድ ስለ ፈጸመ፥ በአጽናፈ-ዓለሙ እጅግ በላቀው የክብር ስፍራ የሚቀመጥበት ጊዜ ነው። ድል አድራጊው ክርስቶስ ወደ ሰማይ ያረገበት ሁኔታ፥ ቅዱሳን መላእክት ከዚያን በፊት ከተመለከቱት ከስተት ሁሉ እጅግ የሚያስደንቅ መሆን አለበት። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፥ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፥ ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ» ይላል (ፊልጵ. 2፡9-10)። ክርስቶስ ወደ ሰማይ በድል መድረስ ብቻ ሳይሆን፥ በክርስቶስ ሞት መንግሥተ ሰማያት እንዲከፈትላቸው የሚጠባበቁትንም በርካታ የብሉይ ኪዳን አማኞች ከእርሱ ጋር አስገብቶአል [መዝ. (68)፡18፤ ኤፌ. 4፡8-10]።

እንዲሁም፥ እግዚአብሔር አብ ይህንኑ ከመላእክት በላይ ከፍ ያለውን ስፍራ ለቤተ ክርስቲያኑ ሰጥቷል (ኤፌ. 2፡6)። አማኞች ከክርስቶስ ጋር ካገኙት ከዚህ ስፍራ የተነሣ ነው አሁን ክርስቲያኖች በሰይጣንና በአጋንንቱ ላይ ሥልጣን የያዙት (ሉቃ. 10፡19፤ ኤፌ. 1፡20-21)። ከዚህ የሥልጣን ስፍራ፥ ክርስቲያኖች አንድ ቀን በዓለምና በመላእክትም ላይ ሳይቀር ይፈርዳሉ (1 ቆሮ. 6፡2-3)።

ኢየሱስ አሁን የነገሥታት ንጉሥ ሆኖ በሚገኝበት ከፍ ባለው ስፍራው ሆኖ ምን እየሠራ ነው?

ከቅዱሳኑ መጻሕፍት እንደምንረዳው፥ ኢየሱስ ባሁኑ ጊዜ በምድር ላይ ሁሉንም ነገድና የሕዝብ ቡድን የመድረሱን ዕቅድ እየፈጸመ ነው። በዚህ ስፍራ እነዚህን እንቅስቃሴዎች በአጭሩ ብቻ አጠቃለን እናቀርባለን።

1. እርሱ አጽናፈ-ዓለሙን በመደገፍና በማጽናት ላይ ይገኛል (ዕብ. 1፡3)።

2. እርሱ የቤተ ክርስቲያኑ ጌታና ራስ ነው (ኤፌ. 1፡22-23፤ 4፡15-16፤ ቆላ. 1፡18)።

3. እርሱ በዓለም ሁሉ ቤተ ክርስቲያኑን እያነፀ ነው (ማቴ. 16፡18፤ 28፡20፤ ኤፌ. 2:19-21)። በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት፥ ክርስቶስ በምድር ላይ ለቤተ ክርስቲያኑ መንፈሳዊ ስጦታዎችንና የተሰጡ ሰዎችን እያበረከተ ነው (1 ቆሮ. 12፡4-7፤ ኤፌ. 8፡4-12) ።

4. እርሱ ለሕዝቡ እየጸለየ ነው (ዕብ. 7፡25፤ ሮሜ 8፡34) ። ኢየሱስ ለሕዝቡ በመማለድ እንደሚጸልይ የሚያሳይ ምሳሌ በዮሐንስ 17፡1-26 ይገኛል።

5. በሰማይ ለሕዝቡ ስፍራ እያዘጋጀና የጠላቶቹን ከእግሩ ሥር መውደቅ እየተጠባበቀ ነው [መዝ. (110)፡1-2፤ ዮሐ. 14፡2-3]።

በ. የሚድነው ማን ነው?

በዚሁ አጋጣሚ መመልከት የሚኖርብን አንድ ተጨማሪ ጥያቄ አለ። ይኸውም የሚድነው ማን ነው? ማንኛውም ሰው ሊድን ይችላል ወይስ የክርስቶስ ማዳን ለተመሰኑ ሰዎች ነው? አንዳንዶች እንደሚሉት፥ ሰዎች ሁሉ ይድናሉ? መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? የሚለውን ጥያቄ ነው።

ማን እንደሚድን የሚያመለክተው ጥያቄ በአፍሪካ ከባድ ጥያቄ ነው። ከተስፋፋው ቤተሰብ ወይም ጎሳ ጠንካራ ግንኙነቶች የተነሣ፥ ለሰዎች ከቤተሰባቸው ወይም ከትውልዶቻቸው አንዳንዶች በሰማይ ከእነርሱ ጋር እንደማይሆኑ ማሰብ በጣም ከባድ ነው። ብዙ ጊዜ «የፍቅር አምላክ የሆነው እግዚአብሔር ማንንም ሰው ከመንግሥተ ሰማይ ውጭ የሚያስቀረው ለምንድን ነው?» የሚል ጥያቄ ይነሣል። ይህ በከፍተኛ ትኩረት ልንመለከተው የሚገባን ስሜታዊ ጥያቄ ነው። የሚያሳዝነው፥ ደግሞ ይህንን አንገብጋቢ ጥያቄ ለማርገብ፥ ሁሉም ሰው እንደሚድን የሚያመለክት ሥነ-መለኮታዊ አሳብ ለማቅረብ ጥቂት የሥነ-መለኮት

ምሁራን መነሻታቸው ነው። ይህም ሁሉን አቀፍ ሥነ-መለኮት ተብሎ የሚጠራ ሲሆን፥ በአፍሪካ በስፋት ተቀባይነት አግኝቷል።

ይሁንና፥ ጥያቄው ስሜታችን ምን ይላል የሚል ሳይሆን፥ ቸሩና አፍቃሪው አምላካችን ምን ይላል? የሚል ነው። ለሰው ልጅ ደኅንነት ልጁን ሰጥቷል። ግን እንደሚድን እውነቱን ለማወቅ፥ መጽሐፍ ቅዱስን ልናነብና የእግዚአብሔርን መገለጽ ልንቀበል ይገባል።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሞት አማካኝነት ደኅንነትን ለሰው ልጆች ሁሉ እንደ ሰጠ ይናገራል። ሐዋርያው ዮሐንስ፥ «እርሱም የኃጢአታችን ማስተሰሪያ ነው፥ ለኃጢአታችንም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን ለዓለሙ ሁሉ ኃጢአት እንጂ» ሲል ጽፎአል (1 ዮሐ. 2፡2)። እንግዲህ፥ ይህ ማለት ሰዎች ሁሉ ይድናሉ ማለት ነው?

በዚህ መጽሐፍ መግቢያ ላይ እንደ ተገለጸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥነ-መለኮት፣ መጽሐፍ ቅዱስ በአንድ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ የሚናገረውን አሳብ ዳር ከዳር ሸመሳከር እንደሚያሻ ተመልክቷል። መጽሐፍ ቅዱስ ተጨማሪ ግብራርያ አስካልሰጠ ድረስ፥ በአንዲት ጥቅስ ላይ ተመሥርቶ ዶክትሪን ግዋቀሩ አደገኛ ልምምድ ነው። የእግዚአብሔርን እውነት ለመረዳት፥ ስለ ጉዳዩ የሚናገሩትን ጥቅሶች ሁሉ መመርመር አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ ግን እንደሚድን ለሚነግው ጥያቄ ምን ምላሽ ይሰጣል? በተለይ፥ ኢየሱስ ራሱ ምን ብሏል?

መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን በጥንቃቄ ስንመረምር፥ ከቶውንም ሰዎች ሁሉ እንደማይድኑ እንረዳለን። ለጥቂት ጊዜ ስለዚህ ጉዳይ ብናሰላስል፥ በትክክል ሌላ አማራጭ ሊኖር እንደማይችል እንመለከታለን። ቤተሰቦቻችን በመንግሥተ ሰማይ እንዲሆኑ እንሻለን፣ ዳሩ ግን በታሪክ በጣም የከፋ ተግባር የፈጸሙትን አንዳንድ ሰዎች ስናስብ፥ እንዲህ ዓይነት ሰዎች በባሕርያቸው በጣም አስካልተለወጡ ድረስ፥ በመንግሥተ ሰማይ ይኑሩ ማለት መንግሥተ ሰማይ ሚናዋን መለወጥ አለባት እንደ ማለት ነው። ይህን የባሕርይ ለውጥ የሚያስገኘው ደግሞ በክርስቶስ የሚገኘው የደኅንነት ወንጌል ብቻ ነው። ይሁንና፥ በዓለም ብዙ ሰዎች ክርስቶስንና በእርሱ የሚገኘውን የባሕርይ ለውጥ ሳይፈልጉ በዘፈቀደ የሚኖሩበትን አሳዛኝ ሁኔታ እንመለከታለን።

ይህ በሰዎች መካከል የሚታየው ግልጽ የልዩነት ሥዕል በክርስቶስ ስቅለት ወቅት ታይቷል። ከክርስቶስ በአንድ በኩል የተሰቀለው መራራና የንስሐ ልብ የሌለው ወንጀለኛ በመጨረሻ ቃሎቹ ክርስቶስን ዘልፉአል

(ሉቃ. 23፡39)። ከክርስቶስ በሌላ ወገን ሌላ ወንጀለኛ ነበር፤ ይሁንና፥ ይህ ሰው በኃጢአቱ ተጸጽቶ ስለ ነበር፥ ለኢየሱስ ሲናገር የንስሐ ልብ እንዳለው ገልጾአል (ሉቃ. 23፡40-42)። ለእነዚህ ሁለት ሰዎች በሰጠው ምላሽ፥ ኢየሱስ የንስሐ ልብ የነበረው ሌባ ብቻ በገነት ከእርሱ ጋር እንደሚኖር ቃል ገብቶአል። ይህ የሰውን ዘር የሚያሳይ አናሳ ሥዕል ነው። ጥቂቶች ንስሐ ገብተው በማመን ሲድኑ፥ ሌሎች ብዙዎች በክርስቶስ ላይ በማፌዝና ንስሐ ባለመግባት ከደኅንነት ርቀው ይጠፋሉ።

በሉቃስ 13፡3 ኢየሱስ፥ «ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንዲሁ ትጠፋላችሁ» ብሏል። በኋላም በዚያው ምዕራፍ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት፥ «ጌታ ሆይ፥ የሚድኑ ጥቂቶች ናቸውን?» ሲሉ ጠይቀዋል (ሉቃ. 13:23)። ኢየሱስም ለዚህ ጥያቄ ሲመልስ፥ «በጠበበው በር ለመግባት ተጋደሉ፤ እላችኋለሁና፥ ብዙዎች ሊገቡ ይፈልጋሉ አይችሉምም» ብሏል (ቁ. 24)። በዚያው ውይይት ውስጥ ጥቂት ቆይቶ ለአንዳንድ ሰዎች፥ «ከወዴት እንደ ሆናችሁ አላውቃችሁም፤ ሁላችሁ ዓመፀኞች ከእኔ ራቁ ... አብርሃምንና ይስሐቅን ያዕቆብንም ነቢያትንም ሁሉ በእግዚአብሔር መንግሥት ባያችሁ ጊዜ፥ እናንተ ግን ወደ ውጭ ተጥላችሁ ስትቀሩ፥ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት» እንደሚሆን ተናግሯል (ቁ. 27-28)። እንደ እውነቱ ከሆነ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ከማንም በላይ ስለ ሲኦል አስከፊ እውነታ የተናገረው ኢየሱስ ነበር። ስለዚያ ስፍራ ሲናገር፥ በዚያ ሰዎች እንደሚኖሩ በግልጽ አስረድቷል።

በማቴዎስ 7፡13-14 ኢየሱስ፥ «በጠበበው ደጅ ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ፥ መንገዱም ትልቅ ነውና ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው፤ ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ፥ መንገዱም የቀጠነ ነውና፥ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው» ብሏል። በመዝሙረ ዳዊት እግዚአብሔር፥ «ኃጢአተኞች ወደ ሲኦል ይመለሳሉ፥ እግዚአብሔርን የሚረሱ አሕዛብም ሁሉ» ይላል (መዝ. 9፡17)።

እም፥ በመስቀል ላይ የተፈጸመው የኢየሱስ መሥዋዕት ከኃጢአቱ ንስሐ ገብቶ በክርስቶስ ለሚያምን ሁሉ ደኅንነትን ለማጎናጸፍ በቂ ነው (1 ዮሐ. 2፡2)። የሚያሳዝነው በዚህ ዓለም ብዙ ሰዎች ንስሐ ገብተው በክርስቶስ አያምኑም። ወንጌሉን ለሰዎች ሁሉ በመስበክ (ማር. 16፡15)፥ ፈቃደኛ የሆኑት ከኃጢአታቸው ንስሐ ገብተው በእርሱ እንዲያምኑ ማበረታቱ የእኛ የአማኞች ድርሻ ነው (2 ቆሮ. 5፡11)።

የክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ ስናጠና፥ እግዚአብሔር ክርስቶስን ለሚቀበሉት ሁሉ ደኅንነትን እንዳዘጋጀ እንረዳለን። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው» ይላል (ዮሐ. 1፡12)። ይህ ጥቅስ ሰዎች ሁሉ እንደሚድኑ አይናገርም። የሚለው ክርስቶስን በግሉ የሚያምንና የሚቀበል ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሚሆን ነው። በሐዋርያት ሥራ 20፡21 ጳውሎስ፥ «ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ንስሐንና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመንን» እንደ ሰበከ እናነባለን። ወደ እግዚአብሔር ፊት በንስሐ መቅረብና በክርስቶስ ማመን ለደኅንነት አስፈላጊ ቅድመ-ሁኔታዎች ናቸው።

የሚድነው ማን ነው? መልሱ ከኃጢአታቸው ንስሐ በመግባት፥ በግላቸው በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑና እርሱንም እንደ ጌታቸውና አምላካቸው አድርገው የሚቀበሉ ይድናሉ የሚል ነው።

ብዙ ሰዎች በክርስቶስ የማመን ዕድል ያልገጠማቸው ሰዎች ዕጣ-ፈንታ ምን እንደሚሆን ይጠይቃሉ። ይህም ስለ ክርስቶስ አዳኝነት ሳይሰሙ ከሚሞቱ ሰዎች ሕይወት ጋር ይዛመዳል። ለዚህ ጥያቄ የሚሰጠው መልስ እግዚአብሔር ጻድቅ ፈራጅ እንደ ሆነ ነው (ዘፍጥ. 18፡25)። በሰዎች ላይ አድልዎአዊ ፍርድ አይሰጥም። በሰዎች ላይ ብያኔ የሚሰጠው ባገኙት የመገለጽ ብርሃን ላይ በመንተራስ እንጂ፥ ባልተቀበሉት አይደለም (ሮሜ 1፡18-21)። ሮሜ 1፡20፥ «የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና፤ ስለዚህም እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙት አጡ» ይላል። እንዲሁም፥ የክርስቶስ መሰቀል እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ሁሉ እንደሚወድ የሚያሳይ መሆኑን ልናስታውስ ይገባል።

የሚያሳዝነው እውነታ ከኃጢአተኛ ተፈጥሮአቸው የተነሣ፥ ሰዎች ከተቀበሉት ብርሃን አኳያ አለመኖራቸው ነው። በመጨረሻም፥ እግዚአብሔር በምድር ላይ የኖሩትን ሰዎች ሁሉ ልብ እንደሚያውቅ ማመን አለብን። በመሆኑም፥ ከልባቸው አኳያ ይዳኛቸዋል። ክርስቲያኖች ግን በምድር ላይ ለሚኖሩ የሕዝብ ወገኖች ሁሉ ወንጌሉን እንዲሰብኩ ታዘዋል።

ማጠቃለያ

ኃጢአት የሰውን ልጅ በአስከፊ ውድቀት ውስጥ ጥሎአል። እግዚአብሔር ለሰዎች ያለው ዕቅድ ከኃጢአት ማዳን በመሆኑ፥ በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን ለደኅንነት ወደ ራሱ ሲጠራቸው እንመለከታለን (ኢሳ. 45፡22፤ ሮሜ 10፡13)። ሰው ራሱን ሊያድን አይችልም። በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ አማካኝነት የደኅንነትን መንገድ ማበጀት የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነበር። እግዚአብሔር በኃጢአታችን ላይ የወረደውን የራሱን ቁጣ ስለ ወሰደ፥ ይቅር ልንባልና በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ተብለን ልንታወጅ ቻልን።

በአብዛኛዎቹ የአፍሪካ ባህላዊ ሃይማኖቶች «ደኅንነት» ማለት በማኅበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት ነው። ከዚህም ጋር፥ ደኅንነት ከጠንቋይና ከክፉ መናፍስት ነፃ ወጥቶ የሕይወት ኃይል መያዝን ያጠቃልላል። እነዚህ አሳቦች እያንዳንዳቸው ከእግዚአብሔር የደኅንነት እውነት ጋር ሊነጻጸሩ ይችላሉ። የእግዚአብሔር ደኅንነት ማለት፡ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ካደረገልን ነገር የተነሣ፥ እርሱን በምንቀበልበት ጊዜ በእግዚአብሔር አብ ተቀባይነትን ማግኘታችን ነው (ዮሐ. 1፡12፤ ኤፌ. 2:12-13)። ቤተ ክርስቲያን በሚባለው የእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ተቀባይነት አግኝተናል ማለት ነው (ኤፌ. 2፡19-20)። በተጨማሪም፥ የእግዚአብሔር ማዳን ማለት በውስጣችን የሚኖር መንፈስ ቅዱስ አለን ማለት ነው (ሮሜ 8፡9)። ከመንፈስ ቅዱስ መኖር የተነሣ፥ እግዚአብሔር ከጠንቋይና ከክፉ መናፍስት ሊጠብቀን ይችላል (2 ተሰ. 3:3፤ 1 ዮሐ. 4:4)። እንዲሁም ደግሞ ለተቀደሰና ለተትረፈረፈ አኗኗር የመለኮታዊ ሕይወት ኃይል ሊሰጠን ይችላል (ኤፌ. 3፡20፤ ፊልጵ. 2፡13)። ስለ ሆነም፥ የእግዚአብሔር ደኅንነት የአፍሪካውያንን ከልብ የጠለቀ ፍላጎት ያሟላል።

በምዕራፍ 7 ላይ የተመሠረቱ የመወያያ ጥያቄዎችና መልመጃዎች

1. አንድ ሰው ለመዳን በእግዚአብሔር ላይ ባለው እምነት እውነተኛ መሆኑ ብቻ ለምን በቂ እንዳልሆነ አብራራ። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በዋቢነት አቅርብ።

2. እግዚአብሔር ሰውን ስለ ኃጢአቱ በትክክል መኮነን እንዴት በክርስቶስ ሞት እንደ ተፈጸመ አብራራ። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በሞቢነት አቅርብ።

3. አንድ ክርስቲያን የኃጢአተኛ ተፈጥሮውን ደካማነት እንዴት ሊያሸንፍ ይችላል?

4. ሰዎች ሁሉ ለምን እንደማይድኑ በግልጽ አብራራ።

5. የሚከተለውን ጥቅስ ለማብራራት አንድ አጭር ወግ ጻፍ። «መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ ብታች ሌላ የለምና» (የሐዋ. 4፡12)።

6. ደኅንነት በሚመጣው ጊዜ ማለት ምን ማለት ነው? ከዚህ አሳብ ጋር የተያያዙ ሁለት ጥቅሶች ስጥ።

7. ሁለት ሁለት ሰዎች ለሚገኙባቸው ቡድኖች ክፍሉን ከፋፍል። እንበልና አንድኛው አባል ስለ ክርስትና ብዙ ለማወቅ የሚፈልግ የሰፈር ሽማግሌ ነው። ተራ በተራ ከባህላዊ ግንዛቤ ጋር በሚዛመድ መልኩ የደኅንነትን ውጤቶች አብራሩለት። ማብራራት የሚያስፈልጓችሁ ቃላት፥ አዲስ ልደት፥ ማደጎነት፥ መቤዠት፥ ጽድቅና ስርየት ናቸው።

8. የቅድስናን ሃላፊ፥ ያሁንና የወደፊት ገጽታዎች አብራራ። ወደ መንግሥተ ሰማይ እስክንደርስ ድረስ ለምን ፍጹም ቅዱሳን ልንሆን እንደማንችል ግለጽ።

9. ከአፍሪካ ዓውድ አንጻር፥ ቅድስና፥ ኃፍረትና በደል ምን እንደ ሆኑ ተወያዩ። ይህንኑ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ የቅድስና፥ ኃፍረትና በደል መገለጥ ጋር አዛምዱ።

10. ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የተነሣ ሁሉም ሰው እንደሚድን ለሚናገር ሰው፥ ምን ምላሽ ትሰጣለህ?

11. በአፍሪካ የደኅንነት፥ የፍቅርና የይቅርታ ጽንሰ-አሳብ ላይ የመስቀሉን ማዕከላዊነት በተመለከተ፥ በቡድን ተወያዩ።

12. በመስቀል ላይ የዋለውን የክርስቶስን መሥዋዕት ከአፍሪካ የመሥዋዕትና የምግብ መሠውያዎች ጽንሰ-አሳብ ጋር እንዴት ታዛምዳለህ?

SUGGESTED FOR FURTHER READING

Adeyemo, Tokunboh. Salvation In African Tradition. Nairobi: Evangel Publishing House, 1979.

Drury, Keith W. Holiness For Ordinary People. Grand Rapids, Michigan: Asbury Press, 1987.

Graham, Billy. Peace With God. Carlisle: OM Publishing, reprinted 1995.

Stott, John. The Cross of Christ. Leicester: InterVarsity Press, 2nd edn 1989.

ምዕራፍ 8

መንፈስ ቅዱስ - ክርስቲያኖችን የሚቀድሰውና የሚያበረታታው

ጆን ኒውተን በዘመኑ ከነበሩት ሰዎች ሁሉ የከፋ ሰው ነበር። ሰዎችን በመሸጥ ገንዘብ የሚያከማች ባርያ ፈንጋይ ነበር። ይህም ሆኖ፥ አሁን ጆን ኒውተንን የምናስታውሰው በእነዚህ ተግባራቱ አይደለም። ይልቁንም፥ «ድንቅኛ ጸጋ» ("Amazing Grace") የሚለውን ጨምሮ አያሌ ውብ መዝሙሮችን የደረሰ መንፈሳዊ የቤተ ክርስቲያን መሪ በመሆኑ እናስታውሰዋለን። በጆን ኒውተንና እርሱን በሚመስሉ በርካታ ሰዎች ሕይወት ይህንን ታላቅ ለውጥ ያመጣው ማን ነው? መንፈስ ቅዱስ ነው። መንፈስ ቅዱስ የሰዎችን ባሕርይና ጠባይ በመለወጥ ይበልጥ ክርስቶስን እንዲመስሉ የማድረግ ኃይል አለው (2 ቆሮ. 3፡18፤ ኤፌ. 3፡20)።

የሐዋርያትን ሥራ መጽሐፍ ስናነብ፥ ምንም እንኳ ዓለም ሙሉ ለሙሉ ማለት ይቻላል ህልውናውንና ተግባሩን ባያውቅም (ዮሐ. 14፡17)፥ ዛሬ በዓለም ውስጥ ከሁሉም በላቀ ሁኔታ የሚሠራው መንፈስ ቅዱስ እንደ ሆነ እንረዳለን። አራቱ ወንጌላት በክርስቶስ ሕይወትና ተግባራት ላይ ሲያተኩሩ፥ የሐዋርያት ሥራ ግን ዘመኑ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በኩል መንፈስ ቅዱስ በሠራው ሥራ ላይ ያተኩራል። የሉቃስ ወንጌል መንፈስ ቅዱስን አሥራ ሁለት ጊዜ ሲጠቅስ፥ ይህ በአራቱ ወንጌላት ውስጥ ከሁሉም የላቀው ድግግሞሽ ነው። ይኸው ጸሐፊ ሉቃስ፥ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ መንፈስ ቅዱስን 42 ጊዜ ደጋግሞ ጠቅሶታል።

ከዚህ እንደምንረዳው ዛሬ በቤተ ክርስቲያንና በግለሰብ ክርስቲያኖች ሕይወት በቀደምትነት በመሥራት ላይ የሚገኘው መንፈስ ቅዱስ ነው። አንዳንድ ክርስቲያኖችን ሊያስደንቅ ቢችልም፥ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን፥ መንፈስ ቅዱስ በማያምኑ ሰዎችም መካከል በከፍተኛ ደረጃ በመሥራት ላይ ይገኛል። በዮሐንስ 16፡8 ኢየሱስ፥ «እርሱም [መንፈስ ቅዱስ] መጥቶ ስለ ኃጢአት ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል» ይላል። ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው፥ ሰዎችን ስለ ኃጢአታቸው በመውቀስ ይቅርታ ወደሚያገኙበት ወደ ኢየሱስ የሚመራቸው መንፈስ ቅዱስ ነው። መንፈስ ቅዱስ ሁልጊዜም በዓለም ሁሉ ስለሚገኝ፥ ከእርሱ

ለመሸሸግ የሚችል ግንም የለም። መዝሙር (139)፡7-10፥ «ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ፥ አንተ በዚያ ነህ፤ ወደ ሲኦልም ብወርድ፥ በዚያ አለህ። እንደ ንስር የንጋትን ኮከብ ብወስድ፥ እስከ ባሕር መጨረሻም ብበርር፥ በዚያ እጅህ ትመራኛለች፥ ቀኝህም ትይዘኛለች» ይላል።

ኢየሱስ በዕለተ-ብዓለ-ሃምሳ መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ላይ በወረደ ጊዜ ከሚፈጽመው ተግባር የተነሣ፥ የእርሱ ከዓለም መሄድ ለጥቅማችን እንደ ሆነ ተናግሯል። ይህም የሆነው ኢየሱስ ባይሄድ፥ መንፈስ ቅዱስ ስለማይመጣና ኢየሱስ ከሄደ ግን መንፈስ ቅዱስን ለክርስቲያኖች ስለሚልክ ነው (ዮሐ. 16፡7)። ኢየሱስ ቢሄድና መንፈስ ቅዱስ ቢመጣ መልካም የሚሆነው ለምንድን ነው? በቀላሉ በትንሣኤ አካሉም ቢሆን፥ ኢየሱስ በአንድ ጊዜ በአንድ ስፍራ ብቻ ይገኝ ስለ ነበር ነው። በተወሰነ ጊዜ የህልውናውን ኃይልና በረከት ሊቀበሉ የሚችሉት ባቅራቢያው የሚገኙ ሰዎች ብቻ ነበሩ። ዛሬ መንፈስ ቅዱስ በዓለም ክርስቲያኖች ባሉበት ስፍራ ሁሉ አለ። ይህም በመሆኑ፥ የጌታ ህልውና በረከት ክርስቲያኖች ባሉበት ሁሉ አለ!

መንፈስ ቅዱስ ማን ነው? እርሱ አካል ነው? ወይስ አንዳንድ ሰዎች እንደሚያምኑት አንድ የሆነ ኃይል ነው? እውን መንፈስ ቅዱስ አምላክ ነው? አምላክ ከሆነ፥ ከእግዚአብሔር አብና ከእግዚአብሔር ወልድ ይለያል? ዛሬ መንፈስ ቅዱስ በዓለም ምን ይሠራል? ህልውናውንና ተግባሩን እንዴት ለይተን እናውቃለን? በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማለት ምን ማለት ነው? በዚህ ምዕራፍ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ እንሻለን፡-

ሀ. መንፈስ ቅዱስ አካል እንደ ሆነ እንዴት እናውቃለን?

ለ. መንፈስ ቅዱስ አምላክ እንደ ሆነ እንዴት እናውቃለን?

ሐ. መንፈስ ቅዱስ ከወልድና ከአብ የተለየ አካል ነው?

መ. በመጽሐፍ ቅዱስ ሥራውን ለመግለጽ ከተጠቀሱት ተምሳሌቶች፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ምን እንማራለን?

ሠ. ዛሬ መንፈስ ቅዱስ በማያምኑ ሰዎች መካከል ምን ይሠራል?

ረ. መንፈስ ቅዱስ ለክርስቲያኖች ምን ይሠራል?

ሰ. ለእያንዳንዱ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ዕቅድ ምንድን ነው?

ሸ. መንፈስ ቅዱስ ክርስቲያኖች ክርስቶስን ይመስሉ ዘንድ እንዴት ይለውጣቸዋል?

ቀ. ለሁሉም ክርስቲያኖች በአጠቃላይ የመንፈስ ቅዱስ ዕቅድ ምንድን ነው?

በ. በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማለት ምን ማለት ነው?

ሀ. መንፈስ ቅዱስ አካል እንደ ሆነ እንዴት እናውቃለን?

አንዳንድ ሰዎች መንፈስ ቅዱስ አካል ሳይሆን፥ እንዲያው ተጽዕኖ የሚያሳድር ስሜት ወይም የሆነ ኃይል እንደ ሆነ ያስባሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን መንፈስ ቅዱስ አካል እንደ ሆነ ያስተምረናል። መንፈስ ቅዱስን ለመግለጽ ያገለገለው የግሪክ ቃል «ኒውማ» ("Pneuma") ጾታዊ ገደብ ያልተደረገበት ሲሆን፥ መጽሐፍ ቅዱስ ግን በዮሐንስ 16፡13 እንደምንመለከተው «እርሱ» በሚል ተውላጠ ስም ይጠራዋል፤ «እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል።» ስለ ሆነም፥ መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስን እንደ አካል ይገልጸዋል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ ተገለጸው፥ መንፈስ ቅዱስ የሰብአዊ አካል አሳብና ፈቃድ አለው። እርሱ ሰው የሚያደርገውን ያደርጋል። ጳውሎስና በርናባስን ለወንጌል አገልግሎት ሲጠራ ትእዛዛትን ሰጣቸው (የሐዋ. 13፡2)። መንፈስ ቅዱስ ነገሮችን ለሕዝቡ ይገልጻል። ለምሳሌ የእግዚአብሔርን መሢሕ እስከሚያይ ድረስ እንደማይሞት ገልጾለታል (ሉቃ. 2፡25-26)። እንዲሁም ሐናንያና ሰጲራ ንብረታቸውን በሸጡ ጊዜ የተቀበሉትን የገንዘብ ልክ በውሸት በመናገር ማታለላቸውን ለጴጥሮስ ገልጾአል (የሐዋ. 5፡1-9)። መንፈስ ቅዱስ ለያንዳንዱ ክርስቲያን የትኛውን መንፈሳዊ ስጦታ እንደሚሰጥ ይወስናል (1 ጴጥ. 4፡10)።

ከአሳብና ፈቃድ በተጨማሪ፥ መንፈስ ቅዱስ እንደ ፍቅር (ሮሜ 15፡30)፥ ደስታ (ሮሜ 14፡17)፥ ኃዘን (ኤፌ. 4፡30) የመሳሰሉ ሰብአዊ ስሜቶች አሉት። መንፈስ ቅዱስ አስራኤላውያን በእግዚአብሔር ላይ ከነበራቸው የዓመፀኛነት አመለካከት የተነሣ ለአርባ ዓመታት በምድረ በዳ

ሲቅበዘበዙ፥ በእነርሱ ላይ የነበረውን ቁጣና ኃዘን ገልጾአል (ኢሳ. 63፡10)።

ለ. መንፈስ ቅዱስ አምላክ እንደ ሆነ እንዴት እናውቃለን?

አንዳንድ ክርስቲያኖችን ጨምሮ ብዙ ሰዎች መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር እንደሚያንስ ያስባሉ። መጽሐፍ ቅዱስስ ምን ይላል?

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር አብና ከእግዚአብሔር ወልድ ጋር እኩል ሆኖ ቀርቧል። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ታላቁን ተልዕኮ ሲሰጥ፥ «ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ... ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው» ብሏል (ማቴ. 28፡19)። ሦስት የተለያዩ ሰዎች ቢሆኑ ኖሮ፥ ሦስት ስሞች ይኖሩአቸው ነበር። ይሁንና፥ አንድ አምላክ ብቻ ስላለ፥ አንድ ስም ብቻ አለ። የእግዚአብሔር ስም አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ነው። ኢየሱስ ሦስቱም የእግዚአብሔር አካላት እኩል እንደ ሆኑ ገልጾአል። አብ እግዚአብሔር ነው፤ ወልድ እግዚአብሔር ነው፤ መንፈስ ቅዱስም እግዚአብሔር ነው።

በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ፥ ጴጥሮስ ለሐናንያ ከንብረቱ የተወሰነውን ስለ ሸጠበት ዋጋ እንደ ዋሸ ነግሮታል። ከዚያም ጴጥሮስ ሐናንያ መንፈስ ቅዱስን እንደ ዋሸ ገለጸለት (የሐዋ. 5፡3)። በዚህም ሐናንያ እግዚአብሔርን ዋሸ (የሐዋ. 5፡4)። በዚህ ታሪክ፥ ጴጥሮስ መንፈስ ቅዱስን እግዚአብሔር ብሎ ይጠራዋል። እንደ ኢሳይያስ 9፡6 የመሳሰሉ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦችም ተመሳሳይ ነገር ያስተምራሉ። በ2ኛ ቆሮንቶስ 3፡17፥ ጳውሎስ፥ «ጌታ ግን መንፈስ ነው» ብሏል። መንፈስ ቅዱስ በኢሳይያስ 61፡1 እና በሐዋርያት ሥራ 8፡39 የጌታ መንፈስ ተብሎ የተጠራ ሲሆን፥ በ1ኛ ሳሙኤል 10፡10 እና ሮሜ 8፡14 የእግዚአብሔር መንፈስ ተብሏል። በመሆኑም፥ መንፈስ ቅዱስ በብሉይም ሆነ አዲስ ኪዳን እንደ እግዚአብሔር ተለይቶ ታውቋል።

ሐ. መንፈስ ቅዱስ ከወልድና ከአብ የተለየ አካል ነው?

አንዳንድ ሰዎች መንፈስ ቅዱስ ለእግዚአብሔር ወይም ለኢየሱስ የተሰጠ ሌላ ስም እንደ ሆነ ያስባሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? ይህንን ጥያቄ ለመመለስ፥ እስኪ የኢየሱስን ጥምቀት ታሪክ እናስታውስ። በዚያን ወቅት፥ መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስ መሢሕ መሆኑን እንዴት እንደ ተረዳ

ገልጾአል። ዮሐንስ፥ «መንፈስ ከሰማይ እንደ ርግብ ሆኖ ሲወርድ አየሁ፤ በእርሱ ላይም ኖረ» ብሏል (ዮሐ. 1፡32)። ዮሐንስ ኢየሱስን በተመለከተበት ተመሳሳይ የጊዜ ቅጽበት፥ የመንፈስ ቅዱስን አካላዊ መገለጽ አየ። ዮሐንስ ገለጻውን በመቀጠል፥ «እኔም (ክርስቶስ እንደ ሆነ) አላውቀውም ነበር፥ ዳሩ ግን በውኃ አጠምቅ ዘንድ የላከኝ እርሱ፥- መንፈስ ሲወርድበትና ሲኖርበት የምታየው . . . እርሱ ነው አለኝ» ብሏል (ቁ. 33)።

መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ በኢየሱስ ላይ ማረፉ ብቻ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር አብም በተመሳሳይ ጊዜ፥ «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» ሲል ተናግሯል (ማቴ. 3፡16-17)። በዚህ ወቅት፥ ሦስቱም የእግዚአብሔር አካላት በተመሳሳይ ጊዜ ተገኝተው የክስተቱ ተካፋዮች ሆነዋል። ይህም መንፈስ ቅዱስ ከኢየሱስና ከአብ የተለየ አካል እንደ ሆነ ያሳያል።

በታላቁ ተልዕኮ፥ ኢየሱስ ተከታዮቹ ሰዎችን በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲያጠምቁ እንዳዘዛቸው አስታውስ። ይህም ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ የተለየና ዳሩ ግን በእኩልነት የሚኖር አካል እንደ ሆነ ያስረዳናል። በዮሐንስ 16፡7 ኢየሱስ፥ «እኔ ብሄድ ግን እርሱን (መንፈስ ቅዱስን) እልክላችኋለሁ» ብሏል። በዚህ ስፍራ ኢየሱስ ራሱን ከመንፈስ ቅዱስ ይለያል።

መ. በመጽሐፍ ቅዱስ ሥራውን ለመግለጽ ከተጠቀሱት ተምሳሌቶች፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ምን እንማራለን?

በመጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስ በቀጥታ የእግዚአብሔር መንፈስ ተብሎ ከመጠራቱ ባሻገር፥ በአያሌ ምስላዊ ማብራሪያዎች ተገልጾአል። እነዚህ ምስል መሳይ ማብራሪያዎች እያንዳንዳቸው ስለ መንፈስ ቅዱስና ተግባሩ ተጨማሪ ግንዛቤ ያስጨብጡናል።

መንፈስ ቅዱስ እንደ እሳት (የሐዋ. 2፡3)

በዕለተ-ብዓለ-ሃምሳ መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ተከታዮች ላይ ሲወርድ ህልውናው ከተገለጸባቸው መንገዶች አንዱ «የእሳት ልሳን» በሚመስሉ ነገሮች ነበር (የሐዋ. 2፡3)። በብሉይ ኪዳን፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ህልውና ከአንድ በበለጡ ሁኔታዎች እንደ እሳት ተገልጾአል። እስራኤላውያን በሲና በረሃ ለአርባ ዓመታት ሲቅበዘበዙ፥ ጌታ

በመካከላቸው እንደ ነበረ የሚያመለክተው በቀን የደመና ዓምድ በሌሊት ደግሞ የእሳት ዓምድ ነበር (ዘኍ. 14፡14)። እግዚአብሔር ለሙሴ ሲናገር፥ እየነደደ በእሳት ከማይቃጠል ቁጥቋጦ ውስጥ ሆኖ ነበር (ዘጸ. 3፡2)።

ናዳብና አብዩድ የተባሉ የካህኑ አሮን ሁለቱ ልጆች ከመገናኛው ድንኳን ፊት ለእግዚአብሔር እርሱ ያላዘዛቸውን እሳት ለማቅረብ ሲሞክሩ፥ የተፈጠረውን ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ በማለት ይገልጽልናል፡- «እሳትም ከእግዚአብሔር ፊት ወጥቶ በላቸው፥ በእግዚአብሔርም ፊት ሞቱ» (ዘሌ. 10፡2)። በዚህ ክፍል እሳቱ እንዲያደርጉ ባልታዘዙት ወይም ሥልጣን ባልተሰጣቸው ነገር ውስጥ ገብተው በመበደላቸው፥ የእግዚአብሔር ፍርድ እንደ ወረደባቸው ያመለክታል (ዘሌ. 10፡1)።

ኤልያስ ግን ጸሎታቸውን ሰምቶ ለመሥዋዕትነት የቀረበውን በሬ በእሳት እንደሚበላ በመጠየቅ የበዓል ነቢያትን በተፈታተነ ጊዜ፥ እግዚአብሔር እሳት በማውረድ ኤልያስ በመሠውያው ላይ ያስቀመጠውን ሥጋ አቃጠለ፤ ይህም የሆነው የበዓል ነቢያት እስከ እኩለ ቀን ድረስ ያለ ምንም ውጤት ሲጮኹ ከዋሉ በኋላ ነበር (1 ነገሥት 18፡23-39)። በዚህ ጊዜ፥ እሳቱ የኤልያስ መሥዋዕት ተቀባይነት ማግኘቱንና በበዓል ባህላዊ ካህናት ላይ ፍርድ መገለጹን አጣምሮ የሚያሳይ ይመስላል።

እሳት የተጣበቁባቸውን ቆሻሻዎች በማስወገድ የከበሩ ማዕድናትን እንደሚያነጻ ሁሉ፥ አላስፈላጊ ነገሮችን በማስወገድ መንጻትን ያስገኛል። መንፈስ ቅዱስ እንደ እሳት በመገለጹ አማካኝነት የማንጻት (የመቀደስ) ሥራው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጸ ይመስላል። ነቢዩ ሚልክያስ (በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተፈጸመው) የክርስቶስ አገልግሎት «እንደ አንጥረኛ እሳት» እንደሚሆን አመልክቷል (ሚል. 3፡2)። መጥምቁ ዮሐንስም ስለ ኢየሱስ ሲናገር አማኞችን «በመንፈስ ቅዱስና በእሳት» እንደሚያጠምቅ ገልጾአል (ማቴ. 3፡11)፤ ይህም ከኃጢአት መንጻትን (መቀደስን) ያመለክታል።

መንፈስ ቅዱስ እንደ ሕያው ውኃ (ዮሐ. 7፡38)

ኢየሱስ እርካታ እርቋት ባዶነት ለተጫናት ሳምራዊት ሲናገር፥ ጥልቅ መሻቱቿን የሚሞላ ሕያው ውኃ እንደሚሰጣት ገለጸላት (ዮሐ. 4፡10-

14)። በአይሁድ የቂጣ በዓል ፍጻሜ ላይ፥ ኢየሱስ አሁንም ገና ተጠምተው ለነበሩት (ላልረኩት) የራሳቸውን ጥልቅ መሻቶች ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን የሌሎችንም ጉድለቶች የሚሞላ ሕያው ውኃ እንደሚሰጣቸው ተናግሯል (ዮሐ. 7፡37-38)። በዚህ ወቅት፥ ኢየሱስ ይኸው ሕያው ውኃ በእርሱ ለሚያምኑት የሚሰጥ መንፈስ ቅዱስ እንደ ሆነ ገልጾአል (ዮሐ. 7፡39)።

በሕዝቅኤልና ራእይ መጻሕፍት፥ በሰማይ የመንፈስ ቅዱስ መኖር እንደ ሕይወት ውኃ ወንዝ፥ እንደ ብርሌ የጠራ፥ ከእግዚአብሔር ዙፋን የሚፈስና በሚፈስበትም አቅጣጫ ሁሉ ሕይወትን የሚሰጥ ሆኖ ታይቷል (ሕዝ. 47፡1-9፤ 22፡1፥ 17)። በእነዚህ ምንባቦች፥ ዝናብና ውኃ ለበረሃ ሕይወት እንደሚሰጡ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ የሰውን ልብ የጠለቁ መሻቶች እንደሚያረካ ሕያው ውኃ፥ ሕይወት ላልነበረባቸው ሰዎች ሕይወትንና ፍሬያማነትን ሲያመጣ ይታያል።

ምናልባትም በውኃ እንድንጠመቅ የታዘዝነው፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ እንደ ሕያው ውኃ ስለ ተጠቀሰ ይሆናል (ማቴ. 28፡19)፤ ይህም መንፈስ ቅዱስ እንዳጠመቀንና በክርስቶስ አካል ውስጥ እንዳስቀመጠን ለማመልከት ነው (1 ቆሮ. 12፡13)። በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡13 በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት «ከአንዱ መንፈስ (ሕያው ውኃ)» እንዳጠጣን ተጠቅሶአል።

መንፈስ ቅዱስ እንደ ርግብ (ዮሐ. 1፡32)

ክርስቶስ በተጠመቀ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወረደ (ሉቃ. 3፡22)። ርግብ ንቁ፥ የዋህና ጎጂ ባሕርይ የሌላት ወፍ ነች። በዕብራውያን መጽሐፍ፥ ኢየሱስ «ቅዱስና ያለ ተንኮል ነውርም የሌለበት» እንደ ሆነ ተገልጾአል (ዕብ. 7፡26)። ከሰዎች ሁሉ በላይ ኢየሱስ በከፍተኛ ደረጃ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶአል። በጥምቀቱ ጊዜ የርግብ መውረድ፥ ግንም ሰብአዊ ሰው ለመቼውም ሊያደርግ በማይችል ሁኔታ የሰውን ልጆች የልብ ጉድለቶች የሚረዳውንና የሚጠነቀቅላቸውን የዋህ፥ ጎጂ ባሕርይ የሌለውና ሩኅሩኅ የእግዚአብሔር መንፈስ ልብ በክርስቶስ ውስጥ ያሳያል።

በተጨማሪም፥ ርግብ በሙሴ ሕግ መሠረት ድሀ ሰው ለኃጢአት መሥዋዕት የሚያቀርባት ትንሿ መሥዋዕት ነበረች (ዘሌ. 5፡7)። ይህም

ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በምድር ላይ የመጨረሻው ድህ ሳይቀር ሊጠቀምበት የሚችል የኃጢአት መሥዋዕት መሆኑን ያሳያል (ዕብ. 9፡14)።

መንፈስ ቅዱስ እንደ ተቀደሰ ዘይት (ሉቃ. 4፡18)

በብሉይ ኪዳን፥ እግዚአብሔር የመገናኛውን ድንኳን ዕቃዎችና ካህናቱ ራሳቸውን ለመቀባት ቅዱስ ዘይት እንዲያዘጋጁ አዞአል (ዘጸ. 30፡22-30)። ይህ ዘይት ለሌላ ለማንኛውም ዓይነት ዓላማ ሊውል አይችልም ነበር (ዘጸ. 30፡32-33)። ኢየሱስ፥ «የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና፤ ለታሰሩትም መፈታትን ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ፥ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል» ብሏል (ሉቃ. 4፡18-19)። ጥቅሱ እንደሚል፥ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ስለ ተቀባ፥ እነዚህን አገልግሎቶች አከናውኗል። የብሉይ ኪዳን የሥርዓት ሕግ ተምሳሌታዊ ደንቦች ሲጠኑና ከግንዛቤ ሲውሉ፥ የቅባት ዘይቱ የመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት አይሳትም።

በብሉይ ኪዳን ነገሥታትም በተቀደሰው ዘይት ይቀቡ ነበር። ንጉሥ ዳዊትን በተመለከተ፥ ሳሙኤል ወጣቱን ዳዊትን በአባቱና ወንድሞቹ ፊት በተቀደሰው ዘይት ከቀባበት ዕለት አንሥቶ፥ «የእግዚአብሔር መንፈስ በዳዊት ላይ በኃይል» እንደ መጣ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል (1 ሳሙ. 16፡13)።

ሰባት ቅርንጫፎች የነበሩት የመገናኛው ድንኳን መብራት ከንጹሕ የወይራ ዘይት የማያቋርጥ ብርሃን ይሰጥ ነበር (ዘጸ. 27፡20)። መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኑ ሕይወት ውስጥ በምሥጢር የሚኖርና ክርስቲያኑ በኃጢአት ለጨለመች ዓለም ግብረ-ገባዊና መንፈሳዊ ብርሃን እንዲፈነጥቅ የሚያስችለው ነው (ማቴ. 5፡14-16)። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁሉ ዘይት መንፈስ ቅዱስን ያመለክታል። ይህም በአማኙ ልብ ያደረው መንፈስ ቅዱስ፥ በክርስቲያኑ ሕይወት ውስጥ የመንፈሳዊ ኃይልና ብርሃን ድብቅ ምንጭ እንደ ሆነ ያስረዳናል። በመንፈስ ቅዱስ ህልውና አማካኝነት፥ ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ብርሃን ነበር (ዮሐ. 8፡12)። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «እግዚአብሔር የናዝሬቱ ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በኃይልም ቀባው፥ እርሱም መልካም እያደረገ ለዲያብሎስም የተገዙትን

ሁሉ እየፈወሰ ዞረ፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረና» ይላል (የሐዋ. 10:38)።

መንፈስ ቅዱስ እንደ ነፋስ (ዮሐ. 3:8)

የግሪክ ቃል «ኒውማ» በጥቅሱ ዓውደ ንባብ ላይ በመመሥረት፥ «ነፋስ» ወይም «መንፈስ» ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ኢየሱስ ከኒቆዲሞስ ጋር ሲነጋገር፥ ይህንኑ የትርጉም መመሳሰል ገልጾአል። «ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል፥ ድምፁንም ትሰማለህ፥ ነገር ግን ከወዴት እንደመጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም፤ ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲሁ ነው» (ዮሐ. 3:8)።

ነፋስ በእርጋታ እየነፈሰ ሕይወትን እንደሚያድስ ሁሉ፥ ከፍተኛና ለመቋቋም የሚያዳግትም ሊሆን ይችላል። የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በነፋስ ተምሳሌትነት መገለጹ ከፍተኛ ትርጉም አለው። ነፋስ የማይታይ ሆኖ፥ ዳሩ ግን ውጤቱ በቀላሉ ከዓይን ሊገባ እንደሚችል ሁሉ፥ መንፈስ ቅዱስም የክርስቶስን ወንጌል በዓለም ሁሉ ያሰራጨ ታላቅና የማይታይ የእግዚአብሔር ነፋስ ነው። በዕለተ-ብዓለ-ሃምሳ የመንፈስ ቅዱስ መምጣት ከተገለጸባቸው ሁኔታዎች አንዱ «ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ» መምጣቱ ነው (የሐዋ. 2:2)። እንዲሁም፥ መንፈስ ቅዱስ በጌታ ለመነቃቃት ለሚሹ ክርስቲያኖች፥ የማይታይ አነቃቂ መንፈሳዊ እስትንፋስ ነው።

ሠ. ዛሬ መንፈስ ቅዱስ በማያምኑ ሰዎች መካከል ምን ይሠራል?

መንፈስ ቅዱስ በዓለም የክፋትን መበራከት ይከለክላል

ዛሬ በዓለም ውስጥ መንፈስ ቅዱስና የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ባይኖሩ ኖሮ፥ በዚህች ዓለም ለመኖር አይቻልም ነበር። የሰዎች ልብ በትክክል ምን እንደሚመስል ሙሉ ለሙሉ ስለማንረዳ፥ ዕድሉ ቢያጋጥማቸው ምን እንደሚያደርጉ አናውቅም።

መንፈስ ቅዱስ ሰዎች ለማድረግ ከሚፈልጓቸው ክፋቶች ብዙዎቹን ይከለክላል። ምናልባት በ2ኛ ተሰሎንቄ 2:7 ሥርዓት-አልበኝነትን እንደሚከለክል ሆኖ የተገለጸው ይሽው መንፈስ ቅዱስ ሳይሆን አይቀርም። በዘፍጥረት፥ አቤሜሌክ ሣራን ለሚስትነት በወሰደ ጊዜ፥ እግዚአብሔር

አቤሜሌክን ከአብርሃም ሚስት ጋር እንዳያመነዝር እንደ ከለከለው ይናገራል (ዘፍጥ. 20፡6)።

ዛሬ በዓለም ውስጥ ብዙ ወንጀልና ጭካኔ ተበራክቶ ስለሚታይ፥ መንፈስ ቅዱስ ሁሉንም ክፋት እንደማይከለክል ግልጽ ነው። ይሁንና፥ መንፈስ ቅዱስ ክፋትን የመቋቋም ተግባሩን ከመቅጽበት ቢያቆም ኖሮ፥ ዓለም ለመኖር የማይቻልባት ስፍራ ትሆን ነበር።

መንፈስ ቅዱስ ክፋትን ለመከልከል የተለያዩ መንገዶችን ይጠቀማል። አንዳንድ ጊዜ መንግሥትን፥ ሕግጋትንና ፖሊሶችን ይጠቀማል (ሮሜ 13፡3-4)። እንዲሁም፥ ለክርስቲያኖች ጸሎት ምላሽ በሚሰጥበት ጊዜ በእግዚአብሔር ቅዱሳን መላእክት ይጠቀማል (የሐዋ. 12፡3-8)። የቅዱሳን መላእክትን ሥራ በተመለከተ በምዕራፍ 10 ውስጥ የበለጠ ማብራርያ እናቀርባለን። ምናልባት መንፈስ ቅዱስ ባጠቃላይ በዓለም ክፋትን የሚከለክልበት ዋንኛው መንገድ ለሰዎች ልብ ስለ ትክክለኛና የተሳሳቱ ነገሮች በመናገርና ለተሳሳቱ ተግባራቸውም በመውቀስ ነው። ኢየሱስ፥ «እርሱም (መንፈስ ቅዱስ) መጥቶ ስለ ኃጢአት ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል» ብሎአል (ዮሐ. 16፡8)። ይህም መንፈስ ቅዱስ በሰው ልጆች የትክክለኛና የተሳሳተ ግንዛቤ ውስጥ የሚሠራውን ተግባር ያመለክታል - የሕሊና ዳኝነት። ከዚህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የተነሣ ነው ሰዎች ይቅርታ የሚያስፈልጋቸው ኃጢአተኞች እንደ ሆኑ የሚገነዘቡት።

መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ስለ ኃጢአታቸው በመውቀስ፥ ትኩረታቸውን ወደ ክርስቶስ ይመራል

ከመንፈስ ቅዱስ ክፋትን የመከልከል ተግባር ጋር በቅርብ ተጎዳኝቶ የምናገኘው ሰዎችን ወደ ክርስቶስ የማምጣት ሥራውን ነው። መንፈስ ቅዱስ ሰዎች ለኃጢአታቸው ምላሽ የሚሰጡበት ፍርድ እንደሚጠብቃቸው ያስገነዝባቸዋል። መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ለኃጢአታቸው የበደለኛነት ስሜት እንዲያድርባቸው በማድረግ ሲወቅስ፥ ፍርድና የኃጢአት ቅጣትም እንደሚጠብቃቸው ያስጠነቅቃቸዋል። በዚህ እውነት ላይ በመንተራስ፥ ሰዎች ንስሐ ገብተው ወደ ክርስቶስ እንዲመለሱ ይለምናቸዋል (ዮሐ. 16፡8-13)።

መንፈስ ቅዱስ ስለ ኃጢአት በደለኛነታቸው በመውቀስና ክርስቶስ እንደሚያስፈልጋቸው በመግለጽ ሥራውን በታማኝነት በሰዎች ልብ ውስጥ

ባይፈጽም ኖሮ፥ ማናቸውም ንስሐ ሊገቡና በክርስቶስ ሊያምኑ አይችሉም ነበር፤ ከመንፈስ ቅዱስ ሥራ ውጭ በክርስቶስ ማመን የማይቻል ነው (ዮሐ. 6፡44፤ ሮሜ 8፡9)።

ሰዎች ስለ ክርስቶስ ለማሰብ መፍቀዳቸውና ያደረገላቸውን ማስተዋላቸው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው። ኢየሱስ፥ «እርሱ ያከብረኛል፥ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና» ብሏል (ዮሐ. 16፡14)። አንድን ሰው ማክበር ማለት ወደዚያ ሰው ድንቅኛ ብቃቶች ቀልብን መሳብ ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ የሰዎችን አትኩሮት ወደ ክርስቶስና ክርስቶስ ወዳደረገላቸው ተግባር ይስባል እንጂ፥ ወደ ራሱ አይስብም (ዮሐ. 15፡26)።

የሚያሳዝነው፥ ሰዎች ይህንኑ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ሊቃወሙና በእግዚአብሔር ላይ ልባቸውን ሊያደነድኑ መቻላቸው ነው። እግዚአብሔር ሰዎች ልባቸውን እንዳያደነድኑ ያስጠነቅቃቸዋል (ዕብ. 3፡15)። ልባቸውን ካደነደኑ እነርሱን ወደ ንስሐ ማምጣት ስለማይቻል (ዕብ. 6፡6)፥ ከደኅንነት ርቀው ይጠፋሉ። የሚያሳዝን እውነት ቢሆንም፥ መጽሐፍ ቅዱስ ልባቸውን በጣም በማደንደናቸው ሕሊናቸው ስለ ደነዘዘና የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ ለመስማት ስላልቻሉት ሰዎች ይናገራል (1 ጢሞ. 4፡2)። ፈርዖን በእግዚአብሔር ላይ ልቡን አደንድኖ ነበር (ዘጸ. 5፡2፤ 8፡15)። በአዲስ ኪዳን ፈሪሳውያንና የአይሁድ መሪዎችም ተመሳሳይ ነገር አድርገዋል (የሐዋ. 7፡1-58)።

ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ ልባቸውን ሲያደነድኑ የትክክለኛነትንና የስሕተተኛነትን እውነተኛ ግንዛቤ ያጣሉ። ለዚህ ነው ዛሬ ሰዎች ክፉ ተግባራቸው ግድ ሳይሰጣቸው፥ እንዲህ ዓይነት ክፉ የወንጀልና የሞኪኔ ተግባራትን የሚፈጽሙት። ሰዎች ልባቸውን ለመንፈስ ቅዱስ ድምፅ እያደነደኑ ስለ ሆነ፥ ዓለማችን ባለማቋረጥ ጨካኝና ክፉ እየሆነች ነው።

ሰዎች ልባቸውን እንደዚህ ሲያጠነክሩ፥ ክፉውን መልካም መልካሙን ክፉ አድርገው ለማሰብ ይታለላሉ (1 ጢሞ. 4፡2-3)። ይህ በቅርቡ በከፍተኛ ደረጃ እያደገ ለመጣው ወሲባዊ ግድፈትና ውርጃ አንዱ ምክንያት ነው። ሰዎች ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ድምፅ ልባቸውን እያጠነከሩ ስለ መጡ፥ እነዚህ አስከፊ ኃጢአቶች ስሕተት እንደ ሆኑ አያስቡም። በብዙ አጋጣሚዎች ስለ ክርስቶስ ቢሰሙም አልተቀበሉትም። አንድ ሰው ክርስቶስን ሲተው፥ የደኅንነትን ተስፋ ያጣና በማያቋርጥ

ምግባረ-ብልሹነት ውስጥ ይዘፈቃል። ወንጀሉ የተረጋገጠባቸው በደለኞች ለጥፋታቸው ምንም የጸጸት ምልክት ሳያሳዩ የመጨረሻ ቃላቸውን ሲሰጡ መስማት እየተለመደ መጥቷል።

ረ. መንፈስ ቅዱስ ለክርስቲያኖች ምን ይሠራል?

ከፍ ብለን ያለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ ግንም ሰው ለኃጢአቱ ንስሐ ገብቶ በክርስቶስ እንደማያምን ተመልክተናል። መንፈስ ቅዱስ ሰውን ስለ ኃጢአቱ በመውቀስ፥ ለኃጢአቱ ፍርድ እንደሚመጣበት እንዲያምን ይገፋፋዋል (ዮሐ. 16:8-11)። እንዲሁም፥ መንፈስ ቅዱስ ሰው ለኃጢአቱ ይቅርታ የሚያገኝበት ብቸኛው መንገድ ክርስቶስ እንደ ሆነ እንዲያምን ይገፋፋዋል። ስለ ሆነም፥ አንድን ሰው ወደ ለውጥ ደረጃ የሚያደርሰው መንፈስ ቅዱስ ነው።

ትክክለኛውን የመለወጥ ተግባር የሚፈጽመውም መንፈስ ቅዱስ ነው። ኢየሱስ ለተማረው የአይሁድ የሃይማኖት መሪ ኒቆዲሞስ፥ «እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፥ ከመንፈስም (ከመንፈስ ቅዱስ) የተወለደ መንፈስ ነው» ብሏል (ዮሐ. 3:5-6)። ዳግመኛ ያልተወለደ ሰው መንፈስ በኃጢአት ምክንያት ሙት ሲሆን፥ ለዚህ ለሞተው የሰው መንፈስ ልደትና ሕይወት ለመስጠት ኃይል ያለው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው (ኤፌ. 2:1-2)። በመንፈሳዊ ሕይወቱ ለሞተ ሰው መንፈሳዊ ሕይወት የመስጠቱ ተግባር «የዳግም ልደት መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ» ይባላል (ቲቶ. 3:5)። ይህ መንፈስ ቅዱስ ለክርስቲያኖች ብግል ከሚፈጽማቸው አያሌ ነገሮች የመጀመሪያው ነው።

አንዳንድ ሰዎች ዳግም ልደት የእግዚአብሔር ሥራ ግብ እንደ ሆነ በማሰብ ይሳሳታሉ። እውነቱ ግን ዳግም ልደት እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ላለው ዕቅድ የመጀመሪያው እንደ ሆነ ነው። ዳግም ልደት ልክ ወደ አንድ አዲስ አገር ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ጣቢያ እንደ መድረስ ነው። በአውሮፕላን ጣቢያው የምንወርደው እዚያ ለመኖር አይደለም። የአውሮፕላን ጣቢያው በአዲሲቱ አገር ለምናከናውናቸው አዳዲስ ተግባራት ሁሉ የመነሻ ነጥብ ብቻ ነው።

በክርስቶስ ዳግም መወለዱም ይኸው ነው። ዳግም ልደት በአዲሱ የእግዚአብሔር መንግሥት አዲስ ክስተት ነው። ከዚህ ቀደም በሰይጣን

አገዛዝ ሥር በዚህ ዓለም ውስጥ ኑረናል (ኤፌ. 2፡2)። አሁን ደግሞ በክርስቶስ በማመን የእግዚአብሔር ልጆች ሆነናል (ዮሐ. 1፡12)። በኢየሱስ ክርስቶስ አገዛዝ ወደሚመራው የእግዚአብሔር መንግሥት ተሻግረናል። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ከጨለማ ሥልጣን አዳነን . . . ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን» ይላል (ቆላ. 1፡13)።

መንፈስ ቅዱስ ለክርስቲያኖች የሚያደርጋቸውን አያሌ ነገሮች ለመረዳት፥ እግዚአብሔር ለያንዳንዱ አማኝ የወጠነውን ዕቅድ መገንዘብ አለብን። በተጨማሪም፥ ለአማኞች ሁሉ በአጠቃላይ (ለቤተ ክርስቲያን) ያዘጋጀውን ዕቅድ መረዳት አለብን። መንፈስ ቅዱስ ለእኛ የሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ከዚያ ዕቅድ ጋር የሚዛመዱ ናቸው።

ሰ. ለእያንዳንዱ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ዕቅድ ምንድን ነው?

እግዚአብሔር ለያንዳንዱ ክርስቲያን ያለው ዓላማ እርሱ ወይም እርስዋ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመምሰል በባሕርይ እንዲለወጡ ነው (ሮሜ 8፡29)። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «እኛም ሁላችን ... የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን» ይላል (2 ቆሮ. 3፡18)።

ሐዋርያው ጴጥሮስ ለዚህ ዓይነቱ ለውጥ ምሳሌ ይሆነናል። በገሊላ ባሕር ዳርቻ የሚኖር ያልታወቀ ዓሣ አጥማጅ ነበር። ስሜታዊ፥ ችኩል (ማቴ. 16፡22፤ ዮሐ. 21፡7) እና ተናዳጅ ሰው ነበር (ዮሐ. 20፡10)። ለኢየሱስ ስላለው ታማኝነትና ቢያስፈልግም ለእርሱ ለመሞት ዝግጁ መሆኑን በትምክህት ቢናገርም (ዮሐ. 13፡37)፥ ከጥቂት ሰዓታት በኋላ በባርነት በምትኖር ልጃገረድ ፊት ክርስቶስን እንደማያውቅ ክዱል (ዮሐ. 18፡17)።

ይሁንና፥ መንፈስ ቅዱስ በጴጥሮስ ሕይወት ትልቅ ተግባር ፈጽሞአል። ክርስቶስን ለገደሉት ለእነዚያው ሰዎች የቤተ ክርስቲያንን የመጀመሪያ የወንጌል መልእክት ለማስተላለፍ ቻለ። በዚህም ሰብከቱ፥ ሦስት ሺህ ሰዎች ዳግም ተወለዱ (የሐዋ. 2፡14-41)! በኋላም እንዲህ ታላቅ መሪ ሆኖ በመለወጡ፥ የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያው ሊቀ-ጳጳስ እንደ ሆነ አውጃለች። በዓለም ከሚገኙ ገናና የቤተ ክርስቲያን ሕንፃዎች አንዱ በእርሱ ስም የተጠራው የሮሙ ቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን ነው።

ይህም ብቻ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ፥ የጴጥሮስ ስም በሰማይ የምትገኝ ዘላለማዊት የእግዚአብሔር ከተማ የመሠረት. ድንጋዮች አንዱ አካል እንደ ሆነ ይናገራል (ራእይ 21፡14)። የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በጴጥሮስ ሕይወት እንዲህ የላቀ በመሆኑ፥ ይህንኑ ያልታወቀ ተራ ዓሣ አጥማጅ ለዘላለም የሚከበር ታላቅ ክርስቲያን መሪ አድርጎ ለውጦታል። በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ ስለ ተጠቀሰው ባርያ ፈንጋይ ጆን ኒውተንም ይህንኑ ልንል እንችላለን።

በሚሊዮን የሚቆጠሩ የአፍሪካ ሕዝቦችም፥ ለዚሁ ሕይወት ለዋጭ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ምስክርነታቸውን ሊሰጡ ይችላሉ። ከጠንቋይ፥ ከአጋንንት እስራት፥ ጭካኔ ከተሞላበት የወንጀል ተግባር፥ ከወሲብ ኃጢአት፥ ከዕፅ ሱሰኛነትና ከሌሎችም በሺህ ከሚቆጠሩ ኃጢአቶች ታድነዋቸዋል። በክርስቶስ ሙሉ አዲስ ሕይወት ሰጥቶአቸዋል። እያንዳንዱ እውነተኛ ክርስቲያን ሕይወትን ለሚለውጠው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ምሳሌ ነው። የተነሳቆለውን ኃጢአተኛ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ወደ ክርስቶስ ባሕርይ መለወጥ የእግዚአብሔር ዓላማ ነው።

ሸ. መንፈስ ቅዱስ ክርስቲያኖች ክርስቶስን ይመስሉ ዘንድ እንዴት ይለውጣቸዋል?

መንፈስ ቅዱስ ወደ ክርስቶስ አምሳል የሚለውጠን እንዴት ነው? መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን የሚያደርገው መኖሪያውን በያንዳንዱ አማኝ ልብ ውስጥ በማድረግ (በእነርሱ ውስጥ በማደር ዮሐ. 14፡16-17) እንደሆነ ይናገራል። መንፈስ ቅዱስ በልባችን ውስጥ ለማደር ሲመጣ፥ የኃጢአት ምኞቶቻችንን ይቃወማል፤ በመሆኑም ክርስቲያኖች በውስጣቸው ከፍተኛ ግጭት ሲካሄድ ይሰማቸዋል። ገላትያ 5፡17፥ «ሥጋ በመንፈስ (ቅዱስ) ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና» ይላል። ምንም እንኳ ኃጢአተኛ ተፈጥሮአችን እነዚህን ለውጦች በከፍተኛ ደረጃ ቢቃወምም፥ ለመለወጥና ክርስቶስን ለመምሰል መሻትና ጥንካሬን የሚሰጠን በውስጣችን ያደረው መንፈስ ቅዱስ ነው (ፊልጵ. 2፡13፤ ገላ. 5፡17)።

ይህም ሆኖ፥ እግዚአብሔር የምርጫ ነፃነታችንን አይጫነውም። ልንለወጥ ከፈለግን የመንፈስ ቅዱስን ትእዛዝ ለመጠበቅ መምረጥ አለብን። ይህም ብዙ ክርስቲያኖች በባሕርያቸው ብዙ ለውጥ ለምን እንደማያሳዩ ይገልጻል፤ የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ ሰምቶ እንደ መታዘዝ ይቃወማሉ። ስለ ሆነም መጽሐፍ ቅዱስ፥ «በመንፈስ ተመላለሱ፤ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ» በማለት ያደፋፍረናል (ገላ. 5፡16)።

ራሳችን የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ ለመታዘዝ ስንመርጥ ብቻ ነው እግዚአብሔር የምንለወጥበትን ብርታት የሚሰጠን። ፊልጵስዩስ 2፡13፡ «ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና» ይላል።

ሁኔታው የኤሌክትሪክን ብርሃን ከማብራት ጋር ሊመሳሰል ይችላል። ማብሪያውን መጫኑ ጠባያችንን ለመለወጥ ውሳኔ ከማድረግ ጋር ሊወዳደር ይችላል። በሽቦዎቹ ውስጥ የኤሌክትሪክ ኃይል ካለ፡ አምፑሉ ይበራል፡ የኤሌክትሪክ ኃይል ከሌለ ግን አምፑሉ አይበራም። የማያምኑ ሰዎች (በማብራሪያው እንደ ተጠቀሰው ማብሪያውን በመጫን) መንገዳቸውን ለመለወጥ ሊፈልጉ ይችላሉ። ይሁንና፡ (በሽቦዎቹ ውስጥ የኤሌክትሪክ ኃይል ላይኖር እንደሚችል ሁሉ) ባሕርያቸውን የሚለውጥ ኃይል ከሌለ፡ ለጥቂት ጊዜ ሊለወጡና ወዲያው ደግሞ የኃጢአት ምኞቶች ሕይወታቸውን ሊቆጣጠሩ ይችላሉ።

ባንጻሩ፡ ክርስቲያኖች ጠባያቸውን ለመለወጥ ሲፈልጉ፡ በትክክል የለውጡን ሂደት ለማገዝ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በሕይወታቸው ውስጥ ይገኛል። እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ሲወስኑ፡ መንፈስ ቅዱስ ጠባያቸውን እንዲለውጡ ይረዳቸዋል። ከዚያም ለሌሎችም ብርሃን ይሆናሉ። ኢየሱስ፡ «መልካሙን ሥራችሁን አይተው፡ በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ» ብሏል (ማቴ. 5፡16)።

ከዓለም የተቀደስነው ወይም የተለየነው የኢየሱስ ክርስቶስን የከበረ ባሕርይ እንድናንጸባርቅ ነው። ጳውሎስ፡ «እግዚአብሔር በመንፈስ መቀደስ አውነትንም በማመን ለመዳን እንደ በኩራት መርጦአችኋልና፡ ለዚህም የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር ለማግኘት በወንጌላችን ጠራችሁ» ሲል ጽፎአል (2 ተሰ. 2፡13-14)። እንደ እኛ ዓይነት ምስኪን ኃጢአተኞችን የእግዚአብሔር ሰዎች እንዲሆኑ የመለየቱ ሥራ በዓለም የክርስትና እምነት አውነት እንደ ሆነ የሚያሳይ ታላቅ ማረጋገጫ ነው። የትኛውም ሌላ ሃይማኖት ወይም ፍልስፍና እንዲህ ዓይነቱን የማያቋርጥ የባሕርይ ለውጥ አላስከተለም - ኃጢአተኞች ክርስቶስን ይመስሉ ዘንድ ሊለውጥ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነውና።

ይህንኑ ኃጢአተኛ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ አምሳል የመለወጥ ታላቅ ተግባር ለመፈጸም፡ መንፈስ ቅዱስ ለክርስቲያኑና በክርስቲያኑ ውስጥ

አያሌ ነገሮችን ያደርጋል። መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኖች ውስጥ ከሚያደርጋቸው ነገሮች ጥቂቶቹ ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

አዲስ ልደት - ይህ ተግባር በምዕራፍ ሰባት ተገልጸአል። መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ለሚያምኑ ሰዎች መንፈሳዊ ልደትና አዲስ ሕይወት ያጎናጽፋል። ይህም ተግባር በአዲስ ኪዳን ውስጥ በአያሌ የቃላት ምስሎች ተብራርቶአል። በቲቶ 3:5፥ የአዲስ ልደት መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ ተብሏል። በዮሐንስ 3:3 «ዳግም መወለድ» ተብሏል። በአንደኛ ቆሮንቶስ 12:13፥ የክርስቶስ የአካል ክፍሎች በምንሆንበት በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅና ከመንፈስ ቅዱስ መጠጣት ተብሏል። እነዚህ ሁሉ መግለጫዎች በዳግም ልደት ጊዜ ወደሚፈጸመው አንድ ታላቅ ተአምር ያመለክታሉ፤ በዚህም በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ሟቹ ሰብአዊ ነፍሳችን ለእግዚአብሔር ሕያው ይሆናል።

ማተም - በክርስቲያን ልብ ውስጥ ያደረው መንፈስ ቅዱስ በዚያ ክርስቲያን ላይ የባለቤትነትን ማኅተም ያኖራል፤ በመሆኑም፥ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ አባል መሆናችን ለዘላለም ዋስትና ያለው ነው (2 ቆሮ. 1:21-22፤ ኤፌ. 1:13-14)። ይህ የባለቤትነት ማኅተም የክርስቶስ መሆናችንን ያረጋግጣል። በጥበቃው ተማምነን እንኖራለን። በተጨማሪም፥ አንድ ቀን የእግዚአብሔርን የማዳን ፍጻሜ እንደምንመለከትና ክርስቶስ ሲመለስ የትንሣኤ አካል እንደምንለብስ ዋስትና ይሰጠናል (ኤፌ. 4:30)። በዚህ ዘልኩ፥ በክርስቲያን ውስጥ የሚገኘው የመንፈስ ቅዱስ ማኅተም አንድ ሰው ቢስክሌት ወይም ሌላ ዓይነት ዕቃ በሚገዛበት ጊዜ የሚከፍለው ቀብድ ዓይነት ነው። ቀብዱ የከፈለው ሰው በኋላ ሙሉውን ሒሳብ እንደሚከፍል ዋስትና ይሰጣል። የመንፈስ ቅዱስ መኖር፥ አንድ ቀን በእኛ ውስጥ የማዳን ሥራውን እንደሚፈጽም በዋስትና የሚሰጠን ቀብድ ነው (2 ቆሮ. 1:22)።

ጽናትና ብርታት – መንፈስ ቅዱስ ለክርስቲያኑ ጽናትና ብርታት ይሰጣል (ዮሐ. 14:16፤ ኤፌ. 3:16)። ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን «አጽናኝ» ይለዋል (ዮሐ. 14:16፥ 26፤ 15:26፤ 16:7)፤ ይህም በግሪክ ኋራቅሊጦስ ሲሆን፥ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሶች «ረዳት» (NASB)፥ «አማካሪ» (NIV) ይሉታል። «ኋራቅሊጦስ» የሚለው የግሪክ ቃል አንድን ሰው ለመርዳት፥ ለማበረታታት፥ ለማጽናት ወይም ለመምከር ከአጠገቡ መገኘት የሚል ትርጉም አለው። ሐዋርያው ጳውሎስ አስቸጋሪ የአገልግሎት ተግባሩን

እንዲወጣ ያስቻለው ይኸው የእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ እንደ ሆነ ይናገራል (ቆላ. 1:29፤ 1 ቆሮ. 15:10)። በብሉይ ኪዳን፥ መንፈስ ቅዱስ ለሶምሶንና ዳዊት እንዲህ የላቀ ሥጋዊ ጽናትና ብርታት ስለ ሰጣቸው በባዶ እጃቸው አንበሳን እንደ ነተበ ጨርቅ በጣጥሰው ገድለዋል (መሳ. 14:5-6፤ 1 ሳሙ. 17:36-37)። በአዲስ ኪዳን፥ መንፈስ ቅዱስ በቀደምትነት ለክርስቲያኑ መንፈሳዊ ግብረ-ገባዊ ጥንካሬ ይሰጠዋል (ኤፌ. 3:16፥ 20)። ይሁንና፥ ለወንጌሉ ሥራ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሥጋዊ ጽናትና ትዕግሥትን ይሰጠዋል (ቆላ. 1:29)።

ጸሎት – ብዙውን ጊዜ ምን እንደምንጸልይ ስለማናውቅ፥ መንፈስ ቅዱስ ክርስቲያኑ እንዲጸልይ ይረዳዋል። መንፈስ ቅዱስ ራሱ በትክክል ለክርስቲያኑ ይጸልያል ወይም ጸሎቱን ለእግዚአብሔር አብ ይተረጉማል (ሮሜ 8:26)። ይህንንም በማድረግ፥ መንፈስ ቅዱስ ክርስቲያኑ ከእግዚአብሔር ፈቃድ አኳያ እንዲጸልይ ያስችለዋል (ሮሜ 8:27)። አንዳንድ ጊዜም መንፈስ ቅዱስ በትክክል የክርስቲያኑን ከንፈሮች ለልሳን ስጦታ መገለጫነት በመጠቀም ይጸልያል (1 ቆሮ. 14:14-15)።

አብርሆተ– ቅዱሳት መጻሕፍት- መንፈስ ቅዱስ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃላት ከማስታወሱም በላይ (ዮሐ. 14:26)፥ ለክርስቲያኑ የእግዚአብሔርን እውነት ምንነት ያበራለታል (ዮሐ. 16:13፤ 1 ቆሮ. 2:10-12)።

ምስክርነትና አገልግሎት– መንፈስ ቅዱስ ክርስቲያኖች ጌታን እንዲያገለግሉ ያነቃቃቸዋል (ፊልጵ. 2:13)። በተጨማሪም፥ ክርስቲያኑ ለክርስቶስ በሚሰጠው ምስክርነትና አገልግሎት ላይ ኃይሉን ይጨምራል (የሐዋ. 1:8፤ ቆላ. 1:29)። ሐዋሪያው ጳውሎስ ለራሱ አገልግሎት ይኸው ኃይልና ድፍረት እንደሚያስፈልገው በመገንዘብ፥ ክርስቲያን ወገኖቹ እግዚአብሔር የአገልግሎት በሮችን እንዲከፍትለትና ይህንኑ ኃይል እንዲሰጠው ይጸልዩለት ዘንድ ጠይቋል (ቆላ. 4:3፤ ኤፌ. 6:19-20)። ለዚህም ነው ክርስቲያኖች ለሚሲዮናውያንና ለወንጌላውያን ዘወትር መጸለይ የሚኖርባቸው።

የመንፈስ ፍሬ – የኢየሱስ ክርስቶስን ውብ ባሕርይ ብቃቶች በክርስቲያኑ ውስጥ የሚያፈራው መንፈስ ቅዱስ ነው። እነዚህም የባሕርይ ብቃቶች «የመንፈስ ፍሬ» ይባላሉ (ገላ. 5:22-23)። በእነዚህም ውስጥ፥ ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ገርነት፥ በጎነት፥ ታማኝነት፥ የዋህነትና ራስን

መንፈስ ቅዱስ – ክርስቲያኖችን የሚቀድሰውና የሚያበረታታው መግዛት ተካተዋል። እነዚህ ብቃቶች በሕዝቡ ውስጥ እያደጉና እየበሰሉ ሲሄዱ እግዚአብሔር በጣም ደስ ይሰኛል።

ምሪት – መንፈስ ቅዱስ ክርስቲያኑን በዕለታዊ ሕይወቱና ለጌታው ባለው አገልግሎት ይመራዋል (ሮሜ 8፡14)። ለዚህ ተግባራዊ ምሳሌ የሚሆነን ጳውሎስ ሁለተኛ የሚሲዮናዊነት ጉዞ፥ ጳውሎስና ሲላስ በቢታኒያ ለመስበክ ሲፈልጉ ወደዚያ እንዳይሄዱ በመንፈስ ቅዱስ መከልከላቸው ነው (የሐዋ. 16፡6-7)።

ምልክቶችና ተአምራት – በተለይም የክርስትና ተቃዋሚዎች በሚኖሩበት ጊዜ፥ አንዳንድ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ምልክቶችንና ተአምራትን በመሥራት የወንጌሉን እውነታ ያጠናክራል። ዕብራውያን 2፡3-4፥ «ይህ (ደኅንነት) በጌታ በመጀመሪያ የተነገረ ነበርና፥ የሰሙትም ለእኛ አጸኑት፥ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ እንደ ፈቀደ በምልክትና በድንቅ በልዩ ልዩ ተአምራትም፥ መንፈስ ቅዱስንም በማደል አብሮ መሰከረለት» ይላል። እግዚአብሔር ተአምራትን የሚሠራው ኢየሱስ ክርስቶስን ለማስከበርና ሰዎች በክርስቶስ ያምኑ ዘንድ ለመሳብ እንጂ፥ ለተመልካች የዓይን እርካታ ለመስጠት አይደለም። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን ጳውሎስ በጠንቋዩ ኤልማስ ላይ ያወረደው የዓይነ-ሕውርነት ተአምር ነው (የሐዋ. 13፡8-12)፤ ይህም የሆነው ኤልማስ ጳውሎስና በርናባስ ለቆጵሮሱ የሮም ገዥ የሚያቀርቡትን የወንጌል ስብከት በጥብቅ በመቃወሙ ነው። ይህ ተአምር የሮማው ገዥ ሰርግዮስን በክርስቶስ እንዲያምን አድርጓል (የሐዋ. 13፡12)።

ሙስጣዊ የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት – መንፈስ ቅዱስ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ልጆች እንደ ሆኑና የክርስቶስም ንብረቶች እንደ ሆኑ በልባቸው ይመሰክርላቸዋል (ሮሜ 8፡16፤ 1 ዮሐ. 5፡10)።

ቅባት – መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በሚገባ ያንጹ ዘንድ ቃሉን የሚያስተምሩትንና የሚሰብኩትን ሰዎች ይቀባል (1 ቆሮ. 12፡28፤ 1 ቆሮ. 14፡4፤ 1 ዮሐ. 2፡27)።

ለአገልግሎት መጥራት – በሐዋርያት ሥራ 13፡2 ጳውሎስንና በርናባስን እንደለየ ሁሉ፥ መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ለአገልግሎት ይለያል። ይህንንም ጥሪ ለማጽናት ብዙውን ጊዜ የተጠራው ሰው ከሚገኝበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ምስክርነትና ማበረታቻ እንዲሰጡት ያደርጋል።

መንፈሳዊ ስጦታዎች - መንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዱ ክርስቲያን አንድ ወይም ከዚያ በላይ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ይሰጣል (1 ጴጥ. 4፡10-11)። መንፈሳዊ ስጦታዎች ቤተ ክርስቲያንን በአንድ መንገድ የሚረዱ እግዚአብሔር የሰጣቸው መንፈሳዊ ችሎታዎች ናቸው። የመንፈሳዊ ስጦታዎች ዓላማ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን መገንባት (ማጠናከርና ማነፅ) ነው (ሮሜ 12፡4-6፤ 1 ቆሮ. 12፡4-11)። በምዕራፍ ዘጠኝ ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች በይበልጥ እንነጋገራለን።

ፈተናን ማሸነፍ - መንፈስ ቅዱስ ለጻሎት ምላሽ በመሆን፥ ክርስቲያኖች ፈተናዎችንና የሰይጣንን ቀጥተኛ ጥቃቶች እንዲቋቋሙ ይረዳቸዋል (ማቴ. 26፡40-41)። ሐዋርያው ዮሐንስ፥ «በዓለም ካለው ይልቅ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና» ሲል ጽፎአል (1 ዮሐ. 4፡4)። እንዲሁም፥ ዮሐንስና ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ ከሰይጣን እንደሚጠብቀን ይናገራሉ (1 ዮሐ. 5፡18፤ 2 ተሰ. 3፡3)። በምዕራፍ 12 ክርስቲያን ከጨለማው ኃይላት ጋር ስላለው ግጭት በይበልጥ እናብራራለን።

ፍቅር - መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስን ፍቅር በክርስቲያኖች ልብ ውስጥ ያፈሳል (ሮሜ 5፡5)። ይህ በዘመናት ሁሉ በግለሰብ ክርስቲያኖችና ክርስቲያናዊ ድርጅቶች ለተጀመሩ አያሌ የምሕረትና የእርዳታ ተግባራት ዓይነተኛ ማብራሪያ ነው። ክርስቲያኖች ድሆችን፥ ዓይነ-ስውሮችን፥ አካለ-ስንኩላንን፥ ባሽተኞችንና በዓለም ውስጥ የተለያየ ጉዳት የሚደርስባቸውን ሰዎች በመርዳት የመጀመሪያዎች መሆናቸውን ታሪክ ደግሞ ደጋግሞ ይመዘግባል። ይህም የሆነው መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስን ፍቅር በእነዚህ አማኞች ልብ ውስጥ ስላፈሰሰ ነው። ምእመናን ከመንፈስ ቅዱስ ምሪት አኳያ ሳይሆን፥ ከራሳቸው የኃጢአት ተፈጥሮ አኳያ እንደሚኖሩ ከሚያሳዩ ግልጽ አመልካቾች አንዱ፥ ሐሜት፥ መከፋፈል፥ ውጥረት፥ ጥላቻና ይቅር አለማለት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መኖራቸው ነው።

የክርስቲያን አንድነት- መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኖች መካከል አንድነትንና ኅብረትን ይፈጥራል (ኤፌ. 4፡3-4)። በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መከፋፈል የሚፈጠረው ክርስቲያኖች ከመንፈስ ቅዱስ ምሪት አኳያ ሳይሆን፥ ከራሳቸው የኃጢአት ተፈጥሮ አኳያ ሲመላለሱ ነው (ሮሜ 8፡5-6)። በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድነት፥ ይቅር መባባልና ፍቅር

ካለ በዚያች ቤተ ክርስቲያን የሚያመልኩ ክርስቲያኖች «በመንፈስ እየተመላለሱ» ናቸው ማለት ነው (ገላ. 5፡16፤ ቆላ. 3፡12-14)።

ቀ. ለሁሉም ክርስቲያኖች በአጠቃላይ የመንፈስ ቅዱስ ዕቅድ ምንድን ነው?

የእግዚአብሔር ሕዝቦች (ቤተ ክርስቲያን)፥ በአጠቃላይ በመጀመሪያ ሲፈጥራቸው ይኖራቸው ዘንድ ያቀደውን የኑሮና የተግባር ውበት እንዲያሳዩ ፈቃዱ ነው (ዘፍጥ. 1፡27-28ን ከኤፌ. 4፡22-24 ጋር አወዳድር)። የዚህ ዓለም ግብረ-ገባዊና ማኅበራዊ ሕይወት በኃጢአት ሙሉ ለሙሉ ተበላሽቶአል። የምንኖርበት ዓለም ግብረ-ገባዊና ማኅበራዊ ውድቀት የተጫነው ነው። እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን አማካኝነት ሕዝቦች ለእርሱና ለእርስ በርሳቸው በፍቅር ላይ ተመሥርተው በማኅበረሰቡ ውስጥ በመግባባት የሚኖሩበት እጅግ የተሻለ መንገድ እንዳለ ለመግለጽ ይፈልጋል። አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ራስ-ወዳድና ክፉ ለሆኑ የዓለም ሕዝቦች የጽድቅና የፍቅር ምስክር ልትሆን ይገባል።

በዚህ ምክንያት ቤተ ክርስቲያን «ቅዱስ ሕዝብ» ተብላለች። ሐዋርያው ጴጥሮስ፥ «እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ» ሲል ጽፎአል (1 ጴጥ. 2፡9)። የእግዚአብሔር ሕዝቦች በከንፈራቸው የእርሱን ምስጋና ሊናገሩ [መዝ. (34)፡1]፥ እርስ በርሳቸውና ለዓለም የፍቅርንና የሰናይ ምግባርን ሕይወት ሊኖሩ ይገባል (ቲቶ 2፡14)። ይህ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የወጠነው ታላቅ ዕቅድ ነው። በምዕራፍ ዘጠኝ ለቤተ ክርስቲያኑ ያለውን ዕቅድ በበለጠ በዝርዝር እናጠናለን።

በ. በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማለት ምን ማለት ነው?

በመንፈስ ቁጥጥር ሥር መሆን ወይም በመንፈስ መያዝ በአፍሪካ የተለመደ ክስተት ነው። አብዛኛዎቹ ሰዎች በአንድ ወይም በሌላ አጋጣሚ በመንፈስ ቁጥጥር የሚኖር ሰው ተመልክተዋል። አንድ ሰው በመንፈስ ቁጥጥር ሥር ሲሆን፥ ባሕርዩና ጠባዩ በሚያስደንቅ ሁኔታ ይለወጣል። እንግዳ የሆነ ሥጋዊ ጥንካሬና ጽናት ሊኖረው ይችላል። የራሱ ባልሆነ አዲስ ቋንቋ ሊናገር ይችላል። ከቅድመ-ትውልድ ወይም ከመናፍስት ትንቢቶችን ወይም መልእክቶችን ሊናገር ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ሰውየው በቢላዋ እንደ መቆረጥ ወይም በእሳት እንደ መቃጠል የመሳሰሉ አንዳንድ

ሥቃይ ሊያሳድሩ የሚችሉ ቁስሎች ላይሰሙት ይችላሉ። በመናፍስት ቁጥጥር ሥር ስለ መዋል ወደፊት በዝርዝር ይብራራል።

መጽሐፍ ቅዱስ ሰው በትክክል በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር በመዋሉ፥ «በመንፈስ ተሞላ» ስለሚባልበት ሁኔታ ይናገራል። በመንፈስ ቅዱስ ሙላትና በትውልድ መንፈስ ቁጥጥር መካከል አንዳንድ ነጥቦችን ማነጻጸር ይቻላል። በትውልዳዊ መናፍስት ቁጥጥር ሥር መዋል ለዚያ መንፈስ ለጊዜው ሙሉ ለሙሉ መታዘዝን ያስከትላል። እንደዚሁም በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር መዋል ለእግዚአብሔር ፈቃድ ለጊዜው ሙሉ ለሙሉ መታዘዝን ያስከትላል። በትውልዳዊ መናፍስት ቁጥጥር ሥር መዋል፥ ሁልጊዜም ለማለት ይቻላል በአንድ በኩል በመናፍስቱ ቁጥጥር ሥር በዋለው ሰው አካባቢ የሚገኙትን ሰዎች ይነካል። በተመሳሳይ ሁኔታ በእግዚአብሔር መንፈስ ቁጥጥር ሥር መዋል ሁልጊዜም ለማለት ይቻላል በመንፈስ ቅዱስ በተሞላው ሰው አካባቢ የሚገኙትን ሰዎች ይነካል። በትውልዳዊ መንፈስ ቁጥጥር ሥር በመዋልና በእግዚአብሔር መንፈስ ቁጥጥር ሥር በመዋል መካከል የሚገኙ ልዩነቶች ከሚቆጣጠረው መንፈስ ባሕርያት የሚመነጩ ናቸው።

አንድ ሰው በእግዚአብሔር መንፈስ ሲሞላ ባሕርዩና ጠባዩ በሚያስደንቅ ሁኔታ ሊለወጥ ይችላል። ይህም ሲሆን፥ ዓሣ አጥማጁ ጴጥሮስና ዮሐንስ ክርስቶስን በገደሉት የአይሁድ መሪዎች ፊት እንዳደረጉት (የሐዋ. 4፡13) ሁሉ፥ ማናቸውም ያልተማረና ዝምተኛ ሰው እጅግ በተማሩ ሰዎች ፊት ስለ ክርስቶስ በከፍተኛ ድፍረት ሊመሰክር ይችላል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ አንዳንድ ሰዎች ከፍተኛ ሥጋዊ ጥንካሬ አግኝተዋል (መሳ. 15፡14-15)። አንዳንድ ሰዎች የማያውቋቸውን ቋንቋዎች ተናግረዋል (የሐዋ. 2፡4)። አንዳንድ ሰዎች ከእግዚአብሔር ዘንድ ትንቢታዊ መልእክቶችን ተናግረዋል (ሉቃ. 1፡41-43)። ከትውልዳዊ መንፈስ በተቃራኒ፥ በክርስቲያን ሕይወት የመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሁልጊዜም ለእግዚአብሔር ሕዝቦችና ለተሞላው ሰው በረከትን ያመጣል። በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ለእግዚአብሔር ክብርንና ምስጋናን ያመጣል።

በቅርቡ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት የመከራከሪያ ርዕሰ-ጉዳይ ሆኗል። እንደ ሌላው የእግዚአብሔር እውነት ሁሉ፥ ስለዚህም ጉዳይ እርግጠኛ ልንሆን የምንችልበት ብቸኛ መንገድ የእግዚአብሔርን ቃል በመመርመር

ነው። ይህንንም ለማድረግ፥ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ እንደ ተሞሉ የሚገልጹትን አያሌ ምሳሌዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ እናጠናለን።

እንዲህ ዓይነት ብዙ ምሳሌዎች አሉ። በብሉይ ኪዳን፥ እግዚአብሔር ባስልኤልን በለየውና የመገናኛውን ድንኳን ይሠራ ዘንድ ልዩ ችሎታ በሰጠው ጊዜ፥ «የእግዚአብሔርን መንፈስ ሞላሁበት» ብሏል (ዘጸ. 31፡2-3)። በሙሴ ላይ ያረፈው የእግዚአብሔር መንፈስ ለሰባው የእስራኤል ሽማግሌዎች ሲታደል፥ ትንቢት ተናግረዋል (ዘኍ. 11፡25)። ጎቶንያልን (መሳ. 3፡10)፥ ጌዴዎንን (መሳ. 6፡34)፥ ዮፍታሔን (መሳ. 11፡29)፥ ሶምሶንን (መሳ. 14፡6) እና ሌሎችንም በተመለከተ፥ መጽሐፍ ቅዱስ የጌታ መንፈስ በኃይል እንደ መጣባቸው ይናገራል፤ ይህም ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከጠላቶቻቸው ይታደጉ ዘንድ ነው።

በአዲስ ኪዳን፥ መልአኩ ገብርኤል ስለ መጥምቁ ዮሐንስ መወለድ ለዘካርያስ ነግሮታል። ገብርኤል ዮሐንስ በእናቱ ማኅፀን ሳለ በመንፈስ ቅዱስ እንደሚሞላ ገልጾአል (ሉቃስ 1፡15)። በመጥምቁ ዮሐንስ ልደት ጊዜ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ዘካርያስ ትንቢት ሲናገር በመንፈስ ቅዱስ እንደ ተሞላ ይገልጻል (ሉቃ. 1፡67)። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን፥ በዕለተ-በዓለ-ሃምሳ ደቀ መዛሙርቱ በተለያዩ ቋንቋዎች ስለ እግዚአብሔር ታላላቅ ሥራዎች ሲናገሩ፥ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ነበር (የሐዋ. 2፡4)። ጴጥሮስ ክርስቶስን ለሰቀሉት የአይሁድ መሪዎች ሲናገር፥ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ እንደ ነበር ከመጽሐፍ ቅዱስ ዘገባ እንረዳለን (የሐዋ. 4፡8)። እስጢፋኖስ በቁጣ ለተሞሉ የአይሁድ መሪዎች ስለ ክርስቶስ ሞት ሲናገር፥ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ እንደ ነበር ከመጽሐፍ ቅዱስ እንረዳለን (የሐዋ. 7፡55)። ጳውሎስ የእግዚአብሔርን የዓይነ-ስውርነት ፍርድ በጠንቋዮ ኤልማስ ላይ ሲያወርድ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ እንደ ነበር ይገልጻል (የሐዋ. 13፡9-11)።

በሐዋርያት ሥራ 1፡8 ኢየሱስ፥ «መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» ብሏል። ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው፥ አንድ አማኝ በመንፈስ ቅዱስ እስካልተሞላ ድረስ ለወንጌል አገልግሎት ኃይል አይኖረውም።

እነዚህ ምሳሌዎች ምን ያስተምሩናል? በያንዳንዱ ምሳሌ፥ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ለጌታ ለመሥራት ኃይልን ወይም ችሎታን ሲሰጥ

እንመለከታለን። አንዳንድ ጊዜ ሙላቱ የእግዚአብሔርን ቃል በኃይል ተግባራት ለማጽናት ይሰጣል። አንዳንድ ጊዜ ሙላቱ ልክ እንደ ባስልኤልና አንዳንድ መሳፍንት · የእግዚአብሔርን ሕዝብ መሪዎች በኃይል ለማስታጠቅ ወይም የተመሰነ ተግባር እንዲፈጽሙ ለማስቻል ይመጣል።

ለአንዳንድ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ መሞላት፥ እግዚአብሔር ለተመሰነ ሥራ ስለ መረጣቸው ጊዜያዊ ልምምድ ነበር። ይህ በብሉይ ኪዳን ዘመን፥ በጌዴዎን (መሳ. 6፡34) እና በሶምሶን (መሳ. 14፡6) እንደ ሆነው በተመሰኑ ጊዜያት የሚፈጸም ይመስላል። መጥምቁ ዮሐንስ (ሉቃ. 1፡15)፥ እስጢፋኖስ (የሐዋ. 6፡5)፥ በርናባስ (የሐዋ. 11፡22-24) እና አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ነቢያትን በተመለከተ ግን (ዳን. 6፡3፤ ሚል‌ክ. 3፡8)፥ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ለረዥም ጊዜ የሚቆይ ልምምድ ይመስላል።

ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ የሚሞላው እንዴት ነው?

በመንፈስ ቅዱስ እንሞላ ዘንድ በእግዚአብሔር እንደ ታዘዝን መረዳቱ አስፈላጊ ነገር ነው። «መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ» (ኤፌ. 5፡18)። በመሆኑም፥ የሕዝቡ በመንፈሱ መሞላት በግልጽ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። በቀድሞዪቱ ቤተ ክርስቲያን በዲቁና ለመመረጥ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት አንዱ መመዘኛ ነበር (የሐዋ. 6፡3)። እስጢፋኖስም እንዲህ ዓይነት በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው ነበር (የሐዋ. 6፡5)።

ክርስቲያኖች ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚፈልጋቸው ሆነው በሚኖሩበት ጊዜ፥ በመንፈስ ቅዱስ መሞላታቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደ ሆነ እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን። ጳውሎስ በኤፌሶን 5፡15-19፣ «እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ (እጸልያለሁ)» እያለ ሲጽፍ፥ በኤፌሶን ስላሉ አማኞች ሁሉ እያሰበ ነበር።

አንዳንድ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ፥ እግዚአብሔር አንዳንድ ሰዎችን ሳይጠይቁ በመንፈሱ ለመሙላት መርጦአል፤ ይህም የሆነው እግዚአብሔር በዚያ ሰው አማካኝነት አንድ ልዩ ዓላማ ለመፈጸም ስለ ፈለገ ነው። ለዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ባስልኤል (ዘጸ. 31፡2-3) እና መጥምቁ ዮሐንስ (ሉቃ. 1:15) ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው።

በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት እንድንጠይቅ አበረታቶናል። እግዚአብሔር ለሚጠይቁት የመንፈስ ቅዱስን ሀልውናና

ኃይል እንደሚሰጣቸው ገልጾአል። በሉቃስ 11፡13 ኢየሱስ፥ «እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፥ በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው?» ብሏል። አማኞች ለሕይወታቸው እግዚአብሔር የፈቀደውን የመንፈስ ቅዱስ ሙላት እውነታ ቢለማመዱ መልካም ነው።

በሮሜ 8፡9 ገለጻ መሠረት፥ በትክክል የክርስቶስ የሆነ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ አለው። ይህ የሆነውም ሰውየው ደኅንነትን በሚያገኝበት ጊዜ አዲስ ልደት የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ ስለ ሆነ ነው (ዮሐ. 3፡3፥ 5፤ ቲቶ 3፡5)። ይህም ሆኖ፥ ሁሉም ክርስቲያን የግድ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ አይደለም። ይህማ ቢሆን ኖሮ፥ በመንፈስ ቅዱስ እንድንሞላ ባልታዘዝን ነበር (ኤፌ. 5፡18)፤ ጳውሎስም የኤፌሶን ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ አይጸልይም ነበር (ኤፌ. 3፡15-19)።

እንደ ሌላው ጸሎት ሁሉ፥ አንድ ሰው ለመንፈስ ቅዱስ ሙላትም ከንጹሕና እውነተኛ ልብ ወደ እግዚአብሔር መጸለይ አለበት። ማንኛውም ግብዝነት ወይም በሰውየው ሕይወት ውስጥ የሚገኝ ኃጢአት ጸሎቱን እንዳይመለስ ያደርጋል። ኢሳይያስ 59፡1-2፥ «እነሆ፥ የእግዚአብሔር እጅ ከማዳን አላጠረችም፥ ጆሮውም ከመስማት አልደነቆረችም፤ ነገር ግን በደላችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች፥ እንዳይሰማም ኃጢአታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል» ይላል።

ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት ከንጹሕና እውነተኛ ልብ ብንጸልይ፥ እግዚአብሔር ይህንን ጸሎት ለመመለስ እንደሚፈቅድ እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን። አሁን እንደ ተመለከትነው፥ ለክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስ ማግኘት ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፥ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ያሉትን ነገሮች ብንጠይቅ፥ ጸሎታችንን ሰምቶ እንደሚመልስልን ያረጋግጥልናል (1 ዮሐ. 5፡14-15)።

በመንፈስ ቅዱስ መሞላታችንን እንዴት እናውቃለን?

አንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ እንደ ተሞላ እንዴት እንደሚታወቅ ክርስቲያኖች በአሳብ ይለያያሉ። አንዳንድ ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው በሌላ ቋንቋ (የልሳን ስጦታ) እንደሚናገር ያምናሉ። ይህንንም የሚያምኑት በሐዋርያት ሥራ ውስጥ፥ በተለይም በዕለተ-ጰንጠ-ቆስጤና ከዚያም ብዙ በማይርቁ ጊዜያት፥ አንዳንድ ክርስቲያኖች በመንፈስ

ቅዱስ ሲሞሉ በተወሰኑ ጊዜያት በልሳን ስለ ተናገሩ ነው (የሐዋ. 2፡4፤ 10፡44-47፤ 19፡2-6)። በአንዳንድ አጋጣሚዎች በሌላ ቋንቋ መናገር በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ምልክት ሊሆን ይችላል።

በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ሰዎች በልሳን የተናገሩባቸውን ሁኔታዎች በጥንቃቄ ብንመረምር፥ አንድ አስፈላጊ ነገር እናገኛለን። በያንዳንዱ አጋጣሚ፥ አዲስ የሕዝብ ቡድን ወደ ቤተ ክርስቲያን ይቀላቀል ነበርና፥ አዲሱ ቡድን በትክክል የክርስቶስ የአካል ክፍል እንደ ሆነ ለአይሁድ ክርስቲያኖች ለማረጋገጥ የልሳን ምልክት በተአምራዊ ሁኔታ ተሰጣቸው (የሐዋ. 11፡15-17ን ከ1 ቆሮ. 1፡22 ጋር አወዳድር)።

በሁሉም ሁኔታዎች የሚሠራና ዓለም-አቀፍ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት መረጃ ይኖር ይሆን? በመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ እንደ ተሞሉ የሚገልጹትን ምሳሌዎች ሁሉ ብንወስድ፥ በሁሉም ሁኔታ ውስጥ የሚገኘው የጋራ ባሕርይ ይህንን ይመስላል፤ በመንፈስ በተሞላው ሰው ቃላትም ሆነ ተግባራት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በግልጽ ሲሠራ ይታይ ነበር። በሌላ አባባል፥ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ሁልጊዜም በሰውየው ቃላትና ተግባራት አማካኝነት እግዚአብሔር በመገኘቱና ኃይሉም በሥራ ላይ በመታየቱ ተለይቶ ይታወቅ ነበር። ለዚህ ዓይነተኛ ምሳሌ የሚሆኑን፥ በመንፈስ ቅዱስ በተሞላው ስብከታቸው በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ የመለሱት ታላቁ የዘመናችን ወንጌላዊ ዶክተር ቢሊ ግርሃም ናቸው።

የተለየ አገልግሎት የማይሰጥ ተራ ክርስቲያንስ? በዚህ ዓይነቱ ሰው ሕይወት የመንፈስ ቅዱስ ሙላት እንዳለ በምን ይታወቃል? በጥቃቅን ዕለታዊ ሕይወቱም ሳይቀር በመንፈስ ቅዱስ የተሞላው ሰው ክርስቶስን የሚመስል ባሕርይ (ገላ. 5፡22-23)፥ ለጓደኞቹና ለቤተሰቡ ጠንካራና ውጤታማ ምስክርነት (የሐዋ. 1፡8)፥ ብሎም በኃይል የተሞላ የጸሎት ሕይወት እንዳለው ሊያሳይ ይችላል (ሮሜ 8፡26-27)። እነዚህ የሕይወት ብቃቶች በመንፈስ ቅዱስ እንደ ተሞሉ በተገለጹት እስጢፋኖስ (የሐዋ. 6፡5) እና በርናባስ (የሐዋ. 11፡22-24) ሕይወት ውስጥ በጉልህ ሳይታዩ አልቀሩም።

ቤተ ክርስቲያን ታድግና እየበሰለች ትሄድ ዘንድ፥ እግዚአብሔር ሕዝቦቹ ሁሉ ለሌሎች በሚሰጡት አገልግሎት ኃይል እንዲኖራቸው ይፈልጋል። ይህንንም ኃይል ለማግኘት፥ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ያሻል። የሕዝቡ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ሆነ፥

ጳውሎስ በኤፌሶን ለነበሩ ወዳጆቹ በእግዚአብሔር ሙላት ይሞሉ ዘንድ እንደ ጸለየ ሁሉ (ኤፌ. 3፡15-19)፥ በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት እግዚአብሔርን በጸሎት መጠየቁ ተገቢ ነው (ሉቃ. 11፡13)።

ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ከተሞላ ኃጢአት የማይነካው ፍጹም ሰው ይሆናል?

አንዳንድ የሕዝብ ቡድኖች አንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ሲሞላ ኃጢአት የማይነካው ፍጹም ሰው እንደሚሆን ያስተምራሉ። ሐዋሪያው ዮሐንስ፥ «ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን እውነትም በእኛ ውስጥ የለም» ይላል (1 ዮሐ. 1፡8)። ዮሐንስ ቀጥሎም፥ «በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው» ይላል (ቁ. 9)። ይቅርታ ልናገኝና ከኃጢአታችን ልንነጻ እንችላለን እንጂ፥ በዚህ ሕይወት ኃጢአት የማይነካን ፍጹማን ልንሆን አንችልም።

በመጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ሰዎች በከፉ ኃጢአት መውደቃቸው አሳዛኝ እውነታ ነው። ለምሳሌ ሶምሶን የእግዚአብሔርን ፍርድ በፍልስጤማውያን ላይ ለማውረድ በመንፈስ ቅዱስ በኃይል ተሞልቶ ነበር (መሳ. 15፡14-15)፤ ይሁንና፥ ብዙም ሳይቆይ ከአንዲት ጋለሞታ ሴት ጋር ዝሙት ፈጸመ (መሳ. 16፡1)። ንጉሥ ዳዊት ከመዝሙረ ዳዊት ግማሽ ያህሉን እስኪጽፍ ድረስ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው ነበር (ማቴ. 22፡43-44)፤ ይሁንና፥ ዳዊት ዝሙትና የነፍስ ግድያ ፈጽሞአል! ከእግዚአብሔር በተሰጠው መገለጥ፥ ጴጥሮስ የኢየሱስን መሢሕነት በመግለጽ ታላቅ ምስክርነት ሰጠ (ማቴ. 16፡16-17)። ከዚያም፥ ጥቂት ቆይቶ ጴጥሮስ ክርስቶስ ወደ ዓለም የመጣበትን ዓላማ ለመከላከል በመሞከር የሰይጣንን ድምፅ አስተጋብቷል (ማቴ. 16፡22-23)።

የኃጢአት ተፈጥሮ ያለብን ሰብአዊ ሰዎች ስለ ሆንን (ሮሜ 7፡14-18)፥ በዚህ ሕይወት ከኃጢአት ጋር ግብግብ መፍጠራችን የሚቀጥል ሂደት ነው (1 ዮሐ. 1፡8-9)። ይሁንና፥ በዚህ ቀጣይ ትግል ኃጢአተኛ ተፈጥሮአችንን እንድናሸንፍ የሚረዳንን መንፈስ ቅዱስ ስለ ሰጠን እግዚአብሔርን እናመሰግናለን (ሮሜ 8፡12-13፤ ገላ. 5፡17-18)።

በመጨረሻም፥ ሁሉም አማኞች በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት መሻት አለባቸው ወይ? የሚል ጥያቄ ልናነግ እንችላለን። ለዚህ ጥያቄ መልሱ «አዎን» የሚል ነው። የአያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምእመን በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ቢሆን ናሮ፥ ኅለግችን በጣም ልዩ ስፍራ በሆነችና ቤተ ክርስቲያንም እስካሁን ድረስ ታሳቁን ተልዕኮ ከዳር ባደረሰች ነበር። ይሁንና፥ የመንፈስ ቅዱስን ሙላት መሻት ያለብን እንድ የሆነ ስሜታዊ ልምምድ ለማድረግ አይደለም። ይልቁን፥ ኢየሱስ ክርስቶስን ከፍ ከፍ ለማድረግ፥ ሕዝቡን ለማነፅና የጠሩትን ወደ ክርስቶስ ለመመለስ የመንፈስ ቅዱስን ሙላት ልንሻ ይገባል (ዮሐ. 16፡14፤ 1 ቆሮ. 12፡7፤ የሐዋ. 1፡8)።

ማጠቃለያ

መንፈስ ቅዱስ በዓለም፥ በቤተ ክርስቲያን፥ እንዲሁም በእያንዳንዱ አማኝ ልብ የእግዚአብሔር ስውር ህላዌ ነው። ሰዎችን ስለ ኃጢአታቸው የሚወቅሳቸው፥ ወደ ክርስቶስ የሚስባቸው፥ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት የሚያደርጋቸውና ይበልጥ ክርስቶስን ይመስሉ ዘንድ እንዲለወጡ የሚረዳቸው እርሱ ነው። የክርስቶስ አካል ከፍል በሚያደርጋቸውም ጊዜ በአማኞች ሁሉ ላይ የባለቤትነትን ማኅተም ያደርጋል። በክርስቶስ ካመንን በኋላ የእግዚአብሔር ልጆች እንደ ሆንን ለሰብአዊ መንፈሳችን ይመሰክራል። እንድንጸልይና ፈተናን እንድንቋቋም ይረዳናል፤ ይመራናል። እርሱ እግዚአብሔር ሲሆን፥ ዳሩ ግን ከእግዚአብሔር አብና ከእግዚአብሔር ወልድ የተለየ አካል ነው።

መንፈስ ቅዱስ የመጽሐፍ ቅዱስን መጻፍ መርቷል። ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ ሲያነቡ አእምሮአቸውን ከግብራቱም በላይ፥ ለዕለታዊ የሕይወት ጉዞአቸው የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት እንዲያስታውሱ ይረዳል። በመጽሐፍ ቅዱስ በዘይት፥ በውኃ፥ በነፋስና በእሳት ተምሳሌቶች ተገልጾአል። የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ለብስለት ትታነፅ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ለእግዚአብሔር ሰዎች መንፈሳዊ ስጦታዎችን ይሰጣል። እርሱ ሰዎችን ለወንጌሉ አገልግሎት በመጥራት፥ አገልግሎቱን የሚወጡበትን ኃይል ይሰጣቸዋል። አንዳንድ ጊዜም የወንጌሉን እውነታ ለማጠናከር ምልክቶችንና ተአምራትን ይፈጽማል። የእግዚአብሔርን ፍቅር በአማኞች ልብ ውስጥ ስለሚያፈስ፥ ይህንኑ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሌሎች ለማካፈል ይነሣሣሉ። ክርስቲያኖችን በህልውናውና በኃይሉ ስለሚሞላቸው፥ ለሌሎች በብታት ስለ ክርስቶስ ሊመሰክሩ ይችላሉ። እርሱ የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ያበረታታል። በሕይወታቸው

ለእግዚአብሔር ከብርን ያመጡ ዘንድ የእግዚአብሔርን ልጆች ይቀድሳቸዋል - ያጠነክራቸዋል።

በምዕራፍ 8 ላይ የተመሠረቱ የመወያያ ጥያቄዎችና መልመጃዎች

1. እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ አማኝ ስላለው ዕቅድና መንፈስ ቅዱስ ያንን ዕቅድ ለመፈጸም እንዴት እንደሚሠራ ግለጽ። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ስጥ።

2. እግዚአብሔር ለሕዝቡ በአጠቃላይ (ለቤተ ክርስቲያኑ) ያለውን ዕቅድና መንፈስ ቅዱስ ያንን ዕቅድ ለመፈጸም እንዴት እንደሚሠራ ግለጽ። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ስጥ።

3. አንድ አረማዊ ተማሪ አንዳንድ የባህል እምነት ተከታዮችና ሙስሊሞች ከአንዳንድ ክርስቲያኖች የተሻለ ባሕርይ እንዳላቸው ይገልጻል። በበኩልህ እውነተኛ ክርስቲያኖች በአብዛኛው ለምን አነስተኛ የጠባይ ለውጥ ብቻ እንደሚያሳዩ እንዴት ታስረዳዋለህ?

4. አራት ተማሪዎች በሚገኙበት ቡድን ተከፋፈሉ። እያንዳንዱ ቡድን ሰዎች በመጸሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ እንደ ተሞሉ የሚገልጹትን አራት ሁኔታዎች ያጥኑ። እያንዳንዱ ቡድን ሰውየው በመንፈስ ቅዱስ መሞላቱን እንዴት እንዳወቀ የሚያመለክት መረጃ ያቅርብ።

5. ስንጸልይ መንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደሚረዳን ተወያዩ።

6. አንዳንድ ሰዎች በሕይወታቸው የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ወይም ጥንካሬና ብርታት ስላገኙባቸው ጊዜያት እንዲመሰክሩ አድርግ።

7. አንዳንድ ሰዎች በገዛ ሕይወታቸው መንፈስ ቅዱስ በመለኮታዊ ኃይል ወይም ተአምራት የወንጌሉን እውነታ ሲያጠናክር ስለ ተመለከቱበት ጊዜ እንዲመሰክሩ አድርግ (ዕብ. 2:3-4)

8. እግዚአብሔር ወደ አገልግሎት ስለ ጠራቸው መንገድ ይመሰክሩ ዘንድ አያሌ ተማሪዎችን ጠይቅ።

9. ቡድኑ በአገሪቱ ውስጥ ለሚገኙ ድሆች ክርስቲያናዊ ፍቅርና ምሕረት የሚንጸባርቁባቸውን ግልጽ አገልግሎቶች እንዲዘረዝር አድርግ። እነዚህም

ለድሆች፥ ለተራቡት፥ ለዓይነ-ሕውሮች፥ ለአካለ ስንኩላን፥ ለበሽተኞችና ለመበለቶች ወይም ወላጆች ለሌሉአቸው ልጆች የሚደረጉትን አገልግሎቶች ሊጨምሩ ይችላሉ።

10. በቡድን ተከፋፍላችሁ የሐዋርያት ሥራ 8:17-24ን አጥኑ። እያንዳንዱ ቡድን የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ከአፍሪካ የመናፍስት፥ የምሥጢራዊ ኃይላት፥ የምትሐትና የትንበያ ጽንሰ-አሳብ ጋር እንዲያዛምድ ጠይቅ። የአስማተኛው ስምዖን ታላቅ ኃጢአት ምን ነበር? ይህስ ለአፍሪካውያን ክርስቲያኖች የሚያስተላልፈው ማስጠንቀቂያ ምንድን ነው?

11. በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና በክፉ መናፍስትና በአጋንንት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

12. አንዳንድ ጊዜ የተለያዩ የክርስቲያን ቡድኖች በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ላይ ጎጂ ክርክሮችን ያደርጋሉ። እነዚህ ክርክሮች ከክርስቶስ አካል (ቤተ ክርስቲያን) ውስጥ ስለሚወገዱባቸው መንገዶች ተወያዩ።

SUGGESTED FOR FURTHER READING

Graham, Billy. The Holy Spirit. London: Fount, 1980.

Green, Michael. I Believe In The Holy Spirit. London: Hodder, 1985.

Packer, J. I. Keep In Step With The Spirit. Leicester: InterVarsity Press,1984.

Packer, J. I. A Passion for Holiness. Cambridge: Crossway, 1992.

Pytches, David. Come Holy Spirit. London: Hodder, 2nd edn 1995.

Smail, T. The Giving Gift. Darton: Longman & Todd, 1994.

Stott, J. Baptism and Fullness. Leicester: InterVarsity Press, 1964.

ምዕራፍ 9

ቤተ ክርስቲያን - የተስፋፋች የእግዚአብሔር ቤተሰብ

«በዚያን ዘመን ንጉሡ ሄሮድስ መከራ ያጸናባቸው ዘንድ ከቤተ ክርስቲያኑ በአንዳንዶቹ ላይ እጁን ሜነባቸው። የዮሐንስንም ወንድም ያዕቆብን በሰይፍ ገደለው። አይሁድንም ደስ እንዳሰኛቸው አይቶ ጴጥሮስን ደግሞ ያዘው . . . በያዘውም ጊዜ ወደ ወኅኒ አገባው . . . እያንዳንዱ አራት ወታደሮች ሆነው እንዲጠብቁት ለአራት ጭፈራ ከፍል አላልፎ ሰጠው። ጴጥሮስም በወኅኒ ይጠበቅ ነበር፤ ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ስለ እርሱ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አጥብቆ ይደረግ ነበር። ሄሮድስም ሊያወጣው ባሰበ ጊዜ፥ በዚያች ሌሊት ጴጥሮስ በሁለት ሰንሰለት ታስሮ ከሁለት ወታደሮች መካከል ተኝቶ ነበር፤ ጠባቂዎችም በደጁ ፊት ሆነው ወኅኒውን ይጠብቁ ነበር። እነሆም፥ የጌታ መልአክ ቀረበ በቤትም ውስጥ ብርሃን በራ፤ ጴጥሮስንም ጎድኑን መትቶ አነቃውና፦ ፈጥነህ ተነሣ አለው። ሰንሰለቶቹም ከእጁ ወደቁ። መልአኩም . . . ልብስህን ልበስና ተከተለኝ አለው። ወጥቶም ተከተለው፤ ራእይንም የሚያይ ይመስለው ነበር እንጂ በመልአኩ የሚደረገው ነገር እውነት እንደ ሆነ አላወቀም» (የሐዋ. 12፡1-9)።

መጋቢ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያኒቱን ለልዩ ስብሰባ ጠርተዋል። በአነስተኛዋ ቤት ውስጥ ቤተ ክርስቲያኒቱ ስትሰባሰብ፥ መጋቢው ፈጠን ብለው የስብሰባውን ምክንያት ያስረዱ ጀመር። ሜይቺቢና ራግቱ በጋብቻቸው ውስጥ ችግሮች ነበሩባቸው። የራግቱ የቤተሰብ ዳራ በክፋትና በኃጢአት የተበከለ እንደ መሆኑ፥ እርሷም ከስድስት ሳምንታት በፊት ሜይቺቢንና ሁለት ልጆቻቸውን ትታ ወደ ግልሙትናዋ ተመልሳ ነበር። ሜይቺቢ የቤተ ክርስቲያን አምልኮውን ከመከተል ባይቦዝንም ልቡ ግን በጣም ከብዶበታል። ስለ ሆነም ለርዳታ ወደ መጋቢው ዘንድ መጣ። መጋቢ ጳውሎስ የሚፈጥሩት መላ እንዳለም ጠየቀ። እርሳቸውም በጉዳዩ ላይ ከቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ጋር ከተወያዩና የሜይቺቢን ፈቃድ ካገኙ በኋላ ቤተ ክርስቲያኒቱ ለራግቱ እንድትጸልይ ምእመናኑን ሰበሰቡ። አሁን አነስተኛ ሕዝብ በተሰባሰበባት ጉባኤ ላይ፥ መጋቢው የሜይቺቢን ታሪክና የቤተሰቡን ችግሮች በአጭሩ አስረዱ።

መጋቢ ጳውሎስ ጉባኤው አራትና አምስት ሰዎች በሚገኙበት ቡድን እንዲከፋፈልና ጌታ የራሳቱን ልብ በመንካት ንስሐ እንድትገባና የፈረሰውም ጋብቻ እንዲታደስ እንዲጸልዩ ጠየቁ። ምእመናኑ በተጋጋዥ መንፈስ ከአንድ ሰዓት ለሚልቅ ጊዜ ለባለትዳሮቹ ጸለዩላቸው። ከአራት ሳምንታት በኋላ ራሳቱ ከሚደቹቢና ከልጆቿ ጋር ወደ ቤተ ክርስቲያን መጣች። ጋጢአቷን በመናዘዝ ከባለቤቷ ጋር ለመታረቅ እንደምትፈልግ ገለጸች። ልክ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ እንዳየነው፥ በዚህም ሰፍራ እግዚአብሔር የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ጸሎት ሲመልስ እንመለከታለን።

እግዚአብሔር በጉባኤው መካከል ኃጢአትና መከፋፈል ሳይኖር፥ በአንድ ልብና በአንድ ድምፅ ሆነው እንደ ፈቃዱ የሚጸልዩትን የሕዝቡን ጸሎት ሰምቶ ይመልሳል። ይህም እውነት በመሆኑ፥ እነዚህ ከላይ የተረቡትን ሁለት እውነተኛ ታሪኮች የሚመስሉ ታሪኮች በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሁሉ በተደጋጋሚ ተከስተዋል። ቤተ ክርስቲያን ምንድን ነች? በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባላት እርስ በርሳቸው ምን ግንኙነት አላቸው? ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ፊት በሚተርብ ጸሎት የማይመጠን ኃይል የሚኖራት ለምንድን ነው? እግዚአብሔር ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ያለው ዕቅድ ምንድን ነው? እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ተግባሯን እንድታከናውን የወጠነው እንዴት ነው? በዚህ ምዕራፍ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ እንሻለን፡-

ሀ. ቤተ ክርስቲያን ምንድን ናት?

ለ. የቤተ ክርስቲያን አባላት እነማን ናቸው?

ሐ. እውነተኛዪቱ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የትኛዪቱ ነች?

መ. የእግዚአብሔር መቅደስ የሚገኘው የት ነው?

ሠ. ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል እንደ ሆነች የሚያሳዩ ሥስት አስፈላጊ ተግባራዊ ተዛምዶዎች ምንድን ናቸው?

ረ. ክርስቲያን የትኛውን መንፈሳዊ ስጦታ እንደ ተቀበለ እንዴት ያውቃል?

ሰ. ቤተ ክርስቲያን ከሰው ልጅ ጋር ላላት ግንኙነት የእግዚአብሔር ዕቅድ ምንድን ነው?

ሸ. የቤተ ክርስቲያን ዓላማ ምንድን ነው?

ቀ. በአዲስ ኪዳን በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያኑ መካከል ያለውን ግንኙነት ለመግለጽ ያገለገሉ ዐበይት ግብራሪያዎች ምንድን ናቸው?

በ. እንዲህ የበረከቱ የተለያዩ የእምነት ከፍሎችና አብያተ ክርስቲያናት የሚታዩት ለምንድን ነው?

ተ. ኢየሱስ ለቤተ ክርስቲያኑ የሰጣቸው ሥርዓቶች ምንድን ናቸው?

ቸ. ዐበይት የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው?

ኀ. በአዲስ ኪዳን መሠረት በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ዐበይት የመሪነት ስፍራዎች የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ቤተ ክርስቲያን ምንድን ናት?

ሉምቤ፡- «ወደ ቤተ ክርስቲያን ከእኔ ጋር ልትሄድ ትፈልጋለህ?»

አዳዚ፡- «ወደ የትኛው ቤተ ክርስቲያን ነው የምትሄደው?»

ሉምቤ፡- «የምሥራች ቤተ ክርስቲያን ወደሚባለው እሄዳለሁ። በዚያ አንተንና እኔን የሚመስሉ አያሌ ወጣቶች ይገኛሉ። እንደምትወደው ተስፋ አደርጋለሁ።»

አዳዚ፡- «ግን የተለያዩ በርካታ አብያተ ክርስቲያናት የሚታዩት ለምንድን ነው? ሁላችሁም በክርስቶስ እንደምታምኑ እስከ ተናገራችሁ ድረስ፥ ለምን ሁላችሁም በአንድ ቤተ ክርስቲያን አታመልኩም? ቀድሞስ ነገር ቤተ ክርስቲያን ምንድን ናት?»

ብዙ ሰዎች ቤተ ክርስቲያንን እንደ አንድ ሕንፃ አድርገው ያስባሉ። ሌሎች ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ቃለ ሕይወት ወይም ባፕቲስት የተመሰነ የእምነት ከፍል አድርገው ይመለከታሉ። ዛሬ ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል በሰዎች ዘንድ ሕንፃን ወይም የእምነትን ከፍል ለመጥቀስ አዘውትሮ ያገለግላል። ለመሆኑ በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ያገለገለው እንዴት ነበር? መጽሐፍ ቅዱስስ ቤተ ክርስቲያን ሲል ምን ማለቱ ነው?

አዲስ ኪዳን በቆላስይስ 1፡24-25 ላይ እንደ ሰፈረው ሁሉ፥ ስለ ቤተ ክርስቲያን ዓለም አቀፍ ገለጻ ያቀርባል። በተጨማሪም፥ እንደ አንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን (የሐዋ. 13፡1) እና የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን (1 ቆሮ.

1:2) በተመሰኑ ስፍራዎች ስለሚገኙ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትም ይናገራል። በሁለቱም፥ ግለትም በጎለም አተሩሮና በአጥቢያ አመለካከት ቤተ ክርስቲያን የሕዝቦችን ቡድን ያመለክታል። በሐዋርያት ሥራ 5:11፥ «በቤተ ክርስቲያን ሁሉና ይህንም በሰሙ ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት ወደቀባቸው» ይላል። ይህ በጎለም በሁሉም ስፍራ የሚገኙትን ክርስቲያኖች ሁሉ መይም በአንድ ስፍራ በየሳምንቱ መደበኛ የአምልኮ ተግባር የሚፈጽሙትን የሚያመለክት ቢሆንም፥ ቤተ ክርስቲያን የሕዝቦች ስብስብ ነች።

ቤተ ክርስቲያን የዘር፥ የብሔር፥ የእምነት ክፍል መይም የሥራ ደረጃ ገደብ ሳይኖረው፥ ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታቸውና አዳኛቸው አድርገው ያመኑትን ሰዎች አጠቃላ ትይዛለች። ገላትያ 3:26-28፥ «በእምነት በኩል (አማካኝነት) ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና . . . አይሁዳዊ መይም የግሪክ ሰው የለም፥ ባሪያ መይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና» ይላል። በዚህ ዓይነት በክርስቶስ ያመኑ ሰዎች ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት አዲስ ልደት አግኝተዋል (በክርስቶስ መንፈሳዊ ሕይወት ተቀብለዋል) (ቲቶ 3:5-7)። በክርስቶስ በማመን በመንፈሳዊ ሁኔታ ከክርስቶስ ጋር የተባበርን ሲሆን፥ የመንፈሳዊ አካሉ ክፍሉች ሆነናል። ሮሜ 6:5፥ «ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን» ይላል።

ቤተ ክርስቲያን በጣም የተለዩ የሕዝቦች ስብስብ ነች። የቤተ ክርስቲያን ምእመናን የእግዚአብሔር ልጆች ስለ ሆኑና እግዚአብሔርም አባታቸው ስለ ሆነ፥ ቤተ ክርስቲያን የተስፋፋች የእግዚአብሔር ቤተሰብ ነች። ሐዋርያው ዮሐንስ፥ «የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን እንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ፥ እንዲሁም ነን» ሲል ጽፏል (1 ዮሐ. 3:1)። ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ መንድሞችና እህቶች የሆኑ ሰዎች የሚገኙባት ዓለም አቀፍ ኅብረት ነች። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ፥ «መምህር ተብላችሁ አትጠሩ፤ መምህራችሁ አንድ ስለ ሆነ እናንተም ሁላችሁ መንድማማች ናችሁ» ብሏል (ማቴ. 23:8)።

ቤተ ክርስቲያን በዓለም እጅግ ታላቅና የተስፋፋች ቤተሰብ ነች። ክርስቲያኖች ከምድራዊ ቤተሰባቸው በላይ የሚዘልቅ ግኑበረሰብ እንዳለ መረዳታቸው በጣም አስፈላጊ ነው። በዚህ ሕይወት ቤተሰብና ጎላ

አስፈላጊዎች ናቸው፤ ይሁንና፥ በክርስቶስ ያመነ ሰው ከምድራዊ ቤተሰቡ በላይ ለረዥም ጀመናት የሚኖር ቤተሰብ አካል ይሆናል። ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አካል ሆኗል። ይህ ሥጋዊ ሕይወት ሲያከትም ክርስቲያኑ ከእግዚአብሔር ቤተሰብ (ግለትም ከሌሎች አማኞች) ጋር ለዘላለም በሰማይ ይኖራል (ራእይ 21:3)። በተጣዩ ሕይወት፥ አብሮ ሊኖር የሚችለው በምድራዊ ሕይወታቸው ክርስቶስን የግል አዳኛቸውና ጌታቸው አድርገው ካመኑት የቤተሰቡ አባላት ጋር ብቻ ነው። ክርስቲያን ከዓለም ይርያ በክርስቶስ ካመኑ ወንድሞችና እህቶች ጋር ቤተሰባዊ ግንኙነት የሚያደርግ ሰው ነው። አንድ ቀን ይህ ግንኙነት ከማንኛውም ምድራዊ የቤተሰብ ግንኙነት ይልቅ በመጠናከር ለዘላለም ይዘልቃል።

ለ. የቤተ ክርስቲያን አባላት እነማን ናቸው?

አፍሪካውያን ሁሉ እግዚአብሔር እንዳለ ያውቃሉ። በአፍሪካ ባህላዊ እምነቶችና በእስልምና ስለ እግዚአብሔር የሚቀርቡ ብዙዎቹ አስተሳሰቦች ትክክል ናቸው። ይሁንና፥ ስለ እግዚአብሔር እውነቱን ማወቅ አንድ ነገር ሲሆን፥ በግል እግዚአብሔርን ማወቁ ግለትም ከእርሱ ጋር የግል ግንኙነት ማድረጉ ፍጹም የተለየ ነገር ነው።

የብዙ ፓይግኖች ተከታዮች የእግዚአብሔር ልጆች እንደ ሆኑ ይናገራሉ። ብዙ አፍሪካውያን እግዚአብሔር የሰዎች ሁሉ አባት እንደ ሆነና ሰዎችም ሁሉ እግዚአብሔር የሰው ልጆች ሁሉ ፈጣሪ በመሆኑ የእርሱ ልጆች እንደ ሆኑ ያምናሉ። ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? እግዚአብሔር ራሱ ልጆቹ እንደ ሆኑ የሚናገረው ማንን ነው?

ዮሐንስ 1:11-12፥ «የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፥ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም። ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው» ይላል። ከእነዚህ ጥቅሶች እንደምንረዳው፥ የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑት ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኛቸውና ጌታቸው አድርገው ወደ ሕይወታቸው ያስገቡት ብቻ ናቸው። ኢየሱስ፥ «የራሴን በጎች አውቃለሁ የራሴም በጎች ያውቁኛል» ብሏል (ዮሐ. 10:14)።

የእርሱ ለሆኑት ሕዝቡ ባቀረበው ጸሎቱ ኢየሱስ፥ «እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት» ብሏል (ዮሐ. 17:3)። ኢየሱስ ራሱ እንደሚለው፥

የእርሱ የሆኑት ከክርስቶስ ጋር የግል ግንኙነት የሚያደርጉ ብቻ ናቸው። በመንፈስ ቅዱስ አዲስ ልደት ያገኙት ከክርስቶስ ጋር እንዲህ ዓይነት ግንኙነት ያላቸው ናቸው። በመሆኑም፥ ኢየሱስ የአይሁድ የሃይማኖት መሪ ለነበረው ኒቆዲሞስ፥ «እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም» ብሏል (ዮሐ. 3፡3)። ኢየሱስ በማቴዎስ 7፡21፥ «በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም» ሲል ያስጠነቀቀው ለዚህ ነው። ከእርሱ ጋር የግል ግንኙነት ሳያደርጉ በውጫዊ ይዘታቸው ክርስቲያኖች ነን የሚሉትን ሰዎች ኢየሱስ፥ «ከቶ አላወቅኋችሁም» ብሎ እንደሚያሰናብት ገልጾአል (ማቴ. 7፡23)። ስለ ሆነም፥ እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስን ጌታቸውና አዳኛቸው አድርገው በግላቸው የሚያውቁና ከዚህም የተነሣ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ሕያዋን የሆኑ (አዲስ ልደት ያገኙ) ሰዎች የሚገኙባት ነች።

እግዚአብሔር በትክክል የማን አባት እንደ ሆነ ከአጥባቂ የአይሁድ መሪዎች ጋር በተደረገው የክረረ ክርክር ላይ ኢየሱስ እውነተኛው አባታቸው እግዚአብሔር ሳይሆን ሰይጣን እንደ ሆነ ገልጾአል! (ዮሐ. 8፡44)። በዚያው ክርክር ላይ ኢየሱስ እግዚአብሔር አባታቸው ቢሆን ኖሮ እርሱን (ክርስቶስን) ይወዱት እንደ ነበር ተናግሯል (ዮሐ. 8፡42)። ስለ ሆነም፥ ኢየሱስ በግልጽ እንዳስተመጠው እግዚአብሔር የሁሉም ሳይሆን፥ ክርስቶስን የሚወዱና የሚቀበሉ ሰዎች ብቻ አባት ነው።

አንዳንድ ሰዎች መጠመቅ፥ ቤተ ክርስቲያን መሳለም፥ ከክርስቲያን መላጆች መወለድ ወይም በክርስትና ስም መጠራት ክርስቲያኖች የሚያደርጋቸው ይመስላቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑት በግላቸው ክርስቶስን ወደ ሕይወታቸው የጋበዙና እርሱን አዳኛቸውና ጌታቸው ያደረጉ ብቻ እንደ ሆኑ ይናገራል (ዮሐ. 1፡12፤ 2 ጴጥ. 1፡10-11፤ 2 ጴጥ. 3፡18፤ ራእይ 3፡20)። እነዚህን ቃላት በምታነብበት ወቅት ክርስቶስን ወደ ልብህ ያልጋበዝህ ከሆነ፥ ለምን አሁኑኑ ግንበብህን ቆም አድርገህ ኢየሱስን ጋጢአትህን ሁሉ ይቅር እንዲልልህ አትጠይቀውም? ከጋጢአት እንዲያድንህና ሕይወትህን በጌትነት እንዲመራ ወደ ሕይወትህ እንዲገባ ጋብዘው። በእውነተኛ ልብ ከጋጢአትህ ንስሐ ከገባህና ጌታህና አዳኝህ እንዲሆን ከጠየቅኸው፥

ደኅንነትን ታገኛለህ፤ የእውነተኛዪቱና የዘላለማዊቱ ቤተ ክርስቲያንም አካል ትሆናለህ።

ሐ. እውነተኛዪቱ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የትኛዪቱ ነች?

የተለያዩ የእምነት ክፍሎች እነርሱ ብቻ እውነተኛ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን እንደ ሆኑ ይናገራሉ። የትኛው ቡድን ነው ትክክለኛው ቤተ ክርስቲያን? እውነተኛዪቱ ቤተ ክርስቲያን የአፍሪካ ኢንላንድ ቤተ ክርስቲያን፥ የሱዳን ኢንተርዩር ቤተ ክርስቲያን፥ የምዕራብ አፍሪካ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት፥ አንግሊካን፥ ሜቶዲስት፥ ባፕቲስት የመሳሰሉ የእምነት ዘርፍ ስያሜዎች የሏትም። ምናልባትም የእውነተኛ ቤተክርስቲያን አባላት በተለያዩ የእምነት ዘርፎች ውስጥ ይገኙ ይሆናል። እንደዚሁም፥ በእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት የሚያመልኩ ብዙዎቹ ሰዎች ደግሞ ዳግም ባለመወለዳቸውና በመንፈስ ቅዱስ ሕያዋን ባለመሆናቸው፥ የእውነተኛዪቱ ቤተ ክርስቲያን አባላት አይደሉም (ቲቶ 3፡5)። እውነተኛዪቱ ቤተ ክርስቲያን ከኃጢአታቸው ንስሐ ገብተው እምነታቸውን በክርስቶስ ላይ ያደረጉ ሰዎች የሚገኙባት ነች።

መ. የእግዚአብሔር መቅደስ የሚገኘው የት ነው?

አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት አንዳንድ ጊዜ በትላልቅ ወይም ትናንሽ ሕንፃዎች፥ አንዳንድ ጊዜ በግለሰቦች መኖሪያ ቤቶችና አንዳንድ ጊዜም በዛፍ ጥላ ሥር ይሰበሰባሉ፤ ሕንፃውና ስፍራው የጎላ አስፈላጊነት የላቸውም። ሕዝቡ ግን ለእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊዎች ናቸው። በዚህ ዓይነት የሚሰባሰቡትን ሰዎች «በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ» ይላቸዋል (ኤፌ. 2፡21)። ግለሰብ ክርስቲያኖችን የዚህ «ቤተ መቅደስ» አካል የሆኑ «ሕያዋን ድንጋዮች» ይላቸዋል። ሐዋርያው ጴጥሮስ፥ «እናንተ ደግሞ ሕያዋን ድንጋዮች ሆናችሁ፥ . . . መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ» ሲል ያሳስበናል (1 ጴጥ. 2፡5)። ስለ ሆነም፥ ክርስቲያኖች ሁሉ የአሁኑን ጊዜ «የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ» የሚመሠርቱ የሕንፃ ጡቦች ወይም «ሕያዋን ድንጋዮች» ናቸው። በመሆኑም፥ ቤተ ክርስቲያን «እግዚአብሔር በመንፈሱ የሚያድርባት ሕንፃ» ነች (ኤፌ. 2፡22 - በ1980 ከታተመው አዲሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂ)።

ይህንን እውነት በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት፥ ከዚህ ቀደም የእግዚአብሔር መንፈስ ያድርባቸው የነበሩትን ስፍራዎች መከለሱ ተገቢ ነው። በእግዚአብሔር የተሞቀረው የዚህ ዓይነቱ የመጀመሪያው ስፍራ

የመገናኛው ድንኳን ነበር። የመገናኛው ድንኳን በድንኳን መልክ የተሠራ ሊሆን፥ በአርባ ዓመታት የመንከራተት ዘመናቸው በሲና ምድረ በዳና በኋላም በተስፋዪቱ ምድር እንዲዘረጉት እግዚአብሔር አስራኤላውያንን ያዘዛቸው መቅደስ ነበር (ዘጸ. 40፡1-34፤ ኢያሱ 18፡1፤ 2 ሳሙ. 7፡5-6)። በእግዚአብሔር የተሞቀረው ቀጣዩ ስፍራ በንጉሥ ሰሎሞን አማካኝነት በኢየሩሳሌም የተሠራው ውብ የቤተ መቅደስ ሕንፃ ነበር (1 ነገሥ. 8፡10-12፤ 2 ዜና 7፡1-3)። የሚያሳዝነው የእስራኤላውያን የጣዖት አምልኮ ባስከተለው መዘዝ የሰሎሞን ቤተ መቅደስ በባቢሎናውያን መፈራረሱ ነው። ይህም ከኃጢአታቸው የተነሣ የእግዚአብሔር ህልውና ከመካከላቸው እንደ ራቀ የሚያስገነዝብ ተምሳሌት ነበር [መዝ. (44)፡9-16፤ ኢሳ. 1፡13-15፥ 21-25)።

በመንፈሳት ውስጥ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ማደሪያ የኢየሱስ ክርስቶስ ምድራዊ አካል ነበር (ዮሐ. 1፡32-33)። ኢየሱስ ወደ አብ ካረገ በኋላ፥ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ትመሰርት ዘንድ በዕለተ-ጰንጠ-ቆስጤ ወደ ክርስቲያኖች ልብ እንዲገባ ተሳክ (የሐዋ. 1፡8፤ 2፡1-4)። ኢየሱስ ከዚያን ጊዜ ልንሥቶ የአማኞች ልብ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ማደርያ እንደሚሆን ተናግሮ ነበር (ዮሐ. 14፡16)። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አባባል፥ ቤተ ክርስቲያን በእሁን ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ የሚኖርባቸው በሰማይና በምድር የሚገኙ ሕዝቦች የተከማቹባት ጎብረት ነች (ዕብ. 12፡23፤ ኤፌ. 2፡20-22)።

ክርስቶስን ወደ ሕይወታቸው ያስገቡ ሰዎች በመንፈሳዊ ሁኔታ ከእርሱ ጋር ተሳስረዋል (ዮሐ. 17፡21፤ 1 ቆሮ. 6፡17)። ይህ እንዲያው ግብራሪያ ሳይሆን፥ ትክክለኛ የሆነ እውነት በመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ በክርስቶስ የሚያምኑትን አካሉ አድርጎ ይጠቅሳቸዋል። ክርስቲያኖች የአካሉ ክፍሎች ናቸው። በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡27 ጳውሎስ፥ «እናንተም የክርስቶስ አካል ናችሁ እያንዳንዳችሁም ብልቶች ናችሁ» ይላል። መንፈሳዊ አካሉን የሚመሠርቱ የእግዚአብሔር ልጆች በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያን ይባላሉ (ቆላ. 1፡18፤ 24)። ክርስቶስ ራስ ሲሆን፥ እኛ ደግሞ አካሉ ነን (1 ቆሮ. 12፡27፤ ቆላ. 1፡18)።

ሠ. ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል እንደ ሆነች የሚያሳዩ ሦስት አስፈላጊ ተግባራዊ ተዛምዶዎች ምንድን ናቸው?

ግኅበረሰብ

ቤተ ክርስቲያን በላቀ ሁኔታ ግኅበረሰብ ነች። ክርስቲያኖች የክርስቶስ አካል እንደ መሆናቸው ራስ ከሆነው ክርስቶስ ጋር በመንፈሳዊ ሁኔታ የተሳሰሩ ሲሆኑ፥ እንደ አካሉ ክፍሎችም እርስ በርሳቸው በመንፈሳዊ ሁኔታ የተያያዙ ናቸው። በዚህ ዓይነት እርስ በርሳቸው የተያያዙ በመሆናቸው፥ በዚህም ሆነ በሚመጣው ሕይወት የእግዚአብሔር የተስፋፋ ቤተሰብ አባላት ናቸው። የእግዚአብሔር መንግሥት አባላት እንደ መሆናቸውም፥ ጌታቸው የነገሥታት ንጉሥ የሆነው እርሱ ክርስቶስ ነው። ክርስቲያን አማኝ እንደ መሆኑ፥ ከሁሉም ነገድና ሕዝብ የተውጣጡ ጎልም አቀፍ የመንፈሶችና እህቶች ቤተሰብ አካል ነው። እግዚአብሔር ለዚህ ቤተሰብ በሰማይ ዘላለማዊ ርስት አዘጋጅቷል (፩ ጴጥ. ፩፡3-6)።

ይህ የተስፋፋው የእግዚአብሔር ቤተሰብ ለዘላለሙ ለክርስቶስ ደም አንድ ላይ ተሣሥሯል። ኢየሱስ ከጋዲኤት የሚያንስ እዳችሁው ቆም ሳይሆን፥ ጌታቸውና ንጉሣቸውም ነው። ሊመጣ ይወዳል። ንብረት ሳቸው፥ ኢየሱስ ሕዝቡን በገዛ ደሙ ገዝቶአቸዋል። ራእይ ፭፡9-10፥ «ታርደሃልና፥ በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው፥ በምድርም ላይ ይነግሣሉ» ይላል።

በብዙ–የአፍሪካ ግኅበረሰቦች አንድ ሰው ከሌላው ጋር ሲተዋወቅ ስሙን ይነገረዋል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮም ከተዋወቀው ሰው ጋር ሕጋዊና መንፈሳዊ ጥምረት ይኖረዋል። እንደዚሁም፥ እምነታችንን በክርስቶስ ላይ ስንጥልና ጌታችንና አዳኛችን አድርገን ስንተበለው በሕጋዊና መንፈሳዊ ሁኔታ ከእርሱ ጋር እንጣመራለን። እርሱም ጌታችንና የሕይወታችን ባለቤት ይሆናል። ይህ በባለቤትነት የሚያስተዳድረን፥ የሚጠብቀንና ጉድለታችንን የሚሞላልን ኢየሱስ ማን ነው? እርሱ የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ (ራእይ 19፡13-16)፥ የፍጥረት ሁሉ ጌታ (ፊልጵ. 2፡9-10፤ ቆላ. 1፡16-17)፥ የምድርና የሰማይ አምላክ ነው (ማቴ. 28፡18፤ ቲቶ 2፡13)።

በአፍሪካ ከሚታየው የሕይወት መዋቅር የተነሣ፥ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን ለምን እንደ ፈጠረ በቀላሉ ልንረዳ እንችላለን። በአፍሪካ ለአንድ ሰው ቤተሰቡና ግኅበረሰቡ በሕይወቱ እጅግ አስፈላጊ እውነታዎች

ናቸው። ቤተሰብ የቤተኛነት ስሜት የሚያድርብን፥ መገናኛነት የሚሰማን፥ ሰዎች ለይተው የሚያውቁን፥ ቋንቋችንን የምንናገርበትና የአስተሳሰብ መንገዳችንን የሚረዱልን የሰዎች ስብስብ ነው። ይህ ተቀባይነት ያገኘንበት የሰዎች ቡድን ነው። ወንድሞችና እህቶች እርስ በርሳቸው እንከብካቤ የሚያደርጉበትና የሩቅ የሆኑ ምንዝሮችም ሳይቀር ወንድሞችና እህቶች ተብለው የሚጠሩበት ነው። በአጭሩ በችግር ወይም በመከራ ውስጥ በምትሆንበት ጊዜ ይረዱኛል ብለህ የምትቆጥረው የሰዎች ቡድን ነው።

በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንም ሁኔታው እንዲህ ሊሆን ይገባል። የቤተ ክርስቲያን አባላት የሚያውቁንና ስለ መንፈሳዊ እውነታ በአንድ ዓይነት ቋንቋ የሚያናግሩን ናቸው። የአስተሳሰብ መንገዳችን እንግዳ አይሆንባቸውም። አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፥ ሁላችንም በእኩል ደረጃ በእግዚአብሔር ፊት ይቅርታ ያገኘን ኃጢአተኞች የምንሰባሰብበት እንደ መሆኗ፥ የዘር፥ የማኅበራዊ ሕይወት ወይም የኅብ ገደብ ሳይደረግ ተቀባይነት የምናገኝባት ማኅበረሰብ ናት። አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናኗ በክርስቶስ ወንድሞችና እህቶች በመሆናቸው እርስ በርሳቸው ለመረዳዳትና እንከብካቤ ለማድረግ የሚገደዱባት ማኅበረሰብ ነች። ሁላችንም የክርስቶስ ስለ ሆንን፥ አንዳችን ለሌላው ግድ ይለናል። ስለ ሆነም፥ ሰዎች በችግር ወይም በመከራ ውስጥ ሲሆኑ፥ ይረዱአቸውና ያበረታቱአቸው ዘንድ በክርስቶስ ወንድሞችና እህቶች የሆኑአቸውን መገናኝ እንደ ቤተሰብ የሚቆጥሩባት ማኅበረሰብ ትሆን ዘንድ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነው። ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ሕዝብ በመሆኗ፥ አብረውን የሚያመልኩ የቤተ ክርስቲያን ምእመናን በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ናቸው።

በአፍሪካ የተስፋፋ ቤተሰብና በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረሰብ መካከል ያለውን ተመሳሳይነት የሚገልጹ ሌሎችም የማወዳደርያ ነጥቦች አሉ። የተስፋፋው ቤተሰብ እሴቶችህን፥ እምነቶችህንና ተዳሚ የሕይወት ሥልጠናዎችን የምታገኝበት ማኅበረሰብ ነው። ይህ እጅግ የጠለቀና ዘላቂ የሕይወት ግንኙነቶችን የምትመሠርትበት ነው። ስምህንና እንደ ሰብእዊ ሰው መለያህን የምታገኘው ከዚያ ነው። ግንኙነትህንም ለመረዳት በመቻልህ የሕይወትን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ የምትጀምርበት ማኅበረሰብ ነው።

ቤተ ክርስቲያንም እንደዚሁ እሴቶችህን፥ እምነቶችህንና በክርስትና ሕይወት ተዳሚ ሥልጠናዎችን የምታገኝባት ማኅበረሰብ ነች። በሕይወትህ እጅግ የጠለቀና ዘላቂ ግንኙነቶችን የምትመሠርትባት ነች። እንደ

ክርስቲያን ስምህን፥ እንደ እግዚአብሔር ልጅም ማንነትህን የምታገኝባት የሕዝቦች ቡድን ናት። እግዚአብሔርንና ሌሎችን በግልገል የሕይወትን ዓላማ የምትረዳባት ማኅበረሰብ ነች።

የአፍሪካ ቤተሰብ በአንድ አዋቂ ሽማግሌ ሰው ይመራል፤ ይህም ብዙውን ጊዜ በቤተሰቡ ውስጥ ታላቁ አባት ይሆናል። ቤተሰብ ባሕርያችን ቢበላሽ የምንገራበትና የምንቀጣበት ማኅበረሰብ ነው። ቤተሰብ በምሽት በእሳት ዳር ቁጭ ብለን ከዚህ ቀደም በነሳችን ውስጥ ጀብዱ ስለ ፈጸመው ሰው ታሪክ እያወራን የምንማርበት ማኅበረሰብ ነው። አሳቦችን በመጋራትና አብሮ በመወያየት ውሳኔዎች የሚተላለፉበት ማኅበረሰብ ነው። በዚህም ዓይነት ከሁሉም በዕድሜ የገፋው አባት በምርታት ወደሚያሳርገው አንድ አሳብ ይደርሳል። እንደ ውልደት፥ ስም የማውጫ ዕለትና የሰርግ በዓላት የመሳሰሉ ልዩ የቤተሰብ ጊዜያት የሚኖሩበት ማኅበረሰብ ነው። አብረን የምንመገብበትና ብዙውን ጊዜ በአንድ ገበታ ላይ ከቀረበው ማዕድ የምንጋራበት ቤተሰብ ነው።

በቤተ ክርስቲያንም እንደዚሁ፥ መሪያችን «ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ጽድቅ ቅድስናም ቤዛነትም» የሆነልን ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (1 ቆሮ. 1፡30)። ቤተ ክርስቲያን ብናበላሽ የምንገራባትና የምንቀጣባት ማኅበረሰብ ነች። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለሚገኙ ታላላቅ የእምነት ጀግኖች እየተረከን የመንፈሳዊ አኗኗርን መመሪያዎች የምንማርባት ማኅበረሰብ ነች። ቤተ ክርስቲያን ነገሮችን በጋራ በመወያየት ውሳኔዎች የሚሰጡባት ማኅበረሰብ ነች። አሳቦችን በጋራ በመወያየት ወደ አንድ ነጥብ እንደርስና ይባርከው ዘንድ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር እናቀርባለን። ቤተ ክርስቲያን ልጆችን ለእግዚአብሔር መስጠት፥ ጥምቀቶችን፥ ጋብቻዎችንና እንደ ገናና ፋሲካ የመሳሰሉትን ልዩ የበዓል ጊዜያት የምናከብርባት ማኅበረሰብ ነች። ጌታችን ለኃጢአታችን መሞቱን ለማስታወስ ከአንድ ማዕድ የምንበላባትና ከአንድ ጽዋ የምንጠጣባት ቤተሰብ ነች።

በአፍሪካ የሚገኙ ሰዎች ለነሳቸውና ለባህላቸው እንዲህ ዓይነት ታማኝነት የሚያሳዩት፥ ማንነታቸው፥ ደኅንነታቸውና የሕይወት ትርጉማቸው ከተስፋፋው ቤተሰባቸውና ነሳቸው ጋር በመቆራኘት የሚከናወን በመሆኑ ነው። የቤተ ክርስቲያንም ሁኔታ የበለጠ ጥልቀት ያለው ከመሆኑ በቀር ይህንኑ የሚመስል ነው። አብዛኛዎቹ ነሳዎችና ነገዶች ታላቅና የተከበረ ቅድመ-ትውልዳቸው በሆነ ሰው ላይ የተመሠረተ ስያሜ አላቸው። የነገዱ አባላት በዚያ ቅድመ-ትውልድ ስም

በመጠራታቸው ኩራት ይሰማቸዋል። ክርስቲያንም የሰማይና የምድር ዓይነተኛ አምላክና የነገሥታት ንጉሥ ንብረት በመሆኑ መታወቂያ፥ ደኅንነትና የሕይወት ትርጉም አለው። እርሱም ሕዝቡን ለመዋጀት ደሙን በምድር ላይ አፍስሶአል። እኛ የታላቁ አምላካችንን የኢየሱስ ክርስቶስ ስም የተሸከምንና (የሐዋ. 11፡26) የእርሱ የሆንን ክርስቲያኖች ነን።

በአፍሪካ የቤተሰቡ ሕይወትና ደኅንነት ለግለሰቡ ሕይወትና ደኅንነት አስፈላጊ ነው። ስለ ሆነም፥ ግለሰቡ ለቤተሰቡ፥ ለጎሳውና ለነገዱ በሁኔታዎች ላይ የማይመሠረት ታማኝነት ያሳያል። የእግዚአብሔር ቤተሰብ ለዘላለም የሚቆይ በመሆኑ፥ ለክርስቲያኑም ከዚህ የበለጠ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ታማኝነት አስፈላጊ ነው። ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደ አዳኙና ጌታው፥ የክርስቶስ አካል ለሆነችው ቤተ ክርስቲያን ደግሞ እንደ መንፈሳዊ ቤተሰቡ ከሁሉም የላቀ ታማኝነት ሊያሳይ ይገባል። ክርስቲያን መሆን ግለት ዘላለማዊ የሆነው የእግዚአብሔር መንግሥት አካል መሆን ግለት ነው።

የጎብረት ጸሎት

ከጸሎት አኳያ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ከመሆኗ እውነት አንጻር በጣም አስፈላጊ ተዛምዶ አለ። እግዚአብሔር አብ የኢየሱስ ክርስቶስን ጸሎቶች ሰምቶ ይመልሳል? አዎን ይመልሳል (ዮሐ. 11፡41-42)። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንንስ? የክርስቶስ አካል በመሆኗ፥ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን ስም ተሸክማለች። ቤተ ክርስቲያን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ ተገለጸው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በጎብረትና ንጹሕ ልብ ስትጸልይ፥ በጸሎት የክርስቶስ ሥልጣን አላት። በእነዚህ ሁኔታዎች እግዚአብሔር (ራስ የሆነውን) የክርስቶስን ጸሎት እንደሚመልስ ሁሉ፥ (አካል የሆነችውን) የቤተ ክርስቲያንንም ጸሎት ሰምቶ ይመልሳል።

እግዚአብሔር የሚሰማው የማንን ጸሎት ነው? የሁሉም ሃይማኖት ተከታዮች በአንድ ወይም በሌላ ጊዜ ይጸልያሉ፤ ይሁንና፥ ጸሎታቸው እንደሚመለስ እርግጠኞች ሆነው ሊጸልዩ የሚችሉት የትኞቹ የሕዝብ ቡድኖች ናቸው? እግዚአብሔር ጸሎታቸውን እንደሚመልስ አስተማማኝ የተሰፋ ቃል የሰጠው ለቤተ ክርስቲያን ብቻ ነው (ማቴ. 18፡19-20፤ ማር. 11፡22-24፤ ዮሐ. 16፡23-24፤ 1 ዮሐ. 5፡14-15)። በእግዚአብሔር ፊት የክርስቶስን ስም ሥልጣን የያዘችው ቤተ ክርስቲያን ብቻ ነች። ኢየሱስ፥ «እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም፤ አብም በስሜ

የምትለምኑትን ሁሉ እንዲሰጣችሁ . . . ሾምኋችሁ» ብሏል (ዮሐ. 15፡16)።

ኢየሱስ ሁለት ወይም ከዚያ የሚበልጡ ክርስቲያኖች በስሙ ቢሰባሰቡ፥ በመካከላቸው እንደሚገኝ ተናግሯል (ማቴ. 18፡20)። በሌላ አባባል፥ (ራስ የሆነው) ክርስቶስና አካሉ የሆነችው (ቤተ ክርስቲያን) በዚያ ይገኛሉ ማለት ነው። ክርስቲያኖች ከመጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሲረዱ፥ በእግዚአብሔር ፊት ንጹሐንና የተጣመሩ ሲሆኑ፥ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጸሎቷ በእግዚአብሔር ፊት ተሰምቶ ምላሽ እንደሚያስገኝ በመተማመን ልትጸልይ ትችላለች። እግዚአብሔር ጸሎታቸው እንዳይሰማ የሚከላከል ኃጢአት ወይም ይቅር አለማለት እስከሌለ ድረስ (ማር. 11፡25፤ ኢሳ. 59፡2)፥ ጸሎታቸውን ለመመለስ የተስፋ ቃል ሰጥቷል (ማቴ. 18፡19፤ ዮሐ. 16፡23-24)። ሐዋርያው ዮሐንስ፥ «በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤ እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል። የምንለምነውን ሁሉ እንዲሰማልን ብናውቅ ከእርሱ የለመነውን ልመና እንደ ተቀበልን እናውቃለን» ብሏል (1 ዮሐ. 5፡14-15)።

እግዚአብሔር የሚሰጣቸው ምላሾች እኛ በምንጠብቀው መንገድ ወይም ጊዜ ላይመጡ ቢችሉም፥ መልስ ግማሽ ታችን የማይቀር ነው (ዮሐ. 15፡7)። የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን በወጎኒ ቤት ለነበረው ጴጥሮስ ስትጸልይ፥ ጴጥሮስ ለክርስቶስ ለመሠቃየትና ለመሞት ጥንካሬ እንዲኖረው ልመና ሳታቀርብ አትቀርም። ይኸውም ያዕቆብ በዚያን ሰሞን ተገድሎ ስለ ነበር ነው (የሐዋ. 12፡2)። በጴጥሮስ ከወጎኒ ቤት መለቀቅ ተስፋ ያደረጉ ባይመስሉም (የሐዋ. 12፡12-16)፥ እግዚአብሔር ግን ለጸሎታቸው ምላሽ የሰጠው በዚያ መልኩ ነበር።

ኢየሱስ የሲኦል ደጆች ቤተ ክርስቲያንን እንደማይቋቋሙ ገልጿል (ማቴ. 16፡18)። በሌላ አባባል፥ ወደ ሰይጣን መንግሥት የሚወስዱ ደጆች የቤተ ክርስቲያንን መረራ ሊቋቋሙ አይችሉም። ኢየሱስ የሰይጣን መንግሥት በቤተ ክርስቲያን እንደሚሸነፍ መግለጹ ነበር። የዚህ ዓረፍተ ነገር እውነትነት ክርስትና በኢየሩሳሌም ከነበረው የጥቂቶች ቡድን ስብስብነት በመላው ዓለም ለመሰራጨት በቻለችበት የታሪክ ሂደት ውስጥ ተደጋግሞ ተረጋግጧል።

የእግዚአብሔር ፈቃድ በመንግሥት በሚተላለፉ ውሳኔዎች አማካኝነት በሰይጣንና በኃጢአተኛ ሰዎች ፈቃድ ላይ ይገዛ ዘንድ፥ ክርስቲያኖች ለመንግሥት መሪዎቻቸው እንዲጸልዩ ታዘዋል (1 ጢሞ. 2፡1-2)። ለመንግሥት መሪዎች መጸለይ ግልጽ የእግዚአብሔር ፈቃድ በመሆኑ፥ እግዚአብሔር ሕዝቡ በጎብረት ለመንግሥታቸው መሪዎች ሲጸልዩ ምላሽ ይሰጣል። ለዚህ ጉዳይ ትልቅና ከፍተኛ ምሳሌ የሚሆነን በቅርቡ በኮሚኒስት አገሮች ለሚኖሩ ክርስቲያኖች ግልጽ ጸሎት በተሰጠው ምላሽ፥ በብዙ የጎለም ከፍሎች የኮሚኒስት እገዛዝ መፈራረሱ ነው። ወደ እግዚአብሔር በጸሎት ለመቅረብ በመቻሏ፥ ቤተ ክርስቲያን የታሪክን ምዕራፍ ከተሳሳተው ወደ ተስተካከለው ለመመለስ የሚችሉ ሕዝቦች የሚገኙባት ብቸኛ ተቋም ናት።

በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ የቀረቡትም ታሪኮች፥ እግዚአብሔር የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን የጎብረት ጸሎት የሚመልስባቸውን አንዳንድ መንገዶች ያብራራሉ። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ፈቃድ በሰማይ እንደሚደረግ በምድርም ይደረግ ዘንድ እንዲጸልዩ ለደቀ መዛሙርቱ አስተምሮአልና (ማቴ. 6፡10)። በተወሰኑ ሁኔታዎች እንደዚህ መጸለይ በእግዚአብሔር ፈቃድ መሠረት መጸለይ ነው።

በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያኑ መካከል ያለው ግንኙነት እንዲህ የጎላ በመሆኑ፥ ኢየሱስ በደማስቆ መንገድ ለጳውሎስ፥ «ሳውል፥ ሳውል፥ ለምን ታሳድደኛለህ?» ብሏል (የሐዋ. 9፡4)። ኢየሱስ ለሳኦል ለምን እንዲህ አለው? ጳውሎስ ተከታዮቹን እንጂ ኢየሱስን እያሳደደ አልነበረም። ይሁንና፥ ኢየሱስ ንግግሩን በመቀጠል፥ «አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ» ብሏል (ቁ. 5)። ኢየሱስ ስለ መንፈሳዊ አውነታ እየተናገረ ነበር። (ራስ የሆነው) ኢየሱስና (አካሉ የሆነችው) ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ሁኔታ እንደ አንድ የተጣመሩ በመሆናቸው፥ በክርስቶስ ላይ የሚፈጸም ማንኛውም ነገር በሕዝቡ ላይ ሲፈጸም፥ በሕዝቡ ላይ የሚደርስ ማንኛውም ነገር በክርስቶስ ላይ ይደርሳል። ኢየሱስ ለተከታዮቹ፥ «ዓለም ቢጠላችሁ ከእናንተ በፊት እኔን እንደ ጠላኝ እወቁ ... እኔን አሳደውኝ እንደ ሆኑ እናንተን ደግሞ ያሳድዱአችኋል፤ ቃሌን ጠብቀው እንደ ሆኑ ቃላችሁን ደግሞ ይጠብቃሉ» ሲል ተናግሯል (ዮሐ. 15፡18-20)። ጳውሎስም፥ «ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፥ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን» ብሏል (ሮሜ 6፡4-5)።

በክርስቶስና በሕዝቡ መካከል ላለው አንድነት አንደኛው ተዛምዶ ክርስቲያኖች የክርስቶስ አምባሳደሮች ተብለው መጠራታቸው ነው (2 ቆሮ. 5፡20)። አምባሳደር በሌላ አገር መንግሥቱን በይፋ ወክሎ የሚቀርብ ሕጋዊ ባለሥልጣን ነው። ከአገሩ መንግሥት ደንብ (ፈቃድ) አኳያ እስከ ተናገረ ድረስ፥ የአምባሳደሩ ይፋዊ ቃላት ከመንግሥቱ የበላይ ባለሥልጣናት እኩል ሥልጣን ይኖራቸዋል! የቤተ ክርስቲያንም ሁኔታ እንዲሁ ነው። ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ስም የመጸለይ፥ በክርስቶስ ስም የመናገርና በዚህ ዓለም የክርስቶስ ወኪል ሆኖ የመሥራት ሥልጣን አላት። የእውነተኛ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ጸሎቶች ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ተስማምተው ከቀረቡ፥ የክርስቶስ ሥልጣን አላቸው። በምድር ላይ ማንኛውም ሌላ ግለሰብ፥ ነገድ፥ ሕዝብ፥ የሕዝብ ቡድን ይህንን ሥልጣን አላገኘም። በዚህ በአሁኑ ዓለም በእግዚአብሔር ፈንታ የምትናገረው የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ነች። ኢየሱስ፥ «በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፥ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል» የሚል አስደናቂ ቃል የተናገረው ለዚህ ነው (ማቴ. 18፡18)።

ይህ የውክልና ሥልጣን የሞንታ ቤተ ክርስቲያን ጸሎት ጴጥሮስን በመለኮታዊ ሁኔታ ከእስር ቤት ካስወጣበት ሁኔታ አንጻር ሊታይ ይችላል። አናሳ ቁጥር ያላቸው የቤተ ክርስቲያን ቡድን ለጴጥሮስ አጥብቀው ቢጸልዩም (የሐዋ. 12፡5)፥ የሐዋርያት ሥራ 12፡15 እንደሚጠቁመን ጴጥሮስ ተፈቶ የማየት ተስፋ አልነበራቸውም። ያልተረዱት ነገር ቢኖር ጸሎታቸው ከእነርሱ እጅግ የበለጠውን አካል እንዳካተተ ነበር። ኢየሱስ ራሱ በሕዝቡ ጸሎት አማካኝነት ለጴጥሮስ መፈታት ወደ አብ እየቃተተ ነበር። አናሳዎቹ ቤተ ክርስቲያን እስክትደነቅ ድረስ፥ እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ ጴጥሮስን ከእስር ቤት አስወጣው (የሐዋ. 12፡7-11)።

በዓለም ሁሉ እውነተኛዎቹ ቤተ ክርስቲያን የኃጢአትን ግርዶሽ በግስወገድ በአንድ ልብና አሳብ ወደ አብ ስትጸልይ የሚሆነው ይኸው ነው። ኢየሱስ ራሱ በአካሉ ግለትም በቤተክርስቲያኑ ሕዝብ በኩል ስለሚታትት፥ አብ ምላሹን ይሰጣል። ኢየሱስ፥ «ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢስማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል። ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በመካከላቸው እሆናለሁና» ያለው ለዚህ ነው (ማቴ. 18፡19-20)።

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የተባበረ ጸሎት በሰጣቸው ምላሾች የተሞላ ነው። በናይጀሪያ ካዱና መንደር ውስጥ የሚገኙ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ክርስቲያኖች እግዚአብሔር በበንደል ግዛት በምሥጢር የተስፋፋውን የእስማኤላውያን ጎብረቲስብ ዕድገት እንዲገታ ለመጸለይና ለመጾም ዘወትር ቅዳሜ ይሰበሰባሉ። ከጥቂት ሳምንታት በኋላ፥ የበንደል ግዛት መንግሥት የምሥጢር ጎብረተሰቡ ሕግ-አልበኝነት የሚገልጽ ሕግ አወጣ። በ1994 የአሜሪካ ሚሳይል በሐይቲ ላይ በሚወነጨፍበት ምሽት፥ የተወሰኑ ክርስቲያኖች ጌታ ከዚያች አገር የብዙ ሰዎችን ሞትና ሥቃይ እንዲያስወግድ ለመጸለይ ተሰባሰቡ። በዚያው ምሽት፥ የሐይቲ ወታደራዊ መሪዎች ውጊያውን ሠረዙ። የፓራሹት ዕቅዶች ለተግባር እየተዘጋጁ ሳለ መረራው ታንደ። ይህ እውነታ፥ እግዚአብሔር ሕዝቡ ከንጹሕ ልብና ከፈቃዱ አኳያ በተባበረ መንፈስ የሚያቀርበውን ጸሎት እንደሚሰማ ያሳየናል (1 ዮሐ. 5፡14-15)።

ሆኖም የሚያሳዝነው ነገር፥ አብዛኞቻቹ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በቃላቸው ጸሎት ዕድላቸው እንደሚገባ አለመጠተግቸው ነው። ይህ ቢሆን ኖሮ፥ ካሁን በበለጠ ስኬት የእግዚአብሔርን መንግሥት ባስፋፉም ነበር። ካሁን የበለጠ መልካም ነገር በዓለም ውስጥ ሊያደርጉ ይችሉ ነበር። እንዲሁም፥ ካሁን የበለጠ የክፉውን ኃይላት በዓለም ሊዘላክሉ ይችሉ ነበር።

በትክክል በክርስቶስ ያሳትን ሥልጣን ብትጠቀም፥ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በተባበረ ጸሎቷ ምን ያህል ተግባር ታከናውን ነበር? መልሱ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክፉ ሰዎችና በሰይጣንም ዕቅድ ላይ ድል እንዲያደርግ ምክንያት ስለምትሆን፥ ክርስቲያኖች በዙሪያቸው ያለውን ዓለም በከፍተኛ ደረጃ ሊለውጡ ይችሉ ነበር የሚል ነው። ኢየሱስ፥ «ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች፥ እንዲሁ በምድር ትሁን» ብሎን እንድንጸልይ አስተምሮናል (ማቴ. 6፡10)። እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነቶቹን ጸሎቶች እንደሚመልስ እርግጠኛ ባይሆን ኖሮ፥ ኢየሱስ ሕዝቡ በዚህ መንገድ እንዲጸልዩ ለምን ያስተምራል?

ችግሩ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ስለ አገራቸው ወይም ስለ ዓለም ታላላቅ ችግሮች እምብዛም አለመጸለያቸው ነው። በዙሪያቸው እየተሠቃየ ላለው ዓለም ከመጸለይ ይልቅ ለራሳቸውና ለችግሮቻቸው መጸለዩን ይመርጣሉ። ይበልጥ ለዓለም ቢጸልዩ ኖሮ፥ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን የወንጌል ስብከት እስከ ምድር ዳርቻ ባደረሰችው ነበር። ኢየሱስ፥ «እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው» ሲል

አዞአል (ማቴ. 28፡19)። በተጨማሪም፥ «የመከሩን ጌታ ወደ መከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት» ብሏል (ማቴ. 9፡38)።

በዓለም ከሁሉም በላቀ ፍጥነት የምታድግ ሚሲዮናዊት ቤተ ክርስቲያን በኮሪያ ትገኛለች። ለምን ይሆን? ምክንያቱም በኮሪያ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ጸሎትን በትጋት ትወጣለችና ነው።

መላዋ ቤተ ክርስቲያን በጸሎት ብትዋጋ ኖሮ፥ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ከአያሌ ከፋቶች ነፃ ይወጡና ብዙዎቹ የሰይጣን ጥቃቶችም ይወገዱ ነበር። ኢየሱስ ሕዝቡ፥ «ክክፉ አድነን» ብለው እንዲጸልዩ አስተምሮአቸዋል (ማቴ. 6፡13)።

መንፈሳዊ ስጦታዎች

የክርስቶስ አካል ክፍል እንደ መሆኑ፥ እያንዳንዱ ክርስቲያን አንድ ወይም ከዚያ የበለጡ መንፈሳዊ ስጦታዎች በመንፈስ ቅዱስ ተሰጥተውታል (1 ጴጥ. 4፡10)። እነዚህም ስጦታዎች የተሰጡት ቤተ ክርስቲያን እንድትጠነክርና በማኅበረሰቡም ውስጥ የእግዚአብሔርን ዓላማዎች ለማከናወን እንድትችል ነው።

አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ታድግና በአገባቡ አገልግሎት ትሰጥ ዘንድ፥ እግዚአብሔር እያንዳንዱ ምእመን በመንፈሳዊ ስጦታው እንዲጠቀም ይፈልጋል (1 ቆሮ. 12፡12-20)። በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፥ ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኘውን የእያንዳንዱን አማኝ ጠቀሜታ ከሰው የአካል ክፍሎች ጠቀሜታ ጋር ያወዳድራል። አካሉ በተገቢው ሁኔታ ግልጋሎት ይሰጥ ዘንድ እያንዳንዱ የሰውነት ክፍል አስፈላጊና ጠቃሚም ነው። እንደዚሁም፥ ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በአገባቡ ግልጋሎት ለመስጠት እያንዳንዱ ክርስቲያን አስፈላጊና ጠቃሚ ነው።

አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ታድግና በአግባቡ ግልጋሎት ትሰጥ ዘንድ፥ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ልዩ ችሎታዎችን ሰጥቷል (1 ቆሮ. 12፡4-7)። ሐዋርያው ጴጥሮስ፥ «ልዩ ልዩን የእግዚአብሔርን ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች እንደ መሆናችሁ፥ እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ፤ ማንም ሰው የሚናገር ቢሆን፥ እንደ እግዚአብሔር ቃል ይናገር፤ የሚያገለግልም ቢሆን፥ እግዚአብሔር በሚሰጠኝ ኃይል ነው ብሎ ያገልግል፤ ክብርና ሥልጣን እስከ ዘላለም ድረስ ለእርሱ በሚሆነው

በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ይከብር ዘንድ» ብሏል (1 ጴጥ. 4፡10-11)።

እንደ ጴጥሮስ አባባል፥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በሁለት ምድብ ተከፍለዋል። የንግግር ስጦታዎችና የአገልግሎት ስጦታዎች አሉ። የንግግር ስጦታዎች ምሳሌዎች እንደ ትንቢት መናገር (ሮሜ 12፡6)፥ ማስተማር (ሮሜ 12፡7)፥ ሌሎችን መምከር (ሮሜ 12፡8)፥ የጥበብ ቃላት ማፍለቅ (1 ቆሮ. 12፡8)፥ በልሳናት መናገርንና በልሳናት የተነገረውን መተርጎምን ያጠቃልላሉ (1 ቆሮ. 12፡10)። የአገልግሎት ስጦታዎች ምሳሌዎች መሪነት፥ ልግስና፥ ምሕረትን ማድረግ (ሮሜ 12፡8)፥ ፈውስ (1 ቆሮ. 12፡9) እና መናፍስትን መለየትን ያጠቃልላሉ (1 ቆሮ. 12፡10)። እግዚአብሔር የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን እርስ በርሳቸው ለመረዳዳትና ለመጠናከር በእነዚህ ስጦታዎች እንዲጠቀሙ ይፈልጋል (1 ጴጥ. 4፡10፤ 1 ቆሮ. 12፡7፤ 14፡12)። ክርስቲያኖች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ለማነፅ ስጦታዎቻቸውን ለመጠቀም እንዲችሉ እግዚአብሔር የትኛውን መንፈሳዊ ስጦታ እንደ ሰጣቸው ማወቃቸው በጣም አስፈላጊ ነው።

ሬ. ክርስቲያን የትኛውን መንፈሳዊ ስጦታ እንደ ተቀበለ እንዴት ያውቃል?

መንፈሳዊ ስጦታህን ለማወቅ አራት ነገሮችን ልታደርግ ትችላለህ።

1. ዝርዝር ስጦታዎችን ከተጠቀሱባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አጥንተህ ተረዳ፤ ለምሳሌ 1ኛ ቆሮንቶስ 12 እና ሮሜ 12።

2. ስጦታዎቹ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት እንዳገለገሉ ለማወቅ በሐዋርያት ሥራ የቀረቡበትን ሁኔታ አጥና።

3. እግዚአብሔር ለጥሳኤው በጎነት በሚጠቀምበትና በሚባርክበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን ልትሠራ እንደምትችል ፈልግህ አማኝ።

4. ሌሎች የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንህን አባላት በመጠየቅ ስጦታህ የትኛው እንደ ሆነ አረጋግጥ።

እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ አማኝ ከሰጣቸው መንፈሳዊ ስጦታዎች በተጨማሪ፥ ብዙ ስጦታ ያላቸውንም ሰዎች ለቤተ ክርስቲያን ሰጥቷል። እነዚህም ሐዋርያትን (ቤተ ክርስቲያን መሥራቾችን)፥ ነቢያትን፥

ወንጌላውያንን፥ መጋቢያንንና መምህራንን ያጠቃልላሉ (ኤፌ. 4፡11)። እግዚአብሔር እነዚህ በስጦታ የበለጸጉት ሰዎች ሌሎችን በተሻለ ሁኔታ ጌታን ለማገልገል እንዲያስታጥቁ ይፈልጋል (ኤፌ. 4፡12)።

ሰ. ቤተ ክርስቲያን ከሰው ልጅ ጋር ላላት ግንኙነት የእግዚአብሔር ዕቅድ ምንድን ነው?

አንዳንድ ሰዎች ዛሬ እግዚአብሔር ለዚች ዓለም ጉዳይ እምብዛም ግድ እንደሌለው ያስባሉ። ሌሎች ደግሞ ለሰው ልጆች ዝናብና እህል በመስጠት ዓለምን ከማጽናት የበለጠ ተግባር እንደማያከናውን ያስባሉ። ብዙ ሰዎች እግዚአብሔር አጽናፈ-ዓለሙን እንደ ፈጠረ ቢያምኑም፥ አሁን ግን ልክ አንድ ሰው ሰዓትን ሞልቶ እንደሚተው ሁሉ እርሱም ዓለምን በራሱ እንዲንቀሳቀስ አድርጎ እንደ ተወው ያስባሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

መጽሐፍ ቅዱስ ዛሬ በዓለም ውስጥ የእግዚአብሔር ዋንኛ ሥራ ቤተ ክርስቲያኑን ከማነፁ ተግባር ጋር የተያያዘ መሆኑን ይገልጻል። ኢየሱስ፥ «ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም» ብሏል (ማቴ. 16፡18)። ኢየሱስ በምድር ከሁሉም ጎሳና ብሔሮች ከሚገኙ ወንዶችና ሴቶች ቤተ ክርስቲያኑን እያነፀ ነው (ራእይ 5፡9)። እግዚአብሔር ከ4000 ዓመታት በፊት ለአብርሃም ይህንኑ ተግባር እንደሚያከናውን ቃል ገብቶለት ነበር። የተስፋ ቃሉም፥ «እግዚአብሔርም አብራምን አለው፡- . . . ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፥ እባርክሃለሁ፥ ስምህንም አከብረዋለሁ . . . ለበረከትም ሁን፤ . . . የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ» የሚል ነበር (ዘፍጥ. 12፡1- 3)።

ለመሆኑ እግዚአብሔር በምድር ላይ የሚገኙትን ቤተሰቦች ሁሉ በአንድ የክብት ጭራ ተከትሎ በሚሄደር ዘላን በኩል የሚባርከው እንዴት ነው? መልሱ በገላትያ 3፡7-9 ውስጥ ተብራርቷል፡- «እንኪያስ ከእምነት የሆኑት እነዚህ የአብርሃም ልጆች እንደ ሆኑ እወቁ። መጽሐፍም እግዚአብሔር አብርሃምን በእምነት እንዲያጸድቅ አስቀድሞ አይቶ፡- በአንተ አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ ብሎ ወንጌልን ለአብርሃም አስቀድሞ ሰበከ። እንደዚህ ከእምነት የሆኑት ካመነው ከአብርሃም ጋር ይባረካሉ።» አብርሃም የክርስቶስ ቅድመ-ትውልድ ነበር። እንዲሁም፥ አብርሃም

እግዚአብሔርን ያመነ ሰው በመሆኑ በክርስቶስ ለሚያምኑት ሁሉ አባት ነው። በሴላ አባባል፥ ከአብርሃም ጀምሮ እግዚአብሔር በእምነት አማካኝነት የደኅንነትን በረከት ለሰዎች ሁሉ አዘጋጅቷል ማለት ነው።

አብርሃም ለእምነቱ በእግዚአብሔር እንደ ተባረከ ሁሉ፥ በክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ የተባረኩ ናቸው። ቤተ ክርስቲያን ወደ ሁሉም የዓለም ነገዶችና ብሔሮች ስትስፋፋ፥ የእነዚያ ነገዶችና ሕዝቦች አባላት በክርስቶስ በማመንና የቤተ ክርስቲያኑ አካል በመሆን ይባረካሉ።

አንዳንድ ሰዎች በአፍሪካና በሌሎችም አገሮች እግዚአብሔር በተለይ ለአይሁዶች እንዳደላላቸው ያስባሉ። ይህ ሐሰት ነው። እግዚአብሔር ለማንም አያዳላም (የሐዋ. 10፡34-35፤ ሮሜ 2፡11)። እግዚአብሔር ይህንኑ እውነት ወግ አጥባቂ አይሁዳዊና ፈሪሳዊ በነበረው ጳውሎስ አማካኝነት ገልጾአል፡- «በአይሁዳዊና በግሪክ ሰው መካከል ልዩነት የለምና፤ አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና፥ ለሚጠሩትም ሁሉ ባለ ጠጋ ነው» (ሮሜ 10፡12)።

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ወንጌሉን ለዓለም ሕዝቦች ሁሉ እንዲያደርሱ ከማዘዙ (ማቴ. 28:19) ከሰባት መቶ ዓመታት በፊት እግዚአብሔር በአይሁዳዊው ነቢይ ኢሳይያስ በኩል፥ «እናንተ የምድር ዳርቻ ሁሉ፥ እኔ አምላክ ነኝና፥ ከእኔም በቀር ሌላ የለምና ወደ እኔ ዘወር በሉ ትድኑማላችሁ» ሲል ተናግሯል (ኢሳ. 45፡22)። እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ ስለሚወድ፥ በንስሐና በእምነት ወደ እርሱ እንዲመለሱ ይሻል። እግዚአብሔር አይሁዳዊ፥ አፍሪካዊ፥ ቻይናዊ ወይም ሌላ ማንኛውም ዜጋ ብሎ አይለይም። እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ሁሉ ለማዳን በወጠነው ዕቅድ ውስጥ አይሁዳውያን ልዩ ሚና ከመጫወታቸው በቀር እግዚአብሔር ለማንም አላደላም (ሮሜ 9፡4-5)።

እግዚአብሔር የቅዱስ መቅደሱን ማለትም የቤተ ክርስቲያንን ግንባታ ለማጋላት ከሁሉም ነገድና ሕዝብ ሰዎችን ወደ ራሱ እየጠራ ነው። በመጀመሪያው የክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ላይ ሐዋርያው ያዕቆብ ይህንኑ ታላቅ የእግዚአብሔር ዕቅድ በሚከተሉት ቃላት አጠቃሏል፡- «ወንድሞች ሆይ፥ ስሙኝ። እግዚአብሔር ለስሙ የሚሆንን ወገን (አይሁዳዊ ካልሆኑት) ከአሕዛብ ይወስድ ዘንድ አስቀድሞ እንዴት እንደ ጎበኘ ስምዖን (ጴጥሮስ) ተርኮአል» (የሐዋ. 15፡13-14)። ዛሬ እግዚአብሔር በዓለም ውስጥ በሥራ ላይ ነው። የቅዱስ ባሕርዩን የላቁ

ደረጃዎች የሚገልጹትን ልዩ ሕዝቦች ለራሱ እየጠራ ነው (1 ጴጥ. 2፡9)። በዓለም ከሚገኙ ወንዶችና ሴቶች ለራሱ ክብር ቤተ ክርስቲያንን እየመሠረተ ነው። አንድ ቀን ይህ ታላቅ የእግዚአብሔር ሥራ ከፍጻሜ ይደርሳል።

ሸ. የቤተ ክርስቲያን ዓላማ ምንድን ነው?

እግዚአብሔር በክርስቶስ ደም በገዛቸው ልዩ ቅዱስ ሕዝቦቹ አማካኝነት ለመፈጸም የሚፈልገው ተግባር ምንድን ነው? ለቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ዓላማዎች ምንድን ናቸው?

ምስጋናና አምልኮተ-እግዚአብሔር

ለዘላለም የምትኖረው ቤተ ክርስቲያን ልታከናውን የሚገባት ቀደምት ዓላማ፥ ለእግዚአብሔር የሚገባውን ምስጋናና አምልኮ ማቅረብ ነው። በኢሳይያስ 43፡21 እግዚአብሔር ሕዝቡን፥ «ምስጋናዬን እንዲናገሩ ለእኔ የፈጠርሁት ሕዝብ» ሲል ገልጾአል። በኤፌሶን 1፡12 አማኞች «ለክብሩ ምስጋና» እንደሚኖሩ ተገልጾአል።

የወንጌል ስርጭትና ምስክርነት

በተጨማሪም፥ ቤተ ክርስቲያን የምትኖረው ሰዎችን ለክርስቶስ ለመግረክና ለዓለምም እግዚአብሔር እንዴት እንዲኖሩ እንደሚፈልግ ለማሳየት ነው። ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር ይከብር ዘንድ የኢየሱስ ክርስቶስን ባሕርይ የምትገልጽ መሣሪያ ነች (1 ጴጥ. 2፡9-12)። ኢየሱስ ሕዝቡ የዓለም ብርሃን እንደ ሆኑ ገልጾአል (ማቴ. 5፡14-16)። ብርሃን ጨለማን ይገፋል። እግዚአብሔርም ቤተ ክርስትያኑ በጨለማው ዓለም ውስጥ ብርሃን እንድትሆንለት ይፈልጋል። ቤተ ክርስቲያኑ ለዓለም ትክክልና ስሕተት የሆነውን በማሳየት የእናኗር ምሳሌነትን እንድታሳይ ይፈልጋል።

እግዚአብሔር እንዴት እንዲኖሩ እንደሚፈልግ በትክክል ለማወቅ፥ ሰዎች ከእርሱ ጋር የግል ግንኙነት ማድረግ አለባቸው። የመጀመሪያው ግንኙነት. በኃጢአት ስለ ተቋረጠ፥ ሰዎች ከሁሉ አስቀድመው ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ አለባቸው። ስለ ሆነም፥ የዓለም ብርሃን እንደ መሆኗ የቤተ ክርስቲያን እጅግ አስፈላጊው የምስክርነት አካል፥ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት እንዴት ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚታረቁና ለኃጢአታቸው ይቅርታ እንደሚያገኙ መናገር ነው

(ሉቃ.24፡46-47)። ቤተ ክርስቲያን በተቻላት ዓቅም ሁሉ ሰዎችን ወደ ንስሐና በክርስቶስ ወደ ማመን ማምጣት አለባት።

ሰናይ ምግባራት

አዲስ ኪዳን፥ «እኛ ፍጥረቱ ነንና፣ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን» ይላል (ኤፌ. 2፡10)። ኢየሱስ ክርስቲያኖች «የዓለም ጨው» እንደ ሆኑ ተናግሯል (ማቴ. 5፡13-14)። ጨውና ሰናይ ምግባራት ተያያዥ አላቦች ናቸው። ጨው የምግብን ጣዕም ለማጣፈጥና ብልሽትን ለመከላከል ይረዳል። በተመሳሳይ ሁኔታ፥ ቤተ ክርስቲያንም እግዚአብሔር ለሰው ልጅ በመጠነው ዕቅድ ከሁሉም የሚሻለውን ለማስገኘት ተቋቁማለች። እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያለው ዕቅድ በሕዝቡ ሕይወት ውስጥ መታየት አለበት። ክርስቲያኖች በሰናይ ምግባራታቸው ሁሉ ሰዎች በጋብቻ፥ በቤተሰብ፥ በሥራ፥ በማኅበረሰብና በሕይወት ግንኙነቶች ሁሉ እንዴት ሊኖሩ እንደሚገባ አርአያ ይሆናሉ።

ታሪክ በተደጋጋሚ ሁኔታ የክርስቶስ ሕዝቦች ምሕረትን፥ በጎነትንና የእግዚአብሔርን ፍትሕ በሚገልጹ ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ግንባር ቀደም ሆነው እንደሚገኙ ያሳያል። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን በዊልያም ዊልበርፎርስ መሪነት የተካሄደው የብሪታኒያው የፀረ-ባርነት ትግል ነው። ይህ ሰው የባርነትን ፍትሕ-አልበኝነትና ክፋት በተመለከቱ ሌሎች ክርስቲያኖች በመበራታት ትግሉን ተጥሎ ነበር። በዓለም ቤተ ክርስቲያን በተተከለችባቸው ስፍራዎች ሁሉ በክርስቲያኖች አማካኝነት መላጅ የሌላቸው ሕፃናት ማሰደጊያዎች፥ የዓይነ-ሕውራንና የደናቁርት ትምህርት ቤቶች፥ የአካለ ስንኩላን አገልግሎቶች፥ ችግርተኞችንና የተጣሉትን ለማገዝ የሚያስችሉ ሌሎችም ሕጋዊና ማኅበራዊ እርምጃዎች ተመስርተዋል።

በተጨማሪም፥ ጨው የምግብን መበላሸት ይከላከላል። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ማኅበረሰቡን የበለጠ ክፉ ከመሆን እንድትጠብቅ ይፈልጋል። በመልካም የምሕረትና የቸርነት ተግባራት፥ እንዲሁም በጸሎት፥ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ዓለምን አሁን ካለችበት ወደ ከፋ አዘቅት እንዳትገባ እንድትከላከል ይፈልጋል። እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያኑ ሰናይ ምግባራት የሰውን ሕይወት ጠቅላላ ገጽታ እንዲጸልሱ ይፈልጋል። የቤተ ክርስቲያን በዚህ ዓለም መኖር መንፈስ ቅዱስ በዓለም ክፋት እንዳይሰፋፋ ከሚያድርባቸው መንገዶች አንዱ ነው።

በቤተ ክርስቲያን አማካኝነት የዓለም ሰዎች ሁሉ እርሱን፥ ማዳኑን፥ በጎነቱን፥ ፍቅሩንና ክብሩን እንዲያውቁ ማድረግ የኢየሱስ ዕቅድ ነው [መዝ. (67)፡1-2፥ 7፤ (98)፡2-3፤ ኤፌ. 3፡1-11]። ክርስቶስ በምድር ላይ ከሚገኝ ዘር፥ ነገድና ቋንቋ ሁሉ ወንዶች፥ ሴቶችና ወጣቶችን በማሰባሰብ ቤተ ክርስቲያኑን እየመሠረተ ነው (ማቴ. 28፡19-20፤ ራእይ 5፡9-10፤ 7፡9-10)። ይህ ግንባታ ሥራ ሲፈጽም ኢየሱስ ይመለስና መንግሥቱን በምድር ላይ ይመሠርታል፤ ያኔም ቤተ ክርስቲያኑ ከእርሱ ጋር በዓለም ላይ ትገዛለች (ራእይ 5፡9-10፤ 11፡15)።

ኅብረትና መታነፅ

ሴላው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ዋና ዓላማ በእግዚአብሔር ሕዝቦች መካከል የሚኖር የጋራ ኅብረትና መደጋገፍ ነው (የሐዋ. 2፡42)። ጭራሮ ከሴሎች ጋር ተሰብስቦ ሲማገድ በደንብ ይነዳል። ከእሳቱ ሲወጣና ለብቻው እንዲነድ ሲደረግ ግን ይጠፋል። ይህም ክርስቲያን በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሴሎች አማኞች ጋር ኅብረት ማድረግ እንዳለበት ያብራራል። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በጌታ ያላቸውን ልምድ በመጋራት (የሐዋ. 2፡42)፥ በቃሉ ትምህርት (ቆላ. 2፡7)፥ እንዲሁም የመንፈስ ቅዱስን ስጦታዎች በመጠቀም (1 ቆሮ. 12፡7-30) በእግዚአብሔር ፍቅርና በኢየሱስ ክርስቶስ ባላቸው እምነት ሊተናነፁ ይገባል (ኤፌ. 4:15-16)።

በክርስቶስ የሚገኝ ዘላለማዊ ርስት

ኢየሱስ ለሕዝቡ ዘላለማዊ ርስት ለመስጠት ያቅዳል (ራእይ 21፡7)። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር የሆነውን ንብረት ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አብረን እንደምንወርስ ይገልጻል። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ርስት ተካፋይ እንድትሆን ዐቅዷል (ሮሜ 8፡17፤ ኤፌ. 1፡9፥11)። ገላትያ 4፡7፥ «ልጅም ከሆንህ ደግሞ በክርስቶስ የእግዚአብሔር መራሽ ነህ» ይላል።

ወላጆች ብዙውን ጊዜ በሕይወት ዘመናቸው ያፈሩትን ንብረት ለልጆቻቸው ያወርሳሉ። ይህ በውርስ ያገኙት እንጂ ያልቆበት ንብረት አይደለም። ወላጆች ኑዛዜ ሳይሰጡ በሚሞቱበት ጊዜ እንኳ፥ ብዙ መንግሥታት የወላጆችን ንብረቶች ለልጆቻቸው የሚያድል ሕግ አላቸው። በተመሳሳይ ሁኔታ፥ የእግዚአብሔር ልጆች የእግዚአብሔር መራሾች ናቸው። ለማመን ሊያስቸግር ቢችልም፥ መጽሐፍ ቅዱስ ግን ክርስቲያኖች

ከክርስቶስ ጋር የእግዚአብሔር የሆነውን ንብረት ሁሉ እንደሚወርሱ ያስተምራል። ጳውሎስ፥ «ሁሉ የእናንተ ነውና . . . ዓለምም ቢሆን ሕይወትም ቢሆን ሞትም ቢሆን ያለውም ቢሆን የሚመጣውም ቢሆን፥ ሁሉ የእናንተ ነው፥ እናንተም የክርስቶስ ናችሁ ክርስቶስም የእግዚአብሔር ነው» ብሏል (1 ቆሮ. 3፡21-23)።

ከዚህ ውርስ መካከል ከፊሉ ክርስቲያኑ አዲስ ሕይወት ከተቀበለበት ጊዜ ጀምሮ የሚታደለው ነው፤ ይህም እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ የምንለምነውን ጸሎት ሰምቶ ለመመለስ ተስፋ የሰጠበት ዓይነት ነው (ዮሐ. 16፡24)። የክርስቶስን የትንሣኤ አካል የሚመስል የትንሣኤ አካል መልበስን የመሳሰሉ የዚህ የተስፋ ቃል ሌሎች ክፍሎች ሲሆኑ እነኝህንም ወደፊት የምናገኛቸው ናቸው (ፊልጵ. 3፡21)።

ቀ. በአዲስ ኪዳን በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያኑ መካከል ያለውን ግንኙነት ለመግለጽ ያገለገሉ ዐበይት ግብራሪያዎች ምንድን ናቸው?

በአዲስ ኪዳን ስለ ቤተ ክርስቲያንና ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር ስላላት ግንኙነት ለመግለጽ ያገለገሉ አያሌ ግብራሪያዎች አሉ። የእነዚህም ግብራሪያዎች ማጠቃለያ እነሆ፡-

1. ክርስቶስ ራስ ሲሆን፥ ቤተ ክርስቲያን አካሉ ነች (ቆላ. 1፡18፤ ኤፌ. 1፡22-23)።

2. ክርስቶስ የማዕዘን ራስ ሲሆን፥ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር መቅደስ የድንጋይ ጡቦች ናቸው (ኤፌ. 2፡19-22፤ 1 ጴጥ. 2፡5-7)።

3. ክርስቶስ ሙሽራው ሲሆን፥ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ሙሽሪት ነች (2 ቆሮ. 11፡2፤ ኤፌ. 5፡25-27፥ 32፤ ራእይ 21፡9)።

4. ክርስቶስ መልካም እረኛ ሲሆን፥ ቤተ ክርስቲያን የማሰማሪያው በግ ነች [መዝ. (100)፡3፤ ዮሐ. 10፡1-16፤ 1 ጴጥ. 5፡2-4]።

5. ክርስቶስ ሊቀ ካህን ሲሆን፥ የቤተ ክርስቲያን ምእመናን በእግዚአብሔር ፊት ካህናት ናቸው (ዕብ. 8፡1፤ 1 ጴጥ. 2፡5፤ ራእይ 5፡10)።

6. ክርስቶስ የወይኑ ግንድ ሲሆን፥ የቤተ ክርስቲያን ምእመናን የወይኑ ቅርንጫፎች ናቸው (ዮሐ. 15፡1-6)።

7. ክርስቶስ ንጉሥ ሲሆን፥ ቤተ ክርነቲያን የንጉሡ መንግሥት ነች (ማቴ. 25፡34፤ ሉቃ. 12፡31-32፤ 22፡29-30)።

በ. እንዲህ የበረከቱ የተለያዩ የእምነት ክፍሎችና አብያተ ክርስቲያናት የሚታዩት ለምንድን ነው?

ክርስቲያኖች በዓለም አቀፍ ደረጃ በክርስቶስ ማንነት፥ በሞቱና በትንሣኤው፥ በፈጸመው ተግባር ላይ በመሠረታዊነት ይስማማሉ። የክርስትናን እምነት የሚተቹ ወገኖች ብዙውን ጊዜ፥ ከእኛ በቀር እውነተኛ የለም የሚሉ ምን ያህል በርካታ አብያተ ክርስቲያናት እንዳሉ በመግለጽ ይነቅፉናል። እንዲህ በርካታ የክርስትና የእምነት ክፍሎች የሚታዩት ለምንድን ነው?

መልሱ ከባድ አይደለም - ምንም እንኳ ክርስቲያኖች ስለ ክርስቶስና ማዳኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተገለጹ ቀደምት እውነቶች ላይ ቢስማሙም፥ ብዙውን ጊዜ እንደ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር፥ በተለያዩ የቤተ ክርስቲያን ልምምዶችና በመሳሰሉት አነስተኛ ጉዳዮች የተለያየ አሳብ አሳቸው። በቤተ ክርስቲያን አደረጃጀት፥ በውኃ ጥምቀት አሠራር፥ በቅዱስ ቁርባን አከባበርና በሌሎችም ጉዳዮች መለያየታቸው፥ ሰዎች የተለያዩ የእምነት ክፍሎችን እንዲመሠርቱ ምክንያት ሆኖአቸዋል። ከእነዚህ በሁለተኛ ደረጃ ከሚታዩ ጉዳዮች አንዳንዶቹ ለአሳብ ልዩነት በር በሚከፍት መልኩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተገልጸዋል። ሰዎች ደግሞ በሕይወት ዘመናቸው በአሳብ ከሚመስሉአቸው ጋር ለመሆን ይፈልጋሉ።

አንዳንድ ጉዳዮችን በተመለከተ በአሳብ መለያየት የግድ ስሕተት እንዳልሆነ መገንዘብ አለብን። ለምሳሌ ሰዎች የተለያየ ዓይነት ምግብ ይመገባሉ፤ የተለያየ ዓይነት ልብስ ይለብሳሉ። በተለያዩ የእምነት ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው ጎብረት የሚያደርጉና የሚዋደዱ እስከ ሆነ ድረስ፥ የተለያዩ የእምነት ክፍሎች መኖራቸው እግዚአብሔርን ብዙም የሚያሳስበው አይሆንም። መንፈስ ቅዱስን የሚያሳዝነው ግን የተለያዩ የእምነት ክፍሎች በክርስቶስ እጅ ለእጅ ተያይዘው ሊቆሙ ሲገባቸው፥ እርስ በርሳቸው መባላታቸውና መተቻቸታቸው ነው። እርስ በርሳቸው ሲነታረኩና ሲተቻቹ

የእግዚአብሔርን ስም በከፍተኛ ደረጃ ከማሰደባቸውም በላይ፥ በዚያ ስፍራ የክርስቶስ ምስክርነት ይዳከማል፤ ወይም ጭራሹኑ ይወድማል።

አንዳንድ ጊዜ አፍሪካውያን ለምን ብዙ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናትና የሚሲዮን ድርጅቶች ሌሎች ከሚሠሩት ወይም ከሠሩት ተግባር ባሻገር፥ በአንድ አገር ወይም በአንድ አካባቢ መሥራት እንደሚጀምሩ በማሰብ ይደነቃሉ። ይህ አንዳንድ ጊዜ የሚደረገው፥ በቤተ ክርስቲያን ወይም በሚሲዮን መሪዎች ግንዛቤ በአካባቢው የሚሠሩ ቡድኖች ለሕዝቡ ሙሉ ወይም ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ግብረሪያ አላቀረቡም በማለት ነው። አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ወይም ሚሲዮኖች ትምህርታቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ስለማይመሠርቱ፥ የዚህ ዓይነቱ ምክንያት ትክክል ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን ወይም የሚሲዮን ቡድን በሁለተኛ ደረጃ ጉዳዮች ላይ የራሳቸውን ደንቦች ለመመሥረት በመፈለጋቸው ብቻ ሌሎች ወዳሉበት አካባቢ ይሄዳሉ።

የዚህ ዓይነቱ የብዙ ድርጅቶች አሠራር የአካባቢው ሕዝብ በክርስትና ላይ እንዲጠራጠርና ግራ እንዲጋባ ሊያደርግ ይችላል። የዚህ ዓይነት ሁኔታ በሚኖርበት ጊዜ ከሁሉም የሚሻለው፥ በአካባቢው ከሚሠሩ ክርስቲያናዊ ድርጅቶች ጋር ኅብረትንና ስምምነትን መሻት ነው። በዚህም ጊዜ የማያምኑ ሰዎች ክርስቲያኖች አንዳንድ ጊዜ በሁለተኛ ደረጃ ጉዳዮች ላይ የተለያዩ አማራጮች እንዳሉአቸውና ዳሩ ግን በሚያድነው የኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ አንድ ዓይነት እምነት እንዳላቸው ሊረዱ ይችላሉ።

ተ. ኢየሱስ ለቤተ ክርስቲያን የሰጣቸው ሥርዓቶች ምንድን ናቸው?

ምንም እንኳ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ለእስራኤላውያን ያዘዛቸው አያሌ ሥርዓቶች፥ መሥዋዕቶችና በዓላት ቢኖሩም፥ በአዲስ ኪዳን ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን የሰጠው ሁለት ሥርዓቶችን ብቻ ነው። እነዚህም ሁለቱ ሥርዓቶች የውኃ ጥምቀት (ማቴ. 28፡19) እና ቅዱስ ቊርባን ናቸው (ማቴ. 26፡26-28)።

የውኃ ጥምቀት

የውኃ ጥምቀት ለአይሁዶች አዲስ ነገር አልነበረም። የአይሁድን ሃይማኖት የተቀበሉ አሕዛብ በውኃ ይጠመቁ ነበር። ለውኃ ጥምቀት የሚያገለግለው ቃል የመጣው አንድን ነገር ውኃ ውስጥ መንከር የሚል

ትርጉም ከሚሰጥ ቃል ነው። በወንጌላት መጥምቁ ዮሐንስ የኃጢአትን ንስሐ በማስመልከት በውኃ ሲያጠምቅ እንመለከታለን (ማር. 1:4)። የአንድን ሰው ሃይማኖታዊ እምነት በተመለከተ የመለወጥና የይፋዊ ምስክርነት አሳብ፥ ኢየሱስ በአደባባይ መስበክ ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ በጥምቀት ምልክትነት ይታወቅ ነበር።

ክርስቶስ ስለ ጥምቀት የሰጠው ትእዛዝ፥ አይሁዶች በጥምቀት ስለ መለወጥና ዮሐንስ ስላከናወነው ጥምቀት ለነበራቸው አሳብ ጥልቅ መንፈሳዊ ትርጉም ሰጥቷቸዋል። ኢየሱስ ተከታዮቹ በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲጠመቁ አዞአል (ማቴ. 28፡19)። ይህ ለሥላሴ እውነታ ግልጽ ማጣቀሻ ነው - ሦስት አካላትና አንድ ስም። የክርስቲያን ጥምቀት በተጨማሪም ሰውዬው ከመንፈሳዊ ሞት ወደ መንፈሳዊ ሕይወት እንደ ተለወጠ (ዳግም እንደ ተወለደ) ይገልጻል።

የክርስቲያን ጥምቀት በክርስቶስ በማመን መለወጥን በይፋ የሚመሰክር ሥርዓት ነው። ገላትያ 3፡26፥ «ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና» ይላል። ብዙ ባህሎች ወደ ብስለት መሸጋገርን የሚያመለክቱ ሥርዓቶች አሏቸው። እነዚህ ሥርዓቶች ብዙውን ጊዜ ወጣቶች ለአቅመ-አዳም ወይም ለአቅመ-ሔዋን ሲደርሱ የሚከናወኑ ናቸው። ብዙውን ጊዜ ሂደቱና ሥርዓቶቹ ስለዚያ ነገድ እምነቶችና ልምምዶች አስፈላጊ የሆነ መረጃ ይሰጣሉ። በተመሳሳይ ሁኔታ የክርስቲያን የውኃ ጥምቀትም፥ ሰውዬው ያለ ክርስቶስ ከነበረበት መንፈሳዊ ሞት በክርስቶስ ወደሚገኝ መንፈሳዊ ሕይወት እንደ ተሸጋገረ የሚመሰክር ሥርዓት ነው። በአንዳንድ አገሮች የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት በክርስቲያኖች የውኃ ጥምቀት ዕለት ይፋዊ ሥርዓትና በዓል ያዘጋጃሉ።

ባህላዊ የመሸጋገሪያ ሥርዓቶች ለባህላዊው የሃይማኖት እምነቶች የጠለቀ ትርጉም በሚሰጡባቸው ነገዶች አካባቢ፥ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ለውኃ ጥምቀት ከፍተኛ በዓል ቢያዘጋጁ መልካም ነው። በዚህ አማካኝነት ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ እውነትና በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ንድረተ-ዓለም መካከልና በባሕላዊ ሃይማኖታዊ እምነቶችና በሕዝቦቻቸው አመለካከት መካከል የሚገኘውን ግልጽ ልዩነት ልታሳይ ትችላለች። በዚህም አዳዲስ ክርስቲያኖች የአፍሪካን ባህላዊ ሃይማኖት እንዲተዉ ለመርዳት ይችላሉ። በምዕራፍ አሥራ ሦስት ስለ አካለመጠን መድረሻ ሥርዓቶች ችግሮች የበለጠ ግብራሪያ እናቀርባለን።

የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን ቡድኖች የተለያዩ ዓይነት የውኃ ጥምቀቶችን ይፈጽማሉ። ከእነዚህም ልዩነቶች አንዳንዶቹ የተለያዩ የእምነት ክፍሎች ስለ ጥምቀት ትርጉምና ዓላማ ከሚይዙአቸው አቋሞች ጋር የተዛመዱ ናቸው። በመሆኑም ካቶሊኮች፥ አንግሊካኖችና ሉተራኖች ሕፃናትን ሲያጠምቁ፥ ባፕቲስቶች፥ የአፍሪካ ኢንላንድ ቤተ ክርስቲያን፥ የምዕራብ አፍሪካ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አዋቂዎችንና ስለ ክርስቶስ በይፋ የሚመሰክሩትን ጎልማሶች ብቻ ያጠምቃሉ። የውኃ ጥምቀት ሙሉውን አካል ውኃ ውስጥ ማጥለቅን፥ በሰውዬው ላይ ውኃ ማፍሰስንና በራስ ላይ ውኃ መርጨትን ያጠቃልላል። የዚህ ዓይነቱ የተለያየ የጥምቀት ዘዴ ብዙም አስፈላጊ አይደለም። ጥምቀትን አስፈላጊ የሚያደርገው፥ የተጠመቀው ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ የአዲስ ሕይወት እንዳለውና ከሕያው እግዚአብሔር ጋር የቃል ኪዳን ግንኙነት እንዳደረገ የሚያሳይ ምልክት መሆኑ ነው።

አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያኖች የክርስቶስ አካል ተካፋይ በምንሆንበት የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት (1 ቆሮ. 12፡13) እና በክርስቶስ መለወጣችንን በሚመሰክረው የውኃ ጥምቀት (ገላ. 3፡27) መካከል ያለውን ግንኙነት ባለመረዳት ይደናገራሉ። መጽሐፍ ቅዱስ አንዲት ጥምቀት ብቻ እንዳለች ስለሚናገር ይህ ልንመረምረው የሚገባን አሳብ ነው (ኤፌ. 4፡5)። አንዱ ብቸኛውና እውነተኛው ጥምቀት የውኃ ጥምቀት ነው ወይስ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት?

በግልጽ እንደምንረዳው፥ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን አባል የሚያደርገን መለኮታዊ የእግዚአብሔር አሠራር ነው (1 ቆሮ. 12፡13)። አንዳንዶቹ እንደሚሳሳቱት፥ የውኃ ጥምቀት በራሱ እኛን የቤተ ክርስቲያን አካል የሚያደርግ መለኮታዊ ኃይል የለውም። ይሁንና፥ የውኃ ጥምቀት በዳግም ልደት የተፈጸመውን መለወጥ እንደሚመሰክር ልብ ልንለው ይገባል።

ስለዚህ ጉዳይ ስናስብ፥ የውኃ ጥምቀት መንፈስ ቅዱስ እኛን የክርስቶስ አካል በማድረግ ያከናወነው ውጫዊ ሥጋዊ ተምሳሌት እንደ ሆነ እንረዳለን። አስቀድመን እንደ ተመለከትነው፥ ቤተ ክርስቲያን አሁን መንፈስ ቅዱስ የሚኖርባት ስፍራ ነች (ኤፌ. 2፡22)። ቤተ ክርስቲያን የአሁኗ መቅደስ ወይም የእግዚአብሔር መንፈስ የማደርያ ስፍራ ነች።

በምዕራፍ ስምንት እንደ ተመለከትነው፥ ውኃ አንዳንድ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ተምሳሌት ሆኖ አገልግሏል።

በዮሐንስ 7፡37-39 ኢየሱስ፥ «ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ። በእኔ የሚያምን፥ መጽሐፍ እንዳለ፥ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ ጮኸ። ይህን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ መንፈስ ተናገረ» ብሏል። ስለ ሆነም በመንፈስ ቅዱስ የመጠመቁ ምልክት በአዲስ ኪዳን በውኃ ጥምቀት በትክክል ተብራርቷል። ከዚህ እንደምንረዳው፥ አንዱ እውነተኛ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ራሱ እግዚአብሔር የሚፈጽመው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው። ይህም ጥምቀት በተምሳሌትነት በውኃ ጥምቀት ተብራርቷል። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የቤተ ክርስቲያን አካል ያደርገናል። ስለ ሆነም፥ የውኃ ጥምቀት በአዲስ ኪዳን ውስጥ በክርስቶስ አዲስ ሕይወት ያገኘንበትን ይህንኑ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ለማመልከት ተያያዥነት ባለው መልኩ አገልግሏል።

ለማጠቃለል ያህል፥ የውኃ ጥምቀት በራሱ የቤተ ክርስቲያን አካል አያደርገንም፤ ይልቁንም፥ የውኃ ጥምቀት መንፈስ ቅዱስ የቤተ ክርስቲያን አካል እንዳደረገን የሚያሳይ ውጫዊ ምስክር ነው።

ቅዱስ ቁርባን

ክርስቶስ ተከታዮቹ ይከተሉት ዘንድ ያዘዘው ሁለተኛው ሥርዓት የቅዱስ ቁርባን ሥርዓት ነበር። ይህ ሥርዓት በሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንና በአንግሊካን አብያተ ክርስቲያናት «ኡካሪስት» (ምስጋና) በመባል ይታወቃል። ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ይህንን ሥርዓት የመሠረተው በመጨረሻው እራት ላይ ነበር (ማቴ. 26፡26-28፤ ሉቃስ 22፡17-20)። ጳውሎስ የጌታ እራት ይለዋል (1 ቆሮ. 11፡20)። ከምዕተ ዓመት ለሚያልፍ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ በሰጠው ጎብስትና ወይን ትከክለኛ ትርጉም ላይ ተከፋፍላ ቆይታለች። የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጎብስቱና ወይኑ በቅዱስ ቁርባን ወቅት በተአምር ትክክለኛ የክርስቶስ ሥጋና ደም ወደ መሆን እንደሚለወጥ ስታስተምር፥ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ግን ጎብስቱና ወይኑ የሥጋውና የደሙ ተምሳሌት መሆናቸውን ያስተምራሉ።

የቅዱስ ቁርባን አከባበር ክርስቶስ ለኃጢአታችን ሲል መሞቱን የሚያስታውስ ሥርዓት እንደ ሆነ ሁሉም የክርስትና እምነት ቡድኖች ያምናሉ። የጎብስቱ ቁራሽ የተቆረሰውን ሥጋውን ሲያመለክት (ማቴ. 26፡26)፥ ጽዋው ደግሞ ለኃጢአታችን ይቅርታ የፈሰሰ ደሙን ያሳያል (ማቴ. 26፡28)። ጳውሎስ የጌታ እራት ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መደበኛ

ልምምድ እንዲሆን ገልጾአል (1 ቆሮ. 11:23-32)። ጳውሎስ ስለ ጌታ እራት ሲያብራራ፥ አማኞች ኅብስቱንና ጽዋውን ከመውሰዳቸው አስቀድመው በጌታ ፊት ልባቸውን እንዲመረምሩና በሕይወታቸው ውስጥ የሚገኘውን ማንኛውንም ኃጢአት እንዲያስወግዱ አበክሮ ያስጠነቅቃል። ይህ ካልሆነ በራሳቸው ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ ይጋብዛሉ (1 ቆሮ. 11:27-30)።

በዚህ ማስጠንቀቂያ ምክንያት አንዳንድ ሰዎች የጌታን እራት ለመውሰድ አይፈልጉም። ይህ መልካም ተግባር ባለመሆኑ ጌታን አያስከብርም። ይልቁንም፥ እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ተናዝዘን ይቅርታውን እንድናገኝና ከዚያም ላደረገው ነገር በማመስገን የጌታን እራት እንድንወስድ ይፈልጋል (1 ዮሐ. 1: 9)።

ክርስቲያኖች የጌታን እራት በየስንት ጊዜው ሊወስዱ ይገባል? በአዲስ ኪዳን ለዚህ የተሰጠ ሕግ የለም። ከተራ ግንዛቤ እንደምንረዳው የጌታን መሥዋዕት እውነት በሕዝቡ ልብ ውስጥ ለማደስ በየጊዜው ማክበሩ ተገቢ ነው፤ ይህም ሆኖ፥ ትርጉም-አልባ ሥርዓት እንዳይሆን መጠንቀቁ አስፈላጊ ነው።

ቸ. ዐበይት የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው?

በክርስቲያን አብያተ ክርስቲያናት መካከል ሦስት ዓይነት ዐበይት የቤተ ክርስቲያን አስተዳደሮች አሉ። አብዛኛዎቹ አብያተ ክርስቲያናት እነዚህን ሦስት የቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር ዓይነቶች በማዋሀድ ወይም በመለዋወጥ ይሠራሉ። እነዚህም ሦስት የአስተዳደር ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

ኤጵስ ቆጶሳዊ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር

ይህ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር የመጣው በግሪክ ኤጵስቆጶስ ግለትም ጳጳስ ወይም ተቆጣጣሪ ከሚለው ቃል ነው። የኤጵስቆጶሳዊ አስተዳደር በቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣናት በሚገባ በተደነገገ መዋቅር ላይ ይመሠረታል። በዚህ ዓይነቱ አስተዳደር፥ ብዙውን ጊዜ ከመሪዎች ወደ ምእመናን የሚወርድ ግልጽ የቤተ ክርስቲያን ሥልጣን አለ። ከላይ አቡን፥ ሊቀ-ጳጳስ፥ ጳጳስ፥ ወይም ሌላ ማዕረግ ያለው ግለሰብ መሪ ይሰየማል። በዚሳዩ ባለሥልጣን እስከ ታችኛው የቤተ ክርስቲያን ምእመን ድረስ

የመሪዎች ተዋረድ አለ። የዚህ ዓይነት አስተዳደር ባለበት ቤተ ክርስቲያን፥ ተራ የቤተ ክርስቲያን ምእመናን በተለያዩ መንገዶች መንፈሳዊ ስጦታዎቻቸውን ከአገልግሎት ላይ ሊያውሉ ቢችሉም፥ አስተዳደራዊ ሥልጣን የላቸውም። አንዳንድ ጊዜም በ«አገልጋዮቹ» (በክፍያ የሚሠሩ ባለሥልጣናት) እና በ«ተራው ምእመን» መካከል ገደብ ይደረጋል። የዚህ ዓይነቱን አስተዳደር ከሚከተሉ የእምነት ክፍሎች የሮም ካቶሊክ፥ አንግሊካንና ሜተዲስት አብያተ ክርስቲያናት ይገኙባቸዋል።

የፕረስቢቴሪያል የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር

ይህ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር «ሽማግሌ» የሚል ትርጉም ካለው፥ «ፕረስቡተሮስ» ከሚል የግሪክ ቃል የተገኘ ነው። የዚህ ዓይነቱ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በእያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሽማግሌዎች ቡድን በመሪነት የሚሠራበት ነው። እነዚህ ሽማግሌዎች የተሰጡ ወይም የተመረጡ ሲሆኑ፥ በቤተ ክርስቲያን የሥራ ስብሰባዎች የተቀረውን ማኅበረ-ምእመን ፍላጎት ይጠብቃሉ። ብዙውን ጊዜ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በተወሰነ መልከዓ-ምድራዊ አካባቢ በብዙ ቡድኖች የሚሰባሰቡ ናቸው። እነዚህም ቡድኖች አካባቢያዊ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ፥ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ፥ ሲኖዶስ ወይም ፕረስቢተሪ ተብለው ሊጠሩ ይችላሉ። የአፍሪካ ኢንላንድ ቤተ ክርስቲያን፥ የ«ECWA» ቤተ ክርስቲያን፥ የፕረስቢተሪያን ቤተ ክርስቲያን እና ክርስቲያን ሪፎርምድ ቤተ ክርስቲያን በዚሁ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ይመራሉ።

ኮንግርጌሽናል የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳር

የዚህ ዓይነቱ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ከፖለቲካዊ የዲሞክራሲ አሳብ ጋር ተዛማጅነት ያለው ነው። ከኮንግርጌሽናል የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር፥ የአስተዳደር እንቅስቃሴው የሚከናወነው ሁሉም ምእመን እኩል ድምፅ በሚሰጥባቸው የጉባኤ ስብሰባዎች ነው። በዚህ ዓይነቱ አስተዳደር እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በፈቃደኛነት ከሚሳተፍበት ልል የጎብረት ስብሰባዎች ካልሆነ በቀር በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ላይ አይደገፍም። በኮንግርጌሽናል አስተዳደር የሚመሩ አብያተ ክርስቲያናት ብዙውን ጊዜ ወደ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ወይም ማኅበራት ሳያጣቅሱ የራሳቸውን ደንቦች ያዋቅራሉ። የዚህ ዓይነቱን የአስተዳደር መንገድ ከሚከተሉት መካከል ባፕቲስት፥ ኮንግርጌሽናልና ብዙዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ገለልተኛ አብያተ ክርስቲያናት ይገኙባቸዋል።

ጎ. በአዲስ ኪዳን መሠረት በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ዐበይት የመሪነት ስፍራዎች የትኞቹ ናቸው?

ለምን የተለያዩ ክርስቲያናዊ የእምነት ክፍሎች እንዳሉ ስንነጋገር፥ የቤተ ክርስቲያንን አደረጃጀትን በተመለከተም ብዙ የተለያዩ አሳቦች እንደሚቀርቡ ተረድተናል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሚገኝ የመሪነት ስፍራ በሚነሣ በማንኛውም ውይይት ወቅት፥ እነዚህን የአሳብ ልዩነቶች ልብ ልንል ይገባል። ይሁንና፥ እነዚህ ልዩነቶች ከሌሎች የእምነት ክፍሎች ጋር በሚኖረን ኅብረት ውስጥ ጣልቃ መግባት የለባቸውም።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከብቃት መሥፈርቶች ጋር የቀረቡ ቢያንስ ሁለት ዓይነት የመሪነት ስፍራዎች አሉ። እነዚህም፥ የሽምግልናና የድቁና ስፍራዎች ናቸው። እነዚህ ሁለት ስፍራዎች በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ የመሪነት ሚናዎች ያመለክታሉ። ይህም ፊልጵስዩስ 1፡1ን እና 1ኛ ጢሞቴዎስ 3፡1-7ን ከ1ኛ ጢሞቴዎስ 3፡8-13 ጋር በማወዳደር ሊታይ ይችላል።

አንዳንድ ክርስቲያኖች ከእነዚህ በተጨማሪ ቢያንስ ሁለት የመሪነት ስፍራዎች በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንደ ተገለጹ ይናገራሉ። እነዚህም ጳጳሳትንና መጋቢዎችን ያጠቃልላሉ። እነዚህ አራት ቃላት ማለትም ሽማግሌ፥ ዲያቆን፥ ጳጳስ (ኤጲስቆጶስ) እና መጋቢ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሁሉ ተጠቅሰዋል። ከእነዚህ ማዕረጎች ሁሉ ጋር የተዛመደውን አገልግሎት ቀጥለን እንመረምራለን።

ሁለቱ ብቸኛ የመሪነት ስፍራዎች ሽማግሌዎችና ዲያቆናት ብቻ እንደ ሆኑ የሚያምኑ ሰዎች ጳጳሳትና መጋቢያን ለስሙ የተመረጡ አገልጋዮች እንደ ሆኑ ያስተምራሉ። ይህ ጳውሎስ የመሠረታቸውን አብያተ ክርስቲያናት ፈለግ የተከተለ ይመስላል።

ሽማግሌ (ግሪክ - ፕረስቡተሮስ)

ሽማግሌ (ፕረስቡተሮስ) እና ጳጳስ (ኤጲስቆጶስ) የሚሉት ቃላት በአዲስ ኪዳን በተለዋዋጭነት አገልግለዋል (ቲቶ 1፡5፥ 7)። ጳውሎስ ስለ ኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ሲናገር (ኤፌ. 20፡17) እግዚአብሔር እነዚህን ሽማግሌዎች የዚያ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት አድርጎ እንደ ሾማቸው ገልጾአል (የሐዋ. 20፡28)። ሽማግሌ የሚለው ቃል የሰውየውን መንፈሳዊ ብስለት ሲያመለክት፥ ጳጳስ የሚለው ግን ሰውየው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን የመንፈሳዊ ኃላፊነት ዓይነት ይገልጻል። በሌላ አባባል፥

አንድ ሰው ጳጳስ ለመሆን (በመንፈሳዊ ሕይወቱ) ሽማግሌ ሊሆን ይገባል። ጳጳስ አዲስ ክርስቲያን ሊሆን አይገባም ነበር (1 ጢሞ. 3:6)።

ለጳጳሳት (ብሎም ሽማግሌዎች) የተሰጡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሥፈርቶች በ1ኛ ጢሞቴዎስ 3:1-7 እና በቲቶ 1:5-9 ውስጥ ተጠቅሰዋል። ወርቃማ ባሕርይ ያላቸውና መንፈሳዊ ብስለት የሚታይባቸው ሰዎች መሆን አለባቸው። በሁለቱም ስፍራዎች፥ የመጀመሪያው መሥፈርት ያለ ነቀፋ መሆናቸው ነበር። በሌላ አባባል፥ በባሕርያቸው ወይም በጠባያቸው ውስጥ ምንም ዓይነት አጠያያቂ ነገር መኖር የለበትም።

ሁለተኛው መሥፈርት የአንዲት ሚስት ባል መሆናቸው ነው። ከዚህም የተነሣ ብዙ ሚስት ያላቸውና የተፋቱ ብሎም ለሁለተኛ ጊዜ ያገቡ ሰዎች የዚህ አግልግሎት ተካፋዮች አይሆኑም። ይህ ማለት ግን ብዙ ያገቡ ወይም ለሁለተኛ ጊዜ ያገቡ ክርስቲያኖች መንፈሳውያን አይደሉም ማለት አይደለም። እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን መሪነት ለጋብቻ ያቀደው የፍጹም ፈቃዱ ምሳሌነት እንዲገለጽ ይፈልጋል ማለት ነው (ማቴ. 19:3-6)።

በተጨማሪም፥ ጳጳሳት በነገር ሁሉ አግባብነትን (ልከኛነትን) የሚያሳዩ ሊሆኑ ይገባል። ራሳቸውን የሚገዙ፥ አስተዋዮች፥ መልካም ምስክርነት ያላቸው፥ እንግዳ ተቀባዮች፥ ለማስተማር ብቃት ያላቸው፥ አስካሪ መጠጥ የማይጠጡ፥ ጋር የሆኑ፥ የማይጨቃጨቁና ገንዘብ የማይወዱ ሊሆኑ ይገባል (1 ጢሞ. 3:2-3)። ቤታቸውን በሚገባ የሚያስተዳድሩና በቅርቡ ወደ ጌታ ያልመጡ ሊሆኑ ይገባል (1 ጢሞ. 3:4-7)።

በአዲስ ኪዳን ሁልጊዜም በያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ከአንድ የሚበዙ ሽማግሌዎች ነበሩ (የሐዋ. 14:23)። ይህንኑ ምሳሌ የምንከተል ከሆነ፥ የማንኛዋም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪነት በአያሌ ሽማግሌዎች የሚከናወን እንጂ በአንድ ሰው ብቻ የሚተገበር አይሆንም። ከኃጢአተኛ ሰብአዊ ዝንባሌያችን የተነሣ፥ አንድ ሰው በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ሙሉ ሥልጣን እንዲኖረው ማድረግ ጥበብ የተሞላበት አሠራር አይደለም። በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሁሉም ሰው ለሌሎች የቤተ ክርስቲያን ምእመናን ኃላፊነት ሊኖረው ይገባል። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ እንጂ የማንኛውም ግለሰብ ንብረት አይደለችም። የቤተ ክርስቲያኑ ራስ ክርስቶስ ብቻ ነው።

ሽማግሌዎች ቤተ ክርስቲያንን የመምራትና የማስተማር ኃላፊነት አለባቸው (1 ጢሞ. 3፡2)። ስለ ሆነም፥ በሽምግልና የሚሾሙ ሰዎች የመሪነትንና የማስተማርን ስጦታ ከመንፈስ ቅዱስ እንደ ተቀበሉ ግረጋገጥ ያሻል። እነዚህ ሰዎች ጉባኤውን በእግዚአብሔር ቃል የማስታጠቅ ኃላፊነቱ ሊኖራቸው ይገባል (1 ጢሞ. 5፡17)።

በብዙ አነስተኛ አብያተ ክርስቲያናት፥ ገንዘብ እየተከፈለው (ሙሉ ጊዜውን ሰጥቶ) የሚሠራ መጋቢ ብቻ የስብከቱንና የማስተማሩን አገልግሎት ይወጣል፤ ይህም የሚሆነው ተገቢውን የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጠና ያገኘው እርሱ ብቻ ሊሆን ስለሚችል ነው። ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ በንግግር የማገልገል ስጦታ የሰጣቸውን ሰዎች ለይታ ብታውቅና እነዚህ ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሥልጠና እንዲያገኙ ብታበረታታ መልካም ነው።

ጳጳስ (በግሪክ - ኤጲስ ቆጶስ)

በቀድሞዪቱ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ስፍራ ተሹመው ያሚያገለግሉ ሽማግሌዎች መንፈሳዊ መሪነትን ያከናውኑ ነበር። ይህም መሪነት የእግዚአብሔርን ቃል ከማስተማሩ ጋር አስተዳደራዊ ኃላፊነቶችንም በመወጣት ቤተክርስቲያኒቱን ያንቀሳቅሳል (1 ጢሞ. 5፡17)። በተጨማሪም፥ የማማከር (ቲቶ 1፡9) እና የሥነ-ሥርዓት (1 ቆሮ. 5፡12-13) እርምጃ አገልግሎቶችን ያካትታል። ለጳጳሳት የሚያስፈልገው መሥፈርት ስለ ሽማግሌዎች በቀረበው አሳብ ሥር ተብራርቷል።

መጋቢ ወይም እረኛ (በግሪክ - ፖይሜን)

መጋቢ ማለት እረኛ ማለት ነው። ይህ ስያሜ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን (በጎችን) በመንከባከብ የሚወጡትን ኃላፊነት ያመለክታል። ክርስቶስ የበጎች ሁሉ ዋንኛ እረኛ ነው (1 ጴጥ. 5፡4)። ኢየሱስ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት አንድ ወይም ከዚያ የሚልቁ እረኞች እንዲኖሩአቸው ዐቅዶአል (1 ጴጥ. 5፡1-3)። እያንዳንዱ መጋቢ ወይም እረኛ የክርስቶስን ኀይለተኛ ምሳሌነት ሊከተል ይገባዋል።

አንድ መጋቢ ቀጥረን የምናሰማራ ከሆነ፥ መጋቢው የመሪነት ኃላፊነቶችን ከሽማግሌዎች ጋር ሊጋራ ይገባል። የተቀጠረውን መጋቢ

ጨምሮ ሽማግሌዎች ሁሉ እርስ በርሳቸው መገዛዛት አለባቸው (ኤፌ. 4፡1-3፤ ፊልጵ. 2፡1-5፤ 1 ጴጥ. 5፡5)።

ኢየሱስ ለሕዝቡ እንደ ተጠነቀቀ ሁሉ፥ መጋቢዎችም ለመንጋዎቻቸው ፍቅር የተሞላበትን እንክብካቤ፥ ትሕትና፥ ትዕግሥትና አሳቢነት በማሳየት ምሳሌዎች መሆን አለባቸው። ሐዋሪያው ጴጥሮስ መጋቢዎች የመሪነት ስፍራቸውን ለግል ጥቅም ወይም ገንዘብ ለማግኛ እንዳይጠቀሙበት ያስጠነቅቃል (1 ጴጥ. 5፡2-3)።

ዲያቆን (በግሪክ - ዲያቆኖስ)

የቃሉ ትርጉም አገልጋይ ማለት ነው። ክርስቲያኖች ሁሉ የክርስቶስ አገልጋዮች ሊሆኑ ይገባል (ዮሐ. 12፡26)። ይሁንና፥ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 3:8-13 የተለዩ መሥፈርቶች ስለ ተሰጡት፥ በቀድሞዪቱ ቤተ ክርስቲያን ተሹመው የሚሠሩ ልዩ አገልጋዮች (ዲያቆናት) ሳይኖሩ አይቀሩም። በተጨማሪም፥ በፊልጵስዩስ 1፡1 በጳጳሳትና በዲያቆናት መካከል ልዩነት ተደርጓል።

ለዲያቆናት የተሰጠው የመሥፈርቶች ዝርዝር አጠር ከማለቱ በቀር ለሽማግሌዎች ከተሰጠው ጋር ተመሳሳይ ነው። ዲያቆናት ጭምቶች፥ የማይነቀፉ፥ የማይናደዱ፥ እውነተኞች፥ አስካሪ መጠጥ የማይጠጡና ነውረኛ ረብ የማይወዱ ሊሆኑ ይገባል (1 ጢሞ. 3፡8)። እምነታቸውን አጥብቀው የሚይዙና መጥፎ ባሕርይ የማያሳዩ ሊሆኑ ይገባል (1 ጢሞ. 3፡9)። ዲያቆናት አንድ ሚስት ብቻ ልትኖራቸውና ቤታቸውን በሚገባ የሚያስተዳድሩ ሰዎች መሆን አለባቸው (1 ጢሞ. 3፡12)። ለዲቁና የሚሾሙ ሰዎች ከመንፈስ ቅዱስ ለማገልገል የሚያስችላቸውን ስጦታ መቀበላቸውን ማረጋገጥ ያሻል።

ዲያቆናት ሊያከናውኑአቸው የሚገቡ አያሌ የተለያዩ ዓይነት አግልግሎቶች አሉ። በሐዋርያት ሥራ 6፡1-6 የተጠቀሱ ሰባት ሰዎች የቀድሞዪቱ ቤተ ክርስቲያን ዲያቆናት እንደ ሆኑ አድርገን ልንወስድ እንችላለን። አገልግሎታቸው ምግብን ማከፋፈል ሲሆን፥ በመንፈስ ቅዱስና በጥበብ መሞላታቸው መሥፈርት ሆኖ መቅረቡ አስገራሚ ነው (የሐዋ. 6፡3)። ሆኖም ለአገልግሎት ከመመደባቸው በፊት ልዩ ሥነ ሥርዓት ይፈጸምላቸው ነበር (የሐዋ. 6:6)።

ከላይ ከቀረበው ማብራርያ፥ በመንፈስ ቅዱስ የተሰጡ ሁለቱ የመንፈሳዊ ስጦታ ምድቦች (ማለትም የንግግር ስጦታዎችና የአገልግሎት ስጦታዎች - 1 ኢጥ. 4፡11) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚገኙ ሁለት የመሪነት ስፍራዎች ጋር የሚዛመዱ ይመስላል።

ማጠቃለያ

ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ነች። ዘላለማዊት እና የተስፋፋች የእግዚአብሔር ቤተሰብ ነች። በምድርና በሰማይ ከብዙ ነገዶች፥ ዘሮችና ሕዝቦች ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኛቸውና ጌታቸው አድርገው ያመኑ ሰዎች ሁሉ የሚገኙባት ማኅበረሰብ ነች። እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን አንዲት ልዩ የእምነት ዘርፍ አይደለችም። ይልቁንም፥ እምነታቸውን በክርስቶስ ላይ በመጣል በመንፈስ ቅዱስ ዳግም የተወለዱትን የአያሌ የክርስትና እምነት ዘርፎች ምእመናን ታካትታለች። ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዘመን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ነች።

ከአፍሪካ ማኅበራዊ መዋቅር የተነሣ፥ እግዚአብሔር ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የወጠነውን ዕቅድ መረዳት ቀላል ነው። በአፍሪካ የአንድ ሰው ቤተሰብና ነገዳዊ ማኅበረሰብ በሕይወቱ ከሁሉም የላቁ እውነታዎች ናቸው። እንደዚሁም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በክርስቲያን ሕይወት ከሁሉም የላቀች ማኅበረሰብ እንድትሆን የእግዚአብሔር ዕቅድ ነው። ቤተ ክርስቲያን እያንዳንዳቸው ክርስቶስን ጌታቸውና አዳኛቸው አድርገው በማመናቸው ከነገዳዊና ማኅበራዊ ትስስሮች ባሻገር፥ ሕዝቦች እርስ በርሳቸው እንደ መንፈሳዊ ወንድማማቾችና እህትማማቾች የሚቀባበሉባት ቡድን ነች። የእግዚአብሔር ቅዱስ ሕዝቦች ማኅበረሰብ በመሆናቸው፥ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን እርስ በርሳቸው የመሸካከም ኃላፊነት አለባቸው። በተጨማሪም፥ ለራሳቸውና ለዓለም እየጸለዩ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የመመላለስ እድልና ኃላፊነት አለባቸው። በዚህም እግዚአብሔር በጸሎታቸው አማካኝነት ፈቃዱ በምድር ላይ እንዲፈጸምና በሰናይ ተግባራታቸው ክብሩ እንዲታይ ያደርጋል። በዓለም ላይ እንዲህ ዓይነት እድል ወይም ኃላፊነት ያለው ሌላ ማኅበረሰብ የለም።

በዚህ ዓለም የቤተ ክርስቲያን ዓላማ ለእግዚአብሔር እውነተኛ ምስጋናና አምልኮ ማቅረብ፥ ለክርስቲያኖች ደግሞ ኅብረትን፥ ዕድገትንና መደጋገፍን ማስገኘት ነው። በተጨማሪም፥ በምስክርነት ቃልና በእግዚአብሔር ሕዝቦች የፍቅር ተግባራት አማካኝነት ከደኅንነት ርቆ

ለጠፋው ዓለም የእግዚአብሔር እውነት እንዲታወቅ ግድረግ ነው። በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር ያላት ግንኙነት በሙሽራ (ክርስቶስ) እና በሙሽራዪቱ (ቤተ ክርስቲያን)፥ በመልካም አረኛና በበጎቹ፥ በራስና በአካል ክፍሎች፥ እንዲሁም በንጉሥና በመንግሥቱ መካከል በሚገኘው ቁርኝት ተብራርቷል።

ኢየሱስ ሁለት አስፈላጊ ሥርዓቶችን ለቤተ ክርስቲያን ሰጥቷል። እነዚህም፥ አንድ ሰው በክርስቶስ ዳግም እንደ ተወለደ የሚመሰክር የውኃ ጥምቀትና ክርስቶስ ለሕዝቡ የኃጢአት ይቅርታ ለማስገኘት እንደ ሞተ ለማስታወስ የሚከናወን ቅዱስ ቁርባን ናቸው። የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት የተለያየ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደሮች አሉአቸው። በመሠረቱ፥ በተለያዩ የእምነት ክፍሎች ውስጥ የሚኖሩ ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው እስከ ተፋቀሩና እስከ ተከባበሩ ድረስ፥ እነዚህ ልዩነቶች ብዙም የሚያሳስቡ አይደሉም። አዲስ ኪዳን በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተለያዩ የመሪነት ስፍራዎችና አገልግሎቶች እንዳሉ ይገልጻል። እነዚህም ስፍራዎች፥ ሽማግሌዎችን፥ መጋቢዎችንና ዲያቆናትን ያጠቃልላሉ። ለእነዚህ የመሪነት ስፍራዎች የሚመደቡ ሰዎች በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተገለጹትን የመንፈሳዊ ብስለትና ባሕርይ መሥፈርቶች ማሟላት ይጠበቅባቸዋል።

በምዕራፍ 9 ላይ የተመሠረቱ የመወያያ ጥያቄዎችና መልመጃዎች

1. እውነተኛዪቱ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የትኛዋ ናት?

2. አንድ ሰው የእውነተኛዪቱ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አባል ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው?

3. ለሁሉም ክርስቲያኖች አንድ እውነተኛ ጥምቀት የሆነው የትኛው ጥምቀት ነው?

4. የተለያዩ የእምነት ዘርፎች የሚታዩት ለምንድን ነው?

5. በእነዚህ ጥያቄዎች ላይ ቡድኑ ይወያይ፡-

ሀ. የቤተ ክርስቲያን ጽንሰ-አሳብ ከአፍሪካ ማኅበረሰብ ሕይወት ጋር የሚዛመደው እንዴት ነው?

ለ. ቤተ ክርስቲያን የአፍሪካን ማኅበረሰባዊ ሕይወት የምታጠናክረው እንዴት ነው?

6. በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ የቤተ ክርስቲያንን ዓላማዎች ዘርዝር። አንተ የምታመልክባት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ዓላማዎች የምታሟላው እንዴት ነው?

7. ቤተ ክርስቲያን ወደፊት ከክርስቶስ የምትወርሰው ምንድን ነው?

8. አራት አባላት በሚገኙበት ቡድን ተከፋፈሉና በሚከተለው ጥያቄ ላይ ተወያዩ፡- አንድ ሰው ብቻውን ከሚጸልይ ይልቅ ብዙ አማኞች ተሰብስበው በኢየሱስ ስም ሲጸልዩ፥ ከፍተኛ ኃይል የሚገለጸው ለምንድን ነው? መልሳችሁን ለማጠናከር የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን አቅርቡ።

9. ከሰባት የተለያዩ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ሰባት ተማሪዎችን ምረጥና ሰለ ራሳቸው ቤተ ክርስቲያን የጸሎት ሕይወት እንዲመሰክሩ አድርግ። ተማሪዎቹ እግዚአብሔር ውስን ጸሎቶችን እንዴት እንደ መለሰ ዝርዝር ጉዳዮችን በማቅረብ ማብራራት አለባቸው።

10. ክፍሉን ከእያንዳንዱ ነገድ ሁለት ወይም ከዚያ የሚበልጡ አባላት በሚገኙባቸው ቡድኖች ከፋፍል። እያንዳንዱ ቡድን ለነገዱ አንገብጋቢ የሆኑትንና ጸሎት ሊደረግባቸው የሚያሻቸውን ጉዳዮች ያቅርብ። ለእነዚህ ጥያቄዎች እያንዳንዱ ቡድን ይጸልይ።

11. አራት አባላት በሚገኙባቸው ቡድኖች ተከፋፈሉና እያንዳንዱ ቡድን ለአገራችሁና ለቤተ ክርስቲያናችሁ መሪዎች እጅግ አንገብጋቢ የሆኑትን የጸሎት ጥያቄዎች እንዲዘረዝር ይሁን። ከዚያም እያንዳንዱ ቡድን ለእነዚህ ጉዳዮች ይጸልይ።

12. ከኤጲስቆጶሳዊ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና ከኮንግሬሽናል የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር የትኛው እንደሚሻል ሁለት ሰዎች እንዲከራከሩ አድርግ። ከክርክሩ በኋላ፥ ክፍሉ በተነሡት ነጥቦች ላይ አሳብ እንዲሰጥ ይሁን።

13. የመንፈሳዊ ስጦታዎችን አጠቃቀም በተመለከተ ሁለት ውይይቶችን አዘጋጅ። የመጀመሪያው ቀን ውይይት በንግግር ስጦታዎች ላይ የሚካሄድ ሲሆን፥ የሁለተኛው ቀን ውይይት በአገልግሎት ስጦታዎች ላይ ይሆናል። በእያንዳንዱ ዕለት የውይይቱ መሪ በምድቡ የሚገኙትን ስጦታዎች በጥቁር ሰሌዳ ላይ መዘርዘር አለበት። የውይይቱ ተሳታፊዎች ስጦታው በአዲስ

ከዳን ዘመን እንዴት እንዳገለገለና በራሳቸው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እንዴት ሊያገለግል እንደሚችል ምሳሌዎችን ይስጡ። ከእነዚህ የሁለት ቀናት ውይይቶች በኋላ፡ እያንዳንዱ ሰው ስጦታው ምን እንደ ሆነ የሚሰማውን ይጻፍ።

14. ክፍሉ በአገራቸው ከሚገኙት ቡድኖች መካከል የጸሎት ፕሮግራም የሚያሻው የትኛው እንደ ሆነ ምርጫ ያካሂድ። ይህም ወንጌል ያልደረሰው ወይም ወንጌሉን በጥብቅ የሚቃወም ቡድን መሆን አለበት። ስለ እንደዚህ ዓይነት ቡድኖች ከቤተ ክርስቲያን ወይም ከሚሲዮን መሪዎች መረጃ ማግኘት ይቻል ይሆናል። ክፍሉ ለመረጣቸው የሕዝብ ወገኖች ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ መጸለይ አለበት። የጸሎቱ አትኩሮት እግዚአብሔር ለእነዚያ ሕዝቦች አስፈላጊዎቹን ወንጌላውያን እንዲልክና በተሰበከላቸውም ጊዜ ይቀበሉት ዘንድ ልባቸውን እንዲከፍት ሊሆን ይገባል።

SUGGESTED FOR FURTHER READING

Green, Michael. Freed to Serve. London: Hodder, 1988.

Johnstone, Patrick. Operation World - You Can Change The World. Carlisle: O. M. Publishing, 1994.

Martin, Ralph P. The Family And The Fellowship. Exeter: Paternoster Press, 1979.

Rye, James and Nina. The Survivor's Guide to Church Life. Leicester: Inter Varsity Press, 1992.

Watson, David. I Believe in the Church. London: Hodder, reprinted 1993.

ምዕራፍ 10

ክርስቲያንና የመናፍስት ዓለም

ሞብዌኒ በዓመፁ እንቅስቃሴ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ እየተሳተፈ መጥቷል። የዓመፁን መሪዎች በሙሉ ልቡ በመደገፉም በሚችለው ዓቅም ሁሉ ሊረዳቸው ፈለገ። ከመንደሩ አሥር ኪሎሜትሮች ያህል ርቆ በሚገኘው ትልቅ የሚሲዮን ጣቢያ ውስጥ ለአያሌ ዓመታት የሠራ በመሆኑ፥ በግቢው በእያንዳንዱ ቤት ውስጥ ማን እንደሚኖርና እያንዳንዱም ቤተሰብ የሚከተለውን መርሐ-ግብር ያውቅ ነበር። እንዲያውም በብዙዎቹ ቤቶች ውስጥ ይገባና ይወጣ ስለ ነበር፥ የክፍሎቹን አወቃቀር ሳይቀር ያውቅ ነበር። በቡድኑ ውስጥ የሞብዌኒን ያህል የሚሲዮኑን ግቢ የሚያውቅ አልነበረም።

ቡድኑ ለአያሌ ዓመታት በጥንቃቄ የወጠነውን የጥቃት ዕቅድ የሚፈጽምበት ጊዜ ደረሰ። በዚህ ሌሊት በሚሲዮን ግቢ ውስጥ የሚገኙትን ሰዎች ሁሉ ለመፍጀት ተስማምተው ነበር። ቡድኑና ሞብዌኒ አስፈላጊውን ዝግጅት አጠናቀዋል። በቁጥር ከመብዛታቸው በተጨማሪ በደንብ ታጥቀው ነበር። በእንቅልፍና በግቢው ውስጥ በመዟዟር የሚያሳልፉትን ሁለት ሽማግሌ ዘበኞች በቀላሉ ሊያሸንፉ ይችሉ ነበር።

ይሁንና፥ ሞብዌኒና የቡድኑ አባላት ወደ ግቢው አጥር በዝግታ ሲጠጉ በፍርሃትና በመደነቅ ቀጥ ብለው ቆሙ! ይህ የሚያስፈራ ብዙ ሠራዊት ከየት መጣ? በግቢው ውስጥ ለሚኖሩት ሰዎች ስለ ሞብዌኒና ስለ ቡድኑ የጥፋት ተልእኮ ማስጠንቀቂያ የሰጣቸው ይኖር ይሆን? ጠባቂዎቹ የያዙት ምንኛ እንደ እሳት የሚያበራ እንግዳ ሰይፍ ነው? ጠባቂዎቹ ብዙና ጠንካሮች ነበሩ። ሞብዌኒና የቡድኑ አባላት ለአጭር ጊዜ በሹክሹክታ ከተነጋገሩ በኋላ፥ ጥቃቱን ላለመሰንዘር ወሰኑ። ጠባቂዎቹ ከቡድናቸው አባላት በጣም ይበዙ ነበር።

ከጥቂት ወራት በኋላ ሞብዌኒ በዓመፅ እንቅስቃሴው ውስጥ በይፋ በመሳተፉ በመንግሥት ታሰረ። ይህ ከሆነ ከሁለት ዓመት በኋላ፥ እነርሱ ሊያጠቁ የፈለጉት የዚያ ጣቢያ አባል የሆነ ሚሲዮናዊ ወጎኒ ቤቱን ይጎበኝ ነበር። ሚሲዮናዊው ከሞብዌኒ ጋር ሲነጋገር፥ ሞብዌኒ ቡድናቸው የሚሲዮን ጣቢያውን ለማጥቃት ቢፈልግም ብዙ ጠባቂዎች አስፈሪ ሰይፎችን ይዘው በግየቱ እንዴት እንደ ተርበተበተ ተናገረ። ቀጥሎም፥ ስለ ጥቃቱ እንዴት እንደ ሰሙና እነዚህን በርካታ ጠባቂዎች ከየት እንደ ቀጠሩ

ጠየቀው። ሚሊዮናዊው ግን ሌሎች ተጨማሪ ጠባቂዎች እንዳልተቀጠሩና በዚያ ምሽት ይጠብቁ የነበሩት ሁለት ተረኛ ዘበኞች እንደ ነበሩ ሲገልጽ፥ ሞብዬኒ እጅግ ተደነቀ።

ይህ ታሪክ በትክክል የመናፍስት ዓለም እንዳለ ይገልጻል። የዚያ ዓለም መናፍስት በዓለማችን ጉዳዮች ውስጥ በቀጥታ የሚሳተፉባቸው ጊዜያት አሉ።

ባህላዊ ሕዝቦች በዙሪያቸው ስለሚገኙ መናፍስት በማሰብ ከጊዜያቸው የሚበዛውን ያሳልፋሉ። ብዙውን ጊዜ በመንደራቸው ለሚገኙ ሕዝቦች የሚያስቡትን ያህል ከቅድመ-ትውልዶቻቸውና ከሌሎች መናፍስት ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነት ያስባሉ። ሊመለከቱ በሚችሉት ዓለም ውስጥ የሚከሰቱት ብዙዎቹ ነገሮች ሊመለከቱ ከማይችሉት የመናፍስት ዓለም ጋር የተያያዙ መሆናቸውን ያምናሉ።

ባህላዊ ሃይማኖት ለሚከተል ሰው፥ የማይታየውን ዓለም መናፍስት ለማስደሰት የሚያስችል ማናችውንም ነገር መናገርና ማድረግ የሕይወቱ ዐቢይ ቁም ነገር ነው። ከዚህ በተቃራኒ፥ በአውሮፓ ወይም በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ ብዙ ሰዎች እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ለመናፍስት ዓለም ይህን ያህል ትኩረት አይሰጡም ነበር። ካለፉት 30 ዓመታት ወዲህ ግን ሁኔታው በመለወጡ፥ ብዙ የአውሮፓና የሰሜን አሜሪካ ዜጎች ምትሐታዊ የአጋንንት ዓለም አስፋፊዎች ሆነዋል። ይህም ሆኖ፥ ዛሬ ብዙዎቹ የእነዚህ አገሮች ዜጎች ስለ መናፍስት በማሰብ የሚያጠፉት ጊዜ እጅግ ጥቂት ወይም ኢምንት ነው ለማለት ይቻላል። ምዕራባውያን ለሚያዩት ነገር ትኩረት ይሰጣሉ። አፍሪካውያን ግን ብዙውን ጊዜ ሊያዩ ስለማይችሉአቸው ነገሮች ያስባሉ። ይህም በአውሮፓውያንና በአፍሪካውያን የዓለም ዕይታ መካከል መሠረታዊ ልዩነት ያስከትላል።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መናፍስት ዓለም ምን ይላል? በዙሪያችን ለሚገኙ መናፍስት ምን ያህል ልናስብ ይገባል? የሰማይና የምድር መናፍስት አሉ? ከምናስበው በላይ ሕይወታችንን የሚነዱ ሌሎች መናፍስት አሉ? በዚህ ምዕራፍ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ እንሻለን፦

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መናፍስት ዓለምና ከዚያ ዓለም ጋር ስላለን ግንኙነት ምን ይላል?

ለ. መላእክት እነማን ናቸው?

ሐ. መላእክት ምን ይመስላሉ?

መ. የተለያዩ የመላእክት ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው?

ሠ. የቅዱሳን መላእክት ባሕርያት የትኞቹ ናቸው?

ረ. ቅዱሳን መላእክት የእግዚአብሔርን ሰዎች የሚረዱባቸው አንዳንድ መንገዶች የትኞቹ ናቸው?

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መናፍስት ዓለምና ከዚያ ዓለም ጋር ስላለን ግንኙነት ምን ይላል?

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መናፍስት ዓለም ብዙ የሚነግረን አለው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ስለ ሆነ፥ ስለ መናፍስት ዓለም የሚቀርቡትን አሳቦች ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚገልጸልን ጋር ማወዳደር አለብን። በምዕራፍ ሁለት መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ ገልጸናል። ከእኛ አመለካከት ጋር ቢስማማም ባይስማማም እግዚአብሔር አንድን ነገር እውነት ነው ካለ እውነት ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ፥ እግዚአብሔር የአንድን አሳብ ውሸትነት ከገለጸልን ቆዲያውኑ ማውገዝ አለብን - ምንም ያህል አሳማኝ ትምህርት የተሰጠን ቢሆንም እንኳ። ይህ ካለሆነ ግን እንሳሳታለን።

በአፍሪካ ሁሉም ሰው ለማለት ይቻላል በእግዚአብሔር ህልውና ያምናል። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር መንፈስ እንደ ሆነና አምልኮአችንም መንፈሳዊ አምልኮ መሆን እንዳለበት ይገልጻል። በሌላ አባባል፥ በአምልኮአችን ውስጥ ምንም ዓይነት ምስሎችን ወይም ጣዖታትን ማካተት የለብንም። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል» ይላል (ዮሐ. 4፡24)። ክርስቲያን ያልሆኑ ሃይማኖቶች የዘወትር ልምምድ መንፈሳዊ ነገሮችን በጣዖታት ወይም በምስሎች መወከል ነው። እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህንኑ ልምምድ አውግዞአል። በዘጸአት 20፡4 እግዚአብሔር፥ «በላይ በሰማይ ካለው፥ በታችም በምድር ካለው፥ ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ። አትስገድላቸውም፥ አታምልካቸውምም» ብሏል።

መጽሐፍ ቅዱስ በአጽናፈ-ዓለሙ የሚገኙ መናፍስት ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተፈጠሩ ይገልጻል። ሁሉም ከእርሱ ሥልጣንና ኃይል ሥር ናቸው። ቆላስይስ 1፡16፥ «የሚታዩትና የማይታዩትም፥ ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት፥ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና። ሁሉ ለእርሱና በእርሱ ተፈጥሮአል» ይላል። ከዚህና ከሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የምንረዳው የመናፍስት ዓለም እንዳለ ነው። እነዚህም መናፍስት በክርስቶስ እንደ ተፈጠሩና ለዓላማው ማስፈጸሚያ እንደሚኖሩ ግልጽ ነው። አንድም ሳይቀር ሁላቸውም ለእርሱ ይገዛሉ። እነዚህ የተፈጠሩ መናፍስት ጠቃሚ ደረጃ ያለው ኃይልና ሥልጣን ይዘዋል። በሚታይ ዓለም በሚከናወን ሁኔታ ውስጥ በጣም ግልጽ የሆነ ተጽዕኖ ሊያስከትሉ ይችላሉ።

የመናፍስት ዓለም ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ሲሆን፥ እያንዳንዱ አፍሪካዊ ይህንኑ ይገነዘባል። ይህም ሆኖ፥ አንዳንድ አፍሪካውያን ስለ መናፍስት የሚይዙት አሳብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር አይስማማም። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መናፍስት ምን ያስተምራል?

ለ. መላእክት እነማን ናቸው?

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሰውን ወይም ምድርን ከመፍጠሩ በፊት የሰማይ ሠራዊት የሚባሉትን እጅግ ብዙ መናፍስት እንደ ፈጠረ ያስተምራል [መዝ. (148)፡2፥ 5]። ሠራዊት የሚለው ቃል እንደ ጦር ሠራዊት እጅግ በርካታ ሰዎች የሚገኙበትን ቡድን ያመለክታል። ሰማያዊ ሠራዊት እግዚአብሔር በምድር ላይ የፍጥረት ሥራውን ከመጀመሩ በፊት የፈጠራቸውን ሁሉ ያመለክት ይሆናል። ምን ያህል ፍጥረታትና ስንት ዓይነት የተፈጠሩ አካላት እንደ ነበሩ አናውቅም። ብዙ መሆናቸውን ግን እናውቃለን። በራእይ 5፡11 እግዚአብሔር በሚሊዮን በሚቆጠሩ መላእክት ተመልኮአል። ነህምያ 9፡6፥ «ሁሉንም ሕያው አድርገኸዋል፤ የሰማዩም ሠራዊት ለአንተ ይሰግዳሉ» ይላል። እንደ መዝሙር (103)፡20-21 እና (148)፡2 አገላለጽ፥ የሰማዩ ሠራዊት መላእክት ናቸው። መልአክ የሚለው ቃል በግሪክ «አንጀሎስ» ከሚለው የተገኘ ሲሆን፥ ትርጉሙም «መልእክተኛ» ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ፥ አንዳንድ ጊዜ መላእክት በከዋክብት ተምሳሌት ተገልጸዋል (ኢዮብ 38፡4፥ 7፤ ራእይ 12፡4፥ 9)። ምናልባት ከዋክብት ተብለው የተጠሩት ከሚያበራው ገጽታቸው የተነሣ

ይሆናል (ሉቃ. 24፡4፤ ራእይ 10፡1)። በተጨማሪም፥ መላእክት «የእግዚአብሔር ልጆች» ተብለው ተጠርተዋል (ኢዮብ 1፡6፤ 38፡7)።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁለት ዐበይት የመላእክት ቡድኖች ተገልጸዋል። የሚበዙት ቅዱሳን መላእክት ሲሆኑ፥ እነዚህ ኃይለኛና ታማኝ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው [መዝ. (103)፡20-21፤ ማር. 8፡38]። አነስተኛዎቹ (ምናልባትም እንደ ራእይ 12፡4 ገለጻ ሲሶ የሚሆኑት) ከሰይጣን ጋር በማመፃቸው የወደቁ ርኩሳን መላእክት ናቸው (ማቴ. 25፡41)።

እንደ ዕብራውያን 1፡14 ገለጻ፥ መላእክት መናፍስት ናቸው። የተለያዩ ዓይነት መላእክት አሉ። መጽሐፍ ቅዱስ የሰማዩን ሠራዊት የገነቡትን በርካታ የመናፍስት ዓይነቶች በሙሉ አለመግለጹ እውነት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ከሚገልጸልን የሥልጣን ደረጃ ያላቸው የተለያዩ ዓይነት መላእክት እንዳሉ እናውቃለን። ከእነዚህ መናፍስት አንዳንዶቹ ያልተለመደ ቅርፅ አላቸው። ሱራፌል ዓይኖች የሞሉአቸውና ስድስት ክንፎች ያሏቸው ናቸው (ኢሳ. 6፡2ን ከራእይ 4፡7-8 ጋር አወዳድር)። ኪሩቤል (ነጠላው ኪሩብ) የሰው ዓይነት ገጽታ እንዳላቸው ሲገለጽ፥ ዳሩ ግን አራት ፊቶችና አራት ክንፎች አሏቸው (ሕዝ. 1፡1፥ 5-8፤ 10፡20-22)። አንዳንድ መላእክት እንደ ሰዎች በሰብአዊ አካል የመገለጽ ችሎታ አላቸው። መላእክት በዚህ መልኩ ለአብርሃም (ዘፍጥ. 18:1፥ 22፤ 19:1) እና በክርስቶስ መቃብር ላይ ተገልጸዋል (ሉቃ. 24፡4)። አጋንንት (ምናልባትም የወደቁ መላእክት) በሥጋ ሊገለጹ ይችላሉ (ራእይ 16፡13)።

የመላእክት በሥጋዊ አካል የመገለጽ ብቃት የሰው ልጅ ከመናፍስት ዓለም ጋር ስላለው ግንኙነት አንድ አስፈላጊ ነገር ይጠቁመናል። መናፍስት ራሳቸውን ለሰዎች ዓይን ዕይታ ሊያቀርቡ ይችላሉ። ይህንንም የሚያደርጉት ከተፈጥሮአቸው አኳያ ለመርዳት ወይም ለማታለል ሊሆን ይችላል። መናፍስት የዚህ ዓይነት ችሎታ ስላላቸው ክፉ መናፍስት ሰውን ሊያታልሉ እንደሚችሉ መገንዘብ አለብን። ምናልባት በዓለም የብዙ ሃይማኖት ተከታዮች የተታለሉት በእንዲህ ዓይነቱ የክፉ መናፍስት አካላዊ መገለጽ ይሆናል። በራስህ ዓይኖች መንፈሳዊ አካል ብትመለከት፥ ያየኸውን የማመን ዝንባሌህ ከፍተኛ ነው። እንዲሁም፥ መንፈሱ የነገርህንም ልታምን ትችላለህ (1 ጢሞ. 4፡1)።

ሐ. መላእክት ምን ይመስላሉ?

መላእክት የሙታን ወይም የከበሩ ሰብአዊ ሰዎች መናፍስት አይደሉም። ከፍተኛ እውቀት ያላቸውና በእግዚአብሔር የተፈጠሩ ኃይለኛ አካላት የሚገኙበት የተለየ ቡድን ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ በሙታን መናፍስትና በመላእክት መካከል ልዩነት ተደርጓል (ሉቃ. 16፡22፤ 20፡34-36፤ ዕብ. 12፡22-23)። መላእክት ከሰው ልጅ በላይ ልቀው የሚገኙ የተፈጠሩ አካላት ናቸው [መዝ. (103)፡20]።

መላእክት እንደ ሰዎች ሁሉ የሚናገሩና የሚሠሩ ናቸው (ለምሳሌ ማቴ. 28፡2-7)። ከሰዎች በተቃራኒ፥ ሊሞቱ የማይችሉ የትንሣኤ አካል ያላቸው ዓይነት ናቸው (ሉቃ. 20፡36)። መላእክት ጋብቻና የቤተሰብ ሕይወት የላቸውም (ማር. 12፡25)። ይሁንና፥ በጌታ ዕርገት ጊዜ መልአኩ ለደቀ መዛሙርቱ እንደ ተናገረ፥ መላእክት ሊናገሩና ከተራ ሰዎች ጋር ሊግባቡ ይችላሉ (የሐዋ. 1፡10-11)። በአንዳንድ አጋጣሚዎች፥ መላእክት ግርማ ሞገስን በተላበሰ ሰማያዊ ክብር ለሰዎች ተገልጸዋል (ራእይ 10፡1-2)። ዳንኤል መልአክን በዚህ ዓይነት ተመልክቷል (ዳን. 10፡4-8)። ይህ ለዳንኤል አስፈሪና አድካሚ ገጠመኝ ነበር (ዳን. 10፡8)።

መልአካዊ መናፍስት በሰዎች ላይ በሚደርሱ ክስተቶችና በተፈጥሮም ላይ ቀጥተኛ ተጽዕኖ እንዳላቸው መገመት ትክክል ነው። በ2ኛ ሳሙኤል 24፡15-16 የእግዚአብሔር መልአክ በንጉሥ ዳዊት ላይ ባወረደው ፍርድ 70000 የእስራኤል ዜጎችን ፈጅቷል። የእግዚአብሔር መልአክ በአንድ ሌሊት የኢየሩሳሌምን ቅጥር ከብበው የነበሩትን 185000 የአሦር ወታደሮች ገድሏል (ኢሳ. 37፡36)። በመጽሐፈ ኢዮብ፥ ሰይጣን ማለትም የወደቀው መልአክ (በእግዚአብሔር ፈቃድ) አሥሩንም የኢዮብ ልጆች የሚገድል ከፍተኛ ዐውሎ ነፋስ አስነሥቷል (ኢዮብ 1፡12፥ 19)። በራእይ መጽሐፍ፥ የእግዚአብሔር መላእክት የእግዚአብሔርን ፍርድ በዓለም ላይ ሲያወርዱ፥ ነፋሳትን (ራእይ 7፡1)፥ ምድርን (8፡6-7)፥ ባሕርን (16፡3-4)፥ ፀሐይን (16፡8) ጎድተዋል።

አፍሪካውያን በመናፍስት ወይም በተፈጥሮ አማልክት ላይ የሚጥሉአቸው አንዳንድ እምነቶች፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ መላእክት ከተገለጸው እውነት ጋር ተመሳሳይነት አላቸው። ይሁንና፥ በባህላዊ

የአግልክት አስተሳሰቦችና በመጽሐፍ ቅዱስ መላእክት መካከል መሠረታዊ ልዩነቶች አሉ። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ገለጻ፥ የቅዱሳን መላእክት እንቅስቃሴዎች በእግዚአብሔር ብቻ በቀጥታ የሚታዘዙ ናቸው [መዝ. (103)፡20-21]። እንደ አንዳንድ ባህላዊ ሃይማኖቶች፥ ሰዎች አግልክትን በምትካቸው አንድን ተግባር እንዲያከናውኑ ሊያግባቧቸው ይችላሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ፥ ሰዎች መላእክትን እንዳያመልኩ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸዋል (ራእይ 19፡10፤ ራእይ 22፡8-9)። ይህም ለእነርሱ መሠዋትን ያጠቃልላል። የባህላዊ ሃይማኖት መናፍስትና አግልክት ብዙውን ጊዜ መሥዋዕቶችን ይቀበላሉ፤ እንዲቀርብላቸውም ይጠይቃሉ።

ሰዎች ለመናፍስት መሥዋዕቶችን የሚያቀርቡ ከሆነ፥ ሙሉ ለሙሉ ለግለት ይቻላል በሰይጣን ወይም ከወደቁ መላእክቱቹ በአንዱ እጅ እንደሚወድቁ የታወቀ ነው። ሰይጣን እንደ ብርሃን መልአክ ሆኖ የመገለጽ ኃይል ስላለው (2 ቆሮ. 11፡14)፥ ይህንኑ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ አድርጓል፤ ሰይጣን የሚፈልገው ሰዎች እንዲያመልኩት ነው (ማቴ. 4፡8-9)። ሰዎች እንዲህ ዓይነት የአምልኮ ተግባራትን እንደሚፈልጉ ለጠየቁአቸው መናፍስት መሥዋዕቶችን በማቅረብ፥ ስለ እግዚአብሔር እና በኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ገለጸው እውነት ከማወቅ ታግደዋል። የዚህ ዓይነቱ መታዘዝ ወይም አምልኮ የመጀመሪያውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ይጥሳል (ዘጸ. 20፡3-5)። ከሰዎች መሥዋዕትን የሚጠይቅ ማንኛውም የባህላዊ እምነት መንፈስ ወይም አምላክ የወደቀው መልአክ ነው። የእግዚአብሔር ቅዱሳን መላእክት በምንም ዓይነት የዚህ ዓይነቱን የአምልኮ ሥርዓት አይጠይቁም (ራእይ 22፡8-9)።

. መጽሐፍ ቅዱስ ሰው እግዚአብሔርንና እግዚአብሔርን ብቻ እንዲያመልክ ያዛል (ማቴ. 4፡10፤ ቆላ. 2፡18-19)። እግዚአብሔር ሰዎች እርዳታ ለማግኘት በቀጥታ እርሱን እንዲሹ ይፈልጋል (ኢሳ. 55፡6-7)። በአግላጅ መናፍስት ወይም እንደ መድኃኒት አዋቂ ወይም ጠንቋዮች በመሳሰሉ ሰብአዊ ጠቢባን በኩል እንዲቀርቡት አይፈልግም። እግዚአብሔር የሚቀበለውና በሰውና በእግዚአብሔር መካከል መካከለኛ ሆኖ የሚሠራው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው (1 ጢሞ. 2፡5)። በዘዳግም 32፡16-17 ሙሴ፥ «(እግዚአብሔርን) በሌሎች አግልክት አስቀኑት፥ በርኩሰታቸውም አስቆጡት። እግዚአብሔር ላልሆኑ አጋንንት . . . ሠዉ» ብሏል። ይህ በዘዳግም የቀረበው ምንባብ በባህላዊ ሃይማኖቶች በኩል

ያለውን የከፋ መታለል ይገልጻል። አማልክትና የቅድመ-ትውልድ መገለጽ እንደ ሆኑ የሚናገሩ አስመሳይ መናፍስት በጥንቃቄ ራሳቸውን ለውጠው የቀረቡ የሰይጣን አጋንንት እንጂ ሌላ አይደሉም።

ሰዎች ከእግዚአብሔር ዘንድ እርዳታ ለማግኘት ከፈለጉ፥ ጥያቄዎቻቸውንና ጸሎቶቻቸውን ለእግዚአብሔር በቀጥታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንዲያቀርቡ ታዘዋል (ዮሐ. 16፡23-24፤ ዕብ. 4፡14-16)። እግዚአብሔር እንዴት ምላሹን እንደሚሰጥ ያውቃል። እግዚአብሔር ሰዎችን ለመርዳት ቅዱሳን መላእክትን ከተጠቀመ፥ የሚያዛቸው እርሱ እንጂ ሰዎች አይደሉም [መዝ. (103)፡20-21]። ሰዎች ከእግዚአብሔር ውጭ ከመናፍስት፥ ወይም ከጠንቋዮች እርዳታ ለመጠየቅ ከሞከሩ በዘዳግም 32፡16-17 እንደ ተጠቀሰው በአጋንንት ቁጥጥር ሥር የመውደቅ አደጋ ይደርስባቸዋል። በዘዳግም 6፡13-15 መጽሐፍ ቅዱስ፥ «አምላክህን እግዚአብሔርን ፍራ፤ እርሱንም አምልክ፤ በስሙም ማል። ... በዙሪያችሁ ያሉት አሕዛብ የሚያመልኩአቸውን ሌሎችን አማልክት አትከተሉ» ይላል። ይህ ዓረፍተ ነገር ለእስራኤላውያን ከ3300 ዓመታት በፊት አስፈላጊ የነበረውን ያህል፥ ዛሬም ለአፍሪካውያን አስፈላጊ ነው።

ከእውነተኛው አምላክ ውጭ የአማልክትን ወይም የመናፍስትን ችሮታ የሚሹ ክርስቲያን ያልሆኑ ሃይማኖቶች ተከታዮች፥ ተታልለው የሰይጣንና የአጋንንት ባርያ ወደ መሆን ይመጣሉ። ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «አሕዛብ የሚሠዉት ለአጋንንት እንጂ ለእግዚአብሔር እንዳይሠዉ እላለሁ፤ ከአጋንንትም ጋር ማኅበርተኞች እንድትሆኑ አልወድም» ሲል አስጠንቅቆናል (1 ቆሮ. 10፡20)። ይህ ከአጋንንት እርዳታ ለሚሹ ሰዎች መናፍስቱ የቱንም ያህል «ደጋግ» ቢመስሉም እውነት ነው። አጋንንት ያልሆኑትን መስለው ለመታየት ብልጣ ብልጦች ናቸው።

አንዳንድ ሰዎች የሚከሰተው ሁሉ የአንዳንድ መናፍስት የተግባር ውጤት እንደ ሆነ ያምናሉ። መጽሐፍ ቅዱስ የሚከሰተው ሁሉ የመላእክት ወይም የአጋንንት ተግባር ውጤት እንደ ሆነ አያስተምርም። ኢየሱስ በሉቃስ 12፡54-55 በተፈጥሮ ውስጥ ክስተቶች በመደበኛና ሊተነበይ በሚችል ምክንያት እንደሚፈጸሙ አመልክቷል። መልካምም ሆነ ክፉ መናፍስት በሕይወት ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ የሚገቡት በተወሰኑ ሁኔታዎች ብቻ ነው። አመለካከታችንን (የእውነታ ዕይታችንን) በባህላዊ የተለምዶ አሳቦች ላይ ከመመሥረት ይልቅ መጽሐፍ ቅዱስ

በሚያስተምረው እውነት ላይ መመሥረት አለብን። ስለ መናፍስትና ሰዎች ዝምድና መንፈሳዊ ጦርነትን በሚያትተው ምዕራፍ 12 ውስጥ የበለጠ ማብራሪያ እናቀርባለን።

መ. የተለያዩ የመላእክት ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው?

የእግዚአብሔር እጅ የሠራው ነገር ሁሉ መልካምና ፍጹም እንደ ነበረ ሁሉ (ዘፍጥ. 1፡31)፥ መላእክትም በተፈጠሩ ጊዜ ቅዱስና ውብ ፍጥረታት ነበሩ (ሕዝ. 28፡12-13)። ኢየሱስ ክርስቶስ የፈጠራቸው የተለያዩ ዓይነት መላእክት ነበሩ (ቆላ. 1፡16)። በአዲስ ኪዳን ውስጥ የመላእክትን የተለያዩ ደረጃዎች ለመግለጽ ቢያንስ ስምንት የተለያዩ የግሪክ ቃላት አገልግለዋል። ምንም እንኳ መጽሐፍ ቅዱስ እያንዳንዱን ምድብ በዝርዝር ባይገልጽም፥ አንዳንድ የመላእክት ማዕረጎች ከሌሎች የበለጠ ሥልጣንና ኃይል አላቸው። የመልአክ ከፍተኛው ማዕረግ ሊቀ-መልአክ ይመስላል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሊቀ-መልአክ የተባለው ሚካኤል ብቻ ነው (ይሁዳ 9)። ይሁንና፥ ዳንኤል 10፡13 ሌሎች መላእክት በዚህ ምድብ ውስጥ ሊኖሩ እንደሚችሉ ያሳያል። ኪሩቤል የተባለው ሌላው ቡድን የእግዚአብሔርን ዙፋን የመከበብ ልዩ ስፍራ ያለው ይመስላል (ሕዝ. 10፡1-19፤ 28፡14)።

ሠ. የቅዱሳን መላእክት ባሕርያት የትኞቹ ናቸው?

ከሁሉም በላይ ቅዱሳን ናቸው (ማር. 8፡38)። እግዚአብሔርን ያለ ምንም ጥያቄ ይታዘዙታል። ከንጹሕ ባሕርያቸው አኳያ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ለመከተል ፈጣኖች ናቸው። መዝሙር (103)፡20፥ «ቃሉን የምትፈጽሙ፥ ብርቱዎችና ኃያላን፥ የቃሉንም ድምፅ የምትሰሙ መላእክቱ ሁሉ፥ እግዚአብሔርን ባርኩ» ይላል።

መላእክት በጣም ከፍተኛ የሆነ እውቀት፥ ኃይል፥ ችሎታና ጥንካሬ አላቸው (2 ጴጥ. 2፡11)። መላእክት ከሰው የሚልቁ የፍጥረት አካላት ናቸው። ለካህኑ ዘካርያስ ለእርሱና ለባለቤቱ ኤልሳቤጥ ስለሚወለደው ልጅ (መጥምቁ ዮሐንስ) የተናገረውን መልአክ ታላቅ እውቀት ልብ በል (ሉቃ. 1፡13-17)። በራእይ መጽሐፍ የእግዚአብሔርን ፍርድ ለማመልከት ባሕሮችንና ንጹሑን ውኃ ሁሉ ወደ ደም የሚለውጠውን መልአክ ኃይል አስብ (ራእይ 16፡3-4)። ከጴጥሮስ እጆች የብረት ሰንሰለቶች እንዲወድቁና

የወኅኒ ቤቱም በሮች በራሳቸው እንዲከፈቱ ያደረገውን መልአክ ችሎታ አስተውል (የሐዋ. 12፡7፥ 10)።

የመላእክት ጥንካሬ ከሰው እጅግ የላቀ ነው። ይህንኑ ታላቅ ጥንካሬ ለመመልከት የሚከተሉትን ምሳሌዎች ተመልከት። አንድ መልአክ ብቻ በአንድ ሌሊት 185000 አምራውያንን ገድሏል (ኢሳ. 37፡36)። አንድ መልአክ የተራቡትን አንበሶች አፍ በመዝጋት፥ በገዛ ጉድጓዳቸው ውስጥ የተጣለውን ዳንኤልን እንዳይነኩ ከልክሎአቸዋል (ዳን. 6፡22)። አንድ መልአክ ከክርስቶስ መቃብር ታላቅ ድንጋይ በቀላሉ አንከባልሎአል (ማቴ. 28፡2)። በዚህ ዘመን መጨረሻ ላይ አንድ መልአክ ሰይጣንን አስሮ ለሺህ ዓመታት ወደ ጥልቁ ይጥለዋል (ራእይ 20፡1-2)። እነዚህ እግዚአብሔር ለሰው በማይታይ ሁኔታ ልጆቹን እንዲረዱ የላካቸው መላእክት ናቸው (ዕብ. 1፡14)!

ረ. ቅዱሳን መላእክት የእግዚአብሔርን ሰዎች የሚረዱባቸው አንዳንድ መንገዶች የትኞቹ ናቸው?

1. መላእክት በብዙ ሁኔታዎች የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ይጠብቃሉ [መዝ. (34)፡7፤ (91)፡11]። ሐዋርያት በሊቀ ካህኑ ታስረው ሳሉ ከእስር ቤት ያወጣቸው መልአክ ነበር (የሐዋ. 5፡17-19)። ማዕበል በበረታበት ባሕር ውስጥ በጳውሎስ አጠገብ ቆሞ ያበረታው መልአክ ነበር (የሐዋ. 27፡22-24)። ብዙ ክርስቲያኖች በሕይወት ዘመናቸው በተለያዩ ጊዜያት የመላእክትን ማንነት ሳያውቁ እንደ ደግ እንግዳ በመቁጠር በቅዱሳን መላእክት ሳይረዱ አልቀሩም (ዕብ. 1፡14፤ 13፡2)። በዚህ ምዕራፍ የመግቢያ ታሪክ ውስጥ እንደ ተመለከተው፥ የሚሊዮኑን ጣቢያ የጠበቁት ቅዱሳን መላእክት ናቸው። ለክርስቲያን በአንገብጋቢ ሁኔታ የተፈለገውን እርዳታ አድርጎ ወዲያውኑ ስለ ተሰወረ ሰው የሚናገሩ ብዙ ምስክርነቶች አሉ። መልአኩ ጴጥሮስን ከወኅኒ ቤት እንዲወጣ ከረዳ በኋላ በዚህ ዓይነት ነበር የተሰወረው (የሐዋ. 12፡10)።

2. መላእክት በሥጋዊም ሆነ አእምሮአዊ ሁኔታ የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ያጸናሉ። ኢየሱስ በምድራዊ አካሉ በጌቴሰማኔ የአትክልት ስፍራ ሊሠቃይ ሳለ ያበረታው የእግዚአብሔር መልአክ ነበር (ሉቃ. 22፡43)። ዳንኤል በሣለ ጊዜ ያበረታው መልአክ ነበር (ዳን. 10፡16-18)። ለኤልያስ

ያልተለመደ ልዩ ምግብ ያዘጋጀውና ለ40 ቀናት ከኤልዛቤል ሊሸሽ ያበረታው መልአክ ነበር (1 ነገሥት 19፡5-8)።

3. መላእክት በተለይም በወንጌል ስርጭት ወቅት አማኞችን ይመራሉ። በሐዋርያት ሥራ 8፡26 መልአኩ ፊሊጶስን ወደ ጋዛ እንዲሄድና ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ እንዲገናኝ ነገረው፤ ጃንደረባውም በፊልጶስ ስብከት በክርስቶስ አመነ። በሐዋርያት ሥራ 10፡3-7፥ መልአኩ ጴጥሮስ መጥቶ ለቆርኔሌዎስ ይሰብክ ዘንድ፥ ቆርኔሌዎስ ወደ ኢዮጴ መልእክት ልኮ እንዲያስጠራው ነገረው። በበለዓምና አህያው ታሪክ ውስጥ እንደ ተመለከተው፥ አንዳንድ ጊዜ መላእክት ሞኞች ሰዎች በኃጢአታቸው እንዳይቀጥሉ ይከለክላሉ (ዘኍል. 22፡21-28)።

4. መላእክት ክርስቲያኖችን ከሰብአዊና አጋንንታዊ አደጋዎች ይታደጋሉ። መዝሙር (34)፡7፥ «የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል፥ ያድናቸውማል» ይላል። መላእክት ሎጥንና ቤተሰቡን ከከፉ የሰዶም ሰዎች (ዘፍጥ. 19፡9-11) እና በኋላም ከከተማዪቱ ውድመት አድነውታል (ዘፍጥ. 19፡16)። መላእክት ኤልሳዕንና ባሪያውን ከሶርያውያን ጥቃት አድነዋል (2 ነገሥት 6፡17-18)። ለዳንኤል መልአክት ለማድረስ ቅዱሱ መልአክ ከርኩሱ መልአክ ጋር ተዋግቷል (ዳን. 10፡13፥ 20)።

ምናልባት አንዳንድ ሰዎች፥ ቅዱሳን መላእክት የእግዚአብሔርን ሕዝቦች በአንዳንድ ሁኔታዎች ሲታደጉ ለምን በሌሎች ሁኔታዎች ዝም እንደሚሉአቸው ሊጠይቁ ይችላሉ። ዳንኤል ከአንበሶች ሲተርፍ (ዳን. 6፡21-22)፥ ብዙዎቹ የቀድሞ ክርስቲያኖች ግን በሮም የመዝናኛ ስፍራ በአንበሶች ተቦጫጭቀው ተገድለዋል። የዕብራውያን መጽሐፍ፥ አንዳንድ የእምነት ጀግኖች በሚያስደንቅ ሁኔታ ከሞት እንዳመለጡና (ዕብ. 11፡32-35) ሌሎች ግን በመከራና በሞት እግዚአብሔርን እንዲያስከብሩ እንደ ተፈቀደላቸው ይነግረናል (ዕብ. 11፡36-37)። አንደኛው ቡድን ከሌላኛው የተሻለ አልነበረም። ለእነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች ምክንያቱን የሚያውቀው ጌታ ብቻ ነው። በዕብራውያን 11 የተጠቀሱትን እያንዳንዳቸውን የእምነት ጀግኖች በተመለከተ፥ ሰዎቹ ለሁኔታቸው በእግዚአብሔር ተግሥጸዋል። ስለ ሆነም፥ በተፈጸመው ነገር እግዚአብሔር ከብሯል። ዋናው መዋታችን ወይም መትረፋችን ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ብንኖርም ሆነ ብንሞት በሚሆነው

ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ከፍ ከፍ ማለቱ ነው። ጳውሎስም በፊልጵስዩስ 1፡19-21 ያስተማረው ይህንኑ ነው።

5. ብዙውን ጊዜ መላእክት እግዚአብሔር የጸሎትን መልስ የሚሰጥባቸው ወኪሎች ናቸው። የእግዚአብሔር መላእክት ለመሥራት ነፃ ቢሆኑም ባይሆኑም፥ ጸሎት አስፈላጊ ሚና እንዳለው ልብ ልንል ይገባል። ለዳንኤል ጸሎት ምላሽ በመሆን መልአኩ በቀጥታ ወደ ዳንኤል መጥቷል (ዳን. 10፡12)። ኢየሱስ በጌቴሰማኔ የአትክልት ስፍራ ላቀረበው የጣር ጸሎት ምላሽ በመሆን መልአኩ አበራትቶታል (ሉቃ. 22፡42-43)። መልአኩ ጴጥሮስን ለማዳን የመጣው ከቀድሞዪቱ ቤተ ክርስቲያን የአንድነት ጸሎት የተነሣ ነበር (የሐዋ. 12፡5፥ 7)። ለጸሎት ብንታክት፥ እግዚአብሔር በመላእክቱ አማካኝነት ሊልክ የሚችለውን እርዳታ መገደባችን ነው።

ምናልባት አንዳንድ አሳዛኝ ሁኔታዎች የሚፈጸሙት ሳንጸልይ በመቅረታችን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና . . . በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት» ይላል (1 ጴጥ. 5፡8-9)። የዲያብሎስን ጥቃት የምንከላከልበት አንደኛው መንገድ ጸሎት ነው። ባንጸልይ፥ ምናልባት ራሳችንን ከእግዚአብሔር መላእክት ጥበቃ ውጭ እንጥላለን። ስለ ሆነም መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ሳታቋርጡ ጸልዩ» (1 ተሰ. 5፡17)፤ «በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ» ሲል ይመክረናል (ኤፌ. 6፡18)።

6. መላእክት የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ስለ አንዳንድ ነገሮች በማስታወስና ከእግዚአብሔር ዘንድ መልእክት በማስተላለፍ ያገለግላሉ። መልአኩ ኤልያስን በማንቃት የተዘጋጀለትን ምግብ እንዲበላ ነግሮታል (1 ነገሥት 19፡5-7)። መልአኩ ገብርኤል ለዘካርያስ ስለሚወለደው ልጅ የሚገልጽ መልእክት አድርሷል (ሉቃ. 1፡11-20)። በኋላም፥ ገብርኤል ስለ ኢየሱስ መወለድ የሚገልጽ መልእክት ለማርያም አምጥቷል (ሉቃ. 1፡26-37)። መልአኩ በኢየሱስ መቃብር ለነበረች ሴት ከሞት የመነሣቱን ዜና አብስሯል (ማር. 16፡4-6)።

7. መላእክት፥ አማኞችን ከዚህ ሕይወት ሲሰናበቱ አጅበው ወደ መንግሥተ ሰማይ ያደርሷቸዋል። ለማኙ አልዓዛር በሞተ ጊዜ፥ መልአኩ ወደ አብርሃም እቅፍ መሰደው (ሉቃ. 16፡22)። ብዙ ክርስቲያኖች

ለመሞት ሲቃረቡ በአጠገባቸው ለሚገኙ ሰዎች ቅዱሳን መላእክት ሊወስዱአቸው እንደ መጡ መስክረዋል።

8. መላእክት የእግዚአብሔርን ፍርድ ያስፈጽማሉ። ሁለት መላእክት በሰዶምና ገሞራ ከተሞች ላይ ከሰማይ እሳትና ዲን በማምጣት አመድ አድርገዋቸዋል (ዘፍጥ. 19፡13)። እግዚአብሔር ዳዊት ሕዝቡን በመቁጠሩ ፍርድን ስላወረደበት፥ መልአኩ 70000 እስራኤላውያንን ፈጅቷል (2 ሳሙ. 24፡10-16)። በዚህ ዘመን መጨረሻ እግዚአብሔር በኃጢአተኞች ላይ በሚያወርደው የመጨረሻ ፍርድ፥ መላእክት ከፍተኛ ተሳትፎ አላቸው (ራእይ 8፣ 9፣ 16)።

9. መላእክት ክርስቶስ ሲመለስ አጅበውት ይመጣሉ። መላእክት በምድር ላይ ክፋትን የሚሠሩትን ሁሉ ሰብስበው በዘላለማዊ እሳት ውስጥ ይጥሉአቸዋል (ማቴ. 13፡41-42፣ 25፡41፥ 46)። መላእክት ከምድር ሁሉ የእግዚአብሔርን ምርጥ ቅዱሳን ይሰበስባሉ (ማቴ. 24፡31)።

10. መላእክት እግዚአብሔርን በማምለክ የሚደሰቱ ሲሆን፥ የእግዚአብሔር ሕዝቦች በምድር ላይ ጌታን ለማምለክ ሲሰባሰቡ ላይተባበሩዋቸው አይቀሩም (ማቴ. 28፡5-8፣ ራእይ 5፡11-14)።

ማጠቃለያ

መጽሐፍ ቅዱስ ሰብአዊ ፍጥረታት መልካምና ክፉ በሆኑና መላእክት ተብለው በሚጠሩ እጅግ በርካታ መንፈሳዊ አካላት እንደ ተከበቡ ያስተምራል። እነዚህ መናፍስት በአንዳንድ መንገዶች በአፍሪካ ባህላዊ እምነቶች ከተገለጹ መናፍስት ጋር የሚመሳሰሉ ቢሆኑም፥ መሠረታዊ ልዩነቶችም አሉአቸው። እነዚህ መላእክት ከሰው በላቀ የፍጥረት ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው። በጥንካሬ፥ በእውቀትና በሌሎችም አያሌ መንገዶች ከፍተኛ ኃይል አላቸው። መላእክት ሁሉ አንድ አይደሉም። መላእክት የተለያዩ ገጽታዎችና የተለያዩ የግዕረግና የሥልጣን ደረጃ ያላቸው እንጂ፥ ሁላቸውም አንድ ዓይነት አይደሉም። እንደ ኪሩቤልና ሱራፌል ሁሉ፥ የተለያዩ ኃላፊነቶች አሉአቸው። የተለያዩ የኃይል ደረጃዎች አሉአቸው። መላእክት የሞቱ ሰዎች መናፍስት አይደሉም።

ከሰዎች በተቃራኒ፥ የማይሞቱና በቁጥር የማይጨምሩ፥ ከጊዜ ጽንሰ-አሳብ ውጭ የሚኖሩ ፍጥረታት ናቸው። ምንም እንኳ ብዙውን ጊዜ

ተግባራቸውን በስውር ቢያከናውኑም፥ በተደጋጋሚ ከሰዎች ጋር ይዛመዳል። ቅዱሳን መላእክት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ያገለግሉ ዘንድ በእግዚአብሔር የሚታዘዙ ሲሆን፥ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ግን መላእክትን እንዳያመልኩ በጥብቅ ተከልክለዋል። ከሰዎች አምልኮ የሚጠይቁ ወይም ያመልኩአቸው ዘንድ አሳብ የሚሰነዝሩ መናፍስት የወደቁ መላእክት ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መናፍስት ዓለም እውነቱን እንደሚነግረን ግስታወስ አለብን። ስለ ሆነም፥ ስለ መናፍስት ዓለም የሚቀርቡ ሌሎች አሳቦች ሁሉ እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሰጠን መገለጥ ጋር መነጻጸር አለባቸው። ልንተበልና ልናምን የሚገባን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ መናፍስት የተገለጸውን እውነት ብቻ ነው፤ ይህ ካልሆነ በሰይጣን እንታለላለን።

በምዕራፍ 10 ላይ የተመሠረቱ የመወያያ ጥያቄዎችና መልመጃዎች

1. በአንዳንድ የአፍሪካ ባህላዊ ሃይማኖቶች ውስጥ በሚገኘው የተፈጥሮ አማልክት ጽንሰ-አሳብና መጽሐፍ ቅዱስ በሚገልጻቸው መላእክት መካከል የሚታዩትን ተመሳሳይነቶችና ልዩነቶች በመወያየት ተረዱ።

2. ቅዱሳን መላእክት ለክርስቲያኖች የሚሰጧቸውን ሰባት አገልግሎቶች ዘርዝራችሁ ተወያዩ።

3. በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያዩ፡-

ሀ) ሰዎች የመላእክትን ተግባራት ባብዛኛው እንዳይመለከቱ የተደረገው ለምን ይመስልሃል?

ለ) ሰዎች ባብዛኛው ከመላእክት ጋር እንዳይነጋገሩ የተደረገው ለምን ይመስልሃል?

ሐ) መላእክትና ሰዎች የሚመሳሰሉባቸውንና የሚለያዩባቸውን መንገዶች ዘርዝር።

4. ከፍሉን ከሥስት እስከ አራት የሚደርሱ አባላት በሚገኙባቸው ቡድኖች ከፋፍልና በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በመወያየት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ድጋፍ ያላቸውን መልሶች እንዲያዘጋጁ አድርግ፡-

ሀ) በዚህ ዘመን ሰዎች ከመላእክት ጋር እንዲያደርጉ የታቀደላቸው ምን ዓይነት ግንኙነት ነው?

ለ) በሰማይ በመላእክትና በሰዎች መካከል የሚኖረው ግንኙነት ምን ዓይነት ነው?

5. ከሦስት እስከ አራት የሚደርሱ አባላት በሚገኙባቸው ቡድኖች ላይ ተከፋፍላችሁ፥ ስለ መላእክት፥ ዳንኤል 10፡1-21ን መነሻ በማድረግና ከቀላል ወደ ውስብስብ እያደገ በሚሄድ የመጽሐፍ ቅዱስ የአጠናን ዘዴ (Inductive Bible Study) በመጠቀም የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡-

ሀ) የመላእክት ባሕርያት ምንድን ናቸው?

ለ) የመላእክት ኃይላት ምንድን ናቸው?

ሐ) መላእክት የእግዚአብሔርን ሕዝቦች የሚያገለግሉት እንዴት ነው?

መ) ሰዎች መላእክት ሲያጋጥሟቸው የሚያድርባቸው ስሜት ምን ዓይነት ነው?

ሠ) በዚህ ምንባብ ውስጥ በግልጽ የተጠቀሱ ቅዱሳንና የወደቁ መላእክት የትኞቹ ናቸው?

ረ) በእግዚአብሔር መላእክትና በሰይጣን መላእክት መካከል ያለው የባሕርይ ግጭት ምን ዓይነት ነው?

SUGGESTED FOR FURTHER READING

Graham, Billy. Angels - God's Secret Agents. London: Hodder, reprinted 1995.

Moreau, Scott. The World Of The Spirits: A Biblical Study In The African Context. Nairobi: Evangel Publishing House, 1990.

ምዕራፍ 11

የክፉት ምንጭና የሰይጣን ዘዴዎች

አንድ በአፍሪካ አገር የሚታተም ጋዜጣ አያሌ ሰዎች ስለ ሞቱበትና ስለ ተነዱበት አስከፊ የመኪና አደጋ ዘግቦ ነበር። በማግሥቱ ደግሞ ለዚህ አደጋ መንስዔው በመኪናውና በተሳፋሪዎቹ ላይ እርግማን በማውረዱ መሆኑን አንድ ቡድን በይፋ አስታወቀ። ለመሆኑ ይህ ቡድን እንዲህ ዓይነት ክፉ ዕቅድ ሊፈጽም የቻለው በምን ኃይል ነው?

ሰዎች በሌሎች ላይ ኃዘንና ጉዳት ስለሚያስከትሉ ጠንቋዮችና አስማተኞች የክፋት ኃይል በትክክል ያውቃሉ። እንዲሁም አስከፊ ነገሮችን ለመፈጸም በምሥጢር የሚሰባሰቡ ኅብረተሰቦች እንዳሉ እናውቃለን። እነዚህ ሰዎች በቀኑ የፀሐይ ብርሃን ወቅት ጨዋ የሥራ ሰዎች ሊመስሉ ቢችሉም፥ በምሽት ግን እጅግ የከፉ ነገሮችን ያደርጋሉ። ሰዎች እንዲህ የከፉ ተግባራትን እንዲያከናውኑ የሚያንቀሳቅሳቸው ማን ነው?

በዓለም ውስጥ ክፋት የሚታየው ለምንድን ነው? አጽናፈ-ዓለሙ የተፈጠረው በሁለመናው መልካምና ቅዱስ በሆነው አምላክ ከሆነ፥ ቀድሞ ነገር ክፋት ከየት መነጨ? በዚህ ምዕራፍ በሚከተሉት አሳቦች ላይ እንነጋገራለን፦

ሀ. የክፋት ምንጩ ምንድን ነው?

ለ. ሌሎች መላእክት በሰይጣን ዓመፅ ውስጥ እንዴት ሊሳተፉ ቻሉ?

ሐ. የአሁኑን የዓለም እሴቶች ዘይቤ የሚቆጣጠረው ማን ነው?

መ. ክርስቲያን ያልሆኑ ሃይማኖቶች ምንጭ ምንድን ነው?

ሠ. አጋንንት ምንድን ናቸው?

ረ. እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ የአጋንንት ሥራዎች ምንድን ናቸው?

ሀ. የክፋት ምንጩ ምንድን ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ፥ የሰው ልጅ በምድር ላይ ከመታየቱ ረዥም ዓመታት በፊት በእግዚአብሔር ላይ ስለ ተፈጸመው ዓመፅ አስደንጋጭ ዘገባ

አለው። ይህም ዘገባ በአጽናፈ-ዓለም የክፋትን ምንጭና ዛሬ ዓለም በክፋት ለምን እንደምትሠቃይ ሊያስረዳ ይችላል።

በሕዝቅኤል 28፡11-18 በቀዳሚነት ለጢሮስ ንጉሥ የቀረበ መልእክት ተጽፎአል። ይሁንና፥ ከፍሉን በጥንቃቄ ስናጠና የታሪኩ ዋንኛ ተዋናይ የጢሮስ ንጉሥ ሊሆን እንደማይችል እንረዳለን። ለምሳሌ በሕዝቅኤል 28፡13 ያ የተቀጠሰው ሰው «በእግዚአብሔር ገነት በዔድን» እንደ ነበረና ፍጡርም እንደ ነበረም ይገልጻል። መጽሐፍ ቅዱስ በዔድን ገነት የነበሩት እግዚአብሔር፥ አዳም፥ ሔዋንና ሰይጣን ብቻ እንደ ነበሩ ይናገራል። በሕዝቅኤል 28፡14 ና 16 የተጠቀሰው ሰው ኪሩብ፥ ማለትም አንድ የመላእክት ዓይነት እንደ ሆነ ተገልጸአል። ከእነዚህ ፍንጮች ስንነሣ፥ በሕዝቅኤል 28፡11-18 የተገለጸው እውነተኛው አካል በምድራዊ ንጉሥ ተምሳሌትነት የቀረበ መልአክ ነው። በጢሮሱ ምድራዊ ንጉሥና በመልአኩ መካከል የሚገኘው ተመሳሳይነት የትዕቢት ችግር ነው።

እንደ ታሪኩ አገላለጽ፥ እግዚአብሔር ከፈጠራቸው መላእክት አንዱ የእግዚአብሔርን ዙፋን እንደሚጠብቅ ይታወቃል (ሕዝ. 28፡14)። ይህ መልአክ በጣም ውብና ጠቢብ ሆኖ ቢፈጠርም፥ ከትዕቢት የተነሣ ተበላሸ (ሕዝ. 28፡17)። በአዲስ ኪዳን፥ መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያው ጳውሎስ በኩል ሰይጣን የወደቀውና የተኮነነው በትዕቢቱ ምክንያት እንደ ሆነ ገልጾአል (1 ጢሞ. 3፡6)። ምንም እንኳ በምንባቡ ውስጥ በስሙ ባይጠቀስም፥ ከዚህ አንጻር ስናየው፥ በሕዝቅኤል 28፡11-18 የተገለጸው ትክክለኛው አካል ሰይጣን እንደ ሆነ ለመረዳት ጠንካራ መረጃ እናገኛለን።

ይህ መልአክ እንዴት በትዕቢት ሊዋጥ ቻለ? እንደ ታሪኩ አገላለጽ፥ በተፈጠረ ጊዜ እግዚአብሔር ስለ ሰጠው ታላቅ ውበትና ጥበብ ያስብ ጀመር (ሕዝ. 28፡13፥ 17)። ምናልባትም ከእግዚአብሔር ይልቅ ስለ ራሱ ብዙ በማሰቡ ታበየ። ትዕቢቱም እያደገ ሲሄድ፥ እግዚአብሔርን በማምለክ ፈንታ ራሱን ያመልክ ጀመር። ክርስቶስ ከሰይጣን ጋር በምድረ በዳ ካደረገው ተግዳሮት (ማቴ. 4፡1)፥ የሰይጣን እውነተኛ ፍላጎት እግዚአብሔር (ክርስቶስ) እንዲያመልከው እንደ ሆነ እንረዳለን (ማቴ. 4፡9)! ሰይጣን በትዕቢቱ ምክንያት ለአእምሮ ንክነት የተጋለጠ ይመስላል። ፈጣሪውን እግዚአብሔርን በማምለክ ፈንታ፥ የተፈጠረውን እርሱን እግዚአብሔር እንዲያመልከው ፈለገ!

በኢሳይያስ 14፡12-14 ከሕዝቅኤል 28፡11-18 ጋር በጣም የሚመሳሰል ምንባብ አለ። ይህ ምንባብ ለባቢሎን ንጉሥ የተጻፈ ሲሆን፥ አሁንም ተመሳሳይ ፍላጎት ያለውንና ከባቢሎን ንጉሥ የላቀውን አካል ያመለክታል። በኢሳይያስ 14፡12 ሰውዬው ሉሲፈር፥ «የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ» ተብሏል። ይህም ሉሲፈር መላእክትን ሁሉ ለመግዛትና ራሱን እንደ እግዚአብሔር ለማድረግ እንደሚፈልግ ገልጾአል (ኢሳ. 14፡13-14)። ሕዝቅኤል 28፡11-18 እና ኢሳይያስ 14፡12-14 ስለ አንድ መልአክ፥ ማለትም ስለ መልአኩ ሰይጣን የሚናገሩ ይመስላል።

ምናልባት ሰይጣን ምን ያህል የከበረ፥ ጠቢብ ፍጥረት እንደ ሆነና እንደ እግዚአብሔርም አምልኮና መሪነት እንደሚገባው አስቦ ይሆናል። ምናልባት የእግዚአብሔር መላእክት እግዚአብሔርን ከማምለክና ከመከተል ይልቅ ለምን እርሱን እንደማያመልኩትና እንደማይከተሉት አስቦ ይሆናል። ይህ እውነት ከሆነ፥ ኢሳይያስ መልአኩ ለራሱ፥ «ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ፥ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ በልዑልም እመሰላለሁ» (ኢሳ. 14፡13-14) እንዳለ ሊጽፍ፥ የሰይጣንን ውስጣዊ አሳቦች መግለጹ ነበር። ከትዕቢቱ የተነሣ፥ ይህ መልአክ በእግዚአብሔር ላይ ለማመፅ ዕቅድ ወጠነ።

ሰይጣን በትዕቢቱና በእግዚአብሔር ላይ ለማመፅ በጥንቃቄ ባተደው ውሳኔ ክፋትን ለአጽናፈ-ዓለሙ ያስተዋወቀ ይመስላል። ትዕቢት ሌሎች ኃጢአቶች ሁሉ ያቆጠቆጡበት ሥር ነበር። ለምን? ምክንያቱም ትዕቢት እኔነትን በማስቀደም፥ በእግዚአብሔር ላይ ወደ ማመፅ ኃጢአት ስለሚመራ ነው። በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ ሰውን ከእግዚአብሔር ሕይወትና ቅድስና ያርቀዋል። እግዚአብሔር የሕይወት፥ የበጎነትና የቅድስና ሁሉ ምንጭ ነው። የሕይወትም አለመኖር ሞትን፥ የበጎነት አለመኖር ክፋትን፥ የእግዚአብሔር ቅድስና ጉድለት ኃጢአትን ያስከትላል። የሰይጣን ዓመፅ ክፋትና ኃጢአት በአጽናፈ-ዓለም እንዲስፋፋ አመቺ ሁኔታዎችን ፈጥሯል። ስለ ሆነም የሰይጣን ትዕቢትና ኩራት ክፋትና ሞት እንዲገኝ አድርጓል።

ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ለማመፅ የመሰደው የታቀደ ምርጫ በታሪክ እጅግ የከፋ ክስተት ነው። እግዚአብሔር የሕይወት፥ የመልካምና የቅድስና ሁሉ ምንጭ ነው። ሰይጣን ለማመፅ ሲመርጥ፥ ራሱን ከእግዚአብሔር ለየ። ይህንን በማድርጉም፥ በቅድስናና በበጎነት ሊያኖረው ከሚችል ብቸኛ አምላክ ራሱን ለይቷል። የሰይጣን ውሳኔ ራስን የሚያጠፋ

ክፉ ተግባር ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ትዕቢት ውድቀትን ይቀድማል» የሚለው ለዚህ ነው (ምሳሌ 16፡18)። እንደ ሰይጣን ከእግዚአብሔር ይልቅ ራሳቸውን ለማምለክ የሚፈልጉ ሞኞች፥ በመጨረሻ እንደ ሰይጣን ራሳቸውን ያጠፋሉ። በተጨማሪም፥ ከሰይጣን ጋር በሲኦል ይሠቃያሉ (ማቴ. 25፡41)።

ሰይጣን ከእግዚአብሔር ቅድስናና ሕይወት ርቆ ክፋትንና ብልሹነትን ተሞላ፤ መንፈሳዊ ሞትም ደረሰበት። ይህ እንዴት እንደ ተፈጸመ ለመረዳት የሚከተለው ቀላል ግብራሪያ ይረዳን ይሆናል። የግንባ ፍሬ ከዛፉ ቅርንጫፍ ጋር አብሮ እስካለ ድረስ ውብና ጣፋጭ ፍራፍሬ ወደ መሆን ያድጋል። ከቅርንጫፉ ሲለይ ግን ሕይወትን ከሚሰጠው የዛፉ ክፍል ይቆረጥና የመበስበስን ሳዳና ይይዛል። ከጥቂት ጊዜ በኋላም መጥፎ ሽታ ማውጣት ይጀምራል። በመጨረሻም ሙሉ ለሙሉ ይሞትና ሕይወት ወደሌለው ቆሻሻነት ይለወጣል። ይህ የመበስበስና የመሞት ሂደት ሕይወት ባላቸው ነገሮች ሁሉ ላይ ከሕይወት ሕልፈት በኋላ የሚደርስ ነው።

በመንፈሳዊው በኩልም፥ በሰይጣንና ከእርሱ ጋር ባመፁ መላእክት ሁሉ ላይ የደረሰው ይኸው ነው። ሕይወት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታ ሲሆን፥ ከእግዚአብሔር መለየት ሞትን ያስከትላል። ሰይጣንና ዓመፀኛ መላእክት ከእግዚአብሔር ሕይወትና ቅድስና ሲለዩ፥ ሙሉ ለሙሉ ክፉዎችና ብልሹዎች ይሆናሉ። የሰዎችም በአዳምና ሔዋን ኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር መለየት እንደዚሁ ነው። በእግዚአብሔር ላይ ከተፈጸመው ኃጢአትና ዓመፃ የተነሣ፥ ዓለም በከፍተኛ ውድቀት ውስጥ ነች። ኢየሱስ ጠላታችን የሆነው ሰይጣን የውሸት አባትና ነፍሰ-ገዳይ እንደ ሆነ ጓልጹአል (ዮሐ. 8፡44)። ይህ አሳብ ሰይጣን በትዕቢቱና በገዛ ምርጫው በእግዚአብሔር ላይ በማመፅ ያስከተላቸውን አስከፊ ውጤቶች ይገልጻል።

አሁን የሰይጣን ዓይነተኛ ፍላጎት ሰዎችን እያታለለ ማጥፋት ነው (1 ጴጥ. 5፡8)። እርሱም የእግዚአብሔር ሕዝቦች፥ የመልካምና የቅዱስ ነገር ሁሉ ጠላት ሆኗል። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ሳያውቅና ሳይፈቅድ ምንም ሊያደርግ ባይችልም (ኢዮብ 1፡6-19፤ 2፡1-6፤ ሉቃ. 22፡31)፥ ሰዎችን ሁሉ ለማጥፋት የሚችለውን ጥረት ሁሉ ያደርጋል። ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም በሚመለስበት ጊዜ፥ ሰይጣን ወደሚያቃጥል የዲን ባሕር ይጣልና ለዘላለም በዚያ ይሠቃያል (ራእይ 20፡10)። የዘላለሙ እሳት

ለሰይጣንና ለወደቁት መላእክቱ መቀጣጫ ይሆን ዘንድ ተፈጥሯል (ማቴ. 25:41)።

እስካሁን ከቀረበው አሳብ፥ እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለምን ትዕቢትን እንደሚጠላ ደጋግሞ እንደ ተናገረ ግልጽ ሊሆን ይገባል (ምሳሌ 6:16-17፤ 8:13)። እግዚአብሔር ትዕቢት ከውድቀት እንደሚቀድም ተናግሯል (ምሳሌ 16:18)። በመጀመሪያ ክፋት በሰይጣን አማካኝነት ወደዚህች አጽናፈ-ዓለም የገባው ከትዕቢት የተነሣ ነው። ፈሪሳውያን ክርስቶስን እንደ መሢሕ ያልተቀበሉትና ለግድያው ያሤሩት ከትዕቢት የተነሣ ነው (ማቴ. 26:4፤ ዮሐ. 7:1)። ኢየሱስ እነዚህ ፈሪሳውያን የሰይጣን ልጆች እንደ ሆኑ ገልጾአል (ዮሐ. 8:44)። ከሲኦል ፍርድም እንደማያመልጡ አስረድቷል (ማቴ. 23:33)። ዛሬም ሰዎች ከእግዚአብሔር ተመልሰው፥ በራሳቸው የሞኝነት መንገድ ወደ ጥፋት የሚሄዱት በትዕቢት ምክንያት ነው።

ለ. ሌሎች መላእክት በሰይጣን ዓመፅ ውስጥ እንዴት ሊሳተፉ ቻሉ?

ሌሎች መላእክት እንዴት እንዳመፁ ለጥቂት ጊዜ መመልከቱ ተገቢ ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንኑ ጉዳይ በቀጥታ ባይገልጽልንም፥ አንዳንድ ፍንጮችን ይሰጠናል። ምናልባት እንደ ሰይጣን ሁሉ እነርሱም ታብየው ይሆናል። ምናልባትም በሰይጣን ምክር፥ እግዚአብሔር ከሰጣቸው የበለጠ ስፍራ ለመያዝ ፈልገው ይሆናል።

የሌሎች መላእክት መውደቅ በ2ኛ ጴጥሮስ 2:4፤ ይሁዳ 6 እና ራእይ 12:4 ተጠቅሶአል። በራእይ 12:4 ዘንዶው (ማለትም ከራእይ 12:9 ጋር በመነጻጸር የምንመለከተው ሰይጣን) ሊሶዎቹን ከዋክብት (መላእክት) ይዞአቸው ወድቋል። ከሰማይ መላእክት ሊሶዎቹ በሰይጣን ዘዴ ተጠምደው በእግዚአብሔር ላይ በግመፅ ሳይታለሉ አይቀሩም። የቀድሞዎቹ የአይሁድ ሃይማኖት መምህራን በይሁዳ 6 እና 2ኛ ጴጥሮስ 2:4 የተጠቀሰውን የመላእክት ዓመፅ በዘፍጥረት 6:1-4 ከተገለጹ ክስተቶች ጋር አያይዘውታል። በዚህ ስፍራ «የእግዚአብሔር ልጆች» «ከሰዎች ሴቶች ልጆች» ጋር ሲጋቡ እንመለከታለን። ከኢዮብ 1:6፤ 2:1 እና 38:7 አንጻር፥ የእግዚአብሔር ልጆች የተባሉት መላእክትን ሊያመለክቱ ይችላሉ። ይህ እውነት ከሆነ፥ እነዚህ ጋብቻዎች በወደቁት መላእክትና በሰዎች መካከል የተፈጸሙ ሕገ-ወጥ ግንኙነቶች ናቸው፤ ውጤታቸውም

እጅግ የከፋ ትውልድና ሕዝብ ማሰገኘት ነበር። በዘፍጥረት 6:4-5 የተጠቀሰውም ይኸው ሊሆን ይችላል። ይህም እግዚአብሔር ከኖኅ ቤተሰብ በቀር ለምን ሕዝቡን ሁሉ በጥፋት ውኃ ሊያወድም እንደ ፈለገ ያብራራል።

ምናልባት አንድ ሰው ሰይጣን እንዴት እግዚአብሔርን በተሳካ ሁኔታ ሊቃወም እንደሚችል እንዳሰበ ይጠይቅ ይሆናል። መልሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባይቀርብልንም፥ የዳዊት ልጅ ከሆነው አቤሴሎም ታሪክ ውስጥ ፍንጭ እናገኛለን። አቤሴሎም የገዛ አባቱ የሆነውን ንጉሥ ዳዊትን ለመፈንቀል ሞከረ። የአቤሴሎም ዘዴ የሰዎችን ትኩረት የሚስቡ የተስፋ ቃሎችን በመስጠት፥ የእስራኤላውያንን ልብ መማረክ ነበር (2 ሳሙ. 15:3-6)። በሕዝቅኤል 28:16 ሰይጣን ይህንኑ የሚመስል ነገር እንዳደረገ የሚገልጽ አሳብ አለ። በተጨማሪም፥ አቤሴሎም እስራኤላውያን የዳዊትን ባሕርይ እንዲጠራጠሩ አደረገ (2 ሳሙ. 15:4)። ሰይጣንስ መላእክትን የእግዚአብሔርን ባሕርይ እንዲጠራጠሩ በተመሳሳይ ዘዴ ተጠቅሞ ይሆን? በመሠረቱ በዔድን ገነት ሔዋን የእግዚአብሔርን ባሕርይ እንድትጠራጠር እንደ ጣረ እውን ነው (ዘፍጥ. 3:3-5)። ምናልባት ሰይጣን የበቂ መላእክትን ልብ ከማረከ፥ ውሎ ሲያድር እግዚአብሔርን የሁሉንም መላእክት ታማኝነት ሊያሳጣው እንደሚችል አስቦ ይሆናል።

ሰይጣን በዓመፃ በወደቁት መላእክት ላይ የተጠቀመው ዘዴ፥ በዔድን ገነት በሰው ላይ ከተጠቀመው ዘዴ ጋር ተመሳሳይ ሳይሆን አይቀርም። በዔድን ገነት የሰይጣን ዘዴ ስለ እግዚአብሔር የተሳሳቱና ውሸተኛ አሳቦችን በማቅረብ አዳምንና ሔዋንን ከታዛዥነት ወደ አለመታዘዝ መምራት ነበር (ዘፍጥ. 3:4-6)።

ለእግዚአብሔር ዙፋን ቅርብ ሆኖ በመቆየቱ፥ ሰይጣን ከእኛ በላይ እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ሁሉ የነበረውን ታላቅ ፍቅር ሳይገነዘብ አይቀርም። የእግዚአብሔር ፍቅር እንደማይለወጥ በትክክል ያውቅ ነበር። ምናልባትም ለፍጥረቱ ካለው ፍቅር የተነሣ፥ እግዚአብሔር እርሱና ሌሎችም መላእክት ቢያምፁ፥ ይመልሳቸው ዘንድ አስከፊ ኃይል እንደማያጠቀም አስቦ ይሆናል።

እግዚአብሔር የፍጥረታቱን ታዛዥነት ለማግኘት በጭካኔ እርምጃ እንደማይጠቀም እውነት ነው። እርሱ ስለ ፈጠርን፥ በራሳችን ምርጫ እንድንወደው ይፈልጋል (ዘዳግ. 6:5)። እርሱን መታዘዝ ለእኛ እንደሚበጅ እግዚአብሔር ያውቃል (ዘዳ. 6:24)። በልባችን እንደ ፈጣሪያችን

በግመስገን እንድንወደውና ኅብረት እንድናደርግ ይሻል። በግድ ሳይሆን፥ ለግንኙቱ እንድንወደው ይፈልጋል። ሰብአዊ መላእኮች ከልጆቻቸው ተመሳሳይ የውዴታ ታዛዥነትን ሲሹ፥ የእግዚአብሔርን ልብ ያንጸባርቃሉ። እነርሱን እንደ መላእኮቻቸው አድርገው ለመውደድና ለመታዘዝ ቢመርጡ ለልጆቻቸው መልካም እንደሚሆንላቸው ያውቃሉ።

ሐ. የአሁኑን የኅሊም አሴቶች ዘይቤ የሚቆጣጠረው ማን ነው?

ከወደቁት ታላቅ የመላእክት ሠራዊት ጋር በመሆን፥ ሰይጣን በዚህ ዓለም ስውር የኅመፅ እንቅስቃሴ አቋቁሟል። ባሁኑ ጊዜ ከርስቶስ ሰይጣን የዚህ ዓለም «አለቃ» ብሎ ሲጠራው (ዮሐ. 12:31፤ 16:11)፥ ጳውሎስ ደግሞ የዚህ ዓለም «አምላክ» ይለዋል (2 ቆሮ. 4:4)። በዚህ ችሎታው የአሁኑን ዓለም ፣ አሴቶች ዘይቤ ይቆጣጠራል። የአሁኑ ዓለም አሴቶች ዘይቤ በሰይጣንና በሌሎችም ክፉ መላእክት ሥር ስለ ሆኑ፥ ከርስቲያኖች ዓለምን እንዳይወዱ (እንዳይመኙ) ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸዋል። ዓለምን ቢወዱ፥ የእግዚአብሔር አብ ፍቅር አይኖራቸውም (1 ዮሐ. 2:15)። የአሁኑ ዓለም ሥርዓት በትዕቢት፥ በራስ ወዳድነት፥ በሥጋ ምኞት እና በዓይን አምሮት፥ ብሎም በስግብግብነት ላይ የተመሠረተ ነው (1 ዮሐ. 2:16)።

ሰይጣን ዲያብሎስ ተብሎ የተጠራ ሲሆን፥ ትርጉሙም (የእግዚአብሔርን ሕዝቦች) የሚከስ ወይም የሚያሳጣ ማለት ነው። ሰይጣን የእግዚአብሔርን ሕዝቦች እግዚአብሔር ባለበት ስፍራ ሳይቀር ይከሳል (ኢዮብ 1:8-11፤ 2:3-5፤ ራእይ 12:10)። ምናልባትም ይህንኑ የሚያደርገው፥ ከፍትሐዊ ባሕርዩ የተነሣ እግዚአብሔር በሚወዳቸው ሕዝቡ ላይ ቅጣትን እንዲያመጣ ይሆናል (ዕብ. 2:2፤ 10:26-27)። በተጨማሪም፥ ሰይጣን «ከፋው» (ማቴ. 13:19)፥ «ፈታኙ» (ማቴ. 4:3)፥ እንዲሁም «የአየር ላይ አለቃ» ተብሎ ተጠርቷል (ኤፌ. 2:2)።

ከታሪክም ሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንረዳው፥ ሰይጣን የሕዝቦችን ብሔራዊ መንግሥታትንም አስተዳደር ለማበላሸት ኃይሉን ሊጠቀም እንደሚችል የሚጠቁም አሳብ ቀርቦአል (ዳን. 10:13፥ 20)። ክፉ መላእክት ሕዝቦችንና ነገሶችን ለክፉ ዓላማዎች ለማነሣሣት መሻታቸው የማይቀር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን ክፉ መላእክት በኤፌሶን 6:12 «የክፋት መንፈሳዊ ኃን ሠራዊት» ሲል፥ በቆላስይስ 2:15 «አለቅነትና

ሥልጣናት» ይላቸዋል። የአጋንንታዊ ተጽዕኖ መረጃ በአንዳንድ ባህላዊ ሃይማኖቶች ክፉ ልምምዶችና በአንዳንድ መንግሥታት አጋንንታዊ ባሕርይ ውስጥ ሊታይ ይችላል። የዚህ ጎይነቱ ባሕርይ በ20ኛው ክፍለ ዘመን በ2ኛው የዓለም ጦርነት የጀርመኑ የናዚ መንግሥት 6 ሚሊዮን አይሁዶችን በጨፈጨፈበት የግፍ ተግባር፥ በቀድሞዱቱ ዩጎዝላቪያ በተካሄደው የጎሳ ፍጅት፥ ብሎም በሩዋንዳ በተከሰተው የጎንድ መተራረድ ታይቷል። የናዚ መንግሥት ክፉ መሪ የነበረው ሒትለር በስውር ከአስማት አዋቂዎች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ከሰይጣናዊ አሠራር ጋር የጠበቀ ትስስር ነበረው።

ከላይ ከቀረበው አሳብ፥ የዚህ ዓለም መንግሥታት ከሰይጣን በታች የዓለምን ሥርዓት እሴቶች በሚቆጣጠሩ በርካታ የክፉ መላእክት ሠራዊት ተጽዕኖ እንደሚሠሩ ተረድተናል። ይህም ሆኖ፥ ሙሉ ለሙሉ እግዚአብሔርን የሚታዘዙና ከክፉዎቹ እጅግ የላቁ ቅዱሳን መላእክት፥ በዚህ ክፉ ዓለም ውስጥ የሚኖሩትን የእግዚአብሔርን ሕዝቦች የመጠበቅ ሥራ ተሰጥቶአቸዋል [መዝ. (103)፡20-21፤ ዕብ. 1፡14]። ይህም እግዚአብሔርን ለሚወዱት ሁሉ ታላቅ ማበረታቻ ሊሆን ይገባል።

መ. ክርስቲያን ያልሆኑ ሃይማኖቶች ምንጭ ምንድን ነው?

ክርስቲያን ያልሆኑ ሃይማኖቶች በአያሌ ምክንያቶች ሳቢያ በዓለም ላይ ሊከሰቱ በቅተዋል። ዋንኛዎቹ ምክንያቶች ምናልባትም ከምትሐታዊ እምነቶችና ከመሐይምነት የመነጩ፣ እውነታን በትክክል ያለ መገንዘብ ችግሮች ይሆናሉ። እነዚህ የተሳሳቱ አሳቦች በሰይጣንና አጋንንት አታላይ ውሸቶች አማካኝነት ለሰዎች አእምሮ ሊተላለፉ ቆይተዋል (1 ጢሞ. 4፡1)።

ይሁንና፥ ልክ ብርሃን ጨለማን እንደሚገፍ፥ እውነትም ምትሐትንና መታለልን ትገፋለች። ለዚህም ነው ኢየሱስ፥ «እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም» ያለው (ዮሐ. 8፡12)። ኢየሱስ ስለ እውነት ሊመሰክር ስለ መጣ (ዮሐ. 18፡37)፥ የዓለም ብርሃን ነበር። ጳውሎስ ለአሕዛብ ወንጌልን በመስበክ «የጋጢአትንም ስርየት በእኔም (በኢየሱስ) በማመን በተቀደሱት መካከል ርስትን ያገኙ ዘንድ፥ ከጨለማ ወደ ብርሃን ከሰይጣንም ሥልጣን ወደ እግዚአብሔር ዘወር እንዲሉ ዓይናቸውን ይከፍት ዘንድ» በኢየሱስ እንደ ተጠራ ይናገራል (የሐዋ. 26፡18)።

በብሉይ ኪዳን፥ እስራኤላውያንን የከበቡ አሕዛቦች በስም የሚያውቋቸው ወንዶችና ሴቶች አማልክት (ጣዖታት) ነበሯቸው። ለምሳሌ፥ ሞዓባውያን ካሞሽ የሚሉትን ጣዖት ሲያመልኩ፥ ሶርያውያን ሞሎክ ብለው የሚጠሩትን ጣዖት ያመልኩ ነበር (1 ነገሥት 11፡7)። ፍልስጤኤማውያን ዳጎን ብለው የሚጠሩትን የእርሻ (የምርት) ጣዖት ያመልኩ ነበር (መሳ. 16፡23)። ሲዶናውያን አስታሮት የተባለች የለምነት ጣዖት ያመልኩ ነበር (1 ነገሥት 11፡5)። አሞራውያን ናሳራክ የሚሉትን ጣዖት ያመልኩ ነበር (2 ነገሥት 19፡36-37)። እነዚህ መናፍስት ብዙውን ጊዜ እንደ የሰው መሥዋዕት (ኤር. 32፡35) እና ወሲባዊ ብልግናን የመሳሰሉትን ከፉ ልምምዶች ይጠይቁ ነበር (ኤር. 2፡20፣ ሕዝ. 16፡25)። እያንዳንዱ ጎሳ የሚያመልከውና የሚታዘዘው አንድ ወይም ከዚያ የበለጡ ባህላዊ መናፍስት የነበሩት ይመስላል። እግዚአብሔርም ራሱ እነዚህን አረማዊ መናፍስት የእነዚህ የእያንዳንዳቸው ሕዝቦች የተወሰኑ «አማልክት» አድርጎ ይገልጻቸዋል (1 ነገሥት 11፡33)።

አብዛኛዎቹ ሰዎች እነዚህ አማልክት የአረማውያን ጣዖታትና ምትሐቶች እንጂ ምንም እንዳልሆኑ ሊያስቡ ቢችሉም፥ እግዚአብሔር ግን እነዚህን በጣዖታት የተወከሉትን ባህላዊ አማልክት እንደ አጋንንት ቆጥሮአቸዋል። አንዳንድ እስራኤላውያን ሊከተሉት ስለ ጀመሩት ሞሎክ ስለ ተባለ የአሞናውያን አምላክ (ኤር. 32፡25) እግዚአብሔር የሚለውን ልብ በል፦ «ከአሕዛብም ጋር ተደባለቁ፥ ሥራቸውንም ተማሩ። ለጣዖቶቻቸውም ተገዙ፥ ወጥመድም ሆኑባቸው። ወንዶች ልጆቻቸውንና ሴቶች ልጆቻቸውን ለአጋንንት ሠዉ» [መዝ. (106)፡35-37]። በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር ለሞሎክ የሰው መሥዋዕት በግልጽ፥ እስራኤላውያን ለአጋንንት ይውጪ እንደ ነበር ይገልጻል። እግዚአብሔር ከምትሐታዊ የጣዖት አምልኮ በስተኋላ ያለውን አጋንንታዊ ምንጭ ይገልጻል።

ከክርስቶስ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ወደሌሉአቸው ሕዝቦች የሚሄዱ ሚሲዮናውያን፥ በተለይም በመጀመሪያዎቹ የአገልግሎት ጊዜዎቻቸው፥ ብዙውን ጊዜ ከአጋንንት ጋር ከፍተኛ ግጭት እንደሚፈጥሩ ይዘግባሉ። ይህም አጋንንት፥ በተለይም ሃይማኖትን በተመለከተ ረገድ በሰዎች ላይ ተጽዕኖ ወይም ቁጥጥር ለማድረግ እንደሚሹ የሚያስረዳውን አሳብ ይደግፋል። መጽሐፍ ቅዱስ አጋንንታዊ ምንጭ ስላላቸው አሳቦችና እምነቶች ይናገራል (1 ጢሞ. 4፡1)። ከዚህም በላይ፥ ሰይጣን (እና

አጋንንቱም) ሊመለኩ ይሻሉ (ማቴ. 4፡9)። እግዚአብሔር ግናቸውንም ዓይነት የአረማውያንን ሃይማኖት ልምምዶች በጥብቅ የሚያወግዝበት አንዱ ምክንያት ይኸው ነው (ዘዳግ. 18፡9-12)። እግዚአብሔር በዘዳግም 32፡16-17፥ «በሌሎች አማልክት አስቀኑት፥ በርኩሰታቸውም አስቆጡት። እግዚአብሔር ላልሆኑት አጋንንት ... ሠዉ» ይላል። «ከእኔ በቀር ሌሎች አምላክት አይሁኑልህ» ለሚለው የመጀመሪያው ትእዛዝ መሰጠት ምክንያቱ ይኸው ነው (ዘጸ. 20፡3)።

ባህላዊ አፍሪካውያን የተወሰኑ መናፍስት ከሚቆጣጠሩአቸው ሰዎች ሥርዓታዊ አምልኮንና ታዛዥነትን እንደሚጠይቁ ያውቃሉ። አንዳንድ ጊዜ እነዚህ መናፍስት እነዚህኑ ጥያቄዎች ይዘው በአካል ሊገለጹላቸው፥ በሌላ ጊዜ በሕልም፥ በሌላ ጊዜ ደግሞ በያዙት ሰው ወይም በሞራ ገላጭ አማካኝነት የሚፈልጉትን ነገር ይገልጻሉ። መረጃው ሁሉ ክርስቲያን ያልሆኑ ሃይማኖቶች ሁሉ ከጨለማው ሰይጣናዊ ኃይሎች ጋር እንደሚተባበሩ ያመለክታል።

ክርስቲያን ያልሆኑ ሃይማኖቶች ምንጭ ምትሐታዊ እምነትንና መሐይምነትን ያካትታል። በተጨማሪም፥ ሰዎች እንዲያመልኩአቸው የሚፈልጉና ሕይወታቸውንም ለመቆጣጠር የሚሹ (ማቴ. 4፡8-9) የወደቁ መላእክት የሚገኙበት ይመስላል (1 ጢሞ. 4፡1ን ከቆላ. 2፡18 ጋር አስተያይ)። ብዙ አፍሪካውያን እንደሚያውቁት፥ ክፉ መናፍስት የማይታዘዙአቸውን ሰዎች በሕመም፥ በኃዘንና በሌሎችም ቅጣቶች እንደሚያሠቃዩ ይዝታሉ።

እንዲህ ዓይነቶቹ መናፍስት በማታለል ዘዴያቸው በጣም ብርቱዎች ናቸው። አማልክት ወይም የሞቱ ቅድመ-ትውልዶች መናፍስት መስለው በመቅረብ ሰዎችን ያታልላሉ። ሰዎችም አማልክትንና የቀድሞ ዘመዶቻቸውን መናፍስት ማክበር ስለሚገባቸው፥ እነዚህ አሳሳች መናፍስት የሚጠይቁአቸውን ሁሉ በታዛዥነት ያደርጋሉ። በእንደዚህ ዓይነት መናፍስት ስለ መሳሳት እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰጣቸውን ማስጠንቀቂያ ተመልከት፡- «አባቶቻቸውም የተከተሉት ሐሰታቸው አስቶአቸዋልና» (አሞጽ 2፡4)። ለቅድመ-ትውልዶች መናፍስት የሚሰጠው ትኩረት ክርስቲያናዊ ባልሆኑ ሃይማኖቶች ውስጥ በዓለም በብዙ ስፍራዎች እንደሚገኝ መረዳቱ ተገቢ ነው። ሰዎች ለቅድመ-ትውልዶቻቸውና ለዘመዶቻቸው ከፍተኛ ስሜታዊ ቁርኝት ስላላቸው፥ ይህ የሚያስደንቅ

አይሆንም። የቅድመ-ትውልዶችን መናፍስት እገዛ የሚሹ ባህላዊ ሃይማኖቶች በጎሰኛ ሁኔታ ሰዎችን የሚያሳስት ተመሳሳይ የእምነት ዘይቤ ይገልጻሉ። እንዲህ ዓይነት እምነቶች ብዙ ሰዎችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ግላዊ የሚያድን ግንኙነት እንዳያደርጉ አግደዋቸዋል።

ኢየሱስ ወንጌሉ ለሕዝቦች ሁሉ እንዲዳረስ ግዘዙ ጠቃሚ ነው (ማቴ. 28፡19)። በዚህ ስፍራ ሕዝቦችን ለመግለጽ ያገለገለው «ኤትኔ» (ethne) የሚለው ቃል በቀዳሚነት ተመሳሳይ ባህልና ቋንቋ ያላቸውን ሰዎች ያመለክታል። በምድር ላይ የክርስቶስ የማዳን ፅቅድ እንዲፈጸም ከተፈለገ፥ ሰይጣን በእያንዳንዱ ነገዳዊ ቡድን ላይ የሚኖረው ቁጥጥር በወንጌሉ ኃይል መወገድ አለበት። ስለ ሆነም፥ ሰዎችን በምድር ላይ ከሚገኙ የሕዝብ ወገኖች ሁሉ ደቀ መዝሙር ማድረጉ የቤተ ክርስቲያን ቀዳሚ ተግባር ነው። በመጨረሻ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰዎች ከነገድ፥ ከቋንቋና በምድር ላይ ከሚገኙ ወገኖች ሁሉ መካተት አለባቸው (ማቴ. 28፡19፤ ራእይ 5፡10፤ 7፡9)። ከእያንዳንዱ የነሳ ቡድን አማኞች ደቀ መዛሙርት እስኪሆኑ ድረስ ታላቁ ተልዕኮ ከዳር አይደርስም።

ሠ. አጋንንት ምንድን ናቸው?

አጋንንት (ክፉ መናፍስት) በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተጠቅሰዋል። እነዚህ ክፉ መናፍስት እነማን ናቸው? አንዳንድ ባህላዊ ሃይማኖቶች፥ ክፉ መናፍስት ከረዥም ዘመናት በፊት የሞቱና ክፉ ባሕርይ የነበራቸው ቅድመ-ትውልዶች መናፍስት ናቸው ይላሉ። መጽሐፍ ቅዱስስ ምን ይላል?

በምዕራፍ ስድስት፡ እግዚአብሔር በሞት ጊዜ የሙታንን መናፍስት ከሕያዋን እንደሚለይ ተመልክተናል። ከሞት በኋላ፥ የሰዎች ነፍሳት እግዚአብሔር ባስቀመጣቸው ስፍራ ተወስነው ይኖራሉ (ሉቃ. 16፡19-31)። ስለ ሆነም፥ ከረዥም ዘመናት በፊት የሞቱት ቅድመ-ትውልዶች መናፍስት ሰዎችን ለማወክ ወይም ተጽዕኖ ለማሳደር ክፉ መናፍስት ሆነው በዙርያችን እንደሚያንጎራበቡ የሚገልጸው አሳብ የመጽሐፍ ቅዱስ ድጋፍ አያገኝም። በሥጋዊ ሞት ዙርያ የሰፈሩትን ምሥጢራት በትክክል ሊገልጽልን የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ እንጂ የባሕላዊ ሃይማኖት ትምህርት ስላልሆነ፥ ይህንን አሳብ መረዳት አስፈላጊ ነው። እግዚአብሔር እነዚህን ምሥጢራት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ገልጾልናል።

ስለ አጋንንት ማንነትና ከየትም እንደ መጡ አያሌ ጽንሰ-አሳቦች ይቀርባሉ። በምዕራፍ 10 መላእክት የተለያየ ደረጃ ያላቸው መንፈሳዊ ፍጡራን እንደ ሆኑ ተረድተናል (ቆላ. 1፡16)። በተጨማሪም፥ ብዙ መላእክት እንዳመፁ ተመልክተናል (ራእይ 12፡4)። ስለ አጋንንትና ስለ መጡበትም ስፍራ ከሚነገሩት የተለያዩ አሳቦች ይበልጥ ትክክለኛ የሚመስለው፥ አጋንንት ከሰይጣን ጋር በእግዚአብሔር ላይ ካመፁ የወደቁ መላእክት እንደ መጡ የሚያስረዳው ነው። በማቴዎስ 12፡24 ፈሪሳውያን ክርስቶስ አጋንንትን የአጋንንት አለቃ በሆነው በብዔልዙቡል እንደሚያስወጣ በመግለጽ ከሰውታል። በማቴዎስ 12፡26 ኢየሱስ፥ «ሰይጣንም ሰይጣንን የሚያስወጣ ከሆነ . . . እንግዲህ መንግሥቱ እንዴት ትቆማለች?» በማለት መልሶአል። በዚህ ስፍራ ኢየሱስ ሰይጣንን የአጋንንት አለቃ አድርጎ ያቀርበዋል። የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት አጋንንትን በሚያወጡበት ዓውድ ክርስቶስ ሰይጣንን ከሰማይ እንደ ወደቀ በሚገልጽበት በሉቃስ 10፡17-18 ተመሳሳይ አሳብ ይገኛል። በመጨረሻም፥ በራእይ 12፡7 ሰይጣንና መላእክቱ ከሚካኤልና ከመላእክቱ ጋር እንደሚዋጉ ተገልጾአል። ምንም እንኳ ስለዚህ ጉዳይ ሙሉ ለሙሉ እርግጠኞች ልንሆን ባንችልም፥ እነዚህ ጥቅሶች አጋንንት ከወደቁት መላእክት ደረጃዎች እንደ መጡ ያሳያሉ።

የአጋንንት ክፉ ባሕርያትና ሥራዎቻቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ ተርዷል። አሁን እንደ ተመለከትነው፥ ሰይጣን ገዥአቸው ነው (ማቴ. 12፡24-26)። ብለ ሆነም፥ በሰይጣንና በአጋንንት ሥራዎች መካከል በቂ ልዩነት አናገኝም። እግዚአብሔር ፈቃዱን ለማስፈጸም ቅዱሳን መላእክትን እንደሚጠቀም ሁሉ፥ ሰይጣንም ፈቃዱን ለማስፈጸም አጋንንትን ይጠቀማል።

ረ. እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ፥ የአጋንንት ሥራዎች ምንድን ናቸው?

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አጋንንት ሥራዎች ብዙ ይናገራል። በዚህ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ መጽሐፍ መጻፍ ይቻላል። በዚህ መጽሐፍ አጋንንት የሚያከናውኗቸውን የሥራ ዓይነቶች ብቻ ጠቅለል አድርገን እናቀርባለን። በምዕራፍ አሥራ ሦስት ሰይጣን ክርስቲያናዊ ያልሆኑ ሃይማኖቶች የሚከተሉትን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችና አንዳንድ ክርስቲያኖች የሚያሳስትባቸውን አያሌ መንገዶች በዝርዝር እንመለከታለን።

የአጋንንት አሠራር ዓይነቶች

ማታለል፡- ምናልባት በዓለም እጅግ የተስፋፋው የአጋንንት ሥራ መዋሸትና ሰዎችን ማታለል ነው። የአጋንንት ሥራዎች ልክ እንደ መሪያቸው ሰይጣን ሥራ ዓይነቶች ናቸው። ኢየሱስ ሰይጣን የውሸት አባት እንደ ሆነ ገልጾአል (ዮሐ. 8፡44)። አጋንንትም ደግሞ በመዋሸት ሰዎች ውሸትን እንዲያምኑ ለማድረግ ይጥራሉ። ይህንንም ልክ ሰዎች እውነተኛ ወይም ሐሰተኛ አሳቦችን ሊለዋወጡ እንደሚችሉ ሁሉ፥ ለሰዎች ውሸተኛ አሳቦችን በማስተላለፍ ያከናውናሉ። አጋንንት የውሸት አሳቦችን ወደ አእምሮአችን ሲያስተላልፉ፥ ራሳችን ያሰብነው ነገር እንደ ሆነ አድርገን ልንቆጥር እንችላለን። አሳቡ የመጣው ከአእምሮአችን ውጭ ከሚገኝ ምንጭ እንደ ሆነ ላናስብ እንችላለን። ከዚህ የተነሣ መጽሐፍ ቅዱስ ለክርስቶስ ለመታዘዝ አሳባችንን ሁሉ በምርኮኛነት እንድናስረክብ ያስጠነቅቀናል (2 ቆሮ. 10፡5)። ይህንንም የምናደርገው አሳባችንን ሁሉ በእግዚአብሔር እውነት በመገምገም ነው። እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚናገረው አሳብ ጋር ይስማማል ወይስ ይቃረናል? ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚስማማ ከሆነ ልንቀበልና የማይስማማ ከሆነ ደግሞ ልንተወው ይገባል።

ብዙ ጊዜ የአጋንንት ውሸቶች የስሜት ድክመት ወደሚታይባቸው ሰዎች አእምሮ ይወነጨፋሉ። በከባድ ችግር ውስጥ ሳለህ ብዙውን ጊዜ ወደ አእምሮህ የሚመጣውን ውሸት አዳምጠህ ይሆን? ይህም ውሸት እግዚአብሔር እንደማይወድህና ለችግሮችህም ግድ እንደሌለው የሚገልጽ ይሆናል። እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ህልቆ መሳፍርት በሌለው ሁኔታና ግንም ሰው ሌላውን ሰው ወዶ በማያውቅበት ልክ ስለሚወድ፥ ይህ አሳብ ከእርሱ ዘንድ ሊመጣ አይችልም። ስለ ሆነም፥ እንዲህ ዓይነቱ አሳቦች አንድም ከራሳችን የኃጢአት ተፈጥሮ ካልሆነም ከአጋንንት መምጣት አለባቸው። ከሁለቱም ምንጮች የሚመጡትን አሳቦች ገለል አድርገን የእግዚአብሔርን እውነት ልንይዝ ይገባል። የእግዚአብሔር እውነት ምንድን ነው? መጽሐፍ ቅዱስ፥ «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና» ይላል (ዮሐ. 3፡16)። በብሉይ ኪዳንም እግዚአብሔር በዘላለም ፍቅር እንደ ወደደን ይናገራል (ኤር. 31፡3)። ምንጩ ምንም ይሁን እግዚአብሔር እንደማይወደን የሚናገረው አሳብ ውሸት ነው።

የውሸት ሃይማኖቶች ትምህርቶችን የመሳሰሉት አንዳንድ አጋንንታዊ ውሸቶች፥ ብዙ ሰዎችን ለማሳሳት የሚላኩ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ አጋንንት የሐሰት ትምህርትን እንደሚያስፋፉ ይገልጻል (1 ጢሞ. 4፡1)። በአፍሪካ ብዙ ሰዎች በባህላዊ ሃይማኖት የውሸት አሳቦችና እግዚአብሔር ተናግሮናል በሚሉ ሐሰተኛ ነቢያት ተታልለዋል። እንደ 1ኛ ነገሥት 22፡22፥ በሐሰተኛ ነቢያት የሚነገረው የማታለል ንግግር ከሐሰተኛ መናፍስት ሊመጣ ይችላል። በብዙ የዓለም ክፍሎች የሐሰት ሃይማኖትን በተመለከተ፥ አንደኛው ውስን ጉዳይ ከቅድመ-ትውልዶች እምነት ጋር የተያያዘ መሆኑ ነው። በምዕራፍ አሥራ ሦስት በዚህ ጉዳይ ላይ የበለጠ ግብራሪያ እናቀርባለን።

አጋንንት ሰዎችን ለማታለል በተቆጣጠሩት ሰው አንደበትም ውሸተኛ ቃላትን ሊናገሩ ይችላሉ። ሰዎችን ከእግዚአብሔር እውነት የሚያርቁ የውሸት እምነቶችን ለማስፋፋት ሲሉ ይዋሻሉ። ለምሳሌ፥ መንፈሱ ከዚህ በፊት የነበረ ሰው ነፍስ እንደ ሆነ በማስመሰል በሰው ውስጥ ሆኖ ሲናገር ስለሚሰሙ፥ አንዳንድ ሰዎች ስለ ሰው ነፍሳት ቅድመ-ህላዌ እርግጠኞች ናቸው። መንፈሱ ቀድሞ ስለ ነበረው ሰው ሕይወት ትክክለኛ ዝርዝር ጉዳዮችን ሊናገር ይችላል። ይሁንና፥ መንፈሱ እንደማይዋሽ በምን እናውቃለን? እውነቱ ግን የዚህ ዓይነቱ መንፈስ ሰዎችን ለማታለል እንደሚዋሽ ነው፤ ምክንያቱም መሪያቸው ሰይጣን የውሸት አባት ነው (ዮሐ. 8፡44)። በዚህም ምክንያት በአጋንንት በተያዘ ሰው አንደበት የሚነገረው የመንፈስ ቃል ሊታመን አይችልም። ስለ ሆነም፥ ሰዎችን ከተቆጣጠረና በአፋቸውም ከሚናገር ክፉ መንፈስ ጋር መነጋገሩ ዋጋ የለውም። የውሸቶቹ ኃይል ከፍተኛ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል

የነፍስ ግድያ፡- ኢየሱስ ሰይጣን ነፍሰ-ገዳይ እንደ ሆነ ገልጾአል (ዮሐ. 8፡44)። ስለ ሆነም፥ ምኞታቸውን ለመፈጸም ከቻሉ አጋንንት ጭካኔ የተሞላበትን ሥጋዊ ጉዳትና ሞት እንደሚያስከትሉ መገንዘብ አለብን። አጋንንት ወደ ሰዎች አእምሮ ካስተላለፉአቸው አሳቦች የተነሣ በታሪክ ውስጥ ምን ያህል የነፍስ ግድያ፥ የነገድ ጦርነቶች፥ የሃይማኖት ጦርነቶችና ብሔራዊ ጦርነቶች እንደ ተደረጉ ስንመለከት እንደነቃለን። በወንጌላት ውስጥ በጌርጌሴኖን በአጋንንት የተያዘው ሰው ሰውነቱን በድንጋይ ይቆራርጥ እንደ ነበር እንመለከታለን (ማር. 5፡5)። አጋንንት የያዘውን ልጅ ወደ ውኃና እሳት ውስጥ በመወርወር ሊገድለው ሲሞክር እናያለን (ማር.

9፡22)። በኢዮብም ላይ ሰይጣን ወይም አንዳንድ አጋንንቱ ኃይለኛ ዐውሎ ነፋስ በማስነሣት አሥር ልጆቹን ገድለዋል (ኢዮብ 1፡12፥ 19)።

በአፍሪካ በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ እንደ ቀረበው ታሪክ፥ በርግማን ምክንያት መከራ፥ ኃዘን ወይም ሞት የደረሰባቸው ብዙ አጋጣሚዎች አሉ። ያለ ጥርጥር አጋንንት በእንዲህ ዓይነቶቹ አሳዛኝ ጉዳዮች ውስጥ ይሳተፋሉ። ኢየሱስ ተከታዮቹ፥ «ከክፉ አድነን» ብለው እንዲጸልዩ ያስተማረበት በጣም አስፈላጊው ምክንያት ይኸው ነው (ማቴ. 6፡13)። ሰዎች መናፍስትን ይፈራሉ። የመናፍስት ሁሉ ጌታ ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በመንፈሳዊ ሁኔታ ካልተጣመሩ፥ መናፍስትን ለመፍራት በቂ ምክንያት አላቸው። ክርስቲያኖች ክርስቶስን እንደ ጌታና አዳኝ አድርገው ሊቀበሉት የሚገባው ለዚህ ነው። ሰዎች ከሰይጣንና ክፉ መናፍስት ፍርሃት ሊላቀቁ የሚችሉት፣ ክርስቶስ እንደ ጌታቸውና አዳኛቸው የማዳን ኃይል እንዳለው የሚያሳየውን እውነታ ተረድተው ሲቀበሉ ብቻ ነው።

ሥቃይ፡- መግደል ባይሆንላቸው፥ አጋንንት ሰዎችን እንደ ዕውርነት፥ ዲዳነት (ማቴ. 12፡22)፥ አካለ ስንኩልነት (ሉቃ. 13፡11-17)፥ ሥጋዊ ሕመም (ኢዮብ 2፡7፤ የሐዋ. 10፡38)፥ የአእምሮ መታወስ (ሉቃ. 8፡27-29) በመሳሰሉ ጥቃቶች ሊያሠቃዩ ይችላሉ። ዛሬ በአእምሮ ሕክምና ሆስፒታሎች በአጋንንታዊ እብደት የሚሠቃዩ ምን ያህል ሰዎች ናቸው? የእግዚአብሔርን እውነት ከማመንና ከመታዘዝ ይልቅ የአጋንንትን ውሸቶች በማመናቸውና በመታዘዛቸው፥ በምሬት፥ በጥላቻ፥ በጭንቀት፥ ከእግዚአብሔር ጋር በመጣላትና በሌሎችም የአእምሮ ሕመሞች የሚሠቃዩ ምን ያህል ሰዎች ናቸው?

የወሲብ ግድፈትና ጭካኔ፡- ክፉ መናፍስት ብዙውን ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ርኩስ መናፍስት ተብለው ተገልጸዋል። ለርኩስ ያገለገለው የግሪክ ቃል (አካታርቶስ) ሲሆን በሥርዓታዊ መንገድም ይሁን ወይም በግብረ-ገባዊ ይዞታው ያልጸዳ፥ ወሲባዊ ግድፈት ያለበት ወይም ጨካኝ የሚል ትርጉም ይሰጣል። በአዲስ ኪዳን፥ ቃሉ በቀዳሚነት ያገለገለው አጋንንትን እንደ ጨካኝ፥ ክፉ፥ ወይም ወሲባዊ ምግባረ-ብልሹ አድርጎ ለመግለጽ ነው (ማቴ. 10፡1፤ ማር. 1፡23፤ 7፡25፤ ኤፌ. 5፡5)። በራእይ 17፡4፥ ከዚህ ጋር በቅርብ የተቆራኘ የግሪክ ቃል (አካታርቲስ) በግልጽ ወሲባዊ ግድፈትን ከዝሙት ጋር አዛምዶ ለማሳየት አገልግሏል። አስገድዶ በመድፈር ወንጀል ውስጥ እንደሚታየው ሁሉ፥ ወሲባዊ ግድፈትና የክፉ

ጭካኔ ብዙውን ጊዜ ጎን ለጎን ይሄዳሉ። ጭካኔ የሞላባቸውና ቀዝቃዛ የመሲብ ግንኙነቶች የሚስተዋልባቸው ትርዒቶች ብዙውን ጊዜ በሲኒማ ኢንዱስትሪ ፊልሞች ውስጥ አብረው ይታያሉ። ይህም የርኩስ አጋንንትን ተፅእኖ በግልጽ ያሳያል።

በመጽሐፍ ቅዱስ የአጋንንትን ወሲባዊ ግድፈት በተመለከተ፥ ኢየሱስ ሴትኛ አዳሪ ከነበረችው መግደላዊት ማርያም ሰባት አጋንንቶችን አንዳስወጣ ልብ በል (ሉቃ. 8፡2)። ንጉሥ ሰሎሞን ከጪህ ሚስቶቹና ቁባቶቹ ጋር በወሲብ እንደ ተጠመደ ግልጽ ነው (መክ. 2፡8)። ይህም ሰሎሞን ለሲዶናዊቱ የለምነት ሴት አምላክ አስታሮት በሚደረገው አረማዊ አምልኮ ተሳታፊ በመሆንና ጣዖት በመሥራት፥ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን ከፈጸመበት ሁኔታ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል (2 ነገሥት 23፡13)።

ወሲባዊ ግድፈት፣ አጋንንታዊ አሳብና ፈተና ከሰው ኃጢአተኛ ልብ ሙሉ ትብብር የሚያገኝበት አንዱ የሕይወታችን ክፍል ነው። ያለ ጥርጥር የዛሬው የሰሜን አሜሪካና የአውሮፓ የወሲብ ባህል ዝቅጠት አጋንንታዊ ነጸብራቅ ይታይበታል።

በመንግሥታት ላይ የሚያስከትሉት ተጽዕኖ፡- በዳንኤል 10፡12-21 ለወደቁት መላእክት ከተሰጡት ስሞች ለመረዳት እንደሚቻለው አጋንንት መንግሥታትን ለክፉ ዓላማዎች ለመለወጥና ለመቆጣጠር እንደሚጥሩ ግልጽ ነው (ራእይ 16፡14)። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «የዚህ ዓለም አምላክ (ሰይጣን) የማያምኑትን አሳብ አሳወረ» ይላል (2 ቆሮ. 4፡4)። ለዚህ ነው በግልጽ ለመንግሥት ባለሥልጣናት እንድንጸልይ የታዘዝነው (1 ጢሞ. 2፡2)። የእግዚአብሔር ሕዝቦች ጸሎቶች የእነዚህን መሪዎች አእምሮ ሰይጣንና አጋንንት ከሚያቀርቡዋቸው ጠንካራ ምክሮች ለማንጻት ይረዳሉ። አእምሮአቸው ከሰይጣን አሳቦች ሲጸዳ፥ እነዚህ መሪዎች በአግባቡ እንዲያስተዳድሩ ጥበብ የሚሰጣቸውን የመንፈስ ቅዱስ የጥህ ድምፅ ይሰማሉ። መሪዎቹ ክርስቲያኖችም ይሁኑ ዓለማውያን፥ ለእነርሱ ከመጸለይ ስንቦዝን በራሳችን ላይ ጉዳት እናመጣለን።

ለወንጌሉ ስርጭት እንቅፋት መፍጠር፡- በ1ኛ ተሰሎንቄ 2፡18 ጳውሎስ ለክርስቶስ ያደርግ የነበረውን ጉዞ ሰይጣን እንዳገደ ገልጾአል። አንድ ሰው በወንጌሉ ሥራ ላይ ሲሰማራ ከፉ መናፍስት አጥብቀው እንደሚታወሙት ለመረዳት ብዙ ጊዜ አይፈጅበትም (ኤፌ. 6፡12)። ስለ ሆነም፥ የወንጌሉ

አገልግሎት እንዲሳካ ከተፈለገ፥ ቋሚ፥ መደበኛና የታማኝነት ጸሎት በፍጹም አስፈላጊ ነው።

ጸሎትን ማገድ፡- አጋንንት የእግዚአብሔርን አገልጋዮች ከሚታወሙባቸው እጅግ አስፈላጊ መንገዶች አንዱ ለጸሎታቸው መልስ እንዳይመጣ ማገድ ወይም ማዘግየት ነው። ጸሎት ውድቀታቸውን ስለሚያፋጥን፥ አጋንንት ጸሎትን አጥብቀው ይቃወማሉ። ክፉው መልአክ ለዳንኤል ጸሎት የተሰጠውን መልስ እንዴት እንደ ተቃወመና ሐዋርያት ኢየሱስ በጌቴሴማኔ አብረውት እንዲጸልዩ በጠየቃቸው ጊዜ በእንቅልፍ እንደ ተወሰዱ ልብ በል (ዳን. 10፡12-13፤ ማቴ. 26፡38-43)።

ባጠቃላይ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ማወክ፡- አጋንንት በተቻላቸው ዓቅም ሁሉ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ማወክ፥ ማሠቃየት፥ መረበሽ፥ ማስጨነቅና ተስፋ ማስቆረጥ ሥራዬ ብለው ይወጡታል። ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮንቶስ 12፡7 የሰይጣን መልእክተኛ የጭንቀቱ ምንጭ እንደ ሆነ ገልጾአል። ኢየሱስ ሰይጣን ጴጥሮስን እንደ ስንዴ ሊያበጥረው እንደ ፈለገ ተናግሯል (ሉቃ. 22፡31)።

የጣዖት አምልኮን፥ ጥንቆላንና የተለያዩ አረማዊና ምትሐታዊ ልምምዶችን ማስፋፋት፡- እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ፥ የጣዖት አምልኮ ከአጋንንታዊ አሠራር ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው [መዝ. (106)፡35-37]። አጋንንት ሰዎች ባህላዊ መሥዋዕቶችን፥ ከሙታን ጋር መነጋገርን፥ ሞራ ገላጭነትን፥ ጥንቆላንና ሌሎች እያሌ ነገሮችን ጨምሮ፥ በተለያዩ ክርስቲያናዊ ባልሆኑ ልምምዶች ውስጥ እንዲሳተፉ በመገፋፋቱ ተግባር ላይ እንደ ተሰማሩ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል (ዘዳ. 18፡9-12፤ 32፡16-17፤ 1 ሳሙ. 15፡23፤ ራእይ 18፡2)። ጠንቋዮችና አስማተኞች የሚጠቀሙበት ከፉ መንፈሳዊ ኃይል ከእግዚአብሔር ዘንድ ሰለማይመጣ ከአጋንንት መመንጨቱ የማይቀር ነው።

እንግዳ ክስተቶችንና አሳሳች ተአምራትን መሥራት፡- የሰው ልጅ ታሪክ፥ ሳይንስ ጭምር ማብራሪያ ሊሰጥባቸው በማይችላቸው እንግዳ መንፈሳዊ ክስተቶች የተሞላ ነው። ዕቃዎች በቤት ውስጥ እጅ ሳይነካቸው ይንቀሳቀሳሉ። መናፍስት ከመታየት አልፈው ለማስታወሻነት በፎቶግራፎች ተቀርጸዋል፤ ያለ ምንም እሳት ዕቃዎችና ሰዎችም ሳይቀሩ ተቀጣጥለዋል። በመንፈስ ቁጥጥር ሥር የሚገኙ ሰዎች በጥንካሬው የታወቀውን የ«ስቲል» ብረት እንደ ማጠፍ፥ ወይም ከ1000 ድግሪ ፋራናይት የበለጠ የሙቀት

መጠን ባለው የሚያቃጥል ምድጃ ላይ በባዶ እግራቸው እንደ መጓዝ የመሳሰሉትን አዳጋች ተግባራት ያለ ምንም ችግር አከናውነዋል። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? መጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣንና አጋንንቱ አሳሳች ተአምራት ለመፈጸም የሚያስችል ኃይል እንዳላቸው ይገልጻል (2 ተሰ. 2፡9፤ ራእይ 16፡13-14)። ኢየሱስ ሰዎች በእርሱ አምነው ይድኑ ዘንድ ተአምራትን እንደ ፈጸመ ሁሉ (ዮሐ. 5፡36፤ 10፡38)፥ ሰይጣንና አጋንንቱም ሰዎችን ለማሳሳትና የእግዚአብሔርን እውነት ከማመን ለመከላከል ሲሉ ተአምራትን ይሠራሉ።

ክርስቲያኖችን በእግዚአብሔር ፊት መክሰስና ማማት፡- ሰይጣን ክርስቲያኖችን በእግዚአብሔር ፊት በከፍተኛ ደረጃ እንደሚከሳቸውና እንደሚያማቸው ሁሉ (ራእይ 12፡10)፥ አጋንንትም ምናልባት መረጃ በማሰባሰብ እንደሚረዱት ልንገምት እንችላለን (ሮሜ 8፡33፥ 38-39)።

ማጠቃለያ

መልካምና ቅዱስ የሆነው አምላክ አጽናፈ-ዓለሙን ፈጥሯል። በዚህም ውስጥ፥ እጅግ በርካታ መላእክትን የፍጹም ፍጥረቱ አካል አድርጎ ፈጥሯል፤ እነርሱም በተፈጠሩ ጊዜ ቅዱሳንና መልካሞች ነበሩ። እነዚህ መላእክት ከፍተኛ እውቀትና የምርጫ ነፃነት የነበራቸው ነፃ ፍጥረታት ነበሩ። ከእነዚህ መላእክት ለእግዚአብሔር ዙፋን ቅርብ የነበረውና ኪሩብ የተባለው መልአክ በውበቱ፥ በጥበቡና በአስፈላጊነቱ በመወጠር፥ በሌሎች መላእክት ፊት ከእግዚአብሔር ጋር ወደ መስተካከሉ ደረጃ ለመሻገር ወሰነ። በዚህም ተግባሩ የሌሎችን መላእክትና ሰዎች ልብ ከእግዚአብሔር ያሸፈተ ይመስላል።

ራሱን የበጎነትና የቅድስና ብቸኛ ምንጭ ከሆነው እግዚአብሔር በለየ ጊዜ፥ በትዕቢቱ ምክንያት በማመፅ፥ ሙሉ ለሙሉ ብልሹ፥ ክፉና ጨካኝ ሆነ፤ ልክ እንደ እግዚአብሔርም ሊመለክ ፈለገ። በዚህም ሉሲፈር ማለትም ሰይጣን፥ እግዚአብሔር ፍጹማዊ አድርጎ በፈጠረው አጽናፈ-ዓለም ውስጥ ክፋትን በማምጣት፥ የእግዚአብሔርና የሕዝቡ ጠላት ሆነ። በተጨማሪም፥ ሰይጣን ሌሎች መላእክት በእግዚአብሔር ላይ ባስነሣው ዓመፅ ውስጥ እንዲካፈሉ አደረገ። ይህ የወደቁት መላእክት ቡድን በዓለም የማይታይ የዓመፅ እንቅስቃሴ መሥርቷል። ክርስቲያናዊ ያልሆኑ ሃይማኖቶች ከተመሠረቱባቸው ምክንያቶች አንዱ አጋንንት የውሸት አሳቦችን ለሰዎች በማስተላለፋቸው ነው።

ከወደቁት መላእክት አንዳንዶቹ ዛሬ በዓለም በከፍተኛ ደረጃ የሚሠሩ አጋንንት ሆነው ይታያሉ። አጋንንት ኃይላቸውን ሌሎችን ለመጉዳት ለሚጠቀሙ እንደ ጠንቋዮችና አስማተኞች ላሉ ክፉ ሕዝቦች መንፈሳዊ ኃይል ይሰጣሉ። ዛሬ የአጋንንት ሥራ በሃይማኖታዊ ማሳሳቻ፥ በዓለም አቀፍ የወንጀል (በተለይም የግድያ) መበራከት፥ በወሲባዊ ግድፈት፥ በአንዳንድ መንግሥታት ውስጥ በሚከሰት ሙስናና ሽብር፥ በጠንቋዮችና አስማተኞች ጥንካሬ፥ ክርስቲያኖች የጌታን ሥራ ሲያከናውኑ በሚጋፈጡአቸው ተቃውሞዎችና በዓለም ውስጥ በሚታዩ ሌሎች አያሌ ክፋቶች ተለይቶ ይታወቃል። ስለ ሆነም፥ ኢየሱስ «ከክፉ አድነን» ብለን እንድንጸልይ አስተምሮናል (ማቴ. 6፡13)።

ከዚህ የላቀ የእግዚአብሔር ቅዱሳን መላእክት ሠራዊት የእግዚአብሔርን ልጆች ለመጠበቅና ለመርዳት ስለ ተመደበ፥ ክርስቲያኖች በዚህ በዓለም ውስጥ በሚሠራው የመናፍስት ሠራዊት ምክንያት ተስፋ መቁረጥ የለባቸውም። በተጨማሪም፥ በእያንዳንዱ አማኝ ልብ ውስጥ እግዚአብሔር (መንፈስ ቅዱስ) ስላለ፥ በዚህ ከማንኛውም ርኩስ መንፈስ በላይ ኃይለኛ በሆነው የእግዚአብሔር መንፈስ ሊተማመኑ ይገባል። ክርስቲያኖች በክርስቶስ የተቀዳጁትን ክብር ሲረዱ፥ በጸሎታቸውና መንፈሳዊ የጦር ዕቃዎችን በመልበስ የአጋንንትን ክፉ ሥራ በተሳካ ሁኔታ ሊታወሙ ይችላሉ።

በምዕራፍ 11 ላይ የተመሠረቱ የውይይት ጥያቄዎችና መልመጃዎች

1. የሰይጣንን ልብ ወደ ሌሎች ኃጢአቶች ሁሉ የመራው የትኛው ኃጢአት ነበር? የመጽሐፍ ቅዱስ ማጣቀሻ አቅርብ።

2. እንደ ኢሳይያስ 14፡13-14 አገላለጽ፥ በሉሲፈር ልብ ውስጥ የነበረው ዕቅድ ምን ነበር?

3. በዔድን ገነት የሰውን ልጅ ለማጥፋት የሰይጣን ዘዴ ምን ነበር?

4. መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ትዕቢት ውድቀትን ይቀድማል» ይላል (ምሳሌ 16፡18)። በቡድን ተከፋፍላችሁ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡-

ሀ. ትዕቢት ወደ ውድቀት የሚመራው እንዴት ነው?

ለ. በአፍሪካ ከትዕቢት ጋር ሊያያዙ የሚችሉ የክፋት ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው?

ሐ. በሳሰኝነትና ትዕቢት መካከል ያለው ግንኙነት ምንድን ነው?

5. ሰይጣንን የምንዋጋባቸው መንፈሳዊ የጦር ዕቃዎች የትኞቹ ናቸው?

6. በቡድኑ ለአንድ ሳምንት የዓለምን ዜና ተከታተሉ። ከዚያም የሰይጣንንና የክፉ መላእክትን ሥራ የሚያንጸባርቁትን ክስተቶች ለይታችሁ አውጡ።

7. የአሁኑ የዓለም ሥርዓት የተመሠረተባቸው ክፉ እሴቶች የትኞቹ ናቸው?

8. ዲያብሎስ «የወንድሞቻችን ከሳሽ» ተብሎ ተጠርቷል (ራእይ 12:10)። ዲያብሎስ በእግዚአብሔር ፊት የሚከሰን ስለምንድን ነው? እንደ 1ኛ ዮሐንስ 1:9 አገላለጽ፥ ክርስቲያን ስለዚህ ኀይነቱ ክስ ምን ሊያደርግ ይችላል?

9. ክርስቲያናዊ ያልሆኑ ሃይማኖቶች የሚታዩት ለምንድን ነው?

10. በሳሳ ቡድኖች ተከፋፈሉ። እያንዳንዱ ቡድን በራሱ ነገድ ባህላዊ ሃይማኖት ውስጥ የሚገኙትንና ከአጋንንት የመጡ የሚመስሉትን እምነቶች ለይቶ ለማውጣት ይሞክር።

11. በአናሳ ቡድኖች ተከፋፈሉና እያንዳንዱ ቡድን የሚችለውን ያህል የአጋንንትን የማታለያ ዘዴዎች ይዘርዝር።

12. ከፍሉ በሙሉ፥ የአጋንንት ፍርሃት በአፍሪካ ምን ያህል ሥር እንደ ሰደደና እንደ ተስፋፋ ይመያይ። ክርስቲያን ለዚህ ኀይነቱ ፍርሃት ምላሽ ሊሰጥ የሚገባው እንዴት ነው?

SUGGESTED FOR FURTHER READING

Green, Michael. I Believe in Satan's Downfall. London: Hodder, 1995

Hillstrom, Elizabeth L. Testing the Spirits. Downers Grove: Inter Varsity Press, 1995.

Koch, Kurt. Occult Bondage And Deliverance.Grand Rapids, Michigan: Kregel, 1986.

ምዕራፍ 12

መንፈሳዊ ውጊያ

«ወደ ባሕር ማዶም ወደ ጌርጌሴኖን አገር መጡ። ከታንኳዪቱም በወጣ ጊዜ፥ ርኩስ መንፈስ የያዘው ሰው ከመቃብር ወጥቶ ወዲያው ተገናኘው እርሱም በመቃብር ይኖር ነበር፥ በሰንሰለትም ስንኳ ማንም ሊያስረው በዚያን ጊዜ አይችልም ነበር ብዙ ጊዜ በእግር ብረትና በሰንሰለት ይታሰር ነበርና ዳሩ ግን ሰንሰለቶቹን ይበጣጥስ እግር ብረቱንም ይሰባብር ነበር፥ ሊያሸንፈውም የሚችል አልነበረም፤ ሁልጊዜም ሌሊትና ቀን በመቃብርና በተራራ ሆኖ ይጮኽ ነበር ሰውነቱንም በድንጋይ ይደቁር ነበር። ኢየሱስንም ከሩቅ ባየ ጊዜ ሮጦ ሰገደለት፥ በታላቅ ድምፅም እየጮኸ፦ የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ፥ ከአንተ ጋር ምን አለኝ? እንዳትሣቅየኝ በእግዚአብሔር አምልሃለሁ አለ፤ አንተ ርኩስ መንፈስ፥ ከዚህ ሰው ውጣ ብሎት ነበርና። ስምህ ማነው? ብሎ ጠየቀው። ብዙዎች ነንና ስሜ ሌጌዎን ነው አለው፥ ከአገርም ውጭ እንዳይሰዳቸው አጥብቆ ለመነው። በዚያም በተራራ ጥግ ብዙ የአሪያ መንጋ ይሰማራ ነበርና፦ ወደ አሪያዎቹ እንድንገባ ስደደን ብለው ለመኑት። ኢየሱስም ፈቀደላቸው። ርኩሳን መናፍስቱም ወጥተው ወደ አሪያዎቹ ገቡ፥ ሁለት ሺህም የሚያህል መንጋ ከአፋፉ ወደ ባሕር ተጣደፉና በባሕር ሰጠሙ» (ማር. 5፡1-13)።

ዶክተሩና ተባባሪው በደን ወደ ተከበበችው መንደር በመግባት የመጀመሪያዎቹ ሚሲዮናውያን ነበሩ። በእነዚህ ሕዝቦች መካከል ቤተ ክርስቲያንም ሆነች ክርስቲያኖች አልነበሩም። ሁለቱ ሰዎች በቋንቋ ትርጉም የሚረዳቸው የአገሬው ተወላጅ ሰው አገኙ። በዚህ በአስተርጓሚያቸው አማካኝነት ሁለቱ ሰዎች የመንደሩን አለቃ፥ እዚያው ጥቂት ጊዜ ቆይተው ስለ እግዚአብሔርና እግዚአብሔር ለሕዝቡ ስላለው ፍቅር አንዳንድ ታሪኮችን መናገር ይችሉ እንደ ሆነ ጠየቁት። አለቃው በአሳባቸው ተስማማና ለሁለቱም ሌሊቱን ተጠልለው የሚያሳልፉበት ቤት ለየብቻ ተሰጣቸው። እያንዳንዱ ክፍል የበርና የመስኮት ቀዳዳዎች ነበሩት። ሰዎች ለእንቅልፍ ከአልጋቸው ላይ ጋደም ሲሉ፥ በመጨረሻው ለብዙ ዓመታት ሲጸልዩ ወደ ነበሩበት ስፍራ ሊደርሱ በመቻላቸው እጅግ ተደሰቱ። ከደስታቸውም የተነሣ እንቅልፍ ሊወስዳቸው አልቻለም ነበር። ጊዜው ጨረቃ የደመቀችበት ብሩኅ ሌሊት ነበር። የጨረቃዪቱ ብርሃን

በበሩና በመስኮቱ ቀዳዳዎች ገብቶ ያበራ ስለ ነበር፥ በትክክል ሊመለከቱ ይችሉ ነበር።

ወዲያውም ሁለት እንደ ብረት የጠነከሩ እጆች የዶክተሩን ጉሮሮ አንቀው ለመግደል ሲጣደሩ ተሰማው። እርሱም ጉሮሮውን የሚያንቁትን እጆች ለማስለቀቅና ራሱን ነጻ ለማድረግ የኋሊት አሰሳ ጀመረ፤ ዳሩ ግን የሚጨበጥ ምንም ነገር አልነበረም! እነዚያ እጆች ግን ማንቁርቱን አጥብቀው ያዙ። በክፍሉ ውስጥ ማንም ሰው እንዳልነበረ ያያል። በዚህም ጊዜ ትንፋሹን ውጦ የኢየሱስን ስም ጠራ፤ ወዲያው እነዚያ እጆች ጉሮሮውን ለቀቁ። በቀጣዩ ጠዋት ቁርሳቸውን እየበሉ ሳለ ዶክተሩ ያጋጠመውን ነገር ለተባባሪው አጫወተው። ተባባሪውም በአድናቆት ተመልክቶት የራሱን ተመሳሳይ ገጠመኝ ያወጋው ጀመር። ከዚያም፥ ሁለቱ ሰዎች ራሶቻቸውን ዝቅ አድርገው እግዚአብሔርን ስለ ጥበቃው አመሰገኑት።

ክርስቲያኖች እንደ መሆናችን የመንፈሳዊ ውጊያ ተሳታፊዎች ነን። ይህም ጦርነት የእግዚአብሔር ባሪያዎች የክርስቶስን ወንጌል በሰይጣን ታስረው ወደሚገኙ ሰዎች ለማድረስ በሚጥሩበት ወቅት በጣም የከረረ ሊሆን ይችላል። ይህ ከላይ የቀረበው እውነተኛ የማሌዢያ አገር ታሪክ በዓለም ሁሉ ወንጌሉን ላልደረሳቸው ሕዝቦች ለማሰራጨት የሚደረገውን ጥረት ከሚያጋጥሙት ተፈታታኝ ታሪኮች ጋር ተመሳሳይ ነው። የሰይጣን አጋንንት ክርስቲያኑን በብዙ የተለያዩ መንገዶች ይቃወማሉ (ኤፌ. 6፡12-13)።

አንዳንድ ጊዜ ተቃውሞው በአሉታዊ አሳቦችና ተስፋ በማስቆረጥ ይመጣል። በሌላ ጊዜም በፈተና መልክ፥ ወይም በከፍተኛ የጤና መታወክ፥ በቤተሰብ ወይም በስሜታዊ ችግሮች ይገለጻል። አንዳንድ ጊዜም በአገር ውስጥ በሚነሣ ከፍተኛ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ፥ ወይም በወንጀልና ጭካኔ ተግባራት ወይም በጦርነት መልክ ይመጣል።

መንገዱ ምንም ቢሆንም ከሰይጣንና ከአጋንንቱ የሚመጣው ተቃውሞ ተስፋ አስቆራጭና አደገኛም ሊሆን ይችላል። ክርስቲያን በመንፈሳዊ ሕይወቱ ሊጋፈጣቸው የሚገቡ ሁለት ጠንካራ ጠላቶች አሉት። ምናልባትም ከሁሉም በላይ ተስፋ የሚያስቆርጠው ጠላት በውስጡ የሚገኘው ነው። ይህም የራሱ የኃጢአት ተፈጥሮ ደካማነትና ብልሽት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር እውቃለሁና . . . የማልወደውን ክፉን ነገር አደርጋለሁና» ይላል

(ሮሜ 7፡18-19)። በተጨማሪም፥ ክርስቲያን ትዕቢትን፥ ራስ ወዳድነትን፥ ስግብግብነትንና ምኞትን በሚያበረታቱ የአሁኑ ዓለም ብልሹ እሴቶች ሥርዓት ተከቦ ይኖራል።

መንፈሳዊ ጦርነት ጨዋታ አይደለም። ዓለም በከፍተኛ ደረጃ ትስበናለች፤ የራሳችንም ሰብአዊ ተፈጥሮ የተባለሸ ሲሆን፥ ሰይጣንም ጨካኝና ኃይለኛ ጠላት ነው። ምስቱን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ጠላቶች ለማሸነፍ ከፈለግን ይህንኑ ጦርነት በትኩረት ልንወጣው ይገባል። እነዚህም ጠላቶች ዓለም፥ ሥጋና ሰይጣን ናቸው። ክርስቲያን እነዚህን ጠላቶች የሚያሸንፈው እንዴት ነው? በዚህ ምዕራፍ የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንመለከታለን፡-

ሀ. አንድ ክርስቲያን ወደ ኋላ የሚጎትተውን የኃጢአት ተፈጥሮውን እንዴት ሊያሸንፍ ይችላል?

ለ. ክርስቲያን የዓለምን ፈተናዎች እንዴት ሊያሸንፍ ይችላል?

ሐ. ክርስቲያን የሰይጣንን ጥቃቶች እንዴት ሊያሸንፍ ይችላል?

መ. የመንፈሳዊ ጦር ዕቃዎች ምንድን ናቸው? እንዴትስ እንጠቀምባቸዋለን?

ሀ. አንድ ክርስቲያን ወደ ኋላ የሚጎትተውን የኃጢአት ተፈጥሮውን እንዴት ሊያሸንፍ ይችላል?

መጽሐፍ ቅዱስ ብልሹ ሰብአዊ ተፈጥሮአችንንና የኃጢአት ምኞቶቻችንን (የሥጋን ምኞት) እንድናስወግድ የሚነግረን እንዴት ነው? መልሱ የኃጢአት ዝንባሌዎቻችንን ለማሸነፍ አንዳንድ ነገሮችን መተውና አንዳንድ ነገሮችን ማድረግ ነው። እነዚህን ለውጦች ለማካሄድ የሚያስፈልገው ኃይል ከራሳችን የሚመጣ አይደለም። ኃይሉ የሚመጣው በሁሉም ክርስቲያኖች ውስጥ ከሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ነው። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ትክክል ያልሆኑትን ነገሮች ከማድረግ ተቆጥበን ትክክለኛዎቹን ነገሮች እናከናውናለን። የኃጢአትን ባሕርይ እግዚአብሔር እንድናደርግ በሚፈልገው ነገር እንዴት እንደምንተካ ማወቅ አለብን።

አንድ ሰው ትክክለኛ ያልሆኑትን ልምምዶቹን ቢያቆምም ቅሉ፥ ብልሹ ባሕርዩን በመንፈሳዊ ባሕርይ እስካልተካ፥ ብዙም ሳይቆይ ወደ ቀደሙት ኃጢአቶቹ እጅግ በተባባሰ ሁኔታ ሊመለስ ይችላል። ለዚህ

ምሳሌ የሚሆነን መጠጣትን ለማቆም የሚወስን ሰካራም ነው። መጠጣቱን ለጊዜው ያቁም እንጂ የመጠጥ ሱሱን በመንፈሳዊ ልምምድ አስካልተካው፥ ከጊዜ በኋላ ከተድሞው ወደ ከፋ የጠጭነት ሕይወት ይመለሳል። ኢየሱስ በወንጌላት ውስጥ ርኩሱ መንፈስ ስለ ወጣበት ሰው ከሚናገረው ታሪክ በስተ ጀርባ የሚገኘውም አሳብ ይኸው ነው። ከፉው መንፈስ ከሰውዬው ሊወጣ ቤት ባለማግኘቱ፥ ከእርሱ የከፉትን ሰባት አጋንንት ጨምሮ ይመለሳል (ማቴ. 12፡43-45)። መንፈሱ የሰውየውን ቤት (ነፍሱን) ጎርቶ ያገኘዋል (ማቴ. 12፡44)። ይሁንና ነፍሱ በተሻሉ ነገሮች ተሞልቶ አልቆየም። ስለ ሆነም፥ በአንዱ ምትክ አሁን ስምንት ከፉ መናፍስት ያድሩበታል።

የኃጢአትን ተግባራት እንዴት በመንፈሳዊ ልምምዶች እንደምንተካ የሚያስረዳ ግልጽ ምሳሌ በኤፌሶን 4፡28 ተሰጥቶአል። «የሰረቀ ከእንግዲህ ወዲህ አይስረቅ፥ ነገር ግን በዚያ ፈንታ ለጎደለው የሚያካፍለው እንዲኖርለት በገዛ እጁ መልካምን እየሠራ ይድከም።» ሌባው ስርቆቱን ማቆም አለበት። ይሁንና፥ ወደ ስርቆት የሚገፋፋውን ስሜት ለማሸነፍ፥ ስርቆት በአንድ መንፈሳዊ ልምምድ መተካት አለበት። በእጁ መሥራትንና የሥራውንም ውጤት ለችግርተኞች ማካፈልን መጀመር አለበት። በዚህም፥ የስርቆት ልማዱ በመጨረሻው ይወገዳል። እግዚአብሔር ለቀድሞው ሌባ ሌሎችን በመርዳት ዘላቂ ደስታ እንዲያገኝ ያደርጋል። በኃጢአት የሚገኝ አጭርና ከፉ ደስታ፥ ሌሎችን በመርዳት በሚገኝ ዘላቂና አስደሳች ልምምድ ይተካል።

የኃጢአት ልማዶችን ለዘለቄታው ለማስወገድ የሚቻልበት ብቸኛው መንገድ፥ የኃጢአት ባሕርይን በመንፈሳዊ ባሕርይ የመተካቱ መመሪያ ነው። መመሪያው በመዝሙር (34)፡14፥ «ከክፉ ሽሽ መልካምንም አድርግ» በሚሉ አራት ቃላት ተገልጾአል። በጥንቃቄ በማሰብ፥ በጸሎትና በምክር፥ ይህንን ጥቅስ በኃጢአታዊ ተፈጥሮአችን ውስጥ ለሚገኝ ለማንኛውም ድክመት ማስወገጃ ልንጠቀምበት እንችላለን።

ለምሳሌ፥ ማንኛውም ወጣት ከወሲብ ፍላጎቶች ጋር ይታገላል። ይህ መመሪያ የምኞትንና የወሲብ ግድፈትን ለማሸነፍ እንዴት ሊያገለግል ይችላል? መልሱ የሚገኘው በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ ከተጠቀሰው የዮሴፍ ታሪክ ነው። ወጣቱ ዮሴፍ ኃጢአት ለማድረግ በጣም ተፈተነ። የፈርዖን የሠራዊት አለቃ የነበረው የጲጥፋራ ሚስት ዮሴፍ ከእርሷ ጋር

እንዲተኛ ደጋግማ ለመነችው (ዘፍጥ. 39፡1-16)። ስንት ወጣቶች ናቸው እንዲህ ዓይነት በተደጋጋሚ በሴት የመለመን ሁኔታ የሚያጋጥማቸው?

ለዮሴፍ ፈተናው በጣም ከባድ ነበር። ዮሴፍ ብርቱና መልከ መልካም (ዘፍጥ. 39፡6) ያላገባ ወጣት ነበር። ከቤተሰቡ በጣም ርቆ ይገኝ ስለ ነበር፥ በግብፅ ስለሚያጋጥመው ነገር የሚያውቅም ሆነ የሚጨነቅ አልነበረም፤ ወንድሞቹ እንደ ባሪያ ሸጠው አስወግደውታል (ዘፍጥ. 37፡28)። የጲጥፋራ ሚስት በዮሴፍ ተግርካ ከእርስዋ ጋር የአልጋ ጨዋታ እንዲጀምር ጠየቀችው (ዘፍጥ. 39፡7)። ይህንንስ ግን ሊያውቅ ይችላል? ምንስ ያስጨንቃል?

የመዝሙር (34)፡14 መመሪያ በ2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡22 ላይ እንደሚከተለው ምኞትን ለመከላከል አገልግሎት ላይ ውሎ እናገኛለን፦ «ከክፉ የነገግሳነት ስሜት ግን ሽሽ፥ በንጹሕም ልብ ጌታን ከሚጠሩ ጋር ጽድቅን እምነትን ፍቅርን ሰላምን አጥብቀህ ተከተል።» ሰው ከምኞት መሸሽ (መሮጥ) አለበት። ከፈተና ራሱን ማራቅ አለበት። ይህም ወደ ሲኒማ ከመሄድ መታቀብ፥ ስሜት[1] ቀስቃሽ ሥዕሎች ያሉበትን መጽሔት አለማገላበጥ፥ ወይም ሚስቱ ካልሆነች ልጃገረድ ጋር በጨለማ ክፍል ውስጥ ለመቀመጥ እምቢ ማለት ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም፥ ሰው ፈተናውን ለመተካት የጽድቅን ተግባር መፈጸም አለበት። ከሌሎች ጋር ኅብረት በመፍጠር ጽድቅን፥ እምነትን፥ ፍቅርንና ሰላምን አጥብቆ መከተል አለበት። ዮሴፍ ተግባራዊ ያደረገው እነዚህን ሁለት መመሪያዎች ነበር።

ምንም እንኳ ዮሴፍ 2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡22ን ባያነብም፥ እነዚህኑ ሁለት መመሪያዎች ተከትሏል። በቀጥታ ከጲጥፋራ ሚስት ሮጦ አመለጠ (ዘፍጥ. 39፡12)። ለምን ይህን አደረገ? መልሱ ለሴቲቱ ከሰጠው ምክንያት ሊገኝ ይችላል፦ «እንዴት ይህን ትልቅ ክፉ ነገር አደርጋለሁ? በእግዚአብሔር ዘንድ እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ?» (ዘፍጥ. 39፡9)። ዮሴፍ ያለ ጥርጥር ራሱን ከሚያስደስተው በላይ እግዚአብሔርን ለማስደሰት ፈልጎ ነበር። በእግዚአብሔር ፊት ንጹሕ ለመሆን ራሱን ለመካድ ፈቃደኛ ነበር። በ2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡22 ላይ እንደ ተጠቀሰው፥ እግዚአብሔርን በንጹሕ ልብ እንደሚጠራ ሰው ጽድቅን ሊከተል ወሰነ።

ዘዳግም 6፡5፥ «አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህ በፍጹም ኃይልህ ውደድ» ይላል። ዮሴፍ እግዚአብሔር አምላኩን በፍጹም ልቡ ለመውደድ ወሰነ። ዮሴፍ ከጊዜያዊ ደስታ ይልቅ የእግዚአብሔርን በረከትና ጎብረት ፈለገ። ለጥቂት ደቂቃዎች በኃጢአት ከመደሰት ይልቅ፥ እግዚአብሔር ጸሎቱቹን እንደሚመልስ እርግጠኛ ለመሆን ፈለገ። ጊዜያዊውን የደስታ ፍላጎት በረሸ ሙ የእግዚአብሔር በረከት ተካ።

መንፈስ ቅዱስ ለአንድ ወጣት በንጽሕና የሚኖርበትን ብርታት ሊሰጠው ይችላል። ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ሙካከል ራስን መግዛት አንደኛው ነው (ገላ. 5፡23)። የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለአንድ ወጣት «ከጎልማሳነት ምኞት» የመሸሽን ፈቃደኛነት ሊሰጠው ይችላል (2 ጢሞ. 2፡22)። ይሁንና፥ ከጎልማሳነት ምኞት መሸሹ ብቻ በቂ አይደለም። ሕይወትን ከግል ደስታ ለበለጠ ነገር ለማዋል መሻት ያስፈልጋል! ለግል ፍላጎቶች አሉታዊ ምላሽ የመስጠት ፈቃደኛነት የሚመጣው፥ ከራስ ይልቅ እግዚአብሔርን ለማስደሰት ከሚኖረን ታላቅ መሻት ነው። እግዚአብሔር አምላክን በፍጹም ልብ መውደድ ማለት ይሄ ነው (ዘጸ. 6፡5)።

ክርስቶስን ለመምሰል ቁርጥ ውሳኔ ካደረግን፥ መንፈስ ቅዱስ ከራሳችን በላይ እግዚአብሔርን የምናስደስትበትን መሻት ይሰጠናል [መዝ. (119)፡9-10፤ ፊልጵ. 2፡13]። ራሱን ለሰጠው ክርስቲያን፥ የራሱን ፍላጎቶች ከማኟላት የበለጠ እግዚአብሔርን ለማስከበር የሚጥርበትን ፍላጎት ይሰጠዋል። ዮሴፍ እግዚአብሔርን ለማስደሰት የራሱን ፍላጎቶች ለመካድ ፈቃደኛ ስለ ነበር፥ ይህንኑ ታላቅ ፈተና እንዲያሸንፍ ብርታት የሰጠው እግዚአብሔር ነበር።

ለ. ክርስቲያን የዓለምን ፈተናዎች እንዴት ሊያሸንፍ ይችላል?

የዓለም የእሴቶች ሥርዓት በትዕቢት፥ ራስ-ወዳድነት፥ ምኞትና ስግብግብነት ላይ የተመሠረተ ነው። እግዚአብሔር የዓለምን የእሴቶች ሥርዓት እንዴት እንድናስወግድ ይፈልጋል? እንደ የኃጢአት ተፈጥሮአችን ሁሉ፥ አንዳንድ ነገሮችን እንድንተውና አንዳንድ ነገሮችን እንድናደርግ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ከክፉት ተመልሰን መልካም ማድረግ አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ . . . ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ የለም» ይላል (1 ዮሐ. 2፡15)። ልባችንን በዓለም ነገሮች ላይ ከማድረግ መቆጠብ አለብን። እንዴት ይህንን ልናደርግ

እንችላለን? ይህንን ልናደርግ የምንችለው ልባችንን በአንድ የተለየና የላቀ ነገር ላይ ካሳረፍን ብቻ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ፥ «እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፥ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን እሹ» ይለናል (ቆላ. 3፡1)። በመንፈሳዊ ባሕርይ ግደግ፥ ሌሎችን መርዳት፥ ቸርነትንና ልግስናን ግሳየት፥ መጸለይ፥ ስለ ክርስቶስ ለሰዎች መናገርና እግዚአብሔርን በተለያዩ መንገዶች ማገልገልን በመሳሰሉ ዘላቂ መንፈሳዊ ነገሮች ላይ ልባችንን ማሳረፍ አለብን። እነዚህ «በላይ የሚገኙ» ነገሮች ናቸው።

ሌሎችን በመርዳቱና በማበረታቱ ተግባር ላይ የምንተጋ ከሆነ፥ የዚህን ዓለም ነገሮች የማሳደድ አሳብ አይኖረንም። እግዚአብሔር እርሱን ስናገለግል፥ ራሳችንን በማገልገል ልናገኝ ከምንችለው ከማንኛውም እርካታና ደስታ የበለጠ ነገር ይሰጠናል። ብዙ ሰዎች በዓለም ደስተኞች የማይሆኑት፥ ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን ሁሉ እግዚአብሔርን ለማስደሰት ከመሞከርና ሌሎችን ከማገልገል ይልቅ ራሳቸውን ለማስደሰት ስለሚጠቀሙ ነው። እግዚአብሔር የፈጠረን ራሳችንን ሳይሆን፥ እርሱን በማስደሰትና ሌሎችን በመርዳት ከሁሉም የላቀውን ደስታ እንድናገኝ አድርጎ ነው።

ያየነውን ሁሉ የምንመኘው ተፈጥሮአዊ መሻቶቻችን በኃጢአት ስለተበላሹ ነው። ነገሮችን በዓይኖቻችን አይተን ልናገኛቸው ስለምንፈልግ እንመኛለን። እሴቶቻችንና ፍላጎቶቻችን በዙሪያችን ባለው የዓለም የእሴት ዘይቤ ተበላሽተዋል። ዓለም የምንችለውን ሁሉ በመሰብሰብ ለራሳችን እንድናካብትና ስለ ሌሎች ሰዎችና ስለ ችግሮቻቸው ግድ የለሽ እንድንሆን ትነግረናለች። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ስጡ ይሰጣችሁማል፤ በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርላችኋልና፥ የተጨቆነና የተነቀነቀ የተትረፈረፈም መልካም መስፈሪያ በእቅፋችሁ ይሰጣችኋል» ይላል (ሉቃ. 6፡38)። የዓለምን ነገሮች ከመውደድ ነፃ የምንሆነው እንዴት ነው? መልሱ ለዓለም ነገሮች ያለንን ፍላጎት ለእግዚአብሔር ነገሮች በሚኖረን ፍላጎት በመተካት ነው። ራሳችንን በማገልገል ልናገኝ ከምንችለው ደስታ ይብልጥ እግዚአብሔርን በማገልገል እንደምናገኝ መረዳት አለብን።

ዓለም፥ ለመደሰት እስከ ፈለግን፥ ኩሩና ከሌሎች የላቅን መሆን እንዳለብን ትነግረናለች። ኢየሱስ፥ «ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን፥ ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የእናንተ ባሪያ ይሁን፤ እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል

ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም» ይላል (ማቴ. 20፡26-28)። የዚህ ዓለም የእሴት ዘይቤ የሰይጣን የማታለያ ውጤት ለመሆኑ፡ በሲኒግ ኢንዱስትሪ የሚገኙትን የአያሌ ምግባረ ብልሹና ሀብታም ተዋንያን (አክተሮች) ሕይወት ከመርመር ሊረጋገጥ ይችላል። እነዚህ ሰዎች ከብዙዎቹ የዓለማችን ነዋሪዎች የበለጠ ሀብት፥ ዝናና ምቾት አላቸው። ይሁንና፥ የግል ሕይወታቸው ከእውነተኛ ደስታ የራቀ ሲኦል ነው። ብዙውን ጊዜ ሕይወታቸው በዝሙት፥ በፍች፥ በመጠጥና ራስን በማጥፋት የተበከለ ነው። እግዚአብሔር የሰው ልጆች እርሱንና ሌሎችን በማገልገል እንዲያስከብሩት እንጂ፥ ለራሳቸው ደስታ እንዲኖሩ አልፈጠራቸውም።

የዓለምን ፈተናዎች ለማሸነፍ ሆነ ብለን የእግዚአብሔርን የእሴት ዘይቤ ለመከተል መምረጥ አለብን። ዋናው ጥያቄ ይህ ነው፡- ልባችንን የሚሰነው በምን ላይ ነው? ልባችንን የሚሰነው ገንዘብን በማከማቸት፥ ዕውቀትን በማካበትና በምድራዊ ጠቀሜታ ላይ ነው ወይስ እግዚአብሔርን በማገልገልና ቸርነቱን ለሌሎች በማሳየት ላይ ነው? ከልባችን ትዕቢትን፥ ስግብግብነትንና ራስ ወዳድነትን ልናስወግድ ከፈለግን፥ በዙሪያችን የሚገኘውን ዓለም የእሴት ዘይቤ ችላ ልንልና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጸውን የእሴት ዘይቤ ልንከተል ይገባል። «ክርስቶስ ባለበት በላይ ያለውን ሳስብ» ማለት ይኸው ነው (ቆላ. 3፡1)።

ሐ. ክርስቲያን የሰይጣንን ጥቃቶች እንዴት ሊያሸንፍ ይችላል?

የዓለም እሴት ዘይቤና የኃጢአት ተፈጥሮአችን ከሚያስከትሉብን ችግሮች በተጨማሪ፥ ሰይጣንና ጨካኝ አጋንንቱ የሚሰነዝሩብን ከፍተኛ የጠላት ጥቃትም ይጋረጥብናል። መጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣን፥ «የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና» ይላል (1 ጴጥ. 5፡8)።

ክርስቲያን ሁሉ በሕይወቱ በሰይጣን ወይም በአጋንንቶቹ ይፈተናል። በተጨማሪም፥ በሰይጣን ወይም በክፉ መላእክቱ ቀጥተኛ ጥቃት የደረሰባቸውም አሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣንን ስለምንርቅበት መንገድ ምን ይለናል? ይህንን ጥያቄ ለመመለስ፥ በመጀመሪያ ሰይጣን ከየት ኃይሉን እንደሚያገኝ መረዳት አለብን። በቆላስይስ 2፡15 ክፉ መላእክት ኢየሱስ በተሰቀለ ጊዜ «ትጥቃቸውን እንደ ፈቱ» እናነባለን። ከመስቀሉ በፊት «የታጠቁት» እንዴት ነበር? መልሱ ክርስቶስ፥ «የሚታወሙንን

በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው» በሚለው የቆላስይስ 2፡14 ኅረፍተ ነገር ውስጥ ይገኛል።

የተከሰሰውን ወንጀለኛ መቀመቅ ለመክተት በዳኛው ፊት ተዘጋጅቶ እንደ ቀረበው አቃቤ ሕግ፥ ሰይጣንና አጋንንቱም በእግዚአብሔር ላይ በፈጸምነው የኃጢአት መዝገብ («የዕዳ ጽሕፈት») ሊያጠቁን ታጥቀው ተነሥተው ነበር። ሰዎችን በእግዚአብሔር ፊት እንደሚከስ አካል (ራእይ 12፡10)፥ ሰይጣን የሰውን ልጅ ለማጥቃት የሚጠቀምበት መሣሪያ፥ ሰዎች ለኃጢአታቸው በእግዚአብሔር ይቀጡና ይፈረድባቸው ዘንድ የሚያቀርበው ሕጋዊ ጥያቄ ነው። ሰይጣን ይህንን ጥያቄ የሚያቀርበው የእግዚአብሔርን ሕግጋት በማፍረስ የእግዚአብሔርን ኩነኔና ፍርድ እንደ ተቀበልን ስለሚያውቅ ነው። ቆላስይስ 2፡14 «ጽሕፈቱ» የተላለፍናቸውን የእግዚአብሔርን ሕግጋት እንደሚያካትት ይገልጻል። «በትእዛዛት» ውስጥ ለኃጢአታችን የተወሰነው ቅጣት ሞት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ «የኃጢአት ዋጋ ሞት» እንደሆነ ይናገራል (ሮሜ 6፡23)። እግዚአብሔር ጻድቅና ቅዱስ በመሆኑ ክሱን ተቀብሎ በኃጢአታችን መሠረት ሊፈርድብን ስለሚገባ፥ ሰይጣን እኛን በእግዚአብሔር ፊት ለመክሰስ ሕጋዊ መብት ነበረው።

ኢየሱስ በመጣ ጊዜ «በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን (ዲያብሎስን) በሞት እንዲሽር» (ዕብ. 2፡14) በኃጢአታችን የተፈረደብንን የሞት ቅጣት በመስቀል ላይ ተቀበለ (ዕብ. 2፡9)። ሰይጣን በእኛ ላይ የሚያቀርበው ክስ መሠረት፥ በክርስቶስ ለሚያምኑት በኢየሱስ ሞት ተወግዷል። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «በበጉ ደም (ሰይጣንን) ድል ነሡት» የሚለው ለዚህ ነው (ራእይ 12፡11)። ሮሜ 8፡1፥ «እንግዲህ፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም» ይላል። በእምነት በክርስቶስ ያመኑ ሰዎች ለዘላለሙ ድነዋል (ዮሐ. 5፡24፤ 10፡28)።

ይሁንና፥ ሰይጣን ብርቱ ጠላት ነው። ምንም እንኳ ክርስቲያኖችን ከኃያሉ የእግዚአብሔር እጅ ነጥቆ ለመውሰድ የሚያስችል ኃይል እንደሌለው ቢያውቅም (ዮሐ. 10፡28)፥ በክርስቶስ ካመኑ በኋላ በኃጢአት ሕይወት እንዲቀጥሉ ሊፈትናቸው ይችላል። በኃጢአት ሕይወት ብንቀጥል፥ በዚህ በአሁኑ ሕይወት ለእነዚሁ ኃጢአቶች ቅጣት እንቀበላለን (ዕብ. 2፡2)። የዕብራውያን ጸሐፊ፥ «የእውነትን እውቀት ከተቀበልን በኋላ ወደን ኃጢአት ብናደርግ ከእንግዲህ ወዲህ ስለ ኃጢአት መሥዋዕት

አይቀርልንምና፥ የሚያስፈራ ግን የፍርድ መጠበቅ ተቃዋሚዎችንም ሊበላ ያለው የእሳት ብርታት አለ» በማለት ያስጠነቅቀናል (ዕብ. 10፡26-27)።

ሰይጣን ይህንን እውነት አሳምሮ ስለሚያውቅ፥ ከአጋንንቱ ጋር በመተባበር ክርስቲያኖችን በኃጢአት ለማቆየት ተግቶ ይሠራል። በክርስቶስ ካመንን በኋላ በኃጢአት ብንቀጥል፥ ሰይጣን ለእነዚህ ኃጢአቶች በእግዚአብሔር ፊት መክሰሱን ይቀጥላል (ራእይ 12፡10)። ሰይጣን በእግዚአብሔር ፍትሕ መሠረት እንድንቀጣ ይፈልጋል (ዕብ. 10፡26-27)። ይህንንም በማድረግ፥ ሰይጣን ክርስቲያኑን ለማጥቃት ሕጋዊ መብት ሊያገኝ ይችላል። ይህ በ1ኛ ቆሮንቶስ 5፡1-5 በተጠቀሰው ዘማዊ ሰው ሕይወት ተከስቷል። መጽሐፍ ቅዱስ ይህ የቤተ ክርስቲያን ምእመን ከዝሙቱ ሊመለስ ባለመፈለጉ፥ ጳውሎስ ለኃጢአቱ ይቀጣው ዘንድ ለሰይጣን ኃይል አሳልፎ እንደሰጠው ይናገራል (1 ቆሮ. 5፡5)። ይህ ሰው ደኅንነቱን ባያጣም (1 ቆሮ. 5፡5)፥ በሰይጣን የጭካኔ ጥቃት ምድራዊ ሕይወቱን አጥቶ ሊሆን ይችላል።

ከዚህ ምሳሌ የሰይጣን ኃይል የተመሠረተው በኃጢአትና በእግዚአብሔር ላይ በማመፅ ላይ እንደ ሆነ እንረዳለን። መጽሐፍ ቅዱስ በግል ቅድስና ላይ ብዙ የሚያተኩረው ለዚህ ነው። ክርስቲያኖች በፈቃደኛነት ኃጢአትን ማድረግ ካዘወተሩ፥ በሕይወታቸው ለሰይጣን «ፈንታ» (በአዲሱ ትርጉም «ስፍራ») ይሰጡታል (ኤፌ. 4፡27)።

ይቅርታ የማያደርገውን ባሪያ በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ በማቴዎስ 18፡21-35፥ ኢየሱስ በግልጽ ለሚያሠቃዩት አልፎ እንደ ተሰጠ ተናግሯል። ይህ በምዕራፍ 11 እንደ ተመለከትነው፥ ሰዎችን በማሠቃየት የሚደሰቱትን አጋንንት ያካትታል። ስለ ሆነም፥ ክርስቲያኖች ይቅርታን እንዲያገኙ ኃጢአታቸውንና ውድቀታቸውን በመናዘዝ መቀጠላቸው በጣም አስፈላጊ ነው። በዚህ ሰይጣን በእነርሱ ላይ የሚሰነዝራቸው ክሶችና ጥቃቶች ይወገዳሉ (ምሳሌ 28፡13)። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው» ይላል (1 ዮሐ. 1፡9)።

ከዚህ ውይይት፥ ለሰይጣን ኃይልና እንቅስቃሴ መሠረቱ ኃጢአት እንደ ሆነ ልንመለከት እንችላለን። ኃጢአት ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ ሲሆን፥ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ላይ ያመፀውም ሰይጣን ነው።

ክርስቲያን በፈቃደኛነት ኃጢአት ማድረግ ቢጀምር፥ ራሱን ለሰይጣንና ለአጋንንቱ ጥቃት ያጋልጣል። ለዚህም ነው ብዙ ክርስቲያኖች እንደ ጥላቻና ይቅር አለማለት በመሳሰሉ የኃጢአት ልማዶች ተጠፍረው የሚታዩት። ኃጢአታቸውን ለመናዘዝና ለመተው ብሎም የእግዚአብሔርን ይቅርታ ለመቀበል ከፈለጉ፥ ከእነዚህ ልማዶች ሊላቀቁ ይችላሉ። በዚህም፥ ሰይጣን በእነርሱ ላይ የሚያመጣውን ተጽዕኖ ያሸንፋሉ። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤ የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል» ይላል (ምሳሌ 28፡13)።

በሰይጣን ጥቃቶች ላይ ድል ለማግኘት፥ አንዳንድ ነገሮችን ትተን አንዳንዶቹን ማድረግ አለብን። በሰይጣን ላይ ድል ለመቀዳጀት ቁልፍ የሆነ ቃል በያዕቆብ 4፡7 ላይ ይገኛል፡- «ለእግዚአብሔር ተገዙ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል።» የመጀመሪያው ክፍል ራሳችንን ለእግዚአብሔር ማስረከብ እንዳለብን ይናገራል። በመዝሙር (34)፡14 አባባል፥ «ከክፉ መሸሽ» አለብን። የእግዚአብሔርን ቃል መታዘዝ አለብን። ሰይጣንን በእግዚአብሔር ሥልጣን ልንቃወም የምንችለው በዚህ ጊዜ ብቻ ነው።

በምድረ በዳ የሰይጣንን ፈተና ለማሸነፍ፥ ኢየሱስ ከራሱ ፍላጎቶች ይልቅ የእግዚአብሔርን ቃል ለመታዘዝ በመምረጥ በመጀመሪያ ለእግዚአብሔር አብ ራሱን አስገዝቷል። ለዚህም ነው በተደጋጋሚ ከመጽሐፍ ቅዱስ እየጠቀሰ፥ « . . . ተብሎ ተጽፎአል» ያለው (ማቴ. 4፡4፥ 7፥ 10)። ኢየሱስ ፈቃዱን ለእግዚአብሔር ቃል ካስገዛ በኋላ ብቻ ነበር ኢየሱስ ሰይጣንን ለመቃወምና እንዲሄድም ለማዘዝ የቻለው (ማቴ. 4፡10)። ክርስቲያንም በእግዚአብሔር ሥልጣን ሰይጣንን ለመቃወምና እንዲሄድ ለማዘዝ፥ ይህንኑ ማድረግ አለበት።

ራሳችንን ለእግዚአብሔር ስናስገዛ፥ ሰይጣን በእኛ ላይ ኃይል የሚያገኝበትን መሠረት፥ ማለትም በእግዚአብሔር ላይ የሚፈጸመውን ኃጢአትና ዓመፅ ያጣል። ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ እንዲያምፁ ለመቀስቀስ ስለቻለ፥ በአዳምና ሔዋን ሕይወት ድል አግኝቷል። ለእግዚአብሔር የማይገዛ ከሆነ፥ ክርስቲያን ለሰይጣን ጥቃት የተጋለጠ ይሆናል። በሌላ በኩል፥ ለእግዚአብሔርና ለቃሉ ስንገዛ፥ በሰይጣንና በአጋንንቱ ላይ የክርስቶስ የወኪልነት ሥልጣን ይኖረናል (ሉቃ. 10፡19፤ ኤፌ. 6፡11-18)። የሚቀጥለው በዛምቢያ የተፈጸመ አንድ እውነተኛ ታሪክ ይህንኑ አሳብ ያብራራል።

በአንድ ቅዳሜ ዕለት ክርስቲያኖች የሚገኙበት ቡድናችን በጎብረት ሲጸልይ፥ አንዲት ልጃገረድ ባሰማችው ከፍተኛ ጩኸት በአጋንንት መያዟን አወቅን። ዓይኖቿ ንጹሕና የጠሩ ነበሩ፤ ይሁንና፥ አጋንንቱ ራሳቸውን መግለጽ እንደ ጀመሩ ዓይኖቿ እንደ ደም ከመቅላታቸውም፥ የፊቷ ገጽታ ተለዋወጠ፤ ድምፅዋም እንዲሁ። ወደ ሌላ ክፍል ልንጸልይላት ወሰድናት፤ ሆኖም ባብዛኛው ውጪት በማይታይበት ጊዜ እንደምናደርገው፥ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ መጸለያችንን አቆምን። ጌታ የጥበብ ቃል ሰጠንና (1 ቆሮ. 12፡8) ብዙ ስውር ነገሮችን ይዛ እንዳለች ነገረን። በጠየቅናትም ጊዜ በቤቷ የጥንቆላ መድኃኒት እንዳላት ነገረችን። በዚህም ጊዜ፥ በጸሎት ቆይተን በሚቀጥለው ቀን ልንገናኝ ተስማማን።

በሚቀጥለው ቀን ወደ ቤቷ ስንሄድ፥ እንድናቃጥለው መድኃኒቱን ትሰጠን ዘንድ ጠየቅናት (የሐዋ. 19፡19)። ሁሉንም ሰበሰበችና በትንሽ ሻንጣ ሞላች። ከዚያም፥ ለሁለት ደቂቃዎች ያህል እንደ ጸለይንላት ነፃ ወጣች።

በግያምኑት ዘንድ ሁኔታው ለየት ያለ ነው። እውነተኛ ክርስቲያኖች ለዘላለሙ የክርስቶስ ሲሆኑ፥ የግያምኑ ሰዎች ግን የሰይጣን ሕጋዊ ንብረቶች ናቸው። ከክርስቶስ ጋር የግል ግንኙነት ስለሌላቸው፥ ቢገባቸውም ባይገባቸውም የሰይጣን ባሪያዎች ናቸው። የግያምኑ ሰዎች ከዚህ ባርነት ነፃ ሊወጡ የሚችሉት ንስሐ በመግባትና በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ ነው። ለዚህ ነው ኢየሱስ ለአይሁዶች፥ «ልጁ አርነት ቢያወጣችሁ በእውነት አርነት ተወጣላችሁ» ያለው (ዮሐ. 8፡36)። ሰዎችን ከኃጢአት፥ ከሞትና ከሰይጣን ባርነት ነፃ ሊያወጣ የሚችለው ኢየሱስ ብቻ ነው።

ቀጥተኛ የአጋንንት ጥቃት

በሰይጣን ቀጥተኛ ጥቃት ፊት ክርስቲያን ተስፋ የሌለው ምስኪን አይደለም (ኤፌ. 6፡13)። በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ እንደ ቀረበው ታሪክ፥ ክርስቲያን ቀጥተኛ የአጋንንት ጥቃት ሊያጋጥመው ምን ያደርጋል? ሰይጣን ልክ ኢዮብን (ኢዮብ 1፡2) እና ጳውሎስን (2 ቆሮ. 12፡7) እንዳጠቃው፥ አንዳንድ ጊዜ በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ፈቃድ አማኞችን የግጥቃት ኃይል አለው። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ፥ ክርስቲያኖች በሰይጣንና አጋንንቱ ላይ ሥልጣን ተሰጥቶአቸዋል (ኤፌ. 1፡19-22፤ 2፡6)። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ፥ «በጠላትም ኃይል ሁሉ

ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ» ብሏል (ሉቃ. 10:19)። ይህም አጋንንትን የማውጣትን ሥልጣን ጨምሮ ይዟል (ሉቃ. 9:1፤ 10:17)።

ከሰይጣንና አጋንንት ጋር ቀጥተኛ መንፈሳዊ ተግዳሮት በምናደርግበት ጊዜ፥ ሁለት አክራሪ አመለካከቶችን ማስወገድ አለብን። በመጀመሪያ፥ አንዳንድ ክርስቲያኖች ማንኛውንም ችግር በሰይጣን ላይ በማላከክ አጋንንት በማስወጣቱ ላይ ያተኩራሉ። ይህ የተዛባና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ አመለካከት ነው። እውነቱ ሲታይ ለዐበይት ችግሮቻችን ተጠያቂዎቹ የኃጢአት ተፈጥሮዎቻችን ናቸው (ሮሜ 7:14-23)። ኃጢአትን ተናዞ ማስወገድ ተገቢ ነው (ምሳሌ 28:13)። ይሁንና፥ የሰይጣን እውነታ ከኃጢአት ተፈጥሮአችን የተነሣ በነበሩን ችግሮች ላይ ከፍተኛ መጠን ያላቸውን አበሳዎች ይጨምራል።

ሁለተኛ፥ አንዳንድ ክርስቲያኖች፥ በተለይም የጌታን ሥራ በመቃወሙ በኩል፥ የሰይጣንን ህልውናና ተግባር ለይቶ ማወቅ ይሳናቸዋል። ብዙ ክርስቲያኖች ሰይጣን በክርስቶስ መስቀል ላይ በይፋ ስለ ተሸነፈ በዓለም ላይ ይህን ያህል ብርቱ ወይም ኃይለኛ አይደለም ብለው ያስባሉ። ይህ እውነት አይደለም። እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ከሰይጣን ጋር የሚደረገው መንፈሳዊ ውጊያ ምን ያህል ከባድ እንደ ሆነ አይገነዘቡም። ከዚህም የተነሣ፥ የብዙ ችግሮችን ሰይጣናዊ ምንጭና የሚወገዱበትንም መንገድ አያውቁም። ክርስቲያኖች፥ በተለይም ወንጌሉን ወዳልደረሰበት ስፍራ ለማድረስ የሚጥሩ ሚሲዮናውያን፥ ብዙውን ጊዜ ከአጋንንት ቀጥተኛ ጥቃት ይደርስባቸዋል። አንዳንድ ጊዜም ራሳቸውን ለመከላከል ታዳጊ የሌላቸው ይመስላሉ። ክርስቲያን ለእንዲህ ዓይነቶቹ ጥቃቶች ምን ሊያደርግ ይችላል?

ኤፌሶን 6:13 የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ስለ መልበስ ይናገራል። የእግዚአብሔር አገልጋዮች በቀጥታ የአጋንንት ጥቃት ወይም ተቃውሞ ሊደርስባቸው፥ ኢየሱስ በምድረ በዳው ፈተና ሰይጣንን ባራቀበት መንገድ፥ እንዴት እነዚህን መናፍስት መጋፈጥና መቃወም እንዳለባቸው ማወቅ አለባቸው (ማቴ. 4:10)። ይህ ሁኔታ የኃይል ተግዳሮት በመባል ይታወቃል። ይህም በእግዚአብሔር ኃይልና በሰይጣን ኃይል መካከል የሚካሄድ ተግዳሮት ነው። በብሉይ ኪዳን ሙሴ የግብፅን አረማዊ ቄሶች ከአጋንንታዊ ምትሐት ጋር በተቃወመበት ጊዜ ለኃይል ተግዳሮት ጥሩ ምሳሌ የሚሆን ትዕይንት ተፈጽሞአል (ዘጸ. 7:11)። ወደ እባብነት በተቀየረው የእግዚአብሔር በትር እግዚአብሔር እነዚህን አጋንንታዊ

ኃይሎች አሸንፎአል (ዘጸ. 7፡12)። ሌላው ደግሞ ኤልያስ በቀርሜሎስ ተራራ ከአረማዊ የበዓል ነቢያት ጋር ያደረገው ነው። በዚህ ሁኔታ እግዚአብሔር በኤልያስ ጸሎት አማካኝነት፥ በነቢያቱ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚገኙትን የጨለማውን ኃይላት አሸንፎአል (1 ነገሥት 18፡21-40)።

በአዲስ ኪዳን፥ ኤልማስ የተባለው አይሁዳዊ የሐሰት ነቢይ የወንጌሉን ስብከት ለማደናቀፍ በመሞከሩ፥ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን የዓይነ-ስውርነት ፍርድ አውጀበታል (የሐዋ. 13፡10-12)። እንዲሁም፥ በፊልጵስዩስም ለወንጌሉ ስርጭት እንቅፋት ከነበረችው ዕድል ተንባይ ልጃገረድም አጋንንትን አስወጥቷል(ሐዋ. 16፡16-18)።

ክርስቲያኖች በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡27 እንደ ተገለጸው፥ በመንፈሳዊ ሁኔታ ከክርስቶስ ጋር የተጣመሩ በመሆናቸው፥ በሰይጣንና በክፉ መላእክቱ ላይ የክርስቶስ ኃይል አላቸው። ይህም ክርስቲያኖችን በሁሉም የጨለማው ሥልጣናትና ኃይላት ላይ የበላይ ያደርጋቸዋል (ኤፌ. 1፡20-21፤ 2፡6)። መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር ወዳለው ዕርቅ የምናመጣ የክርስቶስ አምባሳደሮች እንደ ሆንን ይገልጻል (2 ቆሮ. 5፡20)። አምባሳደር በሌላው አገር መንግሥቱን የሚወክል ሕጋዊ አካል ነው። እኛ ለዚህ ዓለም የኢየሱስ ክርስቶስ ሕጋዊ ወኪሎች ነን። በሕጋዊ ጉዳዮች ላይ በሚናገርበት ጊዜ፥ አምባሳደር የአገሩን መንግሥት የበላይ አካል ወክሎ ይናገራል። በእንዲህ ዓይነት ሕጋዊ ንግግሮች፥ የእርሱ ቃላት ከአገሩ መንግሥት የበላይ አካል እኩል ሥልጣን አላቸው። ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዓለም እግዚአብሔርን ወክላ ትናገራለች። ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በመስማማት የሚነገሩ የእግዚአብሔር ቃላት የራሱ የእግዚአብሔርን ያህል ሥልጣን አላቸው (ማቴ. 18፡18-20)።

በሉቃስ 10፡17፥ 70ዎቹ የክርስቶስ ተከታዮች ይኸው የክርስቶስ የውክልና ሥልጣን እውነት በመሆኑና አጋንንትም በኢየሱስ ስም ሊታዘዙላቸው በመቻላቸው የተደነቁ ይመስላሉ። በዚህ የውክልና ሥልጣን ክርስቲያኖች አጋንንት የማስወጣት ሥልጣን አላቸው (ማቴ. 12፡29፤ 18፡18-20፤ ሉቃስ 10፡19)። በመንፈሳዊ ውጊያ አጋንንት በኢየሱስ ስም እስኪወጡ ድረስ፥ ከባድ ችግር የማይፈታባቸው አጋጣሚዎች አሉ (የሐዋ. 16፡18)። በተለይ ወንጌል ለመጀመሪያ ጊዜ ብሚሰበክባቸው ሕዝቦች አካባቢ ይህ እውነት ነው። ሰይጣን ግዛቱን ያለ ውጊያ አይለቅም።

በተጨማሪም፥ አጋንንት ከክፉ መናፍስት ጋር በተዛመዱ ወይም ምትሐታዊ ልምምዶች፥ በኃጢአት ሱሶች፥ ወይም በልጅነት ጊዜ በሚፈጸሙ አላግባብ ተግባራት ሳቢያ፥ በሰው ሕይወት ውስጥ ሲሰለጥኑ ማስወጣቱ አስፈላጊ ይሆናል። በእንደዚህ ዓይነት አጋጣሚዎች ወቅት፥ ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ከሚፈጸም ኃጢአትና ዓመፅ የተነሣ ኃይል እንዳለው ልብ ማለቱ በጣም አስፈላጊ ነው። ሰዎች በሕይወታቸው ውስጥ ያለውን ኃጢአት ለመናዘዝና ለማስወገድ ፈቃደኛ ካልሆኑ፥ አጋንንት ለማስወጣት መሞከሩ ከንቱና ብዙውን ጊዜም አደገኛ ነው (የሐዋ. 19:16)። አጋንንት የሚይዙአቸውን ሰዎች የሚያውቁ ሲሆኑ፥ የሚለቁትም ኃጢአታቸውን በእውነተኛነት ተናዝዘው የሚተዉትን ብቻ ነው። የሕፃናትን መጠቃት በተመለከተ፥ አጋንንት ገብቶባቸው ኢየሱስ ነፃ ካወጣቸው ሰዎች አንዳንዶቹ ልጆች እንደ ነበሩ መረዳቱ አስፈላጊ ነው (ማር. 9፡17-21)።

ከሰይጣንና አጋንንት ጋር በቀጥታ መገዳደር በጣም አደገኛ ሊሆን ይችላል (የሐዋ. 19፡14-16)። ይህ ተግባር በግለሰብ ክርስቲያኖች ሳይሆን፥ በቤተ ክርስቲያን ምእመናን በሙሉ ወይም በክርስቲያኖች ቡድን ቢከናወን መልካም ነው። ቡድኑና ሁኔታው ያሳሰባቸው ወገኖች ሁሉ፥ ስለ ጥበቃውና ማዳኑ እግዚአብሔርን እየጠሩ ባለማቋረጥ መጸለይ አለባቸው [መዝ. (50)፡15፤ ማቴ. 6፡13]። በሚጸልየው ቡድን ውስጥ የሚገኘውን ማንኛውንም ግልጽ ኃጢአት መናዘዝና መተው አስፈላጊ ነው። አንደኛው ቡድን እየጸለየ ሌላኛው አጋንንት ለማስወጣት እንዲችል፥ በሁለት ቡድኖች መከፋፈሉ መልካም ነው። አጋንንት የሚያስወጡ ክርስቲያኖች ለጌታ የምስጋና መዝሙሮችን መዘመር አለባቸው [መዝ. (96)፡1-9]። ጌታ ሕዝቡ በሚያመሰግነው ስፍራ ስለሚገኝ፥ አጋንንት ለኢየሱስ ምስጋና በሚቀርብበት ስፍራ ሊቆዩ አይችሉም [መዝ. (22)፡3፤ ማቴ. 18፡20]።

ለመንፈሳዊ ውጊያ መንፈሳዊ መሣሪያዎች

መንፈሳዊ ጦርነትን ለመዋጋት፥ ክርስቲያኖች መንፈሳዊ መሥሪያዎችን መጠቀም አለባቸው። ለእንዲህ ዓይነቱ ጦርነቱ ሥጋዊ መሣሪያዎች ጥቅም የላቸውም። መንፈሳዊውን ጦርነት በሥጋዊ መሣሪያዎች ለመዋጋት ለተደረገው ጥረት ታሪክ አሳዛኝ ምሳሌ የሚሆኑን የመስቀል ዘመቻዎች ናቸው። የመስቀል ዘመቻዎች ከ1095 እስከ 1272 ዓ.ም. ድረስ፥ በአውሮፓ ክርስቲያን ወታደሮችና በሙስሊም ኃይሎች

መካከል በቅድስቲቱ ከተማ (በኢየሩሳሌም) የተደረጉ ጦርነቶች ናቸው። ክርስቲያኖቹ ሙስሊሞችን የክርስቶስ ቅድስት ከተማ ከሆነችው ኢየሩሳሌም ለማስወጣት የጦር ኃይሎችን መጠቀም እንዳለባቸው አድርገው አሰቡ። እነዚህ ጦርነቶች ለ177 ዓመታት ያህል ሲቆዩ፥ ከሁለቱም ወገኖች አያሌ ሰዎች ለሕልፈት ተዳርገዋል። በመጨረሻም፥ ሙስሊሞች ወደ ክርስትና እምነት ባለመምጣታቸው ኢየሩሳሌም ዳግም በሙስሊሞች እጅ ወደቀች። ከመስቀል ዘመቻዎች የተነሣ ሙስሊሞች እስካሁንም በክርስቲያኖች ላይ መራራ ጥላቻ አላቸው። ከዚህ ምን ልንማር እንችላለን?

የአውሮፓ ወታደሮች መንፈሳዊውን ጦርነት በሥጋዊ መሣሪያዎች ለመዋጋት በመሞከራቸው ትልቅ ስሕተት ፈጽመዋል። አንዳንድ ሰዎች ከታሪክ ባለመማራቸው ዛሬም ተመሳሳይ ነገሮችን ለማድረግ ይሞክራሉ። ይህንንም ሲያደርጉ፥ የእግዚአብሔርን ጠላቶች ለማጥፋት ሥጋዊ መሣሪያዎችን መጠቀሙ የእግዚአብሔር ፈቃድ ባለመሆኑ፥ ተመሳሳይ አሳዛኝ ውጤቶች ይከሰታሉ። ይልቁንም፥ ክርስቲያኖች ለጠላቶቻቸው እንዲጸልዩ ታዝዘዋል (ማቴ. 5፡44)።

ጴጥሮስ የኢየሱስን ደኅንነት ለመጠበቅ ሥጋዊ መሣሪያ ለመጠቀም ሲፈልግ፥ ጌታ ሰይፉን ወደ ሰገባው እንዲመልስ ነግሮታል (ዮሐ. 18፡10-11)። ጠላቶቹ በከበቡት ጊዜ፥ ኢየሱስ እነርሱን ለመቃወም ሥጋዊ ኃይሎችን አልተጠቀመም፤ ምንም እንኳ ይህንኑ በቀላሉ ለማድረግ ቢችልም። ስለ ሆነም፥ ክርስቶስ ለጴጥሮስ የተናገረውን ልብ ልንል ይገባል፡- «ሰይፍ የሚያነሡ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉና ሰይፍህን ወደ ስፍራው መልስ» (ማቴ. 26፡52)።

ለመንፈሳዊ ጦርነት ሥጋዊ መሣሪያዎች ጠቃሚ አገልግሎት ያሚይሰጡት፥ እውነተኞቹ ጠላቶች ሥጋና ደም የለበሱ ሰዎች ሳይሆኑ፥ የክፋት መንፈሳዊ ኃይላት (የክፋት መላእክት) በመሆናቸው ነው (ኤፌ. 6፡12)።

መ. የመንፈሳዊ ጦር ዕቃዎች ምንድን ናቸው? እንዴትስ እንጠቀምባቸዋለን?

በተለይ በመንፈሳዊ ውጊያ ላይ በሚያተኩረው ምንባብ ውስጥ (ኤፌ. 6፡10-19)፥ መንፈሳዊ መሣሪያዎች (የጦር ዕቃዎች) እንደሚከተለው

ተዘርዝረዋል፡- እውነት፥ ጽድቅ፥ የሰላም ወንጌል፥ እምነት፥ ደኅንነት፥ የእግዚአብሔር ቃልና ጸሎት።

እውነት

ክርስቲያኖች የሰይጣንን ውሸት ለማስወገድ «በእውነት መቀነት እንዲታጠቁ» ተነግሯል (ኤፌ. 6፡14)። ክርስቲያን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘውን የእግዚአብሔርን እውነት ካጠናና ከተረዳ፥ ሰይጣን በዓለም የእሴቶች ዘይቤ፥ ክርስቲያናዊ ባልሆኑ ሃይማኖቶችና በሌሎችም ሁኔታዎች በሚያቀርባቸው ውሸቶች በቀላሉ አይታለልም።

ጽድቅ

ክርስቲያን ከሚፈትነው ኃጢአት ልቡን ለመጠበቅ፥ «የጽድቅን ጥሩር» እንዲለብስ ተመክሯል (ኤፌ. 6፡14)። ክርስቲያን ሰይጣንን ሊታወም የሚችለው ንጹሕና ቅዱስ ሆኖ ለእግዚአብሔር የሚገዛ ልብ ሲኖረው ብቻ ነው። ክርስቶስ በምድረ በዳ ከሰይጣን ጋር በተገዳደረ ጊዜ ያደረገው ይህንኑ ነው። ለብሉይ ኪዳን በመታዘዝ ለእግዚአብሔር ተገዝቶአል (ማቴ. 4፡4-10)። ስለ ሆነም፥ ክርስቶስ ከሰይጣን ጋር በነበረው ተግዳሮት «የጽድቅን ጥሩር» ለብሶአል።

ኢየሱስ ለአብ በነበረው የመገዛት ስፍራ፥ ሰይጣንን በመታወም አስወግዶታል (ማቴ፡ 4፡10-11)። ጸሎታችን ከንጹሕ ልብ የማይመነጭ ከሆነ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምላሽ አያገኝም (ኢሳ. 59፡1-2)። ልባችን ንጹሕ ካልሆነ፥ ሁኔታውን ልንለውጥ እንችልም። «በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው» (1 ዮሐ. 1፡9)።

የሰላም ወንጌል

በሰላሙ ወንጌል በመዘጋጀት እግሮቻችን ተጫምተው እንዲቆሙ ታዝዘናል። ጫማን ወደ አንድ ስፍራ ለመሄድ እንጠቀማለን። ክርስቲያን እምነትን መጠበቅ ወይም ራሱን ከሰይጣን መጠበቅ ብቻ ሳይሆን፥ የሰላሙን ወንጌል ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ለሌላቸውና ከክርስቶስም ጋር ግላዊ ግንኙነት ላላደረጉ ሰዎች በትጋት ማዳረስ አለበት።

እምነት

ክርስቲያን የሰይጣንን ነበልባልማ ፍላጻዎች ለማጥፋት የእምነትን ጋሻ እንዲያነሣ ተመክሯል (ኤፌ. 6፡16)። እምነት ከሰይጣን ጥቃቶች

የሚጠብቀን የመከላከያ መሣሪያ ነው። እነዚህ የሚንበለበሉ ፍላጻዎች ተስፋ በማስቆረጥ፥ በመጥፎ ዜናና በችግሮች፥ በስደት፥ በበሽታ፥ በአደጋ፥ በመንጀል፥ በጋዘንና በሌሎች በርካታ መልኮች ሊመጡ ይችላሉ። በሁሉም አጋጣሚ፥ እነዚህን ፍላጻዎች ለማቆም የእምነትን ጋሻ እንድናነሣ ተነግሮናል። ሰይጣን በሚያጠቃን ጊዜ እነዚህ ችግሮች ወደ አእምሮአችን ከሚያመጡአቸው ጥርጣሬዎችና ፍርሃቶች ይልቅ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች ማመን አለብን።

እምነታችን በአያሌ መንገዶች ሊጠነክር ይችላል። ሮሜ 10፡17፥ «እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው» ይላል። የእግዚአብሔርን ቃል ስናጠናና ከዚህ ቀደም በእርሱ ያመኑትን አማኞች እንዴት እንደ ረዳቸው ስንመለከት፥ እምነታችን ሊጠነክር ይችላል። የቀደሙትን አማኞች ለመርዳት ፈቃደኛ ከነበረ፥ ዛሬም በችግራችን እኛንም ለመርዳት ፈቃደኛ መሆን እንዳለበት መረዳት እንጀምራለን።

እምነታችንን ለማሳደግ ሁለተኛው መንገድ፥ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች ተግባራዊ ማድረግ ነው። እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን ሲፈጽም ስናይ እምነታችን ያድጋል። ለምሳሌ፥ በአስቸጋሪ ውሳኔ ምን ማድረግ እንዳለብህ ጥያቄ አለህ? እግዚአብሔር ለእንዲህ ዓይነቶቹ ውሳኔዎች ጥበብ (ያዕ. 1፡5) እና ምሪት [መዝ. (32)፡8] እንደሚሰጥህ ተስፋ ሰጥቶሃል። ለምትፈልገው ጥበብና ምሪት እግዚአብሔርን ስትተማመን፥ እግዚአብሔር የምትፈልገውን ጥበብና ምሪት ሲሰጥህ ታያለህ። ይህንንም ስትመለከት፥ በሚቀጥለው ጊዜ ለምትወስነው ውሳኔ በእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች እንድትታመን እምነትህ ይጠነክራል። ሌሎችንም የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች ትኩረት ሰጥተህ ስትጠቀምባቸው ተመሳሳይ ውጤት ይገኛል።

እምነታችን ሊያድግ የሚችልበት ሦስተኛው መንገድ፥ እግዚአብሔር ጸሎታችንን የመለሰበት ሁኔታ በመዘርዘር የተጻፈበትን የማስታወሻ ደብተር መመልከት ነው። የቀደሙትን ጸሎቶች በመመለስ እግዚአብሔር ያሳየንን ታማኝነት ከተጻፈው ደብተር ስንመለከት፥ ለአዳዲስ ጉዳዮች በምናቀርበው ጸሎት እምነታችን ይጠነክራል። ኢየሱስ፥ «የጸለያችሁትን የለመናችሁትንም ሁሉ እንዳገኛችሁት እመኑ፥ ይሆንላችሁማል» ብሏል (ማር. 11፡24)።

ደኅንነት

«የመዳን ራስ ቁር» ጭንቅላትን ለመከላከል የሚደፋ ነው። ጭንቅላት ከሰውነት ሁሉ ዋነኛው ክፍል ነው። ጭንቅላት ከተበላሸ ጠቅላላ ሰውነት ይሞታል። የደኅንነት ዋስትና አእምሮአችንን ከማንኛውም ፍርሃት፥ ጥርጣሬ፥ መከራና አስቸጋሪ የሕይወት ገጠመኝ ይጠብቃል። ስለ ዘላለማዊ ደኅንነታችን እርግጠኞች ስንሆን፥ በዚህ ሕይወት የሚያጋጥመን ሁሉ ከቁብ የሚገባ አይሆንም። የምንሄድበትን የምናውቅ ስንሆን፥ ያንንም የሚለውጥ ሰው ወይም ኃይል የለም። ምድራዊ ሕይወታችን ሲያከትም፥ በሰማይ ለዘላለም ከጌታ ጋር እንደምንኖር እናውቃለን። የዘላለም ሕይወት ደስታ በመዝሙር (27)፡1 እንደሚከተለው ተገልጾአል፦ «እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው፤ የሚያስፈራኝ ማን ነው?» የኃጢአት ይቅርታ እንዳገኘንና ወደ መንግሥተ ሰማይም እንደምንሄድ እርግጠኞች ስንሆን፥ በሕይወታችን ጽኑዎችና ዓላማ ያለን እንሆናለን፤ ምክንያቱም ለምንሰማራበት ግብ አለንና። ወደ ክብር የምንገባበት የምረቃ ዕለት አለ። በመሆኑም፥ አእምሮአችን በመዳን ቁር ይጠበቃል።

የእግዚአብሔር ቃል

የእግዚአብሔር ቃል «የመንፈስ ሰይፍ» ተብሏል (ኤፌ. 6፡17)። ሰይፍ፡ ጠላትን ለማጥፋት የሚያገለግል የማጥቂያ መሣሪያ ነበር። ጠላቶቻችን፥ ችግሮች ቢሆኑ ሰዎች ወይም የጨለማው ኃይላት፥ በእግዚአብሔር ቃል የተስፋ ቃሎች ይሸነፋሉ። እግዚአብሔር በሕይወት ውስጥ ለምንጋፈጠው ችግር ሁሉ መፍትሔ የሚሆኑትን መመሪያዎችና የተስፋ ቃሎች በቃሉ ውስጥ ሰጥቶናል። የእግዚአብሔር ቃል ለኑሮአችን የመመሪያ መጽሐፍ ነው።

ጸሎት

ከርስቲያን ዘወትር መጸለይ እንዳለበት ተገልጾአል (ኤፌ. 6፡18)። ጸሎት ለምንጋፈጠው ሁኔታ ሁሉ የእግዚአብሔርን መንፈስና የእግዚአብሔርን መላእክት እርዳታ ያስገኝልናል። በብዙ መዝሙሮች መዝሙረኛው እግዚአብሔር ከጠላቶቹ እንዲያድነው ይጸልያል። እነዚህ ጸሎቶች ለእኛ ለምሳሌነት የተቀመጡልን ናቸው። ሁልጊዜም ከኃጢአት ተፈጥሮአችን፥ ከአሁኑ የዓለም ዘይቤና ከሰይጣን ጋር እንታገላለን። በመዝሙር (50)፡15 ጌታ፥ «በመከራ ቀን ጥራኝ፥ አድንህማለሁ አንተም

ታከብረኛለህ» ይላል። በመዝሙር (143)፡9 ጸሐፊው፥ «አቤቱ፥ ወደ አንተ ተማፅኛለሁና ከጠላቶቼ አድነኝ» ሲል ይጸልያል።

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ፥ «ከክፉ አድነን» ብለው እንዲጸልዩ አስተምሮአቸዋል (ማቴ. 6፡13)። እነዚህን ጸሎቶች እምነትና ትሕትና በተመላበት ልብ የምንጸልይ ከሆነ፥ እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን ርዳታ ይልክልናል። ጸሎት ከእግዚአብሔር ኃይል ጋር ያያይዘናል። ጸሎት ዓለምን የሠራውን እጅ ያንቀሳቅሰዋል። ለመጸለይ የማይቻልበት ሁኔታ የለም። በንጹሕ ልብ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስንጸልይ ደግሞ፥ እግዚአብሔር ሰምቶ ይመልሳል።

ለምን እንጸልያለን?

ሀ) ምክንያቱም ጸሎት በሁሉም ሁኔታ የእግዚአብሔርን እርዳታ ያመጣልናል [መዝ. 3፡3-4፤ (34)፡4፥ 6]።

ለ) ምክንያቱም ጸሎት የሰይጣን ኃይልና ሥራ ለመቃወም እግዚአብሔር የመረጠው መንገድ ነው (ማቴ. 6፡13፤ ኤፌ. 6፡12፥ 18)።

ሐ) ምክንያቱም ጸሎት እጅግ በሚያስፈሩ ሁኔታዎች ውስጥ ሰላምን የሚያስገኝ መንገድ ነው (ፊልጵ. 4፡4-7)።

መ) ምክንያቱም፣ ጸሎት የሌሎች ሰዎችን ልብና አመለካከት የመለወጫ መንገድ ሊሆን ይችላል (ነህ. 2፡4-8)።

ሠ) ምክንያቱም ጸሎት ለሥጋዊና ስሜታዊ ሕመም የመፈወሻ መንገድ ሊሆን ይችላል (ያዕ. 5፡14-15)።

ረ) ምክንያቱም ጸሎት መሰናክሎችንና ግርዶሾችን ሊያስወግድ ይችላል (ማር. 11፡23-24)።

ሰ) ምክንያቱም አንድ ሰው ተስፋ በሚቆርጥበትና በሚሸነፍበት ጊዜ ጸሎት ብርታትንና ጥንካሬን ሊያመጣ ይችላል (ቆላ. 1፡9-11)።

ትሕትና

የመጨረሻው የመንፈሳዊ ውጊያ ገጽታ ትሕትና ነው። ትሕትና የትዕቢት ተቃራኒ ነው። ክርስቲያን በጌታ ፊት ራሱን እንዲያዋርድ ታዝዞአል (ያዕ. 4፡10፤ 1 ጴጥ. 5፡6)። በዚህ መንገድ፥ በትዕቢታቸው ምክንያት በሰይጣንና ራሳቸውን ከእግዚአብሔር የጠላትነት ኀራ

በሚፈርጁት ሁሉ ላይ ከመጣው ኩነኔ ልናመልጥ እንችላለን (1 ጢሞ. 3፡6)።

ማጠቃለያ

የክርስትና ሕይወት ቀላል መንገድ አይደለም። ክርስቲያን ከሦስት የነፍስ ጠላቶች ጋር ይዋጋል። እነዚህም ጠላቶች ዓለም (ብልሹ የዓለም እሴቶች ዘይቤ)፥ ሥጋ (የራሳችን ኃጢአተኛ ሰብአዊ ተፈጥሮ) እና ዲያብሎስ (ሌሎች በርካታ የወደቁ መላእክትን የሚቆጣጠረው ሰይጣን) ናቸው። ክርስቲያኖች በውስጣቸው የሚያድር የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ባይኖራቸው፥ ያለ ጥርጥር በእነዚህ ሦስት ታላላቅ ጠላቶቻቸው ይሸነፋሉ።

ይሁንና፥ ወንጌሉ ላለፉት ኃጢአቶች ይቅርታ በማስገኘቱ ብቻ ሳይወሰን፥ ባሁኑ ጊዜም ክርስቲያን በእነዚህ ሦስት ጠላቶቹ ላይ በድል እንዲመላለስ የሚረዳውን የእግዚአብሔር ኃይል የሚያስገኝ በመሆኑ፥ የምሥራች ነው። በእያንዳንዱ ጠላት ላይ ድልን ለመቀዳጀት የምንጠቀምባቸው መንገዶች ተመሳሳይ ናቸው። ክርስቲያን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚቃረኑትን አመለካከቶች፥ ባሕርያትና እምነቶች ሊያስወግድና በእነርሱም ምትክ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የታዘዙትን አመለካከቶች፥ ባሕርያትና እምነቶች ሊተካ ይገባዋል።

ኃጢአተኛ ሰብአዊ ተፈጥሮአችንን በተመለከተ፥ የኃጢአት ልማዶችን በመንፈሳዊ ልማዶች ልንተካ ይገባል። መመሪያው «ከክፉ ሽሽ» ተብሎ በመዝሙር (34)፡14 ላይ ተቀምጦአል። በጥንቃቄ በማሰላሰል፥ በጸሎትና በምክር፥ ይህ ጥቅስ ለኃጢአተኛ ተፈጥሮአችን ድካም ሁሉ ሊዛመድ ይችላል። ክርስቶስን ለመከተል ቁርጥ ውሳኔ ስናደርግ፥ መንፈስ ቅዱስ ራሳችንን ከማስደሰቱ በላይ እግዚአብሔርን ለማስደሰት እንድንሻ ይረዳናል። እንዲሁም፥ የራሳችንን ኃጢአተኛ ፍላጎቶች ከመከተል ይልቅ መንፈሳዊ ተግባራትንና ቃላትን እንድንከተል ይረዳናል።

በዙሪያችን ያለውን ብልሹ የዓለም የእሴቶች ዘይቤ በተመለከተ፥ ልባችንን ከዓለም ነገሮች ይልቅ በእግዚአብሔር ነገሮች ላይ ለማሳረፍ መግር አለብን። ክርስቶስን ለመከተል ቁርጥ ውሳኔ ስናደርግ፥ መንፈስ ቅዱስ ከዓለም ነገሮች በላይ የእግዚአብሔርን ነገሮች የምንፈልግበትን መሻት ይሰጠናል።

የዲያብሎስን ጥቃቶች በተመለከተ፥ የሰይጣን ኃይል ከልል በእግዚአብሔር ላይ የሚፈጸም ኃጢአትና ዓመፅ እንደ ሆነ ልንረዳ

ይገባል። ቅድስናን የሕይወታችን ዋንኛው ቀዳሚ ነገር ስናደርግ፥ ሰይጣን በሕይወታችን የሚያደርገው ተጽዕኖ ይከሽፍበታል። በሰይጣን ላይ ድል ለማግኘት የሚረዳን ቁልፍ ጥቅስ በያዕቆብ 4፡7 ላይ ይገኛል፡- «እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል።»

ክርስቲያን እንደ ጠንቋይ ወይም አጋንንታዊ ርግማን የመሳሰሉ ሰይጣናዊ ጥቃቶች በቀጥታ ሲሰነዘሩበት ምን ሊያደርግ ይገባል? ለእንደዚህ ዓይነት መንፈሳዊ ጥቃቶች በአዲስ ኪዳን ለክርስቲያኑ የመንፈሳዊ ውጊያ መሣሪያዎች (የጦር ዕቃዎች) ተሰጥተውታል። ለአጋንንት ቀጥተኛ ጥቃቶች እነዚህን መሣሪያዎች መጠቀም ይቻላል። ከእነዚህ መሣሪያዎች ሦስቱ የእግዚአብሔር ቃል የተስፋ ቃሎች፥ ጸሎትና እምነት ናቸው። በእግዚአብሔር ቃል የተስፋ ቃሎች መሠረት፥ ክርስቲያኖች አጋንንትን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የማስወጣት ሥልጣን አላቸው። በጸሎትና በእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች በማመን፥ የዲያብሎስ ጥቃቶች ሊረቱ ይችላሉ።

በምዕራፍ 12 ላይ የተመሠረቱ የመወያያ ጥያቄዎችና መልመጃዎች

1. ለውድቀት በሚስበን የራሳችን የኃጢአት ተፈጥሮ ላይ ዘላቂ ድል ለማግኘት ልናደርጋቸው የሚገቡን ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው?

2. ክርስቲያን ከመመኘት ነፃ ለመሆን ከፈለገ፥ ምን ውሳኔ ሊያደርግ ይገባል?

3. በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ የሚያገለግሉትን ሰባት መሣሪያዎች ለልጆች ለማስተማር፥ እያንዳንዱ የውጊያ መሣርያ የተጻፈበትን ልብስ አዘጋጅ። ይህም እውነት የሚል የተጻፈበትን ቀበቶ፥ ደኅንነት የተጻፈበትን ቆብ፥ የእግዚአብሔር ቃል የተጻፈበትን ሰይፍ፥ መዘተ. ማካተት አለበት።

4. ሰይጣንን ለመቋቋም ክርስቶስ ራሱ ያደረገውና ክርስቲያንም ሊያደርግ የሚገባው ነገር ምንድን ነው?

5. ኤልያስ በቀርሜሎስ ተራራ ከበዓል ነቢያት ጋር ያደረገው ግድድር እንዴት የኃይል ተግዳሮት እንደሚሆን ግለጽ።

6. ሦስት ወይም አራት አባላት በሚገኙባቸው ትናንሽ ቡድኖች ተከፋፈሉ። እያንዳንዱ ቡድን እግዚአብሔር በጸሎት አማካኝነት ሕዝቡን እንደሚረዳ የሚያስባቸውን መንገዶች ሁሉ ይዘርዝር።

7. በቡድኑ ውስጥ እያንዳንዱ ሰው የጸሎት ጥያቄዎች መመዝገቢያ ደብተር መጠቀም ይጀምር። በአንደኛው ዓምድ «ለጸሎት የቀረቡ ጉዳዮች» የሚል ይጻፍ። በቀጣዩ ዓምድ፥ «እግዚአብሔር ጸሎቱን የመለሰበት መንገድ» የሚል ይጻፍ።

8. በመጽሐፍ ቅዱስ አጋንንት ሰዎችን እንደ ያዘ የተጠቀሰባቸው ብዙ አጋጣሚዎች አሉ። ሰዎች በአጋንንት እንዲያዙ ያደረጉ ሁኔታዎች ምን ምን እንደ ሆኑ በክፍል ውስጥ ተወያዩ።

9. አዲስ ክርስቲያን እምነቱን ሊያሳድግ የሚችልባቸውን አንዳንድ መንገዶች ዘርዝር።

10. ሰው በአጋንንት እንደ ተያዘ የሚታወቅባቸው አንዳንድ ምልክቶች ምንድን ናቸው?

11. ክርስቲያን በአጋንንት መያዝን ከአእምሮ በሽታ እንዴት ሊለይ ይችላል?

SUGGESTED FOR FURTHER READING

Duewel, Wesley L. Mighty Prevailing Prayer. Grand Rapids, Michigan: Zondervan, 1990.

Duewel, Wesley L. Touch The World Through Prayer. Grand Rapids, Michigan: Zondervan, 1986.

Foster, Richard. Prayer. London: Hodder, 1992.

Parker, Russ. The Occult. Leicester: Inter Varsity Press, 1989.

Sherman, Dean. Spiritual Warfare. Seattle, Washington: Frontline Communications, 1990.

Warner, Timothy. Spiritual Warfare. Wheaton, Illinois: Crossway Books, 1991.

ምዕራፍ 13

በባህላዊ እምነቶችና ልምምዶች ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት

«ከስድስት ቀንም በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስንና ያዕቆብን ወንድሙንም ዮሐንስን ይዞ ወደ ረጅም ተራራ ብቻቸውን አወጣቸው። በፊታቸውም ተለወጠ፥ ፊቱም እንደ ፀሐይ በራ፥ ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ። እነሆም፥ ሙሴና ኤልያስ ከእርሱ ጋር ሲነጋገሩ ታዩአቸው። ጴጥሮስም መልሶ ኢየሱስን፦ ጌታ ሆይ፥ በዚህ መሆን ለእኛ መልካም ነው፤ ብትወድስ፥ በዚህ ሦስት ዳስ አንዱን ለአንተ አንዱንም ለሙሴ አንዱንም ለኤልያስ እንሥራ አለ» (ማቴ. 17፡1-4)።

ያኩቡ ዘመዶቹን ጎብኝቶ እየተመለሰ ነበር። የእርሻውን ሥራ በማከናወኑ ረገድ እገዛ ሲያደርግ፥ ለሦስት ሳምንታት ያህል በአጎቱ መንደር ሰንብቶ ነበር። ወደ መንደሩ ሊደርስ በተጠጋ ጊዜ፥ አንዲት አነስተኛ የምንጭ ውኃ ዘንድ ቀረበ። ምንጭዋንም ሲያቋርጥ ለረዥም ዓመታት የሚያውቃቸውን ባባ ይኑሳ የተባሉ ሽማግሌ አገኘ። ለሽማግሌው ሰላምታ ከሰጠ በኋላ፥ ስለ ቤተሰቡ ደኅንነት ጠየቃቸው።

የሚገርመው ባባ ይኑሳ ለሰላምታው አጸፋ ሊመልሱለት አልቻሉም። ያኩቡ ደጋግሞ ቢያናግራቸውም መልስ አልሰጥ አሉት። ምን እንደ ነካቸው ቢጠይቅ እንኳ፥ ሽማግሌው ባባ ይኑሳ ዝም አሉ። ያኩቡ በጣም ተጨነቀ። ይሁንና ወደ መንደሩ የሚያደርገውን ጉዞ ቀጠለ። ወደ ቤቱም በደረሰ ጊዜ፥ ያጋጠመውን ለቤተሰቡ ካጫወተ በኋላ፥ በይኑሳ ቤተሰብ ላይ የደረሰ የሚያውቁት ችግር እንዳለ ጠየቃቸው። የያኩቡ ቤተሰቦች በመገረም ትክ ብለው ተመለከቱትና፥ «አ፥ አይፈረድብህም። ለሦስት ሳምንታት እዚህ ስላልነበርህ ያወቅኸው ነገር የለም። ከሦስት ቀናት በፊት ባባ ይኑሳን ቀብረናቸዋል!» አሉት።

ይህ የያኩቡ ታሪክ ባህላዊ እምነቶችንና ልምምዶችን በተመለከተ አያሌ ጥያቄዎችን ያስነሣል። እውነተኛውና እውነት ያልሆነው የትኛው ነው? በአፍሪካ ባሕላዊ ሃይማኖቶች ውስጥ ትክክል የሆኑና ትክክል ያልሆኑ እምነቶች የትኞቹ ናቸው?

በአፍሪካ ባህላዊ ሃይማኖት፥ በሕያዋንና በቅርቡ በሞቱት (ሕያዋን ሙታን) መካከል በጣም አስፈላጊ የሆነ ግንኙነት አለ። የባህላዊ ሕይወት አያሌ ገጽታዎች በሕያዋንና በሕያዋን ሙታን መካከል የሚገኘውን ልዩነት ይመለከታሉ። በብዙ የሕዝብ ቡድኖች እምነት፥ የነሳው ማኅበራዊና ግብረ-ገባዊ ጽኑነት ከዚህ በፊት ሞተው ወደ ቅድመ-ትውልዳዊ መንፈስነት ማዕረግ የተለወጡ የነሳ መሪዎች ኃላፊነት ተደርጎ ይወሰዳል። ከነሳው ባህላዊና ማኅበራዊ ሥርዓት ጋር በሚዛመዱ ጉዳዮች የቅድመ-ትውልዶችን ፈቃድ ችላ ማለት ትልቅ ጥፋት ነው።

ኢየሱስ መልኩ በተለወጠበት ተራራ ላይ ከሙሴና ከኤልያስ ጋር መነጋገሩ፥ የሞቱት ሰዎች ከሥጋዊ ሞት በኋላ ንቁዎች ሆነው እንደሚኖሩ የሚያስተምረውን የባህላዊ ሃይማኖቶች እምነት በግልጽ ያጠናክራል። ሙሴ ከክርስቶስ ልደት 1200 ዓመታት ቀደም ብሎ ሲሞት፥ ኤልያስም ከክርስቶስ ልደት ከ700 ዓመታት በፊት በሕይወት ሳለ ተወስዷል። ይሁንና፥ በዚህ ጊዜ ሐዋርያው ያዕቆብ፥ ጴጥሮስና ዮሐንስ ሙሴና ኤልያስ ከኢየሱስ ጋር ሲነጋገሩ ተመለከቱ። በመሆኑም፥ ሥጋዊ ሞት ወደ መንፈሳዊ ዓለም መሸጋገሪያ ድልድይ እንደ ሆነ የሚያመለክተው የአፍሪካውያን አመለካከት ከእግዚአብሔር ቃል አንጻር እውነት ነው። ይሁንና፥ ከመንፈሳዊ ዓለም እውነታ የሚመነጩ አንዳንድ የባህላዊ ሃይማኖት እምነቶችና ልምምዶች ፍጹም ስሕተት በመሆናቸው፥ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ከእግዚአብሔር ጋር ግላዊ ግንኙነት እንዳያደርጉ እንቅፋት ይሆናሉ።

ሰይጣን ሰዎችን የሚያታልልባቸው ብዙ መንገዶች አሉት። በዓለም ሁሉ ክርስቲያናዊ ባልሆኑ ሃይማኖቶች፥ መጽሐፍ ቅዱስ በሚያስተምረን የእውነት ብርሃን እየተረዳን ልንገነዘባቸው የሚገቡ አንዳንድ ልምምዶች አሉ። እነዚህም ልምምዶች ከሙታን ጋር መነጋገርን፥ ነጭና ጥቁር ምትሐትን (መድኃኒት፥ ድግምት፥ ጥንቆላ)፥ በአጋንንት መያዝን፥ ሞራ ገላጭነትን (ያሁኑን ወይም የወደፊቱን ክስተቶች የመተንበይ መንገዶች)፥ የሽግግር ሥርዓቶችንና ሌሎችንም ይጨምራሉ። ሰዎች በተገለጸው ኃይል ወደ እነዚህ ልምምዶች ይሳባሉ። ሰዎች ዓለማቸውን ይቆጣጠሩ ዘንድ ኃይልን ይሻሉ።

ምንም እንኳ በዛሬዪቱ አፍሪካ የሕይወት ለውጥ እየታየ ቢሆንም፥ የባህላዊ እምነቶችና ልምምዶች ጥያቄ አሁንም በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው። ባህላዊ እምነቶች ሰዎች የእግዚአብሔርን እውነት እንዲገነዘቡ

የሚረዱባቸውና ሰዎችን ከእግዚአብሔር እውነት የሚያስቱባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው? መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሙታን መናፍስት ምን ይላል? ሰዎች ከሞቱ በኋላ ምን ይከሰትባቸዋል? እግዚአብሔር ሕያዋን ከሙታን ጋር እንዲያደርጉ የሚፈልገው ግንኙነት አለ? ያኩቡን ላጋጠመው ዓይነት ነገር የምንሰጠው ግብራሪያ ምንድን ነው? እንደ ሞራ ገላጭነት፥ ምትሐትና ምሥጢራዊ ኃይላት በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት ምንድን ነው? ክርስቲያን የሴት ልጅ ግርዛት የመሳሰሉትን የአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓቶች እንዴት ሊመለከት ይገባል? ምንም እንኳ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ብዙ ለመናገር የሚቻል ቢሆንም፥ ይህ መጽሐፍ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ይጥላል፦

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሙታን መናፍስት ምን ያስተምራል?

ለ. ክርስቲያን ከቅድመ-ትውልዶቹ ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት፥ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

ሐ. የሙታንን መናፍስት በተመለከተ፥ እውነቱ ምንድን ነው? በአጋንንት የመታለል ውጤቱ ምንድን ነው?

መ. በጋኔን ስለ መያዝ የመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት ምንድን ነው?

ሠ. የአጋንንት ተጽዕኖ የደረሰባቸውን ወይም በአጋንንት ቁጥጥር ሥር የወደቁትን ሰዎች ክርስቲያኖች እንዴት ሊረዱአቸው ይችላሉ?

ረ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መንግሥተ ሰማይና ሲኦል ምን ይላል?

ሰ. መጽሐፍ ቅዱስ ከሙታን ጋር ስለ መነጋገር ምን ይላል?

ሸ. በአካለ መጠን መድረሻ ባህላዊ ሥርዓቶች ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት ምንድን ነው?

ቀ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ምትሐት ምን ይላል?

በ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ምዋርተኝነት ምን ይላል?

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሙታን መናፍስት ምን ያስተምራል?

በአፍሪካ ብዙ የሕዝብ ቡድኖች የቅድመ-ትውልዶቻቸውን መናፍስት በተመለከተ ጠንካራ እምነቶች አሏቸው። ለሁሉም ነገዶች ማለት ይቻላል በሕያዋንና በሕያዋን ሙታን መካከል አስፈላጊ የሆነ ግንኙነት አለ።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሙታን ሁኔታና ከእነርሱ ጋር ስለሚኖረን ግንኙነት ምን ይላል?

በኢየሱስ፥ በሙሴና በኤልያስ መካከል የተደረገው ውይይት እንደሚገልጽልን፥ የሞቱ ሰዎች ንቁዎች ሆነው መኖር እንደሚቀጥሉ መናገሩ ትክክል ነው። በሕይወት ዘመናቸው የተፈጸመውን የሚያስታውሱ ሲሆን፥ ሙሴና ኤልያስ በቅርቡ በኢየሩሳሌም ከተማ ስለሚፈጸመው ሞቱ ከክርስቶስ ጋር የመነጋገራቸው እውነታ እንደሚገልጸው፥ ተጨማሪም እውቀት ያላቸው ይመስላል (ሉቃ. 9፡31)። ኢየሱስ ስለ ሀብታሙ ሰውዬና አልዓዛር በሉቃስ 16፡19-31 የተናገረው ታሪክ ከሞት በኋላ ስለሚሆነው ነገር ተመሳሳይ ግንዛቤ የሚያስጨብጠን ሲሆን፥ ስለ ሙታን ሁኔታ የሚያስረዳን ሌላም አስፈላጊ የሆነ መረጃ አለ። ለምሳሌ፥ ሀብታሙ ሰውዬ ሲሞት እግዚአብሔርን ባለማገልገሉ የፈጸመውን ትልቅ ስሕተት በጸጸት ያስታውስ ነበር። ስለ ስሕተቱ ለወንድሞቹ ይናገር ዘንድ አልዓዛር እንዲላክ በጣም ፈልጎአል (ሉቃ. 16፡25-28)። ይሁንና፥ ጥያቄው አዎንታዊ ምላሽ አላገኘለትም (ሉቃ. 16፡29-31)። በተራራው ላይ ሙሴና ኤልያስ ከኢየሱስ ጋር ባደረጉት ውይይት ውስጥ፥ ምንም እንኳ ጥንታዊዎቹን ነቢያት ቢመለከቱና ንግግራቸውንም ቢሰሙም፥ ሐዋርያቱ የተናገሩት ነገር አልነበረም።

እነዚህ ታሪኮች በመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ የቀረበውን እውነት ይገልጻሉ። እግዚአብሔር ሕያዋን ከሙታን ጋር እንዲነጋገሩ አይፈልግም። በዘዳግም 18፡10-11 ጌታ፥ «ሙታን ሳቢም በአንተ ዘንድ አይገኝ። ይህንም የሚያደርግ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነው» ሲል ያስጠነቅቃል። ይህ ማስጠንቀቂያ ለምን እንደ ተሰጠ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እንነጋገራለን።

በተጨማሪም፥ በሉቃስ 16፡19-31 የቀረበው ታሪክ በሞት ጊዜ በሕይወት ሳሉ እግዚአብሔርን ይወዱና ያገለግሉ የነበሩት ሰዎች መናፍስት ይህንኑ ካላደረጉት ጋር ለዘለቄታው እንደሚለያዩ ይገልጻል። አልዓዛር እግዚአብሔርን ይወድ የነበረ ድሀ ነበር። ሲሞት መላእክት ወደ መጽናኛ ስፍራ አጅበው ወሰዱት (ቁጥር 22፥ 25)። ሀብታሙ ራሱን ብቻ ይወድ ነበርና፥ ወደ ሥቃይ ስፍራ ተወሰደ (ቁጥር 23፥ 24)። በዚህ ስፍራ ኢየሱስ በሞት ጊዜ ሰዎች ከሰዎች እንደሚለዩና ኃጢአታቸው ያልተሰረየላቸው ሰዎች ለሥቃይ እንደሚወሰዱ የሚያስረዳ አሳዛኝ እውነት ገልጾአል።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ በሚገኝ አንድ ታሪክ፥ ንጉሥ ሳኦል ነቢዩ ሳሙኤል ከሞተ በኋላ ከመንፈሱ ጋር ለመነጋገር እንደ ፈለገ ተገልጸአል (1 ሳሙ. 28፡8-19)። እርሱ ራሱ በእግዚአብሔር ሕግ መሠረት ከዚህ በፊት ይሽው ልምምድ በእስራኤል እንዳይፈጸም የከለከለ በመሆኑ፥ ንጉሥ ሳኦል ሙትን በማማከሩ ትክክል ያልሆነ ተግባር መፈጸሙን ያውቅ ነበር (ዘሌ. 19፡31፤ 1 ሳሙ. 28፡9)። ሳኦል ከሙታን ጋር ለመነጋገር የፈለገው ከችግሩ የተነሣ ነበር (1 ሳሙ. 28፡15)።

የሳሙኤል መንፈስ ለሳኦል በታየ ጊዜ፥ ሳሙኤል እግዚአብሔርን መታዘዝ እንደ ነበረበት በመግለጽ ጠንካራ የኩነኔ ቃል ሰንዘረበት (1 ሳሙ. 28፡16-19)። እግዚአብሔር ሳሙኤል ሳኦልን በዚህ ባልተለመደ ሁኔታ እንዲያበረታታው ወይም እንዲረዳው ሳይሆን፥ እንዲኮንነው ፈቀደ። ከዚህ ታሪክ እግዚአብሔር ሕያዋን ከሙታን ጋር እንዲነጋገሩ እንደማይፈልግ ልንመለከት እንችላለን። በብዙ ባህላዊ ሃይማኖቶች እንደሚታሰበው፥ ከሙታን ጋር መነጋገር ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚመጣ የእርዳታ ወይም የማበረታቻ ምንጭ እንዳልሆነ እንመለከታለን።

የሚሞቱ ክርስቲያኖች ምን ይሆናሉ? ኢየሱስ በመሞት ሂደት ላይ ለነበረው ወንጀለኛ እንደ ተናገረው (ሉቃ. 23፡41-43) እና ጳውሎስም እንደሚለው (2 ቆሮ. 5፡1-8)፥ ክርስቲያኖች ሲሞቱ ክርስቶስ ወዳለበት ገነት (መንግሥተ ሰማይ) ይሄዳሉ። ሙታን ሁሉ ከመነሣታቸው በፊት በሚሆነው በዚህ የሽግግር ወቅት፥ አማኞች እርስ በርሳቸው የሚነጋገሩበትና የሚግባቡበት ሰማያዊ አካል ይሰጣቸዋል (2 ቆሮ. 5፡1-4)። ኢየሱስ በተራራ ላይ በተናገራቸው ጊዜ ጴጥሮስ፥ ያዕቆብና ዮሐንስ የሙሴንና የኤልያስን ሰማያዊ አካላት አይተው ንግግራቸውንም ሰምተዋል (ሉቃ. 9፡28-32)።

የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ክርስቲያኖች በሚሞቱበት ጊዜ በቀጥታ ከጌታ ጋር ለመኖር የሚሄዱት እጅግ በጣም ጥቂቶች (እነርሱም ካሉ) እንደ ሆኑ በመግለጽ የምታቀርበውን ትምህርት ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አይቀበሉም። ካቶሊኮች ክርሲቲያኖች በመጀመሪያ በእሳት ወደሚነጹበት የማጣሪያ ስፍራ ይወስዱና ከዚያ በኋላ ወደ መንግሥተ ሰማይ እንደሚገቡ ያስተምራሉ። ይህም ማጣሪያ ስፍራ «ፐርጋቶሪ» ("purgatory") በመባል ይታወቃል። ይህ አሳብ ከብዙ የአዲስ ኪዳን ትምህርቶች ጋር ይቃረናል። ጳውሎስ «ከሥጋ ተለይተን . . . በጌታም

ዘንድ ማደር ደስ ይለናል» ይላል (2 ቆሮ. 5፡8)። ጳውሎስ በተጨማሪም፥ ክርስቶስ ስለ እኛ ስለ ሞተ፥ በሥጋ ሙታን ወይም ሕያዋን ብንሆን ከክርስቶስ ጋር አብረን እንደምንኖር አስተምሮአል (1 ተሰ. 5፡10)። ኢየሱስ ከእርሱ አጠገብ በመስቀል ላይ ለተሰቀለው ሌባ፥ «ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ» ብሎታል (ሉቃ. 23፡43)። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እነዚህና ሌሎችም ጥቅሶች እንደሚያመለክቱት፥ ይቅርታ ያገኘ ኃጢአተኛ በሚሞትበት ጊዜ፥ በቀጥታ ክርስቶስ ወደሚገኝበት ወደ ገነት ይገባል።

ከክርስቶስ ጋር የሚያድን የግል ግንኙነት ሳያደርጉ የሚሞቱትስ ሰዎች? ኢየሱስ ራሱ ለአይሁዶች፥ «በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ አልኋችሁ እኔ እንደሆንሁ ባታምኑ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁና» ሲል ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ሰጥቷል (ዮሐ. 8፡24)።

የኃጢአትን ይቅርታ ሳያገኙ መሞት የሚያስከትለው ውጤት ምንድን ነው? በሀብታሙ ሰውዬና በአልዓዛር ታሪክ ውስጥ ኢየሱስ ከሞት በኋላ ምን እንደሚሆን ገልጾአል። የሁለት ሙታንን ሁኔታ ገልጾአል። ኢየሱስ ራስ ወዳድ ሆኖ እግዚአብሔርን ለማገልገል የሌሎችን ሰዎች ጉድለቶች ለመሙላት ግድ ያልነበረው ሀብታሙ ሰው ወደ ሥቃይ ስፍራ እንደ ተወሰደ ገልጾአል (ሉቃ. 16፡23-24)። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በሰው ዘር ላይ ስለሚመጣው የመጨረሻው ፍርድ ሲናገር፥ የእርሱ ያልሆኑት ሁሉ ወደ ሥቃይ ስፍራ እንደሚሄዱ ገልጾአል (ማቴ. 25፡31-46)።

ለ. ክርስቲያን ከቅድመ-ትውልዶቹ ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት፥ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

ብዙውን ጊዜ ባህላዊ ሃይማኖቶች በሕያዋንና በሕያዋን ሙታን መካከል ግንኙነቶችን ለማድረግ ይፈልጋሉ። እነዚህም ግንኙነቶች ሥርዓቶችንና ቅድመ-ትውልዶችን (አያት ቅድማያት) ለማርካት ወይም ለማግባባት የሚያደርጉትን መሥዋዕቶች ያጠቃልላሉ። በተጨማሪም፥ በሞራ ገላጭ ወይም መንፈሱ በያዛቸው ሰዎች አማካኝነት በቀጥታ በሚነገሩ ቃላት ከሙታን ጋር መነጋገርን ይጨምራሉ። እነዚህ ባህላዊ እምነቶች ሁልጊዜም ለማለት ይቻላል ሕያዋን ለምሪት፥ ለእርዳታ፥ ለእርምትና ለበረከት በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር ከሚመለከቱ ይልቅ፥ ወደ አያት ቅድማያቶቻቸው ወይም ወደ ሌሎች መናፍስት እንዲመለከቱ ያደርጋሉ። ይህንንም በማድረግ፥ እንዲህ ዓይነት ሰዎች እግዚአብሔር ከእርሱ በፊት

ሌላ ማናቸውም ዓይነት «አማልክት» እንዳይኖሩ የሰጠውን የመጀመሪያውን ትእዛዝ ይጥሳሉ (ዘጸ. 20፡3)።

የአያት ቅድማያት መናፍስት የሚካተቱባቸው ባህላዊ እምነቶችና ልምምዶች ከእግዚአብሔር አይደሉም። እነዚህ ሰይጣን ሰዎችን ለማሳሳትና ትእዛዛቱን በመጣሳቸው ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች እንዲወድቁ ለማድረግ የሚጠቀምባቸው ስውር ዕቅዶች አካል ናቸው። ከአያት ቅድማያት መናፍስት ጋር የሚዛመዱ እምነቶችና ልምምዶች፥ ብዙ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ከእግዚአብሔር ጋር የግል ግንኙነት እንዳያደርጉ አግደዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ሰው ከወላጆቹና በማኅበረሰቡ ውስጥ በዕድሜ ከገፉት ሰዎች ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት ምን ይላል? መጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ መመሪያ ይሰጠናል፡- «በሽበታሙ ፊት ተነሣ፥ ሽማግሌውንም አክብር፥ አምላክህንም ፍራ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ» (ዘሌ. 19፡32)። ይህ ከሙሴ ሕግ የተወሰደው ዓረፍተ ነገር ሰዎች ለሽማግሌዎች ሁልጊዜም አክብሮት መስጠታቸው ትክክልና በእግዚአብሔርም ፊት ደስ የሚያሰኝ እንደ ሆነ ይገልጻል። እንዲያውም፥ የዚህ ዓይነቱን አክብሮት ማሳየት ራሱ እግዚአብሔርን ከመፍራት ጋር በሆነ መንገድ መገናኘቱም ተጠቁሟል።

ሰው ከራሱ ወላጆች ጋር ስለሚኖረውስ ግንኙነት? ከአሥርቱ ትእዛዛት አምስተኛው፥ «እናትህንና አባትህን አክብር» ይላል (ዘጸ. 20፡12)። ይህ ትእዛዝ ሰዎች ሁሉ ወላጆቻቸውን ማክበራቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደ ሆነ ያሳያል። ወላጆቻቸውን በማክበርና ምክራቸውን በጥንቃቄ በመከተል ይህንን ሊፈጽሙ ይችላሉ (ምሳሌ 1፡8)። በሕይወት ለሚገኙ ወላጆቻቸው በመገዛትና የእግዚአብሔርን ቃል እንዲተላለፉ በማያደርጋቸው መንገድ ሁሉ ታዛዥነትን በማሳየት ይህንኑ ሊፈጽሙ ይችላሉ (ኤፌ. 6፡1፤ ቆላ. 3፡20)። ለወላጆቻቸው ሊሰጡ የሚችሉት እጅግ ከፍተኛ የአክብሮት ዓይነት መንፈሳዊ ባሕርይና ጠባይ ያለው ቅዱስ ሕይወት በመኖር ነው።

ሕያዋን ከሙታን ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነት መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? በሕይወት ለሚገኙ ወላጆቻችን ከተሰጡት መመሪያዎች አንዳንዶቹ የሞቱትን ከማክበርም ጋር ይዛመዳሉ። መንፈሳዊ ባሕርይና ጠባይ ያለው የተቀደሰ ሕይወት በመኖር፥ ለስማቸው አክብሮት በመስጠት፥ በምድር ላይ በሕይወት በነበሩበት ጊዜ የሠሩአቸውን

መልካም ሥራዎች በማከበርና ክርስቲያኖች ከነበሩ የእምነት ፈለጋቸውን በመከተል፥ ለሞቱት የቤተሰባችን አባላት አክብሮት ልንሰጥ እንችላለን።

ይሁንና፥ ክርስቲያኖች አያት ቅድማያቶቻቸውን ሲያከብሩ ወደ ባህላዊ ሃይማኖት እምነቶችና ልምምዶች እንዳይመለሱ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው። ክርስቲያናዊ ባልሆኑ ሃይማኖቶች በተለምዶ እንደሚደረገው፥ እግዚአብሔርን በማክበር ፈንታ አያት ቅድማያቶቻቸውን እንዳያከብሩ መጠንቀቅ አለባቸው። ክርስቲያን ለሕይወቱ ምሪት፥ እርምት፥ እገዛና በረከት ለማግኘት፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ወደ እግዚአብሔር ብቻ ሊቀርብ ይገባዋል። አንድ ሰው ችግር ሲገጥመው፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ወደ እግዚአብሔር አብ መጸለይ አለበት። አንድ ሰው ከራሱ ከእግዚአብሔር ሌላ የማንኛውንም አያት ቅድማያት፥ ሞራ ገላጭ፥ ወይም መንፈስ በረከት፥ ምሪት፥ ወይም እገዛ መፈለግ የለበትም። መዝሙረኛው በጥበብ፥ «ወደ ሌላ ለሚፋጠኑት መከራቸው ይበዛል፤ የቁርባናቸውን ደም እኔ አላፈስሰውም፥ ስማቸውንም በከንፈሬ አልጠራም» ሲል ይመክረናል [መዝ. (16) :4]።

የቤተሰባቸውን አባላት እንዲያከብሩ ቢጠየቁም፥ ሕያዋን ሙታንን ለማነጋገር ወይም የሙታን ዘመዶቻቸውን እገዛ ለማግኘት ከቱውንም መሞከር የለባቸውም (ዘዳ. 18:10-11)። እግዚአብሔር እነዚህ ሰዎች ለአያት ቅድማያቶቻቸው የምግብ ወይም የመጠጥ መሥዋዕት እንዲያቀርቡ አይፈልግም (ዘዳ. 26:14)። እንዲህ ዓይነት የምግብ ወይም የመጠጥ መሥዋዕት ማቅረብ ክርስቲያናዊ ሃይማኖቶች ያልሆኑትን የአረማውያን ልምምድ መከተል ነው። ይህም እግዚአብሔር የሚከለክለው የጣያት አምልኮ ዓይነት ነው (ዘዳ. 20:18)። በምዕራፍ 11 እንደ ተመለከተው፥ የዚህ ዓይነት መሥዋዕቶች ለአያት ቅድማያት መናፍስት ሲሠዉ፥ መሥዋዕቶቹን የሚቀበሉት ከቱውንም አያት ቅድማያቶች ሳይሆኑ አጋንንት ናቸው (ዘዳ. 32:16፥ 17፤ 1 ቆሮ. 10:19-20)።

እግዚአብሔር ሕዝቡ አያት ቅድማያቶችን ወይም ሌሎች ማናቸውንም መናፍስት በእግዚአብሔር ፊት ከሚያስቀምጡ ባህላዊ ሃይማኖቶች ጋር የሚያያዙትን ዕቃዎች እንዲያቃጥሉና እንዲያጠፉ አዝዞአል። በተጨማሪም፥ የዚህ ዓይነቶቹን እምነቶችና ልምምዶች ሙሉ ለሙሉ መተው አለባቸው። እግዚአብሔር ሕዝቡ የሆኑትን እስራኤላውያንን፥ «ነገር ግን እንዲህ አድርጉባቸው፤ መሠዊያቸውን አፍርሱ፥ ሐውልቶቻቸውንም ሰባብሩ፥ የማምለኪያ ዐፀዶቻቸውንም ቁረጡ፥ የተቀረጸውን ምስላቸውንም

በእሳት አቃጥሉ» ሲል አስጠንቅቆአቸዋል (ዘዳ. 7፡5)። እግዚአብሔር ይህን ትእዛዝ በዚያው ምዕራፍ ደግሟል (ዘዳ. 7፡25)። በቤቶቻቸው ክርስቲያናዊ ያልሆኑ ሃይማኖቶችን ዕቃዎች እንዳያስቀምጡ ተከልክለዋል (ዘዳ. 7፡26)። በአዲስ ኪዳን፥ የኤፌሶን ሰዎች ይህ ከኃጢአታቸው ንስሐ በገቡበት ሁኔታ ውስጥ እንደሚጠቃለል ተረድተው ነበር። ከዚህም የተነሣ፥ የኤፌሶን ሰዎች ዳግም ሲወለዱ ክርስቲያናዊ ካልሆኑ እምነቶቻቸውና ልምምዶቻቸው ጋር የተዛመዱትን ዕቃዎች አቃጥለዋል (የሐዋ. 19፡18-19)። የአፍሪካ ክርስቲያኖችም ይህንኑ ለማድረግ መማር አለባቸው።

ከባህላዊ ሃይማኖት በግልጽ ለዘለቄታው አለመለየት የአፍሪካን ቤተ ክርስቲያን በእጅጉ ጎድቶአታል። ክርስቲያናዊ ያልሆኑ ልምምዶችን ሙሉ ለሙሉ አለማስወገድ የከፋ ኃጢአት በመሆኑ፥ የእግዚአብሔርን ፍርድ ያስከትላል፤ ከአንድ ሰው ሕይወት የእግዚአብሔርን ጥበቃ ሊያሳጣ ይችላል። እስራኤላውያን በዙሪያቸው የሚገኙትን ሕዝቦች ባህላዊ ሃይማኖቶች ሙሉ ለሙሉ ባለማስወገዳቸው፥ እግዚአብሔር፥ «እናንተ ግን ተዋችሁኝ ሌሎችንም አማልክት አመለካችሁ፤ ስለዚህም ደግሞ አላድናችሁም። ሄዳችሁም የመረጣችኋቸውን አማልክት ጥሩ፤ እነርሱም በመከራችሁ ጊዜ ያድኑአችሁ» ብሏል (መሳ. 10፡13-14)። ይህም ብዙ የአፍሪካ ክርስቲያኖች ከጎሰኝነትና ቅይጥ አምልኮ በሚመነጩ ችግሮች ለምን እንደሚሠቃዩ በከፊል ሊያብራራ ይችላል።

ሐ. የሙታንን መናፍስት በተመለከተ፥ እውነቱ ምንድን ነው? በአጋንንት የመታለል ውጤቱ ምንድን ነው?

መናፍስት ባብዛኛዎቹ የዓለም ክፍሎች በአንድ ወይም በሌላ ጊዜ ታይተዋል። እነዚህም መናፍስት ብዙውን ጊዜ አያት ቅድማያት እንደ ሆኑ ይናገራሉ። ቁርጥ የሞቱትን ዘመዶች ሊመስሉና እንደ እነርሱም ሊናገሩ ይችላሉ። በአንዳንድ ስፍራዎች መናፍስት ("ghosts") ተብለው ይጠራሉ።

እነዚህ መናፍስት እነማን ናቸው? በምዕራፍ ስድስት እግዚአብሔር ለሞቱት ሰዎች መናፍስት የተወሰነ ስፍራ እንደሚመድብና ከዚያም ስፍራ እንደማያስወጣቸው ተመልክተናል (ሉቃ. 16፡24-26፤ 2 ቆሮ. 5፡8)። ልክ እንደ ነቢዩ ሳሙኤል (1 ሳሙ. 28፡15-19) ልዩ ፈቃድ እስካልተሰጣቸው ድረስ፥ ከዚያ ስፍራ ሊነቃነቁ አይችሉም። በመሆኑም፥ የመንፈስ መታየት የአያት ቅድማያት መታየት የመሆኑ ዕድል ብዙም አያወላዳም።

አጋንንት በፈለጉት መንገድ ለሰዎች ሊታዩ ስለሚችሉና (2 ቆሮ. 11:14፤ ራእይ 16:13) ከሰዎች የላቀ ኃይልና እውቀት ስላላቸው፥ የሞቱትን ዘመዶች አኳኋንና ድምፅ ተላብሰው መምጣታቸው ሊያስገርመን አይገባም። ልክ በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ እንደ ቀረበው እውነተኛ ታሪክ ሁሉ፥ የሞተውን ሰው መንፈስ እንዳዩ የሚናገሩ ሰዎች ብዙ ምስክርነቶችን ሰጥተዋል።

አጋንንት የሞቱትን ሰዎች መስለው የሚታዩት ለምንድን ነው? ይህንን የሚያደርጉት፥ ሰዎች ክርስቶስን ከማመን ይልቅ አያት ቅድማያቶችን ወይም መናፍስትን እንዲያምኑ የሚያስተምሩትን ክርስቲያናዊ ያልሆኑ አሳሳች ሃይማኖቶች ለማሳደግ ነው። የተወሰነ የመንፈስ መታየት የሞተው ሰው መንፈስ ይሁን ወይም የአጋንንት ማስመሰል በእርግጠኝነት መናገሩ አስቸጋሪ ነው። ይሁንና፥ ብዙው አጋጣሚ የአጋንንት የማሳሳቻ ክንውን እንደ ሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ መገለጽ ይነግረናል።

በቅርብ ጊዜያት፥ ዶክተሮች አንዳንድ በሽተኞችን ልባቸው መምታት ካቆመበት የሞት ሜፍ ለመመለስ ችለዋል። የዚህ ዓይነት ሁኔታ ያጋጠማቸው አንዳንድ ሰዎች መንፈሳቸው ከሥጋቸው ተለይቶ እንደ ነበር ተናግረዋል። መንፈሳቸው ከሥጋቸው ሲለይ ምን እንዳደረጉና ማንን እንዳዩ በትክክል እንደሚያስታውሱ ይናገራሉ። አንዳንዶች መንግሥተ ሰማይን ወይም ሲኦልን እንዳዩ ይተርካሉ።

የማያምኑ ሰዎች ከሚናገሩአቸው ከእነዚህ ታሪኮች አንዳንዶቹ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ከሞት በኋላ ስለሚሆነው ነገር ከሚያስተምረው ጋር አይስማሙም። ለምሳሌ፥ አንዳንዶች ከሞት በኋላ ሰዎች ቸኃጢአታቸው የሚሠቃዩበት ሲኦል የሚባል ስፍራ እንደሌለ ይናገራሉ። የዚህ ዓይነቱ የውሸት ምስክርነት የሚሰጠው ለብዙ ምክንያቶች ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ጊዜ የልቡ ምት ሲቆም የሰውየው (የሴትዮዋ) አንጎል ሊነካ ይችላል። በሌላ በኩል፥ ሰውዬው በአጋንንት ተታሎ ይሆናል። በተጨማሪም፥ በእንዲህ ዓይነቶቹ ከሥጋ የመለየት አጋጣሚዎችና በመጽሐፍ ቅዱስ በተገለጸው እውነተኛ ሞት መካከል ልዩነት እንዳለ ልብ ልንል ይገባል። በእውነተኛ ሞት ጊዜ፥ የሰውዬው የሰብአዊነት መንፈስ ለዘለቄታው ይለየዋል።

አንዳንድ ሰዎች ከሙታን ጋር እንደ ተነጋገሩ ይገልጻሉ። በዚህ ዓይነት አጋጣሚዎች፥ የ«ሞተው» ሰውዬ ቃላት ከእግዚአብሔር ጋር የማይስማሙ ከሆነ፥ ከሞተ ሰው ጋር እንደ ተነጋገሩ የሚያስቡ ሰዎች ተታለዋል። የራሳችን አእምሮ ሊያታልለን ይችላል። አጋንንት በቀላሉ ሰዎችን

ሊያታልሉ ይችላሉ። አጋንንት በተለይም ከሙታን መናፍስት ጋር ለመነጋገር የሚሞክሩትን ሰዎች ያታልላሉ። የሰይጣንን ኃይል ማናናቅ የለብንም። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ሲሆን፥ እግዚአብሔርም በቃሉ አማካኝነት እውነቱን ይነግረናል።

እግዚአብሔር ሰዎች ከሙታን ጋር እንዳይገናኙ የሚያስጠነቅቀው ለምንድን ነው? እስካሁን ከተነጋገርነው አኳብ እንደምንረዳው፥ እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ ከሙታን ጋር መገናኘቱን የሚቀጥሉ ሰዎች ለአጋንንት መታለል ራሳቸውን አጋልጠው ይሰጣሉ። ዘመዳቸው እንደ ሆነ ከማያምኑትና እርሱም አያት ቅድማያታቸው እንደ ሆነ ከሚናገር መንፈስ ጋር ሊገናኙ ይችላሉ። መንፈሱም እውነትም ትክክለኛ ዘመዳችን ነው ብለው እንዲቀበሉት፥ ምሥጢራዊ የሆነ መረጃ ሊሰጣቸው ይችላል። ይህም ሆኖ፥ አጋንንት በጣም አዋቂዎችና ኃይለኞች መሆናቸውን ልብ ልንል ይገባል። ኢየሱስ የውሸት አባት እንደ ሆነ የተናገረውን ጌታቸውን ሰይጣንን ያገለግላሉ (ዮሐ. 8፡44)። ከሞተ ሰው ጋር ለመገናኘት በመፈለግ፥ ሰው ከሐሰተኛ መንፈስ ጋር ሊገናኝ ይችላል። እንዲሁም፥ እግዚአብሔር ይህንኑ ልምምድ በቃሉ ስለ ኮነነ፥ ሙታንን ለማነጋገር በመሞከሩ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ሊወድቅ ይችላል (ዘዳ. 18፡11-12)። ክርስቲያን ሁልጊዜም ይህንኑ ልምምድ ማስወገድ አለበት።

መ. በጋኔን ስለ መያዝ የመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት ምንድን ነው?

በመንፈስ መያዝ በብዙ ያኅሰም ከፍሎች የተለመደ ክስተት ነው። ሰዎች በመንፈስ ሲያዙ ልዩ ጥንካሬ፥ ትዕግሥት ወይም ሕመምን የመቋቋም ዓቅት ሊኖራቸው ይችላል። ብዙውን ጊዜ (በውስጣቸው በሚያድረው መንፈስ) ልዩ ድምፅ ይናገራሉ። እነዚህ ድምፆች አያት ቅድማያት እንደ ሆኑ ወይም ከአያት ቅድማያቶች መልእክት እንዳመጡ ሊናገሩ ይችላሉ። በመንፈስ ከመያዝ በስቲያ ያለው እውነታ ምንድን ነው?

ብዙ ሳይንቲስቶችና ስለ ሰዎች ጥናት የሚያካሂዱ አንትሮፖሎጂስቶች፥ በመንፈስ መያዝ ከራስ የመነጨ ጠባይ ወይም የተልድ ትወና እንደ ሆነ ያምናሉ። በዚህ ንድፈ-አሳብ አገላለጽ፥ ሰዎች ከግላዊ ችግራቸው ለማምለጥ፥ የሌሎችን አትኩሮት ለመሳብ፥ ወይም ለሌላ ኅይነት ምክንያት ባሕርያቸውን ሊለውጡ ይችላሉ። በመንፈስ መያዝ ተብሎ የተወሰደው ትዕይንት፥ በሕዝቦቻቸው ዘንድ ተቀባይነት ባለውና

በታመነው መንገድ የአትኩሮት ማዕከል ያደርጋቸዋል። ይህ ግብራሪያ በአንዳንድ አጋጣሚዎች እውነት ሊሆን ይችላል።

ከዚህ በተጨማሪ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ክፉ ወይም ርኩስ ተብለው በሚጠሩ መናፍስት ስለ ተያዙት ሰዎች አያሌ ገጠመኞችን ይገልጻል (ማር. 1:23፤ 5:8፤ 9:25)። ኢየሱስ እንዲህ ዓይነት ብዙ ገጠመኞችን አስተናግዱል (ማቴ. 8:16፤ 9:32፤ ማር. 7:25፤ ሉቃ. 9:42)። በእነዚህ ገጠመኞች ኢየሱስ አካባቢያዊ አጉል እምነቶችን እንደሚቀበል፥ ወይም እንደ ተዋጣለት ተዋናይ የሥነ-ልቡናን ብልሃት ሊጠቀምበት ስለ መሞከሩ የተጠቀሰ ነገር የለም። እንደ እውነቱ ከሆነ፥ እነዚህ መናፍስት ለኢየሱስ በዚያ መገኘት የሰጡዋቸው የቃላት ምላሾች፥ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቅዱስ የመሆኑን እውነታ (ማር. 1:24) ከደቀ መዛሙርቱ እጅግ ቀደም ብለው መረዳታቸውን ይገልጻሉ (ማቴ. 16:15-16)። ርኩስ መናፍስት የኢየሱስን ኃይል በከፍተኛ ደረጃ መፍራታቸውን አልሸሸጉም። ከሁሉም በላይ፥ በእነርሱ ላይ የሚያመጣውን ፍርድ አምነዋል (ማቴ. 8:29)። ከእነዚህ ታሪኮች እንግዲህ እነዚያ በመንፈስ የተያዙት ሰዎች ይቀልዱ እንዳልነበር ግልጽ ነው። በውስጣቸው ርኩስ መናፍስት ነበሩባቸው።

የጌርጌሴኖኑን ሰውዬ በተመለከተ፥ አጋንንቱ ኢየሱስ በአቅራቢያቸው ወደሚገኙ አሳማዎች ይገቡ ዘንድ እንዲፈቅድላቸው ለመኑት (ማቴ. 8:31)። ኢየሱስም በፈቀደላቸው ጊዜ፥ አሳማዎቹ አበዱና ራሳቸውን ለጉዳት ዳረጉ፤ ይህም ክፉ መናፍስት ከሰውዬው ወደ አሳማዎቹ እንደ ተሻገሩ ያሳያል (ማቴ. 8:32)። መጽሐፍ ቅዱስ ክፉ መናፍስት ሰዎችንና እንስሳትንም እንኳ የመያዛቸውን እውነታ ይገልጻል። ክፉ መናፍስት የሚይዙት እንዴትና ለምንድን ነው?

በምዕራፍ አሥራ አንድ የሰይጣን ኃይል የሚሠለጥንበት አካባቢ ኃጢአትና በእግዚአብሔር ላይ የሚፈጸም ዓመፅ የተለመደበት እንደ ሆነ ተገልጸአል። ኃጢአት ወይም በእግዚአብሔር ላይ በፈቃዳቸው የሚያምፁ ሰዎች፥ በሕይወታቸው ለአጋንንታዊ ጥቃት በር ይከፍታሉ። በኤፌሶን 4:26-27 ጳውሎስ የጽድቅ ያልሆነው ቁጣ በሰው ሕይወት ለሰይጣን ፈንታ ሊሰጥ እንደሚችል ገልጸአል። እንግዲህ፥ በእውነተኛው አምላክ ፊት (ክርስቲያናዊ ባልሆኑ ሃይማኖቶች ዓይነት) ሌሎችን አማልክት በፈቃዱ በሚያስቀምጥ ሰው ሕይወት ሰይጣን የሚያገኘው በር (ፈንታ) ምን ያህል የጠነከረ ይሆን? በብዙ ባህላዊ ሃይማኖቶች፥ መናፍስት ሰውን

እንዲይዙ ግብግ ያቀርቡላቸዋል። ምንም እንኳ የሚጋብዙአቸው ሰዎች ቸር የአያት ቅድማያት መናፍስትን ወይም ደጋግ አማልክትን እንደሚጋብዙ ቢያስቡም፥ አጋንንት የእነዚህን ሰዎች ሕይወት ለመቆጣጠር ፍጹም ፈቃደኞች ናቸው።

ራሳቸውን ለጋጢአት አሳልፈው በሚሰጡ ሰዎች ሕይወት ሰይጣን የሚያገኘው በር ምን ያህል የሰፋ ይሆን? የሰው ታሪክ ጭካኔ የሞላበት ገጽታ ለዚህ ጥያቄ አንደኛው ምላሽ ነው። በአጋንንት ተጽዕኖ በሰዎች ሕይወት ምን ያህል የግድያ ወንጀሎች፥ የነገድ ጦርነት፥ ሥቃይና ሴቶችን አስገድዶ የመድፈር ተግባራት እንደ ተፈጸሙ ስናስብ ከመደነቅ በቀር የምንጨምረው የለንም። አንደኛው የክፋት ገጽታ በራሳቸው ምሳሌነት፥ አሳቦች፥ ወይም አግባብነት በጎደላቸው ተግባራት፥ ለልጆቻቸው ጋጢአትን የሚያስተዋውቁትን ክርሲቲያን ያልሆኑ ወላጆች የሚመለከት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የወላጆች ጋጢአት እስከ ሦስትና አራት ትውልድ ድረስ በልጆች ላይ እንደሚቆጠር ይገልጻል (ዘጸ. 34፡7)። ይህ በተለይ ወላጆች በሕይወታቸው ከእግዚአብሔር መንፈስ ባሻገር ሌሎችን መናፍስት በሚያስተናግዱበት ስፍራ እውነት ነው (ዘጸ. 20፡5)። ምናልባት ብዙ ልጆች በሕፃንነታቸው በአጋንንት የሚያዙበትና በሌሎችም ተጽዕኖዎች የሚሠቃዩበት አንዱ ምክንያት ይኸው ይሆናል።

መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ መያዝ የአጋንንት ሥራ እንደ ሆነ በግልጽ ይናገራል። መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ሰዎችን ከመናፍስት ተጽዕኖ ስላዳነበት ሁኔታ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲገልጽ፥ «በመሸም ጊዜ አጋንንት ያደረባቸውን ብዙዎችን ወደ እርሱ አመጡ . . . መናፍስትን በቃሉ አወጣ፥ የታመሙትንም ሁሉ ፈወሰ» ይላል (ማቴ. 8፡16)። በዚህ ስፍራ ሰዎችን የሚይዙ መናፍስት በግልጽ አጋንንት ተብለው ተጠርተዋል። በሐዋሪርያት ሥራ መጽሐፍ ኢየሱስ ሰዎችን በመፈወስና አጋንንትን በማስወጣት ያበረከተው አገልግሎት፥ እንደሚከተለው ጠቅለል ብሎ ተገልጾአል፡- «እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በኃይልም ቀባው፥ እርሱም መልካም እያደረገ ለዲያብሎስም የተገዙትን ሁሉ እየፈወሰ ዞረ፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረና» (የሐዋ. 10፡38)።

ሠ. የአጋንንት ተጽዕኖ የደረሰባቸውን ወይም በአጋንንት ቁጥጥር ሥር የወደቁትን ሰዎች ክርስቲያኖች እንዴት ሊረዱአቸው ይችላሉ?

ክርስቲያኖች በኢየሱስ ስም አጋንንት እንዲያስወጡ ክርስቶስ ራሱ ሥልጣን ሰጥቶአቸዋል (ማር. 16፡17፤ ሉቃ. 9፡1፤ 10፡17፥ 19)።

ክርስቲያኖች ከሥልጣናትና አጋንንታዊ ኃይላት ሁሉ በላይ በመንፈሳዊ ሁኔታ ከክርስቶስ ጋር ስለ «ተቀመጡ» (እንደ አካሉ ከክርስቶስ ጋር ስለ ተጣመሩ)፥ ይህ ሥልጣን በእጃቸው ነው (ኤፌ. 1፡19-22፤ 2፡6)። በመንፈስ የተያዘው ሰው የሚሠቃየው ከአጋንንታዊ ጥቃት እንጂ ከተራ የጠባይ ለውጥ እንዳልሆነ ሲረጋገጥ፥ ክርስቲያኑ አጋንንቱን ለማስወጣት የሚሞክር ከሆነ የኃይል ተግዳሮት ይኖራል።

ለአጋንንት መኖር መሠረቱ ኃጢአት እንደ መሆኑ፥ በአጋንንት የተያዘው ሰው ኃጢአቱን ለመናዘዝና ለመተው፥ ብሎም ክርስቲያናዊ ያልሆኑ እምነቶቹንና ልምምዶቹን ለማስወገድ ካልፈለገ፥ ለዘለቄታው ከአጋንንት ጥቃት ለመላቀቅ አይቻልም። እንዲህ ዓይነት ኑዛዜና ኃጢአትን የመተው ተግባር ለመፈጸም ከማይፈልግ ሰው አጋንንት ለማስወጣት መሞከር ጥበብ የጎደለውና አደገኛ የሆነ ልምምድ ነው። ማንኛውም ዓይነት ስኬታማ አጋንንትን የማያስወጣት ተግባር ከመፈጸሙ በፊት፥ ግልጽ የሆኑትን ኃጢአቶች መናዘዝና ማስወገድ የግድ አስፈላጊ ነው።

አንዳንድ ሰዎች ሙሉ ለሙሉ በአጋንንት ተጽዕኖ ሥር ስለሚወድቁ፥ በሰውዬው ምትክ አጋንንቱ ይናገራል (ማር. 5፡9-10)። እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ፥ ክርስቲያኖች ከሰዎቹ ጋር ስለ ኃጢአታቸውና ንስሐ መግባትም እንደሚያስፈልጋቸው ለመነጋገር፥ አጋንንቱን ማሰር፥ ዝም ማሰኘት ወይም ማስወጣት አለባቸው። በአጋንንት የተያዙትን ሰዎች ለማማከር፥ በመጀመሪያ ደረጃ አጋንንት ጥቃት ለማድረስ ወይም ፈንታ ለማግኘት የቻሉበትን ኃጢአት ማወቅ ያሻል። ለዚህም፥ ሰዎቹ ቢያንስ ለጊዜውም ቢሆን፥ አጋንንት በአእምሮአቸውና በስሜታቸው ላይ ከሚያስከትሉት ተጽዕኖ መላቀቅ አለባቸው። ስለ ሆነም፥ አጋንንትን በኢየሱስ ስም ዝም ማሰኘት ወይም ማስወጣት አስፈላጊ ይሆናል። ይሁንና፥ አጋንንት ውሸታሞችና በማታለልም የተካኑ በመሆናቸው ከእነርሱ ጋር መነጋገሩ አላስፈላጊ ነው።

ሰውዬው ለዘለቄታው ከአጋንንታዊ ተጽዕኖ ከመላቀቁ በፊት፥ ግጋለጥ፥ መናዘዝና መተው የሚያስፈልገው መሠረታዊ ነገር ኃጢአቱን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በዋናነት ስለ ኃጢአት እየተናገረ በጥቂቱ ብቻ ስለ አጋንንት የሚናገረው ለዚህ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ፥ ንስሐ መግባት ኃጢአትንና የሰይጣን ሥራዎች ሁሉ መካድን ያጠቃልላል። በቀድሞዪቱ የክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ዓይነቶቹ ክህደቶች፥ «አንተን ሰይጣንን፥ ሥራዎችህንና መንገዶችህን ሁሉ እክዳለሁ» በሚል ዓረፍተ ነገር፥ የሰውዬው የዳግም ልደት አካል ተደርገው ይዘወተሩ ነበር።

በአንዳንድ አጋጣሚዎች ዛሬ ይህ አስቀድመው የሞቱትን ጨምሮ፥ የወላጆችን ወይም የሌሎች ዘመዶችን አላግባብ ልምምድ ወይም የኃጢአት ተጽዕኖ መካድን ሊያካትት ይችላል! አንድ ሰው ኃጢአቱን ከካደ በኋላ፥ በክርስትና እምነት በትዕግሥት ማስተማርና ማበረታታት አስፈላጊ ነው፤ ይህ ካልሆነ ወደ ቀድሞ ኃጢአቱ ይመለስና ለበለጠ አጋንንታዊ ወረራ ራሱን ያጋልጣል።

አጋንንት ከሚቆጣጠሩአቸው ሰዎች ሲወጡ ይናደዳሉ። የወጡባቸውንም ሰዎች በብዙ መንገዶች ለማጥቃትና ለመጉዳት ይሞክራሉ። አጋንንት የወጡባቸው ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል በመታዘዝ ራስን ስለ መግዛት ብዙ ሊማሩ ይገባል። እንዲሁም፥ ሌሎች ክርስቲያኖች በድጋፍ፥ በጸሎትና በደቀ መዛሙርትነት ሊረዱአቸው ይገባል።

ጳውሎስ በኤፌሶን ሲሰብክ፥ በዚያ ስፍራ የነበረውን ክርስቲያናዊ ያልሆነ ሃይማኖት ይከተሉ የነበሩ ሰዎች፥ የሃይማኖታቸውን የመገልገያ ዕቃዎች በመሰባበርና ኃጢአታቸውን በመናዘዝ፥ ልምምዳቸውን ለመተውና ለመካድ እንደሚፈልጉ አሳይተዋል (የሐዋ. 19፡18-19)። አንድ ሰው በሕይወቱ ሙሉ ለሙሉ ከሰይጣን ተጽዕኖ እንዲላቀቅ ከተፈለገ፥ አረማዊ ወይም የኃጢአት ልምምድን እንደዚህ በግልጽ መናዘዝና መተው አስፈላጊ ነው።

እግዚአብሔር ጌዴዎንን እስራኤላውያንን ከምድያማውያን ጭቆና ነፃ እንዲያወጣ ሲጠራው (መሳ. 6፡11-14)፥ በመጀመሪያ ሕዝቡ የገነቡትን አረማዊ ጣዖት ማፍረሱ ለጌዴዎን አስፈላጊ ነበር (መሳ. 6፡25-27)። ጌዴዎን የቤተሰቡን የውሸት ሃይማኖት እስኪያስወግድ ድረስ፥ እግዚአብሔር ምድያማውያንን ያሸንፍ ዘንድ ጌዴዎንን በኃይል አያስታጥቀውም ነበር። ዛሬም እንደዚሁ፥ አንድ ሰው ክርስቲያናዊ ያልሆነ ሃይማኖትን እምነቶችና ልምምዶች በሕይወቱ ውስጥ ከሚገኙ ሌሎች የታወቁ ኃጢአቶች ጋር ካላስወገደ፥ እግዚአብሔር ሰይጣንን እንዲያሸንፍ አያስችለውም።

ከእንዲህ ዓይነቱ ኃጢአትን የመካድ ውሳኔ በኋላ፥ ክርስቶስን በመከተልና ለቃሉ በመታዘዝ እያደጉ ብርቱ ደቀ መዝሙር መሆን አስፈላጊ ነው። የዚህ ዓይነቱ ክትትልና ደቀ መዝሙርነት ከሌለ፥ አዲስ ያመነው ሰው ችግር ሲገጥመው ወደ ቀድሞው ክርሲትያናዊ ያልሆነ ሃይማኖቱ ሊመለስ የሚችልበት አደገኛ ሁኔታ ይኖራል። በአፍሪካ ብዙ ክርስቲያኖች በችግራቸው ጊዜ ወደ ባህላዊ ልምምዶች የሚመለሱት፥

ጥንቃቄ የተመላበት የደቀ መዛሙርነት ክትትል ባለመደረጉ ነው። ዛሬ ለአፍሪካ ቤተ ክርስቲያን ትልቁ አስፈላጊ ነገር ደቀ መዝሙርነትና ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ በክርስቶስ ወደ ብስለት ማደግ ነው።

ረ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መንግሥተ ሰማይና ሲኦል ምን ይላል?

መጽሐፍ ቅዱስ መንግሥተ ሰማይና ሲኦል በትክክል መኖራቸውን ይገልጻል። መንግሥተ ሰማይ እግዚአብሔር የሚያድርባት ብፅዕት ስፍራ ነች። ኢየሱስ መንግሥተ ሰማይን ገነት ይላታል። ከኢየሱስ ግራና ቀኝ ከተሰቀሉት ሁለት ሌቦች አንደኛው ከጋጢአቱ ንስሐ ስለ ገባና በክርስቶስ ስላመነ፥ ክርስቶስ፥ «ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ» ብሎታል (ሉቃ. 23፡43)። ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «እንዲህ ያለው ሰው ከአሥራ አራት ዓመት በፊት እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ ተነጠቀ . . . ወደ ገነት ተነጠቀ፥ ሰውም ሊናገር የማይገባውን የማይነገረውን ቃል ሰማ» ብሏል (2 ቆሮ. 12፡2-4)። በራእይ 21፡2–22፡15፥ ሐዋርያው ዮሐንስ መንግሥተ ሰማይን «ቅድስቲቱ ከተማ፥ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም» በማለት ይገልጻታል (ራእይ 21፡2)።

ከዚህ በፊት መንግሥተ ሰማይን አይተው ወደ አካላቸው እንደ ተመለሱ ከተጠቀሱት ሰዎች አንዳንዶቹ፥ ቅድስቲቱን ከተማ ልክ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደ ተገለጸችው አድርገው አብራርተዋል። ሐዋርያው ዮሐንስ አንዳንዶች በቀጥታ ሌሎች ደግሞ በተምሳሌትነት የሚተረጉሟትን ቅድስቲቱን ከተማ በዝርዝር ገልጾአታል (ራእይ 21፡10-27)። የፍጻሜው እውነታ ቅድስቲቱ ክተማ ማንኛውም ሰው ለመቼውም ከሚገልጸው በላይ የላቀችና የከበረች መሆኗ ነው። በምዕራፍ አሥራ ስምንት መጨረሻ አካባቢ ስለ መንግሥተ ሰማይና ስለ ዘላለማዊ የእግዚአብሔር መንግሥት ተጨማሪ ግብራሪያ ይቀርባል።

እንደ ተመለከትነው፥ መጽሐፍ ቅዱስ የሞተ ሰው መንፈስ እግዚአብሔር ወዳለበት ስፍራ (መንግሥተ ሰማይ) ወይም ወደ ሥቃይ ስፍራ (ሲኦል) ይሄዳል። የሙታን ዘለቄታዊ መለየት ኢየሱስ ስለ ሀብታሙ ሰውዬና ስለ አልዓዛር በተናገረው ታሪክ ውስጥ ተገልጾአል (ሉቃ. 16፡19-31)። ኢየሱስ አልዓዛር የመጽናኛ ስፍራ ወደ ሆነው የአብርሃም እቅፍ ሲወሰድ፥ ሀብታሙ ሰውዬ ወደ ሥቃይ ስፍራ እንደ ተወሰደ ገልጾአል (ሉቃ. 16፡24)። ክርስቶስ ካረገበት ጊዜ አንሥቶ፥ የሚሞቱ አማኞች ሁሉ ጌታ ወዳለበት ይሄዳሉ (2 ቆሮ. 5፡8)። ክርስቲያን ሲሞት

ቅዱሳን መላእክት መንፈሱን ክርስቶስ ወዳለበት አጅበው ያደርሳሉ። የእነዚህ ክርስቲያኖች መናፍስት ክርስቶስ ወደ ምድር ሲመለስ አብረውት የሚመጡ ሲሆን፥ የትንሣኤ አካላቸውንም በዚህ ጊዜ ይቀበላሉ (1 ተሰ. 4፡14-17)።

የአልዓዛርን መንፈስ ቅዱሳን መላእክት ወደ መጽናኛ ሰፍራ መውሰዳቸውን መረዳት አስደሳች ነው። ከሞት የተነሡ ብዙ ክርስቲያኖች በሞቱ ጊዜ መላእክትን እንደ ተመለከቱ መስክረዋል። ምናልባት እግዚአብሔር መላእክቱን የሚልከው በዚህ ዓለም ከሚገኙ ክፉ መናፍስት ሕዝቡን ለመጠበቅ ይሆናል (ኤፌ. 2፡2)። ሀብታሙ ሰውዬ የእግዚአብሔር ንብረት ባለመሆኑ፥ እንዲህ ዓይነት ጥበቃ እንደ ተደረገለት አልተጠቀሰም።

በመጽሐፍ ቅዱስ ከሁሉም በላይ አሰቃቂና አስቸጋሪው የሲኦል መናር ነው። እንደ ክርስቶስ አገላለጽ፥ ሲኦል በትክክል አለ። ኢየሱስ በማቴዎስ 18፡9፥ «ዓይንህ ብታሰናክልህ አውጥተህ ከአንተ ጣላት ሁለት ዓይን ኖሮህ ወደ ገሃነመ እሳት ከምትጣል ይልቅ አንዲት ዓይን ኖራህ ወደ ሕይወት መግባት ይሻልሃል» ብሏል። ይህ የክርስቶስ ማስጠንቀቂያ እጅግ በጠነከሩ ቃላት ተገልጾአል። ኃጢአታቸው ላልተሰረየላቸው ሰዎች ሲኦል በትክክል አለ። ዓይኑን አውጥቶ መጣል ከሲኦል የሚያድን ከሆነ፥ ይህንኑ ግድረግ በተገባ። ይሁንና፥ ኃጢአት የሚመጣው ከውስጥ ከልብ በመሆኑ፥ ዓይንን አውጥቶ እንደ መጣል ያለው ተግባር የሰውን ኃጢአት ሊያስወግድ አይችልም። ኢየሱስ የሚለው ውጤቱ ወደ ሲኦል መግባት ከሆነ፥ ምንም ያህል የኃይል መጠን፥ ምንም ያህል የሥልጣን ደረጃ፥ ምንም ያህል የብልጽግና ብዛትና ምንም ያህል የምቾት ዓይነት ዋጋ እንደሌለው ነው (ማር. 8፡36)። ኢየሱስ ብቻ የሰውን ኃጢአይ ይቅር ብሎ ከገሃነመ እሳት ሊያድነው ይችላል (ኤፌ. 1፡7፣ 2፡8-9)።

በማቴዎስ 18፡9 «ገሃነመ እሳት» ተብሎ የተተረጎመው የግሪክ ቃል «ገሃና» ነው። ከማቴዎስ 18፡9 ጋር አንድ ዓይነት በሆነው በማርቆስ 9፡47 ኢየሱስ «ትላቸው ወደማይሞትበት እሳቱም ወደማይጠፋበት ወደ ገሃነመ እሳት» የሚል ገለጻ አክሏል። ይህ ምናልባት በራእይ መጽሐፍ (ራእይ 20፡14-15) ይቅርታን ያላገኙ ኃጢአተኞች ከታላቁ የነጭ ዙፋን ፍርድ በኋላ የሚጣሉበት «የእሳት ባሕር» ይሆናል (ራእይ 20፡11-13)። እግዚአብሔር የእሳቱን ባሕር «ሁለተኛው ሞት» በማለት ይገልጸዋል (ራእይ 20፡14)። የሰውነት ሥጋዊ ሞትና የነፍስ ሲኦል ወደ ተባለው

ስፍራ ተለይታ መሄድ የመጀመሪያው ሞት ነው (ራእይ 20፡13)። ክርስቲያኖች ክርስቶስ ስለ ገሃነመ እሳት የተናገራቸውን ቃላት በተለያዩ መንገዶች ይተረጉማሉ። አንዳንዶች ቃል በቃል ሲተረጉሙ፥ ሌሎች ደግሞ ተምሳሌታዊ ያደርጉታል። ክርስቶስ የትኛውንም ትርጉም (ቀጥተኛ ወይም ተምሳሌታዊ) ለመስጠት ቢፈልግ፥ እውነቱ ግን ኢየሱስ ገሃነመ እሳት አስፈሪ ስፍራ እንደ ሆነ ግልጽ ማድረጉ ነው።

ከታላቁ የነጭ ዙፋን ፍርድ በፊት፥ ያልዳኑት ሙታን ፍርዳቸውን በሲኦል ሆነው ይጠባበቃሉ (ሉቃ. 16፡23፤ ራእይ 20፡12-13)። እንደ ክርስቶስ አገላለጽ፥ ላልዳኑት ሰዎች ሲኦልም የሥቃይ ስፍራ ነው (ሉቃ. 16፡23-24)። እንደ ኢየሱስ አገላለጽ፥ እንደ አብርሃም ያሉ አምነው የሞቱ ቅዱሳን የሚጽናኑበት ሌላም ስፍራ ነበር። የብሉይ ኪዳን አማኞች ኢየሱስ በዕርገቱ ጊዜ ወደ ሰማይ እስኪወሰዳቸው ድረስ፥ በሰላማዊ ስፍራ አርፈው ነበር (ኤፌ. 4፡8-9)። ሲኦል (የሙታን ስፍራ) የተባለው የብሉይ ኪዳን ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ አገልግሏል።

የሚያስፈራው እውነታ ኃጢአታቸው ያልተሰረየላቸው ሰዎች ከሞት በኋላ ለዘላለም መሠቃየታቸው ነው (ማቴ. 25፡41)። ሲኦል ጨለማ፥ ለቅሶና ጥርስ ማፋጨት በሚሉ ቃላት ተገልጾአል (ማቴ. 8፡12፤ 22፡13፤ 25፡30)። ክርስቶስም ዘላለማዊ እሳት፥ ሥቃይና ቅጣት በሚሉ ቃላት ገልጾታል (ማቴ. 13፡41-42፤ ማር. 9፡43፤ ራእይ 14፡10-11)። ኢየሱስ የሲኦል ሥቃይ ለሰው ልጆች ሳይሆን፥ ለሰይጣንና ከእርሱ ጋር ላመፁት እንደ ተዘጋጀ ገልጾአል (ማቴ. 25፡41)። የሚያሳዝነው፥ ከሄድን ገነት ጀምሮ የሰው ልጆች ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ በሚያካሄደው ዓመፅ ተካፍለዋል። በኢየሱስ ክርስቶስና በመስቀል ላይ በከፈለው መሥዋዕትነት በማመን ለኃጢአታቸው ይቅርታ እስካላገኙ ድረስ፥ የሰው ልጆችም የሰይጣንን ቅጣት ይጋራሉ (ዮሐ. 8:24)።

አፍቃሪ የሆነው እግዚአብሔር ሰውን ወደ ሲኦል እንደሚልክ ለማመን የሚቸገሩ ሰዎች፥ በመጽሐፍ ቅዱስ የሲኦልን እውነትነት ከማንም በላይ የገለጸው ሁሉንም የሚያውቀው ኢየሱስ እንደ ሆነ ሊረዱ ይገባል። እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ፈራጅ ነው። ኃጢአትን ሊታገሥ አይችልም። ለዚህም ነው በዓመፀኛ መላእክትና ሰዎች ላይ ስለ ኃጢአታቸው ሊፈረድ የሚገባው (፩ጢ. 2፡2)። ኢየሱስም ሰዎች ከሲኦል ሥቃይ ይድኑ ዘንድ ለኃጢአታቸው ዋጋ ለመክፈል በመስቀል ላይ

ሕይወቱን የሰጠው ለዚህ ነው። ይሁንና፥ የእርሱን ሞትና ትንሣኤ **ማወቁ** ብቻ አይበቃም። ወንዶችና ሴቶች ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ሕይወታቸው በማስገባት እንደ ጌታቸውና አዳኛቸው አድርገው ሊቀበሉት ይገባል (ዮሐ. 1፡12)። ይቅርታ ሊያገኙና እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ከሚያወርደው ፍርድ ሊድኑ የሚችሉት በዚህ መንገድ ነው (ማር. 1፡14-15)።

ከኃጢአታቸው ንስሐ ገብተው ክርስቶስንና ይቅርታውን ለማይቀበሉ ሰዎች፥ የሲኦል እውነታ ይጠብቃቸዋል። ይህ እውነታ ክርስቲያኖች በኢየሱስ ክርስቶስ የሚገኘውን የኃጢአት ይቅርታ ወንጌል ለማሰራጨት እንዲፈጥኑ ሊያንቀሳቅሳቸው ይገባል።

ሰ. መጽሐፍ ቅዱስ ከሙታን ጋር ስለ መነጋገር ምን ይላል?

በብዙዎቹ የአፍሪካ ማኅበረሰቦች፥ የቀብር ሥነ-ሥርዓት በጣም አስፈላጊ ክስተት ነው። ይህም የሆነው ሕያዋን ለሙታን መናፍስት ኃላፊነት እንዳላቸው የሚያመለክት ባህላዊ እምነት በመኖሩ ነው። በአንዳንድ ቡድኖች፥ አንድ ሰው ሲሞትና በተጨማሪም ከብዙ ዓመታት በኋላ ለሞተው ሰውዬ መንፈስ አስፈላጊዎቹን ግዴታዎች ለመፈጸም ዳግመኛ የቀብር ሥነ-ሥርዓት ይካሄዳል። በባህላዊ ሃይማኖቶች፥ ከሞተው ሰው መንፈስ መልእክቶችን መቀበል በጣም አስፈላጊ ነው። እግዚአብሔር ሕያዋን ከሞቱት ሰዎች ጋር ስለሚያደርጉት ግንኙነት ምን ይላል?

በመጽሐፍ ቅዱስ በሕያዋንና በሙታን መካከል እንዲደረግ የተጠቀሰ ግንኙነት የለም። እግዚአብሔር በዘዳግም 18፡10-13 ሕያዋን ከሙታን ጋር እንዳይነጋገሩ በግልጽ ይከላከላል። ሙታንን ለማነጋገር መሞከር ኃጢአት ነው።

አስቀድመን እንደ ገለጽነው፥ እግዚአብሔር ይህንን ትእዛዝ የሰጠው፥ አጋንንት የሞቱ አያት ቅድማያት በመምሰል ሰዎች ውሸትን እንዲያምኑ ሊያሳስቱአቸው እንደሚችሉና እንደሚያሳስቱአቸውም ስለሚያውቅ ነው። የሞቱ አያት ቅድማያቶቻቸው መንፈስ በመምሰል፥ አጋንንት ሰዎችን ለመቆጣጠር እንዲያመቻቸው ሊያታልሉአቸው ይችላሉ። አያት ቅድማያቶች የተወደዱና የተከበሩ በመሆናቸው፥ ሰዎች እነዚህ መናፍስት የሚነግሯቸውን ሁሉ ለማመንና ለመታዘዝ የተዘጋጁ ናቸው። ይህ ሰይጣን በዓለም ሁሉ አያሌ ሰዎችን ወደ መንፈሳዊ ሞት የነዳበት ስኬታማ ወጥመድ ነው።

በሉቃስ 16፡23-31 ሀብታሙ ሰውዬ አልዓዛር በሕይወት ለሚገኙ ወንድሞቹ ስለ ሲኦል መኖር እንዲነግራቸው ቢፈልግም፥ አብርሃም ግን የመለሰለት ከሞት በኋላ ስላለው እውነታ ለማወቅ ብሉይ ኪዳንን ሊያነቡ እንደሚችሉ ነው። አሁንም በዚህ ዘመን መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ የሞትን ምሥጢራት ለማወቅ እግዚአብሔር የወሰነው ብቸኛ መንገድ ነው።

ክርስቲያን ከሙታን ጋር ስለ መነጋገር ምን ምላሽ ሊኖረው ይገባል?

ባህላዊ ሃይማኖት የሚከተሉ ሰዎች ለሞቱ ዘመዶቻቸው አክብሮት ለማሳየትና ለማስደሰት፥ መሥዋዕቶችን ያቀርባሉ። አያት ቅድማያቶች በደስታ ካልኖሩ፥ ሕያዋንን በሕመም ወይም በሌላ ዓይነት ችግር እንደሚቀጡአቸው በማሰብ ይፈራሉ። በተጨማሪም፥ በተለይ ጋብቻን ወይም ልጅ መውለድንና በሽታን ስለ መሳሰሉ የተለያዩ ጉዳዮችና ችግሮች ምን ውሳኔ እንደሚሰጡ የአያት ቅድማያቶቻቸውን ምክር ይፈልጋሉ።

እግዚአብሔር ለሕይወት ጉዳዮች ምሪት እንድናገኝ የሚፈልገው ከየት ነው? እግዚአብሔር ከሙታን ጋር የሚደረገውን ማንኛውንም ዓይነት ግንኙነት እንደሚከለክል ተመልክተናል። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «መናፍስት ጠሪዎችንና ጠንቋዮችን ጠይቁ ባሉአችሁ ጊዜ፥ ሕዝቡ ከአምላኩ መጠየቅ አይገባውምን? ወይስ ለሕያዋን ሲሉ ሙታንን ይጠይቃሉን?» ይላል (ኢሳ. 8፡19)። እግዚአብሔር፥ «መናፍስት ጠሪዎችንና (ሙታንን የሚጠሩ) ጠንቋዮችንም በሚከተል፥ በሥራቸውም በሚያመነዝር፥ በዚያ ሰው ላይ ፊቴን አከብዳለሁ፥ ከሕዝቡም መካከል ለይቼ አጠፋዋለሁ» ሲል ሕዝቡን በጥብቅ ያስጠነቅቃል (ዘሌ. 20፡6)።

እግዚአብሔር ምሪትና እርዳታ እንደሚያስፈልገን ስለሚያውቅ፥ እነዚህን ነገሮች ለማሟላት የሚያስችሉትን ሁኔታዎች አመቻችቷል። በመዝሙር (119)፡105 መዝሙረኛው፥ «ሕግህ ለእግሬ መብራት፥ ለመንገዴ ብርሃን ነው» ይላል። እግዚአብሔር ለዕለታዊ አኗኗር የምንፈልገውን ምሪት በቃሉ ውስጥ ከሚገኙ መመሪያዎች እንድናገኝ ይፈልጋል። በመዝሙር (32)፡8 እግዚአብሔር፥ «አስተምርሃለሁ በምትሄድበትም መንገድ እመራሃለሁ፤ ዓይኖቼን በአንተ ላይ አጠናለሁ» ሲል የተስፋ ቃል ይሰጠናል። እግዚአብሔር ይህንን ተግባር የሚያከናውነው በመጽሐፍ ቅዱስና በክርስቲያኑ ውስጥ በሚኖረው መንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነው።

አያት ቅድማያቶች ይሰጣሉ ስለሚባለው እርዳታ፥ የእግዚአብሔር ቃል እርዳታችን ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሚመጣ በግልጽ ይናገራል። የመዝሙር (121)ን ቃላት በማስተዋል እንብብ፦ «ረዳቴ ከወዴት ይምጣ? ረዳቴ ሰማይንና ምድርን ከሠራ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። እግርህን ለመናወጥ አይሰጠውም፤ የሚጠብቅህም አይተኛም . . . እግዚአብሔር ከክፉ ሁሉ ይጠብቅሃል፥ ነፍስህንም ይጠብቃታል። ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም እግዚአብሔር መውጣትህንና መግባትህን ይጠብቃል» [መዝ. (121)፡1- 3፥ 7- 8]። ሰውን በችግሩ ጊዜ ሊረዳ የሚችለው ሕያው እግዚአብሔር ራሱ እንጂ አያት ቅድማያት ወይም ሌላ አይደለም። አንድ ሰው ከኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ዕለታዊ ግንኙነት ካለው፥ የሞተ ዘመዱን ማማከር ከቶውንም አያስፈልገውም። እግዚአብሔር የምንፈልገውን እርዳታ ሁሉ ሊሰጠን ቃል ይገባልናል።

አዳዲስ ክርስቲያኖች ተገቢውን ሥነ-ሥርዓት ካልፈጸሙና ተገቢውን ትኩረት ካልሰጡ፥ የአያት ቅድማያቶቻቸውን ቁጣ ሊፈሩ ይችላሉ። እነዚህ ክርስቲያኖች ኢየሱስ ክርስቶስ በምድርም ሆነ በሰማይ ሥልጣን ሁሉ እንዳለው ሊያስታውሱ ይገባል (ማቴ. 28፡18)። ክርስቲያኖች እንደ መሆናቸው፥ አሁን እግዚአብሔር አፍቃሪ አባታቸው ነው። እንዲሁም ደግሞ፥ አያት ቅድማያቶች፥ መላእክት ወይም አጋንንት ቢሆኑ፥ በአጽናፈ-ዓለሙ ሁሉ የሚገኙ መናፍስት ጌታና ንጉሥ እርሱ ነው (ዕብ. 12፡9)። እግዚአብሔር ስለሚጠብቃቸው፥ ክርስቲያኖች ከእንግዲህ ማንኛውንም ሌላ መንፈስ ወይም ሰው መፍራት አያስፈልጋቸውም [መዝ. (121)፡7-8]። ጌታቸው ኢየሱስ ብቻ ነው።

የማንኛውንም መንፈስ ቁጣ ከፈሩ፥ ማድረግ የሚገባቸው የነገሥታት ንጉሥ የሆነው ጌታችን ይህንን መንፈስ እንዲያስወግደው መጠየቅ ብቻ ነው። ክፉ መናፍስት በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት እንደሚንቀጠቀጡ መረዳት የመንፈሳዊ ጥንካሬ ምንጭ ነው (ማቴ. 8፡29)። መዝሙረኛው፥ «እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው፤ የሚያስፈራኝ ማን ነው? እግዚአብሔር የሕይወቴ መታመኛዋ ነው፤ የሚያስደነግጠኝ ማን ነው?» ብሏል [መዝ. (27)፡1]።

ሸ. በአካለ መጠን መድረሻ ባህላዊ ሥርዓቶች ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት ምንድን ነው?

በአፍሪካ ባህሎች፥ የብስለት (የአካለ መጠን) መድረሻ ሥርዓቶች ሽክልጅነት ወደ አዋቂነት መሸጋገሪያ ወሳኝ ሥርዓቶች ናቸው። ከአካለ መጠን መድረሻ ዐበይት ዓላማዎች አንዱ ለወጣቶች የያታን ምሥጢራት፥ እርባታ፥ ጋብቻና ቤተሰባዊ ሕይወትን ማስተማር ነው። ይህ ለጋብቻና ለብስለት ዝግጅት የሚደረግ ሥርዓት ሲሆን፥ ማኅበረሰቡ በሙሉ ተካፋይ ይሆንበታል።

በአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓት አማካኝነት፥ ወጣቶች በማኅበረሰባቸው ወደ አዋቂነት ሕይወት ለመግባት ተቀባይነት ያገኛሉ። ይህ ክሰውዬው የማንነት ስሜት፥ ከቤተሰቡና ከጎሳው ጋር በቅርብ የተጎዳኘ በመሆኑ፥ የአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓት በሃይማኖታዊና ባህላዊ አሳቤ የተሞላ ነው። በአፍሪካ በማኅብረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት ከሁሉም የላቀ አስፈላጊ ነገር በመሆኑ፥ የአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓት ተካፋይ አለመሆን ለወጣት ትልቅ ችግር ነው።

ለክርስቲያን የአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓቶች ከፍተኛ መንፈሳዊ ችግሮችን ያስከትላሉ። በመጀመሪያ፥ ሁልጊዜም ግለት ይቻላል ከአካለ መጠን መድረሻ ልምምዶች ጋር ባህላዊ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ይኖራሉ። ስለ ሆነም፥ የዚሁ ሥርዓት ተካፋይ መሆን ለወጣት የሕዝቡን ባህሎች ክርስቲያናዊ ያልሆኑ ነገሮች እንደ ተቀበለና እንዳመነባቸው ይፋዊ ምስክርነት ይሰጣል። በሁለተኛ ደረጃ፥ በሥነ-ሥርዓቱ ላይ የሚቀርቡ አሌቶችና ልምምዶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር የሚቃረኑ ናቸው።

የአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓቶች ከነገድ ነገድ ይለያያሉ። አንዳንድ ጊዜ የነገዱ ወይም የጎሳው መለያ የሚሆን ምልክት በሰውነቱ ላይ ይደረጋል። አንዳንድ ጊዜ ለወንዶች ወይም ለሴቶች ልጆች ወይም ለሁለቱም ያታዎች ግርዘት ይደረጋል። ሁልጊዜም ለግለት ይቻላል ይህ ግርዘት የሚደረገው ለጤንነት አስተማማኝ በማይሆኑ ሁኔታዎች ነው።

ክርስቲያን ወጣትና ቤተሰቡ እግዚአብሔርን የሚያስደስት ነገር አድርገው ከማኅበረሰባቸው መወገድን ቢያተርፉ፥ ወይም ክርስቲያናዊ ያልሆኑትን ተግባራት ፈጽመው ማኅበረሰባቸውን ቢያስደስቱና ከእግዚአብሔር ዘንድ ፍርድ ቢቀበሉ እንደሚሻል በማሰብ ያመነታሉ። በጎሳው ውስጥ ተቀባይነት ለማግኘት ተገቢውን ማካካሻ አስካላደረገ

ድረስ፥ ለአካለ መጠን ሥርዓት የሚቀርብ ማንኛውም መፍትሔ ውጤታማ ሊሆን አይችልም።

የሴት ልጅ ግርዘት እንደ አካለ መጠን መድረሻ

በብዙ የአፍሪካ ክፍሎች የሴት ግርዘት ለልጃገረዶች የሚደረግ የአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓት አካል ነው። ለክርስቲያኖች ይህ ልምምድ ከፍተኛ ችግሮችን ስለሚያስከትል፥ በዚህና ባጠቃላይም በግርዘት ላይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከትን እናቀርባለን። የሴት ግርዘት ለአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓት አስፈላጊ ልምምድ መሆኑን የሚጠቁሙ አያሌ ባህላዊ ምክንያቶች ተሰጥተዋል።

1. ብዙውን ጊዜ ለሴት ግርዘት የሚቀርበው ምክንያት የሴቲቱን ወሲባዊ ፍላጎት በመገደብ ለባሏ ታማኝ ያደርጋታል የሚል ነው። ከተገረዘች፥ ካገባች በኋላ ከሌሎች ጋር ዝሙት እንደማትፈጽም ይታመናል። ከክርስትና አንጻር፥ ለዚህ አመለካከት ሁለት ከፍተኛ ተቃውሞዎች አሉ።

በመጀመሪያ፥ በከፍተኛ ወሲባዊ ፍላጎት የሚሠቃዩት ወንዶች እንጂ ሴቶች እንዳልሆኑ ማንም ሰው ያውቃል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲገረዙ የታዘዙት ወንዶች ብቻ እንጂ ሴቶች አለመሆናቸው ለዚህ አንደኛው ምክንያት ሊሆን ይችላል። ሁለተኛ፥ በብዙ ነገዶች ለሴቶችና ለወንዶች ሚዛናዊ ያልሆነ እጥፍ የግብረ-ገብ መመዘኛ አለ። ወንዶች ባሻቸው ጊዜ ተጨማሪ የወሲብ ጓደኞችን ሲፈልጉ በዝምታ እየታለፈ፥ ከሴቶች ከብረ-ንጽሕናና ታማኝነት መፈለጉ አግባብ አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የዝሙት ኃጢአቶችንና ወሲባዊ ግድፈትን በተመለከተ በወንድና ሴት መካከል ገደብ አያበጅም (ዘጸ. 20፡14፤ ዕብ. 13፡4)። እነዚህ ለወንዶችም ለሴቶችም ኃጢአት ናቸው። ይህ በሴቶች ላይ የተጣለ ድርብርብ መመዘኛ የራስን ምኞት ለማርካት በወንዶች የኃጢአት ልብ የተዘጋጀ ነው።

2. የሴት ግርዘት በጎሳዋ አዋቂዎች ዓይን ልጃገረድን ከልጅነት ወደ ሴት አዋቂነትና ብስለት የሚያሸጋግር አስፈላጊ ደረጃ ተደርጎ ይቆጠራል። ይህም ልምምድ የሚቀጥለው፥ በጎሳው አባላት የአዋቂነትን ተቀባይነት ማግኘቱ ዋንኛ ነገር በመሆኑ ነው። በባህሉ ተቀባይነት ማግኘት አስፈላጊ ሊመስል ይችላል። ይሁንና፥ እግዚአብሔር ሰዎችን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመናቸው ሁኔታ እንዲሁ እንደሚቀበል ልብ ልንል ይገባል።

3. ሌላው የሴት ግርዘት ጠቀሜታ፥ ከትክክለኛው የግርዘት ሥርዓት ቀደም ብሎና ቀጥሎ በሚመጡ ሳምንታት ወይም ወራት ውስጥ አስፈላጊው ትምህርትና ሥልጠና መሰጠቱ ነው። ይህም ትምህርት በጋብቻ፥ በየታዊ ግንኙነቶች፥ ልጅ በመውለድና በቤተሰብ ሕይወት የአዋቂዎችን ኃላፊነቶች የሚጨምር ነው። በዚህ የትምህርት ጊዜ ጎሳዊ እሴቶች፥ ወጎችና እምነቶች ላይ ትኩረት ይደረጋል።

ለወጣቶች የብስለትን ሕይወት በተመለከተ ባህላዊ ትምህርት መስጠቱ አስፈላጊ ነው። ይሁንና፥ አንድ ክርስቲያን ወጣት መጽሐፍ ቅዱስ ለሰው ልጆች ሁሉ ለጋብቻና ለቤተሰብ ጉዳዮች የሚያስፈልጉትን መለኮታዊ መመዘኛዎች እንደሚያስተምር ሊረዳ ይገባዋል። ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔር መመዘኛዎች ከጎሳዊ ባህሎች የተለዩ ናቸው። ክርስቲያናዊ እግዚአብሔርን ለማስደሰትና በሕይወታቸውም የእርሱን በረከት ለመቋደስ ከፈለጉ፥ የእግዚአብሔርን መመዘኛዎች መከተል አለባቸው።

አንዳንድ ባህላዊ ልምምዶች ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚጋጩባቸው ጊዜያት አሉ። የዚህ ዓይነት ግጭት በሚኖርበት ጊዜ፥ ክርስትያን የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት መታዘዝ አለበት። ይህ ግን አስቸጋሪና ከጎሳው ዘንድ ተቀባይነት ማጣትንና ስደትን ሊያስከትል ይችላል። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ፥ ክርስቲያኖች በሕይወት ውስጥ ከሁሉም የሚልቀው ምን እንደ ሆነ ራሳቸውን መጠየቅ አለባቸው። ለዚህች አጭር ሕይወት ብለው የባህላቸውን ሕዝቦች ሊያስደስቱና የእግዚአብሔርን ኩነኔና ፍርድ ሊቀበሉ ነው? ወይስ እግዚአብሔርን በማስደሰት፥ በዚህ ዓለምም ሆነ በዘላለሙ መንግሥት በሕይወታቸው የእግዚአብሔርን በረከት ሊቀበሉ ነው?

ከብዙ ጊዜያት በፊት፥ ኢያሱና የእስራኤል ሕዝብ በዙሪያቸው የሚገኙትን ባህላዊ ሕዝቦች ልምምዶች ወይም እግዚአብሔርን ከመከተል አንዱን መምረጥ ነበረባቸው። የኢያሱ ምላሽ ምን ነበር? ኢያሱ፥ «እግዚአብሔርንም ማምለክ ክፉ መስሎ ቢታያችሁ፥ አባቶቻችሁ በወንዝ ማዶ ሳሉ ያመለኩአቸውን አማልክት ወይም በምድራቸው ያላችሁባቸውን የአሞራውያንን አማልክት ታመልኩ እንደ ሆነ፥ የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ። እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን» ብሏል (ኢያሱ 24፡15)። ኢያሱ እግዚአብሔርን ለማምለክና ለማገልገል በመምረጡ፥ እግዚአብሔር ለዚህ አደሙ አትረፍርፎ ባርኮታል።

4. ወደ አዋቂው የጎሳው ኅብረተሰብ ተቀባይነት ከግንኙቱ ጋር፥ ከሞቱትና በሕይወት ካሉ ከጠቅላላዎቹ ጎሳዎች ጋር የመደባለቁም ጉዳይ አለ። በግርዘት ወይም በሌሎች የአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓቶች ላይ ደም መርጨት፥ ብዙውን ጊዜ ወንዱን ወይም ሴቷን ልጅ በቃል ኪዳን ከጎሳው ጋር ለማዋሃድ ታስቦ የሚደረግ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ልዩ የሆነ በደም የሚፈጸም ቃል ኪዳን ያስተምራል። እግዚአብሔር ለአብርሃም የግርዘት ደም እግዚአብሔር የመረጣቸው ሰዎች በደም ቃል ኪዳን ከራሱ ከእግዚአብሔር ጋር እንደ ተዋሃዱ የሚያመለክት ተምሳሌት እንደ ሆነ ነግሮታል። እግዚአብሔር፥ «ቃል ኪዳኔንም በእኔና በአንተ መካከል ከአንተም በኋላ ከዘርህ ጋር በትውልዳቸው ለዘላለም ኪዳን አቆማለሁ፥ ለአንተና ከአንተ በኋላ ለዘርህ አምላክ እሆን ዘንድ» ብሏል (ዘፍጥ. 17፡7)። በመቀጠልም፥ «በእኔና በአንተ መካከል ከአንተም በኋላ በዘርህ መካከል የምትጠብቁት ቃል ኪዳኔ ይህ ነው፤ ከእናንተ ወንድ ሁሉ ይገረዝ። የቁልፈታችሁንም ሥጋ ትገረዛላችሁ፤ በእኔና በእናንተ መካከል ላለውም ቃል ኪዳን ምልክት ይሆናል» ብሏል (ዘፍጥ. 17፡10-11)።

የደም ቃል ኪዳን ጉዳይ በባህላዊ ግርዘትና መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ግርዘት በሚያስተምረው አሳብ መካከል ግልጽ ልዩነት ያመጣል። ዋናው ጥያቄ በቃል ኪዳን የምንዋሃደው ከማን ጋር ነው? የሚለው ነው። የአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓት ግርዘትን ወይም ሌላ ከንውን ቢያካትት፥ ይህ እውነት ነው። እግዚአብሔር ለእርሱ ያለንን ታማኝነት የሚተካ ማናኛውንም ዓይነት ሌላ ቃል ኪዳን እንድናደርግ አይፈልግም። አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ሳይሆን፥ ከአያት ቅድማያት ጋር የሚያዋህደው የደም ቃል ኪዳን በመፈጸሙ፥ የመጀመሪያውን ትእዛዝ ይተላለፋል (ዘጸ. 20፡3)።

ክርስቲያኖች እንደ መሆናችን፥ በራሳችን ደም ሳይሆን ራሱ ባፈሰሰልን ደም ከጌታችንና ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በደም ቃል ኪዳን ተዋህደናል (ራእይ 5፡9)። የወደደንና ከኃጢአታችን በደሙ ያጠበን ኢየሱስ ነው (ራእይ 1፡5)።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ግርዘት የሚሰጠው አጠቃላይ ትምህርት

1. እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ውስጥ እንዳዘዘው፥ ግርዘት ለወንዶች ብቻ የተሰጠ ሥርዓት ነው። እግዚአብሔር ሴቶች እንዲገረዙ ያዘዘበት ስፍራ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝም (ዘፍጥ. 17፡10)።

2. የብሉይ ኪዳን ግርዘት በእግዚአብሔር እና በሰዎች እንጂ በሰዎችና በሰዎች መካከል የሚደረግ የቃል ኪዳን ምልክት አልነበረም (ዘፍጥ. 17፡11)። ይህም የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ከራሱ ጋር በልዩ ግንኙነት ለመመሥረት የታሰበ ቃል ኪዳን ነው (ዘፍጥ. 17፡7)። ስለ ሆነም፥ ይህንኑ ተምሳሌት በጎሳዎች መካከል የሚከናወን ቃል ኪዳን አድርጎ መውሰዱ፥ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተሰጠውን የግርዘትን ዓላማ መቀልበስ ነው።

3. የብሉይ ኪዳን ግርዘት ለአካለ መጠን ሲደርሱ ሳይሆን፥ በስምንተኛው የልደት ቀን የሚከናወን ነበር (ዘፍጥ. 17፡12፤ ዘሌ. 12፡3)። በእግዚአብሔር ዕቅድ፥ ከጉርምስናና የአዋቂነት ሥልጠና ጋር የሚያገናኘው ነገር አልነበረም። የሚገረዙት ገና የተወለዱ ሕፃናት በመሆናቸው፥ የሕመም ትውስታ አይኖርም ነበር።

4. በመጽሐፍ ቅዱስ የግርዘት ፍች የሕይወትን ቅድስና የሚያስከትል ግላዊ የቃል ኪዳን ግንኙነትን ያካትታል። «የልብ ግርዘት» ማለትም ይሽው ነው (ዘዳ. 30፡6፤ ቆላ. 2፡11)። ይህም ከጌታ ጋር በልብና በነፍስ ከመዋሃድ የሚገኝ ነው። ስለ ሆነም፥ በመጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛው ግርዘት ሥጋዊ ሳይሆን መንፈሳዊ ነው። ይህ መንፈሳዊ ፍች ሥጋዊ ግርዘት በተጠየቀበት አዲስ ኪዳን ሳይቀር ተገልጾአል (ዘዳ. 10፡16፤ 30፡6፤ ኤር. 4፡4፤ 9፡26)።

5. የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የመጀመሪያው ጉባኤ የተጠራው በአዲስ ኪዳን ዘመን ለመዳን ሰዎች የሥጋ ግርዘት ይፈጽሙ ዘንድ ይገባቸው እንደ ሆነ ለመወሰን ነበር (የሐዋ. 15፡1-6)። የዚህ አስቸጋሪና ረዥም ጉባኤ ውጤት፥ ሥጋዊ ግርዘት የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝብነት ምልክትነቱ ለዘላለም እንደ ቀረ የሚያመለክት ነበር (የሐዋ. 15፡8-10፥ 23-29)።

በጎላም ጳውሎስ እጅግ የሚያስፈልገው የልብ መንፈሳዊ ግርዘት ሲሆን (ቆላ. 2፡11-13)፥ ሥጋዊ ግርዘት ዛሬ ምንም መንፈሳዊ ጠቀሜታ እንደሌለው ገልጾአል (1 ቆር. 7፡19)። ዛሬ ክርስቲያን ወንዶች በሥጋ

የሚገረዙበት መንፈሳዊ ምክንያት የላቸውም። ለወንዶች ግርዘት አስፈላጊ የሆኑ የሕክምና ምክንያቶች ሊኖሩ ቢችሉም፥ እነዚህ ግን ከመንፈሳዊ ጉዳይ ጋር አይዛመዱም። የልብ መንፈሳዊ ግርዘት በሮሜ 2፡29 እና ቆላስይስ 2፡11-13 እንደ ተገለጸው፥ በሞቱና ትንሣኤው ከክርስቶስ ጋር በሚኖረን መንፈሳዊ ውህደት ዳግም መወለዳችን ነው።

6. በአዲስ ኪዳን፥ አንድ ሰው የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝብ አባል እንደ ሆነ ለማመልከት፥ የሥጋዊ ግርዘት ሥርዓት በውኃ ጥምቀት ምልክት ተተክቷል። ይህን ሮሜ 6፡1-4ን ከቆላስይስ 2፡11-12 እና የሐዋርያት ሥራ 2፡38 ጋር በማስተያየት ሊታይ ይችላል።

በአካለ መጠን መድረሻ ባህላዊ ልምምዶች ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ አመለካከት

1. ባህላዊ የአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓቶች ለጎሳና ለእምነቶቹ፥ ብሎም ለልምምዶቹ የቃል ኪዳን ታማኝነትን ይጠይቃሉ። እንዲህ ዓይነቱ የቃል ኪዳን ታማኝነት ለእግዚአብሔርና በመጽሐፍ ቅዱስ ለተገለጹ ሕጎቹ ብቻ ሊሰጥ ይገባል። ባህላዊ የአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓት እግዚአብሔር የሚከለክላቸውን የባህላዊ ሃይማኖት እምነቶችና ልምምዶች ያካትታል። ብሉይ ኪዳን፥ «እንደ ተቀመጣችሁባት እንደ ግብጽ ምድር ሥራ አትሥሩ፤ እኔም ወደ እርስዋ እንደማገባችሁ እንደ ከነዓን ምድር ሥራ አትሥሩ፤ በሥርዓታቸውም አትሂዱ። ፍርዴን አድርጉ፥ በእርስዋም ትሄዱ ዘንድ ሥርዓቴን ጠብቁ፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ» ብሏል (ዘሌ. 18፡3-4)። አዲስ ኪዳንም፥ «ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ . . . ብርሃን ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው? . . . ስለዚህም ጌታ፡- ከመካከላቸው ውጡና የተለያችሁ ሁኑ . . . እናንተም ለእኔ ወንድ ልጆችና ሴት ልጆች ትሆናላችሁ ይላል» ብሏል (2 ቆሮ. 6፡14-18)።

2. ባህላዊ ግርዘት ጤናማ ባልሆኑ ሁኔታዎች ሊከናወን ሕመምን የሚያስከትልና አደገኛ ልምድ ነው። ለልጃገረዶች ከፍተኛ ሕመም የሚያስከትል ነገር ነው። ክርስቲያን ልጃገረድ ሰውነቷ የመንፈስ ቅዱስ መቅደስ ስለ ሆነ፥ ይህ እግዚአብሔርን የሚያስከብር አይደለም (1 ቆሮ. 6፡19)።

3. የሴት ልጅ ግርዘት አንዲት መጣት ከባለቤቷ ጋር አጥጋቢ የፈቃደ-ሥጋ ግንኙነት እንዳታደርግ ያቅባታል። ከዚህም የተነሣ፥ የጋብቻ አጋር

እንደመሆን ለባለቤቷ የስሜቱ ግርኪያና የልጅ ግስገኛ መግሪያ ትሆናለች። ይህ ክርስቲያን ባል ሊቀበለው የማይገባው የራስ ወዳድነት ዝንባሌ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ» ይላል (ኤፌ. 5፡25)።

4. ባህላዊ ግርዘት የኤድስ ቫይረስ የማስተላለፍ አደጋ አለው። የሴት ልጅ ግርዘት ብዙ የደም መፍሰስ፥ የደም ሥሮችና የዳሌ አጥንት መጎዳት፥ ብሎም ሞት ሊያስከትል ይችላል። በወሊድ ጊዜም ችግር፣ አደጋና ሥቃይ ይጨምራል። የሴትን ግርዘት የሚደግፍ ክርስቲያን የሕክምና ዶክተር አይኖርም።

ለጎሳዊ የአካለ መጠን መድረሻ ልምድ ክርስቲያናዊ አማራጭ

መጽሐፍ ቅዱስ በጋብቻ፥ በቤተሰብ ሕይወት፥ በየታና የአዋቂዎችን ኃላፊነቶች በሚመለከቱ ክርስቲያናዊ እሴቶች ላይ በቂ መልእክት አለው። መጽሐፍ ቅዱስ ልጆቻቸውን በእግዚአብሔር ሕዝብ እምነቶች፥ ልምዶችና መመዘኛዎች አሠልጥኖ ማሳደግ የመንፈሳዊ ወላጆች ኃላፊነት እንደሆነ በግልጽ ይናገራል (ዘዳ. 6፡6-9)። ይህም ወጣቶችን ለአዋቂነት ኃላፊነቶች ማሠልጠንን ይጨምራል (ምሳሌ 1፡8-9፤ ኤፌ. 6፡4)። የዚህ ዓይነቱ ትምህርት (እንደ ባሕላዊ የአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓት ላሉ) ክርስቲያን ላልሆኑ የጎሳ ሽማግሌዎች ወይም እንደ አንዳንድ ዘመናዊ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች የየታ ትምህርት መርሐ ግብር አራማጅ ልቅና ዓለማዊ የመንግሥት ባለሥልጣናት ሊተው አይገባም። ክርስቲያን ወላጆች ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር በመተባበር፥ የራሳቸውን ክርስቲያናዊ የቅድመ-ጋብቻ ትምህርት መርሐ-ግብር መመሥረት አለባቸው። ይህ በጥበብ ቢደረግ፥ ለባህላዊ የአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓቶችና ለዘመናዊ ዓለማዊ የየታ ትምህርት መርሐ-ግብሮች መንፈሳዊ አማራጭ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

በዘዳግም 6፡1-14፥ እግዚአብሔር ሕዝቡንና እውነቱን ከከነዓንና ከሃይማኖታዊ አስተሳሰባቸው በግልጽ ይለያል። ይህም የእግዚአብሔር ሕዝቦች በዙሪያቸው የሚገኙ ሰዎች ከሚፈጽሙአቸው የአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓቶች እንዲለዩ ያስጠነቅቃል። ክርስቲያናዊ ያልሆኑትን እምነቶችና ልምምዶች በክርስቲያናዊ እውነት መተካት አለብን። ወጣቶች ዋነኛው ታማኝነታቸው ለእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔር ሕዝቦች እንደ

ሆነ ሊረዱና ለቤተሰብና ለጎሳ የሚደረገውን ኃላፊነት ከዚህ አንጻር ሊመለከቱ ይገባል።

ለባህላዊ የአካለ መጠን መድረሻ የክርስቲያን መፍትሔ፥ ለጎሳዊ የተቀባይነት ስሜት ተገቢ ምትክ ካላስገኘ ላይፈለግ ይችላል። የክርስቲያን መፍትሔ ለውጫዊና ከአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓት ጋር ለተያያዘ ትምህርት ጭምር ምትክ ሊያዘጋጅ ይገባል።

ለዚህ ችግር እንደ አንዱ መፍትሔ፥ ወላጆችና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወጣቶች የአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓቶች በሚፈጽምበት ጊዜ የሚከናወን፥ ክርስቲያናዊ የግብረ-ገብ ሥልጠና መርሐ ግብር ሊመሠርቱ ይችላሉ። የክርስቲያን መርሐ-ግብር የክርስቲያን እምነቶች ከባህላዊና መንግሥታዊ አሴቶች በሚለያዩባቸው ነጥቦች ላይ ማተኮር አለበት።

በዚህ ዓይነቱ መርሐ-ግብርና በባህላዊ የአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓቶች መካከል፥ አያሌ አስፈላጊ ግወዳደሪያዎች ይኖራሉ። በአፍሪካ ባህል፥ ተቀባይነት የሚገኘው በጎሳና ነገድ ደረጃ በሚገኘው ማኅበረሰብ ውስጥ ነው። የማስተማሩን ኃላፊነት የሚወጡት ባህላዊ ሽማግሌዎች ናቸው። የጎሳው ግብረ-ገባዊና ሥነ-ምግባራዊ ሥልጠናዎች የዚህ ትምህርት አካል ናቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ፥ ተቀባይነት የሚገኘው በተዋጁ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ማኅበረሰብ ውስጥ ነው። የማስተማሩን ኃላፊነት የሚወጡት ወላጆችና የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ናቸው። የመጽሐፍ ቅዱስ ግብረ-ገባዊና ሥነ-ምግባራዊ ትምህርቶች የመንፈሳዊ ትምህርት ርዕሰ-ጉዳዮች ናቸው።

የዚህ ዓይነቱ የትምህርት መርሐ-ግብር ወጣቱን ወደ አዋቂ ክርስቲያን አግኞች በሚያሸጋግር ከፍተኛ ይፋዊ ሥርዓት፥ በምስክር ወረቀት፥ በሽልማቶች፥ ከክርስቲያን መሪዎች በሚቀርቡ መልእክቶችና ምስክርነቶች፥ በልዩ መዝሙር፥ ተውኔትና የበዓል አከባበር ሊፈጸም ይችላል። አሥራ ሁለት ዓመት ለሞላቸው የአይሁድ ወንዶች ልጆች ለዘመናት ተመሳሳይ የበዓል አከባበር ሲደረግ ቆይቷል። ይሁንና፥ አሁን የሚዘጋጀው መርሐ-ግብር ለክርስቲያን ወንዶችና ሴቶች ሊያገለግል ይችላል።

የሥልጠና መርሐ-ግብሩ ባህላዊ የአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓቶችንና የመንግሥትን የያታ ትምህርት ለመተካት ሆን ተብሎ የታቀደ መሆን አለበት። እንዲህ ዓይነቱ መርሐ-ግብር የወንዶች ከበብና

የሴቶች ከበብ ከመሳሰሉ ወጣት ክርስቲያናዊ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ሊካሄድ ይችላል። ጠቅላላው ክርስቲያናዊ ግጎበረሰብ በዚህ ጎይንቱ መርሐ-ግብር ውስጥ የሚሳተፍ ከሆነ፥ በግጎበረሰቡ ውስጥ ለክርስቲያን ወጣቶች ውጤታማ የሆነ የመተኪያ አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል።

ቀ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ምትሐት ምን ይላል?

በአፍሪካውያን ግንዛቤ መሠረት፥ ምትሐት አንድ ሰው ፈታዱን ወይም ፍላጎቱን ለማሟላት የሚጠቀምበት ምሥጢራዊ ኃይል ነው። የምትሐት፥ የክታብ፥ የድግምት፥ ሰዎችን ለመተናኮል በመሬት ላይ የሚጣል የመድኃኒት ኃይል በዓለም ሁሉ ይሠራበታል። ሰዎች ከክፉ ዕድል፥ ከአደጋ፥ ከክፉ መናፍስት፥ ከክፉ ሰዎች፥ ከበሽታ ራሳቸውን ለመጠበቅና በሌሎች ሰዎችና ሁኔታዎች ላይ በበላይነት ለመግዛት እነዚህን ኃይሎች ይጠቀማሉ። አንዳንዶች ደግሞ ሌሎችን ለመጉዳት በእነዚሁ ኃይሎች ይጠቀማሉ። ሰዎች ይህንን ኃይል ስለሚያምኑ በጣም ይፈልጉታል።

መድኃኒት በአፍሪካ ብዙ ነገሮችን የሚያጠቃልል ሰፊ ቃል ነው። ቅጠላ ቅጠሎች፥ ሥራ ሥሮች፥ ቅርፊቶች የሚገኙበትን የአትክልት ቅይጦች፥ የእንስሳት አካል ወይም ሌሎችን ቁሳዊ ነገሮች ሊያመለክት ይችላል። እንደዚሁም ክፉ መናፍስትን፥ ክፉ ሰዎችን ለመከላከል ወይም አደጋን ለማስወገድ የሚያገለግሉትን ፍጹም ምሥጢራዊ ኃይላት ሊያመለክት ይችላል። በይበልጥ የሁለቱንም ግለትም የቁሳዊና መንፈሳዊ ነገሮችን ውህደት የሚያመለክት ሲሆን፥ የሥጋዊ ነገሮች ኃይል ከመንፈሳውያኑ ኃይል ብርታት እንደሚያገኝ ይታመናል። በዚህ ስፍራ መድኃኒት ስንል ሳይንሳዊ መድኃኒት ማለታችን ሳይሆን አፍሪካዊ የባህል መድኃኒት ማለታችን ነው። መድኃኒቱንም የሚጠቀሙት መድኃኒት አዋቂዎች፥ ጠንቋዮች፥ አስማተኞች፥ ቅጠላ ቅጠል ተማሚዎችና ተራ ሕዝቦች ናቸው። ብዙውን ጊዜ በሁለት ሰዎች ወይም ቡድኖች መካከል የሚካሄደው ግጭት ወይም ትግል ማን የበለጠ ጠንካራ መድኃኒት እንዳለው ለመወሰን እንደ ሆነ ይታሰባል።

ክታቦች መልካም እድል እንደሚያመጡ ወይም ክፉውን እንደሚያርቁ ለማመን ሰዎች በእንግታቸው ላይ የሚያንጠለጥሉአቸው ናቸው። ድግምቶች ሰዎች በድግምተኛው ፈታድ ይንተሳቀሱ ዘንድ የሚሰነዘርባቸው ተጽዕኖ ነው። ድግምቶች ሰዎችን ለመቆጣጠር ወይም ለመጉዳት የሚያገለግሉ ናቸው፤ ለምሳሌ የሥራ ጓደኛው በሥራው ስኬታማ እንዳይሆን ድግምትን የሚጠቀም ሰው ይኖራል። ብዙውን ጊዜ በክታቡ

ውስጥ መንፈሱ እንዲሰፍር የሚደረገው በመድኃኒት አዋቂ፥ በደብተራ ወይም በጠንቋይ አማካኝነት ነው። ድግምቶች አካላዊ ህልውና የሌላቸው ተደርገው ሲቆጠሩ፥ በአንገት ላይ የሚንጠለጠሉ ከታቦች ግን በውስጣቸው ከሚኖረው መንፈስ የተነሣ አካላዊ ህልውና እንዳላቸው ይታመናል።

ምትሐት ሰፊ የምሥጢራዊ አጠቃቀሞችን ሁኔታ ሊያመለክት ይችላል። የመድኃኒት አዋቂዎች፥ ጠንቋዮች፥ ዝናብ አውራጆች፥ ደብተሮች፥ አስማተኞችና ተራ ሕዝቦች የምትሐትን ተግባር ሊያከናውኑ ይችላሉ። ጥቁር (አደገኛ) ምትሐት፥ ነጭ (ጠቃሚ) ምትሐት፥ በሰውነት ንኪክ (በመተላለፍ) የሚሠራ ምትሐትና በተመሳሳይነት ሕጎች የሚሠራ ("homeopathic") ምትሐት እንዳለ ይታመናል። ስለ መድኃኒትና ምትሐት ኃይል የሚናገሩ ታሪኮች በአፍሪካ አያሌዎች ናቸው። ስለ ተለያዩ የመድኃኒት ዓይነቶች፥ ምትሐት፥ ከታቦች፥ ድግምቶች፥ የእርግማንና በመሬት ላይ የሚጣሉ መድኃኒቶች ኃይል ብዙ ይነገራል። በኢትዮጵያ ስለሚገኘው ተላላፊ ምትሐት የሚያሳየው ቀጣዩ እውነተኛ ታሪክ፥ በሺህ ከሚቆጠሩ ተመሳሳይ ታሪኮች አንዱ ነው፦

አንድ ወጣት በአንዲት ልጃገረድ ፍቅር ሊታጠል እርሷ ግን አትወደውም ነበር። ወጣቱም ወደ አንድ አስማተኛ ሳራ ብሎ የልጅቷን ፍቅር የሚያገኝበትን መላ ጠየቀው። አስማተኛውም የልጅቱን ደብተር እንዲያመጣለት ጠየቀው። ደብተሩንም ባመጣለት ጊዜ አስማተኛው በደብተሩ ላይ ከምትሐት መጻሕፍት ጥቅሶችን በቀይ ቀለም ጻፈ። ከዚህ በኋላ ልጅቱ በሚያስገርም ሁኔታ ወደ ልጁ በፍቅር ተሳበች። ሌላ የትኛዋም ልጃገረድ እንድትቀርበው አትፈልግም ነበር።

በኋላም ልጁ ሞተ፤ ልጂቱ ግን የልጁን መሞት ቶሎ አልሰማችም ነበር። የልጁን ሞት እስክትሰማ ድረስ፥ በከፉ መናፍስት ትሠቃይ ነበር። የልጁን መሞት እንደ ሰማች፥ መናፍስቱ ጥለዋት ሄዱ።

የመድኃኒትና የምትሐት ኃይል የሚመጣው ከየት ነው? እንደ ምትሐታዊና ምሥጢራዊ ኃይላት ላለው ሰፊ ርዕሰ-ጉዳይ ሁሉንም አስተያየት ማስተናገድ ይቻላል። በሌላ በኩል፥ ብዙ ጊዜ ምትሐት ነው ተብሎ የታመነው ነገር ብልሃት የታከለበት ማታለያ ከመሆን አላለፈም። ይህም ሆኖ፥ በታመኑ ምስክሮች የተረጋገጡ ብዙ የመንፈሳዊ ምትሐት ኃይላት ታይተዋል። በእነዚህ ሁለት እውነታዎች መካከል መድኃኒት፥ ምትሐት፥ ድግምት፥ እርግማንና ሌሎችም ስያሜዎች የተሰጡአቸውና ለግብራት የማይሞከሩ የአያሌ ክስተቶች ምሳሌዎች ታይተዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ ስላሉ ኃይላት ምን ይላል? እግዚአብሔር በእነርሱ መገልገልን ይደግፋል? የመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት ምንድን ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ በምትሐት አጠቃቀም ውስጥ የመንፈሳዊ ኃይልን መኖር ያረጋግጣል (ዘጸ. 7፡11-12፤ ዘዳ. 18፡10-12)፤ ይሁንና፥ እግዚአብሔር በእነዚህ ኃይላት መጠቀምን ይኮንናል (ዘዳ. 18፡10)። የሚጠቀሙባቸውንም ሰዎች ይኮንናል (ዘጸ. 22፡18፤ ኤር. 27፡9-10)። በመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ፥ እግዚአብሔር አንድ ሰው ሌሎችን ሰዎች ወይም ሁኔታዎች ለመቆጣጠር ወይም በመሣሪያነት ለመገልገል በምሥጢራዊ ኃይላት መጠቀሙን ይኮንናል። ይህም ክርስቲያን ያልሆኑትን የብዙ ሰዎች (ምሳሌ 28፡9፤ ኢሳ. 1፡15) እና አንዳንድ ጊዜም፥ ክርስቲያኖች ነን የሚሉትንም ወገኖች ጸሎት ይጨምራል (ያዕ. 4፡3)። እግዚአብሔር የሚደግፈው ጸሎት፥ ከቶውንም የራሳችንን ፈቃድ ለማድረግ ሰዎችን በብልሃት ለመቆጣጠር ወይም እግዚአብሔርን በኃይል ለማስገደድ መሞከር አይደለም። ይልቁንም፥ እውነተኛ ጸሎት የእግዚአብሔር ፈቃድ በሰዎች ጉዳዮች ውስጥ እንዲፈጸም ከእግዚአብሔር ጋር መተባበር ነው። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ፥ «መንግሥትህ ትምጣ፥ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን» ብለው እንዲጸልዩ አስተምሮአቸዋል (ማቴ. 6፡10)።

በምትሐት፥ በመድኃኒት፥ በድግምት፥ በእርግማን፥ በክታብና በሌሎችም ተጽዕኖዎች መንፈሳዊ ኃይል በሚገለጽባቸው ሁኔታዎች፥ የኃይሉ ምንጭ እግዚአብሔር ሳይሆን፥ ሰይጣንና አጋንንቱ ናቸው። አጋንንት በኃጢአት ለሚመላለሱና ሌሎችን ሰዎች ለመቆጣጠር ወይም ራሳቸውን ለመጠበቅ ምሥጢራዊ ኃይሉ ለሚሹ ሰዎች ኃይላቸውን ለማጋራት ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው።

ሰዎች ምትሐት፥ ባህላዊ መድኃኒት፥ ድግምትና ሌሎችንም ተመሳሳይ ተግባራት ሲፈጽሙ፥ ምንም እንኳ ዓላማቸው መልካም ሊመስል ቢችልም የአጋንንትን ኃይልና ሥራ እያከናወኑ ናቸው ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ፥ የእግዚአብሔር ባሪያዎች ሁልጊዜም ምትሐታዊ ኃይል ከሚጠቀሙ ሰዎች ጋር በመጋጨትና ተቃውሞ በማሳየት አሳልፈዋል። ሙሴ የግብፅን አስማተኞች ሲቃወም (ዘጸ. 7፡10-12)፥ ጴጥሮስ ደግሞ ስምዖን የተባለውን የሰማርያ አስማተኛ ተቃውሞአል (የሐዋ. 8፡18-23)።

በምትሐት አጠቃቀም ውስጥ ሁለት መሠረታዊ ችግሮች አሉ። በመጀመሪያ፥ እውነተኛ ጸሎት የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲፈጸም ሲሻ፥ ምትሐት ግን የምትሐተኛው ሰው ፈቃድ እንዲፈጸም ይፈልጋል። ምትሐት በራስ-ወዳድነትና የምትሐተኛውን ፈቃድ በመፈጸሙ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ነው። ሁለተኛ፥ ምትሐቱን የሚጠቀመው ሰው እግዚአብሔርን በመታመን የምትሐቱን ውጤት ለመተው አይፈልግም። ይልቁንም፥ ምትሐት የሚጠቀመው ሰው በምሥጢራዊ ኃይል የራሱን ፈቃድ ለመፈጸም ይወስናል። ስለ ሆነም፥ ምትሐት በትክክል ኃጢአትና በእግዚአብሔር ላይ የሚፈጸም ግልጽ ዓመፅ ነው።

በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ላይ ያመፀው ሰይጣን ስለ ሆነ፥ በምትሐት አማካኝነት ምኞታቸውን ለማሟላት ለሚሹ ሰዎች በአጋንንቱ በኩል መንፈሳዊ ኃይል ለመስጠት ከፍተኛ ፍላጎት አለው። ነገሩ መልካም (ነጭ) ወይም ክፉ (ጥቁር) ምትሐት ሊመስል ቢችልም ይህ እውነት ነው። በዘዳግም 18፡10-12 እግዚአብሔር፥ «ምዋርተኛም፥ ሞራ ገላጭም፥ አስማተኛም፥ መተተኛም፥ በድግምት የሚጠነቁልም፥ መናፍስትንም የሚጠራ፥ ጠንቋይም፥ ሙታን ሳቢም በአንተ ዘንድ አይገኝ። ይህን የሚያደርግ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነው» ይላል።

እግዚአብሔር እነዚህን ልምምዶች የኮነነበት ምክንያት ከሙታን ጋር መነጋገርን ከኮነነበት ጋር በጣም ተመሳሳይ ነው። ይህ ኃጢአት ነው። ሰዎችን ወደ ሰይጣን ወጥመድ፥ በዚያውም ወደ መንፈሳዊ ሞት ይመራል (ዘዳ. 32፡16-18፤ 1 ቆሮ. 10፡20-22)። አንዳንድ ደካማ የአፍሪካ ክርስቲያኖች አሁንም ምትሐት ወይም ከታቦችን ይጠቀማሉ። ይህም በችግራቸው ጊዜ ከእግዚአብሔር የተለየ አካል እንዲረዳቸው የሚፈልጉ መሆናቸውን ይገልጻል። በእግዚአብሔር አለመተማመናቸውን ያሳያል። እግዚአብሔር በርሱና በርሱ ብቻ እንድንተማመን ይፈልጋል። መዝሙር (40)፡4፥ «እግዚአብሔርን የታመነ . . . ወደ ሐሰተኛ ያልተመለከተ ሰው ምስጉን ነው» ይላል። መዝሙር 62፡8ም፥ «የሕዝብ ማኅበር ሁላችሁ፥ በእርሱ ታመኑ» ሲል፥ ምሳሌ 29፡25 ደግሞ፥ «በእግዚአብሔር የሚታመን ግን እርሱ ይጠበቃል» ይላል።

ኢየሱስን ጌታቸውና አዳኛቸው አድርገው የማያምኑ ሰዎች፥ በሚያታልሉ መናፍስት መንፈሳዊና ሥጋዊ ጥቃቶች እንደሚደርሱባቸው መገንዘብ አስፈሪ አሳብ ነው። ባህላዊ ልምምዶችን የሚከተሉ ሰዎች መድኃኒቶችና ምትሐቶች ከክፉ መናፍስትና ከጠንቋዮች ኃይላት

እንደሚጠብቋቸው በማሰብ የተሳሳተ ተግባር ይፈጽማሉ። የሚያስፈራው እውነት ግን በዚህ ዓይነቱ ዘዴ የሚጠቀሙት ሰዎች በሰይጣን ወጥመድ እንደሚያዙና ከዚያም ወደ ኃጢአትና መንፈሳዊ ሞት እንደሚያመሩ ነው። ከክፉ ይጠብቀናል ብለው ያሰቡት ነገር ራሱ በቀጥታ ለሰይጣን ኃይል ያጋልጣቸዋል! ምንኛ የሚዘገንን መታለል ነው! ከክፉ ሊያድነን የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው [መዝ. (27)፡1]። ለዚህም ነው ከክፉ ያድነን ዘንድ ወደ እርሱ ብቻ እንድንጸልይ የተነገረን (ማቴ. 6፡13)።

በምትሐት ስለ መገልገል የክርስቲያን ምላሽ ምንድን ነው?

እግዚአብሔር በሕይወት ዘመናችን ችግሮችና ቀውጢ ሁኔታዎች እንደሚጋረጡብን ቀድሞውኑ ያውቅ ነበር። ስለ ሆነም፥ እነዚህን ችግሮች የምንቋቋምበትን መንገድ ሳይጠቁመን አልቀረም። በምትሐትና ከታብ ከመታመን ይልቅ፥ እግዚአብሔር ሕዝቡ ለሚያጋጥሙአቸው ችግሮችና ጉድለቶች በጸሎት ወደ እርሱ እንዲመለሱ ይፈልጋል። በማቴዎስ 7፡7 ኢየሱስ፥ «ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ መዝጊያን አንኳኩ፥ ይከፈትላችሁማል» ብሏል። የዕብራውያን ጸሐፊም፥ «እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ» ብሏል (ዕብ. 4፡16)።

ለክርስቲያኖች ችግሮቻቸውን ለማቃለል ወይም በሌሎች ላይ ኃይል ለማግኘት የምትሐት፥ የከታብ፥ የድግምት ወይም ሌላ ስውር ኃይል መጠቀም ትክክል የሆነበት ጊዜ ከቶውንም አልነበረም። እነዚህ ነገሮች ኃጢአት ናቸው። በእግዚአብሔር ላይ እምነት አለመጣሉን ያመለክታሉ። ስለ ሆነም፥ እነዚህን ነገሮች መናዘዝና መተው አስፈላጊ ነው፤ ይህም ካልሆነ የእግዚአብሔርን ፍርድ ሊያስከትሉ ይችላሉ (ምሳሌ 28፡13)። በኤፌሶን፥ አዳዲሶቹ ክርስቲያኖች የምትሐት ዕቃዎቻቸውን ሁሉ በግውደም፥ ንስሐ የመግባታቸውንና በክርስቶስ የማመናቸውን እውነተኛነት አሳይተዋል (የሐዋ. 19፡18-19)። ዛሬም ክርስቲያኖች ክርስቲያናዊ ያልሆነ እምነት የሚንጸባረቅባቸውን ዕቃዎች ማስወገድ አለባቸው። እግዚአብሔር በሕዝቅኤል ዘመን ለነበሩ ሰዎች፥ «እነሆ፥ እኔ ነፍሳትን እንደ ወፍ ወጥመድ በምታጠምዱባት በመከዳችሁ ላይ ነኝ፥ ከክንዳችሁም ወስጄ እቀድዳታለሁ» ብሏል (ሕዝ. 13፡20)።

እንዲሁም ክርስቲያናች በራሳቸውና በአያት ቅድማያቶቻቸው ሕይወት፥ ከሰይጣን ኃይል ጋር የሚደረገውን ግንኙነት በእንደበታቸው

ሊከዱና ሊያወግዙ ይገባል። እንደ እግዚአብሔር ቃል አገላለጽ፥ የአያት ቅድማያት ኃጢአቶች በኋለኞቹ ትውልዶች ላይ ይመጣሉ (ዘጸ. 20:5፤ 34:7፤ ዘዳ. 5:9)። ሰይጣንም ይህንን ስለሚያውቅ፥ የሕዝቦችን ትውልዶች ለማጥቃት ይጠቀምበታል። ለክርስቲያን ሰይጣን በአያት ቅድማያቶቹ ላይ የነበረውን ቁጥጥር፥ በአንደበቱ ማውገዝና በኢየሱስ ስምና በደሙ ኃይል መተማመን አስፈላጊ ነው።

በሙሴ ሕግ ውስጥ እግዚአብሔር ወቅታዊ ፍርድና ሥቃይ ከቀድሞው ትውልዶች ኃጢአት ጋር ስለሚገናኝባቸው አንዳንድ ገጠመኞች ተናግሯል፤ እግዚአብሔር፥ «ከእናንተም ተለይተው የቀሩት በጠላቶቻቸው ምድር ላይ በኃጢአታቸው ይከሳሉ፤ በአባቶቻቸውም ኃጢአት ደግሞ ከእነርሱ ጋር ይከሳሉ። . . . ኃጢአታቸውንም የአባቶቻቸውንም ኃጢአት ይናዘዛሉ . . . በዚያን ጊዜ ያልተገረዘው ልባቸው ቢዋረድ፥ የኃጢአታቸውንም ቅጣት ቢቀበሉ፥ እኔ ለያዕቆብ የማልሁትን ቃል ኪዳኔን አስባለሁ፤ ደግሞ ለይስሐቅና ለአብርሃም የማልሁትን ቃል ኪዳን አስባለሁ፤ ምድሪቱንም አስባለሁ» ብሏል (ዘሌ. 26:39-42)።

ክርስቲያኑን ከሰይጣን ኃይል የሚጠብቀው እግዚአብሔር እንጂ የምትሐት ኃይል አይደለም (ኤፌ. 6:10-11)። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዛቸዋልና» ይላል [መዝ. (91):11]። ክርስቲያን ራሱን ከክፉ መናፍስት ለመከላከል እንደ እምነት፥ ጸሎትና የእግዚአብሔር ቃል ያሉትን መንፈሳዊ የጦር ዕቃዎች እንዲያነሣ ተመክሯል (ኤፌ. 6:12-18)።

ቢ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ምዋርተኛነት ምን ይላል?

በአፍሪካ፥ ምዋርት አንድን ሰው ለሕመም፥ ለችግሮች ወይም ለሞት የዳረገውን ሰው ለመለየት የሚጠቀሙበት የተለመደ ዘዴ ነው። ሰው ማንን እንደሚያገባ፥ የተወሰኑ እህሎችን መቼ እንደሚዘራ፥ ወይም አንድን ጉዞ መቼ እንደሚያደርግ፥ ወዘተ. ለመወሰን ወይም ምክር ለማግኘት የሚጠቀሙበት ነው። አያት ቅድማያቶችን ስላስቀየሙበት ሁኔታ ተረድተው መፍትሔ ለመሻትም ይገለገሉበታል። ሰዎች የትኛው ሥርዓት ወይም መሥዋዕት አንድን ችግር እንደሚፈታ ለማወቅ በምዋርት ይጠቀማሉ። አንዳንድ ጊዜ ጠላትን ለመበቀል ይፈልጋሉ። ምዋርት የወደፊቱንም ለመተንበይ ይረዳል። እንደዚሁም በእግዚአብሔር ላይ ሳይደገፉ ስለ አንድ ሁኔታ እውቀት ወይም ምክር ለማግኘት

ሊጠቀሙበት፥ የዚህ ኃይል ባለቤቶች ግን እግዚአብሔር ይህንን ኃይል እንደ ሰጣቸው ይናገራሉ (ሕዝ. 13፡6፥ 9)።

ምዋርት፥ ጠጠር በመጣል፥ የእንስሳትን አካላት በማየት፥ የትናንሽ ጭራሮዎችን ወይም በመሬት ላይ የወደቁትን የሸክላ ስብርባሪዎች በመመልከት፥ በተወሰኑ ምሥጢራዊ ዕቃዎች ላይ በትር እንዲወዛወዝ በማድረግ፥ ሕልሞችንና ራእዮችን በመተርጎም፥ ጣቶችን በመንካት፥ የእጅ መዳፎችን በመመርመር፥ ካርታ ወይም ሌሎች ነገሮች በማየት፥ የሻይ ወይም የቡና ጭላጭ መስመሮችን በማንበብና በሌሎችም አያሌ መንገዶች ሊከናወን ይችላል። ምዋርት ከመናፍስት ጋር በመነጋገር ከመናፍስት ዓለም ምሥጢራዊ መረጃ ተቀብሎ ለሚያማክረው ሰው ችግር መፍትሔ የሚሰጠው ነው።

እንደ አንዳንድ ምትሐትና የመንፈስ መጠመድ፥ ብዙው የምዋርት ሥራም ከማታለያ ጨዋታ ያለፈ አይደለም። አንድ ብልህ ሽማግሌ ሕዝቡን በሚገባ ስለሚያውቅ፥ ከአያት ከቅድማያት መንፈስ እንደ ተነገረ በማስመሰል በጣም የተገናዘበ ምክር ሊሰጥ ይችላል። ግንኙነታቸውን፥ ምቀኝነታቸውን፥ ጥላቻቸውን፥ ጭንቀቶቻቸውን፥ የአመለካከት ችግሮቻቸውንና እርስ በርሳቸው የሚያጋጥሙአቸውን እክሎች ስለሚያውቅ፥ ባህሉ በሚቀበለው መንገድ መፍትሔዎችን ያቀርባል። ምናልባትም አብዛኛዎቹ የአፍሪካ ጠንቋዮች በዚህ መንገድ የሚሠሩ ናቸው።

በግኅበረሰቡ ውስጥ የምዋርትን ተግባር ከሚያከናውነው ብልህ ሽማግሌ በተጨማሪ፥ ከራሳቸው ግንዛቤና ፍርድ በላይ በትክክል ከመንፈሳዊ ኃይላት ምሥጢራዊ እውቀት የሚቀበሉ ግለሰቦች አሉ። መጽሐፍ ቅዱስ የዚህ ዓይነቱ ርኩሰት እንዳለ በመግለጽ (ዘዳ. 18፡10)፥ ለምሥጢራዊው እውቀት ምንጩ የምዋርት መንፈስ ግለትም አጋንንት እንደ ሆነ ያመለክታል። ጳውሎስ በፊልጵስዩስ ይኸው ኃይል ከነበራት ሴት ጋር ካደረገው የኃይል ተግዳሮት ታሪክ፥ ኃይሉ የመጣው በሴቲቱ ውስጥ ከነበረው መንፈስ እንደነበር እንረዳለን (የሐዋ. 16፡16-19)። በዚህ ታሪክ ውስጥ የተጠቀሰችው ሴት የምዋርተኝነት ኃይል የነበራት ሲሆን፥ የተወሰኑ ሰዎች በኃይሏ ገንዘብ ለማከማቸት ችለው ነበር። እንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች የወደፊት ክስተቶችን በትክክል ሊተነብዩ ወይም ሌሎች የምሥጢራዊ ኃይል መግለጫዎችን ሊያሳዩ ይችላሉ። ጳውሎስ ከሴቲቱ

መንፈሱን ባስወጣው ጊዜ፥ ሴቲቱ የምዋርተኝነት ኃይሏን አጣች፥ ጌቶቿም የገንዘብ ምንጫቸው በመድረቁ በጣም ተቆጡ (የሐዋ. 16፡18-19)።

እግዚአብሔር ምዋርተኛነት የሚኮንነው ለምንድን ነው?

በዘዳግም 18፡10-12 ጌታ፥ «ምዋርተኛ፥ ሞራ ገላጭም . . . በአንተ ዘንድ አይገኝ። ይህንም የሚያደርግ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነው» ይላል። በዘሌዋውያን 19፡26 ጌታ፥ «አስማትም አታድርጉ፥ ሞራ ገላጭም አትሁኑ» ይላል። እግዚአብሔር ምዋርትን የሚኮንንበት ምክንያት ምትሐትንና ከሙታን ጋር መነጋገርን ከሚኮንንበት ጋር በጣም ተመሳሳይ ነው። እንደ ሌሎቹ ክርስቲያናዊ ያልሆኑ ሃይማኖቶች ልምምዶች ሁሉ፥ ምዋርተኝነት ሰው ከሕያው እግዚአብሔር ይልቅ በሌላ ነገር ወይም ሰው እንደሚታመን ይገልጻል። ሰዎች ከእግዚአብሔር ይልቅ በሌላ ሰው ወይም ነገር ሲታመኑ፥ የመጀመሪያውን ትእዛዝ በመጣስ ኃጢአት ይፈጽማሉ (ዘዳ. 5፡7)። እንዲሁም፥ ራሳቸውን ለአጋንንታዊ መታለልና ተጽዕኖ ያጋልጣሉ።

ልምምዱ ከፋት ስለማይመስል፥ ክርስቲያናችን ጨምሮ ብዙ ሰዎች በምዋርት ይታለላሉ። ሰዎች እንዲህ ዓይነት ኃይል ያላቸውን ግለሰቦች መልካም አድራጊዎችና ሌሎችን ረዷዎች አድርገው ይመለከቱአቸዋል። ለተመሳሳይ ምክንያቶች ኃጢአተኛውን ወይም ጠንቋዩን የማጎበረሰቡ ወዳጅ አድርገው ያዩታል! በአንዳንድ ስፍራዎች አንድ ሰው ምዋርተኛና መድኃኒተኛ በመሆን ይሠራል። የማጎበረሰቡ አባላት በሽታ ወይም ችግር ያስከተለባቸውን ሰው ግወቁ ምን ጥፋት እንዳለው ሊጠይቁ ይችላሉ።

ከሰይጣን እንደሚመጡ ሌሎች ኃይላት ሁሉ፥ ትክክለኛው የምዋርተኝነት መንፈስ በሚሠራበት ጊዜ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚከናወን መታለል አለ። ሰዎች የተንባይን ወይም የጠንቋይን ቃል ወደ ግመኑ ያዘነብላሉ። ይሁንና፥ የጠንቋዩን ቃላት እውነተኛነት እንዴት ያውቃሉ? ኢየሱስ ሰይጣን ውሸተኛና የውሸትም አባት እንደ ሆነ ተናግሯል (ዮሐ. 8፡44)። ትክክለኛ የምዋርተኝነት ኃይል ያላቸው ሰዎች ኃይሉን የተቀበሉት ከዚህ መንፈስ እንደ መሆኑ፥ የምዋርተኛውን ቃላት የሚያምኑ ሰዎች በአጋንንት ውሸት መታለላቸው አይቀርም።

ብዙውን ጊዜ ምዋርት የበሽታን ወይም የመጥፎ ገጠመኝን ምክንያት በሌላ ሰው ወይም በአያት ቅድማያት ላይ ያላክካል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን የችግሮቻችንን መንስዔ እኛው በእግዚአብሔር ላይ በፈጸምነው ኃጢአትና

ኀመፀኛነት ላይ ያሳርፋል (ያዕ. 5፡16)። ብዙውን ጊዜ የምዋርተኝነት ችግሮቻችን የሚመነጩት ከአያት ቅድማያት መቀየምና ቅጣት እንደ ሆነ ይገመታል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ሕዝቡን የሚቀጣው እግዚአብሔር እንጂ አያት ቅድማያቶች እንዳልሆኑ ይገልጻል (ዕብ. 12፡6)። ስለ ሆነም፥ ክርስቲያኖች አያት ቅድማያቶቻቸውን ሳይሆን እግዚአብሔርን እንዳያሳዝኑ ሊጠነቀቁ ይገባል።

በተጨማሪም፥ ጠንቋዩ ተጻራሪው በሆነ ሌላ ጠንቋይ ወይም አስማተኛ ላይ ለምን ተፈታተነኝ በማለት የበቀል እርምጃ ወደ መውሰዱ ያመራል። በአንድ ሰው እርግማን ያወረደውን ሰው ከእግዚአብሔር በቀር ማን ሊያውቀው ይችላል! ጠንቋዩ ግን ራሱን በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ በማስቀመጥ ታላቅ ኃጢአት ይፈጽማል። በተጨማሪም፥ በቀል የእግዚአብሔር በመሆኑ፥ በቀልን እንዳንመልስ መጽሐፍ ቅዱስ በጥብቅ ያስጠነቅቀናል (ሮሜ 12፡19)። ስለ ሆነም፥ ለጎብረተሰቡ በጎነት ቢመስልም ባይመስልም ጠቅላላው የጥንቆላ መሠረት ኃጢአትና መታለል ነው።

ለምዋርተኝነት የክርስቲያን ምላሽ ምንድን ነው?

ጌታ ሕዝቡ ለአሁንም ሆነ ለወደፊት በእርሱ እንዲታመን ይፈልጋል። መዝሙር (62)፡8፥ «ዘወትር በእግዚአብሔር ታመኑ» ይለናል (ከ1980 ዓ. ም. አዲስ ትርጉም)። በሌላውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፥ «በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፥ በራስህም ማስተዋል አትደገፍ፤ በመንገድህ ሁሉ እርሱን እወቅ፥ እርሱም ጎዳናህን ያቀናልሃል» ተብለናል (ምሳሌ 3፡5-6)። መንገዳችንን በጸሎት ለእርሱ አሳልፈን ብንሰጥ፥ እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን መረዳት ይሰጠናል። እግዚአብሔር ከእርሱ እንጂ ከምዋርተኞች ምክርንና ምሪትን እንድንሻ አይፈልግም [ዘሌ. 19፡26፤ መዝ. (25)፡12፤ (32)፡8]።

በሕይወታችን የመንገዳችን ብርሃን የሚሆነው የጠንቋዩ (የምዋርተኛ) ምክር ሳይሆን፥ የእግዚአብሔር ቃል ነው [መዝ. (119)፡105]። ስለማናውቀው ነገር በእርሱ መታመን አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ምሥጢሩ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው፤ (በመጽሐፍ ቅዱስ) የተገለጠው ግን የዚህን ሕግ ቃሎች ሁሉ እናደርግ ዘንድ ለእኛ ለዘላለምም ለልጆቻችን ነው» ይላል (ዘዳ. 29፡29)።

ማጠቃለያ

ምንም እንኳ በዛሬዪቱ አፍሪካ የሕይወት ለውጥ እየታየ ቢሆንም፥ የባህላዊ እምነቶችና ልምምዶች ችግር አሁንም በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው። ብዙዎቹ ባህላዊ ሃይማኖቶች እንደ ጠንቋዮችና የአያት ቅድማያት መናፍስት ያሉ አማላጆች፥ የሕይወትን ችግሮች ለማቃለል ወደ እግዚአብሔር እንደሚያቀርቧቸው ያምናሉ። ከዚህም የተነሣ፥ በሥርዓቶች፥ በመሥዋዕቶች፥ በምዋርት፥ በምትሐት፥ በእርግማን፥ በጠንቋይና በአስማት ላይ የሚደረጉ እምነቶች የብዙዎችን አመለካከት ይቀርጻሉ። በተጨማሪም፥ እነዚህ እምነቶች በተለይም ለእግዚአብሔርና ለቃሉ ደካማ ግንዛቤ ያላቸውን ብዙ ክርስቲያኖች ያሳስታሉ።

በችግር ጊዜ፥ አያሌ ደካማ ክርስቲያኖች ችግሮቻቸውን ለማቃለል አሁንም ወደነዚህ ልምምዶች ይመለሳሉ። በዚህም፥ ሌሎችን አግልክት በእግዚአብሔር ፊት በማስቀመጥ ክርስቲያኖች ከአሠርቱ ትእዛዛት የመጀመሪያውን ይተላለፋሉ (ዘዳ. 5፡7)። እንዲሁም፥ በእነዚህ ኃጢአቶች ላይ በሚወርደው ፍርድ በራሳቸው ላይ መከራን ይጋብዛሉ። ሌሎች አግልክት ያድኑአቸው ዘንድ ስለ ተግመኑባቸው፥ (የሚፈልጉትን) የእግዚአብሔርን ከክፉ ነገር የመጠበቅ ኃይል ያጣሉ። ሰይጣንም የሚፈልገው ይህንኑ ነው፤ ሰዎች በችግራቸው ጊዜ ምትሐትና ምዋርት የመሳሰሉትን ባሕላዊ ልምምዶች እንዲያደርጉ ይፈትናቸዋል።

ሰይጣን የውሸት አባት ስለ ሆነ፥ ሰዎችን ግታለልና ክርስቲያናዊ ያልሆነ ሃይማኖት ሐሰተኛ አሳቦች በማስፋፋት ከክርስቶስ ማራቅ የሰይጣን ዕቅድ ነው። ስለ ሆነም፥ መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎችን በክርስቶስ ከመታመን የሚያርቁትን ከሙታን ጋር መነጋገር፥ ምትሐት፥ ምዋርት፥ ከታብ፥ ድግምት፥ ክርስቲያናዊ ያልሆኑ ሥርዓቶችና መሥዋዕቶች ይኮንናል።

ለክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ አንዱን የእውነት ትክክለኛ አመለካከት እንደሚያስቀምጥ መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው። የአያት ቅድማያት መናፍስት፥ በመንፈስ መጠመድ፥ የአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓቶች፥ ምዋርት፥ ምትሐት፥ እርግማን፥ አስማት፥ ጠንቋዮችና ሌሎችንም ከባህላዊ እምነቶች ጋር የተያያዙትን ጉዳዮች ከመዳንታችን በፊት፥ የመጽሐፍ ቅዱስን አመለካከት ልንረዳና ልናምን ይገባል። በተለይም መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሙታንና አንድ ሰው ከሞተ በኋላ ስለሚሆነው ነገር የሚሰጠውን ትምህርት መረዳት አስፈላጊ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ የነገሥታት ንጉሥና በማይታይ ዓለም ውስጥ የሚገኙትን መናፍስት ጨምሮ የፍጥረታት ሁሉ አምላክ ነው። በእምነት የቀረበውን ጸሎት በመመለስ፥ እግዚአብሔር ከፉ መናፍስት ወይም ከፉ ሰዎች የሚያመጡትን ማንኛውንም ዓይነት ችግር ለማስወገድ ከሚፈለገው በላይ ብቁ ነው። ክርስቲያኑን ከችግሩ ላለማውጣት ወይም በቀጥታ ችግሩን ላለማቃለል ቢመርጥ እንኳ፥ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን ለሚወዱት ነገር ሁሉ ለበጎ እንደሚደረግ ያስተምራል (ሮሜ 8፡28)።

ዛሬ በአፍሪካ ክርስቲያኖች ክርስቲያናዊ ካልሆኑ እምነቶች ሁሉ ንስሐ መግባታቸውና ከእነዚህ እምነቶች ጋር የተያያዙትን ዕቃዎች ሁሉ ማውደማቸው በእጅጉ አስፈላጊ ነው። ችግሮች በሚከሰቱበት ጊዜ ክርስቲያኖች ለምሪት፥ ለጥንካሬ፥ ለእርዳታና ከክፉ ለመዳን በጌታ ላይ እንዴት መደገፍ እንዳለባቸው ያውቁ ዘንድ፥ አብያተ ክርስቲያናት አዳዲስ አማኞችን በጌታ ቃል በክርስቶስ ወደሚገኝ ብስለት ማሳደጋቸው በእጅጉ አስፈላጊ ነው።

በምዕራፍ 13 ላይ የተመሠረቱ የመወያያ ጥያቄዎችና መልመጃዎች

1. መዝሙር (40)፡4 እግዚአብሔር የምትሉትን፥ ከታብንና ድግምትን አጠቃቀም የሚኮንንበትን ምክንያት እንዴት እንደሚያብራራ አሳይ።

2. በምትሉት፥ በድግምት፥ ወዘተ. ከመጠቀም ይልቅ የሕይወትን ችግሮች ለማስወገድ የእግዚአብሔር መንገድ ምንድን ነው? መልስህን በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች አስደግፍ።

3. በባህላዊ የአፍሪካ ኅብረተሰብ ውስጥ የቀብር ሥርዓቶች አስፈላጊ ክስተቶች የሚሆኑት ለምንድን ነው? ክርስቲያን በቀብር ሥርዓቶች ላይ ምን ዓይነት አመለካከት ሊኖረው ይገባል? አመለካከትህን በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች አስደግፍ።

4. የአያት ቅድማያት መናፍስት ምልጃ ሥርዓቶች በዓለም ሁሉ በሚገኙ ባህላዊ ሃይማኖቶች ለምን እንደሚዘወተሩ ተወያዩ። ለእነዚህ ሥርዓቶች የእግዚአብሔር አመለካከት ምንድን ነው?

5. በአያት ቅድማያት ልምምዶችና በኅሰኛነት መካከል የሚገኘውን ግንኙነት አራት አባላት በሚገኙባቸው ቡድኖች ተከፋፍላችሁ ተወያዩ።

6. ለሞቱት ዘመዶች የክርስትያን አመለካከት ምን መሆን እንደሚገባ አንድ ሰው ለቡድኑ ያብራራ። ተናጋሪው አመለካከቱን ከጉዳዩ ጋር በሚዛመዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማስደገፍ አለበት።

7. ብዙ ሰዎች፥ የሞቱት ሰዎች ንስሐ ገብተው በክርስቶስ የሚያምኑበት ዕድል ይኖራቸው ይሆን? በማለት ይጠይቃሉ። ለዚህ ጥያቄ ከመጽሐፍ ቅዱስ መልስ ለማግኘት አራት አባላት በሚገኙባቸው ቡድኖች ተከፋፍላችሁ ተወያዩ። የምታገኙአቸውን ጥቅሶች ከየቡድኑ ውስጥ አንድ አንድ ሰው ይጻፍ።

8. መጽሐፍ ቅዱስ በራእይ 21 እና 22 በሚያስተምረው መሠረት መንግሥተ ሰማይን ግለጹ።

9. በመጽሐፍ ቅዱስ ገለጻ መሠረት፥ ከሞት በኋላ ክርስቲያኖችና የማያምኑ ሰዎች ምን ይሆናሉ?

10. ቡድኑ ሕዝቦቻቸው ስለሚጠቀሙባቸው የምትሐትና የመንፈስ መድኃኒት ዓይነቶች ይወያይ። እግዚአብሔር የምትሐትን አጠቃቀም ለምን እንደሚኮንን ግለጹ።

11. የቡድኑ አባላት በአካባቢያቸው በሚከናወኑ ዋንኛ የጥንቆላ ዘዴዎች ላይ ይወያዩ። ሁለት ሰዎች ለተቀሩት የክፍሉ አባላት ምዋርተኝነት ለምን ትክክል እንዳልሆነ ያብራሩ። የምዋርተኝነትን ተግባርና ሐሰተኛ ትንቢትን የሚኮንኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች አግኙ።

SUGGESTED FOR FURTHER READING

Gehman, Richard J. African Traditional Religion in Biblical Perspective. Kijabe, Kenya: Kesho Publications, 1989.

Mbiti, John S. African Religions And Philosophy. London: SPCK, 1969.

Parrinder, Edward G. African Traditional Religion. London: Sheldon Press, 1974.

ምዕራፍ 14

አምስት አስፈላጊ ጉዳዮች በአፍሪካ - አመራር፥ የሐሰት ነቢያት፥ ቅይጥነት፥ አማላጆች፥ መንግሥት

በአንዲት የአፍሪካ ከተማ አንድ ፖሊስ በውካታ እጅግ በተቆጡ ሕዝቦች መካከል ተከብቦ ነበር። ፖሊሱ ሕዝቡን ለመበተንና ሥርዓት ለማስከበር ሲፈልግ፥ ጥቃት ተሰንዝሮበት ከመሬት ላይ ተዘረረ። በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ሊገደልም እንደሚችል ተገንዘበ። ስለ ሆነም፥ እግዚአብሔር እንዲያድነው ተማጸነ።

በመሬት ላይ ተዘርሮ በሕዝቡ እየተደበደበ ሳለ፥ ጌታ በድንገት ተገለጸለትና እንደማይሞት ነገረው። በተጨማሪም፥ ከተሻለው በኋላ የፖሊስነት ሥራውን በመተው ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ገብቶ ለአገልግሎት እንደሚዘጋጅ ነገረው። ፖሊሱም ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ከሕዝቡ ጥቃት ተረፈ።

በዚህ ገጠመኝ ላይ ሲያሰላስል፥ ጌታ በዚህ ራእይ እንደ ተናገረው እርግጠኛ ሆነ። የፖሊስነት ሥራውን ለመልቀቅና ከእምነት ዘርፉ ጋር በሚስማማ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ለማመልከት እርምጃውን ቀጠለ። ኮሌጁም ተቀበለውና ከአራት ዓመታት በኋላ ተመረቀ። ዛሬ ይህ ሰው በእምነት ከፍሉ ውስጥ በመጋቢነት በግልገል ላይ ይገኛል። ይህ ሰው ጌታ በዚህ እንግዳ በሆነ ሁኔታ እንደ መራው ያውቅ ነበር፤ እርሱን ከሚያውቁት አንዳቸውም ጥሪውን የሚጠራጠሩበት ምክንያት አልነበራቸውም።

ይህ ታሪክ ለክርስቲያኖች አንድ አስፈላጊ ጥያቄ ያስነሣል። ዛሬ እግዚአብሔር አማኞችን ለመምራት የትኞቹን መንገዶች ይጠቀማል? ከምሪት በተጨማሪ፥ ለአፍሪካ ክርስቲያኖች አስፈላጊ የሆኑና ሊመረመሩ የሚገቡ ሌሎችም ጉዳዮች አሉ። በዚህ ምዕራፍ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ እንሻለን፦

ሀ. በዛሬው ጊዜ እግዚአብሔር ክርስቲያኖችን የሚመራው እንዴት ነው?

ለ. ክርስቲያን ሐሰተኛና እውነተኛ ነቢያትን የሚለየው እንዴት ነው?

ሐ. የመቀየጥ ችግሮች - ክርስቲያን ሊሳተፍባቸው የሚችልባቸው ልማዶች፥ ሥርዓቶችና ሌሎች ባህላዊ ልምምዶች የትኞቹ ናቸው?

መ. በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሊያግልድ የሚችል ማን ነው?

ሠ. ክርስቲያን ለአገሩ መንግሥት የሚኖረው ኃላፊነት ምንድን ነው?

ሀ. በዛሬው ጊዜ እግዚአብሔር ክርስቲያኖችን የሚመራው እንዴት ነው?

ለሁሉም ክርስቲያን አስፈላጊው ጉዳይ ምሪት ነው። ባሁኑ ዘመን እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚመራው እንዴት ነው? በአፍሪካ ለሚገኙ አያሌ ሕዝቦች የዚህ ጉዳይ አስፈላጊው አካል ሕልም ነው። ሕልሞችን ከእግዚአብሔር እንደ ተሰጡ ምሪቶች አድርገን ልናምናቸው የምንችለው መቼ ነው?

በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ምሪት ብዙ መልኮች ነበሩት። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር በቀጥታ ለሰዎች ይናገራል፤ ይህም በብሉይ ኪዳን ዘመን ለአብርሃም (ዘፍጥ. 12፡1-3)፥ በአዲስ ኪዳን ደግሞ ለጳውሎስ እንደ ተናገረው ግለት ነው (የሐዋ. 9፡5-6)። አንዳንድ ጊዜ ለጌዴዎን የምድያማውያንን ሠራዊት እንደሚመታ እንዳረጋገጠለት ምሪቱን በሕልም ይሰጣል። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ጌዴዎንን በምድያማዊ ወታደር ሕልም አማካኝነት መርቶታል (መሳ. 7፡9-15)። በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔር ዮሴፍ ከሄሮድስ ቁጣ ለማምለጥ ግርያዎንና ኢየሱስን ወደ ግብፅ እንዲወስድ በሕልም መርቶታል (ማቴ. 2፡13)።

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ፥ ጴጥሮስ ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት ሄዶ ወንጌል ይሰብክለት ዘንድ እንዳደረገው በራእይ ይመራል (የሐዋ. 10፡10-17)። አንዳንዴም እስራኤላውያንን በምድረበዳ በደመናና በእሳት ዓምድ እንደ መራቸው፥ በተአምራዊ ከስተቶች ምሪቱን ይገልጻል (ዘጸ. 40፡36-37)። አንዳንድ ጊዜም፥ በብሉይ ኪዳን እንደምንመለከተው ሳሙኤል (1 ሳሙ. 15፡1-3) እና በአዲስ ኪዳን አንደ ተገለጸው አጋቦስ (የሐዋ. 21፡10-11)፥ እግዚአብሔር ምሪቱን በነቢያት መልእክቶች አማካኝነት ይሰጣል። አንዳንዴ በበለዓም (ዘኍል. 22፡21-35)፥ በፊልጶስና በኢትዮጵያዊ

ኛንደረባ ታሪክ ውስጥ እንደ ተመለከተው (የሐዋ. 8፡26)፥ ምሪቱን በመላእክት ቀጥተኛ ጣልቃ ገብነት ይሰጣል።

ዛሬስ የእግዚአብሔር ምሪት እንዴት ነው? አሁንም በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን የነበሩትን ዘዴዎች ይጠቀማል ወይስ ሌሎችን? ዛሬ ምሪቱን ከሁሉም በላይ ልንጠብቅ የሚገባን በየትኞቹ ዘዴዎች ነው?

እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ፥ ሁለት ነገሮች ማስታወስ አለብን። በመጀመሪያ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን የማተሚያ ማሽን ገና ስላልተዘጋጀ ተራው ምእመን የግል መጽሐፍ ቅዱስ አልነበረውም። ሰዎች ምሪት ለማግኘት ለራሳቸው መጽሐፍ ቅዱስ የሚያነቡበትና የሚያጠኑበት መንገድ አልነበረም። ብዙዎቹ አይሁዶች መጽሐፍ ቅዱስ በምኩራብ ሲነበብ ከመስማት የበለጠ ዕድል አልነበራቸውም። ሁለተኛ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ምሪት ለሕዝቦች ባስፈለገባቸው ሁኔታዎችና ዛሬ ሰዎች ምሪት በሚፈልጉባቸው ሁኔታዎች መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት አለብን።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሰውን ስላዳነበት ታሪክ ይነግረናል። ያ ታሪክ ባብዛኛው ያልተለመዱ ክስተቶችን ያካትት ነበር። እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ ምሪቱን ለመፈጸም ያልተለመዱ ዘዴዎችን ተጠቅሟል። ክስተቶቹ ተደጋጋሚ በሚሆኑባቸው ጊዜያት፥ እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ ምሪቱን ተመሳሳይ በሆኑ መንገዶች ገልጾአል።

ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን አስራኤላውያን መንገድ-አልባ በሆነው የሲና ምድረ በዳ ሲቀበዘበዙ፥ እግዚአብሔር የደመናውንና የእሳቱን ዓምድ ግበረታቻና ምሪት መስጠቱ ነው (ዘኁ. 9፡16-23)። እንዲሁም፥ በመለኮታዊ አሠራር መና በግውሪድ መግቦአቸዋል (ዘጸ. 16፡14-21)። ይሁንና፥ ወደ ከነዓን ምድር በገቡ ጊዜ የመና አስፈላጊነት ስላከተመ፥ የመና ተአምርም አበቃ (ኢያሱ 5፡12)። በተመሳሳይ ሁኔታ፥ ወደ ተስፋዱቱ ምድር ገብተው ሲደላደሉ በደመናና በእሳት ዓምድ መመራቱም አስፈላጊ ባለመሆኑ አበቃ። ስለ ሆነም፥ ወደ ከነዓን ምድር ከገቡ በኋላ እግዚአብሔር አስራኤላውያንን በደመናና እሳት ዓምድ ሲመራቸው አንመለከትም።

የዕለት ተዕለት አኗኗርን በተመለከተ፥ እግዚአብሔር ለአስራኤላውያን በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ እንዴት እንደሚመላለሱና ምን እንደሚያደርጉ፥ በተጻፈው የሙሴ ሕግ አማካኝነት ዝርዝር መመሪያዎችን ሰጥቶአቸዋል (ዘጸ. 21፡1)። በብሉይ ኪዳን ብዙ ጊዜ፥ የእግዚአብሔር

ሕዝቦች እነዚህን ሕጎችና ደንቦች እንዲታዘዙ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸዋል (ዘጸ. 23:21-22፤ ዘዳ. 11:26-28)። በመጽሐፍ ቅዱስ፥ እግዚአብሔር ለቃሉ መታዘዝ ለጥቅማችንና ለሕይወታችን እንደ ሆነ በአጽንኦት ይናገራል። በዘዳግም 6:24 ሙሴ፥ «እንደ ዛሬም በሕይወት እንዲያኖረን፥ ሁልጊዜም መልካም እንዲሆንልን፥ አምላካችንን እግዚአብሔርን እንፈራ ዘንድ፥ ይህችንም ሥርዓት ሁሉ እናደርግ ዘንድ እግዚአብሔር አዘዘን» ብሏል።

አንዳንድ ሰዎች የእግዚአብሔር ትእዛዛት ከባዶች እንደ ሆኑ በግሰብ ይሰሳታሉ። የእግዚአብሔር ትእዛዛት የወላጆች ሕግጋት ለልጆቻቸው ከሚከብዱት በላይ ሸክሞች አይሆኑም። ወላጆች ለልጆቻቸው መልካም እንዲሆንላቸው ደንቦችን እንደሚሰጡ ሁሉ፥ እግዚአብሔርም ለሰው ልጅ መልካም ይሆንለት ዘንድ የግብረ-ገብ ሕግጋትን አስቀምጧል። በ1ኛ ዮሐንስ 5:3 ሐዋርያው ዮሐንስ፥ «ትእዛዛቱም ከባዶች አይደሉም» ይላል። እውነቱ እንግዲህ እግዚአብሔር ስለ ፈጠረን፥ ለእኛ ከሁሉ የሚሻለውንና ለሕይወታችን በረከት የሚያመጣውን እርሱ ብቻ እንደሚያውቅ ነው። ስለ ሆነም፥ በቃሉ ውስጥ የምንመለከታቸውን ትእዛዛትና መመሪያዎች ሰጥቶናል። እነዚህን ትእዛዛት ስንጠብቅና መመሪያዎቹን ስንከተል እንባረካለን። የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ስንጠብቅ እግዚአብሔር ለሰዎች ባዘጋጀው ዕቅድ መሠረት እንኖራለን።

ስለ ሆነም፥ በቃሉ አማካኝነት የሚያስፈልገንን ምሪት መስጠት የእግዚአብሔር ዕቅድ ነው። መዝሙረ ዳዊት፥ «ምስጉን (የተባረከ) ነው በክፉዎች መንገድ ያልሄደ፥ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ . . . ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል፥ ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያስባል» በማለት ይጀምራል (መዝ. 1:1-2)። በመዝሙረ ዳዊት እግዚአብሔር በቃሉ አማካኝነት ሊመራን እንደሚፈልግ ተገልጾአል። «ሕግህ ለእግሬ መብራት፥ ለመንገዴ ብርሃን ነው» [መዝ. (119):105]።

እነዚህ ቃላት እንደሚያስተምሩን፥ እግዚአብሔር በዕለታዊ ሕይወታችን ሊመራን የሚፈልግበት ቀዳሚው መንገድ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ነው። ለዚህ ነው ለክርስቲያን ዕለታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በጣም አስፈላጊ የሚሆነው። መጽሐፍ ቅዱስ ሁልጊዜም ለምንመስናቸው ውሳኔዎች ሁሉ ግልጽ መልሶችን ላይሰጠን ቢችልም፥ ዳሩ ግን ለትክክለኛ ውሳኔ የሚረዱንን ግልጽ መመሪያዎች ይሰጠናል። ትክክለኛ ውሳኔዎችን

በግድረግ ለሕይወታችን በረከትን፥ ለአምላካችን ደግሞ ክብርን እናመጣለን።

በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ከሚገኙ መመሪያዎች በተጨማሪ፥ በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ ለአማኝ የመንፈሳዊ ሰዎችን ምክር መጠየቅ መልካም እንደ ሆነ ይገልጻል። ምሳሌ 15፡22፥ «ምክር ከሌለች ዘንድ የታሰበው ሳይሳካ ይቀራል፤ መካሮች በበዙበት ዘንድ ግን ይጸናል» ይላል። ቆላስይስ 3፡16፥ «የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፤ በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገሥጹ» ይላል። በሕይወት ውስጥ ለምንፈጽማቸው ውሳኔዎች የበሳል ክርስቲያኖች ምክር ሌላው እግዚአብሔር ምሪቱን የሚሰጥበት መንገድ ነው።

ከላይ ከጠቃቀስናቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች እንደምንረዳው፥ ዛሬ እግዚአብሔር በሕይወታችን ሊመራን የሚፈልግባቸው ቀዳሚ መንገዶች፥ ቃሉና በሳል ክርስቲያን ወዳጆች የሚሰጡት ምክር ናቸው። የእግዚአብሔር ቃል ምሪት ክርስቶስ በመንጌላት ውስጥ ካስተማረውና ሐዋርያት ባቀረቡአቸው የአዲስ ኪዳን መልእክቶች ውስጥ ሊገኙ ይችላሉ። ምሪት በመጽሐፈ ምሳሌ ውስጥ ከሚገኙ ምክሮች ሊገኝ ይችላል። በተጨማሪም፥ የብሉይና አዲስ ኪዳን ታሪኮችን በትክክል ከሕይወት ጋር በማዛመድ ምሪት ማግኘት ይቻላል።

ዛሬም እግዚአብሔር በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ ለፖሊሱ ያደረጋቸውን ዓይነት ያልተለመዱ የምሪት ዘዴዎች ሊጠቀም ይችላል። ያልተለመዱት ምሪቶች ሕልሞችን፥ ራእዮችን ወይንም የመላእክትን ቀጥተኛ ጣልቃ ገብነት የሚያካትቱትን ልዩ ሁኔታዎች ሊያጠቃልሉ ይችላሉ። እንዲህ ዓይነት ዘዴዎች መጽሐፍ ቅዱስ በማይኖርበት ጊዜ ወይም ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ለማንበብ በማይችሉበት ጊዜ ከጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። በተጨማሪም ጦርነት፥ እስራት ወይም የተፈጥሮ አደጋ በሚኖርበት ጊዜ ጌታ የዚህ ዓይነቱን የምሪት ዘዴ ሊጠቀም ይችላል።

በሕልም አማካኝነት እንደ ተሰጠ የተገለጸውን ቀጣይ የምሪት ታሪክ ተመልከት፡—

ጴጥሮስ የተባለው አንድ ወጣት ታልቱ በተባለች ወጣት ፍቅር ተነደፈ። ብዙ ጊዜም ታልቱን መንገድ ላይ ያገኛት ነበር። እርስዋም በጣም ትቀርበው ነበር። ጴጥሮስ ታልቱን እንዲህ ዘወትር እንዲያገኝ የሚያደርገው እግዚአብሔር መሆን እንዳለበት ወሰነ። ጴጥሮስ

እግዚአብሔር ታልቱን ያገባ ዘንድ ይመራው እንደ ሆነ በግሰብ ይደነቅ ጀመር። ይብልጥ ከታልቱ ጋር ግላስፍ በመጀመረ ቁጥር፥ ይብልጥ እየወደዳትና ሌሊትና ቀን ስለ እርስዋ እያሰላሰለ ሄደ። ታልቱ ከባህላዊ ቤተሰብ የመጣችና ራሷም የወገኖቿን ባህላዊ ሃይማኖት የምትከተል ልጅ ነበረች።

ምንም እንኳ መጽሐፍ ቅዱሱን በብዛት ባያነብም፥ ጴጥሮስ ታልቱን ሊያገባት እንደሚገባው ወይም እንደማይገባው እግዚአብሔር እንዲመራው በጸሎት ጠየቀ። አንድ ሌሊት ጴጥሮስ ከታልቱ ጋር መጋባቱን የሚያሳይ በጣም ግልጽ ሕልም አየ። ከሕልሙም በነቃ ጊዜ እግዚአብሔር ለጸሎቱ ምላሽ በመስጠት ታልቱን እንዲያገባት እንደ መራው ወሰነ። ይህ የእግዚአብሔር ምሪት ነበር?

ጴጥሮስ መጽሐፍ ቅዱሱን በጥንቃቄ ቢያነብ ኖሮ፥ እግዚአብሔር ለክርስቲያኖች በጋብቻም ይሁን በንግድ ወይም በሌሎች መንገዶች ከምን ዓይነት ሰዎች ጋር ሊተባበሩ እንደሚገባ አስቀድሞ ይረዳ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠ መዱ . . . ብርሃን ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው? . . . ወይስ የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው?» ይላል (2 ቆሮ. 6፡14-15)። የዚህ ምንባብ አንድ ተዛምዶ እግዚአብሔር ክርስቲያን ክርስቲያን ካልሆነ ሰው ጋር እንዲጋባ አለመፈለጉን በግልጽ ያሳያል። እንግዲህ፥ ጴጥሮስ ለምን እንዲህ ዓይነቱን ሕልም ተመለከተ?

ለዚህ ሕልም ምክንያቱ ጴጥሮስ ለታልቱ የነበረው ጠንካራ ፍላጎት ነበር። ብዙዎቻችን ስሜቶቻችን የምናስብበትን መንገድና የምናልምባቸውን ነገሮች እንዴት በከፍተኛ ደረጃ እንደሚጸናወቱ አንገነዘብም። እግዚአብሔር ከቶውንም ከራሱ ጋር ስለማይጋጭ፥ ሕልሙ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሊመጣ አይችልም። እግዚአብሔር በቃሉ አንድ ነገር ከተናገረ፥ በሕልም ሌላ የተለየ ነገር አይናገርም። ስሜታችን ምንም ያህል ቢገፋንም፥ ማንኛውም ሕልም፥ ራእይ ወይም ያልተለመዱ ሁኔታዎች፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኘው ቃል ጋር የሚቃረኑ ከሆነ፥ ከእግዚአብሔር እንደሚመጣ ምሪት ተደርገው ሊወሰዱ እንደማይችሉ ልንረዳ ይገባል።

ለትምህርት ርቆ የሄደው ልጅ አባት፥ ልጁ እንዲያደርግ የሚፈልገው ነገር ሲያጋጥመው ደብዳቤ ይጽፍለታል። እግዚአብሔርም እንደዚሁ ደብዳቤ ጽፎልናል። ለሕይወታችን ፈቃዱን እናውቅ ዘንድ በመጽሐፍ ቅዱስ ተናግሮናል።

ሕልም ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ዓይነተኛ መንገድ እንደ ሆነ ከሚገመት ባህል የመጣውን አሻሽ ለመምራት፥ እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ በሕልም መጠቀሙ እውነት ነው። እንደ አጠቃላይ መመሪያ፥ እግዚአብሔር ለአንድ ባህል ተገቢ እንደ ሆነ የሚቆጠረውን የምሪት ዓይነት ሊጠቀም ይችላል። ያንኑ ተመሳሳይ የምሪት መንገድ ደግሞ ተገቢ እንደ ሆነ በማይቆጠርበት ሌላ ባህል ላይጠቀምበት ይችላል። ለጥንቃቄ ያህል፥ ክርስቲያን እግዚአብሔር በሕልም እንደ ተናገረው ሲያስብ፥ በሕልም ስለሚመጣ ምሪት የሌሎች ክርስቲያኖችን ምክር ሊጠይቅ ይገባል። እንዲሁም፥ በሕልም የመጣውን ምሪት ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር በጥንቃቄ ማስተያየት ያሻል። በሕልም የመጣው ምሪት በመጽሐፍ ቅዱስ ከሚገኙ መመሪያዎች ጋር ሙሉ ለሙሉ የማይስማማ ከሆነ፥ ሕልሙን ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣ ምሪት አድርጎ መቀበል አያስፈልግም።

አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ሁኔታዎች በሚስማሙበት መንገድ ይመራናል። ይሁንና፥ የዚህ ዓይነቱን ምሪት በጥንቃቄ ማስተናገድ አለብን። ከላይ በጴጥሮስ የሕልም ታሪክ ውስጥ እንደተመለከትነው፥ አንዳንድ ጊዜ ሁኔታዎች ሙሉ ለሙሉ ከእግዚአብሔር ዕቅድ በስተያ ሊወሰዱን ይችላሉ። ሁኔታዎችን እንደ እግዚአብሔር ምሪት አድርገን የምናምንበት ብቸኛው ጊዜ፥ ሁኔታው ከመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያዎች ጋር ሙሉ ለሙሉ ሲስማማና በሳል ክርስቲያን ወዳጆቻችንም እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ የእግዚአብሔር ምሪት ሊሆን እንደሚችል ሲያጠናክሩ ነው። ሁኔታዎች ምንም ዓይነት መልክ ቢኖራቸው፥ እግዚአብሔር ምሪቱን ግልጽ ሳያደርግልን አይቀርም። በቀላሉ የምንረዳውንና የምንከተለውን የምሪት መንገድ ይመርጥልናል።

ባጠቃላይ፥ እግዚአበሔር ሁልጊዜም በመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮና መመሪያዎች እንደሚመራን ልንናገር እንችላለን። በተጨማሪም፥ በበሳል ክርስቲያን ወዳጆች ምክር አማካኝነት ሊመራን ይችላል። አንዳንድ ጊዜም በሕልሞች፥ በራእዮችና በሌሎች ይብልጥ ባልተለመዱ መንገዶች ሊመራን ይችላል። ይሁንና፥ ያልተለመዱ የምሪት መንገዶች ሊታመኑ የሚችሉት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘውን ትምህርትና መመሪያዎች ሲያጠናክሩ ነው። እግዚአብሔር ከቶውንም ከራሱ ጋር ስለማይቃረን፥ ክርስቲያን በየቀኑ ለቃሉ ጥናት በቂ ጊዜ ሊመድብ ይገባዋል።

ለ. ክርስቲያን ሐሰተኛና እውነተኛ ነቢያትን የሚለየው እንዴት ነው?

በአዲስ ኪዳን ዘመን ገና አዲስ ኪዳን ተጽፎ ስላላለቀና የእግዚአብሔር እውነት ልዩ መንገዶች ያስፈለጉባቸው ጊዜያት ስለ ነበሩ፥ እግዚአብሔር በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በነቢያት አማካኝነት ይናገር ነበር። ዛሬ በአፍሪካ የእግዚአብሔር ነቢያት እንደ ሆኑ የሚናገሩ ሰዎች ሞልተዋል። ከእነዚህም ሰዎች አንዳንዶቹ በሽተኛን መፈወስና የወደፊቱን ክስተት መተንበይ የመሰሰሉ ያልተለመዱ ኃይላት አሏቸው። እነዚህ ራሳቸው ስለ ራሳቸው ነቢይነት የሚናገሩ ነቢያት በትክክል ከእግዚአብሔር መሆን አለመሆናቸውን እንዴት እናውቃለን?

ክርስቲያኖች ሊጠነቀቁ ይገባል። ብዙ የአፍሪካ ነቢያት በርቱዕ አንደበታቸውና በሚያከናውኑአቸው ተግባራት ሰዎችን ለመግረክ የሚችሉ ናቸው። በተጨማሪም፥ መጽሐፍ ቅዱስ አጋንንት ለሰዎች ተአምራዊ ምልክት የማሳየት ችሎታ እንደሚሰጣቸው ይናገራል (2 ተሰ. 2:9፤ ራእይ 16:14)። ብዙውን ጊዜ እነዚህ ተአምር ሠሪዎች ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ መጡ ይናገራሉ።

የእግዚአብሔር ነቢያት እንደ ሆኑ የሚናገሩ አንዳንድ ሰዎች ከሰይጣን ኃይል የሚቀበሉ የውሸት ነቢያት ናቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመንም እንዲህ ዓይነት ነቢያት ነበሩ (ለምሳሌ ዘጸ. 7:11-12፤ የሐዋ. 8:9-10)። በሚያታልሉ መናፍስት ኃይላት ተአምራዊ ምልክቶች ለማድረግ ይችሉ ነበር። ለዚህ ዓይነቱ ገጠመኝ አንድ ምሳሌ የምትሆነን በሐዋርያት ሥራ 16:16-18 የወደፊቱን ትተነብይ የነበረች ባሪያ ሴት ነች። ጳውሎስ ከዚህች ሴት አጋንንትን ካስወጣ በኋላ፥ የወደፊት ክስተቶችን ለመተንበይ አልቻለችም (የሐዋ. 16:19)።

ክርስቲያን እውነተኛውን ነቢይ ከሐሰተኛው እንዴት ይለየዋል? አንድ ሰው እውነተኛ ሊሆን የሚችለው ትንቢቱ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ እንደ ሆነ ብቻ ነው። ትንቢቱ ከእግዚአብሔር መሆኑን ክርስቲያን እንዴት ለይቶ ያውቃል? ከእግዚአብሔር የመጣ ትንቢት ሁለት ጥያቄዎችን በመመለስ ሊታወቅ ይችላል፦

1. ትንቢቶቹ የተሰጡት ሰዎችን በክርስቶስ መዳለው እምነት ለማምጣት ነው ወይስ ከክርስቶስ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማጠናከር? ዛሬ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚመጡ እውነተኛ ትንቢቶች፥ በክርስቶስ ላይ ከሚኖረን እምነት ጋር የተያያዙ ብቻ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ በራእይ

19፡10፥ «የኢየሱስ ምስክር የትንቢት መንፈስ ነው» ይላል። ስለ ሆነም፥ «ይህ ታዋቂ ድምፃዊ በሚቀጥለው ወር በመኪና አደጋ ይሞታል» የሚለው ዓይነት የተለመደ ትንቢት ፍጻሜ ቢያገኝም እንኳ ከእግዚአብሔር አለመሆኑ ግልጽ ነው። እንደ እግዚአብሔር ቃል አባባል ትንቢት አንድን ሰው ወደ ክርስቶስ የማያስጠጋው ከሆነ፥ ከአታላይ መናፍስት እኀደ መጣ እንረዳለን። ሰዎች ስለ ወደፊቱ የመተንበይ ችሎታቸውን ከየት እንዳገኙ ቢናገሩም ይህ እውነት ነው።

2. ለመሆኑ የሰዎቹ ትንቢቶች ሁልጊዜም ትክክል ናቸው? ይህ ካልሆነ፥ በዘዳግም 18፡21-22 መሠረት ከእግዚአብሔር ዘንድ አይደሉም። ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ ትንቢት አንድ ጊዜ እንኳ አይሳሳትም። ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ ትንቢት እነዚህን ሁለቱንም ፈተናዎች ማለፍ አለበት።

ምንም እንኳ እግዚአብሔር ለሰው ስለ ራሱና ስለ ግዳኑ የሰጠው መገለጽ ሙሉ ለሙሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተካተተ ቢሆንም፥ ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በትንቢት አማካኝነት የማበረታቻ ወይም የማጽኛ ቃል መስጠቱ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የዚህ ዓይነት ትንቢቶች ሲሰጡ፥ ሁልጊዜም ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር በጥንቃቄ ማስተያየቱ ተገቢ ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚስማሙ ከሆነ፥ እነዚህ ትንቢቶች ከእግዚአብሔር ዘንድ ሊሆኑ ይችላሉ። በአንድም መንገድ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የማይስማሙ ከሆነ፥ ወይም በአንድ መንገድ መጽሐፍ ቅዱስን ቢለውጡ፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሊመጡ አይችሉም። ዛሬ በቤተ ክርስቲያን እጅግ የሚያስፈልጉን የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል የሚያስተምሩና የሚገልጹ ወገኖች ናቸው። ዛሬ በቤተ ክርስቲያን እጅግ አስፈላጊው የትንቢት አገልግሎት፥ መጽሐፍ ቅዱስን በትክክል የማብራራት አገልግሎት ነው።

ሐ. የመቀየጥ ችግሮች - ክርስቲያን ሊሳተፍባቸው የሚችልባቸው ልማዶች፥ ሥርዓቶችና ሌሎች ባህላዊ ልምምዶች የትኞቹ ናቸው?

ክርስቲያናዊ ካልሆነ ዳራ የመጡ ሰዎች ብዙውን ጊዜ፥ ክርስትናን በመጡበት ሃይማኖታዊ ሥርዓት ላይ ለማከል ይፈተናሉ። የዚህም ውጤቱ የሁለት ሃይማኖቶች መቀየጥ ይሆናል። ቅይጥነት ("syncretism") ለሁለት ወይም ከዚያ ለሚበልጡ ሃይማኖቶች መቀየጥ የተሰጠ ስያሜ ነው።

አስራኤላውያን ይህንኑ ልምምድ በመከተል እግዚአብሔርን በድለዋል። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «እግዚአብሔርንም ይፈሩ ነበር፥ ከመካከላቸውም

ለኮረብታው መስገጃዎች ካህናት አደረጉ፥ በኮረብታውም መስገጃዎች ይሠዉ ነበር። እግዚአብሔርንም ሲፈሩ ከመካከላቸው እንደፈለሱት እንደ አሕዛብ ልማድ አምላካቸውን ያመልኩ ነበር» ይላል (2 ነገሥት 17፡32-33)። እግዚአብሔር በዚህ በጣም አዝኖ ነበር። በመሆኑም ለእስራኤላውያን፥ «ከእናንተም ጋር ያደርግሁትን ቃል ኪዳን አትርሱ፤ ሌሎችንም አማልክት አትፍሩ። አምላካችሁን እግዚአብሔርን ፍሩ፤ እርሱም ከጠላቶቻችሁ ሁሉ እጅ ያድናችኋል» ብሏል (2 ነገሥት 17፡38-39)።

ይሁንና፥ እስራኤላውያን ቅይጥ ልምምዳቸውን አላቆሙም (2 ነገሥት 17፡40)። እግዚአብሔር ቅጣት ይሆናቸው ዘንድ ለ70 ዓመታት ምርኮ አሳልፎ የሰጣቸው፥ እስራኤላውያን በአካባቢያቸው የነበሩትን ሕዝቦች አረማዊ ልምምዶች ስለ ተከተሉ ነበር (ኤር. 25፡5-11)። በ2ኛ ነገሥት 17፡7-9፥ «የእስራኤልም ልጆች . . . አምላካቸውን በድለው ነበርና . . . እግዚአብሔርም ከእስራኤል ልጆች ፊት ባሳደዳቸው በአሕዛብ ሥርዓት . . . ሄደው ነበርና እንደዚህ ሆነ። የእስራኤልም ልጆች በአምላካቸው በእግዚአብሔር ላይ ቅን ያልሆነን ነገር በስውር አደረጉ» የሚል እናነባለን።

ስለ ሆነም፥ ለክርስቲያን ከሕዝቡ ባህላዊ ሃይማኖታዊ እምነቶች ጋር የተያያዙትን ሥርዓቶችና ልምምዶች አለመከተል በጣም አስፈላጊ ነው። ከረዥም ጊዜያት በፊት እግዚአብሔር ሕዝቡን፥ «እንደ ተቀመጣችሁበት እንደ ግብፅ ምድር ሥራ አትሥሩ፤ እኔም ወደ እርስዋ እንደማገባችሁ እንደ ከነዓን ምድር ሥራ አትሥሩ፤ በሥርዓታቸውም አትሂዱ» ሲል አስጠንቅቆአቸዋል (ዘሌ. 18፡3)።

ክርስቲያን የዚህ ዓይነት ቅይጥ ልምምድ የሚከተል ከሆነ፥ እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ፍርድ በራሳቸው ላይ እንዳመጡ ሁሉ፥ እርሱም የእግዚአብሔርን ፍርድ ይቀበላል። ቅይጥነት ኃጢአት ነው። ይህም እውነት የሚሆነው ብዙ ባህላዊ ሥርዓቶች ክርስቲያናዊ ካልሆኑ ሃይማኖቶች ጋር የተያያዙ በመሆናቸው ነው።

አንዳንድ ሥርዓቶች ሰውን ከክፉ መናፍስት ጋር ወደ መገናኘት ሊያመጡ ይችላሉ። ጳውሎስ ይህ ሁኔታ በባህላዊ የቆሮንቶስ ሃይማኖት ውስጥ ይፈጸም እንደ ነበር ገልጾአል። «አሕዛብ የሚሠዉት ለአጋንንት

እንዲሆን እንጂ ለእግዚአብሔር እንዳይሠዉ እላለሁ፣ ከአጋንንትም ጋር ማኅበረተኞች እንድትሆኑ አልወድም» (1 ቆሮ. 10:20)።

አፍሪካውያን ቅይጥ ልምምድን የሚከተሉበትን ምክንያት ለመረዳት የሚያስቸግር አይደለም። በአፍሪካ ባህላዊ ተሐድሶ ብዙ ሰዎች የቀድሞውን ማንነታቸውን ዳግም እንዲገነዘቡ አድርጓል። በአፍሪካ ባህልና ሃይማኖት በቅርብ የተቆራኙ እንደ መሆናቸው፣ ይህ ወደ ባህላዊ ሃይማኖታዊ ልምምድ እንዲመለሱ መርቷል። ከዚህም ጋር ወንጌል ከመድረሱ በፊት ለሞቱት ዘመዶች መንፈሳዊ ደኅንነት ማሰባቸው፣ ቀደም ሲል የሥነ-መለኮት ምሁራን የነበሩትን ጨምሮ፣ ብዙዎችን ሰዎች የቅድመ-ክርስትናን ባህላዊ ሃይማኖቶች ፍትሐዊነት ለማረጋገጥ እንዲጥሩ አድርጓቸዋል። በአፍሪካውያን አመለካከት፣ ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር ሩቅና የማይደረስበት ሆኖ ይታያል። ስለ ሆነም፣ ለተራ ችግሮች ሰዎች እግዚአብሔርን ከማወክ ይልቅ በአናሳ መናፍስትና አማልክት መገልገሉን ፍጹም ተስማሚ አድርገው ይወስዳሉ። እንዲያውም፣ «የአፍሪካ ሥነ-መለኮት» ዕድገት፣ የባህላዊ ሃይማኖቶች ልምምድ እግዚአብሔር ለክርስቶስ ወንጌል መስፋፋት ያመቻቸው ቅድመ ዝግጅት እንደ ሆነ ለማረጋገጥ የሚደረግ ጥረት ሆኗል። ይሁንና፣ ይህንን አመለካከት በመጽሐፍ ቅዱስ ልናስደግፍ አንችልም።

በአፍሪካ በሚገኙት በብዙዎቹ ለዘብተኛ የሥነ-መለኮት ትምህርት በሚራመዱ ጥንታዊ የቤተ ክርስቲያን የእምነት ከፍሎች ዘንድ፣ እውነተኛ እስከ ሆንህ ድረስ የምታምነው ነገር አስፈላጊነቱ ውስን ነው የሚል አስተሳሰብ እየጎለበተ ነው። በተጨማሪም፣ ብዙ አዳዲስ ክርስቲያኖች እምብዛም የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት የላቸውም። ስለ ሆነም፣ እግዚአብሔር ክርስቲያናዊ ካልሆነ ልምምድ ጋር አጣምረው ሲያመልኩት ሊታገሥ እንደማይችል አይገነዘቡም።

ክርስቶስን ለመከተል የሚወስኑ ብዙ ሰዎች ማንነቱንና እርሱንም ለምን እንደሚከተሉ በሚገባ ሳይገነዘቡ ይህንኑ ውሳኔ ያደርጋሉ። ምናልባት ኢየሱስ ለኃጢአታቸው ይቅርታ ለማስገኘት እንደ ሞተ ይረዱ ይሆናል። ይሁንና፣ ኢየሱስ የአጽናፈ-ዓለሙ ጌታና በምድርም ሆነ በሰማይ ሥልጣን ሁሉ እንዳለው አይረዱም። ኢየሱስ ብቻ የሚያጋጥማቸውን እጅግ የከፋ ጉድለት ወይም ችግር ከመሙላት የላቀ ችሎታ እንዳለው አይገነዘቡም።

ስለ ሆነም፥ የግል ችግር ሲያጋጥማቸው ወደ አያት ቅድማያት መናፍስት ወይም ወደ ምሥጢራዊ ኃይላት ይመለሳሉ። ወላጆቻቸውና አያት ቅድማያቶቻቸው ለአያሌ ትውልዶች የባህላዊ ሃይማኖቶችን ልምምዶች ስለ ተከተሉ፥ በትልቅ ችግር ጊዜ እነዚህ ልምምዶች ብቻ እውነተኛ ኃይል ያላቸው ይመስላቸዋል። ወደ እነዚህ መናፍስትና ኃይላት በመመለስ በሕያው እግዚአብሔር ፊት ሌሎች አማልክት እያስቀመጡ መሆናቸውን አይገነዘቡም። ይህንንም በማድረግ፥ ከራሱ ከእግዚአብሔር ሊያገኙ ይችሉ የነበሩትን እርዳታና ጥበቃ አጥተው በምትኩ የእግዚአብሔርን ፍርድ ይጋብዛሉ። ይህንን ለሚያደርጉ ሰዎች እግዚአብሔር፥ «እናንተ ግን ተዋችሁኝ ሌሎችንም አማልክት አመለካችሁ፤ ስለዚህ ደግሞ አላድናችሁም። ሄዳችሁ የመረጣችኋቸውን አማልክት ጥሩ፤ እነርሱም በመከራችሁ ጊዜ ያድኑአችሁ» ይላል (መሳ. 10፡13-14)።

ሕያው እግዚአብሔር የተከፋፈለ ታማኝነት የማይቀበል ሲሆን፥ ሌሎች «አማልክት» እንዲረዱአቸው የሚፈልጉትን ሰዎች አይረዳም። ለዚህ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ ከሁሉም የምትበልጠው ትእዛዝ «አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ» የምትል እንደ ሆነች የተናገረው (ዘዳ. 6፡5፤ ማቴ. 22:37-38)።

ብዙ የአፍሪካ ክርስቲያኖች ክርስቶስን እንከተላለን እያሉ የግል ችግር ሲያጋጥማቸው ለእርዳታ ወደ ጠንቋይ ወይም ምዋርተኛ መሄዳቸውን ሲቀጥሉ፥ በቅይጥ ልምምድ ፈተና ይጠመዳሉ። ክርስቲያኖች የክርስትና እምነታቸውን ከእነዚህ ባህላዊ ልምምዶች ጋር ሲያዋህዱ ቅይጥነትን ይከተላሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መሥዋዕቶችና ሥርዓቶች ምን ይላል? በብሉይ ኪዳን ብዙ ሥርዓቶችና የእንስሳት መሥዋዕቶች መቅረባቸው እውነት ቢሆንም፥ መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ለኃጢአት እግዚአብሔር የሚቀበለውን አንድ መሥዋዕት እንዳቀረበ ይናገራል። ከአዲስ ኪዳን እንደምንረዳው፥ የብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶችና ሥርዓቶች ኃጢአትን ሊያስወግዱ አይችሉም (ዕብ. 10፡4)።

እንግዲህ፥ የእነዚህ የብሉይ ኪዳን ሥርዓቶች ዓላማ ምንድን ነው? ቆላስይስ 2፡17 እነዚህ ነገሮች ወደፊት የሚመጡ ነገሮች ጥላ እንደ ሆኑና እውነታው ግን በክርስቶስ እንደሚገኝ ይገልጻል። በሌላ አባባል፥ የብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶችና ሥርዓቶች እግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ

መሥዋዕትና ደኅንነት የሰጣቸው መግለጫዎች ናቸው። አዲስ ኪዳን፥ «(የብሉይ ኪዳን) ሊቀ ካህናትም ሁሉ ዕለት ዕለት እያገለገለ ኃጢአትን ሊያስወግዱ ከቶ የማይችሉትን እነዚያን መሥዋዕቶች ብዙ ጊዜ እያቀረበ ቆሞአል፤ እርሱ (ኢየሱስ) ግን አንድን መሥዋዕት . . . አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጎአቸዋልና» ይላል (ዕብ. 10፡11-14)።

ለብዙ አፍሪካውያን የሥርዓቶች ተካፋይ መሆን አስፈላጊ ነገር ነው። ኢየሱስ የሰውየውን ዳግም ልደት ለመመስከር ለአንዱና ለመጨረሻ ጊዜ የሚፈጸም ሥርዓት አዝዞአል። ይህም የውኃ ጥምቀት ሥርዓት ነው (ማቴ. 28፡19)። በምዕራፍ አሥራ ሦስት ከአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓቶች ሥር እንደ ቀረበው፥ በተለይ በአፍሪካ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለውኃ ጥምቀት ይፋዊ እውቅና ብትሰጥ መልካም ነው። በቤተ ክርስቲያን ጎብረተሰብ ውስጥ ይህ ዐቢይ ክስተት ሊሆን ይገባል።

ኢየሱስ ክርስቲያኖች ለኃጢአታቸው ሲል በመስቀል ላይ መሞቱን ያስቡ ዘንድ ሌላም ሥርዓት ሰጥቶአቸዋል (ማቴ. 26፡26-28)። ይህ ሥርዓት በዓለም በሁሉም ክርስቲያኖች ዘንድ መደበኛ ሥርዓት ሆኖ ይከበራል። ይህም የቅዱስ ቁርባን ሥርዓት ነው። የኢየሱስ ሞት እውነታ በሕዝቡ አእምሮ ውስጥ አዲስ ሆኖ እንዲቆይ ይህ ሥርዓት በመደበኛነት ሊዘወተር ይገባል።

በአፍሪካ ክርስቲያናዊ ካልሆኑ ሃይማኖቶች ጋር ያልተዛመዱ አንዳንድ ሥርዓቶች አሉ። አንዳንድ የሕዝብ ቡድኖች በእያንዳንዱ አዲስ ዓመት መጀመሪያ ትልቅ በዓል ያደርጋሉ። አንዳንዶች ደግሞ የአደን ውሎአቸው የተሳካ እንዲሆን ልዩ በዓል ያዘጋጃሉ። በዓለም ሁሉም ባህል ሰርግንና ልጅ መወለድን ተከትለው የሚመጡ ልዩ ወጎችና ባህላዊ ልምምዶች አሉት። በአብዛኛው ምዕራባዊና ዘመናዊ የአፍሪካ ሰርጎች፥ ሙሽራውና ሙሽራዪቱ የሰርጉን ኬክ በጋራ ቆርሰው ሁለቱም ትንሽ ቁራሽ የሚበሉበት የሥርዓት ልምድ አለ። ይህ ጉዳት የማያመጡ ልምምዶች ምሳሌ ነው።

ክርስቲያን በየትኞቹ ሥርዓቶች እንደሚካፈልና የትኞቹን እንደሚተው እንዴት ይወስናል? እንደ አጠቃላይ መመሪያ፥ ክርስቲያናዊ ካልሆኑ ሃይማኖቶች ጋር ባልተጠላለፉ፥ መጽሐፍ ቅዱስ የሚኮንነውን ማንኛውንም ነገር በማያካትቱ ወይም የክርስቲያኑን ምስክርነት በማያጠፉ ልምምዶች ውስጥ መሳተፍ ጉዳት ላይኖረው ይችላል። ክርስቲያን በሚያደርገው ነገር

ሁሉ አምንታዊ ክርስቲያናዊ ምስክርነት ለመጠበቅ መሻት አለበት። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ለማስከበር ሲባል፥ ሁልጊዜም ባሕርዩ ነቀፋ የሌለበት ሊሆን ይገባል (ፊልጵ. 2፡15)። ኢየሱስ፥ «መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ» ብሏል (ማቴ. 5፡16)።

ብዙ ልምምዶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሰም አልተዘረዘሩም። አንድ ሰው ስለ አንድ ልምምድ እርግጠኛ ካልሆነ፥ አያሌ በሳል ክርስቲያን ሽማግሌዎችን በማማከር የሚሉትን መስማቱ ከሁሉም የተሻለ ነው። ሽማግሌዎቹ ስለ ልምምዱ ማንኛውንም ዓይነት ማስጠንቀቂያ ወይም ጥርጣሬ ካላቸው፥ ከዚያ ልምምድ መታቀቡ ሳያውቁ ኃጢአት ከመፈጸም ያድናል።

ሌላም የተያያዘ ጉዳይ አለ። በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያልተጠቀሱትን ልምምዶች ማድረግ ለአንዳንድ ክርስቲያናች ኃጢአት ሲሆን፥ ለሌሎች ደግሞ ኃጢአት አይመስላቸውም። በዚህ ጊዜ፥ ልምምዱን ማድረግ ትክክል ነው ብሎ የሚያምነው «ጠንካራ» ክርስቲያን ስሕተት ነው ብሎ ለሚያምነው (ለ«ደካማው» ክርስቲያን) ሕሊና ሲባል፥ ከልምምዱ መራቅ አለበት። ጳውሎስ በሮሜ 14፡1-16 እና 1ኛ ቆሮንቶስ 8፡7-13 ያስተማረው ይህንኑ ነው።

ለዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ምሳሌ የሚሆነን ምናልባት ሲሞት ያልደማውን እንስሳ ሥጋ መብላት ሊሆን ይችላል። ይህም ለምሳሌ በመንገድ ላይ በመኪና ተገጭቶ የሞተውን እንስሳ ሥጋ ሊሆን ይችላል። በዘሌዋውያን 17፡12-14 እና የሐዋርያት ሥራ 15፡29 በተገለጸው መሠረት፥ ሙስሊሞች ሁሉና አንዳንድ ክርስቲያናች እንዲህ ዓይነቱን ሥጋ መብላት ኃጢአት እንደ ሆነ ሊያስቡ ይችላሉ። ሌሎች ክርስቲያናች ደግሞ በማርቆስ 7፡19 ላይ በመመሥረት ኃጢአት እንዳልሆነ ሊያስረዱ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ፥ ሥጋውን መብላት ኃጢአት እንዳልሆነ የሚያስቡ ክርስቲያናች፥ ሌላው ሰው የሚሰናከል ከሆነ ከመብላት ሊታቀቡ ይገባል።

በበሽታ ጊዜ የመድኃኒት እርዳታ መፈለግን በተመለከተ፥ በተለይም ከባህላዊ መድኃኒት ጋር ባህላዊ ሃይማኖት የሚከተሉትን ሰዎች ማስወገዱ አስፈላጊ ነው። ባህላዊ መድኃኒት ከሚቀምሙ ሰዎች አንዳንዶቹ ንጹሕ የቅጠላቅጠል ወይም የአጥንት ባለሙያዎች (ወጌሻዎች) ይሆናሉ። በዚህ ጊዜ ክርስቲያናዊ ያልሆነ ሃይማኖት ስለሌለበት፥ እነዚህን ሰዎች ማማከሩ ኃጢአት አይሆንም። ይሁንና፥ ብዙ ቅጠል ቀማሚዎች ባህላዊ

መድኃኒቶቻቸውን ሊያዘጋጁ የመናፍስትን እገዛ ይሻሉ። ክርስቲያን የዚህ ዓይነቱን መድኃኒት በመውሰድ፥ ባለማወቅ አጋንንትን በሚያካትት ነገር ውስጥ ሊዘፈቅ አይገባም።

በተግባር ሲታይ፥ መንፈሳዊ አደጋ ባይኖርበት እንኳ የአንዳንዱ ንጹሕ ቅጠል ቀማሚዎችን መድኃኒት መጠቀም ጤናማ ሳይሆን ይችላል። ይህ በተለይ ለፅንስና ለጉበት በሽታ መድኃኒትነት በሚውልበት ጊዜ አደገኛ ነው። ክርስቲያን ሰውነቱ ለእግዚአብሔር ከብር ሊውል የሚገባ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ እንደ ሆነ ሊያስታውስ ይገባል (1 ቆሮ. 6፡19-20)፤ ስለ ሆነም፥ ክርስቲያን ከሁሉም የተሻለውን የሕክምና እርዳታ ለማግኘት መሻት አለበት።

መ. በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሊያግልድ የሚችል ማን ነው?

በአፍሪካ አማላጆች በጣም አስፈላጊዎች ናቸው። ብዙ ልምምዶች በአማላጅ አገልግሎት ዙሪያ ተመሥርተዋል። አማላጅ ሁለት ሰዎችን ወይም ቡድኖችን ወደ መስማማት የሚያመጣ አካል ነው። ብዙ የአፍሪካ ጋብቻዎችና አንዳንድ የሥራ ግንኙነቶችም ሳይቀሩ በአማላጅ አማካኝነት የሚፈጸሙ ናቸው። ብዙ ባህላዊ ሃይማኖቶች እግዚአብሔር እንደ አያት ቅድማያት መንፈስ በመሳሰሉ አማላጆች አማካኝነት ብቻ እንጂ በቀጥታ ሊመለክ (ሊቀርቡት) እንደማይቻል ያምናሉ።

በእግዚአብሔር ፊት የሰውን ልጅ፥ በሰው ልጅ ፊት ዳግሞ እግዚአብሔርን ሊወክል የሚችለው ማን ነው? የአናሳ መናፍስትን አማላጅነት ሳይጠቀሙ በቀጥታ ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት ይቻላል? ክርስቲያናዊ ያልሆኑትን ሃይማኖቶች የሚከተሉ ሰዎች ብዙውን ጊዜ የአያት ቅድማያት መናፍስት፥ አግልክት፥ ነቢያት፥ ወይም ሌሎች አዋቂዎች በሰው ልጆችና በእግዚአብሔር መካከል የአማላጅነትን ተግባር እንደሚፈጽሙ ያምናሉ። አንዳንድ ክርስቲያኖችም ሳይቀሩ የሞቱት ክርስቲያኖች ወይም የኢየሱስ እናት ማርያም በእነርሱና በእግዚአብሔር መካከል ሊያግልዱ እንደሚችሉ ያምናሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጉዳይ ምን ይላል?

መጽሐፍ ቅዱስ፥ «አንድ እግዚአብሔር አለና፥ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው» ይላል (1 ጢሞ. 2፡5)። ይህ ጎረፍተ ነገር በእግዚአብሔርና በሰው ልጅ መካከል እግዚአብሔር የሚቀበለው አንድ ሥልጣን ያለው አማላጅ እንዳለ ያመለክታል። እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ

ነው (ዕብ. 9፡15)። ሌሎችን አማላጆች የሚፈልጉ ሰዎች በአጋንንታዊ መናፍስት ሊጠቁ ይችላሉ።

ይህም ክርስቲያኖች ለአማኝ ወዳጆቻቸው ሊጸልዩ አይችሉም ማለት አይደለም። ሊጸልዩ ይችላሉ፤ መጸለይም አለባቸው። ይሁንና፥ የሰውን ልጅ በእግዚአብሔር ፊት የመወከል ሥልጣን ያለው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። እግዚአብሔርንም ለሰው ልጅ የመወከል ሥልጣን ያለው ክርስቶስ ብቻ ነው። በመስቀል ላይ ሞቶ ሰውንና እግዚአብሔርን ያስታረቀው እርሱ ብቻ ነው (ቆላ. 1፡19-20)። በተጨማሪም፥ ከክርስቶስ ጋር በሚኖረን የግል ግንኙነት ላይ ካልተመሠረተ፥ ለእግዚአብሔር መጸለዩ ዋጋ የለውም። «በኢየሱስ ስም» የመጸለዩ ትርጉም ይኼ ነው (ዮሐ. 16፡24-27)። ጸሎታችን በእግዚአብሔር አብ እንዲደመጥ ሊያደርግ የሚችለው ኢየሱስ ብቻ ነው። ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ በመናፍስት የማማለዱ አሳብ በጠቅላላው የአጋንንት ማታለያ ነው (1 ጢሞ. 4፡1)። ይህ ማታለያ አንዳንድ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ከእግዚአብሔር ጋር ግላዊ ግንኙነት እንዳያደርጉ አቅቦአል።

ሠ. ክርስቲያን ለአገሩ መንግሥት የሚኖረው ኃላፊነት ምንድን ነው?

በዓለም በሚገኙ አገሮች በሙሉ ማለት ይቻላል ክርስቲያኖች ስለ አገራቸው መንግሥት ያጉረመርማሉ። በታሪክ ሙሉ ለሙሉ እውነተኞች የነበሩ የመንግሥት ባለሥልጣናት መኖራቸው እውነት ነው። ክርስቲያኖች በአገራቸው መንግሥት ላይ ምን ዓይነት አመለካከት ሊኖራቸው ይገባል? መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

ይህንን ጥያቄ ለመመለስ፥ አንድ ክርስቲያን የሰብአዊ መንግሥትን ጅማሬ መረዳት አለበት። ከሰው ዕይታ አንጻር፥ የተወሰነ መንግሥት የሚኖረው የተወሰኑ ጠንካራ ሰዎች በወታደራዊ ኃይል ወይም ፖለቲካዊ ጥረት አማካኝነት፥ በሌሎች ላይ ኃይል ሊቀዳጁ በመቻላቸው ምክንያት እንደሆነ ማሰቡ ቀላል ነው።

ይሁንና፥ መጽሐፍ ቅዱስ በሰብአዊ መንግሥታት ላይ የተለየ አመለካከት አለው። በምዕራፍ አራት እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ለመቆጣጠር ኃይል እንዳለው ተመልክተናል። እርሱ ሉዓላዊ ነው [መዝ. (103)፡19]። እግዚአብሔር ሉዓላዊነቱን በተግባር ላይ ከሚያውልባቸው መንገዶች አንዱ የሰብአዊ መንግሥታት መውደቅና መነሣት ነው። በሮሜ 13፡1-2 እነዚህን አስገራሚ ቃላት እናነባለን፡- «ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት

ባለ ሥልጣኖች ይገዛ። ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው። ስለዚህ ባለሥልጣንን የሚቃወም የእግዚአብሔርን ሥርዓት ይቃወማል፤ የሚቃወሙትም በራሳቸው ላይ ፍርድ ይቀበላሉ።» መጽሐፍ ቅዱስ ሰብአዊ መንግሥታት በእግዚአብሔር እንደ ተመሠረቱ ያስተምራል።

ብዙዎቹ ክርስቲያኖች፥ በተለይም በጣም ብልሹ ወይም ጨቋኝ በሆነ መንግሥት አገዛዝ ሥር ሲወድቁ፥ ከላይ የተመለከተውን ምንባብ ለመቀበል ይቸገራሉ። ጳውሎስ ይህንን መልእክት የጻፈው በሮም ለነበሩት ክርስቲያኖች እንደ ነበር ስንረዳ፥ እነዚህ ቃላት ይበልጥ ያስገርሙናል። ሮም ቄሣሮች ተብለው የሚጠሩ አንዳንድ ብልሹና ጨቋኝ ገዥዎች የሚገኙባት አረማዊት ከተማ ነበረች። ጳውሎስ መልእክቱን ለሮም አማኞች ከጻፈ ብዙም ሳይቆይ፥ ከእነዚህ ቄሣሮች አንዳንዶቹ ክርስቲያኖችን በከፋ ሁኔታ አሳደዋቸዋል።

ይሁንና፥ መንፈስ ቅዱስ በጳውሎስ አማካኝነት እግዚአብሔር ከመሠረተው በቀር የመንግሥት ሥልጣን እንደሌለ ይነግረናል። ይህን ሲል መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉም መንግሥት መልካም እንደ ሆነ መግለጹ አይደለም። የሰው መንግሥት እግዚአብሔር ለሰው ልጅ በጎነት ያቀደው ነገር እንደ ሆነ ብቻ ይገልጻል። ሰብአዊ መንግሥት እግዚአብሔር በአንዲት አገር ሕግና ሥርዓት የሚያስከብርበት መንገድ ነው (ሮሜ 13፡3-4)። በአንዲት አገር መንግሥት ባይኖር፥ ሁኔታው ምን ሊመስል እንደሚችል አስብ። ሰዎች እንቀጣለን የሚል ሥጋት ሳይኖርባቸው ሙሉ ለሙሉ የኃጢአት ተፈጥሮአቸው እንደ ፈቀደላቸው ይሆኑ ነበር። ወንጀል ከቁጥጥር ውጭ ይሆን ነበር። የፖስታ አገልግሎት ወይም ሌላ የመንግሥት ድርጅት አይኖርም ነበር። በዚህም፥ ሕይወት የማይወጣት አቀበት ትሆን ነበር። በሮሜ 13፡4፥ «(የመንግሥት ባለሥልጣን) ክፉ አድራጊውን የሚበቀል የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና» የሚል እናነባለን።

አንዳንድ መንግሥታት ከሌሎች በላይ ብልሹዎች ናቸው። ክርስቲያኖች በክፉ መንግሥት አገዛዝ ሥር ሲኖሩ ምን ሊያደርጉ ይገባል?

መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያን ለአገሩ መንግሥት በሚኖረው ኃላፊነት ላይ በጣም ግልጽ ነው። መጸለይና መታዘዝ ይኖርበታል። በ1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡1-2፥ «ልመናና ጸሎት . . . ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ» የሚል እናነባለን። ክርስቲያኖች ስለ አገራቸው መንግሥት በማማረር ብዙ ጊዜ ያሳልፋሉ። ይሁንና፥

ለመንግሥትና ለመንግሥት ባለሥልጣኖች በመጸለይ የሚያሳልፉት ጊዜ ምን ያህል ነው? ይህ መልካም አሳብ ብቻ ሳይሆን ከጌታ የተሰጠ ትእዛዝ ነው። እንዲያውም፥ የመጀመሪያው አስፈላጊ ነገር ነው። ሐዋርያው፥ «ከሁሉ በፊት እመክራለሁ» ይላል (1 ጢሞ. 2፡1-2)።

ለክርስቲያኖች ለአገራቸው መንግሥት አለመጸለይ ትልቅ ኃጢአት ነው። አላስፈላጊ የሆኑ ብዙ ሥቃዮችና መጥፎ አገዛዞች የሚመጡት፥ የእግዚአብሔር ሕዝቦች አዘወትረውና ትኩረት ሰጥተው ለመንግሥታቸው ባለመጸለያቸው ነው። ዲያብሎስ ሰብአዊ መንግሥታትን በመጠቀም ዓለምን ለመቆጣጠር እንደሚፈልግ በምዕራፍ አሥራ አንድ ተመልክቷል። ለመንግሥት ባለሥልጣኖች በምንጸልይበት ጊዜ ሰይጣን በእነዚህ ባለሥልጣናት ላይ ያለውን ተጽዕኖ እናቀርባለን። በተጨማሪም፥ በጸሎታችን እነዚህ ባለሥልጣናት የእግዚአብሔርን ጥበብና እገዛ እንዲያገኙ እናደጋለን። ክርስቲያን ሁሉ በየሳምንቱ የተወሰነ ጊዜ ለአገሩ መንግሥት ቢጾምና ቢጸልይ፥ ይህ እጅግ የተገባ ልምምድ ይሆናል። በዓለም ሁሉ የሚገኙ ክርስቲያኖች ይህንን ቢያደርጉ፥ የሰው ልጅ የታሪክ ምዕራፍ ይለወጥ ነበር። አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትም ለአገራቸው መንግሥት ለመጸለይ ልዩ ጊዜ መመደብ አለባቸው።

እግዚአብሔር የሕዝቡን ጸሎት ለመመለስ የተስፋ ቃል ሰጥቷል (ማቴ. 18፡19)። ከክርስቲያኖች ባሻገር፥ ለአገራቸው መንግሥት እርዳታ ለማግኘት ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ ዕድል ያለው የለም።

እግዚአብሔር ለመንግሥት መሪዎቻችን እንድንጸልይ ስላዘዘን፥ እነዚያን ጸሎቶች ለመመለስ ዝግጁ ነው። መንግሥቱ በጣም ከፉ ከሆነ፥ እግዚአብሔር ሙሉ ለሙሉ ሊለውጠው ይችላል። በዳንኤል 2፡21፥ «(እግዚአብሔር) ነገሥታትን ያፈልሳል፥ ነገሥታትንም ያስነሣል» የሚል እናነባለን።

እግዚአብሔር ሁልጊዜም ጸሎታችንን በመመለስ ጠቅላላውን መንግሥት ላይለውጥ ቢችልም፥ በሥልጣን ላይ የሚገኙትን ሰዎች ልብ ሊለውጥ ይችላል። በቅርቡ የተፈጸመው የዚህ እውነታ አስደናቂ ምሳሌ፥ እግዚአብሔር በኮሚኒስት አገሮች የነበሩትን የአያሌ መሪዎች ልብ መለወጡ ነው። ኮሚኒዝምን በግበረታታት ክርስቲያኖችን ያስሩ የነበሩ ሰዎች ራሳቸው፥ በ1990ዎቹ መጀመሪያ ላይ ኮሚኒዝምን ከደዋል። የቀድሞዪቱ ሶቭየት ኅብረት፥ ከሃዲያን ኮሚኒስቶች፥ ክርስቲያኖች ወደዚያው መጥተው በሕዝብ ትምህርት ቤቶች ክርስትናን እንዲያስተምሩ

ጠይቀዋል! እንዲህ የሰውን ልብ ሊለውጥ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

በቀድሞዋ ሶቭየት ኅብረት ለምን እንዲህ ዓይነት ታላላቅ ለውጦች እንደ ተፈጸሙ ምናልባትም በርካታ ምክንያቶች ይኖራሉ። ይሁንና፥ ከሁሉም የሚበልጠው ምክንያት ስደትን የተቀበሉ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ያቀረቡት ጸሎት ነው። እነዚህ ክርስቲያኖች በ70 የግርክሲስት አገዛዝ ዓመታት፥ የኮሚኒስት ጭቆና ያከትም ዘንድ መጸለያቸውን ቀጥለው ነበር። ሕዝቡ በታማኝነት ቢጸልይ እግዚአብሔር የአፍሪካን የመንግሥት መሪዎች ልብ ሊለውጥ ይችላል።

የአገሪቱ መንግሥት ዲሞክራሲያዊ እስከ ሆነ ድረስ፥ በመንግሥት ምርጫዎች በጸሎት መካፈል የክርስቲያን ኃላፊነት ነው። የአንዳንድ ዲሞክራሲያዊ መንግሥታት ልምድ እንዳመለከተው፥ ክርስቲያኖች በአሳሳቢ ጉዳዮች ላይ ድምፃቸውን አስተባብረው ሲያሰሙ፥ የመንግሥታቸውን ፖለቲካና ሕግጋት ከእግዚአብሔር ፈቃድ አኳያ በጽድቅ ለመለወጥ ይችላሉ።

ክርስቲያኖች ለመንግሥታቸው ያላቸው ሁለተኛው ኃላፊነት፥ መንግሥትን መታዘዝና ሕግጋቱን መጠበቅ ናቸው። በ1ኛ ጴጥሮስ 2፡13-15፥ «ስለ ጌታ ብላችሁ ለሰው ሥርዓት ሁሉ ተገዙ፤ ለንጉሥም ቢሆን ከሁሉ በላይ ነውና፤ ለመኳንንትም ቢሆን፥ ክፉ የሚያደርጉትን ለመቅጣት በጎም የሚያደርጉትን ለማመስገን ከእርሱ ተልከዋልና ተገዙ። በጎ እያደረጋችሁ የማያውቁትን ሞኞች ዝም ታሰኙ ዘንድ እንዲህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነውና» የሚል እናነባለን።

ክርስቲያኖች የአገራቸውን መንግሥት ሊታዘዙ የማይገባበት ብቸኛው ምክንያት፥ መንግሥት ክርስቲያኖች ስለ ክርስቶስ እንዳይናገሩ ሲከለክል ወይም የእግዚአብሔርን ሕግ የሚተላለፍ ነገር እንዲያደርጉ ሲያዛቸው ብቻ ነው። በሐዋርያት 4፡17-20፥ ሐዋርያው ጴጥሮስና ዮሐንስ ስለ ክርስቶስ እንዳይናገሩ የአይሁድ መሪዎች ከልክለዋቸው ነበር። በዚህም ጊዜ፥ በጉዳዩ ላይ ከሰው ይልቅ እግዚአብሔርን መታዘዝ እንዳለባቸው ገለጹ (የሐዋ. 4፡19-20)። በዳንኤል 3፡13-18፥ ሦስቱ የዳንኤል ጓደኞች ንጉሡ ላቆመው ጣዖታዊ የወርቅ ምስል ወድቀው እንዲሰግዱ በንጉሥ ናቡከደነፆር ተጠየቁ። ይሁንና፥ ሁለተኛውን ትእዛዝ ጥሰው (ዘጸ. 20፡4-5)፥ ለናቡከደነፆር ምስል ሊሰግዱ አልፈለጉም። በዚህም ምክንያት ወደ

እቶን እሳት ተጣሉ። ይሁንና፥ ናቡከደነፆር በዓይኑ በብሌኑ ፈጦ እያየ እግዚአብሔር አድኖአቸዋል (ዳን. 3፡19-27)።

ክርስቲያኖች ከግጉረምረም ይልቅ ለመንግሥታቸው በመጸለይና ሕግጋቱን በመታዘዝ፥ በዓለም ፊት ስለ ክርስቶስ መልካም ምስክርነት ይኖራቸዋል። እንዲሁም «የማያውቁትን ሞኞች ዝም ያሰኛሉ» (1 ጴጥ. 2፡15)።

ማጠቃለያ

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት ሕዝቡን ለመምራት የተለያዩ መንገዶችን እንደ ተጠቀመ ያመለክታል። ይሁንና፥ እነዚህ ሁኔታዎች የተፈጸሙት መጽሐፍ ቅዱስ ከመጻፉ ወይም እንደ ዛሬው በእግዚአብሔር ሕዝብ እጅ ከመገኘቱ በፊት ነበር። ዐ.ጽ.ሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በታሉ አማካኝነት ሕዝቡን የሚመራበትና የሚያስተምርበት ቀዳሚ መሣሪያ እንደ ሆነ ይገልጻል [መዝ. 1፡1-2፤ (119)፡105]። በተጨማሪም፥ መጽሐፍ ቅዱስ ወላጆችን ጨምሮ ከመንፈሳዊ አማካሪዎች ምክር መጠየቁ መልካም እንደ ሆነ ይገልጻል (ምሳሌ 1፡8፤ 11፡14፤ ቆላ. 3፡16)። ባልተለመዱ ሁኔታዎችና እግዚአብሔር እንደ ሕልም ያሉትን ሌሎች የምሪት መንገዶች በተጠቀመባቸው አንዳንድ ባህሎች፥ ዛሬም እንዲህ ዓይነት መንገዶችን ሊጠቀም ይችላል። ይሁንና፥ ክርስቲያን እግዚአብሔር ባልተለመዱ መንገዶች እየመራው እንደ ሆነ ሲያስብ የዚህ ዓይነቱ ምሪት ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ጋር ፅመሳከር አለበት። እግዚአብሔር ከቶውንም ከቃሉ ጋር የሚጻረር ምሪት አይሰጥም።

ዛሬ በአፍሪካ የእግዚአብሔር ነቢያት እንደ ሆኑ የሚናገሩ ብዙ ሰዎች አሉ። ሰዎች እውነተኛውን የእግዚአብሔር ነቢይ እንዴት ይለያሉ? መጽሐፍ ቅዱስ፥ «የኢየሱስ ምስክር የትንቢት መንፈስ ነው» ይላል (ራእይ 19፡10)። ዛሬ ብቸኛዎቹ እውነተኛ የእግዚአብሔር ነቢያት፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚነገረውን እውነት የሚያውጁና የሰዎችን ልብ ወደ ክርስቶስ የሚመልሱ ናቸው።

በባህላዊ ሥርዓቶች የመካፈሉስ ጉዳይ? የዚህ ዓይነቱ ተሳትፎ ዓለምን መመሰልና ቅይጥ ልምምድ የሚሆነው መቼ ነው? ክርስቲያናዊ ያልሆኑ እምነቶች ሰዎችን በግታለል በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ከእግዚአብሔር ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አንዳያደርጉ ስለሚከላከሉ፥

እግዚአብሔር ሕዝቡ የሐሰት ሃይማኖቶችን፥ እምነቶችና ልምምዶች እንዲያስወግዱ ያዛል (ዘሌ. 18፡3፤ 2 ነገሥት 17፡38-39)። ስለዚህ፥ ክርሲቲያናዊ ያልሆነ ሃይማኖት ልምምዶችን የሚያካትቱ ሥርዓቶች ወይም በዓላት መወገድ አለባቸው። ጉዳዩ ግልጽ ካልሆነ፥ የበሳል ክርስቲያን ሽማግሌዎችን ምክር መጠየቁ ጥበብ ነው።

በአፍሪካ ባህል ወደ እግዚአብሔር በአማላጆች አማካኝነት ብቻ መቅረቡ የተለመደ ነው። ይሁንና፥ በሰዎች ፈንታ ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ ብቃት ያለው ማን ነው? የአያት ቅድማያት መናፍስት ነን የሚሉ አጋንንት እንዳልሆኑ ጥርጥር የለውም። መጽሐፍ ቅዱስ የሰውን ልጅ በእግዚአብሔር ፊት፥ እግዚአብሔርን ደግሞ በሰዎች ፊት የመወከል ብቃት ያለው አንድ አካል ብቻ እንዳለ ይናገራል። እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (1 ጢሞ. 2፡5፤ ዕብ. 9፡15)።

በክፉ ወይም ጨቋኝ መንግሥት ሥር የሚኖሩ ክርስቲያኖች ምን ሊያደርጉ ይገባል? መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያኖች ሁሉ በሁኔታዎች እንዲጸልዩ (1 ጢሞ. 2:1-2) እና እንዲታዘዙ (1 ጴጥ. 2፡13-15) ያዛል። መጽሐፍ ቅዱስ ሰብአዊ መንግሥትን የመሠረተው ራሱ እግዚአብሔር እንደ ሆነ ይናገራል (ሮሜ. 13:1)። እግዚአብሔር ክፉውን መንግሥት ለማሻሻል ወይም በሌላ ለመተካት ይችላል(ማቴ. 6:10)። ታሪክ ሕዝቡ በታማኝነት በጸለየ ጊዜ፥ እግዚአብሔር እነዚህን ሁለት ነገሮች በተለያዩ ጊዜያት እንዳደረገ ይገልጻል።

በምዕራፍ 14 ላይ የተመሠረቱ የመወያያ ጥያቄዎችና መልመጃዎች

1. በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ሕዝቡን የመራባቸው አንዳንድ መንገዶች የትኞቹ ናቸው?

2. እግዚአብሔር ዛሬ ለሕዝቡ ሁሉ ምሪት ለመስጠት የሚጠቀምባቸው ሁለት መንገዶች የትኞቹ ናቸው?

3. ሦስት አባላት በሚገኙባቸው ቡድኖች ተከፋፈሉና በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።

ሀ) እግዚአብሔር በምን ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ ሕዝቡን በሕልም እንደሚመራ ታስባለህ?

ለ) እግዚአብሔር በምን ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ ሕዝቡን በቀጥተኛ የመላእክት ጣልቃ-ገብነት እንደሚመራ ታስባለህ?

4. ሦስት ሰዎች እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አማካኝነት፥ ግልጽ ውሳኔዎችን ለማስተላለፍ እንዴት እንደመራቸው ይናገሩ።

5. ሦስት ሰዎች እግዚአብሔር በበሳል ክርስቲያን ወዳጆቻቸው አማካኝነት፥ ግልጽ ውሳኔዎችን ለማስተላለፍ እንዴት እንደ መራቸው ይናገሩ።

6. በቡድኑ ውስጥ እንደ ሕልም ወይም የመላእክት ጣልቃ-ገብነት በመሳሰሉ ያልተለመዱ መንገዶች የእግዚአብሔርን ምሪት የተቀበለ ሰው ካለ፥ ታሪኩን ለተቀሩት የቡድኑ አባላት ያካፍል። ምስክርነቱ ካበቃ በኋላ፥ እግዚአብሔር በዚያ ሁኔታ ውስጥ ለምን ይህንን ዓይነት ምሪት እንደ መረጠ ተወያዩ።

7. በቡድኑ ውስጥ የአፍሪካዊን ነቢይ ስበከት የሰማ ሰው እንዳለ ጠይቅ። እንዲህ ዓይነት ሰው ከተገኘ፥ ነቢዩ ስለ ምን እንደ ተናገረና ዋና መልእክቱም ምን እንደ ነበር ጠይቅ። ቡድኑ ትንቢቱ እውነት ወይም ውሸት መሆኑን ምክንያት በመስጠት ይወስን።

8. አራት ያህል አባላት በሚገኙባቸው ቡድኖች ተከፋፈሉ። የቡድኑ አባላት በአካል የተመለከቱአቸውንና በክርስትናና በአረማዊነት መካከል የሚዘወተሩትን የቅይጥ ልምምድ ምሳሌዎች በተቻለ መጠን በርከት አድርገው ይዘርዝሩ።

9. የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፥ የኢየሱስ እናት ማርያም ለጋጢአተኞች ቆማ በእግዚአብሔር ፊት ልታማልድ ትችላለች የሚለው እምነት የተሳሳተ የሚሆነው ለምንድን ነው?

10. ለአገሩ መንግሥት የክርስቲያን ሁለት ዐበይት ኃላፊነቶች የትኞቹ ናቸው?

11. እንበልና በአንዲት አገር የሚገኘው መንግሥት ከፍተኛ ፀረ-ክርስቲያን አቋም አለው። ለዚህ ዓይነቱ ሁኔታ የክርስቲያኖች ምላሽ ምን መሆን እንዳለበት ተወያዩ።

12. አፍሪካውያን ምሪትን ለመፈለግ አዘወትረው የሚጠቀሙባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው? ከእነዚህ ውስጥ እግዚአብሔር የተቀበላቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው? መልስህን በመጽሐፍ ቅዱስ አስደግፍ።

13. የአፍሪካን ሥርዓቶችና በዓላት ገጽታና በአፍሪካ ሕይወት ውስጥ ያላቸውን ሚና በማንሣት ተወያዩ። እነዚህ ሥርዓቶች ከክርስቲያን ጎብረተሰብ ጋር የሚዛመዱት እንዴት ነው?

14. የአፍሪካን አማላጆችና አማልክት ከኢየሱስ ክርስቶስ አማላጅነት ጋር በማነጻጸር ተወያዩ።

15. የእግዚአብሔርን ቃል ከመንደር ሽማግሌዎች ምክር ጋር እንዴት ታዛምዳለህ?

16. አፍሪካውያን ስለ መንግሥት ወይም ሥልጣን ስላላቸው ሰዎች ያላቸው ግንዛቤ ምንድን ነው? ይህስ ከዘመናዊ የአፍሪካ ማኅበረሰብና ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እንዴት ይዛመዳል?

SUGGESTED FOR FURTHER READING

Duewel, Wesley. Let God Guide You. Grand Rapids, Michigan: Zondervan, 1988.

Hastings, Adrian. African Christianity. London: Geoffrey Chapman, 1976.

Hastings, Adrian. A History of African Christianity, 1950-1975. Cambridge: Cambridge University Press, 1979.

Hastings, Adrian, The Church in Africa, 1450-1950. Oxford: Oxford University Press, 1995.

Kato, Byang. African Cultural Revolution And The Christian Faith. Jos, Nigeria: Challenge Publications, 1975.

Pytches, David. Does God Speak Today? London: Hodder, 1989.

Yamamori, Tetsumao, and Taber, Charles R. eds. Christopaganism Or Indigenous Christianity. Pasadena, California: William Carey Library, 1975.

ምዕራፍ 15

ቤተ ክርስቲያንና ባህላዊ መድልዎ

«በዚህም ወራት ደቀ መዛሙርት እየበዙ ሲሄዱ ከግሪክ አገር መጥተው የነበሩት አይሁድ በይሁዳ ኖረው በነበሩት አይሁድ አንጎራጎሩባቸው፥ በየቀኑ በተሠራው አገልግሎት መበለቶቻቸውን ችላ ይሉባቸው ነበርና። አሥራ ሁለቱም ደቀ መዛሙርቱ ሁሉን ጠርተው እንዲህ አሉአቸው፡- የእግዚአብሔርን ቃል ትተን ማዕድን እናገለግል ዘንድ የሚገባ ነገር አይደለም። ወንድሞች ሆይ፥ በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስና ጥበብ የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ፥ ለዚህም ጉዳይ እንሾማቸዋለን፤ እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን። ይህም ቃል ሕዝብን ሁሉ ደስ አሰኛቸው፤ እምነትና መንፈስ ቅዱስም የሞላበትን ሰው እስጢፋኖስን ፊልጶስንም ጵሮኮሮስንም ኒቃኖሮንንም ጢሞናንም ጳርሜናንም ወደ ይሁዲነት ገብቶ የነበረውን የአንጾኪያውን ኒቆላዎስንም መረጡ። በሐዋርያትም ፊት አቆሙአቸው፥ ከጸለዩም በኋላ እጃቸውን ጫኑባቸው። የእግዚአብሔርም ቃል እየሰፋ ሄደ፥ በኢየሩሳሌምም የደቀ መዛሙርት ቁጥር እጅግ እየበዛ ሄደ፤ ከካህናትም ብዙ ሰዎች ለሃይማኖት የታዘዙ ሆኑ» (የሐዋ. 6፡1-7)።

በመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ የሚማሩ ባለትዳር ተማሪዎች ለቤተሰባቸው ጥራጥሬና ሌሎች እህሎች ይዘሩበት ዘንድ ሰፊ መሬት ተሰጣቸው። ከመሬቱ የተወሰነው ክፍል በከረምት ወራት ሩዝ ለማምረት በጣም ተስማሚ ነበር። አንድ የውጭ ዜጋ የሆነ መምህር ለባለ ትዳር ተማሪዎች ለእርሻ አገልግሎት ለሚያስፈልጉ ነገሮች ተቆጣጣሪ እንዲሆን ተመድቦ ነበር። እርሱም አንድ ተማሪ በየዓመቱ የእርሻ መሬቱን በማከፋፈል እንዲያግዘው አደረገ። ይህም ተማሪ በተራው ሌሎች ሁለት ተማሪዎች በዚህ የመሬት ክፍፍል ወቅት እንዲረዱት አደረገ። መምህሩ ያላወቀው ነገር ቢኖር፥ በእርሻው ኮሚቴ ውስጥ የነበሩ ሦስቱም ተማሪዎች ከአንድ ጎሳ የመጡ መሆናቸው ነበር።

የእርሻው ኮሚቴ ሥራውን ከተረከበ ከሦስት ዓመታት በኋላ፥ አንዳንድ ባለትዳር ተማሪዎች ወደ መምህሩ መጥተው ስለ መሬቱ ክፍፍል የተሰማቸውን ቅሬታ ገለጹ። ሩዝ ለማብቀል የሚሻለው መሬት ሁሉ በሦስት ዓመታት ቀስ በቀስ ከአንድ ጎሳ ለመጡ ተማሪዎች እንደ ተሰጠ ያውቅ እንደ ሆነ ጠየቁት። ከሁሉም የተሻለው የእርሻ መሬት

የኮሚቴው አባላት ለሆኑ የአንድ ጎሳ ተማሪዎች መመደቡን ስለ ማወቅ አለማወቁ ጠየቁት። በጉዳዩ አንገቱን የደፋው መምህር ችግሩን እንዳላወቀ ገለጸላቸው። የቀድሞውን የእርሻ ኮሚቴ አፈረሰና እያንዳንዱ አባል ከሌላ ጎሳና ከሌላ አገር የተሰባሰበበት ሦስት አባላት የሚገኙበት አዲስ ኮሚቴ አዋቀረ። መሬቱ ዳግም ያለ አድልዎ ለባለ ትዳር ወጣቶች ተከፋፈለ። በዚህም ሰላም ተገኘ።

ምንም እንኳ ከላይ የጠቀስናቸው ሁለት ክስተቶች በቤተ ክርስቲያን ታሪክ በተለያዩ ስፍራዎችና በተለያዩ ጊዜያት ቢፈጸሙም፥ አንድ አስፈላጊ የሆነ የጋርዮሽ ባሕርይ አላቸው። ይኸውም ቤተ ክርስቲያንን የሚያውክ አደገኛ ችግር የሚያንጸባርቁ መሆናቸው ነው። ችግሩም ባህላዊ አድልዎ ነው። በዚህ ምዕራፍ፥ መጽሐፍ ቅዱስ የአንድን ሰው ባህላዊ ማንነት የቤተ ክርስቲያን አካል ከመሆኑ አንጻር፥ እንዴት እንደሚገልጽ ቀረብ ብለን እንመለከታለን። በመሆኑም፥ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ እንሞክራለን፦

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቲያኖች ባህላዊ ጅማሬ (ጎሳ፥ ነገድ፥ ዘርና ቋንቋ) ምን ይላል?

ለ. የተለያየ ባህል ባላቸው አባላት ሳቢያ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተከሰቱ አንዳንድ ችግሮች የትኞቹ ናቸው?

ሐ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የባህላዊ መድልዎ ችግሮች እንዴት ይቃለላሉ?

መ. ከተለያዩ ባህሎች፥ ዘሮችና ቋንቋዎች አኳያ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ያለው ዕቅድ ምንድን ነው?

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቲያኖች ባህላዊ ጅማሬ (ጎሳ፥ ነገድ፥ ዘርና ቋንቋ) ምን ይላል?

የአንድን ሰው ባህላዊ ጅማሬ ለመግለጽ የተለያዩ የእንግሊዝኛ ቃላት አገልግለዋል። በተለያዩ ጊዜያት ስለ አንድ ሰው ጎሳ፥ ነገድ፥ ወገን፥ ዘር ወይም ብሔር እንነጋገራለን። አንዳንድ ጊዜ የጎሳ ቡድን ወይም የጎሳ ጅማሬ እንላለን። በዚህ ምዕራፍ የማንኛውንም የሕዝብ ቡድን ባህላዊ ጅማሬ ለማመልከት የጎሳ ቡድን በሚል አጠቃላይ ስያሜ እንጠቀማለን።

መጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ የሕዝብ ቡድኖችን ባህላዊ ጅግራዎች ለመግለጽ አያሌ ቃላትን ይጠቀማል። በራእይ 7፡9፥ እጅግ ብዙው ሕዝብ «ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም» እንደ ተውጣጣ ተገልጾአል። እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ከፍፍል የሚጠቀምበትን መንገድ ለመረዳት፥ አዘወትሮ ሲነገር የምንሰማውን «አገር» የተባለ ቃል መጽሐፍ ቅዱስ «ሕዝብ» የሚለውን ቃል ከሚጠቀምበት ሁኔታ ጋር እናነጻጽራለን። (ሁለቱም በእንግሊዝኛ «nation» በሚል አንድ ቃል ይጠራሉ።)

አዘውትረን የምንሰማው «አገር» የተባለው ቃል በዓለም የሚገኙትን የተለያዩ የፖለቲካ ድንበሮች (አገሮች) ያመለክታል። በ1980 ዓ.ም. የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት 223 እንዲህ ዓይነት አገሮች ስለ መኖራቸው እውቅና ሰጥቷል። የዚህ ዓይነት አገሮች ቁጥር ከዓመት ዓመት ይለዋወጣል። በታሪክ ሁሉ፥ የፖለቲካ አዋቂዎችና መታደሮች የራሳቸውን ፖለቲካዊ ወይም መታደራዊ ዓላማ ለማሳከት ሕዝቦችን በፖለቲካዊ አገሮች ከፋፍለዋቸዋል። ብዙውን ጊዜ እነዚህ ክፍፍሎች የአካባቢው ሕዝቦች ራሳቸውን በቋንቋና በባህላዊ ተመሳሳይነቶች ከሚመድቡአቸው ሁኔታ ጋር እምብዛም የማይገናኙ ናቸው። የፖለቲካ ድንበሮች ብዙውን ጊዜ የሕዝቡን ባህላዊ ልዩነቶች ወይም ተመሳሳይነቶች ከግምት ውስጥ ሳያስገቡ የሚከናወኑ ናቸው። ከዚህም የተነሣ፥ ብዙ የዓለም አገሮች ከአንድ የበለጡ ባህሎች ወይም የቋንቋ ቡድኖች አሉአቸው። ብዙውንም ጊዜ በተለያዩ ቡድኖች መካከል ውጥረት ወይም ግጭት ይኖራል።

በብዙ ገጠመኞች፥ አንድ ዓይነት የጎሳ ቡድን ከአንድ በበለጡ አገሮች ይኖራል። በአፍሪካ፥ የግሳይ ሕዝቦች በኬንያና በታንዛንያ ይኖራሉ። የግልንኪ ሕዝቦች በሴነጋል፥ በማሊ፥ በጊኒና በሌሎችም አገሮች ይገኛሉ። የዳሰኝች ሕዝቦች በኬንያ፥ በኢትዮጵያና ሱዳን ይኖራሉ። ፉላኒዎች ደግሞ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ አፍሪካ በብዙ አገሮች ውስጥ ተበታትነው ይገኛሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ «ሕዝብ» ሲል ምን ማለቱ ነው? በአዲስ ኪዳን ውስጥ «ሕዝብ» ተብሎ የተተረጎመው ቃል «ኤትኖስ» ("ethnos") የሚለው የግሪክ ቃል ነው። የአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮታዊ መዝገበ ቃላት እንደሚያብራራው ኤትኖስ፥ «በአንድ ዓይነት ጠባያት፥ ባህሎች ወይም ሌሎች የተለያዩ ገጽታዎች የተያያዙ እጅግ ብዙ ሕዝቦች» የሚል ፍች ይኖረዋል። «ኤትኒክ» (ጎሳ) የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል የመጣው ከኤትኖስ ነው። ጎሳ «ከዘር፥ ከብሔር ወይም ከባህላዊ ቡድን ጋር የሚዛመድ» ማለት

ነው። ስለ ሆነም፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ገለጻ መሠረት ሕዝብ (ኤትኖስ)፥ የተወሰነ የጎሳ ቡድን ነው። ከዚህም መጽሐፍ ቅዱሳዊውና ዘመናዊው የ«ሕዝብ» ("nation") የቃላት አጠቃቀም የተለያየ መሆኑን እንመለከታለን።

እግዚአብሔር የሰውን ዘር፥ ሰዎች በሚገኙበት ቋንቋና የባህል ቡድኖች አኳያ እንደ ተከፋፈለ አድርጎ ይመለከታል። እንደ ዘፍጥረት 10፡4፥ 20፥ 31-32 ገለጻ፥ የሰው ልጆች ወደ ተለያዩ ቋንቋዎችና የባህል ቡድኖች የተከፋፈሉት ከኖኅ ልጆች ነው። እንዲሁም፥ መጽሐፍ ቅዱስ በባቢሎን ግንብ ላቢያ «እግዚአብሔር የምድርን ቋንቋ ሁሉ ደባልቋልና፤ ከዚያም እግዚአብሔር በምድር ሁሉ ላይ እነርሱን በትኖአቸዋል» ይላል (ዘፍጥ. 11፡9)። ሰዎች ሊግባቡ ባለመቻላቸው ከየቋንቋቸው አኳያ ተለያዩ። ከዚያም በአንድ ዓይነት ቋንቋዎች ላይ የተመሠረቱ የተለያዩ ማኅበረሰቦችን አቋቋሙ። እነዚህ የቋንቋ ቡድኖች እያንዳንዳቸው የራሳቸውን የባህል ፈለጎች እንዳስፋፉ መገመት ይቻላል። ስለ ሆነም የሰው ዘር ወደ ተለያዩ ብሔሮች መከፋፈል በባቢሎን ግንብ ሰበብ ከተከሰተው ነገር የመጣ ነው።

ጊዜ እየረዘመ ሲሄድ፥ ምናልባትም ከእነዚህ የመጀመሪያዎቹ ቡድኖች ብዙዎቹ የተለያዩ ቋንቋዎችና ባህላዊ ልዩነቶች ወደሚገኙባቸው ትናንሽ ቡድኖች መከፋፈላቸው አልቀረም። ዛሬ የቋንቋ ምሁራን በዓለም ከ5000 በላይ የቋንቋ ቡድኖች እንዳሉ ተረድተዋል። አንዳንድ አገሮች በፖለቲካዊ ድንበሮቻቸው ውስጥ እንዲህ ዓይነት በርካታ ጎሳዊ ቡድኖች አሉአቸው። ለምሳሌ፥ በናይጄሪያ ከ400 የሚበልጡ የጎሳ ቡድኖች አሉ።

ከእግዚአብሔር ዕይታ አንጻር፥ እነዚህ እያንዳንዳቸው የቋንቋ-ብሔል ቡድኖች የተለዩ የሕዝብ ወገን ናቸው። በሐዋርያት ሥራ 17፡26፥ «በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩ የሰውን ወገኖች (ኤትኖስ) ሁሉ ከአንድ (አዳም) ፈጠረ፥ የተወሰኑትንም ዘመኖችና ለሚኖሩበት ስፍራ ዳርቻ መደበላቸው» ይላል። በታላቁ ተልዕኮ በእያንዳንዱ ቡድን ደቀ መዛሙርት ለማድረግ፥ ደቀ መዛሙርቱ ለእነዚህ ለእያንዳንዳቸው የሕዝብ ቡድኖች ወንጌሉን እንዲወስዱ ኢየሱስ አዝዞአቸዋል። በማቴዎስ 28፡19-20 ኢየሱስ፥ «እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን (ኤትን) ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው» ብሏል።

ከዚህም ምንባብ የክርስቶስ መንጌል በዓለም ሁሉ ወደሚገኙ የጎሳ ቡድኖች መዳረስ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደ ሆነ እንረዳለን።

በራእይ መጽሐፍ የእግዚአብሔር ዓላማዎች ሊፈጸሙ፥ ሕዝቦች ከእነዚህ ከእያንዳንዳቸው የጎሳ ቡድኖች እግዚአብሔርን ለማምለክ በዙፋኑ ዙሪያ እንደሚሰባሰቡ እንመለከታለን። በራእይ 5፡9-10፥ «መጽሐፉን ትወስድ ዘንድ ፥ ማህተሞቹንም ትፈታ ዘንድ ይገባሃል፥ ታርደሃልና፥ በደምህም ለእግዚአብሔር ነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ . . . »፤ በራእይ 7:9-10 «ከዚህ በኋላ አየሁ፥ እነሆን፥ አንድ እንኳ ሊቆጥራቸው የማይችል ከሕዝብና ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ . . . በታላቅም ድምፅ እየጮኹ፦ በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለአምላካችንና ለበጉ ማዳን ነው አሉ» የሚል እናነባለን።

እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው የአንድ የተወሰነ ቋንቋ-ባህል ቡድን (ሕዝብ) አባል አድርጎ እንደሚመለከተው እነዚህ ቁጥሮች ግልጽ ያደርጉልናል። ዕቅዱ ከእነዚህ ቡድኖች ሁሉ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው የቤተ ክርስቲያኑ አካላት እንዲሆኑ ነው። በራእይ 7፡9-10 የሚገኘው ትንቢት በታሪክ ፍጻሜ ላይ የእግዚአብሔር ዕቅድ በመጨረሻው እንደሚፈጸም ግልጽ ያደርግልናል፤ በዚህም ጊዜ በምድር ላይ ሰዎች ከተለያየ የጎሳ ቡድን በክርስቶስ አካል ውስጥ ይሆናሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ማንኛውንም የባህል ቡድን ከሌሎች የባህል ቡድኖች ሁሉ በላይ እንደሚመለከት የሚጠቁም ነገር የለም። እስራኤላውያን በእግዚአብሔር የመመረጥ ዕድል ነበራቸው (ሮሜ 9፡4-5)። ይሁንና፥ የተመረጡት ከሌሎች የባህል ቡድኖች ስለ በለጡ አልነበረም። እንዲያውም፥ በዘዳግም 4፡37-38 እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን የሚበልጡትንና የበረቱትን ሕዝቦች ከእስራኤላውያን ፊት እንደሚያስወግድ ይናገራል። ይህ ዓረፍተ ነገር ምናልባትም የእነዚህ የሌሎች አገሮች የሕዝብ ብዛትና መታደራዊ ጥንካሬ ያመለክት ይሆናል፤ ይሁንና፥ በዚህም ሆነ በሌላ ስፍራ ግንኙውም የጎሳ ቡድን ከሌሎች የጎሳ ቡድኖች እንደሚበልጥ የሚያመለክት አሳብ አናገኝም። የዘር ወይም የጎሳ የበላይነት ከሰው ትዕቢት የመነጨ አሳብ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የልብን ትዕቢት እንደሚጠላ ይናገራል (ምሳሌ 16፡5)። በክርስቶስ፥ እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ በተመሳሳይ መንገድ ይመለከታል።

ክርስቲያኖች ከዘር ወይም ከብሔር ጅግራአቸው ባሻገር ይቅርታ የተደረገላቸው ኃጢአተኞች ናቸው (ሮሜ 3፡23-25፤ ቆላ. 2፡13)።

ለ. የተለያየ ባህል ባላቸው አባላት ሳቢያ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተከሰቱ አንዳንድ ችግሮች የትኞቹ ናቸው?

በዓለም፥ ከተለያዩ ባህሎች፥ ዘሮችና የጎሳ ቡድኖች የመጡ ሰዎች በሰላም አብሮ የመኖር ችግሮች አሉባቸው። ብዙውን ጊዜ እርስ በርሳቸው አይተማመኑም። ብዙውን ጊዜ እነርሱ ከሌሎች ቡድኖች እንደሚበልጡ ያስባሉ። የብሔርተኝነት ትዕቢት ዝንባሌ ጎሰኛነት ("ethnocentrism") ይባላል። አንዳንድ ጊዜም ሌሎችን ሰዎችና ባህላቸውን ይንቃሉ። የሚያሳዝነው ሁኔታው በአንዳንድ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትም የተሻለ አለመሆኑ ነው። ብዙውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከጎሳ ቡድኖች አንዳንዶቹ የራሳቸውን የተለየ ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት ከሌሎች ይለያሉ።

የባህል ጅግራ ልዩነቶች በዓለም በተለያዩ የሕዝብ ቡድኖች መካከል ብዙ ችግሮችን ፈጥረዋል። የዘር፥ የባህልና የሃይማኖት ልዩነቶች ጦርነቶችን ሳይቀር አስነሥተዋል። ይህ በመካከለኛው ምሥራቅ በዓረቦችና አይሁዶች፥ በሕንድ በሙስሊሞችና በሂንዱዎች፥ በሩዋንዳ በሑቱዎችና ቱትሲዎች፥ ብሎም በዘመናዊቱ ዩጎዝላቪያ በክሮኤቶች፥ ሰርቦችና ቦስንያውያን መካከል በሚደረጉ በርካታ ግጭቶች ውስጥ ሊታይ ይችላል። መጽሐፍ ቅዱስ በክርስቲያኖች መካከል ስለሚነሡ ባህላዊ ልዩነቶችና ስለ ቤተ ክርስቲያን አንድነት አስፈላጊነት የሚላቸው አንዳንድ አስፈላጊ ነገሮች አሉ።

እግዚአብሔር በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊመለከት ከሚፈልጋቸው እጅግ አስፈላጊ ጠባያት አንዱ በክርስቲያኖች መካከል የሚገኝ ስምምነትና አንድነት ነው። የአለመስማማትን፥ የመጣላትንና አንድነት የማጣትን ያህል የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ምስክርነት የሚጎዱ ችግሮች በጣም ጥቂቶች ናቸው። የመስማማት አስፈላጊነት በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተደጋግሞ የተጠቀሰ ጉዳይ ነው። ጳውሎስ በፊልጵስዩስ የሚገኙትን ክርስቲያኖች፥ «በአንድ አሳብ ተስማሙ፥ አንድ ፍቅር አንድም ልብ አንድም አሳብ ይሁንላችሁ» (ፊልጵ. 2:2) በማለት ተማጽኖአል። ለኤፌሶን ሰዎች በጻፈው ደብዳቤም፥ ጳውሎስ ክርስቲያኖችን «በተጠራችሁበት መጠራታችሁ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ

አለምናችኋለሁ . . . በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ» ሲል ለምኖአቸዋል (ኤፌ. 4፡1፥ 3)።

ኢየሱስ፥ «አኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ» ሲል (ዮሐ. 17፡22) በተከታዮቹ መካከል አንድነትና ስምምነት እንዲኖር ጸልዮአል። በግቴዎስ 12፡25 ኢየሱስ፥ «እርስ በእርስዋ የምትለያይ መንግሥት ሁሳ ትጠፋለች» ብሏል። ይህ የክርስቶስ ዓረፍተ ነገር ጠንካራ ማስጠንቀቂያ ይዞአል። በእንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው ሰላም ከሌላቸው፥ ምስክርነታቸው በከፍተኛ ደረጃ ይጎዳል። በቤተ ክርስቲያን ሕይወታቸው የጌታን በረከትና ኃይል አይለማመዱም።

ከአንድ ዓይነት ቋንቋና ባህል የሚመጡ ሰዎች በሚታወቁበት፥ በሚከበሩበትና ሌሎች በሚረዱአቸው አንድ ቡድን ወደ መሰባሰቡ ያዘነብላሉ። በተመሳሳይ ጊዜም የሌሎችን ሰዎች ቋንቋና ባህላዊ ልምምድ ሰለማይረዱ፥ ባዕዳን ወይም እንግዶች አድርገው ይቆጥሩአቸዋል። ሌሎችን ቡድኖች ስለማይረዱ፥ ከእነርሱ ያነሰ ጠቀሜታ ወይም እውቀት እንዳላቸው ያስባሉ። ይህም ወደ ትችት፥ ጥርጣሬ፥ የእምነት ጉድለት፥ የግንኙነት እጦት፥ አለመግባባትና ግልጽ ጠላትነት ያመራል። ከተለያዩ የባህል ቡድኖች የሚመጡ የቤተ ክርስቲያን ምእመናን አንዳንድ ጊዜ የዚህ ዓይነት ስሜት ያድርባቸዋል።

ከልዩነቶቻቸው የተነሣ፥ የሰዎች ቡድኖች በባቢሎን ግንብ እንዳደረጉት እርስ በርሳቸው ወደ መለያየቱ ያዘነብላሉ። በተጨማሪም፥ የራሳቸው ቡድንና የራሳቸው ባህል ከሁሉም እንደሚበልጥ ያስባሉ። ከዚህ የተነሣ፥ በዓለም ታሪክ ሁሉ በተለያዩ የባህል ቡድኖች አድልዎና በአሳብ አለመገናኘት የተለመደ ነገር ሆኖ ቆይቷል። የዚህ ዓይነቱ አድልዎ እንደ ጦርነትና ባርነት የመሳሰሉትን አያሌ መጥፎ ልምዶችን አስከትሏል። የመሬት ባለቤትነት ሙግቶች፥ የፖለቲካ ጭቆናና የጎሳ ጦርነቶች ከባህላዊ አድልዎ አቆጥቁጠዋል። ባመዛኙ መሠረታዊው ችግር ሰዎች ከራሳቸው የሚለዩትን ሰዎች አለመውደዳቸውና አለማመናቸው ነው።

በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ እንደ ተመለከተው፥ ገና ከመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጀምሮ ተመሳሳይ ባህላዊ አድልዎች ነበሩ። የግሪክ ቋንቋ ተናጋሪ አይሁዶችና የራሳቸውን የዕብራይስጥ ቋንቋ የሚናገሩ አይሁዶች በቀድሞዪቱ ቤተ ክርስቲያን አብረው ማምለክ ሲጀምሩ፥ የዕብራይስጥ ቋንቋ ተናጋሪዎች፥ አማኞች አብረው በሚመገቡበት ጊዜ

የግሪክ ቋንቋ ተናጋሪዎቹን አይሁዶች መበለቶች ችላ ይሉቸአው ነበር (የሐዋ. 6፡1)። ይህ የቀድሞው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፥ በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ ከተጠቀሰውና ከ2000 ዓመታት በኋላ በአፍሪካ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ከተፈጸመው ታሪክ ጋር በሚገባ ይመሳሰላል። እንደ እውነቱ ከሆነ፥ በዚህ ሁሉ የጊዜ ርዝመት የሰዎች ልብ ብዙም አልተለወጠም!

እግዚአብሔር የዚህ ዓይነቱ አድልዎ እንዲቀጥል አለመፈለጉን መረዳቱ መልካም ነው። በመሆኑም፥ ለቀድሞዎቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይህንን የአድልዎ ጠባይ የሚያስወግድ መፍትሔ እንዲፈጥሩ ጥበብን ሰጥቶአቸዋል (የሐዋ. 6፡2-6)። ሐዋርያት መልካም ምስክርነት የነበራቸውን፥ መንፈስ ቅዱስና መንፈሳዊ ጥበብ የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች ለመምረጥ ወሰኑ። ከስማቸው እንደምንረዳው፥ እነዚህ ሰዎች የግሪክ ክርስቲያኖች ሳይሆኑ አይቀሩም። ምናልባትም ከሚያጉረመርመው ቡድን የመጡ ይሆናሉ። በመሆኑም፥ መበለቶቻቸው ትክክለኛ የምግብ ድርሻቸውን እንዳገኙ የግረጋገጥ ኃላፊነት ነበረባቸው (የሐዋ. 6፡2-6)። ይህም መፍትሔ ጉባኤውን ሁሉ አስደሰተው። የቀድሞዪቱ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛውን አለመስማማትና አለመጣጣም እንድታስወግድ አስችሎአታል። ከዚህ እግዚአብሔር ከሰጠው መፍትሔ የተነሣ፥ ወዲያውኑ ቤተ ክርስቲያኒቱ በቁጥር ትበራከት ጀመር (የሐዋ. 6፡7)። አንድነት ያላት ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ ጠንካራ ምስክርነት ነበራት።

ይህ እውነተኛ ታሪክ አንድነት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን እንደሚገነባና መከፋፈል ደግሞ እንደሚያጠፋት የሚያሳየውን አስፈላጊ እውነት ይገልጻል። ከአንድነት የሚመነጨው ጥንካሬ በመክብብ 4፡12 ተገልጾአል፤ «አንዱም አንዱን ቢያሸንፍ ሁለቱ በፊቱ ይቆማሉ፤ በሦስትም የተገመደ ገመድ ፈጥኖ አይበጠስም።»

ሐ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የባህላዊ መድልዎ ችግሮች እንዴት ይታለላሉ?

በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 6 ውስጥ ከሚገኘው ታሪክ፥ እግዚአብሔር የባህልን መድልዎ ለማስወገድ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጥበብ ሊሰጥ እንደሚችል እንመለከታለን። እግዚአብሔር በእምነት ጥበቡን እንዲሰጠን ስንጠይቅ፥ ችግሮችን ለማታለል መንፈሳዊ ጥበብ እንደሚሰጠን ታል ገብቶልናል (ያዕ. 1፡5-6)። በሐዋርያት ሥራ 6፡1 እግዚአብሔር የሰጠው መፍትሔ ለቤተ ክርስቲያን በረከት አምጥቷል። ይህም የባህል መድልዎና ጎሰኛነት መፍትሔ የሌለው ችግር እንዳልሆነ በግልጽነት ያበረታታናል።

ሕዝቡ ምሪቱን ለመከተል የሚፈቅድ ከሆነ፥ እግዚአብሔር መፍትሔ ሊሰጥ ይችላል። የባህልን መድልዎና የኅሰኛነትን ችግሮች ለማስወገድ የሚረዱ አጠቃላይ መመሪያዎች የትኞቹ ናቸው?

መረዳት የሚያሻን የመጀመሪያው መመሪያ፥ መድልዎና ያለመተማመን፥ አብረው የሚያመልኩትን የቤተ ክርስቲያን ምእመናን በክፉ ሁኔታ ማስተናገድ ኃጢአት መሆኑን ነው። ሐዋርያው ያዕቆብ አድልዎ የእግዚአብሔርን ሕግ የሚጥስ ኃጢአት እንደ ሆነ ገልጾአል። በያዕቆብ 2፡9፥ «ለሰው ፊት ግን ብታደሉ ኃጢአትን ትሠራላችሁ፥ ሕግም እንደ ተላላፊዎች ይወቅሳችኋል» ይላል።

ባህላዊውን መድልዎ ለማስወገድ የሚያስፈልገው ሁለተኛው መመሪያ፥ ትሕትና የታከለበትና ከራስ-ወዳድነት የጠራ ፍቅር ነው። ክርስቶስ አብረውን የሚያመልኩትን ክርስቲያኖች እንድንወድ አዝዞናል (ዮሐ. 15፡12)። ጳውሎስ በፊልጵስዩስ ሁለት ሴቶች በአንድነት መሥራትን እንዲማሩ ነግሮአቸዋል (ፊልጵ. 4፡2)። የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ከራስዋ ያለመስማማት ችግር ጋር ትታገል ነበር። ሐዋርያው ሌላው ከራሳቸው በላይ አስፈላጊ እንደ ሆነ እያሰቡ፥ በአንድ ልብና ዓላማ እንዲመላለሱ ይገፋፋቸዋል (ፊልጵ. 2፡2-3)። የትሕትናና የመተባበርን ዝንባሌ መከተል የክርስቶስን ፍቅር በተግባር ማሳየት ነው። ይህም ጌታን የሚያስደስትና ቤተ ክርስቲያንን የሚያንፅ ነው (ኤፌ. 4፡15-16)።

ፍቅር በጣም አስፈላጊ ነው። ኢየሱስ፥ «እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፥ ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ» ብሏል (ዮሐ. 13፡35)። ከራስ-ወዳድነት የራቀ ፍቅርና የባህል መድልዎ አብረው ሊኖሩ አይችሉም። በአንድ ሰው ዝንባሌ ውስጥ ከራስ-ወዳድነት የራቀ ፍቅር ካለ፥ መድልዎ ስፍራ መልቀቅ አለበት። እርስ በርሳችን ፍቅር ከሌለን፥ በትክክል የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት እንዳልሆንን እንገልጻለን። ክርስቲያኖች አንዳቸው ለሌላቸው ፍቅር የማያሳዩ ከሆነ፥ በማያምነው ዓለም ፊት ምስክርነታቸው የተበላሸ ይሆናል። በዚህም፥ የማያምኑ ሰዎች በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን ላይ ይሳለቃሉ።

የባህል መድልዎን ለማስወገድ ሦስተኛው መመሪያ፥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መመረጥ ያለባቸው በሰብአዊ ችሎታዎች፥ በትምህርት ደረጃ ወይም ዓለማዊ ታማኝነት ሳይሆን፥ በመጽሐፍ ቅዱስ መመዘኛዎች መሠረት መሆኑ ነው። በሐዋርያት ሥራ 6 አድልዎ የታከለበትን የምግብ ክፍፍል

ችግር ለማቃለል የተመረጡት 7 ዲያቆናት የተመረጡት ጠቢባን፥ መልካም (ጠባይ) ምስክርነት ያላቸውና በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ በመሆናቸው ነው (የሐዋ. 6:3)። የጎሰኝነትንና የባህልን መድልዎ ሊያስወግድ የሚችለው የመንፈስ ቅዱስ ጥበብና ሥራ ብቻ ነው።

በክርስቶስ ዘመን፥ አሕዛቦች የሚባሉት አይሁዶች ያልሆኑት ሕዝቦች ሁሉ ነበሩ። አይሁዶች ከሌሎች ሕዝቦች ሁሉ የሚበልጡ ስለሚመስላቸው፥ አሕዛብን ይንቁአቸው ነበር። አሕዛብን እንደ ውሾች ይቆጥሩአቸው ነበር። እግዚአብሔር አይሁዳዊው ጴጥሮስ ለአሕዛብ ወታደር ቆርኔሌዎስ ወንጌሉን እንዲመስድለት ሲፈልግ፥ ለጴጥሮስ በሽማ የተጠቀለሉ ንጹሕና ንጹሕ ያልሆኑ እንስሳት ራእይ ማሳየት አስፈልጎት ነበር። ይህንንም ያደረገው፥ ለጴጥሮስ እግዚአብሔር አሕዛብን በመንፈሳዊ ሁኔታ ንጹሕ ለማድረግ እንደሚቻል ለማሳየት ነበር (የሐዋ. 10:10-28)። በአድልዎአዊነት የተጠመደውን አይሁዳዊ ለማሳመን፥ እግዚአብሔር ራእዩን ሦስት ጊዜ ደጋግሞ ማሳየት አስፈልጎት ነበር (የሐዋ. 10:16)፤ ይሽውም (እንደ ጴጥሮስ ያለ) ማንኛውም ትክክለኛ አይሁዳዊ በርኩስ አሕዛብ ቤት ውስጥ ሊገባ አይደፍርም ነበርና ነው!

ከዚህ ገጠመኝ የተነሣ፥ ጴጥሮስ እግዚአብሔር በሌላ የባህል ቡድን ስለሚገኙት ሰዎች እንድናስብ ስለሚፈልገው ነገር አንድ አስፈላጊ ዓረፍተ ነገር ተናግሯል። በሐዋርያት ሥራ 10:28 ለቆርኔሌዎስና ለወዳጆቹ ሲናገር፥ ጴጥሮስ፥ «ለእኔ ግን እግዚአብሔር ማንንም ሰው ርኩስና የሚያጸይፍ ነው እንዳልል አሳየኝ» ብሏል። ትንሽ ቆይቶም ጴጥሮስ ለዚሁ አድማጭ፥ «እግዚአብሔር ለሰው ፊት እንዳያደላ ነገር ግን በአሕዛብ ሁሉ እርሱን የሚፈራና ጽድቅን የሚያደርግ በእርሱ የተወደደ እንደ ሆነ በእውነት አስተዋልሁ» ብሏል (የሐዋ. 10:34-35)።

ይህ የጴጥሮስ አሳብ በሕይወቱ የተፈጸመውን ታላቅ የመንፈሳዊ እድገት እርምጃን ያመለክታል። ይህ እግዚአብሔር በክርስቶስ የሚያምን ሰው ሁሉ እንዲከተለው የሚፈልገው እርምጃ ነው። ክርስቲያን ሁሉ ከባህላዊ፥ ከዘርና ከጎሳ አድልዎ ነፃ እንዲሆን የእግዚአብሔር ፈቃዱ ነው። ክርስቲያኖች ሌሎችን ክርስቲያኖች እግዚአብሔር እንደሚያያቸው ሊያዩአቸውና እግዚአብሔር እንደሚወዳቸው ሊወዱአቸው ይገባል።

ክርስቲያኖች ከባህላዊ መድልዎ በትክክል ነፃ ካልወጡ እንደ ምን በመንግሥተ ሰማይ ደስተኞች ሊሆኑ ይችላሉ? በመንግሥተ ሰማይ፥ በምድር ከሚገኙ የሕዝብ ቡድኖች ሁሉ ከተሰባሰቡ፥ በክርስቶስ ውድ

ወንድሞችና እህቶች ከሆኑ ወገኖች ጋር ጎን ለጎን ይኖራሉ (ራእይ 7፡9-10)።

መ. ከተለያዩ ባህሎች፥ ዘሮችና ቋንቋዎች አኳያ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ያለው ዕቅድ ምንድን ነው?

ቤተ ክርስቲያንና በክርስቶስ የሚያምኑ ሰዎች ዘላለማዊት ማኅበረሰብ ነች። ይህም ሙተው ወደ ሰማይ የሄዱትንና ገና በምድር ላይ የሚገኙትን ይጨምራል (1 ቆሮ. 12፡27፤ ኤፌ. 3፡15)። አንድ ቀን ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ ከሚገኝ ባህል፥ ዘርና የጎሳ ቡድን የተሰባሰቡትን ወንዶችና ሴቶች ሁሉ ታካትታለች (ዘፍጥ. 12፡3፤ ራእይ 5፡9-10፤ ራእይ 7፡9-10)።

በቤተ ክርስቲያንና በባህላዊ ጅማሬ መካከል አንድ በጣም አስፈላጊ የሆነ ግንኙነት አለ። ቤተ ክርስቲያን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የተገነባች ባለ ብዙ ባህል፥ ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ነች። አንድ ሰው ክርስቲያን ሲሆን፥ በመንፈሳዊ ሁኔታ ከክርስቶስ ጋር ይጣመራል። ከክርስቶስ ጋር በመጣመሩም፥ ከሌሎች ባህሎች ከመጡ ሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ይተባበራል (1 ቆሮ. 12፡20፤ ኤፌ. 4፡25)። በዚህም ዘላለማዊና ዓለም አቀፋዊ ቤተሰብ አካል ይሆናል።

እውነታው ሞት ሰዎችን ሁሉ በሁለት ምድቦች እንደሚፈርጅ ነው - ከክርስቶስ ጋር የተጣመሩና ከክርስቶስ የተለዩ (ማቴ. 25፡31-46፤ ራእይ 21፡7-8)። ኢየሱስ ስለ ሀብታሙ ሰውና ስለ አልዓዛር በተናገረው ታሪክ ውስጥ አብርሃም፥ «ከዚህ ወደ እናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ እንዳይችሉ፥ ወዲያ ያሉ ደግሞ ወደ እኛ እንዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል ተደርጎአል» ብሏል (ሉቃ. 16፡26)።

ምንም እንኳ ከብዙ የተለያዩ ባህሎችና ዘሮች ቢመጡም፥ ከሞት በኋላ የክርስቶስ የሆኑቱ አይለያዩም። የቤተሰቡ አባላት የክርስቶስ እስካልሆኑ ድረስ፥ የሰዎች ቤተሰባዊ ጎብረቶች ከዚህ ከምድራዊ ሕይወት አያልፉም። በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ሰዎች መንፈሳዊ ጎብረት ግን በዚህ ምድር ብቻ የተወሰነ አይደለም። ከአንድ ቤተሰብም ይምጡ ወይም ደግሞ ከተለያዩ ባህሎችና ዘሮች፥ አንድ ዘላለማዊ ቤተሰብ ይሆናሉ።

ብዙ ባህላዊ ሃይማኖቶች ስለ ቤተሰቦች የሚያስተምሩት ትክክል አይደለም። አያሌ ጥንታዊ ባህሎች የሕዝባቸው ማኅበረሰብ ከሞት በኋላም

እንደሚቀጥል ያምናሉ። የሞቱት አያት ቅድማያቶቻቸው መናፍስት በቤተሰብና በጎሳ ጉዳዮች በንቃት መሥራታቸውን እንደሚቀጥሉ ያምናሉ። ዛሬ በሕይወት የሚገኙ ሰዎች አንድ ቀን ሲሞቱ በእነዚህ የአያት ቅድማያት መናፍስት መካከል ስፍራ እንደሚሰጣቸው ያምናሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን አያስተምርም። በሞት ጊዜ የሚሆነው መለየት፥ የሚሞቱት ሰዎች የክርስቶስ በመሆናቸውና ባለመሆናቸው ላይ ይመሠረታል (ማቴ. 7፡22-23)። የክርስቶስ በሆኑትና ባልሆኑት መካከል ቀጣይ ግንኙነት አይኖርም (ሉቃ. 16፡26)።

ስለ ሆነም፥ ክርስቲያኖች ምንም እንኳ ከራሳቸው በጣም ከሚለዩ ባህሎች ቢመጡም እንኳ፥ በዚህ ሕይወት በክርስቶስ ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው የሆኑትን ወገኖች ቢወዱአቸውና ቢቀበሉአቸው መልካም ነው (ማቴ. 23፡8፤ ራእይ 7፡7-9)። በሰማይ ቤተ ክርስቲያን፣ ከክርስቶስ ጋር ባላቸው ግንኙነት ምክንያት እርስ በርሳቸው የተዛመዱና ከተለያየ ባህል የመጡ ቤተሰቦች የሚገኙባት ዘላለማዊት ተቋም መሆኗ በግልጽ ይታወቃል።

እግዚአብሔር ያ ግንኙነት በዚህ ምድራዊ ሕይወት ተጀምሮ በሰማይ ለዘላለም እንዲቀጥል ይፈልጋል። የክርስቶስ አካል ክፍሎች እንደ መሆናቸው፥ ክርስቲያኖች ለሰብአዊ ቤተሰባቸው፥ ለነገድ ወይም ለጎሳ ከሚኖራቸው የበለጠ የታማኝነት ግዴታ ለቤተ ክርስቲያን ሊኖራቸው ይገባል።

በአፍሪካ ሰዎች ለጎሳዎቻቸውና ለባህል ቡድኖቻቸው እንዲህ ያለ ጠንካራ ታማኝነት የሚያሳዩት፥ ማንነታቸው፥ ደኅንነታቸውና የሕይወት ትርጉማቸው የቤተሰብና የጎሳ አካል ከመሆናቸው ጋር በቀጥታ የተዛመደ በመሆኑ ነው። ይህ የእግዚአብሔርንም ቤተሰብ በተመለከተ የበለጠ እውነትነት ያለው ነው። ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤተሰብ አካል በመሆኑ፥ ማንነቱና ደኅንነቱ አስተማማኝ ከመሆኑም ለሕይወቱም ትርጉም አለው። ከምድራዊ ቤተሰቦቻችን ጋር የሚኖረን ግንኙነት ከእግዚአብሔር ቤተሰብ ጋር ከሚኖረን ዘላለማዊ ግንኙነት ጋር ሲወዳደር እጅግ አናሳ ነው።

የቤተሰብ ታላቅ ደስታና ጥንካሬ አንዱ ሌላውን «የእኔ ነው» ለማለት መቻሉ ነው። በእግዚአብሔርም ቤተሰብ ውስጥ ይኸው ነው። እግዚአብሔር አባታችን ሲሆን፥ የክርስቶስ በመሆናችን አንዳችን የሌላውን (1 ዮሐ. 3፡1-2)።

ማጠቃለያ

የቤተ ክርስቲያን አባላት እንደ መሆናቸው፥ ክርስቲያኖች በሰላም በመኖር የመንፈስን አንድነት የመጠበቅ ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው (ኤፌ. 4፡3)። ይህንንም ለማድረግ፥ ክርስቲያኖች የባህል፥ የዘር ወይም የብሔር ልዩነት ሳይታይ፥ የቤተ ክርስቲያንን ምእመናን መውደድ፥ ማመንና ማክበር አለባቸው። ባህላዊ መድልዎ ኃጢአት ነው። ሳስኝነት የቤተ ክርስቲያን ጠላት ነው።

አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ከትዕቢት፥ ከጥላቻ፥ ይቅር ካለማለት፥ ከባህላዊ መድልዎችና ከጎሰኝነት የተነሣ ስትከፋፈል፥ ምስክርነቷ ደካማ፥ ጸሎቷ ኃይል የራቀው ይሆንና ለእግዚአብሔር ምንም ነገር መሥራት ያቅታታል። ምእመኖቿ ቡቀላሉ በፈተና፥ በኃጢአትና በሽንፈት ይወድቃሉ። በሌላ በኩል ምእመኖቿ እርስ በርሳቸው በሚኖራቸው ፍቅር የተሳሰሩ ከሆነ፥ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኗ ለክርስቶስ በሚኖራት ምስክርነትና በጸሎቷ፥ በማጎበረሰቡ ውስጥ የሚታየውን ክፋት ለመቋቋም ጠንካራ ትሆናለች። የሰዎች ሠራዊት ተባብረው ሲቆሙ ጠንካራውን ጠላት ሊያሸንፉ ይችላሉ። አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በምእመኖቿ ከራስ-ወዳድነት የራቀ ፍቅርና ትሕትና ከተባበረች፥ በጸሎቷና በምስክርነቷ ለእግዚአብሔር ታላቅ ነገር ልትሠራ ትችላለች።

ለክርስቶስ ያልተከፋፈለ ታማኝነት ለመስጠት አንድ ሰው ክርስቲያን ሲሆን በዓለም ሁሉ ከሚገኘው ባህል የተውጣጡ ዘላለማዊ የወንድሞችና የእህቶች ማኅበረሰብ አካል እንደ ሆነ ሊረዳ ይገባል። ይህ ሰፊ የእግዚአብሔር ቤተሰብ የእግዚአብሔርን በግ እያመለከ በመንግሥተ ሰማይ ይኖራል (ራእይ 7፡9-10)። የእግዚአብሔር ቃል ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ የዚህን ታላቅ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ባሕርይ ይገልጻል፡- «አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና» (ገላ. 3፡28)። ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንድትበረታና በጸሎቷም የእግዚአብሔር ፈቃድ በምድር ላይ ሲፈጸም ለማየት ከተፈለገ፥ ይህን ስለ ቤተ ክርስቲያን እና ባህል የተነገረውን እውነት በታማኝነት ማስተማር ያሻል።

በምዕራፍ 15 ላይ የተመሠረቱ የመወያያ ጥያቄዎችና መልመጃዎች

1. በመጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ ቋንቋዎችንና ጎሳዊ ቡድኖችን ጅማሬ የምናገኘው የት ነው?

2. በመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ባህል፥ ዘር ወይም ቡድን ከሌላው እንደሚበልጥ የሚጠቁም አሳብ አለ? የእርሱ ቡድን ከሌላው እንደሚበልጥ ለሚያምን ሰው ገላትያ 3፡28 ምን ይላል?

3. በዓለም እጅግ ብዙ ሰዎች የራሳቸው ባህል ወይም ቡድን ከሌሎች ሁሉ እንደሚበልጥ የሚያስቡት ለምንድን ነው? ለባህላዊ መድልዎችና ጎሰኛነት እውነተኛው ምክንያት ምንድን ነው?

4. ከዚህ በላይ የቀረበውን ጥያቄ በምሳሌ 18፡12 ብርሃንነት መርምር። የባህል፥ የዘር ወይም የጎሳ የበላይነት ስሜት ግለሰቦችን ሊያወድምና ቤተ ክርስቲያኒቱን በሙሉ ሊያደክም የሚችለው እንዴት ነው?

5. ሦስት ተማሪዎች የባህል ወይም የጎሳ የበላይነት ዝንባሌዎች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ስለ ጎዱበት እውነተኛ ገጠመኝ ምስክርነት ይስጡ። ከምስክርነቶቹ በኋላ፥ አራት አባላት በሚገኙባቸው ቡድኖች በመከፋፈል፥ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የጎሳ አድልዎ በሚቀንስባቸው መንገዶች ላይ ተወያዩ። የያንዳንዱ ቡድን ሊቀ መንበር የውይይቱን ውጤቶች ያቅርብ።

6. አንድ የክርስቲያን ቡድን የባህላዊ መድልዎን ችግር እንዴት እንዳቃለለ ሊመሰክሩ የሚችሉትን ሦስት ሰዎች አግኝ።

7. በጎሳ ቡድኖች ተከፋፈሉ። ወንጌሉን ለሌላው ቡድን ትርጉም የሚሰጥና ተዛማጅ የሚያደርጉትን ዘዴዎች በመጠቀም፥ እያንዳንዱ ቡድን ለሌላ የጎሳ ቡድን የወንጌል ስርጭት ዕቅድ ያውጣ። ይህ ወንጌልን አካባቢያዊ ወይም ዓውዳዊ የማድረግ ሂደት ("contextualization") ይባላል።

8. በመጽሐፍ ቅዱስ የትኞቹ የጎሳ ቡድኖች ወደ መንግሥተ ሰማይ እንደሚገቡ የሚገልጽ ጥቅስ አግኝ።

9. ቡድኑ አፍሪካውያን በሚረዱበት ሁኔታ ነገድ በሚለው ቃል ፍች ላይ ይወያይ።

10. በአፍሪካ ሁኔታ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ስፍራ ምንድን ነው?

11. ለዘረኝነት፥ ጎሰኝነት፥ ብሔርተኝነትና የመደብ ወገናዊነት መሠረታዊ መነሾ ምን እንደ ሆነ ተወያዩ።

12. በገላትያ 3፡28፥ ኤፌሶን 2፡11-19 እና ፊልጵስዩስ 2፡3-8 መሠረት ክርስቲያን ለዘረኝነት፥ ጎሰኝነትና ብሔርተኝነት በሚሰጠው መፍትሔ ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ለማካሄድ በትናንሽ ቡድኖች ተከፋፈሉ።

SUGGESTED FOR FURTHER READING

Clement, Atchenemou, Raymond Hassan and Moyo Ozodo. Cross Cultural Christianity. Jos, Nigeria: Nigeria Evangelical Missionary Institute, 1989.

Lausanne Theology and Education Group. The Willowbank Report - The Gospel And Culture. Wheaton, Illinois: LCWE, 1978.

Loss, Myron. Culture Shock. Middleburg, Pennsylvania: Encouragement Ministries, 1983.

McGavran, Donald A. The Clash Between Christianity And Cultures. Washington, D.C.: Canon Press, 1974.

Stott, John and Cooke, R.T. (eds), Down to Earth: Studies in Christianity and Culture. Grand Rapids: Eerdmans, 1980.

ምዕራፍ 16

ጋብቻ፥ መሲብና ቤተሰብ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር

«አብርሃምም ሽመገለ በዘመኑም አረጀ፤ እግዚአብሔርም አብርሃምን በሥራው ሁሉ ባረከው። አብርሃምም ሎሌውን የቤቱን ሽማግሌ የከብቱን ሁሉ አሣዥ አለው፦ እጅህን ከጭኔ በታች አድርግ፥ እኔም አብሬ ከምኖራቸው ከከነዓን ሴቶች ልጆች ለልጄ ሚስት እንዳትወስድለት በሰማይና በምድር አምላክ በእግዚአብሔር አምልሃለሁ . . . «ሎሌውም ከጌታው ግመሎች መካከል አሥር ግመሎችን ወስዶ፥ ከጌታውም ዕቃ መልካም መልካሙን ይዞ . . . ወደ ናኮር ከተማ ሄደ። ሊመሽም ሴቶች ውኃ ሊቀዱ በሚመጡበት ጊዜ ከከተማዪቱ ውጪ በውኃ ጕድጓድ አጠገብ ግመሎቹን አስበረከከ። እንዲህም አለ፦ የጌታዬ የአብርሃም አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፥ እለምንሃለሁ፤ መንገዴን ዛሬ በፊቴ አቅናልኝ፥ ለጌታዬም ለአብርሃም ምሕረትን አድርግ። እነሆ፥ በዚህ የውኃ ምንጭ አጠገብ እኔ ቆሜአለሁ፥ የዚህችም ከተማ ሴቶች ልጆች ውኃውን ሊቀዱ ይመጣሉ፤ ውኃ እጠጣ ዘንድ እንስራሽን አዘንብዪ የምላት እርስዋም፦ አንተ ጠጣ፥ ግመሎችህን ደግሞ አጠጣለሁ የምትለኝ ቆንጆ፥ እርስዋ ለባሪያህ ለይስሐቅ ያዘጋጀሃት ትሁን . . . ይህን መናገሩንም ሳይፈጽም እነሆ፥ . . . ርብቃ እንስራዋን በጫንቃዋ ተሸክማ ወጣች . . . ብላቴናዪቱም መልከዋ እጅግ ያማረ፥ ወንድ የማያውቃት ድንግልም ነበረች፤ ወደ ምንጭም ወረደች እንስራዋንም ሞላች፥ ተመልሳም ወጣች።

«ሎሌውም ሊገናኛት ሮጠና፦ ከእንስራሽ ጥቂት ውኃ ታጠጪኝ ዘንድ እለምንሻለሁ አላት። እርስዋም፦ ጌታዬ ሆይ፥ ጠጣ አለችው፤ ፈጥናም እንስራዋን በእጅዋ አውርዳ አጠጣችው። እርሱንም ካጠጣች በኋላ፦ ለግመሎችህ ደግሞ ሁሉም እስኪረኩ ድረስ ውኃ እቀዳለሁ አለች» (ዘፍጥ. 24፡1-19)።

«ይስሐቅም ወደ እናቱ ወደ ሣራ ድንኳን አገባት፥ ርብቃንም ወሰዳት፥ ሚስትም ሆነችው፥ ወደዳትም» (ዘፍጥ. 24፡67)።

በዓለም ሁሉም ባህል ጋብቻን፥ መሲብንና ቤተሰብን በተመለከተ የራሱ የሆነ ልማድና ደንብ አለው። እግዚአብሔር ስለ ጋብቻና ቤተሰብ ምን ይላል? እግዚአብሔር ስለ መሲብ ምን ይላል? የሰውን ልጅ ወንድና

ሴት አድርጎ የፈጠራቸውና የመጀመሪያዎቹ ወንድና ሴት በጋብቻ ያጣመራቸው እግዚአብሔር ስለ ሆነ፥ እርሱ ስለ ጋብቻ፥ ወሲብና ቤተሰብ የሚሰውን ማወቅ በጣም አስፈላጊያችን ነው። በዚህ ምዕራፍ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ እንሞክራለን፦

ሀ. ለጋብቻ የእግዚአብሔር ዕቅድ ምንድን ነው?

ለ. ለባሎችና ሚስቶች የእግዚአብሔር ዕቅድ ምንድን ነው?

ሐ. ስለ ወሲብ የእግዚአብሔር ዕቅድ ምንድን ነው?

መ. ለክርስቲያኖች ቤተሰባዊ ሕይወት የእግዚአብሔር ዕቅድ ምንድን ነው?

ሠ. ከአንድ በላይ ስለ ማግባት ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት ምንድን ነው?

ረ. እግዚአብሔር ስለ ፍች ምን ይላል?

ሰ. የትዳር ጓደኛ ስለ መምረጥ አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያዎች ምንድን ናቸው?

ሸ. ክርስቲያን ባለትዳሮች የመካንነትን ችግር እንዴት ይወጣሉ?

ሀ. ለጋብቻ የእግዚአብሔር ዕቅድ ምንድን ነው?

ጋብቻ የእግዚአብሔር አሳብ ነበር

ከመጀመሪያው ጋብቻ የእግዚአብሔር አሳብ ነበር። ጋብቻ የሰው አሳብ አልነበረም። ጋብቻን እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ለአብሮነት፥ ለፍቅር፥ ለጋራ ግበረታቻ፥ ለተግባራዊ እርዳታና ለወሲባዊ እርካታ የሚኖረውን ፍላጎት ለማርካት ያቀደው ውጥን ነበር (ዘፍጥ. 2፡18፤ 1 ቆሮ. 7፡2-3)። በሕይወት ዘመናቸው በሙሉ አንዳቸው ለሌላቸው በጋብቻ በተሳሰሩ አንድ ወንድና አንዲት ሴት በተፈጠረ ደኅንነትና ፍቅር መስጥ ልጆች እንዲወለዱና እንዲያድጉ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነበር [መዝ. (127)፡3፤ ሚል. 2፡14-16፤ ማቴ. 19፡6]።

እግዚአብሔር አዳምን በዔድን ገነት ውስጥ ሲፈጥር፥ ፍጹም ሰው አድርጎ ፈጥሮታል። ይሁንና፥ ለአዳም አንድ ነገር ያስፈልገው ነበር። እግዚአብሔር፥ ፍሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፤

የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት» ብሏል (ዘፍጥ. 2፡18)። እግዚአብሔር ለአዳም ፍጹም አጋር ለመፍጠር ወሰነ። ለአዳም የሴሳ ሰብአዊ ፍጥረት ጎብረት ያስፈልገው ነበር። እግዚአብሔር ሌሎቹን ፍጥረታት ወንድና ሴት አድርጎ ፈጥሮአቸው ነበር (ዘፍጥ. 6፡19)። አዳም ወንድ ስለ ነበረ፥ እግዚአብሔር ከአዳም የጎድን አጥንቶች አንዱን በመውሰድ የሴት ጓደኛ አበጀለት። ይህንንም በማድረግ፥ እግዚአብሔር ለአዳም በሕይወት ዘመኑ ሁሉ አብራው የምትኖር ጓደኛና ለጋብቻውም ፍሬያማነት የወሲብ አጋር ሰጠው። በአዳምና ሔዋን ሥጋዊ ውህደት፥ እግዚአብሔር የሰው ዘር እንዲቀጥል ዐቀደ (ዘፍጥ. 1፡27-28፤ ዘፍጥ. 2፡24)።

ጋብቻ - በሰብአዊ ግኑበረሰብ የመጀመሪያው ተቋም

እግዚአብሔር ጋብቻን የመሠረተው ከሌሎች የሰው ልጆች ተቋሞች ሁሉ በፊት ነበር። ይህም ጋብቻ የሰው ልጅ ግኑበረሰብ መሠረት እንደ ሆነ ያሳየናል። ጋብቻ የተመሠረተው ሰው በኃጢአት ከመውደቁ በፊት ነበር። ይህም የጋብቻን ቅዱስነት ያሳየናል።

እግዚአብሔር በጋብቻ ደስ ይለዋል። በቃና ዘገሊላ በነበረው የሰርግ በዓል ኢየሱስ ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ የለወጠበት ተአምር (ዮሐ. 2፡1-11)፥ እግዚአብሔር ሰዎች በጋብቻ ሙሉ ደስታ እንዲኖራቸው እንደሚፈልግ ያሳያል። ወንዶችና ሴቶች ፍቅርንና ተቀባይነትን እንዲለማመዱና ምሉዓን እንዲሆኑ ይሻል። ጋብቻ የተሠራው ለዚህ ዓላማ ነው።

በእግዚአብሔር ዕቅድ፥ ጋብቻ ግብረ-ገባዊና ግኑበረሰባዊ ጽናት ላለው ጎብረተሰብ መሠረት ነው። ይህም እግዚአብሔር ዝሙትን (ዘጸ. 20፡14)፥ ወሲባዊ ግድፈትን (1 ተሰ. 4፡3-6)፥ የቤተ ዘመድ የፈቃደ-ሥጋ ግንኙነትን (ዘሌ. 18 ከቁጥር 6 ጀምሮ) እና ግብረ ሰዶምን (ሮሜ 1፡24-28) የሚጠላበት ዋነኛው ምክንያት አካል ነው። እነዚህ ነገሮች እግዚአብሔር ለጽኑ ሰብአዊ ግኑበረሰብ የወጠነውን ዕቅድ ያኮላሻሉ፤ ያጣምማሉ። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል» በማለት ያስጠነቅቀናል (ዕብ. 13፡4)።

ዛሬ ብዙ ግኑበረሰቦች ግኑበራዊና ግብረ-ገባዊ ብልሹነት ውስጥ ከሚዘፈቁበት ምክንያት ከፊሉ፥ የእግዚአብሔርን ሕግጋት ሳይጠብቁ

ለመኖር በመወሰናቸው ነው። የሚያሳዝነው የወሲብ ጋጢአቶች የከፉ ውጤቶች የሚያስከትሉ መሆናቸው ነው። ከእነዚህም የከፉ ውጤቶች ሁለቱ የፍችና የፈራረሱ ቤቶች በከፍተኛ ደረጃ መጨመርና ዓለም አቀፋዊ የኤድስ መቅሠፍት ናቸው።

ጋብቻ በዓለም ለሁሉም ሰዎችና ለሁሉም ባህሎች እግዚአብሔር ያቀደው ነው (ዘፍጥ. 2፡24፤ 12፡3፤ ማቴ. 19፡3-9)። እግዚአብሔር ለሰው ልጅ በወጠነው ዕቅድ ቤተሰብ በሌላ በማንኛውም ተቋም ሊተካ አይችልም። አንድ ሰው የቤተሰብን ሕይወት ቢያበላሽ፥ እግዚአብሔር ለጠቅላላው የሰው ዘር በወጠነው ዕቅድ ውስጥ ጣልቃ መግባቱ ነው። በዔድን ገነት የመጀመሪያውን ጋብቻ የመሠረተው እግዚአብሔር ነበር (ዘፍጥ. 2፡21-25)። ጋብቻን በራሳቸው ምግባረ-ብልሹነትና አለመታመን ያበላሹት ሰዎች ናቸው።

ለጋብቻ የእግዚአብሔር ዕቅድ

የእግዚአብሔር ዕቅድ አንድ ወንድ አንዲትን ሴት እንዲያገባ ነው። እግዚአብሔር ለፈጠረው ወንድ አንዲት ሴት ፈጥሮለታል (ዘፍጥ. 2፡22-24)። ይህ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል የሚገኘው አጋርነት ለሕይወት ዘመን ሁሉ እንዲቆይ ፈለገ። በማቴዎስ 19፡5-8 ኢየሱስ፥ «ስለዚህ ሰው አናቱንና አባቱን ይተዋል፥ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል . . . እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው» ብሏል። ይህ የዕድሜ ልክ ቃል ኪዳን ለብዙ ምክንያቶች አስፈላጊ ነው።

በመጀመሪያ፥ ጋብቻ ለሚስት በሕይወት ዘመኗ ሁሉ እንክብካቤ፥ ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑት ነገሮች አቅርቦትና ዋስትና ይሰጣታል (ቆላ. 3፡12-13፤ 1 ጴጥ. 3፡7)። ሁለተኛ፥ ለስሜታዊ ደኅንነትና ልጆችን ለማሳደግ አስፈላጊ ነው። ልጆች እግዚአብሔር እንደሚፈልገው እንዲያድጉ ከተፈለገ፥ አስተማማኝና የተረጋጋ አካባቢ ያስፈልጋቸዋል። ወላጆች ሲለያዩ ወይም ሲፋቱ፥ ልጆች በከፍተኛ ስሜታዊ ሥቃይ ይጠቃሉ። እግዚአብሔር ጋብቻን ከመሠረተበት ዓላማ ከፊሉ፥ ልጆች በመንፈሳዊ ሁኔታ የሚያድጉበትን እርጋታና ፍቅር የተመላበት አካባቢ መስጠት ነው። ሚልክያስ 2፡15፥ «እግዚአብሔር . . . የሕይወትን መንፈስ አንድ አድርጎ ጠብቆልን የለምን? እርሱም የሚፈልገው ምንድር ነው? ዘር አይደለምን? ስለዚህ መንፈሳችሁን ጠብቁ፥ ማንም የልጅነት ሚስቱን አያታልል» ይላል።

እግዚአብሔር በሕይወት ዘመኑ ሁሉ አንድ ወንድ አንዲት ሴት እንዲያገባ ያቀደበት ሌላው ምክንያት፥ ከሴቲቱ የስሜት ደኅንነት ጋር ይዛመዳል። አንዲት ሴት ባሏ እርሷን ብቻ እንደሚያፈቅር ማወቅ ያሻታል። ወንድ ብዙ ጋብቻ በሚፈጽምበት ቤት የሴት ስሜታዊ መሻቶች ሊሟሉላት አይችሉም። አንድ ሰው ከአንድ የሚበዙ ሚስቶች ካሉት፥ ሁልጊዜም በሚስቶቹ መካከል ቅንዓትና ጥላቻ ይኖራል። በእግዚአብሔር ፊት ወንዶችና ሴቶች እኩል ናቸው (ገላ. 3፡28)። ለሚስት የባሏን ሥጋዊ መሻቶች ማሟላት እንደሚገባት ሁሉ፥ ለባልም የሚስቱን ስሜታዊ መሻቶች ማሟላት አስፈላጊ ነው።

ከአንድ በላይ ማግባት የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም

በፍጥረት እግዚአብሔር ለአንድ ወንድ አንዲት ሴት ስለ ሰጠ፥ የብዙ ጋብቻ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። ከአንድ በላይ ጋብቻ መልካም ጅማሬ አልነበረውም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰው የመጀመሪያው ብዙ አግቢ (ላሜሕ) ነፍሰ-ገዳይም ነበር (ዘፍጥ. 4፡23)። ይሁንና፥ ከአንድ በላይ ጋብቻ እንደ ዝሙት አይደለም። በብዙ ጋብቻ ባል ሚስቶቹንና ልጆቻቸውን የመቀለብ ኃላፊነት አለበት። በብዙ የአፍሪካ ጥንታዊ ባህሎች ዘንድ የብዙ ጋብቻ የተለመደ ነገር ነው።

እንደ ንጉሥ ዳዊት በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን እግዚአብሔር የተጠቀመባቸው አያሌ ሰዎች ብዙ ሚስቶችን አግብተው ነበር። አንዳንድ ሰዎች የብዙ ጋብቻን በአፍሪካ ፍትሐዊ ለማድረግ ይህንኑ እውነት ይጠቀማሉ። ምንም እንኳ እግዚአብሔር እነዚህን ሰዎች ለኃላፊው ቢጠቀምም፥ ብዙ ሚስቶች እንዲያገቡ አልፈለገም ነበር። ነገሥታትን በተመለከተ እግዚአብሔር፥ «ልቡም እንዳይስት ሚስቶችን ለእርሱ አያበዛም» ብሏል (ዘዳ. 17፡16-17)። እውነቱ ሲታይ፥ እግዚአብሔር የብሉይ ኪዳን ባለ ብዙ አግቢዎችን፥ ብዙ ሚስቶች በማግባታቸው በውጤቱ እንዲሠቃዩ አድርጓል። ይህ በአብርሃም ሕይወት ውስጥ ሊታይ ይችላል (ዘፍጥ. 16፡1-6)።

አጋርን ሁለተኛ ሚስት አድርጎ ከመሰደቡት ጊዜ ጀምሮ፥ አብርሃም በቤቱ ደስታ አልነበረውም። በአጋርና በግራ፥ በይስሐቅና በእስማኤል መካከል ቀናተኛነት ነበር። በይስሐቅና በእስማኤል እንዲሁም በቀጣይ ትውልዶቻቸው መካከል የተነሣው ቅንዓትና ጥላቻ እስከ ዛሬ ድረስ ለ4000 ዓመታት ቆይቷል። ይህም በአይሁዶች (የይስሐቅ ዘሮች) እና በዓረቦች (የእስማኤል ዘሮች) መካከል በሚካሄደው ጥላቻ ውስጥ ሊታይ

ይችላል። ወደ በኋላ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሚታየው የብዙ ጋብቻ ችግር ተጨማሪ ማብራሪያ እናቀርባለን።

የእግዚአብሔር ዕቅድ በጋብቻ ውስጥ ለሚኖር አንድነት

በእግዚአብሔር ዕቅድ፥ ጋብቻ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል ሦስት ገጽታ ያለውን አንድነት ያካትታል። ይህ ባለ ሦስት ገጽታ አንድነት፥ ሥጋ፥ አእምሮ፥ መንፈስ ተብሎ ከሚገለጸው የሰብአዊ ፍጥረታት ባለ ሦስት ገጽታ ተፈጥሮ ጋር ይዛመዳል (1 ተሰ. 5:23፤ ዕብ. 4:12)።

1. ሥጋዊ አንድነት

እግዚአብሔር ለጋብቻ ባቀደው ነገር ውስጥ የመጀመሪያው አንድነት፥ የወሲባዊ ግንኙነት ሥጋዊ አንድነት ነው። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሴቲቱን ወደ ወንዱ ሲያመጣት፥ ሁለቱም ዕራቁታቸውን ሆነው አይተፋፈሩም ነበር (ዘፍጥ. 2:25)። ጌታ፥ «ስለዚህ ሰው እናቱንና አባቱንና ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ» ብሏል (ዘፍጥ. 2:24)። መጽሐፍ ቅዱስ ሥጋዊ የጋብቻ ጥምረት በእግዚአብሔር ፊት መልካምና የተቀደሰ እንደ ሆነ ያስተምራል (ዘፍጥ. 1:27-28፥ 31፤ ምሳሌ 5:18-19፤ ዕብ. 13:4)።

ከጋብቻ ሥጋዊ አንድነት ልጆች ከመወለዳቸውም በላይ፥ ለቤተሰቡ የጋራ ኃላፊነት ይመሠረታል። ባል ቤተሰቡን ለመመገብ የመሥራት ኃላፊነት አለበት (ዘፍጥ. 2:15)። ሚስት ልጆችን የመውለድና ቤቱን የመንከባከብ ኃላፊነት አለባት (1 ጢሞ. 5:14)።

2. አእምሮአዊ እና ስሜታዊ አንድነት

እግዚአብሔር ለጋብቻ በወጠነው ዕቅድ ሁለተኛው ዓይነት አንድነት፥ አእምሮአዊና ስሜታዊ አንድነት ነው። አእምሮአዊና ስሜታዊ አንድነት የሚመጣው ሁለት ሰዎች በኅብረትና በስምምነት ሲኖሩ ነው። ለዚህ ዓይነቱ አንድነት፥ ባልና ሚስት ቢያንስ የተወሰኑ የጋራ እሴቶች፥ የጋራ ዓላማዎችና የጋራ ፍላጎቶች ሊኖሩአቸው ይገባል። የልጆች መወለድ እነዚህን የጋራ እሴቶች፥ ዓላማዎችና ፍላጎቶች ለማዘጋጀት ይረዳል። አንድ ዓይነት ቋንቋና ባህል ለአእምሮአዊና ስሜታዊ አንድነት አገዛ ያደርጋል። የዚህ ዓይነቱ አንድነት ነው የሰዎችን የኅብረት፥ የተቀባይነትና የእሴት መሻቶች የሚያሟላው።

በዓለም ሁሉም ሰው በሌላ ሰው ሊፈለግ፥ ሊወደድና ሊደነቅ ይፈልጋል። እንዳልተፈለገና ዋጋ እንደሌለው ሆኖ የሚሰማው ሰው የመኖር ዓቅም አይኖረውም። በአእምሮአዊና ስሜታዊ አንድነት ለማደግ፥ ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው ለመጫወትና አሳቦችን ለመጋራት ጊዜ መውሰድ አለባቸው። አንዳንድ ነገሮችን በጋራ ለማከናወንና ለአጋራቸው የሚያሻውን ነገር ለማጣላት ጊዜ መውሰድ አለባቸው (ፊልጵ. 2፡4)። በፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን የነበረውን የአንድነት መታጣት ችግር በተመለከተ፥ ጳውሎስ፥ «የመንፈስ ኅብረት ቢሆን፥ ምሕረትና ርኅራኄ ቢሆኑ ደስታዬን ፈጽሙልኝ፤ በአንድ አሳብ ተስማሙ፥ አንድ ፍቅር አንድም ልብ አንድም አሳብ ይሁንላችሁ» ብሏል (ፊልጵ. 2፡2)። ይህ የአእምሮአዊና የስሜታዊ አንድነት መግለጫ ነው። ምንም እንኳ ጳውሎስ በዚህ ዓረፍተ ነገሩ በጋብቻ ውስጥ ስለሚኖር አንድነት እየተናገረ ባይሆንም፥ የዚህ ምንባብ እውነታ ለጋብቻ ግንኙነትም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን አንድነት ሊዛመድ ይችላል።

ባልና ሚስት አእምሮአዊና ስሜታዊ አንድነት ለማሳደግ በትዕግሥት የማይጠብቁ ከሆነ፥ ብዙም ሳይቆይ ይራራቃሉ። እርስ በርሳቸው ብዙም አንደማይቀራረቡ ሲሰማቸው፥ ጋብቻቸውም ደስታ እየተለየው ይሄዳል። ይህም ሥጋዊ ግንኙነታቸውን ይጎዳል። ባል ሚስቱን እንደ ሰብአዊ ፍጥረት በመመልከት በእርሷ ደስ መሰኘቱን ሳያሳይ ሲቀር፥ ሚስት ከባሏ ጋር የወሲብ ግንኙነት ለመፈጸም አትፈልግም። ለታመመ ጋብቻ መድኃኒቱ ባል ሚስቱን በእመኝነታቸው ጊዜ ያደርግ እንደ ነበረው ማፍቀር፥ መንከባከብ፥ ማክበርና ትኩረት ሰጥቶ ማስተናገድ ነው። ይህ በኤፌሶን 5፡25 «ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ» የሚለው ምንባብ ትርጉም አካል ነው።

3. መንፈሳዊ አንድነት

እግዚአብሔር ለጋብቻ በወጠነው ዕቅድ ሦስተኛው ዓይነት አንድነት መንፈሳዊ አንድነት ነው። ይህ ሁለቱም ባልና ሚስት ክርስቲያኖች በመሆን ጌታን ለመከተል ሲፈልጉ የሚገኝ አንድነት ነው። እግዚአብሔር በጋብቻ ውስጥ መንፈሳዊ አንድነትን ስለሚፈልግ አንድ ክርስቲያን ክርስቲያን ያልሆነውን ሰው እንዲያገባ በፍጹም አይፈልግም። መጽሐፍ ቅዱስ «ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ። የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው?» ይላል (2 ቆሮ. 6:14-15)።

እጅግ ጠንካራ መንፈሳዊ አንድነት የሚገለጸው ባልና ሚስት መጽሐፍ ቅዱስ ሲያነቡና አብረው ሲጸልዩ ነው። ከመንፈሳዊ አንድነት በላይ ጋብቻን ሊያስተሳስር የሚችል ጠንካራ ማጣበቂያ አይገኝም። ተወዳጁ ምሳሌ «አብሮ የሚጸልይ ቤተሰብ አብሮ ይሰነብታል» ይላል። በጌታ አንድ የሆኑ ባልና ሚስት መንፈሳዊ ልጆችን ሊያሳድጉ ይችላሉ (ዘዳ. 6:6-7)። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር መንፈሳዊ ትውልዶችን እንደሚፈልግ ይገልጻል (ሚል. 2:15)።

መንፈሳዊ አንድነት ለጋብቻ ትልቅ ሰላምና በረከትን ያመጣል። ለቤተሰቡ፥ ክርስቶስ የቤቱ ግዕዝል ሲሆን የሚመጣውን ሰላም ያስገኛል (ዮሐ. 14:27)። በተጨማሪም ቤተሰቡ ለክርስቶስ ጠንካራ ምስክር እንዲሆን ያስችላል። መጽሐፍ ቅዱስ «ባሎች ሆይ ደካማ ፍጥረት ስለሆኑ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ፥ጸሎታችሁ እንዳይከለከል አክብሩዋቸው» ይላል(1 ጴጥ. 3:7)።

በጌታ ፊት ራሳቸውን በጸሎት የሚያስተባብሩ ክርስቲያን ባለትዳሮች ከፍተኛ መንፈሳዊ ኃይል ሲኖራቸው ለእግዚአብሔር መንግሥት በርካታ ውልካም ነገሮችን ሊያከናውኑ ይችላሉ። ማቴዎስ 18:19 «ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢስማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል» ይላል። ጌታ በዚህ ኃይለቱ መንፈሳዊ አንድነት ደስ ይሰኛል። በጌታ አንድነት ያላቸው ክርስቲያን ባለትዳሮች የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ዘር ናቸው። ኢየሱስ «ሁለት ወይንም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እገኛለሁ» ብሏል (ማቴ. 18:20)።

ለ. ለባሎችና ለሚስቶች የእግዚአብሔር ዕቅድ ምንድን ነው?

ጋብቻ እግዚአብሔር እንደሚፈልገው ይሆን ዘንድ እያንዳንዱ የትዳር ጓደኛ እግዚአብሔር የሰጠውን የተወሰኑ ኃላፊነቶች መወጣት አለበት።

የእግዚአብሔር ዕቅድ ለባል

የክርስቶስን የቤቱ ክርስቲያን የእረኝነት አገልግሎት ምሳሌ፥ ባሎች ሁሉ በሚተሰበዎቸው ዘንድ ሊከተሉት የሚገባ የመሪነት አርአያ ነው (ኤፌ 5: 25)።

1. ባል ሚስቱን ከራስ ወዳድነት በጠራ መንገድና ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን የሚወደውን ያህል መውደድ አለበት (ኤፌ. 5:25)። ይህም ራስን መሠዋትንና ራስን መካድን ይጠይቃል።

2. መልካሙ እረኛ ኢየሱስ ሕዝቡን በየዋህነት እንደሚመራ ሁሉ ባል ሚስቱንና ልጆቹን በየዋህነት መምራት አለበት [መዝ. (23)፤ ኤፌ. 5:23]። ይህ በዓለም እንዳለው የአምባገነንነት መሪነት ሳይሆን ራስን የመካድ የባርነት መሪነት ነው። ብዙ ባሎች ሚስቶቻቸውን በአምባገነንነት በማስተዳደር በራሳቸውና በቤተሰቦቻቸው ላይ የሚመጣውን የእግዚአብሔር በረከት ያቅባሉ።

3. ባል ለቤተሰቡ የሚያስፈልገውን ማኟላት አለበት። ይህም ለማኅበራዊ፥ ስሜታዊና መንፈሳዊ ብሎም ሥጋዊ መሻታቸው የሚያስፈልገውን ነገር ማሟላትን ይጨምራል [መዝ. (23):1፤ 1 ጢሞ. 5:8]።

4. ባል ቤተሰቡን መንከባከብ አለበት (ኤፌ. 5:28-29)። እያንዳንዱ አባት የኢዮብን ምሳሌነት በመከተል በየዕለቱ ለሚስቱና ለልጆች መጸለይ አለበት (ኢዮብ 1:5)።

5. ባል ሚስቱን ማክበር አለበት (1 ጴጥ. 3:7)።

6. ባል ሚስቱን ማነፅ እና በክርስቶስ ማበረታታት አለበት (ኤፌ. 5:26).

7. ባል ሚስቱን በአሳብ እንደሚረዳት ማሳየት አለበት (1 ጴጥ. 3:7)።

8. ባል ልጆቹን ለማሠልጠን፥ ለማረም፥ ለመቅጣት እና በመንፈሳዊ መንገድ ለማስተማር ኃላፊነት መውሰድ አለበት (ኤፌ. 6:4)። ይህ በቤት የባል የመሪነት ኃላፊነት ነው። በፍርድ ቀን ለቤተሰቡ መንፈሳዊ ሁኔታ እግዚአብሔር በኃላፊነት የሚጠይቀው ባልን እንጂ ሚስትን አይደለም። ይህም በዔድን ገነት ለተፈጸመው ኃጢአትና ዓመፀኛነት ሔዋንን ሳይሆን አዳምን በኃላፊነት ከጠየቀበት ሁኔታ ይታያል (ሮሜ 5:12,15, 18-19)።

የእግዚአብሔር ዕቅድ ለሚስት

ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስን መውደድና ለእርሱም መገዛት ይኖርባታል (ኤፌ. 5:24)። በዚህ ግብራዊያ ቤተክርስቲያን ሚስት ልትከተላት የሚገባት ምሳሌ ናት።

1. በእግዚአብሔር ዓይን ፊት ወንዶችና ሴቶች እኩል ስለ ሆኑ (ገላ. 3:28)፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወንዶችና ሴቶች ለክርስቶስ ካላችው ፍርሃት የተነሣ አንዳችው ለሌላቸው ሊገዙ ይገባል (ኤፌ. 5:21)። ይህም እርስ በርሳቸው ለጠባያቸው ተጠያቂዎች መሆን አለባቸው ማለት ነው። ይህ በጋብቻ ግንኙነትም በሚስቶችና ባሎች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

በወንዶችና ሴቶች መካከል ከሚኖረው ከዚህ አጠቃላይ ግንኙነት በተጨማሪ እግዚአብሔር በፈጠራቸው ተቋማት ሁሉ እንደ ሆነው በጋብቻም ውስጥ የተዋረድ ሥርዓት አለ። በእግዚአብሔር የተዋረድ ሥርዓት ክርስቶስ የቤተክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ ሁሉ፥ ባልም የቤተሰቡ ራስ ነው (ኤፌ. 5:23)። ይህንኑ ፈለግ በመከተል ሚስት ልክ ለክርስቶስ እንደምትገዛው ለባሏ መገዛት አለባት (ኤፌ. 5:22-24)። ይሁንና ይህ የተዋረድ ሥርዓት ንጉሥ በጭፍሮቹ ላይ እንደሚያደርገው፥ ባል ሚስቱን ለመጨቆንና ለመደብደብ የሚያስችለውን መብት አይሰጠውም። በሌላ በኩል መጽሐፍ ቅዱስ የዚህን አሳብ ተገላቢጦሽ ያስተምራል። ባል ሚስቱንና ቤተሰቡን የሚመራበት መንገድ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑን እንደሚወዳትና እንደሚመራት ሁሉ፥ በመሥዋዕትነት በመሠዋት አገልግሎትና ራስን በሚክድ ፍቅር ተለይቶ መታወቅ አለበት (ኤፌ. 5:25)።

2. ሚስት ባሏን ልታበረታታና ልትረዳ ይገባል። ሚስት ባሏን ከምታበረታታባቸው እጅግ አስፈላጊ መንገዶች አንዱ ለእርሱ መጸለይ ነው (ዘፍጥ. 2:18)።

3. ልጆች ትወልዳለች (1 ጢሞ. 2:15)።

4. ሚስት በቤት ጣፋጭ መንፈስ ሆና መቆየት አለባት (1 ጴጥ. 3:3-4)።

5. ሚስት ቤተሰቧን በጥሩ ሁኔታ መያዝ አለባት (ምሳሌ 31:37)።

6. ሚስት መልካም ምስክርነት ሊኖራት ይገባል (ምሳሌ 31:31፤ ቲቶ 2:3)። ይህም ድሀን ለመርዳት እጅ መዘርጋትን ይጨምራል (ምሳሌ 31:20)።

7. በዕድሜ የገፉ ሚስቶች ሴት ልጆቻቸውን ጨምሮ ወጣት ሴቶች ባሎቻቸውን እንዲወዱና እንዲያከብሩ በመንፈሳዊ መንገድ ሊያስተምሯቸው ይገባል (ቲቶ 2:4)።

የእግዚአብሔር ዕቅድ ለባልና ለሚስት እንደ ወላጆች

እግዚአብሔር ወላጆች ሁሉ ልጆቻቸውን ሲያሳድጉ ሊከተሉት የሚገባ ምሳሌ ነው (ኤፌ. 5:1-2)። በትንሽ ልጅ አእምሮ ስለ እግዚአብሔር የሚታሰበው የመጀመሪያ አሳብ ብዙውን ጊዜ የወላጆች በተለይም የአባት ምስል ነው።

1. ወላጆች ክርስቶስን በመምሰል በልጆቻቸው ፊት የመንፈሳዊ አኗኗርን ምሳሌ መቅረጽ አለባቸው (ኤፌ. 5:1-2)። ልጆች ከወላጆቻቸው ምክር ይልቅ ምሳሌአቸውን ወደ መከተሉ ያዘነብላሉ።

2. ልክ እግዚአብሔር ወላጆችን እንደሚወድ ወላጆች ልጆቻቸውን መውደድ አለባቸው (ኤፌ. 5:2)።

3. ወላጆች ልጆቻቸውን ስለ እግዚአብሔር መንገዶች ማስተማር አለባቸው (ምሳሌ 1:7-8)። ይህ በተለይ ትክክለኛና ትክክለኛ ስላልሆኑ፥ መልካምና ክፉ አሳቦች፥ እንዲሁም መሠረታዊ ስለ ሆኑ ግብረገባዊና መንፈሳዊ እሴቶች ሊነገራቸው ይገባል። ክርስቲያን ወላጆች የልጆቻቸውን ግብረገባዊና መንፈሳዊ ሥልጠና ለባህላዊ መሪዎች ወይንም ለመንግሥት ት/ቤቶች መርሐ ግብሮች መተው የለባቸውም። እግዚአብሔር ወላጆች ልጆቻቸውን ስለ ሕግጋቱና ስለ መንገዶቹ እንዲያስተምሯቸው ይፈልጋል (ዘዳ. 6:6-7)።

4. ልክ እግዚአብሔር በፍቅር እንደሚቀጣን ወላጆች ልጆቻቸውን በፍቅር መቅጣት አለባቸው። ይህ የአባት ኃላፊነት ነው (ኤፌ. 6:4፤ ዕብ. 12:9)።

5. ልክ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚያስፈልገውን እንደሚሰጥ ወላጆች ለልጆቻቸው የሚያስፈልጉትን ነገሮች ማሟላት አለባቸው [መዝ. (23):1፤ 1 ጢሞ. 5:8]።

6. እግዚአብሔር እኛን እንደሚጠብቀን ወላጆች ልጆቻቸውን በሥጋዊ፥ በአእምሮአዊና በመንፈሳዊ ሁኔታዎች መጠበቅ አለባቸው [መዝ. (18):2፤ (144):2]።

7. እግዚአብሔር እኛን እንደሚመራን ወላጆች ልጆቻቸውን መምራት አለባቸው [መዝ. (32):8]።

ሐ. ስለ ወሲብ የእግዚአብሔር ዕቅድ ምንድን ነው?

እግዚአብሔር ሰዎችን ሲፈጥር ለወሲባዊ እርካታ ዓላማ ወንድና ሴት አድርጎ ፍጥሮአቸዋል (ዘፍ. 1:27-28)። ለክርስቲያኖች ወሲብ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች በጎነትና ደስታ ያሰበው ነገር እንደ ሆነ መረዳት መልካም ነው። ወሲብ በጋብቻ ውስጥ ሲፈጸም ኃጢአት አይደለም። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ ወሲብ መልካምም (ዘፍጥ. 1:31) ቅዱስም ነው (ዕብ. 13:4)። ወሲብ ሰው በኃጢአት ከመውደቁ በፊት በዔድን ገነት የተሰጠው ነው (ዘፍጥ. 1:27-28፤ 2:21-25)። መጽሐፍ ቅዱስ «ምንጭህ ብሩክ ይሁን፤ ከጕብዝናህም ሚስት ጋር ደስ ይበልህ። እንደ ተወደደች ዋላ እንደ ተዋበችም ሚዳቋ፥ ጡትዋ ሁልጊዜ ታርካህ፥ በፍቅርዋም ሁልጊዜ ጥገብ» ይላል (ምሳሌ 5:18-19)።

የመጀመሪያው የሰው [illegible] ኃጢአት አዳም ከሚስቱ ጋር ወሲብ መፈጸሙ እንደ ሆነ በስፋት ይታመናል (ዘፍጥ. 4:1)። ይህ ግን ሐሰት ነው። የመጀመሪያው ኃጢአት እግዚአብሔር መልካምና ክፉ ከምታስታውቀው ዛፍ እንዳይበላ የተሰጠውን ትእዛዝ የመተላለፍ ተግባር ነበር (ዘፍጥ. 2:17፤ 3:6)።

ከኃጢአት የተነሣ ሰው እግዚአብሔር ለወሲብ የወጠነውን ዕቅድ አጣጂል። በእግዚአብሔር ዕቅድ መሠረት ወሲባዊ ግንኙነትን ባልና ሚስት በጋብቻ ቃል ኪዳን ውስጥ ብቻ እንዲፈጽሙት በጥብቅ የተደነገገ ነው (1 ቆሮ. 7:2-5፤ ዕብ. 13:4)። ወሲብን ከጋብቻ ውጭ መፈጸም የከፋ ኃጢአት ነው። ዛሬ በዓለም ውስጥ ብዙ ችግሮች በኃጢአት ከሚፈጸም ወሲብ የመነጩ ናቸው። እንደ ዝሙት፥ ከጋብቻ በፊት የሚፈጸም የወሲብ ግንኙነት፥ ግብረ ሰዶም (በተመሳሳይ ፆታዎች መካከል

የሚደረግ ግንኙነት)፥ በቤተሰብ አባላት መካከል የሚደረጉ ያታዊ ግንኙነቶች፥ ከእንስሳት ጋር የሚፈጸሙ ወሲባዊ ክንውኖች ሌሎችም አዳፋ ልምምዶች ለእግዚአብሔር ርኩሰት ናቸው። በዘሌዋውያን 18 እና 20፡10-21 እግዚአብሔር ንጹህ ያልሆኑትንና የከፋ ቅጣት የሚያስከትሉትን ልምምዶች ዝርዝር ይሰጠናል።

ወሲብ እንደ እሳት ኃይለኛ ነው። እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረበት መንገድ የተነሣ እሳትን መቋቋም ይቻላል። እሳት በጣም ሊጠቅመን ይችላል። ምግባችንን ለማብሰልና ቤታችንን ለማሞቅ ልንጠቀምበት እንችላለን። ይሁንና ቤት በእሳት ከተቀጣጠለ ቤቱን ሊያወድምና በውስጡ ያሉትን ሰዎች ሊገድል ይችላል። ወሲብም እንዲሁ ነው። ወሲብን መቋቋም የሚቻለው እግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶችን ከፈጠረበት መንገድ የተነሣ ነው። በእግዚአብሔር ምሪት ውስጥ ወሲብ እግዚአብሔር ለተጋቡ ሰዎች ከሰጣቸው በረከቶች አንዱ ነው። ታላቅ እርካታ የሚገኝበትና ልጆችን ወደ ዓለም ለማምጣት የሚረዳ መሣሪያ ነው። የእግዚአብሔርን ምሪት ከጣሱ ግን ወሲብ ቤትን እና የሰውን ሕይወት ሊያጠፋ ይችላል።

ሰዎች የወሲብ ፍላጎታቸውን ከጋብቻ ውጭ ለማርካት ሲሞክሩ ጋብቻ ይፈራርሳል፤ ቤተሰብ ይታመሳል፤ የግለሰቦችም ሕይወት ከእግዚአብሔር የፍርድ እርግማን በታች ይወድቃል። እግዚአብሔር ለኃጢአት ይቅርታ ያደርጋል ማለት በዚህ ሕይወት የኃጢአቱ ውጤቶች አይከተሉንም ማለት አይደለም። ይልቁንም ውጤቶቹ እጅግ የከፉ ሊሆኑ ይችላሉ። አንድ ሰው ሌላውን በከፍተኛ ንዴት ተነሣሥቶ ቢገድልና በኋላ በከፍተኛ ጸጸት ንስሐ ቢገባ እግዚአብሔር ይቅር ሊለው ይችላል። ይሁንና ንስሐና ይቅርታ የሞተውን ሰው አያስነሡትም። ንጉሥ ዳዊትን በተመለከተ፥ ምንም እንኳ እግዚአብሔር ከኦሪዮን ሚስት ጋር የፈጸመውን የዝሙት ኃጢአት ይቅር ቢለውም፥ የቤተሰቡ ሕይወት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ተበላሽቷል (2 ሳሙ. 12:11-13)።

አንዳንድ ባህሎች ከጋብቻ በፊት የሚፈጸመውን ዓይነት የተወሰኑ ወሲባዊ ኃጢአቶች አይኮንኑም። አንድ ክርስቲያን ከእንደዚህ ዓይነት ባህል የመጣ ከሆነ፥ እንዲህ ዓይነቱን የወሲብ ግድፈት የኮነነው ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን ማወቅ አለበት። ክርስቲያን ለጠባዩ የሚጠየቀው በባህሉ ሳይሆን በእግዚአብሔር ነው። የእግዚአብሔር ሕግጋት ፍጹማን በመሆናቸው፥ ከባህል ጋር ለማጣጣም ብሎ አይለውጣቸውም።

ስለ ተበላሸ የወሲብ ግንኙነት ጥቂት ማለት አለብን። ዛሬ በአንዳንድ የዓለም ክፍሎች፡ ብዙ ሰዎች ወደ ግብረ ሰዶም ፊታቸውን መልሰዋል። ይህ እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረበትን መንገድ ሙሉ ለሙሉ ማበላሸት ነው። እንስሳት እንኳ ወንዶችና ሴቶች ሆነው ተፈጥረዋልና ዛሬ ግብረ ሰዶማውያን ልምምዳቸው ተገቢና አማራጭ የሕይወት ዘይቤ እንደ ሆነ ለመጋገት ይፈልጋሉ። እውነታው ግን እንደ እነዚህ ዓይነት ልምምዶች ለእግዚአግሔር ርኩሰት መሆናቸው ነው (ዘሌ. 20:13)። መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ወሲባዊ ብልሹነትን ሲከተሉ እግዚአብሔር ለኃጢአታቸው አሳልፎ እንደሚሰጣቸውና በሕይወታቸው ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ እንደሚያመጡ ይናገራል (ሮሜ 1:24፡ 26)። እግዚአብሔር ጥንታዊዎቹን የሰዶምና ጎሞራ ከተሞች በወሲባዊ ብልሹነት ኃጢአታቸው ሙሉ ለሙሉ እንዳወደማቸው ልብ ልንል ይገባል (ዘፍጥ. 19:1-25)። እግዚአብሔር ዛሬም አልተለወጠም።

ለግብረ ሰዶማዊ ሰው ትከከለኛ የክርስቲያን አመለካከት ምንድን ነው? የእግዚአብሔር ሕዝቦች ሁልጊዜም ለግብረ ሰዶምና ለሌሎች የኃጢአት ልምምዶች ባሪያ ለሆኑት ሰዎች ፍቅር፡ ትዕግሥትና ርህራሄ ሊያሲዩ ይገባል። ክርስቲያኖች ለእንደዚህ ዓይነት ሰዎች እርዳታንና በክርስቶስ የሚገኘውን የመላቀቂያ ምክር ሊለግሷቸው ይገባል። በተመሳሳይ ጊዜም፡ ክርስቲያኖች ይህ ብልሹ ልምምድ ምንም እንዳልሆነ፡ ወይም ይኸኛው የሕዝቦች ቡድን ልዩ መብቶችን ሊያገኝ እንደሚገባ የሚሰነዝረውን አሳብ ሊታገሡ አይገባም። ይህና ሌሎችም የወሲብ ኃጢአቶች በእግዚአብሔር ኩነኔና ቁጣ ሥር ናቸው (1 ተሰ. 4:3-6)።

የምኞት ችግር

ምኞት የሚታየው የሰዎች ተገቢ ፍላጎቶች በኃጢአት በመበላሸታቸው ነው። ፍላጎቶች በራሳቸው ክፉ አይደሉም። ፍላጎታችን እግዚአብሔር ከፈጠረን ሁኔታ ይመጣል። ለምሳሌ፡ እግዚአብሔር ሰዎች ሕይወትን ለግቆየት እንዲመገቡ አድርጎ ፈጥሮአቸዋል። ሰው ሲርበው የመመገብ ፍላጎት ቢያሳይ ኃጢአት አይደለም። ይሁንና፡ ከመጠን በላይ መመገብ ለምግብ ከሚኖረን ተገቢ ፍላጎት ያለፈ ብልሹ ተግባር ነው። ይህ የምኞት ዓይነት ነው።

እግዚአብሔር ወንዶችንና ሴቶችን እርስ በርሳቸው ከሚኖራቸው ተፈጥሮአዊ፡ ሥጋዊና ስሜታዊ ስበት ጋር ፈጥሮአቸዋል። ያ ስበት ኃጢአት አይደለም። ወደ ተቃራኒ ፆታ መሳብ የመጀመሪያው

የእግዚአብሔር ፍጥረት አካል ሲሆን፥ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ውስጥ ሁሉም መልካም እንደ ሆነ ገልጾአል (ዘፍጥ. 1:31)።

ችግሩ እግዚአብሔር የሰጠን ወሲባዊ ፍላጎት በኃጢአት መበላሸቱ ነው። ከዔድን ገነቱ ውድቀት ጀምሮ፥ ሰዎች ፍላጎታቸውን ጨምሮ በሁሉም የባሕርያቸው አካል ተበላሹ። ከኃጢአተኛ ተፈጥሮአቸው የተነሣ፥ ወንዶችና ሴቶች እግዚአብሔር እንዳቀደላቸው በጋብቻ አጋሮቻቸው አይረኩም። ይልቁንም፥ ሌላውን ወንድ ወይም ሴት በምኞት ይከተላሉ።

ፍቅር ወይስ ምኞት?

ብዙ ወጣቶችን የሚያስጨንቀው አንደኛው ጥያቄ በፍቅርና በምኞት መካከል የሚገኘው ልዩነት ነው። ሁለቱም ፍቅርና ምኞት ከፍተኛ የወሲብ ፍላጎትን ያካትታሉ። ልዩነታቸው ምንድን ነው? ፍላጎቱ ፍቅር ወይም ምኞት መሆኑን ለመወሰን አንድ ሰው ሊጠቀምበት የሚችለው ቀላል ሙከራ፥ ራስ ወዳድ ያለመሆን ሙከራ ነው። አንድ ወንድ አንዲትን ሴት በመንፈሳዊ ፍቅር ከወደዳት ለእርስዋ በሚኖረው ፍላጎት ራስ ወዳድ አይሆንም፤ የሚወዳትን ልጅ ከጋብቻ በፊት እንድትገናኘው በማደፋፈር አያሳፍራትም፥ ወይም አያረክሳትም።

ይህ መመሪያ የንጉሥ ዳዊት ልጅ የነበረው አሞን በአባት በኩል እህቱ በሆነችው በትዕማር ላይ በፈጸመው የአመንዝራነት ተግባር ታሪክ ውስጥ በግልጽ ይታያል (2 ሳሙ. 13:1-12)። ትዕማር አስፈላጊ ከሆነ አሞንን ለማግባት ፈቃደኛ ብትሆንም፥ አሞን ግን ፍላጎቱን ለማርካት እስከ ጋብቻው ዕለት ለመጠበቅ አልፈለገም ነበር (2 ሳሙ. 13:13-14)። አሞን ለትዕማር የነበረው የራስ ወዳድነት ፍላጎት ፍቅር ሳይሆን ምኞት ነበር። በሌላ በኩል፥ አናጺው ዮሴፍ ማርያምን ሚስቱ አድርጎ በመውሰድ ወሲባዊ ግንኙነት ከመፈጸሙ በፊት ለእመቤትነት ዓመትና ለኢየሱስ ልደት ሲል በቆይታ ለመጠባበቅ ፈቃደኛ ነበር (ማቴ. 1:24-25)። ዮሴፍ ለእርስዋ እውነተኛ ፍቅር ስለ ነበረውና እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ስለ ፈለገ፥ ማርያምን በትዕግሥት ለመጠበቅ ፈቃደኛ ነበር። በፍቅርና በምኞት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

ፍቅር ለመስጠት ሲፈልግ፥ ምኞት ግን ለማግኘት ይሻል።

ፍቅር ራስን መካድ ሲሆን፥ ምኞት ራስን ማገልገል ነው።

ፍቅር የእግዚአብሔርን ጊዜ በትዕግሥት ለመጠባበቅ ሲፈቅድ፥ ምኞት ግን ለመጠበቅ አይፈቅድም።

ፍቅር ለተፈቃሪዋና ለልጆቿ የዕድሜ ልክ ኃላፊነት ለመውሰድ ሲፈቅድ፥ ምኞት ከወሲብ ጋር የሚሄደውን ኃላፊነት ለመሸከም አይፈልግም።

ፍቅር የተፈቃሪውን ደስታና በጎነት ሲሻ፥ ምኞት እርካታን ብቻ ይፈልጋል።

ፍቅር ለተወደደው ሰው ከቶውንም ኃፍረት የማያስከትል ሲሆን፥ ምኞት ግን ለሌላው ኃፍረት ቢያመጣም ግድ የለውም።

ፍቅር ለሕይወት ዘመን ሁሉ የሚቆይ ሲሆን፥ ምኞት ግን ጊዜያዊ ነው።

ፍቅር ከእግዚአብሔር የሚመጣ ታላቅ በረከት ሲሆን፥ ምኞት ጉልቅ የኃጢአት እርግማን ነው። ባሎች ሚስቶቻቸውን እንዲወዱ የታዘዘ ሲሆን (ኤፌ. 5:25)፥ ከምኞት እንድንሸሽ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል (2 ጢሞ. 2:22)።

ፍቅር ሁሉንም ሲፈውስና ሲረዳ፥ ምኞት ሁሉንም ይጎዳል።

ፍቅር ደስታን፥ ሐሜትንና ሙሳትን ሲያመጣ፥ ምኞት ሐዘንን፥ መራርነትንና ኃፍረትን ያስከትላል።

የፍቅር ጅማሬ የእግዚአብሔር ቅዱስ ባሕርይ ሲሆን፥ የምኞት ጅማሬ የሰው የኃጢአት ተፈጥሮ ነው።

የምኞት ችግር ላጤዎች ብቻ የሚጋፈጡት ሳይሆን፥ ብዙውን ጊዜ ባለትዳሮችም የሚታወኩበት ነው። ለባለትዳሮች አንደኛው ከምኞት የማምለጫ መንገድ መደበኛ የፈቃደ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ነው (1 ቆሮ. 7:3-5)። በብዙ የአፍሪካ ባህሎች፥ ልጅ ከተወለደ በኋላ ለሁለት ዓመታት ወይም ከዚያ ለሚበልጡ ጊዜያት ሚስቶች ከባሎቻቸው ጋር የፈቃደ ሥጋ ግንኙነት ለማድረግ አይፈልጉም። ይህ ብዙ ወንዶችን ወደ ምኞትና ዝሙት ስለሚመራ፥ መልካም አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ለጸሎት ትተጉ ዘንድ ተስማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር፥ እርስ በርሳችሁ (ፈቃደ-ሥጋን) አትከላከሉ፤ ራሳችሁን ስለ አለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈትናችሁ ደግሞ አብራችሁ ሁኑ» ይላል (1 ቆሮ. 7:5)።

ሚስት ከወሊድ በኋላ ወዲያው አረግዛለሁ በሚል ፍርሃት ከባሏ ጋር የወሲብ ግንኙነት ለማድረግ ካልፈለገች፥ ከባሏ ጋር ሆና በቤተሰብ ምጣኔ ላይ ጠቃሚ ሀሳብ ሊሰጡ የሚችሉትን ክርስቲያን ሐኪሞች ማማከር ይኖርባታል። በቅድስና መውለድ ቤተሰቡንና ጋብቻውን ራሱ በብዙ መንገዶች ይረዳል።

አንዳንድ ባሎች ሚስቶቻቸውን በማፍቀር ፋንታ ምኞታዊ እርካታ ለመፈጸም ስለሚፈልጉ፥ የሚስቶቻቸውን ስሜት ይጎዳሉ። እግዚአብሔር ባሎች ሚስቶቻቸውን ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደሚወዳት አድርገው እንዲወዱአቸው አዝዞአል (ኤፌ. 5:25)፤ ይሁንና፥ ከምኞት ይርቁ ዘንድ አስጠንቅቆአቸዋል (2 ጢሞ. 2:22)። ይህም ባሎች በተለይም በወሲባዊ ግንኙነት ለሚስቶቻቸው ታላቅ ትዕግሥትና የዋህነትን ማሳየት አለባቸው ማለት ነው። ከጋብቻ በኋላም ቢሆን፥ ልክ ከጋብቻ በፊት ያደርግ እንደ ነበረው ለሚስቱ ፍቅር፥ ቸርነትና ትዕግሥት የሚያሳይ ሰው ደስተኛ ሚስት ይኖረዋል። ሚስቱን ከራስ-ወዳድነት በራቀ መንፈስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ለመውደድ ከፍተኛ ጥረት የሚያደርግ ወንድ ሚስቱ የበለጠ ምላሽ ስትሰጠውና ስትወደው ይመለከታል። ባሎች መኃልየ መኃልይ በምዕራፍ 4:1-5:4 የሚገኘውን ታሪክ ማንበብ አለባቸው፤ በዚህም ታሪክ ከብዙ ጊዜ በፊት አንድ ባል በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ለሚስቱ ያለውን ፍቅር እንዴት እንደ ገለጸ እንመለከታለን።

ላገቡ ሰዎች የምኞት ችግር በጣም ትልቅ ሊሆን ይችላል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህንን ፈተና ለመቀነስ ሊረዱ የሚችሉ ሁለት መመሪያዎች አሉ። የመጀመሪያው መመሪያ ክርስቲያኖች ዓይኖቻቸው ይመለከቱ ዘንድ በሚፈቅዱት ነገር ሁሉ ራሳቸውን መግዛት እንዳለባቸው ነው። በተለይም ወንዶች ለሚመለከቱት ነገር ስሜታውያን ናቸው። ንጉሥ ዳዊት ቤርሳቤህ ገላዋን ስታትጠብ በግየቱ ከእርሷ ጋር ዝሙት ፈጽሞአል (2 ሳሙ. 11:2)። ኢዮብ፥ «ከዓይኔ ጋር ቃል ኪዳን ገባሁ፤ እንግዲህስ ቀንጄይቱን እንዴት እመለከታለሁ?» ብሏል (ኢዮብ 31:1)። ኢየሱስ፥ «ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል» ብሏል (ማቴ. 5:28)። ክርስቲያኖች ምን ዓይነት መጽሐፍ እንደሚያነቡ፥ ምን ዓይነት ፊልሞችና ሥዕሎች እንደሚመለከቱ መጠንቀቅ አለባቸው።

ሁለተኛው መመሪያ ከሥጋዊ ዳሰሳ ጋር የተያያዘ ነው። ሰውን መዳሰስ የወንዶችንና የሴቶችን የወሲብ ስሜት ስለሚቀሰቅስ ወደ ከፋ

ፈተና ሊወስድ ይችላል። መጽሐፍ ቅዱስ፥ ወንድ ሴትን ባይነካት እንደሚሻል ይናገራል (1 ቆሮ. 7:1)። ወንዶች ከወጣት ሴቶች ጋር በሚሆኑበት ጊዜ ራሳቸውን ሊገዙ ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስ እንደ አሀቶቻቸው አድርገው እንዲመለከቱአቸው ይናገራል (1 ጢሞ. 5:1-2)። ለሰው ሚስቱ ካልሆነች ሴት ጋር በስውር ስፍራ መገኘት መልካም አይደለም።

መ. ለክርስቲያኖች ቤተሰባዊ ሕይወት የእግዚአብሔር ዕቅድ ምንድን ነው?

1. የክርስቲያን ጋብቻ ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር ሊኖራት የሚገባውን ግንኙነት ለማሳየት ምሳሌ ሆኖ አገለግሏል (ኤፌ. 5:25-32)። ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሁሉ ባልም ሚስቱን ያለ ምንም ቅድመ-ሁኔታና በፍጹም መሥዋዕትነት መውደድ አለበት (ኤፌ. 5:25)። ሚስትም ለክርስቶስ እንደምትገዛ ሁሉ ለባሏም መገዛት አለባት (ኤፌ. 5:22)። እነዚህ ሁለቱም ኃላፊነቶች ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ብቻ ነው።

2. የወላጆች ልጆችን የማሳደግ ተግባር ለልጆቻቸው በጌታ መንገዶች ደንበኛ የክርስቲያን ትምህርት መስጠትን ያካትታል (ዘፍጥ. 18:19፤ ኤፌ. 6:1፥ 4)። በዘዳግም 6:6-7 ጌታ፥ «እኔም አንተን የማዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ። ለልጆችህም አስተምረው፥ በቤትህም ስትቀመጥ በመንገድም ስትሄድ፥ ስትተኛም፥ ስትነሣም ተጫወተው» ይላል።

ልጆችን የማሠልጠንና የማስተማር ድርሻ እግዚአብሔር ለወላጆች የሰጠው ኃላፊነት ነው። ምሳሌ 1:8፥ «ልጄ ሆይ፥ የአባትህን ምክር ስማ፥ የእናትህንም ሕግ አትተው» ይላል። እግዚአብሔር ቤት ለልጅ የደህንነት፥ የፍቅር፥ የእንክብካቤ፥ የፍላጎቱ ማሟያ፥ የሥልጠናና የፍቅር መቅጫ እንዲሆን ይፈልጋል። ጌታ በጳውሎስ በኩል፥ «አባቶች ሆይ፥ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሣጽ አሳድጉአቸው እንጂ አታስቆጡአቸው» ብሏል (ኤፌ. 6:4)። ቤተሰብ ልጆች በትክክለኛው መንገድ ያድጉበት ዘንድ በእግዚአብሔር የታቀደ ልዩ ስፍራ ነው። እግዚአብሔር ሕዝቡ እርሱን የሚያውቁና የሚታዘዙ ልጆች እንዲያሳድጉ ግድ ይለዋል (ዘዳ. 4:40፤ 5:29)።

3. ክርስቲያን ወላጆች ለልጆቻቸው ፍላጎት የመጠንቀቅ ኃላፊነት አለባቸው። ይህም እንደ ምግብ፥ ልብስና ሕክምና የመሳሰሉትን ሥጋዊ ፍላጎቶች ይጨምራል። እንዲሁም፥ ለፍቅርና ለደኅንነት የሚኖሯቸውን ስሜታዊ ፍላጎቶች ያካትታል። የፍቅርና የደህንነት ፍላጎት በሙላት የሚገኘው፥ ወላጆች እርስ በርሳቸው በሚዋደዱበትና በአንድነት በሚኖሩበት ቤት ነው።

ሠ. ከአንድ በላይ ስለ ማግባት የመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት ምንድን ነው?

ከአንድ በላይ ማግባት በአፍሪካ የከፋ ችግር ነው። ከአንድ በላይ ማግባት የጋብቻን ቃል ኪዳንና ኃላፊነቶች ስለሚያካትት፥ እንደ አመንዝራነት ወይም ዝሙት አይደለም። በአፍሪካ ማኅበረሰብ ከአንድ በላይ ማግባት በመደገፍ የሚነሡ ጠንካራ ሙግቶች አሉ፦

1. በአፍሪካ ባህላዊ ማኅበረሰቦች ዘንድ ብዙ ሚስቶችን ማግባት ለአያሌ ምዕተ ዓመታት የኃይል፥ የሀብትና የዝና ተምሳሌት ሆኖ ቆይቷል። ምናልባት በብሉይ ኪዳን ነገሥታት አያሌ ሚስቶችን የሚያገቡት ለዚሁ ይሆናል? በጥንቱ ዓለም እጅግ ባለጸጋ የነበረው ንጉሥ ሰለሞን 700 ሚስቶችና 300 ቁባቶች ነበሩት (1 ነገሥት 11:3)። ይሁንና፥ የሰለሞን ብዙ ሚስቶች በመንፈሳዊ ሕይወቱ ለውድቀት ዳርገውታል (1 ነገሥት 11:3-5)።

2. በባህላዊ ኅብረተሰብ፥ ሰው የቤተሰቡን ስም ወደሚቀጥሉት ትውልዶች ማስተላለፉ አስፈላጊ ነው። ብዙውን ጊዜ አያሌ ሚስቶችን ማግባት ስሙን ለመቀጠል ብዙ ወንዶች ልጆች እንዲኖሩት ዋስትና ይሰጣል።

3. የቤተሰብን ስም ከመቀጠሉ ጋር በቅርብ የተያያዘው አሳብ፥ ብዙ ልጆችንና የልጅ ልጆችን በመውለድ አንድ ሰው ከሞተ በኋላ ለረዥም ጊዜያት እንደሚታሰብና እንደሚከበር ነው። በባህላዊ ኅብረተሰብ ውስጥ ይህ በጣም አስፈላጊ ነው።

4. በእርሻ ሥራ በሚተዳደሩ ኅብረተሰቦች ዘንድ፥ ብዙ ሚስቶችን ማግባት፥ ለግብርና፥ ለከብት እርባታና ለቤት ውስጥ ሥራ የሚያስፈልጉትን አያሌ ልጆች ለማፍራት ያስችላል። ይህም አንድ ሰው በሚታመምበት ጊዜ እንደሚሆነው፥ ችግር ሲያጋጥም አስፈላጊውን እርዳታ

መስጠትን ያጠቃልላል። ብዙ ቤተሰቦች የሚገኙበት ማኅበረሰብ የጥንካሬ ምልክት ተደርጎ ይታያል።

5. በብዙ የአፍሪካ ማኅበረሰቦች ከወሊድ በኋላ እስከ ሁለት ዓመታት ድረስ ሚስቶች የፈቃደ-ሥጋ ግንኙነት ስለማይፈጽሙ፥ ብዙ ሚስቶችን ማግባት ባል የዝሙት ተግባር እንዳይፈጽም ያደርጋል።

6. የአፍሪካ ባህል በጣም ጠንካራ የማኅበረሰብ እሴቶች ስላሉት፥ ብዙ ሚስቶችን ማግባት ሰፊ ቤተሰብን ይመሠርታል፤ ይህም በሕይወት ደስታንና ትርጉምን እንደ መጨመር የሚቆጠር ነው።

7. አንድ ሰው ብዙ ሴት ልጆችን ከወለደ፥ በጋብቻ ወቅት ከጥሎሽ በሚገኘው ገንዘብ ሀብቱ ይዳብራል።

8. በብዙ ነገዶች ለጤና ልጅ አልባ ሴት መሆን እጅግ ከፉ እንደ ሆነ ይታመናል። ከዚህም የተነሣ፥ ብዙ የአፍሪካ ሴቶች ላጤ ከመሆን ይልቅ ከአያሌ ሚስቶች አንዱ መሆንን ይመርጣሉ። በተጨማሪም፥ በላጤነት የምትኖር ሴት የዝሙት ምክንያት በመሆን በማኅበረሰቡ ላይ ኃፍረት እንደምታመጣ የሚገልጽ አሳብ አለ።

9. ከአንድ በላይ ማግባት አንድ ወላጅ ብቻ ያላቸውን እናቶች ችግር ያቃልላል።

10. ብዙ ሚስቶችን ማግባትና የብዙ ልጆች መኖር ሰውየው በሽምግልናው እንደሚጦር ያረጋግጥለታል።

እነዚህ የመጀመሪያ ነጥቦች እንደሚያመለክቱት፥ ከአንድ በላይ ጋብቻ ከባህላዊ የአፍሪካ አመለካከት አንጻር ተገቢ ይመስላል። ይሁንና፥ መጽሐፍ ቅዱስ ከአንድ በላይ ጋብቻ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳልሆነ በግልጽ ያስቀምጣል። ምንም እንኳን ከአንድ በላይ ጋብቻ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ ታላቅ ኃጢአት ሆኖ ባይቀርብም፥ በማንኛውም መንገድ እግዚአብሔር ያልደገፈው ተግባር መሆኑ ጥርጥር የለውም። ከአንድ በላይ ጋብቻ ክርስቲያናዊ ካልሆነ፥ አመለካከቱ የሰውን ምኞቶች ለማርካት የተዘጋጀ ሰው ሠራሽ ክንውን ነው። በመሆኑም፡ ለሕይወት ለሚያስፈልጉ ነገሮች እግዚአብሔርን በመተማመን በመንፈስ ከመመላለስ ይልቅ በሥጋ መመላለስን ይወክላል። መጽሐፍ ቅዱስ ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት እንደማይቻል ይናገራል (ዕብ. 11:6)።

እግዚአብሔር ለአብርሃም ልጅ እንደሚሰጠው ቃል ገብቶለት ነበር (ዘፍጥ. 15:2-4)። ይሁንና፥ አብርሃም ባለቤቱ ሣራ መካን መሆኗን እንዳየ፥ ሣራ ከግብፃዊቷ ሠራተኛዋ ከአጋር ልጅ እንዲወልድ ያቀረበችለትን አሳብ ለመቀበል ወሰነ (ዘፍጥ. 16:1-3)። ስለ ሆነም፥ አብርሃም ከባህላዊ አፍሪካ ጋር ለሚመሳሰሉ ምክንያቶች ሌላ ሚስት ወሰደ። ከዚያን ጊዜም ጀምሮ በአብርሃም ቤት ውስጥ ሰላም አልነበረም። የእግዚአብሔር ዕቅድ በተአምራዊ ሁኔታ እንጂ በሁለተኛ ሚስት በኩል ልጅ መስጠት አልነበረም (ዘፍጥ 17:15-19)። ከአጋር ልጅ የመውለድ መጥፎ ውጤቶች አብርሃም ከሞተ በኋላም ለረዥም ጊዜያት ቀጥለዋል። ዛሬ በእኛ ዘመን እንኳን በዓረቦችና በአይሁዶች መካከል የሚታየው ግጭት እንደ ቀጠለ ነው። ብዙ ጋብቻ መፈጸም የእግዚአብሔር ዕቅድ ወይም የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደ ሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ መረጃ አስደግፎ መግገት አይቻልም።

በአፍሪካም፥ ከአንድ በላይ ጋብቻን በመደገፍ ከቀረቡት የመከራከሪያ ነጥቦች ባሻገር፥ ከአንድ በላይ ጋብቻ መጥፎ ውጤቶች ከትውልድ ትውልድ በመቀጠል ላይ ናቸው። ከአንድ በላይ ከሆነ ጋብቻ በተሳሰሩ ቤተሰቦች፥ ሚስቶችና ልጆች መካከል የሚታየው የስሜት ሥቃይ፥ ቅንዓትና ውድድር፥ የዚህ ዓይነቱ ጋብቻ የግል ፍላጎትን ለማርካት የታቀደ የመሆኑን እውነት ይገልጻል። ከአንድ በላይ ጋብቻ እግዚአብሔር ሚስት የባሏን ያልተከፋፈለ ፍቅርና አትኩሮት በመቀበል የስሜትን ምልዓት እንድታገኝ የወጠነውን ዕቅድ ያከሽፋል።

አንዳንድ ለዘብተኛ የሥነ-መለኮት ምሁራን፥ የብዙ ጋብቻ ለአፍሪካ ባህል አስፈላጊ ማስተናገጃ እንደ ሆነ ያስባሉ። ለዚህ አሳብ በሚሰጠው ምላሽ፥ የብዙ ጋብቻን በመደገፍ የሚቀርቡ ባህላዊ ምክንያቶች ክርስቲያናዊ ያልሆኑ እሴቶች እንደሚያስተናግዱ ማመልከቱ ተገቢ ነው። ክርስትያናዊ ያልሆኑ ባህላዊ እምነቶች የእግዚአብሔርን ፍርድ እንጂ በረከት አያመጡም። ለምሳሌ ክብርን መሻት በባህሉ የተደገፈ ቢሆንም፥ እንደ እውነቱ ግን እግዚአብሔር ለሚጠላው የትዕቢት ኃጢአት መጋለጥ ነው (ምሳሌ 16:5፤ 21:4)። ወደፊት በሚመጡት ትውልዶች ዘንድ ስለ አንድ ሰው ስም መቀጠልም ተመሳሳይ አሳብ መናገር ይቻላል። ባህላዊ የአያት ቅድማያት እምነቶች ሰዎችን በኢየሱስ ክርስቶስ ካለው እምነት ያርቃሉ እንጂ አያቀርቡም። የጥሎሽን ገንዘብ መቀበልም ራሱ ሌላው

እግዚአብሔር የሚጠላው የስግብግብነት ኃጢአት ነው (ኢሳ. 57:17፣ ሉቃ. 23:25)።

ጋብቻን ለመደገፍ የቀረቡት አብዛኛዎቹ የመከራከሪያ ነጥቦች፣ ክርስቲያናዊ ባልሆነ አመለካከት ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ሰፊ ቤተሰብ መመሥረት በረከት እንደ ሆነ የሚያስረዳ አሳብ ቢኖርም በመጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ መገለጽ ብርሃንነት መታየት አለበት። አምን፣ መጽሐፍ ቅዱስ ሰፊ ምድራዊ ቤተሰብ በረከት ሊሆን እንደሚችል ያመለክታል [መዝ. (127):4-5]። ይሁንና፣ ይህ በረከት ሰዎች እግዚአብሔር ለጋብቻ ያቀደውን ፈቃድ ሲያበላሹ የሚመጣ አይደለም። በረከት ባሎች ተጨማሪ ሚስቶችን በማግባት የሚስቶቻቸውንና የልጆቻቸውን አንድነትና ሰላም ሲያደፈርሱ የሚመጣ አይደለም። ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚመጣውንና በሁኔታ የማይገደበውን በረከት የሚያስገኘው ማኅበረሰብ ሰፊ ምድራዊ ቤተሰብ ሳይሆን፣ ዳሩ ግን ሰፊ ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ቤተሰብ የሆነው ማለትም ቤተ ክርስቲያን ነው።

ግብረ-ገብነትን በማሻሻል ላይ የተመሠረተው የመከራከርያ ነጥብ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ነው። በእርግጥ ምግባረ ብልሹነት ስሕተት ነው፤ ይሁንና፣ ብዙ ጋብቻ መፈጸም ለችግሩ እግዚአብሔር የሰጠው መፍትሔ አይደለም። መፍትሔው በአንድ ባልና በአንዲት ሚስት መካከል የሚፈጸም መደበኛ ወሲባዊ አንድነት ነው። ሚስት ይህንን አሳብ ከተቃወመች፣ ባል ከቤተክርስቲያን መሪዎች ወይም ከሕክምና አዋቂዎች ማስተዋል የታከለበትን ምክር ሊጠይቅ ይገባዋል። ዝሙትን በተመለከተ ባጠቃላይ እውነታው አንድም ሆነ ብዙ ሚስቶች ቢኖሩአቸው አያሌ ወንዶች ዝሙት መፈጸማቸውን እንደሚቅጥሉ ነው። የምኞት ችግር በብዙ ጋብቻ ሊቃለል አይችልም። አንድ ሰው ዝሙት ከፈጸመ በኋላ የዝሙት ተግባሩን ሕጋዊ ለማድረግ፣ በኋላ ሴቲቱን በሚስትነት የሚወስድባቸው አያሌ ገጠመኞች አሉ። ንጉሥ ዳዊት ምንም እንኳን ብዙ ሚስቶች ቢኖሩትም፣ ይህንኑ አድርጓል፤ ለዚህም ለኃጢአቱ እግዚአብሔር ዳዊትን ኮንኖታል (2 ሳሙ. 11:26-27)።

ዳግም የተወለደውንና ከአንድ በላይ ሚስቶች ያሉትን አባወራ፣ የመጀመሪያዋን ሚስቱን አስቀርቶ የተቀሩትን እንዲፈታ መጠየቅ፣ ከአንድ በላይ ጋብቻ ለሚያስከትለው ችግር ክርስቲያናዊ መፍትሔ አይደለም። ይህ ለሚስቶቹ እንክብካቤ ለማድረግ ቃል ኪዳን ለገባው ባል ፍትሐዊ ያልሆነና ኃላፊነት የጎደለው ጠባይ ይሆናል (ዘኁ. 30:1-2፣ 16)። ይልቁንም፣ መፍትሔው እግዚአብሔር በራሱ ፍጹም መንገድ ነገሮችን

እንዲያከናውን፥ የአጥቢያ ቤተክርስቲያን መጋቢዎችና ሽማግሌዎች በጸሎት መደገፍና በምክር መርዳት ነው። ሰዎችን በማያስፈልግ ሁኔታ የማይጎዳ መፍትሔ ሊያመጣ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ለጸሎት ምላሽ በመስጠት ችግሩን ሊያቃልል የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። የእግዚአብሔር መንገድ ለተግባራዊነት ብዙ ጊዜ ሊወስድ ቢችልም፥ መፍትሔዎቹ ሁልጊዜም ርኅራኄና ፍጹምነት የተካተተባቸው ናቸው። ብዙ ሚስቶች ያሉት ሰው ላለበት ሁኔታ የእግዚአብሔርን ምላሽ ያገኘ ዘንድ ጸሎትና ትዕግሥት ብቸኛ መንገዶቹ ናቸው።

ከአንድ በላይ ጋብቻ ከመፈጸም ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለማቃለል በጣም ከባድ ነው። ይህም ገና ላላገቡት ማሰጠንቀቂያ ሊሆን ይገባል። ለወንድ ከአንድ በላይ ሚስቶችን መውሰድ ትልቅ ስሕተት ነው።

ብዙውን ጊዜ ወደ ክርስቶስ የተመለሰ ባለ ብዙ ሚስቶች ግለሰብ ጥምቀት መውሰድ ይኖርበት እንደ ሆነ ይጠየቃል። ለጥያቄው ምላሽ የሚሰጠው ስለ ጥምቀት ፍች መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን ከማገናዘብ ነው። ጥምቀት አንድ ሰው የክርስቶስ አካል ክፍል እንደ ሆነ የሚያመለክት ይፋዊ ምስክርነት ነው። ወደ ክርስቶስ ከመመለሱ በፊት ዘማዊ፥ አመንዝራ ወይም ሌባ ለነበረ ሰው ጥምቀትን እንከለክል ይሆን? በፍጹም አይከለክልም (1 ቆሮ. 6:9-11)። እንዲህ ዓይነት ግለሰቦች ሁሉ እውነተኛ ንሰሐ ገብተው በክርስቶስ ካመኑ፥ አዲስ ፍጥረት ናቸውና ሊጠመቁ ይገባል (2 ቆሮ. 5:17)። የባለ ብዙ ሚስቶችም ሁኔታ ከዚህ የተለየ አይደለም። አንድ ሰው ከጋጢአቱ ንስሐ ገብቶ ክርስቶስን ጌታውና መድኃኒቱ አድርጎ ሲቀበል፥ ከአንድ በላይ ጋብቻን ጨምሮ የቀደሙ ኃጢአቶች ሁሉ ይቅር ይባላሉ (ቆላ. 2:13፤ 1 ዮሐ. 2:12)።

ምንም እንኳን የውኃ ጥምቀት ሊወስድ ቢችልም፥ ብዙ ሚስቶች ያሉት ሰው በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከቶውንም ሽማግሌ ወይም ዲያቆን ሊሆን አይችልም። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ኤጲስ ቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፤ የማይነቀፍ፥ የአንዲት ሚስት ባል» (1 ጢሞ. 3:2)። በኋላም ሐዋርያው፣ «ዲያቆናት . . . አያንዳንዳቸው የአንዲት ሚስት ባሎች ይሁኑ» ብሏል (1 ጢሞ 3:12)። ይህም የሆነው እግዚአብሔር በጋብቻ አንድ ወንድ ለአንዲት ሴት የሚለው ዕቅድ በቤተክርስቲያን መሪዎች ሕይወት በትክክል እንዲታይ ስለሚፈልግ ነው።

ከደኅንነት በኋላ ያለው ከአንድ በላይ ጋብቻ ጉዳይ በጣም የተለየ ነው። ከአንድ በላይ ጋብቻ የእግዚአብሔር ፈቃድ ስላልሆነ፥ ለክርስቲያን

ሁለተኛ ሚስት ማግባት በግልጽ የዓመፅ ተግባር ነው። ይህ ኃጢአት ስለ ሆነ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ልታስወግደው ይገባል። እግዚአብሔር ለአንድ ወንድ እንዲት ሚስት ብቻ እንድትኖረው ይፈልጋል። ሁለተኛ ሚስት የሚያገባ ክርስቲያን በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀጣ ይገባል (1 ቆሮ. 5:11-13)።

ረ. እግዚአብሔር ስለ ፍች ምን ይላል?

ከአንዲት ሚስት በላይ ማግባት ሕጋዊ ባልሆነባቸው አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ፥ ዝሙትና አመንዝራነት ወደ ፍች ይመራል። ብዙውን ጊዜ የተፋቱት ሰዎች ከዝሙት ሽርኮቻቸው ጋር ይጋባሉ። በአንድ ጊዜ በአንድ ቤት ውስጥ የተለያዩ ሚስቶችን ካለማስተናገዱ በቀር፥ ይህ ከአንድ በላይ ጋብቻ ጋር የሚመሳሰል ነው። ይሁንና፥ ብዙውን ጊዜ ፍች ከብዙ ጋብቻ በላይ ለተጎዳው ባል ወይም ሚስት የስሜት ሥቃይን ያስከትላል፤ ይህም የሚሆነው ባል ወይም ሚስት ሌላ ሰው በመምረጥ የቀድሞ ፍቅራቸውን ስለሚተው ነው። ፍች ለልጆችም ከፍተኛ ሥቃይ ነው።

እግዚአብሔር ፍችን ይጠላል (ሚል. 2:16)። ፍች እግዚአብሔር ለጋብቻና ለቤተሰብ የወጠነውን ዕቅድ ያጠፋል። የወላጆቻቸው ፍቅር ወደ ጥላቻ ሲመለስና በመጨረሻም ሲፋቱ የሚመለከቱ ልጆች በሕይወታቸው በጥልቀት ይጎዳሉ። ብዙውን ጊዜ በጋብቻ ላይ መራራና አሉታዊ አመለካከት ሲኖራቸው፥ በሁሉም ሰው ይበሳጫሉ። በቤት ውስጥ ፍች ሲካሄድ ይበልጥ የሚጎዱት ልጆች ናቸው። ልጆች የዚህ ዓይነት ዝቅተኛ የጋብቻ አመለካከት ስለሚኖራቸው፥ በወላጆቻቸው የተመለከቱትን ተመሳሳይ ዝሙትና ፍች ይደግማሉ።

ምንም እንኳን እግዚአብሔር ፍችን ቢጠላም፥ ፍች እንደሚፈጸም ያውቃል። ከሰዎች ጋር ባሉበት ስፍራ ሁሉ ይገናኛል። ሌሎችን ኃጢአቶች ይቅር እንደሚል ሁሉ እግዚአብሔር ይህንንም ኃጢአት ይቅር ይላል [መዝ. (103):3]።

ፍች በዓለማችን በተለይም በትላልቅ ከተሞች ከፍተኛ ችግር በመሆን ላይ ይገኛል። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው ጋብቻን የዕድሜ ልክ ቃል ኪዳን ለማድረግ የሚፈቅዱ ሰዎች በጣም ጥቂት ናቸው (ማቴ. 19:6)። በአሁኑ ጊዜ በሰሜን አሜሪካ፥ ፍች ከዕድሜ ልክ ጋብቻ ይበልጥ እየተዘወተረ መጥቷል። የዚህ ዘይቤ ውጤት በአፍሪካ ሁሉ በመዘውተር

ላይ ይገኛል፤ ይህም የሆነው ብዙ አፍሪካውያን በዝሙትና ፍች የተሞሉትን የአሜሪካ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ስለሚመለከቱ ነው።

ብዙውን ጊዜ ወጣቶች ከቤተሰብ አካባቢ ሲርቁ፥ ሥነ-ምግባራዊና መንፈሳዊ እሴቶቻቸውን ያጣሉ። በመሆኑም፥ ወሲባዊ ግድፈትንና ዝሙትን ሊፈጽሙ ይችላሉ። እነዚህ ደግሞ ጋብቻን ለፍች የሚዳርጉ ኃጢአቶች ናቸው።

የትዳር ጓደኛው ታማኝ ሳይሆንለት ሲቀር እግዚአብሔር ሰው ምን እንዲያደርግ ይፈልጋል? እግዚአብሔር ሰዎች እርስ በርሳቸው ይቅር እንዲባባሉ ይፈልጋል (ቆላ. 3:13)። ንስሐ መግባት፥ ይቅርታና የፈራረሱትን የሰው ልጆች ግንኙነቶች ማደስ፥ ሁልጊዜም የእግዚአብሔር ፍጹም ፈቃድ ነው። ጴጥሮስ ኢየሱስን፥ «ጌታ ሆይ፥ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ልተውለት? እስከ ሰባት ጊዜን? አለው፤ ኢየሱስ እንዲህ አለው፦ እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ አልልህም» (ማቴ. 18:21-22)። ይህ የይቅርታ መመሪያ በሆሴዕ ሕይወት ውስጥ ሊታይ ይችላል። ምንም እንኳ ጋለሞታ ብትሆንና ብዙ ጊዜም ሆሴዕን ብትከዳውም፥ እግዚአብሔር ታማኝ ያልሆነች ሚስቱን ጎሜርን ዳግም እንዲወስዳት ነግሮታል (ሆሴ. 3:1-3)።

ችግሮች በጋብቻ ውስጥ

በጋብቻ ውስጥ ታማኝነትን ከማጉደል በተጨማሪ፥ ሌሎችም ብዙ ችግሮች አሉ። ከሁሉም የሚልቁ ችግሮች የሚከሰቱት በመዋለ ንዋይ አለመስማማት፥ ለተስፋፋው ቤተሰብ (ዘመድ አዝማድ) በሚሰጥ ታማኝነት ውጥረት፥ በባህላዊ ልዩነቶችና በነገሮች ላይ ካለመወያየት ነው። አብዛኛዎቹ የጋብቻ ችግሮች ሁለት ገጽታዎች አሉአቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኘው አስገራሚ ጥቅስ፥ «በአደባባይ በመጀመሪያ ቀርቦ የሚናገር ሰው፥ ተከራካሪው መጥቶ ጥያቄ እስኪያቀርብለት ድረስ፥ ዘወትር እርሱ ብቻ ትክክል የሆነ ይመስለዋል» ይላል (ምሳሌ 18:17 – ከ1980 ዓ. ም. አዲስ ትርጉም)። ይህ በብዙ የጋብቻ ክርክሮች ውስጥ እውነት ነው። አንደኛው በትዳር ጓደኛው እጅግ እንደ ተበደለ አድርጎ ሊያስብ ይችላል። ይሁንና፥ ጠቅላላው ታሪክ ሲገለጽ መልካም መስተንግዶ ያልተደረገለት ሰው ሌላውን ፍቅር በመንፈግ፥ በሚጎዱ ቃላት ወይም በሞካኔ ባሕርይ ይጎዳዋል።

የጋብቻን ችግር ለመፈውስ የሚረዳ መድኃኒት አለ። ይህም መድኃኒት ሁለት ክፍሎች አሉት። ሁለቱ ክፍሎች ፍቅርና ይቅርታ ይባላሉ። ምሳሌ 10:12፥ «ፍቅር ግን ኃጢአትን ሁሉ ትከድናለች» ይላል። ቆላስይስ 3:13-14፥ «ማንም በባልንጀራው ላይ የሚነቅፈው ነገር ካለው፥ ይቅር ተባባሉ፤ ክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ፤ በእነዚህም ሁሉ ላይ የፍጻሜ ማሰሪያ የሆነውን ፍቅርን ልበሱት» ይላል።

ሰ. የትዳር ጓደኛ ስለ መምረጥ አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያዎች ምንድን ናቸው?

በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ ከቀረበው ታሪክ ውስጥ፥ የትዳር ጓደኛን ስለ መምረጥ አንዳንድ ጠቃሚ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያዎች እናገኛለን። የአብርሃም ዋንኛ የቤቱ አለቃ የነበረው ኤልዔዘር፥ ከአብርሃም በተቀበለው ትእዛዝ መሠረት ለይስሐቅ ሚስት ሊፈልግለት መጣ። ኤልዔዘር በሳል ሰው ነበር። አንዲት ሚስት ሊኖራት የሚገባት ዋንኛ ነገር መልካም ባሕርይ እንደ ሆነ ያውቅ ነበር። ኤልዔዘር እግዚአብሔር ጸሎትን እንደሚመልስ ያምን ነበር። በጣም በጣም ግስተዋል የታከለበት ጸሎት አቅርቦአል። በጸሎቱም፥ «ውኃ እጠጣ ዘንድ እንስራሽን አዘንብይ የምላት እርስዋም፦ አንተ ጠጣ፥ ግመሎችህንም ደግሞ አጠጣለሁ የምትለኝ ቆንጆ፥ እርስዋ ለባሪያህ ለይስሐቅ ያዘጋጀሃት ትሁን» ብሏል (ዘፍጥ. 24:14)።

የኤልዔዘር ጸሎት እግዚአብሔር ተባባሪ፥ ረዢ፥ ለጋስና ትጉ ሠራተኛ ወደ ሆነች ልጅ እንዲመራው የጠየቀበት ነበር። እነዚህ ብቃቶች የሴላት ልጅ «ውኃ አጠጪኝ» ስትባል ለግመሎች ጭምር ለመቅዳት እንደማትፈልግ ግልጽ ነው። ርብቃ ግመሎቹ ገና ከሩቅ አገር መድረሳቸው እንደ ሆነ ታውቅ ነበር። ግመሎች ብዙ ውኃ ስለሚጠጡ፥ ጥማታቸውን ለማርካት አድካሚ ሥራ ሳይጠይቅ አልቀረም። ኤልዔዘር ለይስሐቅ ሚስት ሲፈልግ የሚከተሉትን መመሪያዎች ተጠቅሟል፦

1. ከሕዝቦች መካከል የአብርሃም ዓይነት እምነት የነበራት ልጅ ፈለገ። የግያምኑትን ሴቶች ለመምረጥ አልፈለገም ነበር (ዘፍጥ. 24:3)።
2. በጸሎት የእግዚአብሔርን ምሪት ፈለገ (ዘፍጥ. 24:12-14)።
3. ግሩም ባሕርይ ያላትን ልጅ ፈለገ (ዘፍጥ. 24:14)።

4. በባህል ከአብርሃም ጋር ከሚቀራረቡ ሰዎች ሚስት ፈለገ (ዘፍጥ. 24:3-4)።

5. እግዚአብሔር ለይስሐቅ ልዩ ሴት እንዳዘጋጀለት ያምን ነበር (ዘፍጥ. 24:14)።

6. እግዚአብሔር ወደ ትክክለኛዋ ልጅ እንደሚመራው ያምን ነበር (ዘፍጥ. 24:14)።

7. በሁኔታዎች ውስጥ የጸሎቱን መልስ በንቃት ይጠብቅ ነበር (ዘፍጥ. 24:17-21)።

መልካም የትዳር ጓደኛ ለመምረጥ ሌሎችም አስፈላጊ መሥፈርቶች አሉ። እነዚህ ተመሳሳይነት በሚለው ቃል ሊጠቃለሉ ይችላሉ። ከሚያገባው ሰው ጋር ይበልጥ ተመሳሳይነት ያለው ሰው፥ ብዙም ለማስተካከል የሚቸግረው ነገር አይኖረውም።

ከሌላ ነገድ፥ ከሌላ ብሔር፥ ከሌላ ቋንቋ ወይም ከሌላ ዘር ጋብቻ መመሥረት ኃጢአት አይደለም። ይሁንና፥ በሁለቱ የተለያዩ ባለ ትዳሮች መካከል ከእነዚህ ዓይነት ልዩነቶች አንድ ወይም ከዚያ የሚበልጥ ነገር ካለ፥ ተስማምቶ መኖሩ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተገለጸውን ዓይነት አንድነት ለማግኘት፥ ባልና ሚስት ከተመሳሳይ ባህሎችና እሴቶች ቢመጡ መልካም ነው። ከመንፈሳዊ ጋብቻ አስፈላጊ ዓላማዎች አንዱ በአንድ አሳብ መስማማት ነው (ፊልጵ. 2:2)። በትዳር ጓደኛሞች መካከል ከፍተኛ ልዩነት ካለ፥ በአንድ አሳብ መስማማቱ ከባድ ሊሆን ይችላል። አብርሃም ኤልዔዘርን ከራሱ ወገን ለይስሐቅ ሚስት እንዲፈልግ በመጠየቁ የጥበብ ተግባር አከናውኗል (ዘፍጥ. 24:3-4)።

የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ሰዎች ቢጋቡ ምን እንደሚፈጠር አስብ። እርስ በርሳቸው ሊግባቡ የሚችሉት ለአንዳቸውም ልብ በማይደርስ ምስተኛ ቋንቋ ነው። ይህም ካልሆነ አንደኛው የሌላውን ቋንቋ የግድ በሚገባ ማወቅ አለበት። እነዚህ መፍትሔዎች ሁለቱም ከሁሉም የተሻለ ዓይነት ግንኙነት አይፈጥሩም። በጋብቻ ወቅት ከማንኛውም ሌላ ሰብአዊ ግንኙነት በላይ፥ በጋብቻ እርስ በርስ በአሳብ መረዳዳትና ወደ ልብ ዘልቆ በሚሰማ ሁኔታ አሳብን መገላለጽ አስፈላጊ ነው።

አንድነትን ለመጠበቅ ከሚያስቸግሩት ሌሎች ልዩነቶች መካከል አንዳንዶቹ፥ የተለያዩ የሕይወት ዓላማዎች፥ ሰፊ የዕድሜ ልዩነት (በተለይም ሴቲቱ በብዙ የዕድሜ ልዩነት የገፋች ከሆነች)፥ የትምህርት

ደረጃ ልዩነት (በተለይም ሚስት በትምህርታ ከበለጠች)፥ በገንዘብ ላይ የሚኖር የተለያየ አመለካከት፥ የባሕርይ (ሰብእና) መለያየት ናቸው። ይህም ሆኖ፥ እነዚህ ልዩነቶች ካሉ ጋብቻ መፈጸም አይቻልም ማለት አይደለም። ይልቁንም፥ በባልና ሚስት መካከል አያሌ ግዙፍ ልዩነቶች ካሉ፥ አንድነት ያለው ግንኙነት ለመመሥረት የበለጠ መትጋት ይኖርባቸዋል።

ሸ. ክርስቲያን ባለትዳሮች የመካንነትን ችግር እንዴት ይወጣሉ?

ጆንና ባለቤቱ ሊድያ በእምነት ክፍላቸው በመጋቢነት ጌታን ለማገልገል የሚፈልጉ የተሰጡ ክርስቲያኖች ነበሩ። ጆን በመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ተማሪ ነበር። እርሱና ባለቤቱ ልድያ ለ12 ዓመታት በጋብቻ ተሳስረው የቆዩ ሲሆን፥ ምንም ልጅ አልወለዱም ነበር። የጆን ጎረቤቶች ልድያ የሌላ ነገድ አባል በመሆኗ እንዳያገባት ጆንን ብዙ ጊዜ አስጠንቅቀውት ነበር። በኋላም እርግማን ያለባት በመሆኑ፥ ልድያ ልጅ እንደማትወልድ ያስገነዝቡት ጀመር። እያንዳንዱ ዓመት ባለፈ ቁጥር፥ ልድያ የበለጠ ስትጨነቅ፥ ጆንም ይብልጥ ቁጡና ተናዳጅ እየሆነ መጣ። እስቲ አንተስ ከእግዚአብሔር ቃል ጆንንና ልድያን እንዴት ትመክራቸዋለህ? ክርስቲያን ባለትዳሮች የመካንነትን ችግር እንዴት ሊወጡት ይገባል?

በአፍሪካ ብዙው የልጅ አልባነት ስሜታዊ ሥቃይ ከባህላዊ የልጅ እሴት ጋር የተያያዘ ነው። ከእነዚህም እሴቶች አንዳንዶቹ የክርስቲያን አሳቦች አይደሉም። ብዙዎቹ የአፍሪካ ባህሎች በጣም ጠንካራ የማኅበረሰብ ስሜት አላቸው። ልጆች ለአንድ ሰው ቤተሰብ መቀጠልና በመንፈሳዊ ዓለም ለሚኖረው ትውልዳዊ ደረጃ አስፈላጊዎች እንደ ሆኑ ይታመናል። በአንዳንድ ባህሎች እነዚህ እሴቶች በጣም አስፈላጊዎች በመሆናቸው ባል ወንድ ልጅ አስኪያገኝ ድረስ ልጅ እንደሌለው ይናገራል።

በአንዳንድ ባህሎች፥ ዘላለማዊ ሕይወት ማለት ፍጻሜ የሌለው የአንድ ሰው የቤተሰብ ሐረግ ቅጥያ ማለት እንደ ሆነ ይታመናል። በእንደዚህ ዓይነት ባህሎች፥ ልጅን መውለድ ሃይማኖታዊ ጠቀሜታ ይኖረዋል። እንዲህ ዓይነት ባህሎች ባለትዳሮች ልጅ ካልወለዱ በእግዚአብሔር የተረገሙ እንደ ሆኑ ያምናሉ። እነዚህ ስለ ልጅ አልባነት የሚቀርቡ ባህላዊ አሳቦች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኙም። ይሁንና፥ ከእንደዚህ ዓይነት ማኅበረሰብ የሚመጡ ክርስቲያኖች እውነቱን ሳይገነዘቡ በሕዝባቸው እምነት ሊለወጡ ይችላሉ። ልጅ በማይወልዱበት ጊዜ መራራና ቁጡ የሚያደርጋቸው ይኸው ተጽዕኖ እንጂ የእግዚአብሔር ቃል

የሚያስተምረው እውነት አይደለም። ባለትዳሮቹ ጌታን በታማኝነት ለመከተል የሚፈልጉ ከሆነና በሕይወታቸውም ውስጥ የተሰወረ ኃጢአት ከሌለ፥ በእግዚአብሔር ተረግመዋል ማለት አይደለም። እንደዚህ የመሳሰሉ ገጠመኞች ሲኖሩ፥ ክርስቲያን ባለትዳሮች በሕዝባቸው ባህላዊ እምነቶች ላይ ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ቃል ዘላለማዊ እውነት ላይ መደገፍን መማር አለባቸው። እነዚህ ሁለት የእምነት መንገዶች፥ የልጅ አልባነትን ጉዳይ በጣም በተለያየ ሁኔታ ይመለከታሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ እንደ ሆኑ ይናገራል [መዝ. (127):3]። ይሁንና፥ ልጅ አለመውለድ በእግዚአብሔር መረገም እንደ ሆነ የሚናገረው አሳብ ሐሰት ነው። በተጨማሪም፥ ዘላለማዊ ሕይወትን ልጅ ከመውለድ ጋር ማያያዝ ክርስቲያናዊ ያልሆነ አሳብ ነው። ለብዙዎቹ ሰዎች እግዚአብሔር የልጆችን ስጦታ ይሰጣል። ይሁንና፡ እግዚአብሔር ልጅ የሚነፍጋቸው ሰዎች አሉ፤ ይህም የሚሆነው፥ ለእነርሱ ልጅ መውለድ በረከት እንደማይሆን ስለሚያውቅ ነው። መዝሙር (84):11፥ «እግዚአብሔር አምላክ ምሕረትንና እውነትን ስለ ወደደ፥ ሞገስንና ክብርን ይሰጣል፤ እግዚአብሔር በቅንነት የሚሄዱትን ከመልካም ነገር አያሳጣቸውም» ይላል።

ሌላው ሰው እንደ ረገማቸው የሚያምኑበት ምክንያት ካላቸው፥ ክርስቲያን ባለ ትዳሮች እንዲህ ዓይነቱን እርግማን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የማፍረስ ሥልጣን አላቸው (ሉቃ. 10:19፤ 1 ዮሐ. 4:4)። በሁሉም ሁኔታ ውስጥ፥ እግዚአብሔር ልጅ እንዲሰጣቸው በጸሎት ሊጠይቁ ይችላሉ። ይስሐቅ ልጅ ላልነበራት ሚስቱ ለርብቃ ያደረገው ይህንኑ ነበር (ዘፍጥ. 25:21)። ልጅ ያልነበራት የሕልቃና ሚስት ሐናም ያደረገችው ይህንኑ ነበር (1 ሳሙ. 1:10-16)።

ከጸለየም በኋላ እግዚአብሔር አሁንም ለክርስቲያን ባለትዳሮች ልጅ ከከለከለ፥ እርሱ ምክንያት አለው። ምናልባት ለእነዚህ ሰዎች ልጅ መውለድ መልካም እንደማይሆን ስለሚያውቅ ይሆናል። ምናልባትም ሚስት በወሊድ በመሞት የባሏን ልብ እንደምትሰብር ስለሚያውቅ ይሆናል። ለእነዚህ ሰዎች የሚወለደው ልጅ ታሞ እንደሚሞት፥ የከፋ በሽታ እንደሚኖርበት ወይም አካለ-ስንኩል እንደሚሆን ስለሚያውቅ ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር ልጆቹን ኣላስፈላጊ ከሆነ ሕመምና ሥቃይ ለመጠበቅ ስለሚፈልግ፥ ለሚጸልዩ መንፈሳዊ ባለትዳሮች ልጅ ሊነሣቸው ይችላል። እግዚአብሔር ልጅን የማይሰጥባቸው ሌሎችም ምክንያቶች

ሊኖሩ ይችላሉ። እግዚአብሔር ልጅ ከከለከላቸው ባለትዳሮች ምን ማድረግ አለባቸው?

ምናልባት እግዚአብሔር ልጅ የከለከላቸው ወላጅ የሌለውን ልጅ እንዲያሳድጉ ስለሚፈልግ ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለመበለትና ወላጅ ለሌላቸው ልጆች እንደሚራራ ብዙ ይናገራል (ዘዳ. 14:29፤ 24:19-21)። ባለትዳሮች ከአብራካቸው የወጡ ልጆች ካሉአቸው፥ ወላጅ የሌላቸውን ልጆች ለማሳደግ አያስቡም ይሆናል። በአንዳንድ ባህሎች፥ ከባህላዊ እምነቶች ሳቢያ መንታዎች ክፉ እንደ ሆኑ ይታመናል። በእነዚህ ማኅበረሰቦች ውስጥ መንታ ልጆች ሲወለዱ፣ አንድም መገደል አሊያም መጣል ዕጣ-ፈንታቸው ይሆናል። ክርስቲያን ባለትዳሮች የተጣለውን ልጅ በመውሰድና ክርስቲያናዊ ቤት በመስጠት ግሩም ክርስቲያናዊ አገልግሎት ሊያበረክቱ ይችላሉ።

ከጥቂት ዓመታት በፊት አንድ ሚሲዮናዊ ዶክተርና ባለቤቱ አካለስንኩላን ልጆች ለማሳደግ ወሰኑ። በዚህም መሠረት ሦስት ልጆች አሳደጉ። ለእነዚህም ልጆች አፍቃሪ ክርስቲያናዊ ቤት ሰጡአቸው። ሌላው ሚሲዮናዊ ዶክተር በከተማ ውስጥ ከሚገኝ የቆሻሻ መጣያ ያልተፈለገችውን ልጅ አተረፈ። ለዚህች ልጅ አፍቃሪ ክርስቲያናዊ ቤት ሰጥተው ስላሳደጉአት፥ አሁን ከዩኒቨርስቲ ተመርቃለች። ለልጅ አልባነት ግደነ በጣም ግሩም ክርስቲያናዊ መፍትሔ ነው።

ማጠቃለያ

ጋብቻ በዓለም ባህሎች ሁሉ ውስጥ በተለያየ መልኩ ይከናወናል። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ፥ ጋብቻ የመጀመሪያው የሰው ማኅበራዊ ተቋም ነው። የሰውን ልጅ ወንድና ሴት አድርጎ በፈጠራቸው ጊዜ፥ ጋብቻን ያቀደውና የመጀመሪያውን ጋብቻ ያከናወነው ራሱ እግዚአብሔር ነበር። ለሰዎች ሁሉና በዓለም ለሚገኙ ባህሎች ሁሉ፥ እግዚአብሔር የወጠነው የጋብቻ ዕቅድ ምንድን ነው?

እግዚአብሔር አንድ ወንድ አንዲት ሴት ሉሕይወት ዘመን የታማኝነት፥ የፍቅር፥ የኅብረት፥ የብርታት፥ የድጋፍ፥ የደስታና የጋራ እርዳታ ቃል ኪዳን በመግባት እንዲያገባት ዐቅዷል። እንደ ብዙ ጋብቻ ያሉ ሌሎች የጋብቻ ዓይነቶች የሰው አሳብ እንጂ የእግዚአብሔር ፈቃድ የሌላቸው ናቸው። ፍቾ እግዚአብሔር ሰው በጋብቻ ውስጥ እንዲያገኘው ያቀደውን ፍጹም ደስታ ስለሚያጠፋ፥ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ነው። በጋብቻ ቃል ኪዳን ውስጥ ወሲብ ቅዱስ፥ ንጹሕና በእግዚአብሔር

የተባረከ ነው። ወሲብ እግዚአብሔር የልጆችን በረከት የሚገልጽበትና ለሚስቶችና ለባሎች የእርካታ መሣሪያ ነው። እንደ ዝሙትና አመንዝራነት ያሉ ከጋብቻ ውጭ የሚፈጸሙ ወሲባዊ ግንኙነቶች ሁሉ የከፉ ኃጢአቶች በመሆናቸው፥ የእግዚአብሔርን ፍርድ ያስከትላሉ።

ጋብቻ የተሳካ ሊሆን የሚችለው ባሎችና ሚስቶች የመጽሐፍ ቅዱስን ትእዛዛት በመከተል፥ እግዚአብሔር ለጋብቻ የወጠነውን ዕቅድ ሲፈጽሙ ነው። ሚስቶችን በመምራቱ በኩል ለባሎች ምሳሌ የሚሆነው ክርስቶስ ራሱ ነው (ኤፌ. 5:23)። ለባሎች በመገዛቱ በኩል ሚስቶች ሊከተሉት የሚገባው ምሳሌ ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር ያላት ግንኙነት ነው (ኤፌ. 5:24)። ባሎች ሚስቶቻቸውን ልክ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደሚወዳት አድርገው እንዲወዱአቸው ታዝዘዋል (ኤፌ. 5:25)። ይህ የአገልጋይነት፥ መሪነትና ራስን የመሠዋት ፍቅር ነው። ሚስቶች ለባሎቻቸው ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ በምትገዛው መልክ እንዲገዙ ታዝዘዋል (ኤፌ. 5:24)። የዚህ መገዛት ምሥጢሩ ለክርስቶስ ብሎ መፈጸሙ ነው። ልጆችን በማሳደጉ በኩል ወላጆች ሊከተሉት የሚገባው ምሳሌ፥ ሰማያዊ አባታችን በመሆን የሚወደን፥ የሚያስፈልገንን የሚያሟላልን፥ የሚመራን፥ የሚያስተምረንና የሚጠብቀን እግዚአብሔር አብ ነው (ኤፌ. 5:1-2)። እነዚህ ኃላፊነቶች ሙሉ ለሙሉ ሊከናወኑ የሚችሉት በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ አማካኝነት ነው።

ልጆች በጋብቻ ውስጥ የእግዚአብሔር ስጦታዎች ቢሆኑም፥ ልጅ አለመውለድ ግን ባለትዳሮቹ በእግዚአብሔር እንደ ተረገሙ አያመለክትም። ይህ አሳብ የመጣው ክርስቲያናዊ ካልሆኑ ሃይማኖቶች የሐሰት ትምህርት ነው። ልጅ በመውለዱ በኩል ችግር ካለ፥ ባለትዳሮቹ ሐኪም ማማከር አለባቸው። ልጅ ለሌላቸው ባለትዳሮች ልጅ የመውለድን ዕድል የሚያሰፋ ውጤታማና ጎጂ ያልሆነ የቤተሰብ ምጣኔ ብልሃት አለ። አራርቆ ለመውለድም ተመሳሳይ መንገድ መጠቀም ይቻላል። እግዚአብሔር ሙሉ ለሙሉ ልጅ ከከለከለ፥ ባለትዳሮቹ በእግዚአብሔር ምሪት የማደጎ ልጅ ሊፈልጉ ይችላሉ።

በምዕራፍ 16 ላይ የተመሠረቱ የመወያያ ጥያቄዎችና መልመጃዎች

1. ከእግዚአብሔር ዕይታ አንጻር ፍጹም ጋብቻን እንዴት ትገልጸዋለህ? መልስህን በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች አስደግፍ።

2. ቡድኑ ፍጹም ጋብቻ ምን እንደ ሆነ ያብራራ። ከዚያም በትናንሽ ቡድን ተከፋፍላችሁ፥ ይህንን ፍጹም ጋብቻ ለመፍጠር ሁለቱም ባልና ሚስት ምን ሊያደርጉ እንደሚችሉ ተወያዩ። እያንዳንዱ ቡድን ለባሎችና ለሚስቶች የሚሆኑትን ነገሮች መዘርዘር አለበት።

3. ባል ከሚስቱ ጋር ሊሠራ የሚችላቸውና አእምሮአዊና ስሜታዊ አንድነታቸውን ለማጠናከር የሚረዱ ነገሮች ምንድን ናቸው?

4. እግዚአብሔር ለምን ፍችን እንደሚጠላ አብራራ።

5. አራት አባላት በሚገኙባቸው ትናንሽ ቡድኖች ተከፋፈሉና በ 1ኛ ጴጥሮስ 3:7 እንደ ታዘዘው፥ ባሎች ሚስቶቻቸውን ሊያከብሩ በሚችሉባቸው መንገዶች ላይ ተወያዩ።

6. ባል ከሚስቱ ጋር የሚኖረውን መንፈሳዊ አንድነት ሊያጠናክር የሚችል ምን ተግባር ሊፈጽም ይችላል?

7. ዝሙት ለምን እንዲህ የከፋ ኃጢአት እንደ ሆነና፥ በጋብቻ ላይ ምን እንደሚያስከትል ግለጽ።

8. ጵርስቅላና አቂላ በሐዋርያት ሥራ 18 እና በአንዳንድ የጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ የተጠቀሱ ባለትዳሮች ነበሩ። በሐዋርያት ሥራ 18:26 በጋብቻቸው ውስጥ የተጠቀሰው ምን ዓይነት አንድነት ነው?

9. በጋብቻ ውስጥ የወሲብ ግንኙነት እንዴት እግዚአብሔርን እንደሚያስከብር ግለጽ።

10. አንድ ወጣት ወደ አንተ ይመጣና ከአንዲት ልጃገረድ ጋር ዝሙት እንደ ፈጸመ ይነግርሃል እንበል። ልጂቱንም እንደሚያፈቅራትና ሊያገባት እንደሚፈልግ ይገልጽልሃል። ሆኖም ልጂቱ ክርስቲያን አይደለችም። ይህንን ወጣት እንዴት ትመክረዋለህ? መልስህን ለማስደገፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ስጥ።

11. ከአንድ በላይ ሚስቶች ያሉት ሆኖ ወደ ደኅንነት ስለ መጣ ሰው ምን እንደምትል ተናገር።

12. ሦስት አባላት በሚገኙባቸው ቡድኖች ተከፋፍላችሁ፥ እግዚአብሔር ስለ ሙከራ ጋብቻዎች ምን እንደሚያስብ ተወያዩ። (የሙከራ ጋብቻ ሁለት ሰዎች ሳይጋቡ አብረው የሚኖሩበትና ለሕይወት ዘመን አብሮ መቆየት ይገባቸው እንደ ሆነ ለመወሰን የሚሞክሩበት ነው።) እያንዳንዱ ቡድን መልሱን በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማስደገፍ አለበት።

13. ባልና ሚስት ሁልጊዜም እንደሚጣሉ በመግለጽ መፍትሔ እንድትሰጣቸው ቢጠይቁህ፥ ምን ትመክራቸዋለህ? ምክርህን በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች አስደግፍ።

14. አንድ ባል ሚስቱ ከርሱ ጋር የፈቃደ-ሥጋ ግንኙነት ለማድረግ እንደማትፈልግ ቢገልጽልህ፥ በኤፌሶን 5:25 ላይ የተመሠረተ ምን ምክር ትሰጠዋለህ?

15. ከቤተ ክርስቲያንህ አንድ ሰው ወደ አንተ መጥቶ ሚስቱ ውጭ ውጭ እንደምታበዛ ቢገልጽልህ፥ ምን እንዲያደርግ ትመክረዋለህ? መልስህን በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች አስደግፍ።

16. በቤተሰብ ላይ የአፍሪካ ግንዛቤ ምን እንደ ሆነ ተወያዩ።

17. ከተለያዩ ነገዶች የተውጣጡ ሦስት ሰዎች በዝሙትና አመንዝራነት ላይ የሕዝባቸው ጥንታዊ ባህላዊ አመለካከት ምን እንደ ሆነ እንዲገልጹ አድርግ።

18. በአፍሪካ ዓውድ ("context") የባል፥ የሚስትና የልጆች ሚና ምን እንደ ሆነ ግለጽ።

SUGGESTED FOR FURTHER READING

Cornes, A.J.C. Divorce and Remariage. London: Hodder, 1993.

Huggett, Joyce. Growing Into Love. Leicester: Inter Varsity, 1982.

Kimathi, Grace. Courting In Marriage. Nairobi: Uzima, 1983.

Phypers, D. Christian Marriage In Crisis. London: Marc Europe, 1985.

Trobisch, Walter. I Married You. Leicester: Inter Varsity, 1972.

ምዕራፍ 17

የመከራና የሕመም፥ የአስማት፥ የጥንቆላና የጉቦኛነት ተያያዥ ችግሮች

በሕይወት ውስጥ ለመመለስ እጅግ የሚከብዱን እንዳንድ ጥያቄዎች አሉ። ለምን መልካም ሰዎች ይሠቃያሉ? ጎዘን የጻድቁን ቤት የሚያንኳኳው ለምንድን ነው? አንዳንድ ሰዎች ታላቅ ሥቃይ ወይም ጎዘን ሲታገሡ ሌሎች ይህንን የማያደርጉት ለምንድነው?

አንድ ወጣት ሚሲዮናዊ ገና ወደ አገሪቱ መድረሱ ነበር። ሕይወቱን ለጌታ አገልግሎት ሰጥቶ ነበርና፥ ልቡን ያሳረፈበትን አገልግሎት በመጀመሩ ደስ ተሰኘ። አንዳንድ ሰሞችንና ሰዎችን ማወቅና አንዳንድ ወዳጆችን ማፍራት ጀምሮ ነበር። አንድ ቀን ከሌላ ሚሲዮናዊ ጋር የሚያሰለች ረዥም መንገድ ይጓዝ ነበር። ድንገት አንድ የጭነት መኪና የሚሄድበትን መሥመር ስቶ ሁለቱ ሚሲዮናውያን የነበሩበትን መኪና ገጨ። መኪናውን ይነዳ የነበረው ሽምገል ያለው ሚሲዮናዊ ወዲያው ሲሞት አዲሱም ሚሲዮናዊ ሬት ለሬት ተቀምጦ ነበርና ከመኪናው ውጭ ተወረወረ። ወዲያውኑ ባቅራቢያው ወደሚገኘው ሆስፒታል ቢወሰድም፥ ሊረዱት አልቻሉም። አንገቱ ተሰብሮ ስለ ነበር፥ ከአንገቱ በታች ያለው አካሉ ሁሉ ሽባ ሆነ። ዳግም ሊራመድ ወይም እጁን ወይም እግሮቹን ሊጠቀም አይችልም ነበር። ቀሪ ዘመኑን በምስኪንነት ማሳለፍ ነበረበት።

አሁን ከብዙ ዓመታት በኋላ የአካል ስንኩላን መጓጓዣ መንበር ("wheelchair") ላይ ተጣብቆ ይገኛል። በየዕለቱ ሸአካባቢው የሚገኙትን ሰዎች እየተመለከተ «ለምን ጌታ ሆይ?» ሲል ይጠይቃል። እግዚአብሔር እርሱን ለማገልገል ሕይወቱንና ብርታቱን በሰጠው ወጣት ላይ እንዲህ የከፋ ነገር እንዲደርስ ለምን ፈቀደ?

በዚያን ጊዜ ለዚህ ጥያቄ የተገኘ ምላሽ አልነበረም፤ ዛሬም ለዚህ ሰው የሚሆን ምላሽ አልተገኘም። ታሪኩ አትኩሮታችንን በሕይወት ውስጥ በሚያጋጥሙ እጅግ ከባድ ጥያቄዎች ላይ ያነጣጥራል። መልካምና ንጹሓን ሰዎች ብዙውን ጊዜ በመረረ ሁኔታ የሚሠቃዩት ለምንድን ነው? አንዳንዶች በታላቅ ሕመምና ጎዘን ሲሠቃዩ ሌሎች ከዚህ ነጻ የሚሆኑት ለምንድን ነው? ከእግዚአብሔር በቀር እነዚህን ጥያቄዎች ሊመልስ የሚችል ሰው የለም። ይሁንና፥ እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

የተናገረውን በማጥናት ስለ ሥቃይ ብዙ ልንማር እንችላለን። በዚህ ምዕራፍ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ እንወያያለን፦

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰው ልጆች መከራ መቀበል ምን ይላል?

ለ. የበሽታ መነሻዎች ምንድን ናቸው?

ሐ. ክርስቲያን አስማት፥ ጥንቆላ፥ ምትሐት፥ እርግማንንና ድግምትን እንዴት መቋቋም ይችላል?

መ. ክርስቲያን የጉበኛነትን ችግር እንዴት ሊመለከት ይገባል?

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰው ልጆች መከራ መቀበል ምን ይላል?

እነዚህ ጥያቄዎች የተለመዱ ናቸው። መጽሐፈ ኢዮብም በሰፊው የሚተርከው ይህን ስለ መሰለው ችግር ነው። ኢዮብ የኖረው ከአብርሃም ጋር ተመሳሳይ በሆነ ዘመን ሲሆን ከክርስቶስ ልደት በፊት 2000 ዓመታት ያህል ቀደሞ ነበር ማለት ነው። ኢዮብ ከጋጢአት የነጻ ሰው ስለ መሆኑ እግዚአብሔር ራሱ ሁለት ጊዜ መስክሮለታል (ኢዮብ 1:8፤ 2:3)። ይሁንና፥ ብቻውን ፍጹም መልካም የሆነው ራሱ እግዚአብሔር ነበር (ማቴ. 19:17)፥ በእነዚህ ሁለት አጋጣሚዎች ሰይጣን በኢዮብ ላይ ታላቅ ጉዳትና ሥቃይ እንዲያመጣ የፈቀደው (ኢዮብ 1:12፤ 2:6)።

መከራ፥ ሥቃይና የተፈጥሮ አደጋዎች ሁሉንም ሰው በከፍተኛ ደረጃ የሚያውኩ ችግሮች ናቸው። ክርስቲያኖችም ሆኑ ክርስቲያኖች ያልሆኑ ሰዎች፥ መልካም ሰዎች ሲሠቃዩና ክፉዎች ግን ደልቶአቸው ሲኖሩ ምሥጢሩን ለመረዳት ይቸገራሉ። አንዳንድ ሰዎች መከራዎችና ሥቃዮች ሁሉ እንደ ጠንቋዮችና አስማተኞች ያሉ ክፉ ሰዎች በቀጥታ የሚሰነዝሩዋቸው ነገሮች እንደ ሆኑ ያስባሉ። አንዳንዶች ደግሞ ሥቃዩ ሁሉ ከክፉ መናፍስት ወይም በሰው ሕይወት ከሚገኝ ጋጢአት እንደሚመጣ ያስባሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ብዙው መከራ ከክፉ ሰዎች፥ ከክፉ መናፍስትና ከጋጢአት እንደሚመጣ ያስተምር እንጂ፥ መከራዎች ሁሉ የሚመጡት በእነዚህ ነገሮች ምክንያት እንደ ሆነ አይገልጽም።

በዚህ ዓለም ውስጥ ነገሮች ለምን በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ እንደሚከሰቱ በትክክል ለመረዳት፥ በፍጥረት ጊዜ የተፈጸሙትን ክስተቶች መለስ ብለን ልንመለከት ይገባል። ሰውን ጨምሮ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ከፈጠረ በኋላ፥ ሁሉም እጅግ መልካም እንደ ሆነ መናገሩን

ከዘፍጥረት መጽሐፍ እንረዳለን (ዘፍጥ. 1:31)። ሆኖም በዚህ ዘመን ፍጻሜ ላይ እግዚአብሔር አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ሲፈጥር፡ ከዚያ ወዲያ ሥቃይ፥ ኀዘን ወይም ሞት እንደማይሰማ ከራእይ መጽሐፍ እንማራለን (ራእይ 21:4)። እነዚህን ሁለት አሳቦች ስናነጻጽር፥ ዛሬ በምድር ላይ የሚገኙ አሠቃቂ ሁኔታዎች እግዚአብሔር ፍጥረታትን በፈጠረበት ጊዜ ያቀዳቸው ነገሮች እንዳልነበሩ እንረዳለን።

ለዚህ ዓለም ሁኔታ ማብራርያ የምናገኘው በዔድን ገነት ሰው በእግዚአብሔር ላይ ከፈጸመው ዓመፅ ነው። የተፈጥሮ አደጋዎችን ጨምሮ በዓለም ውስጥ ለምንመለከተው ብልሹ ከንውን ሁሉ ኃላፊነቱ የሚያርፈው በኃጢአት ላይ ነው። ከውድቀት በኋላ፥ እግዚአብሔር በግዑዟ ምድር ላይ ሳይቀር የደረሰ እርግማን በሰው ልጅ ላይ አወጀ (ዘፍጥ 3:16-19)። እርግማኑም ራሷ በምድር ላይና በምታበቅላቸው ነገሮች ላይ አሠቃቂ ለውጦች እንደሚከሰቱ ነበር (ዘፍጥ. 3:17-18)። በሌላ አባባል፥ እግዚአብሔር መልካምና ለሰው ጥቅም የፈጠረው ነገር በእግዚአብሔር ላይ በተፈጸመው ኃጢአት ተበላሸ። ይህም አንድ ሰው ለሌላው ሰው ቢስክሌት ቢሰጠው፥ የተቀበለው ሰው ቢስክሌቷን በግዴለሽነትና በሚገባ ባለመንከባከብ እንደሚያበላሻት ዓይነት ማለት ነው።

በሮሜ መልእክት፥ ሐዋርያው ጳውሎስ ሰው በእግዚአብሔር ላይ ከግመፁ የተነሣ ተፈጥሮአዊው ዓለም ምን እንደ ደረሰበት ያብራራል። በምድር ላይ ስለ ወረደው መርገም ሲያብራራም፡ «ፍጥረት ሁሉ ዋጋ ቢስ እንዲሆን ተፈርዶበታል፥ ይኸውም በራሱ ፈቃድ ሳይሆን በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው» ይላል (ሮሜ 8:20 – የ1980 ዓ. ም. አዲስ ትርጉም)። ጳውሎስ በመቀጠል፥ «ፍጥረት ሁሉ እስከ ዛሬ ድረስ በምጥ ሞንቀት ተይዞ በመቃተት ላይ መኖሩን እናውቃለን» ይላል (ቁ. 22)።

በሌሎች ሰዎች እጅ የሚሠቃዩ ሰዎች እግዚአብሔር ራሱ በክርስቶስ ንጹሕ አካል ውስጥ ሆኖ በክፉዎች እጅ መከራቸውን እንዴት እንደ ተጋራ ሊያስታውሱ ይገባል። ራሱን ያቆሳሰሉ የእሾህ አክሊሎች፥ ከፊቱ ላይ የተነጩ ጸጉሮች፥ ጀርባውን የተለተለው ጅራፍ፥ የቅርብ ወዳጆቹ ክህደት ሁሉ እኛን የሚጎዱትን ያህል በሰማይ ቅዱስ አምላክ ላይ የከፋ ሥቃይ አስከትለዋል። ግንም እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ አግባብነት የጎደለውን መከራ የተቀበለ የለም። ያለ ትክክለኛ ምክንያት መራራ ሥቃይ የሚደርስባቸው ብዙ የአፍሪካ ዜጎች፥ ልክ እንደ ተራ ወንጀለኛ በመስቀል ላይ

ከተቸነከረው ቅዱስና ንጹሕ አዳኝ ጋር የጠለቀ ትስስር ሊመሠርቱ ይችላሉ።

አዳምና ሔዋን ሰይጣንን በማመን ከእግዚአብሔር ይልቅ እርሱኑ ለመታዘዝ ስለ መረጡ፥ ሰይጣንና መላእክቱ በአሁኑ ዓለም ላይ የተወሰነ ቁጥጥር ሊያገኙ ችለዋል። በኋላ ኢየሱስ ሰይጣንን የዚህ ዓለም ገዥ ብሎታል (ዮሐ. 12:31፤ 14:30)። በተጨማሪም፥ ኢየሱስ እንደ እባብና ጊንጥ የመሳሰሉ አንዳንድ የዚህ ዓለም አሠቃቂና ከፉ ሁኔታዎች (ሉቃ. 10:19)፥ በቀጥታ ከሰይጣን ኃይል ጋር የተያያዙ መሆናቸውን ገልጾአል።

ኢየሱስ በሉቃስ 10:19 ካቀረበው አሳብ እንደምንረዳው፣ እነዚህ በዓለም ውስጥ የምንመለከታቸው አሠቃቂና ከፉ ለውጦች እግዚአብሔር በመጀመሪያ ለፍጥረት ያቀዳቸው ነገሮች አልነበሩም። ሰው በእግዚአብሔር ላይ በማመፁ ምክንያት የተከሰቱ ሲሆኑ፥ ሰይጣን በዓለም ላይ ኃይል እንዲኖረው አድርገዋል። በመጽሐፈ ኢዮብ ሰይጣን አሥሩንም የኢዮብ ልጆች የፈጀ ኃይለኛ ዐውሎ ነፋስ ለማምጣት መቻሉን ለዚህ አሳብ ተጨማሪ መረጃ አድርገን ልንጠቅስ እንችላለን (ኢዮብ 1:18-19)። ስለ ሆነም፥ ከፍተኛና አጥፊ ማዕበሎችና የተፈጥሮ አደጋዎች የሰይጣን ሥራዎች ሆነው ሊገኙ የሚችሉባቸው ጊዜያት እንዳሉ ሊታይ ይችላል። ይህም የከፉ ማዕበሎች ሁሉ የዲያብሎስ ሥራዎች እንደ ሆኑ ለማመልከት አይደለም። ይሁንና፥ ሰይጣን በአየር ላይ ሥልጣን ያለው አለቃ በመሆኑ (ኤፌ. 2:2)፥ እነዚህን የመሳሰሉ ነገሮች ለማድረግ ይችላል።

ከዚህና ከሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ማጣቀሻዎች እንደምንመለከተው፥ የዚህ ዓለም ሕመም፥ ሥቃይና መከራዎች ሰው በእግዚአብሔር ላይ በማመፁ ምክንያት የተከሰቱ ናቸው። ይህ ዓመፅ ሰይጣን በአሁኑ ዓለም ላይ ኃይል እንዲያገኝ አስችሎታል። በተጨማሪም፥ በዓለም ላይ እርግማን አስከትሏል። ኢዮብ እንዳስተዋለው፥ «የአሞራ ግልገሎች ግን ወደ ላይ እየበረሩ ከፍ እንዲሉ፥ ሰው እንዲሁ ለመከራ ተወልዶአል» (ኢዮብ 5:7)።

መጽሐፈ ኢዮብ፥ ምንም እንኳን ኢዮብ ይህንን መከራ የሚያመጣውን ኃጢአት ባይሠራም፥ ሰይጣን በእግዚአብሔር ፈቃድ በሕይወቱ የፈጸማቸውን መራራ ሥቃዮች ይተርካል። ፍጹም ልዩ በሆነ ሁኔታ፥ ኢየሱስ ለ18 ዓመት ጎባጣ የነበረችውን ሴት ፈውሶአል። ኢየሱስ ሴቲቱ የአብርሃም ልጅ እንደ ሆነች በመግለጽ አይሁዳዊ እምነቷን

ከመጠቆሙም፥ ያንን ሁሉ ዘመን በሰይጣን ታስራ እንደ ነበረች አስረድቷል (ሉቃ. 13:11-16)።

ከኃጢአት የተነሣ የሚመጣውን ሥቃይ በተመለከተ፥ ኢየሱስ ለ38 ዓመታት ታሞ የነበረውን ሰው ፈውሶአል (ዮሐ. 5:5-9)። ሰውየውን ከፈወሰው በኋላ ኢየሱስ፥ «እነሆ፥ ድነሃል! ከዚህ የሚብስ እንዳይደርስብህ ወደፊት ኃጢአት አትሥራ» ብሎታል (ዮሐ. 5:14)። በዚህ ጊዜ፥ ኢየሱስ የሰውየው ኃጢአት ከበሽታው ጋር የተያያዘ መሆኑን ገልጾአል። በያዕቆብ መልእክት ውስጥ ጸሐፊው፥ «እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ፥ ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ» ብሏል (ያዕ. 5:16)። ይህም ምንባብ፥ አንዳንድ ጊዜ በተወሰነ ኃጢአትና በበሽታ መካከል ግንኙነት ሊኖር እንደሚችል ያመለክታል።

በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ አያሌ ሰዎች መከራና ሥቃይ ከክፉ መናፍስት ወይም ከኃጢአት ጋር በፍጹም እንደማይገናኝ ያስባሉ። የሚፈጸመው ነገር ሁሉ የዕድል ጉዳይ እንደ ሆነ ያምናሉ። ይህን አመለካከት በመጽሐፍ ቅዱስ ለማስደገፍ አይቻልም። ለምሳሌ፥ ኢየሱስ በማርቆስ 9:17-27 ከተጠቀሰው ልጅ አጋንንት ካስወጣ በኋላ፥ መንስዔው የጸጸትና የደንቆሮነት መንፈስ እንደ ነበር ገልጾአል (ማርቆስ 9:25)። አጋንንቱ ከወጡለት በኋላ የልጁ መፈወስ፥ በአጋንንት መንስዔ ታሞ እንደ ነበር ያሳያል።

ኢየሱስ በሴሊሆም ግንብ መደርመስ 18 ሰዎች ስለ ሞቱበት የሉቃስ 13:2-4 ታሪክ አስተያየት ሲሰጥ፥ ከስተቱ የተፈጸመው የሞቱት ሰዎች በአካባቢያቸው ከሚገኙት የበለጠ ኃጢአተኞች በመሆናቸው እንዳልነበረ ገልጾአል። ይሁን እንጂ፥ ኢየሱስ ሰዎች ሁሉ በኃጢአታቸው ምክንያት እንዲህ ዓይነቱንና ከዚህም የሚበልጥ መከራ ቢቀበሉ እንደሚገባ አመልክቷል (ሉቃ. 13:3፥ 5)። ይህንን በመናገር፥ ኢየሱስ አንዳንድ የሰው ልጅ ሥቃይ ከሰው ኃጢአተኛነት እንደሚመጣ ጠቁሟል።

ከኃጢአትና ከክፉ መናፍስት በተጨማሪ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ለሰው ልጅ መከራ ሌሎች ምክንያቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ያመለክታል። ለምሳሌ፥ በዮሐንስ 9:2-3፥ ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን የሆነ ሰው ለምን ዕውር ሆኖ እንደ ተወለደ ጠይቀዋል። ዕውር ሆኖ እንዲወለድ ኃጢአት ያደረጉት እርሱ ይሆን ወይስ ወላጆቹ? በግለት ጠየቁት። ኢየሱስ ግን

እርሱ ወይም ወላጆቹ ኃጢአት እንዳልሠሩና ከስተቱ የተፈጸመው የእግዚአብሔር ሥራ በሕይወቱ እንዲገለጽ መሆኑን አስታወቃቸው።

ሐዋርያው ጴጥሮስ፥ እግዚአብሔር መከራ ወደ ሕይወታችን እንዲመጣ የሚፈቅድበት አንድ በጣም አስፈላጊ ምክያት፥ ሕይወታችንን ከኃጢአት ለማጥራት እንደ ሆነ ያሳስበናል (1 ጴጥ. 4:1)። ጴጥሮስ እነዚህ ልምምዶች የኃጢአት ተፈጥሮአችንን ክፉ ምኞቶች ከማርካት ይልቅ፥ በሕይወታችን የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዴት እንድንሻ እንደሚያደርጉን ማሳየቱን ይቀጥላል (1 ጴጥ. 4:2)።

ከላይ ከተመለከትናቸው ምሳሌዎች አንድ ግለሰብ መከራ የሚቀበልባቸው ምክንያቶች ፍጹም የተለዩ ሊሆኑ ይችላሉ። በሁኔታዎች ሁሉ ሙሉውን መልስ የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ስለ ሆነም፥ አንድ መጥፎ ነገር ሲከሰት ምዋርተኛ ወይም ጠንቋይ ማማከሩ ስሕተት ነው። ይልቁንም፥ ክርስቲያን በሕይወቱ ውስጥ የሚገኘውን ኃጢአት ሁሉ ሊከድና ጌታ ሁኔታውን ለመቋቋም የሚያስችል ጸጋና እርዳታ ሊሰጠው እንደሚችል ሊያምን ይገባል (ዕብ. 4:16)።

መከራ በምንቀበልበት ጊዜ ሁሉ እንድንፈጽመው የተነገረን ነገር አለ። በያዕቆብ 5:13፥ «ከእናንተ መከራን የሚቀበል ማንም ቢኖር እርሱ ይጸልይ» የሚል ተጽፎአል። ይህ ልናደርግ የምንችለው እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። ሁኔታው ምንም ቢሆን፥ በተለይም በችግራችን ጊዜ ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ያገናኘናል። ዕብራውያን 4:16፥ «እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ» ይላል።

መጽሐፍ ቅዱስ መከራን ስለ መቀበል ቀላል መልስ አይሰጥም። ይሁንና፥ መከራው ምንም ቢሆን እግዚአብሔር ሊረዳን ዝግጁ እንደ ሆነ ይነግረናል (ዕብ. 4:16)። እግዚአብሔር የሕይወታችንን መዘርዝር ሁሉ ስለሚያውቅ፥ ያለ ፈቃዱ ከልጆቹ አንዱን ሊነካ የሚችል ነገር የለም። የኢዮብን መከራ በተመለከተ፥ ሰይጣን በኢዮብ ላይ ክፉ ዕቅዶቹን ከመፈጸሙ በፊት ከእግዚአብሔር ዘንድ ፈቃድ ማግኘት ነበረበት። ይህ እውነት በክፉ መከራ ውስጥ ለሚያልፍ ክርስቲያን የጥንካሬና ብርታት ምንጭ ሊሆን ይችላል።

እግዚአብሔር ራሱ ፍጹም እንደ ሆነ እየመሰከረለት፥ ሰይጣን በኢዮብ ሕይወት እንዲህ ያለ ክፉት እንዲፈጽም የፈቀደለት ለምንድ ነው? እግዚአብሔር በፍጥረታቱ ላይ ለሚፈጽመው ማንኛውም ነገር ግብራሪያ

የመስጠት ግዴታ የለበትም። የኢዮብን ጉዳይ በተመለከተ፥ እግዚአብሔር ለኢዮብ ስለ መከራው መግለጫ አልሰጠውም ነበር (ኢዮብ 38:1-40:2)። ይሁንና፥ በመጽሐፈ ኢዮብ ውስጥ የሚገኘውን የእግዚአብሔርና የሰይጣን ውይይት በጥንቃቄ በመመርመር፥ እግዚአብሔር ሰይጣን ኢዮብን እንዲያሠቃይ የፈቀደበትን ምክንያት አንዳንድ አሳቦች ልናገኝ እንችላለን።

ኢዮብን በተመለከተ፥ እግዚአብሔር ለመላእክቱ ኢዮብ እርሱን የሚወደው ሀብት፥ ጤንነትና በረከት ስለሰጠው ብቻ እንዳልሆነ ለማሳየት ስለ ወሰነ ይመስላል። በኢዮብ መከራ አማካኝነት፥ እግዚአብሔር ለመላእክቱ ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚወደው ለእርሱነቱ እንደ ሆነ ገልጾአል። ይህንንም በማድረግ እግዚአብሔር ሰይጣን በእርሱና በመላእክቱ ፊት የተናገረውን ውሸት አጋልጦአል፤ ኮንኖአልም (ኢዮብ 1:6-11)። ውሸቱም፥ «በውኑ ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚፈራው በከንቱ ነውን? . . . እጅህን ዘርግተህ ያለውን ሁሉ ዳብስ፤ በእውነት በፊትህ ይሰድብሃል» የሚል ነበር (ኢዮብ 1:9፥ 11)።

ኢዮብ ሰይጣን የልጆቹን ሁሉ ሕይወት በነጠቀ ጊዜ ሳይቀር በእምነቱ ጸንቶ በመቆም፥ ይህንኑ መራራ ፈተና ተቋቁሟል (ኢዮብ 1:18-19)። የኢዮብ ምስክርነት፥ «እግዚአብሔር ሰጠ፥ እግዚአብሔርም ነሣ፤ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን» የሚል ነበር (ኢዮብ 1:21)። ታሪኩ፥ «በዚህ ሁሉ ኢዮብ አልበደለም፥ ለእግዚአብሔርም ስንፍናን አልሰጠም» እያለ ይቀጥላል (ቁ. 22)። የኢዮብ የልብ ዝንባሌ በኑዛዜው ውስጥ ተገልጾአል፦ «እነሆ፥ ቢገድለኝ እንኳን እርሱን በትዕግሥት እጠባበቃለሁ» (ኢዮብ 13:15)። ኢዮብ በተጨማሪም፥ እግዚአብሔር በመከራ አማካኝነት ሕይወቱን ከኃጢአት የማጥራት ዓላማ እንደ ነበረው ተረድቷል። በመሆኑም ኢዮብ፣ «የምሄድበትን መንገድ ያውቃል፤ ከፈተነኝም በኋላ እንደ ወርቅ እወጣለሁ» ብሏል (ኢዮብ 23:10)። ስለዚህ፥ እግዚአብሔር ሕይወታቸውን እርሱ ከማይፈልጋቸው ነገሮች ያጠራ ዘንድ በብዙ ክርስቲያኖች ሕይወት መከራ እንደሚያመጣ ግልጽ ነው (1 ጴጥ. 4:1)።

በተጨማሪም፥ እግዚአብሔር ሕዝቡ በራሳቸው ጥንካሬ ሳይሆን፥ በእርሱ ጸጋና ጥንካሬ ላይ እንዲደገፉ ለማስተማር መከራን ይጠቀማል።

እግዚአብሔር ለሐዋርያው ጳውሎስ በሕይወቱ ስለ ነበረው መከራ የሰጠው ምክንያት ይኼው ነበር (2 ቆሮ. 12:8-10)።

ከጠቅላላው የመከራ ጉዳይ ጋር የተያያዘው ችግር፥ መከራ መቀበል እንደማይገባን ማስባችን ነው። ሰው ገና ከመጀመሪያው በእግዚአብሔር ላይ ያመፀ ኃጢአተኛ መሆኑን በፍጥነት እንዘነጋለን። አዳም እግዚአብሔር የሰጠውን ትእዛዝ አሳምሮ ያውቅ ነበር፤ ይሁንና፥ እግዚአብሔር እንዳይበላው ያዘዘውን ፍሬ በመብላት በፈቃዱ በእግዚአብሔር ላይ ማመፁን መርጧል (ዘፍጥ. 3:6)። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ላይ ከማመፅ አልቦዘነም። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «በምድር ላይ መልካምን የሚሠራ ኃጢአትንም የማያደርግ ጻድቅ አይገኝምና» ይላል (መክ. 7:20)። እንግዲህ እግዚአብሔር ኢዮብ ፍጹም እንደ ነበረ ሲናገር ምን ማለቱ ነው? (ኢዮብ 1:8)። በመክብብ 7:20 መሠረት፥ እግዚአብሔር ስለ ኢዮብ የተናገረውን አሳብ፥ ምንም እንኳ ኢዮብ እንደ ሌሎች ሰዎች ሁሉ የኃጢአት ተፈጥሮ ቢኖረውም፥ በእግዚአብሔር የሚያስቀጣው የተወሰነ ኃጢአት እንዳልፈጸመ የሚገልጽ አድርገን መውሰድ አለብን።

በተራ ሕይወት፥ አንድ ወንጀለኛ ሕግ ሲተላለፍ ከተገኘ፥ በመንግሥት ተገቢው ቅጣት ይበየንበታል። ስለ ቅጣቱ ሊያማርር ቢችልም፥ እውነቱ ግን በወንጀሉ ምክንያት ቅጣቱን ሊቀበል እንደሚገባው ነው። በተጨማሪም፥ ይህ ሰው ካልተቀጣ ስለ ወንጀሉ የሚያውቁ ሰዎች ይቆጣሉ። ይቀጣልን ሲሉ የጠይቃሉ። ይህም እግዚአብሔር ኢዮብ እንዲሠቃይ የፈቀደበትን ምክንያት ተጨማሪ ፍንጭ ይሰጠናል፤ ዛሬም ብዙ ክርስቲያኖች እንዲሠቃዩ ለምን እንደሚፈቅድ ይገልጽልናል።

እግዚአብሔር ፍትሐዊና ጻድቅ ዳኛ ነው። ሰይጣንና መላእክቱ ሰዎች ሁሉ ከሚቀበሉት እጅግ የላቀ መከራ የሚገባቸው ኃጢአተኞች እንደ ሆኑ ያውቃሉ። በመሆኑም እግዚአብሔር ኢዮብን እንዲሠቃይ በመፍቀዱ ሰይጣን በዚህ ሳቢያ እግዚአብሔርን ፍትሕ አጓድሏል ሲል ሊከሰው አይችልም። እግዚአብሔር በአጽናፈ-ዓለሙ ውስጥ ከሚገኘው ፍጥረት ሁሉ ጋር አንድ ዓይነት የፍትሕ መመዘኛ ለመጠበቅ፥ ሰይጣን በኢዮብ ላይ ላቀረበው ክስ የኢዮብን መሠቃየት ፈቀደ። በመጽሐፍ ቅዱስ ኢዮብ ራሱ፥ «በዚህ ሁሉ ኢዮብ አልበደለም፥ ለእግዚአብሔርም ስንፍናን አልሰጠም» ይላል (ኢዮብ 1:22)። በምድር ላይ የሚገኙ ሰዎች ሁሉ ለኃጢአታቸው መከራ ሊቀበሉ ስለሚገባ፥ እግዚአብሔር ኢዮብ እንዲሠቃይ መፍቀዱ ስሕተት አልነበረም። ይሁንና፥ እግዚአብሔር

ታላቅ ምሕረት ያለው አምላክ በመሆኑ፥ ሰዎች የሚገባቸውን ያህል መከራ እንዲቀበሉ አያደርግም። መዝሙር (86):5፥ «አቤቱ፥ አንተ መሐሪና ይቅር ባይ ነህና፥ ምሕረትህም ለሚጠሩህ ሁሉ ብዙ ነውና» ይላል። ቁጥር 15 ደግሞ፥ «አቤቱ፥ አንተ ግን መሐሪና ሩኅሩኅ አምላክ ነህ፤ መዓትህ የራቀ ምሕረትህም እውነትህም የበዛ» ይላል።

መዝሙር (130):3፥ «አቤቱ፥ ኃጢአትንስ ብትጠባበቅ፥ አቤቱ፥ ማን ይቆማል?» ይላል። «አንተ ግን፥ አንተ ግሩም ነህ፤ ቁጣህን ማን ይታወግል?» [መዝ. (76):7]። የሚያስደንቀው ሰዎች ከሚፈጽሙት ኃጢአት የበለጠ ለኃጢአታቸው አለመሠቃየታቸው ነው።

ኢየሱስ ተከታዮቹ እግዚአብሔር አንዳንድ የገሊላ ሰዎች በጲንጤናዊው ጲላጦስ እንዲገደሉ ለምን እንደ ፈቀደ ሲጠይቁት ያስተማረው ይህንኑ ነበር (ሉቃ. 13:1-2)። በተጨማሪም፥ እግዚአብሔር ለምን የሰሊሆም ግንብ በ18 ሰዎች ላይ ወድቆ እንዲገድላቸው እንደ ፈቀደም ጠይቀውታል (ሉቃ. 13:3)። ኢየሱስም ሲመልስ፥ «ወይስ . . . እነዚያ . . . በኢየሩሳሌም ከሚኖሩት ሁሉ ይልቅ በደለኞች ይመስሉአችኋልን? አይደለም፥ እላችኋለሁ፤ ነገር ግን ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንደዚሁ ትጠፋላችሁ» ብሏል (ሉቃ. 13:4-5)። ስለ እግዚአብሔር ምሕረት እውነተኛነት በመዝሙር (103):10 ላይ ተገልጸአል፦ «እንደ ኃጢአታችን አላደረገብንም፥ እንደ በደላችንም አልከፈለንም።»

ሰዎች ከሚቀበሉት የበለጠ መከራ እንደሚገባቸው የሚገልጸው እውነት፥ ከዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ የቀረበውን ወጣት ሚስዮናዊ ዓይነት ሰዎችን አይረዳቸውም። ለጌታ ራሱን እምብዛም ያልሰጠ ክርስቲያን ከመከራ እያመለጠ፥ ሌላው ለምን ይሠቃያል? የሚል ዓይነት ጥያቄ ብዙዎችን ያስጨንቃቸዋል። እንዲያውም ይበልጥ በተለመደው መልኩ፥ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ልጆች ያልሆኑ ክፉ ሰዎች ከመከራ እያመለጡ ለምን እነርሱ እንደሚሠቃዩ ሊጠይቁ ይችላሉ።

መዝሙረኛው አሳፍም ከዚህ ጥያቄ ጋር ታግሏል። «የኃጢአተኞችን ሰላም አይቼ በዓመፀኞች ቀንቼ ነበርና። ለሞታቸው መጣጣር የለውምና፤ ኃይላቸውም ጠንካራ ነውና» ሲል ጽፎአል [መዝ. (73):3-4]። በመጨረሻም፥ አሳፍ ሁኔታውን ከእግዚአብሔር ዕይታ አንጻር ተመለከተ። በመዝሙር (73):16-19፥ «አውቅም ዘንድ አሰብሁ፥ ይህ ግን በፊቴ

ችግር ነበረ። ወደ እግዚአብሔር መቅደስ አስከገባ ድረስ፥ ፍጽሜአቸውንም እስካስተውል ድረስ . . . ወደ ጥፋትም ጣልኻቸው። እንዴት ለጥፋት ሆኑ! በድንገት አለቁ ስለ ጥፋታቸውም ጠፉ» ብሏል። ስለ ሆነም፥ ክፉዎች ለምን ሁልጊዜ እንደማይሠቃዩ ለመረዳት ቁልፉ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኃጢአተኞች የመጨረሻ ፍርድና የጻድቃን ዕጣ ፈንታ የሚናገረውን ማወቅ ነበር። በመጨረሻው ፍርድ፥ እግዚአብሔር በትክክል ኃጢአተኞችን በከፋ ሁኔታ ይቀጣል (ማቴ. 25:41)።

መዝሙር (73) የሕይወትን ከባባድ ጥያቄዎች ለመረዳት ያግዘናል። ስለ ችግራችንና መከራችን የምናስበው ከአሁኑ ሁኔታችን አንጻር ብቻ ነው። እግዚአብሔር ግን ይህ ሕይወትና ያሁኑ ሁኔታ የጠቅላላው አካል ትንሽ ክፍል ብቻ እንደ ሆነ ይናገራል። ገና ብዙ የታሪክ ክፍል አለ። ገና ብዙ የሚመጣ ነገር አለ። አንድ ቀን ኃጢአተኞች ለኃጢአታቸው ሙሉ ዋጋ ይከፍላሉ። አንድ ቀን ጻድቃን፥ በተለይም ለክርስቶስ ታማኝ በመሆናቸው መከራ የተቀበሉ፥ ለታማኝነታቸው ይሸለማሉ። በኢዮብ መከራ ፍጻሜ፥ እግዚአብሔር በመጀመሪያ የነበረውን ንብረት በእጥፍ ሊመልስ፥ አሥር ልጆችንም ሰጥቶታል (ኢዮብ 42:10-13)።

ጳውሎስ ይህንን እውነት ተረድቷል። «ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ» ለማለት ይችል ነበር (ሮሜ 8:18)። በመንፈሳዊው ዓለም አብርሃም ለሀብታሙ ሰውዬ፥ «ልጄ ሆይ፥ አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደ ተቀበልህ አስብ፤ አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ፤ አሁን ግን እርሱ በዚህ ይጽናናል አንተም ትሠቃያለህ» ብሏል (ሉቃ. 16:25)። ሐዋርያው ጴጥሮስ፥ «ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በመነሣቱ ለሕያው ተስፋና ለማይጠፋ፥ አድፈትም ለሌለበት፥ ለማያልፍም ርስት እንደ ምሕረቱ ብዛት ሁለተኛ የወለደን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፤ ይህም ርስት በመጨረሻው ዘመን ይገለጥ ዘንድ ለተዘጋጀ መዳን በእምነት በእግዚአብሔር ኃይል ለተጠበቃችሁ ለእናንተ በሰማይ ቀርቶላችኋል። በዚህም እጅግ ደስ ይላችኋል፥ ነገር ግን በእሳት ምንም ቢፈተን ከማይጠፋው ወርቅ ይልቅ አብልጦ የሚከብር የተፈተነ እምነታችሁ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ፥ ለምስጋናና ክብር ለውዳሴም ይገኝ ዘንድ አሁን ለጥቂት ጊዜ ቢያስፈልግ በልዩ ልዩ ፈተና አዝናችኋል» ሲል ጽፎአል (1 ጴጥ. 1:3-7)።

እግዚአብሔር ለከባባድ የሕይወት ጥያቄዎች የሚሰጠው ምላሽ ታሪኩ እንዳልተጠናቀቀና በትዕግሥት መጠበቅ እንደሚያስፈልግ የሚያስገነዝብ ነው። ወደ መንግሥተ ሰማይ ስንደርስ ታሪኩ ይቋጭና መልስ እናገኛለን። የእግዚአብሔር ሽልማት፥ ከብርና በረከት ቢያንስ በክርስቶስ ስም የደረሰባቸውን መከራ በታማኝነት ለተወጡት ይገለጻል። በመከራቸው ታማኞች የነበሩ ሰዎች እጅግ ታላቅ ከመሆኑ የተነሣ ዛሬ ቢብራራላቸው የማይረዱትን ሽልማት ይቀበላሉ። በ1ኛ ቆሮንቶስ 1:9፥ «ጎይን ያላየችው ጀሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው ተብሎ እንደ ተጻፈ፥ እንዲህ እንናገራለን» የሚል እናነባለን። በሮሜ 8:28ም፥ «አግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን» ይላልና በመንግሥተ ሰማይ የመከራ ምክንያቶች ምን እንደ ሆኑ እናውቃለን።

ለ. የበሽታ መነሾዎች ምንድን ናቸው?

አንድ ክርስቲያን በመንደር ውስጥ ታሟል። ባቅራቢያው አንድ ጥሩ የቤተ ክርስቲያን የሕክምና ስፍራ ነበርና ቤተሰቦቹ ወደዚያው ይዘውት ሄዱ። የሚያሳዝነው ሰውዬ ከዚህ በፊት የጉበት፥ የአሜባና የወባ በሽታዎች ነበሩት። እነዚህ በሽታዎች የሰውየውን ጉበት ክፉኛ ጎድተው ነበር። አሁን ለታመመበት በሽታ መድኃኒት ሲሰጠው፥ ከዚህ ቀደም ጉበቱ በጣም ተጎድቶ ስለ ነበር ይብልጥ ታመመ። ከጥቂት ቀናት በኋላም ሕይወቱ አለፈች። በቀብር ሥነ-ሥርዓቱ ላይ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ መጋቢ ስለዚህ ወንድም የሕይወት ታሪክና ከሌሎችም ጋር ስለ ነበረው ግንኙነት ንግግር አደረጉ። ይህ ሰው መልካምና ታማኝ ክርስቲያን ነበር። ከዚያም መጋቢው የሚከተለውን መግለጫ ሰጡ፡- «ወንድማችን ከጉበት መጎዳት የተነሣ እንደ ሞተ ከሐኪሙ ገለጻ ተረድተናል። ይሁንና፥ ሁላችንም በእርሱ ላይ የተፈጸመውን በትክክል እናውቃለን፤ ቡዳዎች እንደ በሉት እናውቃለን።» የመጋቢው አባብ ትክክል ነው? ስለ በሽታ መጽሐፍ ቅዱሳዊና ሳይንሳዊ እውነቶች ምንድን ናቸው?

ይህ እውነተኛ ገጠመኝ በአፍሪካ ስለ በሽታዎችና መንስዔያቸው ወደ አለው ግንዛቤ ይመራናል። ሁሉም ሰው ከበሽታ ችግር ጋር ይታገላል። በዓለም በሕይወት ዘመናቸው ታመው የማያውቁ ሰዎች ቢኖሩ እጅግ ጥቂቶች ብቻ ናቸው። መጽሐፍ ቅድስ ስለ በሽታ፥ መንስዔዎችና የመዳኛ መንገዶች ምን ይላል?

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሰውን ከምድር አፈር እንዳበጀውና የሕይወትን እስትንፋስ በአፍንጫው እፍ እንዳለበት ይናገራል (ዘፍጥ. 2:7)። እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካምና ፍጽም ስለ ነበር [ዘፍጥ. 1:31፣ መዝ. (18)፡30]፥ እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ፍጹም የሆነ አካል እንደ ሰጠው መግለጹ ተገቢ ነው። በሽታ የመጀመሪያ ፍጥረት አካል አልነበረም። እግዚአብሔር ለአዳም መልካምና ክፉ ከምታስታውቀው ዛፍ ፍሬ እንዳይበላ ትእዛዝ ሲሰጥ፥ የሚከተለውንም ማስጠንቀቂያ አክሎለት ነበር፡– «ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና» (ዘፍጥ. 2:17)። አዳም እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ የተከለከለውን ፍሬ በላ። ኃጢአትና ሞት ወደ ዓለም የገባው ከዚህ የአዳም አለመታዘዝ መሆኑን ከሮሜ 5:12 እንረዳለን።

ሞትና በሽታ ተያያዥ ሂደቶች ናቸው። በሽታ የጤንነት ተቃራኒ ነው። ብዙውን ጊዜ ሞት የማይሽር ከፍተኛ ሕመም የሚያስከትለው ውጤት ነው። ፈውስ ወይም ጤንነት ወደ ሕይወት ሲመራ፥ ሕመም ወደ ሞት ሊመራ ይችላል።

ከእነዚህ ጥቅሶች የበሽታና ሞት ሂደት ወደ ዓለም የመጣው በአዳምና ሔዋን አለመታዘዝ መሆኑን ልንመለከት እንችላለን። ባጠቃላይ በሽታ የሚኖረው በሰው መውደቅ ምክንያት መሆኑን ልንናገር እንችላለን። ይህም ማለት በዓለም ውስጥ በሽታ የሚታየው በኃጢአት ምክንያት ነው። ይሁንና በሽታ ሁሉ የተወሰነ ኃጢአት ውጤት ነው ማለት አይደለም።

በሽታ ሁሉ የአንድ የተወሰነ ኃጢአት ቀጥተኛ ውጤት እንደ ሆነ የሚያስቡ ሰዎች አሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን አያስተምርም። ለምሳሌ፥ ሰይጣን ወደ ኢዮብ ሕይወት ሥጋዊ በሽታ አምጥቷል (ኢዮብ 2:7)። ዳሩ ግን፥ እግዚአብሔር ራሱ የኢዮብን ፍጹምነት ስለ መሰከረ (ኢዮብ 2:3)፥ ይህ በኢዮብ ሕይወት ውስጥ ከሚገኝ ኃጢአት ጋር የተያያዘ አልነበረም።

በተጨማሪም፥ መጽሐፍ ቅዱስ የአንድ የተወሰነ ኃጢአት ቀጥተኛ ውጤት ሆነው የሚከሰቱ አንዳንድ በሽታዎች እንዳሉ ያስተምራል። ይህም ኢየሱስ ለ38 ዓመታት ታሞ የነበረውን ሰው በፈወሰበት ጊዜ ተመልክቷል (ዮሐ. 5:5-14)። ዛሬ በቀጥታ ከኃጢአት ጋር ለተገናኙ በሽታዎች እጅግ ግልጽ የሆኑ ምሳሌዎችን ለመጥቀስ፥ እንደ ኤድስና ቂጥኝ የመሳሰሉት ከወሲብ ግድፈት የሚመጡ በሽታዎች መሆናቸውን ማመልከቱ በቂ ነው።

በያዕቆብ 5:14-16 የታመሙ ክርስቲያኖች፥ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ይጸልዩላቸው ዘንድ እንዲጠሩአቸው ተነግሮአቸዋል። ያዕቆብ 5:15፥ «ኃጢአትንም ሠርቶ እንደ ሆነ ይሰረይለታል» ይላል። ይህ ዓረፍተ ነገር በሽታ አንዳንድ ጊዜ የተወሰነ ኃጢአት ቀጥተኛ ውጤት እንደ ሆነ ያመለክታል። ከዚህ የተነሣ፥ ክርስቲያን ሲታመም ሁልጊዜም በሕይወቱ ውስጥ የሚገኘውን ማንኛውንም ኃጢአት መናዘዝና መተው፥ ብሎም እግዚአብሔር ይቅር እንዲለው መጠየቅ በጣም አስፈላጊ ነው። ይህ ካልሆን፥ እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ከሚያወርደው ፍርድ የተነሣ በሽታው እየከፋ ይሄዳል።

ሳይንቲስቶች ብዙ ዓይነት በሽታዎች በማይክሮስኮፕ ብቻ ሊታዩ በሚችሉ ረቂቅ ተሐዋስያን መነሻነት እንደሚመጡ ተረድተዋል። እነዚህም ረቂቅ ተሐዋስያን ቫይረስ፥ ባክቴሪያዎች ወይም አሚባዎች ይባላሉ። በተለምዶ ግን ተሐዋስያን (ጀርሞች) በመባል ይታወቃሉ። የተስቦ ትኩሳት፥ ወባና የጉልበት በሽታ በተለያዩ ተሐዋስያን የሚመጡ በሽታዎች ምሳሌዎች ናቸው። የተስቦ ትኩሳት ከባክቴሪያ፥ ወባ ከደም መጣጭ ጥገኛ ትል፥ የጉበት በሽታ ከቫይረስ ይመጣሉ። ከሰው የመራቢያ ሕዋሳት መጎዳት የተነሣ የሚመጡ ሌሎችም የበሽታ ዓይነቶች አሉ። ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑት የሚጥል በሽታ ("epilepsy") እና አንዳንድ የካንሰር በሽታ ዓይነቶች ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪም ሳይንቲስቶች አንዳንድ በሽታዎች ከሰዎች አእምሮአዊና ስሜታዊ ሁኔታዎች ጋር ሊያይዙ እንደሚችሉ ተረድተዋል። የአእምሮ ጤንነት ከአካላዊ ጤንነት ጋር በቅርብ ሊገናኝ ይችላል። አንድ ሰው በጣም ተሰፋ ከቆረጠ፥ በጣም ከፈራ፥ በጣም ከተቆጣ ወይም በሌላ አባባል የአእምሮ መታወክ ከደረሰበት፥ አካላዊ ሕመም ሊደርስበት ይችላል።

አንድ ሰው ለተሐዋስያን ከተጋለጠና ሰውነቱ እነዚህን ተሐዋስያን ለመከላከል ወይም ለማጥፋት የሚያስችል ብልሀት ካልፈጠረ፥ ተሐዋስያኑ የተወሰነ በሽታ ያስከትሉበታል። በማንኛውም ጊዜ ሰውነታችን በደም ውስጥ ብዙ ዓይነት ተዋሐስያን ሊሸከምና እኛ ግን ሕመም ላይሰማን ይችላል። ይህም የሚሆነው የሰውነታችን በሽታን የመከላከል ዓቅሙ ጠንካራ ስለ ሆነ ነው። የሰውነት የመከላከል ዓቅሙ ጠንካራ በሚሆንበት ጊዜ፥ ተሐዋስያን ጠቅላላውን ሰውነት በበሽታ ሊያጠቁ አይችሉም። የሰውነት የመቋቋም ዓቅሙ ደካማ ሲሆን ግን ተሐዋስያን በሽታ ሊያመጡ ይችላሉ። የአንድ ሰው በሽታ የመቋቋም ዓቅም የሚያንሰው በደንብ

ካለመመገብ፥ ለሌሎቹ ተሐዋስያን በመጋለጡ ወይም በአእምሮአዊ ወይም ስሜታዊ ውጥረት ምክንያት ሊሆን ይችላል። ብዙውን ጊዜ አእምሮአዊ ውጥረት ወይም ጭንቀት የሚመጣው ከሌላ ሰው ጋር ከሚኖረን መጥፎ ግንኙነት የተነሣ ነው።

ከዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ መጋቢው እንደ ገለጸው፥ ቡዳዎች የሰውን ነፍስ በመብላት ሞት የማስከተላቸውስ ጉዳይ? ብዙውን ጊዜ በአፍሪካ ሰዎች ጠንቋይን በጣም ከመፍራታቸው የተነሣ አካላዊ ሕመም ይደርስባቸዋል። በሌላ አባባል፥ የሰውየው ፍርሃት እጅግ በማየሉ ሰውነቱ በደሙ ውስጥ ከሚገኙ ተሐዋስያን ጋር መዋጋት ይሳነዋል ማለት ነው። ሰውየው በከፍተኛ ደረጃ እንዲታመምና አንዳንድ ጊዜም እንዲሞት የሚያደርገው ትክክለኛው ጠንቋይ ሳይሆን በአሳቡ ውስጥ የሚመላለሰው ጠንቋዩን የመፍራት ሁኔታ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ፥ ብዙ አስማተኞችና ጠንቋዮች ትክክለኛ አጋንንታዊ ኃይል አላቸው። የእነዚህ አስማተኞችና ጠንቋዮች ኃይል የሚመጣው በውስጣቸው ከሚሠሩ አጋንንት ነው። አጋንንት የእነዚህን ሰዎች አርግማንና ድግምት ሊፈጽሙ ይችሉ ይሆናል። በአስማትና በጥንቆላ አማካኝነት አጋንንታዊ ኃይል በሰዎች ላይ በሚወነጨፍበት ጊዜ፥ አጋንንቱ ሥጋዊና አእምሮአዊ በሽታ ሊያስከትሉ ይችላሉ። በመጽሐፈ ኢዮብ፥ ሰይጣን ኢዮብ በቁስል እንዲመታ አድርጓል (ኢዮብ 2:6-7)። ይህም ሰይጣን ወይም አጋንንቱ ኢዮብን በበሽታ ለሚያጠቁ ተሐዋስያን አሳልፈው እንደ ሰጡት ያመለክታል። ንጉሥ ሳኦል በክፉ መንፈስ በተያዘ ጊዜ፥ እብድና ጨካኝ በመሆን የክፉውን መንፈስ ባሕርይ ገልጾአል (1 ሳሙ. 18:10-11)።

በአራቱ ወንጌላት ውስጥ ከቀረቡት አያሌ ምሳሌዎች፥ አጋንንት ሰዎችን በተለያዩ ሥጋዊና አእምሮአዊ ችግሮች እንደሚጎዱና ሊጎዱ እንደሚችሉ እንመለከታለን። እግዚአብሔር ወይም ቅዱሳን መላእክት ካልገቱአቸው በቀር፥ አጋንንት ክፉ ዓላማቸውን ከመፈጸም እንደማይመለሱ መገመት ተገቢ ነው። ስለ ሆነም፥ ጠንቋዮች፣ አስማተኞችና ምሥጢራዊ ጎብረተሰቦች ለሰዎች መሞት ወይም መታመም ወይም ለአደጋዎች ኃላፊነት ሲወስዱ፥ የሰይጣን አጋንንት ኃይል ከበስተጀርባቸው ስላለ እውነት ሊሆን ይችላል። ኢየሱስ ሰይጣን ከመጀመሪያው ነፍስ ገዳይ እንደ ሆነ አስተምሮናል (ዮሐ. 8:44)።

ክርስቲያን የነገሥታት ንጉሥ ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር መንፈሳዊ አንድነት ስላለው፥ በሰይጣንና በአጋንንቱ ላይ ሥልጣን እንዳለው መገንዘብ በጣም አስፈላጊ ነው። ክርስቲያን አስማተኞችን፥ ጠንቋዮችን ወይም አጋንንት በመፍራት ሊመላለስ አይገባውም። ክርስቲያን ስለ እነዚህ ሰይጣናዊ ኃይሎች፥ እርግማኖች ወይም ድግምቶች ምን ሊያድርግ እንደሚገባ ቀጥለን እንመለከታለን።

በሽታ ሁሉ ከጠንቋይ ወይም ከአጋንንት እንደሚመጣ አድርገን እንዳናምን መጠንቀቅ አለብን። ብዙው ሕመማችን የሚመጣው በሽታውን ከሚያመጡ ተሐዋስያን ጋር ከሚኖረን ግንኙነት ነው።

በሽታን ለማሻል የሚረዱ መንገዶች የትኞቹ ናቸው? ክርስቲያን ፈውስን እንዴት ሊፈልግ ይገባል?

የታዘዙትን የሕክምና መድኃኒቶች መውሰድ የእምነት ድህነትን እንደሚያሳይ የሚያስቡ አንዳንድ ክርስቲያኖች አሉ። ይህ አሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ሊደገፍ አይችልም። አራቱን ወንጌላት ከጻፉት ሰዎች አንዱ በሙያው ዶክተር የሆነው ሉቃስ ነበር (ቆላ. 4:14)። የዶክተሮች ሥራ ለተወሰነ በሽታ ትክክለኛውን መድኃኒት መስጠት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ወዳጁ ጢሞቴዎስ ለሆዱ ሕመም በተለምዶ ይወሰድ የነበረውን መድኃኒት እንዲጠቀም መክሮአል (1 ጢሞ. 5:23)። በሽታን ሊፈውሱ የሚችሉ ብዙ ዓይነት መድኃኒቶች እንዲያዘጋጁ ለዶክተሮችና ሳይንቲስቶች እውቀትና መረዳት የሰጣቸው ራሱ እግዚአብሔር እንደ ሆነ መገንዘቡ የሚያዳግት አይሆንም። ክርስቲያን ሲታመም ምን ሊያደርግ ይገባል?

በመጀመሪያ ደረጃ ከሁሉም በላይ፥ ክርስቲያን በሽታን ጨምሮ የእግዚአብሔር ፍርድ የሚያስከትል ግልጽ ወይም የተሰወረ ኃጢአት በሕይወቱ እንደሌለ ማረጋጋጥ አለበት። ክርስቲያን በሕይወቱ ውስጥ የሚገኘውን ኃጢአት ሁሉ በመናዘዝ ንስሐ መግባት አለበት። ይህ በተለይ እንደ ይቅር አለማለት፥ በሌሎች ላይ የሚኖር ጥላቻ፥ መራርነትና ቅንዓት የመሳሰሉትን የተሰወሩ የልብ ኃጢአቶች በተመለከተ እውነት ነው። በልቡ የኃጢአት ዝንባሌ ያለው ክርስቲያን የታዘዘውን መድኃኒት ቢጠቀምም እንኳን የፈውስ በር ላይከፍትለት ይችላል።

ዘላቂ ጤንነት የአእምሮንና የመንፈስን፥ ብሎም የሰውነትን መፈወስ ይጠይቃል። በሰውነት ጤንነትና በሰው አእምሮ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚገልጸው አስገራሚ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ፥ «የሰው ነፍስ

ሕመሙን ይታገሣል፤ የተቀጠቀጠን መንፈስ ግን ማን ያጠነክረዋል?» የሚለው ነው (ምሳሌ 18:14)። ሌላው ጥቅስ፥ «ሰላም ያለው አእምሮ ለሰውነት ጤንነትን ያስገኛል» ይላል (ምሳሌ 14:30 - ከ1980 ዓ. ም. አዲስ ትርጉም)።

በሰዎች መካከል የሚገኙ የፈራረሱ ግንኙነቶች የሰውን መንፈስ ሊሰብሩ ይችላሉ። አንድ ሰው እውነተኛ ጤንነት እንዲሰማው ከተፈለገ፥ የፈራረሱ ግንኙነቶች መጠገን በጣም አስፈላጊ ነው። ኢየሱስ ለተከታዮቹ ጸሎታቸው (ከበሽታ ለመፈወስ የጸለዩትን ጨምሮ) እንዲመለስ ከፈለጉ፥ ወደ እግዚአብሔር ከመጸለያቸው በፊት የተቀየሙአቸውን ሰዎች ሁሉ ይቅር ማለት እንዳለባቸው አሳስቦአቸዋል (ማር. 11:25)።

አንድ ክርስቲያን ድግምት ወይም እርግማን እንደ ተደረገበት ከተጠራጠረ፥ ከዚህ በታች እንደ ተመለከተው ድግምቱን ወይም እርግማኑን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሊያፈርስ ይችላል። በሁሉም የሕመም ጉዳዮች ክርስቲያን መጸለይ አለበት (ያዕ. 5:13)። ፈውስ መድኃኒት በመጠቀም ወይም ያለ መድኃኒት ሊመጣ ቢችልም፥ እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ ፈውስን ይልካል። ሕመሙ በጣም ከፍተኛ ከሆነ ወይም መድኃኒት ግግኘት ካልተቻለ፥ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑን ሽማግሌዎች በመጥራት በያዕቆብ 5:14-16 በተገለጸው ዕቅድ መሠረት እንዲጸልዩለት ማድረጉ ብልህነት ነው።

የታመመ ክርስቲያን የሚቻለውን ያህል ጥሩ ሕክምና ቢያገኝ መልካም ነው። ክርስቲያን ለሕመሙ መድኃኒት ለማግኘት ወደ ባህላዊ መድኃኒት አዋቂ ዘንድ መሄድ እንደሌለበት በምዕራፍ አሥራ አራት በቅይጥነት ችግር ርዕሰ ሥር ተገልጾአል። ከእነዚህ ሰዎች ብዙዎቹ በባህላዊ ሃይማኖት አማካኝነት ከክፉ መናፍስት ጋር የሚገናኙ ናቸው። ከባህላዊ ሃይማኖት ጋር ግንኙነት ባይኖራቸው እንኳ፥ ከባህል የመድኃኒት አዋቂዎች የሚመጡ መድኃኒቶች አስተማማኝነት አይኖራቸውም። አንድ ክርስቲያን በባህል መድኃኒት አዋቂውን መድኃኒት ከመጠቀሙ በፊት፥ ሰውየው የመድኃኒት እውቀቱን እንዴትና ከየት እንዳገኘ በጥንቃቄ መመርመር አለበት። በተጨማሪም፥ ስለዚያ አዋቂ ሃይማኖታዊ እምነቶች በአካባቢው የሚገኙትን በሳል ክርስቲያን ሽማግሌዎች መጠየቁ መልካም ነው። በመጨረሻም፥ የዚያን ሰው መድኃኒት ከተጠቀሙ ሌሎች ሰዎች በሽታው

ዳግም ተመልሰባቸው እንደ ሆነ ወይም የሚያስከትላቸው መጥፎ ውጤቶች እንዳሉት ማጣራት አለበት።

የክርስቲያን ሰውነት የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ነው (1 ቆሮ. 6:19)። ስለ ሆነም፥ ክርስቲያን ሊጠቀም የሚችለው በሽታውን ለመፈወስ አስተማማኝ የሆኑትን ባህላዊ መድሐኒቶች ብቻ ነው። አንድ መድኃኒት አስተማማኝ እንደ ሆነ ሊገለጽ የሚችለው፥ ያለ ምንም ከፉ ውጤቶች ሁልጊዜም ስኬታማ ምስክርነት ያለው ሲሆን ነው። በመንግሥት ወይም በቤተ ክርስቲያን የሕክምና ጣቢያዎች የሚገኙ መድኃኒቶች ብዙውን ጊዜ ለአስተማማኝነታቸው በሳይንቲስቶች የተረጋገጡ ናቸው። በመሆኑም፥ በትክክለኛ መንገድና በትክክለኛ መጠን የተወሰዱ እንደ ሆኑ ጠቅለል ባለ መልኩ አስተማማኞች ናቸው።

የበሽታን መንስዔዎች ለማጠቃለል፥ በሽታ በዓለም ውስጥ የሚታየው በኃጢአት ምክንያት መሆኑን ልንናገር እንችላለን። አንዳንድ በሽታዎች በተወሰነ ኃጢአት ምክንያት በቀጥታ የደረሱ ሊሆኑ ቢችሉም፥ ብዙዎቹ በሽታዎች በሰው ሕይወት የሚገኝ የአንድ የተወሰነ ኃጢአት ውጤቶች አይደሉም። አንዳንድ በሽታዎች በአስማተኛ ወይም በጠንቋይ አማካኝነት ከሚሠራው ክአጋንንት ኃይል ሊመጡ ይችላሉ። ሌላው በሽታ ደግሞ ከሰው አእምሮአዊ ወይም ስሜታዊ ሁኔታ፥ በተለይም ከሰብአዊ ግንኙነቶች ጋር የተያያዘ ነው።

ብዙዎቹ በሽታዎች በሽታ ከሚያስከትሉ ተሐዋስያን ጋር ከመገናኘታችን የተነሣ የሚደርሱብን ናቸው። ይህ ብዙውን ጊዜ ንጹሕ ያልሆነ ውኃ ከመጠጣት ወይም ተሐዋስያን የሚገኙበትን ምግብ ከመብላት የተነሣ ይከሰታል። ብዙውን ጊዜ የቆሸሹ እጆቻችንን ሳንታጠብ ስንመገብ ለተሐዋስያን እንጋለጣለን። እጆቻችን እንደ ገንዘብና የሌሎች እጅ የመሳሰሉትን ብዙ ነገሮች ይነካሉ፤ በዚህም ተሐዋስያንን ይቀበላሉ። እንዲሁም፥ ወደ ታመሙት ሰዎች ቀረብ ብለን ሲያስላቸው ወይም ሲያስነጥሳቸው በአየር ላይ የበተኑአቸውን ተሐዋስያን ከአየር ጋር ወደ ሳንባችን ስናስገባ፥ ለበሽታ እንጋለጣለን።

የበሽታው መንስዔ የትኛውም ቢሆን፥ እግዚአብሔር መሓሪ በመሆኑ፥ ብዙውን ጊዜ በጸሎትና አስተማማኝ በሆኑ መድኃኒቶች አማካኝነት ፈውስን ይሰጣል። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ያለ ምንም መድኃኒት ፈውሱን ይልካል። ይህም የተለየ ነገር አይደለም። የእግዚአብሔር

ፈውስ በመድኃኒትም ሆነ ያለ መድኃኒት የሚገለጽ የቸርነት ስጦታ ነው [መዝ (103)፡3]።

በተጨማሪም፥ ፈውስ ሁሉ ከእግዚአብሔር እንዳልሆነ ማወቅ አለብን። ሰይጣን ሰውን በበሽታ ሊመታና ቆይቶ ደግሞ በሽታውን ሊያስወግድ ይችላል። ይህንንም ፈውስ በማድረግ፥ ሰይጣን ሰዎችን ያታልልና እግዚአብሔርን በመተማመን ፈንታ፥ በጠንቋዮችና በሌሎች ባህላዊ ፈዋሾች እንዲያምኑ ይገፋፋል።

ሐ. ክርስቲያን አስማት፥ ጥንቆላ፥ ምትሐት፥ እርግማንና ድግምትን እንዴት መቋቋም ይችላል?

አስማትና ጥንቆላ በዓለም ሁሉ ይገኛሉ። እነዚህ ልምምዶች በብዙዎቹ የአፍሪካ ባህሎችም ውስጥ ይገኛሉ። ዛሬም እንኳ እነዚህ ነገሮች ሕዝቡን በጣም ያስፈራሉ። ስለ ሆነም፥ አስማትንና ጥንቆላን ብሎም ከጀርባቸው ያለውን ኃይል ልንረዳ ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እነዚህ ነገሮች የሚለውን ልንረዳ ይገባል። ከሁሉም በላይ፥ ክርስቲያን እንደዚህ ስላለው ክፉት ምን ሊያደርግ እንደሚገባ መረዳት አለብን።

አንዳንድ የአፍሪካ ባህሎች በአስማተኛና በጠንቋይ መካከል ልዩነት ያደርጋሉ። አስማተኛ አንድን ሰው ለመጉዳት ወይም ለመጥቀም ሆን ብሎ በምሥጢራዊ ኃይል የሚጠቀም ሰው ነው። በአስማት ሁልጊዜም ለማለት ይቻላል እንደ ምትሐት፥ ድግምት፥ እርግማን ወይም የመድኃኒቶችን ቅመማ ለመለማመድ የተወሰነ ሥነ-ሥርዓት ማጀባት ይጠይቃል። ደግሞም ብዙውን ጊዜ ሴቷም ትሁን ወንዱ አስማተኛ ለአገልግሎታቸው ገንዘብ ይጠይቃሉ።

በአስማተኛና ጠንቋይ መካከል ልዩነት በሚያደርጉ ባህሎች፥ ጠንቋይ በክፉ መናፍስት ኃይል ለመቋቋም በማይቻል ከፍተኛ ደረጃ የሚሠራ ሰው እንደ ሆነ ይታሰባል። በእነዚህ ባህሎች ግንዛቤ መሠረት፥ ጠንቋይ የሚሠራው በውስጡ ሊቋቋመው የማይችለው ክፉ ኃይል በመኖሩ ነው። አንዳንድ ጊዜ የሚያደርጉትን ሳያውቁ በደመ-ነፍስ አንዳንድ ተግባራት እንደሚያከናውኑ ይታመናል።

ጠንቋዮች አንድም ከዚህ ክፉ ኃይል ጋር እንደሚወለዱ ወይም የጠንቋዮች ማኅበረሰብ አካል በመሆን እንደሚያገኙት ይነገራል። ጠንቋይ በውስጡ የሚገኘው ክፉ መንፈስ አስረኛ እንደ ሆነ ይታመናል። ስለ ሆነም፥ ጠንቋዮች ክፉ ተግባራቸውን ለመፈጸም ሥርዓታዊ ቃላት፥ ምትሐት፥ ድግምት ወይም እርግማን መጠቀም አያስፈልጋቸውም።

ይልቁንም፥ ክፋትን ለመፈጸም የሚያስችለው ኃይል ከውስጣቸው ይመጣል።

የጥንቆላ ተግባር ጠንቋይ በእንቅልፍ ውስጥ ሳለ ሳይታወቅ እንደሚፈጸም ይታሰባል። ጠንቋይ ሰውነቱን ጥሎ በሌሊት የሰውን ሥጋ ለመብላት በረራ እንደሚያካሂድ ይታመናል። ጠንቋይ (ወይም ቡዳው) የሰውን ሥጋ ሲበላ፥ ሰውየው ደካማና በሽተኛ በመሆን በመጨረሻ እንደሚሞት ይታመናል። ይህ ስለ ጠንቋይና ጥንቆላ የሚነገረው እምነት በብዙ የአፍሪካ ክፍሎች በጣም ጠንካራ ነው።

አንዳንድ ደካማ ክርስቲያኖችን ጨምሮ፥ ብዙ ሰዎች ጠንቋዮችንና አስማታቸውን በሕይወታቸው ከማንኛውም ነገር አስበልጠው ይፈራሉ። ስለ በሽታ በተነጋገርንበት ክፍል እንደ ተጠቀሰው፥ ለጥንቆላ የሚኖረው ፍርሃት እጅግ ታላቅ በመሆኑ ሰዎች የአካልን ወይም የአእምሮን ሕመም የሚያመለክቱ ምልክቶች ሊያሳዩ ይችላሉ። ትክክለኛ የጥንቆላ ተግባር ቢኖርም ባይኖርም፥ ራሱ የፍርሃትን ኃይል ማናናት የለብንም።

መጽሐፍ ቅዱስ አስማትና ጥንቆላ እንዳሉ ቢገልጽም፥ በሁለቱ መካከል ጠንካራ ልዩነት አይመሠርትም፤ ለምሳሌ፥ በሚከያስ 5:12 እና ናሆም 3:4 ላይ ተመሳሳይ የዕብራይስጥ ቃል (በአማርኛ «መተት» ተብሎ የተተረጎመው) በተለያዩ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ እትሞች አስማትና ጥንቆላ ተብሎ ተተርጉሞአል። ጥንቆላ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደ ተብራራው ከተቀሩት አስማቶች ጋር ተመሳሳይ የኅላማ ባሕርይ አለው። በዘዳግም 18:10-11፤ ኢሳይያስ 47:9፥ 12 እና ሚከያስ 5:12 እንደምንመለከተው፥ ብዙውን ጊዜ ከድግምት አሠራር ጋር ተያይዞ ተጠቅሶአል።

መጽሐፍ ቅዱስ ድግምቶችና እርግማኖች፥ ብሎም እንደ ጠንቋዮችና አስማተኞች ያሉ ሰዎች ኃይል እንዳላቸው ይገልጻል። ይሁንና፥ ኃይላቸው ሁሉን ቻይ ከሆነው አምላክ ጋር ሲነጻጸር ኢምንት ነው (ኢሳ. 47:9)። ይህም የቱንም ያህል ከፍተኛ ጥንቃቄ ቢውጠነጠንም፥ ክርስቲያን የአስማተኛን ወይም የጠንቋይን ድግምቶች ወይም እርግማኖች መፍራት እንደሌለበት ግልጽ የሆነ ፍንጭ ይሰጠናል። በክርስቲያን ልብ ውስጥ የሚኖረው ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ከማንኛውም በአጽናፈ-ዓለም ካለው አስማተኛ፥ ጠንቋይ፥ ከፉ መንፈስ ወይም ከፉ ኃይል ህልቆ መሳፍርት ጊዜ ይልቃል። እንደ እውነቱ ከሆነ፥ እንዲህ ዓይነት ሰዎችና ኃይላት በክርስቲያኑ ልብ ውስጥ በሚያድረው ክርስቶስ ፊት ይንቀጠቀጣሉ። ይህም ሐዋርያው ጴጥሮስና ዮሐንስ በተገኙበት ስፍራ ራሱን ባሞረደው

የሳምራዊው አስግተኛ ሲሞን ታሪክ ውስጥ ተመልክቷል (የሐዋ 8:9-24)። በተጨማሪም፥ በክርስቶስ ፊት ዝቅ ብሎ በታየው የጌርሴናን አጋንንትም ገጠመኝ ተስተውሷል (ማር. 5:1-8)።

አስግትና ጥንቆላ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተጠቀሱበት ስፍራ ሁሉ፥ ሆን ተብለው በዓላማ የሚከናወኑ ክፉ ተግባራት እንደ ሆኑ ተገልጸአል። በዘሌዋውያን 19:26 እና ዘዳግም 18:10 ላይ እንደምንመለከተው፥ እግዚአብሔር በከፍተኛ ደረጃ የኃጢአት ተግባሮች እንደ ሆኑ በመግለጽ ኮንኖአቸዋል። የንጉሥ ሕዝቅያስ ልጅ ምናሴ አስግትና ጥንቆላ በመከተሉ እግዚአብሔር በከፍተኛ ደረጃ ኮንኖታል (2 ነገሥት 21:6፤ 2 ዜና 33:6)። ምትሐት በብዛት የአስግተኛ ተግባር አካል በመሆኑ፥ ለመልካም ወይም ለክፉ ዓላማ ይከናወናል ቢባልም፥ እግዚአብሔር የምትሐትን አጠቃቀም በሙሉ እንደሚኮንን ከዚሁ እንረዳለን።

ምንም እንኳ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጠንቋዮች ከላይ እንደ ተገለጸው ልዩና ለመቆጣጠር የማይቻል አድርጎ ባያቀርብም፥ በአጋንንት ስለ ተያዙት ሰዎች ይናገራል። በአጋንንት የተያዙ ሰዎች በውስጣቸው የሚገኙትን አጋንንት ርኩስና ክፉ ባሕርያት ያሳያሉ። በምዕራፍ አሥራ አንድ እንደ ተመለከትነው፥ አጋንንት ሰዎችን በበሽታ፥ በአካል ስንኩልነትና በሞት ማሠቃየትን ጨምሮ አያሌ የክፋት ተግባራት ያከናውናሉ። ስለ ሆነም፥ ክፋትን ይፈጽሙ ዘንድ ኃይል የሚሰጡአቸው ክፉ ኃይላት በውስጣቸው ያሉባቸውና በአጋንንት የተያዙ ሰዎች መኖራቸውን ለማመን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት አለን። አንዳንድ ወንጀለኞች ወንጀሉን በፈጸሙበት ጊዜ፥ ውስጣዊ ክፉ ኃይል ይገፋፋቸው እንደ ነበር በችሎት ፊት መስክረዋል። ብዙ ሰዎች እንግዳና ክፉ ተግባራት እንዲፈጽሙ የሚገፋፉ ድምፆች ከውስጣቸው ሆነው ሲናገሩ መስማታቸውን መስክረዋል።

ይህን ዓይነቶቹ ምስክርነቶች አጋንንት በሰዎች ውስጥ እንደሚኖሩና እንደሚሠሩ ያረጋግጣሉ። እነዚህ ሰዎች አሁንም ለሚፈጽሙአቸው ተግባራት ተጠያቂዎች ቢሆኑም፥ የሰዎቹ ባሕርያት በውስጣቸው በሚኙ አጋንንት እንደሚመሩ ያሳየናል። እነዚህ ሰዎች በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ራሳቸውን ለኃጢአት አሳልፈው በመስጠታቸው፥ አጋንንት በአእምሮአቸውና በፈቃዳቸው ላይ የቁጥጥር ተጽዕኖ እንዳገኙ ያሳየናል! ይህም በመሆኑ፥ ጠባያቸው በውስጣቸው የሚገኙ አጋንንት ክፉ ፍላጎት በመሆን ይቀየራል። በመጽሐፍ ቅዱስ በአጋንንት የመያዝ ትርጉሙ

ይሽው ነው። ስለ ሆነም፥ በጌርሴናን የአጋንንት ግደርያ የነበረው ሰው የእርሱን ሰውነት ሲቆርጥና ሲያሠቃይ፥ ብሎም በሙታን መቃብር አካባቢ ሲባዝን እንመለከታለን (ማር. 5:5)። ንጉሥ ሳኦል የአጋንንት መስፈሪያ በሆነ ጊዜ፥ የእርሱን ልጅ ዮናታንን ለመግደል አስኪሞክር ድረስ ጨካኝ የግድያ መንፈስ አደረበት (1 ሳሙ. 16:14፤ 20:32-33)።

በአጋንንት የተያዙትን ሰዎች በተመለከተ፥ አፍሪካውያን ስለ ጠንቋዮች ያላቸው አስተሳሰብ በአጋንንት ከተያዘ ሰው ጋር ሊነጻጸር ይችላል። በእንዲህ ዓይነት ሰዎች ውስጥ የሚኖሩ ክፉ ኃይላት አጋንንት ናቸው። በሌሊት እንደ አውሬ በጩኸት የመብረርና የሰው ሥጋ የመብላት አሳቦች የባህላዊ እምነት ጉዳዮች ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ግን እንዲህ ዓይነት እምነቶችን አይገልጽም።

ከመጽሐፍ ቅዱስ የምንረዳው በአጋንንት የተያዙ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ በሰይጣን ኃይል እንግዳ አጋንንታዊ ተአምራት ሊፈጽሙ መቻላቸው ነው (2 ተሰ. 2:9)።

አንድ ጠንቋይ ወይም አስማተኛ ዓይነት ክፉ ሰው በአንድ ሰው ላይ ድግምት ወይም እርግማን ቢያደርግ፥ አጋንንት ከድግምቱ ወይም ከእርግማኑ አኳያ ሊሠሩ እንደሚችሉ የሚያጠራጥር አይደለም። እግዚአብሔር ካልከለከላቸው በቀር አጋንንት ድግምት ወይም እርግማን በተፈጸመበት ሰው ላይ በሽታ ወይም መከራ ሊያመጡ ይችላሉ። እግዚአብሔር ሰይጣን በኢዮብ ላይ ታላቅ መከራና ጉዳት እንዲያመጣ ፈቅዶአል። የሰይጣንና የአጋንንት ተግባር ሞትንም እንኳን ሊያስከትል ይችላል። ይህም ምናልባትም በሰይጣን ወይም በወደቁ መላእክት አማካኝነት በተከሰተው ከፍተኛ ዐውሎ ነፋስ በሞቱት የኢዮብ ልጆች ላይ ተፈጽሞአል። በተጨማሪም፥ አጋንንት አደጋዎችን፥ ወንጀልና ሌሎችንም ዓይነት የክፋት ተግባራት ሊፈጽሙ ይችላሉ።

ክርስቲያኖች ግን የነገሥታት ንጉሥ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በውስጣቸው ስለሚኖርና ከእነዚህም መናፍስት ህልቆ መሳፍርት ጊዜ ስለሚልቅ፥ ከጠንቋዮችና ከክፉ መናፍስት ፍርሃት በላይ ከፍ ብለው በመተማመን ሊመላለሱ ይችላሉ (1 ዮሐ. 4:4)። እግዚአብሔር ክርስቲያኑን ከወደቁት መላእክት ከፍ አድርጎ በክርስቶስ ውስጥ አስቀምጦአቸዋል (ኤፌ. 1:20-21፤ 2:6)። ኢየሱስ ለተከታዮቹ የሰይጣንን ኃይል ሁሉ እንዲያሸንፉ ሥልጣን እንደ ሰጣቸው ተናግሯል (ሉቃ. 10:19)። ይህ የቃላት ጉዳይ ሳይሆን በክርስቶስ የሚገኝ እውነተኛ

መንፈሳዊ ሥልጣን ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች አጋንንትን የማስወጣት ሥልጣን አላቸው (ሉቃ. 10:17)።

እንደ አስማተኞችና ጠንቋዮች ያሉ የአጋንንት ኃይል ማደሪያዎች፥ በሽታ በማምጣትና መልሶ በመውሰድ እውነተኛ ፈውስ እንደ ተፈጸመ ሊያስመስሉ ይችላሉ። በአንዳንድ ባህላዊ ሰዎች ላይ የሚስተዋለው ክፉ ዓይን አጋንንታዊ ኃይል ነው። የክፉ ዓይን ሥልጣን ያላቸው ሰዎች ዓይናቸውን በሰዎች ላይ በማሳረፍ፥ የከፋ አካላዊ ወይም አእምሮአዊ መዛባት ሊያስከትሉ ይችላሉ። ባህላዊ የመድኃኒት አዋቂ (ፈዋሽ) አጋንንታዊ ኃይሎች ሊኖሩት ይችላሉ። ባህላዊው ፈዋሽ በአስማተኛ፥ በጠንቋይ፥ ወይም ክፉ ዓይን ባለው ሰው አማካኝነት አጋንንት ያመጡትን በሽታ ሊያስወግድ (የሚፈውስ ሊመስል) ይችላል። በዚህ ዓይነት፥ ሰይጣን በአስማትና በባህላዊ ሃይማኖት፥ ብሎም በጠንቋዮች ላይ የሚመሠረተውን እምነት ሊያጠናክር ይችላል። ይህንንም በማድረግ፥ ሰይጣን ሰዎችን እግዚአብሔር በኮነናቸው ነገሮች እንዲታመኑ ይፈትናቸዋል። ለአጋንንታዊ ፈውስ የሚከተለውን እውነተኛ ታሪክ ተመልከት፡—

በመንደሩ ከፋ ዓይን እንዳላት የምትታወቅ አንዲት ሴት አንድ ሕፃን ከመሬት ብድግ አድርጋ አቀፈች። በዚያው ዕለት ሕፃኑ ከፍተኛ የሆድ ሕመም ደረሰበት። ልጁ እያደገ ሲሄድ ሕመሙም እየቀጠለ ሄደ። የልጁ ወላጆች ልጁን ወደ ተለያዩ የሕክምና ጣቢያዎች ቢወስዱትም፥ ችግሩ አልተቃለለም። የመንደሩ ሰዎች የልጁ ወላጆች ወደ ጠንቋይ እንዲሄዱ በከፍተኛ ደረጃ ገፋፉአቸው። ወላጆቹ ግን ይህንኑ አሳብ ለረዥም ጊዜያት ሲቃወሙት ቆይተው ነበር። ይሁንና፥ የልጁ ችግር እልባት ሲያጣ ወላጆቹ በመጨረሻው የጎረቤቶቻቸውን ግፊት ተቀበሉ። ባህላዊ ፈውስ በማካሄድ የታወቀችውን ሴት ጠሩዋትና የበሽታውን መንስዔ ለማስወገድ «መንፈሳዊ ቀዶ ጥገና» አደረገች። ሕመሙም ወዲያው ልጁን ለቀቀውና ሳይመለስበት ቀረ።

በግልጽ እንደሚታየው፥ በመጀመሪያ ደረጃ ሕመሙን ያመጡት አጋንንት ሲሆኑ፥ ዳግም ፈውስ መሳይ ማታለያ ሠርተዋል። እግዚአብሔር ለምን እንደዚህ ዓይነት ወላጆች በአጋንንታዊ ኃይል በግልጽ እንዲታለሉ እንደሚፈቅድ ከመጠየቅ በቀር ምንም ልንፈይድ አንችልም። በመጀመሪያ ደረጃ ለምን ልጁ እንዲታመም ይፈቅዳል? ይህንን ጥያቄ ለመመለስ፥ ሰዎች በትጋት ሊከተሉት የሚገባው ምርጫ በእግዚአብሔርና እርሱ በሚሰጣቸው የተሰፋ ቃሎች መታመን ብቻ እንደ ሆነ ልብ ልንል ይገባል። ሔዋን ከእግዚአብሔር እውነትና ከሰይጣን ውሸቶች መካከል አንዱን

መምረጥ እንደ ነበረባት ሁሉ፥ ዛሬም ክርስቲያኖች ተመሳሳይ ምርጫዎችን ማድረግ አለባቸው። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ሰይጣን ወይም አጋንንቱ ኢዮብን እንዲፈትኑ እንደ ፈቀደው፥ ዛሬም ሕዝቡን እንዲያውኩ ይፈቅዳል። ይሁንና፥ እግዚአብሔር በቃሉ የተስፋ ቃሎች አማካኝነት እንዲህ ዓይነት የክፉውን ጥቃቶች የምናሸንፍባቸውን መንፈሳዊ የጦር ዕቃዎች ሰጥቶናል። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ ጦር አንሡ» ይላል (ኤፌ. 6:16)።

ክርስቲያኖች አስማት፥ ምትሐት፥ ድግምት፥ ወይም እርግማን እንደ ተደረገባቸው ሲጠረጥሩ ምን ማድረግ አለባቸው?

ከሰይጣንና አጋንንት የተነሣ አስማት፥ ምትሐት፥ ድግምትና ርግማን ኃይል ስላላቸው፥ በሕይወት ቅጽበት የሚመላለስ ክርስቲያን የጠንቋዮችን ኃይል ለማፈራረስ ከጌታ ዘንድ ሥልጣን አለው፤ እንዲሁም፥ የእነዚህን ምትሐት፥ ድግምትና ርግማን ኃይል በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሊበታትን ይችላል። ኢየሱስ ክርስቶስ በመናፍስት ሁሉ ላይ ኃይል ስላለው፥ አስማቱ ወይም እርግማኑ ይፈርሳል።

ክርስቲያን የሚከተለውን ዓይነት ነገር ሊናገር ይችላል፦ «ይህንን ድግምት (ወይም እርግማን) በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አፈርሳለሁ» ወይም፥ «የዚህን አስማተኛ (ወይም ጠንቋይ) ኃይል በመካድ፥ በእኔ ላይ የተሰለፉትን እነዚህ ከፉ ኃይላት ይበታትን ዘንድ የጌቶች ጌታና የንጉሥታት ንጉሥ የሆነውን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም እጠራለሁ።» የዚህ ዓይነቱን የመንፈሳዊ ውጊያ ጸሎት በማድረግ፥ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ጠላቶች በመቃወም እንዲህ ዓይነት አያሌ ጸሎቶችን ካቀረበው መዝሙረኛ ጋር ይተባበራል። ለእንዲህ ዓይነት የመንፈሳዊ ውጊያ ጸሎቶች መዝሙር (35):1-10፤ (83):1-3፥ 13-18 በምሳሌነት ተመልከት።

በሉቃስ 10:17 የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት፥ «ጌታ ሆይ፥ አጋንንት እንኳ በስምህ ተገዝተውልናል» ብለዋል። ከዚያም ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ፥ «በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ» ብሏል (ቁ. 19)። በተጨማሪም፥ ክርስቲያን አስማት፥ ምትሐት፥ ድግምት ወይም እርግማን በሽታ አድርሰውበት ከሆነ፥ ጌታ እንዲፈውሰው ሊጸልይ ይችላል። ከጌታ ጋር የቅርብ ግንኙነት ኖሮአቸው በሚመላለሱ ክርስቲያኖች አፍ ሲነገሩ፥ እነዚህ ቃላት ከፍተኛ ኃይል አላቸው።

ኢየሱስ ክርስቶስ በአጽናፈ-ዓለም ውስጥ በሚገኙ ፍጥረታት ሁሉ ላይ ሥልጣን አለው (ኤፌ. 1:20-22)። ክርስቶስ በሁሉም አማኝ ልብ ውስጥ ስለሚኖር (ዮሐ. 14:23)፥ ለክርስቲያን የሚያስፈልገው የኢየሱስን ስም በመጥራት በቃላት የአጋንንትን ኃይል ማፍረስ ብቻ ነው፤ በዚህም ጊዜ በክርስቲያኑ ውስጥ በሚኖረው በክርስቶስ ኃይሉ ይፈራርሳል። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «አሸንፋችሁዋል፥ በዓለም ካለው ይልቅ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና» ይላል (1 ዮሐ. 4:4)። በአጽናፈ-ዓለሙ ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስን ሊቋቋም የሚችል አጋንንት ወይም የወደቀ መልአክ የለም።

አስማት፥ ጥንቆላ፥ እርግማንና ድግምቶች ኃይል ከሚሰጣቸው ከአጋንንት የተነሣ በትክክል ይሠራሉ፤ ይሁንና፥ የምድርና የሰማይ አምላክ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ከፉ መናፍስትን በማሸነፍ እንዲህ ዓይነት አስማቶችን ያጠፋል። ጌታ ብርሃኑና መድኃኒቱ ስለ ሆነ፥ ክርስቲያን በፍርሃት መኖር አያስፈልገውም [መዝ (27):1፤ 2 ጢሞ. 1:7]። እግዚአብሔር በጳውሎስ በኩል፥ «በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ (አትፍሩ)» ይለናል (ፊልጵ. 4:6)።

መ. ክርስቲያን የጉቦኛነትን ችግር እንዴት ሊመለከት ይገባል?

በአንድ የክርስቲያን ትምህርት ቤት ውስጥ መምህር የሆነው ጆሹዋ፥ የእርሻ ተግባራት ለማከናወን ፈልጎ ትንሽ መሬት ገዛ። በአገሩ የሚገኘው የግብርና ሚንስቴር በቅርቡ አንዳንድ የእርሻ መኪኖች (ትራክተሮች) ገዝቶ ነበር። ለእርሻው ሥራ እነዚህን ትራክተሮች መከራየት ይቻል ነበር። ጆሹዋ የእርሻ ወቅት ከመድረሱ በፊት ወደ ግብርና ሚንስቴር በመሄድ መሬቱን ለማልማት ስለሚከራየው ትራክተር ተነጋገረ። ከዚያም ትራክተሩን ለማቆየት የሚረዳ የቀብድ ገንዘብ ከፈለና ትራክተሩን የሚወስድበት ቀን ተነገረው።

ቀነ-ቀጠሮው ሲደርስ የትራክተሩ ሾፌር ትራክተሩን ሳይዝ በእግሩ መጣ። ሰውየውም ትራክተሩ በጥገና ላይ እንደ ሆነ ገለጸለት። ጆሹዋ ለሚቀጥሉት ሁለት ሳምንታት ከቢሮው ጋር መገናኘቱን ባያቋርጥም፥ በሚሄድበት ጊዜ ሁሉ የሚሰጠው፣ «ትራክተሩ አሁንም ገና እየተጠገነ ነው» የሚል አንድ ዓይነት ምላሽ ነበር። ጆሹዋ በሁለተኛው ሳምንት ሾፌሩ የጎረቤቱን መሬት ለማረስ በትራክተሩ ሊጠቀም ተመለከት። ከዚያም ወደ ሾፌሩ ዘንድ በመሄድ ትራክተሩን ለወቅቱ እንደ ተከናተረ

በግግረር ገለጸለት። በመጨረሻም ፖሬሩ ጀሹዋ መሬቱ እንዲታረስለት ከፈለገ የተለየ (እና በጣም የበረከተ) ገንዘብ መክፈል እንዳለበት በግልጽ አስታወቀው።

ጀሹዋ የተፈለገውን ሒሳብ ከከፈለ በኋላ ፖሬሩ ባለመተባበሩ አግረረ። በኃላፊነት ወንበር ላይ ለተቀመጠው የሚንስትሩ ባለሥልጣን ሁኔታውን ቢገልጽም ትራክተሩን ማምጣቱና ማረሱ በፖሬሩ መርሐ ግብር እንደሚከናወን ተነገረው። ጀሹዋን ለመርዳት ምንም ሊያደርጉ አይችሉም ነበር። ጀሹዋ በሁኔታው በጣም ተናደደ፤ መሬቱም ሳይታረስ ቆየ። ፖሬሩም ያለ ጉቦ እንደማይሠራ ግልጽ ነበር። በመጨረሻም፥ ጀሹዋ መሬቱን የሚቆፍሩለትን ሰዎች ለመቅጠር ተገደደ።

ጀሹዋን በዚህ ጊዜ ብታገኘው ኖሮ፥ ምን እንዲያደርግ ትመክረው ነበር? እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ ክርስቲያን የጉቦን ችግር እንዴት ሊያስተናግደው ይገባል?

በዓለም በሁሉም አገሮች ለማለት ይቻላል የጉቦኛነት ችግር ተንሰራፍቶ ይታያል። አንድ ክርስቲያን የተወሰነ የጉቦ ጉዳይ በተሳካ ሁኔታ ከማስተናገዱ በፊት መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ብልሹ ተግባር ምን እንደሚል ማወቅ አለበት። ባጋጠመህ ጊዜ ከከባድ ውሳኔ ጋር ከመፋጠጥ ይልቅ፥ እንደዚህ ባሉ ጉዳዮች ላይ በጥንቃቄ ማሰቡና ቀደም ብሎ መወሰኑ ከሁሉም የተሻለ ነው። አንድ ነገር ከመድረሱ በፊት አእምሮህ የሚሠራውን የሚያውቅ ከሆነ፥ ጠንካራ ፈተናዎችን ልትቋቋም ትችላለህ።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጉቦ ምን ይላል?

በጉቦ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ከእግዚአብሔር ቃል አንዳንዶቹ እንዲህ ይላሉ፦ «ጻድቁን የምታስጨንቁ፥ ጉቦንም የምትቀበሉ፥ በበሩም አደባባይ የችግረኛውን ፍርድ የምታጣምሙ እናንተ ሆይ፥ በደላችሁ እንዴት እንደ በዛ፥ ኃጢአታችሁም እንዴት እንዳደገ እኔ አውቃለሁና» (አሞ. 5:12)። በዚህ ጥቅስ እግዚአብሔር ጉቦ በችሎት ፊት የድህውን ፍርድ የማጣመምን ያህል ኃጢአት እንደ ሆነ ይገልጻል። በዘጸአት 23:8 ጌታ፥ «መማለጃን አትቀበል፤ መማለጃ የዓይናማዎችን ሰዎች ዓይን ያሳውራልና፥ የጻድቃንንም ቃል ያጣምማል» ይላል። ጉቦ መቀበል፥ ያለ ጉቦ ትክክለኛውንና ትክክል ያልሆነውን ይለዩ የነበሩትን ሰዎች ዓይን የሚያሳውር ከሆነ፥ ጉቦ መስጠቱም ኃጢአት ነው። ጉቦ መስጠት የሚቀበለውን ሰው የማበላሸት ውጤት አለው። ጉቦ መስጠት አንድ ሰው ፍትሕን ትቶ ሕግን እንዲያፈርስ መፈተን ነው።

ጉቦ ስሕተት የሆነው ለምንድን ነው?

ምሳሌ 15:27 ጉቦ ስግብግብነትን እንደሚጨምር ይገልጻል። ስግብግብነት (የገንዘብ ፍቅር) በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ ክፋትና ኃጢአት ነው። አዲስ ኪዳንና ሰብአዊ ልምዶች እንደሚያስተምሩን ስግብግብነት ሰዎችን ያጠፋል (1 ጢሞ. 6:9)። ሰዎች በገንዘብ ሲታመኑ በእግዚአብሔር መታመን ይሳናቸዋል (1 ጢሞ. 6:17) ። ሰዎች ከስግብግብነት የተነሣ ይሠርቃሉ፤ ይገድላሉ። ከገንዘብ ፍቅር የተነሣ በዓለም በዓመቱ ብዙ ግድያዎች ይፈጸማሉ። ከስግብግብነት የተነሣ አገሮች ለጦርነት ይዘምታሉ። የአስቆሮቱ ይሁዳ በገንዘብ ፍቅር ተሸንፎ ኢየሱስ ክርስቶስን አሳልፎ ሰጥቷል (ማቴ. 26:14-15) ። ከዚህም የተነሣ ይሁዳ ነፍሱን አጥቷል። ጉቦኛነት በግልጽ ስግብግብነትን ይጨምራል፤ ስግብግብነትም ሕዝቦችንና አገሮችን ያጠፋል።

ምሳሌ 17:23 እና ዘዳግም 16:19 ጉቦኛነት ሐቅን እንደሚያዛባ ያስተምራሉ። «ጉቦ የጥበበኞችን ዓይን ያሳውራልና፥ የጻድቃንንም ቃል ያጣምማልና፥ ጉቦ አትቀበል» (ዘዳ. 16:19)። መክብብ 7:7 «ጉቦም ልቡን ያጠፋዋል» ይላል። ስለ ሆነም ጉቦኛነት ለማኅበረሰባዊ ብልሹነት አስተዋጽኦ በማበርከት ለሁሉም ሰው ሕይወትን አቀበት ያደርጋል።

ከዚህ በላይ ጀሹዋ የተጋፈጠውን ችግር ተመልከት፤ ለሾፈሩ ጉቦ ቢሰጥ ኖሮ ሾፈሩ በሕግ ተሳላፊነቱና ለግል ጥቅሙ ገበሬዎችን በመጨቆን እንዲገፋ ማበረታታቱ ነበር። የአገሩ ሕግ በግብርና ሚንስቴር ተገቢ ሒሳብ ከተከፈለ የገበሬው መሬት ያለ ምንም ተጨማሪ ክፍያ እንደሚታረስለት ይገልጻል።

ጀሹዋ ጉቦ ለመስጠት ባለመፈለጉ መሬቱ የዝናቡ ወራት ከግለፋ በፊት በትራክተር አልታረሰለትም። በመጨረሻም ብዙ ሰዎችን በመቅጠር በቁፋሮው እንዲረዱት ለማድረግ ተገደደ። ምንም እንኳን በእግዚአብሔር ፊት ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ የወሰደው እርምጃ ከባድና ተጨማሪ ገንዘብ የሚያስወጣው ቢሆንም፥ ለትራክተሩ ሾፌር ግን ጉቦ አለመስጠቱ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰነዘረ ተግሣጽ ያህል የጉቦኛነት ክፉ ባሕርይን የሚጠቁም ነበር። ከዚያም በላይ ጀሹዋ በምሳሌነቱ በትምህርት ቤቱ የሚገኙ ሌሎች ክርስቲያኖች ጉቦ የመስጠቱን ፈተና እንዲቋቋሙ አበራትቶአቸዋል። ጌታ ታማኝ በመሆኑ፥ ለጀሹዋ የሚያስፈልገውን አዘጋጅቶለታል። ከሁሉም በላይ ጀሹዋ ለጻድቅ ባሕርዩ በሰማይ ከኢየሱስ እጅ ሽልማት ተቀብሏል።

በግኅበረሰቡ ውስጥ በዚህ የኃጢአት ልምምድ ውስጥ የማይካፈሉ ብርቱ ክርስቲያኖች ከሌሉ፥ ሰዎች ከጉቦኛነት ጠንቅ እንዴት ሊላቀቁ ይችላሉ? ብዙ ክርስቲያኖች ያለ ጉቦ ነገሮች ሊከናወኑላቸው እንደማይችሉ በማመናቸው በዚህ ተግባር ተሰማርተዋል። እግዚአብሔር ባይኖር ኖሮ ይህ እውነት ይሆን ነበር። እግዚአብሔር እስካለ ድረስ ግን ክርስቲያን ሊጸልይና የእግዚአብሔርን እርዳታ ሊጠይቅ ይችላል። እግዚአብሔር የሞተውን ሰው ሊያስነሣ ከቻለ ያለ ጥርጥር እንደዚህ ዓይነቱን ጸሎት ሊመልስ ይችላል።

የክርስቲያኑን ጸሎት በመመለስ እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ ምስክርነቱን ይጠብቃል። የክርስቲያኑን መሻት በሌላ መንገድ ሊያሟላ ይችላል። የሌሎችን ሰዎች ልብ ለመለወጥ የክርስቲያኑን ተግባር ሊጠቀም ይችላል። በጉቦ ተግባር ባለመሰማራት ክርስቲያን ከማኅበረሰቡ ሁሉ ብልሹነትን ሊቀንስ ይችላል። በአንዲት አገር የሚኖሩ ክርስቲያኖች ሁሉ በጉቦ ተግባር ላይ ባይሳተፉ የአገሪቱ ባህል ይለወጣል።

በጉቦኛነት ተግባር ላይ ለመሳተፍ የማይፈልግ ክርስቲያን እንደ ጅሎዋ ሁሉ በከፉ ሰዎች መከራ መቀበሉን ወይም መሰደዱን መታገሥ አለበት። መጽሐፍ ቅዱስ ከመከራና ስደት እንደምናመልጥ የተስፋ ቃል አይገባልንም። ይልቁንም እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚረዳ ቃል ይገባልናል። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በታማኝነት የሚያገለግሉትን እንደሚሸልም ቃል ይገባልናል። በዮሐንስ 12:26 ኢየሱስ፥ «የሚያገለግለኝም ቢኖር አብ ያከብረዋል» ብሏል። በማቴዎስ 5:11-12 ኢየሱስ፥ «ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዱአችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁአን ናችሁ። ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ፥ ሐሤትም አድርጉ» ብሏል። ወደ መንግሥተ ሰማይ እስክንደርስ ድረስ ስለ በጎ ተግባራችን ሽልማቱ ላይደርስን ይችላል።

ጉቦ ብንሰጥ ለጊዜው የምንፈልገውን እናገኝ ይሆናል፤ በሰማይ ግን እናዝናለን። በተጨማሪም ጉቦ በመስጠት አብረውን የሚያመልኩትን ክርስቲያኖች እምነት እናደክማለን። እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን እንደሚሰጠን መተማመን አለብን። ለሌሎች ክርስቲያኖች ጠንካራ ምሳሌነት መተው አለብን። ጉቦንና ሌሎች ብልሹ ልምምዶችን በተመለከተ ክርስቲያኖች ሊከተሉአቸው የሚገቡ ምርጫዎች እንደዚህ ዓይነት ናቸው።

ማጠቃለያ

ከአዳምና ሔዋን ዘመን ጀምሮ የሰው ልጅ በመከራ ውስጥ ሲያልፍ ቆይቷል። የመከራውም ምክንያት አዳምና ሔዋን በኤደን ገነት በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ ማመፃቸው ነበር። እግዚአብሔር አዳምን በኤደን ገነት ሲያስቀምጠው «ከእርሱ (ከተከለከለው የዛፍ ፍሬ) በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና» በማለት አስጠንቅቆት ነበር (ዘፍጥ. 2:17)። አዳም ወይም የተቀረው የሰው ልጅ በኃጢአት ላይ የሚወርደው የሞት ቅጣት ምን ያህል የከፋ እንደ ሆነ ብዙም አላስተዋሉም ነበር። ከኃጢአት ከፋ ውጤቶች የተነሣ መከራ ተፈጥሮን ጨምሮ ሁሉንም የሰው ልጅ የህላዌ ክልሎች ዳስሶአል (ሮሜ 5:12፤ 8:20-21) ። ይሁንና አሁንም አንዳንድ ሰዎች ከሌሎች የበለጠ ለምን መከራ እንደሚቀበሉና እንዳንዱም መከራ ለምን ፍትሕ የጎደለው እንደሚመስል ምሥጢር ነው። ብዙውን ጊዜ ወንጀለኞች ከቅጣት ሲያመልጡ፥ ንጹሑ ሰው በክፉዎች እጅ የሚሠቃይበትና ጻድቁ መራራ መከራ የሚቀበልባቸው ጊዜያት አሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ለሰው ልጆች ሁሉ አንድ የመጨረሻ የፍርድ ቀን እንደ ተቀጠረና በዚያን ጊዜም ሰዎች ለተናገሩአቸው ቃላትና ለፈጸሙአቸው ተግባራት ምላሽ እንደሚሰጡ ይነግረናል (ማቴ. 12:36፤ ራእይ 20:11-15)። በተጨማሪም አንድ ቀን ሰይጣንና መላእክቱ በምድር ላይ ለፈጸሙት ታላቅ ክፋት ዋጋ ይከፍላሉ (ማቴ. 25:41፤ ራእይ 20:10)። በዚህ ሕይወት በክፉ ሰዎችና በክፉ መላእክት የተሠቃዩ ጻድቃን ከእግዚአብሔር ዘንድ ዘላለማዊ ሽልማት ይመጣላቸዋል፤ ይህም እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ገለጻ የዚህ ዓለም መከራ ከምንም የሚቆጠር እንዳልሆነ የሚያሳይ ነው (ማቴ. 5:11-12፤ ሮሜ 8:18) ።

በሽታ በዚህ ሕይወት የመከራ ገጽታ ሲሆን ይህም በበኩሉ ከሰው ልጅ ኃጢአት ጋር የተያያዘ ነው። ይሁንና ብዙውን ጊዜ ለአንድ ለተወሰነ በሽታ ምክንያቱን ማወቅ አስቸጋሪ ነው። አንዳንድ በሽታ በቀጥታ በአንድ የተወሰነ ኃጢአት ምክንያት የሚመጣ ሲሆን፥ ሌላው ደግሞ በአለማት ወይም በጥንቆላ በኩል በአጋንንት ኃይል የሚመጣ ነው። አንዳንድ በሽታ ከታማሚው አእምሮአዊ ወይም ስሜታዊ ሁኔታ ጋር የተያያዘ ሲሆን፥ ብዙውን ጊዜ የዚህ ዓይነት ስሜታዊ ችግሮች የሚመጡት ከፈራረስ የሰዎች ግንኙነት ነው። አብዛኛው በሽታ የሚመጣው በሽታውን የሚያስከትሉ የተወሰኑ ተሐዋስያን ሲተላለፉብን ነው። የሕመሙ መነሾ ምንም ቢሆን እግዚአብሔር መሐሪ በመሆኑ ብዙውን ጊዜ በጸሎትና

በእስተግግኝ መድኃኒቶች አግኳኝነት ፈውስን ይልካል። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ያለ ምንም መድኃኒት ይፈውሳል።

መጽሐፍ ቅዱስ አስግት፥ ጥንቆላ፥ ምትሐት፥ ርግግንና ድግምቶች የሰይጣን ሥራ አካላት እንደ ሆኑ ይናገራል። ይሁንና፥ ኢየሱስ ከክፉ መናፍስት እጅግ አብዝቶ ስለሚበልጥና በሁሉም እውነተኛ ክርስቲያን ልብ ውስጥ ስለሚኖር (1 ዮሐ. 4:4)፥ ክርስቲያኖች እነዚህን ክፉ ኃይላት ሳይፈሩ በመተግመን ሊመላለሱ ይችላሉ። ክርስቲያን በእነዚህ የአጋንንት ኃይላት እንደ ተጠቃ ከተጠራጠረ፥ ያፈራርሳቸው ዘንድ የክርስቶስን ስም ሊጠራ ይችላል። ኢየሱስ በጌርጌሴኖኑ ሰው ውስጥ የሰፈሩትን የአጋንንት ጭፍራ (ሌጌዎን) ለግስወጣት በቀረበ ጊዜ በፊቱ እንደ ተንቀጠቀጡና እንዳያመታያቸው እንደ ለመኑት ግስታወሱ መልካም ነው (ሉቃ. 8:26-31)።

በጉቦና በምግባረ ብልሹነት አያሌ ችግሮች ተከስተዋል። ክርስቲያኖች የሚፈልጉአቸው ነገሮች ይፈጽሙላቸው ዘንድ ጉቦ ለመስጠቱ ግፊት ለመገፋት ሊፈተኑ ይችላሉ። ለዚህ ዓይነቱ ፈተና እጃቸውን ሲሰጡ የጌታን ትእዛዝ ይተላለፋሉ (ዘጸ. 23:8፤ አሞ. 5:12)፤ በዚህም መጥፎ ምሳሌነትን ይመሠርታሉ። በአንዳንድ ስፍራዎች ክርስቲያኖች ለጉቦ ሳይገዙ መኖር እንደማይቻል ሊናገሩ ይችላሉ። በእርግጥ እግዚአብሔር ባይኖር ይህ እውነት ይሆን ነበር። ይሁንና እግዚአብሔር ስላለ ክርስቲያን እግዚአብሔር ይረዳው ዘንድ በጸሎት ሊጠይቅ ይችላል። በአፍሪካው የሞንት መኪና ላይ የተንጠለጠለው መረቀት እንደሚለው፥ «እግዚአብሔር አምን ካለ አይደለም የሚል የለም።»

በምዕራፍ 17 ላይ የተመሠረቱ የመወያያ ጥያቄዎችና መልመጃዎች

1. ከቡድኑ አራት ሰዎች በመምረጥ፥ ፍትሕ የጎደለው መከራ ስለ ተጋፈጡ ስለሚያውቋአቸው ሰዎች የሚገልጽ ታሪክ ይናገሩ። ከእያንዳንዱ ታሪክ በኋላ ሰዎቹን እንዴት ይመከሩአቸው እንደ ነበር በመግለጽ ከተወያያችሁበት በኋላ፥ አጋዥ ሊሆኑ የሚችሉ ግልጽ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን አግኙ።

2. አንድ ሰው ለቡድኑ እግዚአብሔር በኢዮብ ላይ ያን ያህል መራራ መከራ እንዲደርስበት ቢፈቅድም ለምን ስሕተት እንዳልሠራ ይግለጽ።

3. በአራት ቡድኖች ተከፋፈሉና፥ የበሽታ መንስኤ ከሚከተሉት አንዱን ስለሚመስልበት ሁኔታ ማስረጃ በማቅረብ ተወያዩ፦

ሀ. በታማሚው ሕይወት ውስጥ የሚገኝ አንድ የተወሰነ ኃጢአት።

ለ. በታማሚው ላይ የአሸማት ሚና።

ሐ. ለአንድ ሰው ቆሻሻ (የተበከለ) ምግብ ወይም ውኃ መስጠትን የመሰለ የግዴለሽነት ስሕተት።

መ. ከባህላዊ ፈዋሽ የመጣ ጎጂ የአገር ባህል መድኃኒት።

ከዚህ በላይ ለተጠቀሱት ለእያንዳንዳቸው ሁኔታዎች በሆስፒታል ወይም በጤና ጣቢያ ተገቢ ሕክምና ከመከተል በተጨማሪ ለታመመው ሰው ምን ሊደረግለት እንደሚገባ ቡድኖቹ መግለጫ ይስጡ።

4. ስለ በሽታና መንስኤዎቹ የአፍሪካውያን ግንዛቤ ምን እንደ ሆነ ተወያዩ።

5. አንድ ሰው ለክፍሉ ከባህላዊ መድኃኒት አዋቂ ነኝ ባይ መድኃኒት ከመቀበል ጋር የተያያዙትን ሁለት ዓይነት ችግሮች ይግለጽ።

6. አንድ ነርስ ወይም የጤና መኮንን ወደ ክፍል በመምጣት ብዙዎቹን በሽታዎች ሊያስወግዱ ስለሚችሉ አንዳንድ ቀላል ተግባራት (ለምሳሌ ከምግብ በፊት እጅን በሳሙና መታጠብ) ማብራሪያ እንዲሰጥ ጋብዙ።

7. በአፍሪካ የክፋትና የእርግማን ጽንሰ-አሳብ ላይ ተወያዩ።

8. ምስት ተማሪዎች እያንዳንዳቸው ድግምት ወይም እርግማን ተደርጎባቸው ሰዎች ስለ ተሠቃዩበት ሁኔታ ይናገሩ።

9. ከአስማት፥ ድግምት ወይም እርግማን በስተኋላ የሚገኘው ትክክለኛው ኃይል ምንድን ነው? መልስህን በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች አስደግፍ።

10. ክርስቲያን አስማት ወይም ጥንቆላ እንደ ተደረገበት ከተጠራጠረ፥ ምን ሊያደርግ ይገባል?

11. በግብረ ገባዊነት፥ ስጦታዎችን በማበርከትና ጉቦ በመስጠት ላይ ባህላዊው የአፍሪካ አመለካከት ምን እንደ ሆነ ተወያዩ።

12. በአፍሪካ ማኅበረሰብና ማኅበራዊ ተቋማት የምግባረ ብልሹነት ባሕርይ ምን እንደሚመስል ተወያዩ።

13. ሁለት ሰዎች እነርሱ ራሳቸው ወይም ሌላ የሚያውቁት ሰው ጉቦ ስለ ሰጠባቸው ትክክለኛ ሁኔታዎች ይግለጹ። ጉቦ ከመስጠት ይልቅ ሰውየው ምን ሊያደርግ ይችል እንደ ነበር ተወያዩ።

14. በአገሪቱ ውስጥ የሚፈጸመውን የጉቦኛነት መጠን ለመቀነስ መንግሥት ምን እርምጃ ሊወስድ እንደሚችል ተወያዩ።

SUGGESTED FOR FURTHER READING

Carson, D.A. How Long, O Lord? Leicester: Inter Varsity, 1994.

Krutza, William, ed. How We Faced Tragedy. Grand Rapids, Michigan: Baker Book House, 1978.

McGrath, Alistair. Suffering. London: Hodder, 1992.

Smith, Anthony M. Gateway to Life. Leicester: Inter Varsity Press, 1994.

Stott, John. Issues Facing Christians Today. Leicester: Inter Varsity Press, 2nd edn, 1990.

Werner, David. Where There Is No Doctor. Palo Alto, California: The Hesperian Foundation, 1983.

ምዕራፍ 18

የክርስቶስ መመለስና የዘመን መጨረሻ

ከፖጋ፡– «ዓለም ይበልጥ እየከፋ የሚሄድ ይመስላል። በከተማ ውስጥ በመንግሥት ሆስፒታል የሚሠራ ወንድም አለኝ። እርሱ እንደ ነገረኝ በአሁኑ ጊዜ በየምሽቱ በሌቦች የተደበደበ ወይም በሽጉጥ የተመታ ሰው ወደ ሆስፒታሉ ይመጣል። በመሆኑም ለወደፊቱ ነገሮች በተሻለ ሁኔታ መልካቸውን ይለውጡ ይሆን? እያልሁ እደነታለሁ።»

ሙንጋዚ፡– «ከዚህ በፊት በአባቶቻችን ዘመን ነገሮች የተሻለ መልክ ነበራቸው። ወደዚያው ዘመን ብንመለስ እንዴት ባማረብን።»

ከፖጋ፡– «በከተማ ውስጥ የሚኖር ክርስቲያን ጓደኛዬ እንደ ነገረኝ፥ እነርሱ የሚሰብኩት ኢየሱስ ወደ ዓለም ሊመለስ ነው። አንድ ሙስሊም እንኳ ኢየሱስ ወደ ዓለም እንደሚመለስ ሲሰብክ ሰምቻለሁ። አንተስ ኢየሱስ ሁኔታዎችን ያሻሽልልናል ብለህ ታስባለህ?»

ሙንጋዚ፡– « አዬም ወደ ክርስትና እምነት የተለወጠ አሳት አለኝ። እርሱም ይኸው ኢየሱስ በሚመለስበት ጊዜ ዓለምን እንደሚያድስ ነግሮኛል። እንዲያውም በፍጥረት ጊዜ ከነበረው ይልቅ የተሻለ ዓለም እንደሚሆን አሜው።ቶኛል።»

ከፖጋ፡– «ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ነገሮች ከረዥም ጊዜያት በፊት በነበሩት የመጀመሪያ ዘመናት ከሁሉም ይሻሉ ነበር።»

ለአንዳንድ ሰዎች ነገሮች ብዙም የሚለወጡ አይመስልም። ዓለም ሁልጊዜም አንድ ዓይነት እንደ ነበረች ያስባሉ። ወደፊትም ነገሮች በዚሁ መልክ እንደሚቀጥሉ ያምናሉ።

ይሁንና፥ ጋዜጣ የሚያነቡ ወይም ሬድዮ የሚሰሙ ሰዎች በዓለም ውስጥ አንድ ነገር እየተፈጸመ እንዳለ ያውቃሉ። መንጀልና ጭካኔ እየተበራከቱ ናቸው። ወጣቶች ከሕዝባቸው ወግ እያፈነገጡ ናቸው። በብዙ የዓለም ክፍሎች በየዕለቱ የኑሮ ውድነት እያሻቀበ ይገኛል። የቤተሰቦች ግንኙነት በመፈራረስ ላይ ነው። በብሔራዊ መንግሥታት ውስጥ ታላላቅ ለውጦች እየተፈጸሙ ናቸው። ምግባረ ብልሹነትና ክፋት በሁሉም ክፍል እየጨመረ የሚሄድ ይመስላል። ይህ ሁሉ ምን ትርጉም ይሰጠናል? መጽሐፍ ቅዱስ ስለምንኖርበት ዘመን ምን ይላል?

ታሪክ ወዴት እያመራ እንዳለ ታውቃለህ? ለዚህ ለአሁኑ ዓለም ፍጻሜ እንዳለው ታውቃለህ? በቅርቡ በመፈጸም ላይ ከሚገኙ ከፍተኛ ለውጦች በስተኋላ ያለው ፍች ምንድን ነው? ከሁሉም በላይ፥ ኢየሱስ ደግሞ ወደዚህ ዓለም እንደሚመለስ የሰጠውስ የተስፋ ቃል እንዴት ነው? (ማቴ. 24:29-31፤ ዮሐ. 14:3)። እውን እንዲህ ዓይነቱ ነገር ይፈጸም ይሆን? ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ ከ40 ቀናት በኋላ ወደ ሰማይ ሲያርግ ቆመው ይመለከቱት ለነበሩ ደቀ መዛሙርት መልአኩ፥ «ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት፥ እንዲሁ ይመጣል» ብሏል (የሐዋ. 1:11)። ይህ የሚሆነው መቼ ነው? ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም የሚመለሰው እንዴት ነው? እርሱ ሲመለስ ምን ይከሰታል?

በዚህ ምዕራፍ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቶስ መመለስና የዚህ ዓለም ፍጻሜ ምን እንደሚል እንመለከታለን። በዚህም የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ እንሞክራለን፦

ሀ. ታሪክ ወዴት እያመራ ነው?

ለ. የዚህን ዘመን ፍጻሜ የሚያመለክቱ ክስተቶች ምንድን ናቸው?

ሐ. የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ምን ይመስል ይሆን?

መ. ክርስቶስ ሞቼ ይመለሳል?

ሠ. አንድ ሰው ለዚህ ዘመን የመጨረሻ ክስተቶችና ለክርስቶስ መመለስ እንዴት ሊዘጋጅ ይችላል?

ረ. ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ ስለሚኖሩ የክስትቶች ቅደም ተከተል ከሚናገሩ ዐበይት ጽንሰ-አሳቦች (ቲዎሪዎች) አንዳንዶቹ ምንድን ናቸው?

ሰ. ክርስቶስ ለምን ይመለሳል?

ሀ. ታሪክ ወዴት እያመራ ነው?

የዓለምን ክስተቶች የሚከታተሉ ሰዎች ታሪክ ወዴት እያመራ እንዳለ በግሰብ ይደነቃሉ። ታሪክ በከፍተኛ ፍጥነት እየተለወጠ በመሆኑ እጅግ ታላላት የዓለም መሪዎች እንኳን ከዚህ ቀጥሎ ምን እንደሚፈጸም ሊተነብዩ አይችሉም። ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ወዴት እያመራ እንደ ሆነ እንዳች ፍንጭ ይሰጠን ይሆን? አዎን መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በዓለም ውስጥ ምን እያደረገ እንዳለ ይናገራል። እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣን እግዚአብሔርን ለመቃወም ምን እያደረገ እንደ

ሆነ ይነግረናል። እነዚህን ሁለት ነገሮች ስንረዳ በዓለማችን ውስጥ ለውጥ ከሚታይባቸው ክስተቶች አንዳንዶቹን እንገነዘባለን።

እግዚአብሔር በዓለም ውስጥ ምን እየሠራ ነው?

እግዚአብሔር በአሁኑ ዘመን ምን እያደረገ እንደ ሆነ ለመረዳት ከዚህ ቀደም ምን እንዳደረገና አሁን በመረጃም ላይ ካለው ክስተት ጋር እንዴት እንደሚዛመድ መገንዘብ አለብን። የክርስቶስ ምጽአት እግዚአብሔር ከዚህ ቀደም ያደረገውና ዛሬም በማድረግ ላይ ያለው ተግባር ፍጻሜ፥ ግብቂያ ነው።

በዔድን ገነት አዳም በፈጸመው አለመታዘዝ አማካኝነት ኃጢአት የፍጹሙን ዓለም መፈጠር ተከትሎ መጣ (ዘፍጥ. 1- 3)። በኃጢአት አማካኝነት በዓለም ሁሉ የሞት ቅጣት በሰው ሁሉ ላይ ደረሰ (ዘፍጥ. 3:17፤ ሮሜ 5:12)። የዚህም ውጤት የሆኑት ሞትና ምግባረ ብልሹነት የሰውን ልጅ ብቻ ሳይሆን በተቀረውም ፍጥረት ላይ ተከስተዋል። ሮሜ 8:22 «ፍጥረት ሁሉ እስከ አሁን ድረስ አብሮ በመቃተትና በምጥ መኖሩን እናውቃለንና» ይላል።

ይህ አስከፊው ሁኔታ የተከሰተው ሰይጣን አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር ላይ እንዲያምፁ ባመጣው ፈተና ነበር። ሰይጣን ራሱ ከረኸም ዘመናት በፊት በእግዚአብሔር ላይ ዓመፆ ነበር (ዘፍጥ. 3:1-6፤ ኢሳ. 14:13-14)። በእግዚአብሔር ላይ በማመፁና በዓመፁም ብዙዎችን የእግዚአብሔር መላእክት ከራሱ ጋር በመውሰድ (ራእይ 12:3-4)ÞሰይጣንÞ የእግዚአብሔር ጠላት ወይም ተቃዋሚ ሆነ፤ ሰይጣን ማለት ተቃዋሚ ማለት ነው። ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ካመፀበት ጊዜ አንሥቶ የእግዚአብሔርና እግዚአብሔር የሚሠራው ነገር ሁሉ ጠላት ሆነ። ዛሬ በዓለም ውስጥ የሚፈጸሙትን ብዙዎቹን ነገሮች ለመረዳት ይህንኑ መገንዘብ አስፈላጊ ነው።

እግዚአብሔር አዳም ኃጢአት በሠራ ጊዜ በመጨረሻው የሰው ልጅ (የሴቲቱ ዘር) ሰይጣንን እንደሚያሸንፍ በዔድን ገነት የተሰጡ ቃል ሰጠ። ዘፍጥረት 3:15 ይህንን የተሰጡ ቃል ከማቅረቡ በተጨማሪ የሰውን ልጅ ታሪክ በሰፋት ያሳየናል። እግዚአብሔር «በአንተና በሴቲቱ መካከል በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፥ አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ» ብሏል። በመጨረሻው የሰይጣንን ራስ የሚቀጠቅጠው የሴቲቱ ዘር ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ሰይጣን በመስቀሉ ላይ መከራና ሞት የኢየሱስ ክርስቶስን ሰኮና ቀጥቅጧል። ይሁንና፥ እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱና በፍቅሩ በመስቀል ላይ የተፈጸመውን ሽንፈት የሚመስል ተግባር፥ ለሰው ልጅ ደህንነትን ለማምጣትና ሰይጣንን ለመርታት ተጠቅሞበታል። ቆላሳይስ 2:13-15፥ «እናንተም በበደላችሁ . . . ሙታን በሆናችሁ ጊዜ፥ ከእርሱ (ከክርስቶስ) ጋር ሕይወትን ሰጣችሁ . . . በደላችሁን ሁሉ ይቅር አላችሁ፤ በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው፤ እርሱንም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል፤ አለቅነትንና ሥልጣናትን (ሰይጣንን) ገፎ ድል በመንሣት በእርሱ እያዘነቸው በግልጽ አሳያቸው» ይላል።

በዔድን ገነት ሴቲቱንና ወንዱን ከፈተነበት ጊዜ አንሥቶ ሰይጣን በዓለም ሁሉ የእግዚአብሔርን ሥራ ነቅቶ ሲቃወም ቆይቷል። እስካሁን ድረስ ዓለም በጦርነት፥ በጭካኔ፥ በወንጀልና በክፋት ውጥረት የተጠለችበት ዓይነተኛው ምክንያት ይኸው ነው።

ለእግዚአብሔር ዓላማዎች ይኸው የሰይጣን ስውር ተቃውሞ ምሳሌ ኢየሱስ በተወለደ ጊዜ ተፈጽሞአል። ሰብአ ሰገል ስጦታዎችን ለመስጠትና አምልኮ ለማቅረብ አዲስ የተወለደውን ንጉሥ ሊፈልጉ ወደ ቤተልሔም ደረሱ (ማቴ. 2:1-2)። ንጉሥ ሄሮድስ ሌላው ንጉሥ ምናልባትም አንድ ቀን ዙፋኑን እንደሚቀናቀን በማሰብ ቅንዓትና ቁጣ ሞላበት። በዚያን ጊዜ ንጉሥ ሄሮድስ አዲሱን ንጉሥ ለማጥፋት በቤተልሔም ሁለት ዓመትና ከዚያ በታች የሆኑትን ወንድ ሕፃናት ሁሉ እንዲፈጁ አሳብ ማቅረቡ ለሰይጣን ቀላል ተግባር ነበር (ማቴ. 2:7-16)። ሄሮድስ የዙፋኑን ተቀናቃኝ ለማስወገድ ፈለገ፤ ሰይጣን ደግሞ የእግዚአብሔርን መሢሕ ለማጥፋት ፈለገ።

ብዙው የሰው ልጅ ታሪክ ይህንኑ ክስተት ይመስላል። ሰዎች በራሳቸው ትዕቢትና የራስ ወዳድነት ምኞቶች ላይ ተመሥርተው ዕቅዶችን ይወጥናሉ። ከዚያም ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ የሚያካሂዳቸውን የራሱን ክፉ የንግግ ዕቅዶች ለመፈጸም፥ የሰዎችን የጋጢአት ጠባይ በመጣሪያነት ይጠቀማል። ከዚህ ሁሉ ክፋት ባሻገር እግዚአብሔር ሰዎችን ከጋጢአት ባርነት ለማላቀቅና የፈጠረውን ፍጹም ዓለም ለማደስ በሥራ ላይ ነው። የእግዚአብሔር ዓለምን የማዳን ሥራ የተጀመረው ከ4000 ዓመታት በፊት አብርሃም በተባለ የእምነት ሰው ነበር (ዘፍጥ. 12:1-3)። ለዚህ ተቅበዝባዥ የከብት እረኛ እግዚአብሔር የሚያስደንቅ የተስፋ ቃል ሰጠው፤

እግዚአብሔር «ስምህንም አከብረዋለሁ ለበረከትም ሁን፣ የምድር ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ» ብሏል (ዘፍጥ. 12:2-3)። በምድር ላይ የሚገኙ ሰዎች ሁሉ እንዴት በአንዱ ሰው በአብርሃም ሊባረኩ ይችላሉ? መልሱ የአብርሃም ዘር በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ግዳን አማካኝነት ነው (ማቴ. 1:1-17)። የአብርሃም ዘሮች የአብርሃም የልጅ ልጅ በሆነው በያዕቆብ አማካኝነት የእስራኤል ሕዝቦች ሆነው አደጉ። እግዚአብሔር ያዕቆብን እስራኤል ብሎ ዳግም ሰይሞት ነበር (ዘፍጥ. 32:28)። እስራኤላዊው ኢየሱስ ከያዕቆብ ልጆች አንዱ የሆነው የይሁዳ ነገድ ትውልድ ነበር (ማቴ. 1:2፥ 24-25)።

በክርስቶስና በተከታዮቹ አማካኝነት የግዳን ወንጌል በዓለም ሁሉ በመሰበክ ላይ ይገኛል (ማቴ. 28:19፤ ማር. 16:15) ። በዚህም ዓይነት የአብርሃም በረከት ወደ ዓለም ሁሉ እየተዳረሰ ነው። በክርስቶስ የሚያምኑ ሰዎች አብርሃም የነበረውን ዓይነት እውነተኛ የእግዚአብሔርን እምነት ስለሚከተሉ፥ የአብርሃም መንፈሳዊ ልጆች ይሆናሉ። ገላትያ 3:7-9፥ «እንኪያስ ከእምነት የሆኑት እነዚህ የአብርሃም ልጆች እንደ ሆኑ እወቁ። መጽሐፍም . . . በአንተ አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ ብሎ ወንጌልን ለአብርሃም አስቀድሞ ሰበከ» ይላል። ስለ ሆነም፥ እምነት ያላቸው ሰዎች የእምነት ሰው ከነበረው አብርሃም ጋር ይባረካሉ።» በምዕራፍ ዘጠኝ እንደ ተመለከትነው በክርስቶስ የሚያምኑ ሰዎች የዓለም አቀፍ ሰፊ ቤተሰቡ ግለትም የቤተ ክርስቲያኑ አካላት ይሆናሉ።

በማቴዎስ 16:18 ኢየሱስ፥ «በዚህ ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆች አይችሉአትም» ብሏል። በማቴዎስ 28:19 ኢየሱስ፥ «እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው . . . ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው» ሲል ለተከታዮቹ ታላቅ ተልዕኮውን ሰጥቷል። በመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ፥ ሐዋርያው ያዕቆብ እግዚአብሔር ዛሬ ምን እያደረገ እንዳለ በሚከተሉት ቃላት አጠቃሎአል፦ «ወንድሞች ሆይ፥ ስሙኝ። እግዚአቤሔር ለስሙ የሚሆንን ወገን ከአሕዛብ (ግለትም ይሁዳዊ ካልሆኑ ሕዝቦች) ይመስድ ዘንድ አስቀድሞ እንዴት እንደ ጎበኘ ስምዖን ተርኮአል» (የሐዋ. 15:13-14)።

ስለ ሆነም፥ ዛሬ የእግዚአብሔር ቀዳሚ ተግባር በዓለም የኢየሱስ ክርስቶስን ቤተክርስቲያን ማነፅ ነው። በቤተ ክርስቲያን አማካኝነት የምድር ሕዝቦች ሁሉ የደኅንነት መንገል ሰምተው፥ ለአብርሃም

የተሰጠውን በረከት የመቀበል ዕድል ያገኛሉ። ኢየሱስ ከአሕዛብ ሰዎችን ለራሱ አድርጎ እየወሰደ ነው። በእግዚአብሔር ዕቅድ መሠረት፥ ቤተ ክርስቲያን ሰዎችን በምድር ከሚገኝ ከሁሉም ነገድና ሕዝብ ማካተት አለባት። በራዕይ 5:9 መጽሐፍ ቅዱስ፣ «መጽሐፉን ትወስድ ዘንድ ግኅተሞቹንም ትፈታ ዘንድ ይገባሃልና፥ ታርደሀልና፥ በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተሃል». ይላል።

ክርስቲያኖች በባህላዊ ግርዶሾች ሁሉ እያለፉ በዓለም ለሚገኙ ሕዝቦች ሁሉ (ለአሕዛብ ሁሉ) የማዳኑን መልካም የምሥራች ሲናገሩና እምነታቸውን ለሌሎች ሰዎች ሲያካፍሉ፥ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያኑን እየገነባ ነው። ቤተ ክርስቲያን ከ100 ወይም ከ500 ዓመታት በፊት ከነበረው በላይ ዛሬ ለክርስቶስ ቀርባለች። ቤተ ክርስቲያን የሚቻላትን ጥረት ሁሉ ብታደርግ አሁን ታላቁ ተልዕኮ በአንድ ትውልድ ሊሳካ እንደሚችል የሚያምኑ ሰዎች አሉ።

ምንም እንኳን ከዓለም ሕዝብ ግማሹ ያህል ቤተ ክርስቲያን እንደሌለው እውነት ቢሆንም፥ በርካታ አዳዲስ ሰዎች በየዕለቱ ክርስቶስን ለመከተል እየወሰኑ ናቸው። አንዳንድ አስገራሚ አሐዛዊ መረጃዎች እንደሚከተለው ተመልክተዋል። በ1000 ዓ. ም. በዓለም ለአንድ ክርስቲያን ምናልባት 220 የማያምኑ ሰዎች ነበሩ። በ1950 ዓ. ም. ለእያንዳንዱ አንድ ክርስቲያን ምናልባት 21 የማያምኑ ሰዎች ነበሩ። በ1989 ዓ. ም. ደግሞ በዓለም ለአንድ ክርስቲያን ሰባት የማያምኑ ሰዎች ብቻ ነበሩ። በእርግጥ እነዚህ አሐዛዊ መረጃዎች የሚያመለክቱትን እናምናልን የሚሉትን ሰዎች ሁሉ ነው። ከእነዚህ መካከል በትክክል የእርሱ የሆኑትንና ከመንፈስ ቅዱስ የተወለዱትን የሚያውቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ይሁንና እነዚህ መረጃዎች ቤተ ክርስቲያን የታላቁን ተልዕኮ ዓላማ ለማሳካት እንደ ተቃረበች ያሳያሉ።

እነዚህ እውነቶች ከኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዓለም መመለስ ጋር የተያያዙ ናቸው። ኢየሱስ ወደ ምድአቱ ስለሚመሩት ክስተቶች ሲናገር፥ «ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፥ በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል» ብሏል (ማቴ. 24:14)። ስለ ዘመን መጨረሻ በሚገልጸው ተመሳሳይ ውይይት ኢየሱስ፥ «ወንጌል ለአሕዛብ ሁሉ ይሰበክ ዘንድ ይገባል» ብሏል (ማር. 13:10)።

አንዳንድ ሰዎች፥ «ክርስቶስ እስካሁን ያልተመለሰው ለምንድን ነው?» እያሉ ይጠይቃሉ። ለዚህ ጥያቄ መልስ የሚሆነው የታላቁ ተልዕኮ አለመፈጸም ነው። በሐዋርያው ጴጥሮስ ዘመን የነበሩ ሰዎች የኢየሱስ ክርስቶስን መመለስ ተጠራጥረዋል። ጴጥሮስ እነዚህ ሰዎች፥ «የመምጣቱ የተስፋ ቃል ወዴት ነው?» ሲሉ (2 ጴጥ. 3:4) ላቀረቡት ጥያቄ፥ «ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፥ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ አንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል» የሚል ምላሽ ሰጥቷል (2 ጴጥ. 3:9)።

ቤተ ክርስቲያን የታላቁን ተልዕኮ ኃላፊነት በበለጠ ትኩረት ብትወጣው፥ በዓለም ወንጌሉ ያልደረሳቸውን ሰዎች ለመድረስ የምትችለውን ጥረት ሁሉ ብታደርግ፥ ይህ የክርስቶስን መመለሻ ጊዜ ያፋጥነዋል። ከሳይ የተጠቀሰው ምንባብ በሚገኝበት ከፍል ጴጥሮስ፥ «የእግዚአብሔርን ቀን መምጣት እየጠበቃችሁ እያስቸኮላችሁ፥ በቅዱስ ኑሮ እግዚአብሔርንም በመምሰል እንደ ምን ልትሆኑ ይገባችኋል?» ብሏል (2 ጴጥ. 3:11-12)።

ክርስቶስ ከመመለሱ በፊት ዓለም በሙሉ በእርሱ ያምን ይሆን? መጽሐፍ ቅዱስ ዓለም በሙሉ ወደ ክርስቶስ እንደማይመለስ በግልጽ ይናገራል። ኢየሱስ፥ «ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ መንገዱም ትልቅ ነውና ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው» ብሏል (ማቴ. 7:13)። በሚመለስበት ጊዜ በምድር ላይ የሚኖሩትን ሁኔታዎች በተመለከተ ኢየሱስ፥ «የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ በምድር እምነትን ያገኛ ይሆንን?» ብሏል (ሉቃ. 18:8)። እርሱ በሚመለስበት ጊዜ ሰዎች በእርሱ እንደማያምኑ ይህ የክርስቶስ ቃል ያመለክታል።

ሰይጣን በዓለም ውስጥ ምን እየሠራ ነው?

ሰይጣን በዓለም ዙሪያ ወደሚገኙ የሕዝብ ቡድኖች ወንጌል በስፋት እየተሰራጨ መምጣቱን በማየቱ፥ ይበልጥ ቁጣውንና ጭካኔውን እያበዛው መጥቷል። የሚቆጣውም በእግዚአብሔር ላይ እንዲያምፁ በማነሣሣት ያሳታቸው ሰዎች አሁን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ለእግዚአብሔር ወደ መታዘዝ በመመለሳቸው ነው። ይህ ሰይጣንን ክፉኛ ያስቆጣዋል። ንብረቱ እንደ ሆነ የሚቆጥረው ክልል ሲወረር በአሜንታ አይቀበልም። ወንጌል ባልደረሰላቸው የሕዝብ ቡድኖች መካከል በመጨረሻው አማኞች ሲገኙ፥ ኢየሱስ እንደሚመለስና እርሱም ራሱ እንደሚታሰር ስለሚያውቅ

ሰይጣን የወንጌሉን መሰበክ ይቃወማል (ራእይ 5:9-10፤ 20:1-3)። የወንጌሉ መሳካት ግለት የዕድሜው ማጠር እንደ ሆነ ስለሚያውቅ፥ የወንጌሉን መሰራጨት በከፍተኛ ደረጃ ይቃወማል (ራእይ 12:12)።

አንዳንድ ጊዜ ሰይጣን መንግሥታትን ወይም የነፃ ቡድኖችን ለጦርነትና ለግድያ በማነሣሣት፥ የወንጌሉን መሰራጨትና የቤተ ክርስቲያንን መስፋፋት ለመግታት ይታገላል። እንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች የወንጌሉን ስርጭትና የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን መስፋፋት ያግዳሉ። ስለዚህም «እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር ልመናና ጽሎት . . . ስለነገሥታትና ስለ መኳንንትም» እንድናደርግ ታዘናል (1 ጢሞ. 2:2)። በዚህ ምንባብ ጳውሎስ በመቀጠል፥ «ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው» ይላል (ቁ. 3)። በሌላ አባባል፥ ለመንግሥት ባለሥልጣናት የምንጸልየው ሰይጣን ለእነዚህ መሪዎች የሚሰጠው የጦርነትና የጭካኔ አሳብ እንዲታቀብ ነው። ሰላም ካለ፥ ወንጌሉ ሊሰበክና አጥቢያ አብያተ ክርስቲያንትም ተግባራቸውን ለጌታ ሊያከናውኑ ይችላሉ።

በተለያዩ ጊዜያት ሰይጣን ክርስቲያኖች ያልሆኑ ሰዎች ክርስቲያኖችን እንዲያሳድዱ በማነሣሣት የወንጌሉን ስርጭት ተዋግቷል። በራእይ 2:10 ኢየሱስ ለሰምርኔስ አማኞች፥ «ልትቀበለው ያለህን መከራ አትፍራ። እነሆ፥ እንድትፈተኑ ዲያቢሎስ ከእናንተ አንዳንዶቻችሁን በወኅኒ ሊያገባችሁ አለው፥ አሥር ቀንም መከራን ትቀበላላችሁ። እስከ ሞት ድረስ የታመንህ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ» ብሏል። ስደት አሠቃቂ ቅጣት ቢሆንም፥ በስደት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን በጣም ቅድስትና ንጽሕት ትሆናለች (ዕብ. 12:5-10)።

ሰይጣን ሐሰተኛ ሃይማኖቶችንና ኑፋቄዎችን በማበረታታት የወንጌሉን ስርጭት ይዋጋል። ሰዎች ውሸትን ሲያምኑ፥ ሊድኑበት የሚችሉትን እውነት ሊቀበሉ አይችሉም። ቢያንስ ከዛሬው የዓለም የሕዝብ ብዛት ግማሹ በሐሰተኛ ሃይማኖቶች ትምህርት ተታሏል። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «መንፈስ ቅዱስ በግልጥ፦ በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያዳመጡ፥ ሃይማኖትን ይክዳሉ ይላል» (1 ጢሞ. 4:1)።

ምናልባት ሰይጣን የእግዚአብሔርን ሥራ የሚቃወምበት እጅግ የተለመደው መንገድ ሰዎች በአሁኑ የዓለም ዘይቤ ሙሉ ለሙሉ

እንዲወሰዱ በግድረግ ነው፤ ይህም ገንዘብ ማከማቸትንና የግል ፍላጎት ማርካትን የመሳሰለው ነው። ሰዎች በገንዘብና በሥልጣን ፍቅር ሲጠመዱ ለእግዚአብሔር ጊዜ አይኖራቸውም። ኢየሱስ፥ «ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም» ያለው ለዚህ ነው (ማቴ. 6:24)።

ለ. የዚህን ዘመን ፍጻሜ የሚያመለክቱ ክስተቶች ምንድን ናቸው?

በአሁኑ ዘመን ማብቂያ አካባቢ ምን እንደሚፈጸም መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ትንቢቶችን ያቀርባል። ብዙውን ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ወደፊት ስለሚሆነው ነገር በጣም ውስን ነው። ይሁንና በትንቢቶቹ ውስጥ ትንበያዎቹ መቼ እንደሚፈጸሙ እምብዛም አይገልጹም። ትንበያዎቹ የሚፈጽሙባቸውን ትክክለኛ ቀናት ለማወቅ መጣር የሰው ልጅ ዝንባሌ ነው። ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ደቀ መዛሙርቱ፥ «ጌታ ሆይ፥ በዚህ ወራት ለእስራኤል መንግሥትን ትመልሳለህን?» በማለት ጠይቀዋል (የሐዋ. 1:6)። ኢየሱስ ለዚህ ጥያቄ በሰጠው መልስ ለደቀ መዛሙርቱ ዘወር ባለ መንገድ፥ «አብ በገዛ ሥልጣኑ ያደረገውን ወራትንና ዘመናትን ታውቁ ዘንድ ለእናንተ አልተሰጣችሁም» ብሏል (ቁ. 7)።

የዚህን ዘመን መጨረሻና የክርስቶስን መመለስ የሚያጅቡትን ክስተቶች በተመለከተ፥ በአእምሮአችን ተመሳሳይ አጠቃላይ አመለካከት ሊኖረን ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስ ከእነዚህ ክስተቶች አንዳንዶቹንና ታሪካዊ መስመራቸውን በተመለከተ ብዙ ዝርዝር ነገሮችን ቢገልጽልንም የጊዜ ሰሌዳውን ግን አልሰጠንም (ማቴ. 24:42-44)። ትንቢታዊ የቀን አቀማመጦችና የመርሐ-ግብር አወቃቀሮች በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሁሉ መልካም ግንዛቤ የነበራቸው ክርስቲያኖች የወደቁባቸው ስሕተቶች ናቸው። ከዚህም የተነሣ፥ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስለ መጨረሻው ዘመን ትንቢቶች የጊዜ ሰሌዳ ማበጀቱን ሆን ብለን አስወግደናል። በምትኩ፥ ትንቢት የተነገረላቸውን ክስተቶች ከአንዳንድ ታላላቅ ትርጓሜዎቻቸው ጋር በማገናዘብ እናቀርባለን። ከእነዚህም ትርጓሜዎች አንዳንዶቹ ወይም ሁሉም ስሕተቶች ሊሆኑ እንደሚችሉ አንባቢው ልብ ሊል ይገባል። የእያንዳንዱ ትንቢት ትክክለኛ ፍች ለቤተ ክርስቲያን ግልጽ የሚሆነው፥ ትንቢት የተነገረላቸው ክስተቶች ከተፈጸሙ በኋላ ብቻ ነው።

ኢየሱስ ከመወለዱ በፊት፥ ብሉይ ኪዳን ስለ መሢሑ የመጀመሪያ ምጽአት ከ300 የሚበልጡ ግልጽ ትንበያዎችን ሰጥቶ ነበር። የእነዚህ ትንቢቶች እያንዳንዱ ዝርዝር ጉዳይ በክርስቶስ መምጣት ተፈጽሞአል።

በኢየሱስ ዘመን የነበሩ አይሁዶች እነዚህን ትንቢቶች ቢያውቁም፥ በትውልዳቸው መፈጸማቸውን ግን አልተረዱም ነበር (ለምሳሌ ማቴ. 2:5-6፤ 27:39-44፤ ሉቃ. 4:17-29)። ቤተ ክርስቲያንም የእነዚህን ትንቢቶች ፍጻሜ በትክክል የተረዳችው በኋላ ነበር።

የኢየሱስ ክርስቶስ መመለስና በዚህ ዘመን ግብቂያ ላይ የሚፈጸሙ ክስተቶች የመጀመሪያ ምጽአቱን ትንቢቶች በሚመስሉ ዝርዝር ጉዳዮች ተገልጸዋል። ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት የሚናገሩ ከ500 የሚበልጡ ትንቢቶች አሉ። ስለ መጀመሪያው ምጽአቱ የተነገሩ ትንቢቶች በቀጥታና በታሪካዊነት ስለ ተፈጸሙ፥ ስለ ዳግም ምጽአቱ የተነገሩ ትንቢቶችም በቀጥታ እንደሚፈጸሙ እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን። ይሁንና፥ እንደ ቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ እኛም በሚፈጸሙበት ጊዜ ፍጻሜያቸውን ወዲያው ላንገነዘብ እንችላለን።

በኢየሱስ ዳግም ምጽአት አቅራቢያ የሚፈጸሙ እጅግ በርካታ ክስተቶች ስላሉ፥ በዚህ መጽሐፍ ጠቅለል አድርጎ ከማቅረብ የበለጠ ተግባር ልናከናውን አንችልም። እነዚህን ትንቢቶች በበለጠ ዘርዝር አድርገው የሚመረምሩ ሌሎች መጻሕፍት አሉ። ይህ መጽሐፍ ግን የእነዚህን ትንቢቶች አጭር መግለጫ ብቻ ይሰጣል።

ስለ እስራኤል ሕዝብ የተሰጡ ትንቢቶች

1. መጽሐፍ ቅዱስ የአይሁድ ሕዝቦች ዳግም ወደ እስራኤል ምድር እንደሚመለሱ ይናገራል (ኢሳ. 11:11-12፤ ዘካ. 10:8-10)። የመጀመሪያው የእስራኤላውያን ወደ ምድራቸው መመለስ የተፈጸመው ከ70 ዓመታቱ የባቢሎን ምርኮ በኋላ ነበር (ኤር. 29:10)።

2. በሕዝቅኤል 37:1-14፥ 21፥ 25 መሠረት፥ የእስራኤላውያን ወደ ምድራቸው መመለስ በሦስት ደረጃዎች ይፈጸማል (የአጥንቶች መያያዝ፥ የሥጋ መውጣትና የሕይወት እስትንፋስ መግባት)። ይህም የሚከተሉትን ሊያጠቃልል ይችል ነበር፦

ሀ. የአይሁዶች አካላዊ መመለስ፥ ይህ የአይሁዶች ወደ ጥንታዊቱ ምድር የመመለስ ዓለም አቀፍ እንቅስቃሴ በ1900 ዓ. ም. አካባቢ የተጀመረ ሲሆን እስካሁንም እንደ ቀጠለ ነው።

ለ. ፖለቲካዊ (አሞ. 9:14-15) እና የምድሪቱ የአርሻ መሬት ተሐድሶ (ኢሳ. 35:1-2)። በታሪክ ደረጃ የአሁኑ ነፃ የእስራኤል

መንግሥት የተወለደው በሜይ (ሚያዝያ) 14 1948 ዓ. ም. ሲሆን፥ ይኸውም ለ2300 ዓመታት አይሁዶች ነፃ ግዛት ሳይኖራቸው ቆይተው ነው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስራኤላውያን በዘመናዊ የእርሻ ጥበብ፥ «በረሀውም . . . እንደ ጽጌረዳ ያብባል» የተባለላቸውን የትንቢት ቃል በሕይወታቸው እያዩ ነው (ኢሳ. 35:1-2)።

ሐ. መንፈሳዊ ዳግም ልደት፥ ይህ ምናልባት ኢየሱስ በሚመለስበት ጊዜ የማያምኑ አይሁዶች በክብሩ መመለሱን ሲመለከቱት ይፈጸማል (ዘካ. 12:9-14፤ ሮሜ 11:23-28)።

3. እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ የኢየሩሳሌም ከተማ ሙሉ ለሙሉ ለአይሁዶች ትመለሳለች (ኢሳ. 37:31-32፤ ዘካ. 12:5-8)። ይህ ክስተት «በአሕዛብ ዘመን» ማብቂያ አካባቢ ይፈጸማል (ሉቃ. 21:24)። በታሪክ ደረጃ፥ የኢየሩሳሌም ከተማ በ1967 ዓ. ም. ከዓረቦች ጋር በተደረገው የስድስቱ ቀናት ጦርነት፥ ከ2600 ዓመታት በኋላ ሙሉ ለሙሉ ለአይሁዶች ተመልሳ ነበር።

4. ከማቴዎስ 24:14-15 እና 2ኛ ተሰሎንቄ 2:4 በመነሣት፥ አንዳንድ ክርስቲያኖች የአይሁድ መቅደስ ዳግመኛ እንደሚሠራ ያምናሉ። ምናልባት በዚህ በታደሰው ቤተ መቅደስ የእንስሳት መሥዋዕት በአምልኮ ይቀርብ ይሆናል (ዳን. 9:27)። «ለአዲሱ መቅደስ ጊዜው አሁን ነው?» በሚል ርዕስ በኦክቶበር 16 1989 አንድ ጽሑፍ ታይም መጽሔት ላይ ወጥቶ ነበር። ይህ ጽሑፍ (ሀ) አይሁዶች ለአዲሱ መቅደስ ዝግጅት እያደረጉ እንደ ሆነና (ለ) በቤተ መቅደሱ ውስጥ ለሚፈጸሙ የተሐድሶ የእንስሳት መሥዋዕት ካህናትን እያሰለጠኑ እንደ ሆነ ይገልጻል።

ስለ ሰይጣን የተሰጡ ትንቢቶች

1. መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ዘመን መጨረሻ የሰይጣንና የአጋንንት እንቅስቃሴ በከፍተኛ ደረጃ እንደሚጨምር ይናገራል (ራእይ 9:1-11፤ 12:7-12፤ 16:13-14)። ይህ ምናልባትም በወንጀል፥ በጭካኔ ተግባራትና ባጣቃላይ ክፋት የሚታየውንም ከፍተኛ እድገት ያጠቃልል ይሆናል (ማቴ. 24:10-12፤ ራእይ 9:20-21)።

2. ሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ ትምህርቶች ይተረፈረፋሉ (ማቴ. 24:10-11፥ 24፤ 1 ጢሞ. 4:1)።

3. ብዙ ክርስቲያኖች፥ ዓለምን በሚቆጣጠረውና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አውሬው (ራእይ 13:1-8)፥ የክርስቶስ ተቃዋሚ (1 ዮሐ. 2:18) እና ዓመፀኛ (2 ተሰ. 2:8-9) በመባል በሚታወቀው ሰው አማካኝነት፥ ሰይጣን ለአጭር ጊዜ ዓለሙን ሁሉ እንደሚገዛ ያምናሉ። ይህ ሰው የመጨረሻው በመሆኑ፥ ምናልባት በታሪክ ውስጥ በሰይጣን ኃይል ከሠሩት ከብዙዎች ፀረ-ክርስቲያን የዓለም መሪዎች ሁሉ የከፋው ሳይሆን አይቀርም (1 ዮሐ. 2:18)። እንዲህ ዓይነት ባሕርይ ከነበራቸው መሪዎች መካከል የሮማው ንጉሥ ኔሮና ለሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተጠያቂ የሆነው ኤዶልፍ ሒትለር ይገኙበታል።

መጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻው ክፉ የዓለም መሪ (አውሬው) በዓለም የገንዘብ ዘይቤ ላይ ተቆጣጣሪ በመሆን፥ ሰዎች ለመግዛት ወይም ለመሸጥ በእጆቻቸው ወይም በግንባሮቻቸው ላይ ምልክቱን እንዲቀበሉ እንደሚጠይቅ ይናገራል (ራእይ 13:16-17)። በዚህ መሪ አማካኝነት ሰይጣን በአይሁዶች (ኤር. 30:5-7፤ ዳን. 12:1: 7፤ ራእይ 12:13-14) እና በክርስቲያኖች (ራእይ 7:14-17፤ 12:17፤ 20:4) ላይ አስከፊ ስደት ይቀሰቅሳል። የአውሬውን የአገዛዝ ጊዜ በትክክል የሚተነትኑ ዝርዝሮች በዳንኤል 7:8፥ 11፥ 20፥ 25፤ 2 ተሰ. 2:3-12፤ ራእይ 13:1-18 እና በሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ ይገኛሉ። ይኸው መሪና ረዳቱ የሆነው ተአምር ሠሪው «ሐሰተኛ ነቢይ» ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመለስ በሕይወት ወደ እሳት ባሕር ይጣላሉ (ራእይ 19:20)።

4. ሰይጣንና አጋንንቱ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ በከፍተኛ ደረጃ ይጨምራሉ፤ ይህም በተለይ በስደት አማካኝነት የሚከናወን ይሆናል (ራእይ 12:9፥ 17)።

ሰይጣን በታሪክ ሁሉ በብዙ መንገዶች እግዚአብሔርን ሲቃወም ነበር። በርካታ ሕዝቦች ወደ ክርስቶስ እየተመለሱ ቤተ ክርስቲያን በከፍተኛ ደረጃ ማደጓን ሲመለከት እግዚአብሔርንና ሥራውን ለመቆጣጠር ጥረቱን ይብልጥ እያጠናከራቸው ነው። ይህም በብዙ የዓለም ክፍሎች ክርስቲያናዊ ያልሆኑትን ሃይማኖቶች በተለይም እስልምናን ለማስፋፋት

ከወሰዳቸው ቁርጥ እርምጃዎች ሊታይ ይችላል። እንደዚሁም በዓለም ሁሉ በሚከናወነው ከፍተኛ የነፍስ ግድያ፥ ወንጀልና የጭካኔ ተግባራት መጨመር ሊታይ ይችላል። በተጨማሪም በአውሮፓና በአሜሪካ እየጨመረ በሄደው የወሲብ ማነቃቂያ ጽሑፍና መጽሔት ("pornography")፥ በወሲብ ጋጢአት፥ በውርጃና የዕፅ ሱሰኝነት ውስጥ ሊታይ ይችላል። እንደዚሁም በአፍሪካ ባህላዊ ሃይማኖቶችን ለመከተል ሕዝቡ ካሳየው የፍላጎት መታደስ፣ በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ ምትሐታዊ ልምምዶችን ለመተግበር ከሚደረገው እሽቅድምድም፥ የሰይጣንን ጥረቶች ልንመለከት እንችላለን። በመጨረሻም በብዙ የዓለም ክፍሎች ክርስቲያኖች በክፋ ሁኔታ ከሚሰደዱበት ተዕይንት መመልከት እንችላለን።

በዚህ ዘመን መጨረሻ የሚኖሩ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች እንደሚከተለው ተገልጸዋል፦ «የቀሩቱ ሰዎች . . . ስለ እጃቸው ሥራ ንስሐ አልገቡም፤ ስለ መግደላቸውም ቢሆን ወይም ስለ አስማታቸው ወይም ስለ ዝሙታቸው ወይም ስለ ስርቆታቸው ንስሐ አልገቡም» (ራእይ 9:20-21)።

ስለ ቤተ ክርስቲያን የተሰጡ ትንቢቶች

1. ባለፈው ታሪክ በማንኛውም ጊዜ ከተፈጸመው በላይ ክርስቲያኖች በክፋ ሁኔታ ይሰደዳሉ (ማቴ. 24:9፤ ራእይ 6:9-10፤ 17:6፤ 20:4)።

2. ከስደትና ከፋት ብርካቴ የተነሣ በአፋቸው ክርስቲያኖች እንደ ሆኑ የሚናገሩ ብዙ ሰዎች ክርስቶስን ይክዳሉ (ማቴ. 24:10፥ 12፤ 2 ተሰ. 2:3፤ 1 ጢሞ. 4:1፤ 2 ጢሞ. 3:1-5)።

3. አመጸኛ ቤተ ክርስቲያን (በክርስቶስ ታማኝ ክርስቲያኖች የሚገኙባት) ከስደት ብሻገር፥ መነቃቃትን ትለማመዳለች (ሉቃ. 21:12-15፤ የሐዋ. 2:17-21፤ ያዕ. 5:7-8)።

4. ወንጌል በዓለሙ ሁሉ ለሚኖሩ የተለያዩ ቡድኖች ይሰበካል (ማቴ. 24:14፤ ራእይ 5:9-10)። በዚህ ጊዜ ከዓለም ሁሉ እጅግ ብዙ ሕዝብ በክርስቶስ ያምናል (ኢዩ. 2:28-32፤ ማቴ. 24:14፤ ራእይ 7:9-15)።

5. በክርስቲያኑ ጎብረተሰብ ውስጥ ከሚገኙና ዳግም ስለ ተወለዱ ወገኖች ከፍተኛ ፖለቲካዊ መስመር የያዘች ዓለማዊት ቤተ ክርስቲያን ትመሠረታለች። ይህች የማትታመን ቤተ ክርስቲያን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፥ እንደማትታመን ሚስት ወይም ጋለሞታ ሴት ሆና ተገልጻለች (ራእይ 17:1-18)።

በማኅበረሰቡ ውስጥ ስለሚኖሩ ሁኔታዎች የተሰጡ ትንቢቶች

1. እየጨመረ የሚሄድ ሥርዓት አልበኝነትና ግልጽ ክፋት ከመስፋፋቱም፥ በተለይም በወላጆችና በሌሎች ባለሥልጣናት ላይ የሚፈጸም ዓመፅ፥ የዚህ ማኅበረሰብ መለያ ይሆናል (2 ጢሞ. 3:1-4)። ጭካኔ፥ ግድያ፥ የምትሐት ልምምድ፥ ሥርቆትና ወሲባዊ ኃጢአቶች በከፍተኛ ደረጃ ይጨምራሉ (ማቴ. 24:10፥ 12፤ ራእይ 9:21)።

2. የማኅበረሰቡ ሁኔታ ከራስ ወዳድነት አኗኗሩና ለእግዚአብሔር ከሚኖረው ግዴለሽነት በኖህ ዘመን ከደረሰው የጥፋት ውኃ በፊት የነበረውን ይመስላል (ማቴ. 24:37-38፤ ሉቃ. 17:26-27)። በተጨማሪም፥ የማኅበረሰቡ ሁኔታ የሰዶምና የገሞራ የተመሳሳይ ፆታዎች ወሲባዊ ግንኙነት የነበረበትን የሎጥን ዘመን ይመስላል (ሉቃ. 17:28-29፤ ዘፍጥ. 19:1-13)። እንዲህ ዓይነት የተመሳሳይ ፆታዎች ወሲባዊ ግንኙነቶች ዛሬ የተለመዱ ጉዳዮች እየሆኑ ናቸው። የተመሳሳይ ፆታዎች ግንኙነትና ሌሎችም የወሲብ ኃጢአቶች በዓለም ውስጥ ለተንሰራፋው የኤድስ መቅሠፍት ዋንኛ ምክንያቶች ናቸው።

3. በብዙ ስፍራዎች ከፍተኛ ረሀብ ይነሣል (ማቴ. 24:7፤ ራእይ 6:5-6)።

4. ከፍተኛ የኑሮ ውድነትና የዓለም የገንዘብ ቀውስ ይኖራል (ራእይ 6:5-6)። እንዲህ ዓይነቱ የገንዘብ ቀውስ ሐሳዊ-መሢሕ የዓለም አገዛዙንና የኢኮኖሚ ዕቅዱን ተግባራዊ እንዲያደርግ ሁኔታዎችን ያመቻችለታል (ራእይ 13:7፥ 16-17)።

5. አሥር የአውሮፓ አገሮች የሚገኙበት ኮንፌዴሬሽን በቀድሞው የሮም መንግሥት አጠቃላይ መልከአ ምድራዊ ክልል የሚነሣ ይመስላል (ዳን. 2:40-44)። አውሬው ምናልባትም በዚህ ኮንፌዴሬሽን አማካኝነት

ወደ ዓለም የፖለቲካ መድረክ ሊሸጋገር ይችላል (ዳን. 7:7-8፥ 19-25፥ ራእይ 17:12-17)።

ስለ ተፈጥሮአዊ ዓለም የተሰጡ ትንቢቶች

1. በዓለም ዙርያ የምድር መናወጥ ይጨምራል (ማቴ. 24:7)። የመጨረሻው የምድር መናወጥ ምድርን በሙሉ ያንቀጠቅጣታል (ኢሳ. 24:19-20፥ ራእይ 16: 18-20)።

2. የምድር አየርና ውኃ ይበከላሉ (ኢሳ. 24:5-6፥ ራእይ 11:18፥ 16:3-4)።

3. የፀሐይ ሙቀት እጅግ ከፍተኛ ይሆንና በምድር ላይ ዛፎችንና ሣሮችን ያቃጥላል፥ ወንዞችንም ያደርቃል (ኢሳ. 30:26፥ ራእይ 8:7፥ 16:8፥ 12)።

4. ከከፍተኛ በረዶ የተነሣ፥ የምድር ነፋሳትና የአየር ሁኔታ ይለወጣል (ራእይ 7:1፥ 11:19፥ 16:21)።

5. ልክ ኢየሱስ ሊመለስ ሲል፥ ፀሐይ ትጨልማለች፥ ጨረቃ እንደ ደም ትቀላላች (ኢዩ. 2:30-31፥ ማቴ. 24:29፥ ራእይ 6:12)።

6. ምድርና መላዋ አጽናፍ–ዓለም ለመጨረሻ ጊዜ ይንቀጠቀጣል፥ ይናወጣል (ኢሳ. 24:19፥ ሐጌ. 2:6፥ ዕብ. 12:26፥ ራእይ 6:12-14)።

ሐ. የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ምን ይመስል ይሆን?

ከ2000 ዓመታት በፊት የመጀመሪያ መምጣቱ እውነተኛ ክስተት እንደ ነበረ ሁሉ፥ የክርስቶስ ዳግም ምጽአትም በቦታና ጊዜ የሚገለጽ እውነተኛ የወደፊት ክስተት ነው (ማቴ. 16:27፥ የሐዋ. 1:11)። የክርስቶስን ዳግም ምጽአት ስንሞት ከኢየሱስ ጋር በአየር ላይ ከምንገናኝበት ሁኔታ ጋር ማምታታት የለብንም (2 ቆሮ. 5:6-8)። በእርግጥም ኢየሱስ በመስቀል ላይ ንስሐ ለገባው ወንበዴ ቃል እንደ ገባው፥ ክርስቲያኖች በሚሞቱበት ጊዜ ከጌታ ጋር ይገናኛሉ (ሉቃ. 23:43)፤ ይሁንና፥ ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ ተገለጸው፥ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን፥ ኢየሱስ ሲመለስ የትንሣኤ

አካላቸውን ያገኙ ዘንድ አስቀድመው የሞቱትን ቅዱሳን ሁሉ ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋል (1 ተሰ. 4:14-16)።

የክርስቶስ መመለስ በሰው ልጅ ታሪክ ሁሉ የላቀ ክስተት ይሆናል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ክርስቶስ መመለስ የቀረበው ገለጻ ከሰው ልጅ ምናብ የራቀ ነው። በታሪክ ውስጥ ከዚህ ክስተት ጋር የሚወዳደር ነገር የለም።

በዚያን ዕለት በምድር ላይ የሚኖር የሰው ልጅ በሙሉ፥ በአድናቆትና በፍርሃት ወደ ሰማይ አሻቅቦ ይመለከታል (ራእይ 1:7)። ይህም የአጽናፈ-ዓለሙ ንጉሥ ወደ ፈጠረው ዓለም እየተመለሰ በመሆኑ፡ ሊደረግ የሚገባው ነው። ዘላለማዊት ሙሽራዋን ማለትም ቤተ ክርስቲያንን ለመቀበል ይመለሳል። የምድርና የሰማይ አምላክ በመሆኑ፥ ዙፋኑንና ዘላለማዊ የግዛት ኃይሉን ለመውሰድ እንደ ድል ነሺ ንጉሥ ይመለሳል። ኢየሱስ «በኃይልና በታላቅ ክብር» እንደሚመለስ ገልጾአል (ማቴ. 24:30)። ልክ በከበረ የትንሣኤ አካሉ እንዳረገ፥ እንዲሁ በአካል ይመለሳል (የሐዋ. 1፥11)። ዓለሙም ሁሉ ሲመለስ ያየዋል (ራእይ 1:7)።

መጽሐፍ ቅዱስ፡ «ከሥልጣኑ መላእክት ጋር ከሰማይ በእሳት ነበልባል» እንደሚመለስ ይናገራል (2 ተሰ. 1:7)። ኢየሱስም፥ በክብሩ ከመላእክት ሁሉ ጋር እንደሚመጣ ተናግሮአል (ማቴ. 25:31)።

የኢየሱስ መመለስ ማለት፡ በምዕራፍ ሰባት እንደ ተመለከትነው፥ የእግዚአብሔር ማዳን ለሕዝቡ ተፈጸመ ማለት ነው። በታላቅ የመለከት ድምፅ ይመለሳል (ማቴ. 24:31፤ 1 ተሰ. 4:16)። ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ፡ አስቀድመው የሞቱት ክርስቲያኖች ከሞት ይነሡና ኢየሱስን በአየር ለመቀበል ይነጠቃሉ። ይህም በዓይን ቅጽበት የሚከናወን ይሆናል (1 ቆሮ. 15:51-52)። በዚያን ጊዜ ክርስቲያኖች ልክ የክርስቶስን የሚመስል የትንሣኤ አካል ይቀበላሉ (1 ቆሮ. 15:52)። ወዲያው ደግሞ በምድር ላይ በሕይወት የነበሩ ክርስቲያኖች በአካል ወደ ክርስቶስ የትንሣኤ አምሳል ይለወጡና ከክርስቶስንና አሁን ከሞት ያነሣቸውን አማኞች ለመገናኘት ወደ ሰማይ ይነጠቃሉ (1 ቆሮ. 15:51-52፤ 1 ተሰ. 4:16)።

መጽሐፍ ቅዱስ፥ «እኛ አገራችን በሰማይ ነውና፥ ከዚያም ደግሞ የሚመጣ መድኃኒትን እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን፤ እርሱም ሁሉን እንኳ ለራሱ ሊያስገዛ እንደሚችልበት አሠራር፥ ከቡር

ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል» ይላል (ፊልጵ. 3:20-21)።

በክርስቶስ መመለስ ጊዜ ብዙ አስደናቂ ነገሮች ይፈጸማሉ። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ሰማይም እንደ መጽሐፍ ተጠቅልሎ አለፈ፥ ተራሮችና ደሴቶችም ሁሉ ከስፍራቸው ተወሰዱ» ይላል (ራእይ 6:14)። የርዕደ-ምድርንም ታላቅነት ሲገልጽ፥ «ሰው በምድር ከተፈጠረ ጀምሮ እንዲህ ያለ ታላቅ መናወጥ ከቶ አልነበረም፤ ከሁሉ በለጠ!» ይላል (ራእይ 16:18)። እያንዳንዳቸው መቶ ፓውንድ (45 ኪሎ ግራም ያህል) የሚመዝኑ በረዶዎች ከሰማይ እንደሚወድቁም ይናገራል! (ራእይ 16:21)። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «የሐይል ይጨልማል፥ ጨረቃም ብርሃንዋን አትሰጥም፥ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፥ የሰማያትም ኃይላት ይናወጣሉ» ይላል (ማቴ. 24:29)።

እንዲህ ዓይነቱን አሠራርና ክስተት ከቶ ማን ሊረዳ ወይም ሊገልጽ ይችላል? በሚሊዮን የሚቆጠሩ የእግዚአብሔር መላእክት በሚያብረቀርቀው ክብራቸውና በእሳት ጠቅላላውን ሰማይ በብርሃን ሲያጥለቀልቁት እንዴት ልንገልጽ እንችላለን! ከመቅጽበት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ክርስቲያናች ከዓለም ሁሉ፥ ከጌታና ከታላላቅ የመላእክቶቹ ሠራዊት ጋር ለመደባለቅ በከበሩ የትንሣኤ አካላት ወደ ሰማይ የሚነጠቁበትን ሁኔታ እንዴት ልናስተውል እንችላለን! ሰማዩ ራሱ እንደ መጽሐፍ የሚጠቀለልበትን ሁኔታ እንዴት ልናስተውል እንችላለን!

በሰማያት ይሽው የሚመስጥና የሚያስደንቅ ትዕይንት እየተፈጸመ፥ ምድር በሙሉ በሰው ልጅ ታሪክ እጅግ ከፍተኛ በሆነ የመሬት ነውጥ ትመታለች (ራእይ 16:18)። መጽሐፍ ቅዱስ የመሬት ነውጡ እጅግ ታላቅ በመሆኑ «ተራራዎችና ደሴቶችም ሁሉ ከስፍራቸው» እንደ ተወሰዱ ይናገራል (ራእይ 6:14)። በሌላ ስፍራም ይህንኑ የመሬት መንቀጥቀጥ፥ «ምድር ተሰባበረች፥ ምድር ፈጽማ ደቀቀች፥ ምድር ተነዋወጠች» ሲል ይገለጻል (ኢሳ. 24:19)። በሐጌ 2:6 ስለ ክርስቶስ መመለስ ጌታ፥ «ገና አንድ ጊዜ በቅርብ ዘመን እኔ ሰማያትንና ምድርን ባሕርንና የብስንም አናውጣለሁ፥ በአሕዛብ ሁሉ የተመረጠውም ዕቃ ይመጣል» ሲል የተስፋ ቃል ይሰጣል።

ደኅንነትን ላገኙ የእግዚአብሔር ቅዱሳን፥ ዋክርስቶስ መመለስ ግለት በመጨረሻ ከዚህ ክፉ የተበላሸ ዓለም ይላቀቃሉ ማለት ነው (ሮሜ 8:21-

23)። የራሱ የክርስቶስ ኢየሱስን የከበረ አምሳል መስለው ይለወጣሉ ማለት ነው (ፊልጵ. 3:21-22)። ለተቀረው የሰው ልጅ የክርስቶስ ምጽአት አስፈሪ ክስተት ነው፤ ይህም ለኃጢአተኛ ጠባያቸው በመጨረሻው ይፈርድባቸዋል ማለት ነው። በመጨረሻው በእግዚአብሔር ላይ ለፈጸሙት ዓመፅ ሁሉ ዋጋ ይከፍላሉ (2 ተሰ. 1:7-10)። የክርስቶስ ምጽአት ላልዳኑ ሰዎች እጅግ አስፈሪ ስለሚሆን፥ በዓለም በብርታታቸው የሚታወቁ ሰዎች ሳይቀሩ በሽብር መሸሸጊያ ሲሹ ይታያሉ። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «የምድርም ነገሥታትና መኳንንት ሻለቃዎችና ባለጠጋዎችም ኃይለኛዎችም ባሪያዎችም ጌቶችም በዋሾችና በዓለቶች ተሰወሩ፥ ተራራዎችንና ዓለቶችንም፦ በላያችን ውደቁ በዙፋኑም በተቀመጠው ፊት ከበጉም ቁጣ ሰውሩን፤ ታላቁ የቁጣው ቀን መጥቶአልና፥ ማን ሊቆም ይችላል? አሉአቸው» ይላል (ራእይ 6:15-17)።

መ. ክርስቶስ መቼ ይመለሳል፡

መጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛውን የክርስቶስ መምጫ ጊዜ ግንም እንደማያውቅ በግልጽ ይናገራል። ይህም ሆኖ፥ መጽሐፍ ቅዱስ የቤተ ክርስቲያን የመጨረሻው ትውልድ የመመለሱ ጊዜ አንደ ቀረበ እንደሚረዳ ያመለክታል። ክርስቶስ ስለ ምጽአቱ የተናገረው ከሁሉም የሚሰፋ መልእክት በማቴዎስ 24:1-25:46 ይገኛል። በዚህ ውይይት ጊዜ ኢየሱስ፥ «እንዲሁ እናንተ ደግሞ ይህን ሁሉ ስታዩ በደጅ እንደ ቀረበ እወቁ። እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ ሁሉ እስኪሆን ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም» ብሏል (ማቴ. 24:33-34)። ይሁንና ኢየሱስ ንግግሩን በመቀጠል፥ «ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም . . . ጌታችሁ በምን ሰዓት እንዲመጣ አታውቁምና እንግዲህ ንቁ» ብሏል (ማቴ. 24:36፥ 42)። እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ስለ ክርስቶስ የመመለሻ ጊዜ የምናውቀውም የማናውቀውም ሁኔታ እንዳለ ይገልጻሉ።

ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው ደብዳቤ፥ ጳውሎስም ስለ ጌታ መመለስ እርግጠኛ ስለ ሆነባቸውና እርግጠኛ ስላልሆነባቸው ነገሮች ተናግሯል። ጳውሎስ፥ «ወንድሞች ሆይ፥ ስለ ዘመናትና ስለ ወራት ምንም እንዲጻፍላችሁ ኣያስፈልጋችሁም፤ የጌታ ቀን ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ እንዲሁ ይመጣ ዘንድ ራሳችሁ አጥብቃችሁ አውቃችኋልና . . . እናንተ

ግን ወንድሞች ሆይ፥ ቀኑ እንደ ሌባ ይደርስባችሁ ዘንድ በጨለማ አይደላችሁምም» ብሏል (1 ተሰ. 5:1-2፥ 4)።

ምናልባት ስለ ክርስቶስ ምጽአት የሚታየውን ግጭት መሳይ ነገር ለመረዳት፥ ከሁሉም የሚሻለው ኢየሱስ ራሱ የሰጠው የምጥ ጣር ምሳሌን መመልከቱ ሳይሆን አይቀርም። በማቴዎስ 24:7- 8 ኢየሱስ፥ «ሕዝብ በሕዝብ ላይ፥ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣልና፥ ራብም ቸነፈርም የምድርም መናወጥ በልዩ ልዩ ስፍራዎች ይሆናል፤ እነዚህም ሁሉ የምጥ ጣር መጀመሪያ ናቸው» ብሏል።

አንዲት ሴት ምጥ ሲይዛት፥ የሚወለደው ልጅ በጣም እንደ ቀረበ ታውቃለች። ይሁንና፥ በዓለም የትኛውም እውቅ ዶክተር ቢሆን የልጁ ጭንቅላት ብቅ የሚልበትን ትክክለኛ ጊዜ ሊተነብይ አይችልም። አንዳንድ ጊዜ ምጥ ብዙ ብዙ ሰዓታት ሲወስድ፥ አንዳንድ ጊዜ ከአንድ ሰዓት ባነሰ ጊዜ ይፈጸማል። እርገጠኛነቱ እንግዲህ፥ እውነተኛ ምጥ ከጀመረ በኋላ፥ ልጁ የሚወለደው በቅርብ ጊዜ ውስጥ እንጂ ከሳምንታት ወይም ከወራት በኋላ እንዳልሆነ ነው።

የክርስቶስም መመለስ እንዲሁ ይሆናል። የምጽአቱ ጊዜ እየቀረበ ሲመጣ፥ በዓለም ከፍተኛ የምጥ ጣር ይኖራል። የምጥ ጣሮች በማቴዎስ 24:1- 25 ተገልጸዋል። የምጥ ጣር ልጁ የሚወለድበት የመጨረሻው ጊዜ ሊቀርብ፥ በከፍተኛ ደረጃ መጣደፍ ይጀምራል። የክርስቶስም መመለስ ጊዜ እንዲሁ ይሆናል። የምጥ ጣር በምድር ላይ በጣም አስቸጋሪ ጊዜ ነው፤ ይሁንና ይህ ለጌታ ሕዝቦች አዳኛቸው ለዘላለም ወደ መንግሥተ ሰማይ ይወስዳቸው ዘንድ ሊመለስ እንደ ደረሰ ያስታውቃቸዋል (ሉቃ. 21:28)።

ሠ. አንድ ሰው ለዚህ ዘመን የመጨረሻ ክስተቶችና ለክርስቶስ መመለስ እንዴት ሊዘጋጅ ይችላል?

የክርስቶስ መመለስ የቤተ ክርስቲያን የተባረከ ተስፋ ነው (ቲቶ. 2:13)። ስለ ሆነም፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቶስ ምጽአት የሚናገሩትን ምንባቦች ማጥናቱ መልካም ነው። ስለ ምጽአቱ ከሚናገሩ አንዳንድ አስፈላጊ ምንባቦች መካከል ማቴዎስ 24 - 25፤ ማርቆስ 13፤ ሉቃስ 21፤ 1 ቆሮንቶስ 15:35-58፤ 1 ተሰሎንቄ 4:13 - 5:10፤ 2 ተሰሎንቄ 1-2፤ 2 ጴጥሮስ 3፤ እና ራእይ 6 - 22 ይገኙባቸዋል።

አስቀድመን በዚህ ምዕራፍ እንደ ተመለከትነው፥ የዚህ ዘመን ፍጽሜ በከፋ ወንጀል፥ ጭካኔ፥ ወሲባዊ ዋልጌነት፥ ምትሐታዊ ኃይልና በክርስቲያኖች መሰደድ ተለይቶ ይታወቃል። ስለ ሆነም፥ ክርስቲያኖች ለመጨረሻዎቹ ቀናት ራሳቸውን ሊያዘጋጁ ይገባል። ለዚህም የሚከተሉትን ግዴታዎች ማጋላት አለብን፡-

1. በጸሎት መትጋት (ኤፌ. 6:18፤ 1 ጴጥ. 4:7)

2. በቅድስና መመላለስ (2 ጴጥ. 3:11፤ 1 ዮሐ. 3:2-3)።

3. በጌታ መበርታትና በሰይጣን ላይ መንፈሳዊ የጦር ዕቃዎችን መጠቀምን መማር (2 ቆሮ. 10:3- 4፤ ኤፌ. 6:10-19)።

4. አብረዋቸው የሚያመልኩትን ክርስቲያኖች ከልብ መውደድና ይቅር ማለት (ቆላ. 3:12-14፤ 1 ጴጥ. 4:8)።

5. ለመበረታታትና ለኅብረት ከሌሎች አማኞች ጋር መሰባሰብ (ማቴ. 18:19-20፤ ዕብ. 10:25)።

6. ስደትን ሳንፈራ፥ ስለ ኢየሱስ ለሌሎች በድፍረት ለመመስከር መዘጋጀት (የሐዋ. 1:8፤ 1 ጴጥ. 3:14-15)።

7. በዓለም ወንጌል ላልደረሳቸው የሕዝብ ቡድኖች ወንጌሉን ለማድረስ በትጋት መሳተፍ (ማቴ. 24:14፤ 28:19-20) ።

በአዲስ ኪዳን በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ላይ የተደረገው ትኩረት በጣም ተግባራዊ ነው። ሌላውም አስፈላጊ ክንውን እንዳለ ሆኖ፥ ሁልጊዜም አትኩሮቱ ባሁኑ የተቀደሰ አኗኗርና ለክርስቶስ በሚቀርብ የታማኝነት አገልግሎት ላይ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በየትኛውም ስፍራ የክርስቶስን ትክክለኛ የመመለሻ ጊዜ እንድናሰላ አያበረታታንም። በየትኛውም ስፍራ በዚህ ዘመን መጨረሻ የሚፈጸሙትን የክስተቶች ቅደም ተከተል በሠንጠረዥ እንድንዘረዝር የሚያበረታታ አሳብ አልተሰጠንም። ይሁንና ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት የሚናገሩ አያሌ መጻሕፍት በዋናነት የክስተቶቹን ቅደም ተከተል ለማረጋገጥ ይጥራሉ። ይህ የተሳሳተ ትኩረት ነው። እንዲሁም፥ አዲስ ኪዳን ስለ ክርስቶስ መመለስ የሚሰጠውን ትምህርት አለመረዳት ነው።

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የመጨረሻዎቹን የታሪክ ክስተቶች ከማወቅ እጅግ የሚበልጥ ነገር አሳይቶአቸዋል። ቢያስፈልግ እስከ መሞት ድረስ

ታማኝ ምስክሮቹ መሆን ነበረባቸው (ራእይ 2:10)። ስለ መምጣቱ ርግጠኞች ስለ ሆንን፥ ለሌሎች በታማኝነት ስለ ክርስቶስ ልንመሰክር ይገባል። ለሚሰማ ሁሉ በታማኝነት ማዳኑን ማወጅ አለብን። ኢየሱስ ይህንን «በኢየሩሳሌም» ማለትም በራሳችን ወገኖች መካከል፥ «በይሁዳና በሰማርያ ሁሉ» ማለትም በአገራችን በሚገኙ ሌሎች የሕዝብ ቡድኖች፥ ብሎም «እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ» በሁሉም የዓለም አገሮችና ባህሎች እንድናደርግ ተናግሯል (የሐዋ. 1:8)።

በመንጌል አገልግሎት ላይ የማታተኩር አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዘመን የእግዚአብሔር ሥራ ዋንኛ አካል አይደለችም። ኢየሱስ ሲመለስ፥ በታማኝነታቸው ላይ ተመሥርቶ በሕዝቡ ላይ ይፈርዳል። ታማኞች ከነበሩ ከክርስቶስ ሽልማትን ይቀበላሉ (1 ቆሮ. 3:14)። ታማኞች ካልነበሩ ደግሞ ሽልማትን አጥተው ያነባሉ (1 ቆሮ. 3:15)። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «መልካም ቢሆን ከፉ እንዳደረገ፥ እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንጋለጥ ይገባናልና» ይላል (2 ቆሮ. 5:10)። ማንኛውም ክርስቲያን አማኝ ሆኖ ስለ ተመላለሰበት ሁኔታ የሚሰማውን ይህንን ፍርድ አያመልጥም። ታማኞች እንድንሆን ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል። እነዚህ ሁለት ትምህርቶች አዲስ ኪዳን የክርስቶስን ዳግም ምጽአት እንዴት ክርስቲያን በዕለታዊ ሕይወቱ ተግባራዊ እንደሚያደርግ አጠቃልለው ያቀርባሉ።

ኢየሱስ ስለ ዳግም ምጽአቱና ምጽአቱን ስለሚያጅቡ ክስተቶች በተናገረው ረጅም የማቴዎስ 24:1-25:46 ክፍል፥ አራት ታሪኮችን አቅርቦአል። የሚያስገርመው እነዚህ አራት ታሪኮች ሁለት ቀላል ትምህርቶችን ብቻ ማስተላለፋቸው ነው፤ ማለትም እያንዳንዱ ትምህርት ሁለት ጊዜ ተተርኮአል ማለት ነው፤ ትምህርቶቹም ዝግጁና ታማኝ ስለ መሆን የሚናገሩ ናቸው። እነዚህ ሁለቱ ትምህርቶች አዲስ ኪዳን የክርስቶስን ዳግም ምጽአት እውነታ ጋር እንዴት እንደሚያዛምድ አጠቃለው ያሳያሉ።

በማቴዎስ 24:37- 44፥ ኢየሱስ ለምጽአቱ ያልተዘጋጁትን እያሉ የሕዝብ ቡድኖች የጠቀሰ ሲሆን፥ ትምህርቱም፥ «እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ» ይሚል ነበር። በማቴዎስ 24:45-51፥ ጌታቸው ወደ ሌላ አገር ስለ ሄደባቸው ሁለት ታማኝ ባሪያዎች እና አንድ ታማኝ ስላልነበረ ባሪያ ተናግሯል። ትምህርቱም፥ «እንግዲህ፥ ታማኝና ልባም

ባሪያ ግን ነው?» የሚል ነው። በማቴዎስ 25:1-13 ስለ አሥሩ ቆነጃጅት የተናገረ ሲሆን፥ ትምህርቱም ለሙሽራው መመለስ መዘጋጀትን ይመለከታል። በማቴዎስ 25:14-30 የተለያየ መጠን ያለው ገንዘብ፥ «መክሊት» ተሰጥቶአቸው እንዲያተርፉ ስለ ተናገራቸው ሦስት ሰዎች ይገልጻል። የዚህም ትምህርት፥ «መልካም፥ አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ» የሚል ነበር።

ስለ ክርስቶስ ምጽአት እጅግ አስፈላጊው እውነት ያለ ጥርጥር እግዚአብሔር በወሰነው ጊዜ የሚፈጸም መሆኑ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝቦች መዘጋጀት አለባቸው። ታማኞች መሆን አለባቸው።

መዘጋጀት ሲባል ምን ማለት ነው? ሐዋርያው ጴጥሮስ ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ሲናገር፥ መዘጋጀት ምን እንደ ሆነ ገልጾአል። «የጌታ ቀን ግን እንደ ሌባ ሆኖ ይመጣል፤ በዚያም ቀን ሰማያት በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ፥ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኩሳት ይቀልጣል፥ ምድርም በእርስዋም ላይ የተደረገው ሁሉ ይቃጠላል። ይህ እንዲህ የሚቀጥል ከሆነ፥ የእግዚአብሔር ቀን መምጣት እየጠበቃችሁና እያስቸኮላችሁ፥ በቅዱስ ኑሮ እግዚአብሔርንም በመምሰል እንደ ምን ልትሆኑ ይገባችኋል?» (2 ጴጥ. 3:10-12)።

ሐዋርያው ዮሐንስ ተመሳሳይ አሳብ ተናግሯል። በ1ኛ ዮሐንስ 3:2-3፥ «ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን። በእርሱም ይህን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ንጹሕ እንደ ሆነ ራሱን ያነጻል» ይላል። ሐዋርያው ጳውሎስ በዚሁ አሳብ ላይ አጽንኦት በመስጠት፥ «ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና፤ ይህም ጸጋ፥ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን፥ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል» ይላል (ቲቶ. 2:11-13)።

እነዚህ ሦስት የክርስቶስ ሐዋርያት እንደሚሉት፥ ለክርስቶስ ምጽአት መዘጋጀት በቅድስና መኖር ነው። ይህም ማለት ከውሸት ከትዕቢትና ከራስ ፍላጎት፥ ከምኞት፥ ከስግብግብነት፥ ከኀሰኝነትና ከአድልኦ፥ ከመራርነትና ይቅር ካለማለት፥ እንዲሁም ሕይወታችንን ከሚያረክሱና ቅድስናችንን ከሚያጎድፉ ሌሎች ነገሮች ሁሉ መራቅ ማለት ነው።

ክርስቲያን የተቀደሰ ሕይወት የማይኖር ከሆነ፥ ለክርስቶስ ምጽአት አልተዘጋጀም ማለት ነው።

ረ. ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ ስለሚኖሩ የክስተቶች ቅደም ተከተል ከሚናገሩ ዐበይት ጽንሰ-አሳቦች (ቲዎሪዎች) አንዳንዶቹ ምንድን ናቸው?

በክርስቶስ ምጽአት ወቅት የሚሆነው የክስተቶች ቅደም ተከተል ለብዙ ክፍለ ዘመናት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲያከራክር ቆይቷል። በየትኛውም ወገን ሆነው የሚከራከሩ ሰዎች መንፈሳዊና ብቁ ምሁራን ነበሩ። የሚያስገርመው የእነዚህ ምሁራን ጽንሰ-አሳቦች ብዙውን ጊዜ የተለያዩ ናቸው። ለምን ይሆን? በመጀመሪያ ደረጃ፥ እነዚህ ክስተቶች ገና አልተፈጸሙም፤ ስለ ሆነም የተለያዩ ትንቢቶችን ትርጉም በተመለከተ የአሳብ ልዩነት አለ። ሁለተኛ፥ የተለያዩ የክርስቲያኖች ቡድኖች የትንቢትን ትርጉም ለማወቅ የተለያዩ ዓይነት የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓገሞችን ማለትም የአተረጓጎም ዘዴ ("hermeneutics") ይጠቀማሉ። እነዚህ የተለያዩ ዘዴዎች ምሁራን ተመሳሳይ የትንቢት ዓረፍተ ነገሮችን በጣም በተለያዩ መንገዶች እንዲተረጎሙ ያደርጓቸዋልና። ሦስተኛ፥ የመጨረሻው ዘመን ክስተቶች ቅደም ተከተል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ አልተቀመጠም። በዚህ ዓይነት በቅደም ተከተል ቢደረደር ኖሮ ምናልባትም አለመስማማት ላይኖር ይችል ነበር።

ከእነዚህ የአሳብ ልዩነቶች አንዱ ቅዱሳን « ከክርስቶስ ጋር ሺህ ዓመት ኖሩና ነገሡ» የሚለው ነው (ራእይ 20:4)። ራእይ 20 ይሽው ክስተት ለ1000 ዓመታት እንደሚቆይ የሚገልጽ ብቸኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ነው። ብዙ ክርስቲያኖች ይህ ትንቢት ክርስቲያኖች ከክርስቶስ ጋር በምድር ላይ በቀጥተኛ ትርጉሙ ለሺህ ዓመታት የሚነግሡበትን ጊዜ ያመለክታል ብለው ያምናሉ። ይህንንም የሺህ ዓመታት መንግሥት ("millenium") ብለው ይጠሩታል። ሌሎች አያሌ ክርስቲያኖች ይህ ትንቢት ቀጥተኛ ክፍለ ጊዜ ወይም በአካል ከክርስቶስ ጋር መግዛትን አያመለክትም ይላሉ።

ከክርስቶስ ጋር በቀጥተኛ ትርጉም ለሺህ ዓመታት እንደምንነግሥ የሚያምኑ ክርስቲያኖች፥ ኢየሱስ ምድራዊ መንግሥት ለመመሥረት ከሚመለስበት ከሺህ ዓመታቱ መጀመር ጥቂት ቀደም ብሎ እንደሚመጣ ያምናሉ። ይህንንም አመለካከት የሚይዙ ክርስቲያኖች ቅድመ-ሺህ-ዓመታት ("pre-millenialists") ተብለው ይጠራሉ። በእነዚህ የቅድመ-

ሺህ-ዓመታት አማኞች መካከል እንኳን፥ ከሺህ ዓመታቱ መንግሥት ጅማሬ በፊት ስለሚከሰተው ነገር የተለያዩ አመለካከት ያላቸው አያሌ ወገኖች አሉ።

ክርስቶስ ከመመለሱ ጥቂት ቀደም ብሎ በዓለም ታላቅ ፍዳ እንደሚመጣ ተተንብዮአል። ይህ ከፍለ ጊዜ በማቴዎስ 24:21 እና በራእይ 7:14 የፍዳ ዘመን ("tribulation") ተብሏል። የቅድመ-ሺህ-ዓመታት አማኞች ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያኑ የሚመለሰው ከዚህ ፍዳ ዘመን በፊት፥ በመካከል፥ ወይስ በመጨረሻው ላይ ነው ሲሉ ይጠይቃሉ። ከመከራው በፊት እንደሚመጣ የሚያምኑ ወገኖች ቅድመ-ሺህ-ዓመታውያንና ቅድመ-ፍዳ-ዘመን ("pre-tribulational") ይባላሉ። በመከራው አጋማሽ ላይ እንደሚመጣ የሚያምኑት ደግሞ ቅድመ-ሺህ-ዓመታውያንና መሀል-ፍዳ-ዘመን ("mid-tribulational") ይባላሉ። ከመከራው ፍጻሜ ላይ እንደሚመጣ የሚያምኑ ወገኖች፥ ቅድመ-ሺህ-ዓመታውያንን ድሕረ-ፍዳ-ዘመን ("post-tribulational") ይባላሉ።

ሌሎች ብዙ ክርስቲያኖች ሺህ ዓመታት በፍጹም ቀጥተኛ ትርጓሜ እንዳለው አያምኑም፤ እነዚህ ወገኖች የራእይ መጽሐፍ ባብዛኛው በቅኔያዊና ተምሳሌታዊ ቋንቋ እንጂ በቀጥተኛ አገላለጽ እንዳልቀረበ ያመለክታሉ። በእነርሱ ግንዛቤ፥ የራእይ 20:4 ትንቢት በተምሳሌት መተርጎም አለበት። እንዳንዶች ሺህ ዓመታት ረዥም የጊዜ ገደብ እንደሚያመለክት ሲናገሩ፥ ሌሎች ደግሞ የሺህ ዓመታቱ መንግሥት ቀጥተኛ ሳይሆን ከክርስቶስ ጋር የምንነግሥበትን መንፈሳዊ እውነታ ያሳያል ይላሉ። የሺህ ዓመታቱ መንግሥት መንፈሳዊ ግዛት እንደ ሆነ ከሚያምኑ ወገኖች መካከል፥ አንዳንዶቹ ባሁኑ ጊዜም በዚሁ ከፍለ ጊዜ ውስጥ እንዳለን ይገልጻሉ። ይሽው አመለካከት ያላቸው ክርስቲያኖች የሺህ ዓመታቱን ቀጥተኛ ከፍለ ጊዜ ስለማይጠባበቁ፥ ኢ-ሺህ-ዓመታውያን ("amillenialists") ተብለው ይጠራሉ።

አሁንም ሌላው ቡድን፥ የወንጌሉ ስብከት ባጠቃላይ ዓለሙን በሙሉ ክርስቲያን ካደረገ በኋላ ብቻ ክርስቶስ ወደ ምድር እንደሚመለስ ያምናል። ለእነዚህ ወገኖች፡ የሺህ ዓመታቱ መንግሥት የሚመሠረተው በዓለም ሁሉ የእግዚአብሔር መንግሥት በመስፋፋቱና በመሰራጨቱ አማካኝነት ቤተ ክርስቲያን ስትበራከት ነው። ለዚህ ቡድን የሺህ ዓመታቱ መንግሥት ባሁኑ ጊዜ በእድገት ላይ እንዳለ ሊታመን ይችላል። የዚህ ዓይነት አቋም ያላቸው ክርስቲያኖች ድሕረ-ሺህ-ዓመታውያን ("post-millenialists")

ይባላሉ። ኢ-ሺህ-ዓመታትና ድሕረ-ሺህ-ዓመታት ታላቁን የፍዳ ዘመን ጊዜ በተመለከተ፥ ክርስቶስ ከመመለሱ በፊት እንዲህ ዓይነት ጊዜ እንደሚኖር ብቻ ያምናሉ።

በተጨማሪም፥ ስለ ራእይ 20:4 ትርጉምና ስለ ሌሎችም የመጨረሻው ዘመን ትንቢቶች፥ ብሎም ከላይ ስለ ቀረቡትም የአመለካከት ልዩነቶች የሚሰጡ ሌሎች አሳቦች አሉ። ይሁንና፥ በዚህ መጽሐፍ ጉዳዩን ለማጥበብ ሲባል ክርስቲያኖች ስለዚህ ዘመን የመጨረሻ ክስተቶች የሚያቀርቡአቸው አሳቦች በቅድመ-ሺህ-ዓመታት፥ ኢ-ሺህ-ዓመታትና ድሕረ-ሺህ-ዓመታት ሥነ-መለኮታዊ አቋሞች ተመድበዋል።

በእነዚህ በእያንዳንዳቸው ቡድኖች ውስጥ የሚገኙ ክርስቲያኖች ሁሉ በእኩል ደረጃ ለመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን ትክክለኛነት የሚገዙ ናቸው። ይሁንና እያንዳንዱ ቡድን የመጨረሻውን ዘመን ትንቢቶች በተለያዩ መንገዶች ይተረጉማሉ። ስለ ሆነም፥ መልካሙ መመሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ በተጠቀሱ ዐበይት ትምህርቶች ላይ መስማማትና በርግጥኛነት በማንናገራቸው ዝርዝር ጉዳዮች ላይ አለመከራከሩ ነው። በመጨረሻዎቹ ክስተቶች የአረጻጸም ቅደም-ተከተል ላይ የተለየ አቋም ያለውን ወንድም መታገሡ አስተዋይነት ነው። ጊዜው ሲደርስ፥ ሁሉም ሰው የእያንዳንዱን ትንቢት ትርጉም ይረዳዋል። ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት ግልጽ እውነቶች አንዱ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም በአካላዊ ትዕይንት የሚገለጽ መሆኑና (የሐዋ. 1:11) ክርስቲያኖች እርሱ ሲመጣ ከሙታን የሚነሡ መሆናቸው ነው (1 ቆሮ. 15:50-54)።

ሰ. ክርስቶስ ለምን ይመለሳል?

የክርስቶስ መመለስ የዚህ ዘመን የፍጻሜ ክስተት ነው። የአሁኑ ታሪክ ፍጻሜ ነው። ኢየሱስ በሞቱ፥ በትንሣኤውና በዕርገቱ የጀመረውን ማዳን ለሕዝቡ የሚፈጽምበት ጊዜ ነው (ሮሜ 13:11፤ 1 ጴጥ. 1:5)። ባሁኑ ጊዜ እግዚአብሔር በክርስቶስ ምጽአት የሚያስተካክላቸው ብዙ የተበላሹ ነገሮች አሉ። ክርስቶስ ሲመለስ ያልተጠናቀቀውን ሁሉ ወደ ፍጻሜ ይመስደዋል።

ባሁኑ ዘመን ብዙውን ጊዜ ኃጢአተኛው ከመከራ እያመለጠ ዳድቁ ይሠቃያል። ብዙውን ጊዜ የሚጎዱአቸው ሰዎች ያለ ቅጣት በነፃ እየተመላለሱ ክርስቲያኖች ይሰደዳሉ፤ ይሠቃያሉም። ብዙውን ጊዜ በሰዎች ሕይወት ውስጥ ከመልካሙ ይልቅ ክፉው ድል ይነግሣል።

ክርስቲያኖች በሥቃይ፥ በጉስቁልና በስደት ያነባሉ፤ ተስፋ በመቁረጥም ይሞታሉ። ይህ ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ምጽአት ይለወጣል። ክርስቶስ በምጽአቱ ምን ይፈጽም ይሆን?

1. ኢየሱስ ሕዝቡን ወደ ራሱ ይሰበስባል (ዮሐ. 14:2-3)

በዚህ ዓለም በክርስቲያኖች ላይ ምንም ግፍ ቢደርስ፥ አንድ ቀን ኢየሱስ ተመልሶ ወዳጆቹ ለዘላለም ከእርሱ ጋር ይሆኑ ዘንድ ስለሚሰበስባቸው ደስ የሚያሰኝ ተስፋ አላቸው (1 ተሰ. 4:16-17)። በዮሐንስ 14:2-3 ኢየሱስ፥ «በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፤ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና ሄጀም ስፍራ ባዘጋጀሁላችሁ፥ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ» ብሏል። እንደ 1ኛ ተሰሎንቄ 4:16-17 አገላለጽ፥ ክርስቲያኖች ጌታ ሲመለስ ከእርሱ ጋር ለመሆን ከሞት ተነሥተው ይነጠቃሉ። «ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክት አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤ ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናልን» (1 ተሰ. 4:16-17)። ይህ እያንዳንዱ ክርስቲያን ሊጠባበቀው የሚገባው ምንኛ የከበረ ተስፋ ነው! ይህ ክርስቲያንን ካጋጠመው ከማንኛውም የፈንጠዝያ ዕለት በላይ እጅግ አስደሳች ይሆናል!

2. ኢየሱስ ሙታንን ሁሉ ያስነሣል (ዮሐ. 5:25-29)

ብሉይ ኪዳን «በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎቹ ይነቃሉ፤ እኩሌቶቹ ወደ ዘላለም ሕይወት፥ እኩሌቶቹም ወደ እፍረትና ወደ ዘላለም ጉስቁልና» ይላል (ዳን. 12:2)። ኢየሱስ፥ «በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን (የክርስቶስን ድምፅ) የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉ» ብሏል (ዮሐ. 5:28-29)። አስቀድመው የሞቱት ክርስቲያኖች ክርስቶስ በሚገለጽበት ጊዜ ከሙታን ይነሡና የክርስቶስን አካል የሚመስል የትንሣኤ አካላቸውን ይቀበላሉ (1 ቆሮ. 15:51-52፤ ፊልጵ. 3:21፤ 1 ተሰ. 4:15-17)።

የቅድመ-ሺህ-ዓመታት አማኞች፥ ክርስቲያኖች ከሞት የሚነሡት ከሺህ ዓመታቱ መንግሥት በፊት ክርስቶስ ሲመለስ ብቻ እንደ ሆነ ያምናሉ። እነዚህ ወገኖች የማያምኑ ሰዎች ትንሣኤ የሚከናወነው በቀጥተኛ ትርጉሙ በሚፈጸመው የሺህ ዓመታት መንግሥት ፍጻሜ ላይ እንደ ሆነ ያምናሉ። ራእይ 20:4-6፥ «ስለ ኢየሱስ ምስክርነትና ስለ እግዚአብሔር ቃል ራሳቸው የተቆረጡባቸውን ሰዎች ነፍሳት . . . አየሁ፤ ከክርስቶስም ጋር ሺህ ዓመት ኖሩና ነገሡ። የቀሩቱ ሙታን ግን ይህ ሺሁ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በሕይወት አልኖሩም። ይህ የፊተኛው ትንሣኤ ነው። በፊተኛው ትንሣኤ ዕድል ያለው ብፁዕና ቅዱስ ነው፤ ሁለተኛው ሞት በእነርሱ ላይ ሥልጣን የለውም፥ ዳሩ ግን የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ካህናት ይሆናሉ ከእነርሱም ጋር ይህን ሺህ ዓመት ይነግሣሉ» ይላል።

ኢ-ሺህ-ዓመታትና ድሕረ-ሺህ-ዓመታት አማኞች፡ የሁለቱም የክርስቲያኖችና ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች ትንሣኤ በክርስቶስ ምጽአት ጊዜ የሚፈጸም የአንድ ታላቅ ክስተት አካል እንደ ሆነ ያምናሉ።

3. ኢየሱስ ባሪያዎቹን፥ ቅዱሳኑንና ነቢያቱን ይሸልማቸዋል (ራእይ 11:18)

ለጌታ በታማኝነት የኖሩ ብዙ ክርሲቲያኖች አሉ። ኢየሱስ ያደረጉትን ስለሚያውቅ፥ ለእርሱ ያከናወኑትን የፍቅር ተግባር አይዘነጋም (ዕብ. 6:10)። የሚያሳዝነው የራስ ወዳድነት ከንቱ ሕይወት ኑረው ያለፉ ሌሎች ክርስቲያኖች መኖራቸው ነው። ጌታ ስለ እነዚህም ያውቃል። ኢየሱስ ሲመለስ፥ በሕዝቡ ላይ ይፈርድባቸዋል (2 ቆሮ. 5:10)። እርሱን በታማኝነት ያገለገሉ ሰዎች ከአገልግሎታቸውና ከታማኝነታቸው አኳያ ሽልማታቸውን ይቀበላሉ (ማቴ. 25: 14-30)።

ካከናወኑአቸው ተግባራት አኳያ በክርስቲያኖች መካከል ታላቅ ልዩነት ይታያል። በዚህ ፍርድ፥ ኢየሱስ ታማኞች ለነበሩት ዘላለማዊ ሽልማቶችን ይሰጣል። ታማኞች ያልነበሩ ሰዎች ግን ከክርስቶስ ሊያገኙአቸው ይችሉ የነበሩትን ሽልማቶች በማጣት ያዝናሉ (1 ቆሮ. 3:13-15)።

4. ኢየሱስ ሰይጣን በዚህ ዓለም ላይ ያለውን ቁጥጥር ከፍጻሜ ያደርሰዋል (ራእይ 19:20፥ 20:1-2)

ኢየሱስ በምጽአቱ ከሚፈጽማቸው እጅግ አስደናቂ ነገሮች አንዱ፥ ከዓለም ላይ የሰይጣንን ኃይል ለሽንፈት መዳረግና የሐሳዊ-መሢሕን

የሽብር አገዛዝ ማብቃት ነው። ኢየሱስ ሰይጣንን በታላቅ ሰንሰለት አስሮ ለሺህ ዓመታት ወደሚታሰርበት ወደ ጥልቁ (መድረሻ የሌለው ጉድጓድ) እንዲከተው መልአኩን ይልከዋል (ራእይ 20:1- 3)። ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ አውሬው (ሐሳዊ-መሢሕ) እና ረዳቱ ሐሰተኛው ነቢይ፥ ለዘላለም ይቀጡ ዘንድ በቀጥታ ወደ ዘላለማዊ የእሳት ባሕር ይጣላሉ (ራእይ 19:20)።

የወደቁት መላእክትም ከጌታቸው ከሰይጣን ጋር ይታሰራሉ (ኢሳ. 24:21-22፤ ማቴ. 12:24-26)። ስለዚያ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ «እግዚአብሔር በከፍታ ያለውን ሠራዊት በከፍታ ላይ፥ በምድርም ያሉትን ነገሥታት በምድር ላይ ይቀጣቸዋል። ግዞተኞች በጉድጓድ ውስጥ እንደሚከማቹ በአንድነት ይከማቻሉ፥ በግዞት ቤትም ውስጥ ተዘግተው ይኖራሉ» ይላል (ኢሳ. 24:21-22)። ሺህ ዓመታት ከተፈጸሙ በኋላ፥ ሰይጣን በክርስቶስ ላይ አንድ የመጨረሻ ዓመፅ ለማድረግ ይሞክራል (ራእይ 20:7-8)። ለዚህ የመጨረሻ ዓመፅ፥ ሰይጣንና አጋንንቱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ወደ ሚሠቃዩበት ዘላለማዊ የእሳት ባሕር ይጣላሉ (ኢሳ. 24:22፤ ማቴ. 25:41፤ ራእይ 20:7-10)።

5. ኢየሱስ ከተግባራቸው አኳያ በሰዎች ሁሉ ላይ ፍርድ ይሰጣል (ማቴ. 25:31- 33)

የፍርድ ቀን እየመጣ ነው። በምድር ላይ የኖሩት ሁሉ ለፈጸሙአቸውና ለተናገሩአቸው ነገሮች ሁሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ መልስ ይሰጣሉ (ማቴ. 12:36 - 37፤ ዮሐ. 5:22፥ 27፤ ሮሜ 14:12)። ክርስቶስ ሲመለስ ጻድቁ ሳይሆን ኃጢአተኛው ይሠቃያል። ኃጢአተኞች ለፈጸሙአቸው ተግባራት ሁሉ ዋጋ ይከፍላሉ [መዝ. (37)፥12-15]።

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ዓመፅ ለዘላለም አይታገሥም። በመጨረሻም ታላቅ ቁጣው በኃጢአተኞች ላይ ይወርዳል። መጽሐፍ ቅዱስ በኖህ ዘመን በወረደው የጥፋት ውኃ ይኸው ከስተት እንደ ተፈጸመ ይናገራል (ዘፍጥ. 6:11-13)። በኖህ ዘመን ሰዎች ለ120 ዓመታት የእግዚአብሔርን መንፈስ ድምፅ ለመስማት ባለመፈለጋቸው (ዘፍጥ. 6:3፥ 5፥ 11)፥ እግዚአብሔር በጥፋት ውኃ ፍርድ አጠፋቸው (ዘፍጥ. 6:13)።

የመጨረሻው ፍርድ በውኃ ሳይሆን በእሳት የሚፈጸም ከመሆኑ በቀር (2 ጴጥ. 3:10)፥ አሁንም ተመሳሳይ ነገር ይከሰታል።

ክርስቶስ ሲመለስ፥ በምድር ላይ ስላሳለፉት ሕይወት መልስ ይሰጡ ዘንድ በቅድሚያ የሚጠሩት ክርስቲያኖች ናቸው (2 ቆሮ. 5:10፤ 1 ጴጥ. 4:17)። እንደ ክርስቲያን ለክርስቶስ ባደረጉት ነገር መሠረት ይፈረድባቸውል (1 ቆሮ. 3:10-15)። በዚህ ፍርድ መሠረት አንድም ዘላለማዊ ሽልማቶችን ያገኛሉ ወይም ያጣሉ (1 ቆሮ. 3:14-15)። ሆኖም ክርስቲያኖች በክርስቶስ ባመኑ ጊዜ ደኅንነትን ስለ ተቀበሉ፥ ይኸው የክርስቲያኖች ፍርድ ደኅንነታቸውን አይነካም (ዮሐ. 3:16፤ 5:24)። የክርስቲያኖች ፍርድ ለክርስቶስ በታማኝነት የተመላለሱ ሰዎች የሚሸለሙበት ጊዜ ነው (ራእይ 11:18)።

እስከዚያው ድረስ በምድር ላይ የሚኖሩ የማያምኑ ሰዎች የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ባስተናገዱበት መሠረት ይፈረድባቸዋል (ማቴ. 25:31-46)። የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ያጉላሉ ሰዎች ወደ ዘላለማዊው የእሳት ባሕር ይጣላሉ (ማቴ. 25:41- 46)።

በተጨማሪም፥ ኢየሱስ ከዚህ ቀደም የሞቱትን የማያምኑ ሰዎች ከሞት ያስነሣል (ዳን. 12:2፤ ዮሐ. 5:28-29)። እነርሱም በእግዚአብሔር ቅዱስ ፍርድ ታላቁ ነጭ ዙፋን ፊት ይቆማሉ (ራእይ 20:11-15)። ይህ ፍርድ እጅግ አስፈሪና አንቀጥቃጭ በመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ «ሰማይና ምድር ከፊቱ ሸሹ፤ ስፍራም አልተገኘላቸውም» ይላል (ራእይ 20:11)። ወንዶችና ሴቶች ሁሉ እንደማያምኑ ሰዎች ስለ ፈጸሙአቸው ተግባራት ሁሉ ይፈረድባቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ሙታንም በመጻሕፍት ተጽፎ እንደ ነበረ እንደ ሥራቸው መጠን ተከፈሉ። ባሕርም በእርሱ ውስጥ ያሉትን ሙታን ሰጠ ሞትና ሲኦልም በእነርሱ ዘንድ ያሉትን ሙታን ሰጡ፥ እያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን ተከፈለ። ሞትና ሲኦልም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣሉ። ይህም የእሳት ባሕር ሁለተኛው ሞት ነው። በሕይወትም መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘው ማንኛውም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣለ» ይላል (ራእይ 20:12-15)።

6. ኢየሱስ በዚህ ዓለም ላይ የጽድቅ መንግሥት ይመሠርታል (ኢሳ. 9:6-7)

መዝሙር (98):9፥ «በምድር ሊፈርድ ይመጣልና። በዓለምም በጽድቅ ለአሕዛብም በትንነት ይፈርዳል» ይላል። ይህ ፍርድ የሚለው ቃል አጠቃቀም ክርስቶስ ከምጽአቱ በፊላ በዓለም ላይ እንደሚገዛ ያመለክታል። በመዝሙረ ዳዊት እግዚአብሔር አብ ለክርስቶስ፥ «ለምነኝ፥ አሕዛብን ለርስትህ የምድርንም ዳርቻ ለግዛትህ አሰጥሃለሁ። በብረት በትር ትጠብቃቸዋለህ፥ እንደ ሸክላ ሠሪ ዕቃም ትቀጠቅጣቸዋለህ» ይላል [መዝ. (2):8-9]። በራእይ 11:17 በሰማይ የሚገኙ ሽማግሌዎች፥ «ያለህና የነበርህ ሁሉን የምትገዛ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥ ትልቁን ኃይልህን ስለ ያዝህ ስለ ነገሥህም እናመሰግንሃለን» እያሉ ይጮኻሉ።

የክርስቶስ ግዛት ለዓለም የጽድቅ፥ የሰላምና ሊገለጽ የማይቻል በረከት ጊዜ ይሆናል። ክርስቶስ ለጦርነት፥ ለወንጀል፥ ለክፋትና ለጭካኔ ተግባር ሁሉ የማቆሚያ ገደብ ያበጃል። በእንስሳት ዓለም እንኳ ሳይቀር በሁሉም ስፍራ እውነተኛ ሰላም ይኖራል (ኢሳ. 11:4-9)። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «በመንግሥቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል፥ ለሰላሙም ፍጻሜ የለውም» ይላል (ኢሳ. 9:7)። በተጨማሪም፥ «ለምድርም የዋሆች በትንነት ይበይናል። በከንፈሩም እስትንፋስ ክፉዎችን ይገድላል። ላምና ድብ አብረው ይሰማራሉ፥ ግልገሎቻቸውም በአንድነት ያርፋሉ፥ አንበሳም እንደ በሬ ገለባ ይበላል። የሚጠባውም ሕፃን በእባብ ጉድጓድ ላይ ይጫወታል . . . በተቀደሰው ተራራዬ ሁሉ ላይ አይጎዱም አያጠፉምም፥ ውኃ ባሕርን እንደሚከድን ምድር እግዚአብሔርን በማወቅ ትሞላለችና» ያላል (ኢሳ. 11:4-9)።

7. ኢየሱስ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ይፈጥራል። ተፈጥሮንም ሁሉ ወደ ፍጹምነት ያድሰዋል (ኢሳ. 65:17፥ ራእይ 21:1)

የክርስቶስ የከበረ ግዳንና ወደዚህ ዓለም መመለሱ በዓለም ውስጥ የሚገኘውን ነገር ሁሉ ይነካል። ከታጪአት የነጹትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ይፈጥራል። ሐዋርያው ጴጥሮስ፥ «ነገር ግን ጽድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደ ተስፋ ቃሉ እንጠብቃለን» ሲል ጽፎአል (2 ጴጥ. 3:13)። ጳውሎስም፥ «ፍጥረት ሁሉ እስከ አሁን

ድረስ አዝኖ በመቃተትና በምጥ መኖሩን እናውቃለንና» ሲል ገልጾአል (ሮሜ 8:22)። ይሁንና፥ የከበረው ተስፋ «ፍጥረት ራሱ ደግሞ ከጥፋት ባርነት ነፃነት ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደሚሆን ክብር ነፃነት እንደ ደረስ ነው» (ሮሜ 8:21)።

የእነዚህ አዲስ ምድርና አዲስ ሰማያት ውብ ገጽታዎች በኢሳይያስ 65:17-25 እና በራእይ 21:1-5 ተብራርተዋል። በሁለቱም ምንባቦች፥ ከእንግዲህ ጎዘን ወይም ለቅሶ እንደማይኖር ተገልጾአል። በተጨማሪም፥ ራእይ 21:4 ሥቃይ ወይም ሞት እንደማይኖር ይናገራል፥ «የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና።» በራእይ 21:5 እግዚአብሔር ነገሮችን ሁሉ አዲስ እንደሚያደርግ ተገልጾአል። በኢሳይያስ የሰላም፥ የአንድነት፥ የእርካታና የበረከት ሁኔታዎች ተገልጸዋል። «ተኩላና ጠቦት በአንድነት ይሰማራሉ . . . በተቀደሰው ተራራዬ ሁሉ አይጎዱም፥ አያጠፉምም፥ ይላል እግዚአብሔር» (ኢሳ. 65:25)።

የኢየሱስ ክርስቶስ ደኅንነት ከኃጢአታችን ይቅርታና ከዘላለም ሕይወት ተስፋ በተጨማሪ ብዙ ነገሮችን አካቷል። ይኸውም ኃጢአትና የኃጢአት አስከፊ ውጤቶች ለዘላለም በተወገዱበት ውብና ፍጹም ስፍራ የአጽናፍ-ዓለሙን ሙሉ ለሙሉ ዳግም መወለድ የሚጨምር ነው። ይህ ምን ማለት እንደ ሆነ አስብ! ከእንግዲህ በሽታ፥ ሥቃይ፥ ሞት፥ ጎዘንና ትካዜ አይኖርም ማለት ነው። ከእንግዲህ የወዳጅ ሞት፥ የልጆች አካለ-ስንኩልነት ወይም የአእምሮ ዘገምተኛነት አይኖርም ማለት ነው። ከእንግዲህ የፈራረሱ ቤቶችና የፈራረሱ ልቦች አይኖሩም። ከእንግዲህ መራርነት፥ ጥላቻ፥ ስግብግብነት፥ ቁጣና በደል አይኖርም። ከእንግዲህ ወንጀልና የጭካኔ ተግባር፥ ጦርነትና መገዳደል፥ የድሆች ጭቆናና ፍትሕ አልባነት አይኖርም።

በኢየሱስ ክርስቶስ ላመኑ ስዎች ይህ እንዴት የከበረ ተስፋ ነው! የእግዚአብሔር ማዳን ማንኛውም የሰው ልጅ በምናቡ ሊዳስስ ከሚችለው ሁሉ የላቀ ነው። ጳውሎስ፥ «ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው» ሲል ጽፎአል (1 ቆሮ. 2:9)። እግዚአብሔር ክርስቶስን ለተቀበሉት የሰጠው ተስፋ ይህንኑ ነው።

ማጠቃለያ

የታሪክ የመጨረሻ ክስተት ምን ይሆናል? መጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ወዴት እያመራ እንደ ሆነና እንዴትም እንደሚፈጸም ይነግረናል። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ቀን የጽድቅ መኖሪያ የሚሆን ሰማይና ምድር እንደሚሰናዳ ያረጋግጥልናል (2 ጴጥ. 3:13)። ይሁንና፥ ከዚያ ወርቃማ ዘመን በፊት ምን ይከሰታል? መጽሐፍ ቅዱስ የታሪክ ፍጻሜ ሲቃረብ የሚፈጸሙትን አያሌ ክስተቶች ያብራራልናል። እነዚህም አሁን ሰይጣንና እግዚአብሔር በዓለም ውስጥ ከሚፈጽሙአቸው ተግባራት ጋር የተዛመዱ ናቸው።

እግዚአብሔር የኢየሱስ ክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ ከሚገኙ ነገዶችና የሕዝብ ቡድኖች እየገነባ ነው። በተመሳሳይ ጊዜ፥ ሰይጣንም እንደ ምግባረ ብልሹነት፥ ወንጀል፥ ጭካኔ፥ ፖለቲካዊ አለመረጋጋት፥ ጦርነት፥ የተፈጥሮ አደጋዎችና ሌሎችም እነዚህም የመሳሰሉ በርካታ ዓይነት ክፉ ተግባራት ወደ ዓለም በማምጣት፥ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመቃወምና ለማዘግየት እየተዋጋ ነው። ይህ ታላቅ መንፈሳዊ ጦርነት የሚያበቃው ኢየሱስ ክርስቶስ ለሁሉም በሚታይ መልኩ በአካል ወደ ዓለም ሲመለስ ነው።

የክርስቶስ ምጽአት በዓለም ውስጥ ከታዩት ክስተቶች ሁሉ በላይ እጅግ የሚያስፈራ ይሆናል። የአጽናፍ-ዓለሙ ንጉሥ ከቅዱሳን መላእክቱ ጋር ሲመለስ ምድርና ሰማያት ይናወጣሉ። ምጽአቱ እርሱን ለሚያውቁትና ለሚወዱት በታላላት ሊገለጽ የማይችል ሐሴት ሲያነናጽፍ፥ ጠላቶቹ ደግሞ በማይነገር ሽብር ይዋጣሉ። ይሁንና፥ የሚመለስበት ጊዜ ግንም ሰው የማያውቀው ምሥጢር ነው። ስለ ሆነም፥ ሕዝቡ ተዘጋጅተው በታማኝነት እንዲኖሩ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸዋል። መዘጋጀት ማለት የቅድስናና ለክርስቶስ የተሰጠ ሕይወት መኖር ማለት ነው። ታማኝ መሆን ማለት እርሱን ባልተከፈለ ልብ ማገልገል ማለት ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ ከሚያከናውናቸው ተግባራት መካከል ሕዝቡን ወደ ራሱ መሰብሰብ (ዮሐ. 14:2-3) ፥ ሙታንን ሁሉ ማስነሣት (ዮሐ. 5:25-29)፥ ቅዱሳንና ነቢያት የሆኑትን ባሪያዎቹን መሸለም (ራእይ 11:18)፥ በዚህ ዓለም የሐሳዊ-መሢሕንና የሰይጣንን አገዛዝ ማከተም (ራእይ 19:20፤ 20:1-2)፥ በሰዎች ሁሉ ላይ እንደየሥራቸው ፍርድ መስጠት (ማቴ. 25:31-33)፥ ክፋት የማይኖርበትን መንግሥት በዚህች ዓለም ላይ መመሥረት (ኢሳ. 9:6-7)፥ እንዲሁም

አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር መፍጠር ይገኙባቸዋል። ፍጥረትን ሁሉ ፍጹም አድርጎ ይለውጠዋል (ኢሳ. 65:17፤ ራእይ 21:1)። እግዚአብሔር በታሪክ የመጨረሻውን ቃል የሚናገር ሲሆን፥ በፊቱም ሊቆም የሚችል ጠላት አይኖርም። ከዘላለም አስከ ዘላለም በክብርና በግርማ የሚነግሥ ሲሆን፥ ሕዝቡም ከእርሱ ጋር ይነግሣል።

በምዕራፍ 18 ላይ የተመሠረቱ የመወያያ ጥያቄዎችና መልመጃዎች

1. ብዙዎቻችን ከረዥም ጊዜያት በፊት፥ በአያት ቅድማያቶቻችን ዘመን ነገሮች የተሻለ መልክ እንደ ነበራቸው እናስባለን። መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ወደ ዓለም ከተመለሰ በኋላ ነገሮች ከቀድሞ ይልቅ እንደሚሻሉ በተለይ የሚገልጽባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው?

2. ዛሬ ከጥናታዊ የ«እስታትስቲክስ» መረጃ እንደምናረዳው፥ ወንጀል፥ ጭካኔና ክፉት በዓለም እየጨመሩ ናቸው። የቡድኑ አባላት በቅርቡ ባጋጠማቸው ወይም በሰሙት ክንውን በመጠቀም ይህንኑ እውነታ ያረጋግጡ።

3. ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም ሲመለስ የሚፈጽማቸውን ሰባት ነገሮች ግለጹ።

4. ሦስት አባላት በሚገኙባቸው ትናንሽ ቡድኖች ተከፋፈሉና፥ ለክርስቶስ ምጽአት መዘጋጀት ማለት ምን እንደ ሆነ ተወያዩ። እያንዳንዱ ቡድን ለክርስቶስ መመለስ ለመዘጋጀት ሊፈጽማቸው የሚችላቸውን ከአምስት እስከ አሥር የሚደርሱ ግልጽ ነገሮች ይዘርዝር።

5. በአፍሪካ የጊዜ ጽንሰ-አሳብ ላይ ተወያዩ። ከዚያም መጽሐፍ ቅዱሳዊ የጊዜ ጽንሰ-አሳብ ላይ ተወያዩና እነዚህን ሁለት አመለካከቶች አወዳድሩ።

6. አራት አባላት በሚገኙባቸው ትናናንሽ ቡድኖች ተከፋፈሉና [መዝ. (2):4-12] እና ዘካርያስ 14:16-21 አንብቡ። ኢየሱስ ክርስቶስ በዓለም ላይ መንግሥቱን በሚመሠርትበት ጊዜ የሚኖሩ ሁኔታዎች ምን ምን እንደ ሆኑ ዘርዝሩ።

7. 1ኛ ቆሮንቶስ 15:35-51 እና ሉቃስ 24:36-43ን አንድ ሰው ድምፁን አሰምቶ ያንብብና፥ በምንባቡ መሠረት፥ ስለ አማኞች የትንሣኤ አካል ጠባይ ተወያዩ።

8. ከሞት በኋላ ስለሚኖረው ሕይወት የአፍሪካውያን ግንዛቤ ምን እንደ ሆነ ተወያዩ። ይህንንም መጽሐፍ ቅዱስ በኢሳይያስ 65:17-25 እና ራእይ 21:1-8፥ በአዲስ ሰማይና በአዲስ ምድር ውስጥ ስለሚኖረው ሁኔታ ከሚሰጠው መግለጫ ጋር አወዳድር።

9. ሁሉም ሰው ለየራሱ ማቴዎስ 24:27-31፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 15:49-53 እና 1ኛ ተሰሎንቄ 4:14-17ን ያንብብ። በእነዚህ ምንባቦች በተሰጠው መግለጫ ላይ በመንተራስ፥ ሁለት ሰዎች ለቡድኑ የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጽና የክርስቲያኖችን ትንሣኤና መነጠቅ እንዲያብራሩ አድርግ።

10. በክርስቶስ ምጽአት በሰይጣንና አጋንንቱ ላይ ምን ይከሰታል? በሐሳዊ-መሢሑስ ላይ? መልስህን ለማረጋገጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን አግኝ።

SUGGESTED FOR FURTHER READING

Berkouwer, G.C. The Return of Christ. Grand Rapids: Eerdmans, 1972.

Cotterell, P. Dealing with Death. London: Scripture Union, 1994.

Hoekema, A.A. The Bible and the Future. Carlisle: Paternoster Press, 1994.

Pawson, David. When Jesus Returns. London: Hodder, reprinted1995.

Pentecost, J. Dwight. Things To Come. Grand Rapids, Michigan: Zondervan, 1990.

Travis, S. I Believe in the Second Coming of Jesus. London: Hodder, reprinted 1994.

የቃላት ፍቺ (Glossary)

አዋልድ (Apocrypha) - የብሉይና አዲስ ኪዳን መጻሕፍት በተጻፉባቸው ከፍለ ጊዜያት መካከል የነበረውን ታሪክ፥ ሥነ-ግጥምና ሥነ-ቃል ያካተቱ መጻሕፍት አጠቃላይ ስያሜ።

ተዛምዶ (Application) - አንድን መመሪያ፥ እውነታ ወይም አሳብ በተግባር ማሳየት።

ዝንጀሮ (Baboon) - ትልቅ ጦጣን የሚመስል፥ በአፍሪካ የሚገኝ ግዙፍ እንሰሳ።

ህላዌ (Being) - በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ህልውናውን ይዞ የሚኖር አካል ወይም መንፈስ።

ሥነ-ሕይወታዊ ሳይንስ (Biological Science) – ሕይወት ስላላቸው ነገሮች የሚደረግ ጥናት።

ቀኖና (Canon) - እስትንፋሰ-አግዚአብሔር እንዳረፈባቸው የታመኑ ብሉይና አዲስ ኪዳን መጻሕፍት።

ሕዋሳት (Cells) - ሕይወት ባላቸው ነገሮች ሁሉ ውስጥ የሚገኙ ረቂቅ ከፍሎች።

ንጥረ ነገሮች (Chemicals) - ነገሮች ሁሉ የተሠሩባቸው የተለያዩ ውህዶች።

ዝልግላጎች (Chromosomes) - የአንድ ሕዋስ ማዕከላዊ አካል ከር መሳይ ጥቅቃቅን ነገሮች ሲሆኑ፥ ለሕዋሱ መራቢያ የሚረዱትን የዝሪያ ትእዛዛት ይይዛሉ።

ኮዲክስ (Codex) - ቀድሞ በእጅ የተገለበጠ መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ደብተር በአንድ ላይ ሲደረግ።

ምሉዕ (Complete) - አንድ ነገር ምሉዕ የሚሰኘው ሙሉ ሲሆን፥ ወይም ፍጻሜ ሲያገኝ ነው።

ዓውደ-ንባብ (Content) - አንድ ነገር የሚገኝበት ሁኔታ።

ዓውድ (Context) - በመጽሐፍ ቅዱስ ከአንድ ጥቅስ ዙሪያ የሚገኙ ምንባቦች።

ዓውዳዊነት (Contextualization) - የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ለአንዳንድ የአካባቢ ባህሎች ተዛማጅ ማድረግ።

የርባታ ጥናት (Controlled breeding experiment) – በአንድ ዓይነት እንስሳ፥ ሕይወት ያላቸው ነገሮች ባሕሪያት እንዴት ከትውልድ ትውልድ እንደሚተላለፉ የሚከታተል ሳይንሳዊ ጥናት።

ኑፋቄ (Cult) - አንዳንድ ጊዜ ክርስትናን መስሎ ሊታይ የሚችል የሃይማኖት ዘይቤ።

አጽንኦት (Emphasis) - ለቃላት ወይም ለአሳቦች የሚሰጥ ልዩ ሚና።

ተግዳሮት (Encounter) - በሁለት ወይም ከዚያ በሚበልጡ ሰዎች መካከል፥ ወይም ደግሞ በሰውና በሌላ ነገር መካከል የሚደረግ ግንኙነት።

ጎሰኛነት (Ethnocentrism) - አብዛኛዎቹ የዓለም ሕዝቦች የራሳቸው የጎሳ ቡድን ከሌላው እንደሚሻል የሚያስብበት ዝንባሌ።

የሚጥል በሽታ (Epilepsy) - በድንገት ራስን የሚያስት የአእምሮ በሽታ።

አዝጋሚ ለውጥ (Evolution) - ሕይወት ያላቸው ነገሮች ቀስ በቀስ እንደሚለወጡ የሚያስረዳ አሳብ።

መተት (Fetish) - መንፈስ እንደሚገኝበት የሚታመን ሰው–ሠራሽ ተፈጥሮአዊ ዕቃ።

የዝሪያ ውርሶች (Genes) - የዝልግልግ እጅግ አነስተኛ ክፍሎች ሲሆኑ፥ እያንዳንዳቸው የዝሪያ ውርሶች ሕይወት ያለውን ነገር አንዳንድ የተወረሱ ባሕርያት ይወስናሉ።

ምትሐት (Ghost) - አንዳንድ ጊዜ ለሕያዋን የሚታይ የሙት መንፈስ።

ጎሪላ (Gorilla) - ትልቅ ዝንጀሮ የሚመስል በአፍሪካ የሚገኝ ግዙፍ እንስሳ።

ሄርመንዩቲክስ (Hermeneutics) - መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት በትክክል መተርጎም እንደሚቻል የሚያስረዳ ትምህርት።

ቅይጥ (Hybrid) - ሁለት የተለያዩ ዓይነት እንስሳት ወይም ዕፅዋት ተዳቅለው የሚያስገኙት ውጤት ሲሆን፥ ይህም ራሱን ሊተካ የማይችል ነው።

ተሠገዎ (Incarnation) - እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ አካል የሰውን ሥጋ ለብሶ መገኘት።

እስትንፋስ-እግዚአብሔር (Inspiration) - መንፈስ ቅዱስ ሰዎች የእግዚአብሔርን መገለጥ ለሌሎች እንዲያስተላልፉ ለመርዳት፥ መጽሐፍ ቅዱስን ሲጽፉ አእምሮአቸውን ያንቀሳቀሰበት ተግባር።

ሚሊኒየም (Millenium) - የሺህ ዓመታት ክፍለ-ጊዜ።

ኒውክላስ (Nucleus) - የሕያው ሕዋስ ማዕከላዊ አካል ሲሆን፥ ሕዋሱ ራሱን ያራባ ዘንድ ጥንተ ነገራዊ ትእዛዛትን ይይዛል።

አረማዊ (Pagan) - ከባህላዊ ሃይማኖት ጋር የሚዛመድ ነገር።

የብዙ ጋብቻ (Polygamy) - የአንድ ወንድ ከአንድ በላይ ሚስቶችን ማግባት።

ማስተሰሪያ ወይም ምትክ (Propitiation) - ብዙውን ጊዜ መሥዋዕት በማቅረብ የተከፋውን መንፈስ ወይም አምላክ ቁጣ ለማብረድ መሞከር።

ጸያፍ ሥዕሎች (Pornography) - ሰዎች ወሲባዊ ተግባር ሲከውኑ የሚያሳይ ሥዕል ወይም ጽሑፍ።

ፐርገትሪ ወይም ሲኦል (Purgatory) - በካቶሊክ ሥነ-መለኮት፥ ሰዎች ሁሉ ከሞቱ በኋላ ለመንግሥተ ሰማይ እንዲስማሙ ለማድረግ ከምድራዊ ኃጢአታቸው የሚነጹበት ስፍራ።

የመጽሐፍ ጥቅልል (Scroll) - የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት በእጅ የተጻፉበት ረዥም ልዩ ወረቀት ወይም ብራና።

ሴፕቱዋጂንት (Septuagint) - በ250 ዓ. ዓ. አካባቢ ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ የተተረጎመ መጽሐፍ ቅዱስ።

የወንዴ ዘር (Sperm) - የወንድ የዘር መራቢያ ሕዋስ።

ማጠቃለያ (Summary) - ቀደም ብሎ በዝርዝር የቀረበውን አሳብ አሳጥሮ መጻፍ።

ቅይጥነት (Syncretism) - የሁለት ወይም ከዚያ የሚበልጡትን ሃይማኖቶች መለኮታዊ እምነቶችና ልምምዶች መቀላቀል።

አዝጋሚ ለውጥ (Theistic evolution) - ሕይወት ያላቸው ነገሮች ሁሉ በእግዚአብሔር ምሪት ቀስ በቀስ ከአንዱ ወደ ሌላው ዓይነት እንደተለወጡ የሚናገር አሳብ።

ታላቅ መከራ (Tribulation) - ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት ጥቂት ቀደም ብሎ የሚከሰት ከፍተኛ የመከራ ዘመን።

እሴት (Value) - በአንድ ሰው አስተሳሰብ በጣም ጠቃሚ ተደርጎ የሚወሰድ ነገር።

ቩልጌት (Vulgate) - በ388 ዓ. ም. ጀሮም በተባለ ምሁር ወደ ላቲን ቋንቋ የተተረጎመ መጽሐፍ ቅዱስ።

ተሽከርካሪ ወንበር (Wheel chair) – አካለ ስንኩል የሆነ ሰው የሚጠቀምበት ባለጎማ ወንበር።

የነተበ (Worn) - ያረጀ ጨርቅ

ያህዌ (Yahweh) - በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ስም ሲሆን፥ "YHWH" ከሚል አናባቢ ከሌላው ቃል የተወሰደ ነው። እንደ ዘፍጥረት 18 ሁሉ፥ "YHWH" በተሠገም ከመገለጹ በፊት በታየባቸው ሁኔታዎች አገልግሎ ነበር።